ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፩
3 me ANNÉE № 1

ሐሙስ ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ.ም።
JEUDI 6 JANVIER 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲረክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ።
Gabré Christos Taklé Haymanot
Diréctéur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ደከፈላል።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ደሸጣል።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ በዓለ ልደት ።

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት የዓለም ደኅንነት የተገኘበት የከበረ ትልቅ የደስታ በዓል ነው ።

ዛሬም በዋዜማው በየቤተ ክርስቲያኑ ካህናቱና ሊቃውንቱ በታላቅ ደስታ ስለ ልደት የምሥራች ቃል እያነበቡና እየዘመሩ ይከበራል ።

ስለ ልደት በዓል ዋዜማ አከባበርም በብዙ ሥፍራ ጌታም ቢሆን ድኃ እንደ ችሎቱ የገና ዛፍ ከተባለው እንጨት አንዱን ክንፍ ቆርጦ በልዩ ልዩ ጌጥ ያስጌጠዋል ። ልዩ ልዩ ሲያዩት የሚብለጨለጭና የሚያንፀባርቅ አበባና ፍሬ የሚመስል ያንጠለጥልበታል ። ይልቁንም በየቤተ ክርስቲያኑ ትልቅ የገና ዛፍ ይተከልና በላዩ ብዙ ሻማና ልዩ ልዩ ጌጥ ለማየት የሚያምር ይደረግበታል ።

በቤተ ክርስቲያንም የሚሰበሰቡት ሰዎች ያማረ ያማረ ልብስ እየለበሱ ገብተው የልደትን ዋዜማ መዝሙር ከዘመሩ ባኋላ ሕፃናቱ በተራ በተራ እየተነሱ መብራቱን አብርተው ስለ ጌታችን ልደት የሚነግር ጥቅስ ከብሉይና ከሐዲስ በምዕራፉና በቁጥሩ እየጠቀሱ ለተሰበሰበው ህዝብ ያሰማሉ ።

ልዩ ልዩ ጌጥ የተደረገበት የልደቱ ዛፍም በላዩ ላይ ሻማ መላው በበራ ጊዜ የሻማው ብርሃንና ጌጡ አንድነት ሲቀላቀል የመድመቁ ነገር እጅግ ድንቅና ደስ የሚያሰኝ ነው ልጆቹም በልደት ለት መላእክት የዘመሩትን መዝሙር ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ የሚለውን ከሙዚቃ ጋር በመተባበር አንድነት ሁነው ሲዘምሩት ዕፁብ ድንቅ ነው ።

ዛሬም ባዲስ አበባ በንዳንድ ቦታ እንደዚህ ምሳሌ አድርገው የመድኃኒታችንን ልደት የሚያከብሩ አሉ የጌታችን የመድኃኒታችንን የልደት በዓል ስናስብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በበረት መተኛቱ መዋረዱ ተዋርደን የነበርነውን እኛን ለማክበር እንደሆነ እንወቅ። በዚህ ሥራ እግዚአብሔር ሰውን እንደ ወደደና ሰው ከኃጢአት እንዲድን ፈቃዱን ገለጠልን ። የልደት ቀን ትልቁን የእግዚአብሔርን ፍቅር የምናስብበት በዓል ነውና በልማድ ሳይሆን በእውነተኛ ናፍቆት በተድላና በደስታ በምልጃናም ልንቀበለው ይገባናልና ከመላእክት ጋራ ሁነን ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ እያልን እንዘምር ።

ለክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሁሉ ብሩክ በዓለ ልደት ያድርግንላችሁ እያልን የልደትን የምስራች እናቀርብለን

ከ፪ኛዓመት የ፩፻፲፩ ገጽ ተከታይ።

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

እነሆም የብረት ሠሪው ከራሹ አራሹም ከሸማኔው ከተራራቁ ግን የሠሩትን ዕቃ በፍጥነት ለመለዋወጥ እንደምን ይችላሉ ። የጋሪ መንገድ ወይም የምድር ባቡር ሠርቶ መንግሥት ካላቀራረባቸው ለመገናኘት ሲፈልጉ አንዱ ወደ አንዱ መንደር ሂዶ እስኪ መለስ ድረስ ብዙ ቀን ሥራ ይፈታል ። ወይም እሱ ራሱ ባይሄድ ደክሞ ከገባው ሥራ ከፍሎ ዕቃውን ለሚያመላልስ ነጋዴ ይሰጣል ። ለሰው የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ምድር በሆዷ ይዛለች ። ማናቸውም ነገር ከምድር መጥቶ እስኪበጅ ድረስ የሚደከመው ድካም ይጠቅማል ። ነገሩ ከተበጀ በኋላ ካንዱ ሥፍራ ወደሌላው ሥፍራ ለመውሰድ የሚደከመው ድካም ግን በነገሩ ላይ አንዳች ትርፍ አይጨምርምና ከንቱ ነው ። ስለዚህም ምክንያት ባንድ አገር ውስጥ ነጋዴ ሲበዛ ለሕዝቡ ትልቅ ጉዳት ነው ።

ባንድ አገርም ውስጥ ነጋዴ ያለ መጠን ሲበዛ ባገሩ ውስጥ ደህና መንገድ የሌለ እንደሆነ ሠራተኞቹ ቶሎ ለመገናኘት ባይችሉ ነውና ከድካሚቸው ራሱ ሳይሠራ ቀምቶ የሚበላ ቢኖር ተባብረው ሊመክቱ አይቻላቸውም ። ስለዚህም ባንድ አገር ውስጥ ነጋዴ ሲበዛ ሹምም ወታደረም ቀማኛም ይበዛል ። የፊት የፊቱም ሥራ ሁሉ በከንቱ እያለቀ በእንደዜህ ያለ አገር ውስጥ ሀብት አይከማችም ። ድኅነትና ችጋር በሽታም ሞትም እጅ ለእጅ ተያይዘው ይገቡበታል ።

ነገር ግን ለኑሮው የሚያስፈልገውን ዕቃ ሁሉ በየይነቱ የሚሠሩ ሰራተኞች አጠገብ ላጠገብ ካልሠፈሩ ምንስ የሚያ ገናኛቸው የጋሪ መንገድ የምድር ባቡርም መርከብም ቢበጅላቸው ጉዳታቸው ይቀላል እንጂ መቸገራቸው ፈጽሞ አይቀርም። ባለጋሪውም ባለምድር ባቡሩም በከንቱ ዕቃ አያመላልሱም ። ሠራተኞቹ ደክመው ከሚያገኙት ትርፍ ተካፍለው ነው እንጂ።ስለዚህም የሠራተኞቹ ቦታ እየተራራቀ ሲሄድ ትርፋቸው እያነሰ ይሄዳል ። ሰፈራቸውም ሲቀራረብ ትርፋቸውም ያድጋል። ጎረቤቶችም ከሆኑ ዘንድ ሥራ በሥራ ሌላ ሰው በመካከላቸው ሳይገባባቸው እየተለዋወጡ የድካማቸውንም ዋጋ ያገኛሉ ።የድካማቸውንም ሙሉ ዋጋ ሲያገኙ ለወደ ፊት የበለጠ ሀብት ለማግኘት ይሆንላቸዋል ። አመላላሾችም ሁነው ሲያገለግሉ የነበሩ ሰዎች ሌላ የሚጠቅም ሥራ ይይዛሉ ፤ በዚሁም የሠራተኞቹ ቁጥር እየበዛ ይሄዳል ። ይህም ብቻ አይደለም ሰራተኞቹ አጠገብ ላጠገብ ከሆኑ ወይም በፍጥነት ለመገናኘት ከተቻላቸው ዘንድ ደክመው ካገቡት ፍሬ ቀምቶ ሊበላ ማንም ቢፈልግ ተባብረው ለመመከት ይሆንላቸዋል ። በዜህም ምክንያት ቀማኛ ይጠፋል ። የሹምና የወታደርም ቁጥር በልክ ይሆናል ። በዚሁም የሠራተኞቹ ቁጥር እንደ ገና ያድጋል ። አገሩም ከዱሮው ይልቅ እየሰፋ ይሄዳል ።

ሕዝብ የሚጠቀምበት ሥራው ሲከፋፈልና የሠሩትን ሥራ የሚለዋወጡ ሠራተኞች ሲቀረቡ ነው ።መንግሥትም የሚበረታውና ሀብት የሚያገኝ ሕዝቡ ሲጠቀም ነው ። ስለዚህም መንግሥት ሊበረታ ከፈለገ ዘንድ በሥራ የሚያሰለጥኑ የትምህርት ቤቶችና ሕዝቡን በፍጥነት የሚያገናኝ መንገድ መሥራት ያስፈልገዋል ።

ከዚህ ቀደምም አንድ ነገር ተረድተናል ። የሠሩትን ሥራ የሚለዋወጡ ሰራተኞች እንደ እየድካማቸው መጠን የሚለዋወጡ ለየሥራቸው የሚያስፈልጋቸው ዕውቀት ሚዛኑ ትክክል ሲሆን ነው ። የዕውቀታቸው ሚዛን ትክክል ካልሆነ የሚለዋወጡበት ዋጋ ትክክል አይሆንም ።

ስለዜህም እውቀት የሌላቸው ሕዝቦች እውቀታቸው ከፍ ካለ ሕዝቦች ጋራ የሠሩትን ነገር ሲለዋወጡ እውቀት የሌላቸው ሕዝቦች የሚያገኙት ጉዳት ትልቅ ነው ። የዜህንም ጉዳት ልክ ፈጽመን እንድንረዳው ቀጥሎ የተጻፈውን ምሳሌ እንመልከት ።

ከኢትዮጵያ ወደ ኤሮፓ አገር ከጥር ፲፱፻፩ዓመት ምሕረት እስከ ጥር ፲፱፻፳ዓመት ድረስ የሄደው ቆዳ ፪፻፵፩ሺ ፬፻፺፬ ፈረሲላ ነው ። ያንዱም ፈረሲላ ቆዳ ዋጋ ባዲስ አበባ ገበያ አሥራ ሰስት ብር ነበረ ። የዚያን የሄደውን ቆዳ የዋጋው ድምር ብናስበው ፫ሚሊዮን ፮፻፴፱ሺ ፬፻፹፯ ብር ይሆናል በፈረንጅ አገር ተበጅቶ የሚመጣው ቆዳ ግን ባዲስ አበባ በፈረሱላ ብናስበው እስከ ፶፪ ብር አወጣ ። እንግዴህ አንዱ ፈረሱላ ቆዳ ከፈረንጅ አገር ተሠርቶ እስኪመለስ ድረስ በፈረሱላው ፹፱ ብር ፈጀ ማለት ነው የኢትዮጵያ መንግሥት ፪፻፵፩ሺ ፬፻፺፬ ፈረሱላ ቆዳ ከዚሁ ካገሩ ማበጀቱን ትቶ ወደ ኤሮፓ ቢሰድ ከሳራው ፳፩ ሚሊዮን ፬፻፺፫ሺ ፱፻፲፩ ብር ይሆናል ። ቆዳው ባገሩ ውስጥ ቢበጅ ይህ አመላላሾችና ሰሪዎች የሆኑት የውጭ ሰዎች የሚበሉት ገንዘብ በኢትዮጵያ ይቀር ነበረ ። በሌላም የንግድ ነገር ሁሉ ሲሆን ከዜህ ይከፋል እንጂ አይሻልም እንደዜሁ እንደ ሆነ አዙሮ ማየት ነው ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ስምንት ቀን ሲሠራ ቢያንስ ቢያንስ ሰባት ቀን ለኤሮፓ ሰዎች ሠርቶ አንድ ቀን ለራሱ ነው ። አሁን ለወሬው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፲ ሚሊዮን ተብሎ ይገመገማል ሠራተኛውም ቢበዛ የሕዝቡ ሶ ሶ ቢሆን ነው ያስሩም ሚሊዮን ሰሙሲሶ ፫ሚሊዮን ፫፻፴፫ሺ ፫፻፴፫ይሆናል ከነዜህም ሠራተኞች ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሰሩ ፬፻፲፮ ሺ ፮፻፷፯ ሰዎች ብቻ ናቸው የ፪ ሚሊዮን ፱፻፲፮ሺ ፮፻፷፮ ሠራተኞች ድካም ለኤሮፓ ሰዎች ጥቅም መሄዱ ነው ስለዚህም ሕዝቡ የድካሙን ፍሬ እንደ ተቀማ ያህል ነውና ከሠራተኛው በላተኛው በዝቶበት እውቀት አግኝቶ ካልሰለጠነ ለወደፊት እየበዛ ሲሄድ ድኅነትም እያደር እየተጫነው ይሄዳል ።

አንባቢው ግን እንደዜህ ብሎ ይጠይቅ ይሆናል ። የቆዳው ምሳሌ ደህና አድርጎ አያስረዳም ፤ የኢትዮጵያ ሰው ቆዳውን ሸጦ ብሩን መቀበል እንጂ ከፈረንጅ አገር ተበጅቶ የሚመጣውን ቁርበት መግዛት አያስፈልገውም ያንን ቁርበት የሚገዙ በገራችን ውስጥ ያሉት ፈረንጆች ናቸው እንጂ የኢትዮጵያ ሰውስ ለኮርቻውም ለመጫኛው ለሌላውም ጉዳይ ለሚያስፈልገው ነገር ሁሉ በገሩ የለፋ ቁርበት ይበቃዋል ፤ ስለዜህም የከብት በሽታ ገብቶ በሬው ሙቶ በከንቱ ሊበሰብስ የነበረው ቆዳ ዋጋ ሲያወጣ ትርፍ ይሆናል እንጂ ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ክሣራ ይሆናል የተባለው ስለምድርነው የተባለ እንደሆን ፤ አስተውለን ከመረመርን ዘንድ የዜህን ጥያቄ ምላሽ በቶሎ ልንረዳው እንችላለን ።

ተሠርቶ የሚመጣውን ቆዳ ባንገዛ አቡጀዲድ ቆጫ የብረት ድስት ማህንም ምንጣፍም ሌላም ደግሞ ልዩ ልዩ የሆነ ዕቃ ከኤሮፓ አገር የሚመጣውን በያይነቱ ብዙ ዕቃ መግዛታችን አይቀርም ። ነገር ግን የሠራተኞቹ እውቀት ሚዛኑ ትክክል በሆነ አገር ውስጥ ሠራተኞቹ ዕቃቸውን ሲለዋወጡ እንደየሥራቸው መጠን መሆኑን ከዜህ ቀደም አውቀናል ። ስለዜህ የአቡጀዲዱ ሠራተኛና የቁርበት ሠራተኛው ሁለቱ በኤሮፓ አገር ሲለዋወጡ እንደየሥራቸው መጠን ነው ። ስለዜህም በቁርበቱ ፋንታ አቡጀዲዱ ወደ ኢትዮጵያ አገር ቢመጣ ለተበጀው ቁርበት ሊሰጥ የነበረውን ዋጋ እንደ ሥራው መጠን ይወስዳል ፤ ማለት ቁርበቱ ተበጅቶ ባይመለስ ወኪሎቹን እንአቡጀዲድንና እነቆጫን ልክ የኢትዮጵያንሕዝብ ድካም ይወስዳል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጉዳቱ ግን ይህ ብቻ አይደለም መሬት ማናቸውንም ነገር ብትሰጥ በብድር ነው ። ብድሯን ካልመለሱ

BRITISH MUSEUM 22 MAY 29

ላት እንደ ባንኮች ሁሉ ታስቸግራለች ። በአይሁድና በክርስቲያን የሃይማኖት መጽሐፍ እንደምናየው እነሆ እግአብሔር አዳምን አለው ። አንተ መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ የሚፈጠር ሁሉ ከመሬት ነውና ወደ መሬት ይመለሳል ። ዘፍጥረት ፫ ፲፱ ።

ምድር ያበደረችውን ነገር ሁሉ ካልመለሱላት ለወደፊት ስጭኝ ቢሏት ትለግማለች ። ሄዶ ሳይመለስ የቀረበትም ነገር ሲበዛ ከናካቴው በጭራሽ እምቢ ትላለች ። ተበድሯት ብድሩንም ሳያመልስላት እምቢ ላለ ሕዝብ በረኃብና በበሽታ ትፈጀዋለች ይህ ቃል አሰት እንዳይደለ ማንም ባላገር ይመሠክራል ።

አንድ ጊዜ ታርሶ እህሉ የተበላ መሬት ፍግ ካልወደቀበት የሚያፈራው እህል በያመቱ እያነሰ ይሄዳል ። አዘውትረውም ከአረሱት ዘንድ ፍግም ሳይወድቅበት ቢቀር የእርሻ መሬት ሁሉ እህል መስጠቱን ፈጽሞ ያቋርጣል ።

ስለዚህ ያገራችን መሬት የዘሆን ጥርስ ዝባድ ቆዳ ቡን እህል በሬ ላም ፈረስ አህያ በቅሎ እየሆነ በያመቱ ወደውጭ አገር ቢሄድ አሁን ለጊዜው ለኛ ባይሰማን የኢትዮጵያ ሕዝብ በዝቶ መሬት እየጠበበ ሲሄድ ጉዳቱን ያገኘዋል ። ሕዝቡ በሥራ ሠልጥኖ ሥራውንም ሁሉ እንደ መጠኑ ተከፋፍሎ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ባገሩ ለማበጀት ቢችል ግን ፍጉ ባገሩ ይቀርለት ነበር ስለዚህም እውቀት ያነሰው ሕዝብ እውቀታቸው ከፍ ካሉ ሕዝቦች ጋራ ሲገበያይ መጀመሪያ ትርፍ ድካም ይሰጣቸዋል ። ሁለተኛም መሬቱ ወደ እነሱ እየተጓዘ ይሄዳል ። እንደዚህ ያለውም እውቀት ያነሰው ሕዝብ ሲበዛ መሬቱ የሚሰጠው ፍሬ አይበቃውም ። ስለዚህም በጊዜ ብዛት ሰርቼ እበላለሁ ሲል መሬቱ ወደሄደበት አገር ተከትሎ እውቀት ወዳላቸው ሕዝቦች አገር ይሰደዳል ባገርም የቀሩ ሕዝቦች ወንድሞቹ ከረኃብና ከበሽታ ጋራ እየታገሉ እርፊት ሳያገኙ ጊዜ ሞታቸው ይደርስና ይሄዳሉ ።

አንባቢው ደግሞ እንደዜህ ብሎ እንደገና ይጠይቅ ይሆናል ። እኛ ቆዳና ቡን ብንሰድ ከኤሮፓ አገር አቡጀዲድና ሱካር ይመጣልናል ። ስለዚህም አንድ ክፍል ቢሄድ አንድ ክፍል ከመሬታቸው ወደኛ ይመጣል ። እንግዴህ በዜህ የሚያገኘንን ጉዳት እንናገር ከመሬታቸውማ አንድ ክፍል እንዲመጣልን እርግጥ ነው ነገር ግን እንደሰጠነው መሬት ልክ አልመጣልንም እንጂ አሁን እስቲ ባንድ አቡጀዲድና ባንድ ክንድ የበሬ ቆዳ ያለውን ፍግ አስተውለን እንመልከት ። ባንዱ ክንድ ቆዳ ውስጥ ያለው ፍግ በይነቱም በብዛቱም ይበልጣል ። አንዱ ክረጃ አቡጀዲድ እስከ መቶ ከሀያ ብር ያወጣል ። ያንድ ጮማ በሬ ዋጋ ግን ቢበዛ ዛሬ ፴ብር ነው ፤ እንግዲህ ላንዱ ክረጃ አቡጀዲድ እስከ ሶስት በሬ ይሰጥበታል ። ስለምን በሬው በሽታ እንዳይገድለው አውሬም እንዳይበላው ከመጠበቅና ወደገበያ ከመውሰድ በቀር ሌላ የሰው ድካምና እውቀት አላለፈበትም ። ያቡጀዲዱ ጥጥ ግን አቡጀዲድ እስኪሆን ድረስ በብዙ ሰዎች እጅና በብዙ መኪናዎች ውስጥ ገብቶ ተደክሞበታል ። በፈረንጅ አገር በሬውም ቢሆን ብዙ ዋጋ ያወጣል ። ስለምን ሕዝቡ በዝቶ አገሩ ጠባብ ስለሆነ በሬው በልቶት የሚያድገው ሳር ተዘርቶ ታጭዶ ተከምሮ ነው ። ሜዳ ለሜዳም አይሰማራም የሚኖረውም በቤት ውስጥ ነው ። ቤቱም የሚሠራ በብዙ ድካም ነው ። ስለዚህም የኤሮፓ አገር በሬ የሚያወጣው ዋጋ ብዙ ነው ያልተደከመበት ነገር ዋጋ አያወጣም ። ወደ እየደኑ ሄዶ አጋምን ለቅሞ የሚበላ ሰው ሄዶ እስኪ መጣ ድረስ ከሚደክመው መንገድ በቀር ሌላ ዋጋ አይፈጅበትም ። ተለቅሞ ወደ ገበያ የመጣውን አጋም ሊበላ ቢፈልግ ግን ዋጋ ሰጥቶ ነው ።

ከዚህ የቀረው በሚከተለው ይታተማል።

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት መጽሐፍ ነው ፤

ስለ ብርሃንና ሰላም ኃዘን ።

፲፱፻፲፱ ዓመተ ምሕረት ታሕሣሣ ፳፩ ቀን እመቤታችን ስለሆነች በዓል ነበረና ከቤተ ክርስቲያን ተመልሼ ከቤቴ ተቀምጬ ብርሃንና ሰላምን ስጠብቅ ልክ ባ፬ ሰዓት መጣልኝ እኔም የምጠብቀው እሱኑ ነበረና በደስታ ተቀብዬው እንጨዋወት ጀመርን በዚሁ በጨዋታችን መካከል አግብቶ ይኸው ከቤትህ ስመላለስ ባንድ ነገር እንኳ ምክንያት የቀጠሮዬን ቀን ሳላሳልፍ ይኸው ዛሬ ሁለተኛ አመቴን ጨረስኩ ብሎ በተናገረኝ ጊዜ የድካሙ ብዛት ትዝ ብሎኝ ። እኔም ይህን ትንሽ ቃል ለመጻፍ አሳሰበኝ ። ጌቶቼ ሆይ ይህ ብርሃንና ሰላም ዘወትር እየተመላለሰ ድካሙን ሳይቆጥር ያሳስባችኋል ። ግን ለድካሙ ዋጋ ያገኘ አይመስልም ይኸውም ሊታወቅ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር አምሳ ሁለት በሁለተኛው አምድ በሀያ ሶስተኛው መስመር ። እንደ አዳል በረሀ አሽዋ የተቀበሉትን በረከት እየጠጡ መዳረሻው ማጥፋት ትልቅ ኃጢአት ነው ብሎ የብስጭት አነጋገሩን ጽፎአል ። ነገር ግን ለኔም እንደሚመስለኝ እውነቱ ነው ።

እስኪ አሁን በረሀብ ሊሞት የቀረበ ሰው ነገ ወይም ከነገ ወዲያ እጅግ የጣፈጠ ምግብ አዘጋጅተን እንሰጥሀለን ቢሉት በተስፋው ይድናልን ። ለጊዜው ጥቂት ካልሰጡት ። ይህም አረማመድ የዘገየበት ምክንያት ። ከታች ወደላይ የሚገፋ ነውና ከባድ ስለ ሆነ ይመስለኛል ።

ከላይ ወደታች የሚገፋ ቢሆን ግን ምንም ከባድ ቢሆን በፍጥነት ካሰቡበት ቦታ ይደርሳል ። ከታች ወደላይ የሚገፋ ከባድ ሸክም ግን ወደላይ እንገፋለን ሲሉ እሱ ከፍ ማለቱ ቀርቶ ። የሚገፉት እርስ በርሳቸው ይጋፋሉ ። አሁን ዛሬ ለኢትዮጵያ የማያስፈልጋትን የላይኞች (ጌቶች) ወደታች ቢገፉት ሌላውስ ይቅርና ብርሃንና ሰላም ማስታወስ ከጀመረበት ቀን ጀምሮ እስካሁን ብዙ እርምጃ እንዲራመድ አይጠረጠርም ።

ይኸውም ሊታወቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ። ስንኳን ለጌቶቹ ባላገሩ ከጭቃ ሹም ቃል ። ወታደሩ ከምሳ አለቃው ቃል እንዳይተላለፍ የታወቀ ነው ። አሁንስ ማነው ብርሃን ልግለጽልህ ቀምበር ላቅልልህ ሲሉት በደስታ የማይቀበል ። ዛሬ ግን የቀስታ አለመሆኑን ማንም አይስተውም ። አንድ አንድ ድሀ ሌሊት እንኳ እንቅልፍ አጥቶ ቢያስብ ስንኳን ብዙ ነገር ለሚያስፈልጋት ኢትዮጵያ ለዕለት ራቱ አይተካከልለትም ። ታላላቆቿ

እርስ በርሳችሁ ተስማምታችሁ ብታስቡላት ግን ፡፡ ስንኳን ለኛ በጠረፋችን ላሉ ዜጐቻችን በፍጥነት ፍጹም ስልጥንናን እንድ ታደርሱላቸው አይጠረጠርም ።

ይህን ያልታረመ ቃል ጽፌ ላቀርብላችሁ ያደፋፈረኝ ምክንያት ስንኳን እላንት ታላላቆቹ ስማችሁ በታሪክ ነገሥት ተጽፎ ልጅ እስከልጅ ሲነበብ የሚኖረው ። እኔ እንኳን እንድ ድሀ ስሜ የማይታወቅ ። ኢትዮጵያ ለዘለአም ትኑር ። ይልቁንም በጊዜዬ ክፋቷን አታሳየኝ ብዬ ፈጣሪዬን እለምናለሁ።በነገሌ ጊዜ እንደዚህ ተደረገ መባልን እሳስበችኋለሁ ፡

ግራዝማች ወልደ ዮሐንስ ወልደ አብ ፤

የመልካም መታሰቢያ በዓል ።

ታኅሣሥ ፲፮ ቀን በተደረገው በፍቅርና በአገልግሎት ማኅበር ዓመት በዓል ከግብዣቸው በኋላ ከማኅበረተኞቹ እያን ዳንዳቸው ከዚህ የሚከተለውን የምርቃን ቃል ተናገሩ ።

ክቡራን ጌቶቼና ወንድሞቼ ሆይ ፡

ከተወለድን ጀምረን በያንዳንዳችን እድሜ ያየነውና የተካፈልነው ልዩ ልዩ የሆነ ደስታ ምንኛ ብዙ ነው ነገር ግን ሁሉ አካል ነው እንደ ዓይን አይሆንም ሁሉም ጣፋጭ ነው እንደ ወይን አይሆንም እንደ ተብለ ከዚህ በፊት ያየነውና የተካፈልነው ደስታ ለእለቱ በስተቀር ከለፈ ወዲያ የማይታሰብ አላፊ ስለ ሆነ እንደ የዛሬ ደስታችን አይሆንም ። የዛሬ ደስታችን ግን ለዘለዓ ለም የማይረሳ በኛና በወንድሞቻችን በእውነተኞች ኢትዮጵያ ውያን ልብ ጽላት ተጽፎ የሚኖር ደስታ ነው ነገር ግን የዚች ማህበር ተካፋዮች (የሆኑ ወንድሞቻችን) በመንግሥት ጉዳይ ተልከው በውጭ ስፍራ ስላሉ ለዛሬ ደስታችን ተካፋዮች ስላ ልሆኑ ለለቱ እጅግ ያሳዝናል ግን ተስፋ የሌለው ሀዘን አይደ ለም ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ እኔ ከላንተ ብርቅ በሥጋ በመንፈስ ከላንተ ጋራ ነኝ እንዳለው እነሱም ምንም በሥጋ ከኛ ቢርቁ በመንፈሳችን አልተለያየንም ስለዚህ እግዚአብሔር በዚህ ላለንና በውጭ ላሉ ወንድሞቻችን እድሜና ጤና ፍቅ ርና አንድነትን ሰጥቶ ላገራችንና ለመንግሥታችን የሚረባ ሥራ ለመሥራት እንዲያበቃን በፍጹም ልቤ እንደተመኘሁ በውጭ አገር ስላሉ ወንድሞቻችን ጤና ይልቁንም ለነጻነታችን ብር ቃት ለሰንደቅ አላማችንም ጽናት የሆኑ ስለ ግርማዊት ንግሥተ ነግሥታታችን ዘውዲቱና ስለ ልዑል ኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሻችን ተፈሪ መኰንን ጤና ጽዋዬን እጠጣለሁ የኢትዮጵያ ነጻነት ለዘለዓለም ትኑር ።

መንገሻ ክፈላ

ክቡራን አባቶቼና ወንድሞቼ ሆይ ።

ይህን ማኅበር ለመወጠን እነሣሥቶ እስከ ዚህ ደረጃ ላደረሰን አምላክ ክብር ምሥጋና አቅርቤ የሚከተሉትን ቃላት እናገራለሁ ።

ይህን ማኅበር ስንጀምር ለሀገር አገልግሎት ስንል ነው ። ይህንኑም ለማስረዳት ስማችን ይመሰክራል ። ደግሞም በስንት ጭንቅና ፍርሃት የነበርን ሕፃናቶች ዛሬ ስማችን ታውቆ የሺ ማግሌ ጓደኞች ሽማግሎች ተባልን ። ይልቁንም ሥራችን ሰፍቶ መንግሥትና ሕዝብ እየረዳን የደስታ ኒሻን በመሸለማችን ሙሉ ጓደኞቻችንን ያስከብራል ያሰምናልም ፡፡ ለዚሽውም ከወንጌል ትንሽ እጠቅሳለሁ ፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሳለ ሐዋርያት ለሱ ሲያገለግሉና ሲረዱ አይሁድን ይፈሩ ነበር ኋላ ግን በጸሎተ ሐሙስ ከጌታችን ማዕድ ተካፈሉና በጰንጠ ቆስጤ ጰራቅሊጦስ ከወረደላቸው በኋላ ሥራቸው ። ለማስፋት በየሀገሩ ተዘርተው ያለ ፍርሃት ወንጌልን እንደ ሰበኩ እንዲሁ እኛም የልዑልን ረድኤት አግኝተን ከጌቶቻችንና ከባቶቻችን ጋራ ሰደቃ ከተካፈልን በሐዋርያት አድሮ ሥራቸውን ያሰፋ አምላክ ሥራችንን ያከናውንልን ፡፡ ነገር ግን ሐዋርያት ሥራ ቸውን ያሰፉ በፍቅርና በትሕትና ነውና እኛም ያለምቀኝነት ከሠራን ሥራችን እየሠፋ እንዲሄድ አይጠረጠርም ። ነገር ግን ሰይጣን እንኳን እኛንና ሐዋርያትንም ተጋደላቸው ፡ የጸኑት ጳኑ ያልጸናው ይሁዳ ግን በክፉ መንፈስ ተታለለ ፤ ክብሩንም ለውርደት ጣለ ፤ አሁንም እኛ በክፉ መንፈስ ተታለን ክብራች ንን እንዳንጥል ጽኑ መንፈስ ይስጠን ፡ ማኅበራችንን ያስፋ ከመ ካመካከላችንም ከመ ጨመር በቀር ፩ ሳይጐድል ረጅም ዕድሜና ጤና ይስጠን ስል ጽዋዬን እነሣለሁ ።

መስፍን ቀለመ ወርቅ

ክቡራን ወንድሞቼ ሆይ ።

ከዚህ ቀጥዬ የምናገረውን ቃል ለመስማት ፈቃዳችሁ እንዲሆንልኝ እለምናለሁ ። ስለ ሀገራችን ሴቶች ምስጋና ይኸ ውም የተገባ ምስጋና መሆኑን በሚከተለው ቃል አስረዳለሁ ።

የፍጥረት እውቀት በተከናወነበት በኤውሮፓ አገር ትም ርታቸው የበዛ የኢውሮፓ ሴቶች ወንዶች በሚጀምሩት የሕ ዝብ ሥራ ሁሉ ስለ ሀገራቸው ጥቅም በሚነካው ነገር ለመር ዳት ሁል ጊዜ ስላሰቡ እስከሁን የሚገልጹበት መንገድ አላገ ኙም ፡፡ አሁን ግን በፍቅርና በአገልግሎት ማኅበር ውስጥ ሁለት ሴት ወይዘሮች አገራቸውን ለመርዳት ሲሉ ከዚሁ ማኅ በር ገቡ ። ማኅበሩም በትልቅ ደስታ ተቀበላቸው ። እነዚሁም ሴቶች ክብርት ወይዘሮ አስቴርና ክብርት ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ ናቸው ።

ከማኅበሩም በመግባታቸው ከዓለም ሴቶች ይህን የጀመሩ እነሱ ብቻ ናቸው ተብለው ሊቆጠሩ ይገባቸዋል ። እነሱን እየ ተመለከቱ ብዙዎች እንዲመስሏቸው ተስፋ አለኝ ። አሁንም በተለየ ስለ ነሱ ክብርና ስለ ኢትዮጵያ የነፃነት ሰንደቅ ዓላማ ጽዋዬን እነሣለሁ ።

ዓለማየሁ ጤና

በከተማና ባገር ቤት ሥራ ፊት እየሆነ አገር ለሚያ ውቅና እከተማ ለሚቀመጥ ወስላታ ። አቋጅ ።

ይኸውና የመታመኛወረቀት አውጥተናልና እስከዚህ ቀን ድረስ የከተማም ሰው እከተማ ያገር ቤትም ሰው አገር ቤት እንድ

ትቀበሉ ይሁን ። እስከዚህ ቀን ድረስ ያልተቀበለ ግን መቀጮ ይኸን ያህል ይከፍላል ብሎ አዋጅ መንገር ነው ። የመታመኛ ውንም ወረቀት ጉርድ አበጅቶ ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ያለ ማድረግ ነው ።

የወታደር መታመኛ ወረቀት ።	የባላገር መታመኛ ወረቀት ፡	የነጋዴ መታመኛ ወረቀት ፡	የሻለቃ ሎሌና አገልጋይ መታመኛ ወረቀት ።	የካህን መታመኛ ፤ ወረቀት ።
የሻለቃው ስም ።	አገሩ ።	ሰፈሩ ።	የጌታው ስም	የደብሩ ስም ።
የሻምበሉ ስም ።	ያገረ ገዢው ስም ።	ቦታው ።	ሰፈሩ ።	አለቃው ።
የመቶ አለቃው ስም	ወረዳው ፤	የንግዱ አይነት ።	አገሩ ፤	ሰፈሩ ፤
ያምሳ አለቃው ስም	የምስለኔው ስም ።	አገሩ ።	የራሱ ስም ።	የመሬቱ ግብር ።
ሰፈሩ ።	የጭቃ ሹም ስም ፡	ያባቱ ስም ፤	እድሜው ፤	የራሱ ስም ፤
ያባቱ ስም ።	መሬቱ ፤	የራሱ ስም ፡		እድሜው ፤
የራሱ ስም ።	ጭሰኛነቱ ፤	እድሜው ፡		
እድሜው ፡	ያባቱ ስም ።			
	የራሱ ስም ።			
መልኩና ልዩ ምልክት	መልኩና ልዩ ምልክት	መልኩና ልዩ ምልክት	መልኩና ልዩ ምልክት	መልኩና ልዩ ምልክት

ይኸን የመታመኛ ወረቀት የሚቀበል መንግሥት እንደቆረጠለት ልክ አንድ ወይም ሁለት መሐለቅ እየከፈለ ቢቀበል መንግሥት ፫ ጥቅም ያገኛል ። መጀመሯ በከተማና ባገር ቤት ያለውን ነዋሪ ለማወቅ ይችላል ። ፪ኛ በዚህ በመታመኛ ወረቀት የሚገባው ገንዘብ አንድ ሥራ ይይዝለታል ፤ ፫ኛ የከተማ ሌባና ያገር ቤት ሽፍታ አለቃና ጌታ ወይም ሌላ አላፊ ስለ አልኖረው ይኸን የመታመኛ ወረቀት ለመውሰድ አይችልምና ሌብነቱ በቶሎ ይገለጣል ። ለዚሁም ሥራ መታመኛ ወረቀት የተቀበለውንና ያልተቀበለውን መርማሪ ያስፈልጋል ። የኸውም መርማሪ የሆነ ሹም የመታመኛ ወረቀት ያሊያዘውን ሰው ይዞ ወደ መታመኛ ወረቀት ሰጭ ዳኞች ወስዶ ይሰጣል ። እነዚያም ዳኞች አዋጅ ከተነገረበት ቀን ጀምረው ሰውየው እተያዘበት ቀን ድረስ አስበው መቀጫውን በጉርድ ወረቀት ይቀበላሉ ። ለሠራተኞቹም ደመወዝ ከዚሁ ይቀበላሉ እንጂ መንግሥት ከግምጃ ቤት አውጥቶ መስጠት የለበትም ። ይኸንንም የመታመኛ ወረቀት የሚቀበሉ ሰዎች ትልልቅ ሰዎች እንደሆኑ በራሳቸው መታመን ለመቀበል ይችላሉ ። የቀረው ግን ወታደር ያለቃውን ማኅተም ወይም ፊርማ አምጥቶ ይወስዳል ። የከተማ ነጋዴም ከንግድ ምንስቴሩ ወይም ከዲረክተሩ ማኅተም አምጥቶ ለመውሰድ ይችላል ። በውጭ አገር ያሉ ነጋዴዎችም ባውራጃው ካሉ ከመንግሥት ነጋድራሶችና ወይም ከየሻለቃው ነጋድራሶች ማኅተም አምጥተው እዚያው አገራቸው ላይ የመታመኛ ወረቀት ለመስጠት ከታዘዙት ሠራተኞች ይቀበላሉ ። ኪራይ ሠራተኞችም መንግሥት ከሾመላቸው አለቃቸው ማኅተም አምጥተው ይቀበላሉ ። ሁሉም በየሥራው የመታመኛ ወረቀቱን ሲቀበል ወስላታና ሌባው በዚህ ጊዜ ይለያል ። የመታመኛ ወረቀትም የጠፋበት ሰው ለሹም ነግሮ ጉርዱን አሳይቶ አንድ ተሙን ወይም አንድ ቤሳ ከፍሎ እንደገና የመታመኛ ወረቀት ይቀበላል ፤ የመታመኛ ወረቀት የያዘ ሰው እመንገድ በሄደ ጊዜ እንደልቡ እመሸበት ቦታ እማንም ቤት አድሮ ለመሄድ ይችላል ። አሳዳሪውም ሰው እንግዳውን አለስጋት አክብሮ ይቀበላል ። ዛሬ ግን እንግዳውም ደህና ሰው ቢሆን ባለመተማመን እንግዳውም አሳዳሪውም ። ሁለቱም ተፋጠው ያድራሉ ። ይልቁንም ከብት ያልያዙ ሰዎችና ወይም አንድ መንገደኛ እመንደር ተጠግቶ ለማደር ብዙ ችግር ነውና እንግዳ አዳሪው ለባለ ቤቱ የመታመኛ ወረቀቱን ካሳየው ባለቤቱ እንዲያሳድረው ማስገደድ ነው ። ስለ አሳደረውም መሣፈሯ ቦታ ይሰጠዋል እንጂ ባለቤቱ ካልሰጠው በግድ ለራሱ ምግብና ለከብቱ ምግብ ለመውሰድ አይችልም ። የመታመኛ ወረቀት የያዘ ሰው አደረበት ቤት ክፉ ሠርቶ ቢሄድ አሳዳሪው ሰውዬ መታመኛ ወረቀቱን አይቶታልና የጉርድ ወረቀት ለማስጠት ማኅተም የሰጠው አላፊ ሆኖ ሰውየውን ሊያቀርብ ይችላል ። ይልቁንም ይኸን የመታመኛ ወረቀት ያልያዘ ሰው የሰው ገንዘብ ይዞና ሰርቆ ለመሄድ አይችልም ። የከተማ ዳርቢበኞችም ከከተማ የሚወጣውን ሰው የመታመኛ ወረቀት መያዙና አለመያዙን መመርመር ያስፈልጋቸዋል ። መንግሥትም ፈቃድና ገቢ ገንዘብነው እንጂ ወጭ የለበትም

በካህንም ወገን ባህታዊ ነኝ እያለ እያታለለ በሰው ድካም አዳሪው ይገለጻል ይኸንንም መጻፌ የታሰበኝን ልግለጸው ብዬ ነውና የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ባነበባችሁት ጊዜ ትንሽ አሣቤን በትልቁ እውቀታችሁ እንድታርሙትና እንድትሞሉት እለምናችኋለሁ ።

ልጅ አበበ ወልዴ ።

ናሁ ሰማዕናሁ በኢትዮጵያ ወረከብናሁ ውስተ አዲስ አበባ ንበውእ እንከሰ ውስተ አብያቲሁ ለኃይለ ሥላሴ ወንሰግድ ውስተ መካን ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ ። መዝ ፻፴፩ ፮ ፯ ተንኰል ኄሮድስ ነግሦበት በነበረ ዘመን ፤ የተፈራ ፅፃ በምትሆን በቤተ ልሔም አዲስ አበባ ፤ ጌታችን መድኃኒታችን ብርሃንና ሰላም ተወልዶ ሳለ መልካም ሐሳቦች ሰብአ ሰገል በለዓም ተስፋ ከከብ ይሠርቅ እምኃይለ ሥላሴ ወያዓትት ኃጢአተ እምእስራኤል ያለውን ሰምተው ከማስተዋል ምሥራቅ ተነስተው የተወለደው የእስራኤል ንጉሥ ብርሃንና ሰላም ወዴት አለ እያሉ ከመመርመር ኢየሩሳሌም ደረሱ ። ምሳሌው የሚሆን ኮከብ ጥበብን እያየን ልንሰግድለት መጥተናልና ብለው ተንኰል

ኄሮድስም ይህን ሰምቶ ደነገጸ አዘነ ። የሰው ልቡና ከተማዉ ቱም ከሱ ጋራ እንደሱ ተደረጸች ። ጸሐፍትንም ሁሉ ሰብስቦ ብርሃንና ሰላም ክርስቶስ ወዴት ይወለዳል አላቸው የተፈሪ ዕፃ በፓትሆን በቤተ ልሔም አዲስ አበባ ነው ። የተፈሪ ዕፃ የምትሆኝ አንቺም ቤተ ልሔም አዲስ አበባ የይሁዳ ነገሥታት ከነገሡባቸው አህጉር ብትበልጭ እንጂ አታንሽም ወገኖቼ እስራኤልን የሚጠብቃቸው ብርሃንና ሰላም ንጉሥ ባንቺ ይወ ለዳል የሚል ጽሑፍ አለና አሉት ። ሚክ ፭ ፪፡ ዮሐ ፯ ፵፪ ከዚህ በኋላ ተንኰል ኄሮድስ መልካም ሐሳቦች ሰብአ ሰገልን በቆይታ ጸርቶ ኮከብ ጥበብን ያዩበትን ቀን ጠየቃቸው ይህን ኮከብ ጥበብ ካያችሁ ምን ያህል ቀን ሆኖታል ብሎ ፪ት ዓመት ሁኖታል አሉት ። ለካ ያም ብላቴና ሁ፪ት ዓመት ሁኖታል አለ ወዲያው ከቤተ ልሔም ሐዲስ አበባ ነው ሂዳችሁ የብ ላቴናውን ነገር ጠይቃችሁ ድርሱን ያገኛችሁት እንደሆነ በኔ በኩል ተመልሳችሁ ንገሩኝ እኔም መጥቼ እሰግድለት ዘንድ አላቸው ። እንዲህ ማለቱ ግን ለተንኰል ኄሮድስ ሸንገላ ልማ ዱ ነውና ሲሸነግላቸው ነው እንጂ እገድለው ዘንድ ሲላቸው ነው ። እነሱም ምንገዳቸውን ሄዱ እነሆም በማስተዋል ምስራቅ ያዩት ኮከብ ጥበብ ሐዲስ አበባ ቤተ ልሔም እስኪያደርሳቸው ድረስ ይመራቸው ነበር ። እሱም ካለበት ሲደርስ የሚመራቸው ኮከብ ጥበብ ቆመ ከቤትም ገብተው ብርሃንና ሰላም ብላቴናን ከእእምሮ እናቱ ጋራ አገኙት ከድንቁርና ፈረስ ከምቀኝነት ሠረ ገላ ወርደው መላልሰው ሰገዱለት ሣጥን ልቡናቸውንም ከፈቱ ። እውነተኝነት ወርቅንና ፍቅር ከርቤ ተስፋ እጣንን እጅ መንሻ አገቡለት ከዚህም በኋላ በተንኮል ኄሮድስ በኩል እንዳይመ ለሱ በራዕይ ነገራቸው በሌላም የእውቀት ጐዳና ወደ ማስተዋ ል ሃገራቸው ተመለሱ መልካም ሐሳቦች ሰብአ ሰገልም ከሄዱ በኋላ ከእግዚአብሔር የታዘዘ ትምርት መልአክ ለትእግሥት ዮሴፍ በሕልም ነገረው ተነስተህ ብርሃንና ሰላም ብላቴናውንና እእምሮ እናቱን ወደ አዋቆች ልቡና ግብፅ ይዘህ ውረድ ተመ ለስም ብዬ እስክነግርህ ከዚያ ኑርተንኰል ኄሮድስም ብርሃንና ሰላም ብላቴናውን ሊገድለው ይሻው ዘንድ አለውና ብሎ ተነስ ቶም በሌሊት ሄዶ ተንኰል ኄሮድስም እስኪሞት ከዝያው ኖረ ሆሴዕ ፲፩ ፩ ተንኰል ኄሮድስም መልካም ሐሰቦች ሰብአ ሰገል እንደዘበቱበት በየ ጊዜ ፈጽሞ ተበሳጨ በቤተ ልሔም ሐዲስ አበባና ባውራጃዋ ያሉትን ሕጻናት ግደሉ ብሎ እነመጣላት እን መከሰስ እነቅናት ምቀኝነት ንቀት ቸልተኝነት በዘንተኝነት መታከት ውስልትና የሚባሉ ጭፍሮቹን አዝዞ ሰደደ ያን ጊዜ በነቢዩ በሁከት መንፈሳዊ ኤምርያስ የተባለው ደረሰ ተፈጸመ እንዲህ ሲል ድምፅ በራማ ኢትዮጵያ ተሰማ ልቅሶ ዋይታም እጅግም ጩኸት የትምህርት ቤት ራኄል ልጆችዋ ስታለቅስ መጽናናትም አልተቻላትም ልጆችዋ ልጅ አልሆንዋትምና ብሎ የተናገረው ትንቢት ደረሰ ተፈጸመ ። ኤር ፴፩ ፲፭፡፡ማቴ ፪ ፩ ፲፰፡፡

ተንኰል ኄሮድስ ግን መልካም ሐሳቦች ሰብአ ሰገል ብር ሃንና ሰላም ክርስቶስ የተወለደበትን ቦታ አግኝተው ሳይነግሩኝ ወደ ሃገራቸው ሔታለውኝ ይሄዳሉ ብሎ ሽፋጭነት እሩር የሚ ባል አሽከሩን ተከትለህ ሂደህ አይተህ አብረህ ተመለስ ብሎ ልኮት ነበርና ከዚያ ሲደርስ መላእክት አስተማሪዎች በመት ጋት ሰይፍ ኖሎት ተማሪዎች በመንቃት ዱላ ገና ተጫወቱበ ትና ሰባብረው ጣሉት በዚህም በገና ጨዋታ ጊዜ አንድ መታ መን የሚባል ዘፋኝ እያወረደላቸው እነመረዳዳት እነመጠቃቀም እነጀምሮ አለመተው እነ የኋላን ማሰብ የሚባሉ አርበኞች የነዚህም ሁሉ ወገኖች ብዙ ሕዝብ እንዲህ ብለው ዘፈኑ መዝ ፸፫ ።

ተፈሪ ዓልጋ ውጣ ቀብቶሃል እግዚአብሔር። ግሩም ዚንጎግራፊ አምጥተህ ብትክብር። ሔዋን ርስትህም በዘራሃት ዘር። ውጅግሬ ዲሞ ትሮር ቱኪ ወታደር። ዓልያዘም ብረቱን የለበትም ስክር። ሙቱዋልና በፊት ተንቀጥቅጠ ፈርቶ። ሪም ወርሶ ነበር በጎነቱን ረሰቶ። በረታም ሰነፈም ላባቱ ምድር። ብቻውን ሔደበት ሮምን ወታደር። ማንም ጎዝቡ ን ደፍሮ ሩቅ ሂደ ውሥጡን። ሰሙም ተመሰለ ጽንዕ ዮሐንስን። ንጉሥ ወርደ በኃይል ህዝቡን የሚያድን። ሰልጥንዋል በምክሩ ረሰቶ ኃኬቱን። ይህም ለሱ ቀድሞ ስውር ትብትብ ወገን። ልቡ ታውኮበት ወጣቶት ኰላሊቱን። ናቀው ተፋቀረው ወደደው ፀላቱን። በገሩ ኢትዮጲያ ተክቶ ወዳጁን። በቃ ሀማም የለም ሰፋች በሥልጣን። ረጋች አረፈች ቀድስት ርስታችን። ተቀድሞውም አሁን ንጉሥ ተክቻልን። ታሪኳን በመጻፍ ርቱዕ ሀጓን ። መጣልን ንቁነት ክርክር ረሳን ። እንዳዪህ ምን አለ ድክም በደበዛብን ። ርኣራኒ ዘወትር ለሁሉ ዓዘን ። ለጋሱ ምኒልክ ደጣሞም ንጋሥታችን። ገድላቸውን ጼመው ኰስትር ሎሌንትን ። ሙታን እሕዛብም ብለው ዳኛችን። ነገ ልናይ ብርሃን ሐሰት ለምናችን። ሙሉ ሕግ ልንሠራ መች ወደድን እንዳችን። ልባችን በዝኖ ዘንጣተን ረሰት ን። ከሱ ቡራኬማ ኰርማን ሎክ ሰጥቶን። ብንሞትም እንኳ ለጭራሽ ብናዝን። እሱ ለኛ እረፍት ደስታ ዊደሁን ። (አዎን) ሁከት እንዳደመ ጣ ምክር ተማከረን ። ግን ሣንማር ጽፈት ከቀረን ወድቀን ። ራብ ሴራ መክሮ ንቆን ግፈ ሥራ ትቶብን ። ደጣሞ ቀላቅሎብን ሹማሌን ኰሎን ። ሎሌ ሙሉ እርስት ለክተን ይዘን ። ጌዋ አስመልሶን ኑረን አገራችን። ፍጹም ራስ ሰጥቶ አብዝቶ ንቃትን። ተስማምቱዋል ሰልጥንዋል ግማሹን ሩቡን ። ምክሩን አሰምቶ ንጣር ተሰጠን ።

ወጣድ መክራክር ኑፋቄ ይቅርልን ። ትእግሥት ቃልህን ወይም ሞገስ ህን ። ለኛ መርቅና ዓገር ትልማልን ። ከብረን እንድንኖር ምክር ሰፍቶል ን ። ማር ይፈልቃ ታፋ ፀጅስ ምን ዕዳችን ። ፍትፍቱም ትርፍ ሐብ ት ምሳ ድርጓችን ። ርስትና ኒሻን ፈቅደው ርቱዓን ። ሃር ትፍትፍ ወርቅ ም አደን ርጣብ መጥቶልን ። መክዳ ትራስም ሰራ በዝቶልን ። ተደረገ ንጥም ሥራ አስቀልን ። ኃገርም ይቀናል ለምለሙ ሥፍራችን ። ላን ድ ሴት ለምኑ ኮከብ ንጣሥታችን ። ኖራልን ከሸዋ መሬት ያገኘን ። ድኖች ጎናቱዋ ኖረን ሙላችን ። ለሱዋ ኰስትር ሎሌ ሙጣት የረሳ ን ። ዋኖች ሃብታሞች ነን ልጆችም ብንሆን ። እንተው ስንፍናን መሥ ራት እናፍጥን ። ምናልባት ፈጣሪ ቃል ዱላ የሰጠን ። አውጥቶ ምሥ ጢሩን ነገር ከቀረልን ። ሰላም ብርሃን እንደ ወጣድ እንቀልፋችን ። ም ክር ተፈጸመ ረዝሞ ፈቃዳችን ። ሕጉም ሊጸናልን ናፈቀ ሆዳችን ። ሙ ዳደ ይጣበ ገንዘብ ብር ሩባችን ። በተፈሪ ዓበበ ለማ ከተማችን ። ብንፅ ራ ፅኑ ዓምባ ወርሰን ሀገርን ። ቡቃያ ለምለሙን ኃብቱን ይስጥልን። ለተፈሪ ሥልጣን ላንደበቱ ሴፍን ።

እንማር ግዕዙን ዚቅ እንድንተው ንን። ኰፋር ሎፊሳውን ሙካሽ እስር ለብሰን። ዓለም ውስጡ ዱሩ ያድራል በሥልጣን ። ውድማ ዑጋዴንም አለማው ምድሩን። ኃገር ለማ ግብሩ ሩፋውን ምንጩን። ዘርፎ ያበላ ውን ወደ ጽጋቡን ። እያየ ነገሩን ፍዳ ሰክ ሙቶልን። ለራሱ መንጣ

ሥትን ላገር እንቅልፍን። ክርክር ትክትክ ወጥቶ ይሂድልን ። ጌታችንም
ርስት ምድር እንዳያምረን ። ምኒስተር ነው ንጋሮው ሥልጣኔ ተፈሪያችን።
ምንም ድኩም ርካሽ ስጉዎች ብንሆን። ሐብታችን ትጋቱ ለኛ አያስጋን።
ብለን ወጣን ወረድን ልጆች ድካም ወደን። መልካም ንጉሥ ፈጥሮ
ስልጣን ቀባቱን ። ዱዳችን ስፍራችን ለምቷል ዓገራችን ። ለአምላክ ምስጋና
ወክብር ለጌታችን ። ዓምላክ ለሱ መርቅ ዓብዛ ለኛም ምግብን ።

እንዲህም እያለ ሲዘፍን በጣም ደስ ያሰኝ ነበር ። ዘፈኑንም ለመስማት ቁጥራቸው ከሰማይ ከከብ ከባሕር አሸዋ የሚበዛ ሕዝብ ከምሥራቅና ከምዕራብ ከሰሜንና ከደቡብ ተሰብስበው ነበረ ። እኔ ግን ትንንቁንና ግፊያውን ፈርቼ በሩቅ ቁሜ አደምጥ ነበር ። ስለዜህ ጨርሼ ባለ መስማቴ የዘፈኑን ቋንቋውንና ግጥሙን አስተካክዬ አልጻፍሁትም ። ከዚህም ሁሉ ሕዝብ ቀርበ የሰማ አይታጣምና በብርሃን ልቡናችሁ አርሙልኝ እንጂ አትንቀፉብኝ ስል ለብርሃንና ሰላም ወዳጅ ሁሉ በፍርሃት አመክታለሁ ።

ሞገስ ዓምደ ሚካኤል ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሆፒታል ቤተ ሣይዳ) ታክሞ ከቡቃ በሽታ የዳነ ሰው የጻፈው የምስጋና ቃል ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው

ከአስራሁለት ዓመት ቢፊት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ቡቃ የሚባል በሽታ አሞኝ በኢትዮጵያ የቡቃ በሽታ ጨርሶ የሚያስለቅቅ ሐኪም ባለ መኖሩ ። የጸና በሽታዬን ተሸክሜ ስራዬን ስሰራ እኖር ነበር ኋላም ለቡቃ በሽታ ጾም መጾም መልካም ነው የሚል ከንድ ደብተር ውስጥ አንብቤ አስራ ሁለት ቀን ጾምሁ በዚህም በጾም ሙሉ ጤና የማላገኝ ብሆን በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ሆፓታል ውስጥ ያሉ የታመኑና በስራቸው የተመሰገኑ ዶክተር ሀነርን ሰው ሁሉ በኦፓሬሲዮን ስራ ሲያመሰግናቸው ሰምቼ ባማክራቸው ለዚህ በሽታ ኦፖሬሲዮን ማድረግ መልካም ነው ብለው ኦፖሬሲዮን አደረጉልኝና በአስራራት ቀኔ በእግዚአብሔር ፈቃድ በደህና ወደቤቴ ተመለስሁ ።

እስከ ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያ ትልቅ አገር ሆና በገንዘብ የከበሩ የብዙመኳንንት እናት ሁና ለሕዝቧ ጤና የምያስብ አጥታ ትኖር ነበር ነገር ግን ታላቁ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ለሕዝባቸው ጤና መጠበቂያ የሚሆን ሆፒታል በመስራት የትምሕርት ቤት በማቆም ቤተ ክርስቲያን በመትከል ተግተው ለሁሉ እንደአባት እንደ እናት ሁነው ሕዝባቸውን ጠብቀው በመኖራቸው በዓለም እንደነገሡ ትልልቆች ነገሥታት ሰማቸው በምስጋና እንዲጠራ በታሪክ ሁሉ አንብበን ተረድተነዋል ።

ዳግመኛ የመልካሙን ንጉሥ ፍለጋ ተከትለው ለሕዝባቸው ጤና መጠበቂያ የሚሆን ሆፒታል በመሥራት የትምርትቤት በማቆም ቤተ ክርስቲያን በመትከል በጣም እንደተጉ በፍጹም ልቡናችን ተረድተን ርኅሩሁን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን ፈጽመን እናመሰግናቸዋለን ዳግመኛ በንግሥት ሥራ ድካም ሳለባቸው ያን ሳያስቡ በ፩ ሳምንት ፩ ሁለት ጊዜ እየገቡ በሽተኞችን ሁሉ በማየታቸው በሽተኞች በብዙ ደስ ይላቸዋል ስለዚህ የድካማቸውን ፍሬ እግዚአብሔር ብዙ ጤናና ዕድሜ ይስጣቸው

ሞዲ

ያገር ውስጥ ወሬ ።

በብረት መንገድ ስለሆነ አደጋ ።

ታሕሣሥ ፳፯ ቀን ወደ አዲስ አበባ በሚወጣው የጳስታ ባቡር ፩፻፴፱ ኪሎ ሜትር ከደረሰ በኋላ ዱኩም የሚባል ጣቢያ ባቡሩ ቆመና አንድ ሰው ወርዶ ባቡር ለመነሳት ዮጮኽ ጊዜ በፍጥነት ሳይወጣ ቀርቶ ባቡር መሄድ ከጀመረ በኋላ እወጣለሁ ብሎ ሲንጠላጠል ወድቆ አንድ እግሩን ከባቱ ስር ቆርጦት አለፈ ስለዚህ በባቡር ላይ ተሳፍሮ ለሚሄድ ሰው ሁሉ ባለመጠንቀቅ እንደዚህ ያለ ሀደጋ አግኝቶት ደሙ ካንቱ ፈሶ ሕይወቱን እንዳያጣ ባቡር በተሳፈረ ጊዜ የተጻፈውን ደምብ ተመልክቶ የሚያዘውን ትእዛዝ መጠበቅ ግድ የሚያስፈልግ መሆኑን እናሳስባለን ።

የውጭ አገር ወሬ ።

የወላጅ ሽልማት

በታሕሣሥ ፫ ቀን በማርሴል ከተማ በወጣው ሐይሲርድ በሚባል በአርመን ጋዜጣ እንደሚከተለው ተጽፏል ። ቤርናር ሽንቤርግ የተባለ ዕድሜው ሰባ ስድስት ዓመት የሆነ የነምሳ ሰው ሰማንያ ስምንት ልጆች ወልዶ ተገኘ ከኒህ ሰማንያ ስምንት ሰማንያ አራት ገና በሕይወታቸው አሉ ።

ይህ ሰው ሁለት ጊዜ ምሽት አግብቷል ፊተኛዋ ሚስቱ አራት ጊዜ አ ራት አራት መንታ ልጆች ወለደች ፡ ሰባት ጊዜ ሶስት ሶስት መንታ ልጆች ወለደች ፡ አሥራ አምስት ጊዜ ፪ት ፪ት ፡ አንድ ጊዜብቻ አንድ ልጅ ወለደች በድምሩ ካንድዋ ሰባ ልጆች ወለደ ። ከነዚህም ስሳ ሰባት ገና በሕይወት አሉ ። ይህ ሰውዬ ፊተኛዋ ምሽቱ ስትሞትበት ጊዜ ሁለተኛ ሚስት አገባና ከሁለተኛዋ ምሽቱ አሥራ ስምንት ልጆች ወለደ ከነሱ ፪ት ጊዜ በሶስት በሶስት መንታ እየሆኑ ተወለዱ የቀሩት ባንዳንድ

ማስታወቂያ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሙዋቸው በማተሚያ ቤታቸውም የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው፤

የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው ፡	፲ ብር

፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው ፤	፲	ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ ።	፭	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውርጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር ።	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፫	ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው ፤	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፪	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት ፤	፩	ብር
ያማሪኛ ሰዋስው ።	፭	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ፤	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን ።		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
ወዳጄ ልቤ ።		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ ።		አላድ
ያማሪኛ ፊደል ፡		ሩብ
አሳብና ምኞት ፤		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት ።		ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር ።	፪	መ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ፤	፩	ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰነደቅ ዓላማ ያጌጠ ።	፩	ሩብ

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ስንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

Berliet



ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ አቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚአን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ።

ARMENAK ZAMANIAN

AGENT GÉNÉRAL

Pour l'Abyssinie et Djibouti

ማስታወቂያ

በጥሩ የፈረንሳዊ አገር ጨርቅ ለኢትዮጵያ መኳንንቶች የሚገባ በጥንቃቄ የተሰፋ ካባ ከሙሴ ፕሪቶ ዘንድ ይገኛል ቤታቸውም በእንግሊዝ ባንክ ቤት አጠገብ ነውና ለሚገዙ ሰዎች ሁሉ በማክበር እናስታውቃለን።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉሙሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ሥፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልሀ ሐዲስ ከሚዎን ሞቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፪
3 me ANNÉE № 2

ሐሙስ ጥር ፭ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 13 JANVIER 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christos Taklé Haymanot
Diréctеur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ስፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ትዳር ።

አንዳንድ ወንዶች የቤታቸው መሠረት ሆነው የሚስታቸውና የልጆቻቸው መሪና አስተዳዳሪ በመሆን ፋንታ ወጥተው ወርደው ፤ አርሰው ነግደው ፡ በብዙ ድካም ያገኙትን ገንዘብ ለመሸታና ለሸርሙጣ ያበክኑታል ። ይህንንም ከንቱ የከንቱ ከንቱ ሥራ በመሥራታቸው ለልባቸው እረፍት ለኑሯቸው ደኅንነት ለቤታቸው ሕይወት የለውም።ይህም ከንቱ ሥራቸው አልበቃቸውም ብሎ ፈትለው፡ሰፍተው፡ፈጭተው፡ጋግረው፡የሞያ ውለው ለልጆቻቸውና ለቤት ሰዎቻቸው መልካም መብራት ሆነው የሚያሳድጓቸውን ሚስቶቻቸውን ፡ እንደ ክፉ ወንበዴ የዱላ መዓት ያወርዱባቸዋል ። ቤታቸውም ሁል ጊዜ ጠብና ሁከት ንዝንዝና ጭቅጭቅ፤በቀር ሰላም የለውም ። ሚስቶቻቸውም ባሎቻቸው ያለ የሌለ ገንዘባቸውን በመሸታና በሸርሙጣ ጨርሰው በዚህ ሥራቸው ሳያፍሩና ሳይጸጸቱ ከድካማቸው ላይ የግፍ ድርብ ቀለባቸው ዱላ ስለሆነ ተመርረው ከመፋታት ይደርሱና ባሎቻቸው እንደ ሥራቸው የከንቱ ከንቱ ሁነው ይቀራሉ።

አንዳንድ ወንዶች ግን በጋ በፀሐይ ክረምት በጭቃና በዝናም ላይና ታች እያሉ በብዙ ልፋት ያገኙትን ገንዘብ ወፍ ጥራ ግራ ያገኘችውን ለልጆቿ እንደምታቀብል ለሚስቶቻቸውና ለልጆቻቸው ይሰጣሉ ። ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸውም በብዙ ደስታ ይኖራሉ ። በቤታቸውም ጸጋና በረከት ፡ ሰላምና ደኅንነት ፍቅርና አንድነት ዘወትር የሞላ ነው ።

በዚህ ደግ ሥራቸውም መልካም መልካም ልጆቻቸውን በቅጣትና በሥርዓት ፤ በጥበብና በእውቀት በትምሕርትም በማሳደጋቸው ልጆቻቸው ለሀገራቸው ስፋት ለመንግሥታቸው ጽናት ይሆናሉ ። እንደነዚህ የሆኑ እናት አባቶቻቸውም የልጆቻቸውን ደግ ሥራና መልካም አካሄድ በመመልከት ሕይወታቸው በደስታ እየታደሰ ይኖራሉ ።

አንድ አንዶች ሴቶችም በቤታቸው እንደ መልአክ ናቸው አሳባቸውም ሥራቸውም ቤታቸውን የሚጠቅም ልጆቻቸውን የሚያሳድግ ባሎቻቸውን ደስ የሚያሰኝ ነው ። ባሎቻቸው ወደ ሥራ እንዲሄዱ ብርዱንና ውርጩን ሳይሰቀቁ ቀደም ብለው ማልደው ተነሥተው የሚገባቸውን አሰናድተው በደስታ በደኅንነት ይመልሳችሁ ብለው ያሰናብቷቸዋል ።

ለትዳራቸውና ለኑሮአቸውም በትሕትናና በገርነት ያስባሉና ይሠራሉ እንጂ በኩራት አይግደረደሩም የእንደነዚህ ያሉ ሴቶች ባል የሆኑ ወንዶችም ኑሮአቸው ደስታና ሰላም ነው እንጂ ንዝንዝና ጭቅጭቅ የለበትም (የመታደል ኑሮ ነው) ።

ብዙ ሴቶች ግን ሥራ ነውሬ የሆኑ ባማረ ቤት በተመቻቸ ፍራሽና በለሰለሰ ምንጣፍ ቁጭ ብለው ግራና ቀኝ አቀበት አቀበት የመሰለ መከዳ ተደግፈው ሲጠጡና ሲበሉ ፡ ሲስቁና ሲበርቁ የሚውሉ ይህንም አድርገው ጊዜ አልመሽላቸው ሲል ያለ ሥራቸው እየዞሩ ሥራ በትክክል የሚሠሩትን ሴቶች አበዝነው የማያስፈልግ በደኅና ሰው አፍ የማይነገር ወሬ ሲቀዱ የሚውሉ ይገኛሉ ። እንደነዚህ ያሉ ሴቶች ሠርተው ቤታቸውን ሊጠቅሙበት ባላቸውን ሊያከብሩበት ራሳቸውን ደስ ሊያሰኙበት የተሰጣቸውን ጊዜና ጉልበት በማጥፋታቸው ለቤታቸው ጉዳት ፡ ለባሎቻቸው ውርደት ለራሳቸው ጥፋት ፡ ሆነው በመሥራት ደኅንነት የሚያገኝ ጤናቸውን ያበላሻሉ በመንቀሳቀስ የሚቀል ሰውነታቸውን ትንፋሽ እስቲከለክላቸው ያከብዳሉ እንደዚህም በመሆናቸው ብዙ ዘመን ታሞ እንደ ኖረ በሽተኛ ያለደገፋ ሊነሡ አይችሉም (ይህም አለመታደል ነው) አንድ አንድ ሠራተኞች ወንዶችም ከሥራቸው ውለው ወደቤታቸው ሲመለሱ እንደ አቅማቸው በቤታቸው ደስ ይለናል ሲሉ እቃው እንዳልሆነ ሆኖ በመጠረግና በመጽዳት ፋንታ ጉድፍ ፡ በማጌጥና በማማር ፋንታ ቈሽሾ ዕቃው ሁሉ ተጕሳቊሎ ሲያዩት በጣም ይበሳጩና በእረ

ፍት ፋንታ ድካም።በደስታ ፋንታ ሐዘን ያገኛቸዋል።ወንድ ከው ጭ ከሥራው ደክሞ ሲመለስ በቤቱ ደስ ቢለው ትንሽ እረፍት ያገኝና ይጽናናል፡ይህም ደስታና እረፍት የሚገኘው ባሏ በውጭ ሥራ ሲደክም ሚስቱ ደሞ እግረ ዝርግ ሥራ ፈት ሳትሆን ባጭር ታጥቃ የቤቷን ሥራ ያለቻልተኝነት እንደሚገባ ስታሰናዳ ስታዘጋጅ ብትውል ነው፤ቤት ልባም ሴት ስትይዘው ምንም እንኳ ልዩ ልዩ ምንጣፍና ጌጠኛ ዕቃ ባይኖረው ያ የተገኘው የድኅነት ዕቃ በሥራት ሲከባከቡት ላይን ደስ ያሰኛል።ብዙ ውድ የሆነ የሐር ምንጣፍ አድሮ፡ ተጉላልቶ ተጐሳቁሎ፡ ተጨማዶ ሲታይ እጅግ ያስቀይማል፡ እውነትም ዕቃ እንደ ያገሯ ነው።በጭቃ ከተለወሰ የብር ዕቃ በጥሩ የተያዘ የሸክላ ዕቃ ደስ ያሰኛል፡እን ግዲህ ለትዳር እንቅፋትና መሰናክል የሚሆነውን ነገር እያስተ ዋሉ ወንዶች ለወንድ የሚገባውን ሥራና ሥርአት መፈጸም ሴቶች ለሴቶች የሚገባውን አገባብና አገልግሎት መፈጸም ያስ ፈልጋል።እንደዚህ ቢሆንም ቤታቸው የደስታና የሰላም፡ የጸጋና የሀብት፡ የፍቅርና ያንድነት ቤት ይሆናል ።

የከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ ሰው ሞኝ ታልሆነ በቀር ሰው ነቱን በመስተዋት አይቶ እድፉንና ጉድፉን ይጠርጋል እንጂ መስተዋቱን አይሰብረውም፡ እንደዚሁ ሁሉ ጋዜጣ የጉሮንና ያስ ተዳደርን ጉድለት ገልጦ ሲያሳይ ጉድለቱንና ጥፋቱን መተው ያስፈልጋል እንጂ ለምን እንደዚህ ያለ ቃል ጻፈብን ማለት እንዳ ይገባ ብርሃንና ሰላም ያስታውሳል።መድኃኒት የሚጠቅም በሽታ ቸውን ለሚያውቁ ሰዎች ነው ።

የ፫ ገጽ ተከታይ።

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

ስለዚህም ከውጭ አገር ለሚመጣልን ነገር ሁሉ ዋጋ የም ንሰጠው ስለሥራው ነው እንጂ ስለብዛቱ አይደለም። ያቡጀ ዲዱ ጥጥ እንጂ ሥራው ወዳገራችን መጥቶ ፍግ እንዳይሆንን የታወቀ ነው ።

እንግዴህ እውቀት አንሶት የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ በገዛ እጁ ለመሥራት የማይችል ሕዝብ የሚያገኘው ጉዳት ምን እንደሆነ ከተረዳነው ዘንድ ይህነን ጉዳትና ባርነት አጥፍቶ ወደ ሀብትና ወደአርነት የሚወስደውን መንገድ እናመልከት ።

ሀብት ማለት የተከማቸ ሥራ ማለት ነው ። ሰውም ነጻነት ያለው ነውና የድካሙን ፍሬ ሁሉ ለራሱ ቢያገኝ ነው ። እው ቀት የሌለው ሕዝብ ግን ሥራው አይከማችለትም ። የፊት የፊቱ ወዲያው ያልቃል ። ከድካሙም ፍሬ የሚያገኘው ጥቅም ጥቂት ነው ። ስለዚህ እውቀት የሌለው ሕዝብ ድኃና የሰው ሎሌ ነው እውቀትም ሳይጨምር እየበዛ ቢሄድ ድኅነቱና ሎሌነቱ እያደገ እየጠነከረበት ይሄዳል፡ ባንድ ሕዝብ ላይ እንደዚሁ ያለው መዓት እንዳይወርድበት እንግዴህ ምን ይበጀዋል ።

ምላሹ አጭር ነው ።

መጀመሪያ እርስ በርሱ በፍጥነት እንዲገናኝ ብልሃት ይበ ጅለት ። ሁለተኛ በየሥራውም እንዲሰለጥን የትምሕርት ቤት ይቁምለት ። ሶስተኛ ለሕዝቡ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ባገሩ ውስጥ እንዲሠራ ለቀረጡ የመንግሥት ሹማምንቶች ይጠብቁት እነዚህን ሶስት ቃላት ግን ለይተን ለየብቻቸው እንመርምራቸው

መጀመሪያ ።

እውቀት በሌለው አገር ውስጥ መነገድም የዖድር ባቡ ርም ቢሠራ ለጊዜው ይንቀዋል ። ለጊዜውም ብዙ ብር ይገባለትና ሀብቱም ያደገ ይመስላል ። ካንድ ባንክ ፲ሺ ብር የተበደረ ሰው አስሩን ሺ ብር አሽክሞ በመንገድ ሲሄድ መበደሩን ላላወቀ ሰው ሀብታም ይመስለዋል ። መበደሩን የሚያውቅ ሰው ግን ወዳጁ እንደሆነ ያዝንለታል ። ጠላቱም እንደሆነ ይንቀዋል ። እውነትም በዚሁ በ፲ሺ ብር ነግዶ ለራሱ የሚቆይ ትርፍ አግብቶ የተበደረ ውን ፲ሺ ብር ከነወለዱ በቶሎ ለባንኩ ካልመለሰ ተይዞ በወህኒ ይሞታል ። በሕዝብም ትዳር እንደዚሁ ነው ። እውቀት ያነሳቸው ሕዝቦች እውቀታቸው ከፍ ካለ ሕዝቦች ላይ ዕቃ ሲገዙ እየተበ ደሩ ነው ። የሚበደሩትም ብድር እኩሌታው ከጕልበታቸው እኩሌታው ከምድራቸው ነው ። ከጥር ፲፱፻፫ ዓ ም እስከ ፲፱፻፬ ዓመት ም ድረስ ። ማለት በፈረንጆች ቍጥር በ፲፱፻፲፩ ዓመት ከኤ ሮፓ በጅቡቲ መንገድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የመጣለት ዕቃ ዋጋው ቢታሰብ ፯ሚሊዮን ፯፻፰፯ሺ ፫፻፺፬ ብር ሆነ ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ካገሩ ወደ ኤሮፓ አገር የዚያን ጊዜ የሰደደው ዕቃ ዋጋው ቢታሰብ ፯ ሚሊዮን ፭፻፹፭ ሺ ፬፻፺ ብር ሆነ ፡ ብናሰላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሸጠው ዕቃ የገዛው ዕቃ ፪፻፩ ሺ ፬፻፶ ብር በለጠ ። ብር የሚመጣ ግን ከባሕር ማዶ ነው የኢትዮጵያ ሕዝብም ብርን የሚያገኝ ምድሩ የሚሰጠውን ነገር እየሸጠ ነው ። ስለዚህ ዕቃውን ሸጦ ካገባው ብር በላይ ትርፍ ብር ሰጥቶ የውጭን አገር ዕቃ ለመግዛት እንዴት ተቻ ለው ።ትርፉንስ ብር ከየት አመጣው ሰው የሌለውን ነገር ሊሰጥ ይችላልን እርግጥ ተበድሮ ለመስጠት ይችላል የተበደ ረውን ገንዘብ ግን ቆይቶ ከነወለዱ ይመልሳል ።

የኢትዮጵያም ሕዝብ እንደዚሁ ተበድርዋል ፡ ማናቸውም የኤሮፓ ሰው ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ አስቦበት እንደ መጣ በት ሥራ መጠን ጥቂት ወይም ብዙ ገንዘብ ይዞ ይመጣል ከዚሁም ገንዘቡ ቤት ይሰራበታል ወይም ይከራይበታል ወይም ምግቡን ይገዛበታል ወይም አሽከር ይቀጥርበታል ወደ ኤሮ ፓም አገር ዕቃ ሳይሰድ ከዚያም ዕቃ አስመጥቶ ሳይሸጥ ዝም ብሎ ያለውን ብር የፈጀ እንደሆነ የሚመጣው ገንዘብ ለኢት ዮጵያ ሕዝብ ጥቅም ይሆናል ብድርም አይባል ።

ነገር ግን ከዚህ ቀደም ገንዘቡን ብቻ ለመፍጀት አንድም የውጭ አገር ሰው ወደ ኢትዮጵያ አገር አልመጣ፡ ሁሉም የመጡት ትርፍ ሲፈልጉ ነው ፤ እንደዚህ ያለውም ሰው በኢ ትዮጵያ መጥቶ ለቤት ኪራይም ለምግቡም ላሽከሩም ደሞዝ ቢሰጥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ማበደር ያህል ነው፡

ይህም ያበደረው ገንዘብ በቶሎ ከብዙ ወለድ ጋራ እን ዲመለስለት ይጥራል፡ እነሆም ካገሩም አቡጀዲድ አስመጥቶ የቤት ኪራይ ለሰጠው ሰውና ለሚያገለግለው አሽከሩ ይሸጥላ ቸዋል፡ አቡጀዲዱንም ሲሸጥ ቲንሽ ትርፍ ያገኛል፡ ያም ቤቱን ያከራየ ሰውና የፈረንጁ አሽከር አቡጀዲዱንና ሌላውንም የሚ ያስፈልጋቸውን ዕቃ ሁሉ ዘወትር ገንዘቡን ከሚሰጣቸው ፈረ

ንጅ ከገዙ የፈረንጁ ትርፍ በጊዜ ብዛት ተጠራቅሞ ፈረንጁ ያመጣውን ገንዘብ ከነወለዱ ያገኛል ፥ አሁን ለምሳሌ አንድ ሰው ቤት ሰርቶ እሱው ራሱ የተቀመጠበት እንደ ሆነ ቤቱ የተሠራበት ዋጋ አይመለስለትም ። ያከራየው እንደሆነ ግን በጊዜ ብዛት በኪራዩ ዋናውን ከነወለዱ ያገኛል የፈረንጆችም አካሄድ በኢትዮጵያ እንደዚሁ ነው ። ብር አይቆረጠምም።አይበላም አይጠጣም የለውጥ መሣሪያ ነው ። ስለ ዜህም ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ የውጭ አገር ሰዎች በቃላቸው ባይናገሩት ስንኳ የኢትዮያን ሕዝብ እንደ ዜህ የሚሉት ይመስላል ። እኛ የመጣነው ያገራችሁን ሀብት ለመውሰድ ነው ፥ ነገር ግን መሬቱ የናንት ነውና እኛ ሠርተን በመሬታችሁ ውስጥ ያለውን ሀብት እንድንወስድስ እሺ አትሉንምን። እሺ የምትሉን እንደሆነ ያገራችንን ሠራተኛ እናመጣም ዋጋው ይበዛብናልና ስለ ዜህ የጉልበታችሁ ዋጋ እጅግ ትንሽ ነውና እናንተው ራሳችሁ ሠርታችሁ ስጡን።ለድካማችሁ ዋጋ ጥቂት ብር እንሠጣችኋለን።በዜሁ በምንሠጣችሁ በጥቂቱ ብር የሚያስፈልገውን መሣሪያና መኪና ገዝታችሁ ልብሳችሁንና ለኑሯችሁ የሚያስፈልጋችሁን ሌላ ዕቃ አትሥሩ ። ከዜህም ቀደም ባገራችሁ ውስጥ ሸማና ጐራዴ ሌላም የሚሠራ ነገር እንዳለ ለእግዴህ ወዴሁ አትሥሩ ። ሁሉንም ነገር ከኛ ግዙ ፥ የሰጠናችሁንም ገንዘብ ከብዙ ወለድ ጋራ በቶሎ መልሱልን ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ነገር ሰምቶ ሸማውን ትቶ ቆሚና አቡጀዲድ ፥ ሸማውንና ማለፊያውንም በርኖስ ትቶ የማይረባውን የብርድ ሌላው ይቅርና ጋሻና ጐራዴንም እንኳን ከነሱ እጅ ይገዛል ። ይህንንም ሁሉ ገዝቶ አንዲት ብር የተረፈችው እንደ ሆነ ሄዶ መሸታ ይጠጣባታል ። ባለ መሸታይቱም ሻሽ እገዛባታለሁ ስትል ያችን አንዲት ብር ይዛ ሄዳ ላመጣት ፈረንጅ ትመልስለታለች ። ለፍቶ ለፍቶም ለኢትዮጵያ ሰው ትርፉ የጉልበት መበከን ፥ ሱካርና ፍሬ የሚሰጠውም የደጎና መሬቱ መሄድ ነው ። ካገሩም ውስጥ ግራና ቀኝ መንገድ ቢሠራ የምድር ባቡርም ቢዘረጋ የሕዝቡ ዕውቀት ካልሰፋ ከዛሬው ሁነታውም ካልበለጠ መበደሩን ያበዛና የተበደረውንም ከነወለዱ እመልሳለሁ ሲል ለውጪ አገር ሰዎች ጥቅም ከዛሬው ይልቅ ይደኸማል ። ብድሩንም ለመመለስ የሚበቃ ጉልበት ስለሌለው ከምድሩ ተበድሮ ይሰጣል ። ኢትዮጵያም ምድር ለጊዜው ብድሬን መልስ ብላ ባታስጨንቀው የሚመጡት ትውልዶች ያበቶቻችሁን ዕዳ መልሱ ተብለው ሳይያዙበት አይቀሩም ፥ ዕውቀትም አግኝተው ያባቶቻቸውን ዕዳ ያልከፈሉ እንደ ሆነ በድኅነትም በችጋርም በበሽታም በሞትም ያልቃሉ ። ከሞትም እና መልጣለን ሲሉ አባቶቻቸው መሬቱን ወደ ሸጡበት ወይም ወደ ሌላ አገር ይሰደዳሉ ። ዕዳውን በጊዜ የማይመልስ ሕዝብ ጉዳቱ ይህ ነው ፥ ስለዜህ ዕውቀት በሌለው ሕዝብ አገር መንገድና የምድር ባቡር ቢሠራ ሕዝቡ እንዲደኸይ ያፋጥናል እንጂ አይጠቅመውም ። ጥቅሙ ከርሱ ጋራ ለሚገበያዩ አዋቂዎች ሕዝቦች ነው ።

ሁለተኛ ።

መንገድና የምድር ባቡር ግን በቶሎ ካወቁበት ትልቅ ጥቅም ይሆናል ። ለየሥራውም ማሰልጠኛ የሚሆኑ የትምሕርት ቤቶች ወዲያው በቶሎ ማቆም ያስፈልጋል ። ሕዝቡም ሲሠለጥን ለኑሮው የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ በገዛ እጁ ይሠራል ። ሥራውም በጣም ተከፋፍሎ ሠራተኞቹም አጠገብ ላጠገብ ይሆናሉ ። የሠሩትንም ሥራ ካንዱ ቦታ ወደ አንዱ ቦታ ለማንቀሳቀስ ድካም የለባቸውም።ስለ ዜህም ሠራተኞቹም በየያዙት ሥራ ብዙ ለመሥራት ጊዜ ያገኛሉ ። በዜህም ምክንያት በየዓመቱ አዲስ አዲስ ብልሃትና አዲስ ሥራ እራሳቸው መርምረው ያገኙና ያወጣሉ በትርፉም የበለጠ ትርፍ ይገኝበታል ። እያደርም የሕዝቡ ሀብትና የመንግሥቱ ኃይል እያደገ ይሄዳል ። ሀብትም ማለት አንዱም ኃይል ነው ። መንገድና የምድር ባቡር ግን ያለ እውቀት አገሩን ያደኸያሉ እንጂ አይጠቅሙም ። ስለዜህም የሕዝቡን ጥቅም የፈለገ መንግሥት እነዜህን ሁለት ነገሮች አይለያይም ባንድነት ለማቆም ይጥራል እንጂ ።

ሶስተኛ ።

መንግሥት ቀረጥ ሲወስድ ሕዝቡን ሊጠቅም ወይም ሊጐዳ ይችላል ። ከገሩ ውስጥ የተበጀውን ዕቃ ሲሸጥና ሲለውጥ በየገባያው የቀረጠ እንደሆነ ዕቃውን ሠርተው የሚለዋውጡትን ሠራተኞች እንደ መራራት ያህል ነው ። እስኪገናኙ ድረስ ከሚደክሙት ድካም በላይ ሌላ ትርፍ ድካም ይሄድባቸዋል ። ስለዜህም ትርፍ ሥራ ለመሥራት ጊዜ ያጥርባቸዋል። ይህም ብቻ አይደለም ደግሞ የሚፈልጉትን ዕቃ ከሚሸጠው ሠራተኛ ጋራ እስኪገናኙ ድረስ የሚፈጅባቸው ድካም ሲበዛ የግድ ካልሆነባቸው በቀር አይፈላለጉም አራሹ ላንድ ዓመት የሚበቃው ልብስ ካገኘ ትርፍ ሸማ እገዛለሁ ብሎ ሸማኔውን አይፈልግም ሸማኔውም ላንድ ዓመት የሚበቃውን እህል ካገኘ ትርፍ አገኛለሁ ሲል አራሹን ለመፈለግ አይሄድም ።

አራሹና ሸማኔው ሊገዙ የሚፈልጉት ነገር ጥቂት ስለሆነ የሚሠሩትም ሥራ ያንሳል ። አራሹ እህል ሰብስቤ ከሆዴ የተረፈውን ሌላ ነገር ልለውጠው ብል ድካሜ ከበዛ እህሉ ቢቆለል ለኔ ምን ይሆናል ይላል ለምግብ የሚበቃውን ያህል አርሶ ከዘራ በኋላ ሥራ ፈትቶ ዝም ብሎ ይቀመጣል ። ሸማኔውም እንዴህ ያስባል ። የሠራሁትን ሥራ የሚገዛኝ ካላገኘሁ ለምን በከንቱ እደክማለሁ ። እሱም የሚሸጥለትን ያህል ሸማ ከሠራ በኋላ ሥራ ፈትቶ ይቀመጣል ። ሠራተኞቹም ሥራ ሲፈቱ በገሩ ውስጥ የሚሠራው ሥራ ያንሣል ። መንግሥትም ብዙ ግብር ሊአገኝ አይችልም ።

ሠራተኞቹም ድካሙን ፈርተው ብዙ ጊዜ የማይገናኙ ስለሆነ መንግሥት የሚያገኘው ቀረጥ ጥቂት ይሆናል ። ሠራተኞቹ ሥራ ከመፍታታቸው የተነሣ የሚቀረው ግብር ይበልጣል ፥ ስለዚህ የሕዝቡን ልማትና የራሱን ጥቅም የፈለገ መንግሥት ባገሩ ውስጥ ካንዱ ወረዳ ወዳንዱ ወረዳ በሚሄደው ነገር ሁሉ ምንም ቢሆን የቀረጥ በር ማበጀት አይገባውም ። ባዲስ አበባ ከተማ ፩ድ ዳውላ ገብስ ፬ት ብር ሲያወጣ አዲስ ዓለም ፩ድ ብር ከሶስት ሩብ ይገኛል ። በሜጫ ግን ያንድ ዳውላ ገብስ ዋጋው ፩ድ ብር ነው ። ደግሞ ጥቂት መንገድ እስከ ጨቦ ድረስ እልፍ ብንል ዋጋው አላድ ይሆናል ።እንግዴህ ገብሱ ከጨቦ ተነሥቶ አዲስ አበባ እስኪገባ ድረስ

ታርሶ ከገባበት ድከም ይልቅ መሰናከያው ስምንት ጊዜ ይበልጣል ። ስለዚህም የጨቦ ባላገር እራቁቱን ሁኖ የግድ ካል ሆነበት በቀር ሸማን ለመግዛት አዲስ አበባ ድረስ አይመጣም ። ትርፍ ልብስና ብርጭቆ ምንጣፍም የብረት ድስትም ሱካርም መቸም የግድ አያስፈልጉትምና እነሱን እገዛለሁ ሲል አይጣጣርም ።

ከዚህ የቀረው በሚከተለው ይታተማል።

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት መጽሐፍ ነው ፤

ስለ ሀገር ጥቅም ።

ብዙ የኢትዮጵያ ልጆች ላገራቸው ጥቅም ምክር ይጽፋሉ ደግሞም በሄዱበት በተቀመጡበት ላገራቸው መልካም ነገር እንዲሆን ስልጣኔ እንዲገባ ይመኛሉ ይኸንንም የሚመኙ መኳንንቶችም ወታደሮችም ባላገሮች ነጋዶች ድሆችም ሕዝብ ሁሉ ናቸው ከትንሽ እስከ ትልቅ መልካም ስራ ሲመኙ እናያለን እንሰማለን ። ክቡራን ወንድሞቼ መልካም ስራ መመኘት ብዙ ማለፊያ ነው ግን መመኘት መልካም የምትሆነው መሥራት ሲከተላት ነው ። ከቶ ላገራችን መልካሙን ሥራ ሁሉ እኛ ካልሰራን ማንም እንዳይሰራልን ብናስረግጥ ማለፊያ ነው አሁን ግን ሁሉንም ስራ መንግሥት እንዲህ ቢያደርገው መንግሥት ቢሠራው እያለ ሕዝቡ ሁሉ ሲጫወት እንሰማለን ይልቁንም በዚህ ነገር መንግሥት ቢያደርገው ማለትን የሚያበዙ በሥራ ላይ የቆሙ መኳንንቶች ጌቶች ናቸው ። እንግዴህ ይኸንን ሐሳብ ብችነን ተርጉሞ ላየው ሰው ላገሪቱ መስራት የሚገባውን ስራ ሁሉ እግዚአብሔር አምላክ የሰማይን ጠል የምድርን ቡቃያ ሁን ብሎ በቃሉ ትዛዝ እንደሚያደርገው ሁሉ መንግሥት ወይም ንጉሥ ያድርገውና ይጥቀመን ማለት ይመስላል ግን እንደዚህ ያለ ስጦታ ለአዳም ልጆች አልተሰጠም ይኸንን የማያውቅ ሰው የለም አሁን እንግዲህ ሁሉም ሰው ትንሹም ትልቁም ድኆቹም በሥራ ላይ የቆሙት ሹሞቹም ሁሉንም መንግሥት ቢያደርገው መልካም ነው ማለት የታሰበበት ምክንያቱ ምን ይሆን ? ለዚህ ምላሽ እኔ የመሰለኝን ልጻፍ ፡ ይህ ነገር ለመንግሥት ሥራ ኦርጋኒዜሽን ካለመኖሩ የተነሳ ነው ኦርጋኒዜሽን ማለት ለስራ ሁሉ የተጻፈ ደንብ አውጥቶ የመንግሥት ሥራ ሁሉ እንደ ደምቡ ከፋፍሎ በተከፋፈለው ስራ ሁሉ ሐላፊነት ያለው የተሾመበትንም ሥራ እጠይቃለሁ ብሎ ሳያመካኝ የሚጨርስ ለሚሰራው ስራ ለመጨረስ ሙሉ ስልጣን ያለው ሹም እንደ አውሮፓ በስራ ላይ ሲቆም ነው ።

ለምሳሌ እንደ አዲስ አበባው ጉምሩክ ስራ ማለት ነው የአዲስ አበባው ጉምሩክ የተሰናዳ ሥራ ያለው በሥራውም ላይ የቆመ ሹም ሐላፊ የሆነ ነው ስለዚህ እነሆ በኢትዮጵያ ካለው ስራ ሁሉ መንግሥት የገቢ ጥቅም የሚያገኝ በጉምሩክ ስራው እንደዚህ መሆኑም በኢትዮጵያ ከሚገኘው ሁሉ ጉምሩክ ብቻ የሚበልጥ ሆኖ አይደለም ስራው ኦርጋኒዜሽን ቢኖረውና ሹሙ በስራው ሥልጣን ቢኖረው ለሚጠፋውም ኃላፊ ሆኖ በትክክል ስለ ሚሰራ ነው እንጂ ። አሁንም ዛሬ ኢትዮጵያን የሚያስፈልጋት እንደ አውሮፓና እንደ አሜሪካ መንግሥታት ላገሩ ሥራ ኦርጋኒዜሽን ማቆም ነው ። ለጊዜው እንኳ የኤሮፓን ኦርጋኒዜሽንና ደንብ አውቆ የሚሰራ ይኸነን ደንብ የተማረ ሰው መንግሥታችን ባያገኝ እንኳን ባገሩ ያለውን ደንብ አሻሽሎ ለጊዜው ላገሩ የሚመችና የሚጠቀመውን ባገሩ ያለውን ደንብ ጽፎ ለዚያውም ኦርጋኒዜሽን ቢቆምበትና ስራው ቢከፋፈል ላገሩ እጅግ ጥቅም ይሆን ነበረ። በጆርናል የሚያመለክቱትም ሁሉ እንደዚህ ያለው ስራ ቢሰራ ብለው ከመመኘት በእገሌ ክፍል ባለው ሥራ እያሉ ለባለ ስራው ቢያመለክቱ የጻፉት ቃል ከታረሰ ከማረ ምድር ላይ እንደ ተዘራ እህል በቅሎ ያፈራ ነበረ ። አሁን ግን የሚመከረው ምክርም ለእገሌ ነው ሳይባል የሚወቀሰውም ወቀሳ ለእገሌ ነው ሳይባል እንዲያው ምኞት ብቻ ቢጻፍ እስከ ሕልፈተ ዓለም እንዳይጠቅመን የታወቀ ነው እስተውለን ብንመለከት የኢትዮጵያ ጉዳት ኦርጋኒዜሽን ያለመኖሩ ብቻ ነው እንጂ እገሌ አጠፋ ብለን የምንፈርድበት ሰው የለም ነገር ግን የምንፈርድበት ሰው የለም ስላልሁ ለወደ ፊት በዛሬ ጊዜ በኢትዮጵያ ያሉ ትልልቆች ጌቶች ሁሉ ተማክረው ላገራቸው ጥቅም ኦርጋኒዜሽን ባያቆሙና የተሻሻለ ደንብ ባያወጡ ስማቸው በታሪክ ላይ በቁጥር ተጽፎ ሳይወቀስ አይቀርም ይመስለኛል ለጊዜው እንኳ እነሱ በዚህ ነገር ሐላፊ አይደለንም ቢሉ በግድ ታሪክ ጸሐፊ ስማቸውን በታሪክ ላይ በዝርዝር ጽፎ ሐላፊ ያደርጋቸዋል። የዛሬው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ቀድሞው አይደለም ጆርናል በመጻፍና ታሪክ በመጻፍ ተግቷል በታሪክ ይጽፋል ይመስለኛል ።

ታሪክ ጸሐፊም እንዳይረሳ ይኸው እስታውሳለሁ ደግሞ ትልልቆቹ ጌቶች ግማሾቹ እጅግም ይኸነን ጆርናል ይመለከቱት አይመስለኝምና የጌቶቹ ልጆች ወይም አሽከሮቻቸው ወይም ዘመዶቻቸው የሆናችሁ ይኸን ጆርናል ያነበባችሁ ንገሩዋቸው ከስብ ስም ይሸታል ብሏልና ሰሎሞን ክቡራን ወንድሞቼ አሁን ዛሬ በእግዚአብሔር ኃይል የኢትዮጵያ ተስፋ የትምሕርት ቤትናት ይኸነንም እርግጥ መሆኑን አውቆ መንግሥታችን የስልጣኔ ትምሕርት ቤት ካቆመ ብዙ ጊዜው ነው ።

ፊታውራሪ ዲሬሳ ።

ስለ ላሞችና ስለ ንህቦች ።

በ፬፻ ፲፰ ገጽ በ፵፱ ቁጥር ። የላህሞችንና ፡ የንህቦችን አስተዳደር ቀኛዝማች አክሎግ እንደጻፉላቸው በትንሽ እውቀቴ ከዚህ በታች እንደተጻፈው ቃል ጀምሬለሁና ስህተትም ቢገኝብኝ ይቅርታ እንለምናችኋለሁ ። ክቡራን የሆናችሁ የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ የላህሞች እውቀታቸው እንደሰውነታቸው ግዙፍ ሆኖ አገኘሁት ማለት ጨፌው ከማረበት ወሐ ከመላበት ቦታ አውለዋቸው ከጠገቡ ዘንድ እዚች ካማረች ጨፌ ውለን ተመግበናልና ጠግበን ቀን ሳይመሽብን ጊዜ ሳያልፍብን ወደጌታችን ቤት እንመለስ ብለው አያስቡትም ። ላህሞች ምንም ተሰብስበው የራሳቸውን ሐፍረት ሳይመረምሩ በጥፍራቸውና በቀንዳቸው ኃይል ሊመከቱበት አይችሉም ነበር ጸሎተ ሐና እመሳሙኤል ነቢይት ም ፩ ቁ ፴፫ ንህቦችም ምንም ለዓይን ሙሉ ባይታዩ አገራቸው ሊያስደፍሩት ሊዘነጉ አይመስለኝም ። ሶፎንያስ ፪ም ፩ቁ የሚጋደልም ቢሆን አክሊል አይወስድም እንደ

ሚገባው ከልተጋደለ ይላል ። ጢሞቴዎስ ፪ም ፫ቁ ተመልከት ።
አለውቀታቸው ነው እንጂ ንህቦችም እንደ ሰውነታቸው ረቂቅ
ጥበብ አላቸው፤ንህቦች አገር አይቀራቸውም የነደፉት አያመልጣቸ
ውም ለንጉሣቸውና ላውራቸው የታመኑ አርበኛ ጦረኞች ናቸው
ለጊዜው ሲያዩዋቸው ሥራ የሚሠሩ መስለው አይታዩም ። አው
ራቸው ንጉሣቸው ባዘዛቸውና በላካቸው ሃገር መሣሪያቸውን
የያዙ ሳይመስሉ በክንፋቸው በረው በእግራቸው ተሽከርክረው
የንጉሣቸውን ጠላት በታጠቁት ረቂቅ መርዛቸው ፩ጊዜ እንደ ው
ሽንፍር ቢያለብሱት ላንድ ጊዜ ጥዝጠዛ ሳያዳርሳቸው ቀረ ይላሉ
እነሱም እንደበረሩ ሄደው እንደ በረሩ በፍጥነት ድል አድር
ገው ተመለሱ ። ንጉሣቸው ግን ቀፎ በሚባለው አዳራሹ ግብር
ተቀምጦ ነበረና ተዋግታችሁ ያመጣችሁትን አሳዩኝ ሳይላቸው
ያመጡለትን አንድዬ ቢያፈሱለት ከግንዘቡ ብዛት የተነሳ ላንድ
ራሱ መቅመሻ አጣ ይባላል ። እነሱም ዘብ ይደሩ ተባሉ ይኸ
ውም ስም ሆኗላቸው ንህቦች ተጢ እንደ ላህሞች እንዳትሆኑ ።
የከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ ፀየሳምንቱ ለምት መላለስልን ብር
ሃንና ሰላም ለምትባለው ፈጣን ሠረገላችን አስበን ብንቀበላት
ከትልቁ ደረጃ አስቀምጠን መልካም ሐሳቧን ብናስፈጽማት ይሻ
ላል ። መክብብ ፲ም ፩ቁ ተመልከት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየ
ሱስ ክርስቶስ አውራችንና ንጉሣችንን ይጠብቅልን ለንባቦቻች
ንም ኃይል ይስጥልን ኢትዮጵያም ለዘለዓለም ትኑር አሜን ።
እምትደቅ አሐቲ ቃል እምአሪት ወእምነቢያት ይቤ እግዚእ ለአ
ርዳኢሁ ።

መዓዛ አክሊሉ ።

የብርሃንና ሰላም ወንድሞች መልስ ።

ማሳሰቢያ ። መዝሙር ፸ ቍ ፭ አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ
ከታናሽነቴ ጀምረህ አንተ ተስፋዬና እምነቴ ነህና ፤ ከማኅፀን
በንተ ተደገፍሁ ። ከናቴም ሆድ ጀምረህ አንተ መሸሸዬ ነህ ። ም
ስጋናየም ሁል ጊዜ ላንተ ነው ።

ድንቁርና ፤ ምቀኝነት የሚባሉ ጠላቶቼ ከሰወሩብኝ አሸከላ
ድኅነት ፤ በብርሃንና በሰላም አድነኝ ። ከዚህ በፊት በብርሃንና
በሰላም እንደ እውቀታቸው መጠን ። የኢትዮጵያ ልጆች በየሳም
ንቱ ለመንግሥታቸውና ለሀገራቸው እርዳታ የሚሆን የምክር
ቃል ሲጽፉ ኃይለ ቃላቸውን እየሰማሁ ፤ በማድነቅና በማንበብ
እኖር ነበር ። ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮ ከማየት የሚገኝ ፍሬ
በሚስቱና በሹመቱ የማይቀና ሰው ቢኖር ወይም ፈሪ ወይም
ደንቆሮ ይባላል እንጂ ሌላ የሞገስ ስም ያገኝ አይመስለኝም
ብሎ ጀምሮ በውስጡ የጻፈውን ምሥጢር ። ከመጀመሪያው እስ
ከመጨረሻው ባነበብሁት ጊዜ ተሻምቶ ከሚበሉት እህል ዝግ
ብሎ የሚበሉት እህል ማዕርግም አለው ያጠግባልም ። ተሻምቶ
መብላት ያለ ሕግ መሥራት ነው ። ዝግ ብሎ መብላት በሕግ
መሥራት ነው ፤ ብሎ ከጻፈው ንባብ በደረስኩ ጊዜ ዮሴፍ በኦሪ
ት ዘፍጥረት ። ምዕ ፵፫ ቍ ፳ ጌታው ጶጢፋርም ከግዞት ቤት
ባገባው ጊዜ እስረኞቹ ያንዱ ፈንታ ራት ሲመጣለት
ተሻምተው ይበሉት ነበር ። ደግሞ ያንዱም ሲመጣ እንደዚሁ
እንዲህ እያሉ ሳይጠግቡ ይኖሩ ነበር ። ዮሴፍ ከግዞት ቤት
ከገባ በኋላ እንደተለመደ ያንዱ ፈንታ እራት ቢመጣ የሌሎቹ
እራት መጥቷልና እንመገብ አሉት ። ቆዩ የሁላችን ፈንታ ከተዘ
ጋጀ በኋላ ባንድ ላይ ሰብስበን እንመገባለን አላቸው ። የንግዱ
ሰው ቃል ይሰማልና እሺ ብለው ቆዩ ። የሁሉም ፈንታ እራታቸ
ው ከተሰበሰበ በኋላ ፤ ገበታ ሠርቶ ባንድ ላይ ምግቡን አሰናድቶ
ኑ እንመገብ አላቸው በልተው ጠግበው ተርፏቸው አደረ
ይባላል ።

የእሥር ጠባቂዎች አለቃም ዮሴፍን አንተ ብልህ ሰው በአእ
ምሮና በእውቀት የተከናወንክ ነህ ብሎ በእሥረኞቹ ላይ ሾመ
ው የሚለው ታሪክ ትዝ አለኝና ለመጻፍ አሰብኩ ።

ደግሞ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፵፱ በገጽ ፫፻፺ በብርሃንና
ሰላም አቶ አስታጥቄ ወልደ አማኑኤል የጥያቄ መልስ ብሎ
ጀምሮ ላገረ ገገርዎች የሚያስፈልጋቸው ሁለት ነገሮች ናቸው
መጀመሪያ ግዛታቸውን ለመንግሥት ለቀው እነሱ በደሞዝ ቢያ
ድሩ አሳብ ይቀልላቸዋል ብሎ የጻፈውን ባነበብሁት ጊዜ
የራሱን መከበር የማይፈልግ ሀገሩንና መንግሥቱን የሚወድ
ለኢትዮጵያ ስንት አሳቢ አላት ብዬ እኔም ከወንድሞቼ አሥር
ጊዜ በሚያንስ እወቀቴ የተቻለኝን ያህል ልጽፍ ጀመርኩ ፤ ከዚህ
በፊት በሀገራችን የሚነግሥ ንጉሥ ግሩምነቱንና ገናንነቱን
ለሰው ሁሉ አድሎ አንድ ክፍል ይዞ ይኖራል ። የሀገራችን
ንጉሥና ሕዝብ ደሀና ገባያ እንደሰማይና እንደ ምድር ተራርቀ
ው ይኖራሉ ። ከዚህ በፊት ባንዱ አውራጃ የተሾመው የሻለቃ
ለራሱ አምስት ሺ ስድስት ሺ ሠራዊት ያሳድራል ። ከዚህ በኋላ
የመንግሥት ሽታ እየመጣ ይሸተዋል ። ከንፈሩንም ይነክሳል
ጐራዴውንም ይነቀንቃል ።

ባገራችንም የነገሠው ንጉሥ እንደ አውሮፓ ነገሥታት
ብዙ መኪናና መሣሪያ እንዳያቆም ከተማውንም እንዳያድስ
እገሌ በዚህ ለገር ሸፈተ ይሉታል ። ያን ሸፍታ በጉልበትም በር
ቅም ብሎ ሲገባለት ደግሞ እገሌም ሸፍቷል ተነገሌ ጋራ ሆኖ
ይመክርብሃል ይሉታል ። በኢትዮጵያ የነገሠውም ንጉሥ ጠላቱ
ን በማጥቃትና በመቅጣት ይኖራል ።

የኢትዮጵያ ሠራዊት በየሻለቃው እየተቆጠረ የኢትዮ
ጵያ ዜጋ መሆኑን የሚያስረዳ ባላንበሳ ጥቅጥቅ ወረቀት እየተ
ቀበለ ሀገርና ሠራዊት በንጉሥ እጅ ሆኖ ለሺ አለቃ ከማዕርግ
ስሙ ጋራ ያሥር ሺ ያምስት ሺ አለቃ መባል ይበቃው ነበር
ቀለቡንም ንጉሥ እንደ ማዕርግ እንደ ማዕርጉ ይሰጠዋል ።
እንዲህ ቢሆን ለመኳንንቶች ሀሳብ ይቀልላቸዋል ተሐሜትም
ይድኑ ነበር ። ገባሩም በተቆረጠ ትእዛዝ የግብሩን ልክ ካወ
ቀው ሳይመረር ደስ እያለው ያመት ግብሩን ያወጣ ነበር ።
ባንድ ክፍል ሀገር አንድ ሰው ይሾማል የሚያስገብራቸው አከሲ
ዶቹ አኀዶቹ ከሆኑ ብቻውን ደስ ቢለው ላረም ላጨዳ ባዘዛቸው
ቁጥር ካዘኑበት ምኑን ተጠቀመ የልዑል አምላክ በጎውን ሐሳብ
በየልቦናችን ያሳድርብን ብለን ፈጣሪያችንን እንለምን ።

ይላል ጸጋ ሥላሴ

የብርሃንና ሰላም ምስጋና ።

ብርሃንና ሰላም የሚባል ምግብ ማርና ወተት የሆነ ክቡ
ራን የኢትዮጵያ ልጆች እየተመገቡ ሲአድጉና ደስ ሲላቸው
እያየሁኝ ፊታቸው ሲያበራ የኔን ፊት ባየው እንደነሱ ሳይሆን

እየሁት ስለዚህም ነገር የስተዛሬውን ምግቤን ትቼው ብርሃንና ሰላምን ማርና ወተት የሆነውን ለመመገብ አሳሰበኝ ይህንኑም ብርሃንና ሰላም ተክቡራን የኢትዮጵያ ልጆች አንድ አንድ ቀን አቀላውጠውኝ ተመግቤ ባደርሁኝ ጊዜ ጧት ስነሳ ፊቴ ትንሽ ፈገግ ብሎ እየዋለሁ ይህም ቅልውጡ ስላሰለቼኝ ብርሃንና ሰላምን ደህናውን ምግብ ልመገብ ብየ የምግቡን ዋጋ አምስት ብር ልኬአለሁ ።

ሁለተኛም የብርሃንና ሰላም ምግብ የሚአዘጋጅልንን አበታችን ምግቡንም እየተቀበሉ ለሚመገቡ ልጆች ለሃገራቸው እውእውቀታቸውንና ምክራቸውን እየገለጹ ለሚአጥናኑ ልዑል እግዚአብሔር አምላካችን ኃይሉንና ብርታቱን ይስጣቸው ብዬ እመኛለሁ።ሰላመ እግዚአብሔር ብርሃንና ሰላምን አይንሳን አሜን ምሳሌ ምዕራፍ ፩ ቁጥር ፰ ሁለተኛም መክብብ ምዕራፍ ፪ ቁጥር ፲፫ እይ ። ደጃዝማች በላይ ።

የከተማ ወሬ ።

ስለ ልደት በዓል አከባበር ።

ታሕሣሥ ፳፱ ቀን በልደት በዓል መንፈቀ ሌሊት በየቤተ ክርስቲያኑ የጌታችን የልደቱን የሚነግር የመጽሐፍ ቃል ሲነበብና ሲዘመር አደረ ። ወዲያው በጥዋቱ የልደት በዓል የምስራች ሰባት የመድፍ ተኵስ ተሰማ ። ከመድፍ ተኵስ በኋላም ነጋሪት ይጐሸም ጀመር ። ስለ ልደት በዓል ደስታም በቤተ መንግሥቱ ሙሉ ግብር ተደርጎ በቤተ መንግሥቱና በየቤቱ ሁሉ የደስታ ቀን ሆኖ ዋለ ።

ስለ ክብርት ወይዘሮ ስኂን ሕመም ።

ክብርት ወይዘሮ ስኂን የልዕልት ወይዘሮ መነን እናት በጠና ታመው እልዑል አልጋ ወራሽ ቤተ ሳይዳ ሆፒታል ገብተው ክቡር ዶክቶር ሐነር ኦፒራሲዮን አድርገውላቸው አሁን ተሽሎአቸዋል ። ፈጽመው ደህና ሁነው እንዲነሡ ተስፋ እያደረግን እግዚአብሔር ይማራቸው እንላለን ።

የፈረስ እሽቅድድም ።

ጥር ፫ ቀን የፈረሶች እሽቅድድም ተደረገና በዚሁ ቀን በጧት ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ በመኳንንታቸውና በሠራዊታቸው ታጅበው እጃን ሜዳ ሄደው እምሮ በተሰናዳ ስፍራ ተቀመጡ ። መኳንንቶቹም በወንበር በወንበር ሁነው ተቀመጡ ። ከልዑል አልጋ ወራሽ በስተቀኝ ክቡር ራስ ሥዩም ፡ በስተግራ በኩል ክቡር ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ነበሩ። ክቡር ሊቀ መኳስ መንገሻና ክቡር ሊቀ መኳስ መኰንን ዋልቴ ክቡር ከንቲባ ነሲቡና ክቡር ቀኛዝማች አሥራቴም እልዑል አጠገብ ቁመው ነበር ። በስተቀኝ በኵል ባለው ቦታ በተሰናዳው ወንበር ደጃዝማቾችና ፊታውራሪዎች ሌሎች መኳንንትም ተቀመጡ ። በስተግራ በኩል ባለው ስፍራም የውጪ አገር ትልልቆች ሰዎችና ወይዛዝሮች ተቀመጡ ። ክቡር አቶ ማህሌ ፀዳሉ የውጪ ጉዳይ ሴክሬቴር ጄኔራልም የውጪ አገር ትልልቅ ሰዎችና ወይዛዝሮችን እያቀረቡ ከልዑል ጋራ ያገናኙ ነበር ።

የሽቅድምድሙ ጊዜ ሲደርስ ፈረሶቹ ተሰናድተው ቀረቡና አንደኛ እሽቅድምድም ተጀመረ ።

፩ኛ ፡ እሽቅድድም ኖቢስ ዋንጫ ።

የሚዳው ርዝመት ፰፻ ሜትር ፤ ፊተኛ ቀዳሚ የወይዘሮ የውብዳር ሚካኤል ፈረስ ሆነና ዋንጫና አርባ ብር ተቀበለ ። ሁለተኛ ቀዳሚ ዶክተር ሐስ ፈረስ ሆነና ሠላሳ ብር ተቀበለ ። ሶስተኛ ቀዳሚ የመሐመድ አሊ ፈረስ ሆነና አሥር ብር ተቀበለ ።

፪ኛ ፤ እሽቅድድም የንግሥተ ነገሥታት ዋንጫ ።

የሚዳው ርዝመት ሺ ፭፻ ሜትር ፡ ፊተኛ ቀዳሚ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ሆነና ዋንጫና አምሳ ብር ተቀበለ ። ሁለተኛ ቀዳሚ የሙሴ ቤንቲንክ የእንግሊዝ ባለሙሉ ሥልጣን ሚንስትር ፈረስ ሆነና ሠላሳ ብር ተቀበለ ። ሶስተኛ ቀዳሚ የሙሴ ጎስን የፈረንሳዊ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ፈረስ ሆነና አሥራ አምስት ብር ተቀበለ ።

፫ኛ ፤ የኢትዮጵያ መኳንንት እሽቅድድም ።

የሚዳው ርዝመት ሺ ፪፻ ሜትር፡ ፊተኛ ቀዳሚ የወይዘሮ የውብዳር ሚካኤል ፈረስ ሆነና ሠላሳ ብር ተቀበለ ። ሁለተኛ ቀዳሚ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፈረስ ሆነና አሥራ አምስት ብር ተቀበለ ። ሶስተኛ ቀዳሚ ደግሞ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ሆነና አሥር ብር ተቀበለ ።

፬ኛ፡እሽቅድድም የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዋንጫ።

የሚዳው ርዝመት ሁለት ሺ ሜትር ፡ ፊተኛ ቀዳሚ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ሆነና ዋንጫና አርባ ብር ተቀበለ ፪ ኛ ቀዳሚ የዶክተር ሐስ ፈረስ ሆነና ሠላሳ ብር ተቀበለ። ፫ ኛ ቀዳሚ የመዳም ቤንቲንክ ፈረስ ሆነና ሀያ ብር ተቀበለ ።

፭ኛ፡ የትልቆች ሰዎች እሽቅድምድም ።

የሚዳው ርዝመት ሺ ፭፻ ሜትር ፤ ፊተኛ ቀዳሚ የመዳም ዋይስ ፈረስ ሆነና አንድ ማለፊያ ዕቃ ተቀበለ ። ፪ኛ ቀዳሚ የኮንት ኮሎምቢያኖ ፈረስ ሆነና አርባ ብር ተቀበለ ። ፫ኛ ቀዳሚ የሙሴ ቤንቲንክ የእንግሊዝ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ፈረስ ሆነና ሀያ ብር ተቀበለ ።

፮ኛ ፡፡ ፕሪድ ፍራንስ ።

የሚዳው ርዝመት ፪ ሺ ፭፻ ሜትር ፤ ፊተኛ ቀዳሚ የሙሴ ጋሴብ ፈረስ ሆነና አንድ ጥሩ ዕቃና አርባ ብር ተቀበለ። ፪ኛ ቀዳሚ የፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው ፈረስ ሆነና ሀያ ብር ተቀበለ ። ፫ ኛ ቀዳሚ የከንቲባ ነሲቡ ፈረስ ሆነና አሥራ አምስት ብር ተቀበለ ።

፯ኛ ፤ የእንጦጦ እሽቅድድም

የሚዳው ርዝመት ፪ሺ ሜትር ፡ ፊተኛ ቀዳሚ የሙሴ ካቺክ ጎርጎርዮስ ፈረስ ሆነና ሠላሳ ብር ተቀበለ ። ፪ኛ ቀዳሚ የልጅ ወሰኔ መታፈሪያ ፈረስ ሆነና ሀያ ብር ተቀበለ ። ፫ኛ ቀዳሚ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ሆነና አስር ብር ተቀበለ

፰ኛ ፡፡ የዝላይ እሽቅድድም።

የሚዳው ርዝመት ፫ሺ ፪፻ ሜትር፡ ፊተኛ ቀዳሚ የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፈረስ ሆነና ዋንጫና አምሳ ብር ተቀበለ።

፪ኛ ቀዳሚ የኢጣልያን ሚኒስትር ሙሴ ክራፈረስ ሆነና አርባ ብር ተቀበለ ። ሶስተኛ ቀዳሚ የዶክተር ሐስ ፈረስ ሆነና ሠላሳ ብር ተቀበለ ። እሽቅድድሙ ፯ሰዓት ተኩል አለቀና ስጦታው ሁሉ በልዑል ፊት ቀረበ ። ልዑልም ለቀደመው ሁሉ በየተራው እያስጠሩ ሰጡት ። ከዚህ በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከመኳንንቶቻቸው ጋራ በሽቅድድሙ ማኅበር ቤት ገብተው ሽምፓኝ ተጋብዘው ወጡና ባማረ አጀብ እቤታቸው ገቡ ።

የጥፋት ሥራ ።

ጥር ፫ ቀን ባሻ ሽሪፍ የተባሉ የዘበኛ አለቃ አሽከራቸው በገዛ ጠበንጃቸው ሊገላቸው ተኵሶ ሳታቸውና ኵታውን ትቶ ሸሽቶ አመለጠ ግን ዘበኞቹ ሳይዙት አይቀሩም ።

ስለ አቡነ ማቴዎስ አርባ

ጥር ፬ ቀን የአቡነ ማቲዎስ አርባቸው ስለሆነ በየቤተ ክርስቲያኑ ካህናቱ ሲፈቱ አደሩ ቀኑ ሮብ ስለሆነም ስለ አርባቸው የተደረገ ድግስ ለጥር ፰ ቀን ይበላል ።

ማስታወቂያ

ስለ ጋምቤላ ከተማና ጉምሩክ ነገር ።

የእንግሊዝ ሱዳን መንግሥት ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ በኤታና አጠገብ አንድ ቦታ ያውሳሉ ብለው የተዋዋሉትን ውል ምክንያት አድርጎ በጋምቢላ አገር ላይ ከተማ ሠርቶ ጉምሩክ አቁሞ ቀረጡን እየቀረጠ ይኖር ነበር ። ነገር ግን በ፲፱፻፱ ዓ ም ልዑል ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ከሆኑ በኋላ ወዲያው ባመቱ ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ ከእንግሊዝ ሱዳን መንግሥት ጋራ የተዋዋሉትን ውሉ ሲመረምሩ በጋምቤላ ጉምሩክ አቁሞ ይቀረጣል ብለው አለመዋዋላቸውን በተረዱት ጊዜ በዚያ ዘመን በአዲስ አበባ ከነበሩት ከእንግሊዝ ሚኒስቴር ከምስተር ተሲጀር ጋራ ነገሩን ለመነጋገር ጀምረው ሳሉ ሳይጨረስ ቆይቶ ነበር ።

ደግም በ፲፱፻፲፭ ዓ ም ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ራሳቸው ወደ ሎንዶን በሄዱ ጊዜ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ከምስተር ራምሴይ ማክዶናልድ ጋራ የወሰኑን ነገር ሁሉ ሲነጋገሩ የጋምቤላንም ጉምሩክ ነገር አንሥተው ተነጋግረው ነበር ነገር ግን በማናቸውም ቢሆን ነገሩ ሳይፈጸም ቆይቶ ነበረና አሁን አዲስ አበባ ከሚኖሩት ከአዲሱ የእንግሊዝ ሚኒስቴር ከክቡር ምስተር ቤንቲንክ ጋራ እንደገና ለመነጋገር ጀመሩ ።

ደግሞ የእንግሊዝ ሱዳን መንግሥት በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በጋምቤላ ጉምሩክም አቁሞ ቀረጥ መቅረጡ የኢትዮጵያን መንግሥት ክብሩን የሚያጐድል መሆኑን አስረድተው በሰኔ ፯ ቀን ፲፱፻፲፰ ደብዳቤ ጻፉላቸው ።

ክቡር ምስተር ቤንቴንክም በዚያው ወራት ወደ እንግሊዝ አገር ሔደው ነበርና የጋምቤላን ጉምሩክ ለባለ ገንዘቡ ለኢትዮጵያ መንግሥት መልቀቅ የሚገባ መሆኑን ከመንግሥታቸው ጋራ ተማክረውና ጨርሰው ሲመለሱ የእንግሊዝ ሱዳን መንግሥት የጋምቤላን ጉምሩክ ቀረጥ እንዲለቅ ቁርጥ አድርጓል ብለው በሕዳር ፲፰ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ በተጻፈ ደብዳቤያቸው ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አስታውቀዋል ይኸውም የ፪ቱ መንግሥቶች ወዳጅነት እየጸና መሔዱን የሚያስረዳ ነገር ነው ። ልዑል አልጋ ወራሽም የይሉባቡር ነጋድራስ ታፈሰ የጋምቤላን ጉምሩክ ተረክቦ እንዲጠብቅና ሥራውን እንዲያሠራ ትእዛዝ አሣልፈውለታል በነጋድራስ ታፈሰም ውስጥ ሆነው የጋምቤላን ጉምሩክ ሥራ ለመሥራት የታዘዙ ዋናው ሹም አቶ መንገሻ ።ዋናው ጸሐፊ አቶ ታክለ ወልደ ሐዋርያት ናቸው ።

ያዲስ አበባ ከተማ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ፳ መሐለቅ ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር ፬ መሐለቅ ።
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፸፳ ብርና ፻፹ ብር ።
የበሬ ቆዳ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ፳ መሐለቅ ።
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር ፳ ብር ፲፪ ብር እንዳ ይነቱ ነው ።
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፪ ብር ፲፫ ብር ፲፬ ብር ።
አቡጀዲ መነጽር ፩ ኮረጃ		፻፴፰ ብር ።
። ። ባለሰይጣን ስእል ። ።		፻፵፯ ብር ።
። ። ባለፈረስ ። ።		፻፴፪ ብር ።
። ። ባለድመት ። ።		፻፴፰ ብር ።
። ። ባለአህያ ። ።		፻፳፫ ብር ።
። ። ባለሳቢ ግመል ። ።		፻፳፱ ብር ።
። ። ባለአንበሳ ። ።		፻፴፯ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፵፳ ብርና ፵፯ ።
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር ።

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፩ ፍራንክ ከ ፳፰ ሣንቲም ነው ።
በአንድ ብር	፲ ሊሬ ከሰባ ሣንቲም ነው ።
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ከሰላሳ አንድ ሳንቲም ነው
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር ተኩል ይሆናል ።

የውጭ አገር ወሬ ።

የአየር መንገድ ከሎንዶን ወደ ህንድ በአይሬዎፕላን ከሎንዶን ተነሥቶ ወደ ህንድ አገር በ፲፪ ቀን ለመግባት መሰናዳት ተደርጓል ። አካሔዱም በኤውሮጳ ቁጥር ፳፯ ታሕሣሥ ከሎንዶን ተነሥቶ በቤንጋዜ አልፎ በባግዳድ በኵል አድርጎ በጥር ፳ ቀን ደልሂ ወደ ተባለው ከተማ በህንድ አገር ለመግባት ነው

ፓርት ፋዓድ ።

ፓርት ሳይድ በሙሐመድ ሳይድፓሻ ስም ተጠርቶ ነበር ። አሁንም የምስር ንጉሥ በፋዓድ ስም አዲስ ከተማ ባፖርት ሳይድ ግምባር ለግምባር ቆመና ተመረቀ ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሙዋቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው ፣	፲	ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ ።	፳	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውርጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር ።	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፫	ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው ፣	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፪	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት ፤	፩	ብር
ያማሪኛ ሰዋስው ።	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ፣	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን ።		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
ወዳጄ ልቤ ።		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ ።		አላድ
ያማሪኛ ፊደል ፣		ሩብ
አሳብና ምኞት ፣		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት ።		ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር ።	፪	መ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ፣	፩	ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ።	፩	ሩብ

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉሙሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ሥፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልሁ ሐዲስ ከሚዎን ሞቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

Berliet



ቤርሊዮ ኦቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዮ አቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ።

ARMENAK ZAMANIAN

AGENT GÉNÉRAL

Pour l'Abyssinie et Djibouti

ማስታወቂያ

በጥሩ የፈረንሳዊ አገር ጨርቅ ለኢትዮጵያ መኳንንቶች የሚገባ በጥንቃቄ የተሰፋ ካባ ከሙሴ ፕሪዮ ዘንድ ይገኛል ቤታቸውም በእንግሊዝ ባንክ ቤት አጠገብ ነውና ለሚገዙ ሰዎች ሁሉ በማክበር እናስታውቃለን።

ኤን ቤ ኤዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምቦሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ስንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፫
3 me ANNÉE № 3

ሐሙስ ጥር ፲፪ ቀን ፤ ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 20 JANVIER 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በግራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christos Taklé Haymanot
Diréctеur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ጥንቃቄ ።

አቶሞቢልና አቶሞቢልን የሚመስሉ መኪናዎች በትክክል ሥራ ለማስኬድ በውስጣቸው ያለውን ትንንሽ መዛሪያ ምስማርም ሳይቀር ጥሩ የተከናወነ ሊሆን ያስፈልጋል ፤ ከነዚሁ መዟሯዎች አንዲት ትንሽ መዟሯ ወይም ምስማር የጐደለ እንደሆነ ዋናው መኪና በትክክል ሊሄድ አይችልም ። መኪናውም ተሠቶር ከተከናወነ በኋላ ኃይል ጉልበት የሚሆነው ጋዝና ቤንዚል ቅባትና ልስላሴ የሚሆነው ዘይትና ዘይትን የመሰለ ቅባት ያስፈልገዋል ። እንደዜሁ ሁኖ ተሰናድቶ ለመሄድ በተዘጋጀ ጊዜ ማሥነሻና ማቆሚያ ፤ ማፍጠኛና ዝግ ማድረጊያ ዋና መኪናዎች አሉት ። በፍጥነት ሲሄድም ላስቲኩ የፈነዳ ፤ ምስማሩ የወለቀ ማሠሪያው መኪና የላላ እንደሆነ ከቶ ሊሄድ አይችልም ። ይልቁንም ሲሄድ ማገጃው (ማቆሚያው) የተሰበረ ወይም የወለቀ እንደሆን አደጋ ነገር አግኝቶት ካልተሰበረ ፤ ቤንዚኑ አልቆ ኃይል ካላጣ በቀር ከቶ ይቆማል ተብሎ የማይጠረጠር ነገር ነው ።

ብዙ አውቶሞቢል ነጂዎችና በአውቶሞቢል ተቀምጠው የሚሔዱ ሰዎችም እንደዚህ ካለው ብርቱ አደጋ የተነሣ ብዙ ጉዳት ያገኛቸዋል ስለዚህ አውቶሞቢል ነጂ የሆኑ ሠራተኞች ሁሉ አስቀድመው የመኪናውን መተካከልና መከናወን ስንፍናውንና ብርታቱን መላላቱንና መጥበቁን ከትልቁ መዛሪያ እስከ ትንሹ ምስማር ሥራ የፈታ እንደሌለ ማወቅና መመርመር በየጊዜው ያስፈልጋል ። እንደዚህ ሳያውቁና ሳይመረምሩ መንዳት ብቻ ቢሆን ግን በነጅዎችና በተቀማጮች ሰዎች ከላይ የተነገረው የጉዳት አደጋ እንዲደርስባቸው እርግጥ ነገር ነው ።

እንዲሁም ሁሉ የሰው አካል እንዳንድ መኪና ነው ። ከአካላቱም ትንንሾችና ትልልቆች ልዩ ልዩ መልክና ስም ያላቸው አካላቶች አሉት ።

ለነዚህ አካላቶችም ሕይወትና ደኅንነት የሚሠጥ ምግብና መጠጥ ያስፈልጋቸዋል ። ምግብና መጠጥም ያስፈልጋቸዋል ስለአልን ለመኪና የሚሆን እስፒርቶና ቤንዚን መጠጣት አይደለም ፤ ብዙ ሞኞች ሰዎች የሚያሰክር መጠጥ ጠጥተው በበነጋው ሰውነታቸው የዛለና የደከመ እንደሆነ ሙቀትና ብርታት እንዲሰጠን ብለው በፊት ደኅንነትና ሕይወት ያሰጣቸውን ። የድካምና የመዛል ምክንያት የሆነባቸውን የሚያሰክር መጠጥ የገደለውን መጠጥ ነው የሚያድነው እያሉ ጠጥተው ለብዙ ዘመን የሚቆይ ሕይወታቸውን ያጠፉሉ ፤ ስለዚህ ለብረት መኪና ኃይልና ጉልበት የሚሆን ነገር ለሚጠጡት ሰዎች ሞትና ጥፋት ነው ።

ሰው በሕመም ወይም በድካም ለሥራ ከተሰናዱ አካሎቹ አንዱ አካሉ ቢበላሽበት ከሥራው ይጐላል ፤ ይልቁንም ለሀሳቡ ሁሉ ዋና መሠረትና መሪ የሆነ አንጐሉ የተበላሸ እንደሆነ ምንም ሥራ መሥራት አይቻለውም ።

ይህም ስለሆነበት ትክክል ሳያስብ ቢናገር እብድ ተብሎ ይጠራል ። ልብ የሰው ሕይወት መሠረት እንደሆነች ፤ አንጐልም የሀሳብ መሠረት ነውና በትክክል መጠበቅ ያስፈልጋል ።

አንጐልም የሚበላሽበት ምክንያቱ ብዙ ነው ። የበለጠ ግን የሚያሠክር መጠጥ በመጠጣት ነው ። ሰው በጉብዝናው ወራት ሰውነቱ ሳይደክም የሚያሰክር መጠጥ ቢጠጣ እንደ ሽማግሌ በጣም አይጐዳውም ፡፡ ከቀን ብዛት ግን ጉልበቱ እየደከመ ፤ ኃይል እያጣ የማጠጡ ኃይል በርትቶ አንሥቶ ይፈነግለዋል ። ለማሰብ የተዘጋጀ ያንጐሉንም አሳብ የመጠጡ ኃይል ያጠፋዋል ።

ባለአቶሞቢል ለመኪናው የሚስማማ ነገር እያደረገ መዘውሩን እየመረመረ በጥንቃቄ እንደሚይዝ የኢትዮጵያ ጀግናም የሚያሰክር መጠጥን በመተው አንጐሉ ለሀሳብ የተዘጋጀ እንዲሆን ያስፈልገዋል ። ብርሃንና ሰላም የሚያሰክር መጠጥ መጠጣት ለሀገር ጥፋት ፤ ለመንግሥት ጉዳት ለሚጠጣው ሰው ሐፍረትና

ውርደት ነው ብሎ በየጊዜው መምከሩን የኢትዮጵያ ጀግና እየተረዳ የሚያስከብርን መጠጥ ትቶ ሀሳቡ እንዲሰፋ ሕይወቱ እንዲበረታ ማሰቡን ተረድተነዋል ።

የ፲፱ገጽ ተከታይ።

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

ስላዚህም ለምግቡና ለልብሱ መግዣ የሚበቃውን ያህል ገብስ አርሶ ከገባ በኋላ ሥራ ፈትቶ ይቀመጣል ። ለመንግሥትም የሚያገባው አሥራት ጥቂት ይሆናል፡እንዲሁም ባዲስ አበባ የሚኖሩ ሸማኔዎች የሠሩትን ሥራ የሚገዟቸው ባዲስ አበባ ዙሪያ ያሉት ባላገሮች ብቻ ይሆናል ። ስለዚህም የሸማኔዎች ቍጥር ያንሣል ። ለመንግሥትም ከሸማኔዎች የሚገባለት ግብር እያደር እያነሰ ይሄዳል ።

እነሆ ከዚህ ቀድሞ ያልነውን አሁንም አስረግጠን እንና ገረው፡፡ ዕቃ የሚረክሰው ገዢውና ሠሪው ሸጩ አጠገብ ላጠብ ቀርቦ ሲኖር ነው ፤ ማለት የተላላኪው ነጋዴ ደመወዝ ይቀራል ፤ ስለዚህ በተላላኪው ነጋዴ ደመወዝ ላይ ቀረጥ ቢጨመር ሠራተኞቹ ከሚያገኙት ዕቃ ይልቅ በከንቱ የሚደክሙት ድካም ይበልጣልና ብዙ ሥራ ለመሥራት ጊዜ አያገኙም ። ይልቁንም የግድ ከሚያስፈልጋቸው በቀር ትርፍ ነገር ለመግዛት አይከጅሉም።ብዙ ሥራ ሊሠሩበት የነበረውንም ጊዜያቸውን ግማሹን በከንቱ ድካም ግማሹንም በስንፍና ያሳልፉታል ። የሕዝቡም ኑሮ እንደዚህ የሆነው መንግሥት ሀብቱና ኃይሉ እያነሰ እንጂ እያደገ እንዳይሄድ በግልጽ የታወቀ ነገር ነው ።

እንግዲህ ከውጭ አገር የሚመጣውስ ዕቃ እንደምን ይሁን ይቀረጥን ወይስ አለቀረጥ ይግባ ። ለዚሁ ጥያቄ እርግጠኛ ምላሽ ለመስጠት ከመቶ ዓመታት ቦፊት ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ብዙ የዓለም ሊቃውንት ይከራከሩ ነበርና ከተከራካሪዎችም ሊቃውንት ከዚህ ቀደም ያሸነፈና የተሸነፈ የለም ። ነገሥታቶች ሁሉ ለጊዜው እንደማይጠቅማቸው እያዩ አንድ ጊዜ ያንዱን ወገን አሳብ ሌላ ጊዜ ደግሞ የሁለተኛውን ወገን አሳብ እየተከተሉ የቀረጣቸውን ደምብ በየጊዜው ይለዋውጡታል ። ይልቁንም ለጊዜው የሚጠቅም መሆኑን ሲረዱት የሁለቱን አሳብ ተቀብለው ከውጭ አገር የሚመጣውን ነገር ግማሹን እንዲቀረጥና ግማሹ ያለቀረጥ እንዲገባ የደነቡ ነገሥታት አሉ ፤ ይህም ሰስተኛው ያቀራረጥ መንገድ እንደጸሐፊው አሳብ እንደ ኢትዮጵያ ላለው አገር የሚበጅ ነውና የሚበጀው ምክንያቱ ምን እንደሆነ ለይተን እንመርምር ።

ከዚህ ቀድሞ እንዳየነው ሕዝብ ሁሉ መሰናከያ ነገር ካላገኘው ከፍ ወዳለው የእውቀት ደረጃ ለመድረስ ይችል ነበር መሰናከያ ነገር ያላገኘው ሕዝብ ግን በዓለም ላይ አይገኝም ። እንዳገኘ፡ውም መሰናከያ ነገር ማነስና ማደግ እንደዚሁ መጠን እውቀታቸውና ሀብታቸው ከፍ ወይም ዝቅ ይላል ፤ በዛሬውም ዘመናችን የዕውቀትን መጀመሪያ ደረጃ የያዙ የኤሮፓና ያሜሪካ ሕዝቦች ናቸው ስለዚህም ያገራቸው ሀብት በብዙ ዘመናት የተሰራና የተከማቸ መሣሪያ መኪና ፋብሪካ እየሆነ ሀብታቸው ከሌሎች ሕዝቦች ሀብት ይበልጣል ሕዝቦቹም በዘመናት ብዛት እውቀትና ጥበብ ትጋትም ከሰውነታቸው ጋራ ስለተዋሀደው ከነሱ ጋራ ለመተካከል ቢፈልጉ ለቀሩት የዓለም ሕዝቦች የሚያስቸግር ነገር ነው ። በመላው ዓለም ሁሉ ለነሱ ሰገዷል። ከጃፓንና ከቱርክ ከሺናም ከሲያምም ከኢትዮጵያ ነገሥታት በቀር ዛሬ ዓለም ሁሉ በመላው ቅኛቸው ሁኖዋል ። ከነዜህም እስከ ዛሬ አርነታቸው ከቆየላቸው ነገሥታቶች አለጃፓን የቀሩት ነገሥታት አርነት አላቸው ቢባል ለስም ብቻ ነው ።

እስቲ አሁን እኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርነት አለን ሊባል ነውን፡ አርነት ያለው ሕዝብ ማለት እውነተኛ ትርጕሙ ለብቻው መንግሥት ያለው ሕዝብ ማለት ብቻ አይደለም፤ ራሱንም የቻለ ሕዝብ ማለት ነው እንጂ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከ ዛሬ ድረስ ገና እራሱን አልቻለም፡ እስቲ የለበስነውን እንይ ወጄት የተሠራና ማን ያመጣው ነው የቤታችንስ ዕቃ ሁሉ ከወዴት የመጣ ነው ፤ የምንለብሰው ልብስ፡የምንጠጣበትና የምንበላበት ምግባችንም የምናበስልበት ዕቃና መሣሪያ ሁሉ ፈጽሞ ከውጭ አገር የመጣ አይደለምን ።

ከዚህም ቀደም በሀገራችን እራሳችን ለመሥራት ስንችለው የነበረው ሥራ ሁሉ ዛሬ ተረሳ፡ቆጪና በፈረንጅ አገር የተሠራ ሸማ ፈትልም ያገራችንን ቡልኮና ጋቢ ያማረውንም ሸማችንን የሴቶቻችንንም ቀጭን ፈትል ከገባያው አባረረው ዋጋውንም ወሰዱት ። የጾማውንና የመጥረቢያውን ነገርማ ዛሬ ምን ብለን እናውጋው ። ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረርጌም ገበያ በኢትዮጵያ ውስጥ የተሠራ ከእነዚህ መሣሪያዎች አንድም አይታይም ። ይልቁንም በትግሬማ በጭራሽ ዛሬ ባላገሩ ማረሻውን እንኳ ሳይቀር ከውጪ አገር አስመጥቶ ነው ። ማለቱ የኤውሮፓ ሰዎች ባገራችን ከመጡና ከገቡ ወዲህ እንኳን እውቀት ልንጨምር አባቶቻችንም ያቆዩልንን ሥራ ሁሉ ግማሹን ዛሬውን ረስተነዋል ። ግማሹንም አሁን ከጅቡቲ ወደ አዲስ አበባ በተሠራው የምድር ባቡር ምክንያት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ፈጽመን ሳንረሳው አንቀርም ። በኢትዮጵያም ሕዝብ ውስጥ ያለው የያንዳንዱ ሰው የዛሬው ጥረቱ በደህና ለመኖር ሰውነቱንና ቤቱን ለማስጌጥ ነው።በማናቸውም ሕዝብ ልብ ውስጥ እንደዚሁ ያለ ጥረት ቢኖር ሕዝቡ እውቀት ፈላጊ እንደሆነ ይመሰክራልና እጅግ ያስመሰግነዋል ። ይህንንም ጥረት አይቶ መንግሥት በደህና መንገድ ከመራው እንደዚህ ያለ ተጣጣሪ ሕዝብ ከፍ ወዳለው የእውቀት ደረጃ ለመድረስና ትልቅ ሀብት ለማግኘት ይችላል ።

ደህናውን መንገድ መንግሥት ለክቶ ካልሰጠውና ካላሳየው ግን እንደዚህ ያለ ጌጥና ምቹ ኑሮ የሚወድ ሕዝብ መጨረሻው ክፉ ነው ። ብዙ ነገር ይለምዳል፡ነገር ግን የለመደውን ነገር ለማድረግ አቅም ያጣል ። ይህም ብቻ አይደለም የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እውቀት ባላቸው አገሮች በመኪናና በተሻለ መሣሪያ ተሰርቶ ሲመጣ ዋጋው ባገሩ ከተሠራው ይረክሣልና ለዋጋው ሲል ባገሩ የተሠራውን ትቶ ከውጪ አገር የመጣውን ዕቃ ይገዛል ። በዚሁም ባገሩ ውስጥ የነበሩት ሠራተኞች የሠሩትን ሥራ የሚገዛቸው አጥተው የለመዱትን ሥራ ትተው የዕለት እንጀራ የሚገኝበትን ሌላ ሥራ ይይዛሉ ። በዚ

ህም የተነሣ ሕዝቡ እውቀት ፈጽሞ ይለየዋልና የውጭ አገር ሕዝቦች ታዛገር ይሆናል አሁን ከውጪ አገር ንግድ ባይመጣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለጊዜው የሚለብሰው አጥቶ ይቸገር ነበር ። የኢትዮጵያ የሰሜን ሕዝቦችማ የብረት ማረሻን አጥተው በእንጨት መሬቱን መቆፈር የግድ ይሆንባቸው ነበር የሐረርጌም ጋላ አካፋ አጥቶ እርሻው ሁሉ ይበላሽበት ነበረ ሠራተኛና ጉልበትም መኪናም ከመታጣት የተነሣ ዛሬ ለምቶ የምናየው የኢትዮጵያ እርሻ የሚበዛው ዱሮና ደን ይሆናል ።

የኢትዮጵያም ሕዝብ ከውጪ አገርብዙ ዕቃ እንዲያስፈልገው የዛሬ ፫ ዓመት ተገለጠ በትግሬ የእህል ሽመታ ተወዶ ሠራዊታቸው ቢቸገር ራስ ስብሐትና ደጃዝማች ሥዩም ተማክረው እህል ወደ ሐማሴን እንዳይወጣ ከለከሉ በዚሁም የተነሣ የሐማሴን ገገር አንዳች የባሕር ማዶ ዕቃ ከሐማሴን ወደ ትግሬ እንዳይሄድ ከለከለ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ራስ ስብሐትና ደጃዝማች ሥዩም ሠራዊታቸው በዚህ ነገር እንደ ተቸገረ አይተው ክልክሉን አፈረሱት ። ስለዚህም የኢትዮጵያ መንግሥት መንግሥትኑቱ ነና የሕዝቡ እርነት በዋዛ እንዳይጠፋበት የፈለገ እንደሆነ መመከቻውን ማሰናዳት ነው ዋናም መመከቻ የሚሆነው የተደላደለ የግምሩክ ደንብና ሥራ ማሰልጠን ነው ።

ሰባተኛ ክፍል ።

ዛሬ ያገራችን ጉምሩኮች ከውጭ አገር የመጣውን ጨርቅ ሲቀርጡ እንደ ሌላው ሁሉ ካሥር አንድ ነው ። የጨርቁም መሥሪያ መማሪያና መኪና ቢወጣ እንዲሁ ካሥር አንድ ይቀረጣል ። የጨርቅም መሣሪያ መኪና ፋብሪካ አቆማለሁ የሚል ሰው ቢመጣ እንደ ዛሬው ያገራችን ሹማምንቶች አያያዝ ቢሆን ይከለከላል ። ያለዚያ ግን ሊሠራው ያሰበው ጨርቅ እንደማይሸጥለት አድርገው ለኋላ የሚሰጠውን ግብር ያበዙበታል ። እንዲሁም ደግሞ በረሃውን መሬት አቅንቼ ጥጡን ዘርቼ አበቅላለሁ የሚል ሰው ቢመጣ ማስቸገር እንጂ እንድም እርዳታ ከኢትዮጵያ ሹማምንት አያገኝም ። ከዚህም ምክንያት የተነሣ በኢትዮጵያ ፋብሪካ አቁሜ ጨርቅ እሠራለሁ የሚልና የሚያስብ አንድም አስተዋይ ሰው በኤሮፓና በአሜሪካ አይገኝም ያገራችንም የዛሬ ዋኖች ሹማምቶች መንግሥታቸውን እንዳገለገሉ ሊታወቅላቸው ሲፈልጉ ደኅና ውል እንደመዋዋል ዛሬ ውል አሰቀረሁ እያሉ በየቤታቸው ያወራሉ ። በዚሁም ድንቁርናቸው እውቀት የሌላቸውና ያለፈው ኑሮዋቸው የማይታወቅ ባሕሪም የሌላቸው እንደ አንድ የውጭ አገር ስደተኞችም በልተን እንደር ሲሉ ያገራችንን ሹማምንት ዛሬ የያዙትንም የስሕተት መንገድ እንዳይለቁ ያጠነክሩታል ። እይዟችሁ እያሉ ከየመጻሕፍቱ የለቀሙትን ትርጉሙ ግን ለራሳቸውም ቢሆን ያልተገለጠላቸውን አንዳንድ የተሰበረ ቃል ያስጠኑዋቸዋል ።

ያገራችንም ሹማምቶች እሩቅ እንዳያዩ እነዚህ የተሰባበሩ ቃላት እንደ ጉም ሁነው ዓይናቸውን ሸፍነው ይከለክሏቸዋል ። እውቀት አለንም ብለው ራሳቸው ያዘራል ። ውሏቸውም ሥራን ትተው በክርክርና በሙግት ብቻ ነው ። አገልጋዮች ተብለው በእንደነዚህ ያሉት መኳንንቶች ላይ የሆነ መንግሥት በእንደነዚህ ላሉ እሩቅ ለማያዩ ሰዎች የተመራም ሕዝብ ተያይዞ ያውም በፍጥነት ወደ ገደል መግባት እንደሆነ ግን የማይጠረጠር ነገር ነው ።

የዛሬው የኢትዮጵያ ሁኔታ ገልጾ ያሳየናል ። በዚህ አገር ውስጥ ወደ አሉት ከተማዎች ወይም ትልልቅ መንደሮች ብንዘር ሕዝቡ የተመቸ ኑሮ እንደለመደ ጌትነቱም እየበዛ እንደ ሄደ እናያለን ። ግን እያሠራም ፤ ወደ አገር ቤትም ብንሄድ ባላገሩ ከድህነት ጋራ ሲታገል እናገኘዋለን ። ባንድ ፊት በየከተማው ሥራ ፈተው የሚኖሩትን ሰዎች እመግባለሁ ሲል ይደክማል ። ባንድ ፊትም የሚመጣበት ገበያ እሩቅ ስለሆነ ባገሩ ቢሠራ ባንድ ጊዜ ያለ ብዙ ድካም ሊያገኘው የነበረውን ጨርቅና የቤት መማሪያ እገዛለሁ ሲል ስምንት ጊዜ ይደክምበታል በዚሁም ጉልበቱ ይባክናል ። በመጨረሻም መሬቱ በዕዳ ተይዞ ወደ ሌላ እጅ ያልፋል ። ወይም ደግሞ ላንድ ቲንሽ እርዳታ ሲል መሬቱን ላንድ ሹም አውርሶ ይሞታል ። ልጆቹም የሚቀመጡበት ቦታ አጥተው ፤ ቦታም ቢያገኙ የባላገሩን መከራ ጠልተው ወደ ከተማ ይሄዳሉ ። ሳይሠሩ የሚበሉትንም ሰዎች ቁጥር ማሳደጊያ ይሆናሉ ፤ ወይም ያንዱ ፈረንጅ አሽከር ሁነው ለራሳቸውም ለአገራቸውም ጥቅም ሳይሆኑ እድሜያቸውን ሙሉ በከንቱ ያሳልፉታል ። እንግዴህም አራሹ እያነሰ ባራሹ ድካም የሚመገቡ እየበዙ ይሄዳሉ ። በሥርአት ተከፋፍሎ የነበረውም መሬት በዕዳም በውርስም ሄዶ በጥቂቶች ሰዎች እጅ ይገባል ። የመንግሥትንም ሥራ በእጃቸው የጨበጡ እነዚህ ጥቂቶች ሰዎች ስለሆኑ በግብር የሚጫናቸው ሰው የለም ፤ መከራው ሁሉ መሬቱን ገና ባልሸጠ ባላገር ላይ ይወድቃል ። ስለዚህም መከራውን ጠልቶ ባላገሩ ሁሉ መሬቱን እየሸጠ ወይም እያወረሰ የነዚህ ጥቂቶች ሰዎች አራሽ መሆን ጀምሯል ። መሬቱም ገንዘቡ ስላልሆነ ያውቃልና ሊያሳምረውና አጥብቆ ሊያርሰው አይተጋም ።

ጥቂቶቹ ባለ መሬቶችም የያዙት መሬት ብዙና ሰፊ ስለሆነ ከየመሬቱ የሚመጣላቸው ጥቂት ትርፍ ተጠራቅሞ በከተማው ተቀምጠው በሰንፍና ለሚያሳልፉት ኑሮአቸው ይበቃቸዋል ። ባይበቃቸውም መሬቱን ገና ያልሸጠውን ወይም ያላወረሰውን ባላገር አስጨንቀው ይዘው ያለ ደንቡ በጉቦና በማስፈራራት ብዙ ገንዘብ ይበሉታል ። በዚሁም ምክንያት ሌሎቹ ባላገሮች መሬታቸውን ለመልቀቅ የግድ ይሆንባቸዋል ።

እነሆ ነገሩን አስተውለን ከተመለከትነው ገገራችን እያንዳንዱ ሰው ብዙ መሬት የያዘ እየጨመረም የሚሔድ ባላገሩም የእርሻን ሥራ ትቶ ሹሞቹን እንደ ውሻ እየተከተለ ሥራ ፈትቶ የሚኖር የመንግሥትም ጥቅም እያነሰ የሚሔድ ዋናው ምክንያቱ አራሹ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ የሚገዛበት ገበያ እሩቅና በውጭ አገር ስለ ሆነ ነው ።

ይህ በሽታ ግን መንግሥት ከተነሣበት ዘንድ መጥፊያውን መድኃኒት በቶሎ ለማግኘት ይሆንለታል ።

እስቲ አሁን ድንገት ከውጪ አገር የሚመጣው ጨርቅና ፈትል ቀረጡ ለእንግዴህ ወዲሁ በመቶው አሥር ፈንታ ከመቶው አምሳ ይሁን ቢባል ጨርቁና ፈትሉ የሚሠራበት መማሪያና መኪና ግን ያለ ቀረጥ እንዲገባ ቢፈቀድ የጨርቅንም ፋብሪካ አቆማለሁ የሚሉ የታመኑ ሰዎች ወደዚህ አገር እንዲ

መጡለት መንግሥት ቢጥር፡ ከመጡለትም በኋላ እንደሚገባ አድርጎ ቢረዳቸው፡ የጥጥን መሬት ማረሻና መቆፈሪያ መሣሪያ ሁሉ የጥጥም ዘር ያለቀረጥ ገብቶለት ጥጥን ዘርቶ የሚያበቅል ሰው፡ ያበቀለውንም ጥጥ ወደ ውጭ አገር ሊሰድ ከልፈለገ በቀር በግብር እንዳይጎዳ የተደላደለ ደምብ ቢያወጣ ከዚህ በኋላ የጨርቅንም ሥራና የጥጥን እርሻ እየሠሩ ሕዝቡን የእሚያሠለጥኑ ጥቂት ገንዘብ በመት በመቶ ሊሰጥ ሠራተኞች ከነአለቆቻቸው መንግሥት ቀጥሮ ከውጪ አገር ቢያስመጣ ከነዚህም ተምረው የሠለጠኑትን የኢትዮጵያን ልጆች ረድቶ ቢያበረታታቸው ከዜህ ሁሉ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ እንዴት እያማረ በሔደ። አሁንም ለወደፊት እንዲሆን ተስፋ እናደርጋለን ።

በመጀመሪያ የጨርቅ ዋጋ ብዙ ይሆናል። ምንም ቀረጡ ቢያድግ የውጪ አገር ጨርቅ መምጣቱ አይቀርምና ብዙ ሰው ይጎዳበታል ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ጨርቁን ከውጪ አገር የሚያመጡ ሰዎች የበለጠ ጥቅም እንዲያገኙ ያውቃሉና በረሃን አቅንተው ጥጥን ለመዝራት የጨርቅንም መሣሪያ ፋብሪካ ለማቆም ከኢትዮጵያ መንግሥት ፈቃድ ይለምናሉ።ቀረጥም የሌለበት ስለ ሆነ በየባላገሩ ቤትም የሚሠራበት የተሻለ የጥጥ መፍተያና የጨርቅ መስሪያ መሣሪያ አምጥተው ለባላገሩ ሁሉ ይሸጣሉ ፤

ከዚህ የቀረው በሚከተለው ይታተማል።

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት መጽሐፍ ነው ፤

መሠረትን ስለ ማጽናት።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከጥንት የቤቷ መሠረት ኃይል እንደነበረ የታወቀ ነው።እስከሁንም ድረስ ሳይናወጥ ቆይቶናል። እንዲሁም ብንመለከተው የሥራ ሁሉ መሠረት በኃይል ሲሆን መልካም ነው።ምሳሌ፡ሰው ቤት በጀመረ ጊዜ በጠሊቅ መሠረት በኖራና በሲምንቶ የተመሰረተ እንደሆን ከግምቡ እስከ ውቅሩ (ጣራው) ድረስ ጠንካራ ይሆናል።ከዳኑም በውበት ይከደናል። ዝናብና በረዶ ነፋስና ብርድ ፀሐይና ሐሩር ከታገዱ በኋላ ባለቤቱ ቤቱ በኃይል እንደተሰራ ያውቃልና በቀስታ ያለ ስጋት ውስጥ ውስጡን እያሰለጠነው ይሄዳል። መጀመሪያ በቀለም፡ ፪ተኛም በመስታዋት በልዩ ልዩ ጌጥ እያሳመረው ይሄዳል። ግብተው ያዩት ሁሉ እስኪያደንቁ ድረስ አሁንም የኢትዮጵያ ቤት ሠራተኞች ውስጥ ውስጡን ሊያስጌጡና ሊያሰለጥኑ የውጭ ጠባቂዎች የኖረው መሠረት እንዳይፈርስ ከዳኑም እንዳያፈስ በኃይል መጠበቅ ያስፈልጋል ኃይል በጊዜዋ ከጥበብ ትበልጣለች በጥበብ የተሰራው ሁሉ በኃይል ይፈርሳልና ኃይል ከሥልጣኔ ትበልጣለች።ማንም ስልጡን ቢሆን ከኃይል ጋር ያለውን ብልግና ድፍሮ የሚጠይቅ የለም። ኃይል በምን ተፈልጋ ትገኝ ይሆን። ይህን ኃሣብና ጥያቄ ለመንግሥት ትተን እንለፈው። አዲስ የሥልጣኔ ደምብን ለመመሥረት ብዙህ ጭንቅ ነው መልካውና መሸጋገሪያው የማይታወቅ ድፍርስ ውሀ የሞላበት ጅረት እንደሚያስፈራ ታስፈራለች፤ያን ጅረት ብዙ ሰው በዘንጉ እየለካ እንዳያጠልቀው ወደ ኋላው መመለስ ይፈልጋል።ወሀው በጠራ ጊዜ ግን ሁሉም መሸጋገሪያ ሁኖ ይገኛል። አሁንም አዲስ ደምብን የሚመሠርት ሰው ክብሩና ጥበቡ በዕለትና በፍጥነት የሚመጣው፤ ጊዜ መርምሮ ለማይመለከት አይገልጥለትምና የሚሠራው ሥራ ሁሉ ደግነቱ ከፋት፡ የሚጠቅመው ጉዳት።የሚያድነው ጥፋት መስሎ ይታያል ።

ከለፈ በኋላ ግን ክብሩና ጥበቡ በምስጋና እንደንጋት ብርሃን እገላለጡ እየበረታ ይሄዳል።ግን የሚበዛው ሰው ሁሉ የጊዜውንና የሚመጣውን መመልከት ትቶ ያለፈውን ያመሠግናል፤ይኸ ያለፈው ጊዜ የሚመሠገን ከሆነ ሰውን በጊዜው የሚሠሬውን ሥራ ፈጥኖ ከመንቀፍ የሥራውንና የነገሩን ፍሬ በትዕግሥት መጠበቅ ያስፈልጋል ፤ደግሞ ካለፈው ጊዜ ይልቅ የሚመጣው ጊዜ የከብረ ነውና በኃይል ታጥቆ በሰልፍ ተዘጋጅቶ አክብሮ ለመቀበል እንዲገባው ለኢትዮጵያ ልጆችና ጅግኖች በማክበር አሳስባለሁ ።

ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ ሰማዕት ።

ስለ ምክር ።

በብርሃንና ሰላም ላይ የምናነባቸው ምክሮች ሁሉ በባለሥልጣኖችና በሕዝብም ዘንድ ደስ እንዲያሰኙ መታመኑ የነዚሁ አስታዋሾች ትጋት ማሸሻልን እንደ ጀመረ ይታያል። ነገር ግን መልካምን ነገር ሁሉ ለመፈጸም ቶሎ ቶሎ ማቻኮል ያስፈልጋል ።

ገበሬ በዘር ወራት ሌላ ጉዳዬን እየሰራሁ አርሳለሁ ቢል የዘሩ ወራት ስለአለፈ አዝመራው ደስ አያሰኘውም፡በረሙም ባጨዳውም ፡ በውቂያውም ወራት መትጋት እንደሚያስፈልገው መልካምንም ነገር ሁሉ ለማሻሻል መትጋት ያስፈልጋል ።

እነሆ እኔ እንደሌባ እመጣሁ የሚተጋ ብፁዕ ነው ልብሱንም የሚጠብቅ ራቁቱን እንዳይሄድ ኃፍረቱንም እንዳያዩ የዮሐ ራዕይ ፲፮ ም ፲፭ ቁ ።

ብርሃንና ሰላም መጀመሪያ ዓመት ፱ ቁጥር ፪፻፳ ገጽ እንዳስታወሰን ለሰው በጊዜው ያለበት ልማድ መልካም መስሎ ይታየዋል ፡ ነገር ግን በተሻሻለው ደምብና ሕግ ላይ ጥቂት ወራት ከቆየ በኋላ ያ ያለፈው ደምብና ሕግ አጥቂው እንደነበረ ይታሰበዋል ። አሁን ለምሳሌ ጉቦ የለመደ ሰው ለትዳርህ የሚበቃህን እሰጥሃለሁ ጉቦ አትቡላ ቢሉት ክብሩ የጐደለ ይመስለዋልና ቅር ይለዋል ፡መተውን ከለመደው በኋላ ግን ልቡ ዕረፍት ስለሚአገኝና በእግዚአብሔርም በሰውም ምስጋና እንዲሆንለት ሲታሰበው ደስ ይለዋል ።

ለሰውም ምግብና ትዳር ሁሉ በየአይነቱ ያስፈልገዋል ነገር ግን በችኮላ የሚያስፈልገው ምግብ ነው።ላገር ጥቅምም ቶሎ የሚያስፈልገው የተማሪ ቤትና የተሻሻለ ደምብ ስለሆነ ከብርሃንና ሰላም ላይ ትዝ ያሉኝን አሳቦቸው የሚመሳሰሉትን ፫ት ማስታወሻዎች አሳስባለሁ ።

፩ኛ በ፫ተኛው ዓመት ፪ ቁጥር ባ፲፪ተኛው ገጽ ስለሐገር ጥቅም ከሚለው ለስራ ሁሉ የተጻፈ ደምብ አውጥቶ የመንግሥት ሥራ ሁሉ እንደ ደምቡ ከፋፍሎ በተከፋፈለው ሥራ ሁሉ አላፊነት ያለው የተሾመበትን ስራ እንዲጨርስ የሚለውና በዜሁ ተርታ ያለው ቃል ።

፪ኛ በ፪ኛው ዓመት ፲፩ ቁጥር ፹፫ ገጽ ስለመጻሕፍት ከሚለው ሸማምት የየስራቸውን አኳኋን በመጽሐፍ ተጽፎ መቀበል እ ደሚያስፈልግና በዜሁ ተርታ ያለው ቃል ፡፡

፫ኛ በመጀመሪያ ዓመት ፯፮ ቁጥር ፪፲፩ኛው ገጽ በደምብ ያልቆመ በጽሕፈት ያልተወሰነ ሁሉም በየአሳቡ የሚያደርገው ፍርድና ሕግ ሁሉ በብዙ ስፍራ ያንዱ አሳብ ካንዱ መለያየቱ አይቀርም የሚለውና በዜሁ ተርታ ያለው ቃል ነው ፡፡ በተረፈ ምንም ንግግሩ ቢለያይ ለስራ ሁሉ መሰረት ደምብና የተማሪ ቤት መሆኑ በብርሃንና ሰላም በብዙ ቦታ ተጽፎአል ስለዚህ እነዚህን ማስታወሻዎች መርምሮ በቶሎ መፈጸም ለስራ አጋጋር ይሆን ይመስለኛል ፡፡

ተፈራ ይፍሩ ፡፡

ጥያቄና ምላሽ ፡

በፊተኛው ጋዜጣ እንደ ተጻፈው ክብርት ወይዘሮ ስሂን ታመው በቤተ ሳይዳ ሆፒታል ስለተኙ የደግነታቸውን ብዛት እያሰበ ሰው ሁሉ አዝኖ መኳንንቱም ሕዝቡም የሆፒታሉን ደጅና ግቢውን ሞልቶት ነበር ከሥራ ዘኋላ ወደ ማታ እኔም እሳቸውን ለመጠየቅ ሂጄ ነበርና አንድ ጥቁር ልጅ ኮትና ጫማ የለበሰ አየሁ ይህ ልጅ ኣነግዳ ነው አይቸው ኣላውቅም ከወዴት መጥቶ ይሆ ነ ብዬ ልጠይቀው ቀረብሁ ፡፡ወዲያው ከወዴት መጣህ ብዬ ብጠይቀው ከእስክንድርያ መጣሁ አለኝ ፡፡ ወደ እስክንድርያ ሊማሩ ከሄዱት አንዱ አንተ ነህን አልሁት ትምሕርት መፈለጋችንን ያወቀ ሰው አባብሎ ወስዶ ወደ እስክንድርያ ሸጦኝ ነበር እግዚአብሔር አወጣኝ እንጂ አለኝ ፡፡ በቅድስት አገር እስክንድርያ ምን ሰው የሚሸጥ አለ አልሁት ፡፡ ለናንተማ እንኳን ኃጢአት እሚሠራ እህልም እሚበላ ሰው በእስክንድርያ ያለ አይመስላችሁም ይልቁንስ ነገሩን ልንገርም ብሎ ነገሩን ከሥሩ ጀመረልኝ ፡ ሙሴ ራጊብ አብራሂም የሚባል የግብጽ ሰው ቀድሞ ለማዘጋጃ ቤት ዘበኞች መርማሪ ነበር አባቱም ወንድሙም ከዚሁ ነበሩ እኔንና ሁለት ሴቶች ልጆች ወደ ተማሪ ቤት ወስጄ ላስተምራችሁ ብሎ አባበለን እምወስዳችሁም ወደ ቅድስት አገር እስክንድርያ ቅዱስ ማርቆስ ከተቀበረበት ቅዱሳን ጳጳሳት ከሚወጡበት ነው ብሎ የኑሮውንና የትምሕርቱን ነገር ሞቅ ሞቅ አድርጎ ባወራልን ጊዜ ወደ ሰማያዊት እንጂ ወደ ምድራዊት አገር እሚወስደን አልመሰለንምና እሺ ብለን በምነት ገመድ ተጎትተንለት እሱም ወደ ተማሪ ቤት ወስጄ በገንዘቤ እማስተምራቸው ልጆች ናቸው ብሎ ፓስ ፖርት (የይለፍ ወረቀት) አስወጣልን ከዚህ በኋላ እስክንድርያ ደረስን እኔን ካንዱ ቤት ወስዶ አስቀመጠኝና አሁን እመለሳለሁ ቆየኝ ብሎኝ ሄደ ሌሎቹንም እንዲሁ አላቸውና ሄደ ምን እናድርግ አረብኛ አናውቅ ታገራችን ሰዎች አያገናኙን መስከት እየዘጉ በጨለማ ውስጥ ሲአሠሩን ሁለት ዓመት ቆየን ከዚህ በኋላ ባሮ የመባል ስም እንግሊዞች ካሰለጡኑት ወዲህ በመንግሥቱ ሕግ ነውር መሆኑን አወቅንና ለዳኛው ጮህን ፡፡ ስንጮህም ዳኛው እስላም ነበርና ያደላብን እንደሆነ ጭራሽ ክርስቲያን ወደ ሌለበት አገር ይሸጡናል ብለን ተጨንቀን ነበር ግን ዳኛው ግፋችንን አይቶ ነፃ አወጣን ሰጭህን አቅ-ርብ ቢለው በገር የለም አለው ለሱም የሚገባ ቅጣቱን ሰጠው እኛንም ወደ ሥራ አገባን ለመሳፈሬና ለልብሳችን የሚሆነን ገንዘብ ስናገኝ ወደ አገራችን መለሱን ብሎ ሲአጫውተኝ አንድ አጥፍ የለበሱ መነኩሴና አንድ የሮፓ ሰው አብረውኝ ነበሩና መነኩሴው ወይ አምላክ ማርቆስ ለካ በእስክ ድርያ ክርስቲያኖች ዘንድ እንዲህ ያለ ኃጢአት ይሠራልን ? አሉ የሮፓው ሰውም አባቴ በልጆቹ መግዛት ለምን ይደነቃሉ ይልቁንስ አዋቆቹ ወዳችሁ ትገዙላቸው የለምን ቢላቸው ምነው ጌታዬ የእስክንድርያን ሃይማኖት ለማጽናት ብለን ጳጳስ እናመጣለን እንጂ መቼ ግዙን አልን፡፡አዬ አባቴ ለሃይማ፣ ቱማ መጻሕፍቱን ተቀብላችኋል ሰው መፈለጋችሁ ስለምን ነው አላቸው ፡፡

ደግሞስ አጼ ዮሐንስ እንዳደረጉት በደመወዝ ታሰድሯቸ ነበር እንጂ አገረ ገዢ ማድረጋችሁ ስለምን ነው አላቸው ፡፡ ሥልጣን እንዲሰጡ ሃይማኖት እንዳይጠፋ ነዋ ቢሉት ፡ ሥልጣን እግዚአብሔር በነጭ እንጂ በጥቁር አያድርምን ? ሃይማኖታችሁስ በውጪ አገር ሰው ካልተያዘች አትጸናምን ? ቢላቸው አይ ጌታዬ ይተው እንዳባቶቻችን እንኖራለን አሉት ፡፡ እንዳባቶቻችሁ ከኖራችሁ በብሉይ አትኖሩም ነበርን ? ለምን በሀዲስ ኪዳን አመናችሁ ? ቢላቸው ተደነቁና ጌታዬ እኔን ብቻ ቢረቱ ማን እሺ ይለዋል ? አሉት ፡፡ ማዕርግህ ላገርህ ለወንድምህ ይሁን ሲሉት ፡ ማን ይከፋዋል ? ቢላቸው እኔስ ያገሬን ሰው ከንፍ አውጥቶ ባየው ፤ ለጳጳስነት ፡ ይገባል አልልም አሉት ፡፡ እንግዲያውማ በምቀኝነት ነዋ ለባዕድ እምትገዙት ቢላቸው ፤ ብዙ አልፍ ገንዘባችንን ሰጥተን ሰጥተን እኛ እንገዛቸዋለን እንጂ ምን እነሱ ይገዙናል አሉት ፡፡ እንግዲያውማ ለገንዘባችሁ ነዋ እምትገዙት ቢላቸው ፡ እመቤቴ ከንዴት ያለ ሰው አጋጠምሽኝ ብለው እየተቆጡ ሄዱ ፡፡ አባቴ አይቆጡ ዛሬስ ተረታችሁ ደርሶባችሁ ነው ቢላቸው ፤ ራቅ ብለው ቆመው ፡ ምን ተረት ነው አሉት ፡፡ ግዛኝ ብለው ለመሸጥ አሰቡኝ ፡ ብላችሁ እምትተርቱት ነዋ ቢላቸው ፤ ፊታቸውን መለስ ሳያደርጉ ሄዱ ፡፡ እሱም ወይ እኔ ልቡ ከደነገዘ ሰው ጋራ ስጫወት ጊዜዬን በከንቱ ከማሳለፍ አንዱን ደንጊያ ውሀ ባጠጣው ይለመልም ነበር ፡፡ እኔማ ስለ እውነት ነው እንጂ መከራከሬ ነጭ ጻድቅ ነው ፤ ጥቁር ኃጥእ ነው ፤ ቢባል ምን ይከፋኛል ፡፡ይህ አጥፍ አጥፊ መሆኑን ዛሬ ተረዳሁት ብሎ ሄደ ፡፡ የውጪ አገር ሰው ራሳችንን እንደማንችል ሕፃናት አድርጎ ሲአላግጥብን ሰምቼ ያዘንሁበትን ነገር ስለጻፍሁ ብዕሬን እሚያነቅፍ እድፍ ይኖር ይሆናል ፡፡ግን ጥፋት ቢሆን የብርሃንና ሰላም ወገኖች በለዘብታ ቃል እንዲያስታውቁኝ ተስፋ አደርጋለሁ ዓይኑን ጨፍኖ ለሚሰድበኝም እውነቴን መክቼ እርሳሴን አሰናድቼ እጠብቃለሁ ፡፡

የብርሃንና ሰላም ወዳጅ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ፡፡

የልዑል ማተሚያ ቤት ሠራተኛ የሁለተኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ተፈጽሞ የሶስተኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ስለ ተጀመረ የጻፈው የምስጋና ቃል ፡፡

በዓለም ላይ ያሉት የሥልጣኔ ሥራ ሁሉ በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ የጥበብ ምንጭ የሚቀዳባቸው መጻሕፍት ናቸው

እነዚህም መጻሕፍት አምረው ተሰናድተው በዝተው የሚገኙት በመጻሕፍት ማተሚያ ቤት ነው ። ልዑል ጌታችንም የመጻሕፍት ማተሚያ መኪና ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ላይ አለመኖሩንና የኢትዮጵያን ችግር አስበው የጥበብ ምንጭ የሚቀዳበት ማተሚያ ቤት አቆሙልን ፤ ይህ የልዑል ጌታችን ማተሚያ ቤት ሥራም ከተጀመረ ወዲህ በዓለም መንግሥታት ሁሉ የሚታዩ መጻሕት በመውጣታቸው ይልቁንም ሕዝቡን የሚመክርና የሚያስተምር ብዙ ዕውቀትና ጥበብ የሚሰጥ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ በመገኘቱ የልዑልን እድልና ደግነት በግልጥ አስታውቆ ይመሰክራል ፡፡

ይህ የኢትዮጵያ ብርሃን የሆነ ማተሚያ ቤት ከቆመ ጀምሮ የኢትዮጵያ ሥራ ሁሉ እየሰፋና እየሰለጠነ መሄዱን ሕዝቡ ሁሉ ተረድቶታል ፤ይህም መሆኑ በልዑል ጌታችን ማተሚያ ቤት የተሠራውን መጻሕፍትና ጋዜጣ ሕዝቡ እየተመለከተ የሥራ ጥቅም እየተረዳው ነው ፤ እኛም ይኸን አዲስ የሥልጣኔ ሥራ ማሰናዳትና ለመሥራት የልዑል ጌታችንን ትእዛዝ በመቀበላችን ደስ እያለን ፈጣሪያችንን እናመሰግነዋለን ፤

ልዑል ጌታችንም በማተሚያ ቤታቸው የተከሉት ተክል ለምልሞ አብቦ ይኸው ዘወትር ፍሬውን ይሰጣል ፍሬውንም የተቸገረና የተራበ ድኃ ሁሉ እንዲመገበው የልዑል ፈቃድ በመሆኑ መላው ሕዝብ ደስ ብሎታል ፤ ይህ በልዑል ማተሚያ ቤት የተገኘ ብርሃን ኢትዮጵያን አልፎ አውሮጳና አሜሪካ ድረስ ይታያል ።

ጥንት የውጭ አገር ሰዎች እየሠሩ ለኢትዮጵያ ዕውቀት አበድረዋት ነበር ። አሁን ግን ልዑል ጌታችን ከድንቁርና ነጻ አውጥተው ማኅበር ስላገቧት ኢትዮጵያ እልልታዋንና ደስታዋን ከፍ አድርጋ እያሰማች ከልጆችዋ የሚገኝ ፍሬዋን ታሳያለች ። እኛም በድንቁርና ሰንሰለት ተይዘን እንኖር የነበርን ልጆችዋ አሁን በልዑል ጌታችን ዕውቀትና ኃይል የሠራነው ሥራ አውሮጳና አሜሪካ ድረስ በመዝለቁ ልባችን በደስታ ተነካ ። ለደስታችንም ፍጻሜ የለውም ።

አሁንም ይህች ዕለት ብርሃንን በሰላም ያገኘንባት ቀን የብርሃንና ሰላም ልደት ናትና የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ የደስታችን በዓል አድርገን ልናከብራት ይገባናል ። ይህች ዕለት የብርሃንና ሰላም ልደት መሆንዋን ካወቅነውና ከተረዳነው ምንም ልናገረው የማይገባኝ ቢሆን ተማሪ ነኝና የብርሃንና ሰላምን ፅንስ ከዚህ አያይዤ ልናገረው (እወዳለሁ)እደፍራለሁ ።

ብርሃንና ሰላም የተጸነሰው ፲፱፻፲፯ ዓመት ሚያዝያ ፳ ቀን ነው ። ቀኑም ረቡዕ ነበር ። ከሚያዝ ፳ቀን ጀምሮ ፲፱፻፲፯ ዓመት ታኅሣሥ ፳፫ ቀን ድረስ ጳጉሜን ፮ ቀን ጨምሮ ፱ ወር ለመሆን ሁለት ቀን መቅረቱ ነው።ሁለት ቀን ሲቀረው መወለዱ ብርሃኑ አሸንፎ በሰላም ማግኘቱን ያስረዳል ።

አሁን ባዲሱ ሥልጣኔ ጊዜ ብርሃንና ሰላም በሁለት ዓመቱ ለኢትዮጵያ የሠራላትን ሥራ ስንቱን እንቆጥረዋለን (መጀመሪ) ሌባሻይ የሚሉትን ትልቅ ሽፍታ አስታውሶ ድል ያደረገልን ብርሃንና ሰላም ነው።ከዚያም በኋላ ብዙ ሥራ ሠርቷል መጀመሪውን ተናግሬዋለሁና ሁለተኛ ሰስተኛ ብዬ ለመናገር የሚያስፈልግ መስሎ አይታየኝም ብርሃንና ሰላም አንድ ረዳትና አንድ ሞግዚት ሳይኖረው በሕጻንነቱ ወራት ይኸንን ያህል ሥራ መሥራቱ በጣም ያስደንቃል ።(ልዑል ጌታችን በዚች ባስር ዓመት ውስጥ ለኢትዮጵያ የሠሩላት ሥራ በታሪክ ነገሥት ይጻፍ እንደሆን ነው እንጂ እኛ ልንጽፈውና ልንቆጥረው አንችልም፣ይህሥራቸው ሁሉ ለግርማዊት ንግሥት ታላቅ ዕድል ነው፤

በኢትዮጵያ ጨለማ ጠፍቶ ብርሃን መውጣቱ እርግጥ ነው ይኸንንም ልዑል ጌታችን አውሮጳን አይተው የተመለሱ ጊዜ ተረድተነዋል ፡ ልዑል ከአውሮጳ ሲመለሱ አዲስ አበባ የገቡት ሐሙስ ቀን ነው የዚያን ዕለት ለኢትዮጵያ ይዘውላት የመጡት ብርሃን ጨለማን ድል አድርጎ ሕዝቡ ሁሉ በብርሃን ተቀምጧል።

ይኸውም ሊታወቅ ሐሙስ ቀን በየሳምንቱ የሚወጣው ብርሃንና ሰላም ብርሃን መገኘቱን ያስረዳል ፤ ይኸንን የማያውቅ ሰው ቢኖር በጣም ያሳዝናል። ኢትዮጵያ በዕውቀት አበባ አጊጻ እንድትኖር ዕድሜ ለልዑል አልጋ ወራሽ ይስጥልን እያልሁ የደስታ ምኞቴን እጨርሳ ሁ

ደምሴ ወልደ ገብርኤል ።

የከተማ ወሬ ።
ስለ ጥምቀት በዓል አከባበር ።

ከቀድሞ አባቶች ጀምሮ ባገራችን የጥምቀት በዓል ክብር ፪ቀን እንዲደረግ የተለመደ ነው ። መጀመሪያው ቀን ከተራ ይባላል ። ከተራ የተባለበትም ምክንያት በዚህ ቀን መኳንንቱና ካህናቱ ወደወንዝ ወርደው ፡ ፈሳሹን ወሀ ባሕር እንዲሆን ከትረው በወንዙም ዳር ድንኳን ተክለው የሚያድሩ ስለ ሆነ ነው ይባላል ። በዚህም ልማድ በመላው ኢትዮጵያ ያሉ ታቦታት ወደ ወንዝ ወርደው ያድራሉ ። ይህም መደረጉ ጌታችን የሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ሊጠመቅ ወደ ዮሐንስ መሄዱን ለማሳሰብ ነው ፡

እንደዚሁ ሁሉ ዘንድሮም ጥር ፲ቀን ፲፱፻፲፱ ዓመተ ምሕረት በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ አድባራት ሁሉ እንደ ልማዱ ታቦታቱን ይዘው በየአያውራጃቸው ወዳለው ወንዝ ወርደው የሚያድሩ ስለሆነ በዚሁ ቀን ማክሰኞ ወደ ማታ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ወደ ጥምቀተ ባሕር የሚወርዱትን ታቦታት ለመሸኘት ከግቢ ተነሥተው ታቦታቱ ወዳሉበት ሥፍራ ሔዱ ። ልዑል አልጋ ወራሽም ከብዙ መኳንንትና ሠራዊት ጋራ ታቦታቱን አጅበው ላሥራንድ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ከጃንሜዳ ደረሱና የመድኃኔ ዓለም ታቦት እስኪመጣ ድረስ ሲጠብቁ ቆዩ ። ከዚህም በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽ ታቦታቱን ሸኝተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ ።

ጥር ፲፩ ቀን ረቡዕ በጧት ልዑል አልጋ ወራሽ ከብዙ መኳንንትና ሠራዊት ጋራ ወደ ጥምቀተ ባሕር ወረዱ ፡፡ በዚያን ጊዜም ነጋሪቱ ሲጐሽም እየ ሰማ የከተማው ሕዝብ ሁሉ ወደ ጥምቀተ ባሕሩ ሲጐርፍ አስተውሎ ለተመለከተው እጅግ ያስደንቅ ነበር ።

ልዑል አልጋ ወራሽና ክቡራን መኳንንቶቻቸውም ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ካህናት የጥምቀቱን ሥርዓት እስቲፈጽሙ ቆመው ይጠባበቁ ነበር ።ካህናቱና ዲያቆናቱ የጥምቀቱን ስራ

ካደረሱ በኋላ ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በውሀው ላይ ጸሎት አደረጉና ሕዝቡን አረጩት ፡፡ ለአንግዶሁ ግን ከሱ ቡተሻለ ወንዝና የጠራ ብዙ ውሀ ባለበት ቢደረግ ለሚጠመቀው ሕዝብ ሁሉ እጅግ ይበልጥ ደስ ባሰኘ ፡፡

ሕዝቡም ተጠምቆ ሲጨርስ ልዑል አልጋ ወራሽና መኳንንቶቻቸው ከወንዙ ወጥተው ከሜዳው ላይ ተቀመጡና ወረብ ተጀመረ ፤ ወረቡም ሲያልቅ በ፪ ሰዓት የከብከብ ጊዜ ተጀመረ ፤ የከብከቡም አኳኋን ላየው ድንቅ ነው ፤ ለሚሰማውም ግሩም ነው ፤ በፊት ቀይ መለዮ የለበሱ ነጋሪት መችዎች ነጋሪቱን እየጐሸሙ በስራት ተሰልፈው ፤ ቀጥለው ጋሻ ጃግሬዎች ቀይ ደማስ የለበሰ ጠመንጃ ይዘው በሥራት ተሰልፈው ክቡር ሊጋባ ወዳጆ ሰማያዊ ካባ ለብሰው ያማረች በቅሎ ተቀምጠው ጠመንጃቸውን አንግተው ፤ ለሊጋባነታቸው የተገባ ዘንግ ጨብጠው በነዚሁ ጋሻ ጃግሬዎች ፊት ይሄዱ ነበር ፡፡ ከነሡ በኋላ ልብሰ ተክህኖ የለበሱ በያይነቱ ለዓይን የሚያንፀባርቅ ጥላና ድባብ ጽናና ቃጭል እየያዙ ታቦታቱን ከመካከል አድርገው ሰልፍ እንደተማረ ወታደር በረድፍ በረድፍ እየሆኑ ሲጓዙ አምረው ነበር ፡፡ ከነሡ በኋላ ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከሊቃውንቱና ከመዘምራኑ ጋር ፤ ቀጥለው ልዑል አልጋ ወራሽ ከክቡራን መኳንንቶች ጋር ፤ በልዑል ቀኝ የግራዝማች ገብረ ዮሐንስ ጭፍራ ባማረ ሰልፍ ፤ በግራ በኩል ያቶ መኰንን ጭፍራ በነዚህ ውስጥ ግራና ቀኝ ነጭ የለበሰ መትረየስ አንጋች ዘበኛ ተሰልፎ ጃን ሜዳ በደረሱ ጊዜ ታቦቱ የሚያርፍበት ክህናቱ የሚዘምሩበት ልዑል ከነመኳንንቶቻቸው የሚቀመጡበት ሕዝቡ የሚያይበት ተሰናድቶ የተቀመጠውን ቦታ ቀኝና ግራ ሲሄድ የነበረው ዘበኛ እንደ አጥር ተደርድሮ ግጥም አድርጎት ቆመና ልዑልም የዙፋን ቤቱ የሽ አለቃ ቀኛዝማች ግፋ ወሰን ባሰናዳው ባለአጎበር ወንበር ተቀመጡ ፡፡

በልዑል ቀኝ ክቡር ራስ ስዩም ፤ ክቡር ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ፤ ክቡር ቢት ወደድ ጌታቸው ፤ ክቡር ደጃዝማች ወልደ ገብርኤልና ክቡር ደጃዝማች ወንድ ይራድ ሌሎች መኳንንቶችም በየማዕርጋቸው ተቀመጡ ፡፡

በግራ በኩልም እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከሊቃውንቱ ጋራ ፤ ቀጥለው የውጭ አገር ሰዎች ሚኒስትሮችና ወይዛዝሮች ነጋዴዎችም ተቀምጠው ነበር ፡፡ ክቡር ሊቀ መኳስ መኰንን ዋልቴና ፤ ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ከልዑል አጠገብ ቆመው ነበር በዚህ ጊዜ መዘምራኑና ካህናቱ ወረባቸውን ሲወርቡ ላይታው ሁሉ እጅግ አስደነቁ ፡፡

ወረቡም ከተጨረሰ በኋላ ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ስለ ጥምቀት ነገር ሰበኩና ሕዝቡን ባርከው አሰናበቱት ፡፡

ከዚህ በኋላ የውጭ አገር ሰዎች ተሰናብተው ሄዱ ፡፡ ጉዞውም እንደፊተኛው ሁኖ ሲጓዝ ወደ አራዳና ወደ ቤተ መንግሥቱ ከሚወስደው መለያያ መንገድ ሲደርሱ ፤ የቅዱስ ጊዮርጊስ ታቦት ተለይቶ ወደ አራዳ ሄደ ፡፡ ግራዝማች ማህሌም የከተማ ዘበኞችን አሰልፈው ቆይተው እንደሚገባ ሰላምታ ሰጡ ፡፡ በዚያን ጊዜ አዲስ ነገር ሆኖ የታየ አቃኢዮብ ያስተማራቸው የፈረስ ዘበኞች ሶስት ሶስት ልሳን ባለው ጦር ብሜ ስንደቅ አላማ አድርገው በሙዚቃ ሰላምታቸውን ሲሰጡ ነው ፡፡

ከዚህ በኋላ ልዑል ከነመኳንንቶቻቸው የሥላሴን ታቦት ከቤተ ክርስቲያኑ አገቡና የቅዱስ ገብርኤልንና የኪዳነ ምሕረትን ታቦት አጅበው ወደ ቤተ መንግሥቱ ገቡ ፡፡

የዘንድሮ የጥምቀት ሰልፍ ከዱሮው የበለጠ መሆኑ የሰልፍ ትምርት የተማሩ ወታደሮች በርክተ በማለታቸው ነው ፤ ከእንግዲህ ወዲህም ሰልፍ የተማረ ወታደር እየበዛና እየሰለጠነ ሲሄድ ለበዓላትና ለደስታ ቀን ደስ አሰኝቶ በብርቱ ሥራ ቢታዘዝም ለሀገሩና ለመንግሥቱ የሚጠቅም ሥራ ሠርቶ እንዲፈጽም ጥርጥር የለበትም ፡፡

የገር ውስጥ ወሬ ፡፡

ደግነትና እርዳታ ፡፡

ክቡር ራስ ጉግሣ አርአያ ለትምርት ለንግድ ፤ ለጌታ አዳሪ ወደ አዲስ አበባ የሚመጡትን ሰዎች ረሀብና ጥማት እንዳያገኛቸው ስንቅ ሰጥተው ጉዳት እንዳያገኛቸው አሸኝተው ፤ በመስደዳቸው የተገባ የደግነት ሥራ በመሥራታቸው የረዱዋቸውና ይህን የደግነት ሥራቸውን የሰሙ ሰዎች በጣም ያመሰግኑዋቸዋል ፡፡ ይህም ተማሪ እንዲማር ነጋዴ እንዲነግድ የጌታ አዳሪ የጌታ እንዲያድር አስበው መርዳታቸው ለሀገራችን ሰላም ለመንግሥታችን ብርታት እንዲሆን የተገለጠ የተረዳ ነገር መሆኑን ስለአስተዋሉ ነው ፡፡

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ፡፡

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ፳ መሐለቅ ፡፡
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር ፬ መሐለቅ ፡፡
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ፤
ሰም	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፴፰ ብርና ፻፵ ብር ፡፡
የበሬ ቆዳ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ፳ መሐለቅ ፡፡
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር ፰ ብር ፲፪ ብር እንዳ ይነቱ ነው ፡፡
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፪ ብር ፲፫ ብር ፲፬ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፫ ብር ፡፡
፡፡ ባለሰይጣን ስእል	፡፡	፻፵፯ ብር ፡፡
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፻፴፪ ብር ፡፡
፡፡ ባለድመት	፡፡	፻፴፰ ብር ፤
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፫ ብር ፡፡
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፱ ብር ፡፡
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፴፯ ብር ፡፡
ሱካር	፩ ጆኒያ	፵፬ ብርና ፵፭ ፡፡
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር ፡፡

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ከ ፳ ሣንቲም ነው ፡፡
በአንድ ብር	፲ ሊሬ ከሰባ ሣንቲም ነው ፡፡
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ከሰላሳ አንድ ሳንቲም ነው

አንድ ወቄት ወርቅ ፴፫ ብር ተኩል ይሆናል ፡፡

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሙዋቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው ።

፻ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ግር ይ ፣ሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው ፡	፲	ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ ።	፫	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር ።	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፫	ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው ፡	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፪	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት ፤	፩	ብር
ያማሪኛ ሰዋስው ።	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ፡	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን ።		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
ወዳጄ ልቤ ።		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ ።		አላድ
ያማሪኛ ፊደል ፡		ሩብ
አሳብና ምኞት ፡		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት ።		ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር ።	፪	መ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ፡	፩	ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ።	፩	ሩብ

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉሙሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ሥፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልሀ ሐዲስ ከሚዎን ሞቶመቢል የፊታውራሪ ዶሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

Berliet



ቤርሊዮ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዮ አቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

ARMENAK ZAMANIAN

AGENT GÉNÉRAL

Pour l'Abyssinie et Djibouti

ማስታወቂያ

በጥሩ የፈረንሳዊ አገር ጨርቅ ለኢትዮጵያ መኳንንቶች የሚገባ በጥንቃቄ የተሰሩ ካባ ከሙሴ ፕሪቶ ዘንድ ይገኛል ቤታቸውም በእንግሊዝ ባንክ ቤት አጠገብ ነውና ለሚገዙ ሰዎች ሁሉ በማክበር እናስታውቃለን።

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጆጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ስንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፥ ቁጥር ፬
3 me ANNÉE № 4

ሐሙስ ጥር ፲፱ ቀን ፥ ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 27 JANVIER 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Éthiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christos Taklé Haymanot
Diréctour

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

መልስ ።

ብርሃንና ሰላም ፪ኛ ዓመት ቁጥር ፴ በግዕዝ ድምጻቸው አንድ፡መልክቸው ልዩ ልዩ የሆነ ፊደላት አሉ ። በድሮ የኢትዮጵያችን ቋንቋ እንደ ልዩ ልዩ መልክቸው ልዩ ልዩ ድምጽ ሳይኖራቸው አይቀርም ፤ የድሮ ሊቃውንትም የሚገቡበትን ስፍራ ያውቁታል፡አሁንም የሚገቡበትን ስፍራ ጨርሰው የሚያውቁ ጥቂቶች ሳይሆኑ አይቀሩም እያለ ብዙ ከተናገረ በኋላ ይህንኑም ሊቃውንቱ ተግተው እንዲያስቡበት ብርሃንና ሰላም ያመለክታቸዋል ብሎ ለጠየቀው ነገር ፤ ክቡር ፊታውራሪ አርአያ ዘረፉ ግሩም የሆነ የሚያስቅ፡በዚህም በዚህም አከላቴ ታየ የሚለውን ምሳሌ አድርገው የጻፉት መልስና ክቡር ኢቶ መኰንን ኢያቄም በድምጽ አንድ ይሁኑ እንጂ በምስጢር ይለዩ የለምን ። በሮማይስጥም ፪ ኢ (I Y) ፪ ዠ (G J) አለ እያሉ ጽፈው መልስ የሰጡትን አነበብነው።ስለ ሆነም ብርሃንና ሰላም የጠየቀ ግን በዚህኛው ፊደል መጻፉ አይገባም የሚል ሰው ይገኛል ስለምን ቢሉት ግን ሳይጨንቀው አይቀርም እያለ ነው።ይህም እርግጥ ነው እኔም እንደ አቅሜ እነዚህ ፊደላት የሚገቡበትን ቦታና ምክንያቱን ልዩ ልዩ ሊቃውንት ብጠይቅ ቦታውን ለይተው ያሳዩኝ ጥቂቶች አገኘሁ ። ያውም በስንት ጥርጣሬ ሰዋስው እያዩ ነው ። ምክንያቱን ግን እንጃ ከማለት በቀር አንድም የሚገልጽልኝ ሊቅ አላገኘሁም።ታዲያ እንጃ የሚባል መልስ ለሚሰጥበት ነገር ለምን በከንቱ እደክማለሁ በማለት ነገሩን ቸል ብየው ዛሬ እንዳጋጠመኝ እጽፋለሁ። መ ብሎ ማ ሲሉ ድምጽ እንደሚለውጥ ሁ ብሎ ሉ ሁልጊዜ ግዕዙ ከራብዑ ልዩ ድምጽ እንዳለበት ጥርጥር የለውም።ስለዚህ የሀና የአ ግዕዝ ኸ አ(E)ራብዕም ኻ ኣ እንደ ነበረ ይመስላል ።ምሳሌ እረ ጉድ ተማለት ለአ እንደ ኸ ያለ ድምጽ ቢሰጡት ያምራል ፊደላቱ መልክቸው ልዩ እንደሆነ ድምጻቸውም በድሮ ዘመን ልዩ እንደ ነበረ የሚያስረዳ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ቃል ነው ። ሊቃውንትና የታሪክ መጻሕፍት እንደ ሚናገሩት የኢትዮጵያ ቋንቋ አወራረድ የሚከተለው ነው ። እብራይስጥ ዓረብኛን ወለደ ዓረብኛም ግዕዝን ወለደ ግዕዝም ትግርኛን ትግርኛም አማርኛን ወለደ ይባላል ። ስለዚህ ሩቅ ሳንሄድ ትግርኛን ብንመረምር የሀና የሐ የአና የዐን የድምጽ ልዩነት እናገኛለን ። በትግርኛ ሐ ዐ በጉሮሮ የሚነገሩ ፊደላትናቸው፤የነሱ ድምጽም በእብራይስጥና ባረብኛ ልክ አለ፡ጠ ብሎ ጨ ሲሉ ድምጽ እንደሚለወጥ ሁሉም በዱሮ ዘመንም ጸ ጸድቁና ፀ ፀሐዩ ድምጽ ነበራቸው ብሎ ድምጹንም እያሰማ አንድ የትግሬ ሊቅ ነገረኝ። ስለዚህም ከዘመን ብዛት ነው የጠፉ እንጂ በትግርኛ ለኅ ብዙኃን ሌላ ልዩ ድምጽ እንደነበረው ጥርጥር የለበትም ። የዚህንም ሁሉ ድምጽ ተቀራርቦ ቃልተነጋገሩ በጽፈት ለይቼ ለመግለጽ ስለቸገረኝ በጣም አዝናለሁ ። ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ የሐ ዐ ኸ ቐ ቘ ኼ ድምጽ እንኳ በማርኛ የለምና ነገሩን ለመረዳት ብትፈልጉ ሁለት ሶስት ትግሮች ጠርታችሁ ተነጋገሩ ብትሏቸው ያንጊዜ የነዚህን ፊደላት ድምጽ ታገኙታላችሁ ። ፊታውራሪ አርአያ ሊቃውንቱማ ያውቁታል ብለዋል ።

ስለዚህ ይህን ቃል ሳነብ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ትዝ አለኝ።አንድ አላግጦ መብላት የፈለገ ወታደር ወታደርነቱን ተወና እራሱ ላይ ትንሽ ጨርቅ መሳይ ጠምጥሞ ዝክር ተዝካር አድርጉ ጠላ ጥመቁ ጠጅ ጣሉ ብሎ እየዞረ ሲሰብክ አንዲት ለመድኃኔ ዓለም ዝክር ያደረገች ሴት አባቴ ይምጡ ብላ ምሳውን አብልታ ጠላም እንደፈቀደው ስታጠጣው ውላ እመጨረሻው ሰሙ አባቴ መድኃኔ ዓለም ማለት ትርጉሙ ምንድነው ብላ ጠየቀችው።እሱም መቸም ትርጉሙን እያውቀውምና

ሰማሽ ልጅ ነገር ይኖረዋል እንጂ በንዲያው መድኃኔ ዓለም ተብለን አላት ይባላል ። አሁንም ሊቃውንቱ ሀ ሃሌታ ሎሀ ወሀሎ ተሚለው ቃል መግባቱ ሥሩ ይህ ስለ ሆነ ምክንያቱም እንዲህ እንዲህ ስለ ሆነ ነው ብለው ገልጠው ቢነግሩን መልካም ነበር ። አለዚያ ሐ ሐመሩ ተብሎ ሰብሐ ስቡሕ ስብሐት እያለ ይገባል ብሎ መልስ ሲሰጡ ጠያቂው ስለ ምን በምን ምክንያት እያለ የጠየቀ እንደሆነ ካባቶቻችን ስለ ቆየ ነው ከማለት በቀር ሌላ መልስ የሚገኝ አይመስለኝምና እላይ ባነበብነው አላጋጭ ወታደር እንዳንመስል ማሰብ ያስፈልጋል ። ሰው ከዘመን ብዛት የተነሣ አለባበሱ አኑዋኑዋሩ አኳኋኑም እየተለወጠ እንደ ሚሔድ ሁሉ ቋንቋውና አጻጻፉም ይለውጣልና ስለ ዚህ እኒህ አሁን የሚያጠያይቁ ያሉ ፊደላት በድሮ ዘመን ለነበረ ቋንቋ እንጂ አሁን ላለው አልተደረጉም ይመስለኛል ። አሁንም ብርሃንና ሰላም እንደ ጠየቀው አነጋገር ድምጻቸው አንድ ከሆኑት ፊደላት አንዳን ብቻ መያዝ ይሻል ይመስለኛል ። ይልቁንም የጽፈት መኪና ለማውጣት የታሰበ እንደ ሆነ ፊደላቱ ቢበዙ ማስቸገሩ ጥርጥር የለበትምና (ኮንሰናንት)እንዳይበዙ ኋ ሏ ሟ ሗ ሯ እንዲሁ እስከ ፏ ሌላ የፊደል መልክ ከመፍጠር እንኳ ሁዋ ሉዋ ሙዋ እያሉ መጻፍ ይሻላል ። አቶ መኰንን ኢያቄም በሮማይስጥም ፪ ኢ (I Y)፪ ገ(G J) አለ ብለዋል ፥ መኖሩ እርግጥ ነው ነገር ግን ኤሮጳችን በሌላው እውቀታቸው እናመሰግናቸዋለን እንጂ በዚሁ አንድ ድምጽ ላለው ቃል ፪ና ፫ መልክ ቢያደርጉለት እናመሰግናቸውም ባሁኑ ዘመናችን ስለ ምን ብለን ጠይቀን ትርጉሙን ካላወቅን እንዳችም ነገር ልንቀበል አይገ ነም ። የእንግሊዝ (ኦርቶ ግራፍ) አጻጻፍ በጣም ያስቸገረነው ስለ ዚህ እንግሊዞች ሊለውጡት አስበው ነበር ስለ ሆነም ከሕፃናቱ ይልቅ በድሮው አጻጻፍ የተማሩ ሰዎች የሚበዙና የሚበልጡ ስለ ሆነ አስቸግሮ ነገሩ ቆይቷል ። ለወደፊቱ ግን ምናልባት ሳይለወጥ አይቀርም ብሎ አንድ የኤሮጳ ሰው አጫወተኝ ይህን መጻፌም አቶ መኰንን ኢያቄም በሮማይስጥ ፩ ድምጽ ላለው ቃል ፪ መልክ አለበት ብለው ምሳሌ ስላመጡ ነው ።

ኪዳነ ማርያም አበራ

የጽገጽ ተከታይ።

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

ቀረጥም ስለሌለው ዋጋው ያንሳልና እንደዚህ ያለውን መሣሪያ ብዙ ሰው ይገዛል ። በጊዜም ብዛት የጥጡ እርሻ ይሰፋል በየባላገሩም ቤት ያሉት ሴቶች ዱሮ በስንፍና የተዉትን ሥራ ዛሬ በዲሱ መሣሪያ ተግተው ይሠራሉ ። አዲሱም መሣሪያ ከዱሮው እንዝርት እጅግ የበለጠ ስለሆነ ሴቶቹም ከዱሮው በ፫ም አብልጠው ይፈትላሉ ። ሸማኔውም ከጥንቱ የተሻለ መን ከኤሮፓ መጥቶለት ከዱሮው አብልጦ በትጋት ይሠራል ።

በከተማውም የሚቆመው የጨርቅ ፋብሪካ በየቀኑ ልዩ ልዩ የሆነ ብዙ ልብስ ይሠራል ። በዚሁም ለባላገሩ የሚያስፈልገው ልብስ ካጠገቡ ይሠራለታልና የተላላኪው ነጋዴ ደመወዝ ስለ ቀረ ባላገሩ ጨርቁን እንደድካሙ መጠን በቅርቡ ያገኛል ። ስለዚህም ለርሱና ለልጆቹ ትርፍ ልብስ እገዛለሁ ሲል በብዙ ያርሳል ። ሸማኔውም ብዙ እህል ሲረልግ እንደድካሙ መጠን በቅርቡ ያገኛል ። ገዢም አጠገቡ ስላገኘ በመፍጠን ብዙ ሸማ ይሠራል ። ከዚህም አጠገብ ላጠገብ ሆኖ መተባበር የተነሣ ሸማኔው ለሸማው ብዙ እህል ፤ አራሹም ለእህሉ ብዙ ሸማ ያገኛል አራሹም ዱሮ የሚያስፈልገው ሸማ የሚመጣለት ከሩቅ ስለነበረ ባንድ ጊዜ ድካም የሚገኘውን ሸማ ለመግዛት ስምንት ጊዜ ሲደክም ነበረ ። ሸማኔው አጠገቡ ከሆነ ወዲያ ግን ዱሮ በከንቱ ለተላላኪው ነጋዴ ደመወዝ ሲባክን የነበረው ድካም ትርፉ ነው ። ስለዚህም ምንስ እንኳ የሚከፍለው ግብር ከዱሮ ባይቀልለት የሸማው ዋጋ ከዱሮው ይልቅ ያንስለታልና ሚዛን ይሆናል ። መሬቱንም ለዕዳ አሳልፎ ለመስጠት ወይም ስለ ጥቂት እርዳታ ሲል ለማውረስ እንደ ዱሮ አይቸኩልበትም ሥራው ሁሉ ተቃሎለታልና ። ዕዳውንም ዱሮ ለሸማ ሊሰጠው በነበረ ትርፍ ይከፍለዋል ። ነገርም ሲያገኘው በዚሁ በትርፉ ጠበቃ ይገዛል ይልቁንም ባገሩ ውስጥ ሥራ ሲበዛ ሕዝቡም ጭቅጭቅንና ነገርን ይጠላል ። ማለት ጭቅጭቅና ጠር ቅምያ የሚበዛው በሥራ ባልሰለጠኑ ሕዝቦች ውስጥ ማለት ነውና ስለዚህም ሕዝቡ ሲሰለጥን የሹሞቹን እርዳታና ቸርነት የሚፈልግበት ምክንያት ሁሉ ያንሳል ። ስለዚህም ባላገሩ እርሻውን ለቆ ወደከተማ ለመሄድ እንደዱሮ የማያስፈልገው ይሆናል ። በታኅሣሥ ፳፫ቀን ፲፱፻፲ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ እስከ ታኅሣሥ ፳፪ቀን ፲፱፻፬ ዓመተ ምሕረት ድረስ ከውጭ አገር የገዛነው ጨርቅ ዋጋው ቢታሰብ ፬ሚሊዮን ፬፻፲፪ ሺ ፻፸ ብር ሆነ ።

ጨርቅ ባገራችን ውስጥ የሚሠራ ቢሆን ይህ ገንዘብ ወደ ውጭ አገር አይሄድብንም ነበር ። ወዲያውም ጨርቅ ሁሉ ባገራችን ውስጥ ቢሠራ ገበያው ይቀርብ ነበርና ሕዝቡ ይህን ያህል ዋጋ ባልፈጀበት ነበር ። ሌላም ነገር ሁሉ እንደ ጨርቁ ባገራችን ውስጥ እንዲሠራ የሚሠራበትን መሣሪያ ሁሉ ያለቀረጥ እንዲገባ ዕቃው በውጭ አገር ተሠርቶ ሲመጣ ግን ከፍ ያለ ቀረጥ ቢያደርጉበት ከውጭ አገር የሚመጣ የተሠራ ዕቃ ሁሉ ተወዶ ባገራችን ውስጥ ሥራ ይጀመር ነበር ። ሥራውም እየተለመደ ይሄዳል ። ዕቃውም ለጊዜው ቢወደድ ሕዝቡ በሥራው ሲሰለጥንበት እያደር ይረክሳል ። የሰሩትንም ዕቃ የሚለዋወጡ ሠራተኞች አጠገብ ላጠገብ ስለ ሆኑ በከንቱ ትርፍ ድካም አይሄድባቸውምና እንደ እየሥራቸው መጠን ይለዋወጣሉ ። የሚፈልጉትንም ነገር ሁሉ ያለ ብዙ ድካም ለማግኘት ሲሆንላቸው በየሥራቸው እየተጉ በመከከላቸውም ጠብ እያነሡ ይሄዳል ።በጠቡምፈንታ ስምምነትና ዕውቀት ደስታም ይገባል ። ከስምምነቱም የተነሣ ሕዝቡ ተባብሮ ይመከታልና ሹሞችና ወታደሮች የሕዝቡ አለቆች መሆናቸው ቀርቶ የሕዝቡ ሎሌዎች ይሆናሉ ። ባላገሩም እንዳይጠቃ ታውቆት ሹምና ወታደር ሁኜ ልብላ አይልም ፤ መሬቱንም ሽጦ ወይም ለሹም አውርሶ ወደ ከተማ ለመሄድ አያስብም ። የሚሸጥበትና የሚገዛበት ገበያ አጠገቡ ስለ ሆነ ዱሮ ለነጋዴው ሊሰጠው በነበረው ትርፍ ድካም ዕዳ እንኳ ቢኖርበት ይከፍላል ። ከዱሮውም ይልቅ በሥራው ሁሉ ትርፍ ስላገኘ የመንግሥትም ግብር ቢበዛበት እንደ ዱሮው አይጫነውም የሚከፍለውን አያጣምና ።

እንደዚሁም ዕቃ ሁሉ ባገሩ ሲሠራ መንግሥትም የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ከውጪ አገር ማስመጣቱን ጥሎ ከገዛ ገበሮቹ ይገዛቸዋል ። የመንግሥትም ሹማምንቶችና ሠራተኞች ለኑሮዋቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ ከገዛ አገራቸው ውስጥ ይገዛሉ ። ከሕዝብ የሚሰበሰበው የግብር ገንዘብ ተመልሶ የሕዝቡ መትጊያ ይሆናል ።

እስቲ አሁን ማናቸውንም ነገር ሁሉ ራሱ መሥራት በሚችል አገር ውስጥ አንድ መንገድ ቢሠራ ስንት ሰዎች በሥራቸው በተጉ ። የብረት ሠሪዎች ዶማንና ድጅኖን እንሸጣለን ሲሉ ፤ አናጢዎችም ያፈር ማመላለሻውን ጋሪ እንሠራለን ሲሉ ሸማኔውም የሠራተኞቹን ልብስ ሲሠራና ሲሸጥ ፤ አረኛውም ለሠራተኞቹ የብርድና የዝናብ ልብስ የሚሆነውን የበግ ጠጉር ሲቆርጥ ። ማለት ሕዝቡ በሰለጠነ አገር ውስጥ መንገድ ቢሠራ ብዙ አዕላፋት ሰዎች በየሥራቸው ይተጋሉ ። ሠራተኞችንም ሁሉ የሚመግብ አራሹ ነውና ትርፉን ሲፈልግ ይተጋል ። ባለርስትም በመሬቱ ይከራል ፤ ከእርስቱም የበለጠ እህል እንዲገባለት በጣም ይጥራል ።

እነሆም በዚሁ በጥረቱ ባጠገቡ ያሉት በያይነቱ ሥራ የሚሠሩ ሠራተኞች በጥቂት ዋጋ ይረዱታል ። ፍሬያማውም መሬት ከጐርፍ ጋራ እየተነዳ እንዳሄድ አረግረግም እንዳይሆን ብልሀት ይበጅበታል ። እህሉንና በሬውን ቆዳውንም የሚሸጥበት ገበያ ቅርብ ስለሆነ ፍጉ በአረብያና በምድር ባቡር በጥቂት ድካም ይመላለስለታል ። መሬቱም ያበደረው እህልና ሣር በቶሎ ስለተመለሰለት ሁለተኛ ለመስጠት ይቸኩላል እንጂ አይለግምም ። ይልቁንም በእውቀት ከያዙትና ብዙ ፍግም ከሰጡት ከዱሮው ይልቅ ብዙ እህል ያበቅላል ። በዚህም ምክንያት የመሬቱ ጌታ በየዓመቱ እየከበረ ይሄዳል ። ዱሮ አባቶቹ በዕዳ ተይዘው ወይም ለሹም አውርሰው እንደሆነ የተነቀለውም ሰው ሁሉ የእጅ ሥራ ተምሮ ሠርቶ ባገኘው ትርፍ እንደገና መሬት ለመግዛት ይጣጣራል ። እነዚያም ያላቅማቸው ብዙ መሬት የያዙትም ሰዎች ከመሬታቸው ከፍለው ይሸጡለታል ። በዚሁም ባገር ውስጥ ያለው ቦታና መሬት ከጥቂት ሰዎች ወጥቶ እንደ ገና ይከፋፈላል ። እያንዳንዱም አራሽ የሚያርሰው መሬት ገንዘቡና ርስቱ እንደሆነ በጣም ይታወቃልና እንዲሻሻልለትና እንዲያምርለት ባለው ጉልበቱ ይተጋበታል ። በዚሁም በትጋቱ ለራሱና ላገሩ ትርፍ ያገባል ።

እነሆ መሬት በጥቂቶች ሰዎች እጅ ሲገባ ላገሩ ክፉ ምልክት ነው ። ሕዝቡ እንደ ደኸየና የመንግሥቱ ኃይል እያነሰ እንደ ሄደ ይመሰክራል ። መሬቱ ተከፋፍሎ በብዙ ሰዎች እጅ የሆነ እንደሆነ ግን የሕዝቡን ሀብትና የመንግሥቱን ኃይል ያመለክታል ። ይህ ስለ ተባለ ግን መሬት አይሸጥ አይለወጥ ተብሎ ቢታወጅ ለሕዝቡ የበለጠ ጉዳት ይሆንበታል ። ባላገሩ ያለው ገንዘቡ መሬቱ ብቻ ነውና ይህንንም ያለውን ገንዘቡን እንደ ልቡ ካልሸጠ ካለወጠ ገንዘቤ ነው የሚለውን ነገር ፈጽሞ ያጣልና በዕዳም ቢያዝ እጁን የሚያወጣበት ነገር ያጣል ።

ግብርም ሲበዛበት እንዳይሸጥ ስለ ተከለከለ ለሌላ ለሚያርስ ሰውም ሳያስረክብ ፤ መሬቱን በዶውን ትቶ ይሰደዳል ። መሬቱም የሚያርሰውና የሚጠብቀው ሰው አጥቶ ቆይቶ ከተበላሸ በኋላ መንግሥት ለሌላው ሰው ቢፈቅድለት እንኳ እንደ ፈቃዱ ልሸጠውና ልለውጠው የማልችለው መሬት ምን ይጠቅመኛል ሲል ደስ ብሎት አያቀናውም ። ምናልባት እንኳ ለእርሻ ማትጊያና እርዳታ ተብለው ባንኮች ቢቆሙ ወይም ማናቸውም ሌላ ዓይነት አበዳሪዎች ቢተባበሩ ባላገሩ ከርስቱ እንዲነቀል ለማፋጠን ነው እንጂ ዛሬ አይጠቅሙትም እስቲ አሁን ባገራችን ከባንክ የተበደረ ባለ ርስት ሁሉ ከመሬቱ ሳይነቀል ወይም መሬቱን ለዋሱ ወይም ለሌላ ሰው ሳይሸጥ ብድሩን የመለሰ ከመቶ ስንት ይገኛል ። ለዚሁም ቃል አንድ አንዱ ሰው እንዲህ ብሎ ይመልስ ይሆናል ። ዛሬ በኢትዮጵያ አገር ያለው ባንክ ለባለርስቱ ሲያበድር ገንዘቡ የሚመለስበት ጊዜ ያጥርበታልና ባላገሩ መሬቱን ሳይሸጥ ብድሩን ለመመለስ አይሆንለትም ፤ ይህ ምላሽ ግን መሠረት የለውም ፤ ለብድሩ መመለሻ ብዙ ጊዜ ቢሰጡት ግን በጥቂት በጥቂቱ ሲል ለመመለስ አያቅተውም ነበር ። ባንኮቹም ለባለ ርስቱ አሥር ወይም ሀያ ዓመትም ጊዜ ቢሰጡት ያው ነውና ለባላገሩ አንዳች ጥቅም አይሆነውም ። ባላገር የሚበደር ከመሬቱ በሚያገኘው ትርፍ ለምግቡ ያህል አስቀርቶ ነው ። ነገር ግን የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ባጠገቡ ተሠርቶ ቢሆን ድካሙ ጥቂት ይሆን የነበረው የሚመጣው ከሩቅ አገር ስለሆነ የስምንት ጊዜ ድካም ሲፈጅበት ጊዜ ደክሞ ለራሱ የሚቀርለት ትርፍ ምንድነው ። ከዚህ በኋላ ደግሞ መከራ ይጫነዋል ። መንግሥትም በባላገር ውስጥ ካሉት ሠራተኞች የሚያስፈልገውን ዕቃ ሁሉ የሚገዛ ቢሆን ዕቃውን የሚሸጡለት ሠራተኞች የሚያስፈልጋቸውን ምግባቸውን የሚገዙት ከባላገሩ ነበርና ያግብር ሆኖ ከባላገሩ እጅ የወጣው ገንዘብ እንደ ገና ይመለስለት ነበር ። ዳሩ ግን ነገሩ ገና እንደዚህ አልሆነም ።

ባላገሩ ዛሬ ሲገብር እንጨት ሰብሮ እህል ጭኖ ወይም ቤት ሠርቶ ወይም ደግሞ አሥራት አፍሶ ነው ። በጉልበቱ የሚገበረው ግብር መቼም ሲገበር ወድያው ያልቃል ። በእህለም የገበረውን ግብር ሥራ የማይሠሩ ሰዎች በከንቱ ይመገቡታል ፤ ማለት እንደ መጀመሪያው ዓይነት ግብር በከንቱ ይባክናል ፤ ሶስተኛውም ዓይነት ግብሩ ብር ነው ። ይህ ብር የሆነ ግብር ግን ለሱ አይመለስለትም ። መርፌ ፤ ምሥማር፡ ቢላዎ መጥረቢያ ዶማ ፤ ጐራዴ ፤ ጠመንጃ ሱሪ ፤ቀሚስ ካባ ፤ ባርኔጣ ፤ ምንጣፍ ፤ መጋረጃ ፡ ወምበር ፤ አልጋ ፤ ሌላውንም ምናምንቴ ዓይነት ዕቃ ሁሉ ለሚያመጡ ነጋዴዎች ከባሕር ማዶ ሆነው ለሚሠሩት ሠራተኞች ይሄዳል ። እነዚህ ሠራተኞችና ነጋዴዎች ግን ከጥቂቶቹ በቀር የሚበዙቱ ምግባቸውን የሚገዙት ከገራችን ባላገር አይደለም ከገራቸው የሚመጣውን ነው እንጂ ።

እነሆ የኢትዮጵያ ባላገር የተጐዳው በሁለት ፊት ነው ። መጀመሪያ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እገዛለሁ ሲል ትርፍ ድካም በከንቱ ይሄድበታል ። ለመንግሥትም የሚከፍለው ግብር ግማሹ በከንቱ ይባክናል ። ግማሹም ለውጭ አገር ሰዎች ጥቅም ነውና መትጊያ አይሆነውም ። እንግዲህ የኢትዮጵያ ገበሬ ትርፉ ምን ይሆን ። ከወዴትስ ይምጣ ለዚሁ መምጊቻ ። ግን አንዱ እንዲህ ይል ይሆናል ፤ እህል ከዱሮ ይልቅ ተወደደ እህሉን እየሸመተ

ብድሩን መመለስ ምን ያቅተዋል ። እንግዴህ የሚመልስ ሰውን የሚያስተውል ሰው ነው ።

ከዚህ የቀረው በሚከተለው ይታተማል።

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት መጽሐፍ ነው ፣

ስለ ጥያቄ አመላለስ ።

አንድ አጽፍ የለበሱ መነኵሴና የአውሮፓ ሰው በቤተ ሳይዳ የተመላለሱትን ቃል ክቡር አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ሰምቶ ብርሃንና ሰላም ለሚባል ወዳጁ አጫውቶት ያ ብርሃንና ሰላም የሚባለው ወዳጁ ከስምንት ቀን ሐሙስ ሐሙስ ቀን እየመጣ ታናሽ ወንድሚ በፈቃዱ ወልደ መስቀልን ሲ ነግረው እይቼና ሰምቼ ይህ ብርሃንና ሰላም የሚባል ወዳጅህ ደህና ደህና ምክር ሲመክርህ አያለሁ አንድ ምክር በከፍለው ይችል ይሆን ብለው አሁን እንዳየኸው ያንዱን ነገር ላንዱ ሲያቀብል ነው ኑሮው አለኝ ። እንኪያማ ነገር አይቋጥርማ አልኩት እምነ አንተም ብትነግረው እስከ ስምንት ቀን ድረስ ለሁሉ ያደርስ ልሃል አለኝ ። ኢትሕሚ ብውሳነ በውስተ ቤትከ እስመ ዖፈ ሰማይ ብርሃንና ሰላም ያወጽኦ ለነገርከ የሚለው ንባብ ለካ ይህ ነው ብዬ አንድ መነኵሴ (አባ አጋቶን)ከቶብ በኋላ የወለደው እምተናግሮ ይሄይስ አርምሞ የሚባል ወዳጄን ብጠይቀው ሕድግ ምዕረሰ እንዲል ። አንድ ጊዜስ ተው ንገረው አለኝ እንኪያስ አንተ ከፈቀድክልኝ ልንገረው ብዬ ወፍ ብርሃንና ሰላም ጭሮ የሚያወጣውን ነገር ጀመርኩ ።

ምሳሌ፡መጀመሪ መንግሥት ከሚገዛው አገር ውስጥ መምር ቢያገኝ ወይም ባያገኝ ከማይገዛው አገር በገንዘቡ ፈልጎ አምጥቶ የወር ቀለብ ሰጥቶ በቀለብ ላይ እርስት ሰጥቶ ያገሩ ልጆች እንዲማሩለት ያኖረው የለምን (ሁለተኛ)ያ መንግሥት ከማይገዛው አገር በገንዘብ ፈልጎ ያመጣው መምር የዘመኑ ልጅ ወረተኛ ነውና ያገሩን ትምርት ጠልቶ ሌላ ትምርት ወዶ ሰይሟላለት ቢደክም ወይም ቢሞት መንግሥት ቀድሞ ካገኘበት አገር ሰው ልክ ሌላ መምር ቀድሞ በተዋዋለው ከንቱራት ያወጣ የለምን)እንደዚሁም ሁሉ እኛ አጽፍ የለበሱ መነኵሴ እንደ ተናገሩት አባት ያበጀው ልልጅ ይበጀው ነውና ምንም ምን ዛሬ የሃይማኖት እናታችን እስክንድርያ አንድ ጥቀርኮት የለበሰ ልጅ እንደ ተናገረው ሥራዋ መጥፎ ቢሆን ቀድሞ አጼ ዮሐንስ ባመጡበት አምኃ ሰጥተን እስክንድርያን እናታችን ጳጳሱን አባታችን ብለን እንኖራለን እንጂ በጥቁር ጳጳስ እጅ አንበረክም ። ጥንቱንስ በስንፍና ብዛት የእስክንድርያ ክፍሏ ወደ ሌላ ሄደብን እንጂ ውስተ ኵሉ ግብዕ አድያሚሃ አድመዕከ በስብከትከ ወንጌላዊ ተብሎ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀሉ ዙሮ ሰበካዋ የእኛ አልነበረምን አሁንም የእስክንድርያ ሀገ፡ አገራችን ፈጣሪዋ ፈጣሪያችን ሃይማኖቷ ሃይማኖታችን ነውና የሚገባውን አምኃ ሰጥተን ጳጳሳችንን አምጥተን እንኖራለን ። አምኃም ብንሰጥ ነውር የለም ። ውሂብስ እምረኪብ ውእቱ እንዲል ። ቀድሞ የሀገራችን ንግሥተ አዜብ ስንኳ መቶ ሀያ መክሊተ ወርቅ ዝባድ ተንከራ ዘኢትዮጵያ ይለዋል ሉል ይህን የመሰለ አምኃ ይዛ ሂዳ ከሰሎሞን ጥበብ መስማት የተነሣ ምኒልክን የመሰለ ፲ኩሎ አምጥታ ከቀዳማዊ ምኒልክ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ከዳግማዊ ምኒልክ እስከ ዘውዲቱ ምኒልክና ተፈሪ መኰንን ደርሶ ቀድሞ ከሚወራው ዓለም ይልቅ የሚበልጥ ዓለም ይዘን ያው የእስክንድርያ ጳጳስ ያስተማረን ሃይማኖት ጸንቶ ክህነቱና ስልጣኑ ተባርኮ ሀገራችን ኢትዮጵያ አብባ አፍርታ ከፍሬዋ ብዛት የተነሣ የቤት ሰምቿን አጥግባ ለውጭ ተርፋ እናያት የለሞይ ።

አሁንም እነሆ የብርሃንና ሰላምን ንባቡን ከነትርጓሜው የእምታውቁ ገለባውን በደህና እውቀት ነፋስ ለያይታችሁ ፍሬ ፍሬውን በጥበብ ውድማ አምርታችሁ ለመንግሥት የሚሆነውን ከሥር አንድ አውጥታችሁ ሁሉን በሚችል ትዕግሥት ጐተራ አኑሩልኝ ስል አመለክታለሁ ።

ገዛረ የስ ወልደ መስቀል ዘመክነ ሥላሴ ዘልጎቀ በውስቴታ።

ለጥያቄ መልስ በትንሹ ።

እድፍ ጉድፍ ትንሽ ሰሀ የሌለበት ብዕር ያገሩን ጥቅም በጉልህ ጽፎ ባይ ምንም ለዚህ የሚበቃ ምስጋና ለመስጠት እውቀት አነስ ቢለኝ እውነቱን የመከተ ነውና አይኔን ጨፍኜ ከሾሉ እርሳሶቹ ጋር የዶለዶመውን የኔን እርሳስ ደመርኩት ።

ብልሁ ራጊብ ለዚያ ለገር ሰው አሁን እመለሳለሁ ቆየኝ ብሎት ሲሄድ ተመልሶ እስኪመጣ መጠበቁ እራሱን ለመቻል እማያሪብ ኖሯል ሰውየው ምንም ጥንቁቅ ቢሆን ንዝህላልነት ይቃወሰዋልና ነው እንጂ የሰውን አገር ሰው ምንስ ቢወዱት የቤቱን ቁልፍ እንዴት ያስረክቡታል ። በጥንቃቄ ሰው እራሱን ለመቻል የሚደርሰው ያለፈውን ጉዳቱን በማሰብ ነው ።

አባ ሆይ የጥቁር በሬ አንጋሬ አጥፍ አይሆንምን የጥቁርስ ፍየል ሌጦ ብራና ሆኖ መጽሐፍ አይጻፍበትምን ተጽፎበትስ ከዚያ ከነጭ ፍየል ሌጦ ብራና ከተጻፈበት ጋር የዚህ የጥቁር ፍየል ብራና ልዩነት አለውን እስቲ ያ ከዚህ ክብር የሚበልጥበት ምክንያቱ ምንድነው የነጭ ክብሩ የባህረው ነው ለማለት ይቻላልን ወይስ አምላክ ምሉዕ በኵለሄ አይባልም አለዚህ ነገር አይሆንም ማለትስ የፍጡር ፍጡር መሆን ነው እነሆ መብራት ይበራል ብዙ ጧፎች አቃጥለው ጨለማ ባለበት ሁሉ ሊያበሩ ይችላሉ ።

ማህሉ ጽጌ ።

የሚጠቅም ብልሃት ።

እግዚአብሔር ዓለምን በጥበብ ፈጠረ ።

ዕውቀት የሚቀበል ሰውን በዚህ ዓለም ላይ አኖረ ።

ሰው በዓለም ላይ ሲኖር በኃዘንና በደስታ ይቀመጣል ።

የሰው ደስታና መከራ ግን በየ ጊዜው ይለወጣል ።

ሰው መከራ ባገኘው ጊዜ ዘመድ ወዳጅ ይታጣል ።

ደስታ ባገኘው ጊዜ ጠላት ወዳጅ ሁኖ ይመጣል ።

የእግዚአብሔር ተግሣጽ ያንቀጠቅጣል ።

ኃያል የነበረውን ያፈልሳል ።

የደከመውን ያነግሣል ።

ከሰው የፈቀደውን ያነግሣል ።

ያልፈቀደውን ይነግል ።

እግዚአብሔር የሰውን ሕሊና ይገልጣል ።

በመማር ጥበብን ለሰው ልጆች ይሰጣል

ጥበብን አጥብቀህ ስትፈልጋት ።

የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርንና ንጉሥን መፍራት ።

የንጉሥ መፈራት ።

ሞትና ሕይወት በእጁ ናት ።

እጣዚአብሔርሳ።
ይታገሣል እስኪነግ ።
የንጉሥና የዳኛ ክፋት ።
የሀገርና የሕዝብ ጥፋት ።
በፍርድ ትክክል የሆነ ዳኛ ።
ገንዘቡን ጠልቶ እንደ ደመኛ ።
ገንዘብን እንደ ነፍሱ ከወደደ ።
ድሆችን ገደል ሰደደ ።
ባሁኑ ጊዜ የሚጠቅመው ብልሐት
ሙያትና ወንድርነት ።
ወታደርነትና ደብተርነት ።
ቋንቋ ማወቅና ጽሬት ።
በሚመጣው ዘመን ወደ ፊት ።
በንጉሀ አድራሻ ማለት ዘበት ።
የሀገራችን ልጆች ሲማሩ ።
አንድ አንድ የእጅ ብልሐት ይጨምሩ ።
ጥርስና ቀንድ ማነጽ እንጨት።
ቈርቅና ብር ነሐስ ብረት ።
ድንጋይ ሸህላ በእጅ መሥራት ።
የእጅ ሥራ ጨምሮ የተማረ ።
በሁሉም ቦታ ከበረ ።
መኳንንት የሚሾመው አገር እነስ ።
ድኃ ሥራ እየጠ ተላቀስ ።
መኳንንት ልጁን ለማስተማር ባይጓደድ
መልክም አረማመድ ።
ድኃ እንዳይርስ ጭቃ ሹሙ መከራ
ሲያርሱ ክርሞ አየበዘሬ ።
ንግድ ቢደዞ ።
መቸገር በዘ በገወንዙ።
የሽፍታ ብዛት ።
ያገረ ገገር ስንፈት ።
ሀገራችን ለምለሙ እናሪያ ።
እናሪያን ማልማት በመሣሪያ ።
እናሪያን አስማሰልጠንና አስማልማት።
የኢትዮጵያ ዕንቅፋት ።
እናሪያ በየት ደልማ ።
ሁሉ እየፈቱ ሲቀማ ።
እናሪያን ማልማት በርትቶ ።
ብዙ ከተማ አበርቶ ።
ስምን ፈልጎ ጥቅምን ትቶ ።
ጫካ መንጥሮ አርሶ በልቶ ።
ሽፍታን በጥንት አጥፍቶ ።
የተማረ ቤት አብዝቶ።
ሺ ዓመት ቢገዛ ጌታቸው ።
የእናሪያ ሕዝቦች ደስ ባላቸው ።
ከተማን በማቅል ብቻ መሥራት
አጥር ሳያጥሩ በር መዝጋት ።
ከተማን በመሳሪያ ማጠንከር ።
እወሰን ላይ ከዳር አገር ።
የዳር አገር ሹም ሲለወጥ ።
ጭፍሩ ከቦታው አደናወጥ ።
ሹም ሽር የበዛበት ሀገር ።
በግ የጋጠው ድምበር ።
ምንም አደገኝበት ያለጥፉ አፈር ።
ድኃ ሲጠቃ ለንጉሥ ማውረስ ።
ባፉ እየማቀ በልቡ ለማልቀስ ።
ከንጉሥ ነገረ ፈጅ መሟገት ።
በገባያ መኻል ሰው መጥራት ።
የድኃን ርስት ንጉሥ መውረስ ።
ጳጳስ በገንዘብ ማደያቶንና ማቅሰስ ።
አምላክ እንዳይሰማ ባደን መጠቃቀስ።
የንጉሥ ርስት ።
ሕዝቡና መንግሥት ።
የጳጳስ ርስት ።
ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ።
ለመኳንንት ግብዝና ።
ለወታደር እልቅና ።
ከተገባቸው በውነት ።
ሁሉ እየፈቱ ደመልከት ።
ሰው በየሚገባው ቢሠራ ።
በከንቱም አያልፍ ደህ አገዘመራ ።
ትንሽ ዳጥም በዜማ ።
እናገራለሁ ለሚሰማ ።
የዳኛው ምኒልክ ሁዳዱን አስፍቶ
በየቦታው ተልሞ ጥበብ አስዘርቶ ።
ገበሬው ሲታዘዝ በየሥራው ተዳቶ ።
ሳይጨርስ አረፈ አገዘመራውን ትቶ ።
ጥንትም በምሳሌ ሁሞ ደተረታል።
ዋዘኛ ገበሬ በሰኔ ደሞታል ።
ቀንበር ተሸክማ ዘውዲቱ እንደወንድ
ተረፈ እያገዛት በርትታ ስትሄድ ።
ደኸንን ጊዜ አደተህ ዳኛው ተመለስ
አታግዝንም ኢትዮጲያ እስካሁን ድረስ
ጠቅል አዘጋጅተህ ያገዘመራ እታህን
እንዳትዘነጋ ተፈሪ ምራን ።

ኃይሌ ጊዮርጊስ ወልደ ሰማዕት ።

ከስመራ አድዋ ።

ከቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዮች ሆይ በልዩ ልዩ አኳ ኋን ምክንያት እስካሁን ድረስ ያየሁትንና የሰማሁትን ለብር ሃንና ሰላም ፀያፂ ፍኖት ሳላመለክተው በመቅረቴ በጣም ኢያ ዘንኩ ከስመራ ወደ አድዋ ስሄድ ያጋጠመኝን ነገር ሁሉ ከዚህ ቀጥዬ አጽፍላችኋለሁና በቅጡ እንድታነቡት ፈቃዳችሁ ሊሆን እለምናለሁ ። በ፬ ተኛ ቀን መስከረም ፲፱፻፲፱ ዓ ም ዓድዋ ከሚ ሄዱ ነጋዴዎች ጋር ሕብረን በአቶሞቢል ተቀምጠን ስንጓዝ ውለን ወደ ማታው መንደፈራ ከተባለ አገር ደንስን ። አቶሞቢል ከሚያርፍበት ቦታ ካራቢኔሬ (ዘበኞች)ቆመው ይጠብቁ ነበር። እኛ ከአቶሞቢሉ እንደወረድንም መንቸክ ያለ ጥያቄያቸውን ያዘንሙብን ጀመር ። ስለ ሆነም ጥያቄያቸው በጅምላ ስለ ነበር እኔ አንድም ነገር ከፌ አላወጣሁም ። ዘበኞቹ ግን እናንተ አስ መራ ብዙ ወራት መቀመጣችሁ እርግጥ ነገር ነው አሁን የት ትሄዳላችሁ?የያዛችሁት ምንድነው?ሳጥናችሁን ክፈቱ እቃችሁ ሁሉንም እንፈትሸው እያሉ ነጋዴዎችን አወኳቸው ። እመጨ ረሻውም እንግዲህ ፍልከት እንዳትሉ ነገ እዚህ መዋላችሁ ነው አሏቸው ። ነጋዴዎቹም ጌቶቻችን ሆይ እኛ አስመራ ብዙ ወራት ይቅርና አንድ ሳምንት ስንኳ አልተቀመጥንም። እኛ አስመራ የዋልነውስ ፪.፫ ቀን ብቻ ነው እረ ምን አጠ ፉን ?ከሁን ቀደም እንኳን ለነጋዴ እንዲህ ጠበቅ ያለ ጥያቄ አግኝቶት አያውቅም እያሉ በትሕትና መልስ ሰጧቸው።እኔን ግን ትክ ብሎ ከማየት በቀር አልጠየቁኝምና አፌን ይዤ ዝም ብየ ነበር ። ዘበኞቹ የነጋዴዎቹን እቃ በቅጡ ፈትሸው ሰዎቹ ንም መርምረው ካበቁ ትተውን ሄዱ።ከዚህ በኋላ ነጋዴዎች ፈርተው ተጨንቀው እረ እባካችሁ እንጠያየቅ ካሁን ቀደም የኢጣልያ መንግሥት ለነጋዴ በየቀኑ ጠመንጃና ጥይት ከመስ ጠት በቀር እንዲህ አድርገው አጥብቀው ተመራምረውት አያ ውቁም ። የዛሬ ምክንያቱ ምን ይሆን?እያሉ ተጠያየቁ ። ምክን ያቱን ያወቅን ሰዎች ግን መንግሥትህን ማገልገል ማለት እን ዲህ አድርጎ ነው ብለን አመሰገናቸው ። ዘበኞቹም ሁለተኛ ተመ ልሰው ነገ ልትሄዱ ትችላላችሁ ብለው ሄዱ ስለ ሆነም እስከ ተነሳንበት ሰዓት ድረስ መጠባበቃቸውን አልተውነም ። በበነ ግታው ተነስተን ስንሄድ አርፍደን ዓዲ ኳላ የተባለ አገር እን ደደረስን መንገዳችንን ስንሄድ(ዝባን መንግሥቱ) በመንግሥት አምላክ እንዳታልፉ የሚል ድምጥ ሰማንና ምነው ብለን ብንጠይቅ ከየበቅሎቻችሁ ውረዱ አሉን።ለካስ ነጋዴዎች ነገሩን ያውቁት ኑሮ ፈጥነው ዝል ዝል ብለው ወረዱ ። እኔ ግን ነገሩን ሳላውቀው እንዴት እወርዳለሁ ብየ ምክንያቱን ጠየቅሁ። ዘበኛው ቀረብ ብሎ እዚህ(ሴንቲ ኔላ)የሚጠብቅ ዘበኛ ጠመ ንጃ ይዞ እያየኸው እንዴት ከበቅሎህ ሳትወርድ ታልፋለህ ቢለኝ ሴንቲኔላ ባዩ ልክ ከበቅሎ መውረድ እንደሚገባ ከየትም አገር አላየሁምናአሁንም በከንቱ አትድከም ሌሎችን አስሞኝ እንጂ እ ኔንስ ማስሞኘት አትችልም።አልኩት እሱም እንኳን አንተ ኢጣ ልያኖቹ ካፒታኖች ማጊሮች ሳይቀሩ እዚህ ቦታ ሲደርሱ ከየበ ቅሎቻቸው እየወረዱ ነው የሚያልፉ ቢለኝ ነገሩ ውሸት መሆ ኑን ስለተረዳሁት ከአቶሞቤልሳ ይወርዳሉ ብየ ብጠይቀው አዎን አለኝ።ሰማህ ኢጣልያኖች ኢጣልያኖች ናቸውና ካፒታኖች ማ ጊሮችም ወታደሮች ናቸው ቢሻው እንደ ፈቃዳቸው ይው ረዱ እኔ ግን ኢትዮጵያዊ ነኝ በምን ምክንያት ከበቅሎየ እወር ዳለሁ ብየ ብጠይቀው አይኑን እያፋጠጠ ከዚህ የዦነራል አሬሞንዲ አጥንት ተቀምጧል እኛ እዚህ መቀመጣችንም አጥንቱን ለመጠበቅና የሚያልፉትን ሰዎች ከየበቅሎቻቸው ለማውረድ ነው አለኝ።እንዲህ ያለ ትእዛዝ ካገረ ገዢው ተቀብ ላችኋልን ብየ ብጠይቀውም መቀበላችን ጥርጥር የለበትም አለ ኝና እኔም አገራችሁ ከመጣሁ ያገራችሁን ደምብ መፈጸም ግድ አለብኝ ይህ ሁሉ መከራከሬ እንኳ ምክንያቱን ላውቀው ብየ ነው እንጂ በሌላ ነገር አይደለም አልኩና ከበቅሎየ ወርጄ ወይ ግሩም የሰለጠኑ በተባሉ አገሮችም እንዲህ ያለ ሥራ ይሠራልን ስል

እየተደነቅሁ መንገዴን ሄድኩ ትንሽ ከለፍን በኋላ አብረውኝ
የነበሩ ነጋዴዎች አንተ ባትሰማ ነውንጂ ኢጣልያኖች ባድዋ ጦር
ነት የሞተውን ወታደር ሁሉ አጥንት በትግሬ እየዞሩ ሲሰበስቡ
ደጃዝማች ተክለሃይማኖት እንኳ ሂደው አጥንቱ ከሚፈለግበት
ቦታ ፪፫፡ቀን ከነሱ ጋር አብረው እዚያ ሰነበቱ አጥንቱ ከተሰበ
ሰበ በኋላም ባ፵ ። ግመሎች አስጭነው ከድዋ ወደ አስመራ ሲወ
ስዱት የትግሬ መኳንንት መረብ እስከ ሚባለው የትግሬና የኤ
ርትሪያ ድምበር ድረስ አድርሰው ሸኝዋቸው መረብ ላይ የኤርት
ሪያ አገረ ገገር ብዙ ፈረሰኞችና ብዙም ወታደር አስከትሎ መጥቶ
ነበረና በረሃው በኢጣልያን ባንዴራ አጊጦ ነበር አጥንቱ አገረ
ገዦው ካለበት ቦታ እንደደረሰም ግሩም የሆነ ሙዚቃ ተመታ
ከዚህ በኋላ አገረ ገዢው ዛሬ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ወዳጅነት
ተገለጠ ታመው ያሉት ጌታችሁ ደጃዝማች ተክለሃይማኖት ሊድ
ኑም ጸሎት እናደርጋለን እስከዚህ ድረስ የወንድሞቻችንን አጥ
ንት ለመሸኘት የመጣችሁ የትግሬ መኳንንት ሁላችሁን እናመ
ሰግናችኋለን እያለ ልዩ ልዩ ዲስኩር ተናገረ አለኝ እኔም አጥን
ቱ ፣ ወዳአስመራ ሊወስዱት ነበር ኣላችሁኝ አሁን ለምን ዓዲ
ኳላ ተቀመጠ ብዬ ብጠይቅ አንድ ጨወታ ወዳጅ ሰው አብሮን
ነበረና ምናልባት የሚጨመርበት ይኖራል ብሎ መለሰልኝ ሌሎ
ችን ብጠይቅ ከትግሬ ሲሰበስቡት ወደ ኢጣልያ አገር ይሄዳል
ተብሎ ነበር ኋላ ግን ነገሩ ተለውጦ ዓዲ ኳላ መቀመጡ ምክን
ያቱ አልታወቀም አሉኝ። ኪዳነ ማርያም አበራ ።

ስለ ክቡር ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ተዝካር ።

እንደ ሀገራችን እንደ ኢትዮጵያ ልማድ ክርስቲያን የሆነ
ሰው ከሞተ በኋላ እስከ አርባኛው ቀን ድረስ ድግስ ሲደገስ
ሰንብቶ በአርባኛው ቀን ቤተ ዘመዶቹና ወዳጆቹ የሆኑ ሰዎች
ሁሉ ወደ ሟቹ ቤት ተሰብስበው ካህናቱን ይጋብዛሉ ። ለነዳያ
ኑም ምጽዋት ይሰጣሉ ። በዚሁም ልማድ የክቡር ፊታውራሪ
ሀብተ ጊዮርጊስ አርባ በ፲፪ ጥር ሐሙስ ቀን ሆኖ ነበር በዚህም
ቀን የቃና ዘ ሊላ በዓል ስለ ሆነ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ
መኰንን ወደ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሔደው ነበርና
ክቡር ራስ ካሣ ወደ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ቤት ሔደው
ከተደገሠው ድግስ ለነዳያኑ ሲያበሉ ምጽዋት ሲያስመጸውቱ
ዋሉ ። ደግሞ ክቡር ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ በያመቱ የጃ
ንሆይ የዳግማዊ ምኒልክን ተዝካር ያወጡ ነበርና ለዚሁ ተዝ
ካር ጠጁ ከተጣለ ሠንጋው ከቀረበ በኋላ በድንገት ታመው
ቢሞቱ ወይዘሮ አልታዬ ወርቅና የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ
ሹሞች ለጃንሆይ ተዝካር የተደገሠውን እንደ ተለመደ እናበ
ላለን ብላው ስለ ተናገሩ በጥር ፲፬ ቀን ቀዳሚ ልዑል አልጋ
ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከመኳንንቱ ጋራ ወደ ፊታውራሪ ቤት
ሔደው ካህናቱን ሲያበሉ ውለው ተመለሱ ደግሞ በጥር ፲፭
እሁድ የፊታውራሪ ተዝካር ነበረና እንደገና ሔደው ካህናቱን
ሲያበሉ ውለው ተመለሱ የድግሱ ብዛት ከልክ ያለፈ ስለ ሆነ
ይህን ያህል ነበር ለማለት አይቻልም ። በጥር ፲፯ ቀን በንጉሥ
ወልደ ጊዮርጊስ ቤት አጠገብ በሰፊውሜዳ ላይ ትልቅድንኳን
ተተክሎ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከመኳንንቱ ሁሉ
ጋራ ጧት በእኩል ሰዓት ወደ ድንኳኑ ደርሰው በተሰናዳው
ዦፍራ ላይ ተቀመጡ ።

በዚያ ጊዜ የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ሠራዊት በጦ
ርነት ጊዜ እንደ አሠላለፉ ተሠልፎ የጦር መሣሪያው ሁሉ
ተጭኖ የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ የማዕርግ ልብሳቸውና
ጌጣቸው የጦር መሣሪያቸው ፈረሶቻቸውና በቅሎቻቸው ሁሉ
በወርቅ ዕቃ እንደ ተጫኑ ሆነው በልዑል አልጋ ወራሽና
በመኳንንቱ ፊት ማለፍ ጀመሩ ። በዚያ ጊዜ ልዑል አልጋ
ወራሽና መኳንንቱ የፊታውራሪን የጦር መሣሪያና የማዕርግ
ልብሳቸውንየወይዘሮ አልታዬንና ያሽከሮቻቸውን ኀዘን ባዩ ጊዜ
ትልቅ ከልብ የሆነ ሐዘን ተላቀሱ ልቅሶውም እንደ አባትና
እንደ ልጅ ሞት ያህል ነበር እንጂ የባዕድ ልቅሶና ሐዘን አይ
መስልም ነበር ።

ይህን በመሰለ በጽኑ ሐዘን ልቅሶው ከተጨረሰ በኋላ
ልዑል አልጋ ወራሽ ከፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ አሽከሮች
ዋና ዋናዎቹን አቅርበው የምክርና የማጽናናት ቃል ነገሩዋቸው
ቃሉም ይህ ነው ። ፊታውራሪ ከሞቱ ጀምሮ ከለት እስከ አርባ
የሚገባቸውን አደረግን ፣ ለሞት ቀዳሚያችንን ለምክር ታማኛ
ችንን ስላጣናቸው እኛ እንዘን እንጂ ለናንተማ እኛ እያለና
ችሁ ምን ጉዳት አለባችሁ ። እራቅ ላለውም ሰው ይኸንን ቃል
ንግሩችሁ ለቅሶውን አስተውት ብለው ከሀዘናቸው አኳሁን
ጋር ከቃላቸው በሰማ ጊዜ ተቀማጩም ቋሚውም እጅግ ደስ
አለው ።

ከዚህ በኋላ እንደ ልማዱ የኑዛዜው ቃል በቤታቸው
ይነገር ብለው ለማስተናበሩም የግቢ ሚኒስቴር ደጃዝማች
ወልደ ገብርኤልና ሊጋባ ወዳጆ ታዘው ሔዱ ልዑል አልጋ
ወራሽም ከመኳንንቱ ጋራ ወደ ትልቁ ግቢ ተመለሱ ።

የኑዛዜ ቃል ።

በሀገራችን በኢትዮጵያ ትልቅ ሰው የሆነ ሁሉ ገና በሕ
ይወቱ ሳለ የቤቱን የርስቱን የገንቡን ነገር አደላድሎ ጽፎ
ያስቀምጣልና ፣ ክቡር ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ በዚሁ
ልማድ አስቀድመው ሳይታመሙ ተናዘው አስጽፈው አስቀም
ጠው ኑሮ እንደ ደንቡ ወራሾቻቸው ቆመው ዳኛና እማኞች
ተደርጎ የኑዛዜው ቃል ተነበበ ።

ወራሾችም ያደረጓቸው የወንድሞቻቸውን ልጆችና ዘመ
ዶቻቸውን ነው እነዚሁም ስማቸው ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው

፩ኛ የፊታውራሪ ኃይለ ማርያም ልጆች አለቃው ነጋሽ ፣
፪ኛ ያቶ ጎሣ ልጆች ፣ አለቃዋ ወይዘሮ ድባቤ ፣
፫ኛ የቀኛዝማች ወልደ ጻድቅ ልጆች ። አለቃው ቀኛዝ
ማች ደገፌ ፣
፬ኛ ቀኛዝማች ገዳ ዳርጌ ፣
፭ኛ ወይዘሮ ሙሉነሽ ፣
፮ኛ የወይዘሮ አልታየ ወርቅ ልጆች ፣
፯ኛ የይቶት ቦካ ልጆች ፣ አለቃው ባላምባራስ ገብረ ሚካኤል
፰ኛ ያቶ ጎሴ ልጆች ።
፱ኛ ። የባላምባራስ ጠራ ልጆች ።

፣ኛ ለሲሶ ልጆች ። አለቃው በሻ ወልደ ሚካኤል ነው ይባላል ። ወይዘሮ አልታየ ወርቅ በእጅዋ ያለውን ገንዘብ ትጨምርና ከወራሾቹ ጋራ ትከፈል ። ቤቱና ርስቱ እስከ እድሜ ልኳ በርስዋ እጅ ይሁንና በኋላ ለወራሾቹ ትልቀቅላቸው ። የምድር ፍሬና የጉልት ግብር ቢገኝ ወይዘሮ አልታዬ ወርቅ አንድ እጅ ወራሾቹ ሁለት እጅ እያደረጉ እየተካፈሉ ይብሉ ።

ከመንገድ በታች ያለውን በታዬን ከነቤቱ በውስጡ ያለውን ንብረት ምንጣፉን አትክልቱንም ጨምሮ ለጃንሆይ ተዝካር እርዳታ ሰጥቻለሁ ።

ወራሾቹ ከዚህ ቀደም የሰጧቸውን ዛሬም ሽክፍያ የወሰዱት ርስቱን ግብር አቅቷቸው ወይም ከሰረው እንሸጣለን እናወርሳለን የሚሉ የሆነ እንደ ሆነ ላለቃው ይልቀቅለት እንጂ ለውጪ አሳልፎ አይስጥ ቢከስርም ዋጋውን አለቃው ያግባለት ። ወራሾቹ ሁሉ ተዝካሬን በወይዘሮ አልታየ ወርቅ እጅ አውጡልኝ እርስዋንም ስለ እኔና ስለ አፀደ ወይን ሆናችሁ ጠብቁት ። ከፈቀደ ወጥታችሁ ክፉ ነገር ያሰባችሁበት እንደሆነ እግዚአብሔር ይፍረድባችሁ ፤ ከሰገሌና ከመቅደላ በፊት ለነበረው ሎሌየ ሁሉ የያዘውን መሣሪያና ክብት መርቄለታለሁ ጠመንጃውንም በቤት ካለው በቀር እንደያዘ ሆኖ ለመንግሥት ይርዳበት ።

በባርነት ስም ተማርኮም የመጣ ወይም የገባ ከዘመድቤትም የመጣ ቢሆን ሁሉም አርነት ለቀቄአለሁና በወደደበት ስፍራ ይኑር ። ተዘንግቶ ያልተከፈለ መሬት ቢገኝ ተስፋዬ እየፈለገ ይያዝና ከእኅቶቹ ጋራ ይካፈል የሚል የኑዛዜው ቃል ተነበበ ።

የርስቱ ቁጥርና ያከፋፈሉ ነገር ሁሉ በዋናው በኑዛዜው ቃል በዝርዝር ተጽፍዋልና አሁን እንደገና ለመጻፍ አያስፈልገንም

ስለ ክቡር ሙሴ ሊዮን ዕረፍት ፤



ሙሴ ሊዎን ያዝጅያን በጥር ፲፯ ቀን ሙተው በ፲፰ ቀን ጥር ተቀበሩ ፤ ብርሃንና ሰላም ለሚስታቸውና ለልጆቻቸው እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

ስለ ክቡር ልጅ አድነው ወልዴ ነ፣፦ት

ልጅ አድነው በጥር ፲፰ ቀን ሙተው በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ ፤ ብርሃንና ሰላም ለዘመዶቻቸው ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናቸው ይላል ፤

አ"ር ወሬ ።

የካንቶን ጄኔራል የንጉቻን ከሞስኮ ፷፱ ቶኔላት በጀርመን ፋብሪካ የተሠራ የጦር መሣሪ ተቀብሏል ። የሻንጋይ ወሬ የነገሩ አኳሆን የሚያሳስብ ነው ይላል ። መቶ የኤውሮጳውያን ዜጎች ተይዘዋል ።

ሎንድራ ፤ ከቺና የሚመጣ ወሬ ነገሩ እየባሰ እንደሚሔድ ይነግራል ። የእስያ ሕዝብ በኤውሮጳውያን ይልቁንም በእንግሊዝ ላይ እንዳይነሡ ያስፈራል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ፰ መሐለቅ ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፰ብር ፰ መሐለቅ ።
ዝባድ	፩ ወቄት	፭ ብር ፤
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፲፰ ብር ።
የበሬ ቆዳ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር ፰ መሐለቅ ።
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፬ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፱ ብር
አቡጀዲ መነጸር ፩ ኮረጃ		፻፴፯ ብር ።
፡፡ ባለሰይጣን ስእል ፡፡		፻፵፰ ብር ።
፡፡ ባለፈረስ ፡፡		፻፴፫ ብር ።
፡፡ ባለድመት ፡፡		፻፴፯ ብር ፤
፡፡ ባለአህያ ፡፡		፻፷፬ ብር ።
፡፡ ባለሳቢ ግመል ፡፡		፻፴ ብር ።
፡፡ ባለአንበሳ ፡፡		፻፴፯ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፬ ብርና ፴፭ ።
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር ።

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፩ ፍራንክ ከ ፺፭ ሣንቲም ነው ።
በአንድ ብር	፲፩ ሊሬ ።
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ከ፭ ሳንቲም ነው
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር ተኩል ይሆናል ፣

ማስታወሻ ።

ክቡራን ወይዛዝርና መኳንንት ሆይ ።

በ፲፱፻፲፰ ዓመት በሚያዝያ ፳፱ቀን ለልዑል ተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ርዳታ ይሆናል ብዬ ቴአትር አድርጌ ባዚያው ውስጥ ብዙ ሰዎች እንረዳለን ብለው አስጽፈው ነበር ነገር ግን እስከሁን ምንም አልደረሰንምና ይህንኑ ገንዘብ ለተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት አለቃ ለክቡር ሃኪም ወርቅነህ እንድትሰጡ እለምናችኋለሁ ይህ ባይሆን ግን የሐገር ፍቅር በናንተ ጐደለ እንጂ በኔ እንዳልሆነ አስታውቃለሁ ።

መስፍን ቀለመ ወርቅ ፡

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና ኀሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምለዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ እመለክታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ስሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉሙሩክ ከየታጂሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ሥፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን ሞቶመቢል የሬታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሄስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

Berliet



ቤርሊዩ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሰማሊ ቤርሊዩ አቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ።

ARMENAK ZAMANIAN

AGENT GÉNÉRAL

Pour l'Abyssinie et Djibouti

ማስታወቂያ

በጥሩ የፈረንሳዊ አገር ጨርቅ ለኢትዮጵያ መኳንንቶች የሚገባ በጥንቃቄ የተሰሩ ካባ ከሙሴ ፕሪዮ ዘንድ ይገኛል ቤታቸውም በእንግሊዝ ባንክ ቤት አጠገብ ነውና ለሚገዙ ሰዎች ሁሉ በማክበር እናስታውቃለን።

ኤን ቤ ኤዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶክለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶክለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተከሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ስንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርክሽ ነው።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቍጥር ፭
5 me ANNÉE № 5

ሐሙስ ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 3 FEVRIER 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen , Héritier du trône d' Ethiopie , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christos Taklé Haymanot
Diréctenr

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ደክፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ደሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የኢትዮጵያ ተስፋ ።

አባቶቼ እንደሚተርኩልኝ ኢትዮጵያ ጨለማ የመሞት እልጋ መሆኑን አውቃ ብርሃንን መውደድ የጀመረች በግርማዊ ንጉሠ ነገሥታት ዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ነው ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም ያባታቸውን አደራ ፈጻሚዎች ስለሆኑ ብርሃኑ እንዲደምቅ በብርታት እየሠሩ አስፍተውታል ። ስለሆነም የኢትዮጵያ ሕዝብ መብራት ሲበራ ሳለ ክንቅልፉ የተነሳ ሙጫ ልጅ ይመስላል ። ሙጫ ልጅ ከመኝታው ሲነሳ መብራት ያየ እንደሆን ዓይኑ አንጸባርቆበት ያመውና እንደገና እያጕረመረመ ይተኛል ይበሳጫልም ። ይህም በሙጫ ልጅ ይበረታል ማለቴ ነው እንጂ ትልቅ ሰውም ቢሆን ክንቅልፉ ተበራብሮ መብራት ያየ እንደሆን ዓይኑን እንደሚወጋው ጥርጥር የለበትም ። ነገር ግን ሙጫ ልጅ ይሁን ወይም ትልቁ ሰው ልብሱን ገለጥ አድርጎ መብራቱን አይቶ እንደገና ፊቱን እየሸፈነ ደጋግሞ ትንሽ በትንሽ ቢያለማምደው መብራቱ ይስማማውና ትልቁ ሰው ሥራውን ትንሹ ሙጫም ጨወታውን በደስታ ይጀምራሉ ። ስለዚህ ከብዙ ዘመን ጀምሮ ድቅድቅ የሆነ ጨለማ የድንቁርና እንቅልፍ ተጭኖበት የነበረው የኢትዮጵያ ሕዝብንም አሁን ተማርና ብርሃኑን ተመልከት ቢሉት ዓይኑን እያንጸባረቀው በመበሳጨት እርስ በርሱ እየተጋጨ የኢትዮጵያን ጥቅም ለመስራት ሌት ተቀን ለሚደክሙ ንጉሦች ማስቸገሩ የታወቀ ነገር ነው ። ስለ ሆነም ከጨለማ የነበረው ዓይን በድንገት ብርሃን ቢያይ ዓይኑ እንዳይታመም በማለት ቀደም ሲል ዳግማዊ ምኒልክ ሲከተልም ልዑል አልጋ ወራሽ ለዚሁ ነገር ፀያሕያን ፍኖት አእምሮና ብርሃንና ሰላም የተባሉ ብርቱ ጀግኖች ምሉ ሥልጣን ሰጥተው የኢትዮጵያን አኳሆን እዘጋጁ ብለው ስለ ላኳቸው ይኸው ክረብታውን ሜዳ ሲያደርጉት ጠላቃውንም ሲያደላድሉት እያየን ብዙ ደስታ እንመገብለን ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከስልጣኔ ሥራ ከተለያየ ብዙ ዘመን ስላለፈ አሁን እንኳንና ለሞላው ኢትዮጵያ ላሰልጥን ብሎ የሚያስብ ንጉሥ በተለየ ቤቱንና ጐረቤቶቹን ላሰልጥን ብሎ ለሚያስብ ተራ ሰው በጣም ያደክመዋልና ተስፋም ያስቈርጠዋል ። ስለሆነም ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር እንደተባለ እግዚአብሔር የኢትዮጵያን ጸሎት ሰምቶ ካለም መንግሥታት ጋር እንዲያስተካክላት መርጦ የሰጣት አልጋ ወራሽ ብርታቱና ግርማው እንደበቱም ተፈሪ ነውና ሁሉን በመታገሥ ደርሶበታል ይደርስበትማል ። ካዲስ አበባ የመጡ ሰዎች ባዲስ አበባ ልዩ ልዩ ትምርት ቤት ቁሞ ለኢትዮጵያ ልጆች መከፈቱን ቢያጫውቱን ልባችን በደስታ ሞላና አሁን እኔ ብሄድ ተማሪ ቤት ልገባ እችላለሁን? ብዬ ብጠይቃቸው ካባትና እናታቸው የሚመገቡ አላንዳች ከሳራ ይማራሉ ምግባችን ምኝታችንም ከተማሪ ቤቱ ይሁንልን ያሉ ልጆች ግን በያመቱ ፺ ብር ይከፍላሉ ። ስለዚህ አንተ በያመቱ ፺ ብር መክፈል የቻልህ እንደሆን ተልዑል አልጋ ወራሽ ተማሪ ቤት መግባት ትችላለህ አሉኝ።እኔም እየ ፺ ብር በያመቱ መክፈል አልችም ቤተሰቦቼ አዲስ አበባ ሁነውልኝ ቢሆን እንኳ ምግቤን ከወላጆቼ እየተመገብኩኝ ለቀለምና ወረቀት ብለው አባቴና እናቴ የሚሰጡኝን ትንሽ ገንዘብ እየከፈልኩኝ እማር ነበር።ግን ይህ ሁሉ አልሆነልኝም ። ወይም አድዋ ላይ ትምርት ቤት የለ እንግዲህ ምን ልሁን? ከሁለቱ ያጣ ጎመን ሁኜ መቅረቴ ነዋ ብዬ በብዙ ሐዘን መልስ ሰጠኋቸው ። ሰዎቹም በዚህስ ተስፋ አትቍረጥ ልዑል አልጋ ወራሽ እንዳንተ ትምርትን እየናፈቁ ማግኘቱ ለሚቸግራቸው በትምርት በሰል ያሉ ልጆችን ወደ ኤውሮጳ እየላኩ ገና በትምርት ያልሰለጠኑትንም ያላንዳች ከሳራ እተማሪ ቤታቸው አግብተው በገዛ ከሳራቸው እየመገቡና እያለበሱ ያስ

ተምሯቸዋል ብለው አሉኝ ። እኔም በመልሳቸው ልቤ በደስታ ሞላና እድሜና ጤና ብርታትም ለልዑል አልጋ ወራሽ ይሁን እንጂ ሳልማር አልቀርም አሁንም አዲስ አበባ እንዳልሄድ እንኳ ገና ልጅ ነኝና ምንገዱ ያስቸግረኛል ብየ ነገሬን ጨረስሁ ክቡር አንባቢ ሆይ አሳቡ ስላልተተከከለ አማርኛው ስላልታረመ አጻጻፉንም እንደምትነቅፈው ልቤ ያውቃል ነገር ግን ትንሽ በተማርኩትና አባቶቼ በሚናገሩት የኢትዮጵያ ጉዳትና የሕዝባችን ስንፍና ስለታወቀኝ በድፍረት ይህን ጻፍኩኝ ስለ ሆነም ገና ያ፲፪ አመት ልጅ ነኝና መንግሥቱ ቢረዳኝ ለትምርት ጊዜ አለኝ ስል አመለከታሁ ትንሹ ልጃችሁ ።

ደስታሁን አበራ ዘዓድዋ ።

የ፳፰ ገጽ ተከታይ ።

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

ዛሬ እህል የተወደደበት ሁለት ምክንያት አለው

መጀመሪያ የባላገሩ ቤተ ሰብ እየበዛ ሄደ ።

ሁለተኛ ገበሬዎቹ ደኅና የእርሻ መሣሪያና የሚበቃ እውቀት የሌላቸው ስለ ሆነ መሬታቸው እያረጀ የሚሰጣቸው ፍሬ የዱሮውን አያህልምና ከምግባቸው ተርፎ ሊሸጥ ወደ ገበያ የሚሄድ እህል ጥቂት ነውና ለሸማቾቹ ስላልበቃቸው የህል ዋጋ እየተወደደ ሄደ ። እንግዴህ ባላገሩ ዱሮ ከምግቡ የሚተርፈው ሁለት ዳውላ ስለ ነበረ በሁለቱ ዳውላ ያገኘው ትርፍ ፰ ብር ሲሆን በኋላ ደግሞ ከምግቡ የሚተርፈው ፬ ቁና ስለ ሆነ ባራቱ ቁና አንድ ብር ቢያገኝበት ከዱሮ ይልቅ ያገኘው ትርፍ ምን ይሆን ። እውነት ነው እንደ ዱሮ ከምግቡ ሁለት ዳውላ ቀርቶት ቢሆን ሁለቱ ዳውላ አምስት ብር ቢያወጡለት ኑሮ ከዱሮው ይልቅ አራት ብር ትርፍ አገኘ ለመበል ይቻል ነበረ ። ዛሬ ከምግቡ የሚቀረው አራት ቁና ብቻ ስለሆነ ግን የሚያገኘው ትርፍ እንደ ዱሮው አንድ ብር ብቻ ነው ስለዚህም ዛሬ እህሉ በገበያ ስለ ተወደደ ባላገር አንድም ትርፍ አያገኝበትምና የተበደረውን ብድር ለመክፈል ጉልበት አያገኝም ።

ተከራካሪው አንባቢ ግን ደግሞም እንደዚህ ይል ይሆናል ። ዛሬ ብር የሚገኘው ከባላገር ቤት ነው ። ትርፍ ካላገኘ በምን ምክንያት ብር አገኘ ። አንዳንድ ሰዎች መሬታቸው ሰፊ ሁኖ ቤተ ሰዎቹ ጥቂቶች ስለሆኑ ብዙ ብር ቢያገኙ ባሁኑ ሂሳባችን አይገባም ። እኛ አሁን የምንመራመረው የያንዳንዱን ሰው ጥቅም አይደለም የመላውን ሕዝብ ጥቅም ነው እንጂ ። ሀያ ቀላድ ያለው ሰው ከሀያው ቀላዱ ፭፻ ብር ባመት ቢያገኝ ከምስቱ መቶ ደግሞ ሶስቱን መቶ ብር ላመት ምግቡ አስቀርቶ ፤ ሁለቱን መቶ ብር ወደባንክ ቢያገባ ትርፍ አግኝቷል ብለን ፫፻ህ ባሁኑ ሂሳባችን አናገባውም ። እኛ የምናገባው ሂሳብ ከያንዳንዱ ቀላድ ባመት ፳፭ ብር ማግኘቱን ነው ።

እነሆም የሚበዛውም ባላገር አንድ ሙሉ ቀላድ ወይም እኩሌታ ቀላድ ብቻ ነው እንጂ ብዙ ቀላድ የለውም ። በዛሬውም መሣሪያው አንድ ቀላድ አርሶ ከምግቡና ከልብሱ የሚቀረው ትርፍ ጥቂት ነው ። ማለት ፤ ቀላዱን ብቻውን ሁኖ ቢያርሰው ጨርሶ በመላው ሊያርሰው አይችልም ። ሌላ ገበሬም ቢጨምር ገበሬውም ምግብና ልብስ ይፈልጋልና ስለዚህም ባለመሬቱ የሚያገኘው ትርፍ ጥቂት ነው ።

አንባቢው ግን ይህንን ነገር አሁንም ቢሆን በጣም ያልተረዳው እንደሆነ እንዲህ ይላል ። ከንዱ ቀላድ ከዱሮው ይልቅ እህል አለማግኘቱ ባላገሩ ደህና መሣሪያ በማጣቱ ነውና ባንክ የሚያበድረው ባላገሩ የተሻለ መሳሪያ ገዝቶ ብዙ እህል ከመሬቱ አግብቶ የሚበቃቸውን ያህል በኢትዮጵያ ለሚኖሩ ሸማቾች ሸምቶ ከነዚህም ሸማቾች የተረፈውን ወደውጭ አገር በባቡር ሰዶ እንዲሸምተው ነው ። ይህ ቃል ግን ሲናገሩት ያምራል ነገር ግን አጥብቀን ከመረመርነው ዘንድ መሠረት አልባ ሁኖ እናገኘዋለን ። ከሁሉ ነገር በፊት አንድ የማይጠረጠር ቃል እናጥና ። ቃሉም ይህ ነው ። በየሥራው ባልሠለጠነ ሕዝብ ውስጥ አራሹ ለብቻው ተለይቶ ሊሰለጥን አይችልም ነገር ግን ደግሞ ቢሽው እስቲ የሚችል ይሁን ። ግን አራሹ ለብቻው ተለይቶ በሥራው ቢሠለጥንም አንዳች ጥቅም አያገኝበትም ። ምክንያቱ ምን ይሆን ዛሬ እህሉ የተወደደው ስለታጣ ነው ። የገበሬው ቍጥር እየበዛ ሄዶ አይደለም ስለዚህም አርሶ ከገባው እህል ከምግቡ የሚተርፈው ጥቂት ነው ። አሁን ግን ድንገት ደኅና የእርሻ መሣሪያ ወጥቶ ባላገሩም በአዲሱ መሣሪያ ቢያርስ ከያንዳንዱ ቀላድ ብዙ እህል ሊያገኝ ይችላል ። ባላገሩም ከምግቡ የሚተርፈው ብዙ ይሆናል ። የተረፈውንም በኢትዮጵያ ውስጥ ሸማቾች የማይጨርሱት ይሆናል ። ከዚያም በኋላ ለገበሬው ቀጥለው ከተጻፉት ሁለት መንገዶች አንዳቸውን መምረጥ የግድ ይሆንበታል ።

አንደኛው ከምግቡና ከሸማቾቹ ምግብ የሚተርፈው እህል ከንቱ እንዳይነቅዝበት ፈርቶ እህሉን ሁሉ ወደገበያ ሊያወጣው ነውና እህሉ ይረክሳል ። ማለት ዱሮ በአራት ቁና ፩ድ ብር ሲያገኝ ኑሮ እንደሆን ያገባውም እህል ከዱሮው ሶስት እጅ በልጦ እንደሆን ፩ድ ብር የሚያገኘው ፲፪ት ቁና ሰጥቶ ነው ።

ሁለተኛው ከምግቡና ከሸማቾቹ ምግብ የሚተርፈውን እህል ወደውጭ አገር የሰደደ እንደሆነ ግን እህሉ የሚሄድበት ገበያ እሩቅ ነውና ይዘውት የሚሄዱት ተላላኪዮች ነጋዴዎች ሊያተርፉበት ከፈለጉ እህሉን የሚሸምቱት በጥቂት ዋጋ ይሆናል ማናቸውም ዕቃውን ወደውጭ አገር የሚሰድ ሰው የመልክተኛውንና የጫኙን ደመወዝ መክፈሉ የታወቀ ነገር ነው ።

ስለዚህም የኢትዮጵያ ባላገር እህሉን ወደኤሮፓ አገር ቢሰድ ከድካሙ ክፍሎ ያውም የሚበልጠውን ክፍል ለተላላኪዎችና ለነጋዴዎች መስጠት የግድ አለበት ። የድካሙን ሙሉ ዋጋ ካላገኘ ዕዳውን ለመክፈል አይቻለውም ። ስለዜ ህም ባላገሩ በተበደረው ገንዘብ የተሻለመሣሪያ ቢገዛ ትርፉ ለሱ አይደለም ለውጭ አገር ነው እንጂ ። የእዳውም መክፈያ ቀን ሲደርስ መሬቱን ለመሸጥ ይሰናዳል ፡ ወይም መሬቱን አሳልፎ ለባለዕዳው ይሰጣል ፡ ከዚህም ምክንያት የተነሣ ለመንግሥት ትልቅ ጉዳት ይሆንበታል ያልነው ነገር ይደርሣል ። ማለት ባገሩ ውስጥ ያለው የእርሻ መሬት በጥቂቶች ሰዎች እጅ ይጠቀለላል ።

ነገር ግን ለዚህም ቃል ቢሆን መከራከሪያ ምላሽ አይታጣበትም ይበልም ይሆናል ። ስለምንድነው እንግዲያው በየኒ

ገሥታቱ አገር ብንሄድ ከመሬታቸው ያገቡትን እህል ወደ ውጭ አገር ሰደው እያቀኑ ትልልቅ ሀብት የሰበሰቡ ይኸው ብዙ የከበሩ ሰዎች በአሜሪካ በመስኮብ በሩማንያ ብዙ አይደሉምን ፡፡ ደግሞም ወደውጭ አገር እየሰደዱ የበለጠጉበት ከነሱ አገር የተገኘው እህል ብቻ አይደለም ። የሕዝብን አስተዳደር የማያውቁ ሰዎች ካልሆኑ በቀር እናውቃለን የሚሉ ሰዎች በዚህ ነገር አይረቱም ፡፡ የማይረቱበትንም ምክንያት ቀጥሎ የተጻፈው ምሳሌ ያሳየናል ፡፡

እነሆ አንድ ሰው ፩፻ ጋሻ መሬት ቢኖረው ከያንዳንዱ ጋሻ መሬቱም ፪፻ ዳውላ እህል ቢያገኝ እንግዴህ ከምስቱ መቶ ጋሻ መሬት ላይ የሚያገኘው እህል በድምር መቶ ሺህ ዳውላ እህል መሆኑ ነው ፡፡ አንዳንዱም ዳውላ እህል ፩ ብር ቢያወጣለት የመቶው ሺ ዳውላ እህል ዋጋ ፻ ሺ ብር መሆኑ ነው ። ከዚህም እዙሌታውን ለገበሬዎቹ ልብስና ቀለብ ቢያወጣለት ለሱ ፺ ሺ ብር ይተርፈዋል ፡፡ ፺ ሺ ብር ላንዱ ሰው በያመቱ ሲገባለት የሚከፍለው የሰው ዕዳ ከሌለበት ሀብታም ነው ለመባል ይቻላል ፡፡ ነገር ግን ከየአንድ አንዱ ጋሻ መሬት ባመት የሚገባለት ትርፍ ስንት እንደ ሆነ እንመርምር ። ብናስበው እነሆ ፻ ብር ብቻ ሆነ እንግዲህ የያንዳንዱ ጋሻ መሬት የተገዛበት ዋጋ ሺ ብር ይሆናል ሺ ብር ባመት ያገባው ወለድ መቶ ብር ብቻ መሆኑ ነው ዛሬ ግን በኢትዮጵያ ያለው ባንክ ሲያበድር የሚፈልገው ወለድ ቢያንስ ቢያንስ በመቶው ፲፪ ብር ነውና እነሆ የሺው ብር ወለድ ባመት ፻፳ ብር ሆነ ። ስለ ዚህ ባለ አምስቱ መቶ ጋሻ መሬት ርስቱን ሁሉ የገዛው በአምስት መቶ ሽህ ብር ሊሆን ነው ። መሬቱንም ሁሉ የገዛው ተበድሮ እንደ ሆነ እነሆ ወለዱ ከመቶው በ፲፪ ሂሳብ ፷ ሽህ ብር ሆነ ፡፡ የሚያገኘው ያመት ትርፉ ግን ፺ ሽህ ብር ብቻ ስለ ሆነ ሌላስ ይቅርና ወለዱንም ብቻ ለመክፈል አይችልም ፡፡ ስለ ዜህም ምክንያት እንኳን ዋናውን ሊከፍልና ለወለዱም ዕዳ ብቻ ሲል ከመሬቱ ክፍሎ በየዓመቱ መሸጥ አይቀርለትም ፡፡ ለዜሁም ነገር ደግሞ አንድ መከራከሪያ ምላሽ አለው ፡፡ ባላገር የሚበደር መሬትን ለመግዛት አይደለም ። መሬቱን አሣምሮ የበለጠ ትርፍ እንዲያገኝ ነው እንጂ ይህም ቢሆን ያው ነው ፡፡ ባላገሮች እርሻቸውን አሣምረው የሚያበቅለውን እህል ባበዙ ቍጥር በመላው እህል ተሸጦ የሚበላበት ገበያው ከቅርብ ካልሆነ በቀር ትርፋቸው እያነሠ ይሄዳል ፡፡ ማለት ለያንዳንዱ ቀላድ መሬት የሽህ የሽህ ብር መሣሪያ ገዝተው አምጥተው ብዙ እህል ቢያገቡ ያ ያገቡት እህል ሲቀና የሚቀናበት ገበያ እሩቅ ሲሆን ከዱሮው ሽህ ብር ያነሠ ዋጋ ያመጣል ። እንደዜህ ያለውም ገበያው ሩቅ የሆነበት ባላገር ምናልባት ትርፍ የሚያገኘው እህሉን በሚሰድበት አገር ከሰማይ መዓት ወርዶ መከሩ ተበላሽቶ ፣ ወይም በሌላ ምክንያት ረሀብ የገባ እንደ ሆነ ነው ። ስለ ዜህም በውጭ አገር መከሩ በጠፋ ቁጥር ትርፍ ሲያገኝ የውጭ አገርም መከር በማረ ቁጥር ደግሞ ሲከሥር ይኖራል ። ማለት የዕድል ሎሌ ሆኖ ይኖራል እንጂ በጭራሽ የተደላደለ ትዳር የለውም ፡፡ በሜሪክና በመስኮብ በሩማንያም የሚታየው ነገር ይኸው ነው ። በእነዚያ አገሮች እንደ አንዳቸው ሰዎች ከባቶቻቸው የወረሱትን ወይም ሰው ሳይገባበት ራሳቸው ያቀኑትን ብዙ መሬት ይዘው ከየመሬታቸው ተጠራቅሞ ባመት የሚገባላቸው ትርፍ ብዙ ነው ። በንደዜህም ያለውም ሕዝቡ ከመሬቱ ያገኘውን ፍሬ ወደውጭ አገር መነደድ የግድ የሆነነ አገር ውስጥ የመሬት ዋጋ ጥቂት ነው በየከተማው ዙሪያ ያለው መሬት መወደዱ ለጊዜው ነው ። የተወደደበትም ምክንያት ሁለት ነው ። አንደኛው ከጅቡቲ ወደ አዲስ አበባ የምድር ባቡር ስለ ተዘረጋ ባለመሬት የሆኑ ሰዎች ለወደፊት ብዙ ትርፍ የሚያገኙ ይመስላቸዋልና አይሸጡም ።

ከዚህ የቀረው በሚከተለው ይታተማል።

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት መጽሐፍ ነው ፤

ክቡር አቶ ገብረየስ ሆይ ።

እረ አንድ ጥያቄ ልጠይቅዎ እፈቅዳለሁ ። እስክንድርያ ሰማይ ነው ወይስ ምድር ይመስልዎታል ። ይህ ቃል ጠያቂውን ሞኝ ያስመስለው ይሆናል ። ግን ለርስዎ ይህንን ቃል መጠየቅ ይገባዎታልና የዚህን መልስ ለሚጠባበቁ የብርሃንና ሰላም ወዳጆች በቶሎ እንዲያስታውቋቸው አመለክትዎታለሁ ፡፡ የዚህን መልስ አውቀው ከመለሱ በኋላም ሌላ የምጽፍልዎ ነገር አለኝ ፤

ከቶ አቶ ገብረየስ ይህንን ቃል ሲጽፍ በፈቃዱ ተመርቶ ይሆን ? ፡፡

ዖ ሰ ፡፡

፪ኛ መልስ ።

የሶስተኛው ዓመት አራተኛው ቁጥር ብርሃንና ሰላም በመጣልኝ ጊዜ መቸም ወረቀት ሲመጣ አስቀድሞ ፊርማውን ማየት ልማድ ነውና ገብረየስ ወልደ መስቀል ዘመካነ ሥላሴ ዘልኅቀ በውስቴታ ሲል ጊዜ የሊቀ ጠበብት ገብረየስ መስሎኝ ከተማረ ሰው ደግ ነገር አይጠፋም ብዬ ማንበብ ጀመርሁ ያዋቂ አጀማመር መሰለና ዝቅ ሲል የልጆች ጨዋታ ሁኖ ቀረ የስም ሞክሼ መሆኑን አወቅሁት ።

መጀመሪያ መንግሥት ከሚገዛው አገር መምህር ቢአገኝ ወይም ባያገኝ ካማይገዛው አገር በገንዘቡ ፈልጎ አምጥቶ የወር ቀለብ ሰጥቶ በቀለቡ ላይ ርስት ሰጥቶ ያገሩ ልጆች እንዲማሩለት ያኖረው የለምን ? ይላል ። ይኸው እውነቱን መክቸ ያልሁት ለዚህ ጊዜ ነው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በመንፈሳዊ ትምርት ታገሬ መምሕር አጥታ ሌላ ሰው ፈልጋ አታውቅም። የሚመጡትም ጳጳሳት እንኳን ዜማውን ቅኔውን መጽሀፉን ቋንቋውን እንኳ ጥቂት ጥቂት የሚአውቁት በብዙ ከተማሩ በኋላ ነው ባገሩ መምህር ታገኘ ባዕድ ሰው እንዴት ያስፈልገዋል ። ባገሩ ውስጥ መምህር ባያገኝ ማለትም የተገለጠ ውሸት ነው።

፪ኛ ያ መንግሥት ከማይገዛው አገር በገንዘብ ፈልጎ ያመጣው መምሕር የዘመኑ ልጅ ወረተኛ ነውና ያገሩን ትምርት ጠልቶ ሌላ ትምርት ወዶ ሳይሟላለት ቢሞት ቀድሞ በተዋዋለው ኮንትራት ያወጣ የለምን ? ይላል ።

የቤተ ክርስቲያንና የቤተ መንግሥት ሥራ ለየብቻው ነው በቤተ ክርስቲያናችን ኮንትራት የለም መንግሥትም አንዱ ሳይሟላለት ሳያስተምር ቢሞት ሁለተኛ የሚይሟላለት ባልጀራውን አያመጣም ምሳሌውም አልሆነም የቋንቋ ትምርትም ቢፈልግ የዛሬ ዘመን ልጅ ወረተኛ አይባልም የቋንቋ ትምርት ያገርን

ጥቅም እንጂ ያገርን ጉዳት አያናግርምና ብዕሬን የሚአነቅፍ አድፍ ይኖር ይሆናል ብየ የፈራሁት ለኔ ብዕር ብቻ ነበር እንጂ ቋንቋ ለሚማሩና ለሚጽፉ ሁሉ እድፍ ያገኛቸዋል አልመሰለኝም ነበር ሥላሴ ያመጡት ነውና ምን ይደረጋል ? ደግሞ እኛ አጽፍ የለበሱ መነኵሴ ሲል ሩቅና ቅርብ የለየ አይመስልምና በከተማ ማደጉን እንጃ እኛ ታለ የለበስን የለበሱ ታለ እኒያ(እነዚያ)ያሰኛል ወረተኛ ሳይሆን የውጭ ትምርት ሳይፈልግ እድሜውን ሙሉ የኖረ ሊቅ እንዲህ አይናገርም ፡፡

፫ኛ የናታችን የእስክንድርያ ሥራዋ መጥፎ ቢሆን ቀድሞ አጼ ዮሐንስ ባመጡት አምኃ (ጉቦ) ሰጥተን እስክንድርያን እናታችን ጳጳሱን አባታችን ብለን እንኖራለን እንጂ በጥቁር ጳጳስ አንባረክም ይላል ፡፡ የሥራዋን መጥፎነት ሲአውቅ ያችን እናቴ ብሎ መጥፎነት ያለየባትን እናቱን እንደምን ነቀፋት ? ተምን ዘር መሆኑን ባያውቅ ይሆን ? ወይስ ከዘመድ ባዕድን ከወዳጅ ጠላትን ከውነት ኃሰትን ወዶ ይሆን ? በጥቁር አንባረክም ማለቱ እውነቱ ነው ፡፡ እንዲህ ያለውን ልጅ አባቱ አይባርከውም ምሳሌ ፳ ፳ ፡፡

ከቶ በልጅነቱ እንኳ በፍልሰታ በጥቁር ካህን ተባርኮ ቆርቦ አያውቅ ይሆን?ወይስ ሥጋውንና ደሙን የሚባርክ ካህን ሰው ለመባረክ አይሆንም?ጥቁረት እንደሆነ የእግዚአብሔር ሥራ ነው በድፍ ወይም በስንፍና አላመጣነውም ፡፡ ጥቁሮችም ብን ሆን ውስጣችን ነጭ ነው ሰሎሞንም ጸላም አነ ወሠናይት እማ ዋልደ ኢየሩሳሌም ፡፡ እኔ ጥቁር ነኝ ውብ ነኝ ብሎ ከነጮች አብልጦ መስክሮልናል ፡፡

ከዚህም ቀደም ከሣ ገብሬ ያገሬ ሰዎች ባዙቅነት ትወዳላችሁ ብሎ አገሩን በሙሉ ሰደበ ፡፡ ከቶ አገራቸውን ካልሰደቡ ብልሆች ወይም ክርስቲያኖች አይሏቸው ይሆን?ባረከ በግዕዝ ባማርኛ አመሰገነ መረቀ ማለት ነው ፡፡ ማናቸውን ነው ክባቱ እንዳያገኝ የጠላው ይሆን?አሁንስ በጥቁር አልገዛም ሳይል አይቀርም ፡፡

አንድ ሰው በመንዝ ብዙ እህል ያለው ነበረ አሉ ፡፡ ጐረቤቶቹ አበድረን ሸምተንም ቢሉት እምቢ አላቸው አሉ ፡፡ እንዴት እናድርግ ሲሉ ታናሽ ወንድሙ እኔን መቸም አይጠረጥረኝምና ፡፡ አዳሬን ሂጄ ሌሊት ሽንቱን እምሸና መስዬ መዝጊያውን እከፍትላችኋለሁ አላቸው ፡፡ በተቃጠሩበት ሌሊት መዝጊያውን ከፍቶ ወንድሙን አሳስሮ አዘረፈው አሉ ፡፡

የወንድሙን ክብር የጠላ እንዲህ ያደርጋል ፡፡ ሞኝ ቢመክር በራሱ ባለጌ ቢተፋ በልብሱ እንዲሉ ፡፡ ቢአውቅስ ምንም ባይጠቀም የገሌ ወንድም መባል ትልቅ ስም ነበር ያገሩን ጥቅም የባዕድን መርገም ያወቀው ብልሁ ልጅ ማህሉ ጽጌማ ለባለአጥሩ መልሶላቸዋል ፡፡ በቃሉም መጣፊጥ ሁሉ ተደንቀን በታል ፡፡

ይህ ግን በተሰናዳ እርሳሴ ዓይኑን ጨፍኖ መግባቱ እርሳስ በሰውነት የተበተነ እንደሆነ ፡፡ የማይድን ነቀርሳ መሆኑን ባይመለከተው ይሆናል ግን ሲደርስበት ያውቀዋል ፡፡ በባዕድ የሚገዙትን መከራ ባያይ እኮ ነው ፡፡ በነፍስ እውቀት አጥርታችሁ እንዳለን በነፍስ እውቀት ማጥራት ባንችል በረጋ እውቀት አጠራነው መረመርነው ፡፡ ፈረንጁ እንዳለው ያው ምቀኝነት ብቻ ነው ዮሐ ፲፫ ዳንኤል ም ፫ቁ ፳፺ ይመልከት ለጊዜው ይህ ይበቃል ለሚመጣውም ያው እርሳሴ ነው ፡፡ ለሰነፍ እንደ ስንፍናው መልስለት በሰውነቱ ዘንድ በአለአእምሮ እንዳይመስል ምሳሌ ቢለኝ ነው እንጂ ይህን ያህል አላዘገያችሁም ነበር ፡፡

ጊዜ በማሳለፌ ከንባቢዎች ይቅርታ አለምናለሁ ፡፡

ማኅተመ ወርቅ እሼቴ፡፡

ለጥያቄ አመላለስ መልስ

አባሆይና የሮፓው ሰው ሲነጋገሩ እንደ ጥንታችን ካላችሁስ በብሉይ እንጂ በሐዲስ አታምኑማ ቢላቸው እናምናለን እንጂ ብለው የተናገሩትን አማናዊ ቃል አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው ብሎ አቶ ገብረ የስ ወልደ መስቀል የጻፈው እንደ ጥንታችን ለማለት ነውና በሐዲስ ማመን አያስፈልገንም የማለት ቃል ያሳያል ፡፡ የቤትን ክብር አዋርዶ የጐረቤትን ክብር ለማላቅ ከመናገር ዝምታ ይሻላል ፡፡ እምተናግሮ ይኄይስ አርምሞ ብሎ አቶ ገብረ የስ የጠቀሰው ያለጥርጥር ልክ በሱው ነው እንዲሁም የሱው ጥቅስ ሕድግ ምእረሰ ያለውን ተመልክቼ ያገሩን ክብር ላበጠለለው አንድ ጊዜ ልንገረው በምሳሌ የተናገረው ቃል እንደውነቱም መንግሥታችን ከውጭ አገር የልዩ ልዩ ጥበብ ሥራ የሚአውቁ መምሕራን አምጥቶ ሊያስተምር የተገደደ ነው እንጂ በሃይማኖትማ ኢትዮጵያ በሊቃውንቶቿና በመምሕራኖቿ ራሷን የቻለች ናት ይኸውም ከብዙ መቶ ዓመታት ጀምሮ ነው ጳጳስ እየመጣ ስልጣን ከመስጠት በተቀር በመንፈሳዊ ጥበብ የኛ ሊቃውንቶች ሌላ ጥበብ የቀጸሉት ነገር እንደ ሌለ የታወቀ ነው ፡፡

አቶ ገብረየስ ሆይ እስክንድርያ ሃይማኖቷ ሃይማኖታችን ነው ያልከው ያለጥርጥር እውነት ነው አምላካቸው አምላካችን ነው ያልከው ግን ለያንዳንዱ መንግሥት ሌላ አምላክ ማድረግህ ነውና የድፍረት ቃልህን ብታርመው ይሻል ይመስለኛል በመከነ ሥላሴ ያደግኸው በጥቁር ሰው እጅ አንባረክም ብለሃልና የኢትዮጵያ ቄስ ሊባርክህና ወይም ሊናዝዝህ አይችልም ይኸውም አንተው በፈረድኸው ነው እንጂ እኛ አላልንህም ከውቀት በጣም የተሳሳትህ ስለሆንክ መላ ኢትዮጵያን ሰደብክ ይሁን እንጂ እንደወደድኸው ከኢትዮጵያችን መካከል ቀላታቸው ከግብጻውያን የሚተካከል መምሕራን አሉና እነዚህ ሊሾሙ አይችሉም ትለኛለህን መልሱን አደራ ፡፡

ማህሉ ጽጌ ፡፡

የጥያቄ መልስ ፡፡

በ፴ኛ ቍጥር ብርሃንና ሰላም ገላባውን ከፍሬው ለይተን እንድንናገር ተለምነን ነበርና እኔም በድርሻዬ የሚከተለውን አጭር ቃል እጽፋለሁ ፡፡

ክቡር ደብተራ ገብረየስ በጥቁር እጅ አንባረክም አሉ ጥቁር ፊትዎስ ከቶ ያለቀይ እጅ አይባረክምን ፡፡ እንግዲያስ እርስዎ የተጸየፉትን ጥቁረት የቶመኙት ነጭ ሊያከብረው እንደማይችል የተረገጠ ነው በሽማግሌቹም ተረት ባለቤት ያቃለለውን አሞሂ

ብለፅዳ አይቀበለውም ይባላል ። ስለዚህ እርስዎም በጥቁር አፍዎ የተናገሩት ይህ ስድብዎ አይረጋብንም ። እንደኔስ ፈቃድ ቢሆን በእስክንድርያ ሃይማኖት ጸንተው ከሚኖሩት ከሀገሬ ሊቃውንት ወገን ለዚህ ማዕርግ በቅቶ ከተገኘ እንኳን እጁን እግሩንም ለ መሳም አልጸየፈውም። ምንም ቆዳው ቢጠቁር ልቡ ቀይ መሆኑን ከሰነፍ ሰው በቀር የማያውቅ የለም ።

ክቡር ደብተራ ገብረየስ ግን ምን ጊዜም ለዚህ ማዕርግ እንደማይበቁ ተስፋ ቆርጠዋልና እኔ ካላገኘሁት ያገሬ ሊቃውንት ባይከብሩ የኢትዮጵያ ክብር ለምኔ በማለት የተበሳጩ ይመስላል ። ወይም በሚመጣው ዘመን ጥቂት ሹመት ለማግኘት የገንዘብ መጨመሪያ ይሁነኝ ብለው የጻፉት ይመስላል ። ነገር ግን ይህ ሁሉ አለማወቅ ነው ። ያገር ክብረት የሁሉ ነው እንጂ የተሹዋሚው ብቻ አይደለም ፤ ከአገራችን መነኮሳት ወገን ቢሾም ስማችንን ያስከብራል ፤ ሀብታችንም ለወንድሞቻችን ይሆናል አገራችንም በውነተኛ አጠባበቅ ይጠበቃል ይልቁንም የኢየሩሳሌም ቦታችን በተጠበቀል ነበር ጆሮ ያለው ይስማ ። ይገርማል የገዛ ራሳቸውን የሚሳደቡ ፪ ደፋሮች አየሁ ። ፩ኛው የጥቁር እጅ አይቅረበኝ ብሎ የሚንገፈገፈው ይህ ነው ፪ኛውም የኢትዮጵያ ልጆች ለባዘቅነት ታዳላላችሁ ብሎ የመሠከረው አቶ ከሣ ገብሬ ነው ፤ በውኑ ጥቁርን የሚጸየፉ እነሱ የዮሮፕ ሰዎች መሆናቸው ነውን ወይ አበላ ማለት ፤ ለዕለት ጥቅም ብሎ ደማችንን ከማዋረድ ዕውነት ተናግሮ ጦም ማደር እንደሚሻል አንባቢዎች ሳያመዛዝኑት አይቀሩም ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ።

አል አዛር ወልዴ ።

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር ።

ባራተኛው ቁጥር ባለፈው ሳምንት ጋዜጣችን ፤ ገብረ የስ ወልደ መስቀል የጻፈውን ቃል አይቼ በብዙ አዘንሁ ነገሩም ያገሬን ልጆች በመላው እንዲያሳዝናቸው አምናለሁ ።

አቶ ገብረ የስ በጻፈው ቃል ካሁን በፊት የግብጽ ዜጎች እንደ ነበርን ወደ ፊትም ዜግነታችንን አጽንተን እንድንኖር ያሳስበናል ። እኛ ግን በፊትም በኋላም በሃይማኖት ከመመሳሰል በቀር ከግብጽ ጋራ ሌላ ነገር የለንም ፤ ግብጽ ገና ፈጽማ ነጻነት አላገኘችም ፤ ነጻዪቱ ኢትዮጵያ የምንወዳት አገራችን አባቶቻችን ደማቸውን አፍስሰው አጥንታቸውን ከስክሰው ባዕድ ገዢ ሳያስገቡባት ነጻነቷን ጠብቀው ብቻዋን ራሷን ችላ እስካሁን የኖረችው አሁን ዜጋ ለመሆን ስንኳን ልታደርገው ልታስበው አትችልም ። አቶ ገብረ የስ ይህን መጻፉ ያገርን ፍቅር ባያውቃት ነው ፤ በጻፈውም ቃል ውስጥ ከድጓ ከመልክ ተክለ ሃይማኖት ካፈ ታሪክም ጥቅስ ይገኝበታል ፤ ይህን ይህን በሚመለከትበት ጊዜ መጻሕፍት ቅዱሳትንና የዓለም ታሪክም ጨምሮ ቢመለከት ወይም ቢጠየቅ ያገር ፍቅር እንዴት እንደ ሆነች ያውቅ ነበረ ። ደግሞም ግብጽ ለኢትዮጵያ የዋለችላትን ውረታ አናውቅም ፤ ቅዱስ ማርቆስ ምስርን አልፎ መጥቶ ኢትዮጵያ ገብቶ አስተማረ የሚል ታሪክ ይገኝ አይመስለኝም እዚያው ምስሮች በሠሌን እንቅው ገደሉት ይባላል እንጂ ለኛ ግን ቀደምትነታችንን ቅዱስ መጽሐፍና የዓለም ታሪክ በመላው ይመሠክርልናል ፤ የሐዋ ሥራ ም ፰ ቁ ፳፯ እስከ ፴፱ ተመልከት ።

በኋላም ክርስትናችንን ያሻሻለልን (ምንም ሹመቱ ከእስክንድርያ ቢሆን)የዮናኒ ደማስቆ ሰው ፍሬ ምናጦስ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የተባለው ነው እንጂ የግብጽ ሰው አይደለም ። አቡነ ማቴዎስም ዲቁና ቅስና ይሾሙ ነበረ አንዳንድ ጊዜም በመንግሥት ላይ ፖለቲክ ለማድረግ የተነሱትን ሰዎች በሥልጣናቸው እያወገዙ ቤተ መንግሥታችንን ይደግፉ ነበር እንጂ በመንፈሳዊ ስጦታቸው እንደሚገባ አድርገው በያውራጃው ተማሪ ቤት አቁመው አላስተማሩንም ። ያስተማሩን ያገራችን ሊቃውንቶች ብቻ ናቸው ። አባታችን አቡነ ማቴዎስ ምንም በኢትዮጵያ ላይ አንድ ዋና መታሰቢያ ባይተዉ ከገራችንም ያገኙትን ሀብት ሁሉ ባገራቸው በእስክንድርያ ላይ ቢያኖሩ አሁን በሞታቸው ልንወቅሳቸው አንችልም ። ነገር ግን ለሚመጣው ጊዜያችን አጥብቀን ልናስብና ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል እንግዲህ አቶ ገብረ የስ በጥቁር እጅ አንባረክም ብሎ በጻፈው ቃል አገሩን እንደ ካደ ፈጽመን ተረድተነዋል እስመ ይክሕዱ ከመ ይኀድሩ የተባለውም በሱ ተፈጸመ በሰማያዊ ንጉሥ ዘንድ ቀይና ጥቁር ረጅምና አጭር አለመኖሩን ባያውቅ ነው ይህን ማለቱ (ከቶ ራሱን የሚያስክድ ነገር ምን ምክንያት አግኝቶት ይሆን) እንደሱም አሳብ በየገዳማቱና በያድባራቱ በየገጠሩም ሁሉ ያሉ ቀሳውስትስ ይቅርና በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ወምበር የተቀመጠው ክቡሩም እጨጌ ቢሆን ከቡራኬ መከልከሉ ነው ።

ለሱ ይህን ሁሉ ለጆሮ የሚያስከፋ ነገር ከመጻፍ አገሩንም ንቆ ከማስናቅ እምተናግሮ ይኄይስ አርምሞ ብሎ ከጻፈው መስመር ሲደርስ ነገሩን አቋርጦ በጨረሰ ይሻለው ነበረ ። ደግሞ ከነገሩ መጨረሻ ላይ ፍሬውን ከገለባ ለይታችሁ አኑሩልኝ ብሏል ፤ እኛስ ከመጀመሯ እስከ መጨረሻው ገለባ እንጂ ፍሬ እንዳላገኘንበት ፈጽሞ ይወቅ ።

መጨረሻ ቃል ።

ዛሬ እኛ የኢትዮጵያ ልጆች ከሀገራችን ሊቃውንት ተመርጦ ጳጳስ እንዲሾምልን ብፁዕ እጨጌም በዚህ ነገር ተግተው እንዲረዱን የታመነ ሙሉ ተስፋ አለን ።

ዛሬ በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክና በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ጊዜ ይህ መልካም ምኞታችን ቢፈጸምልን ፤ መታሰቢያቸው እንደ ደህና ሐውልት በዓለም ታሪክ ላይ ተቀርጾ ዓለም እስኪ ያልፍ ይቆይላቸዋል እነሱም ይህን የተመረጠ ዕድል ለተከታዮቻቸው አሳልፈው ይሰጡታል ብለን እንጠራጠርም ። ለሁሉም ነገር የልዑል እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን (አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን)

አስታጥቄ ወልደ አማኑኤል ።

መልስ ።

በ፫ኛው ዓመት ቁጥር ፩ ፳፰ ገጽ ገብረየስ ወልደ መስቀል በጥቁር እጅ አንባረክም ብሎ መጻፉ ያገሩን ሰው አባቱንና መምሕራኑን ስለ ናቀ ነው ። እግዚአብሔር ሥልጣንን ለሚያምኑትና ትእዛዙን ለሚጠብቁ ይሰጣል እንጂ ። ለዚህ አገር

ሰው ሥልጣን ይሰጠዋል ለዚያኛውም አገር ሰው ሥልጣን አይሰጠውም ብሎ አይመርጥም ። ኢየሱስ ከናቱና ከወንድሞቹ በተሰወራቸው ጊዜ እናትህና ወንድሞችህ ይፈልጉሃል አሉት ። እነማናቸው እናቴና ወንድሞቼ ያባቴን ፈቃድ የሚፈጽሙናቸው አለ ። ማርቆ ም ፫ ቁ ፴፪ ። ሰብእሰ ገጸ ይሬኢ ። ወእግዚአብሔርሰ ልበ ይሬኢ አለ ። ሰው የሰውን መልክና የቁመቱን ማማር አይቶ ያመሰግነዋል ። የቁመቱን ማጠርና የመልኩን ጉስቁልና አይቶ ይንቀዋል ። እግዚአብሔር ግን የመልክን ማማርና የመልክን ክፋት አያይም ክፉ አሳብና ምኞት የማያበቅል ልቡና ሲያገኝ ያድርበታል እንጂ ። በመንፈሳውያን ሰዎች ሁሉ ላይ ሥልጣነ እግዚአብሔር ካደረ ቀይን ሰው መርጠህ ጥቁሩን ለምን ትንቅፋለህ ። አባቱን አያውቅ አያቱን ናፈቅ እንደሚሉ ሁሉ በጥቁር ሰው እጅ አንባረክም ምን አሰኘህ ። የእግዚአብሔር ሥልጣን ለሐዋርያት የተሰጠው ሲወርድ ሲዋረድ በዓለም ላይ ሁሉ መልቷል ። ለኢትዮጵያም ከግሪክ በመጡ በሰላማ ከሣቴ ብርሃን ደርሶናል ። ጳጳሱ ሲሞት ሲሞት ሥልጣነ እግዚአብሔር ተመልሶ አገሩ ገብቷልና እናምጣው ለማለት አይቻልም ።

ይህነን ነገር ሊቃውንቱና መምሕራኑ ሊመራመሩት ይገባል ። አመንዝሬ ሰው በ፩ ሴት ተወስነህ ሥጋ ወደሙ ተቀብለህ ኑር ቢሉት የውጭዋን ለምደዋልና ጭንቅ ይሆንበታል እንደዜሁም እኛ የውጭውን ጳጳስ ስለ ለመድን ነው እንጂ ሥልጣነ እግዚአብሔር በኛም መምሕራን ላይ አለ ። ያገራችን ሰው ቢከብር የምንወድ ከሆን ያገራችን የሲሶ መንግሥት ገንዘብስ እዜሁ ይቀር አልነበረም ። ታቦት ረከሰ እየተባለ ለመባረኪያ ፲፲ ብር ለመቀደሻ የሚሰጠው ብቻ ስንት ሚልዮን ይሆን ሰው ኃጢአት በሠራ ጊዜ ራሱ ይረክሳል ንስሐ ገብቶ ይቀደሳል እንጂ ታቦት ረከሰ እየተባለ ቄሱ ለማስባረክ ተሸክሞት ሲሄድ ያየ እስላምና አረመኔው ሁሉ ያማሬ እዝጌር ረክሰ ሰው ሊባርከውና ሊቀድሰው ተሸክመውት ይሄዳሉ ይሉናል ። መምሕራንና ሊቃውንቱ ጉባዔ አድርገው ሊመረምሩትና ሥርዓት ሊሠሩ ያስፈልገናል ።

ቄም ጸሐፌ ገብረ ጻድቅ ።

ጭውውት ከጥያቄ ።

ገብረየስ ወልደ መስቀል ለታናሽ ወንድማቸው መክሬ ለብርሃንና ሰላም ያወሩለትን ጨዋታ ጥር ፲፱ ቀን ሐሙስ ካንዱ የፍቅር ወንድሜ ቤት መጥቶ ሲያጫውተው እንዳጋጣሚ እኔም ከዚያ ደረስኹ ጨዋታቸውን ከጨረሱ በኋላ እባክህ ወንድሜ ምንም እውቀትና ለድካምህ ዋጋ የሚሆን አጥቼ ዘወትር ከቤቴ እየመጣህ ባንላመድ አልፎ አልፎ በመንገድ እንተዋወቃለንና ትንሽ ጨዋታ አጫውትህ ዘንድ ፈቃድህ ይሁን ግን እውቀት ያጠረኝ ነኝና በንግግሬ ውስጥ ስህተት ብታገኝበት አርመው እንጂ አትንቀፈኝ ካልኩት ወዲህ እሱም ይህማ ስራዬ አይደለም ። አስተውዬ አደምጽሀለሁ በል ንገረኝ አለኝ እኔም በንጋገሬ ያለመቀልጠፍ ስፈራ ስቸር ወሬዬን ጀመርኹ መንግሥት ከሚገዛው አገር ውስጥ መምር ቢያገኝ ወይም ባያገኝ ከማይገዛው አገር በገንዘቡ ፈልጎ አምጥቶ የወር ቀለብ ሰጥቶ በቀለብ ላይ እርስት ሰጥቶ ያገሩ ልጆች እንዲማሩለት ያኖረውየለምን የተባለው ። ይህማ እርግጥ ነው መንግሥት የሃማኖትና የእውቀት መሬ የሚሆን ሰው ከሐገሩ ውስጥ ቢያጣ ከሚስማማው አገር ልክ ያስመጣል ። ኋላ ግን ሕዝቡ ከሰለጠነ ደቀ መዛሙርትም ከበዙ በኋላ ከዚያው ከሐገሩ የመጣው መምር ከስተማረው ተማሬ መርጦ የሚገባውን በወንበሬ ተቀመጥ ብሎ ቢያደርገው የትኛው ሕግ ይከለክለው ኑሮዋል?ይህም በችሎታ ሳይሆን ቀርቶ መምሩ ቢደክም ም ወይም ቢሞትም መንግሥት ከደቀ መዛሙርቱ የሚገባውን መርጦ ስልጣን አስቀብሎ ለሐገሩ መምህር አድርጎ እራሱን ቢችል ከውጪ አገር በወርቅ ገዝቶ በየጊዜው ከማንጣት የማይሻል ይሆን?ከውጪ ካልሆነ ከሐገሩ ውስጥ የተማሬ ቢገኝ ለሃይማኖት አባት መሾም አይገባው ይሆን ወይስ የቀድሞው ኮንትራት ምንም ከሐገራችሁ የተማሬ ቢገኝ አይሾምም ከኛ እንጂ የሚል ይኖር ይሆን?ወይንስ ክርስቶስ ወንጌልን በሰበከ ጊዜ ስልጣንና ክህነት ለቀይ እንጂ ለጥቁር አይሁን ብሎ ይሆን?ወይንስ በቀይ እንጂ በጥቁር መንፈስ እግዚአብሔር አያድርበትምና የሃይማኖት አባት ለመሆን አይችልም ተማሬ እንጂ የሚል መጻፍ ይኖርን?ይህን ለይቶ በሚበቃ ምስክር የሚያስረዳኝ ባገኘሁ ልቤ በማሰብ አፌ በመጠየቅ ባልታከቱም ነበረ ። የዘመኑ ልጅ ወረተኛ ነውና ያገሩን ትምሕርት ጠልቶ ሌላ ትምሕርት ወዶ ሳይሟላለት ቢደክም ወይም ቢሞት የተባለው ። ብልሁ አለቃ ታየ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ባጭር ቃል በጻፉት መጽሐፋቸው በ፫፻፴፪ ዓመተ ምሕረት በኢትዮጵያ ክርስትና መጣ ይላል ከዚያ አንስቶ እስከ ዛሬ የተማረና ለዚህ ማዕርግ የሚገባ ሰው ታጥቶ ይሆን?በጥቁር እጅ አንባረክም ማለት በቀይ ቄስ እጅ እንጂ በጥቁር ቄስ እጅ ሥጋ መለኮት አልቀበልም ለማለት ይሆን?እንዲያው ዝም ብለን አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው የሚሉት ብሉይ ተረታችንን ይዘን ዜማችንን እያራረቅን ቅኔአችንን እያንገዶገድን እንኑር እንጂ ለዚህ ምን አግዶን ማለት ይሆን?እባክህ ለጨለማው ብርሃን ለጠቡ ሰላም የሆንክ ጌታዬ ሆይ ንገረኝ ንግግሬ ስለበዛብህ አትቀየመኝ ብለው ወዳጄ ሆይ ሥራዬን ለይተህ አታውቀውምና የሰማሁትን ማውራት ስህተት ሳገኝ መምከር ነው እንጂ ለጠየቀኝ ሁሉ መልስ ለመስጠት ጊዜ ያልፍብኛልና አይቻለኝም ምናልባት ለወዳጆቼ አጫውቻቸው እረፍት ባገኝ ዳግመኛ ስመጣ አጫውትሃለሁና ከዚሁ ቤት እንድንገናኝ ብሎኝ ተለያየን ።

በብርሃን ሰርታችሁ ባሰላም ለመኖር ትጉሃን የሆናችሁ አንባቢዎች ሆይ ከሰው ስህተት ክብረት ዝገት አይታጣምና ስለአለማወቄ ይቅርታችሁን ታረጉልኝ ዘንድ እለምናለሁ ።

ዘለቀ ደራጅ ።

መልስ ።

በመከነ ሥላሴ ያደጉ ክቡር ሙሴ ገብረየስ ሆይ ፤ ኢትሕሚ ብዑላነ በውስተ ቤትከ እስመ የፊ ሰማይ ብርሃንና ሰላም ያወፅኦ ለነገርከ የሚል ። ከደብተርነትዎ ብዛት የተነሣ የጠቀሱትን ቃል ባነበብኩ ጊዜ እጅግ ተደነቅሁልዎ ። ይኸው የደብተርነት አነጋገርዎ ጊዜ ስላጠፋብዎ ከዚህ አስቀድሞ ብርሃ

ንና ሰላምን በይመለከቱት ይሆናል እንጂ፡እንደዚሁ እንደርስዎ ያለ ቃል (በሁለተኛው ዓመት ብርሃና ሰላም ቁጥር ፳፰ በ፪፻፳ ገጽ) ስለ ከተማችን ጠቀሜታ ብለው አቶ ሚናስ ኬርቤጊያን በጻፉት መልስ ያዲስ አበባ ሰው ሁሉ እጅግ አድርጎ ተደንቆ ላቸው ነበር ። ቃላቸውም ፡ እርስዎ ከደጉበት ከመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ወደ ራስ መኰንን ድልድይ በሚወስደው መንገድ ዳር የተጀመረውን የአግረኛ መንገድ አይመሰገንም የሚል ጥልቅ ከሆነ ምኞታቸው የተገኘ የነቀፌታ አነጋገር ነበር ። በዚህም አገልግሎታቸው የድካማቸውን ዋጋ እንደሚገባቸው አገኙ ።

አሁንም የእርስዎ አይነተኛ ነገርዎ በጥቁር እጅ አንባረክም የሚገባው አምኃ ሰጥተን ነጭ አምጥተን እንበረካለን (እንኖራለን) ማለት ነውና ይህንን የሰሙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንደ ድካምዎ መጠን ዋጋዎን ለመመለስ አይበዝኑልዎትምና በዚህ ነገር እንዲፀናኑ ተስፋ ሰጥቼ አረጋጋዎታለሁ ።

ይልቁንም ደግሞ ይኽ አሳብዎ አሁን ብቻ መጀመሩ አይደለም ። ከዚህ አስቀድሞም እንደዚሁ እንደ እርስዎ ሁሉ ሲሞን የሚባል አስማተኛ በሐዋርያት እጅ መጫን መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጥ በየ ጊዜ ብር አመጣላቸው እንደዚህ ሲል ፡ ለኔም ደግሞ ይህን ማዕርግ ስጡኝ እጄን የጫንሁበተ ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይቀበል ዘንድ ። (ሐዋ ፡ ሥራ ፰ ፲፰ ፲፱ ።)

ከዚህ በኋላ ግን የእግዚአብሔርን ጸጋ በብር እገዛው ብለህ አስበሃልና ብርህ ካንተ ጋራ ለጥፋትህ ይሁን የሚል የድካሙን ዋጋ ከጴጥሮስ አፍ ተቀበል ። አሁንም ቢሆን ይኽ የእርስዎ አሳብ ከዚሁ የተለየ አይደለምና እድል ፋንታዎን ከሲሞን ጋራ ያድርግልዎ ።

በወደቀ ግንድ ገብረየስ፡ምሳር ብርሃንና ሰላም ይበዛበታል እንደሚሉት ሁሉ ነገር ረዘም ያደረግሁብዎ መስሎኛልና በነገሩ የሚፀፀቱበት ስለ መሰለኝ ነገሬን አጠር አደርጋለሁ ።

ልጅ ካሣ ነህ ።

መልስ፡

በብርሃን የሚደናበረውን የምቀኞች አባት የሰላም ልጆች እያዩ ይደነቃሉ ፡ ገብረ የስ ወልደ መስቀል ሆይ በመላ ኢትዮጵያ ንዴትና ጸጸት ላይ በድፍረት የምቀኝነት ሰማዕትነትዎን ስለ ገለጹ ኢትዮጵያን አሳዘኑዋት እርስዎ ወገን አለኝ ብለው ቢያስቡ እንኳን ለሞት የተቃረቡ የማይድኑ ወገኖች ናቸው ትንሽ ቆይተው የጥቁር ንጉሥ አይገዛንም እንዳይሉ ያስፈራል ወይም ደግሞ ጥቁር ቄስ አይቀድስ (አይባርክ) ይሉ ይሆን፤ ይኸን የጥያቄ መልስዎን በ፪ ነገር እጠረጥረዋለሁ ፩ኛ የሕዝቡን ሐሳብ ለማየት እንደሆነ እነሆ ይመልከቱ ።

፪ተኛ ጳጳስ ከእስክንድርያ ሳይመጣ አይቀርምና ብዬ ነበር እያልሁ እወደዳለሁ ብለው ያሰቡ እንደሆነ የሚወድዎት የለም ወገንዎን የሚሰድቡ ለነጭም አይረቡ ማንም እስክንድርያን የጠላ የለ ከተሸጠባትና ከተገዛባት ሰውዬ በቀር ለገንዘቡስ ፺ ብር ያሙጡ ቢሉዎ በጣትዎ ባልነኳት ነበር ። የዘመኑ ልጅ ወረተኛ ነው ። ያገሩን ትምርት ጠልቶ ሌላ ትምርት ወዶ ማይሟላለት ቢደክም ወይም ቢሞት አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው እያሉ መሻሻልንና አዲስ ትምርትን እንደ ሰይጣን ተመልከው በልምድ በሽታ ወድቀዋልና እግዚአብሔር ይማርዎ ።

ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ ሰማዕት ።

የከተማ ወሬ ።

ጥር ፳፫ ቀን ልጅ ተፈራ የክቡር ፊታውራሪ ገብረ ማርያም ልጅ ከወለጋ የፊታውራሪ ኃይሌን የደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔርን የልጅ ልጅ አገባ። የሰርጉ ማማርም እጅግ አስደንቆ በደስታ ተፈጸመ ።

ብርሃንና ሰላም ለክቡር ፊታውራሪ ገብረ ማርያምና ለሙሽሮቹ እንኳን ደስ አላችሁ እያለ የተባረከ ትዳር እንዲሆንላቸው ይመኝላቸዋል ።

የውጭ አገር ወሬ ።

ሽሽት

በቺናና በእንግሊዝ መካከል በሆነው ጠብ ፫ መቶ ሴቶችና ሕጻናት ከሐንከው ሸሽተው እሻንጋይ ገቡ በሐንኮው ብዙ ጭንቅ እንዳለ ይወራል ። የቺና ሰዎች በእንግሊዝና በመስኮቦች መሐከል ለመለያ የሚሆን በመስከባውያን ቤት ምልክት አድርገዋል ።

ልዩ የሆነ መብረር ።

ሰር ሳሙኤል ሆአር ከሎንዶን ተነሥቶ ወደ ዴልሂ (ህንድ አገር) ሁሉት ጊዜ በ፲፫ ቀን በአሬውፕላን በሮ ገባ ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ከ፲፪ መሐለቅ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፹ ብር ።
የበሬ ቆዳ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ፰ መሐለቅ ።
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፭ ብር
የፍየል ሴጠ	፩ ኮረጃ	፲፫ ብር ተሩብ
አቡጀዲ መነጽር ፩	ኮረጃ	፻፴፭ ብር ።
፡፡ ባለሰይጣን ስእል ፡፡		፻፺፩ ብር ።
፡፡ ባለፈረስ ፡፡		፻፴፬ ብር ።
፡፡ ባለድመት ፡፡		፻፴፭ ብር ።
፡፡ ባለአህያ ፡፡		፻፳ ብር ።
፡፡ ባለሳቢ ግመል ፡፡		፻፴ ብር ።
፡፡ ባለአንበሳ ፡፡		፻፲፱ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፪ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር ።

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፲ ፰ ማንቲም ነው ።
በአንድ ብር	፲፩ ሊሬ ፴ ፰ ።
በአንድ ጊኒ	፱ ብር ፺፬ ፺፮ ሳንቲም ነው
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አስን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምለዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ እመለክታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ስሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉሙሩክ ከየታጁሮቹ ቤት]ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ሥፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን ሞቶመቢል የፊታውራሪ ዱፌሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሄስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጉበርና አጉበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዐይነቱ ፤ መጫሚያ በየዓይነቱ ፡ ወንበር በየዓይነቱ ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነቱ ፡ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

Berliet



ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ አቶሞቢልና በእንጩት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወዴ ፍል ወሀ መውረጃ ፡፡

ARMENAK ZAMANIAN

AGENT GÉNÉRAL

Pour l'Abyssinie et Djibouti

ማስታወቂያ

በጥሩ የፈረንሳዊ አገር ጨርቅ ለኢትዮጵያ መኳንንቶች የሚገባ በጥንቃቄ የተሰፋ ካባ ከሙሴ ፕሪቶ ዘንድ ይገኛል ቤታቸውም በእንግሊዝ ባንክ ቤት አጠገብ ነውና ለሚገዙ ሰዎች ሁሉ በማክበር እናስታውቃለን፡፡

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን ኦዶኮለኝ አምበሬጭቃ በያይነቱ የሽቶና የኦዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ስንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፮
3 me ANNÉE № 6

ሐሙስ የካቲት ፫ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 10 FEVRIER 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christos Taklé Haymanot
Dirécteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ጥቂት ብርሃን ።

የፍትሐ ነገሥትና የዕብን እልዓሣል ታሪክ እስከ ዛሬ ድረስ ባገራችን ገና አልታወቀም።ስለዚህ የሁለቱንም ነገር ከዚህ ቀጥዬ ባጭሩ ብርሃን ሆኖ እንዲታወቅ እጽፈዋለሁ ። የቀረውን ግን ሊቃውንቱ እያዩ እየመረመሩ እያረሙ በስፍራው ቢአገቡት ደገባቸዋል ። እንዲህ ማለቴ ግን ስለታሪኩ ማስተካከል ብዬ ነው እንጂ እዉን ተንኳዲህ በዚሁ ፍትሐ ነገሥት የፍርድ ነገር ተጨርሶ ይሠራበታል ብዬ አይደለም ። የዕብን እልዓሣልና የፍትሐ ነገሥቱ ታሪክ ያልሁትም ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው

የኢትዮጵያ መምሕራን ከምስር አገር በዓረብ ቋንቋ የተጻፈ የምክር መጽሐፍ በግዕዝ ተተርጉሞ መጥቶላቸው በቆስጠንጢኖስ ጊዜ የነበረው ፍትሐ ነገሥት ነው እያሉ በዚያው መጽሐፍ የተማሩትን ሲያስተምሩበት ይኖራሉ ። ነገር ግን በዓረብ ቋንቋ የተጻፈውና በግዕዝ የተተረጐመው ብዙ ልዩነት አለበት ። ልዩነቱን የሚያውቁት ግን በዓረብ ቋንቋ የተጻፈውን የሚያውቁት የወዲያ አገር መምሕራን ናቸው በግዕዝ የተተረጐመው እውነት ነው ። በዓረብ የተጻፈው ሐሰት ነው እንዳይባል በግዕዝ ለተተረጐመው ምስክሩ የተቀዳበቱ ምንጭ በዓረብ የተጻፈው ነው ። የተበላሸው ግን ከትርጉሙ ብቻም አይደለ ከታሪኩም ጭምር ነው ። ስለምን ከነገሩ ሁሉ በፊት በግዕዝ ተተርጉሞ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው በሠለስቱ ምዕት ጊዜ የነበረው ዋናው ፍትሐ ነገሥት አለመሆኑ እርግጥ ነው ። ደግሞ የሚያስደንቀው ነገር ጻፈው የተባለው ዕብን እልአሣል የተወለደ ከሠለስቱ ምእት በኋላ ዘጠኝ መቶ ዓመት ቆይቶ ነው ። ይኸው ዕብን እልአሣል ትልቅ ምሁር ነበረና በቆስጠንጢኖስ ጊዜ ከነበረው ከዋናው ፍትሐ ነገሥት ከመንፈሳዊውም ከሥጋዊውም የወደደ የወደደውን ነጣጥቆ ከሌሎችም መጻሕፍቶች ቀድቶ ከልቡም አንቅቶ ከነዛ እውቀቱም አስፋፍቶ ለነዛ ሀገሩ ጥቅም የሚሆነውን ሁሉ ምክር ጽፎ ሰጠ። ይኸው እሱ በዓረብ ቋንቋ የጻፈው የምክር መጽሐፍ በግዕዝ ተተርጉሞ ወደ ኢትዮጵያ ሲወጣ ፍትሐ ነገሥት ነው ተባለ ። ከዚሁ መጽሐፍ ተመቅድሙ ላይ ወጸሐፈ ለዛቲ መጽሐፍ ዕብን እልአሣል ወመሀብም ለቆስጠንጢኖስ ወልደ እሌኒ ወንግሥ በሀገረ ዮናኒ ይላል ። ነገር ግን ምንና ምን ። የዘመን ብዛት ይሰብራል ብረት እንደሚሉት ሁሉ ታሪክ ሲያረጅ ተረት ይሆናልና ይበላሻል ። ስለዚህ በቆስጠንጢኖስ ጊዜ እንኳን ዕብን እልዓሣል ይወለድ ያያቶቹ ቅድመ አያቶችም ለመወለድ አልታሰቡም ነበረ ። ነገር ግን ታሪክ አፋለሱና ዕብን እልዓሣልን በቆስጠንጢኖስ ጊዜ ፍትሐ ነገሥት ጻሐፊ አደረጉት ። ይኸ ጭራሹን ውሸት ነው ። የውነተኛው ነገር ግን በ፲፪፻፳፰ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ እስከ ፲፪፻፴፮ ዓ ም ድረስ በእስክንድርያ አገር በተጥህዶ ሃይማኖት ትልቅ ሀውከት ተነሥቶ ስለነበረ በ፲፪፻፵ ዓ ም ዕብን እልዓሣል ትልቅ ምሁር ነበረና የተዋህዶን ሃይማኖት ለማጎልበትና በጣም ለማበርታት ሲል በሠለስቱ ምእት ጊዜ ከነበረው ከውነተኛው ፍትሐ ነገሥት ከሥጋዊውም ከመንፈሳዊውም ቅድም እንደተናገርሁት ሁሉ ቀድቶ ከሌሎችም መጻሕፍት የወደደውን ጨማምሮ ጻፈ ። ከዚሁ ከጻፈው መጽሐፍ ይበልጠው ወገን ከእስላም መንግሥት ውስጥ ከምስር አገር ለሚኖሩት ክርስቲያኖች ተፋቅሮ በሰላም ለመኖር እሚገቡ ምክር ጽፎበት ነበረ ። ይኸው እሱ የጻፈው የምክር መጽሐፍ በግዕዝ ተተርጉሞ ወዳገራችን ወጣ።ያገራችን ሊቃውንት በቆስጠንጢኖስ ጊዜ ሠለስቱ ምእት የጻፉት ዋናው ፍትሐ ነገሥት ነው ብለው በደስታ ተቀበሉት ። ዕብን እልዓሣል ግን እሱ ራሱ የምክር መጽሐፍ ብሎ ተናገረ እንጂ ፍትሐ ነገሥት ነው ብሎ ደፍሮ አልተናገረም ። ስሁሉም ነገር ይኸው መጽሐፍ የዚያን ጊዜ ለነበሩት ላገሩ ለምስርና ከዚያ ለሚኖሩት ክርስቲያኖች በጣም የሚጠቅም ምክር ስለተጻፈበት ወገኖቹ ሁሉ እልል ብለው ተቀበሉት ። ይህ ወሬ ቆይቶ በኢትዮጵያ በደረሰ ጊዜ ምንም ኢትዮጵያን የሚያጥርድ ነገር ቢጻፍበት በግዕዝ ተተርጉሞ ባጤ ዘርዓ ያዕቆብ ጊዜ መጣ ። የዚህንም ታሪክ ለደተው ከስር እስከ ጫንደ እስከ ወንዛፉ አጣርተው መርምረው የሚያውቁት የዓለሙን ሁሉ ታሪክ በየቋንቋው የሚጽፉት የኤውሮፓ መምሕራን ናቸው ። ይልቁንም አሁን በቅርቡ ዓለሙ ያወቃቸው ፍጥረቱ ያደነቃቸው ፕሮፌሶር ሴናቶር ኢኛሲዎ ጉኢዲ ናቸው ። እኒህ ሊቅ ከሌላው ሁሉ እውቀታቸው ሌላ የዓረብን ቋንቋ አስተማሪ ናቸውና ዕብን እልዓሣል በዓረብ የጻፈውን በግዕዝ ከተተረጐመው ጋራ እያስተያዩ እያነበቡ አርመው አሳምረው አሳትመው በድፍን ዓለሙ ዘርተውታል ።

ዕብን እልዓሣል በኢትዮጵያ የዋለው ግፍ ።

ዕብን እልዓሣል በኢትዮጵያ ግፍና ጡር ሚሠራ እንዲህ ብሎ ጻፈ ።አንቀጽ ራብዕ ቁጥር ፵፪ ወሰብአ ኢትዮጵያ ኢይሚሙ ላዕሌሆሙ ሊቀ ጳጳሳት እማዕምራኒሆሙ ወኢበሥምረተ ርእሶሙ እስመ ጳጳስሙ ይከውን እምታሕተ እዴሁ ለበዓለ እስክንድርያ ወውእቱ ዘይደልዎ ከመ ይሚም ላዕሌሆሙ ሊቀ እምኀቤሁ ዘውእቱ መትሕተ ሊቀ ጳጳሳት ። ግዕዝ ለማያውቁ ትርጉሙ ኢትዮጲያውያን ከወገኖቻቸው ከሊቃውንቱ መርጠው ሊቀ ጳጳስ አይሹሙ እንሱ ራሳቸው የወደዱትና የመረጡትም አይሾም ። ስነሱ የሚሆነው ጳጳስ ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ውስጥ ነው ። ይኸው የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ብቻ ነው ከወገኖቹ ከምስር ተወላጅ መርጦ እየሾመ መስደድ የሚገባው ማለቱ ነው ። ባጭሩ ለማስረዳት ግን ከኢትዮጵያ ዘር ሊቀ ጳጳስ አይውጣበት ማለቱ ነው ።

ዕብን እልአሣል እንዲህ ማለቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት አደገባውም ከኛ በታች ይሁን በኛ ፈቃድ በኛ ትእዛዝ ብቻ ይኑር ሲሆን ባፊያ ሳይሆን ዜጋ ገባር ይሁንን ማለቱ በጉልህ ይታያል። ለመረመመረው ሰው እንዲህ ለማድረግ ደገባዋል ስለምን በኢትዮጵያ ላይ ቂሙን ማስታወቂ ነው ስለምን ከዚያ ዘመን በፊት የኢትዮጵያ ንጉሦች እየወረዱ አገሩን ምስርን በግድ ሲያስገብሩት ነበረ ። ቂሙ በዚህ ነው ። አለዚያ ግን በኒቅያ ጉባኤ በተደነገገውና በነበረው በውነተኛው

ፍትሐ ነገሥት ውስጥ እንዲህ ያለ ገደብና ክልከላ አልተጻፈብንም ነበረ ። ዕብን እልዓሣል ግን በስህተቱ ቂሙን ባለመርሳቱና በምቀኝነቱ ፖለቲክ አድርጎ የኢትዮጵያን ነፃነት ለማጥፋት የጻፍ ቃል ጻፈብን።ፖለቲክ የሌለው ልዑል እግዚአብሔር ግን የሚያምነውን አይከዳ የሚወደውን አይጠላ ስንጭና ለጥቁር ለቀይና ለጠይም አደል ፍርደ. ትክክል ነውና እንደቂመኛው እንደሰነፉ ዕብን እልዓሣል ከኢትዮጲያ ሕዝብ መካከል ጳጳስ አይውጣ አይሾም አላለም።ከሉ ፊት ከሉ ዘንድ ሁላችን ትክክል ነን ።

ዕብን እልአሣል ግን በጣም ግፉን ለማብዛት እኛን ብቻም አይደለ እኛን አጥብቆ ለመጉዳት ሲል ከእስክንድርያ ተሹመው የሚመጡት ጳጳሶች ሳይቀሩ ሥልጣናቸውና መዓርጋቸው እንዲቀነስ ብሎ እንዲህ ሲል ጻፈ ። ወሶበ ተሠይመ ጵጵስና ዝንቱ ዘንኩር በስመ ሊቀናት ኢብውሕ ለቱ ከመ ይሢጵስ ጳጳሳተ በከመ ያጵጵሱ ሊቃነ ጳጳሳት ። ትርጉሙ ከእስክንድርያ ተሹሞ ወደኢትዮጵያ የሚሔደው ጳጳስ ምንም ጳጳስነት ቢኖረው በሌላ አገር የተሾሙት ጳጳሶች እንደሚሾሙት ሁሉ እሱ በበታቹ ሌላ ጳጳስ ለመሾም ሥልጣን የለውም አልተፈቀደለትም አይገባውም ማለቱ ነው ።

ወበእመ ኮነ ዓብር ዘይትጋብኡ. ቦቱ በምድረ ሮም ወመጽአ ንጉሠሙ ዝንቱ ኢትዮጵያዊ ለይንበር ውስተ መንበር ሳምን እምድኅረ በዓለ ስልቅ እንተ ይእቲ እምአህጉረ አይያም ዘውስቴቶን ባቢሎን ወእልእሬቅ በመንግሥተ ሳዑር እስመ አብሕዎ ሎቱ ከመ ይሲም ኢጲስ ቆጶሳተ በአድያመ ዚአሁ ። በማሬ/ ሲተረጐም ሊቃነ ጳጳሳቱ ሮም ላይ ጉባኤ ለማድረግ በተሰበሰቡ ጊዜ ደኹ የኢትዮጵያው ሊቀ ጳጳስ ከስልቁ ሊቀ ጳጳስ ቀጥሎ በስምንተኛው መዓርግ ወንበር ይቀመጥ ይላል (የስልቅ ቁጥር በሳዑር መንግሥት ውስጥ ከባቢሎንና ከእልዕሬቅ ጋራ ነው) ለዚህ ለስልቁ ሊቀ ጳጳስ በተሾመበት አገር ውስጥ በየአውራጃው በበታቹ የሚሆኑ ኤጲስ ቆጶሳት ለመሾም ሥልጣን አለው ተቀብሏል ለኢትዮጵያው ሊቀ ጳጳስ ግን በበታቹ ለየአውራጃው ኤጲስ ቆጶሳት ይሾም ዘንድ አልተፈቀደለትም ማለት ነው ።

የኢትዮጵያ መምሕራን የዚህን ትርጉም ሲተረጉሙ እንደሚዕዙ ዘይቤ ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሾም የተፈቀደለት ለኢትዮጵያው ሊቀ ጳጳስ ነው ይላሉ ። በዓረብ ቋንቋ የተጻፈው ምንቤቱ ግን ሥልጣን የተቀበለው የስልቁ ሊቀ ጳጳስ ነው እንጂ ለኢትዮጵያው አልተፈቀደለትም ነው የሚል። እውነት የሚመስለው ግን ሥልጣን የተቀበለው የስልቁ ሊቀ ጳጳስ ነው ። ስለምን እውነት ለኢትዮጵያው ሊቀ ጳጳስ ኤጲስ ቆጶሳት ለመሾም ሥልጣን ኖሮት ቢሆን እስከ ዛሬ ወደሐገራችን የመጡት ጳጳሶች የኢትዮጵያ ልጆች በክረምት በውጋ መላትና በዝናብ በጭቃ መከራቸውን ደዩ በበጋ በበረሃና በውሀ ጥማት ደለቁ ብለው ገዝም ባላሉም ነበረ በየውራጃው ኤጲስ ቆጶሳት እየሾሙ ሳይሰጹ ባልቀሩም ነበረ ።

የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሞኝነት ።

ያገራችን ሕዝብ እስ፡ ዛሬ ድረስ የዕብን እልዓሣልን ቃል ተከራክሮ ሳይስፍቅ ዝም ብሎ ከእስክንድርያ ብዙ ወርቅ እየደፋ አቡኖች እያስመጣ ደፋና ቅስና እየተቀበለ ታቦት እያስባረከ ይኖራል ። አቡኖችም ከዚህ መጥተው እንደ ሐዋርያት ደፋንት ወደው በትሕትና ወንጌል መስበካቸውንና ሃይማኖት እንዲሰፋና እንዲበረታ ማድረጋቸውን ትተው ከሁለት ደጃዝማች የሚበልጥ አገር እየገዙ በዚሁም ላይ ለዲቁና ለክህነት ለቅስና ዋጋ እየተቀበሉ ይኖራሉ ። መንፈስ ቅዱስን መሸጥ እፍረት አልሆነባቸውም መንግሥታችንም ደሞዝ መስጠቱን ትቶ የገዛ ድሀው በድኅነት ታንቆ ሲኖር ለውጭ አገር ሰው ለባእድ ያን ያህል ግዛት መስጠት አይገባውም ነበረ

ዋናው ጥፋት ደግሞ ያገራችን ሊቃውንት ነው ። ስለምን የሃይማኖትን ነገር እነሱ ደልቀ አሳምረው አብልጠው አጣርተው ሲያውቁ እንዴት ዕብን እል ዓሣል በደነገገው ቃል ተጥርደው ተንቀው መኖር ተቻላቸውን ግፉም ነው ያሳዝናል ያስደንቃል ።

መንፈስ ቅዱስ በእስክንድርያ ክህናት በኩል ብቻ ነውን የሚገኘው፤ ወይስ የእስክንድርያ ክህናት ብቻ ጥዋትና ማታ ከእግዚአብሔር ቆይታ ያደርጋሉን ፤ ወይስ ለነሱ ብቻ ከሥላሴ ጋራ የሚነጋገሩበት የተለየ በውቅ የተሠራ ስልክ አላቸውን ፤ ወይስ የኢትዮጵያ ክህናት በቀጥታ አይሰምሩኝ በእስክንድርያ ክህናት በኩል ብቻ ይስምሩኝ ይመኑኝ ብሎ እግዚአብሔር ደንብ ሰጥቶናልን ፤ ለሁሉም ነገር ያስፈውስ አስፈ ፤ ለእ፡ገዴህሳ የኢትዮጵያ ሊቃውንት በዚህ ነገር ምንም አያስቡበት ይሆን የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሆይ፥ እስከ ዛሬ ድረስ ራሳችንን ባለመቻላችንና ከሰው በታች በመሆናችን ዓለሙ ሁሉ ሳቀብን ። አሁን ግን በእስክንድርያ ሞግዚትነት ከመኖር ደልቅ በነጻነት የተዋህዶን ሃይማኖትና ወንጌልን እስተምሩ ። ደጉ ፤ ሀብታሙ ፤ የዋሁ አባታችን አቡነ ማቴዎስ ለዘለዓለሙ ኑረውልን ቢሆን እስከ መቼውም አይጐረብጡንም ነበረ ። ስለምን አርባ አምስት ዓመት ሙሉ ከኛ ጋራ ሲቀመጡ ባሕርያችንን ባሕርይ ፤ ደስታችንን ደስታ ፤ ኃዘናችንን ኃዘን አድርገው፥ብንጣላ አስታርቀው፥በመንግሥታችን ሑከት እንዳይገባ ጥቃት እንዳያገኘው ተጨንቀው እኛን መስለው ይኖሩ ነበረ ። ስለዚህ ከዚህ እንደ ተወለዱ እንጂ ከባዕድ አገር እንደ መጡ አናያቸውም ነበረ አሁን ግን እሳቸው ቃረፉ ሌላ ባዕድ ሊቀ ጳጳስነት ተሹሞ ቢመጣ መቀበል አይገባንም ። ለኢትዮጵያ ትልቅ ውርደት ይሆናል ። ከዚህም ቀደም ባዕድ ጳጳስ በመቀበላችን ድፍን ኤውሮፓ ስቆብናል ።

የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሆይ ።

እንግዲህ ተእንቅልፋችሁ ንቁና ዕብን እልዓሣል በምቀኝነት የደነገገብንን ቃል እናስፍቅና ነጻነታችን ይታወቅ ። መንግሥታችን ደጊቱ ኢትዮጵያ በሥጋዊና በፖለቲካ ነገር ራስዋን ችላ በነጻነት እንደምትኖር በመንፈሳዊም በኩል ነጻነትዋን እናስረግጥ ። እንዴት ማለት ከኢትዮጵያ የተወለዱት ባላባቶች በበረሃ ተዘርተው በዱር በገደል ፤ በዋሻ ተወስነው ፤ ወይም በገዳምና በደብር በከተማም ቢሆን ተቀምጠው መጽሐፍ እየተረጐሙ ፤ ሃይማኖት እያስተማሩ ፥ የክርስቶስን ወንጌል እየደላደሉ ፤ የድንቁርናን ጾር እየመነጠሩና እየጠረጉ ፤ የኃጢአትን እሾህ እየነቀሉና እየጠሩ የሚኖሩ አበው መምሕራን አሉን ። ከነዚሁ አበው እኛ እየመረጥን ወደ እስክንድርያ እየሰደድን ዋናው የሃይማኖት አባታችን የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት እየሾመ ማርያን እየቀቡ እንዲሰጡን እናድርግ ። እኛም ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ፈቃድ ለመውጣት ምንም ሐሳብ የለን ። እኛ የምንላቸው ከወገኖችን የመረጥናቸውን አበው ሾመው ፤ መርቀው ፥ ቀብተው ይስጡን ነው ። ከዚህስ ያገስ ምን ነገር እንለምናለን ። የእስክንድርያውም ሊቀ ጳጳሳት እኛ የሃይማኖት አባታችን ብለን ስንለምናቸው እሳቸውም የሃይማኖት ልጆቼ ብለው የምንለምናቸውን ነገር ደስ ብሏቸው እሺ ማለት ይገባቸዋል ። የዕብን እልዓሣልን ቃል ተከትረው አይሆንም እንደ ተለመደ ያገሬን ሰው እሾምላችኋለሁ ይላሉ ብለን አንጠረጥርም ። አለዚያ ግን ባርያ ሁኑኝ፥ነጻነት አይገባችሁም ፤ ሃይማኖቱም የኛ ብቻ ነው ። እግዚአብሔርም የኛ ብቻ ነው ። እናንተን አያውቃችሁም፥አልፈጠራችሁም ከማለት ቁጥር ነው ። እንዲህ የማለት ነገር ያየንባቸው እንደ ሆን ግን እኛም መካዳችንን ማወቃችን ነውና ከፈቃዳቸው መውጣት ኃጢአት አይሆንብንም ። በቀረውም አባት ልጁቹን አስጥፋት የካደ እንደ ሆን ልጆቹም ሌላ አባት ቢፈልጉ ኃጢአት አይሆንባቸውም ። በሁሉም ነገር ባርያ ነጻነቱን ይፈልጋል እንጂ ጌታው እባክህ ነጻነትህን ተቀበለኝ ብሎ መለምን የለበትም ። እኛም ከሁሉ ቀደም ባንፈልገው ይሆናል እንጂ ፈልገነው ቢሆን የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ነጻነታችንን አይነሱንም ነበር ። አሁንም ያለፈው አለፈና ለእንግዲህ ነጻነታችንን እንፈልጋለን ። ለልማደ. ባርያ በወርቅ ደገኘ ነበር ። ከሁሉ የሚደንቀው ነገር እኛ ለእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ወርቅ እየደፋን በዚያው ላይ ነጻነታችንን አጥተን እንኖራለን ። የምንደፋው ወርቅ ለባርነታችን ማጠንከሪያ መሆኑ ነውን ወይስ መንፈስ ቅዱስ በወርቅ መሸጥና መገዛት ይገባዋልን ፤ እንዲህ የድፍን ዓለሙ መሳቂያ መሆናችን በጣም ያሳዝናል ።

እንዲህም ባሉ በሃይማኖት ረገድ ዓለሙ ሁሉ ራሱን ችሎ ሲኖር ኢትዮጵያ ብቻ በእስክንድርያ ሞግዚትነት ነጻነቷን ሳታገኝ-ትኖራለች።እንዲጎስ ሌላ የሮማ የእስክንድርያ የአፊሶን የአንጾኪያ እኒህ ያሉቱ አህጉር ሊቃነ ጳጳሳት በኒቅያ ጉባኤ እንደ ተደነገገው ቃል ባንድ ሃይማኖት ባንድ አሳብ ባንድ ምኞት የክርስቶስን ወንጌል ሊሰብኩ ሃይማኖት ሊአስፉ ሊአጸኑ ሊአጠምቁ ባስፈለገም ጊዜ በየዓመቱ እየተሰበሰቡ ጉባኤ ሊያደርጉ ነበረ ። ኋላ ግን እነዚሁ ዋኖች ሊቃነ ጳጳሳት ሳይቀሩ ተለያይተው ሁሉም ራሳቸውን ችለው አንዱን አንዱ ሳያገዘው በምክርም ተለያይተው በነጻነት ይኖሩ ጀመሩ ።

ኢትዮጵያ ብቻ ነገሩ ሳይጠፋት የተዋሀደን ሃይማኖት መርምራ አጥርታ አሳምራ ስትኖር ዓይን አፋር ሆና እንደ መንፈቅ ልጅ በእስክንድርያ ሞግዚትነት ነጻነቷን ሳታገኝ ትኖራለች በዚህ ነገር ድፍን ዓለሙ ሲደንቅ ሲስቅ ወይም ሲአዝን ይኖራል ። አሁን ግን ጊዜው ደርሱዋልና ነጻነታችንን ማወቅ መጠየቅ መቀበል ይገባናል ። ራሱን ችሎ ለሌላ የሚተርፈውን አንዱን ጌታ አልፎ ሲሔድ ወይም አርፎ ከተቀመጠበት ስፍራ አንዱ ደርሶ ባርያ ሎሌ ገባር ሁነኝ ቢለው እሺ ሊለው ይገባዋልን ወይስ ያ ሰው ባርያ ሁነኝ ማለት ይገባዋልን ። ዕብን እልዓሣል ግን እንዲህ ብሎ ጻፈብን ።

ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ ወፈድፋደሰ በኀበ አዝማዲሁ ።

አሁን እኛ ያገራችንን ነጻነት ስንፈልግ ካገራችን አበው ተመርጠው ጳጳስነት ይሾሙልን ስንል አንዳንዱ ሰው ወደ በድንቁርና ብዛት ወይም በየዋህነት ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ ወፈድፋደሰ በኀበ አዝማዲሁ የሚለውን ቃል ተከትሎ አይሆንም እንደ ጥንት አባቶቻችን እንኑር ይል ይሆናል ። እንዲህ የሚለው ሰው ግን የገዛ አገሩን ነጻነት የሚአስጠላ በሺታ ያደረበት ለርግማን የተገባ ሰው መሆኑ ነው በቀረውም ከጥንት አባቶቻችን ልማድ አንወጣም ማለት ከጨለማ ወደ ብርሃን አንሔድም ማለት ነው ። በእውቀትና በስልጣኔ ነገር ካባቱ የሚደሻል ልጅ ካልተወለደ ቁጥር ነው ። እንደ ጥንት አባቶቻችን ኑረን ቢሆን እስከ ዛሬ የአዳምንና የሔዋንን

ቅጠል ከየ ዛፉ በተሻማንነው ነበረ ። ለሁሉም ነገር እንዲህ ላለው ሞኝ ሰው ብርቅና ድንቅ አንዳንድ ቀን አዲደምቅ የሚሉትን ተረት ማስጠናት ደሻላል። ስለምን አንድ ጊዜ ከኢትዮጵያ አበው ጳጳስነት መሾም ሲጀመር ብርቁ ካንድ ቀን የበለጠ አይቀመጥም። ባለቤት ያቀለለውን አሞሌ ባለዳ አይቀበለውምና ደልቅስ የገዛ ራሳችንን መናቁ ደቅር መከበር ደገባናል። ነጻነት ከማር ከሱካር ደጣፍጣል ነጻነት የሌለው የሰው ተገጋር መሆን ግን የተደፈቀ ሬት መጠጣትና በሾህ አልጋ በኅግ ጉዝጓዝ መተኛት ነው ። ያንት ያለህ አያድርስ ያንጣጣል ደወጋል ደለበልባል። አያድርስ አያድርስ።

አፈወርቅ ዘብሔረ ዘጌ።

የ፴፮ ገጽ ተከታይ ።

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

ሁለተኛው ደግሞ በየከተማው ያሉ ሰዎች በዝተው በከተማቸው ዙሪያ ታርሶ የሚገባው እህል ለባላገሩና ለነርሱ ምግብ እንደ ዱሮ የማይበቃ ሆነ ከዱሮውም የበዛ እህል እንዳይገባ ባላገሩ ደህና መሣሪያና የሚበቃ እውቀት የለውም ። ከከተማዎቹም ራቅ ያሉት አገሮች ታርሰው እኅላቸው ወደ ከተማ ይመጣል እንዳይባል ደህና የጋሪ መንገድና የምድር ባቡር ስለሌለ ድካሙ ብዙ ነውና አይቻልም ። ከዚህ ምክንያት የተነሣ ባዲስ አበባ ዙሪያ ካለው አንዱ ቀላድ ሁለት ወይም ሶስት ሺህ ብር ሲያወጣ በባሌ ወይም ወለጋ ያለው መሬት ፲ ብር እንኳ ሊያወጣ አይችልም ።

አሁን እንግዴህ ስ፡ወደ ፊት በዲስ አበባ ዙሪያ ያለው ባላገር የሚበቃ ዕውቀትና ደህና መሣሪያ አግኝቶ ካጠገቡ መሬት ብዙ እህል አርሶ ለማግባት የተቻለው እንደሆነ እህሉ በከተማ ውስጥ ካሉት ሸማቾች ምግብ ተርፎ ሊረክስ ነውና በየከተማው ዙሪያ ያለው መሬት ወድያው ይረክሳል ፤ ይህም ቀርቶ ወደ ባሌ ወደ ሲዳሞ ወደ ወለጋ የጋሪ መንገድ ወይም የምድር ባቡር ቢዘረጋ ከነዚያ ወረዳዎች ብዙ እህል ወደ አዲስ አበባ ሊመጣ ነውና ስለዚህ በአዲስ አበባ ዙሪያ ያለው መሬት ሁሉ ይረክሳል።የባሌውና የወለጋው መሬት ግን እህሉ ወደ አዲስ አበባ ሊመጣ ነውና ባዲስ አ.ብ ዙሪያ ያለው መሬት የረከሰውን ያህል ጨምሮ ዋጋው ከፍ ይላል ።

ስለዚህ ባላገሩ እንዲጠቀም ተብሎ ገንዘብ ቢያበድሩት ለዛሬው የኢትዮጵያ ባላገር አንዳችም ጥቅም አይሆነውም ይልቁንም መሬቱ እየተሸጠ በጥቂቶች ሰዎች እጅ ይገባል ። እነዚህም ጥቂቶች ሰዎች የሚያገኙት ጥቅም ብዙ መሆኑ ተጠራቅሞ ነው እንጂ ከያንዳንዱ መሬት የሚያገኙት ትርፍ ቢታሰብ ጥቂት ነው ። ይህ ስለ ተባለ መቼም አልፎ አልፎ አንዳንዱ ደህና መሬት ተገኝቶ ብዙ ትርፍ አይገኝም ማለት አይደለም። ጭራሹን አንዳች ነገር የማይገኝበት መሬት መልቶ የለምን።ስለዚህ እንደዚህ ያለ ድንገተኛ ነገር በሂሳባችን አይገባም ።

በሂሳባችን የሚገባ ከሥርዓት ጋራ የሚስማማ ነገር ሁሉ ነው ። ይህም ሥርዓት እንዲህ ይለናል ባንድ አገር ውስጥ ባለ መሬት የሚጠቀም መጀመሪያ ከጠገቡ መሬት ብዙ እህል ለማግባት የሚበቃ መሣሪያና እውቀት ሲያገኝ ነው ።

ሁለተኛም አርሶ ያገባው እህል የሚሸጥበትና የሚበላበት ገበያው ቅርብ ሲሆን ነው ።

የማናቸውም መንግሥት መሠረት ግን እርሻ እንደሆነ ብጣም እንረዳለን ፡፡ ባለእርሻው ሲጠቀም መንግሥትም ኃይል ያገኛል ። ባለእርሻው ሲጐዳ የመንግሥትም ኃይል እየነሰ ይሄዳል ። ስለዚህም ሕዝቡ እንዲረዳና እንዲበረታ የፈለገ መንግሥት ግን ከሁሉ ነገር በፊት የባላገሩ ትዳር እየተሻለ እንዲሄድ መጣጣር አለበት ፡፡ የባላገሩ ትዳር ግን እየተሻለ የሚሄድ ምናልባት ለያንዳንዱ ነገር አልፎ አልፎ የውጭ አገር ደምብ ሲያወጡለት አይደለም ። የነፍስ ገዳዩ አቀጣጥ ደምብ በመስቀል ወይም በጐራዴ እንዲሆን ፤ ዳኛው የሚፈርደው ባንድ ደንጊያ ላይ ተቀምጦ እንደሆነ ወይም ባማረ ወምበር ላይ እንዲሆን ፤ አስረኛውንም የሚይዝና የሚጠብቅ ዘበኛ ጥሩ ልብስ ወይም ቀዳጅ ጨርቅ ቢለብስ ፤ ከቀረጥም የሚገኘው ገንዘብ ቢያንስ ወይም ቢበዛ መንገድና የምድር ባቡር ቢሥራ ወይም ባይሠራ ባለ እርሻው አንዳች ጥቅም አይሆነውም ። በእንደዚህም ያለው ነገር ሁሉ ባለመሬቱ ካልተጠቀመበት መንግሥትም አይጠቅምም የማናቸውም ቤት መስከት ወይም መዝጊያ የሚጠቅም የቤቱ መሠረት ሲጠና ነው ። የቤቱም መሠረት ካልጠና ለመስኮቱና ለመዝጊያው የወጣው ገንዘብ ኪሣራ ይሆናል ። በሕዝብም ትዳር እንደዚሁ ነው ፡፡ ቤቱም ሊጠነክርና ሊያምር የፈለገ መንግሥት መስኮትና መዝጊያ ጣራም በረንዳም ሳያበጅ ከሁሉ ነገር በፊት የቤቱን መሠረት ማጠንከር ያስፈልገዋል ። የቤቱ መሠረት ግን የሚጠነክርለት በምን ነው ። እስኪ እንመርምር ።

የዚህ ጥያቄ ምላሽ በጣም አጭር ነው ማናቸውም ለሕዝቡ ኑሮ የሚያስፈልግ ዕቃ ሁሉ ባገሩ ውስጥ እንዲሰራ ካገሩም ወደ ውጭ አገር የሚሄድ ዕቃ ሁሉ የተሰራ እንደሆነ መንግሥት አጥብቆ እንዲጥርበት ተስፋ እናደርጋለን ። መንግሥት እንደዚህ አድርጎ ሲጥር ግን ከሁሉ በፊት ዋና አጋዥ የሚሆነው የተደላደለ መሠረት ያለው የጉምሩክ ደምብ ነው ። መሠረትም ያለው የጉምሩክ ደምብ ለሕዝቡ ጥቅምና መሠልጠኛ የሚሆነውንና ባገሩ ውስጥ ሊበጅ የማይቻለውን መሣሪያና መኪና ሁሉ ያለ ቀረጥ እንዲገባ ይፈቀዳል ። ያለ ቀረጥ እንዲገቡ በተፈቀዱ መኪናዎችና መሣሪያዎችም ሊሠራ የሚቻል ነገር ሁሉ በብዙ እንዲቀረጥ ይደነግጋል ።

ዳሩ ግን ዋናው የመንግሥት አጋዥ ደህና የጉምሩክ ደምቡ ነው ስለ ተባለ ብቻውን ይበቃል ማለት አይደለም ። ደግሞ የጉምሩኩን ደምብ የማይለዩት ሶስት ባልንጀሮች አሉት እነዚህም ባልንጀሮች ።

አንደኛው የሕዝብ ማሰልጠኛ የትምሕርት ቤት በያይነቱ ማቆም ነው ።

ሁለተኛው ሕዝቡን እርስ በርሱ የሚያቃርብ መንገድና የምድር ባቡር ማሰራት ያስፈልጋል ።

ሶስተኛው በገሬችሁ ውስጥ ሁኜ እሠራለሁ የሚለውን ሰው ሁሉ የማናቸውም መንግሥት ዜጋ ቢሆን በደስታ ተቀብሎ በቸገረው ነገር መርዳት ነው ። ሶስቱ ዋና ባልንጀሮቹ የተባሉ እነዚህ ናቸው ።

መቼም የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስፈልገውን ዕቃ ሁሉ የሚገዛው ከውጭ አገር ሰዎች ነው ። ሠራተኞቹ ያሉበት ቦታ እሩቅ ስለ ሆነ ግን ዕቃውን አገኛለሁ ሲል ብዙ ትርፍ ድካም

ይሄድበታል ጥቅሙን የሚያገኙ ግን ነጋዴዎች ናቸው ። ስለ ዚህ የውጭ አገር ሰዎች ድካማችንን መውሰዳቸው ላይቀር አጠገባችን እየሠሩ ቢወስዱት ይሻላል ። ባገራችን ውስጥ ሆነው የሠሩ እንደሆን ግን የመልከተኞቹ ነጋዴዎች ትርፍ ይቀራልና ያገራችን ሰው የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እንደ ድካሙ መጠን ያገኛል።የመሥሪያውም ፋብሪካ ባገሩ ውስጥ ስለ ቆመለት እየየ ሕዝቡም ይሰለጥንበታል ። በጊዜም ብዛት ለኑሮው የሚያስፈልገውን ዕቃ ሁሉ ራሱ ለመሥራት ዕውቀት ያገኛል።ስለ ዚህም ባገራችን ውስጥ ሆኖ ሊሠራ የሚፈልግ ሰው ቢመጣ የማናቸውም መንግሥት ዜጋ ቢሆን በመልካም ቢቀበሉት ይጠቅማል እንጂ አይጎዳም።መንግሥትም እንዲህ ያሉ ሰዎች እንዲመጡለትና ባገሩ ውስጥ አስቀምጦ ሕዝብን ለማሰልጠን ሥራዬ ብሎ መጣር ይገባዋል።መንግሥት እነዚህን የተጻፉትን መንገዶች አጥብቆ ቢከተል ኃይሉና ሀብቱ እያደገ እንዲሄድ የታወቀ ነው ፤

እነሆም በብዙ ድካም ተለቅሞ አንዳች ነገር ሳያበስል ወይም ሳያሞቅ ነዶ ያለቀ እንጨት በከንቱ መጥፋቱ ነው ፤ አንዲሁም የማይሠራ ሰው የበላው እህል በከንቱ ይጠፋል ፤ በዚህ ምክንያት ያ ከጥር ፲፱፻፬ ዓ እስከ ጥር ፲፱፻፳ ዓመተ ምሕረት ድረስ ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር የሄደ ቆዳ ሳይሠራ ስለ ሄደ ያሳዝናል ። ሳይሠራም ስለ ሄደ ያወጣው ዋጋ በፈረሲላ ፲፫ ብር ስለ ሆነ ብናስበው የዋጋው ድምር ፻፵፱ ሺ ፱፻፹፯ ብር ብቻ ሆነ ። በኢትዮጵያ ደህና ሆኖ ተሠርቶ ቢሆን ግን እጅግ ቢያንስ ቢያንስ ፈረሱላው ፶ ብር ያወጣ ነበር ማለት የዚያን ጊዜ የሄደው ቆዳ በዚሁ ሂሳብ የዋጋው ድምር ፲ ሚልዮን ፰፻ ሺ ፱፻፵ ብር ይሆን ነበር ። ይህም ሆኖ ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚያ ዓመት የበላው እህል እንኳ ሊጠፋ ሥራ ሆኖ ተሸጦ ትርፍ ጨምሮ ይመለስ ነበር ።

ካገር የሚገኝ ነገር ሁሉ ተሠርቶ ወደ ገበያ ሲወጣ ሕዝቡ የበላውን ምግብ ጨምሮ ይሄዳል ሁለቱም ወደ ገበያ ተያይዘው ሂደው ዋጋ ያወጣሉ የተበላውም እህል ፍጉ ባገሩ ውስጥ ይቀራል በተሠራውም ዕቃ ውስጥ የሄደው ፍግ ዋጋ ያወጣል ። ስለ ዚህም በሥራ በሠለጠነ መንግሥት ውስጥ ማናቸውም አንድ ጊዜ የተደከመበት ነገር ቢበላም ባይበላም ጠፍቶ አይሄድም ለወደ ፊት መንግሥቱ የበለጠ ሀብትና ኃይል እንዲያገኝ ይረዳል እንጂ ደግሞም እንደዚሁ ባገሩ ውስጥ የተደከመበት ነገር ሁሉ ዋጋ ሳያወጣ የፊት የፊቱ ወድያው የሚባክንበት መንግሥት ኃይልና ሀብት አይጨምርም ።

እነሆ ባጭሩ ባንድ ሕዝብ ውስጥ በብት ምን እንደሆነ የሚያድግበትና የሚያንስበትንም ምክንያት ባጭሩ ተረዳን የሕዝብ ሀብት የሚያንሰው በላተኛው ከሠራተኛው ሲበዛ ነው ። ሕዝቡም ዕውቀት በሌለው መንግሥት ውስጥ የሕዝቡም ትዳር ቀጥሎ እንደ ተጻፈውና እንደ ተሳለው ነው ።

የመጀመሪያ ስእል ምሳሌ እውቀት ባሌለው መንግሥት ውስጥ ንግድና ጦርነት እየሰፋና እየታደሰ የእጅ ሥራ እየተና ቀና እያነሰ ይሄዳል ። መሬትም ከዚህ ምክንያት የተነሳ ምድረ በዳነት እየበዛበት የተመሠረተው እርሻ አንዕ ከሁሉ በታች ሆኖ ይቀራል ። የሚያርሱትም ጥቂቶቹ ሰዎች ስለ ሆኑ ከሠራተኛው በላተኛው በዝቷልና ለሕዝቡ ምግብ ስላልበቃው ያ እውቀት የሌለው መንግሥት ለሥራ ፈቶቹ ከውጭ አገር ምግብ ለማስመጣት ይሰናዳል ። ሀብቱና ኃይሉም እያነሰ ይሄዳል ።

ከዚህ የቀረው በሚከተለው ይታተማል ።

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት መጽሐፍ ነው ።

ምክር ።

ምክር ሠናይት ለኵሉ ዘይገብራ የሚለውን መሠረት አድርጌ አሣቤን ለክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቦች እገልጻለሁ ይሄውም እንደኛ ኢትዮጵያ በእንዴት ያለ ምንገድ ገንዘብ ልታገኝ እንደምትችል የሚመስለኝን እመለከታለሁ ኢትዮጵያ በሆዷ ውስጥ ብዙ ወርቅና ብር ልዩ ልዩም የማዕድን ነገር እንዳላት በሁሉ ተመስክሮላታል ነገር ግን ነበረኝ ከማለት አለኝ የሚሉት ተረት እንዳይሆንባት ፤ የማዕድን ሥራ የሆነውን ሁሉ እያወጣች ገንዘቧን ወደ እጅዋ ካልያዘች አለኝ ልትል አትችልም ብትልም እንዳላት አይቆጠርም ስለ ዚህ ልጆችዋን አስተምራ መቈፈር የሚያስፈልጋት ሆነ ስለ ሆነም ለትምህርቱም ብዙ ገንዘብ ያስፈልጋልና ለዚሁ እርዳታ ምን ይደረግ እንደኔ አሣብ የሚያስፈልግ የሚያስፈልገውን ነገር ኢያዩ ወደ ሚያስፈልግ ሥራ ማዋል ነው ለዚሁም ፩ ትንሽ ታሪክ እተርካለሁ ያንድ መንግሥት ሕዝብ ካንድ መንግሥት ሕዝብ ጋራ ጦርነት ገጠሙ ይባላል ሲዋጉ ሲዋጉም ገንዘብ ቸገራቸው ጠላትም በረታባቸው ያንጊዜም የማዕድን ሥራ ለመሥራት እንዳይሄዱም የጦርነት ጊዜ ነው እንጂ የሥራ ጊዜ አይደለምና ጠላቱ የሚያገኘው ሆነ ስለዚህ ሴቶቹ እንደወንድ ልብስ ኢየለበሱ ጠበንጃቸውንም ኢያነገቱ ስለ አገራቸው ሲሉ ወደ ጦርነት መሄድ ግድ ሆነባቸው ነገር ግን መቸም ካገር ብልህ አይጠፋምና ከማከሮቹ አንዱ ተነስቶ አማካሮቹን ሰማችሁ ጠላታችን እኮ በገንዘብ ነው እንጂ በወታደር አልበለጠንም ስለዚህ ባገራችን ከሴቶች ያለ እዚህ ይውላል የማይባል ጉልቊ የሌለው ወርቅና የብር ሽልማት አለና ይህንኑ ኢያስገፈፍን ገንዘብ ብናሰራው ጠላታችንን ድል ለመንሣት እንችላለን ሴቶችም እጦርነት ከመሄድ ሽልማታቸውን መስጠት እንዲመርጡ የታወቀ ነው አላቸው።ስለ ዚህ ምንስቴሮቹ ሁሉ ነገሩን ተረድተውት አላንዳች ጥቅም በከንቱ የተሰራው ጉልቊ የሌለው የሴቶች ሽልማት ወርቅ ዘበኞች ኢየገፈፉ ሊያመጡ አዋጅ ተደረገ መቸም ሴቶቹም ላገራቸው ቅናት ታጥቀው ገና ዘበኞቹ ስራቸውን ሣይጀምሩ ይህነን አዋጅ እንደሰሙ ከየማጥናቸው ያዩቶቻቸው እንኳ ሣይቀር ሽልማት የተባለ የወርቅ መሣሪያ ሁሉ ኢያመጡ ለየከተማው ማዘጋጃ ቤት አስረከቡ ይባላል አንዳንድ ብርቱ ሴቶችስ እንኳ ምንም አይሆንም ኢያሉ የወታደር ልብስ ለብሰው እጦርነት ገብተው እንደጀግኖች ሁሉ ማርከው ገቡ ይባላል።በንደዚህ ያለ ምንገድ መንግሥታቸው በረታ ጠላታቸው ተበረረ፤ይኸን አይተው የነበረ ብዙ ትርፍ ገንዘብ አገኙ እንተስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ ጠላት የለኝም እንዳትል እንኳ በድብቅ የነበሩ የዱሮ ጠላቶችህ ዘሬስ አንገታቸውን ከፍ አድርገው ሰማየ ስማይ ኢያዩ በግልጽ ይፎክሩብሃልና ነገሩን ሳትረዳው አትቀርም ።

ደግሞስ ለወደፊቱ እጥለዋለሁ ኢያለ ከጨለመ ስር ተጠግቶ የሜርከርብህ ድንቁርና የተባለ ጠላትህን አላወቅኸውም መሰለኝ እንጂ ብታውቀውስ በግልጽ ከሚያስፈራሩህ ያሉ ጠላቶችህ ይልቅ የበረታ ብዙችንም ከንተ የሚበልጥ ሕዝብ ያጠፋ ጠላት ነውና ትጠነቀቅበት ነበር።

እንግዲህ እንዲህ ያሉ ጠላቶች እያሉን እንዴት እንተኛለን ተኛን እንዳንባል አልተኛንም መንቃትስ ነቅተናል ነገር ግን ለሥራ አልተጋንምና እንደተኛን እንጂ እንደተነሣን አይቈጠርም እግዚአብሔር ይመስገን አሁን በኢትዮጵያችን የትምህርት ጠቀሜታ ታውቀዋል የጠፋውስ ለትምህርት የሚሆን ገንዘብ ነው።ስለዚህ አውቀን እንዳላወቁ እንዳንሆን የከበራችሁ መኳንንትና ወይዛዝር ኢትዮጵያውያን ሆይ ለጌጥ ብላችሁ ያሠራችሁት ሽልማት ሁሉ ሳገራችሁ ልትሰጡ በላይ እንዳነበብነው ነው፡አገራችን ከጠላቶችዋ አማብ እንዲያስቀራት ነበር ለኛ የማያስፈልገውን ፤ ለመንግሥታችን ግን ብዙ እርዳታ የሚሆን ሽልማት ቀጥሎ ያለው ነው በወርቅና በብር ያጌጠው የፈረስ መጣብር የበቅሎ ወርቅ አልቦና ወርቅ እቃ በንደዚህ ያለ አይነት የተደረገ ሽልማት ባለ እውቀት የደረገ ነው ባለ ዕውቀት የተደረገ ማለቱ እንዲህ ነው ሰው ፈረስና በቅሎ ሲቀመጥ እንዲመቸው ኰርቻ ሠራ ለመውጣት እንዲመቸውም እርካብ አደረገ በቅሎይቱን ወደፈቀደው እየመራ እንዲወስደውም ልጓም አበጀ እስካሁን ድረስ የሠራው ሁሉ የሚያስፈልገው ስለሆነ በእውቀትና በምርምር የተሠራ ነው ይህን አልፎ በወርቅና በብር የተሠራ መጣሪያ ግን በድሮ በድኅና ጊዜ መሆኑን ግልጥ ነው ነገር ግን በቅሎና ፈረሱ በብርና በወርቅ ካላጌጡ አይሄዱም መውጣትም አይቻልም የሚል ይኖር ይሆን አንድ እንኳ አይገኝም እስቲ በሥልጣኔና በሃብት የሚበልጡ አሮጳውያንን እንመልከት በፈረሶቻቸውና በበቅሎቻቸው ከንድ ሁለት ጠፍር ቆዳ በቀር ምንይታያል ድሆችን እንዳይበሉ ብዕላሞች ናቸው ስለዚህ ነገሩን የድንቁርና መሆኑን ተረድተውት ጥለውታልና ያለ ድንቁርና ሽልማታችን ሁሉ ለመንግሥታችን እንድናስረክብና መንግሥታችንም ይህንን ተቀብሎ ገንዘብ አሰርቶ ለልጆቻችን ማስተማርያ እንዲያደርገው እመለክታለሁ ።

እንዲሁም የከበራችሁ ወይዛዝሮች ሁላችሁ እንደነኛሴቶች ስለ አገራቸው የሰሩት ያነበባችሁትም ተከትላችሁ መልካችን ባህሪያችን ነው ትምሕርታችንም ሶራችን ነው ብላችሁ በድንቁርና በጥንት ልማድ ካንገታችሁ ከጆሮዋችሁ የተንጠለጠለውን ከጃችሁ ከግራችሁ የታሰረውን የወርቅ ሰንሰለት ፈታችሁ ከማጥን ያለውን ሁሉ ለመንግሥታችሁ ብታስረክቡ በኢትዮጵያ የታሪክ መጽሐፍ ተጽፋችሁ ለዘለዓለም ስማችሁ እየተጠራ ይኖራል ብየ አስታውሣለሁ መንግሥታችንም ይህን አማብ ባዋጅ ቢያስፈጽመው ሕዝባችን ደስ ይለዋል እንጂ ቅር የሚለው አይመስለኝም ፤

አንባቢዎች ሆይ ምናልባት ከሰው ስህተት አይጠፋምና ቅርታ ቢኖረው ይቅርታችሁን እለምናለሁ ፤

ፊታውራሪ ሊበን አጋሜ

መልስ ።

ስለ ሀገራችን ስለ ኢትዮጵያ ግፍ የተቻለኝን ጽፌአለሁ በመካነ ሥላሴ ያደጉት ገናናው ገብረየስ ወልደ መስቀል በብርሃንና ሰላም ያስጻፉትን ባየሁ ጊዜ በብዙ አዘንኩ ።በመካነ ሥላሴ ያደገ ሰው ስነ ፍጥረቱን አያውቅምን ሌሎቹን መጻሕፍት ባያውቅ ፤የገብረየስ ወልደ መስቀል ስነ ፍጥረታቸው ምን ሆነና ነው ሰውን የነቀፉበት ። ሥላሴ ነጭ ጥቁር ሳይሉ ንግበር ሰብአ በአርአያነ ብለው እንደ ፈጠሩት አያውቁምን መጽሐፍ ባይመለከቱ ነው እንጂ ያገኙት ነበረ ። ወይም ከሌሎች የተማሩት ፈላስፋነት ይኖራል እንጂ ፤አንባቢ ሆይ ተመልከት ። ሳሙኤል መልክ መርጦ ኤልያብን እሾማለሁ ቢል ኢትርአይ ግርማ ርእየቱ ለኤልያብ አለው ። በግ ጠባቂ የነበረ አጪር ቀጪን ዳዊትን አነገሠ፤ ጌጥሮስም በቆርነሌዎስ ምክንያት አማነ ርኢኩ ከመ ኢያደሉ ለገጸ ሰብእ ዘእንበለ ዘፈርሆ ወገብረ ጽድቀ ። ኀሩይ ውእቱ በኀቤሁ ብሂል ።ሰውን በመልክ መንቀፍ ፍጡሩን ብቻ እንዳይደለ እግዚአብሔርን መስደብ እን ደሆነ በዚህ ይታወቃል ። የቄስ ሚስት አወቀች ቢሏት መጣፍ አጠበች እንዲሉ ያገራችን ደብተራ በውቀት ሠለጠነና ኢትኩን ዝሉፈ በአፋከ ያለውን ባይመለከት ተመቀኘሁ መስሎት እራሱንና አገሩን ሰደበ ። በጥቁር ጳጳስ እጅ አልባረክም የሚል ጋዜጣ አወጣ ። ኢትዮጵያ ስንኳን በገዛ አገሯ ሰው አፍ በሌላው አገር ሰው አፍ አትሰደብም ።ቋንቋዋ ግዕዝ ስምዋ አግዓዚት ትባላለች ።

በጥቁር ጳጳስ እጅ ካልተባረክ ሥጋውና ደሙን እንደምን እንቀበላለን ፤ ገብረየስ ወልደ መስቀል አሁንማ ያንተ አያያዝ የግብጹን ጳጳስ ከሥጋው ደሙ ልታበልጠው ይመስለኛል ። አንተማ ምን ታደርግ የበላ ሰው ብድሩን ሳይከፍል አይሞት ከናት ትሻል ሞግዚት ኢትዮጵያ እናትህን በምን ተክደች ይሆን ፤ ጥቁርማ ከተነቀፈ የሰው ሕይወቱ ነፋስ ነው እስመ ነፋስ ጸሊም በአርአያሁ ይላል ። ዓይናችን የሚያየው ጥቁሩ ነው ። እስኪ ጥቁሩን ዓይንህን በሐኪም አስወጣውና ነጩ ይይልህ ፤ እንዴሁ ይህን ያለ ሰው ከቤተ እግዚአብሔር አገልጋይ ነኝ ይላል ፤ በጥቁር ጳጳስ ያለ መባረክን ከመጽሐፍም አግኝቶ እንደሆነ ኢትዮጵያንም ስደብልኝ ያለው ሰው እንዳለ ከቤተ እግዚአብሔር ውስጥ ሁኖ ስድብ እንዳይገባ አቅርበውሊቀ ካህናቱ ቢጠይቁት ደግ ይመስለኛል ።

የውጭ አገር ሰዎች ስንኳን ሲያስተምሩ መጀመሪያ አገራችሁን ውደዱ እያሉ ነው ። ቅዱስ ጳውሎስም ያገሮቹ ሰዎች ዘመዶቹ ትምርቱን አንቀበልም አይወዱንም ቢሉት ያገሩን ስለ ዘመዶቹ ስለ እስራኤል ተክርስቶስ ብለይ እወዳለሁ አለ ። ጌታም በተወለደበት አገር በኢየሩሳሌም ዘመዶቹን እስራኤል አስተማረ እንጂ ከሰው አገር ሄደ ላስተምር አላለም ። ሐዋርያትም ጌታ ከሞተ በኋላ አንድ ሁነው መጀመሪያ ያገራቸውን ሰው አስተማሩ ። ያገራችሁን ሰው ስደቡ የሚል አላገኘም እንጂ ቢገኝ ብቻውን ከሚሆን ሁላችንም ባገዝነው ነበር ። ጉባኤ ማኅበር ተሰብስበ የምትሠሬው ሥራት ያልተማረው እንዲማር ያላመኑ ጋሎች ሽንቅሎች እንዲያምኑ ነበር ። በጥቁር ጽድቅ

ከተከለከለ ማን ያስተምሩ ። በማ ፳ ም በ፴፫ ቁ ። ኢ.ያ አምርኑ ከመ ይትለአክ ወልደ እጓለመ ሕያው ጻው ሮሜ ም ፲፬ ፳ ቁ ምንትኑ ዘትግዕዝ ቢጸክ ።

ንዋይ ዘገነተ ጽጌ ።

ፍርድ ማደላደል ።

ፍጡሕ ይጠብቅ፥ ወንጀለኛን ያውድቅ የብርሃንና ሰላም ፈጣሪ ልዑል ተፈሪ መኰንን ። የራቀውን በመድፍ የቀረበውን በሰይፍ የኢትዮጵያን ጠላቷን አርዶ ፈርዶ ይጣለው ።

እኔንም ለቀይ ለጥቁር አያሰኘኝ ለናቷቱ ለቸሪቱ ኢትዮጵያና ስለ ልጆቿ ፍቅር የቆማችሁ ጠበቃዎቿ ሁሉ ሁላችሁም አዋቆች ሆናችሁና ፍጆታ ከለከላችሁ ። ለፈራጅም አስቸገራችሁ ፤ መሲና ሳለች ክበድን ሲያርዱ ጠላት እያለ በወዳጅ ሲፈርዱ ከቶምን ያሳዝን፡፡አሁንስ አለማወቅን የመሰለ ዕውቀት ያለ አይመስለኝም ደብተራ ገብርየስ በነጭ እንጂ በጥቁር አንብረክም አለ፤ ወየው ጉድ እኔስ በሀገሬ ነጭና ጥቁር የሚመረጥ ከዕህልና ከልብስ ነው እንጂ ከሰው ነጭና ጥቁር ይመረጥለታል ሲሉ በየትም ከቶ አልሰማሁም ነበር።

(ምሳሌ) እንሆ ለንዋሳታችን መብራት ዓይን ነው ። ይሁን እንጂ ለዓይን መደቡ ነጭ ሲሆን አስተካክሎ የሚያይና ብርሃን የሚሰጠው ጥቁሩ አደለምን ጥቁሩ ዓይኔ አያይልኝም የሚል ቢኖር እንዳለው ይሁንለት ይደረግለት ፤ ይልቁንም ዓይኔን ግምባር ያርገው ብሎ የማለ ይመስላል ።

(ሁለተኛ) እንደተጻፈው ከራስህ ጠጕር አንዷን ነጩን ጥቁር ለማድረግ የሚችል ማነው አለ ። ጥቁር ከነጭ በታ ገብቶ የነጩን ማዕርግ እንዳይፈልግ አደለምን ። ነጭስ ከጥቁር በታ ገብቶ የጥቁርን ማዕርግ እንዳይመኝ አልነበረምን ለዩቱም ልዩ ልዩ ማዕርግ አላቸውና ይህ ምሳሌ ከየበታቸው እንዳይተላለፉና እንዳይበላለጡ ያሳያል ። ይህም ከሆነ አምላክ በዕድን ያስከትላል ። መጽሐፉን አይቶ ዓባይ ጠንቋይ ቡሐ በግ ነጭ በግ ። ቀይ ዶሮ ነጭ ዶሮ ገዝታችሁ አምጡና አድናችኋለሁ እንዲል እንዲሁም እኛ በነጭ መስቀል ካልተባረክን ጥቁር አይባርከንም ማለት ዓባይ ጠንቋይ መሆን ነው ።

ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ አለና በዛሬ ጊዜ መሆኑን ሊያስረዳ ። ወፈድፋደሰ በኀበ አዝማዲሁ ማለቱ ጥቁሩ ጥቁርውን ድሜ አይባርከኝም በማለቱ ያሳያል ።

የሀገር ፍቅር ። የወንድም ክብር የተሳለባቸው አቶ አስታጥቄ ወልደአማኔኤል ከመልክ ተክለ ሃይማኖት ውስጥ ትጠቃቀሳለህ ብለውታል ። አሁንም የተክለ ሃይማኖት መልክ ምስክር ይሁንና ጥቁር የነቀፈ እንደሆነ መርታትና መረታታችሁን በዚህ ታውቁታላችሁ ።

ይህ ደብተራ ገብርየስ የጻፈው ጋዜጣ ጕዳቱ ባንድ ወገን ብቻ አደለም በ፪ና በ፫ት በኩል ነው ብየ ነው እንጂ ለመቃወም የፈረድኹ አደለሁም ደግሞም የፍርድ ነገር ምኑ ይታወቃል ያንተው ነገር ይታያቸውና ብዙ ገልባጮች ወዳንተ ይፈርዱ ይሆናል አትዘንብኝ ፡፡

ነገር ቢያበዙት በአኅያ አይጫንምና ላሳጥርላችሁ ውርርድ፥ እንደ ገቡ ፤ ሙክትን እንዳሰቡ ነውና የሀገራቸውን ፍቅር ፤ የወንድሞቻቸውን ክብር የሚሹ በቀኝ የቆሙት እነ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ናቸው ፤ ደብተራ ገብርየስ የሀገርን ፍቅር የወንድምን ክብር ክደህ አስተክለሃልና እነሱ ይርቱ ስል በሚያነጣጥረው በጥቁር ዓይኔ የታየኝን በብርሃንና ሰላም ፈርጃለሁ ።

ቀዮ ንጉሤ

ሕዝቧ ጥሬ ሥጋ ስለሚበሉ ኢትዮጵያ በየዓመቱ የምትከፍለው ዕዳ ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ፫ ሚሊዮን ፭፻ ሺህ የሚሆኑ ክርስቲያኖች ናቸው ይባላል ። ክርስቲያኑ ሁሉ ጥሬ ሥጋ ይበላል፤ ሌላም ብዙህ ክርስቲያን ያልሆኑ ሕዝቦች በገራችን ጥሬ ሥጋ የሚበሉ አሉ ። በዚህ በ፫ ሚሊዮን፭፻ ሺ ሕዝብ ምክንያትና ስሕተት የሚመጣውን የአንድ ዓመት እዳ በጭሩ ላስረዳ እወዳለሁ ።ጥሬ ሥጋ የሚበላ ሰው ሁሉ ኰሶ ይጣባዋል ፤ ኰሶ የሚጣባውም ሰው ሁሉ በሁለት በሁለት ወር ኰሶ ይገዛል ፤ ኰሶም የተጣባው ሁሉ ኰሶ ይጠጣል ፤ ኰሶም የጠጣ ሰው ሁሉ አቤቱ አላንድ ስራ ሲንቀላበስ ይውላል ። ጥሬ ሥጋ የሚበላ ሰው በሁለት ወር ኰሶ እየተጣባው ኰሶ ይጠጣል፡(ማለት በዓመት ፮ ጊዜ ይጠጣል ።

ኰሶም ሻጭ በየገባያው ሁሉ ለሌላ ነገር መሥሪያ የሚሆነውን ጊዜ ኰሶ ለመሸጥ ሲአበላሸው ይውላል ። ኰሶ ለቃሚም ሌላ ሥራ የሚሠራበትን ጊዜ ኰሶ ለመልቀም ሲያጠፋ ይውላል የኰሶ ነጋዴም ሌላ ነገር የሚጭንበትን አጋሰስ ኰሶ ጭኖ እራሱም ጉልበትና ሰዓቱን ያጋሰሱንም ጉልበት በከንቱ ያጠፋል ። ይኸን በላይ የቆጠርሁትን ሁሉ እንደምን እዳ እንዲያመጣና እዳው እንዲታወቅ ለመግለጽ ትላቅ መጽሐፍ ያሻል ። ስለዚህ እኔ በጥቂቶቹ ነገሮች ባጭር ለማስረዳት እወዳለሁ ። መጀመሪያ ለኰሶ መግዣ የሚወጣ ገንዘብ ሂሳብ ፤ ሁለተኛ ኰሶ የጠጣ ሰው በዓመት በኰሶ መጠጣቱ ምክንያት የሚከስረው ከሳራ በሰዓቱ ታስቦ ፤ ሶስተኛ ኰሶ ሻጭ ኰሶ ሲሸጥ የሚያጠፋው ሰዓት በቀን የሚያገኘው ግምት ታስቦ ፤ አራተኛ ጠቅላላ ድምር ከዚህ ወዲያ በመላው አደጋውን መዳኛውን ይኸን የመሰለውን ነገር ለመግለጽ ነው ።

፩ኛ ፡ በአንድ መሐለቅ የሚገዛ ኰሶ ለሁለት ጊዜ መፈወሻ የሚበቃ ይሆናል ። ስለዜህ አንድ ሰው በዓመት ፮ጊዜ ስለሚጠጣ ፫መሐለቅ ለኰሶ መግዣ ያወጣል ። ግን የኢትዮጵያ ፫ሚሊዮን ፭፻ሺህ ክርስቲያን ሁሉ እንደዚሁ ጥሬ ሥጋ እየበሉ ኰሶ እየተጣባቸው ኰሶ ለመጠጣት ለኰሶ መግዣ እያንዳንዳቸው ፫፫መሐለቅ በየዓመቱ ያወጣሉ ።

ስለዚህ በዓመት ፫ሚሊዮን ፭፻ሺህ ሠራዊት የሚአጠፋው መሐለቅ ድምር ፲ሚሊዮን ፭፻ሺህ መሐለቅ ይሆናል ። ማለት ፫ጊዜ ፫ሚሊዮን ፭፻ሺህ ፲ ሚሊዮን ፭፻ሺህ ይሆናል ። በብር ቤት ለማወቅ ፲ሚሊዮን ፭፻ ሺህ በ፲፮ ሲከፈል ፮፻፶፮ ሺህ ፪፻፶ ብር ይሆናል ።

፪ተኛ።ኰሶ ጠጥቶ እቤቱ በመዋል ስለ ሰዓቱ መጥፋት የሚመጣ ከሳራ አንድ ሞያተኛ ቀኑን ሁሉ ሰርቶ ማታ የሞያተኝነቱን ፩መሃለቅ ከቀጣሪው ይቀበላል ። እንደዚሁም ኰሶ ስለጠጣ ሳይቀጠርና ሳይሰራ ቢውል ፩መሃለቅ መክሰሩ ነው እንደ

ዚሁም ሞያተኛ ብቻ አይደለም በዚህ ምክንያት የሚከስር ግን ሥራ ፈትቶ ተዋለ ግምቱ የሚአጠፋው ሰዓት ካራት መሃለቅ ያነሰ አይገመትም ። ለምሳሌ አንድ ወንበር (ዳኛ) ክሶ ጠዋቶ በዋለ ጊዜ የስንት ሰው ነገር ተዘግቶ እንዲውል ማሰብ ነው ። አንድ መኳንንት ክሶ በጠባ ጊዜ የስንት ያሽከሮች ነገር እንደ ዘገየና እንደታጐለ ማሰብ ነው ። ስለዚህ ያክሶ የጠባ ሰው ባ'ድ ቀን ክሶ መጠባቱ አራት መሃለቅ ሲከስር ጊዜ በዓመት ፮ ጊዜ ሲጠባ ጊዜ ያመቱ ከሳራ ፳፬ መሃለቅ ይሆናል ፤ (ማለት ፮ጊዜ ፬ መሐለቅ ፳፬ መሐለቅ ይሆናል) ። ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲህ የሚያደርጉት ፫ ሚሊዮን ፭፻ ሺህ ይሆናሉ ብለን ስለ ገመትን ፤ እነዚህ ሁሉ እያንዳንዳቸው እንደዚሁ ይከስራሉ ። ስለዚህ በዚህ ባንዱ ሰው ያመት ከሳራ ፫ሚሊዮን ፭፻ ሺሁን ስናበዛው ጠቅላላ ከሳራውን ይሰጠናል ። ማለት አንዱ ፳፬ ጊዜ ፫ ሚሊዮን ፭፻ ሺህ ፹፬ ሚሊዮን መሐለቅ ይሆናል ። በብር ቤት ሲታሰብ፡ ፹፬ ሚሊዮን መሐለቅ በ፲፮ ሲከፈል ፭ሚሊዮን ፪፻፶ ሺህ ብር ይሆናል ።

፫ተኛ ደግሞ ክሶ ሻጭ ክሶውን ሲሸጥ የሚአጠፋው ሰዓት ከሳራ ግምት ። በአራዳ ገበያ ቢጠፋ ቢጠፋ ፲ ክሶ ቸርቻሪ በየ ገበያው ቀን አይታጣም ። እስቲ የፊት ባራዳገበያ ብቻ ፲ክሶ ሻጭ የሚአጠፋውን የጊዜ ከሳራ እናስበው። በሻህ ውረድ ሀ ወ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

የከተማ ወሬ ።

ለነገር ከመቸኰልና ሰው ሆኖ በሰው ኀጢአት ከመፍረድ በራሴ አይድረስብኝ ብሎ ማዘን ይሻላል ።

ታህሣሥ ፳፩ ቀን ባላንባራስ ታደሰ እሚባል ሰው ከፍል ውሃ ባላይ ሴት ሌቦች በቅሎውን ሰርቀውት ኖሮ ደንግጦ ቢወጣ ከምድራሁ ላይ የዘበኛ መለዮ ወድቆ ቢአገኝ የተቻለውን ያህል በቅሎውን መፈለግ ትቶ በፍጥነት መለዮውን ይዞ ወደ አደባባይ ወጥቶ ለንግሥትና ለልዑል አልጋወራሽ ዘበኛው በቅሎ ሲሰርቅ መለዮውን አስጥዬ አመለጠኝ እያለ የዘበኞችን ስም ለማጥፋት በጉባኤ መሐከል ተናገረ።መንግሥትም ለከተማ ጥበቃ አምኖ ያቆመው ዘበኛ ስለሆነ ነገሩን አስመስሎ ስለተናገረ ይህን ጥፋት ያጠፋ ዘበኛ በቶሎ ተፈልጎ እንዲገኝ ወደዘበኛው አለቃ ትእዛዝ አለፈ ።

ከዚህ በኋላ ዳሞት የሚባል ዘበኛ የጐጃም ሰው ሰምቶ በኔ በአንድ ሰው ምክንያት ዘበኛው ሁሉ ለምን ይሰደባል መለዮውም የኔ ነው ብሎ ለአለቃው ቢነግር አብለህ ነው እስክት መረመር ታሰረህ ቆይ ተብሎ አንድ ወር ከታሰረ በኋላ እውነተኛው አምላክ ያንዱን ነገር ባንዱ ይገልጻልና ከልጅ ኃይለማርያም ገሠሠ ቤት ካሣና አየለ እሚባሉ ሌቦች የሱን ሙሉ ልብስና የወርቅ ሰዓት የባለቤቱን ነጭ ሐር ቀሚስና ሌላም ልብስ ሰርቀው በዘበኛ ተይዘው ከባሻ ደነቀ ላይ ቀርበው ሲመረመሩ እነዚሁ ሌቦች ገንዘቡን ካስቀመጡበት አምጥተው አስረከቡ።

ከዚህ በኋላ በተንኮል የተሰወረውን ነገር በእውነት ለመግለጥ ለእግዚአብሔር ልማዱ ነውና በአንድ ሴት በባልንጀራቸው ቀንተው በላቸው እሚባል ሌባ የኛ ጓደኛ አለ ከዚህ ቀደም ያዘበኛውን መለዮና ልብስ ሰርቆ ወዲያው በዘበኛ ለማስመሰል የባላንባራስ ታደሰን በቅሎ ሰርቆ ሸጧል ዘበኛ ስጡንና እናስይዘው ብለው በላቸውን አስይዘው ሲመረመር ነገሩን አስረዱን እንደምን ሰረቀ ቢሉአቸው ። አየለ እሚባለው ሌባ እውነቱን ልናገር ይህ በላቸው፡ በሌላ ጊዜ ጓደኛችን ነው እንጂ የዘበኛውን መለዮና ልብስ ከተኛበት ከራስጌው አንስቼ መለዮውን አርጌ ባልንጀሮቹ ከተኙበት ቤት ብገባ ዘበኛ መጣ ብለው ደንግጠው ተነሱ አይዞአችሁ እኔ ወንድማችሁ ነኝ ብዬ የልብሱን ሰለባ ጥየላቸው ወዲያው ከጐረቤት በቅሎ አይቼ ነበርና ኑና በቅሎዋን ሰርቀን በዘበኛ እንዲመከኝ መለዮውን ከዚያው ጥዬው መጣሁ ብሎ ተናገረ እነዚሁም ሌቦች ታሕሣሥ ፳፯ቀን ከልዑል አልጋ ወራሽ ችሎት ቀርበው ይህንኑ ጥፋታቸውን አምነው ከአደባባይ ተፈርዶባቸው ተቀጡ

የውጭ አገር ወሬ ፤

የመንግሥታት ማሕበር ያለፈው ዓመት ሥራ ፤

የመንግታት ማሕበር ከተጀመረ ዛሬ ሰባተኛ ዓመቱ ነውና በ፲፱፻፳፮ ዓ ም የተደረገውን ሥራ መለስ ብሎ መመልከት የተመቸ ጊዜ ነው።ባለፈው ዓመት ውስጥ በሉክርኖ ነገር የግሪክና ቡልጋርያ መከራከርና የሙሱል ነገር ማለቅ የበለጠ ነገር አልታየም ዋና ነገር የነበረም የጀርመን ወደ መንግሥታት ማሕበር መግባት ነው፡ስፓንያ ፖላንድ ብራዚል ጀርመን እንዳትገባ የከለከሉብትን የመጋቢት (ማርስ) ጉባኤ ሳይከናወን ቀርቶ በመስከረም (ሴብተምብር) ወር እንደገና ተነሥቶ ነበር በዚያን ጊዜ ጀርማንያ በምክርቤት ገብታ ነዋሪ መቀመጫ ተቀበለች ስፓንያና ብራዚል ከማሕበር ወጡ የምክር ቤት ደግሞ ከአራት ኑዋሪና ስድስት ኑዋሪ ያልሆኑ ማሕበርተኞች ኑሮ እስከ አምስት ኑዋሪና ዘጠኝ ኑዋሪ ያልሆኑ ማሕበርተኞች በማግኘቱ በዛ።

አሰናጂዎች ሽማግሌች ስለ የዓለም ገንዘብ ነገር እኰሆን የሚሆነውን ጉባኤ ሰበሰቡ ጉባኤውም በግንቦት (ሚያ) የሚውል ነው የምክር ቤት በፖላንድና ሊትዋንያ በግሪክና በቱርክ መካከል ገብቶ አስታራቂ ሆነ፡ ኢትዮጵያ እንግሊዝና ኢጣልያን በንግድ ጠቀሜታ ወረዳዎች ኢትዮጵያን ሊከፍልዋት ስለ ተዋዋሉ ተቃወሙች ። እንግሊዝና ኢጣልያን ደግሞ የፖሊቲክ ምኞት እንደ ሌላችው በግልጥ አስታወቁ፡አሰናጂዎች ሽማግሎች ደግሞ ዓመት ሙሉ ለዓለም ጉባኤ የሚሆን መንገድ ለማሰናዳት የጦር መሣሪ ለማሳነስ ሥሩ ፤ የምክር ቤት የጀርመን ያውስትርያ የሁንጋርያ የቡልጋርያ የጦር መሣሪያ መተውነገር ከኢንቴር አልያድ ሽማግሎች እጅ ወደ መንግሥታት ማሕበር ሽማግሎች እጅ እንዲያልፍ ምክር አበጀበት፡፯ኛው ጉባኤ የባርነትን ንግድ ለማስቀረትና ባርነትን ለመከልከል የግድ ሥራ ለመለከት ስለ ባርነት ውል አወጣ የማሕበሩ ስልጣን ለአውስትርያና ሁንጋሪያ ፍጻሜ አገኘለት ከቡልጋርያ ለሽሹ የብድር ነገርና የገንዘብ አቋቋም ነገር የተቀበለ ሆነዋል፡ከሌላ ነገሮች ጋራም ማኅበሩ በፔርስያ የአፕዩም (የሚያሰክር ተክል)ንግድና የፖፒ (የአፕዩም አይነት) መዝራት ለማስቀረት ተነጋገሩበት ስለ ልጅ ደኅንነት ሰፊ ፕሮግራም አበጁ ስለ ማጋዝ ስለ ፓስፖርት ስለ ቀረጥ ስለ ጤናም ሥራ ሥራውን ፈጸሙ ፡በሌሎች መንግሥታት ጥግ ስላደሩ አገሮችም ነገራቸውን መረመሩ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉሙሩክ ከየታጄሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ሥፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን ሞቶመቢል የፌታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዐይነቱ ፡ መጫሚያ በየዓይነቱ ፡ ወንበር በየዓይነቱ ፡ ብረት ሣጥን በየዓይ ነቱ ፡ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣል ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፩ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ከ፳ መሐለቅ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፱ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፹ ብር ።
የበሬ ቆዳ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ።
የበግ ቆዳ	፩ ከረጂ	፳ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጂ	፲፫ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ከረጂ	፻፴፫ ብር ።
፡፡ ባለሰይጣን ስእል ፡፡		፻፵፩ ብር ።
፡፡ ባለፈረስ ፡፡		፻፴፱ ብር ።
፡፡ ባለድመት ፡፡		፻፴፭ ብር ።
፡፡ ባለአህያ ፡፡		፻፳፯ ብር ።
፡፡ ባለሳቢ ግመል ፡፡		፻፳ ብር ።
፡፡ ባለአንበሳ ፡፡		፻፳፳ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፪ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር ።

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፭ ፳፭ ሣንቲም ነው ።
በአንድ ብር	፲፩ ሊሬ ፭ ፶ ።
በአንድ ጊኒ	፱ ብር ፺፪ ፺፭ ሳንቲም ነው
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፩ ብር ።

ቤርሊዮ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዮ አቶሞ ቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

ARMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ስንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ። የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሦስተኛ ዓመት ፡ ቁጥር ፯
3 me ANNÉE № 7

ሐሙስ የካቲት ፲ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 17 FEVRIER 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen , Héritier du trône d' Ethiopie , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christos Taklé Haymanot
Diréeteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ስፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የብርሃንና የሰላም አንባቢዎች ሆይ ።

እኔም እንደናንተ በአቡን ተክኛለሁና እስክንድርያ እናቴ በሉ እያሉ ካስተማሩን ቃል እስክንድርያ እናቴ በማለት ኢትዮጵያእናቴ በሉ ብለው አላስተማሩንምና ለሹመታቸው ማስከበር አድልዎ መሆኑንየሚአውቅ ሰው የለም ብለው የሚኑን ሽክም ተሸክመን እስከከሁን ቆይተናል ደብተራ ገብርየስም ይህን ሸክም ለመጣል ጭንቅ ሆነባቸውና ያመነ የተማረ ሰው የመንፈሳዊ ሹመት አይገባውም መስሎአቸው በጥቁር አልባረክም ብለው ጻፉ ምን አልባት እናታችው አትባረክ ብላ መከሩቸው እንደሁ ምን በደል አለ ከኢትዮጵያ ጳጳስ እንዳይሾም ሰለስቱ ምዕት ገዝተዋል እየተባለ ቢወራ እውነት መስሎኝ ተመራመርኩ ግዝት አለመኖረን እርግጡን አገኘሁት ወደፊት ስለ ጳጳስ ለሚአስፈልገው ጉዳይ ጉባኤ ይደረግ በሆነ በጉባኤው ማስረጃ ሊቃውንቱን ለመርዳት የተዘጋጀሁ ነኝ ። አዳኙ ኢትዮጵያን ሊአድን በመጣ ጊዜ የኢትዮጵያን ዱካ ይህ ነው ብሎ ያስረከበ ማነው በኢየሩሳሌም የነበረውን የኢትዮጵያን እርስት ያጠፋ ማነው ለዚህ ጥያቄዬ የልቤ ስር እስቲነክ የሚመልስልኝ የብርሃንና የሰላም ወዳጅ ነው ። ጉባኤ መፈለጉ የመንፈሳዊ ሹመት ከዓለማዊ ሹመት ጥቂት የተለየ መሆኑ ለማስረገጥ ነው ። ደግሞ የሰው ልጆች ግብፅና ኢትዮጵያ በስነ ፍጥረታቸው መበላለጥ የለባቸውምና በክርስትናቸውም አንድ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና የውጭ አገር ቄስ ቢሆን የኢትዮጵያም ቄስ ቢሆን የእግዚአብሔርን ስም ያስተምራል አሁን ግን በየሀገሩ የጳጳሱና የነገሥታቱ ኑሮ የተለየ ይመስላል ። በዚህ በኢትዮጵያ ግን የጳጳሱ ኑሮ እንደገዥ ነውና ለዚህ ሹመታቸው ከጃቸው እንዳይወጣ ይጥራሉ ፡ እኛ ግን እነሱ ካልተሾሙ የምንልበት ምክንያት ምን ይሆን፡ ስለ ነፃነታችን ልማድን መሻር የሚአስፈልግ መሆኑን ካወቅነ አቶ ልማድ ሳይዋረድ ሹልኽ ብሎ ከገራችን እንዲወጣ የግድ ሆነበት አሁን አቶ ልማድ እያዘነ እያለቀሰ ጕዞ ጀምሯልና ተዉት አታባብሉት ልማድን የተሸከማችሁ እስቲ ልማድን ከጫንቃችሁ አውርዱትና አስተውሉት የልማድ ሸክምነት ስንቅ አይሆንም የልማድን ቀንበር ወዲያ መስበር ነው እንጂ እንግዴህ ወዲህ አንድ ፊርም አያወጣ ልማድ የተናቀ ሆነ የብርሃንና የሰላም አንባቢዎች ደበደቡት ሰባብረው ጣሉት ይህንን ሰበራ እንግዴህ ማን ይሸከመዋል ከሰነፍ በቀር ።

ነጋድራስ ደስታ ምትኬ ።

የ፵፩ ገጽ ተከታይ ።

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

መጀመሪያ ሰው የተፈጠረ የምድር ጌታ ለመሆን ነበረ ነገር ግን በመጀመሪያ ጥቂት እራሱን ስለሆነ የሚበቃ መሣሪያ የለውምና የምድር ተገገር ሆነ ።

ሁለተኛ ።በኋላ ግን እውቀት ስላገኘ ተገዛ ተባበረም ።

ሶስተኛ ። በገዞ ከተባበረም ዘንድ ሥራውን ተከፋፍሎ የሠራውን ሥራ እንደ እየሥራው መጠን መለዋወጥ ጀመረ ዋጋ ማለት የሥራ መለኪያ ነው እንዳልነው ሁሉ ።

አራተኛ ። ሀብት ማለት የዓለም ጌትነት መልኪያ ነው ። ሰው ግን ምንስ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ለማግኘት ቢችል አንቀሳቅሶ ከማጋጠም በቀር ሌላ አቅም እንደሌለው የታወቀ ነገር ነው ። ሁሉንም የምትሰጥ መሬት ናት ። ማንቀሳቀስና ማጋጠም ግን የሚሆነው በሥራ ብቻ ነውና ሀብት ማለት የተከማቸ ሥራ ማለት ነው ።

አምስተኛ ። ማናቸውም የተሰራ ሥራ ከኋላ የሚከተለውን ሥራ ያቀላል ። ማናቸውንም ሀብት የበለጠ ሀብት ይከተለዋል ። በመጀመሪያ ግን ሥራ ሁሉ እጅግ ያስቸግራል ፡ ጅ

ማሬም የሌለው ሥራ ፍጻሜ አያገኝም ። ሀብትም ሳይጀመር
አያድግም ። ስለዚህም ጅማሬው ወዲያው ወዲያው ሲጠፋ አ
ንዳች ሥራ አይጠራቀምም ከዚህም ምክንያት የተነሳ እውቀት
በሌለው ሕዝብ ውስጥ በላተኛው ከሰራተኛው ይበዛልና አን
ዳችም የተሠራ ነገር አይከማችም እንደዚህም ያለው ሕዝብ
ከድህነት አይወጣም ።

ስድስተኛ ፤ የህዝብ ሀብት የሚሰፋው ሕዝቡ የሚያስፈል
ገውን ሁሉ ለመሥራት ሥራውን በብዙ ተከፍሎ የተለዋወጠ
እንደሆን ነው ። የሰሩትን ሥራ የሚለዋወጡ ሠራተኞች የተ
ራራቁ እንደሆነ ግን እስኪገናኙ ድረስ ብዙ ድካም በከንቱ
ይሄድባቸዋል ። የሚያገናኛቸውም ነጋዴ ከሆነ ከየድካማቸው ከ
ፍለው ይሰጡታል ። ስለዚህም የድካማቸውን ሙሉ ዋጋ አያ
ገኙም ። ከንቱ ድካም ሲበዛባቸው ልባቸው ይሰንፋል ። በዚህም
ምክንያት በገሩ ውስጥ የሚሠራ ሥራ ጥቂት ነውና ያገሩ ሀብት
አያድግም ። ይልቁንም ድኅነት እየሠፋና እየተጫነ ይሄዳል ።

ሰባተኛ ። ስለዚህም የድካማቸውን ፍሬ የሚላዋወጡ ሠራተ
ኞች እንዲቃረቡ መንግሥት መጣር ይገባዋል ። ይህም ማቃረ
ብ የሚሆነው በመንገድና በምድር ባቡር ነው ። ባንድ መንግ
ሥትም ውስጥ ካንድ አውራጃ ወደ አንደ አውራጃ የሚመላለስ
ዕቃ ሲቀረጥ ሰራተኞቹን እንደ ማራራቅ ያህል ነውና ሕዝብን
ም መንግሥትንም ይጐዳል ።

ስምንተኛ ። መንገድና የምድር ባቡርም ጥቅም የሚሆን
ው የሥራ ማሰልጠኛ የትምሕርት ቤቶች በየይነቱ ሲሠሩና
ማናቸውም ዕቃ ሁሉ እንደ ሚቻል መጠን ባገሩ ውስጥ እን
ዲበጅ መንግሥትም ሲጥርበት ነው ። በዚሁም ጥረቱ ዋና አ
ጋዥ የሚሆነው የተደላደለ የጉምሩክ ደምብ ነው ። በቀረጥ
የሚገባ ገንዘብ ቢበዛ ለመንግሥት ትልቅ ጥቅም አይሆነው
ም ። ዋና ጥቅሙ ያገሩ ገባር ሀብት ጥቅም ነው ።የሚያስፈ
ልገውን ነገር ሁሉ ከውጭ አገር የሚያመጣ ሕዝብ ግን ፍጹም
ድኃ ነው ። ገበያው እርቆበት ዕቃውን ለሚያመጣለት ነጋዴ
ዕቃው በውነት ከሚያወጣው ዋጋ ብዙ አብልጠ ይሰጣል ።

ዘጠኛ ፤በእንደዚህ ያለውም አገር ውስጥ የባላገሩ ጥቅም እ
ያነሠ ይሄዳልና ፤ መሬቱም ይረክሳል ። በጥቂቶችም ሰዎች እጅ
ይገባል ። መሬቱም በጥቂቶች ሰዎች እጅ የገባ ሕዝብ በጣም
ይደኸያል ። ሕዝቡ በየይነቱ ሥራ ባልሰለጠነም አገር ለባላገሩ
ቢያበድሩት ይጎዳዋል እንጂ አይጠቀመውም ።

አስረኛ ፤ የመንግሥት መሠረት እርሻ ነው ። ባለእርሻ
የሚያገኘው ጥቅም ሲያንስ የመንግሥት መሠረት አይጠናም ።
ባለእርሻ ሲጠቀም ግን መንግሥትም ይጠነክራልና ይበረታል ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት ነው ።

እግዚአብሔር ያበርህ ሊተ ያድኅነኒ ምንትኑ ያፈርሃኒ ።

ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ፍሩሃን የነ
በሩ ጥቡዓን ሆኑ ከብልየት ታደሱ በአእምሮ ጉለመሱ ፩ ቋንቋ
ያውቁ የነበሩ ብዙ ቋንቋ ተጨመረላቸው ያለፍርሃት ያለመጠ
ራጠት በተላኩበት ሁሉ ሥራቸውን ሠሩ ። አሁንም አእምሮን
ገንዘብ አድርገው ብርሃንና ሰላምን ቢቀበሉ በሚላኩበትና በሚ
ሾሙበት ሥራ ሁሉ ያለአንቀፋት ያለመሰናከል በመልካም ሥራ
ቸውን አሳምረው ታዛዦቻቸውን አስመስግነው የክብር ክብር
አግኝተው ከጌቶቻቸው ከሹመት እሹመት ይዘዋወራሉ ። አንዳ
ንዶች የተሾሙበትን ሥራ ትተው ያረጀ ተረትና ውዝግብ በየት
አለፈ እያሉ ሲፈላለጉ ሥራቸው እያነሰና እየጐደለ ይሄዳል
ምክትሉም ጥፋት ነው ። እግዚአብሔርን እንደሚያውቁ ይገለ
ጣሉ በሥራቸው ግን ይክዱታል እርሳቸውም የተጠሉ ያልታ
ዘዙም በመልካምም ሥራ ሁሉ ያልተፈተኑ ሁልጊዜም ይማራሉ
ወደ እውነትም እውቀት ለመምጣት ከቶ አይችሉም ብሎ ቅዱስ
ጳውሎስ የተናገረው እንዳይፈጸም አእምሮ ባ፲ ብርሃንና ሰላም
ባ፳ ሲሾመት ላመት ቀለብ እንዴት ያለ ስንፍና ነው በቀን
፪ ወይም ሺ ብር ገቢ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ሹምተው አለ
ማኖራቸው ። ብልሆች ታዛዦች ሹምተዋል አሉ ። ብርሃን ወሰ
ላምን አእምሮን ሊበሉ ። ጋዜታ ማንበብና መስማት የሚያስፈ
ልጋቸው ከኛ ይልቅ በላያችን ለተሾሙ ሹማምት ነበር ታዛዦቹ
አንባቢና ሰሚ ስንሆን አዛዦቹ ያላነበቡና ያልሰሙ እንዳይሆኑ
፲፭ ብር ማውጣት ጨክነውም ባይሆንላቸው መንግሥት በትእ
ዛዝ ግድ ይበላቸው በሕዝብ ላይ ተሹመው የሚያዙና የሚፈ
ርዱን በያደባሩቱም ላለቃ ላለቃው በጥቂር እጅ አልባረክም
ያለውን ስንኳን ያልሰሙ ይበዛሉ ይኸን ለሚመስለው ሁሉ ሊቃ
ውንት ሥርዓት ሊሠሩልን ደምብ ሊያቆሙልን አገባባቸው
ነውና ማንበብና መስማት ያስፈልጋቸዋል ። ይህም ትእዛዝ ላንድ
ጊዜ ብቻ ነው ጣዕሙን ከቀመሱት ፍሬውን ከበሉት ስንኳን
፲፭ ብር ብዙም ለመስጠት ቅርታ የላቸውም ። አሁን ግን
እኩሉ ስለፍርሃት እኩሉ ስለ እውቀት ይሁን እማኅበር ያልገ
ቡበትን ነገር አላወቅንም ። ጋዜታ ብሂል (ማለት) መስተዋት
በመስተዋት ክፉውንም በጎውንም እንደምናይ በጋዜታም በጎ
የሠራውንና ክፉ የሠራውን በሀገርና በሕዝብ እንደ ሥራው
መጠን ቢገለጽ ብዙ ጥቅም ይገኛል ወይሰ ለሰብአ በዘኢኮነ
ድልዎቱ ያለውን ይዘን አንዳንድ ወዳጆችንን ብናመሰግን ግን
ጥቅም ለማግኘታችን እስከ የለውም ። ብርሃን ወሰላምን አእ
ምሮን ሳያውቁ ። አይሾምም እንግዴህ በብሩ በወርቁ ። ወደቀ
ደመው እንመለስ ፤ አገረ ገዢዎች አገራቸው እንዲለማ ሕዝባ
ቸው እንዲሰለጥን እንደሚወዱ ጥርጥር የለበትም ብሎ ብርሃ
ንና ሰላም በማይታበል ቃሉ ስለ መሰከረላቸው እጅግ ግሩም
ነው ። እንግዴህ አገራቸው እንዲለማ ሕዝባቸው እንዲሰለጥን
ምን ማድረግ ይገባቸዋል ብሎ ወዳጆቹን ጠይቆ ነበረና ብዙ
ዎች የታያቸውንና የተሰማቸውን ጽፈዋል ። ከሁላቸው ትንሽ
የምሆን እኔ ግን ከገዦዎች ወገን አገራቸውንና ሕዝባቸውን
የሚወዱ ሐሳባቸውን በብርሃን ይገልጹልናል ብዬ ተስፋውን
ስጠብቅ ከገዦዎች አንዱ ብቻ መልካም ሐሳባቸውን ሲጽፉ
የቀሩት ስለሥራ ብዛትም እንደሆን እንጃ እስከሁን አልጻፉል
ንም ላገረ ገዦዎች ሁሉ ትእምርት (ምልክት) የሚሆኑንን መል
ካም ስምዋን በመሰወርዋ ሳዝን ጌታ የተናገረውን አሰብሁ አገር
በተራራ ላይ ተሠርታ መሰወር አይቻላትም የሚለውን ። ኤል
ሳዕ ለጊዜው ሊናገረው ያልወደደውን ። አምጽዑ ሊተ ሠናየ
ዘይዜምር ብሎ ፲ሩን ጣቶቹን ባ፲ሩ አውታረ በገና ላይ አድ

ርን ሲዘምርለት ከድምፁ ማማር የተነሣ መንፈስ ረድኤት አድሮበት ትንቢት እንደተናገረ እኔም የብርሃን ሰላም ምስክርነት ትልቅ ሁኖ ስለተሰማኝ ከገዦዎች አንዱ የጻፉት ቃል ስለተስማማኝ መንፈሳዊ ቅንዓት ስላደረብኝ እነሆ ምኞቴን እጽፋለሁ ።

ስለ ሕዝብ ማዘንና መራራት በእስራኤል ላይ የተሾመ ሙሴ እምትጠስዮሙስ ለእሉ ጠስየኒ እመጽሐፍ ዘጸሐፍከኒ ብሏል ሕዝቡ ለሙሴ አርሰው ቆፍረው ነግደው የወር ያመት ግብር አይሰጡትም ነበር ። የሱን ምክርና ተግሣፅ ከመጠበቅ በቀር ያንን ሁሉ ተአምራት ሲያደርግላቸው ማን ሾመህ አለቃ መኰንንስ አድርጎ እያሉ ሲከዱትም አልተበቀላቸውም ንጉሥ ዳዊትም ምንተ ገብሩ እሉ አባግዕ ሕዝብ እንዘ አነ ኖላዊሆሙ ዘአበስኩ ብሏል ። አላፊ ጠፊው ገንዘብ ቀርቶ ስለሕዝቡ እራሱን ማሳለፉን ያሳያል ። ይህ ሁሉ ሲሆን በዘመናቸው አልተመሰገኑም ነበር ። አሁንም ያባት ልጆች ነውና አገርና ሕዝብን መውደድ ከግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና ከልዑል ተፈሪ መኰንን ዘንድ ይገኛል ። ይኸንኑም በስንት ክፍል ለሀገር ሀብትና ልማት ለሕዝብ ጥቅምና በረከት የሚሆን ሥራ በማቆማቸው እንረዳለን ። ጌታችን መድኃኒታችን እኔ ጌታ መምሕር ስሆን እግራችሁን ካጸብሁ እላንተም ደግሞ ይገባችኋል የባልንጀራችሁን እግር ታጽቡ ዘንድ እርስ በርሳቸው ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና ብሏል ። ቅዱስ ጳውሎስ እኔን ምሰሉ እኔ ክርስቶስን እንደመሰልሁ ብሏል ። እንግዲህ አገረ ገዦዎች ይኸን ምሳሌ መርምረው የልዑል ተፈሪ መኰንንን ፍለጋ መከተል ያስፈልጋቸዋል ተመልከት ዓላማህን ተከተል አለቃህን ነውና በቆመው ሥራ ሁሉ መስሎ ይዞ መገኘት ነው ። ያላገር መግዛት መንዳት ያለሕዝብ መክበር መኩራት መታጀር መታየት ባለወርቅ ባለብር ባለሱቅ ባለመደብር መሆን አይገኝምና ሁሉን ባንድ ሰው ሐሳብ መወስንማ ከዓለመ ኢትዮጵያ ተከፋዮች አይደለንም ማለትን ያሳይባቸዋል ። የኢትዮጵያ ልማት የሁላችን ክብር ነው ጥፋቷም የሁላችን ሞት ነው ካሁን ያማረ ካሁን የተሻለ ጊዜ የለም በፍቅር አንድ ሁነን እናስብላት ለቅድስት ሀገራችን ። የመንግሥት ገንዘብ ሽማግሌዎች የሚጦሩበት ነዳያን የሚረዱበት ሕጻናት የሚማሩበት አገር የሚለማበት ሕዝብ የሚሰለጥንበት ሲሆን አገረ ገዦዎች ደግሞ በተሰጣቸው ሀብት ቢረዱ በያይነቱ ፋብሪካ ለማቆም ይቻላል መንግሥት ሁሉን ያቁም የሚሉ ከሆነማ ነጋድራስ በየግዛታቸው ሊሾምባቸው ግድ ይሆንባቸዋል ። መንግሥት ነጋድራስ ሹሞ ገቢ ገንዘብ ካገኘ ብዙ ፋብሪካ ለማቆም ይችላል ፤ ፋብሪካም ከቆመ አገር ይለማል ሕዝብ ይሰለጥናል ገንዘብም ይገኛል ።

አገረ ገዦዎች በተሾሙበት አገር የንግድ ሥራ መሥራት ባያስቡ መልካም ነው ። ቢያስቡ ግን ጉዳት ነው ሕዝቡ አርሶ ቆፍሮ ወጥቶ ወርዶ ተግቶ ነግዶ የሚገባቸውን ግብር ይሰጣልና ገንዘብ ከሀገርና ከሕዝብ ዘወትር ይገኛል ገዢዎች ደግሞ ለመፍቅዳቸው የሚበቃቸውን ይዘው የቀረውን ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠቅም ሥራ ቢሠሩበት አሁን እንደ ሥራቸው መጠን እና መሰግናቸዋለን ኋላም እግዚአብሔር ዋጋቸውን አያጠፋባቸውም ማቴ ፲ ፵፪ ። ያንድ አባት የኢየሱስ ክርስቶስ ልጆች እንደሆን እንዲሁም ያንዲት እናት የኢትዮጵያ ልጆች ነንና አንድ ልብ መክረ አንድ ቃል ተናጋሪ ሁነን አገራችንን ለማልማት ሕዝባችንን ለመርዳት መንግሥታችንን ለማጽናት ፈቃዱ የሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን እስከዚህ የማይባል ዕድሜ ኃይል ወጽንዕ ይስጥልን በቀኝ በግራ ቁመው በፊት በኋላ ሁነው በበጎ ምክር የሚያግዟቸውን ሊቃውንትና መኳንንትንም በድሜ ያስንብትልን መንፈሰ እግዚአብሔር ከነርሱ ጋራ ይሁን አሜን ።

ኢትዮጵያ ሆይ ስሚኝ ልንገርሺ ። ሁሉ ካንቺ ሲገኝ ባዕድ ለምንሺ ። እስካሁንስ ድረስ ያለውቀት ነበርሺ ። ያለፈውን ትተን ወደፊት ይብቃሺ ። ሊቃውንቱ ሁሉ በወንጌል ያዙሺ ። ከህናቱም አንድነት ከተነሱ ብሺ ። ዳኛው ተፈሪ ነው ማነው ጠበቃሺ ። በኃይለ ሥላሴ ራስ ያስችልሺ ። ዓይንሽ ተፈሪ ነው ዘውዲቱ ግርማሺ ። ከብዙ ምቀኞች የሚጠብቁሺ ፡ እውነተኛው ብርሃን ወጣቱ ልጅሺ ሰላምን ለማምጣት ሮም ሄደልሺ ። ከሮምም ገሥግሶ ሎንዶን ገባልሺ ። ብሔረ አግአዚት እናቱ የትነሺ ። የውጭ አገር ሰዎች የሚናፍቁሺ ። በብርሃን ተፈጥሮ ሰላም ነው መልክሺ ፡ ግርማዊት ዘውዲቱ ተፈሪ ተስፋሺ ፡ ለመንግሥታት ማኅበር አደራ ሰጡሺ ፡ ነጻነትን ወደሽ በጥበብ ጐልምሺ ። ቀምበሩም ቀላል ነው የሚያሸክሙሺ እንሸከማለን ኃያላኖችሺ ።

በዘውዲቱ መንግሥት ዛሬ ነው ሠርግሺ ። መርዓዊው ተፈሪ መርዓቱ አንቺ ነሺ ። ሁሉን ያከበረ አእምሮ ሙዜሺ ። ጠቢባኑን ጠራ እንዲቀበሉሺ ። ከሁሉ አስቀድሞ ቃል ኪዳን ካለሺ ። እንዳይሰጥ አምነናል አባት ፈጣሪሺ ። በማታውቁት ሥራ መሾም አይመራችሁ ፡ በየውቀቱ ቢሾም አሁን ለምናችሁ ። እንዳይወድቅ አጥብቀህ በጅህ ደግፈው ፡ ተፈሪ መኰንን አክሊል ያንተ ነው ።

አክሊሉ ደጀን ።

መልስ ።

ገብረ የስ ወልደ መስቀል ሆይ በጥቁር እጅ አንባረክም ብለህ ፳፰ ገጽ በብርሃንና ሰላም የጠቀስከውን መልክ ተክለ ሃይማኖት ባየሁት ጊዜ ብዙህ አደነቅሁ ምነው ውሂብሰ እምረኪብ ውእቱን ብቻ ነውን የተማርከው ከፍ ብሎ ተክለ ሃይማኖት ቄርሎስ ዘላፌ ረሲአን እለ አውጣኪ ። ባርከኒ አባ ለወልድከ ዝኬ ። እስመ ልማዱ ለመምሕር ቡራኬ ። ይልልህ ነበርና ነገር ግን የያዙትን ከወረወሩ ፈሪም አይባሉ እንዲሉ ሁሉ የተማርካትን ተናገርክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወላሞ ወርደው ሙተሎሜን ባሳመኑ ጊዜ የማረከውን ታቦት አግኝተው ሚ አግበር እግዚአ በእንተ ዝንቱ ታቦት ዘነበረ ውስተ ቤተ ርኩሳን ወበምንት እሰርዕ ሥጋከ ቅዱስ ወደመከ ክቡረ ይከውንኒሁ እቀድስ ዘተቀደሰ በእደ ጳጳስ አቡነ ሰላማ ። ብለው ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክቱ አፍቁርየ ተክለ ሃይማኖት አኮ አነ ፈኖኩከ ትሥዓር ጣዖተ ወትቀድስ ታቦተ ወትሢም ቀሳውስተ ወዲያቆናተ ወይእዜኒ ቀድስ ታቦተ ወኢትፍራህ ረሰይኩከ ብርሃነ ዓለም ከማየ ውስተ ዛቲ ብሔረ ጽልመት አከ ከመ ካልዓን ጳጳሳት ዘይሠይምዎሙ ሊቃነ ጳጳሳት ወለከሰ ሤምኩከ በአፈ ዚአየ ብሎ የሾማቸው አቡነ ተክለ ሃይማኖት አባታቸው እናታቸው ቡልጋ እቲሳ አይደሉምን ደግሞስ ብዙህ ጻድቃን ሰማዕታት ከኢትዮጵያ የተወለዱ ሞልተው የለምን እግ

ዚአብሔር ያከበራትን አገር ኢትዮጵያን ከነልጆቿ አንተ ለማዋ
ረድ እንደምን ደፈርከ አፉከ አብዝኃ ለእኪት ። ወልሳንከ
ጸፈረ ለሀብል ትነብር ወትሐምዮ ለእሁከ ። ወአንበርከ እቅፍተ
ለወልደ እምከ ። የተባልክ ገብረ የስ ወልደ መስቀል ዘመከነ
ሥላሴ ይኸንን ላይን የከፋ ላፍንጫ የከረፋ ነገር መጻፍሕን
ትተህ ተገኃስ እምእኩይ ወግበር ሠናየ ያለውን ጨምረህ
ሚም እግዚኦ አፃቤ ለአፉየ። ወማእፆ ዘአቅም ለከናፍርየ ። ኢት
ሚጦ ለልብየ ውስተ ነገር እኩይ ። ያለውን ብትመለከት ምን
ቸገረህ ነበር ከመጠምጠም መማር ይቀደም የሚሉ ነገር አለና
ፊት አንተን መማር ያስፈልግሀል በጥቁር እጅ አንበረክም ያል
ከውን ሰባኪነትሀን አንቀበልህም ፤ ይሁዳ ለሹመት ቢመረጥ ከክ
ቡርነት ውርደት ከሕይወት ሞት ይሻለኛል ብሎ መባ ተቀብሎ
ኢየሱስ ክርስቶስን አሰቅሎ ታንቆ ሞተ የተቀበለውንም መባ
አልበላው አንተም ባልቸገረህ ነገር መባ ተቀብለህ ኢትዮጵያን
ከነ ልጆቿን ሰድበሀልና የተቀበልከውን መባ ከደጀ ሰላም ጥለህ
የወንድምህን ርስት እንድትከፈል ያለጥርጥር ይገባሀል ። ከመ
ልከ ተክለ ሃይማኖትና ከገድላቸው መጥቀሴ ከቅዱሳት መጻሕ
ፍት አጥቼልህ አይደለም በቆጠርከው ውድ ፤ በጣልከው ውር
ርድ ተረታ ብዬ ነው ። ደብተረ ገብረ የስ ወልደ መስቀል
በገዛ ወንድሞቹ ይህን ያህል የስድብ ቃል ጽፎ በፈቃዱ ዕዳ
ገባ ።

ወልደ ሚካኤል ወልዱ ለኃይለ ሥላሴ ። ዘሀገረ ግሼ።

የ፴፯ ገጽ ተከታይ ።

ሕዝቧ ጥሬ ሥጋ ስለሚበሉ
ኢትዮጵያ በየዓመቱ የምትከፍለው ዕዳ ።

አንድ ቀን የዚህን ትል (ሹቦ) ነገር ለትምህርቱ ሳጠና ከሀ
ገራችን እርሻሽና አለ አንድ ነውር እየተወጋ መኖሩን ስላወቅሁ
አስተማሪዬ ፣ ሄጂ የዚህ ትል አደጋ በሰው ላይ ምን ያህል እን
ደሆነ እጠይቀው ዘንድ አሰብሁ ። ሄጄም እንዳሰብኩት ሁሉ ጠየ
ቅሁት ። እሱም እንዲህ ብሎ መለሰልኝ ። ሹቦ እንደ በግ ጉበት
ትል የሰው ሕይወት በጣም አይተናኮልም ስለ ሆነ አራብ ምታ
ታም እንቅልፋም ቢሉትው አይጠግቡ ሹቦ የበላነውን ስለ ሚለው
ፈዛዛ አበጭም አንድ አንድ ጊዜም እስከሞት የሚአደርስ በሽታ
ያመጣል። በግብጽና በሱዳን የበግጉበት በሽታ ሞልቷልና ፤ በሱዳ
ን ካለ በናንተም አገር ሳይኖር አይቀርም አለኝ እኔም ይኸን የጉበ
ት በሽታ ባነሳብኝ ጊዜ ሥጋ ቤቶች በግ ጠብተው ጉበቱን አውጥ
ተው መርምረው አይተው በሽተኛውን ሲጥሉ ደህነኛ የመሰላቸ
ውንም ሲያስቀምጡ አይ ነበረና ያ ትዝ አለኝ። ነገር ግን ለጊዜው
ሊአስረዳኝ እምሻው የሹጡን ነበረና የጉበቱን በሽታ ነገር ትተን
ስንነጋገር እንዲህ አለኝ ፤ የእንደዚህ ያሉ ፓራሳይት (በነፍሳት ላይ
ኖሮ በደሙ እየ ተመገበ የሚኖር ነፍሳት) ሕይወት ተተናኳዎችን
ነፍሳቶች የሚአመለክት መጽሐፍ አለና ፈልገህ አንብብ ምን
ያህል ጉዳት በሰው ሕይወትና በከብት ላይ እንዲያአመጣ ታገ
ኘዋለህ አለኝ እኔም እንደነገረኝ መጽሐፉን ፈልጌ አገኘሁት
ግን ለጊዜው መጽሐፉ በጣም ትልቅ ስለሆነ አንብቦ ለመጨ
ረስ ስለማያደርሰኝ ባጭር የሚአያስረዳውን ለቅሜ አውጥቼ እን
ደዚሁም ከትምሕርቱ መጽሐፍ ያገኘሁትን አጭር ማስረጃ ለመ
ተርጐምና ጥቂት እኔ የታሰበኝን እርዳታ ጨምሬ ለመግለጽ ወደ
ድሁ ።

፩ተኛ ጠቅላላ ድምር ።

ለኮሶ መግዣያ የሚወጣ በያመቱ በ፫ ሚሊዮን ፰፻ ሺህ ሠ
ራዊት ፯፻፶፯ ሺህ ፪፻፶ ብር ኮሶ ጠጭ በየ ፪ ወር የሚአጠፋው ሰዓ
ት ከሳራ የ፫ሚ፰፻ሺህ ሰራዊት ፰ሚ ፪፻፶ሺህ ብር ፪፻፲ ኮሶ ሻጮች
ባ ገት አገር የሚአከስሩት ስአት በማበከን ፲፰ሺህ ፯፻፶ ብር
ድምር የኢትዮጵያ ዕዳ በ፫ ነገር ብቻ የመጣ ስለ አንድ ዓመ
ት ፰ ሚ ፱፻ ፳፪ ሺህ ብር ሆነ ።

አይገርምምን ኢትዮጵያ በያመቱ ይኸን ያሃክል ዕዳ ጥሬ
ሥጋ መብላት ከተጀመረበት ዘመን (፴፻ ዓመት የሚሆን) እስከ
ዛሬ ከ፰ ሚሊዮን የበለጠ መሸከሟ አጥብቆ ለተመለከተው ሰው
ብዙህ ይደንቃል ።

ይኸስ ከብዙው ጥቂቱን ለማስረዳ ብዬ የገለጽኩት ነው
እስኪ ኮሶ ለታሚ ከሶውን ሲለቅም የሚአጠፋውን ሰዓትና
ጉልበት ኮሶ ጠጭም ከሶውን ሲገዛ የሚአጠፋውን ሰዓት የኮሶ
መጫኛው መሳሪያና አጋሰስ ከሳራ ኮሶ አላሚ የምታጠፋውን
ሰዓት ብናስበው የትእየለሌ በሆነ ። ትንሽ እንኳ ጥቅም በነበ
ረበት አያስቆጭም ነበረ ። ነገር ግን ጉልበት ይሰጣል አይባል
ወይ ገንዘብ ፤ ጌጥ ነው አይባል ወይ አመል ፤ ያወፍራል አይ
ባል የሚያከሳ በከንቱ ይኸን ያህል ዕዳ መሸከም ያሳዝናል ።

ያራዳ ገበያ ፯ ቀን በሳምንት ይውላል ፤ ፩ ኮሶ ሻጭ ኮሶ
መሸጡን ትቶ የሞያ ቢሠራ ለራሱም አራት መሐለቅ አግኝቶ
ለቀጠረውም ሰው ብዙን ጥቅም ያለው ሥራ ሰርቶለት ይውል
ነበረ ። ስለ ዚህ ላገሩ የሚጠቅም ሥራ ስላሊያዘ ከኮሶ ገጋ
እጅ ብቻ በዙኘ ስለ ሆነ ለራሱ ጥቅም የሚአደርገው ከከሳራ
ይቆጠራል ። የቀኑም ያገር ከሳራ በኮሶ ሻጭ ባንዱ ሰው ፬ መሐ
ለቅ ይገመታል ። በሳምንት ግን ስድስት ቀን ገበያ የሚውል
በት ከሳራው ፮ ጊዜ ፬ መሐለቅ ፳፬ መሐለቅ ይሆናል ። ያስሩ
ኮሶ ሻጭ ግን በሳምንት ፲ ጊዜ ፳፬ መሐለቅ ፪፻፵ መሐለቅ
ይሆናል ። በብር ቤት ፪፻፵ መሐለቅ ባ፲፪ ሲከፈል ፲፰ ብር ይሆ
ናል ። በዓመት ግን ፶፪ ሳምንት አለና ሁለቱን ሳምንት
ትተን በ፶ ሳምንት አስሩ ኮሶ ሻጮች የሚአጡት ፲፰ ጊዜ ፶
፯፻፶ ብር ይሆናል ። ግን በኢትዮጵያ ገበያ የሚቆመውና ኮሶ
የሚሸጥበት ባራዳ ብቻ አይደለምና ፤ በየወረዳው ሁሉ ያለውን
ገበያ ሁሉ ፳ አራዳን የሚሃክል እናድርገው ። በ፳ው በያንዳንዱ
ገበያ ፲፲ ኮሶ ሻጭ መሆኑን እንገምት ። ስለ ዚህ በ፳ው በያን
ዳንዱ ገበያ በመት ፲ሩ ኮሶ ሻጭ የሚአጠፉት ከሳራ ፯፻፶
ብር መሆኑ ነው ። ፯፻፶ በ፳ ሲባዛ ፲፭ሺህ ብር ይሆናል ። ያዲስ
አበባው ያስሩ ኮሶ ሻጭ ከሳራ ፯፻፶ ብር ሲደመር ፲፰ሺህ፯፻፶
ብር ይሆናል ።

ያገሬ ሰው ጠንቅቀህ አስብ ጠንቅቀህም ተመልከተህ ትዝ ይ
በልህ ከዚህ በላይ ለማስረዳ ያህል ጥሬ ሥጋ በመብላት ምክንያት
ኮሶ እየተጣባ ከዚህ አደጋ ለመዳን ስንጣጣር የሚጠፋውን ከሳራ
የኢትዮጵያን የያዓመት እዳ በተቻለኝ አሳይቻለሁ ።

ግን ደግሞ በኮሶ መጣጣት ምክንያት መጋኛ በሚባል አደ
ገኛ በሽታ የሚሞቱ ስንት እንደሆኑ ትዝ ይበልህ ደውያም የሆ
ኑ ስንት እንደሆኑ አስብ ፤ ቅስማቸው የተሰበረ ስንት እንደሆኑ

አስብ ፤ የሚአመጣውን እፍረትና ውርደት ስንት እንደሆነ አስብ ።

ደግሞም አንድ አንድ ሰዎች ጥሬ ሥጋ መብላት ጉልበት ይሰጣል ይሉ ይሆናል ፤ እርግጥ ነው ጥሬ ሥጋ የሚበላ ሰው ጉልበተኛ ሳይሆን አይቀርም ፡ ግን ከፋችን ደህና መግቢቱን መዋጣችንን ለጊዜውም ሆዳችን መሙላቱን ተመልክተን እንዲህ ብንል እርግጥ ነው ለማለት አይቻልም ። የማሽላ ጉድጓድ ማሽላ በተሞላ ጊዜ ክፍትነቱ ቀርቶ እንደዱሮው ድፍን ሆኖ ይኖራል ግን ማሽላ በላተኞቹ ሰዎቹ በመጡ ጊዜ እህሉን ዝቀው ባዶውን ትተውት ሲሄዱ ክፍቱን ይቀራል ፡ እንደዚሁም ሁሉ እኛ ስንበላው ለጊዜው ሆዳችን ሲጕሰር የጠገብን ይመስለናል ፤ ግን ጥቂት በላተኛው ሹተ በተካፈለን ጊዜ ሆዳችንና ሙላ አካላችን ወና ቀርቶ አመዳችን ይወጣል ።

ጉልበተኛ እንድንሆን ብለን መብላት ቢአምረን፡ እንድንጠግብ ብለን መብላት ቢአምረን ፡ ጤናችንን መጠበቅ ቢአምረን በጣም የተጠበሰ ሥጋ ፡ በጣም የደረቀ ቋንጣ፡ በጣም የተቀቀለ ሥጋ በጣም የደረቀ ዋጠላ መብላት ይሻላል ጉልበትም ሆኖ ጣሙም ጣፍጦ ከቈጠርነውም እጸና መከራ ሁሉ ያድነናል ። ስለምን ማለት ሹተ የሚያመጣው እርጥብ የበሬ ሥጋ ወይም ያሳማ ሥጋ መብላት ነውና የሚመጣው ከዚህ ስንርቅ ወደ ተሻለው አኗኗር እንቀርባለን ጉልበትና ክብደትም እንድናገኝ እናምናለን ።

መወቃቀስ

፩ኛ ፡ የመንግሥት ስራ ስራትና እርቅ ሕግም ክስራ በኋላ የተሰራውን ሕግ የተሰራውን ስራት በዘበኛ በወታደር ሕግና ስራቱ እንዳይናወጥ ማስጠበቅ ደካማውን ብርቱ እንዳይበድለው መመልከትና መጠበቅ በሕዝቡ ላይ የሚመጣን አደጋ ከውጭ አገርም ጦር ቢመጣ በሽታም ቢመጣ የሚድኑበትን የሚመክቱበትን የሚዋጉበትን መሳሪያ መሻት መዘጋጀት ነው እንግዲህ ባንድ ቲንሽ ነፍሳት ምክንያት ይኸን ያህል ሰው ጤናው ሲታወክ ዝም ይል መንግሥት ይኸን ያለ እዳ በኢትዮጵያ ላይ ሲወድቅበት ያልተመለከተ መንግሥት ያውም በቲንሽ ብልሃት የሚጠፋ ። እንደምን አድርጎ ከዚህ የበረታ አደጋ ይጠብቀናል ተብሎ ይታመናል ያለፈው አለፈ ለወደፊት ግን መንግሥታችን በጣም እንዲነቃበትና ተግቶ ብልሃት እንዲአደርግበት ተስፋ እናደርጋለን ።

፪ተኛ መምሕራንም የሕዝብን ጉዳትና ስሕተት መመልከት ስራቸው ነበረ ። ክፉን ለማስተው ደጉንም ለማስተማር ይገባቸው ነበረ ። ያገራችን መምሕራኖች አትስከሩ ፡ ሕዝብም እንዳይሰክሩ አስተምሩ ተብለው ቢላኩ እንኳን ለሕዝብ መልካም ሊአስተምሩ ለራሳቸው የሚበዙት ትዕግሥት አቀተዋል ።

ጥሬ ሥጋ እንኳን ዛሬ እውቀት በሰፋበት ዘመንና ገና በአሪት እንዳይበላ ተብሎ ሲከለከል ኖሯል ፤ ግን ካሕናቶቹ እራሳቸው እንጂ ሲበሉ አያፍሩም አይገርምምን ግሩም ይኸ ሥራ ደግ መልካምና ልክ ያለው አይደለም ።

አዋጅ ያስነገረ ሰው አዋጁን እራሱ ካላከበረ ሌላሰው ያከብርልኛል ማለት ከንቱ ውዳሴ ነው ። ካሕናትም ይኸን መስራት አይገባም እያሉ ለሕዝብ ቢአስተምሩ ፡ እራሳቸው ግን የከለከሉትን አውቀው ታልተከለከሉ ያስተማሩት ቃል ይፈጸማል ይከብራል ማለት ጥርጥር ነው ። ስለዚህ እንደ ወጉ መጀመሪያ ካሕናት ጥሬ ሥጋ መብላት እንዲከለክሉ ይገባቸዋል ፤ በዚህ ላይ ሕዝቡ በመላ ጠቅላላ ጉዳቱን ተመልክተው ሊተው ይገባቸዋል ። ደግሞም እንደዚሁ ወደ ፊት ፡ የተጻፈውን ተቀብይና አማኝ ከሆኑ ጉዳትና አደጋውን ተመልክተው ከዚህ የጤና ነገር የለምና ፡ በዚህ ነገር ነቅተው እራሳቸውም ታግሠው ፤ መሐይምኑንም መክረው አስተምረው ከሌላም አደጋ ከዚህ አደጋና እዳ እንዲ አሰግዱት ፡ እንዲአሥታግሡት ሙሉ ተስፋ እናደርጋለን ።

በሻህ ውረድ ሀ ወ

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

በአእምሮ ጋዜጣ ፻፴፰ ቁጥር ስለ ጳጳስ ነገር የተጻፈውን ቃል ሁሉን ለማተም በፍራ ቢጠብብን ከፍለን ከዚህ በታች ያለውን ቃል ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እና መለክታለን ።

ኢትዮጵያ በነጻ መንግሥቷ ላይ ነጻ ቤተ ክርስቲያን ትፈልጋለች ።

ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አዲሱ አለቃ ማን ይሆናል ።

ግብጾች የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ይህን ያህል ዘመን ሲገዙት የኖሩበትን ነገር እየቀጠልን እንመረምራለን ኢትዮጵያ ከቶ ከግብጽ አቡን ምንም ጥቅም አላገኘች ። አሌግዛንድሪያም ያሉት የግብጽ ሊቀ ጳጳሳት ለኢትዮጵያ ካህናት መሰልጠን ምንም አልተጠነቀቁ የኢትዮጵያንም ሕዝብ ለማስተማር በሚያስፈልገው ሥራ ምንም አልተጉ ።

በኢትዮጵያ ውስጥ የጳጳሳት መኖሯ ስፍራ የታለ፡ በየአገሩ ሁሉ ። የተሰሩት ቤተ ክርስቲያኖች የታሉ ። በያገሩ የቆሙ ተማሪ ቤቶች የታሉ ። መነኲሉስትን ቀሳውስት የሚማሩባቸው ዋና ዋና ገዳሞች የታሉ ።

የታተሙ የሃይማኖት መጻሕፍት የታሉ ። የቤተ ክርስቲያናት ቅዳሴ መጻሕፍት የታተሙ የታሉ ። ለድሆችና ለሽማግሌዎች አባት እናት ለሌላቸው ለተጐዱ ልጆች የሚሆኑ ሆፒታሎች የታሉ ። የቤተ ዘመድ እድገትና ክፍታ የታለ ። ለጉልማሳ ልጆችና ልጅ አገረዶች ጥንቃቄ የትአለ ። የጋብቻ መልካም ሥርአት የትአለ ። ሙታን የሚቀበሩበት መልካም የመቃብር ስፍራ ወዴት ነው ፤ ሕዝቡን ከፍ ለማድረግ ይህ ሁሉ ሥራቸው ነበረ ። ዳሩ ግን በአገሩ ውስጥ አቡኑ ሌላ አቡን እንዲሾም ሥልጣንና ፈቃድ የለውም ።

የአሌክሳንድርያ የግብፅ ጳጳሳት ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያኖች ታላቅ ቅዝቃዜ አለመጠንቀቅን ዝንጉነትን አሳይተው ሌሎች ሕዝቦች ሲያሻሽሉና ሲሰለጥኑ የኢትዮጵያን ሕዝብ በጨለማ ውስጥ ጣሉት ይልቁንም የጃፓን ሕዝብ እንኳ በ፶ዓመት ውስጥ ብቻ ሰልጥኖ በዓለም ውስጥ ታላቅ ንጉሠ ነገሥት ሆነ። የኢትዮጵያ አቡኖች ጳጳሳት ለመሾም ሳይችሉ ጊዜ ደጐቹን የተማሩትን ካህናት እንኳን ለመሾም አልተጠነቀቁም ግን ብልሀነታቸውን ሳይመረምሩ ለማንም ቅስና ይሰጡ ነበረ ። እናንተም አበላልጡት ።

ታላቁ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ለሀገሩ መሰልጠንና ለኢትዮጵያ ጉልማሳ ልጆች ትምሕርት ለማስተማር ስለ

ተጠነቀቁ አስተማሪዎቹ ግብጾች የተባሉበት መልካም የተማሪ ቤት አቆሙ ። በዋናዋ ከተማ ውስጥ ነዋሪዎች የዚህን የተማሪ ቤት ፍሬዎች አላዩም ።

ከጥቂት ጊዜ በፊት የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን አንድ ተማሪ ቤት አቆሙ ይህም ተማሪ ቤት በመምሕራኖቻቸው የተደነቁትን ወደ ኤሮፓ ወደ ምስር ወደ አሜሪካ ተማሪዎቹን ለመስደድ ማዘጋጀት ችሎት አድርጓል፡

የልዑል አልጋ ወራሽ ማተሚያ ቤት በጥቂት ጊዜ በኢትዮጵያ የግብጽ አቡኖች በዘመናት ሁሉ ያላተሙትን ብዙ የሃይማኖት መጻሕፍት አትሙዋል ። እዚህ ለአንድ አቡን አን ናገርም ። ነገር ግን ብዙኅ ዓመት የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ሲገዙ የኖሩትን የግብጾችን አቡኖች ሥራ ነው ። የመሰልጠንን መንፈሳዊ ብርሃን የክርስቲያንን ዓለም ሐሳብ የጐተተው የቤተ ክርስቲያን አለቃው ዋናው ከተማ አዲስ አበባ አይደለም። ስለ ምን ማለት ወደዚህ የሚላኩት አቡኖች የኦርቶዶክስ የካቶሊክ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያኖች እንዳሉዋቸው ያሉ የጂዎሎጅግ ሥራ በጣም የላቸውም ።

አንድ ጊዜ የግብጽ ሊቀ ጳጳሳት አቡን የሚሆን አንድ መነኰሴ እዚህ ላኩ ይህም የፈረንሳዊ ታሪክ ጸሐፊ ሞሬ በኢትዮጵያ በመልካሙ ታሪክ ላይ እንደ ጻፈው ቃል ነው ።

የምስር ግብጽ ሊቀ ጳጳሳት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አለመጠንቀቃቸው እንደዚህ ያለ ነው ። በንጉሥ ነገሥት ምኒልክ በመንግሥታቸውና በኢትዮጵያ ሊቃውንት ለኢትዮጵያ ጥቅም የሚሆነው ነገር ሁሉ የተደረገ ነው ።

እንዲሁም በግብጽና በኢትዮጵያ መካከል የሚያጋጥመውን ዝምድና ወዴት ይመሰርቱት ይሆን ። ከግብጽ ሊቀ ጳጳሳት ጋራ ያለው ዝምድና እንደ ክርስቲያኖች ሁሉ ሕግ በወዳጅነት እንዲኖር ጥርጥር የለውም ዳሩ ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለነሱ የበታች ተገዢ ሆና መኖር አይገባትምና ኢትዮጵያ በነጻ መንግሥቷ ላይ ነጻ ቤተ ክርስቲያን ትፈልጋለች ።

ለኢትዮጵያ ጠቀሜታ ይሆን ዘንድ ይህንን የትሁትነት ሐሳብ በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት ልናቀርበው ብርታት አለን ይልቁንም ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር አንድ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስም ለኢትዮጵያ ለተወደደችው አገራችን እድልና ሐብት ወደ ተሻለው አወሳሰን እንዲያበራላት እንመኛለን ።

ማስታወሻ ።

የኢትዮጵያን ጥቅምና ነጻነት ስንፈልግ ከሀገራችን ሊቃውንት ተመርጠ ሊቀ ጳጳሳት እዲሾሙልን ብለን ምንም ከማካሪዎች ቁጥር ባንገባ የታሰበንን በብርሃንና ሰላም ገልጸን ይኸንኑም አሳባችንን ዳግማዊ ምኒልክ እእምሮ ብለው ደሰየሙት የኢትዮጵያ መጀመሪያ ጋዜጣ በ፫ተኛ ዓመት ፻፴፰ ቁጥር ሕዝባችን ሁሉ እንዲረዳው አድርጎ አከናውኖ ገልጾታል ። ስለ ዚሁም ለአእምሮ ጥልቅ ምስጋና ይገባዋል ። ነገር ግን የምጣዱ ሳለ የንቅቡ ተንጣጣ እንደተባለው ምሳሌ በስም ብቻ ወንድማችን የተባለ ደብተራ ገበረየስ በጥቁር ጳጳስ እጅ አንባረክም ብሎ ቃሉን አሰምቶ በድፍረት ተናገረ ። ይህም የደብተራው ነገር የኢትዮጵያን ልጆች ልባችንን ከየሥፍራው አንቀሳቀሰው አገሩን ለማያውቀው አገር ለውጦ ነጻይቱን አገራችንን እጅግ አዋረዳት ። ሕዝቦቿን የሚያዋርድ ነጻነቷን የሚጐዳ የንጉሦቿን ክብር የሚነካ ጕስቋላ ነገሩ ሌትና ቀን በጆሯችን ይጮህብናል ። ማነው ይህን ነገር ሰምቶ ለመታገስ የሚችል? ።

ይህ ነገር ባማካሪዎች ቤት ብቻ ሳይፈጸም ትልቅ ጉባዔ እንዲደረግልንና ሕዝቡም ሁሉ እንዲመክርበት በማክበር እመለክታለሁ ። የጉባዔውም ቀን በጋዜጣ (በአዋጅ) ከተነገረ በኋላ በዚያው ቀን የኢትዮጵያን ክብሯንና ነጻነቷን እንጂ ጥቃቱን የማይወዱ የሀገርዋ ሊቃውንት በቀኝ ቁመው ዛሬ ላገራችን የሚያስፈልጋትንና የሚገባትን ነገር ሁሉ እንዲያደርጉላት አረጋግጣለሁ ። ሌላው ዋና ዋናው ነገር በጉባዔው ቀን ይሆናል ብዬ ነገሬን ቆጥቤ አሳጥራለሁ ።

አስታጥቄ ወልደ አማኑኤል ።

ስለ ህዝብ ቀምበር ።

በሐገር ውስጥ ፩ የጋማ ከብት ቢጠፋ ወይም ፩የቀንድ ከብት ቢታረድ ያ የጠፋበት ሰው ሄዶ ለዳኛ ጩኸቱን ያሰማል ዳኞቹም አፈርሳታ ይውጣልህ ይሉትና ፈቃድ ይሰጡታል በዚያም በፈርሳታ ምክንያት የሚወጡ ሰዎች በከተማ የሆነ እንደሆን ከ፳፫ አያንሱም ባገርቤቱ ግን ከ፪፻ ፥ከ፫፻ አያንሱም በዚሁም ምክንያት ከነዝያ አንዱ በነፋስና በፀሐይ በሺታ ገብቶት ቢሞት በጣም ጉዳት ነው ባይሞት እንኳን ያምስቱ መቶ ሰው መጉላላትና የሕፃናቱ መላቀስ በሚዛን ይገመት ቢሆን ያንድ ሰው ሞት ያህል ሳይወጣው አይቀርም ነበር ። ስለዚህም ሰብዕ ይከብር እምኵሉ ፍጥረት ያሰውን ላንድ እንስሳ ደም ያንድ ሰው ደም መለወጡ በጣም ያሳዝናል ነገር ግን መንግሥትንና ሕዝብን የሚነካ ሌላም ደዌም ነገር ታልሆነ በስተቀር ለማናቸውም ለየጥቂቱ ነገር ሕዝቡ እንዳይጉላላ አፈርሳታን የሚያህል የከበደ ቀምበር መንግሥት ተሕዝቡ ላይ ቢያቀልለት እጅግ መልካም ነበር ። ዳግም ሌብሻይ መቅረቱ ምስክርነቱ ባይበቃ ይመስለኛል ባፈርሳታም ውስጥ እንደዚሁ ብዙ የማታለል ሥራ ሞልቶበታል በሐገር ውስጥ አንድ አንድ ሰዎች የሰውን ገንዘብ አደራ ያስቀምጡና ወይንም መንግሥት የሰጣቸውን የደንብ መሣሪያቸውን ይሸጡ ይለውጡና ከቺግራቸው ያገቡታል ኋላ ግን እንደማይጠረጠሩ አስመስለው እንደዚህ ያለ ጠፋብን እያሉ ጩኸታቸውን ለዳኛ ያሰማሉ ብልጥ ዓይን አስቀድሞ ያለቅሳል እንደሚሉ ዳኛውም አፈር ሳታ ይውጣላችሁ ይላቸውና የፈቃድ ይሰጣቸዋል እነሱም እንግዲህ ቢወጣ ይወጣል ባይወጣ መንግሥት ያውቃል እያሉ ሕዝብን ያለ አገባብ እያጉላሉ መንግሥትን እያታለሉ የሚኖሩ አያሌ ሰዎች ሞልተዋል ይኸውም ይታወቅ ዘንድ በሐረር ከተማ ፪ ስፍራ በ፪ ሰዎች ተገልጸባቸዋል፤ በሌላውም አገር እንደዚሁ ሳይሆን አይቀርም ይኸንን የመሰለ ማታለያ ጕዳና በብዙ ማዕረግ ላይ ለተሾሙ ዳኞች ተግተው ለመመርመር ሳያስፈልጋቸው አይቀርም ።፪ኛ ። ስለ ጠንካራ ንፍገት ።

አንድ አንድ ሰዎች በዓለም ላይ ተቀምጠው መንፈሳዊንም ሥጋዊንም ሥራ ሳይሰሩ ጊዜ አቸውን በከንቱ የሚያሳልፉ ናቸው በሥራም ላይ ተቀምጠው ሆነ ብርሽም በንግድም ሆነ ያገኙት አያሌ ገንዘብ እያለ ክብረታችንን መንግሥትና ሕዝብ ያውቅብናል እያሉ የበቃ ቤት ሳይቀልሱ የበቃ ልብስ ሳይለብሱ በደሳሳ ቤት ተቀምጠው ባርኔ ዝተት ተጨብጠው እድሚአቸውን ይጨርሱታል ኋላም ጊዜ አቸው እንዳለቀ አጥንታቸው እንደ ደረቀ አውቀው ገንዘባቼውን ለልጆቻቸውም ሆነ ለወዳጃቸው ሳያሳዩት ለኑዛዜ የማያበቃ የድንገት ሞት ይዞአቸው ይሄዳል ገንዘባቸውንም በተቀበረበት ስፍራ ባክኖ ይቀራል እነዚሁም ሰዎች ይዘግቡ ወየኢያእምሩ ለዘ ያስተጋብዑ የተባለውን ቃል ለመፈጸም በጣም የተጉ ሆነዋል እንደዚህ ያሉ ፍጠረታት ሞቱ ተብሎ እንዳይታዘንላቸው በሕይወታቸውም ሳሉ ፈጽመው የሞቱ ናቸው ነገር ግን ገንዘባቸው ባመራማሪና በሰላይ የሚገኝ ቢሆን ለመንግሥትና ለህዝብም ጥቅም የሚሆን ብዙ ሥራ በረዳ ነበር ፡፡

ማንደፍሮ እርገጤ ።

ስለ ሕዳር በሽታ ።

በኤውሮጳ (ቲፉ) የሕዳር በሽታ ድሮ በ፲፱፻፲፩ ዓመተ ምሕረት በዓለም ገብቶ የነበረ ገብቷል ይባላል እንዴት ያለ መዓት የሆነ ክፉ በሽታ እንደነበረም ዓለሙ ሁሉ ያውቀዋል ። በአዲስ አበባም በዚያን ጊዜ ብዙ መኳንንትና ወይዛዝር ብዙ ወታደርና ነጋዴ አልቋል ። የሕዳር በሽታ የተባለበት ምክንያትም በኢትዮጵያ በሕዳር ወር ስለገባ ነው ።

እንዲህ ያለው በሽታ እንዳይደርስብን እንዲያርቅልን ወደ እግዚአብሔር መማለድ ያስፈልገናል ። በአዲስ አበባ ያሉ ሐኪሞችም ስለ ጤንነት የጥንቃቄ ምክር ለሕዝቡ ጽፈው እንዲገልጹለት በሽታው ሳይገባ በሽታውን የሚቃወም ነገር እንዲያሰናዱለትም ተስፋ እናደርጋለን ። ለሕዝብ ጤንነት የሚበጅ ምክር እየጻፉ ቢሰጡንም በደስታ እናትምላቸዋለን ።

ያገር ውስጥ ወሬ ።

ከኀሬ ከተማ በስልክ የመጣ ።

የእሳት አደጋ ፡፡

የካቲት ፮ ቀን የክቡር ራስናደው የበጅሮንዳቸው ፷ቤት ተቃጠለ ። ሁለተኛ የካቲት ፯ ቀን የመንግሥቱ አራዳ ፴፫ ቤት ተቃጠለ ። ሱቅም የነጋዴውም የባሻ ወርቄ ቤትም ተቃጠለ ።

ሶስተኛ በከተማው በስተ ምስራቅ ፹፬ ቤት ተቃጠለ ። መቃጠሉ ብቻ ነው የሚታየው እንጂ እሳቱ የሚነሣበት ቦታ አይታወቅም ። የካቲት ፱ ቀን ፲፱ ፻፲፱ ዓ ም ፤

ከማንቸስተር ጋርዲያን ጋዜጣ የተገለበጠ ።

ስለ ባሪያ ነገር በኢትዮጵያ ፡፡

በኢትዮጵያ በዋናዋ ከተማ ነጻ ለወጡ ባሮችና ፤ ለደሃ ልጆች የቆመውን ተማሪ ቤት የውጭ ጉዳይ ምኒስትር ቤት እንዲረዳ በሎንዶን ያለው የባርነት ተቃራኒ አቦሪሲስ ፕሮቴክሴን ማሕበር ፤ ከለመነውና ፤ በትጋት እሺ ብሎ ነገሩን ከተቀበለው ፤ በጥቂት ጊዜ ሆነ እየ ተባለ ይወራል ፤ ይኸም የሚገርም ወሬነው በሺ ፱፻ ፳፫ ዓ ም ኢትዮጵያ ወደ ዓለም ማሕበር ፤ እንድትገባ ፤ በሺ ፱፻ ፳፭ በኢትዮጵያ ካሉ ጣሊያኖች መካከል ስለ ውል ነገር በተደረገው ጉባዔ ክርክር በተነሳ ጊዜ ፤ ወደ ማሕበሩ ገብታ ከጕረቤቶቿ እንዳትስ ተካከል ። ለጊዜው አንፈቅድም ያሉበት፤ ዋናው ምክንያት ፤ ባሪያን በባርነት እስካሁን ድረስ ስለ ማሳደራቸው እንደሆነ ነገሩ አይሳተንም ፤ ነገሩም አይፈጸም እንጂ ፤ የዕውቀት ምንጭ በተሰጣቸው በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፡ እንደራሴነት ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ስለ ባሪያ ነጻነት መትጋቷን ፤ ለመከላከል የሚያስረዳውን ነገር ሁሉ ፡ ለጊዜው ማሕበሩ አልተቀበለም ነበር ። ነገር ግን ባሪያ ሁሉ ጭራሽ አርነት ካልወጣ ፤ ነጻ ለወጡ ባሮች ብቻ ተማሪ ቤት ማቆም እንደማይረባ አውቀው ፡ አሁን በቅርብ ጊዜ ያቆሙት ተማሪ ቤት በነገሩ ትጋታቸውና ፡ በፊትም እንደ ጣሩበት ፡ አሁንም እንደሚጥሩ ይመሰክራል ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽና እንደራሴ ፡ የሚከላከሉትን ፍጹ ሰው አያውቅላቸውም ። ባሪያን በባርነት ማሳደር በሌላም በስተ ምስራቅ በኩል ባሉ አገሮች እንደተለመደ በኢትዮጵያ ሲወርድ ሲዋረድ ከጥንት ተያይዞ የመጣ የቆየ ልማድ ነው ። ነገር ግን በቀን ብዛት ቀስ ቀስ ብሎ ይኸን ክፉ ልማድ ፤ መግሰስና መተው ይቻላል ። የዓለም መንግሥታት በዚህ ነገር ጉዞ መጀመር አለባቸው ። ነገሩንም ለማደስና ለማሻሻል የኢትዮጵያ መንግሥት ብዙ ስለ ለፋችበት ከሁከት ዳነች ልዑል አልጋ ወራሽን መደገፍና መጽናናት ስለሚገባ የሚያነቃቃ ጅማሬ ተይዟል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ፬ መሐ ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፰ብር ፲፪ መሐ ።
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፲፪ መሐለቅ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ፲፰ መሐ ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፹ ብር ።
የበሬ ቆዳ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ፫ ሩብ ።
የበግ ቆዳ	፩ ክረጃ	፰ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ክረጃ	፲፫ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር ፩ ክረጃ		፻፴፬ ብር ።
፡፡ ባለሰይጣን ስእል ፡፡		፻፵፩ ብር ።
፡፡ ባለፈረስ ፡፡		፻፴፫ ብር ።
፡፡ ባለድመት ፡፡		፻፴፭ ብር ፤
፡፡ ባለአህያ ፡፡		፻፳፫ ብር ።
፡፡ ባለሳቢ ግመል ፡፡		፻፰፬ ብር ።
፡፡ ባለአንበሳ ፡፡		፻፶ ብር።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፩ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር ።

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፭ እስከ ፲ ሣን ነው ።
በአንድ ብር	ሊሬ።
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ፫ እስከ ፯ ሳንቲም ነው
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉሙሩክ ከየታጁሮቹ ቤት፤ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ሥፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን ሞቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሄስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ፤በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዐይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

Berliet



ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ አቶሞ ቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚአን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

ARMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኔዲሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶክለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የኦዶክለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ ሙተከሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ስንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፰
3 me ANNÉE № 8

ሐሙስ የካቲት ፲፯ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 24 FEVRIER 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲረክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christos Taklé Haymanot
Diréсteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

በኢትዮጵያ ላይ ያልሆነ ወሬ ስለ ማውራት ።

በኢትዮጵያ ውስጥ እየዞሩ አገር ለማየት ከመጡት ያሜሪካን ሰዎች ጋዜጣ ጸሐፊው ስለ ኢትዮጵያ አኳኋን ከጻፈው ቃል በኮሬሬ ዴላ ሴራ በተባለ የኢጣልያን ጋዜጣ ተገልብጦ ስንመለከት ውነትነት የሌለው ብዙ የሐሰት ቃል ተጽፎ አገኘን ከርሱም በጥቂቱ እናመለክታለን ።

ባዲስ አበባ ጥቂቶች አውቶሞቢሎች አሉ ፡ የአውቶሞቢሎች ጌቶችም ከበርቴዎችና መኳንንቶች ናቸው ፡ ስለ ሆነ ግን በኢትዮጵያ እየተሰቀሉ መሞት የሚያዝ ፤ ፍትሐ ነገሥት ስለ አለ ፤ አንድ አውቶ ሞቢል ነጂ ሰው አስድጦ የገደለ እንደ ሆን ያለ ጥርጥር ታንቆ ይሞታልና አውቶሞቢል በኢትዮጵያ ምንም አይቀናውም ። ኢትዮጵያውያውንም መኪናውን እንደ ምትሐት ይፈሩታልና አውቶሞቢሉን መንዳት ለሱዳን ሰዎችና ለግብጽ ሰዎች ለቀዋል ይላል ።

ይህን ከዚህ በላይ የጻፈ ጋዜጠኛ የጻፈው ቃል ካምስት ላይ ተሳስቷል ።

፩ኛ ፡ ባዲስ አበባ ጥቂቶች አውቶሞቢሎች አሉ ያውቶሞቢሎች ጌቶችም ከበርቴዎችና መኳንንቶች ናቸው ላለው ባዲስ አበባ ብዙ አውቶሞቢሎች አሉ ያአውቶሞቢል ጌቶችም መኳንንቶችና ከበርቴዎች ብቻ አይደሉም ብዙ የሚያከራዩ ነጋዴዎችም አሉ ።

፪ኛ ፡ በኢትዮጵያ እየተሰቀሉ መሞት የሚያዝ ፍትሐ ነገሥት ስለ አለ ፡ አንድ አውቶሞቢል ነጂ ሰው አስድጦ የገደለ እንደሆን ያለ ጥርጥር ታንቆ ይሞታል ስላለው በኢትዮጵያ መንግሥት ነፍሰ ገዳይ ቅጣቱ ብርቱ ይሁን እንጂ እንኳን አውቶሞቢል ነጂ ሰው ቢያስድጥ ታንቆ ተሰቅሎ ይሞትና በልዩ ልዩ ምክንያትም ነፍስ የገደሉ ሰዎች መንግሥት የቆረጠላቸውን ልዩ ልዩ ቅጣት ይቀበላሉ እንጂ ታንቆ ተሰቅሎ መሞት የለም ።

፫ኛ ፤ አውቶሞቢል በኢትዮጵያ አይቀናውም ላለው አውቶሞቢል በኢትዮጵያ እያደረ እየበዛ መንገዱም እየተከከለ ፤ ሥራውም እየሰለጠነ ወደፊት እንደሚሄድ ብዙ ሰዎች ይመሰክራሉ ።

፬ኛ ፤ ኢትዮጵያውያን መኪናውን እንደምትሐት ይፈሩታል ላለውም የኢትዮጵያ ልጆች መኪናውን እንደምትሐት መፍራታቸው ይቅርና ባገኙት በማናቸውም መኪና ሁሉ ሥራውን በፍጥነት ለምደው አስተካክለው እንደሚሠሩ ጥርጥር የለበትም ።

፭ኛ ፤ አውቶሞቢሉንም መንዳት ለሱዳንና ለግብጽ ሰዎች ለቀዋል ላለው መኪና ሠራተኞች ኢትዮጵያውያን ይቅርና ስንት መኳንንትና የመኳንንት ልጆችና ወታደሮችም አውቶሞቢል የሚነዱ አሉ ፤ በቤተ መንግሥቱም ዋና ዋና የታወቁ አውቶሞቢል ነጂዎች የኢትዮጵያ ልጆች ናቸው እንጂ አንድ ነጂ የሱዳንና የግብጽ ሰው የለም ።

እንደዚህ ሁሉ አንድ አንድ የውጭ ሰዎች ስለ ኢትዮጵያ ሲጽፉ ባለማስተዋልና ባለመመርመር ያልሆነና ያልተደረገ ነገር ልብ ወለድ ይጽፋሉ ያላዩትንና ያልመረመሩትን ነገር አንስቶ መጻፍ የማይገባ ጸሐፊውን የሚያስነውር ፤ ጋዜጣውን የሚያስነቅፍ ነገር ነው ።

የ፶ ገጽ ተከታይ ።

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

፫ተኛ ክፍል ።

እስኪ የለውጥን አገባብ ምን እንደሆነ እንመለስና እንመርምር ። እነሆ ሰው ሁሉ ትልቁም ትንሹም ቢሆን ብርን ሲያ

ኛኛት ደስ ይለዋል ። ማናቸውም ሰው ጌታ መሆኑን ሊያስታውቅ ብርን ያከማቻል ። እኛም ጌትነቱን ስናደንቅለት እገሌ እከብር ሞልቶታል እያልን እናወራለን ። ድኃ የሆነ ሰው ደግሞ ያየን እንደሆነ እገሌ አንድም ብር የለው ወይም ደግሞ አንድም ትሙን የለውም እንላለን ። ደግሞ ሰው ሁሉ ባለውድካሙ ብርን ለማግኘት ይጥራል ። አንዱም በእውነተኛ መንገድ ፤ አንዱም በቅጥፈትና በሌብነት መንገድ ፤ አንዱም በንጹሕ ሥራ ፤ አንዱም በጉቦ ማለት እያንዳንዱ ሰው ብርን የሚፈልግበት መንገድ ምንስ ቢለያይ ሰው ሁሉ በዚያው በሚፈልግበት መንገድ ብዙም ብር ቢያገኝ በቃኝ አይልም ። የገንዘብ ፍቅር አድሮበታልና ብርን የሚጠላ ሰው የለም ። ሰውም ሁሉ ብር እንዳይበላ እንዳይቆረጠም ተበጥብጦም እንዳይጠጣ ተለብሰም እንዳይሞቅ እያወቀ ብዙ ድካም ደክሞ ያለውንም ዕቃ ሰጥቶ ብር ቢያገኝ እጅግ ደስ ይለዋል ። ሌላ ዋጋም አይፈልግም ። ከብር ግን ደግሞ ወርቅ ይወደዳል ። ዳሩ ግን ምክንያት የሌለው ነገር የለም ። ስለ ዜህም ደግሞ ብርና ወርቅን የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ይህነን ያህል የሚወድዋቸው ምክንያት ይኖረዋልና ይህ ምክንያት ምን እንደሆነ እንመርምር ።

ሰው የተፈጠረ የምድር ጌታ ሆኖ በዓለም ሊኖር ነበረ ። በመጀመሪያ ጥቂት ራሱን ስለ ነበረ ይህነን ጌትነት ለማግኘት የሚበቃ አቅም አላገኘም ። በኋላ ግን እየተባዛ መሬትንም አሸንፋለሁ ሲል ተባብሮ ሥራውንም ተከፋፍሎ በየባሕሪውሞያ ሞያውን ያዘ ። ሥራውን መከፋፈሉ ግን ከየሠራው ሥራ ከራሱ የተረፈውን እንዲለዋወጥ ነው ። ነገር ግን መሬትን ለመቆፈር ዶማ ፤ ዛፍንም ለ ‹ቁረጥ መጥረቢያ ፤ ወጥንም ለማብሰል ማናቸውንም አንድ ዓይነት ድስት እንዴሁም ለወጥ አንድ ዓይነት መሣሪያ እንዲያስፈልግ የግድ የታወቀ ነገር ነው ። የለውጥም መሣሪያ ባይኖር እያንዳንዱ ሰው የሠራውን ሥራ እስኪለዋወጥ ድረስ ብዙ ጊዜ ማናቸውም የሰው ሥራ ሁሉ አይፋጠንም ነበር ። ሰውም ከፍ ያለ የእውቀት ደረጃ አግኝቶ የምድር ጌታ ለመሆን አይችልም ነበር ፡

እነሆ በያንዳንዱ ቦታ ሁሉ ላይ ለያንዳንዱ ሰው የሚያስፈልግ ዕቃ ሁሉ አይገኝም ፤ እስቲ አሁን ለምሳሌ ባለ በርበሬና ባለጤፍ ባንድ መንደር ውስጥ አጠገብ ላጠገብ ከኖሩ ዘንድ ባለበርበሬው ጤፍን ሲፈልግ ባለጤፉ በርበሬ የፈለገ እንደሆነ የለውጥ መሣሪያ ባይኖር ያለችግር መለዋወጥ ይሆንላቸዋል ። ነገር ግን ባለበርበሬው ጤፍን ሲፈልግ ባለጤፉ የሚፈልገው አቡድዲድ እንደሆነ እነዚህ ሁለት ጐረቤቶች አንድ የሚያስማማቸው የለውጥ መሣሪያ ባይኖር ሊሰማሙ አይሆንላቸውም ። እንግዴህ የለውጥ መሣሪያ ባይኖር ባለበርበሬው አጠገቡ ያለውን ጤፍ እሸምታለሁ ሲል በርበሬውን ይዞ አቡጀዲድ የሚሸጠውን ሊፈልግ ይሄዳል ። ባለአቡጀዲዱንም ነጋዴ ካገኘ በኋላ ምናልባት ነጋዴው ደግሞ እንዴህ ይለው ይሆናል ። ወንድሜ ሆይ በከንቱ መድከምህ እጅግ ያሳዝነኛል ። የኔን አቡጀዲድ ከፈለግህ ዘንድ ለጨው ነውና እምሸጠው ጨው እንዳለህ አምጣና ውሰድ ይለው ይሆናል ።

እነሆ ያ ባለበርበሬውም ሰው ጨው የሚሸጠውን ነጋዴ ፈልጎ አግኝቶ ለውጠኝ ቢለው እንዲህ ብሎ ይመልስለት ይሆናል እኔ በርበሬ ሞልቶኛል አሁንስ የጐደለኝ የብረት ድስት ብቻ ነው ብረት ድስት እንዳለህ አምጣልኝና ጨው ልስጥህ ይለዋል ። ነገሩም ሁሉ እንደዚህ ባለበርበሬው ከጐረቤቱ ያለውን ጤፍ ለመሸመት ሲል መከራው ሊበዛበት ነበርና በመሀከል ሲዞር የፈለገውንም ሳያገኝ አለጊዜው ወይ ሞቶ ይቀር ነበረ ። ደግሞ የግድ ካልሆነበትም በቀር ሁለተኛ ማናቸውንም አንድ ዓይነት ሊለዋወጥ አይከጅልም ነበር ። ከመለዋወጡም የተነሣ እያንዳንዱ ሰው ለየብቻው እየሆነ ለኑሮው የሚያስፈልገውን ዕቃ ሁሉ ሊሠራ ነበረና ሰው ሁሉ አቅም አንሶት እስከ ዛሬ ድረስ የምድር ሎሌ ሆኖ ሊኖር ነበር ።

እነሆ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ነገር ከጥንት ጀምረው ተረድተውት የሚስማሙበትን አንድ ዓይነት የለውጥ መሣሪያ አውጥተው ሲገበያዩበት እንደ ነበሩ የዓለም ታሪክ ያስረዳናል ።

የዱሮ ዘመን ግሪኮች የለውጥ መሣሪያቸው ከብት ነበረ ከብትንም የለውጥ መሣሪያ ያደረጉት ካንድ ቦታ ወደአንዱ ቦታ ለማንቀሳቀስ የሚመችና ሰው ሁሉ የሚቀበለው ዕቃ ስለሆነ ነው ። እንግሊዞችም የዱሮ የለውጥ መሣሪያቸው ከብትና ባሪያ ነበረ ። የቀሩትም አንዳንዶቹ ሕዝቦች በአሣና በትንባሆ የሚያስፈልጋቸውን ዕቃ ሲገዙ ነበር ። በሀገራችንስ ቢሆን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ዋናው የለውጥ መሣሪያችን ጨው አልነበረምን ። ይህ የተጠራው የለውጥ መሣሪያ ሁሉ ግን የማይመች ሆኖ ነበር ። ከብትና ባሪያው ሲከሳ ወይም በበሽታ ሲሞት ትምባሆውና ዓሣውም ሲበላሽ ጨዉም ጥቂት ወሀ የነካው እንደሆነ ሲሟሟ ለመለወጥ ለየሰዉ ሁሉ እጅግ ጉዳት ነበረበት ። ይህንንም የኋላ ጉዳቱን እየፈራ ሰው ሁሉ በጣም ካልቸገረው በቀር ለውጥ ይሆነኛል ብሎ ደክሞ ያገኘውን ዕቃ ሰጥቶ ሊገዛቸው ፈቃድ አልነበረውም ብረትና መዳብም ከታወቁ በኋላ የተሻሉ የለውጥ መሣሪያዎች እንደሆኑ ታይተው ከላይ በተጠሩት የለውጥ መሣሪያዎች ፈንታ ገቡ ። ዳሩ ግን ብረትና መዳብም ቢሆኑ እየዛጉና እየተበላሹ እምቢ አሉ ወዲያውም ከመሬት ውስጥ የሚወጡበት ብልሀት ከታወቀ በኋላ እጅግ በረከቱ ። ያለ ብዙ ድካምም ይገኙ ጀመሩ በጣም ምም ረከሱ ። ከመርከሳቸውም የተነሣ ለያንዳንዱ ነገር መግዣ የሚያስፈልገው ብረት ወይም መዳብ ሸክሙ እየበዛና እየከበደ ካንዱ ቦታ ወደአንዱ ቦታ ለማንቀሳቀስ የማይመችና የማይቻል ሆነ ። ስለ ዜህም ለሸክም የማይከብዱ ካንዱም ቦታ ወደአንዱ ቦታ ያለብዙ ድካም የሚላኩ የማይዝጉና የማይበላሹ ሌሎች የለውጥ መሣሪያዎች ተገኙ ። በመላውም ዓለም አውቀው ተለመዱ እነሱም ብርና ወርቅ ናቸው የመላውም ዓለም ሕዝቦች ምንስ ተሰብስበው ተማክረው ባይዋዋሉ በዘመናት ብዛት ለምደዋቸው ብርና ወርቅ የለውጥ መሣሪያዎቻቸው እንዲሆኑ ተስማምተውባቸዋል ። ስለዚህም ብርና ወርቅ የተወደዱበት ዋናው ምክንያት የለውጥ መሣሪያዎች ስለ ሆኑ ነው ሰው ሁሉ ብርን ሲፈልግ ብርን እራሱን አይደለም ያንን በብር የሚለወጠውን ለኑሮው የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ሲፈልግ ነው እንጂ ብርና ወርቅን ሰው ሁሉ በዘመናት ብዛት የተስማማባቸው ምልክቶች ናቸው ።

እንሆ አንድ የበርኖስ ሰፊ ጤፍን ከተቀበለ በኋላ ላንዱ አራሽ አንድ ዓይነት ምልክት ሰጥቶ ይህንን ምልክት ይዘህ

ሄደህ ከሚስቴ በርኖስ ተቀበል ብሎ እንደሚፈቅድለት እንዲሁም እንዳች ነገር ተቀብሎ ብር የሚሰጥ ሰው ሁሉ ከፈቀድኸው ቦታ ሄደህ የፈለግኸውን ነገር ሉሉ በዚህ ምልክት ተቀበል ብሎ ብርን ለተቀበለ ሰው እንደ ፈቀደለት ያህል ነው ብርና ወርቅን እንደ ምልክት የያዘ ሰው የትም አገር ቢሄድ የፈለገውን ዕቃ ሁሉ ይለውጥበታል ።

ብርና ወርቅን ስለ ምልክት ተቀብሎ ስንት እንደ ሚሰጥ የተወሰነ ነውና ማንም ሰው ብርና ወርቅን ሲቀበል ደክሞ ካገኘው ዕቃ ስንት እንደሚሰጥ አይጠፋውም ። ብርና ወርቅ ምንስ የለውጥ መሣሪያ ቢሆኑ እንደ ሌላው ለኑሮ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ከመሬት የሚወጡት በድካም ነው ። ይልቁንም ብርና ወርቅን ለመቀበል የሚደከመው ድካም ከሌላው ድካም ሁሉ ይበልጣል ከዚህ ምክንያት የተነሣ ምልክት እንዲሆኑት ብርንና ወርቅን የፈለገ ሰው እንደ ተደከመበቸው መጠን የሠራውን ወይም ያለውን ዕቃ ይሰጥባቸዋል ። ዋጋ ማለት የሥራ መለኪያ ነውና ብርና ወርቅም ካንዱ እጅ ወደ አንዱ እጅ ሲያልፉ እንደ ተደከመባቸው መጠን ዋጋ እየተሰጠ ነው ። ስለዚህም ብርና ወርቅ እንደ ሌላው ምልክት ሁሉ የሚሳቱ ምልክቶች አይደሉም። እነዚህም ሁለቱ የለውጥ መሣሪያዎች ባይኖሩ ሰው ምድርን አሸንፎ ጌታዋ ለመሆን አይችልም ነበር ። መርከብ የምድር ባቡር ጋሪ ምንስ የተመሰገኑ የሕዝብ ማቃረቢያ መሣሪያዎች ቢሆኑ ምንም ፍጥነት ቢያበዙ እንደ ብርና እንደ ወርቅ አያቃርቡም ። ብርና ወርቅም አውራው የሚመሠገኑበት ምክንያት በብዙ ትንንሽ ክፍሎች እየተከፋፈሉ ሰው ከየሥራው ትንንሽ ክፍል በነሱ አማካይነት እንዲለዋወጥ ስለ አደረጉ ነው ። እስቲ አሁን ከገበያ ሂደን ባንድ ተሙን ዳብ ስንገዛ የስንት ሰዎች የድካማቸውን ትንንሽ ክፍል መግዛታችን ነው ።

ያንድ ተሙን ዳብ የሚጋገረው ከራሱ ከጐልጓዩ ከጮጁ ከወቂው ከሜኙ ከፈጫይቱ ምጣዱን ከሠራችው የሸህላ ሠሪ፤ እንጨት ለቃሚው ከብዙዎችም ሌሎች ሠራተኖች ብዙ ትንንሽ ድካም እየተከፈለ ተጠራቅሞ አይደለምን ። ባገራችን ብር ከታወቀ ብዙ ጊዜው ነው ። ነገር ግን እንደ ዛሬው አልተለመደም ነበር ። ዱሮ ከትልልቅ ለውጥ በቀር ትንንሽ ለውጥ እንዲለዋወጥ ሕዝብን የሚያስችል የለውጥ መሣሪያ አልነበረምና የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ባገሩ መልቶ ሳለ የኢትዮጵያ ሰው ሲቸገር ነበር ። ዱሮ ተሙን ሩብ አላድ ሳይለመድ ጐመን እገዛለሁ የሚል ሰው አልነበረም ። ባንድ በሙሉ ብር ገዝቶ እንዳያስቀምጠው አንድ ቀን ሳያድር እንዲበሰብስ እወቀው ከብርም በነሰ ነገር እንዳይገዛው ከብርያነሰ የለውጥ መሣሪያ አልነበረም። ስለዜህ የዚያን ጊዜ ጐመን ሊበላ የፈለገ ሰው ወይም ለምኖ ወይም ዘርቶ አብቅሎ ነው ። ያልለመነና ያልዘራ ሰው ግን ጐመን አግኝቶ ለመብላት አይሆንለትም ነበር ። እንዲሁም የዚያን ጊዜ ሰው ወደ መንገድ ሲሄድ ስንቁን ተሸክሞ ከቤቱ ካልተነሣ በቀር መከራውና ችጋሩ ይበዛበት ነበር ። ለብዙ ቀን የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ባንድ ጊዜ ካልሸመተ በቀር የዕለት ምግቡን የሚያገኝበት የለውጥ መሳሪያ አልነበረም ። ዛሬ ግን ለየጊዜው የሚበቃውን በተሙን እየገዛ ማንም ሰው ቢሆን መንገድ ሲወጣ አይቸገርም ። ባላገሩም ዱሮ ለማኙ መንገደኛ ሲበዛበት ሲመረር የነበረው ዛሬ ባጠገቡ የሚሄደው መንገደኛ ሲያንስ ያዝናል ። ተሙን ሩብ አላድ ከታወቁ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ እርስ በርሱ ይጠቃቀም ጀመር ። ነቃም ። ስለዜህም የለውጥ መሣሪያውን በትንንሽ ክፍሎች ከፍለው ትንንሾቹን ክፍሎች ባገራቸው ሕዝብ ውስጥ እንዲለመዱ ስላደረጉ ለአጼ ምኒልክ ትልቅ ምስጋና ይገባቸዋል ። እውነት ነው የዛሬው የለውጥ መሣሪያችን የተደላደለ መሠረት የለውምና ሕዝቡ ብዙ ይጐዳበታል ። የሚጐዳበትንም ምክንያት ቆይተን እናስረዳለን ፡ ስለሆነ ግን ጀማሪው አጼ ምኒልክ ናቸውና ለዜሁም ምክንያት ተብሎ ምንም ቢሆን ለርሳቸው የሚገባው ምስጋና አይቀርም

እነሆ ማናቸውም ሕዝብ ከፍ ወዳለው የእውቀት ደረጃ እንዲደርስና ሀብት እንዲያገኝ በውስጡ ያሉት የያይነቱ ዕቃ ሠራተኞች በቶሎ እየተገናኙ የተለዋወጡ እንደሆነ ነው ባገሩ ውስጥ ያለው የለውጥ መሣሪያ ከነሰ ዘንድ ግን የምድር ባቡርና መንገድ ምንስ ቢበዙ ትልቅ ጥቅም አይሆኑም ። የዚህ ዓለም ሕዝቦች የለውጥ መሣሪዮቻችው ብርና ወርቅ ብቻ ስለ ሆነ ብርና ወርቅ ያነሰበት ሕዝብ ከፍ ወዳለው የእውቀት ደረጃ ደርሶ ሀብታም ሊሆን አይችልም ። እነሆ ነገሩ እንዳልተገለጠልን ብርና ወርቅ ላንድ ሕዝብ ሀብትም የሚሆኑት የሚበሉና የሚቆረጠሙ ሆነው አይደለም ። ሕዝቡ የሠራውን ሥራ ሲለዋወጥ መሣሪያዎች ስለ ሆኑት ነው እንጂ ።

ይህነንም ከወቅን ዘንድ ባንድ አገር ውስጥ እነዚህ ፡ የለውጥ መሣሪያዎች በእንዴትያለ ምክንያት እንዲበዙ ፥ በእንዴትስ ያለ ምክንያት እንዲያንሱ እንመርምር ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት ነው ።

ሥራን ስለ ማከናወን ።

ባለፈው ዓመት ለኢትዮጵያ ልጆች የስልጣኔ ትምህርት ቤት በማህበር እንድናቆም በጆርናል አስታውሼ ነበረ ነገር ግን በሕዝብ ቸርነት ሊሰጥ ተስፋ የተደረገው ገንዘብ የትምህርት ቤት ለማቆም ያልበቃ ስለሆነ ገና ገንዘቡ እስቲበቃ ብለን በሙሉ ተስፋ እንጠብቃለን ግን ጊዜ አይቀመጥም እንደ ባቡር ይገሰግሳልና አሁንም እሱ እስቲሞላ ፩ ሐሳብ አሰብሁ። መቼም ያ ያል ነው የትምህርት ቤት ቢቆምም ለኢትዮጵያ ስልጣኔ ለማግባት አይቆጠርም ፪፻ ፫፻ ልጅ ቢማር በኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት መካከል በአባይ የገባ አሞሌ ይሆናል በአባይ ውሀ ውስጥ ከፍ ብሎ አሞሌ ጨው በጥብጦ በታች በኩል ቀምሶ አላጣፈጠውም ማለት ይሆናል ስለዚህ በኢትዮጵያ አውራጃ ሁሉ ሕዝብ ባመት በቤት ጢስ ቁጥር ፩፩ ሩብ ቢያወጣ ካንድ የሸለቃ አገር አርባ ሺህ ፬ ሺህ ጢስ ቢገኝ ፵፬ ሺህ ሩብ ይሆናል ይኸም ባመት አስር ወይም ፲፪ ሺህ ብር ይሆናልና በዚያው የሸለቃ ከተማ ፩ የስልጣኔ ትምርህት ቤት ያቆማል በነዚህም የትምህርት ቤቶች የያገሩ ልጆች ይማራሉ ካገራቸው ስለሆነ ለተማሮችም ምግብ አይታስብላቸውም ከቤታቸው እየበሉ ይማራሉ ይኸም የሚደረገው በሁሉም የኢትዮጵያ አውራጃ ነው በዚህ መንገድም በጥቂት ቀን ብዙ ሺህ ልጆች ይማራሉ የዚሁ ነገር ማስረጃ ለትምህርት ቤት ገንዘብ እንዲገኝ በመንግሥት ፈቃድ

የሄሬ ዓመት በጉምሩክ ቀረጥ ተደርጎ ነበረ ግን ባገሩ ሥራ እንደ ኤውሮፓ ኦርጋኒዜሽን ባለመኖሩ ገና ሥራው አልተጀመረም ተሀያ ዓመት ወዲህ በኢትዮጵያ ሁልጊዜ መልካም ሥራ ይታሰባል ይጀመራልም ግን ኦርጋኒዜሽን ባለ መኖሩ አይፈጸምም ። ከነዚሁም ሥራ በጥቂት ስም ስማቸውን እጽፉለሁ የአባይ ድልድይ ሊሠራ የሚሰራበት ብረት በብዙ ገንዘብ መጥቶ ሳይሠራ ቀረ የጥይት ፋብሪካ የቆዳ ፋብሪካ የካህናት የትምህርት ቤት የስልጣኔው የትምህርት ቤት ትልቁ ሆስፒታል ሌላም ይኸን የመሰለ ብዙ ነው ።

እንግዴህ ይኸን ስራ ያለስተካከሉት እገሌና እገሌ ናቸው ለማለት ለፈራጅ ያስቸግራል እንደምን ቢባል ለአገሩ ስራ ኦርጋንዜሽን ኑሮት በየስራው ላይ ለመጨረስ ሙሉ ስልጣን ። ለጥፋቱ ሐላፊነት የተቀበለ ሹም ስለሌለ ያልሰራው ማን ነው ይባላል ። ከዚህ የተነሣ ብዙ ጥቅም ይሆናል ተብሎ የታሰበው ስራ ሁሉ ገንዘብ ብቻ በማጥፋቱ ጉዳት ሆነ ። አንባቢዎች ሆይ ይኸ ሁሉ መልካም ስራ ለሌላ አገር ጥቅም የሚሆነው ለኛ ጉዳት ብቻ መሆኑ ከምን የተነሣ ይመስላችኋል? እኔ እንደማስበው መንግሥታችን የኤውሮፓን ስልጣኔ በዩኒቨርስቲ እንደሚገባ የተማሩ ሰራተኞች ስላላገኘ ነው በሌላ አገር በእንደዚህ ያለ ትልልቅ ስራ ላይ ዋና ድርክቴር የሚሆኑና በስራው ላይ ሐላፊነትና ስልጣን የሚቀበሉ ሰዎች በዩኒበርስቲ የስልጣኔ ትምህርት የተማሩ ሰዎች ናቸው ። ግን በኛ ሕዝብ ዘንድ መኪናና ሰራተኛ ከተገኘ ማንም የስልጣኔ ትምህርት ያልተማረ ሰው ድሬክተር ሆኖ እንዲያሰራው ይታሰባል ። ይኸ የሚቻል ተሆነ ይኸ ሁሉ ለምን ስራ ሆኖ ሳይቆም ቀረ ። የፍልውሃ ስራ እንኳ ብዙ ዓመት ሳይተካከል ቆይቶ አሁን በቅርብ ሐኪም ወርቅነህ ፩የተማሩ ሰው ተገኝተው ስራውን እንዲያስተካክሉ ቢታዘዙ በ፪ ዓመት ስራውን አሳምረውት አሁን ለመንግሥት ጥቅም ይገኝበታል ለወደፊትም ቢሆን የኤውሮፓን የስልጣኔን ስራ የስልጣኔ ትምህርት ያልተማርን ሰዎች ድሬክቴር ሆነን ለማሰራት የሥልጣኔ ሥራ ወይም በተውሶ ሰው ለመስራት ከባድ ነገር ነው ማንም የማይሸከመው ። እንግዴህ ይኸ ሁሉ ጉዳት የሚመጣው የስልጣኔ ትምህርት ከማጣት የተነሣ መሆኑ ኢየታወቀ መንግሥታችን ለስልጣኔ ትምህርት ወደ አውሮፓ የሚልካቸው ልጆች ፲ ፳ ልጆች መሆናቸው ፳ ፴ ልጆች በየትኛው ስራ ላይ እንዲቆሙ ነው ። ፳ ፴ ልጆች እንኳን ለመንግሥት ለ፩ትልቅ ኩፓኒያ ሥራስ መቸ ይበቃሉ ። ሲሆን እንደ ጃፓን መንግሥት በሺህ የሚቆጠሩ ልጆች ለመላክ ይገባን ነበረ ባይሆን ደግሞ ሁለት ሶስት መቶ ልጆች እንኳ ቢላኩ በቅርብ ቀን ተምረው ላገራችን ትንሽ ይረዱ ነበረ ። አሁን ፫ ፻ ልጆች ቢሄዱ ለመንግሥታችን ጉዳቱ ምንድርነው ባመት ፫፻ ሺ ብር ነው ለቀለባቸው የሚሰጥ ይኸም ፫ ፻ ሺህ ብር በድሬ ደዋና በአዲሳበባ ጉምሩክ በ ፩ ወር ቀረጥ የሚገኝ ነው ። በቀረም ለትምህርት ቤት የሚቀረጠው ገንዘብ በቂ ነው ። ይኸነንም ፫፻ ሺህ ብር አንድ ደሃ የራሱን ድህነት ገምቶ ብዙ እንደሆነ ቢያወራ መንግሥታችን እንዳይቀበል ሙሉ ተስፋ አለን ይኸ ግምት የተገመተው ለ፩ ሰው ጉልበት አይደለም በመንግሥት አቅም ነው የተገመተው ይኸነን ማለቴም የመንግሥትን ሥራ እንደ አንድ ሰው ቤት ሥራ አንዳንድ ሰው ግቢ በ፩ ስፍራ በጠባቡ በትንሹ ለመሥራት የሚያስቡ ሰዎች ምናልባት ይኖራሉ ብየ ነው ። እንደዚህ የሚያስቡ ሰዎች ቢኖሩ ሁሉንም በጠባቡ ማ፡ባቸው አይቀርም ይኸነን የሚያስቡ ሰዎች ግን ይኸ ሐሳብ በጓዛ አገራቸው ለኢትዮጵያ ምቀኛ መሆን እንደሆነ ተረድተው ይተውታል ብለን ተስፋ አለን ። ደግሞም በፊት እንደ ጻፍሁት ለስልጣኔ ትምህርት ከሌላው ሥራ የተለዩ አማካሮችና የስልጣኔን ትምህርት ሥራ ለማስኼድ ለሥራው ሙሉ ስልጣንና ሓላፊነት የተቀበለ ድሬክቴር በሥራው ላይ በተለየ እስቲቆሙ ይኸ ከዚህ በላይ የተጻፈው ሥራ ቢጀመር ገንዘብ ከማጥፋት በቀር እድግ ጥቅም አይገኝበትም ።

ደግሞም የኤውሮፓን የስልጣኔ ትምህርት ያልተማርን ሰዎች በዚህ በማናውቀው ባልተማርነው ሥራ ክብርና ሹመት የሚሆነን መስሎን ሥራውን ስጡን ብለን መንግሥታችንን ማስቸገርና ለሥራው እንቅፋት መሆንን ብንተወው ትልቅ አውቀትና ክብር ነው ። ቀድሞ ባገሩ የነበረው ሹመትና ልማድ አገር ማዛት እኛ ሥራውን የምናውቀው ሥራ ለክብርም ለሹመትም ቢሆን ብዙ ነው እሱ ይበቃናል ሁሉን ልውሰድ ባይ ሁሉን ያጣል የሚባል ተረት እንዳይደርስብን እናስብ ።

የማናውቀውን ሥራ ለምንን ወስደን ተሾመንበት ሥራው ቢበላሽ ይኸነን ሥራ እገሌ ነው ያጠፋው በእገሌ እጅ ተቀምጦ ሳይሠራ ይኸን ያህል ቀን ተቀመጠ መባል ክብር አይሆንም ውርደት ይሆናል እንጂ ይኸን ልናስተውል ይገባናል። ደግሞም ፩ ሰው ብዙ አይነት ሥራ ሹም ሁኜ ልሥራ ማለት በ ፩ በቅሎ ጀርባ የ ፫ በቅሎ ጭነት ልጫን ማለት እንደሆነ እናስተውልና ብዙ ሥራ መመኘትን እንተወው ። በቀረ ያለኦርጋኒዜሽንና ያለትምህርት በተፈጥሮ ባህርይ ብቻ እንሥራ ብለን ብናስብ አይቻልም የዛሬው ሥራ እንደ ቀድሞው አይደለም ሰፊ ነው የዛሬውን ሰፊ ሥራ በቀድሞው በጠባቡ ደንብ እንሥራ ማለት የዚህ ምሳሌ ቀድሞ ወርቅ የሚነግድ ነጋዴ በጊዜ ብዛት ነግዱ ቀንቶት ገንዘቡ ሲበረክት የዝሆን ቀንድና ሰም ለንግድ መግዛት ጀምሮ ግን ሚዛኔን ለውጬ ትልቅ ሚዛን አላበጅም በወርቁ ሚዛን የዝሆን ቀንድ እመዝናለሁ ማለት ይሆናልና ልብ እናድርገው ።

ፊታውራሪ ዴሬሳ ።

የ፶፫ ገጽ ተከታይ ።

ሕዝቧ ጥሬ ሥጋ ስለሚበሉ

ኢትዮጵያ በየዓመቱ የምትከፍለው ዕዳ ።

፫ተኛ ፡ በመጀመሪያ ቁጥር መንግሥት ይትጋባት ስላልን መንግሥት አለሕዝብ ኣይገኝም ፡ ስለዚህ ሕዝብ እራሱ እያንዳንዱ ከክፉ መራቅና በሌላም ክፉ እንዳይሠራ እራሱም እንዳይሰራበት ጠንቅቆ መመልከት ይገበዋል ። ሰው እራሱን መጠበቅ ከሚቻለው ነገር ተጠብቆ ካልዳነ ። ሌላ ሰው ከማልችለው ብርቱ አደጋ ጠብቆ ያድነኛል ማለት ከንቱ አሳብ ነው ። ስለዚህ መንግሥት ያልበረታበትን ነገርእና ደንብ ሊአጠነክር አይችልም

የመንግሥት አቋቋም በሕዝብ መካከል እንደዚህ ነው ፤ አንደኛው ሰው ለራሱ መልካም የሆነን ነገር ሁሉ ቢአገኝ ቢሰራ ሰውም ቢሰጠውና ቢሰራለት ይወዳል ። እንደዚሁም ሁለተኛው ሰው ለራሱ መልክም የሆነን ነገር ሁሉ ቢአገኝ ቢሰራ ሰውም ቢሰጠውና ቢሰራለት ይወዳል ። ግን ዘወትር ላንድ ሰው ደስ የሚአሰኝ ነገር ሁሉ አብሮ ኖዋሪውን ሁሉ ደስ አያሰኝ ምና ፤ የዚያ መጀመሪያው ሰው አንዱ ሥራው ለሁለተኛው ሰው የሚአስከፋ ሆኖ ይገኛል ፤ እንደዚሁም አንዱ የሁለተኛው ሰው ሥራ ለመጀመሪያው ሰው ስራ የሚአስከፋው ነገር ሆኖ ይገኛል ። በዚህ መካከል ክርክር ተነሳ በሁለቱ ሰዎች መካከል ። እነሱም ከመጣላትና ነፍስ ከማጥፋት እርቅ እናድርግ ብለው ውል ይዋዋላሉ ።

የመጀመሪያው ሰው ሁለተኛው ሰው የጠላውን ነገር እንዳይሰራ ቃል ገባ ። የሁለተኛውም ሰው የመጀመሪያው ሰው የጠላውን ነገር እንዳይሰራ ቃል ገባ ውላቸውንም ተዋዋሉ በዚህ ጊዜ ሁለቱም ሰዎች የሚወዱትን ነገር አንድ አንድ አጥተው ተወስነው ይኖሩ ጀመረ ።

በነዚህ በሁለቱ ሰዎች መካከል የተገኘ ውል ፤ ውላቸውን የሚአበረታ እርቃቸው የሚአደ ላድል ፤ በዳዩን የሚቀጣ ተበዳዩን የሚአስክስ ፤ ጉልበታሙ ደካማውን በግድ ብሎ ውሉን እንዳያፈርስበት የሚመለከት መንግሥት ይባላል ። ነገር ግን እነዚህ ሁለት ሰዎች ውላቸውን እሚመለከትና ተመልካች ባይኖራቸው ። ሁለቱም እንደ ልባቸው የወደዱትን ቁብ አጥተው ቢኖሩ ከእለታት አንድ ቀን ተጣልተው አጥፊና ጠፊ ሳይሆኑ አይቀሩም ። በዚያን ጊዜም መንግሥት የለም ይባላል ።

እንደዚሁም ሁሉ እኛ ሕዝቡ መጀመሪያ አጥፊ የሆነ ውን ነገር አውቀን ። እራሳችን የጠላነውን ነገር ትተን አሰማ ደን ሥራት ሰርተን መንግሥት በዚህ ነገር ይግባበት ይጠብቀ ንም እስክንል ድረስ ለሹማምነት ክልከላ መንግሥት የለም ።

መንግሥት የለም ማለታችን በኢትዮጵያ ሥራት ሁሉ ማለት አይደለም ፤ ግን በዚህ ባንዱ በምንናገረው ነገርና ፤ ከዚህ ባልተሰራ ነገር እንጂ ።

አሁን ለምሳሌ ባገራችን ሴትን በጀርባዋ የወሃ እን ስራ እንዳትሸከም የሚከለክላት ስራት የለም ። በብብቷም ታቅፋ ብትሸከም የሚከለክላት ወይም የሚፈቅድላት ሕግ የለም። ስለዚህ ለወኃ እንስራ አሸካከም መንግሥት የለምና እንደ ወደዱ መሸከም ይቻላል ። ግን ሕዝቡ ተስማምቶ በጀርባዋ ትሸከም እንጂ ለምን በሌላ ወገን ተብሎ ደንብ ቢደረግና በዘበኛ በወታደር እየተጠበቀ ሥራቱ ቢበረታ መንግሥት በዚህ ሥራት ወጥቷል ለማለት ይቻላል ።

የጥሬ ሥጋም አበላል አሁን እንደ መሰልነው ምሳሌ መን ግሥት ይብላም አይብላም ብሎ የሚአዝበት አደለምና መንግ ሥት መኖሩን ስለዚህ ነገር አናውቅም ።

ለወደፊቱ ግን ሕዝቡ ጉዳትና ጥቅሙን ተመልክተው መንግሥት በዚህ ነገር እንዲአወጡበት ተስፋ እንአደርጋለን በዚህ ጊዜ መንግሥት በዘበኛና በወታደሮቹ ሕዝቡንና እራሱን ከዚህ አደጋ ለመጠበቅ ይችል ይሆናል ።

ትርጒም ።

ቴይፕዋርም (የጥብጣብ የመሰለ ትል ወይም ሹጥ) የከረከረ አጥንት ባላቸው እውሬዎች ምግብ መዋሃጃ አካል ክፍል ውስጥ ይገኛል ። እንደወጉ እሰው አካል ውስጥ የሚገኘው ፈጽሞ የሚአስደንቅና የሚአሰጋ ነው (ማወቅ የሚአስፈልግ ነው ሁለት አይነቶች ትላልቆች በሰው ላይ የሚኖሩ ፖራሳይቶች በሕይወት ሳለ በላዩ እየተመገቡ የሚኖሩ ፤ አሉ ። አንደኛው በበሬ ሥጋ ውስጥ የሚገኝ ቴይፕዋርም አለመሳሪያ የሆነው ዓለም ያወቀው ። ሁለተኛው በአሳማ ሥጋ ውስጥ የሚገኝ ቴይ ፕዋርም ባለመሳሪያ ። በበሬ ሥጋ ውስጥ የሚገኘው በጣም ያልተቀቀለ ሥጋ በመብላት ከሰው ሆድ ውስጥ ይገባል ።

በአሳማ ሥጋ ውስጥ የሚገኘው በጣም ያልተቀቀለ ያሳማ ሥጋ በመብላት ከሰው ሆድ ይገባል ። በአሳማ ሥጋ ውስጥ የሚገኘው ብዙህ በጣም የሚአስፈራ ነው ፤ በበሬ ሥጋ ውስጥ የሚገኘው ባያለበት ይገኛል ቢሆንም ብዙህ አስቀያሚ ሆኖ ስለ አደጋው ግን እንደዚያኛው አያስፈራም ።

በበሬም ሥጋ ውስጥ የሚገኘው ቴፕዋርም የሕይወት ታሪክ ባጭሩ እንደ ሚከተለው ነው ። ይኸ ልጅ እግር ቴይፕ ዋርም እሰው አንጀት ውስጥ ይኖራል ፤ ብዙህ ጊዜ አንድ ቴይ ፕዋርም በአንድ ሰው ውስጥ ይገኛል ። ደግሞም ይኸ ብቻ አይ ደል በብዙ እስከ ፶፱ ድረስ መገኘቱ ተነግሮዋል ። ይኸ ትል ቲኒሽ እራስ አለው ቤተ ስፋቱ ሁለት ክንድ (ሜትር) እሺህ ተከፍሎ ከዚያ ክፍል ሁለቱን ያህል የምትሆን (፪ ሚሊ ሜትር ዳሜትር)አራት እንደ ዋግምት ደም የሚስብበት መም ጠጫ አለው ፤ ግን በራሱ ዙሪያ ሜንጦ የለውም ፤ (እንዳሳማ ቴይ ፕዋርም መጣበቂያ ያለ ሜንጦ የለውም) ከዚህ ከራሱ ቀጥሎ ሰልከክ እያለ እያደረ ከፍ ከፍ እያለ የወረደ አንገት አለው፤ ከዚያም እንደዚሁ ወደ ኋላው እስከጫፉ ድረስ ከፍ ከፍ እያለ ይሄዳል ። እመሃከል ቤት ሲደርስ አንድ ሳንቲም የሚሆን ስፋትና ሁለት ሳንቲም እስከ ሶስት ሳንቲም እርዝመት አለው። አንድ ትልቅ ትል ውስጥ ሺህ ወይም የሚበልጥ የሚሆን አን ጓዎች አሉ ። ድምር እርዝመቱ ፲፫ ክንድ እስከ ፳፬ ክንድ ይበ ልጣል ። የያንዳንዳቸው አንጓ ባሕርዩ ተፈጥሮ ፍጹም ወንዳገ ረድ ነው (ሴትና ወንድ ነው) በየጊዜው እየተቀጣጠሉ እየተቆ ረጡ አንድ ባንድ ወይም ሁለት በሁለት ከዓይነ ምድር ጋራ አልፈው በመቀመጫ ወደውጭ ይወጣሉ ። (ስዕሉን እይ)

ባመት አንዱ ትል (ቴይፕዋርም የሚቀፈቅፈው ቢታሰብ ፲፯ ሚሊዮን እንቁላል ሆነ ። ይኸ ሁሉ አንድጋ ከነዋነኛው ጋራ ወጥቶ ምናልባት የቀንድ ከብት ከሳር ጋራ እበላው ወይም ከወሃ ጋራ ጠጥቶት እበላው ምግብ መስማምያ አካል ክፍል ይገባ ይሆናል ፤ ይኸ እንቁላል ገና በአንጓ ሳለ ይበስልና (ጠንቶ) አድጎ ትኒኒሽ ሽል ይሆናል ፤ ይህ ሽል በቀንድ ከብት የተበላ እንደሆነ አንጀቱ ውስጥ ሲገባ የተሸፈነበት መጠቅለያ ይፈነዳል ባንጀቱ ገበርም ውስጥም ሰርስሮ ገብቶ የፊኛ ቅርጽ ያለው ትል መስሎ (የፊኛ ትል) በጡንቻ ነብሮ ይልቁንም እምላስና አመንዣጌ ጡንቻ ውስጥ ይሰፍራል (ይታቀፋል ይቀፈቅፋል) ይኸም ጡንቻ ተነቅፍቅፉ እንደገና በቅጡ ሳይቀቀል ሰው የበላው እንደሆነ ሥጋው ፈጽሞ ሲዋሐድ ፤ ቅፍቅፉ አንጀት ውስጥ

አድጎ ልጅ እግር ትል ሆኖ አዲሱ መከረኛ ሰው ውስጥ ይኖራል ።

ጥብጣብ የሚመስለው ትል (ቴኒያ ወይም ሹጥ)በሴቶች ይበዛል ፡ ይልቁንም ከሀያ ዓመት እስከ አርባ ዓመት በሆናቸው። ይኸም ትል ምናልባት በመልካም መድኃኒት ካልተፈወሱት ብዙህ ዓመት ይኖራል ። በርግጥ ጥሬ ሥጋ ወይም በጣም ያል ተቀቀለ ሥጋ ካልተበላ ሊተናኮል አይችልም ።(ስዕሉን እይ)

ይኸን ቅፍቅፍ ይፈጀዋል ብለው ስላሰቡ በለሥጉያዎቹ ሥጋውን ሁሉ በብድር ሳጥን ማስቀመጫ እስከ ሶስት ሳምንት ድረስ ስለሚአስቀምጡት የሚበዛው መተናኰል የሚመጣው በየቤቱ ከስጉያ ውጭ ከሚታረድ ከብት ሥጋ ነው ። ጨው በብዙ ነስንሶ ማስቀመጥም እንደዚሁ ይኸን ቅፍቅፍ ይፈጀዋል።

ከሳማ ሥጋ የሚገኘውም ትል የሕይወት ታሪክ ልክ እንደ በሬው ሥጋ ትል ነው ። ብቻ የሚተላለፍበት ከብት የቀንድ ከብት መሆኑ ቀርቶ በአሳማ ሥጋ ነው ወደሰው የሚተላለፈው ። እራሱ ቲኒሽ የመርፌ እራስ የምታህል ሜንጦ በዙሪያው ያለው ነው ። ስለዚህ ባለመሳሪያ ትል ተብሎ ተጠርቶዋል ። የዚህ የባ ለመሳሪያ ትል ቅፍቅፍ እብርድ ሳጥን ውስጥ በማስቀመጥ አይሞ ትም እንደ ባዶ እጁ ትል ስለዚህ ጥሬ የአሳማ ሥጋ መብላት ብዙህ አደጋ አለበት ። ይልቁንም ከዚህ የሚብስ ሌላ መከራ እዚህ ያልተጻፈ ያመጣል ።

የአሳማ ትል እጋ (ሀይዳቲደስ) የሚባል ፊኛ የሚመስል ከረጢት አብጅቶ እስከ ሞት ድረስ ስለሚአደርስና እሰው አካ ላት ውስጥ ስለመቀፍቀፉ ምቾት ብዙህ ማሚአስፈሩ ፓራሳይት (በሕይወት ባለ ሰው ላይ ተቀላቢ) አደገኛ ነው ።

በሹጥ የሚነሳ በሽታ ።

፩ መቆሸብና መጨፍገግ ።
፪ ደመ መጣጥነጥ ።
፫ ያንጀት በሽታ ።
፬ የሳምባ በሽታ ከናላ በመጀመር ።
፭ እራስ ማዞር ።
፮ በድንገት መዛልና መድከም ።
፯ ማስታወክና ቅልሽልሽታ ።
፰ የአንጐል ስር መናወጥ (ዕውቀት ማናወጥ) ።
፱ ማለስለስ ማላላት ።
፲ በድንገት መበደን ።
፲፩ አእምሮ ማጣት ከትንፋሽ ማጠር ጋራ ።
፲፪ ባሪያ መጣል ።
፲፫ እበጭ ወሽ ።
፲፬ ግርጣትና ንጣት ። በዚህ ላይ ሌላም ብዙህ በሽታ ያመጣል ።

ስዕልና ገበታ ስለ ጥቂት ማስረጃ ።

የሹጥን አስተዳደግና ብልት ማመልከቻ ስዕል ።



ሹጥ





፩ ፡ እንቁላል ከሽል ጋራ ።
፪ ፡ሽል ።
፫ ፡ የስራ ቀርጽ ሊአበጅ የጀመረ ሽል ።
፬ የፊኛ ትል ወይም እቅፍ ቅፍ ራሱን እንዳቀረቀረ ።
፭ ፡ ራሱን እንደዘረጋ ።

የጥቂቶች ሹጦች ሕይወት ታሪክ ገበታ ።

የትል ወይም የሹጥ ስም በየዓይነቱ	ለጥቂት ጊዜ የሚኖርባቸው አውሬዎች ስም	የመጨረሻ ሕይወቱ የሚያልፍባቸው ያውሬዎች ስም።
፩ ፡ ቲኒያ ሳጂራታ የሚባል በበሬ ሥጋ ውስጥ የሚገኝ ።	በሬ ። ቀጭኔ ፡ (እጡንቻቸው ውስጥ)	ሰው ።
፪ ፡ ቲኒያ ሲራታ የሚባል ።	እሁለት አይነቶች ጥንቸሎች አይጥ (እጉበታቸው ውስጥ አንድነት ቆዳቸው ውስጥ።	ውሻ ።
፫ ፡ ዳይፒሊዲያም ክኒናም የሚባል ።	የውሻ ቁንጫ (እሆዱ ውስጥ ።	ሰው ፡ ውሻ ፡ ድመት ።
፬ ፡ ሃይመኖሊፒስ ዲሚናታ የሚባል ።	የእሳት ራት (ሌላም ነቀዝና ፌንጣ የመሰሉ ነፍሳቶች ፡	ሰው ፡ አይጥ ፡ አይጠመጐጥ ።
፭ ፡ ድሪፓኒዶቴኒያ ሲታጀራ እሚባል ።	የውኃ ቁንጭ (ወይም የውኃ እናት ።	ዳክዩ ።
፮ ፡ ቦትኤዎሲፍላስ ላታስ የሚባል ።	ፓይክ (Pike) የሚባል ዓሣ ፐርች (Perch) የሚባል መጐራጉርጣም ዓሣ ነጭ ዓሣ ።	ሰው ። ውሻ ።

የገበታውን ማስረጃ እንዲህ ብለህ አንብብ ።

ቴኔያ ሳጂናታ የሚባለውን በሬ በላው ። በሬውን ሰው በላው ። ሰው ከሶ ተጣበው ። በየቂጥሩ እንዲህ ዝለቅ ።

በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድ ።

ሹም ሽር ።

ክቡር ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ከጉብዝናቸው ዠምሮ እስከ ሽምግልናቸው ባላቸው ጉልበትና እውቀት በመታመን ያገለግሉ ነበረና ። ስለ ዚህ በየ ጊዜው በሹመት ላይ ሹመት በማዕርግ ላይ ማዕርግ እየ ጨመሩላቸው ብዙውን ሥራ በንድነት ደርበው ይዘውት ኖሮ ይኸው ባሁኑ ሹም ሽር ተገለጠ ። ለያንያንዱ ሥራ አላፊ ስለ ተደረገለትና የመንግሥቱም ሥራ እንዲጠራ በያንዳንዱ ሥራ አላፊ በማግኘቱ ይታወቃል ። መንግሥቱም የሕዝቡን አስተ ዳደር ችግር እንዳያገኘው መጣሩን ያስረዳናል ። ከቦረና ምስለኔነት ከገሙ ግዛትና በላይነት በቀር ከዚህ በታች እንደ ተጻፈው ይዘውት የነበረውን ሥራ አከፋፈሉ ይታያል። ክቡር ደጃዝማች ወልደገብርኤል በግቢ ምኒስተርነታቸው ይዘውት በነበረው ጋንገብ ላይ የበቾንና የማረቆን በላይነት ጨምረው ቢትወደድ ተባሉ እሳቸውም በትጋትና በማገልገላቸው ከደጅ አጋፋሪነት እሊጋበነት ከሊጋበነት ደጃዝማችነት ከደጃዝማችነት ቢትወደድነት ወድረሳቸው በቅንነት መንግሥቱን ለሚያገለግል ሁሉ ደስ የሚያሰኝ ነው ።

ክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ በመታመን የገንዘብ ምኒስተርነት ሥራ ይዘው የነበሩት ከገሙ በቀር ፊታውራሪ ገበየሁ ይዘውት የነበረውን ሲናድር ያዠይዘው የጦር ምኒስተርነቱን ጨምረው የጦር ምኒስተር ተባሉ ።

ክቡር ሊጋባ ወዳጄ ከደጅ አጋፋሪነት ወደሊጋባነት ከተሾሙ ጀምረው በቅንነትና በትጋት አገልጋይ በመሆናቸው በያዙት ሹመት ላይ ወታደር በግዛቱ በማደሪያው ቢጣላ ዳኘነቱ የጦር አዝማችነቱን የጥንት ያበጋዙን ግዛት ጡጤን ሉሜን ጨምረው ተሾሙ ።

ክቡር አዛጋ ደገፌም በርሻ ምኒስትርነት እያገለገሉ መንግሥታቸውን ደስ ስለ አሰኙ ወሀኒ አዛጋ ተብለው አንከበር ተሾሙ ።

ክቡር ነጋድራስ ዘለቀም የንግድ ምኒስትር ሁነው ለመንግሥት ስላገለገሉ የገንዘብ ምኒስትርነት ተሾሙ ።

ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል የጽሕፈት ምኒስትር ሁነው በሥራቸው ላይ ስለ መትጋታቸው የእርሻ ምኒስትርነት ጨምረው ተሾሙ ።

ክቡር በጅሮንድ ዘለቀም የመንግሥት አገልጋይ ስለ ሆኑ ወረገኑነትን ተሾሙ ።

ክቡር በጅሮንድ ሣህለ ድንግል የመንግሥት አገልጋይ ስለ ሆኑ የበቾን ምስለኔነት ተሾሙ ።

ብርሃንና ሰላም ለዚህ ማዕርግ ላበቋችሁ ለግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱናለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በቅንነት ሆናችሁ ፍጹም አገልጋይ እንድትሆኑና ለመንግሥታችሁም የታመናችሁ ሠራተኛ እንድትሆኑ እየመረቀ ደስታችሁን ይከፈላል ።

ማስታወቂያ ።

በየዓይነቱ የደብዳቤ ወረቀትና ካርት ብሲት ጉርድ ወረቀትም በርካሽ ዋጋ በልዑል የኢ መ አ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ይገኛል።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ክች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድክሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉሙሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ሥፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን ሞቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሂስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዐይነቱ ፤ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ፳ መሐ ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፳ብር ።
ዝበድ	፩ ወቄት	፫ ብር ፫ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ፳መሐ ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፹ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፫ብር ፳መ
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ፳ መ
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፫ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፪ ብር ።
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፻፴፪ ብር ።
፡፡ ባለ ድመት ፡፡		፻፴ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፭ ብር ።
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፴ ብር ።
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፶ ብር።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፩ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፬ መ

ስለ ምንዛሪ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ እስከ ፴ ማን ነው ።
በአንድ ብር	፲ ሊሬ ፹ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ፪ሳንቲም ነው
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር ።

ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ አቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ።

AMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶከለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶክለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ስንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቍጥር ፱
3 me ANNÉE № 9

ሐሙስ የካቲት ፳፬ ቀን ፤ ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 3 MARS 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲረክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christos Taklé Haymanot
Diréctеur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የከበደውን የግብጽ ቀምበር ከኢትዮጵያ ትክሻ ለማውረድ ።

ሠለስቱ ምዕት በኒቅያ ጉባዔ ያልሠሩትን ሕግና ሥርዓት ዕብነ እልዓሣል በኢትዮጵያ ላይ ጫነ ። ወሰብአ ኢትዮጵያ ኢይሚሙ ሊቀ ጳጳሳት እማዕምራኒሆሙ ብሎ በመጻፉ ። ይህ ነገር የቈጫቸው ሰዎችም ኢይሚሙ አለን እንጂ ኢይሠየሙ አላለንም ሲሉ እሰማቸዋለሁ ። ይህ አያወጣነም ከመ ይሚም ላዕሌሆሙ ሊቀ እምኀቤሁ ያለው አጻፉው ፤ ለበዓለ እስክንድርያ ነውና ። የሚያወጣነ ግን የእርሱን አድላዊነትና ኃሰተኝነት የሚያስረዳው የብርሃንና ሰላም ወዳጆች የጻፉት ቃል ያወጣናል ። የዕብነ ዕልአሣል ቃል የርሱን ወገኖች ግብጻውያንን ከፍ ለማድረግና የኢትዮጵያን ሕዝብ በበታች አድርጎ ለመኖር መሆኑን የኢትዮጵያ ሊቃውንት አላጡትም ። ግን ሕዝቡ እንደዛሬው መሰልጠን አልጀመረም ነበርና መንግሥታችንና ሕዝባችን እርስ በርሱ ከዚህ ክርክር የተነሣ እንዳይታወክብን ብለው ዕውቀታቸውን በመልካም መዝገብ ልቡናቸው አኑረውት በትዕግሥት ዝም ብለው ቈዩ ። ለሁሉ ጊዜ አለውና መክብብ ፫ ፩ ዛሬ ግን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታታችንና ልዑል አልጋ ወራሻችን የተባረኩ እድላሞች ስለ ሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ የዕውቀት ኵል ተኳለና ዓይኑን ቊልጭ ቊልጭ ማድረግ ጀመረ ። መልካምኛ አዝማቡ እነጣጠረ ። ተኩሶ መጣሉም አልቀረ ።

የዕብነ እል አሣልን ሐሰት የሚገልጽ ዋና ነገር ደግሞ ይህ ነው በ፫፻፴፩ ዓ ም የእስክንድርያው በትሪያርክ አትናቴዎስ ጳጳስና ሰጥቶ ወደኢትዮጵያ የላከው ሰው ሰላማ የተባለው ፍሬ ምናጦስ የግብጽ ሰው እስክንድርያዊ አይደለም ። የጢሮስ ሰው ኧፊንቂ ከፍልስጥኤም አገር የተወለደ እስከ ሰሙ የሚመሰክር ስለ አገሩ ይህ እርግጥ መሆኑ በኢትዮጵያ ክብረ ነገሥትና በኤሮጳውያን ታሪክ ተጽፎአል ።

እንግዲህ ሠለስቱ ምዕት ወሰብአ ኢትዮጵያ ኢይሚሙ ሊቀ ጳጳሳት እማዕምራኒሆሙ ብለው ብቻ የግብጽ ሰው እንዲሾም ከዘዙ አትናቴዎስ የግብጽን የሀገሩን ሰው ሹም በመላክ ፈንታ ስለ ምን የሌላ አገር ሰው ሹም ላከ ።

እውነት ነው አትናቴዎስ እንደ ዕብነ እልዓሣል አድላዊና ኃሠተኛ ባይሆን የጢሮስን ሰው ፍሬ ምናጦስን ሰላማ ብሎ ስሙን ሰይሞ ወደ ኢትዮጵያ ላከ በ፫፻፴፩ ዓ ም ።

ደግሞ የኢትዮጵያ ሰው እንዳይሾም ስለምን የጢሮስ ሰው ፍሬ ምናጦስ በኢትዮጵያ ላይ ጳጳስና ተሾመ የሚልና በክብረ ነገሥት የተጻፈውን የፍሬ ምናጦስን ታሪክ የማያውቅ ቢኖር ታሪኩ እንደ ተከታዩ ነው ።

ፍሬ ምናጦስና ሲድራኮስ ሁለቱ ወንድማሞች ከአጎታቸው ጋራ ሁነው ከጢሮስ ወደምጽዋ በምትመጣ የንግድ መርከብ ገብተው ወደ ባሕረ ኤርትራ መጥተው ምጽዋ አጠገብ ሲደርሱ መርከብ ተሰበረችባቸው ። ከዚያም ወደባሕር የተሠጠሙት ተሰጠሙ ጥቂቶች የመርከብ ስባሪ ሳንቃ ይዘው እየዋኙ ወደ ምድር ደረሱ ። ከነዚያም በሰው እጅ የሞቱት ሙተው ፍሬ ምናጦስና ሲድራኮስ ሁለቱ ወንድማሞች ከባሕር ስጥመትና ከሰውጅ ዳኑ በእግዚአብሔር ኃይል ። ምጽዋ አጠገብ ያለችው ድኖና ወይም አርኪኮ የምትባለው አገር ሹም ናዒብ የሚባለው እሊህን የሚያምሩ ወጣቶች የፈረንጅ ልጆች ከመግደል ይልቅ ለንጉሥ ወስዶ መስጠት ይገባል ብሎ ወስዶ ለአብርሃ ወአጽብሐ ለኢትዮጵያ ነገሥታት በረከት ሰጣቸው ። አብርሃ ወአጽብሐም ባለሟሎች አድርገው አሳደጉአቸው እያስተማሩ ።

ያን ጊዜ የኢትዮጵያ ሰዎች ገና አረማውያን ነበሩ ሊቀ ካህናታቸውም ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋራ ሁኖ ጽላተ ሙሴን ቅብቲቱን ይዞ የመጣው የዓዛርያስ ወገን እንበረም ነበረ ። ከዕለታት

አንድ ቀን ፍሬ ምናጦስ እንበረምን የኢትዮጵያ ሰዎች ነገ
ራችሁ ይገርመኛል ግዝረት አላችሁ በክርስቶስም ታምናላ
ችሁ ። ጥምቀትና ቁርባን ግን የላችሁም ብሎ ጠየቀው።እን
በረም ደግሞ በክርስቶስ ማመንን የኢትዮጵያ ንግሥት የሕን
ደኬ ባለሟል ጃንደረባ ፦ አመጣልን የሐዋርያት ስራ ፰ ቁ
፳፮ ፵ ግዝረትንም ከእርሱ በፊት አባቶቻችን ሌዋውያን አመ
ጡልን ። አለመጠመቃችንና የክርስቶስን ሥጋና ደም አለመቀ
በላችን ግን ሐዋርያ ባይላክልን ነው ብሎ መለሰለት ። ፍሬ
ምናጦስም ታዲያስ ለዚህ ምን ይበጃል ቢለው ለዚህ የሚበ
ጀው አንት ብትላከን ነው አለው።ፍሬምናጦስም እሽ እላከለሁ
አለ።እንበረምም ከንጉሥ አስፈቅዶ ፍሬ ምናጦስን ወደ እስክ
ንድርያ ላከው ወደ በትረያርኩ ወደ አትናቴዎስ ለኢትዮጵያ
ሕዝብ ሐዋርያ የሚሆን ጳጳስ ላክልን የሚል ደብዳቤ ሰጥቶ።
አትናቴዎስም ደብዳቤውን ባነበበ ጊዜ እጅግ ደስ አለውና
አንተ በኢትዮጵያ ያደግኸው ያገሩን ግዕዝና ልማድ የምታ
ውቀው ሐዋርያም ጳጳስም ብትሆን ለኢትዮጵያ ይሻላታል
ብሎ ፍሬ ምናጦስን ሰላማ ብሎ የግብጻዊ ስም ሰጥቶ ጵጵስና
ሾሞ ላከው በ፫፻፵፩ ም።ይህም የዕብነ እልዓሚልን ኃሠ
ተኝነትና ምቀኝነት ያስረዳናል ።

የኒቅያ ጉባዔ በ፫፻፳፭ ዓመት ባተደረገ ጊዜ አትናቴዎስ
ከሠለስቱ ምእት ጋራ አብሮ ነበረ ዲቁና ተሹሞ።በኢትዮጵያ
ላይ ከግብጽ ሰው በቀር ሌላ ሊቀ ጳጳሳት አይሾም ብለው
ሠለስቱ ምዕት አዘው ኑረው ቢሆን አትናቴዎስ የሌላ አገር
ሰው ሹም ባላከም ነበር ግብጻዊን ይሾም ነበር እንጂ፡ከሠለስቱ
ምዕት ጋራ አብሮ የነበረው አትናቴዎስ ያልሰማውን የሠለስቱ
ምዕትን ትእዛዝ ከሠለስቱ ምዕት በኋላ በዘጠኝ ፻ ዓመት የተ
ወለደው ዕብነ እልዓሚል እኔ ነኝ የጻፍሁት ብሎ አወራ ኒጋድ
ራስ አፈ ወርቅ እንዳሉት ይህም እጅግ የሚገርም ነው ።

የኢትዮጵያ ንጉሥ ገላውዴዎስና በርሳቸው ዘመን የነ
በሩት ሊቃውንት ዛሬ እኛ ያሰብነውን አሳብ ጨርሰው አድር
ገውት ኑሮአል።አጼ ገላውዴዎስ በ፲፭ ፻፵፱ ዓ ም ተድባበ ማር
ያምን በተከሉ ጊዜ የተድባበ ማርያሙን መምሕር በትረ ያሬክ
ብለው በመሾማቸው።ይህ የኢትዮጵያ ሰው በትረ ያሬኩ የኢ
ትዮጵያውን ሰው ጳጳስ አድርጎ በበታቹ እንዲሾመው ጳጳሳቱም
ከኢትዮጵያ ሰዎች ኤጲስ ቆጶሳት በበታቻቸው እንዲሾሙ
አሁን አባቶቻችን ወጥነውት የሔዱትን ስራ እኛ ልጆቻቸው
እንድንፈጽመው እግዚአብሔር ይርዳን።በአጼ ዮሐንስ ጊዜ
አቡነ አትናቴዎስ ወዳሉበት የተድባበ ማርያሙ በትረያሬክ
ብዙ ሰው አጅቦአቸው ወደ አቡነ አትናቴዎስ በመጡ ጊዜ
አቡነ አትናቴዎስ ይህ በብዙ አጀብ ሁኖ ወደኔ የሚመጣው
ማነው ብለው ጠየቁ።አስተርጓሚውም የተድባበ ማርያሙ በትረ
ያሬክ ናቸው ወደ እርስዎ ለመባረክ ነው የሚመጡ ቢላቸው
አቡንም ምን እኔ እባርከው እርሱ ይባርከኝ እንጂ ብለው ቀለዱ.
አላገጡ ዋዛ ነገር ተናገሩ አሁን ግን ያ ዋዛ ቁም ነገር ሊሆን
ነው ። ቀያፋ በዚያ ወራት ሊቀ ካሕናት ነበረና ይኄይስነ ንቅ
ትል አሐደ ብእሴ እም ይትሐጐል ኵሉ ሕዝብ ሕዝቡ ሁሉ
ከሚሞት አንድ ሰው ብን ገድል ይሻለናል ብሎ ትንቢት ተናገረ
እንዲሁም አባታችን አቡነ አትናቴዎስ በሹመታቸው ዘመን
የተናገሩት ትንቢት ሊፈጸም ነው ።

አሁንም ለዚህ መደገፊያ ይሆን መወድስ አስከትላለሁ
ዕብነ እልዓሚል የጻፈውን ሥርዋጽ አንቀጽ አድርጎ ዘኒቅያ
ብሎ የሐሰት ስም ስለ አወጣለት ።

እምነ ማዕምራን ካህናት አእይንተ ወልድ ።
ሢመተ ጳጳስ ኃሠረ ፤
እንተ ታወጽእ በአምሳለ ቢጽ ።ማቴ፳፫
እምዓይነ ገጽከ ቅድም ፤ አውጽኦተ ሰርዌ ሥርዋጽ ።
ወቤተ መቅደስነ ኢይባእ ፤
ዘኢነጽሐ ርእሱ እምሐኬት ለምፅ ።
ወሠራቄ በግዕ ሥርዋጸ ዕፅ ።
ቤተ ዓባግዕ ፍትሐ ዘኢበአ እንተ አንቀጽ ዮሐ ፲፡፩ ።
ወይንዒ በትረ ያሬክ ፤ ተድባበ ማርያም ሠርጽ ።
ይፍረይ ፍሬ ጳጳስ ተክለ ሃይማኖትነ ኢይሕጽፅ ።
እግዚአብሐር በፍትሕ ፡ ዘኢታደሉ ለገጽ ።
ለጵጵስና አፀደ ወይን አምጣነ አፍለስከ እምነ ግብጽ ።
እንግዳ ደስታ ዘብሔረ ጎንደር ።

ጥያቄ።

በተማሪቤቱ ደምብ እንደተጻፈው ። በተፈሪ መኰንን ተማ
ሪቤት ኑዋሪዎች ሁነው የሚማሩ ተማሪዎች እሁድ እሁድ በየ
ሳምንቱ ወደ ቤተክርስቲያን ቁመው ለማስቀደስ ይሄዳሉና እንደ
ልማዳችን በየከቲት ፳ ቀን ወደ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን
አብሬአቸው ሄጄ ስንመለስ አንድ መልካም ጐበዝ ወንድሜ
እባክህ ቆየኝ አለኝ ማን ይሆን? ብዬ ቆየሁት ወዲያው ወን
ድሜ እተማሪቤት ነህና ምስጢር አይጠፋህም ። አንድ ነገር
ልጠይቅህ አለኝ።ወንድሜ ሆይ ባውቀውም ባላውቀውም እሺ
ነገሩን እስቲ ልስማዋ አልሁት።ከዚህ በኋላ እሥራኤልን በጣም
ደስ ያላቸው ምን ጊዜ ነው የእግዚአብሔር ኀይሉ በጣም የታ
ወቀ ምን ጊዜ ነው?ብሎ ጠየቀኝ እኔም እንዳቅሜ መልስ ልሰ
ጠው ተግደረደርሁ እሱ ግን ይህ ጥያቄ በድንገት አይገኝምና
ዘመዶችህን ሁሉ ሰብስበህ አሙስ መልስ እንድትሰጠኝ እለም
ንሃለሁ አለኝ።ማን ትባላለህ ብለው ጥያቄዬን ሳትመልስ ስሜን
አልነግርህም አለኝ የብርሃንና የሰላም ልጆች ወንድሞቹ ሆይ
መቸም ዘመዶችህን ሰብስበህ ያለኝ እናንተን ነውና መልስ እን
ድትረዱኝ እለምናችኋለሁ ።

ትንሽ ወንድማችሁ ማኅተመወርቅ እሸቴ

የ፷፱ ገጽ ተከታይ ።

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

፱ኛ ምዕራፍ ።

ወደ አንዱ አገር ብርና ወርቅ ከገባ በኋላ ከሕዝቡ ውስጥ
ያለው እያንዳንዱ ሰው ከብሩና ከወርቁ የሚያገኝበትና የሚ
ያጣበት መንገድ ልዩ ልዩ ነውና ተቆጥሮ አይጨረስልንም ።
ደግሞ በሂሳባችን አይገባም ። ወደ አንድ መንግሥት አገር
የሚመጣው ብርና ወርቅ የሚበዛበትና የሚያንስበት ምክንያት

ግን ታውቆ የተለየ ነው ። ይህም ምክንያት በቶሎ እንዲገለጽ ልንና መሪ እንዲሆነን ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል አጥብቀን እና ስተውል ።

እነሆ ያልለፋ ቆዳ የሚረክስ ካራጁ ቤት ፣ የሚከብረውም ከፋቂው ቤት ነው ። የለፋ ቆርበት ግን የሚረክሰው ከፋቂው ቤት ነው አራጁም ከፈለገው ዘንድ ብዙ ዋጋ ይፈጅበታል ። እንዲሁም ጥጥ ታርሶ በበቀለበት አገር ረኪስ ነው ። ወደ ሸማ ኔው ሲደርስ ግን ይከብራል ። ሸማ ግን በረኪስ ዋጋ የሚገኝ ከሸማኔው ቤት ነው ። ጥጡን ዘርቶ ላበቀለው ሰው ግን ሸማው ውድ ይሆንበታል ። እንግዴህ ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ዕቃ ብንመለከት ዕቃው ሁሉ አጠቃቀሙ ወደ ታወቀበት ቦታ ይሄዳል ። አጠቃቀሙ ግን በዚያው በታወቀበት ቦታ ይረክሳል ። አጠቃቀሙ ወዳልታወቀበትም ቦታ ሲደርስ እንደገና ይከብራል እንግዴህ በምሳሌ ብንነጋገር ጥጥ እንዴት እንደሚጠቀም የሚያውቅበት ሸማኔ ነውና ፣ ጥጥ ሁሉ ዞሮ ዞሮ ወደ ሸማኔ ይሄዳል ። የጥጥም አጠቃቀም በሸማ ነው ። ሸማም የሚረክስ በሸማኔ ቤት ነው ። አጠቃቀሙን ሳያውቅበት ቀርቶ ጥጡን ወደ አዋቂው ሸማኔ በሰደደው ከጥጥ ተካይ ቤት ተመልሶ ሲደርስ ሸማ እንደ ገና ይከብራል ።

እነሆ የብርና የወርቅም ነገር እንደዚሁ ነው ። የእውቀታቸው ደረጃ ከፍ ያለ ሥራቸውም ልዩ ልዩ ሁኖ የሠሩትን ዕቃ የሚለዋወጡ ሕዝቦች ሥራ ከሚያውቁ ሕዝቦች ይልቅ የለውጥን መሣሪያ አጠቃቀም ያውቁበታልና የሰሩትን ሥራ እየሰጡበት የለውጥ መሣሪያ የሆነው ብርና ወርቅ ሁሉ ወደ ነሱ ይሄዳል ። ሲበደሩትም አጠቃቀሙን ስላወቁበት የብርና የወርቅ ወለድ በነሱ አገር ያንሳል ። ሸማ በሸማኔ ቤት እንደሚረክሰው እንግዴህ ለኑሮው የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እራሱ ሊሠራ የሚችል ሕዝብ በገሩ ውስጥ ያለውን ብርና ወርቅ እርስ በራሱ ይለዋውጥበታል እንጂ ሊለውጥበት ሲል ወደ ውጭ አገር አይሰደውም ። ለጊዜውም ቢሰደው እንደ ቆዳ ፣ ሰም ፣ የዝሆን ጥርስ የመሰለውን ያልተሠራ ነገር ለመግዛት ነውና ይህ ሁሉ ዕቃ ከተሠራ በኋላ ለኑሮው የሚበቃውን ያህል አስቀርቶለት ሕዝቡ በሥራ ወደ አልሰለጠኑበት አገር ትርፉን እንደ ገና ሰዶ ዕቃው ሳይሠራ የፈጀበትን ብርና ወርቅ ይመልስበታል ።

ይኸውም የኢትዮጵያ ሕዝብ በያመቱ ያልተሠራ ቆዳ ወደ ውጭ አገር ይሰዳል ። ያንዱም ፈረሱላ ቆዳ ዋጋ በገራችን እስከ ፲፫ ብር ነው ። ይህን አሥራ ሶስት ብር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ እርስ በርሱ እንዳይለዋወጥበት በየሥራው ስላል ሰለጠነ በሥራ የሠለጠኑ ሕዝቦች የሠሩትን ዕቃ ሲገዛ ስለ ቆዳው ዋጋ የተቀበለውን ብር እንደ ገና ይመልሰዋል ።

አንድ ፈረሱላ ቆዳ ባዲስ አበባ ዋጋው ፲፫ ብር ብቻ ነው ። ከፈረንጅ አገር ሄዶ ተሰርቶ የተመለሰው ቆዳ ግን አንዱ ፈረሱላ እስከ ፻፱ ብር ድረስ ይሰጥበታል ። ስለዚህም የኤሮፓ ሰዎች ለቆዳ ሲሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብርና ወርቅ ሲሰጡት ፤ ቆዳው ከተሠራ በኋላ ለኑሮአቸው የሚበቃቸውን አስርተው የተረፈውን ቁርበት እንደ ገና ወደ ኢትዮጵያ ሰደው ያን በመጀመሪያ ያወጡትን ፲፫ ብር ይመልሱበታል ። ቆዳውም ራሱ ተሠርቶ በምትኩ እነ ቆጫ እነ አቡጀዲድ ሌሎችም ዕቃዎች መጥተው ወደ ኢትዮጵያ የመጣውን ብር ወደ ኤሮፓና ወደ አሜሪካ ይመልሱለታል ፣ እነሆ ሸማኔ ብር ሰጥቶ ካንድ ባላገር ጥጥ ቢገዛ ሸማውን ከሠራ በኋላ ለራሱ ትርፍ አስቀርቶ የቀረውን ሸማ ለባላገሩ ይሸጠዋል ። በዚሁም ያ በመጀመሪያ ለጥጡ ዋጋ ያወጣው ብር ይመለስለታል ። በሕዝቦችም ትዳር እንዲሁ ነው በሥራ የሰለጠኑ ሕዝቦች ብርና ወርቅ ቢያወጡ ትርፍ ካገኙበት በኋላ ይመለስላቸዋል ። ስለሆነ ግን ሸማኔው ብዙ ብር ትርፍ የሚገባለት ሸማውን የሠራበት ጥጥ ሳይገዛው የራሱ የሆነ እንደሆነ ነው እንጂ ። ጥጡን ከውጭ ከገዛው ሸማውን ሠርቶ ሲሸጥ የሚያገኘው ትርፍ የድካሙን ዋጋ ብቻ ነው ። እንዲሁም ያልተሠራውን ዕቃ ከውጭ አገር እያስመጣ ሠርቶ እንደ ገና የሚሸጥ ሕዝብ የድካሙን ዋጋ ያገኛል እንጂ ሌላ ትርፍ አይገባለትም ። ትጉ ሕዝብ ከሆነ ዘንድ ግን በድካሙ የሚያገኘው ትርፍ ትልቅ ሊሆን ይችላል ። ብርና ወርቅም አብዝተው የሚሄዱ ከውጭ አገር ሳይገዛ ከመሬቱ ውስጥ ያወጣውን ነገር ብቻ ሠርቶ ከሠራው ዕቃ ለኑሮው የሚበቃውን ያህል አስቀርቶ የተረፈውን ዕቃ ለውጭ ሕዝቦች ወደሚሸጥ አገር ነው ። ይህንን የሚያደርግ ግን አንድም ሕዝብ በኤሮፓ የለም ። እንደ እያገሩ ሁኔታ ይነስ ይደግ እንጂ የኤሮፓ ሕዝቦች ኑሮዋቸው ሁሉ ከውጭ አገር ያልተሠራውን ዕቃ እያስመጡ ነው ። ሕዝብ በሥራ ሰልጥኖ ቢሆን ግን እንደ ኢትዮጵያ ብርና ወርቅ የሚበዛበት አገር አልነበረም ። ባገራችን ሁሉ ነገር ሊበቅል ይችላል ሁሉ ነገር ሊሠራ ይችላል ። የበቀለውና የተሠራውም ከሕዝብ ተርፎ ብዙ ብርና ወርቅ ወደ ሀገራችን ያመጣ ነበር ። ብርና ወርቅም እየበዛ ቢሄድ መለዋወጡ እየፈጠነለት የኢትዮጵያ ሰው በየያዘው ሥራ ጠንክሮ እየሠራ እየተለዋወጠ እየተደጋገፈ ከፍ ያለውን የእውቀት ደረጃ ለማግኘትና ብዙ ሀብት ለማከማቸት ይሆንለት ነበር ።

መንግሥቱም በርትቶ በዓለም ነገሥታት ፊት ያድግ ነበር ። ብርና ወርቅ መፈለጉ እኮ ስለ መሣሪያነቱ ነው ። የለውጥ መሣሪያም ባልበዛበት አገር ከሕዝቡ አንዳንድ ሰው ከየሥራው የተረፈውን ለመለዋወጥ ይቸግረዋልና ። በየሥራው ሊሰለጥን አይችልም ። እንዲሁም ደግሞ በሥራ ያልሰለጠነ ሕዝብ የለውጥ መሣሪያ ሲያገኝ ሊለዋወጥበት አይችልምና የለውጡን መሣሪያ ለሚፈልጉት ሕዝቦች መልሶ ይሸጠዋል ። ስለዚህም ሕዝቡ እንዲበለጥግና እንዲበረታ የሚፈልግ መንግሥት ከሁሉ ነገር በፊት ለሕዝቡ ኑሮ የሚያስፈልግ ነገር ሁሉ በገሩ ውስጥ እንዲሠራ መጣጣር ይገባዋል ። ይህንንም ከደረገ ዘንድ ብርና ወርቅ በዝተው ወደ አገሩ እንዲገቡለት የታወቀ ነው ። ብርና ወርቅም በብዙ ቁጥር ከመርከብ ፣ ከምድር ባቡር ፣ ከጋሪ ከሌላም ነገር የበለጡ የለውጥ አፋጣኞች መሣሪያዎች ናቸውና የሠሩትን ሥራ የሚለዋወጡ ሠራተኞች እስኪለዋወጡ ድረስ በከንቱ የሚሄድባቸው ድካም እያነሰ ሠራተኞቹም በየያዙት ሥራ ለመሥራት የሚተርፋቸው ጊዜ እየበዛ ይሄዳል ። የሚሠሩትም ትርፍ ሥራ ላገሩ ሀብት ጭማሬም ይሆናል ። እንጨት በሌለበት ቦታ መጥረቢያ አያስፈልግምና መጥረቢ

ያው ወደ ተፈለገበት ቦታ ይሸጣል ። እንጨት ባለበት ቦታ ግን መጥረቢያ ይፈለጋል ። መጥረቢያውም ሲበዛ የሚቆረጠው እንጨት ይበዛል ። የብርና የወርቅም ነገር እንደዚሁ ነው ። እነዚህ ሁለት የለጡጥ መሣሪያዎች በያይነታቸው በሥራ ሰልጥነው እርስ በእርሳቸው ከማይለዋወጡ ሕዝቦች እጅ አይቀመጡም ። ወደ እሚፈለጉበት ቦታ ይሸጣሉ እንጂ ። በየሥራው በሰለጠነ ሕዝብ እጅ ሲገቡ ግን እርስ በርሳቸው መለዋወጡን እያፋጠኑለት እያንዳንዱ ሰው በየሥራው እንዲሰለጥንና የበለጠ ሀብት እንዲያገኝ ይረዱታል ።

እነሆ ብርና ወርቅ ምን እንደሆኑ በምንስ ምክንያት እንዲያንሱና እንዲበዙ ተረዳነው ። እንግዲህም ሥራቸውን እንመርምር ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት ነው ።

ጉቡዓን ወሰንዐዋን እንዘ ይነብሩ በሰላም ።

ጉቡዓን ወንድሞቼ ሆይ እኔ እደነቃለሁ እንዴት ቸኵላችሁ ወደ ክፉ ጨለማ ትመለሱ ዘንድ ነገር ግን ፈጽሜ እንዳልፈርድባችሁ ያውኩአችኋል የብርሃንን ትምሕርት ይለውጡ ዘንድ የሚወዱ አሉና እኔም ከብዙ ከወገኖቼ ይልቅ እጅግ እቀና ነበርኩ አባቶቼ ላስተማሩኝ ልማድ ዛሬ ግን ያበቶቻችንን ልማድ ክፉ ጨለማና ጽጋግ እንደሆነ ስለ ተረዳሁት ዓይኖቼ ከጨለማና ከጽጋግ ወጥተው ብርሃንን ለማየት ተቅበዘበዙ ከብርሃን ብርሃናትን የፀነሰች ወላዲቱ እናታችን ኢትዮጵያ ፅንሷ ተለውጦ ጨለማን እንዳትወልድና የጨለማ እናት ተብላ ስሙዋ እንዳይከፋ ።

እንዘርኑ ለክሙ ወኢዘፈንክሙ አስቆቀውነኒ ለክሙ ወኢበክይክሙ እንዳለው አትሁኑ የሐዲሳት መምሕራችን ብርሃንና ሰላም እንቅልፍ አታብዙ ብሎ በየሳምንቱ ዓዋጅ ሲነግረን እኛ እርስ በርሳችን እየተመቃቀንና የሹመት ጣውንት እየተባባልን ስለ መረዳዳት ፈንታ መዘባበት ሆነ ሥራን ለወደዱና በብርሃን ለሚሄዱ ሹመት ርስታቸው ናት ሥራን ጠልተው በጨለማ የሚሄዱ ግን የናትና ያባታቸውንም ርስት ይነቀላሉ የሹመት ጣውንታችን ስንፍና እንደሆነ እወቁ የሹመት ጣውንታችን ፊታውራሪ ስንፍና አገራችንን ይዘራልና የሚውጠውን ሰው ሽቶ በብርሃን ተዘጋጅታችሁ ጠብቁት ይልቁንም አለቆች የሚመስሉ የሕዝብ ሽማግሎች ብርሃን በከንቱ የሚሮጥ ወይስ አስቀድሞ በከንቱ የሮጠ መስሏቸው ይሆን ያለፈው ዘመን ይበቃናል በጨለማና በመመኘት ተጠብቀን የኖርነው ደግሞ ዛሬ በኛ መመኘት እንዳይኖር ሰላም በሚቀርብበት ዘመን ሁሉ የብርሃንን ፈቃድ እንፈጽም ።

አሁንም ተመልካቾችን አትመልከቱ እያሉ በጥቁር ጳጳስ እጅ አንባረክም የሚሉ የመምሬ ልማድ የልጁ ልጆች አሉና ከነሱ መንገድ ፈቀቅ በሉ ። ከግብጽ የመጡ ጳጳሳት ስንኳ በጥቁር እጅ የተፈተተ ሥጋ አምላክ አንቀበልም አላሉም ነበር ። የተቀደሰችቱ አገራችን ልዕልት ኢትዮጵያ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምራ እስከ ባዜን መንግሥት በኦሪት ያመነች ናት እምነትንም የሕንደኬ ንግሥት ጃንደረባ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ከሐዋርያው ከፊልጶስ ተምሮበፊልጶስ እጅ ተጠምቆ መጥቶ እምነትን ለኢትዮጵያውያን አስተምሮዋልና ፊልጶስ ለኢትዮጵያ ሐዋርያ መሆኑ አይጠረጠርም ። የሐ ፰፰፮—፵

ከዚህ በኋላ በ፫፻፴፩ ዓመተ ምሕረት በፍሬ ምናጦስ ጥምቀት ተሰበከ ፍሬ ምናጦስም ከኢየሩሳሌም መጥቶ በኢትዮጵያ ሲኖር የኢትዮጵያ ሊቀ ክህናት እንበረም የያሬድ አባት በፈቃዱ ወደ ኢየሩሳሌም ልኮት ከአቡነ አትናቴዎስ ጵጵስና ተቀብሎ መጣ እንጂ ግብጻውያን መርጠው አልሾሙልንም ነበር። ምንም በየጊዜው የእስላም ኃይል እየበረታ መጻሕፍቶቿንና መምህራኑዋን ቢያጠፋባት ክርስቲያንነቷን ሳትለቅ በሃይማኖቷ ጸንታ የቆየች ኢትዮጵያ ናት ።

ዛሬም የብርሃንና ሰላም ጓደኞች ተባብረው የኢትዮጵያ መንግሥት ነፃ እንደ ሆነች ቤተ ክህነቷም ነጻ እንድትሆን ስለ ወደዱ ከሐገራችን ጳጳስ እናውጣ የማለታቸው አሳብ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነው ። ምንም ቢሆን እምቤተ መንግሥት የዓቢ ክህነት ተብሎ አልና መንግሥቷ ነጻ ሲሆን እንዲሁም ክህነቷ ነጻ ሊሆን ይገባታል ዛሬም በድንገት ለጵጵስና የሚሾሙትን ምረጡ ቢሉን ንጽሐ ልብና ንጽሐ ሥጋን ከመማር ጋራ አስተባብሮ የሚገኝ ብዙ ሰው እናገኛለን ለወደፊቱም እኔን እንደሚመስለኝ ነገር አሁኑኑ ለጵጵስና የሚሾሙትን በመንግሥትፈቃድ ከዲያቆናቱ ሀያና ሠላሳ ሕፃናት መርጦን በየገዳማቱእየተማሩ እስከ ተወሰነላቸው ጊዜ ድረስ በመጠበቅ ቆይተው ከነዚያ እየመጥረን ብንሾም ይገባናል ። እኔን የሚያሳዝነኝ ነገር ልጆቻችን የፈረንጅ ቋንቋ እንዳይማሩ የነጭ ቋንቋ መማር ሃይማኖት ይለውጣል እያለ መምሬ ልማድ ይገዝታቸዋል ። ክህነት ለመቀበል ግን በነጭ ቋንቋ ካልተመረቃችሁ በጥቁር ቋንቋ አትመረቁ ይላል ። ይህ መምሬ ልማድ ሕጉን ያፈረሰ ቄስ ነውና ሥልጣኑ አያስርም ያፈ ገዝት ነው ። እኔ ግን እንደጠቢባን እጽፍላችሁ ዘንድ አልቻልኩም እንደ ሰነፎች እንጂ ።

ሰላመ አብ ወሰላመ ወልድ ወሰላመ መንፈስ ቅዱስ የሀሉ ምስሌክሙ አኃው ።

ይቤ ገብረ እግዚአብሔር ኤልያስ ታሪክ ነገሥት ጸሐፊ።

ስለ መስማማት ።

ካሁን ቀደም የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ስለመስማማት የሚለውን ቃል አርእስት አድርገው ለጆሮ የሚስማማ ላንደበት የማይገለማ ሁሉ በደስታ የሚቀበለው ምኞታቸውን በብርሃንና ሰላም እንደገለጹ ከኔው ይልቅ ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ትርጓሜውን ከንባቡ ለይታችሁ ትገነዘቡት ይሆናል ። ነገር ግን ምንምንኳ ሺ ጊዜ ቢጠፋ ካልተፈጸመ አርእስት ሁኖ የተጻፈውን ቃል አርእስት እያደረግን ተነግሮ ላልተደረገ ነገር እየመላለስን መጻፍ ወይም ማስታወስ ግድ ይሆንብናል ።

አንደኛ ። ባገር ውስጥ ስምምነት ቢታጣ በዚያው አገር የሚኖሩ ነገዶች ይደኸያሉ እነሱ ስለ ደኸዩም የመንግሥት

ገቢ ያንሳል ። ይልቁንም መንግሥታችን ፋብሪክ አቁሞ ባገር ውስጥ ያለውን መዓድን ቁፍሮ ስላላገኘው ግምጃ ቤቱ ባገሩ ውስጥ ካሉ ነገዶች በሚያገኘው ገቢ ነው የሚሞላውና ስምምነት ስለታጣ ገቢ እንዳያንስበት ያሰጋል ።

ሁለተኛ ። ከሥልጣኔ ደረጆች አንዱ ደረጃ መስማማት ነውና ስምምነት ካልተገኘ ሥልጣኔ ከገር ፈጽሞ ጠፋ ማለት ነው ። ምንምንኳ ፈጽሞ ባይጠፋም ወደላይ ማለት ቀርቶ ወደታች ሲያቈለቍል እንደሚኖር ጥርጥር የለበትም ። ስምምነት የሥልጣኔ መሰላል ነው።ይህም መሰላል መውጫውና መውረጃው ይሆነዋል ። ስምምነት በተገኘ ልክ ወደላይ ይወጣበታል ስምምነት ከገር በጠፋ ልክም ወደታች ይወረድበታል ። ይህም አካሂድ እስከ ዓለም መጨረሻ ከርሱ ጋራ ይኖራል ከቶ አይለይበትም ።

ሶስተኛ።ስምምነት ከገር ፈጽሞ እንዲጠፋ የሚያደርጉት ያሉም የሻለቆች ናቸው።እኒህ የሻለቆች ያልናቸው በያገሩ ሁሉ ዳኛ ይሾሙበታል ለሾሙት ዳኛም ባገሩ ውስጥ ከሚገኘው ወርቅ አበል የለብህም ለመንግሥት ገቢ ነው ብቻ ያንተ አበል ካገሩ ከሚገኘው ዳኝነት ነው ብለው ያዙታል።እርሱም፡ሹመት መለመኑ እንዲከብር ነውና አበል ካልተገኘ ክብረት አይገኝም ሲል የርሱ አበል የሚበዛበትን ምንገድ ያበጃል ።

እርሱ የሚያበጀው መንገድም ሙግትና ክርክር ባገር እንዲበዛ ማድረግ ነውና ስምምነትን ከአገር ፈጽሞ አበረረው ድርሻውንም አጠፋው።ከፈንካች ከተፈንካች ደም ዳኝነት ብሎ ህግ ያቆመም ያገር ዳኛ ሳይሆን አይቀርም፡ ምናልባትንኳ መንግሥት አቁሞት ቢሆንም በሻለቆች በኩል ተጠግቶ ይህነን ነገር ህግ ሁኖ እንዲቆምለት ደጅ የጠና እርሱ ይሆናል ። መንግሥትም ይህነን ነገር እፊቱ ሲቀርብ ሳለ ፈንካቹስ እውነትም ጠግቦ ተፈናክቷልና እዳ ቢጣልበት አያሳዝንም ተፈንካቹስ ስለ ተፈነከተ ደግሞ ከእመሙ በላይ ለምን እዳ ይጣልበታል ብሎ መጠየቁ አይቀርም ይሆናል ። ያንን የሻለቃም ደጅ ጠኚው ጢ.ት ማታ እየተመላለሰ ነዝንዞታልና ነገሩን ሊያቀናለት ሲል አየ ጌታዬ ተፈንካቹስ ቢሆን ቀን ጥሎት ነው ተፈንክቶ ያለንጂ ጠብ አንሺው እሱ እራሱ ሳይሆን መች ይቀራል ብቻ እዳ ከሁለቱ ላይ ሲሆን ይፈራሉና ጠብ ከአገር ይርቃል ብሎ ይመልሳል ነገሩም በእሺታ ያልቃል ።

ዛሬ ግን እንጨት ተፈንጥሮበትም ደም ቢወጣ እርሱም ወድቄ ነው ደም የወጣኝ ብሎ ቢያመሃኝ አንዲት ቤሳ ብትሆን የሚምረው የለም ። ወይ እንጨት ሲመታው ሳለ ሰው ኑሮ እማኝ ካላደረገ ።

አራተኛ ፡ መንግሥት ስምምነት ባገር ሊነግሥ ቢፈልግ ግን ለሻለቃና ላገር ዳኛ በደሞዝ አሳድሮ ያገር ወርቅና ዳኝነትን ወደርሱ ቢያዞር ሳይሻል ባልቀረም ብየ ሐሳቤን አሳጥራለሁ ።

ፍ ወ ሚ ዘአ ።

ሥራን መፈጸም እንጂ መጀመር ብቻ አይጠቅምም ።

ካለፈው ዘመን አስቀድሞ ባለፈ ዘመን ከማኅበሩ አንድላቹው ባህገራችን እየተደመረ የሚቀረው ሥራ ብዙ ነው ብሎ በ፫ተኛው ቁጥር ጽሮ አስታውቆን እንደነበረ ወትሮ እናስበዋለን ሥራን ከመጀመር ሥራን መጨረስ ይሻላል የሚለውንም ቃል ብዙዎች መላልሰው ይናገሩታልና አንባቢ ይሰለቻል ብለን እንተወዋለን።ይልቁንም በዚህ ነገር ተቈርቋሪዎችና ሌሎች የማኅበሩን ጓደኞቹ መላልሰው በየጊዜው ጽፈዋል።ነገር ግን በ፭፮ ቍጥር አንባቢው መልሶ ምክንያቱን ጠየቀ እንጂ የሚገባውን ምላሽ ሰጥቶ ልባቸውን የሚያሳርፍ ላቸው ሌላ ሰው እንደሚገኝ ተስፋ መስጠቱን ጋዜጣው ለማኅበሩ አላመለከተም።ነገሩም ይህ ነው ኢትዮጵያዊ የሆነሰው ሁሉ በያንዳንዱ እግዚአብሔር በቸርነቱ ከሰጠው ገንዘብ እንዳቅሙና እንደ ችሎቱ መጠን ለመክፈልና ሥራውን ለመጀመር በገዛ ፈቃድ እንዳለው በየሐሳቡና በጽፈቱም እንዲጣጣር እናያለን ።

ይህንም ብዙ ባላገሮችና ቤተ ዘመዶች የውጭ አገር ሰዎች እንኳ ሳይቀሩ የትምሕርት ቤት እንዲቆም ነገሩን አበርትተው በሞቀ መንፈስ ሲጽፉ አይተን እንረዳዋለን ።

አዎን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለሀገሪቱ መልካም ነገር ይመኝላታል ስለ ሀገሩም መልካም ነገር እየፈለገ ማንበብና መተረክ ጀምረዋል ። እንዲያውም በጠቅላላው ለሀገር መልካም ነገር ማድረግ መልካም እንደሆነ በየቤቱ ይጨዋወተዋል ። ነገር ግን ያ ተጀምሮ የነበረ የስጦታ መንፈስ እየደከመ ሄደና እስከሁን ሥራው ሳይጀመር ቈይቱዋል ። ይህንም የማኅበሩን ሥራ ለማስታወስ ባለፈው ጋዜታ አንስተውታል ።

እንግዲህ ምክንያቱ ምን ይሆን ብለን ልንጠይቅ ግድ ይሆንብናልና ይህ ፈቃድ ተጀምሮ መቅረቱ ምክንያቱ ምን ይሆን ለዚህም ጥያቄ ምላሽ እናገኝለታለን ። በመጀመሪያው መስመር እንዳመለከትን በሀገራችን እየተጀመረ የሚቀረው ሥራ ብዙ ነው በሚባለው ቃል የሰው ሁሉ ልቡ ተናውጡዋል ወነደ እሳት እምአንብቦትየም እንደሚል ነገሩ አንገብግቦታል። ስለዚህ ባለ ገንዘቦች ሥራው ተጀምሮ እንደሚቀር አይተው አንክካ ገብቱዋቸው እየተጠራጠሩ የሥራው ሁኔታ በማን ላይ እንደሚሆን ለማወቅ አሻግረው ይመለከቱ ይሆናል ። ሌሎችንም በገዛ ማሰባቸው ሳይቀር የስጦታቸውን መልክ በጉባዔ ለመግለጽ ያስፈራቸው ለልግሥናቸውም መሰናክል ሆኖ ወደ ማኅበሩ ለመቅረብ ሳያስደፍራቸው የቀረ ምክንያቱ ይህ ይመስላል ።

አሁንም ደግመን ሌላውን እንጠይቃለን በጋዜታው እንደተባለ ገንዘቡ ተጠራቅሞ ለሥራ መብቃቱን ሰምተው ማኅበሩ ሥራውን የሚያደራጅላቸውና የሚያሰተነትንላቸው ፈጣን ሰው መርጠው እንዲያቆሙ ሥራውም እንዲጀመር ተፈቅዶላቸው አልነበረምን ወይስ ሥራ ሁሉ ያላንዳች ሰሪ እንደሚበቃ ሆኖ አለመገኘቱን የማያውቅና የማይረዳ ሰው ይኖር ይሆን ምስጋና ለርሱ ይሁንና እግዚአብሔር ዓለምን ሳይፈጥር አስቀድሞ አንዳች ነገር አልተፈጠረም ።

እንዲሁም ምሳሌውን ቀጥለን እንጽፋለን በየቤታችን ነዋሪ ሆኖ የሚገኝ ተንቀሳቃሽ ዕቃ ሁሉ እርስ በርሱ ተንቀሳቃሽና አንቀሳቃሽ ስላልሆነ አንዱን ወዳንዱ ሌላውንም ወደ ሌላ ለማዛወር ግድ ባለ አእምሮ አንቀሳቃሽ ይፈለግለታል ።

እጅና እግር ስንኳ በሰነፍ ሰው ጥግ ነዋሪዎች ሲሆኑ ሕያ ዋን መሆናቸው ሳይቀር ትጉህ ሕሊና ባለ ማግኘታቸው ለሥራ መንቀሳቀሳቸው ቀርቶ ያአካል ክፍል እስከ አለ መሆን ይደር ሳሉ ብለን እንጠራጠራለን የነገሩ እውነት ነው ታካች አንድ ጊዜ ከተወዘፈ ተመልሶ እንዳይነሣ ስንፍና አንዳንድ ከባድ ሸክም ሆኖ ይሰማዋልና ስለ ዚሁ ፈቃዱ እየ ደከመ ሂዶ እጅ ና እግሩ ደንዝዘው ከስፍራው እንዳይንቀሳቀስ ያደርጉታል እላ ንት ጉበዛዝት አፍአዊን ምሳሌ ተከትለን የውስጥ ጠባያችን ብንመረምር እንደ ምን ባለ ሁኔታ ተይዘን እንደ ምንኖር ፈጽ መን በተረዳነው ነበር ።

እንግዴህ የሆነ ሁኖዋልና ለበጎ ሥራ መጀመሪያው በክፉ ሥራ መናዘዝ ነው ። የተፈጸመ ንሥሐም ክፉ ልማድ ያለውን ጠባይ መተው ብቻ ነው ሁሉ ይቀራል ነገሩም ይረሳል መል ካም ስም ግን ለዘላለም ይኖራል ነገር ግን ይህንን ማወቅ ወዴት ይገኛል ደጋግ መምሕራንና የትምሕርት ቤቶች ቢኖሩ አልነበረምን ። በጨለማ ለመሄድ አስተዋይና ንቁ መሪ እንደ ሚያስፈልግ ማወቅ መልካም ፈሊጥ መሆኑን ልናስብ ይገባና ልና ይነስም ይደግም ለተመደበው ሥራ አስተዋይ ሰው ማቅ ማና ሥራውን ማስኬድ የተሻለ ሆኖ ይታየናል።

እንዲህ ቢሆን ግን ይህ በየጥቂቱ የሚፈስ የስጦታ ምንጭ በዝቶ ያለልክ እየጐረፈ ሁሉን እንደሚያደርስ ማለት ለተመ ደበው ሥራ እንደሚበቃ መሆኑ ጥርጥር የለበትም ።

ጸሐፊው ለዚሁ ሥራ በያመቱ ፳፫ ፳፫ ብር ሊረዳ መዘጋ ጀቱን በጽሕፈቱ ያመለክታል ።

ገብረ ሥላሴ ወ ።

የከተማ ወሬ ።

ትልቅ ግብር ከቤተ መንግሥት ።

የካቲት ፲፱ ቀን በትልቁ ቤተ መንግሥት ለመኳንንቱና ለሠራዊቱ ትልቅ ግብር ተደርጎ መኳንንቱና ሠራዊቱም የደ ስታ ምሳ ሲጋበዝ ዋለ ።

ትልቅ ግብር በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ቤት

የካቲት ፳ ቀን እሁድ ዕለት ቅበላ ነበረና በዚሁ ቀን በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ግቢ መኳንንቱና ሠራዊቱ በየመ ዓርጉና በየደምቡ የደስታ ግብር ሆኖለት ምሳ ሲጋበዝ ዋለ ።

ሥራትን በመተላለፍ ።
የሚመጣ አደጋ ።

በአዲስ አበባ ከተማ መንገድ በሚሄደው ሕዝብ ላይ ጉዳ ትና ጥፋት እንዳይመጣበት መዘጋጃ ቤት አስቀድሞ ባለ አቶ ሞቢልና ባለጋሪ በጥንቃቄና በልክ እንዲነዳ ። ባለፈረስም ያለ ልክ እንዳይጋልብ ልጓሙን አጥብቆ ይዞ በዝግታ እንዲሄድ የሕዝቡን ሕይወት መጠበቂያ ማስታወቂያ አውጥቶ ነበር ። ግን ይህን የማዘጋጃ ቤት ማስታወቂያ በመተላለፍና ሥራቱን ባለ መጠበቅ ብዙ አቶሞቢልና ጋሪ ነጂዎች ከልክ አሳልፈው በፍ ጥነት ሲነዱ ይታያሉ ። ብዙ ፈረሰኞችም በከተማው መንገድ የሚሄደው ሕዝብ መድረሻ እስኪያጣ ድረስ ልጓሙን ለቀው የማስታወቂያውን ቃል ጥሰው ሽምጥ አስነስተው ሲሄዱ ይታ ያሉ ። እንደዚሁም ሁሉ የካቲት ፳፩ቀን ፲፩ሰዓት አንድ የውጭ አገር ሰው ማዘጋጃ ቤት ያወጣውን ማስታወቂያ ተላልፎ ባራዳ መካከል ሽምጥ አስነስቶ ሲሄድ አንድ መንገደኛ አስዳጠና የተዳጠው መንገደኛ እንደወደቀ ደም ሲተፋ ዘበኞች ደርሰው ከወደቀበት አንስተው ወደ ሱቅ አስጠግተው ቆመው ሳለ ክቡር ከንቲባ ነሲቡ በአቶሞቢል ሲያልፉ በፈረስ ተድጦ መንገደኛ ሰው እንደወደቀ ግራዝማች አማረ ቢያመለክቷቸው ከአቶሞ ቢሉ በፍጥነት ወርደው በፈረስ ወደተዳጠው መንገደኛ ሰውዬ ቀርበው ቁስሉንና ደም ሲተፋ ጉዳቱ እንደበዛ አይተው ወደ ሆፒታል ዘበኞች በአቶሞቢል ወስደው እንዲያሳክሙት አዘ ዙና ዘበኞች በአቶሞቢል ወደሆስፒታል ይዘውት ሄዱ ። ያስ ዳጠውንም የውጭ አገር ሰው ግራዝማች አማረ በዘበኛ አስ ያዙት ።

እንደዚህ ያለ የድንገት አደጋ በመንገደኛ ላይ መድረሱ መዘጋጃ ቤት ለሕዝቡ መጠበቂያ ያወጣውን ማስታወቂያና ደንቡ አውቶሞቢልና ጋሪ ነጂዎች ፈረሰኞችም ባለመጠበቃቸውና በመተላለፋቸው ነውና ፤ ለወደፊቱ እንደዚህ ያለ አደጋ በመ ንገደኛ ላይ እንዳይደርስ ባለአቶሞቢል ፥ ባለጋሪ ፤ ባለፈረስም አተርፍ ባይ አጉዳይ እንዳይሆኑ ማዘጋጃ ቤት እንዳወጣው ማስታወቂያና ደንብ በዝግታ ሊሄዱ ግድ ያስፈልጋቸዋል ። የማስታወቂያውን ቃል ተላልፈው ትእዛዝ ጥሰው ያለልክ በአ ቶሞቢልና በጋሪ በፈረስም የሚሄዱትን ሰዎች ያገር ቤት ሰው ነው የውጭ አገር ሰው ነው ነጭ ነው ጥቁር ነው ሳይሉ በየ መንገዱ ዳር የሚቆሙ የከተማ ዘበኞች ደንቡን ሳይተላለፉ በልክ እንዲሄዱ እንዲያደርጓቸው እናሳስበቸዋለን ።

የዓድዋ ጦርነት መታሰቢያ በዓል ።

በሺ ፰፻፹፰ ዓ ም ዓድዋ የሆነው የጣልያንና የኢትዮጵ ያውያን ጦርነት በዓል መታሰቢያ የካቲት ፳፫ ቀን ነበረና ግርማ ዊትንግሥተ ነገሥታትና ልዑል የኢ. መ አ ወ ተ መ በዓሉን ለማክበር ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ወጡ ። የኢት ዮጵያ፥መኳንንትና ሠራዊትም በዚያ ተሰበሰበ ። በዐሉን ለማ ክበር የተሰበሰበ ሕዝብም ቦታ ጠቦት ይጨናነቅ ነበር ።

ወደዚያውም ዑደት ተደረገና አምሮ በተነጠፈ ደረጃ ላይ ልዑል ፀወንበር ተቀመጡ መኳንንቱም ግራና ቀኝ ከበው በመዓርግ በመዓርጋቸው ተቀመጡ ። በዚያን ጊዜ የቅዱስ ጊዮ ርጊስ ካህናትና መዘምራን ሲያሸበሽቡ አምረው ታዩ ።

ዝማሬው ከተፈጸመ በኋላም ብፁዕ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በዓሉ ስለሚከበርበት የዓድዋ ጦርነት ተርከው በጦርነቱ ሥራቸውን ፈጽመው ስላገራቸው የሞቱትን ጀግኖች በክቡር ስም አንስተው በመሰገኑዋቸው ጊዜ የጀግኖቹ የኢትዮጵያ ልጆች ልብ ተነካ። እግዚአብሔርን መፍራትና ትእዛዙን መጠበ ቅ ለመንግሥት እየታዘዙና እያገለገሉ ስላገር መመከትና መሞት በእግዚአብሔርና በመንግሥት ፊት ክብር የሚያሰጥ መሆኑን

እስረድተው መንፈሳዊና ሥጋዊ ምክር መክረው አሳርገው ሕዝቡን ባርከው አሰናበቱት ።

ከዚህ በኋላ ታቦቱ ገባና ፻፩ ጊዜ መድፍ ተተኵሶ ስድስት ሰዓት ሩብ ጉዳዩ ሲሆንም ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከቤተ ክርስቲያኑ ወጥተው ባማረ ዓጀብ ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመለሱ ።

የውጭ አገር ወሬ ።

ስለ ዱክ ዴሊ አብሩሲ ወደ ኢትዮጵያ መንገድ የመጐብኘቱ አኳኋን ።

ኮሬሬ ደላሴራ የተባለ የጣሊያን ጋዜጣ እንዲህ ሲል ይጽፋል ፥ ባለፈው መስከረም ዋና የሚያስፈልግ ነገር በጣሊያንና በኢትዮጵያ የሚሆን መልካም መገናኛ በሚመጣው ፀደይ እንዲሆን ታስቦአል ። ወራቱም ግንቦት ነው ይህ ኦፊሴል (እንደ መንግሥት ማዕርግ) የሆነ መጐብኘት ከዱክ ዴሊ አብሩሲ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ልዑል ተፈሪ መኰንንን ወደ አዲስ አበባ ሔዶ በማየት ይፈጸማል ። ዱክ ዴሊ አብሩሲም የሚመጣው በኢጣልያን ንጉሥ በቪክቶር አማኑኤል ስም ነው ። ፲፱፻፳፬ ሐምሌ በኤውሮጳ ቁጥር የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መከፈረንሳዊ ወደ ሮማ አፊሴል ሆነው መጥተው በጐበኙ ጊዜ ንጉሣችን ተቀብሏቸው ወደ ኢትዮጵያ ከመመለሳቸው በፊት በዋና ከተማችን በሮማ አያሌ ቀን ተቀመጡ። ብዙ ተከታዮችና ሚኒስትርም አብረዋቸው ነበሩ አሁን የኢጣሊያ ንጉሥ የሚቀርበው ትልቅ ዘመዱን ወደ አዲስ አበባ ሔዶ ይህን መጐብኘት እንዲመልስ ለመነው ። ዱክ ዴሊ አብሩሲም የመንገዱን ነገር ለማከናዎን በዚህ ጊዜ ከቶሪኖ ወደሮማ ይመላለሳል ከያሌ ሳምንት በኋላም ወደ ኤሪትሪያ ይሄዳልና በዚያ ጉቤርናቶሬ ጋስፖሪኒ ተቀብሎት ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ መነሻው እስቲደርስ ድረስ ከዚያው ይሰነብታል ፥የመነሻው ጊዜም በግንቦት እኩሌታ ይሆናል በኤሪትሪያ ጉበርናቶሬ ተሸኝቶ ዱክ ዴሊ አብሩሲ ከኢትዮጵያ ሲመለስ የጥጡን አተካከል የትፀነይን ቦታ እርሻውንና መስኖውን ባለፈው አመታት የመሻሻሉን ነገር በመረመረባት በክር በሆነች ቅኝ አገራችን ኤሪትሪያ አያሌ ሳምንት ይቆያል ። በኤርትሪያ ከተማ በከረን ያውስታ ዱኬስ (የንጉሥ ዘመድ) አለች።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተቀብለውት ዱክ ዴሊ አብሩሲ በኢትዮጵያ የሚቆየው ከአሥር እስከ አስራምስት ቀን ነው የመጐብኘቱም አኳኋን ድንቅ ይሆናል ።

ኢትዮጵያና ጣሊያን እንዴት ባለ መገናኘት በተገናኙበት ጊዜ ፤ በአፍሪቃ ነገር አሳቡ በጣም የታሠረ ከፍ ያለ በሥራው ቅን በሆነው በንጉሥ ወገን የመጐብኘቱ አሳብ መድረጉ ለፖሊቲካችንና ለቅኝ አገር አሳባችን ልብ የሚነካ ሆንዋል ። ወሬውም በኢትዮጵያ ደስ የሚያሰኝ ሆንዋል ትልቁ የኢጣሊያን ንጉሥ እንደራሴም በናፍቆት ይጠበቃል ።

የመንገዱ መሰናዳትም በሚሆን ነገር ሁሉ ተከናውንዋል ። ከዱክዴሊ አብሩሲ ጋር የሚሔዱ ሰዎች እንደተለመደው በጣም ስንዱ የሆኑ ናቸው ።

ማለፊያ ፖሊቲካ ።

በሮማ የተነገረው የመንግሥት ቁርጥ አሳብ ደስ የሚያሰኝ የብልህነት ፖሊቲካ አለው ። በኢትዮጵያና በኢጣሊያን ያለውን ፍቅር ለማጽናት በምሥራቅ አፍሪቃ ላለን ጥቅም የሚያስፈልግ የታወቀ ሀሳብ ነው ። ባለፉት ዓመታት ይህ መስማማት በግልጥ ጠነከረ ፤ ይልቁንም በኢትዮጵያና በኤሪትሪያ በሆነው መስማማት ነው ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንን ወደሮማ መጥተው የጣሊያንን ንጉሥ በጐበኙ ጊዜ የፊተኛው ክፍል ተፈጸመ ። እንደዚሁ ሁሉ የንጉሥ ወገን በሆነው ፤ በንጉሥ ስም በሚሄደው ፤ የሚፈልገውን ጉዳይ የሚያቀና የኢትዮጵያም ሕዝብ በሚወደው ፤ በሁለመናውም ከፍ ያለ መልክተኛ ሆኖ በሚታየው ለሚቀበለው አገር ደስ በሚያሰኘው ፥ እሱን በመላክ ከበሬታ ላለው አገርም በጣም የሚጠቅመው በዱክ ዴሊ አብሩሲ መጐብኘት የሁለተኛው ክፍል ይፈጸማል ።

የኢጣልያ መንግሥትና የእንግሊዝ መንግሥት የተስማሙበት የንግድ ጠቀሜታ መስማማት ፥ የሌላ ነገር ሳይሆን ፥ የንግድ ጠቀሜታ ብቻ ነበር ። እነዚህ ሁለቱ የኤውሮጳ ነገሥታት ከኢትዮጵያ መንግሥት ለርሻና ለንግድ የሚሆን ለሁለቱም የሚጠቅም ውል እንዲያገኙ ለመኑና በኢትዮጵያ በክፉ ቱተፈጐመ በኤውሮጳ ጋዜጦችም የኢጣሊያና የእንግሊዝ መስማማት የኢትዮጵያን መንግሥት ነፃነት የሚነካ አስመስለው የመቃወም ቃል ጽፈው ነበረ ።

ይህም መቃወም በጄኔብራ በመንግሥታት ማሕበር በብርቱ ተነሥቶ ነበር ፥ ግን የኢጣልያን መንግሥት ጠቅላይ በኢጣልያ በኩል አንዳች የተደበቀ ኃሳብ እንደ ሌለ በግልጥና በብርታት ቁርጥ አድርጎ ባስታወቀ ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት በመላክተኞቿ ያቀረበችው የመቃወም ቃል ቀረ ። ይህን በማድረጉ ክቡር ሙሶሊኒ የብልህነት ፖሊቲካ ሠራ ። አሁንም የንጉሥ ወገን በሆነው በሚደረገው መጐብኘት የብልህነት ፖሊቲካ ይሠራል ። ይህም ነገር ባለፉት ጊዜያት በፖሊቲካ ጋዜጣና የቅኝ አገር ሀሳብ ባላቸው የኤውሮፓ ሰዎች በኢትዮጵያ ላይ የተነዛውን ያልሆነ ትርጓሜ ያለው ወሬ ለማፍረስ እንዲጠቅም ጥርጥር የለበትም ።

ዱካውን መላክ ከሁሉ የበለጠና የታወቀ ትርጓሜው እንደሚከተለው ነው ። ከመንግሥት ጠቅላይ የተሰናዳውን ነገር ባገባብና ሁለተኛ ትርጓሜ በሌለው አነጋገር እንዲፈጸም የኢጣልያ ፖሊቲካ ከኢትዮጵያ ጋራ ሁለት መሠረት ያለው ፖሊቲካ እንዳልሆነ ሊገልጽ ነው ።

በፖሊቲክና በሕዝብ አሳብ በምክር ሥልጣን ያላቸው የኢትዮጵያ የየአውራጃው ገዦዎችና ራሶች ይህነን ሊረዱት ይገባቸዋል ፥ ባዲስ አበባ ያሉ ለመንግሥቱ ባለሟል የሆኑ የውጭ አገር ሰዎችም የሆነም ወገን ቢሆኑ ይህነን ነገር ሊረዱት ይገባቸዋል ፥ ደግሞም የኤውሮጳ የየዋናው ከተማ ጋዜጦች ቆይቶ የምቀኝነትን ነገር ከመናገር አሁን የኢጣልያን ንጽሕናና ቅንነት ይመልከቱ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ፳ መሐ ።
ያሲዳሞ ቡና	፩	፲ብር ።
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ፳መሐ ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፹ ብር ።
የበሬ ቆዳ ደጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፫ብር ከሩብ
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ፳ መ
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፫ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር ፩ ኮረጃ		፻፴፩ ብር ።
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፻፴፩ ብር ።
፡፡ ባለ ድመት ፡፡		፻፳፫ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፫ ብር ።
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፴ ብር ።
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፵ ብር።
ሱከር	፩ ጁኒያ	፴ ብ ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፬ መ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ እስከ ፳፫ ማን ነው ።
በአንድ ብር	፲ ሊሬ ፺ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ፳ ሳንቲም ነው
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉሙሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ሥፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን ሞቶመቢል የፊታውራሪ ጴሬስ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ቤርሊዮ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዮ አቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሜኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

AMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሂስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዐይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ማጥን በየዓይነቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላሸው ፣ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

ኤን ቤ ኔዳሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ግሪፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን ኦዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የኦዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ኮዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ስንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ። የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቍጥር ፲
3 me ANNÉE № 10

ሐሙስ መጋቢት ፩ ቀን ፤ ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 10 MARS 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲረክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christos Taklé Haymanot
Diréctеur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ወንድምነትና ወዳጅነት ።

ምስር የተባለ የግብጽ ጋዜጣ ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በምሥራቅ ወገን የአፍሪቃን መንግሥትና በደቡብ በኩል ለሱዳን ድንበር በጣም የተቃረበች አገር ናት ፡ ለምስር ልብ የሆነው የዓባይ ምንጭም የተገኘው ከዚህችው አገር ነው የኢትዮጵያ ሕዝብና የምስር ሕዝብም ደሙ አንድ ነው ዓባይ መገጣጠሚያቸው ነውና በሁለቱ አገሮች መካከል ያለው ዝምድና እንዲጠነክር ይገባል ።

የኢትዮጵያ አየርና ነፋስ ለሰውነት በጣም የተስማማና መልካም ነው ኢትዮጵያ ወርቅና ብር መዳብና ነሐስ ብረት ይህንን የመሰለ ብዙ መአድን ያለባት ዋና አገር ነች በእርግጥ ኢትዮጵያ ይህንን መአድን የውጭ አገር ሰዎች እንዲያወጡት አትፈቅድም ፡ ግን እኛ ምስሮች ከእነሱ ጋራ በመልካም ወዳጅነትና ዝምድና በሆነ ጊዜ ጉዳዮቻቸውን የተሻሻሉ ለማድረግ እንድንረዳቸው ኢትዮጵያዎች ምስሮችን እምቢ አይሉም ብሎ መጻፉን ከአእምሮ ጋዜጣ አነበብኩ ፡

ነገሩን ብመረምረው የምስር ጋዜጣ እንደጻፈው ቃል ኢትዮጵያና ምስር የተሳሰረ የወንድምነትና የወዳጅነት ፍቅራቸው እየጠነከረና እየበረታ እንዲሄድ ማስፈለጉ ጥርጥር የሌለበት ነገር ነው ፤ ከላይ እንደተጻፈው የኢትዮጵያና የምስር ሕዝብ ያንድ አባይ ወንዝ ልጆች ወንድማማች መሆናቸውን ዓለም ሁሉ ያውቃል ፤ በሀገራችንም ቢሆን የፍቅርና የወንድምነት ነገር ሲነገር ያገሬ ልጅ የወንዜ ልጅ የማር እጅ ይባላል ስለ ዚህ እንደዚህ ያሉ ወንድማማቾች በመስማማት ፍቅራቸው እንዲሰፋ አንድነታቸው እንዲገፋ ይገባል ። ለሁለቱ አገሮች በሚሆን ጠቀሜታም እርስ በራሳቸው እየተረዳዱ ቢሠሩ ኃይልና ብርታት አግኝተው ጠቀሜታቸው እየበዛ መሄዱ አይጠረጥርም ።

የምስር መንግሥትና ሕዝብ የኢትዮጵያን መንግሥቶችና ሕዝብ እንደሚወዱና እንደሚያፈቅሩ ደግሞ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ የምስርን መንግሥትና ሕዝብ እንደሚወዱና በመካከላቸው የወንድምነት መተባበር እንዲጸና መፈለጋቸው የተገለጠ ነገር ነው ።

ኢትዮጵያውያንስ የምንጠላው አጥብቀንም ልንቃወመው የሚገባን ጥፋትና ጉዳት የሆነብን ሁለት ነገር ነው ።

፩ኛው የግብጽ ከፍት ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያን ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ልግዛ ማለቷን ይህም የሚያደክም ሥጋዊ ጉልበታችንን ጭምር ነው እንጂ መንፈሳዊ ጉልበታችንን ብቻ አይደለም በዚህም ነገር ውስጥ የምስር መንግሥት አይገባበትም።

፪ተኛም በገራችን ውስጥ የአረቁን መርዛምነትና ጉዳትነቱን ባላወቀ ሕዝብ መካከል ዘር የሚያጠፋ መርዛም አረቂያቸውን እየነዙ የኢትዮጵያ ዘር ደህና ሆኖ እንዳይበቅልና ወደ ፍሬ እንዳይደርስ የሚያምሱና የሚቆሉ ወገኖችን ነው ፤

ተስፋሁን አበበ ።

የ፰፰ ገጽ ተከታይ ።

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

አስረኛ ክፍል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በያመቱ ከሚሸጠው ዕቃ የሚገዛው ዕቃ እንደ በዛ ከዚህ ቀደም አስረድተናል ። ትርፉንም ዕቃ የገዛው በምን ገንዘብ እንደሆነ ብንመረምር ከውጭ ሕዝቦች ብዙ ገንዘብ መበደሩን ተረዳነው ። እንግዴህ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳሁኑ መበደሩን ትቶ ለወደፊቱ የሚገዛውንና የሚሸጠው ዋጋው ትክክል የሆነለት እንደሆን ይጠቀማልን ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ግን ይህ ነው ። እንደ ዛሬው የንግድ ሁኔታ እንደ ሆነ ሕዝቡ አይጠቀምም ፡ ከውጭ አገር የሚመጣለት ዕቃ ያልተ

ሠራ ፡ ከአገሩ ወደውጭ አገር የሚሰደው ዕቃ ግን የተሠራ ቢሆን ግን ትርፍ ድካም አይሄድበትም ነበርና ሕዝቡ ይጠቀም ነበር እንደ ዛሬው ሁኔታ ግን ሕዝቡ የሚገዛውና የሚሸጠው ዕቃ ዋጋው እዚህ ምንስ ትክክል ቢሆን ተሠርቶ የሚመጣው ዕቃ ስለ መጣበት መንገድ ርቀት ዋጋ እየጨመረ ከዚህ የሚ ሄደው ዕቃ ግን ሄዶ የማሠራበት ቦታ ስለ ራቀ ዋጋው እየ ጐደለ ነው እንጂ ፤ የገቢውና የወጭው ዕቃ በእውነት ትክ ክል ሆኖ አይደለም ። ስለዚህም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲገዛ በዙ ዋጋ እየሰጠ ሲሸጥ ግን ጥቂት ዋጋ እየተቀበለ ነውና ጉዳት አይቀርለትም ። ደግሞም ሌላ ጥያቄ እንጠይቅ ። የኢትዮጵየ ሕዝብ በየዓመቱ ከሚገዛው ዕቃ ዋጋ የሚሸጠው ዕቃ ዋጋ ቢበዛሳ ሕዝቡ ይጠቀምበታልን ። የዚሁም ጥያቄ ምላሽ እንደ ፊተኛው ነው ። ሕዝቡ የሚሸጠው ዕቃ ያልተሠራ ከሆነ ዘንድ ሕዝቡም በተረፈው ብርና ወርቅ ከውጭ አገር መሣሪያ አስ መጥቶ ካልሰለጠነበት ብር ቢሰበስብ ለሕዝቡ አንዳች ጥቅም አይሆነውም ። ብርና ወርቅ ለሕዝቡ እውነተኛ ጥቅም የሚሆነው በሕዝቡ ውስጥ አንዳንዱ ሰው እርስ በርሱ ሲለ ዋወጥ ረድ መሣሪያ ሲሆኑ ነው እንጂ በያንዳንድ ባላገር እን ቅብ ውስጥ ተቆልለው ቢቀመጡ አይደለም ። አንድ ባላገር ከሉት ከብቶች በያመቱ አንዳንዱን በ፴ በ፴ ብር እየሸጠ ባ፲ ብር ልብ ሱን እየገዛ ፳ ፳ ብር ከምድር በታች ቢቀብር ለባላገሩ ትርፍ መሆኑ ነውን ። ብር አይበላ አይቆረጠም ፡ ላሚቱ ከተሸጠችበት ፴ ብር ሀያ ብር ቢቀበር ፡ ላሚቱ ታርዳ የሥጋዋ ሲሶ ተበልቶ ሁለቱ እጅ በከንቱ እንደ ተጣለ ያህል ነውና ። እንደዚህ ያለው ባላገር አይረባም ። ላሚቱን በ፴ ብር ሸጦ ባ፲ ብር ልብሱን ገዝቶ በ፳ ብር የተሻለ የእርሻ መሣሪያ ገዝቶ ለርሱና ለቤተ ሰዎች የሚሆን እህል አብዝቶ ቢያገባ ግን ብልህ ይባል ነበር ።

በሕዝቦቹም ትዳር ልክ እንደዚሁ ነው ። ራሱ ሳይሠራ ከመሬቱ እየተበደረ እየሸጠ ብዙ ብር ሰብስቦ የሚያስቀምጥ ሕዝብ የማይረባ ሕዝብ ነው ። ይህንንም ሲያደርግ መሬቱ ፍጉ እየሄደበት በቶሎ አርጅቶ እህል ማብቀሉን እንዲያቋርጥ ማፋጠኑ ነውና በኋላ ልጆቹና የልጅ ልጆቹ በረሀብ እን ዲያልቁ የታወቀ ነው ። በሥራ ያልሰለጠነውም ሕዝብ የሰበሰ በው ብርና ወርቅ በያንዳንዱ ሰው ቤት ሥራ ፈትቶ መቀመጡ ቀርቶ ተሰብስቦ ወደ ባንክ ገብቶ ወለድ ቢያተርፍ ለንደዚህ ያለው ሕዝብ ጥቅም አይሆነውም ። ለጊዜውም ወለድ ቢያ መጣ ብር ይጨመራል እንጂ ሌላ ትርፍ አይገባም ። ወለዱስ የሚገባው ከምንድር ነው ። ከገዛ አገሩ መሬት የሚበደረው ብድር ካለፈው ዓመት ይልቅ ሲበዛ አይደለምን ።

እነሆም ስድስት ላም ያለው ባላገር አንዲት ላም በ፴ብር ሸጦ ወለድ እንዲያመጣለት ሲል ፴ውን ብር ላንድ ነጋዴ ቢያ በድር ። ነጋዴውም ሰላሳውን ብር ተቀብሎ ከበደረው ሌላ ላም ገዝቶ ላሚቱን ወደ ሩቅ አገር ወስዶ በ፵ብር ሸጦ ፡ በሽያጩ ወዲያው አቡጀዲድ ገዝቶ አምጥቶ ላበዳሪው ባርባ አምስት ብር ሸጦ ከዚያ በኋላ እንደዚህ ቢለው ። ወንድሜ አንተ ያበደርከኝ ፴ብር ነው ። እነሆ ከነወለዱ ፴፫ብር መሆኑ ነውና ተቀበለኝ ቢለው ። እንግዴህ ከበዳሪውና ከተበዳሪው ማናቸው መጠቀሙ ነው ፡ ያበዳሪው ትርፍ ፫ብር ሲሆን የተበዳሪው ትርፍ ፲፪ብር ሆነ ፡ ነገሩ ይህ ብቻ ቢሆን አበዳሪው ተጐዳ ባላልን ነበር ፡ ነገር ግን ሲገዛም ሲሸጥም ያገኘው ትርፍ ከበዳሪው ብቻ ነውና አበዳሪው ያገኘው ጉዳት ሁለት ነው ። አንዱ ወለዱ ጥቂት ስለ ሆነ ። ሁለተኛው በፊት ስድስት ላሞች ነበሩት አሁን ግን አራት ላሞች ብቻ ቀሩት ። ላሞቹም ባይሸጡ ረብተው ሀብቱን ያበ ዙት ነበር ። ሁለቱንም ላሞች ከሸጣቸው በኋላ ያገኘው ትርፍ ፲፰ብርና የማይረባ በቶሎ የሚቀደድ አቡጀዲድ ብቻ ነው ፡ እንግዴህ ባላገሩ አስራ ስምንቱን ብር በፊተኛው ወለድ ሂሳብ እንደ ገና ያበድር ፡ ይህ ከሆነለት ዘንድ ነጋዴው ያገኘውን ፲፪ ብር ትርፍ ጨምሮ ከበዳሪው ፴ብር ላም ይገዛል ። ያችንም ላም እሩቅ አገር ወስዶ ሸጦ በሽያጭዋም እንደ ገና አቡጀዲድ ገዝቶ አበዳሪው ባ፵፫ብር ሸጦ ብሩንም በ፳ተመውን ሸርፍ ምንዛሪ አስበ ላበዳሪው ፲፰ብር ከነወለዱ ሲመልስ ሲመልስ ለራሱ ፳፫ብር ከ፯ ተመውን ይተርፈዋል ። እንደዚህም ከበዳሪው ላም እየገዛ በያመ ቱም ላበዳሪው ባ፵፫ ብር አቡጀዲድ እየሸጠ ይህንን ንግድ በያ መቱ ቢደጋግም ያበዳሪው ባላገር ላሞች ፈጽመው ተሸጠው አልቀው ባላገሩ የሚበላውና የሚለብሰው አጥቶ ለነጋዴው ሎሌ ሊሆን የግድ ይሆንበታልና ከጥንት ኑሮው ተሥፋ ቆርጦ ነጋዴውን ይከታተላል ። ይህንንም እንድንረዳ ቀጥሎ የተጻፈ ውን ሰንጠረዥ ሂሳቡን አስተውለን እንይ ። ይህም ሰንጠረዥ ነጋዴው ትርፍ እያገኘ መሄዱንና አበዳሪ እየከሰረ መሄዱን ያስ ረዳናል ።

	የባላገሩ የላም ቁጥር		የባላገሩ የገንዘብ ቁጥር		ነጋዴው ከባላገሩ ያገኘው ትርፍ የገንዘብ ቁጥር		
	ቀሪ	የተሸጡት	ብር	መ	ብር	መ	
መጀመሪያ ።	፮						ሳይሸጥ የነበሩት ነጋዴው ግን ምንም የለው ነበር
ሁለተኛ ጊዜ ።	፭	፩	፴				
ሶስተኛ ።	፬	፩	፲፰		፲፪		
አራተኛ ።	፫	፩	፲፱	፲፬	፳፫	፯	
አምስተኛ	፪	፩	፱	፲፬	፵፬	፲፯	
ስድስተኛ።	፩	፩	፲፱	፲፬	፶፬	፲፯	
ሰባተኛ።					፸፬	፲	
		፮			፸፬	፲	ሆነ። ነጋዴው ከባላገሩ ያገኘው ትርፍ በለጠ

ተጠራጣሪው አንባቢ ግን የሰንጠረዡን ማመልከቻ በመ ልካም ተመራምሮ ስላልተረዳ እነሆ ደግሞ እንደገና በግልጽ ተርጉመንለት እንዲረዳ እንጥራለን ።

የመጀመሪያው ሰንጠረዥ ምሳሌ ባላገሩ ስድስት ላሞች እንደ ነበሩት ስላስረዳን ፤ በኋላ ግን ትርፍ አገኛለሁ ሲል አን ዲቷን ላም ራሱ ለ፴ ብር ሸጦ በወለድ ለነጋዴው አበደረው ሁለተኛ ነጋዴውም ከባላገሩ ላይ በተበደረው ብር እንደ ገና ደግሞ ከርሱው ላይ አንዲት ላም በ፴ብር ገዝቶ እሩቅ አገር ወስዶ ላ፵ብር ሸጦ ባ፵ው ብር አቡጀዲድ ገዝቶ ወደ ባላገሩ ቢያመጣው እነሆ ባላገሩ ባ፵፭ብር ገዛው ከዚሁ ከርባ አምስት ብር ሰላሳ ሶስቱን ብር ከነወለዱ ለባላገሩ ከፈለና ለራሱ ፲፪ብር

ትርፍ አገኘ ። ያን ጊዜ ባላገሩ ፩ላሞች ቀርተውት ነበር ። ባላገሩ ያገኘው ከዋና ገንዘቡ ግን ፲፰ብርና የማይረበ አቡጀዲድ ብቻ ነው ።

ስስተኛ ያ ነጋዴ ፈጽሞ እራሱን ስላልቻለ ያንን የባላገሩን ፲፰ ብር በወለድ ይበደርና ራሱ ያገኘውን ትርፍ ፲፪ ብር ጨምሮ ከባላገሩ አንዲት ላም በ፴ ብር ገዝቶ ይዞ ሄዶ በውድ ይሸጥና በሸጠው ብር አቡጀዲድ ገዝቶ አምጥቶ ለባላገሩ እንደ ልማዱ ሸጠ ፲፱ ብር ከ፲ ፬ መሐለቅ ከነወለዱ እዳውን ለዚያ ባላገረ ይከፍልና ለራሱ ፳ ፫ ብር ከ፮ መሐለቅ አተረፈ ። ባላገሩ ግን ያን ጊዜ ፫ ላሞች ቀርተውት ነበር ።

በአራተኛው ጊዜ ። እንግዴህ ያነጋዴ ራሱን ሊችል ፳ት ብር ብቻ ስለ ጐደለው አምስቱን ብር ከባላገር ተበድሮ በ፴ ብር ደግሞ ከቀሩት ከሶስት ላሀሞች አንዲቷን ገዝቶ ወስዶ ወደ ተወደደበት ሸጠና እንደ ቀድሞ ልማዱ እግረ መንገዱን አቡጀዲድ አምጥቶ ለዚያው ለባላገር ሸጠለትና ከዚያው ላይ ፬ ብር ከ ፲፬ መሐለቅና አንድ መጥር አቡጀዲድ ለዕዳው ከፍሎ ለራሱ ፵ ፬ ብር ከ ፲፮ መሐለቅ አተረፈ ። ነጋዴውም እንግዴህ እራሱን ችሏል ። ብድሩን ጨርሶ ከፍሏልና ከዚያ ከባላገሩ ሁለተኛ ብድር አይፈልግም ለወደ ፊቱ ። ያን ጊዜ ባላገሩ ፪ ላሞች ናቸው የነበሩት ።

በአምስተኛው ጊዜ ደግሞ ከቀሩት ከሁለቱ ላሞች አንዲቷን በ፴ ብር ገዝቶ እንደ ፊተኛው አድርጎ መልሶ ለባላገሩ ሸጠና ፳፬ ብር ከሥራ ስድስት መሐለቅ አተረፈ ። በስድስተኛው ጊዜ ያችኑ ለባላገሩ የተ!ፈቿውን አንዲቷን ላም ገዝቶ ሄዶ ሸጠና ሲመለስ እንደ ወትሮ ልማዱ አቡጀዲድ ገዝቶበት ቢመጣ ፹፬ ብር ፲ መሐለቅ ተሸጠለት ። ስለዚህም የነጋዴው እያደገ የባላገሩ ሀብት እያነሰ ሄደና የሚበላውና የሚለብሰው ስላጣ ለነጋዴው ሎሌ ሊሆን ይሰናዳል ።

እነሆ ፡ ነጋዴው በራተኛው ጊዜ ትርፉ ከ፷ ፳ት ብር ስለበለጠ ከባላገሩ የተበደረው ፳ት ብር ብቻ ነው ከዚያ በኋላ ግን አልተ በደረውም ። ያገኘው ትርፍ እራሱን አስችሎት በገንዘቡ ገዝቶ አቡጀዲድ ማምጣት ጀመረ ። ባላገሩም በየ ዓመቱ የሚገዛው ልብስ በ፵ ፳ት ብር ስለ ሆነ በእጁ የቀረው ብር ላቡጀዲድ መግዣ ባይመላለት በስድስተኛው ጊዜ የቀሩትን ላሞች ሁሉ ሸጠ ። በሰባተኛው ጊዜ ግን የቀረው ብር ለልብሱ መግዣ የማይበቃው ሆነ ላምም እንዳይሸጥ ላም ስለ አጣ በረሀብና በብርድ እንዳይሞት ሲል ለነጋዴው ሎሌ ሆኖ ያድራል ። በሕዝቦችም ትዳር እንደዚሁ ነው ። በሥራ ያልሰለጠኑ ሕዝቦች ያልተሠራ ዕቃ ከገራቸው አውጥተው ሸጠው ትርፍ ብር ቢያገኙ ለጊዜው ነው እንጂ አያዛልቃቸውም ። መሬታቸውም በጊዜ ብዛት አርጅቶ እህል መስጠቱን ሲያቋርጥ የሚሸጡት ነገር ሲጠፋ የልብስ መግዣና ምግብ አጥተው እናገኛለን ሲሉ ወደ ሌላ አገር ይሰደዳሉ ።

እንደዚህ ያለውም ሕዝብ በመጀመሪያ ያገኘውም ትርፍ ብር ከባንክ ገብቶ ቢወልድለት ወለዱ ከገዛ ጉዳቱ የተገኘ ነው እንጂ ከውጭ አገር የመጣ ትርፍ አይደለም ። እንደዚህ ያለውም ሕዝብ እራሱ ሊነግድ የሚበቃ ዕውቀትና ኃይል የለውምና በባንክ የገባውን ብር ተበድረው የሚነግዱበትና የሚያተርፉበት የውጭ አገር ሰዎች ናቸው ። ተበድረው የሚነግዱበትም ነጋዴዎች ያገሩ ሰዎች ቢሆኑ ያው ነው ። ባለ መሬቱ እየደኸየ ነጋዴው ግን እየተጠቀመ ይሄዳል ። ማለት ያገሩ ሀብት በጊዜ ብዛት በጥቂቶች ሰዎች እጅ ይጠቀለላል ። እነዚህም ጥቂቶች ሰዎች የተወለዱበት አገር ብዙ ፍሬ እንደ እማይሰጥ ሲያዩ የሰበሰቡትን ብርና ወርቅ ይዘው በደህና ወደ ሚኖሩበት አገር ይሄዳሉ ብዙ ሀብት ያከማቸ ሰው በሄደበት አገር ሁሉ ይመቸዋልና ያገር መውደድን ነገር ከጉዳይ አይቆጥረውም ።

የሚበላውንና የሚለብሰውንም ያጣ ድኃ የተወለደበትን አገር የሚወድበትን ምክንያት ያጣልና ያገሩ መንግሥት ቢበረታ ወይም ቢጠፋ ግድ የለውም ። ስለ ዚሂም መንግሥት የሚጠቀም ያገሩ ሀብት በጥቂቶች ሰዎች እጅ ሲሰበሰብ አይደለም ያገሩን ሀብት በመላው ሕዝቡ ሲከፋፈለው ነው እንጂ ። የሀብታሞቹ አንዋዋርና የሠራተኛው ድኃ አንዋዋር ዓይነቱ እንበለ መጠን የሚራራቅበት አገር መንግሥቱ ከጥፋት አፋፍ እንደደረሰ ያስረዳል ። የኢትዮጵያንም ሕዝብ ሁኔታ ብንመለከት እንዚሁ ያለ ጥፋት እንዳይርስበት ያስፈራል ። ባንድ ፊት ነግደው የሚያድሩት የውጭ አገር ሰዎችና ለሕዝቡ አንዳች ጥቅም ሳይሠሩ ድካሙን እየቀሙ አንድ አንድ ሹማምንት ደህና ደህና ቤት እየሠሩ እያጌጡ የተመቸ ኑሮ ሲኖሩ እናያለን ። ባንድ ፊትም የእለት ምግብና ያንድ ዓመት ልብስ እናገኛለን ሲሉ ብዙሺህ ድሆች ወባና ችጋር ፈጅቷቸው ከድሬ ደዋ እንስቶ እስከ አዲስ አበባ ድረስ ከምድር ባቡር ጐን ለጐን አልፈው አልፈው ተቀብረዋል ። ግማሾቹም የተቀበሩበት መቃብር ጠሊቅ ስላልሆነ አጥንታቸው ዱሮ ወጥቶ ከምድር ባቡር መንገድ ግራና ቀኝ ተበታትነዋል ።

ደግሞም ይኸነን ያህል እሩቅ መንገድ መሄድ አያስፈልገንም ። ነገሩ በየከተማው ውስጥ ይገለጽልናል ። ያማረ የግምብ ቤትና ቷንንሽ ጐጆ አጠገብ ላጠገብ ተሰርተው እናያለን ። ባንዱ ቤት ውስጥ ትልቁ ጌታ ሕዝቡ ደክሞ ያፈራውን ገንዘብ በከንቱ ሲያባክን በጐጆው ውስጥ የሚኖረው ደሀ የሚበላውና የሚለብሰው የሚያበራውም አጥቶ በረኃብና በብርድ ተጨብጦ በኩበት ጢስና በእድፍ ውስጥ ይጨማለቃል ። ባንዱ ቤት ጌትነቱ እየበዛ ሲሄድ ባንዱ ቤት ድኅነቱ እየሰፋ ይሄዳል ። የጐጆውንና ያዲሱን ግምብ ቁመት ብናስተያይ ባገራችን ደሀና ጌታ እንዴት እየተራራቁ እንዲሄዱ ይገልጽልናል ። ይህ ግን ለመንግሥት ክፉ ምልክት ነው ። ይኸም ክፉ ነገር እየሠፋ እንዳይሄድ መንግሥት ሕዝቡን በሥራ እንዲሰለጥን ያስፈልገዋል ። ሕዝቡ በሥራ ከሰለጠነ ዘንድ ጌታና ድኃ እንደ ገና ይቃረባሉ ። በምክርና በኃይልም ተደጋግፈው የመንግስታቸውን መሠረት ያጠነክራሉ ። ብርና ወርቅም እረዳቶች የለውጥ መሣሪያዎች የሚሆኑት የዚያን ጊዜ ነው ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት ነው ።

ለጥያቄ መልስ ባጭር ቃል ።

(ከቡር አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ።)

ባለፈው ሳምንት በቁጥር ዘጠኝ ብርሃንና ሰላም አንድ

መልክም ጕበዝ እንዲህ ሲል ይጠይቃቸዋል እስራኤልን ደስ ያላቸው ምን ጊዜ ነው የእግዚአብሔርስ ኃይሉ የታወቀ ምን ጊዜ ነው ይላል ክቡር ተጠያቂውም ለጊዜው እንደ ሚአስፈልግ መልስ መስጠት ሳይጠፋባቸው ጠያቂው ሰምንት ድረስ ቀን ሰጥቷቸዋልና እሳቸውም ያገራቸውን ልጆች ማነቃቃትን ማስረዳት ዘወትር ፈቃዳቸው ስለ ሆነ ምክሩን ለብርሃንና ሰላም ልጆች ያከፍሉናል ፡፡እኔም ትንሹ ወንድማችሁ ጥቂት የብርሃን ውጋጋን ስለ ታዬኝ ያገሬን መንፈሳዊ ነጻነት አጥብቄ እወዳታለሁና ትንሽ ቃል (እንደመሰለኝ እንደ እስራኤል ነጻነትን ለማግኘት ደስ ስለ አለኝ መልሱን ቀጥዬ እጽፋለሁ ፡፡ ኦሪት ዘጸአትም ፯ ቁ ፯ እንዲሕ ይላል እግዚአብሔር ፡፡ እኔ እግዚአብሔር ከምስሮች ባርነት አወጣችኋለሁ ከመገዛታችሁም አድናችኋለሁ በተዘረጋችውም ክንድ በታላቅ ፍርድ ከምስር እጅ አስጥላችኋለሁ የኔ ወገንም አደርጋችኋለሁ አምላክም እሆናችኋለሁ እኔም እግዚአብሔር አምላካችሁ እንደሆንኩ ታውቃላችሁ ከምስር ባርነት ሳወጣችሁ ብሎ ያላቸው ጊዜ ነጻነትን የመሰለ ማአረግና ሺልማት በዓለም ላይ ከዚህ የበለጠ ደስታ የለምና ቤቷን ንብረቷን ፡፡ ርስቷን ጉልቷን ስንቋን ጨርቋን ሳይሉ ከባርነት ወደ ነጻነታቸው ተነስተው ሄዱ ለኛም እናታችን ኢትዮጵያ ይህን ታላቅ በጀርባዋ ያለ የመንፈሳዊ ባርነት ሸክም እንዲወረድላት እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታ ልመናዋን ታቀርባለች እግዚአብሔርም ልመናዋን ሰምቶ ሳለ ፩ ፩ ሰዎች ስነ ተፈጥሮአቸውን ባለ ማወቅ ፡፡ (ሥላሴዎች) ንግበር ሰብአ በአርያነ ወበእምሳሊነ ጥቁር ቀይ ሳይሉ የፈጠሩንን በተለዬ በጥቁር እጅ አንባረክም እያሉ ፈጣሪአችንን ያስቀይሙታል እንጂ ከአገራችን ሊቃውንት ተመርጦ እንዲሾምልን ሙሉ ተስፋችን ነው ደግሞ አቶ አስታጥቄ ወልደ አማኑኤል እንዳሉት እኔም የሳቸው ተከታይ ሆኜ ደስ ስለ ተሰኘሁ ዛሬ በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክና በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ጊዜ ይህን መልክም ምኞታችን ቢፈጽምልን እንደ ደህና ሐውልት በዓለም ታሪክ ላይ ተቀርጾ ዓለም እስኪአልፍ ይቆያቸዋል እነሱም ይኸን የተመረጠን እድል እስራኤልን ከምስር ባርነት እንዳወጡአቸው የሙሴና የአሮን ምሳሌ ሆነው መንፈሳዊ ነጻነታችንን ለማስገኘት የሚጣጣሩልንን በሙሉ ተስፋ እንጠብቃቸዋለን (እድሜ ለንግሥታችን) እድሜ ለ አተፈሪ መኰንን ፍጻሜውን ለማየት ያብቃን አሜን ፡፡

ኃይሌ መኰንን ፡፡

ማመልከቻ ፡፡

ምነው የኢትዮጵያ ክህናት የኦርቶዶክስ የተዋህዶን ሃይማኖት በማስተማር ሰነፉ በአንድ ስፍራ እንኳ የሃይማኖት ተማሪ ቤት ነው ተብሎ ቤት ተሰርቶ አስተማሪ በቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ወይም በማህበር ገንዘብ እንደሚገባ በደሞዝ ተቀጥሮ የሚያስተምር የለም ተማሮቹ ብቻ እንደቀድሞው ደንብ በየገዳማቱ ኢየዞሩ ይማራሉ ግን የቤተ ክርስቲያኑ ሹመትና ማአርግ በትምህርት ብልጫ መሆኑ ቀርቶ በደጅ ጥናት ስለሆነ ተማሮቹ እጅግም እንደቀድሞው አይደክሙበትም ከዚህም የተነሣ ወደ ፊት የሊቃውንትን ትምህርት ደክሞበት የሚማር ሰው ጠፍቶ ሊቅ እንዳይጠፋ ያስፈራል ፡፡ ደግሞ በየቤተ ክርስቲያኑ መኽሳት እሁድ ቀንና በሌላም በዓል ቀን የመጻሕፍት ትርጉም ይነግራሉ ይኸ ግን ሃይማኖት ለመማር አይበቃም አሁን እስተውለን ብንመለከት የእስላሞች መስጊድ በደቡብ ኢትዮጵያ ከሀረር እስከ ገንቤላ ተዘርግቷል ፉቂራዎችም በትጋት ያስተምራሉ ደግሞም ከክርስቲያን ሃይማኖት የኦርቶዶክስ ሃይማኖት በጋላ አገር ለማስተማር የኢትዮጵያ መምሕራን ስለ ሰነፉ ፳፮ የሚሆኑ የፕሮቴስታንት ተማሪ ቤት ቁመዋል ያስተምራሉ ይልቁንም የካቶሊኮች መምሕራን ከሐረር እስከ ገንቤላ እስከ ማጂ ቁጥሩ የበዛ የትምህርት ቤት አቁመዋል የጣሊያኖች የነሙሴ ባርለሲና እንኳ ፲፭ ያህል የሃይማኖት ተማሪ ቤት አለ ምነው የኢትዮጵያ ክህናት በማስተማር እንዲህ ሰነፋችሁ

ስለ ዚህ ወደ ፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ ልጆቻችሁን ወደ ስልጣኔና ትምህርት ቤት አግብታችሁ ስልጣኔና ያአገር ነጻነት ፍቅር ማስተማር ለአገራችሁና ለልጆቻችሁ ጥቅም ይሆናል ፡፡ ደግሞም የኢትዮጵያ ክህናት የስልጣኔ ትምሕርት ቤት ትዳራችሁን የሚያጠፋብችሁ መስሏችሁ የስልጣኔውን ትምሕርት ቤት ከመቃወም የሃይማኖቱን ትምሕርት ቤት ቅኑብትና ኢየተማከራችሁ (የኦርቶዶክስን) የተዋህዶ ትምሕርት ቤት አስፋኢያወቃችሁ የስልጣኔውን ትምሕርት ቤት ትዳራችሁን የሚያጠፋብችሁ መስሏችሁ ክፉ ስም አታውሩበት ማለት ነው እንጂ እናንተ አሁን ትልቅ ትዳር ያላችሁ መስሏችኋል ምን ትዳር አላችሁና ይጠፋብችኋል ይኸ ፩ ፩ ጋሻ ጫካ መሬት ነውን? ወይስ ሌላ አላችሁ ፡፡ሕዝብ ቢማርና ቢሰለጥን ግን የሐብት ደረጃ ያድጋል ከሕዝቡ ሐብት መብዛት የተነሣ የክህናትም ሀብት ከፍ ይላል ሕዝቡ ሲሰለጥንም ክህን ይልቁን ይከበራል እንጂ አይዋረድም ፡፡

አሁን ከናንተ ከኢትዮጵያ ክህናት ይልቅ የእንግሊዝ የፈረንሳይ ክህናት መቶ ጊዜ ጌቶች ናቸው ደግሞ ለናንተ እንደሚመስላችሁ በናንተ ዛሬ ባላችሁት ክህናት ጊዜ የስልጣኔ ደምብ አይቆምም ፡፡ ለወደ ፊት ደግሞ የስልጣኔ ትምህርት ከሚማሩት ትውልድ ጋራ እንዲስማሙ እንደሌላው ዓለም ክህን ልጆቻችሁን የሃይማኖትንና የስልጣኔ ትምህርት አስተምሯቸው ሕዝብ ተምሮ ሲሰለጥን ለብቻቸው ወደ ኋላ እንዳይቀሩ ፡፡ የስልጣኔ ተማሪ ቤት ማለትም ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ቁሞ የተጀመረው የግርማዊ ንጉሥ የዳግማዊ ምኒልክ ትምሕርት ቤትና የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ትምሕርት ቤት ናቸው ፡፡

አስተማሮቹም በነዚህ በ፪ቱ ትምሕርት ቤት የሚያስተምሩ ሕዝብ ናቸው እንጂ ክህናት አይደሉምና ሃይማኖት አያስተምሩም ፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ ክህናት መንግሥትን ሌላ የሃይማኖት አስተማሪ ከልክሉልን ከማለት እናንተ እየተቀዳደማችሁ ብታስተምሩ ሕዝቡ ከባዕድ ያገሩን ሰውና ያገሩን ፍቅር ይቀበላል ፡፡ መቼም በሌላ አገር የክህናት የሃይማኖትና የስልጣኔ ትምሕርት ቤት በጣም ትልልቅ ነው የእስክንድርያው ጳጳስ አቡነ ዮሐንስ ያቆሙት የትምሕርት ቤት ስምንት መቶ

የሚያህሉ ሕጻናት ይማሩበታል በጣም ትልቅ ነው ሕጻናቱም የሚማሩት የሃይማኖት ትምህርት ብቻ አይዶለም የእንግሊዝን የፈረንሳይ ቋንቋ ጭምር ነው ። ይኸ መቼም ለአገራቸው ቢሆን ነው እንጂ ወደ አገራችን የመጡትማ የግብጽ ጳጳሳት እስካሁን ፩ም ጐጆ ለሐበሻ ልጅ ኣላቆሙም ። እነሱ ከዚህ ገንዘብ ወስ ደው ወገናቸውን ይረዱበታል ከቶ እኛ ወገኖችንን የሚረዳንን በምን ምክንያት ጠላነው ይሆን ባናውቅ ይሆናል ። እንግዴህ የኢትዮጵያም ካህናት በየወረዳው የትምሕርት ቤት ቁሞላ ቸው ደሞዝም ከቤተ ክርስቲያን ገቢ ገንሀብ ለመምህራን ወጥ ቶላቸው የሃይማኖት ተማሪ ቤት የሚበረታው ጳጳሱ የኢትዮ ጵያ ሰው ቢሆን ነው አፍንጫን ቢመቱት ዓይን ያለቅሳል ይባ ላል በዚህ ነገር ከዚህ ቀድሞም ብዙ ሰዎች ከየመጻሕፍቱ ጠቅሰው ጽፈዋል ደግሞ ጥቂቶች ሰዎች ልማድን እንደ በዓለ ፋሲካ የሚአከብሩ የለመድነውን ትተን ያልለመድነው ያልነበረ ለምን ይሰራል ሲሉ እንሰማለን ልማድ ግን ከሃይማኖት አይ ቆጠርም ግን የዓለምነገሥታት ለአገራቸው ጥቅም ሐዲስ ትል ልቅ ስራ ሲሰሩ በታሪክ ነገሥት ስማቸው በክብር ይጻፋል ለአ ገራቸው የሚጠቅም ሐዲስ ትልቅ ስራ ያልሰሩ ነገሥታት ጊዜያቸውን በከንቱ አሳለፉት ከማለት በቀር ክብርና ምስጋና አይጻፍላቸውም ደግሞ ጥቂቶች ሰዎች ከግብጽ ጳጳስ ማምጣ ታችንን እንደ ሃይማኖት ይቈጥሩታል ግን ይኸ ባፋቸው ነው ንጂ የልባቸውስ ሐሳብ አንዱ ወንድማችን ለምን ጳጳስ ሆኖ ይከበራል ብሎ ለምቀኝነት እንደ ታሰበ ተረድተነዋል ።

የኢትዮጵያ ልጆች በሌላ ጊዜ በታሪክ የእስራኤል ልጆች ን እንላለን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ ስልጣን ሲሰጥ ጴጥሮስ ሐዋርያን እስራኤላዊዉን የመንግሥተ ሰማያትን መክ ፈቻ ስልጣን ሰጥቼሃለሁ አለው እንጂ የግብጽን ሰው የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ ስልጣን ሰጥቼሃለሁ አላለውም ። የቀሩትም ፲፪ ሐዋርያት የእስራኤል ልጆች ናቸው እንጂ ግብጾች አይደ ሉም እንግዲህ የኢትዮጵያ ልጆች የእስራኤል ልጆች ተሆኑ እንዴት ብለን ክርስቶስ ያከበራቸውን የእስራኤልን ልጆች ኢትዮጵያዎችን ስልጣን አይገባችሁም ለግብጽ እንጂ ማለት እንችላለን ። ከክርስቶስስ ቃል የሚከብር የማን ቃል ነው ። ደግሞ በመጀመሪያም እግዚአብሔር ክህነትን ሲሰጥ ለአሮንና ለሌዊ ነው የሰጠ ለእስራኤል ልጆች እንጂ ለግብጽ ሰዎች አይደለም በምን ምክንያት ይሆን አንድ አንድ ሰዎች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን በታች ካልተገዛች ክብር አይሆነንም የሚሉ ይኸ በጣም ይገርማል ከሌላ በታች መሆን እንዴት ክብር መስሎ ታየን ።

ደግሞ አለቃ ነጋሽ ዘብሔረ ጐንደር በ፫ ተኛው ዓመት በ፻፴፱ ቁጥር አእምሮ ለደብተራ ገብረየስ ምላሽ ሲሰጡ እስ ራኤልን አርነት ያወጣ እግዚአብሔር እኛን በክህነት አርነት ማውጣት አይችልም ማለቱ ነውን ብለው የጻፉትን ቃል አነበብሁ ግን እስራኤል ነጻነትን እንዲያገኙ እግዚአብሔርን ቢለምኑት ሰጣቸው እንጂ ከግብጽ ጳጳስ በታች ካልተገዛን ክብር አይሆ ነንም ለሚሉ ሕዝቦች አይደለም ። ደግሞም አቶ ማህተመ ወርቅ እሸቴ በ፫ ተኛው ዓመት በ ፱ ቁጥር ብርሃንና ሰላም እስራኤል ደስ ያላቸው መቼ ነው ብሎ ጠየቀን መቼም እሱ የፈለገው ምላሽ ከግብጽ የወጡ ለት ነው ማለትን ነው ። አቶ ማህተመ ወርቅ መቼ ከግብጽ ወጣህና ነው ከግብጽ የወጣህ ለት መልስ እንጽፍልሃለን ።

የኢትዮጵያ ካህናት ሆይ ሕዝቡ በየጆርናሉ የጳጳስን ነገር መጻፉ ሕዝቡ ሊቀ ጳጳስ ወይም ለየወረዳው ጳጳስና ኤጲስ ቆጶስ ለመሆን ፈልጎ አይደለም የዚህ ክብርና ማእርግ ለናንተ ብቻ ነው ሕዝቡ የሚፈልገው የሌላ ዜጋ ተገዢ የሆነ ጳጳስ መጥቶ በኢትዮጵያ የምስጢር ምክር ገብቶ ነጻነቷን እንዳያውክ ብቻ ው እንጂ ሌላ አይደለም ።

የኢትዮጵያ ነጻነት ወዳጅ

በ፱ነኛው ቁጥር መልስ እንድንረዳ ተለምነናልና
በትንሹዋ እውቀቴ ለመርዳት ተመኘሁ ።

ክቡር አቶ ማህተመ ወርቅ እሸቴ ሆይ ። እስራኤልን በጣም ደስ ያላቸው ምን ጊዜ ነው የእግዚአብሔር ኃይል በጣም የታወቀ ምን ጊዜነው ብለው ስለጠየቁ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተመለከትሁት በጭሩ እጽፋለሁ የእስራኤሎች ደስታቸው ከውሐ ዳር የተገኘው የእግዚአብሔር ባርያ ሙሴ የሚባለው ጀግናው ከዚያ ከጨካኝ ዲያብሎስ ከፈርኦን እጅ በታላቅ ፈተና ከባርነት አውጥቶ ነጻነታቸውን ይዘው ከሙሴ ጋር ተሰ ደው በተቀመጡ ጊዜ ነው እንደዚሁም ሁሉ ልዑል ተ መ እንደ ሙሴ ከለም ማያ ውሐ ያገኘናቸው ስለሆኑ አምሳለ ሙሴ ብለ ኢትዮጵያን ሙሉ መንፈሳዊ ነጻነት በሰጧት ጊዜ መታሰ ቢያ መሆናቸውን አመኛለሁ ። ደነቀ ተክለ ጊዮርጊስ ።

የጥያቄ መልስ ።

በ፫ተኛው ዓመት ብርሃንና ሰላም ቁጥር ፱ከአቶ ማህተመ ወርቅ እሸቴ ጋራ ለተጨዋወተ ቀይ ጐበዝ ከብዙ በጥቂቱ መልስ አሳቤ ተንቀሳቀሰ እስራኤልን በጣም ደስ ያላቸውምን ጊዜ ነው የእግዚአብሔርስ ኃይሉ የታወቀ ምን ጊዜ ነው ብሎ ከተ ናገረ በኋላ ፩ድ ሰው ይህን ሊመልስልኝ አይችልም መስሎት ይህ ጥያቄ በድንገት የሚገኝ አደለምና ዘመዶችህን ሰብስበህ ሐሙስ መልስ እንድትሰጠኝ እለምንሃለሁ ስላለ እኔም ወዝንቱ ዘመድ እንዳለው ያይደለ ወአዝማዱ በሥጋ እንዳለው ያለ ዝም ድና አለኝና ከዘመዶቼ ጋራ ይህቺን መልስ እጽፋለሁ

ይህ ቀይ ጐበዝ የጠየቀ ከእስራኤል ትካሻ የግብጽ ቀምበር የቀለለበትንና ፳ኤል ፈጽመው ደስታ ያደረጉበትን ቀኑን ለይታ ችሁ ንገሩኝ ብሏልና ፍጹም ደስታ የተደረገና የእግዚአብሔር ኃይሉ የታወቀ በኤርትራ መሆኑን እናስታውቃለን እግዚአብሔ ርም እንጂ ቢሆን ነዳሪና ማኀደር እየሆነ ሥራውን ይሠራል እንጂ ያለምክንያት ሠርቶ አያውቅም ለዚህም ጥቂት ምሳሌ ዎች እናሳያለን ።

ክቡደ መዝራዕት ሙሴ አሣዕነ ፍርሃትን ከልቡናው አርቆ ከማያውቀው አገር ሄዶ ምክንያት ሆኖ እስራኤልን ከግብጽ አወ ጣቸው እንደዚሁም ለክቡደ መዝራዕት ሙሴ ምሳሌ የሚሆኑ ልዑል ተፈሪ መኰንን ሰውነታቸውን አሳልፈው ለባዕድ ሰጥተው

ከድንቀ‐ርና ባርነት ነጻ ሊያወጡን መገስገሳቸውን አስበ መና ገር ነው ። እንደ እስራኤል ጩኸት ፣ ብርሃንና ሰላም ነው ጩኸ የተናገሩት ከሩቅ እንዲሰማ እንዲሁም ብርሃንና ሰላም ቃሉን ከፍ ከፍ አድርጎ በተናገረ ጊዜ ጽንፍ እስከ ጽንፍ ተሰምቶለታል ኃጢአቱን ሽሎ እንደ ማይሠራ እንደ ፈርዖን በኢትዮጵያ ላይ ተጭኖ የሚኖረው የግብጽ መንፈሳዊ ቀምበር ነው፤እስራኤልለግብ ጽ ባሮች ሆነው እንደ መኖራቸው ከቀድሞ ጀምሬ ዓውቃ የምት ኖረው ኢትዮጵያ እንደማታውቅ ሁሉ መንግሥቷ ነጻ ስትሆን ክህነቷ ነጻነት አጥታ የማያስፈልጋትን የግብጽን መነዋሴ ስት ለማመጥ መገኘቷ ነው ይኸውም ሲገዙ ይገዙ ማለትን ያጠይ ቃል ሙሴ እስራኤልን ቀን በደመና ሌሊት በመብራት እንደ መራ ቸው የናታችን የኢትዮጵያ ልጆች የልዑል ተፈሪ መኰንን ውጋ ጋን እየታያቸውና ባዲሱ ስልጣኔ እየተመሩ ሔደው ከንድኛው ደረጃ ወደ ፱ተኛው ከ፱ተኛው ወደ፲ተኛው መድረሳቸው ነው ። እንደ በትረ ሙሴ ግርማዊት ንግሥታችን መሆናቸውን ያሳያል ፈርዖን በበትረ ሙሴ ምክንያት እንደ ሰጠመ ። እንዲሁም በግር ማዊት ንግሥታችን ዕድሜና ጤና ልዑል ተፈሪ መኰንን ምክ ንያት አድርጋ የኢትዮጵያ ክህነት የነጻነቷን ተስፋ ያሳስባል ባሕረ ኤርትራ የኢትዮጵያ መንግሥት ምሳሌ ናት ፈርዖን ስለ ሰጠመ ክህናተ እስራኤል ፈጣሪቸውን አመስግነዋልና የኢት ዮጵያ ክህነት ንሴብሖ ማለትን ያሳስባታል ።

ይህ ምሳሌ ለሰም እያደላ መጥቷልና የብርሃንና ሰላም ደቀ መዛሙርት ጥልቅ በሆነ ዕውቀታችሁ መርምሩና ወርቁ እንዳያመልጣችሁ ከግብጽ መፈለግ ነው ።

ባለቅኔም ባለፈው ጋዜጣ እንዲህ ብሎ ወስዶታል እግዚአ ብሔር በፍትሕ ዘኢታደሉ ለገጽ አለና ለጽጽስና ዓፀደ ወይን እምጣነ አፍለስከ እምነ ግብጽ ብሎ ነገሩን ደስ ስላለኝ ነው እንጂ ሳይሰማ የቀረ ነው ብዬ አይደለም ሰምና ወርቅ ማለት ይህ ነው ቢሆን የእስራኤል አምላክ ፍጻሜውን ያሳየን ባይሆንም ወዳጃችን ብርሃንና ሰላም በየሳምቱ ከምስጢሩ አይንፈገን ዓሜን ።

የፍታሔ ንጉሤ ።

ስለ አቡን ነገር ከአእምሮ ጋዜጣ የተገለበጠ ።

ከዛሬ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያናችን ነጻ እራሱን የቻለ ለማ ረግ ብናስብ በዚህ በነገር ውስጥ አንድም ሰው ሳይገባበት ለማ ድረግ ይቻላል ። ስለምን ማለት ነጻ የሆነ ሕዝብ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያኑ አለቃ የወደደውን ቢመርጥ ስለሚገባቸው ነው ። ይህን ያህል ዘመን ሃይማኖቱ የበታች ተገዢ ሆኖ የኖረው ይበቃኛል አሁን ግን ነጻ ላወጣው እፈልጋለሁ ብላ ኢትዮጵያ ባለች ጊዜ እንኳን እንደዚህ ያደረገሽ በጅተሻል ኢትዮጵያ እያለ ማንም ሰው ያመሰግናታል ነገሩንም ይረዳዋል ። የኢትዮ ጵያ ቤተ ክርስቲያን ከማንም እጅ ነጻ እንድትወጣ የተገባና የተስማማ ነው ። ስለምን ለኢትዮጵያ ሊቃውንት ክብርና ሞገስ ለሕዝቦቿም ደስታ ስለሚሆን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነጻ የሆነች እራሷን የቻለች ተብላ መጠራት ይገባታል ። የሃይማኖት ነጻነት ከመንግሥት ነጻነት ፖለቲካ ጋር የሞላ ስለሆነ የኢትዮ ጵያ ቤተ ክርስቲያን ከወገኑዋ አለቃ ጋር ነጻ መሆን ኀብርዋ ነው ። ለእንደዚህ ያለው ቁም ነገር ያለበት ጉዳይ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነጻ መውጣት ስለሆነ እንዲህ የሚል አንድ ድምጽ ይሰ ማ ዘንድ ይገባል ፣ ነጻዋ ኢትዮጵያ ነጻ ቤተ ክርስቲያን ትፈልጋለ ች ። ነቢዩ ኤልያስ እስራኤልን እስከመቸ ድረስ ትጠራጠራላችሁ እግዚአብሔርን አምላክ ቢሆን እግዚአብሔርን አምልኩ ቤል ጣዖት አምላክ ቢሆን ቤልን አምልኩ አላቸው ። እንደዚሁም አእ ምሮ ጋዜጣም የኢትዮጵያን ሕዝብ ይጠይቃል የኢትዮጵያ ሕዝብ በአቡን ነገር እስከመቼ ድረስ ትጠራጠራላችሁ የኢትዮጵያን ሰው ሊቀ ጳጳስ መሾም ብትወዱ ቶሎ መሾም ነው የግብጽን ሰው አቡን ብትፈልጉ ሹሙ ነገር ግን የግብጽን ሰው ብትሾሙ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለግብጽ ቤተ ክርስቲያን ዜጋ ተወራጅ ሁና ለዘለዓለም ትኖራለች ። የኢትዮጵያን ሰው ግን ሊቀ ጳጳስነት ብትሾሙ በነጻ መንግሥቱዋ ላይ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነጻ ሁና ትኖራለች ።

ግን የኢትዮጵያ የጀግኖቹ ድምጽ እንደዚህ የሚል አንድ ነው ነጻዋ ኢትዮጵያ ከነጻ ቤተ ክርስቲያን ጋራ ብቻዋን ፡፡

ከኢትዮጵያ ወገን
አቡን እንዲሾም ምኞታቸ ውን የጻፉ ሰዎች ስም ።

የታተመላቸው ።

አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ።
አቶ ማህሉ ጽጌ ።
አቶ ያ ስ ።
አቶ አልዓዛር ወልዱ ።
አቶ አስታጥቁ ወልዳማኔል ።
አቶ ገብረ ጻድቅ ።
አቶ ዘለቀ ደራጅ ።
ልጅ ከማገሀ ።
አቶ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ ሰማዕት ።
ነጋድራስ አፈ ወርቅ ።
አቶ ንዋይ ዘገነተ ጽጌ ።
አቶ ቀየ ንጉሤ ።
ነጋድራስ ደስታ ምትኬ ።
አቶ አክሊሉ ደጀኑ ።
አቶ ወልደ ሚካኤል ።
አእምሮ ።
አለቃ እንግዳ ደስታ ።
አቶ ገብረ እግዚአብሔር ኤልያስ ።
አቶ ኃይሌ መኰንን ።
አቶ ደነቀ ተክለ ጊዮርጊስ ።
ፊታውራሪ ዲሬሳ ።
ልጅ አየነው ገብረ መድኅን ።

ያልታተመላቸው፡

አቶ ደምሴ ወልደ ገብርኤል ።
አቶ ጥሰደሁን ንጉሤ ።
አቶ ክበረ ኃይለ ሥላሴ ።
ብላታ ኃይለ ማርያም ።
አቶ ወልደ ጻድቅ ሀብተ ሚካኤል ።
አቶ አየለ መኰንን ።
አቶ ገብረ ሚካኤል ።
አለቃ ዳኜ ።
አቶ ተገኝ ኃይሉ ።
አባ ወልደ ገብርኤል ።

ከኢትዮጵያ ወገን
አቡን እንዳይሾም ምኞታቸ ውን የጻፉ ሰዎች ስም ።

የታተመ ፡፡

አቶ ገብረ የስ ወልደ መስቀል ።

ያልታተመ ።

አቶ በፈቃዱ ወልደ መስቀል ።

መልስ ።

የአእምሮ ልጆች ብርሃንና ሰላም እሚባሉ ወዳጆቼ ስለ አገር ፍቅር አጥንታቸውን ከስክሰው ደማቸውን አፍስሰው እሚ ሰጡ አሉና የእውቀት ምንጭ እሚባል መሐንድሳቸውን ይዘው የእግዚአብሔርን ምንገድ ጽረጉ በምድረ በዳ ለአምላ ካችን ምንገድ አስተካክሉ የተባለውን ለመፈጸም ሲሄድ ራሳቸውን ለመቻል ደብተራ ገብረየስና አቶ እንደልማድ ሁለቱ ጓደኞች በድቁርና ሥፍራ በምቀኝነት ሠረገላ ሆነው ዕብን እልአማል ያበጀውን ቀምበር ተሸክመው ሲሄዱ ላይን ትንሽ ሆነው ይታዩ ነበር ። የርቀታቸው ብዛት ብርሃንና ሰላም በነ ጠር መስቀል ቢያዩ በጥፋት የተተከለው ብልጥግና አይነቅ ለው እንደሚሉት ተረት ሆኖ እሚቀር መስሎት የጥቁር መስ ቀል አላይም ብሎ ሲሸሽ ፋጠን የተሸከመውን የዕብነ እል ማል ቀምበር አስጥለን ሰባበርነው ደብተራ ገብረየስ ካቶ እንደ ልምዳቸው ከገራትው ፍቅር መና ቀፋክቶ እንደልማድ ጋራ በረሩ እያሉ ሲያሚውቱኝ ከብርሃንና ሰላም ዘለፋ፡ ካቶ እንደ ልምዳ ችን ተስፋ እድነኝ ስል ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች ያገር ፍቅ ራቸውን አለኝተኝነት የ ጋሻቸውን አመክከት አጥብቄ አመሰግ ናለሁ ።

አየነው ገብረ መድኅን ተምቤን

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፫ብር ።
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ፲መሐ ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፲ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፫ብር ፲ መ
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ፲ መ
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፩ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴ ብር ።
። ባለፈረስ	።	፻፵ ብር ።
። ባለ ድመት ።		፻፳፫ብር ።
። ባለአህያ	።	፻፳ ብር ።
። ባለሳቢ ግመል	።	፻፳ ብር ።
። ባለአንበሳ	።	፻፴፮ ብር።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፩ መ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ እስከ ፲ ሣን ነው ።
በአንድ ብር	፲ ሊሬ ፳፭ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ፳፬ ፳፭ሳንቲም ነው
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፩ ብር ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መ ንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነ ዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የ ሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመ ቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶ መቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል ።

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢ ትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈ ልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያ ስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞ ችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመ ቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያ ዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፈታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤኄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ማጥን በየዓይነቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያኄጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

አዲስ አበባ በላጋር ጕዳና ላይ በሙሴ ተረስ ሆቴል አጠገብ አንድ ክፍል የሙሴ ሳቡሬ ቦታ ከነቤቱና ከነዛፉ ይሸጣል ፡ ቦታውን ለመግዛት የሚፈልግ ሰው በሙሉ ወይም በገሚስ አለዚያም የሚችለውን ያህል ክፍሎ ለመግዛት ይችላል የቦታውም ስፋት ፰ሺ ሜትር ካሬ ነው ፡ ለመግዛትና ለማየት የሚፈልግ ሰው ሙሴ ሳቡሬን ይጠይቅ

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ቤተ ሳይዳ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሆፒታል በመጋቢት ፮ ቀን ይከፈታል ። ሕመምተኛውንም ከጧቱ በሶስት ሰዓት ጀምረው እስከ ዮድስት ሰዓት ከእሁድ በቀር ይቀበላሉ ሕመምተኛም የሚጠይቁ ሰዎች ከሶስት ሰዓት እስከ ስድስት ሰዓት ይፈቀድላቸዋል ። ከስድስት ሰዓት በላይ ግን በተለየ ከሐኪሙ ፈቃድ መጠየቅ አለባቸው ።

ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ አቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

AMENAK ZAMANIAN

AGENT GÈNÈRAL

Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኤዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶከለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶከለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፡ ቁጥር ፲፬
3 me' ANNÉE № 14

ሐሙስ መጋቢት ፰ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 17 MARS 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix ; a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ። Gabré Christos Taklé Haymanot Diręcteur	የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።	Abonnements Ethiopie: Un an 5 Thalers Etranger: Un an 7 Thalers le numero 2 piastres

መልስ

ክቡር አቶ ማኅተመ ወርቅ እስራኤል መቼ ነው ደስ ያላቸው እግዚአብሔርስ ፈጽሞ ደስ ያለው መቼ ነው ብሎ ስለ ጠየቀው የትሕትና ጥያቄ መልስ የተቻለኝን ያህል መልሱን አመለክታለሁ ።

ወንድማችን አቶ ማኅተመ ወርቅ ይህን ጥያቄ የጠየቀ ስለ ሁለት ነገር ነው ፡ አንደኛ የበጎ ሥራ ሁሉ መጀመሪያ ትሕትና ነውና የብርሃንና ሰላምን ማኅበር ለማክበር ነው እንጂ ዕውር በዳሰሳ የሚያገኘው ምሥጢር ተሰውሮት ይሆናል የሚል ይገኝ አይመስለኝም ፡ ባገራችንም ልማድ ነው ዲያቆን ለወንጌል መስበክ ከመቅደስ ወጥቶ ምስማኩን አጥንቶ መስቀሉን ይዞ ቆሞ ሳለ ማን ልበል ብሎ ስለ ትሕትና ሊቃውንቱን ይጠይቃል እንጂ ቀለሙን ካወቅሁት ድምጡ ካማረ ብሎ እንዲያው ደርሶ አይሰብክም (አይሬጭህም) ሁለተኛም ወደው ይቀበሉት ማለት ይመስላል ፤ ለኔ ግን እንደሚመስለኝ እንኳን ፲፱፻፲፰ ዘመንና ፲ ዓመት ያገለገለ የተገዛ ባሪያ ነፃ ቢወጣ ለደስታው ልክ የለውም፡ከፍጡር ባርነት ወደ ፈጣሪ ባርነት ከመሄድ በቀር ሌላ ምን ደስታ ይገኛል፡ምንም አንዳንድ የሰይጣን ቁራኛነት ያልለቀቃቸው የፈርዖንን ፍርፋሪ የበላ የግብጽን ጉድጓድ ወሀ የጠጣ ብፁዕ ነው ቢሉ ይኸውም የአግብርተ እግዚአብሔር እስራኤል ክብራቸው ነው ከአግብርተ ሰይጣን በመለየታቸው ፡ የእግዚአብሔርንስ ኃይሉን ፍጡር ተናግሮ ሊፈጽመው እንደማይቻል ክርስቲያን ይቅርና አሕዛብ ሳያውቁት አይቀሩም።ግን ባሪያ በጌታው ላይ ሲታበይ መንግሥት ተከፋይ ሲሆን ፲ ጊዜ አማላጅ መላክ ግሩም ነውና የአንክሮ ደስታ እናቀርባለን እንጂ ሸክላ ሠሪ ሸክላውን ቀጠቀጠውት ብሎ ከደስታ አይቆጠርም ጥያቄም አያሰፈልግም ።

እግዚአብሔርስ እኛ ኃጢአት ስንሰራ ማለት እውነቱን በሐሰት ጽድቅን በኃጢአት ስንለውጥ ያዝናል እንጂ ዘለዓለማዊ ደስታ ያለው ንጉሥ እንደሆነ እምናለሁ ።

ስለ ሥርዓት ማሻሻልም አንዳንድ ሰዎች ስለ መንፈሳዊ ቅንዓትና ስለ ኢየሱስ ፍቅር ተናደው አሳባቸውን በብርሃንና ሰላም ስለ ገለጡ ኢትዮጵያ በብሉይ በሐዲስ ከተመሠረተ ሃይማኖቷ የምትናወጥ አስመስለው ያወራሉ።እንዲህ ያለው አሳብ ከጥንት የተጀመረ ነው ዲያብሎስ ከሔዋን ዘንድ መጥቶ ከገነት መካከል ካለችው ፍሬ አትብሉ ያላችሁ ስለምን ነው ብሎ ጠየቃት እውነተኛ መስሏት እንዳንሞት ነዋ አለችው እንዳትሞቱ ብሎ አይደለም አምላክ እንዳትሆኑ ክፉና መልክም እንዳታውቁ ብሎ ነው እንጂ አላት።ከዚህ ወዲያ ሰተት ብላ ከወጥመዱ ገባች ። ኢትዮጵያም ከሃይማኖት ትናወጣለች ማለት የዲያብሎስ ተከታይ መሆን ነው ።

ዳግመኛም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በርኅራሔውና በጸጋው የሠራልንን ሥራ ሁሉ ማመንና መውደድ፡ እሱን መውደድ ሥራውን መጥላትና አለማመን እሱን መጥላት እንደሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት በብዙ ሥፍራ እናያለን ፡ ግብ ሐዋ ም ፱ ቁጥ ፬ ሳውል ለምን ታሳድደኛለህ ብሎ የምዕመናንን ጉዳት ለራሱ አድርጎ ፡ ማቴ ም ፳፭ ቍ ፵ ፡ ብራብ አላበላችሁኝ ብሎ በሌላውም ሥፍራ በኔ ላመኑ ምዕመናን አለማድረግ ለኔ አለማድረግ ነው ብሎ ከተናገረ ለዓለሙ ሁሉ ያደረገውን ነፃነትና ቸርነቱን ለኢትዮጵያ ብቻ ከቀረበት የጌታችን ካሳ ጎደሎ ነው የኢትዮጵያም ሃይማኖት እንደ ጨቅላ ልጅ በሞግዚት ዘላለም ሲጠበቅ መኖሩ ነው ማለት ይሆናል ።

ክቡራን የኢትዮጵያ ሊቃውንት መምሕራን በእኛ ጊዜ ሥርዓት ተለወጠ እንባላለን በማለት ነው እንጂ ዝምታችሁ

የውነቱስ ፍሬ ነገሩ ከልባችሁ በቅሎ ካንደበታችሁ ላይ አፍርቶ ላይን ያስጎመጃል ።

ሥርዓትም እየተሻሻለ እንደመጣ ማለት ሕገ ልቡና በኦሪት ፡፡ ኦሪት በወንጌል እንደ ታደሰና እንደ ተሻሻለ አስተምራችሁናል ፡፡ ደግሞ ይህን ሁሉ የሠራ አብነታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፡፡ እሱ ሠርቶ እሱ አፈረሰው በሱ ጊዜ አዲስ ሕግ መጣ ይሉኛል አላለም ፡፡ መምራችሁ ጌታችሁ እንዲህ ካደረገ ይህ ይሉኝታ ከወዴት መጣ?እንግዲህ ይህ ነገር እውነት እንደ ሆነ በነሱ ጊዜ ተደረገ ብሎ ክፉ ወቃሽና ተቃዋሚ የለብንም ፡፡ ያለፈው ትውልድ ተመልሶ እንዳይወቅሰን ለጭቅጭቅና ለወቀሳ የሚለቀው የለም ።

ወደፊትም የሚነሳ ትውልድ ይወቅሰናል እንጻንል ሕግና ሥርዓት እየተሻሻለ መምጣቱን ተርከን ጽፈናል ። ወይም አባቶቻችን ሰለስቱ ምዕት የጻፉልን ፍትሐ ነገሥት የኢትዮጵያን ነፃነት አልፈቀደም እንዳልን ለካ እሱም እንደእኛው ሰነፍ ኖሯል ፡፡

ያሸከሙትን ሸክም ቀላል ዕብነ ዕልዓዛል ከባድ ነገር እንስቶ መጫኑ እጅግ የሚገርም ነው ግን ዋቢ እንዳለው ማን ያውቃል እስቲ ጴጥሮስ ወልደ አብድ ሰይድን እንመርምር አምላክ ብርሃን ወሰላም ይርዳን ፡ አለቃ ዳኜ፡

የ፸፭ ገጽ ተከታይ ።

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

፲፩ኛ ክፍል ።

እነሆም በላይኛው ክፍል ሁለት ሶስት ጊዜ ያህል እየመላለስን የባንክን ስም አነሣን ፤ ባንክ ማለት ምን ይሆን ፤ የሚገባበትስ ምክንያት ምን ይሆን ። እስቲ እንመልከትና እንመርምር ።

በዱሮ ዘመን በኤሮፓ አንዳንድ ሰውና ነጋዴው ያገኘውን ብር ወርቅ በየቤቱ ሲያስቀምጥ ነበር ብርና ወርቁም እንዳይጠፋበት ሰው ሁሉ እርሱው ራሱ ሲጠብቅ ነበረ።በኋላ ግን ደህና ቤት ሠርተው ጥቂት ዋጋ እየተቀበሉ ያመናቸውን ሰው ሁሉ ብርና ወርቅ የሚያስቀምጡ ሰዎች ተገኙ ። እነዚህም የገንዘብ አስቀማጮች የሚበዙት የብርና የወርቅ ሠራተኞች ነበሩ ። ብርና ወርቁንም በተቀበሉ ቁጥር ፊርማቸው ያለበትን የደረሰኝ ወረቀት ሲሰጡ ነበሩ ። በኋላ ግን በኢጣሊያ አገር ገንዘብ እየተቀበሉ የሚያስጠብቁና ገንዘቡን ካንዱ ቦታ ወደ አንዱ በኀወላ የሚሰዱ ባንክ የሚባሉ ማኅበሮች ቆሙ ። ለዚሁም ሥራቸው ከገንዘብ አስቀማጩ ወይም ስዳጁዋን ሲቀበሉ ነበሩ ይህም የባንክ ሥራ በቀሩት የኤሮፓ ነገሥታት አገር በጊዜ ብዛት ተለመደ ፡፡ እነሆም ወደ ሺ፩፻ ዓመተ ምሕረት ግድም በሆላንድ አገር በምስቴርዳም ከተማ የብርና የወርቅ አደራ አስቀማጩ ማኅበር ቆመ ፡፡ የአምስቴርዳም ባንክ ተብሎም ተሰየመ ፡፡ ይህም የአምስቴርዳም ባንክ በመጀመሪያ ዋና ሥራው አደራ የሰጡትን ገንዘብ ማስቀመጥ ነበረ ። አደራ የሚያስቀምጡም ሰዎች ሲያስቀምጡም ሲያወጡም የጠባቂነት ዋጋ ለማህበሩ ዋጋ ሲከፍሉ ነበሩ ። አደራ አስቀማጮች እንዳይከሥሩ ግን የሆላንድ መንግሥት ራሱ ዋስ ሆነ ፡፡ ባንክም በመቆሙ ለሆላንድ ሕዝብ ትልቅ ጥቅም ሆነ ዱሮ እያንዳንዱ ሰው ያለውን ብርና ወርቅ እራሱ ሲያስቀምጥ ወይም ደግሞ እሱ እራሱ ላመነው ሰው አደራ ሲሰጥ አሳብ ይበዛበት ነበረ ። መንግሥት የተዋሰው የታመነ የገንዘብ ማስቀመጫ ቦታ ከቆመ በኋላ ግን ለያንዳንዱ ሰው አሳብና መጨነቅ ቀረለት ፡፡ ይህም የባንክ ሥራ እያደረ ለሕዝቡ የበለጠ ጥቅም ሆነ ። በመጀመሪያ በባንክ ያስቀመጠውን ገንዘብ ለሌላ ሰው አሳልፎ ሊሰጥ የፈለገ ሰው ሁሉ ባለቤቱ እየሄደ ሲያሰጥ ነበረ ፡፡ በኋላ ግን ለእገሌ ይህነን ያህል ስጡልኝ ብሎ በፊርማው ካስታወቀ ዘንድ ይበቃል ተብሎ ተደነባ ፡፡ ይህም ደንብ ትልቅ ጥቅም ሆነ ። የገንዘቡ ከፋይና የገንዘቡ ተቀባይ ብርን ሲቆጥሩ ብዙ ጊዜ በከንቱ ሲሄድባቸው ኑሮ አረፉ ፡፡ እንደ አምስቴርዳም ባንክም ዓይነት በጊዜ ብዛት በኤሮፓ ትልልቅ ከተሞች ሌሎች ባንኮች ቆሙ ፡፡ ከዚህም ባንኮች ቀጥለው የዲስኮንቶ የሚባሉ ባንኮች ወጡ ። ዲስኮንቶ ማለት የሂሳብ ትርፍ እንደ ማለት ያህል ነው ፡፡ እነዜህም የዲስኮንቶ ባንኮች የቆሙት በማኅበር ገንዘብ ነበርና ሥራቸው ሁለት አይነት ነበረ አንዱ የማህበሩን ገንዘብ እያበደሩ የዲስኮንቶ ወይም የሂሳብ ትርፍ ማግኘት ፡፡ የዲስኮንቶ ወይም የሂሳብ ትርፍ ማለትም ወለድም እንደ ማለት ያህል ነው ፡፡ ሁለተኛው ያደራ ገንዘብ እየተቀበሉ እየጠበቁ ካደራ ሰጭዎቹ ሲቀበሉ ነበሩ ።

በዚህም አዲስ አይነት ባንኮች የሕዝቡ ጥቅም አደገ። በፊት እያንዳንዱ ሰው ያለውን ገንዘብ ሁሉ በየቤቱ ሲያስቀምጥ ገንዘቡ ለርሱም ላገሩም ጥቅም አልሆነውም ወለድ እንዲያመጣለትም ሲል ገንዘቡን ቢያበድር ከትርፉ ጭቅጭቁ እየበዛበት እያንዳንዱ ሰው ያለውን ብርና ወርቅም ዝም ብሎ ቀብሮት ሲቀመጥ ነበረ ፡፡ በኋላ ግን እነዚህ ባለገንዘቦች ተባበሩ ከመካከላቸው አለቆች መረጡ ገንዘባቸውንም ባንድነት ሰብስበው እነዚህ የተሾሙት አለቆች ስለ ማህበሩ ጥቅም እያበደሩ ወለድ ሊያተርፉበት ፈቀዱ ።

ማኅበረተኞቹም ያገቡትን ገንዘብ ልክ የሚያሳዩበት የምስክር ወረቀቶች ተቀበሉ፡፡ይህ እንደዚህ ሆኖ የተሰበሰበውም ገንዘብ ለባለ ገንዘቦቹም ለሕዝቡም ትልቅ ጥቅም ሆነ ። ዱሮ በያንዳንዱ ባለ ገንዘብ እጅ ሳለ ሥራ ፈትቶ ኑሮ አሁን ባለመሬት ወይም ነጋዴ እየተበደረው ይሠራበት ጀመረ ፡፡ በዚሁም ለባለገንዘቦቹ ወለድ አመጣላቸው ፡፡ ተበድረው የሰሩበትም ሰዎች ትርፍ አገኙበት ። ጥቅሙም በዚሁ ብቻ አላለቀም ፡፡ ባንኩንም ያቆሙት ማኅበረተኞች ገንዘብ ባስፈለጋቸው ቁጥር በእጃቸው የያዙትን የማህበር የምስክር ወረቀት ለመሸጥና ለመለወጥ ተፈቅዶላቸው ነበርና በባንኩ የተሰበሰው ገንዘብ አንድ ሳለ በሁለት ፊት ተሠራበት ፡፡ ተበዳሪዎቹ በተበደሩት ገንዘብ ሲሸጡ ሲለውጡ አበዳሪዎቹ ከማህበሩ የተቀበሉትን የምስክር ወረቀት ሸጠው የፈለጋቸውን ነገር ሁሉ ለመግዛት ተቻላቸው ፡፡

እነሆም በዚሁ አዲስ ጥበብ አንዱ የለውጥ መሳሪያ ስለ ሁለት እየሆነ ስለ ሠራ ባገራቸው ባንክ ያቆሙ ሕዝቦች መለዋወጣቸው እየፈጠነላቸው በውስጣቸው ያለው እያንዳንዱ ሠራ

ተኛ በያዘው ሥራ ተጋ ስለጠነበትም ። የሕዝቦቹም ሀብት እየደገ ሄደ ። ጥቂት ጊዜም ይህነን ሀብት የሚያሰፋ ሌላ መንገድ ተገኘ ። በመጀመሪያ እያንዳንዱ ሰው በባንክ ገንዘቡን አደራ ያስቀመጠ ሰው ሁሉ ባንኮቹ ገንዘቡን ስለ ጠበቁለት ከገንዘቡ ክፍሎ ዋጋ ሲሰጣቸው ነበረ ።

በኋላ ግን ገንዘባቸውን በባንክ የሚያስቀምጡ ሰዎች ሁሉ ባንድነት ተሰብስበው ያስቀመጡትን ገንዘብ ባንድ ጊዜ ከባንክ እንዳያወጡ ታየ ። ብልሃትም ወጣበት ፤ ባንኮቹ ሰው አደራ ከሰጣቸው ገንዘብ ከፍለው ለታመኑ ሰዎች እያበደሩ ወለድ ያተርፉበት ጀመሩ ። በዚሁም የሚበቃ ትርፍ አግኝተው ከባለ ገንዘቦቹ እንደ ዱሮ የጠባቂነት ዋጋ መፈለጋቸውን ተዉት ይህም አዲስ የባንክ ደምብ ሕዝቡን በሁለት ፊት ጠቀመ ። መጀመሪያ አደራ አስቀምጡልኝ ብሎ ገንዘቡን ለባንክ የሰጠ ሰው ገንዘቡን እንዳይሠረቅ ወይም እንዳይቀማ አውቆት አሳብና ጭንቅ ቀረለት ። ወዲያውም ገንዘቡን ለጠባቂዎች ሲሰጥ ዋጋ የማይወስድበት ሆነ ። ገንዘቡንም ከባንክ በፈለገ ጊዜ ሲያወጣ ከቤቱ ሳይንቀሳቀስና ሥራ ሳይፈታ ወረቀት አስይዞ አንዱን አሽከሩን እየላከ ገንዘቡ እስከቤቱ ድረስ ይመጣለት ጀመር ዕቃም ገዝቶ ገንዘብ ሲከፍል የሚከፍለውን ገንዘብ ሲቆጥር ጊዜው በከንቱ ሳይባክንበት ሼክ የሚባለውን ይህን ያህል ገንዘብ ለእገሌ ስጡ የሚለውን ትኒሽ ወረቀት ጽፎ ዕቃውን ለሸጠለት ሰው ሰጥቶ ወደባንክ ሊልክ የሚበቃ ሆነ በየባንኩም በአደራ የተቀመጠ ገንዘብ ሁሉ ጌታው መልሶ እስኪወስደው ድረስ በሠራተኞች ሰዎች እጅ ገብቶ ሲሠራ ለመላው ሕዝብ ጥቅም ሆነ ። ብርና ወርቅ እኮ የለውጥ መሣሪያዎች ናቸው እንጂ ሌላ ብልሃት የላቸውም ። ሕዝቡም እርስ በርሱ ሲለዋወጥ ካልረዱ በያንዳንዱም ሰው ቤት ውስጥ ከመሬት በታች ቢቀበሩ ለባለ ገንዘቡም ለመላውም ሕዝብ አንዳች ጥቅም ሊሆኑ አይችሉም ። ሥርዓት በሌለበት አገር የሰው ርስትና ገንዘብ በማይታፈርበት በማናቸውም ትንሽ ምክንያት ሰው በብዙ ድካም ያከማቸውን ገንዘብ በሚወረስበት አገር ውስጥ ግን ብርና ወርቅ ምንስ ቢበዙ በያንዳንዱ ሰው ቤት እየተሸሸጉ ይኖራሉ ። እንጂ በሚገባ አይረዱም ።

የተደላደለ ሥርዓት በሌለበት አገር ሁሉ ሕዝቡ እርሱ በርሱ ካለ መተማመኑ የተነሣ ያለውን ወርቅና ብር ሲሆን ይቀብረዋል ፤ ያለዚያ ግን እንደ ጌጥ አድርጎ በሚመክትበት ጋሻ ላይ ይለጥፈዋል ። ወይም በሚዋጋበት ፈረስ መጣምር ያደርገዋል ። ወይም ጐራዴውን ያስጌጥበታል ። እውቀት የሌለውም ሕዝብ ይህነን የመሰለውን ጌጥ ሁሉ መውደዱ ዋና ምክንያቱ ባለው ብርና ወርቅ ሌላ ሥራ ሲይዝበት መሰናከያ ነገር እንዲበዛበት ሰውነቱ እያወቀበት ነው ። ከዚህም ምክንያት የተነሣ እውቀት የሌለው ሕዝብ ሁሉ ተመችቶት እንዲኖር ቢፈልግ እንደማይሆንለት ያውቃልና ምቹ ኑሮ እንዲያገኝ መጣሩን ትቶ ለጌጥ ያስባል ። በእንደዚህ ያሉ እውቀት ያነሣቸውም ሕዝቦች ውስጥ ብዙ ሰው አምስት ብር የሚያወጣውን ልብስ ለብሶ የጋሻውና የፈረሱ ጌጥ ወደ ሁለቱ መቶ ብር የሚያወጣ ሆኖ ቢገኝ የሚገርም ነገር አይደለምን ሰው ከውጭ ይልቅ የቤት ምቹነት የሚያስብ የተደላደለ ሥርዓት ሲያገኝ ነው ። ያንዱ አገር ሥርዓት ግን ምንስ የተደላደለ ቢሆን ለሌላው አገር ሕዝብ የተመቸ ሥርዓት አይሆንም ። ሕዝብ የሚወድ ለባሕሪው የሚመች ሥርዓት ሲያወጡለት ነው ። ስለዚህም አንዳንዱ የሀገራችን መኳንንት ወይም ሹማምንት አስቀድመው የትምህርት ቤት ሳያቆሙ የኤውሮፓን ሥርዓት እናግባ ብለው ቢጥሩ ከንቱ ድካም ነው ።

እነሆም ሥርዓት የሚመች ይሆናል ተብሎ በብልሆች ሰዎች ልብ ውስጥ ተፈጥሮ አይጻፍም ከሕዝቡ ልብ ይቀዳል እንጂ ። ንጉሥ ወይም ሹም በኋለኞች ትውልዶች የሚመሰገንም በልቡ ፈልስፎ ደንብ ሲያወጣ አይደለም ። የሕዝቡን አሳብ ተርጕሞ በትርጕሙ ሲሄድ ነው እንጂ ። የኤውሮፓ ሕዝቦች የዛሬ ሥርዓታቸው ባንድ ቀን አልተደነባም ። በዘመናት ብዛት የተጣራ ነው እንጂ ፤ ስለ ዚህም የሕዝቡ እውቀት እየሰፋ ሲሄድ ለወደ ፊት ደግሞ እንደ ገና እየተጣራ ይሄዳል ። ስለዜህም ባገሩ የኤሮፓን ሥርዓት ሊያገባ የሚፈልግ መንግሥት አስቀድሞ የትምሕርት ቤት አቁሞ ለሕዝቡ የኤሮፓን ባህል ማስተማር ያስፈልገዋል ። እንደዜሁም አድርጎ ሕዝቡን ካሰለጠነ በኋላ የኤሮፓን ሥርዓት ባገሩ ቢያገባ ሕዝቡ ይጠቀማል ፤ እርሱም ይበረታል ። ትምሕርት በሌለበት አገር ለሥርዓት የሚሆን መሠረት አይገኝም ። ሥርዓት የሚፈለግ በትምሕርት ነውና ትምሕርት የሌለው ሕዝብ ሥርዓት አይወድም ። አይጠቅመውም ስለዜህም ዛሬ የኢትዮጵያ መንግሥት አዲስ ደንብ ያወጡልኛል ሲል ለውጭ አገር ሰዎች ደመወዝ በያመቱ ቢከስር መሰረት ያለው ጥቅም አያገኝም ። የትምሕርት ቤት አቁሞ ሕዝቡን ቢያስተምር ግን የሚያስፈልገው ደንብ ምንድር እንደሆነ በኋላ ሕዝቡ ራሱ ያውቀዋል ፤ ይረዳዋል ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት ነው።

ስለ እጅ ጥበብ ትምሕርት ።

በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት የቋንቋ ትምሕርት እየሰፋና እየሰለጠነ በመሄዱ ደስ አሰኝቷል ። እንደዚሁ ሁሉ የእጅ ሥራ ትምሕርት በተማሪ ቤታቸው እንዲሰፋና እንዲሰለጥን የልዑል አሳብ ስለሆነ የእጅ ሥራ ትምሕርት የሚያስተምሩ የኢትዮጵያ ልጆች ለዚሁ ሥራ ቁመዋል ። ከዚህ በፊት ለማስተማር የቆመው የእጅ ሥራ ተማሪ ቤት እንጨት ማነጥና ሸማ መስራት ነው ። ያናጢነት ሥራ አስተማሪ አቶ ገብረ መድኅን ናቸው ። የሸማ ሥራ የሚያስተምሩ አቶ ማማስ ጐሹ ናቸው ። ልጆቹም ይህ የእጅ ሥራ ትምሕርት ደስ ደስ እያላቸው በመጋዝ ሲሰነጥቁና በመላጊያ ሲልጉ እጅግ ያምራሉ ።

እንደዚሁ ደግሞ የሸማሥራ የተከናወኑ መኪናዎች መጥተው ላቸው ሠራተኞቹ መኪና መኪናቸውን ይዘው ሲያወዛውዙት የመኪናው አፈጣጠንና የሥራው ማማር በጣሙ ደስያሰኛል ።

ይህ የትምሕርት መጀመሪያ የሆነ የጅ ሥራ እየገፋና እየሰፋ እንዲሄድ ሌላውም ያልተጀመረው የጅ ጥበብ ሥራ እንደዚሁ በፍጥነት ተጀምሮ እንድናይ ሙሉ ተስፋ አለን ።

ከዚህ ከባድ ቀንበር ማን ያወጣን ይሆን ? እህህህህ ።
ቆዩ ፤ ቆዩ ፡ ቆዩ ፡ ብልሃቱ ተገኝቷል ።

ከባዱን ቀንበር ከኛ ላይ ሰባብረህ የምትጥል ፤ ድካማችን ንም የምታቀል ምስጋና ላንተ ይሁን ።

አንድነት ያበረታል ። መለያየት ግን ያደክማል ።

ይድረስ ለክቡራን መምሕራነ ዘመን ብርሃንና ሰላም ሰላምታ አቀርባለሁ በአቶ ገብረ ኢየሱስ ወልደ መስቀልና በአቶ ማኅተመ ወርቅ እሼቴ መካከል ስለ ተነሳው ንግግር የጻፋችሁትን ቃል ሰማሁ ሰምቼም በውነት መስክሬ ለማስታረቅ የጻፍኩትን ጥቅስ ልኬላችኋለሁ የነገር መጀመሪያ ለቀይ ለጥቁር አያሰኝ ሰማሁን አቶ ገብረ ኢየሱስ አንተስ እንደዚህ ያለውን ነገር ተየት አገኘኸውና ጻፍከው ከመጻሕፍትን ነው ከሊቃውንት በዚህ ነገር አቶ ማኅተመ ወርቅ ብቻ የተጐዳ አይደለም ኢትዮጵያ የወለደችው ሁሉ ታውኳል እንጂ ብርሃንና ሰላም የሚአነቡ ሰዎችም ሁሉ እውነት ይመስላቸዋል ጌቶቻችን በባቶቻቸው ልማድ ቢአመጡልን ይባላል እንጂ ግስ ገሶ መጽሐፍ ጠቅሶ ብሥርናን መልቀቅ እንዴት ይሆናል እስክንድርያ ኢትዮጵያ ማለት ያገር ስም ነው ከኢትዮጵያ ተወልዶ እስክንድርያ እናታችን ማለትም ውሸት ነው እስክንድርያ እናታችን ማርቆስ አባታችን የምንል ሰዎችም ሁሉ ኢትዮጵያ እናታችን እግዚአብሔር አባታችን ብንል የምንጐዳ ሆኖ አይደለም የንግግር ልማድ ነውና አይልመድህ ሰሚ አንባቢም ሁሉ ልብ አድርጉ በጥምቀት ይቀደሙናል በሃይማኖት ይመስሉናል እንጂ በክብር በሹመት አይበልጡንም ።

መጀመሪያ

ለመንፈሳዊ ሹመት እምነት እ[illegible]ጂ ቀይና ጥቁር እንዳይመረጥ እለ ጸውአ ውስተ ክብሩ ወአስተጋብአ አኮ እምአይሁድ ባሕቲቶሙ ዳዲ እምአረሚኒ በከመ ይቤ ሆሴዕ ነቢይ እሬስዮ ሕዝብየ ለዘኢኮነ ሕዝብየ ወእሬስያ ፍቅርትየ ለእንተ ኢኮነት ፍቅርትየ ወይከውኑ ኵሎሙ እለ አምኑ ውሉደ እግዚአብሔር ኢሳይያስኒ ይቤ በእንተ እስራኤል ለእመ ኮነ ኍልቆሙ ለደቂቀ እስራኤል ከመ ኆፃ ባሕር እለ ተርፉ ይድኅኑ ብኋል ጳውሎስ በሮሜ ፱ም ፳፯ ቁጥር ።

ዳግመኛም

ወባሕቱ ርቱዕ ይሠየም ጳጳስ ዘኢያደሉ ለገጽ ወዘአልቦ ምክንያት ንቁሕ ወጠቢብ ወመፍቀሬ ነግድ ዘአንጽሐ ርእሶ መምሕር ወመገሥጽ ዘኢያበዝኅ ሰትየ ወይን ወኢያፈጥን እዴሁ ለዘቢጥ ወኢያፈቅር ንዋየ ዘሠናይ ሥርዓተ ቤቱ ይሰየም ጳጳሰ ወእንተ ተዓቢ ሢመተ ይግበሩ ሎቱ እለ እንጂ ቀይ ጥቁር አላለም ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ፫ ም ፫ ቁጥር ።

ዳግመኛም ፡ ለጢሞቴዎስ እመቦ ዘአንጽሐ ርእሶ እምዝ እኩይ ይከውን ንዋየ ክብር ቅዱሰ ወባቁዓ ለመልእክተ እግዚኡ ወድልወ ለኵሉ ምግባረ ሠናይ አለ እንጂ ቀይ ጥቁር አላለም ፪ ም ፪ ቁጥር ።

፫ቱ፻ ም ወለሕዝባዊኒ ሶበ ኮኑ ስምዓ ከመ ውእቱ ድልው ለነሢአ መዓርገ ቅስና ኢይስድድዎ በእንተ ዘኢኮነ እምዘመደ ካህናት እስመ ቤተ ክርስቲያን ወለደቶሙ ለኵሎሙ በጥምቀተ ክርስትና ወፈድፋደሰ ለዓቃብያነ ሕግ ወይቤ ጳውሎስ ሐዋርያ ኵሎሙ እለ ተጠምቁ በክርስቶስ አሐዱ እሙንቱ በክርስቶስ አለ እንጂ ቀይ ጥቁር አለየም በአንቀጸ ካህናት ፺፭ ።

ዳግመኛም ፡፡ አምኖ የተጠመቀ ሁሉ እኩል እንደሆነ ሲአጠይቅ ዘአምነ ወዘተጠምቀ ይድኅን ። ወዘኢአምነ ይደየን ብሎ ለእለ አምኑ በስመ ዚአየ ይትልውዎሙ ለሐዋርያት ወያወጽኡ አጋንንተ ወይትናገሩ በካልእ ልሳን አለ ጌታ በወንጌል ማርቆስ ፲፮ም ፲፯ ቁጥር ። ጥዑመ ልሳን፣

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

የከተማ ወሬ ።

ስለ ክቡር ራስ ጉግሣ አርአያ ።
ከትግሬ ወደ አዲስ አበባ መግባት።

ክቡር ራስ ጉግሣ አርአያ ከትግሬ ወደ አዲስ አበባ መጋቢት ፩ ቀን ገቡ ብርሃንና ሰላም እንኳን ደኅና ገቡ እያለ ደስታውን ይገልጻል ።

ስለ ቀኛዝማች በየነ ሀብተ ማርያም ሞት ።

ክቡር ቀኛዝማች በየነ ሀብተ ማርያም መጋቢት ፺ ቀን አርፈው በመጋቢት ፺ ቀን በዑራኤል ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበሩ ብርሃንና ሰላም ለክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያምና ለባለቤታቸው ለዘመዶቻቸውም ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል

የውጭ አገር ወሬ ።

ፋሺስትና ኢትዮጵያ ።

በኤውሮጳ ከተነሳው ጦርነት ወዲህ በጣልያን ሕዝብ መሃከል ጉልበት እያደረገ የሄደው የፖሊቲክ ወገን ፤ ፋሺስት ይባላል ። ፋሺስት ፋሺስ ካለው ከላቲን የመጣ ቃል ነው ። ትርጉሙ በንድነት የታሠረ ዘንግ ማለት ነው ። በሮማውያን ዘመን የቤተ መንግሥት ሹም ወደ አደባባይና የሹመቱን ሥራ ሊሰራ ወደሚሄድበት ስፍራ ሲወጣ በትክክል ተከርክሞ ከሶስት ከአራት ላይ በንድነት የታሠረ አያሌ ዘንግ ከትከሻው ላይ ያደረገ ወታደር በስተ ፊቱ ይሄድ ነበር ። ይህም አንድነት ብርታት እንደ ሆነ ለማሳየት ተብሎ የተደነገገ ሕግ ነበርና ምሳሌው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነበር ። ዛሬ ደግሞ በጣልያን ሕዝብ ውስጥ በፖሊቲክ የበረታው ወገን ፋሼስ ካለው ፋሺስት በሉኝ ብሎ ይህን ሰላማዊ ዘንግ የመለዮ ስም ቢያደርገው ሰው አልጠላለትም ። የፋሺስት ወገንም ላገሩ በብዙ ነገር ረድኤት ሆኖታል ። ነገር ግን ከርሱ በፊት አገሩን ይዘው የነበሩትን የፖሊቲክ ወደረኞቹን አጥቅቶ የጣልያንን አገር እጅ እስኪያደርግ ድረስ የሠራውን ሥራ ቢመለከቱት ፡ በኃይል በግፍና በማስጨነቅ እንጂ በትዕግሥትና በምክር ያቀናው ሥራ እጅግ ታናሽ ነው ። የፋሺስት አለቃ ሙሶሊኒ ይባላል ። ይህም ሙሶሊኒ ሕዝብ አማካሪነት የሰደዳቸውን ሸማግሎች ምክሩን አልቀበልለት ሲሉ ዓይኑን አፍጦ አፋችሁን ይዛችሁ እኔ የምሠራውን ሁሉ ዝም ብላችሁ እዩ የሚል ጉበዝ ነው ። ነፃነት እጅግ በተወደደበትና በከበረበት በጣልያን ሕዝብ መሃል እንዲህ አድርጎ እንቀጥቅጦ የሚገዛው ሰው በሰላም ማደሩ አገራቸውን ለምናውቀው ሰዎች እጅግ እጅግ ያስገርመናል ። ከጦርነቱ በፊት ኋላም ፋሺስት እስኪነሣ ድረስ በጣልያን አገር ነፃነት የበዛበት ስለ ሆነ በዋና በዋናው የመንግሥት ጉዳይ ሥራቸው የታወቀላቸውና ስማቸው የተጠራው ሰዎች ብዙ ነበሩ ። አገሩን የፋሺስት ወገን ሳይዙት ፡ ከያዙት ወዲህ ግን የሙሶሊኒ እንጂ የሌላ ሰው ስም ሲጠራ አይሰማም ። ሙሶሊኒ በገራቸው ፡ ሙሶሊኒ በውጪ ጉዳያቸው ፡ ሙሶሊኒ ተቆጫቸው ፡ ሙሶሊኒ አዛዥቸው ሁኖ ሌሎቹ ሁሉ ይኑሩ አይኑሩ አይታወቅም ።

ከዚህ ቀጥሎ ያለው ቃል ሙሴ ሉዘን ባንድ ሬቡሉሲዮን ፕሮሌታሪዬን በተባለ ጋዜጣ ያሳታሙት ነው ። መቼውንም ቢሆን ባለ ጋዜጣ የመሰለውን ይናገራል እንጂ የመንግሥት ሰዎች ከጓዳቸው ሁነው እናጥፋው እናልማው ሲባባሉ ሰምቷቸው አይደለምና ወሬውን የሚጽፍ ስለዚህ ይህን ቃል የሚያነብ እገሌ ወዳጃችን ነው ። እገሌ ጠላታችን ነው ከማለት አይድረስ ። ፍቅርና ጠላትነት ሥራ ካልተፈጸመ አይታወቅምና ባለ ጋዜጣ ይህን ካለ ብሎ ሕዝብ ከመዘለል ወይም ከፍርሃት መድረስ አይገባውም ።

የሙሴ ሉዘን ቃል ይህ ነው ። የፋሺስት ወገን የእስከ ዛሬውን መንገዱን ትቶ ዘወር ማለት ጀምሯል ። ፋሺስት የፊተኛው አሳቡ አስቀድሞም ለባለ ጠጎቹ የሠራላቸው ጉዳይ ሞያ ውሎ የሚበላውን ድኃ በጫማው ተረግጦ አፈር ማስላስ ነው ። ባለጠጎችን ደስ ለማሰኘት ይህን ሥራ ፈጽምዋል ። በጣልያን ውስጥ ያለውን የድኃ ሰራተኛ ወገን በጦር እንደበዝትና በሰንሠለት መንግሥት ከሆንሁ እያለ በማንገራገርና በማስፈራራት ያለ ሕግም ሰው በመግደል ፋሺስት ላሁኑ ድል አድርጎታል ። ግን የጣልያን ባለጠጋ ፋሺስት ይህን ስላደረገለት ገና የልቤ አልሞላም ፡ ለዚህ ብዬ ላንተ መታዘዝ ይቸግረኛል ። ደግሞ ሌላ የምታደርግልኝ አለህ ይለዋል ። ምን አድርግልኝ ሊለው ይሆን ።

የጣልያን ሕዝብ እየበዛ ከሄደ ዘንድ ለዜጋው የበቃ ምግብ ካገሩ አያገኝም ፡ ስለ ዚህ ባ፲፱፻፲፬ ዓመት አራት መቶ ሺህ ባ፲፱፻፲፯ ዓ ሶስት መቶ ሺህ ጣልያኖች እንጀራ ፍለጋ አገራቸውን ትተው ስደት ሂደውበታል ፡ ባለጠጋው ስደት በመሄዳቸው ሳያዝን ዜጎቹ ሶስት አራት መቶ ሺህ እየሆኑ ከሰው አገር የጌታ አዳሮቹ ሲሆኑበት ጊዜ እኔን ባለጠጋውን ማን ሰርቶ ያብላኝ ድኃ ከሌለ የምወዳትን አገሬን ማን ያገልግላት የድኃዬን ጉልበት እኔ ልቡን አጠፋዋለሁ እንጂ ለምን የሰው አገር ባለጠጋ ይፈጀዋል እያለ ይጮሃል ፡ እንግዴህ ፋሺስት እገዛለሁ ካለ የጣልያንን ድኃ ባገሩ ባለጠጎች ውስጥ ቀጥቅጦ ለማስገዛት ዜጎቹ ወደሰው አገር እንዳይሄዱበት ሊያደርግ ነው ፡ ለዚህ ሁለት መንገድ አለበት ፩ኛው ሙሶሊኒ እንደሚለው ባገር ውስጥ ያለውን ሥራ እያሰፋ ስደት ከሚሄደው ሰው ብዙውን ከስደቱ ማስቀረት ፪ኛው የቅኝ አገርን እያሰፋ ሰራተኛን ወደዚያው እየሰደዱ ሰርቶ የሚያወጣው ገንዘብ በሰው አገር ቀልጦ እንዳይቀር ማድረግ ነው ፡

የፊተኛው አሳቡ ሥር አልይዝለት ሲል ጊዜ ሙሶሊኒ ወደ የቅኝ አገር ፍለጋ ልቡን አዘነበለ ። ዓይኑን የጣለበት አገር የቱ ይሆን ።

ሙሶሊኒ ዓይኑን ከጣለባቸው አገሮች አንዱ ኢትዮጵያ ነው ። እንግሊዞች ከሙሶሊኒ ጋራ ሲዋዋሉ እነርሱ በጣና

ባሕር ሊያዙበት ሙሶሊኒ ምጥዋ አንሥቶ ትግሬን ጐንደርን አድርጎ አዲስ አበባን ወደምሥራቅ እየተወ እስከ ሀንድ ውቅያኖስ የምድር ባቡር ሊሰራ ለዚኸው ስራቸው ሁለቱም ሁሉ የኢትዮጵያን መንግሥት ፈቃድ ሊለምኑ በዚህ እርዳኝ እረዳሃለሁ ተባብለዋል ።

እስተውሎ ላላየው ሰው ስለምን ሙሶሊኒ ከባሕር የራቀ ስለሆነ ብዙ ፍሬ የሌለበትን የኢትዮጵያን ምዕራቡን አስፈልገው ያሰኝ ይሆናል ። ግን እንደዚህ አይደለም ሙሶሊኒ የኢትዮጵያን ምዕራቡን የመረጠበት በሁለት ነገር ነው ምንና ምን ቢሉ ስለ ኤኮኖሚና ስለ ፖሊቲክ ኤኮኖሚ ማለት ገንዘብን አለማባክን መቈጠብ ጥሪትን በሥርዓት ማዘጋጀት ነው ፡ ከዚህ ላይ ግን ኤኮኖሚ ከሰውና ከሰው ሥራ ካገርም ትርፍ የሚያገኙበት ነገር ማለት ነው ። ፖሊቲክ ዘይቤው የከተማ ጉዳይ ማለት ነው ፡ የቀድሞ ሕዝብ መንግሥት ከመሆን ሳይደርሱ በየከተማቸው ይኖሩበት በነበረው ዘመን ለከተማቸው የዳኝነት የንግድ የጥዳት ሥርዓት ሲተክሉ ሌላውንም ይህን የመሰለውን ለከተማ የሚሆነውን ሥራንና ምክርን ሲይዙ ፖሊቲክ ይሉት ነበር ። ሕዝብ እየበዛ ኳንዲህ እንደ ዛሬው ሰፊ መንግሥት በያዘበት ዘመን ግን መንግሥትንና መንግሥትን ሕዝብንና መንግሥትን ወገንና ወገንን በምክር በሥርዓት ለማሳደር በሥውርና በገሃድ የሚሰራው ሥራ ሁሉ ፖሊቲክ ይባላል ፡ ሙሶሊኒ ስለ ኤኮኖሚ የኢትዮጵያን ምዕራብ የመረጠበትን ምክንያት አስቀድመን እንመርምረው ።

በኤርትራ ባሕር ጠረፍ ወደ ምሥራቅ ያለው የኢትዮጵያ ክፍል ደረቅ በረሃ ነው ። ከርሱ አስቀጥሎ ያለው አገር ግን ከተራራ ግምብ ላይ የተሰጣ ሜዳ ነው ቈላውም ደጋውም የእህል የከብት አገር ነፋሱ ጤናማ የሆነ ስፍራ ነው ። ይህም ኢትዮጵያ የተባለ አገር ግምብ የመሰለው ተራራው ነው እምባ ምሽግ ሆኖለት በአፍሪቃ ከሉት አገሮች ራሱን ችሎ የሰው አገር ገዢ ሳያስደርስ እስከዛሬ በነፃነት ቈይቶ ያለ።የኢትዮጵያ ገደል በንድ ወገን ያዳልን የሶማሊን ሜዳና ባሕሩን ከሰማይ ላይ ሁኖ አቈልቍሎ የሚጠባበቅ ሲመስል በምዕራብ በኵል ጥቂት በጥቂት ዝቅ እያለ ይሂድና ዓባይ ከሚያጠጣው ገነት ከሆነው አገር ሲደርስ መሬት ይንካል ። በዓባይ አውራጃ ያለው አገር ዝናቡ ትክክል በሆነ.ት ዘመን ባመት ሶስት ጊዜ አዝመራ ይሰበሰብበታል ይባላል ። ሙሶሊኒም ብቻየን በኤኮኖሚ ልሠልጥንበት ያለው የኢትዮጵያ ምዕራብ ከመሬቱ መባረክ ሌላ ወደ ኢትዮጵያ ለማዝገም አምባና ተራራ ያነሠበት አገር ስለሆነ ነው

ግን ይህ የኢትዮጵያ ምዕራብ ከኤኮኖሚ ሌላ ደግሞ የፖሊቲክ ነገር አለበት ።

የፈረንሳይ ባለ ጠጋ ከኢትዮጵያ ጋራ የሚያገናኘው ትርፍ ያለበት ሥራ እንዳለው የታወቀ ነው።እንግሊዞች ዓደን ላይ ቢሰፍሩ ፈረንሳይ ደግሞ ከነርሱ እንዳልሰንፍ ሲል ባዓደን ትይዩ ኦቦክ ከሶማሊዎች አገር ሂዶ የመርከቦች ማረፊያ አሰናድቶ ሲኖር የኢትዮጵያ ንግድ ወደ ባሕር የሚሻገርበት ያለ ምጥዋ የጣልያኖች ግዛት ሌላ ጠረፍ እንደ ሌለ አየና ከዚህ ሁኚ መርከብ ከመጠባበቅማ ስራየን ሳልፈታ የኢትዮጵያ ንግድ ሁሉ እኔ ባለሁበት አድርጎ እንዲያልፍ አላደርግምን የሚሉ አሳብ አደረበት ። መቸም በስራ ከተጉ ከፍጥረቱ የመርከብ ማረፊያ የሆነውን ውድማ ውድማውን የመርከብ ማረፊያ አቋራጭ የነበረውን ረጅም ረጅም የነበረውን አቋራጭ መንገድ ማድረግ አይቸግርምና ፈረንሳ ኦቦክ የተባለውን የባሕር ጠረፍ ትቶ ጅቡቲን ቈረቈረና ከዚያ እስከ አዲስ አበባ የምድር ባቡሩን አውጥቶ የኢትዮጵያ ንግድ ወደርሱ እንዲገለበጥ አደረገ ።

የፈረንሳ ባለጠጋ እንዲህ አድርጎ ሥራ የያዘበትን የኢትዮጵያን ምሥራቅ መተያየት ለፋሺስት ፈረንሳን በግልጥ እንጣላ ማለት የሚመስልበት ሆነ ። ስለዚህም ከውሉ ላይ ፡ የምዕራቡን ብቻ በስተ ምዕራብ ያለውን ነው የምፈልግ እያለ ይደጋግመዋል ። መደጋገሙንስ ለፈረንሳ የግዳ ምሥራቁን እንደያዝህ ላንተ ምዕራቡን ለኔ እያለ ደጋግሞ ነግሮት አብረው በተነሡ ባማረ ነበር ። በፖሌቲክ አካሄድም እንዲህ ያለው መንገድ ማለት ባለጋራን ፍቅረኛ ማድረግ ብዙ እርዳታ የማይታጣበት መንገድ ነው የነበረ።ግን ፋሺስት የተመኘውን የምዕራቡን ወገን ለመያዝ በፍጹም የሚረዳው ባለ ቃል ኪዳን ያስፈልገው ነበርና ፈረንሳን ገለል አድርጎ ተወው ።

የኢትዮጵያ ምዕራቡ የዐባይ መውረጃ ነው ። እንግሊዝም የነጭ ዐባይ ጌታና ተጠባባቂ ሁኖ በሐበሾች ዐባይ ላይ ደግሞ የዚያን ያህል ጌትነት ቢያገኝ ሲመኝ የሚኖር ነው ፡ አሁንም ጣልያንና እንግሊዝ አንድ ልብ እንሁንበት ብለው የተስማሙበት ዓይነተኛው ሁለተኛው ውል ፤ ያባይን አውራጃ እንግሊዝ ብቻ እንዲሠለጥንበት ማድረግን ነው ። በፋሺስት ዘንድም ይኸ መፈቀዱ በሐማሴንና በሱማሌ ባለው የጣልያን ግዛት የጦርነት ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት አስቸጋሪ ነውና ከመተማ ወደ ደቡብ ያለው የእግሊዝ ብዛት ግን ሐበሻን እይዛለሁ ላለ ሰተት አድርጎ ያስገባልና የጦርነት ጊዜ የእንግሊዝን ረዳትነት እናጣውም በማለት ነው ።

ፋሺስት የኢትዮጵያን ምዕራብ መመኘቱም ቢሆንም ይሉኝታ የሌለበት ፖሊቲኩና ክፋቱ ያለ መጠን ከበዛ ዘንድ የስራው ስንፍና ተገለጠበት።የያዘው ጠማማ ፖሊቲክም ከጥቍር ልብስ ላይ እንደ ተሸለለ ነጭ ክር ጐልህ ሁኖ ታየበትና ሁላሁሉ ጌረሰበት እንጂ አያያዙ ስልት ያለበት ኑርዋል።የፈረንሳይ ባለ ጠጎች በዚህ ነገር ከፋሺስት ጋራ መተባበርን አልወደዱትም።ምክንያቱም ያዲስ አበባው ባቡራቸው የኢትዮጵያን ምሥራቁንና ማህሉን ከጅቡቲ እንሥቶም ዐባይን አድርጎ ተሱዳን አልፎ ፋሾዳን ይደርስልናል የሚሉት ተስፋ ስላደረባቸውና የወዘፋት ሥራ ስላለባቸው ነው ። ስለዚህ የፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ምኒስትር እንግሊዝና ጣልያን የተባበሩበትን ውል ለማፍረስ ፈጥኖ ተነሣ።አገባብ በሌለበት መንገድ ግዛቴን እንደ ማንም አድርጌ እሰፋለሁ የሚለውን መንግሥት ሁሉ ወደ ሚቃወመው ወደሕዝብ ማኅበር ኢትዮጵያን ከጩኸት ያደረሰብን ፈረንሳ ነው እያለም የፋሺስት ጋዜጣ የሚያወራው ሁሉ ሐሜት ያለበት ነገር አይመስልም ፡ እንግሊዞችም በውሉ ጠጠት ያደረባቸው ይመስላል ፡ የሆነ ሆኖ ደስ እንዳላሰኛቸው ምኒስ

ትሪቸው ከምክር ቤት የተናገረውና የጋዜጣቸው ቃል ያስረ ዳል ። ደግሞም እንግሊዝ ላሁኑ ጣልያንን ያባይን ምንጭ ተውልኝና የኢትዮጵያን ምዕራብ ሁሉ መያዝህን እፈቅዳለሁ ቢል የኋላ ኋላ እርሱ አባይን ይዞ ጣልያን በሴተምዕራብ ሠል ጥኖበት ቢኖር ልቡ እርፎለት እንዳይቀመጥ የታወቀ ነው ፤

እንግዴህ ሙሶሊኒ ወደኢትዮጵያ እገባለሁ ቢል ብቻውን ይገባም እንደሆነ እንጂ እንግሊዝ በሱዳን አውራጃ እንዳይረ ዳውና ፈረንሳ ደግሞ በጅቡቲ እያደረገ ለኢትዮጵያ መሣሪያ ከማቀበል በቀር ዝም ብሎ እንዳያየው የታወቀ ነው ፤ እንዲህ ከሆነም ሙሶሊኒ በጦር እንጂ ከማናቸውም መንግሥት ጋር በፍቅር የሚያቀናው ጉዳይ ላያገኝ ነው ጦርነቱም ሙሶሊኒ ከደፈረው ለማንኛቸውም መቅናቱን እግዚአብሔር ነው የሚ ያውቀው።ደግሞ ኢትዮጵያ መልካም አገር ስለ ሆነ በአፍሪቃ ውስጥ መሆኑ አልቀረለትምና በመካከለኛው ባሕር ጠረፍ እንዳለው አገር ሆኖ ለጣልያን ዜጎች እንዳይመቻቸው የታ ወቀ ነው ፤ ለዚኸው ተብሎም ከጦርነት ቢደረሱት ፍጹም ከንቱ ነው ።

የቴሌግራም ቃል ።

ቶኪዮ ፤ በምድር መናወጽ አምስት ሺ ሰዎች ሞቱ ። ከነ ዚሁም ሁለት ሺ ከኪዎች አውራጃ ናቸው ። ያደጋው ክፋትም ሊረዱ ለሚፈልጉ የሚያስቸግር ሁኗል።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ። ከ፫ ሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፰ብር ተኩል ።
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ፳መሐ ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፫ብር ፳ መ
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ፳ መ
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፬ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴ ብር ።
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፻፴ ብር ።
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፳፰ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳ ብር ።
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፪ ብር ።
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፶፩ ብር።
ሱከር	፩ ጁኒያ	፳፱ ብር ።
ቻዩ	፩ ነጥር	፲፬ መ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ እስከ ፲፫ ማን ነው ።
በአንድ ብር	፲ ሊሬ ፶ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ፳፪ ሳንቲም ነው
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መ ንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነ ዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የ ሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመ ቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶ መቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቀቀዎታል ።

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢ ትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈ ልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያ ስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶ መቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞ ችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመ ቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያ ዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ክች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መኃላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፌታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሄስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ማጥን በየዓይነቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

አዲስ አበባ በላጋር ጉዳና ላይ በሙሴ ተረስ ሆቴል አጠገብ አንድ ክፍል የሙሴ ሳቡሬ ቦታ ከነቤቱና ከነዛፉ ይሸጣል ፡ ቦታውን ለመግዛት የሚፈልግ ሰው በሙሉ ወይም በግሚስ አለዚያም የሚችለውን ያህል ክፍሎ ለመግዛት ይችላል የቦታውም ስፋት ፫ ሺ ሜትር ካሬ ነው ፡ ለመግዛትና ለማየት የሚፈልግ ሰው ሙሴ ሳቡሬን ይጠይቅ

Berliet



ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቀኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ አቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ውሀ መውረጃ ።

AMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ኮዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፲፪
3 me ANNÉE № 12

ሐሙስ መጋቢት ፲፭ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 24 MARS 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Éthiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር
ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Diŕecteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፹፫ ገጽ ተከታይ ።

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

የመንግሥት መሠረት የትምሕርት ቤት ነው ። ትምሕርት በሌለበት አገር አዲስ ደንብ ቢወጣ ከሚጠቀመው የሚጐዳው ይበልጣል ። አሁን በላይ እንደ ተናገርነው ሕዝቡ በሥራ በሰለጠነ አገር ውስጥ ባንክ ሲቆም ትልቅ ጥቅም ነው ። በሥራ ያልሰለጠነውን ሕዝብ ግን ባንክ ይጎዳል እንጂ አይጠቀመውም ። ባንክ የሚቆም ፤ ባገር ያለው ብርና ወርቅ ሥራ እንዳይፈታ ባንድነት ሰብስቦ ሥራ ለሚያውቅ ሰው እያበደረ እንዲሠራበት ነው ።እውቀት የሌለውና በሥራ ያልሰለጠነ ሕዝብ ግን ራሱ ሊሠራ አይችልምና ገንዘቡን በባንክ ቢያስቀምጥ ጥቅሙ ለውጭ አገር ሰዎች ነው ። በኢትዮጵያ የቆመው የእንግሊዝ ባንክ ከታሕሣሥ ፳፱ ቀን ፲፱፻፩ ዓመተ ምሕረት እስከ ታሕሣሥ ፳፱ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት ድረስ ያበደረው ገንዘብ ብናስበው ወደ ፩ ሚሊዮን ፱፻፳ ሺ ፰፻፶፱ ብር ይሆናል ። ከዚሁም የኢትዮጵያ ሕዝብ የተበደረው ከ፶ ሺ ብር በላይ አይሆንም ይመስላል ። የቀረው ግን ፩ ሚሊዮን ፰፻፸ ሺ ፰፻፶፱ ብርን የውጭ አገር ሰዎች ተበድረው ሰሩበት ። ፶ውን ሽህ ብር የኢትዮጵያ ሰዎች ተበድረውት ይሆናል ስለ ተባለ ደግሞ ብድሩ ያለ ጥርጥር ሞያ አልተሠራበትም ። የኢትዮጵያ ሰው ገንዘብ ቢበደር እጅግ ቢበረታ ከፈረንጅ አገር የመጣውን ዕቃ ገዝቶ ለገዛ አገሩ ሰዎች በትርፍ ሸጦ ዕዳውን ለመመለስ ነው። ይህነን ሲያደርግ ግን ዕቃውን ለሸጠለት ፈረንጅ ወኪል ሆኖ ያገሩን ሰዎች ድካም በከንቱ መውሰዱ ነውና የኢትዮጵያን ሕዝብ አይጠቅምም ። ብዙ ሰው የነጋዴን ሥራ ያመሰግናል ለመንግሥትም ዋና ጠቃሚው ነጋዴ ነው ይላል ። ይህ ቃል ግን መሠረት የለውም ። ባንድ መንግሥት ውስጥ ከንዱ ወረዳ ወዳንዱ እየተመላለሰ የእያንዳንዱ ወረዳ ሠራተኞች የሠሩትን ዕቃን የሚያለዋውጥ ነጋዴ በእውነት ላገሩ ይጠቅማል ። እንደ ዚህ ያለውንም ነጋዴ መንግሥት በማናቸውም ረገድ ቢረዳና ቢያበረታታ የተገባ ነው ።

ከውጭ አገር እቃ አስመጥቶ የሚነግድ ነጋዴ ግን ያገሩን ድካምና ሀብት የውጭ አገር ሰዎች በከንቱ እንዲወስዱት ሊረዳ እንደተነሳ ያህል ነውና ከመንግሥት አንዳች እርዳታ አያስፈልገውም ። ነጋዴውም የውጭ አገር ሰው ከሆነ ዘንድ አንዳች እርዳታ አይገባውም ። ስለዚህ የውጭ አገር ነጋዴዎች በተቈጠረ ቁጥር ብዙ ያገራችን ሹማምንት ቢሸበሩ ምክንያት የሌለው ሽብር ነው ። ባገር ውስጥ ነጋዴና ወታደር ሲበዛ ለሕዝቡም ለመንግሥትም አይረባም ። የመንግሥት ዋና መሠረቱ እርሻ ነው ።ስለዚህ ያገራችን ሰው ከባንክ እየተበደረ ቢነግድ ለኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ደስ የሚያሰኝ ነገር አይደለም ።ስለሆነ ግን ገንዘብ ከባንክ እየተበደረ በከንቱ ከሚያባክን ሰው የሚነግድበት ይሻላል ። ከባንክ የሚበደሩ የኢትዮጵያ ሰዎች ግን ሹማምንቶች ናቸው።እነሱም የሚበደሩ ከየገባራቸው የሚመጣላቸው ግብር እስኪደርስላቸው ድረስ በከንቱ የሚያባክኑትን ገንዘብ ሲያጡ ነውና በተበደሩት ገንዘብ የረባ ነገር ለመሥራት በህልማቸውም ቢሆን አያስቡትም ።

ከጥቂት አመት በፊት አያሌ ያገራችን ባለገንዘቦች ተሰብስበው ለእርሻ ማስፊያ ሲሉ አንድ የባንክ ዓይነት ማሕበር አቁመው ነበር ። ነገር ግን ከዚህ ቀደም አንድም ጥቅም ለባላገሩ አላመጣም ለወደ ፊትም አያመጣለትም ። ይልቁንም ብዙ ሰው ከዚሁ ማኅበር ገንዘብ እየተበደረ የብድሩ መክፈያ ጊዜው ሲደርስ ለዕዳው የሚከፍለው ገንዘብ እያጣ ከርስቱ ተነቀለ። ከዚህ ቀደም በምርም እንደ ተረዳነው ሕዝቡ በሥራ ባልሰለጠነ አገር ባላገር ከባንክ ገንዘብ ቢበደር የተበደረውን ገንዘብ ሊመልስ አይችልም ። የተበደረውም ፤ ገንዘብ የሚጠቀመው ለኑሮው የሚያ

ከፈልገው ዕቃ ሁሉ ባገሩ የተሠራለት እንደሆነ ነው ። ይህንንም በዜህ መጽሐፍ ውስጥ በውል አይተነዋል ተረድተነዋልም ።

እንግዴህ እንደ ምድር ባቡርና የጋሪ መንገድ ባንክም የሚጠቅም በሥራ የሰለጠነውን ሕዝብ ነው ። የኢትዮጵያም ሕዝብ መንግሥት ባገሩ የምድር ባቡር እንዲሠራና ባገሩ ባንክ እንዲቆም ፈቅዷልና ሕዝቡን ከጥፋት ሊያድን ፈቃዱ ከሆነ ዘንድ ፣ በፍጥነት ሕዝቡን በሥራ ማሰልጠን አለበት ። የምድር ባቡሩ በአዲስ አበባ ደርሷል ። ባንኩም ይኸው ቁሞ ይሠራል የኢትዮጵያ መንግሥት ሕዝቡን ሊጠቅም ፈቃዱ ሆኖ ለወደፊት የሚሠራበትን ደህና መንገድ አስቀድሞ ለይቶ ነድፎ የነደፈውን ንድፍ ለመፈጸም ታጥቆ ቢነሣ የምድር ባቡሩና ባንኩ በብዙ ሳይረዱት አይቀሩም ። ለሕዝቡ ማሰልጠኛ የሚሆነውን ነገር ሁሉ የምድር ባቡሩ በፍጥነት ሲያመላልስ የኢትዮጵያ ሕዝብ እርስ በርሱ ሲለዋወጥም ባንኩም በሰበሰበው ገንዘብ ሲረዳ የኢትዮጵያ መንግሥት ሕዝቡን ለማሰልጠን ቢነሣ ማለፊያ አጋዦች ይሆኑት ነበር ። የኢትዮጵያ መንግሥት ይህ ሐሳብ ከሌላው ግን የምድር ባቡሩና ባንኩ ወደአገራችን አመጣጣቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ መቃብር ለመማስ እንደሆነ ጥርጥር የለውም ።

፲፪ተኛ ክፍል ።

ብርና ወርቅ በሥራ በሰለጠኑ ሕዝቦች እጅ ሲደርሱ አንዱ ብር ስለ ሁለት ስለ ሶስት ብር እየሆነ እንዲሠራ አይተናል ። የብርንና የወርቅንም ጥቅም እንደዜህ አድርጎ የሚያስፋፋ ባንክ ነውና ፤ በሥራ የሠለጠነ ሕዝብ ሁሉ ያለ ባንክ አይሳካለትም ። ብርና ወርቅ ባገር ስለ በዛ ጥቅም አይሆነውም ። ብርና ወርቅ የሚጠቅም ካንዱ እጅ ወደ አንዱ እጅ በፍጥነት እየተላለፈ ሲያለዋውጥ ነው እንጂ ። ቤት ያለው ሰው ቤቱን ቢሸጥ ምናልባት ቀላድ ለመግዛት ይሆናል ። ባለ ቀላዱም መሬትን የሚሸጥ ምናልባት በሬና ላም ለመግዛት ይሆናል ። በሬውንና ላሙንም የሸጠ ሰው ምናልባት ቤት ሊሠራበት ይሆናል ። ቤቱንም የገነቡ ሠራተኞች በደሞዛቸው ምግባቸውንና ልብሳቸውን ሊገዙበት ይሆናል ። ማለት የብር ሥራው ካንዱ እጅ ወዳንዱ እጅ እየተላለፈ ማለዋወጥ ብቻ ነው ። በያንዳንዱም እጅ ገብቶ ወዳንዱ እጅ እስኪያልፍ ድረስ ቢዘገይ ለሕዝብም ለመንግሥትም ጉዳት ነው ። ሕዝቡ በሥራ ባልሰለጠነ አገር ግን ብር ካንዱ እጅ ወዳንዱ እጅ እስኪያልፍ ድረስ ይዘገያል ። በእንደዜህ ያለው አገር ደህና መንገድና የምድር ባቡር ስለ ሌለ ሕዝቡ በቶሎ እየተገናኘ ለመለዋወጥ አይችልም ። ቢገናኝም አይለዋወጥም ። ሥራው አንድ ዓይነት የሆነ ሕዝብ እርስ በርሱ ምንስ ሊለዋወጥ ይችላል ። ሕዝብ እርስ በርሱ መለዋወጥ የሚችል በየዓይነቱ ሥራ ሠልጥኖ ሥራው የተከፋፈለ የሆነ እንደሆነ ነው ። በሕዝቡ ውስጥ ያለውም እያንዳንዱ ሰው የሰለጠነበት ሥራ ልዩነት ሲበዛ ሕዝቡ የሚለዋወጠው ለውጥ ይበዛል ።

በሕዝቡ ውስጥ ያለውም ብርና ወርቅ ካንዱ እጅ ወዳንዱ እጅ በፍጥነት ይተላለፋል ። ሕዝቡ በሥራ ባልሰለጠነ አገር ግን እያንዳንዱ ሰው የፈለገውን ነገር በፍጥነት አያገኝምና አንዳች ነገር ሸጦ የተቀበለው ብር ወደ ሌላ እጅ እስኪያልፍ ድረስ ብዙ ጊዜያት ይሄዱባታል ። አንቺ አሁን አንድ የመንዝ ባላገር አንዲት ላም ሸጦ ብር ካገኘ በኋላ ለራሱና ለልጆቹ ልብስ የሚሆነውን አቡጀዲድ እስኪገዛበት ድረስ ብሩ በርሱ እጅ ሥራ ፈትቶ የሚቀመጥበት ጊዜ ጥቂት ነውን ። ሕዝቡ በሥራ ባልሰለጠነ አገር ብር ቢበዛ እንደ ብዛቱ አይጠቅምም ። ብሩ ከሚሰራበት ቀን ሥራ ፈትቶ በየቤቱ የሚቀበርበት ጊዜ ይበልጣልና ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ብር ጥቂት አይደለም ። እስከ ፩ መቶ ሚሊዮን ይሆናል ተብሎ ይገመገማል ። የሚሠራበት ብር ግን ከሀያ ሚሊዮን አይበልጥም ። ስለዚህም በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ፈትቶ የተቀመጠው ብር ፹ ሚሊዮን ይሆናል ። ይህም ፹ ሚሊዮን ብር ግማሹ ጌጥ ሆኖ ይሆናል ። ግማሹም ከመሬት በታች ተቀብሮ መልኩን እያበላሸ ሥራ ፈትቶ ተቀምጦ ይሆናል ። ከዚህም ምክንያት የተነሣ የኢት ዮጵያ ብር ያለ አይመስልም ። የሚበዛው ብር ተቀብሮ ስለ ተቀመጠ ወደ ገበያ የሚወጣው ብር ጥቂት ነው ። በኢትዮጵያ ብር የሚበደረው ሰው ወለድ ይበዛበታል ። ሌላው ባለ ገንዘብስ ይቅርና በኢትዮጵያ ያለው ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ሲያበድር የሚቀበለው ወለድ በመቶው አሥራ ሁለት ይሆናል ። የኤውሮፓ ነገሥታት ግን ባገራቸው እያንዳንዱ ሰው ሲበደር ስርዓቱ የሚያስከፍለው ወለድ ስንት እንደሆነ ለይተው ወስነውታል ። ይህም በያምቡ የተወሰነው ወለድ እንደ እያገሩ ሁኔታ ከፍና ዝቅ ይላል ። ስለ ሆነ ግን በማናቸውም መንግሥት በመቶው ከስድስት ብር አያልፍም ።

ይህንን መናገራችን ግን ምናልባት የኢትዮጵያ መንግሥት እንደዚሁ ወለድ ከመቶው ስድስት እንዳይበልጥ ደምብ ያድርግ ማለታችን አይደለም ። ስለሆነ ወሰኑ እንኳ ይህን ያህል ዝቅ ባይል ሕዝቡ እንበለ መጠን እንዳይጎዳ አንድ ወሰን መደንገግ ነው ። መንግሥት ባገሩ ወለድ ዝቅ እንዲል ከፈለገ ግን ሕዝቡን በየሥራው ያሰልጥን ። መንገድና የምድር ባቡርም ያሰራ ። በየወረዳውም የባንክ ቤት እንዲቆም ይጣር ። ባገሩም የውጭ አገር ገንዘብ እንዳይገባ ሥርዓት ይደረግ ። ይህም ሁሉ ከሆነ በኋላ እያንዳንዱ ሰው የሚፈልገውን ነገር ሁሉ በፍጥነት ሲያገኝ የተቀበለውን ብር ቀብሮ አያስቀምጥም ። ወዲያው ወደ ገበያ ያወጣዋል እንጅ ። የፈለገውንም ነገር ሁሉ ገዝቶ ብር ቢያተርፈው ብሩ ሥራ ሲፈታበት አይወድምና ወይም ራሱ አንዳች ነገር ይሠራበታል ። ወይም ደግሞ ወለድ እምትሰጠውን ባንክ ባጠገቡ ሲያገኝ ብሩን በዚያው ያስቀምጣል ። ባንኩም ብሩን ለሚሠሩ ሰዎች አበድሮ ያሠራበታል ። ከዜህም ምክንያት የተነሣ ወደ ገበያው የሚወጣው ብር ይበዛል ። ተበዳሪው የሚከፍለው ወለድ ምንም ቢሆን ማነስ አይቀርም ።

የማናቸውም መንግሥት ሀብትና ኃይል የሚያድግ ሕዝቡ በሥራ የሠለጠነ የሆነ እንደሆነ ነው ። ማናቸውም ሕዝብ በሥራ መሠልጠኑንና ያለመሠልጠኑን ለማወቅ ስንፈልግ ባገሩ የሚከፍለውን ወለድ ማየት ነው ። ባንድ አገር ወለድ ከፍ ሲል የዚያ አገር መንግሥት ሀብትና ኃይል እንዳነሰ ፣ ሕዝቡም በሥራ እንዳልሰለጠነ ይመሠክርልናል ። ባገሩ ልማድ የሆነውም ወለድ ዝቅ ሲል መንግሥቱ እንደ በረታና ሀብቱ እንዳደገ ሕዝቡም በሥራ እንደሠለጠነለት ያስታውቃል ። ከዜህ ቀደም እንደ

ተረዳነው ሕዝቡ በሥራ ክልሠለጠነ ዘንድ በባንክ አማካይነት አንዱ ብር ስለ ሁለት ሆኖ ሊያለዋውጥ ይችላል ። ይህም የሚሆነው በእንዴት ያለ መንገድ እንደሆነ መልሰን እናሳይ ።

ባንድ አገር ባንክ የቆመ እንደሆነ የባንኩ ማህበረተኞች የያዙትን ሥራ ማህበረተኛ መሆናቸውን የሚያስታውቅ የምሥክር ወረቀት ሽጠው የፈለጉትን ነገር ለማግኘት ይችላሉ ። በባንኩ የገባው ገንዘብ ግን ሌሎች ሰዎች ተበድረውት ይሠራበታል ። የባንክ ሥራ የሠለጠነውን ሕዝብ የሚጠቅምበት መንገድ ግን ይህ ብቻ አይደለም ገንዘብ ያለው ሰው ገንዘቡን በባንክ ቢያስቀምጥ በፈለገው ጊዜ እንደፈለገው መጠን ባንድ ጊዜ ወይም በየጥቂቱ ያስቀመጠውን ገንዘብ መልሶ ሊወስድ ይችላል ። ወዲያውም ጥቂት የጠባቂ ዋጋ መክፈል አያስፈልገውም ። ባለ ገንዘቡ በባንክ ያስቀመጠውን ገንዘብ መልሶ እስኪወስድ ድረስ ግን ገንዘብ ሥራ ፈትቶ አይቀመጥም ፤ ባንክ እያበደረ ይሠራበታል እንጂ ። በዚሁም አንዱ ብር ስለ ሁለት እየሆነ ይሠራል ። ባንክም የሠለጠነውን ሕዝብ የሚጠቅምበት ደግሞ ሌላ መንገድ አለ ። ገንዘቡን በባንክ ያስቀመጠ ሰው ከገንዘቡ ከፍሎ ለሌላ ሰው እሰጣለሁ ቢል ከቤቱ መነቃነቅ አያስፈልገውም ። ቼክ በሚባለው ወረቀት ላይ ይህነን ያህል ገንዘብ ከኔ ሂሳብ ለእገሌ ሰው ብሎ ሲልክ የሚበቃ ይሆናል ።

ስለዚህም ገንዘብ በመቍጠር በከንቱ የሚደክመው ድካም ለባለ ገንዘቡ ይቀርለታል ። ባንድ ከተማ ውስጥ ባንክ ከቆመ በኋላ ገንዘብ ያለው ሰው ሁሉ የገንዘብ ጠባቂ እንዲሆነው ሊል ሠራተኛ መቅጠር አያስፈልገውም የገንዘብ ጠባቆችም ሆነው በየቤቱ ሊቀጠሩ የነበሩ ሰዎች ሌላ ሥራ ይዘው አገራቸውን ይጠቅማሉ ። መቶ የገንዘብ ጠባቂዎችም ሆነው በየቤቱ ሊሠሩበት የነበረ ሥራ ገንዘብ ሁሉ በባንክ ሲገባ ባንድ ሰው እጅ ይሠራል ባንክም በሥራ የሰለጠነውን ሕዝብ የሚጠቅምበት መንገድ ይህ ብቻ አይደለም እያንዳንዱ ሰው በባንክ ያስቀመጠውን ብር ለእገሌ ስጥልኝ ብሎ ከጻፈ በኋላ ፤ ያ ገንዘቡን ሊቀበል ሽክ የተጻፈበት ሰው ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት ሲፈልግ በወረቀቱ ጀርባ ላይ ስሙን ከመጻፍ በቀር ሌላ ድካም የለበትም ። ቼክ በሁለት እጅ ከደረሰ በኋላ ግን ያስቸግራልና ፤ ቼኩ ካልተለወጠ አይሆንም ከዚህም ምክንያት የተነሣ ሌላ ብልሃት ተበጀ ። ባንኩ ራሱ ባንክ ኖት የሚባል የታተመ ወረቀት አወጣ ።

ይህም ባንክ ኖት የሚባለው ወረቀት ምንድር እንደሆነ እንዲገልጽልን ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል እንመልከት የሰው ኑሮ መሠረት እምነት ነው ሰው እጸድቃለሁ ብሎ ከማመኑ የተነሣ በጐ ሥራ ይሠራል ዳኛም የምስክርን ቃል አምኖ ይፈርዳል ሴትም ባሏን አምና ወላጆቿን ትታ ትሄዳለች ። ተማሪውም መምሕሩ የነገረውን ቃል አምኖ የተማረውን ትምሕርት የሀሳቡን መሠረት ያደርጋል ። አስተማሪው የነገረውን ቃል ተጠራጥሮ የተማረው ነገርእውነት መሆኑንና ያለ መሆኑን የሚመራመር ተማሪ ከሺ አንድ አይገኝም ። በዚህ ዓለም የሚሠራው ሥራ የሚበዛው በእምነት ነው ። ከሰው ልብ እምነት ቢጠፋ አንዳችም ሥራ አይሠራም ነበር እውቀት የሌለው ሕዝብ እርስ በርሱ አይተማመንም ስለዚህም የሚሠራው ሥራ ጥቂት ነው ሕዝቡ እውቀት ሲጨምር ግን እርስ በርሱ መተማመኑ ይበዛል እውቀት ለሌለው ሰው ቼክ ሰጥተው ከባንክ ብር ተቀበል ቢሉት እያምንም አታልለው ከቤት ሊያስወጡት ያሰቡ ይመስለዋል ብሬን ቆጥራችሁ በእጄ ካልሰጣችሁኝ አልለቃችሁም ይላል በዚሁም ራሱ ሥራ ፈትቶ ገንዘብ የሚሰጠውንም ሰው ሥራ ያስፈታል የተማረ ሰው ግን ብሩን ቆጥረው በእጁ ከሚሰጡት ቼክ ጽፈው ወደ ባንክ ቢዳርጉት ይወዳል በቼኩም ጀርባ ፊርማውን አድርጎ ገንዘቡን ወደ ሂሳቤ ጨምራችሁ የደረሰኝ ወረቀት ላኩልኝ ብሎ ለባንኩ ይጽፋል ባንኩም ቼኩን ተቀብሎ ብሩን ሲቆጥር ጊዜ በከንቱ ሳይባክንበት በቼኩ ላይ የተደረገው ገንዘብ ከከፋዩ ሂሳብ ወደ ተቀባዩ ሂሳብ ያሸጋግራል ከዚህም መተማመን ምክንያት የተነሣ እውቀት ባላቸው ሕዝቦች መካከል ማንም ሰው ገንዘብ ሲሰጥም ሲረከብም ጊዜውን በከንቱ አያባክንም ። ሌላ የሚጠቅም ሥራ ይሠራበታል ። በመንግሥትም ታምኖ የቆመ ባንክ መተማመኑንም መንግሥት ከመሠከረለት ዘንድ ወይም መንግሥት ከተዋሰው ሕዝቡም እንዲያምነው የተገባ ነው ። ስለዚህም ነገሥታት የተዋሷቸው ባንኮች ይህነን ወረቀት ይዞ ወደ እኛ የመጣ ሰው ይህነን ያህል ገንዘብ እንሰጠዋለን እያሉ ወረቀቶች እያተሙ ያወጣሉ እነዚህንም ወረቀቶች ሕዝቡ እየተቀበላቸው እንደ ብርና እንደወርቅ ይገበያይባቸዋል ወረቀቶቹንም የሚቀበል ሰው ምናልባት ወረቀቱ እራሱ ብር ነው ብሎ አይደለም ነገር ግን ብር በፈለገ ጊዜ ወረቀቱን ሲያሳይ ባንኩ በወረቀቱ ላይ የተጻፈውን ገንዘብ ወዲያው እንዲሰጠው እያመነ ነው እንጂ ። ባንክ ኖትም የሚባል እንደዚሁ ያለው ወረቀት ነው በኢትዮጵያም የቆመው ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ እንደዚሁ እንደ ተናገርነው ያለ የብር ባንክ ኖት አውጥቷል ። አንባቢው ግን እንዲህ ብሎ ይጠይቅ ይሆናል ። ባንክ ይህንን ያህል ገንዘብ እሰጣችኋለሁ እያለ ብዙ ባንክ ኖት በመላው አገር ዘርቶ ሕዝቡን አታልሎ በኋላ የሚከፍለው ያጣስ እንደሆነ ሕዝብ አይጎዳምን ። እንደዚህ ያለ ወረቀት ባገር ቢለምድ ምን ይረባናል ።

ለዚህ ጥያቄ ግን እኛ ብንመልስ አንባቢው አይጠቀምም ። ባንክ ኖት የሚታተም እንዴት እንደሆነ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን አንብቦ ይረዳ ። ከዚያም በኋላ እሱው እራሱ ይፍረድ ባንክ ሲቆም ባንኩን ያቆሙ ማኅበረተኞች ያገቡትን ገንዘብ ልክ የሚያሣዩ የምሥክር ወረቀቶች ይቀበላሉ ። እነዚህም የምሥክር ወረቀቶች አክሲዮን ይባላሉ ።

እነሆም ባንክ አፍ አቢሲኒያ ሲቆም ፲ሺህ አክሲዮን ታተመ ለባንኩ ማቆምያ የሚሆነውንም ገንዘብ እናገባለንያሉትም ማኅበረተኞች ሊያገቡት እንደ ፈለጉ ገንዘብ መጠን ለ፶ብር አንድ አክሲዮን ለ፶ብር አንድ አክሲዮን ተቀበሉ ። ማለት ። መቶ ብር አገባለሁ ያለ ማኅበረተኛ ሁለት አክሲዮን አምስት መቶ ብር አገባለሁ ያለ አስር አክሲዮን ። ሺህ ብር አገባለሁ ያለ ፳አክሲዮን ተቀበለ ። ስለዚህም በ፲ ሺህ አክሲዮን ይገባል የተባለው ገንዘብ ፭ሚሊዮን ብር ሆነ ። ነገር ግን በኢትዮጵያ ገና ሥራ አልሰፋምና ይህ አምስት ሚሊዮን በሙሉ ገና አልተሰበሰበም አምስቱ ሚሊዮን በሙሉው ጨርሶ ከማኅበረተኞቹ ቢሰበሰብ

ሥራ ይፈታል ተብሎ እያንዳንዱ ማኅበረተኛ በመጀመሪያ የሚከፈለው አገባለሁ ካለው ገንዘብ ሩብ ይሁን ተባለ ። የቀረውንም ፫ሩብ ያግባ በተባለ ጊዜ እንዲመላ እያንዳንዱ ማኅበረተኛ የሚበቃ ዋስ ሰጠ ።

ስለዚህም ዛሬ ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ የሚሠራበት ገንዘብ ልኩ ፩ሚሊዮን ፪፻፶ ሺህ ብር ብቻ ነው ። የቀረው ፫ሚሊዮን ፯፻፶ ሺህ ብር ግን እንደሚያስፈልግ እየታየ ለወደ ፊት ይሰበሰብ ይሆናል ። እንግዴህ ባንኩ ዛሬ የሚሠራበት ገንዘብ ፩ሚሊዮን ከ፪፻፶ ሺህ ብር ከሆነ ዘንድ ባንክኖት ሲወጣ ቢያንስ ቢያንስ በዚሁ ገንዘብ ልክ ያትማል ። ባንክኖቱም ሁሉ ሕዝብ የተቀበለለት እንደሆን ፩ሚሊዮን ፪፻፶ ሺህ ብር እንደ ውስትና በባንክ ውስጥ ተቀምጦ ያ፩ሚሊዮን ፪፻፶ ሺህ ብር ባንክኖት ሕዝቡ ይገበያይበታል ። ነገር ግን ባንክኖት የያዙ ሰዎች ሁሉ ባንድነት ተሰብስበው ባድነት ወደ ባንክ መጥተው በባንክኖት ፈንታ ብር ስጡን እንዳይሉ የታወቀ ነውና በባንኩ ቤት ውስጥ ስለ ውስትና ከተቀመጠው ፩ሚሊዮን ፪፻፶ ሺህ ብር እጅግ ቢበዛ እኩሌታው ያህል ለመጠባበቂያ ቀርቶ እኩሌታውን ሰው ተበድሮት ይሠራበታል ። ይህም የሆነ እንደ ሆነ ማኅበረተኞቹ ያገቡት ፩ሚሊዮን ፪፻፶ ሺህ ብር ስለ ፫ሚሊዮን ፻፳፭ ሺህ ብር ሆኖ መሥራቱ ነው ።

ይህንንም ያህል የሚሆንበትን ምክንያት ቀጥሎ የተጻፈው ያሳየናል ። በእጃቸው አክሲዮን የያዙ ሰዎች አክሲዮኑን በከፈሉት ገንዘብ ልክ ለሌላ ሰው አሳልፈው ሸጠው በዋጋው የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሊገዙበት ይችላሉ ። መቶው ሺህ አክሲዮንም የተከፈለበት ዋጋው ፩ ሚሊዮን ፪፻፶ ሺህ ብር የታተመው ባንክኖትም ስለ ፩ ሚሊዮን ፪፻፶ ሺህ ብር ባንኩም የሚያበድረው ጥሬ ብር ፮፻፳፭ ሺህ ብር ።

አንድ ላይ ድምሩ ፫ ሚሊዮን ፻፳፭ ሺህ ብር ነው ።

እነሆ ባንክኖት የሚታተም በእንደዚህ ያለ ሒሳብ ነው ። ከታኅሣሥ ፳፱ ቀን ፲፱፻፩ ዓ ም እስከ ፲፱፻፭ ዓመተ ምሕረት ድረስ ባንኩ አደራ ለማስቀመጥ የተቀበለው ገንዘብ ወደ ፰፻ ፲፫ ሺህ ብር ይሆናል ። ዛሬም ቢሆን ይበዛል እንጂ አያንስም የታመነ ተበዳሪም ከተገኘ ከዚሁ ገንዘብ ቢያንስ ቢያንስ እኩሌታውን ያህል ከፍሎ ባንኩ ያተርፍበት ይሆናል ። ስለዚህም ላይ ከደመርነው ፫ ሚሊዮን ፻፳፭ ሺህ ብር ፬፻፮ ሺህ ፭፻ መጨመሩ ነውና የባንኩ የራሱ ገንዘብ ፩ ሚሊዮን ፪፻፶ ሺህ ብር ብቻ ሆኖ ባንኩ የሚሠራበት ገንዘብ ፫ ሚሊዮን ፭፻፴፩ ሺህ ፭፻ ብር ሊሆን ነው ። ይኸንንም ያህል እንዲሆን ቀጥሎ የተጻፈው ሒሳብ ያስረዳናል ።

የአክሲዮን	፩ ሚሊዮን ፪፻፶ ሺህ ብር
የባንክኖት	፩ ሚሊዮን ፪፻፶ ሺህ ብር
ባንክ የሚያበድረው ጥሬ ብር ከራሱ	፮፻፳፭ ሺህ ብር
አደራ ከተቀመጠው ገንዘብ ከፍሎ	፬፻ ፮ ሺህ ፭፻ ብር
አንድ ላይ ድምሩ ።	፫ ሚሊዮን ፭፻፴፩ ሺህ ፭፻ ብር

እነሆ በሥራ በሠለጠኑ ሕዝቦች አገር እንኳን ብዙው ገንዘብ ሥራ ሊፈታ ጥቂቱም ብር ቢሆን ስለ ብዙ ሆኖ በሁለትና በሶስት ወገን ሊሠራ ይችላል ። በዚሁም ሒሳብ እንደ እምናየው ብር የለውጥ መሣርያ ነው እንጂ ሌላ ብልሀት የለውም ። በተፈለገ ጊዜ የታመነ ባንክ ከመሰከረ ዘንድ ፤ ሰው በምሥክሩ ወረቀት ሊገበያይ ይችላል ። ከዚህም እምነት የተነሣ ጥቂቱ ብር እንደ ብዙ ብር እየሆነ ያገሩን ሕዝብ ሊያገለግል መንግሥት ካወቀበት ለሕዝቡ ትልቅ ጥቅም ነው ። በሥራ የሰለጠነ ሕዝብ ባገሩ ቼክና ባንክኖት ሌላውም የባንክ ሥራ ሁሉ ሲታወቅ ይጠቀምበታል ። ባንድ አገርም የምድር ባቡር ወይም አረብያ ሲበዛ ለሕዝቡ ሀብት ማስፈያ እንዲሆን እንደዚሁም ብር የሚያገለግልበት መንገድ ሲበዛ የሕዝቡም ሀብት ያድጋል ። ለተበዳሪውም ወለድ ያንስለታል ። ያልሰለጠነ ሕዝብ ግን ባገሩ ምንስ እጅግ ያማረ የባንክ ደንብ ቢቆምለት አንዳች ጥቅም አያገኝበትም ። ጥቅሙ ከርሱ ጋር ለሚገበያዩ ለውጭ አገር ሕዝቦች ነው ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት መጽሐፍ ነው ።

በምክረ ዚአከ መራህከኒ ።

ወምስለ ስብሐት ተወከፍከኒ ብርሃንና ሰላም ።

ስለ ኢየሩሳሌም ርስታችን ነገር ከክቡር ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ጋራ በሄዱ ጊዜ ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ተከትዬ ሄጄ ነበር ።

ምስር ከተማ ። ከታላቁ ሊቀ ጳጳሳት ካቡነ ቄርሎስ በተገናኘን ጊዜ ። ብላታ ኅሩይ ለእጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስና ለክቡር አቶ ፋሲካ ፥ የመጣንበትን ጉዳይ እንንገራቸው ብለው ምክር ቢያከፍሉዋቸው ። ለእጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሰው መውደድና ትሕትና ገንዘባቸው ስለሆነ ። ፈቅጃለሁ እርስዎ ይናገሩ ብለው አፈ ጉባኤ መሆንን ፈቀደውላቸው ። ክቡር ብላታ ኅሩይ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል ተናገሩ ።

አባታችን ሆይ ግብጽና ኢትዮጵያ በሃይማኖት አንድ ከሆነ ሺ ፯፻ ዓመት ነው ። ይህን ያህል ዘመን አንድ ስንሆን በትንሽ ነገር ብንጣላ የውጭ ጠላቶቻችን ግብጽና ኢትዮጵያ ተጣሉ እያሉ መዘባበቻ ሆነን ።

ደግሞ በዚህ ነገር ጃንሆይ አጤ ምኒልክ ኢቴጌ ጣይቱም እንደ ደከሙበት አባታችንም ያውቃሉ ። አሁን እኛን የኢየሩሳሌም ሹም ለርስታችሁ መጥታችሁ ግጠሙ ብሎ ቢልክብን መጣን ። ከዳኛ ላይ ከተቋቋቁዋምን ። ከባቶቻችን ጋራ መቀያየማችን የግድ ሆነብንና ። መጀመሪያ አባታችን አይተውት ይሆናል ብለን ወደዚህ መጣን ። ደግሞስ እናንተ አባቶቻችን እኛ ልጆቻችሁ ስንሆን ርስትስ ባይኖረን እናንተ ትሰጡን አልነበረም ። ስንኳን የኛን ርስት ትከለክሉን ፤ አባት ለልጅ ርስት ይተክላል እንጂ የልጁን ርስት እንደምን ይነቅላል ። አሁንም በርቁ መንገድ የሚሆንልን እንደሆነ ክቡር ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ለዚሁ ነገር ኢየሩሳሌም ሄደዋል ፈቃድዎ ይሁንልንና እናስጠራቸው አሉዋቸው ። ታላቁ አባታችን አቡነ ቄርሎስም በየዋህ ጠባያቸው ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን መልስ ሰጡን ።

ነገሩም ትንሽ ነው የሚያጣላም አይደል ከሐበሻ አንዳንድ ተንኮለኛ መነኰሴ እየመጣ ይሆናል አሉ ፥ እኛም የነዚያ ጠብ ወደታላላቆች ሊደርስብን ቢሆን ነው አልናቸው ፥ በኢየሩሳሌም ርስት ነገር የኢትዮጵያ ሕዝብ ትንሹም ትልቁም እጅግ አዘኑ

መንግሥታችንም በግብጽና በኛ መካከል መለያየት መጣ ብሎ አዝኑዋል አሏቸው ። ታላቁ አባታችንም በኔ ዘመን የግብጽና የኢትዮጵያን መለያየት አያሳየኝ የኢየሩሳሌምን ጳጳስና ሹማ ምንት እኔ ከዚሁ አስጠርቼ አያችኋለሁ ምንም የሚያጣላ ነገር የለ ብለው ደስ የሚል ተስፋ ሰጡን ።

የቀጠሩንም ቀኑ በደረሰ ጊዜ የኢየሩሳሌም ጳጳስ አቡነ ጢሞቴዎስ የገዳመ አስቄጥስ ራይስ አባ ዮሐንስ ደግሞ ያገሩ ዋና ሹም ማርቆስ ባሻ የሚባል ሌሎችም ስማቸው ያልተጻፉ ብዙዎች አሉ ። አፈ ጉባዔው ማርቆስ ባሻ የሚባለው ነው ከታላቁ አባታችን ቤት ተሰብስበው የኢትዮጵያ ሰዎች ምን አድርጋችሁልናል ቢቸግረን ገንዘብ አትረዱን የናንተን ልጅነት ምን እናገኝበታለን ብለው እየሳቁ ተናገሩ ፤ ለኛም አፈ ጉባዔ የሆኑት ብላታ ኅሩይም በኢትዮጵያ አውራጃ ብዙ ሺ የሚሆኑ አብያተ ክርስቲያን አሉ ከነዚሁም የሚበዙት አሁን ለጊዜው በግብፃውያን እጅ ናቸው አሏቸው ። ይህን እኛ የት እናገኘዋለን ቢሏቸው የተሾመውን ሊቀ ጳጳሳት ጠይቁ እንጂ እኛ ገንዘቡ የሚሄድበትን ለማወቅ አይቻለንም ፤ እናንተ በሾማችሁት በሊቀ ጳጳሱ እጅ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ገንዘብ መግባቱን ብቻ አስረዳናችሁ አሏቸው ። ለዚሁም ነገር መልስ ለመስጠት አልቻሉም ። ስለ ኢየሩሳሌም ርስታችን ነገር ሲማከሩ ሰንበተው ነበርና የኢትዮጵያ ሰዎች በኢየሩሳሌም ርስት አለን ትላላችሁ ምን ርስት አላችሁ።

አሁንም የያዛችሁት እርስት ልጆቻችን ናቸው ይቀመጡበት ብለን ነው እንጂ እርስቱ የኛ ነው አሉ ። ጎልጎታ ውስጥ ባንዱ ክፍል የሚካኤል ታቦት ፤ ባንዱ ክፍል የበዓለ እግዚአብሔር ታቦት ነበረበት የሚሉት የኛ ቤተ ክርስቲያን አለ ። በቱርክ ጊዜ እጅ አድርገዉት ኖሮ ያንን ቤተ ክርስቲያን ባዶውን ቆልፈው የኛ ሰው ወደ ጎልጎታ እንዳያልፍ ይከለክላሉ ። ግብጻውያንና እኛ የምንጣላበት ዋናው እሱ ነው ። ከዚህ በፊትም ብዙ ደም ፈሶበታል ይባላል ።

የነገራቸውንም ፍጻሜ ያስታወቁበት ቃል ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ። ቤተ ክርስቲያኑ ያለበትን ወደ ጎልጎታ የምታልፉበትን መንገድ አንሰጥም ። አሁን የያዛችሁትን ከሮቁ በላይ ያለውን ብላጭ ሰላሳ ሺ ብር ስጡንና ብትሠሩበትም ብትሠሩበትም ፈቅደንላችኋል አሉ ። ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ክቡር ብላታ ኅሩይ ፤ ክቡር አቶ ፋሲካ ከኔ በቀር ባንድ ቃል ሆነው ገናናው የኢትዮጵያ መንግሥት ስለ ኢየሩሳሌም ርስታችን ነገር በዕርቅ እምቢ ቢሉ በሙግት ተነጋገሩ አለን እንጂ በገንዘብ ግዙ አላለንም ። ግዙም ያላችሁን አሁን እኛ በጃችን ጭብጥ በእግራችን እርግጥ አርገን ከቀድሞ ጀምሮ የያዝነውን እርስታችንን ነው ብለው ይህን መልስ ሰጧቸው ። ከዚህ በኋላ በምድር ባቡር ዕለቱን ተሳፍረን ኢየሩሳሌም ገባን ። ኢየሩሳሌም ከደረስን የሆነውን ሁሉ ለመጻፍ አንባቢ ይሰለቻል ። ታቦት ረከሰ እየተባለ ከትግሬ ከጐንደር፤ከጐጃም ከሸዋም አውራጃ ሁሉ ከቡን ዘንድ ሊባረክ ይመጣል ። ረከሰ መባሉ ቄስ ከሕግ ወጥቶ ዓለማዊ ሥራ ሲሠራ ቢገኝ ይመስለኛል ። ፍትሐ ነገሥቱም የሚያዘው አረማዊ ንጉሥ ታቦቱን ማርኮ ወስዶ ያንገላታው እንደ ሆነ ዳግመ ይቀደስ ይላል ። ዳግም ጳጳስ ሜሮን ይቀባው ሲል ነው ብለው ያገሬችን ሊቃውንት ይተረጕማሉ ። ቄሱ በበደለ ፈንታ ታቦቱ መንገላታቱ ስለ ምን ይሆን ፤ አዳም በበደለ መድኃኔ ዓለም ክሶ እንደሚሉት ይሆን ። ከቶውንም ይመስላል ።

ታ ገሩስ ሲመጣ መቸውንም ረክሱዋል ተብሏልና በየጋላው ቤት ባረመኔው ደጅ ቢያድር ምን ይደረጋል ።

ጳጳሱ እንደገና አክብረው ሾመው ከቀደሱት በኋላ ታቦቱ ወደሀገሩ ሲመለስ የዓለማዊ ሥራ ከሚሠራበት ቤትና ከየጋላው ቤት አጠገብ ሰፍሮ ያድራል እስላሙም ከየመንገዱ ያማራ አምላክ መጣ እያለ ሲዘብበት ይውላል የታቦትም ክብሩ ከቤተ መቅደስ ቢቀመጥ ነው እንጂ አንዳንድ ቄስ እያዘለው በየመንገዱ ቢንገላታ ጥቅም የለውም ።

አቡቀለምሲስ ፲፩ ም ፲፱ ቍ ወአስተርአየት ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር እንተ ውስተ መቅደሱ ይላል የጳጳሱንስ ነገር ከግብጽ ቢያመጣም ባያመጣም ገናናው የኢትዮጵያ መንግሥት የወደደውን ሊሠራ ይችላል ይህን ሁሉ ሐተታ የጻፍኩበት ምክንያት ባላገር በርስቱ ጉልማሳ በሚስቱ ንጉሥ በመንግሥቱ አምላክ በምልክቱ እንደሚሉት ሁሉ የኢየሩሳሌም ርስታችሁ ነገር ሁላችሁንም በየቤታችሁ ሳያሳዝናችሁ አይቀርም ብዬ ነው ። ክቡራን ወንድሞቼ በናንተ ባዋቆች መካከል ደፍሬ ስለ ጻፍሁ ይቅርታችሁን እለምናለሁ ።

ንቡስ ጸጋ ሥላሴ ጌታሁን ።

ሕግን ስለ መጠበቅ ።

የእግዚአብሔርን ሕግ ብንጠብቅ የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ለሕይወት እንደሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎልን እናነባለን ሕጉን ባንጠብቅ(ብናፈርስ) ግን ለሕይወት የተፈጠረው ለጥፋትና ለሞት እንደሆነ እናውቃለን ቅዱስ ጳውሎስ በሮም ክታቡ ም ፱ ቍ፳፪ እግዚአብሔር ከሃሊነቱን ሊገልጽ በወደደ ጊዜ ታግሦ የቍጣውን መላእክት ለጥፋት የተዘጋጁ አድርጎ ያመጣል ዳግመኛ የቸርነቱን ምላት ስፋት ሊገልጽ በወደደ ጊዜ ለይቅርታ የተዘጋጁ አድርጎ መላእክትን ያመጣል ብሎ ነግሮናል እንዲህ ማለት እግዚአብሔር ያዘዘንን ካልጠበቅነው ለሕይወት የተፈጠረው ሁሉ ለጥፋታችን ይሆንብናል ማለት ነው ።

አሁን ባለፈው ዘመን ከዝናም ብዛት የተነሳ ብዙ አዝመራ እየተላለፈ ብዙ መከራ ጎደለብን ይህ መሆኑ ከሕጉ ብንተላለፍ ይመስላል ። አሁንም ያለፈ ቅጣት እንዳይመለስብን እግዚአብሔርን ፈርተን ንጉሥን አክብረን እንኑር በነፍስ በሥጋ እንገዛላቸው በነፍስ ማለት በጸሎት ማለት ነው ሲል ብርሃንና ሰላም ምክሩን ያበረክታል ።

ስላልተደረገ ወሬ መልስ ።

አውቶ ሞቢል ነጂ ሰው አስድጦ የገደለ እንደሆን ያለ ጥርጥር ታንቆ ይሞታልና አውቶ ሞቢሉም በኢትዮጵያ ምንም አይቀናውም ኢትዮጵያውያንም መኪናውን እንደ ምትሐት ይፈሩታልና አውቶሞቢልን መንዳት ለሱዳን ሰዎችና ለግብጽ ሰዎች ለቀዋል ብሎ ላለው አውቶ ሞቢል ነጂው ሰው ያስደጠ እንደሆነ ያለ ጥርጥር ታንቆ ይሞታል ያለው ባይን ያላየትን ነገር

ማውራት ትልቅ ውርደት ነው ለጸሐፊውም ያልተከከለ ወሬ በጋዜጣ ማግባት ዝንጋታ ነው ፡ የኢትዮጵያ መንግሥት የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ለህዝቡና ለነጂው የሰጠውን ደንብ ህዝቡም ነጂውም አክብሮ ጠብቆ ይኖራል ። ይኸውም የማዘጋጃ ቤት ደንብ አውቶ ሞቢል ነጅው ለማስኬድ በቻለ ጊዜ ተመርምሮ ሰርተ ፊካውን ተቀብሎ ስራውን በትክክል ያስኬዳል ነጅውም ሰው ቢአስድጥ መዘጋጃ ቤት በሰጠው ደንብ ነጅው ደንብ አፍራሽ ሆኖ ከተገኘ ወደ ቅጣት ቤት ይሄዳል እንጂ ታንቆ መሞት የለበትም ።

አውቶ ሞቢል አይቀናውም ያለው የሌላው ቀርቶ ከኢጣልያን አገር ከፊያት ፋብሪካ ቢጠይቅ ብዛታቸውን ለማወቅ ይችላል ። ካሜሪካንም የመጡ ብዙ አውቶ ሞቢሎች አሉ ። መኪናዋንም እንደ ምትሐት ይፈሯታል ብሎ የጻፈው ከምን ፀታ አገኘው? የኢትዮጵያ ልጆች እንኳን አውቶ ሞቢል ቤንዚን የሚአንቀሳቅሰውና ሰይፍ መዞ ጦር ይዞ ቢመጣ እንዳይፈሩ የታወቀ ነው ። የኢትዮጵያ ልጅ በድፍረቱና በአውቀቱ በየው ሥራ ቶሎ በመንቃቱ የሚያዩት ሰዎች ሁሉ ያደንቃሉ ።

ለግብጽና ለሱዳን ለቀዋል ያለው የሱዳን ሰው በኢትዮጵያ የሚነዳ አንድም የለ ፡ ይኸውም የሌለውን አለ ብሎ መጻፉ ትልቅ ሐፍረት ነው ። የግብጽ ሰዎችም ያላቸው የኢትዮጵያ ልጆች ያስተማሯቸው ናቸው እንጂ ከሐገራቸው ተምረው የመጡ የሉም ። በፋብሪካም ሥራ ውስጥ የኖሩ የግብጽና የሱዳን ሰዎች አይደሉም እንጂ ሌሎች ሰዎች ጋርያጋ እያቆሙ የሚነግዱ አሉ ። ለዚሁም ጥቃታችንን የማይወድ የጥበብ መሪ ብርሃንና ሰላም መልሶለታል ።

የፊያት ሼፌር ወልደ ጻድቅ ዘሊቀ መኳስ መኰንን

ስለ ዱክ ዴሊ አብሩሲ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በ፲፱፻፲፮ ዓ ም የአውሮጳን ትልልቆች መንግሥቶች ለመጐብኘት ሔደው ነበርና በዚያው ዘመን ግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ ቪክቶር አማኑኤልን ለመጐብኘት ወደ ኢጣልያ ዋና ከተማ ወደ ሮማ ደርሰው በታላቅ ማዕርግና ክብር ተቀብለዋቸው ነበር ።

አሁን ደግሞ ግርማዊ ንጉሥ ቪክቶር አማኑኤል ፫ኛ በበኩላቸው የመጐብኘት ብድር ለመመለስ አጐታቸው ልዑል ዱክ ዴሊ አብሩሲ በዚሁ ዓመት በግንቦት ወር ውስጥ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ግርማዊት ንግሥተ ንግሥታት ዘውዲቱንና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን እንዲጐበኙ ሊሰዷቸው ነው የማለት ወሬ በእርግጥ ስለ ተወራ የአቀባበሉ ነገር ሁሉ መሰናዳት ተጀምሯል ።

ይህም አደራረግ የሁለቱን መንግሥቶች ወዳጅነት የሚያሰፋና የሚያጸና መሆኑን ያስረዳል ።

በዚህም መካከል አንድ ሰው በመጋቢት ፫ ቀን በብርሃንና ሰላም አንድ የጋዜጣ ቃል አሳትሞ ስለ አወጣ የወጣውን ጋዜጣ የሚያነቡ አንዳንድ ሰዎች ይህ ጋዜጣ የተጻፈበት ምክንያቱ ሳይገባቸው ቀርቶ ተቸግረው ነበር ።

ነገር ግን ይህን ጋዜጣ ያሳተመ ሰው ለሀገሩ እንግዳ መሆኑንና የመንግሥት ሠራተኛ አለመሆኑን በመጀመሪያ አውቀው ቢሆን አይቸገሩም ነበር ። እርሱም የራሱን አሳብ አንድ ገጽ ያህል እንደ መቅድም አድርጎ ጨምሮ ጽፎ ስለ አሳተመ ነው እንጂ የሚበልጠው ቃል ከውጭ አገር ጋዜጣላይ የተገለበጠ ነው። በዚህም እንደ መቅድም ሆኖ በተጨመረው ቃል ውስጥ በሁለት መስመሮች ላይ የበረታ ቃል ገብቶ ስለ ተጻፈ ምንም እንኳ ባለጋዜጣ ነጻነት ቢኖረው ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለጊዜው የማያስፈልግ መስሎ ስለ ታያቸው መቅድሙን የጻፈው ሰውና ያተመው የብርሃንና ሰላም ዲሬክተር መቀጫ እንዲከፍሉ አዘዋል እየተባለ ሲወራ ሰምተናል።ስለዚህ በመጋቢት ፫ ቀን የወጣው ጋዜጣ እንደ ቁም ነገር አለ መቆጠሩን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሁሉ ሳያውቁት አይቀሩም ፡፡

በቴሌግራም የመጣ የውጭ አገር ወሬ ።

ፓሪስ ፤ ትርፍ እናገኛለን ባዮች በባለ ጥቂት ገንዘብ ላይ በተደረገው ጉዳት ከ፴ ሚሊዮን የሚበልጥ ገንዘብን ያጠፉ ሔንሪ ሮሽት የሚባል ባለ ባንክ ከተያዘ በኋላ በቅጡ የሚያዙ ሌሎችንም በመታየት የሚገርም እንቅፋት ተገልጠዋል ።

ሪጋ ፤ ያኒስ ካርኮሰተየ ለቶንያ ረፒብልክ ፕረዚዳን ሙቶዋል ።

ካልኩታ ፤ በካልኩታና በማደረስ ምድር ባቡር ማገናኛ ዘንድ ባቡሮች በመጋጨት የተነሣ ፴፪ ሰዎች ሙተዋል ፻፳ ም ቈስለዋል ፡፡

በርሌኖ ፡ እስተርዝማን የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ፤ የኢጣሊያንና የመስኮብንም አምበሳደሮች በማክበር ተቀብሎ ተነጋግሮዋቸዋል ። ጋዜጣው እንግዲህ ፡ የተደረገውን ቈይታ ዋና ቁም ነገር በሆነ ሥራ ነው ይላል ።

ማልታ ። ዮህን ዱካን (የሚባል) ጀነራል ለደሴቱ ኀበርነር ተሾሙዋል ።

ፐኪኖ ፤ (ቺና) የኖርዲስታ ሠራዊቶች የዋፐይፉ የሚባል ጀነራል ሠራዊቶችን ወግተው ከንኪዮው የሚባል አገርን ይዘዋልና ድል የተነሱ ሠራዊቶች ወደ ያንግ በኩል ሸሽተዋል ።

ሻንጋይ ፤ ባለፈው ሳምንት በሺና ሠራዊቶች ተማርኮ የነበረ ያሜሪካን መርከብ እንደገና ያሜሪክ ሠራዊቶች ወስደውታል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሙዋቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው ፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው ። ፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው ። ፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው ፣ ፲ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ። ፭ ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ
ታሪክ ደስታና ክብር ። ፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው ፮ ብር

ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፫	ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው ፤	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፪	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት ፤	፩	ብር
ያማሪኛ ሰዋስው ።	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ፡	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን ።		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
ወዳጄ ልቤ ።		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ ።		አላድ
ያማሪኛ ፊደል ፡		ሩብ
አሳብና ምኞት ፡		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት ።		ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር ።	፪	መ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ፡	፩	ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ።	፩	ሩብ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ብር ።
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፹፭ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፫ብር ፳ መ
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ከሩብ
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፬ ብር
አቡጀዲ መነጸር	፩ ኮረጃ	፻፴፪ ብር ።
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፻፴፱ ብር ።
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፳፫ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፭ ብር ።
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፮ ብር ።
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፵፮ ብር።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፪ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፬ መ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ እስከ ፲፭ ሣን ነው ።
በአንድ ብር	፲ ሊሬ ፺ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ፴ ሳንቲም ነው
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፯ ብር ።

ሩ ግ
RUGBY
ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል ።

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

የዘህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፤ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፊታውራሪ ጴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሂስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፤ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፤ መጫሚያ በያይነቱ፣ ወንበር በየዓይነቱ፣ ብረት ሣጥን በየዓይነቱ፣ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

አዲስ አበባ በላጋር ጐዳና ላይ በሙሴ ተረስ ሆቴል አጠገብ አንድ ክፍል የሙሴ ሳቡሬ ቦታ ከነቤቱና ከነዛፉ ይሸጣል ፡ ቦታውን ለመግዛት የሚፈልግ ሰው በሙሉ ወይም በግሚስ አለዚያም የሚችለውን ያህል ከፍሎ ለመግዛት ይችላል የቦታውም ስፋት ፰ ሺ ሜትር ካሬ ነው ፡ ለመግዛትና ለማየት የሚፈልግ ሰው ሙሴ ሳቡሬን ይጠይቅ

Berliet



ቤርሊዩ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዩ አቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚአን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

AMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፣ ቁጥር ፲፫
3 me ANNÉE № 13

ሐሙስ መጋቢት ፳፪ ቀን ፣ ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 31 MARS 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen , Héritier du trône d' Ethiopie , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር
ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Diréсteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የተነገረ ተስፋ የሚጨረስበት ጊዜ አለው ።

መምሕር ብርሃንና ሰላም ጉባዔውን ዘርግቶ ማስተማር ከዠመረ ፫ኛ ዓመት ሆነ ትምርቱም እንደ ነፍስና እንደ ሥጋ ተዋሕዶ ከሰው ልብ ጋራ እየተዋሐደ ነፍስን በእውቀት እያሳደገ መንግሥት ከመንግሥት እያፋቀረ ሕዝቡን እየመከረ ይሂዳል የደንብና የሥርዓትንም ሕግ ብዙ ጊዜ አስተምሮ በሕጉ ይሠራበታል ነገር ግን አንዳንድ አስተዋይ ሰው መምራችን ብርሃንና ሰላም ያስተማረን ብዙው ላገር የሚጠቅም ሥራ ሁሉ አልተሠራም ከከበደ ሞትን ከመሰለ እንቅልፋችን ቀስቅሶን እንቅልፉ አልለቀን ብሎ ያንጎላጀናል ሥራው ላይደረግና ላይሠራ በየነምነቱ ምን ያደክመዋል የሚል ይገኝ ይሆናል ። መልሱን እንዲህ ብለን አምላክ ብርሃን ወሰላም በገለጸልን እውቀት እንመልስለታለን ፀሐይ የሚሞቀኝ የለም ብሎ መውጣቱን ውሀ የሚጠጣኝ የለም ብሎ መፍሰሱን ይተዋልን የተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ በተፈጥሮው ጸንቶ ይኖራል ብርሃንና ሰላም ከራሱ አንቅቶ የሚናገር ይመስልሃልን ሥላሴ ለሕዝባቸው ስለ አዘኑ ዳኛ እንዳያደላ ድኃ እንዳይጉላላ ብለው በሰው ልቡና በጸጋ ዙፋናቸው እየተገለጹ ያናገሩታል እንጂ ያውስ ቢሆን ሁሉ አንድ ጊዜ ይደረጋልን ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር ያለውን አታስብምን ቦ ጊዜ ለኵሉ ያለውንስ አልተማርኸውምን ብለን እንመልስለታለን ክቡራን አንባቢዎች በጎውን ነገር ሁሉ በኛ ዘመን ተደርጎ ካላየነው ብላችሁ አትሰቀቁ አትመረሩ ይልቅስ አጭር ስርጥ መንገድ ላሳያችሁ በጎውን ነገር ሁሉ መፈጸም የሚቻለው እግዚአብሔር ነውና ብርሃንና ሰላም ያስተማረውን ተፈጽሞ ለማየት አብቃን ብላችሁ ጸሎት አድርጉ ።

ዳግመኛ ለጊዜው የተወረወረ ኃይለ ቃል ቢስት ያስደነግጣል ባይገድል ያቆስላል ብርሃንና ሰላምም ለጊዜው ያስተማረውን ትምርት ማቆም ባይመቸው አሳቡና ጥቅሙ ለልጅ ልጆቹ ነው እንጂ ለጊዜው ብቻ አይደለምና ክቡራን አስተዋዮች ወዳጆቹ ድካሙን አትዘንጉበት በጎ ሥራ የሠራ ማንም ቢሆን ዋጋውን እንዳያጣ ታውቃላችሁ ።

በዘመነ ብሉይ የነበሩ ጻድቃን ነቢያት ካህናት በጊዜው የሚደረገውን የክርስቶስን መምጣት ለእስራኤል በነገሯቸው ጊዜ እንደማይደረግ እየቆጠሩት እንደ ድናሚት እየተነሡባቸው መከራቸውን ሲቀበሉ ይኖሩ ነበሩ ። ከቶ ከተናገሩት ነገር አንዱ ሳይደረግ የቀረ የለም ። አሁንም መምሕራችን ብርሃንና ሰላም ከሰበከው ስብከት ፡ ካስተማረው ትምርት አንዱ ይቀራል ተብሎ አይጠረጠርም ። ኢትዮጵያ ሥልጣኔ ከተደላደለላቸው ነፃነት ከጸናላቸው መንግሥታት አንድ ማኅበር ሆና እንድትኖር ሌትና ቀን ለሚጥር መምሕር ሊቀ ማኅበር ብርሃንና ሰላም ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይሉን እንዲሰጥልን እንመኛለን ።

የ፺፪ ገጽ ተከታይ ።

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

፲፫ተኛ ክፍል ።

እነሆ በላይ እንዳየነው የባንኩ ገንዘብ ወደ ፩ ሚሊዮን ፪፻፶ ሺህ ብር ነው ። ባንክኖት ከተለመደ በኋላ ግን ይህ ገንዘብ ቢያንስ ቢያንስ ስለ ፫ ሚሊዮን ፯፻፶፩ ሺህ ፯፻ ብር ሆኖ ያገለግላል ። ባለ አክሲዮን የሆኑትም ማህበረተኞች መቸም አክሲዮኑን ለሌላ ሰው ሸጠው ጥሬ ብር ሊያገኙ እንደሆነ ነው እንጂ እንዲሠራበት ብለው ለባንክ የሰጡትን ብር ከባንክ መልሰው ለመውሰድ አይቻላቸውም ። ማህበሩ ሲቆም ለ፶ ዓመት ይሠራል ተብሎ ነውና ። ማህበረተኞቹ ሁሉ ተሰብስበው ከማናቸውም አንድ ምክንያት የተነሣ የባንኩ ሥራ ይቅር ካሉ በቀር ሃምሳው ዓመት እስኪያልቅ ድረስ ለባንኩ ሥራ ያገባውን ገንዘብ መልሱልኝ ቢል አይሆንለትም ። ችግር ያገኘው እንደ

ሆኖ ግን ማኅበረተኛ መሆኑን የሚያስታውቅ በእጁ የያዘውን የምስክር ወረቀት ለሌላ ሰው አሳልፎ ሊሸጥ ይችላል ። ስለዚህም ምክንያት ሸያጩ ማኅበረተኛ መሆኑ ይቀራል ። አክሲዮኑንም የገዛ ሰው ደግሞ ጥሬ ብር ካስፈለገው እንደ ገና ይሸጣል እንጂ ማኅበሩ የመደበው ሃምሳ ዓመት እስኪያልቅ ድረስ በአክሲዮኑ ላይ የተጻፈውን ገንዘብ ከባንኩ ሊቀበል አይችልም ።

ስለ ዚህም አክሲዮኑን የያዙ ሰዎች የሰጠናችሁን ገንዘብ መልሱልን ብለው ያለ ጊዜ ያስቸግሩናል ብለው የባንኩ አለቆች አይሰጉበትም ። ስለ ዚህም ባንኩ ይሠራበታል ከተባለው ፫ ሚሊዮን ፳ ፱ ፹ ፩ ሺህ ፳፱ ብር ያክሲዮኑ ዋጋ የሆነው ፩ ሚሊዮን ፱፻ ፺ ሺህ ብር ጊዜው ሳይደርስ መልሱ እንባላለን ብለው የባንኩ አለቆች አይሰጉበትም ከልነው ገንዘብ ስጡን እንባላለን ብለው የሚሰጉበት ቀጥሎ የተጻፈው ገንዘብ ብቻ ነው ።

የባንክ ኖት	፩ ሚሊዮን ፱፻፺ ሺህ ብር
አደራ ካስቀመጡት ገንዘብ	
ከፍለው ያበደሩት ።	፬፻ ፲ ሺህ ፳፱ ብር
ድምሩ	፩ ሚሊዮን ፲፱ ፶ ፲ ሺህ ፹፱ ብር ።

ለዚሁም መክፈያ በባንክ ቤት ውስጥ ስለ ውስትና የሚቀመጠው ወደ ፲፱ ፹፫ ሺህ ብር ይሆናል ። ስለዚህም ባንኩ ከሚሠራበት ገንዘብ ፩ ሚሊዮን ፹፩ ሺህ ፳፱ ብር ፣ ሕዝቡ በእምነት ሊሠራበት ነው እንጂ ዋስ የለውም ።

በሥራ ሰልጥኖ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እራሱ የሚሠራ ሕዝብ በእንደዚህ ያለው ነገር ይጠቀምበታል እንጂ አይጐዳበትም ። እርስ በርሱ ሲለዋወጥ መግሪያ ሆኖ የሚረዳው ብርና ወርቅ እንዳያንስ እንደዚህ ያለ ብልሀት ያወጣበታል ። በዚህም ብልሀት ጥቂት ብር እንደ ብዙ ሆኖ ያገለግለዋል ። በሥራ ያልሰለጠነ ሆኖ የሚያስፈልገውን ነገር እራሱ ለመሥራት የማይችል ሕዝብ ግን ባገሩ ባንክ ኖት ቢለመድ የሚጠቀመው መሆኑን ያስጠረጥራል ። የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እራሱ ለመሥራት የማይችል ሕዝብ መቼም ልብሱና የቤቱ መግሪያ የሚመጣለት ከውጭ አገር ነው ። ደግሞ ልብሱንና የቤቱን መግሪያ የሚሸጡለት ሕዝቦች ግን የሚቀበሉት ዋጋቸው ጥሬ ብር ብቻ ነው ። ባንክ ኖት አይቀበሉም ። ባገራቸው ዋጋ ሳይጐድል በገበያ የሚሄደው ያገራቸው ባንክ ያተመው ባንክ ኖት ብቻ ነው ። ጥሬ ብር ግን የትም ቢሄዱ ከዋጋው የሚያጐድለው ብዙ አይደለም ።

እንግዲህም ባንድ አገር ባንክ ኖት ሲለመድ አንዱ ብር ስለ ሁለት ሊሠራ ነው ። አንድ ሰው አንድ ነገር ሸጦ ባንክ ኖት ሲቀበል ከንዱ ሰው በባንክኖቱ ላይ የተጻፈውን ጥሬ ብር ይቀበላል ። ባንክኖቱን የሚቀበለው ሰው መቼም ብሩን በፈለግሁ ጊዜ በባንክ ተቀምጧልና እወስዳለሁ ብሎ ከማመኑ የተነሣ ነው ። ባንኩ ግን ብሩን አያስቀምጥም ፣ ለሌላ ሰው ያበድረዋል እንጂ ። ስለዚህም አንዱ ብር ስለሁለት ብር ሆኖ ስለ ሠራ ባገሩ ውስጥ ያለው ብር ባንድ ጊዜ እጥፍ የሆነ ይመስላል ሕዝቡም የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እራሱ የሚሠራ ከሆነ በሕዝቡ ውስጥ ልብስና የቤት መግሪያ ለማስመጣት የሚያስቡ ሰዎች እጥፍ ሊሆኑ ነው ። ጥሬ ብር የያዙ ሰዎች መቼም ለሚያስመጡት ዕቃ ዋጋ ጥሬውን ብር ይሰጣሉ ። ባንክኖት የያዙ ሰዎች ባንክኖቱ ወደ ውጭ አገር አይሄድላቸውምና ወደ ባንኩ አገር ሄደው ለብር ሊለውጡት ነው ።

በመጀመሪያ ባንኩ አይቸገርም ይሆናልና ፣ ባንክ ኖትን እየተቀበለ ባንክ ኖቱን ለሚያመጡ ሰዎች ጥሬውን ብር ይሰጣል ። ችግር የሚያገኛቸው ግን በመጀመሪያ ብቻ ነው ። ባንክ ኖት የያዘው ሰው ሲበዛ ግን ሳይቸገሩ አይቀሩም ። መቼም ባንክ ኖቱን የያዘ ሰው ለኑሮውም የሚፈልገውን ነገር ካልገዛበት ባንክ ኖቱ አይጠቅመውም ። የሚያስፈልገውም ነገር ሁሉ ባገሩ የሚሠራ ቢሆን ወደ ባንክ ቤት ሂዶ በባንክ ኖቱ ላይ የተጻፈውን ብር በጥሬው ስጡኝ ሳይል ባንክ ኖቱ ብቻ ሁሉንም ነገር ለመግዛት ይችላል ። በሥራ ያልሰለጠነ ሕዝብ ግን አንዳች ነገር ባገሩ አይሠራም ። ሁሉም ነገር የሚመጣለት ከውጭ አገር ነው ።

ስለዚህም የተቀበለውን ባንክ ኖት ከውጭ አገር የሚመጣውን ዕቃ ሊገዛበት ሲፈልግ ወደባንክ ሂዶ ለብር ይለውጠዋል ። ባንኩም የራሱ ብር ቢያንሰው አደራ ከተቀመጠው ጥሬ ብር ከፍሎ ይሰጣል ። ገንዘቡን አደራ ያስቀመጠ ሰውም ገንዘቤን ስጡኝ ሲል ቢመጣም ባንክ ኖት ይሰጡታል ። ሰውየውም ገንዘብ ያስፈለገው ባገር ውስጥ ለሚፈጽም ጉዳይ ከሆነ ባንክ ኖቱ በገበያ እንዲሄድ ያውቃልና ፣ ሸክሙ ስለ ቀለለለት ከጥሬ ብር ባንክኖት ሊቀበል ይወዳል ። በጊዜም ብዛት ባገር ባንክኖት እየበዛ ይሄዳል ። ጥሬው ብር ግን ለተሠራ ዕቃ መግዣ ወደ ውጭ አገር ይሄዳል ። ይህም ከሆነ በኋላ ባንክ ኖት በእጁ የያዘ ሰው ከባንክ ጥሬ ብር እንዳይፈልግ ብልሀት ካልተደረገ በቀር ባንኩ በጣም ሳይቸገር አይቀርም ። ባንኩ መቼም እራሱ ወደ ጭንቅ እንዳይገባ ይፈልግ ይሆናል ። ስለ ዚህም ከርሱ የተበደሩትን ሰዎች አስጨንቆ ይይዛል ። ተበዳሪዎቹም የሚከፍሉትን ገንዘብ ሳያገኑ ቢያዙ ፣ ነጋዴዎች እንደ ሆኑ ፣ በእጃቸው ያለውን ቆዳና ቡን ባላገሮችም እንደሆኑ መሬታቸውን በርካሽ ለመሸጥ የግድ ይሆንባቸዋል ። ቆዳውና ቡናው ሌላውም ከገሩ የሚገኘው ዕቃ በርካሽ ሲሸጥ የሕዝቡ ድካም በከንቱ ስለ ሄደ ሕዝቡ መክሰሩ ነውና መንግሥት ይጐዳል። ባላገሮም መሬቱን በርካሽ ለመሸጥ የግድ ሲሆንበት ባገሩ ውስጥ ያለው መሬት በጥቂቶች ሀብታሞች ሰዎች እጅ ሊጠቀለል ነውና ባገሩ ውስጥ የሚያርፍበት ቦታ ያጣ ደኃ ሊበዛ መሆኑን ያሳየናል ። ከዚህ ቀደምም እንደ ተረዳነው ባገሩ ድሀ ሲበዛ ፣ ለመንግሥት ጉዳት ነው ። መሠረቱ ይነቃነቃል ።

ስለ ዚህም ሕዝቡም በሥራ ባልሰለጠነ አገር ባንክ ኖት ሲለመድ ባገሩ ላይ ትልቅ ጉዳት ሊያወርድ ይችላል ። ባገሩ ባንክ ኖት ሲለመድ መንግሥት ወድያው ሕዝቡን በሥራ ለማሠልጠን ቃጥቆ ከተነሣ ግን ባንክ ኖት ቢለመድ ጉዳት የለበትም ። ይልቁንም ትልቅ ጥቅም ይገኝበታል ። ባገሩ ውስጥ የሚበቃ የለውጥ መግሪያ የሌለው ሕዝብ ብዙ ሀብት እንዳያገኝ ከዚህ ቀደም ተረድተነዋል ። ስለ ዚህም አንዱ ብር ስለ ሁለት

ስለ ሶስት እየሆነ እንዲያገለግል የሚያደርግ ባንክ ኖት ነውና ሁሉንም ነገር ራሱ ሊሠራ የሚችል ሕዝብ ይጠቀምበታል።

የሚአስፈልገውን ነገር ሁሉ ከውጭ አገር የሚአስመጣ ሕዝብ ግን ጥሬው ብር በባንክ የተቀመጠ መስሎት እርስ በርሱ በባንክ ኖት ሲለዋወጥ በገሩ ያለ ጥሬ ብር ሁሉ ለዕቃ መግዣ ተብሎ ወደ ውጭ አገር ይሄዳል ። ከዚህም ምክንያት የተነሣ ሕዝቡ በልሠለጠነ አገር ውስጥ ባንክ ኖት ሲለመድ ከላወቁበት ጉዳት ያመጣል ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት መጽሐፍ ነው ።

መልስ ።

በ፫ተኛው ዓመት ብርሃንና ሰላም ቁጥር ፲፪ብርሃንና ሰላም ኀዳሪና ማኅደር ተናጋሪና አናጋሪ ሆኖ የእግዚአብሔርን ሕግ ብንጠብቅ የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ለሕይወት እንደሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎልን እናነበለን ። ሕጉን ባንጠብቅ ብናፈርስ ግን ለምሕረት የሚሆኑ መላእክት ። ለመዓት ይሆኑና ታዘው ያጠፋሉ ። ለመዓት ሆነው የሚያጠፉ መላእክትም ለምምሕረት ሆነው ያድናሉ ። ቅዱስ ጳውሎስም በሮም ክታቡ ም ፬ ቍ ፲፪ ነገረን አለ ። እውነት ነው ትእዛዙንም ካልጠበቅን መጥፋታችን አይጠረጠርም ። ብርሃንና ሰላም ሲያስረዳ አሁን ባለፈው ክረምት ከዝናም ብዛት የተነሣ ብዙ አዝመራ እየተላለፈ ብዙ መከር ጕደለብን ይህ መሆኑም ከሕጉ ብንተላለፍ ይመስላል አለ ።

እንዲህ ማለቱ እያወቀ አላዋቂ መስሎ ወዘፍ አደረገው እንጂ ። እውን የዝናም ብዛት ዕኽል ያጠፋብንና ረኀብ ይሰለጥናል ማለት አልመሰለኝም ፡ ነቢዩ ሄኖክ የስነ ፍጥረትን ነገር ሲናገር ቆይቶ በመዋዕለ ኃጥአን የሐጽራ ክራማት አለ እንጂ ዝናም ይበዛል ለላለም ትርጓሜውም በኃጢአተኞች ዘመን ድርቅ በና ይሆናል ማለት ነው ። ስለዚህም እድላሞቹ ግርማዊት ንግሥታችንና ልዑል አልጋ ወራሻችን ፍጹም ደስታ ይገባቸዋል ። ግርማዊት ንግሥታችንና ልዑል አልጋ ወራሻችን ከኃጢአት ንጹሖችና እድላሞች ባልሆኑ በዘመናቸው ዝናም በማጣት እንቸገር ነበር እንጂ ፡ ከቶ ከዝናም በዛ በማለት ባልተቸገርንም ነበርና ደስታ ይገባቸዋል ።

ብርሃንና ሰላም ዘለፋ ይመስልብኛል ብሎ ስለ ትሕትና ማዕበሉን ሳይደፍረው ቀርቶ ነው እንጂ ነገሩስ እንዲህ ይመስላል ። ዝናም ቢበዛ ጨርሶ አላጠፋም እኽሉ ግን ደምበኛ ዝናም የመታው ሆነ እንጂ በጣም አልተቸገርንም ፤ ሁለተኛም ዝናም ቢበዛ ለጕመኑ ለድንቹ በዝናም ለሚገኙ ቅጠላ ቅጠሎች ሁሉ ልምላሜ ሆነዋቸው ፈጥነው ይደርሳሉ ማለት ሁል ጊዜ ሰኔና ሐምሌን አይጠብቁም ። የድርቅ የበና ብዛት ከሚያወጣው ጥጋብም የዝናም ብዛት የሚያወጣው ረሃብ አይጐዳም ።

እውነት መናገር ከሆነስ ትልቅ ጕዳት (ከዚህ) አለላችሁ የኢትዮጵያ መኳንንቶች ብዙ ዘመን ለመንግሥታቸው አጥንታቸውን ከስከሰው ደማቸውን አፍስሰው ደጅ ጠንተው ከተሾሙ ኋላ ነገ ዛሬ እንሔዳለን በማለት ከተማ ስለተቀመጡ እነሱም ይቸገራሉ ሠራዊታቸውም እነሱም እየተራቡ ሹመታውንም ያስወድዳሉ ከተሾሙ በኋላ በፍጥነት ሔዶ አገር መጠበቅ በግድ ያስፈልጋል የተሻሩትም የተሾሙትም ከተማ ሲቀመጡ ጊዜ ። እንግዲህ ድሆቹ ማን ይመለከከታቸው ። ዕኽል የተወደደበት ምክንያቱ አዳንና በቆን ታምኖ ሁሉ ከተማ ከመቀመጡ የተነሣ ነው እንጂ ዝናምስ ያጠፋው ነገር የለም ።

ይህም ነገር የኢትዮጵያ መንግሥት አክብሮ ለሾማቸው ለሚኒስትሮቹ ያሳስባቸዋል በከተማ ያሉት ሳይወጡ ዳራገር የነበሩት ወደ ከተማ እንዳይገቡ ለማድረግ የሚችል ስልጣን የተሰጠ ለነሱ ነውና ።

ይልቁንም ፈጽመው ዕኽሉን አስወድደውት የነበሩ ቸር ቻሪዎቹ ናቸው ስለዚህ ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ። እንደሚበላው መጠን ከሚሸምት ሰው በቀር በጅምላ እየሸመተ የሚሸጠውን ዘበኛ አቁመው ስላስጠበቁት ሰው ሁሉ በጣም ደስታ አድርጓል ።

ስለሆነ ግን ሕዝብ የተስማማበትንና ጊዜ የወደደውን ማድረግ ይሻላል ማለት ነው እንጂ ገንዘባችን ስለተወደደ በጥቂት በጥቂቱ ሸጠን አራሾቻችን ብዙ ብዙ ብር አገኙ ብለን ዕድግ አያሳዝነንም ነበር ።

አንባቢ ሆይ ብርሃንና ሰላም የጻፈውን ስመለከት በምስጢሩ ወደ ዕህል መወደድ ሔደና ምክንያቱን እያወቀ ለዝናም ሰጠ እኔም ደቀ መዝሙር የመምሩን ቅኔ ይዞ እንደሚከራከር ጀምረህ ለምን ተውኸው ስል ነው እንጂ ሌላ የለበትምና እንዲያው መልስ ከሌ ብለህ የመቃወም ቃል እንደ ሌለበት መርምር ።

ዝናማችን ንጹሕ ሀገራችን ለምለም እኽሉስ መቻነሰው።
አረም እምቢ አለ እንጂ መጭ እየወረሰው ።

የፍታሔ ንጉሤ ።

መልሽና የፍቅር ተግሣጽ።

በ፫ተኛው ዓመት ብርሃንና ሰላም ቁጥር ፲፪ አቶ ጸጋ ሥላሴ ጌታሁን ስለ ኢየሩሳሌም ርስታችን ብሎ ጀምሮ ክቡር ብላታ ኅሩይ እስከ ተመላለሱት ቃል ከልብ የሚገባ ነገር ጽፏል ። ከቃሉ መተካከል እውነት መሆኑ ፡ እውነት ከመሆኑ የቃሉ መተካከል ያስደንቃል ።

በኋላ መልከሙ ነገር ሳያልቅ ምንጊዜም የፍጡር ዕውቀት የጸጋ ነው እንጂ የባሕርይ አይደለም ብሎ የጻፉን ነገር ገናናው የኢትዮጵያ መንግሥት ከግብጽ ቢያመጣም ባያመጣም የወደደውን ሊሠራ ይችላል አለ ። እውነት ነው ።

ገናናው የኢትዮጵያ መንግሥት የሚወድ በክህነት ነፃነቱን ነው ። ከራሱ ሰውን ወዶ ፡ ከሰው ራሱን ይጠላና ፡ ሕዝብ የወደደውን ጠልቶ ፡ ሕዝብ የጠላውን ይወዳል የማለት አሳብ እንዳያስብ ይህን የሚሰማ ጆሮ ምን ጆሮ ነው ፡ አይደረግም ።

ወየው ጉድ አሁን ምን ቸገረህና ቢሆን የቤተ ክህነትን ነፃነት ባይሆን እንደ ቀድሞ መኖርን ማን ይከለክለኝ ብለህ ፈራህና ምኞትህን ለግብጽና ለኢትዮጵያ ታሻማለህ ፤ ፍልጥ (ለይ) ለይተህ ተመኝ ነው ። አይደለም ሲሉ ቆመው የቀሩብትን

ምን እንደ ሆነና አንተ እንድታውቀው አይጠረጠርም ።

የፍታሔ ንጉሜ ።

ስለ ድሬዳዋ የ ክምና ቤት ።

የድሬዋ ከተማ እየሰፋና ሕዝቡ እየበዛ ስለ ሔደ የምድር ባቡር ኩምፓኒያ ለሠራተኞቹ ያመጣው ምንም አንድ ሀኪም ቢኖር እንኳ ለከተማው ሰው ሁሉ የሚበቃ አልሆነም ። ስለዚህ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በድሬዳዋ ያለው ሀኪም አንድ ብቻ በመሆኑ ሕዝቡ መቸገራቸውን አውቀው ዶክቶር ብሩንስ የተባለ ሀኪም ከጀርመን አገር አስመጥተው በዚሁ ዓመት በመጋቢት ፳ ቀን ወደ ድሬዳዋ ሰደዱት ። ሥራውንም እስከ አንድ ወር ይጀምራል ይባላል ።

የድሬዳዋ ከተማ ሕዝብ ለከተማ ጥዳት ፣ ለጤና መጠበቂያ እያሉ ገንዘባቸውን ይከፍላሉና አሁን አዲስ የሀክምና ቤት በመከፈቱና ሀኪሙ በመምጣቱ ደስ ሳይላቸው አይቀርም ።

የምድር ባቡር ኩፓኒያም ሀኪም አምጥቶ እስከ ዛሬ የከተማውን ሕዝብ እንዲታከም እያደረገ በመርዳቱ ምስጋና ይገባዋል ።

ወደ ፊትም ልዑል ተፈሪ መኰንን በኢትዮጵያ አውራጆች እንደ ድሬዳዋ በመሰለው ከተማ ሁሉ የሀክምና ቤት እንዲከፈትና ሀኪም እየተቀጠረ እንዲያክም ያደርጋሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን ።

የበለጠ ትምርት ።

ትምርትን ማሠልጠንና መንግሥትንም ማክበር የሚያስገድድ እንደ መሆኑ ስለመግለጽ በሚመስል አካሄድ ዘንድ ጋዜጣ ከቆመ ጀምሮ እስታሁን ድረስ እየቀጣጠለ የሚነገር ያለው አንዳንድ ትንንሽ ማመልከቻ በቀር ትምርት ትምርት በመባል ብቻ በተጻፉ ቃሎች ላይ የሚያሳይ ትንሽ ትርጓሜን በማቀርብበት ጊዜ ይቅርታን እለምናለሁ ።

እያንዳንደ የዓለም መንግሥታት ሁሉ ነው አስተማለት መቻል ድረስ ፡ ምንም የየመንግሥቱ ቋንቋ ትምርት ካለመስፋቱ የተነሣ በየወረዳው ከሚገኝ ተራራ መጋረጃ ተከናንቦ እየተራራቀ (የባሥ በኛ ላይ ሲሆን) ባልሠለጠኑ አገሮችም እንዲሁ እንዳለ ሲሆን በያለበት ሥራውን ለመሥራት እርስ በራሱ የሚስማማበት አዳዲስ ዲያለት ቋንቋ እያወጣ ቢኖር ነው እንጂ አሁን ባላት ሥፋት ላይ ገና ሊጨመርላት ዘንድ ተሥፋ ያለን ባንድ እረኛ የምትመራ ኢትዮጵያ ሁሉዋ የግዕዝ ልጅ መሆንዋን ከንዳንድ አታላይ በቀር የሚጠራጠር ሰው አይኖርም ።

መንግሥት ማለትም እንግዴህ በዓለም ሁሉ እንዳለው ልክ ንጉሥና የመንግሥቱ ሕዝብ የሚናገርበት ወደተመረጠች እንዲት ቋንቋ በመዘንበል አባሎች ጭምር ሲሆን ባንድ እረኛ ትመርታ የታመኑ ወዳጆችን ዘማበጀት ነቀፌታ የማይኖርበትንም ደምብ በማቆም እራስዋን አክብራ በሁሉ አካሄድዋ በሌሎች ዘንድ ለመታፈር የምትጣጣር አገር ማለት ነው ።

ግዕዝ ስል በመስማት የሚደነግጡ ይኖራሉ ።

ነገር ግን ግዕዝንም ብል የመናገሻውን ዋና አማርኛ ቋንቋ ወልዳልናለችና ወላዲቱን ለንዋየ ቅድሳት አስረክበን ዞር ሲያንስብን ተሌላ መበደራችን ጭምር ሲሆን ወደእናቲቱ እየተመላለስን እስቲቻለን ድረስ ልጅዋን ከፍ ከፍ በሚልልን መንገድ ሁሉ ለማግኘት መጣጣር ነው የሚያስፈልገን የነበረ ።

ብቻ እሳት ቢዳፈን የጠፋ ይመስላል እንደሚል ቢሆን፤ ኩነትም ነው ። ስለምን መቸም የቀሩ ሌሎችስማ በትንሽ ሲሆን፤ መለያየታቸው ነው እንጂ እኒያ በእስላም ተጠቅተው ፈጽሞ ከ ዙ ዘመን ከትምርት የራቁ እንደነጋላና እንደነሻንቅላ ምንም በቋንቋቸው ምናልባት ፈጽሞ የራቁ ቢመስሉ ፤ አስተውሎ ለተመለከተው ግን እነሱም በንግግሩ መካከል አልፎ አልፎ ያንን የናቲቱን ልዩ ልዩ ዘር የሚገኝባቸው መሆኑ አለመታወቃቸው ነው መሰለኝ ብላ የሚሻል ሲሆን ፡ አንዳንድ አዋቆች ነንባዮች ፤ የአማርኛንም ልጆች ፤ የግዕዝንም ልጆች የትግሬኛም የጋሊኛም የሻንቅላም ልጆች ፤ በማለት ፤ ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ ባለመማር የተነሣው ፤ በየወረዳው የሚነገር ዲያነት የሚባል ልዩ ልዩ የባላገር ንግግር በሚነገርበት አውራጃ ያለው ልዩ ልዩ የሕዝብ ክፍል ሁሉ ነው እስተማለት ነው መሰለኝ።

ሕዝቡን አ ዱ ከሌላው መለያየት በሚያመጣበት አኳሆን ሳይጻፉበት ባለመቅረታቸው ስላወቅሁ ነኝ እና ፡ ይህንን ሥራ እንዲህ ብሎ ወደ ፊት ያለ እንደሆን ኢትዮጵያን ፈጽሞ ወደ መለያየትዋ የሚያስኬዳት ነው ፤ ስለዚህ ተሁሉ ተሁሉ በፊት መንግሥቱና ባላገሩ በየብቻው ቋንቋ ከተናገረ ዘንድ የገጋና የተገዢ አገር ነው የማለት እንጂ ወንድማማች ለማለት ጥርጣሬ ያለበት ስለሆነ ፡ በዚህ መጠንቀቅ ያስፈልገናልና በሌላው እጅ ያለውን ጽፈት ከመጥቀስ አሁን ላልኩት ማስረጃ አሁን ጊዜ የሚደረግ ያለውን ማመልከት ይሻለኛል ።

ምንም ልኩን ባላውቀው እንደ ማየው ግን በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ማለት ሳያውቅ በክርስትና የሚኖር ሕዝብ ጋላ ለወደፊት ከመረጠው ሃይማኖት እንዲገባ በክንቱ እንዳይጠፋ እናስተምረው ብለው ከልዩ ልዩ ውጭ አገር መንግሥታት አገር እየመጡ ወዲህ የደረሱና የሚደርሱ የልዩ ልዩ ባህል ክርስትና ሃይማኖት መምሕራን ትምርቱን ሲወጥኑት ሳሉ የሚያስተምሩበት ቋንቋ ስላልነበራቸው በየያዙት ያገራቸው ቋንቋ መጀመራቸው ባላስጎዳም ነበር ።

ነገር ግን ካ፵ ዓመት የበለጠ ጊዜ ከውስጥዋ ሲኖሩና የያንዳንድ መንግሥት ሁሉ አኗኗር እንዴት እንደመሆኑ አገባቡን በቀጥታ ሲያውቁት የባላበት መንግሥት ቋንቋ በሚያስተምሩት ሥራና መሣርያም ሳይቸግራቸው ፤ ከጥንት ጀምሮ በጠዳችው ግዕዝ ዘንድ ከነ መጽሐፍቶችና ከነ ሊቃውንቶችም የነበረች ያለችም ኢትዮጵያ በአረመኔነት እንደበት ናት የነበረች በማለት ከቀሩት ባሉ አገሮች ሕዝብ ለማሣማትዋ እስታሁን ድረስ በፊደላቸው እየጻፉ ያንን በዲያለት ንግግር ሲናገር የነበረውን ሕዝብ ምናልባት ከየ ቋንቋ ጭምር ሲሆን በዚያው ዲያለት ብቻ በማሥተማራቸው ሕዝቡ ከባላባቱ መንግሥት ቋንቋ ተለይቶ መቅረቱ መሆኑ ባለ መጠንቀቃቸው አላበጁም ።

የጥርማዊት ኢትዮጵያ መንግሥታችን ምኒሥትሮች እስተዳዳሪዎች ሆይ ፤ መቸም ይኸ ዋናው ሥራ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል እምልዑላን አልጋ ወራሽ ተፈሪ ሲሆ

ንላቸው ፈቃዳቸው መሆኑን የሚጠረጥር የለምና ፤ የጠፋውን ተገኘ መድኃኒቱ እንደ ሚባል ለዚሁ ሁሉ መድኃኒት ለማግኘት ተማክራችሁ እንደሚከተለው ሳታደርጉ አትቀሩም ብሎ ሕዝቡ የናንተን ተሥፋ ይጠባበቃል ።

፩ኛ ። ከሁሉ በፊት ግርማዊ ምኒልክ ካቆሙት ትምርት ቤት በትንንሽ ቀለበተኛ መምሕራን ወደፊት ሊል የሚችል ያማሪኛ ቋንቋ ትምርት በቶሎ ማቆም ።

፪ኛ ። በከተማ ያለም ሆነ ባ፡ሬቱም ውስጥ በልዩ ልዩ አውራጃ ያሉም የውጭ አገር መልክተኞች መምሕራንም ሁሉ እንደሠለጠኑ መንግሥታት አገር ደምብ ፡ አማሪኛ የመንግሥቱ ቋንቋ ጭምር የሌለው ትምርትን አታስተምሩ ብሎ አዋጅ መንገር

፫ኛ፡በየትምሕርት ቤቶቹ ሁሉ በእጅ ያለም ሆነ ተበድረው ይዘውት ያለክፍልም ሆነ በጥሩ ፎቶግራፍ የተነማ የኢትዮጵያ ጆግራፊ አቁሞ ለማስተማር ማፋጠን ።

፬ኛ በሚበልጥ ጆግራፊና ሐሳብ ላጡ ሲሆን ከተማሮች በብልጫ የተገኙ የሚቀበሉት ትንንሽ ገንዘብ መወሰን ።

፭ኛ አዋቂና ፍቅረ ብሔር ያለው ባላባት ምኒሥቴር መሾም

፮ኛ ትምሕርት ቤት በሚዘጋበት በየዓመቱ ባመቱ የተገኘውን ፍሬ መመርመር ።

፯ኛ ወዳጆቹ መንግሥታት ፈቃዳቸው ቢሆን ከሁሉ ትምርት የሚበልጥ ያው ነውና ንባብና ሐሳብ ካወቀ ወዲያ ፈቃደኛ የመሰለ ሁሉ የሚማረው የጥበብ ትምርት መምሕራን ማስመጣት ።

፰ኛ ምንም ትምርት አይፈጸምም ቢሆን እንዳቅሙ ዘመምሕሩ ይበቃዋል የተባለው ተማሪ ሁሉ ተመንግሥት ቤትም ሆነ ተያውራጃው የሚገኙ መኳንንቶችና አገረ ገዦዎችንም ሆነ የሁለቱን ፈቃድ በመጠየቅ ቀለቡን እየተቈረጠለት መላክ እንጂ ትንሽ ጊዜ በቦዘን ያሳለፈው እንደሆን ይረሳልና የመንግሥቱን ገንዘብ ፍሬ አልባ ሁኖ እንዳይቀር ተማሪውን አለማቦዘን ።

፱ኛ ፡ በ፯ተኛው ክፍል ተጽፎ ያለው ወዲህ መምጣታቸው የማይቻል እንደሆን እኛ ወዳጆቹ መንግሥታት የጥበብ መምሕራንን ወዲህ ከመስደድ ወዲያ ሂዶ ጥበብ ለማስተማር ካልሆነ በቀር ከዚህ ሊገኝ የሚቻለው የንባብና የጽፈት ትምርት ብቻ ለማስተማር ወደ ኤውሮጳ አለመስደድ ፤ ስለ ምን የሚከተለውን መመልከት ።

፲ኛ ፡ ምንም ልኩን ባላውቀውና እፊን መልቼ ባልናገር በኤውሮጳ ያሉናአሁን የሚሄዱ ተማሪዎች ሁሉ ተመቶ የሚያንሱ አይመስለኝም ። እንደምን ሰማው ልክ ቢሆን ወደኤውሮጳ የሚሄዱ ሁሉ ያውም ባይበቃቸው እየተዋረዱ ሲሆን ተ፶ ብር ያነሠ በወር አይቀበሉም መስለኝና ፶ውን ብር በመቶ ተማሪ ብናበዛው በየወር ፭ሺ ብር መሆኑ ነው ። በዚሁ አምስት ሺ ብር አሁን ካሉ መምራኖች ላይ የተመረጡ ሌሎች መምሮች ለመቅጠር አስመጥቶ መጨመር የሚቻል መሆኑን ስላወቅሁ ነኝና ግንዘብ መጥፋቱ ካልቀረ ምግብ ከኤውሮጳ ውድ በመሆኑ የተነማ ረሀብ ተማሪዎቹን ጤና የሚያስጣቸው መንግሥቱንም የሚታማበት ስለ ሆነብኝ ነው ስል አቀርባለሁ

ወደ ጥንት ነገራችን እንመለስ ።

መንግሥት ማለት እንግዲህ ከዚህ ቀደም ብለን አመልክተነው እንዳለን ልክ ምንም ልዩ ልዩ ዲያለት የሚናገር በመከከሉ ባይ ጠፋ ፡ እየተማረ በመንግሥቱ ቋንቋ እየ ተናገረ ባንድ እረኛ ከነ አባሎቹ ጋራ ተመርቶ የሚኖር የሕዝብ ማሕበር ነው ።

አሁን ከጠራነው የሕዝብ ማሕበር መከከል በተለየ ዋና መንግሥት ግን ፤ እርሻን በማረስና ከብቶችን በማርባት ንግድንም በማሰልጠን ሌላ ልዩ ልዩ ሥራንም በመሥራት ሀቡ ዘእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር ወዘ ቄሣር ለቄሣር እንዳለን በወንጌሉ መሪውን ግብርንና የተደነበው ልዩ ልዩ ቀረጥንም በቀጥታ መክፈል ብቻ ሳይሆን ደግሞስ በእግዚአብሔር ዘንድ ይችላል ተብሎ ተመርጦ አገሩን ለመጠበቅና እንዲሁም ላገሩ ጠቀሜታ የሚያገኝበት መሆኑ በአምላክ ዘንድ ተገልብጦለት አስገድዶት በሚሸው የሆነም ይሁን ዓይነትና ሥራ ሁሉ ለረኛው እየ ረዳ በሰላማዊ አንድነት የሚኖር የሕዝቡ ዋና ክፍል ነው እንዲሁም መንግሥት ማለት ፤ እግዚአብሔር ገደልን ፈጥሮ መሰላልን ያበጃል እንደ ሚባል የሰይጣን አምሳያ የሆነ ጠላትን ሳይገ፡ድል ፤ ሳለ ማጥፋቱ የተመኘለትን ሕዝብ ማዳኑ ሲያምረው እረፍት ተብሎ የተፈጠረ የጥንታዊ ባሕርይ ምኞታቸውን ፈጽሞ ከልባቸው አስርቆ ሁሉ ያውቀው ዘንድ በማይችል አኳሆን ለድካም ብቻ የላካቸው ሲሆን ዋናውን ሕዝብ ለመጠበቅ በንጉሥና በልዩ ልዩ አባሎች ከነሠራዊት ጭምር የቆመ የዋናው ሕዝብ ምክትል ነው ማለት እደፍራለሁ።እንዲህ ከሆነ እንግዴህ ከሁሉ በፊት ሰው ሁሉ አይደል ብል የማያስከፋኝ ሲሆን ፡ ሳያውቀው ቢኖር ነው እንጂ ፡ መንግሥት ማለት መሬቱን እያረሰ እንደ ንጉሥ የመንግሥት ምክትል መሪ በንጉሥ ዘበኛ ነት ዘንድ ተጠብቆ ወተቱንም ቅቤውንም ሥጋውንም ከቤቱ ለራሱ ችሎ ለሌላ እያካፈለ አርሶ ባወጣው ፍሬን እየበላ እንጂ ባለጠጋ ጌታዬ ይሰጡኝ ይሆን ወይምይነሱኝ ይሆን እንደሚል ውሻ ሳይሆን ወይልጆቹን ወይም ቢኖሩት ሎሌዎቹን እየላከ አለዝያ በሌሎች ዘንድ እንዳይገዛ የተፈጠረ ጉልበቱን ሳያዋርድ እርሱ ባለቤቱ ለእግዚአብሔርና ለምድር የሰጠው የከብትንና የእህልን ዘር ካገኘው ፍሬ በማየት ቈርቶ እኔ በጕጆዬ አጤ በድንኳናቸው እያለ እቤቱ ቈጭ ብሎ እየበላ ጣጣ ያልበዛበት ትንሽ መንግሥትን አዝዞ ናዝዞ የሚኖር ንጉሥ ነው ።

ስለዚህም ንጉሥና አባሎችም ሠራዊቱም ሁሉ የዋናው ንጉሥ የገበሬ ዘበኞች ስለ መሆናቸው ኢትፍጽሞ ለሳሕም ሰበ ያከይዶ እስመ ይደልዎ ዓስቡ ለዘይትቀነይ እንዲል ወንጌል ፡ የዚሁ መንግሥት ሕዝብ የእራስን መጠበቂያ በሚያስፈልገው ሁሉ ለቀለበተኛ ባለደመወዝ ጠባቂው በቀጥታ መክጠት ያስገድደዋል ።

እንዲህ ተሆነ እንግዴህ ዘእንበለ ሥጋ ኢትቀውም ነፍስ ነውና የሕይወት ዋና ሥር ፤ ሉልና ወርቅም ብርም ሊመዝኑት የማይቻል ፤ ያ እህል የተባለ አለብዙ ድካም የሚገኝ የምድር ፍሬ ነውና ሕዝብም አለ እህል አገሩን ሊኖርበት አለ

መቻሉ ሲሆን ፥ እንዲሁም የገበሬው ጠባቂዎች ያልናቸው የመንግሥት ምክትል ክፍልም ምንም የገበሬውን ሥልጣናዊ መንግሥት ጌትነት ሳያውቁት በይኖሩና አገራቸውን ስለመጠበቅ ሲንገላቱ መኖራቸውን ቢአውቁት አለ እህል አገራቸውን ሊጠብቁ አይችሉምና አለመሬት እህል ማግኘት እንደማይቻል ያህል አለ እህል ደግሞ መሬትም መንግሥትም ሊቆሙ አይቻላቸውም ስለሆነ ዋና ትምርት ማለት እንግዴህ ያ የመሬት ማረሰና የማሰራትም የንግድ ሥልጣኔም ነው ።

ምናልባት ማረስና ከብት መጠበቅም ንግድም ምንያህል ችግር አላቸው ብሎ የሚጠይቀኝ ቢኖር ፤ መቸገር አይቸግርም ነገር ግን ምንም በሩቅ ለሚያየው የሚያደክም ይመስላል እንጂ የተሰናዳ እርሻና የሚያስፈልገው የመሰለ መሣርያ ሁሉ ያንድ ዓመት ምግብ ጭምር ለያዘ ከሱ የሚቀል ሥራ የለምና ማረስን ወይ መሣሪያ ላጣ ሁሉ መንግሥት በያመቱ የተቻለውን ቢረዳ እጅግ መልካም ይሆን ነበር ስል ይቅርታን እለምናለኍ

ብላታ ኅይለማርያም ።

የከተማ ወሬ ።

ክቡር ደጃዝማች ብሩ ከግዛታቸው ወደአዲስ አበባ መምጣት ።

የአቢጋርና የወለጋ ገገር ክቡር ደጃዝማች ብሩ ወልደ ገብርኤል ከግዛታቸው ወደ አዲስ አበባ መጋቢት ፳፯ ቀን ገብተው ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ከልዑል አልጋ ወራሽ በደስ ስለ ተገናኙ ብርሃንና ሰላም የከበሩ ወዳጆ በክብር አዲስ አበባ ስለ ገቡ እንኳን ደህና ገቡ እያለ ለክቡሩን ወዳጆቹ ደስታውን ይገልጻል ።

የክቡር ከንቲባ ነሲቡ የተገባ የደግነት ሥራ።

ክቡር ከንቲባ ነሲቡ እግዚአብሔርን የሚፈሩ መንግሥታቸውን የሚያከብሩ ስለ ሆኑ ሥራቸውን ሁሉ በትጋትና በጥንቃቄ ያሠራሉ ።

አሁን የበለጠ ሥራ፥በሬዳ ገበያ ውስጥ አገር አሸባሪ እግረኛ በሬሬ ፡ ቸርቻሪ ተነሥቶ የከተማውን ሰው እንዳወከው ሰምተው በማዕርጋቸው አድሮ ያለ ኃይለ እግዚአብሔር አነሳሥቷቸው አንድ ቀን ቢያጣፍሩት የከተማው ሰው በየቤቱ እልል አለ ። ይኸ ለሕዝብና ለመንግሥት ጥቅም የሚሆን አሳባቸው ወደ ፊት እየገፋና እየበረታ እንዲሄድ ብርሃንና ሰላም ሙሉ ተስፋ አለው ።

በቴሌግራም የመጣ የውጭ አገር ወሬ ።

ብሮማ ። ይኅዝላብ በአልባንያ ላይ የምታሰናዳው ባለች የወታደርነት ሥራ ላይ ለውጭ አገር መንግሥታት አስተውሎ በሉዋቸው ብላ ኢጣልያ መንግሥት አዋቆቹዋን ልካለች። በሰርብያ ያሉ የኢጣሊያና የእንግሊዝ ባለ ሙሉ ስልጣን ሚኒሥትሮች ወደ ውጭ አገሮች ሚኒሥተር ቢሮ ሂደው ፤ ከዮሳዝለም መሬት ለመጠጋት ሊሻገሩ የሚቻለው የአልባንያ ወታደሮችን ይሳዝላብ መንግሥት ያልከለከላቸው እንደሆን የባሰ ጠብ ሊሆን ይቻላልና ፥ የበልግራድ መንግሥት (ሰርብያ) ሰላማዊ የሆነ የፖለቲክ መንገድን ለመያዝ አበበዋል ብለው አመልክተዋል፡ ከበልግራድ (ከሰርብያ) የተደረገው የደጥታት ጉባዔ ዘንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒሥቴር ሲናገር የዮሳዝላብ ቅን የሆነ ምኞት ከኢጣሊያ ጋራ እንዳለች ውል ልክ በሰላማዊ ፖለቲክ መንገድ መቀጸል መሆኑን እየገለጸ ፤ አልባንያ በዓለም መንግሥታት ማሕበር አላፊነት ነጻነትዋ የታወቀ መሆኑን እ ስረገጠ ፥ የወታደርነት ሥራ ተሰናድቶዋል የሚሉውንና በኢጣሊያና በአልባንያ ላይ ያደጋ መጣጣል አሳብ አለ የሚለውን ወሬ ያስዋሸል ።

እንደ አጀን ሐበከ (ጋዜጥ) ወሬ ዘንድ የፈረንሳዊ ውጭ ጉዳይ ሚኒሥተር ከበልግራድ (ሰርብያ) ላለ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስተር ዘንድ ትእግሥትና ብልሀትም ያስፈልግሀል ብለህ ለዮሳዝላብ መንግሥት ምከረው ብሎ ልኮለታል ።

አጀን ሐባል የሚባል (ጋዜጥ) ኩሬሴልማ እንደረባው ማስታወቂያ ዘንድ በኢጣሊያና በአልባንያ ወሰን መሬት ርዝመት ሁሉ የዮሳዝላግ ወታደሮች ተሰናድተውበታል የተባለውን ወሬንና የሳዕ ዝላብ አሁን ያለው ቲራኖ የሚባለውን መንግሥት ለማጥፋት አሳብ አላት የተባለውን ወሬ በልግራድ (ሰርብያ) ታስዋሸዋለች ይላል ሪዮ አነይሮ ። ደፒነዶ የአርዮፕላን አለቃ ማናያስ የሚባለውን አገር ለቶፓራ ወደሚባል ለመሄድ ተነስተዋል ።

ኒዮ ዮርክ ። የሳዝላብ በአሜሪክ ላይ ያለበት ፴ ሚሊዮን ዶላር የባልግራድ መንግሥት ወታደሮችን ይሰበስባል በተባለ ወሬ ምክንያት እንዲያው ቆይቶዋል ።

ሻንጋይ ። የመዘጋጃ ቤት ጉባዔ ዘንድ ተደርጎ ያለውን ውል እንዲጠብቅና በውጭ አገር መንግሥቶች ላይ የተደረገውንም ውል እንዲፈጸም በቺናና የዓለም መንግሥታት አጋዥ ያስፈልገኛል ብሎ አስታውቆዋል ።

የደበባውያን አድመኞች ሠራዊቶች ከገቡ በኋላ የባሰ ክፋት ሥራ አልተደረገም ።

ሞስኮ ።"የቺና አድመኞች ሠራዊቶች ሻንጋይን በመያዛቸው የተነሣ የመስኮብ ከተሞች ሕዝብ ሁሉ እየተሰበሰበ የደስታ በዓል አድርጉዋል ።

ፓሪስ ። መንግሥት ጠብ እንዳይነሣ በማለት ፍራት አቢኞን የሚባል የጥትራሪክ ዝክር እንዳያረግ ከልክሎዋል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሙዋቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው ፥	፲	ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ።	፭	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር ።	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
መጽሐፈ ቅኔ ።	፫	ብር

ሕዝቅኤል ንባቡ ከነርትጓሜው	፯ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፫ ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፬ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትጓሜው ፥	፬ ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትጓሜው ።	፬ ብር
የሕይወት ታሪክ	፬ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት ፥	፩ ብር
ያማሪኛ ሰዋሰው ።	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ፥	፩ ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን ።	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ ።	አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ ።	አላድ
ያማሪኛ ፊደል ፥	ሩብ
አሳብና ምኞት ፥	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት ።	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር ።	፬ መ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፬ መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ፥	፩ ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ።	፩ ሩብ

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፰ብር ከ፫ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ፫ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፲፰ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፫ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፮ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፩ ብር ።
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፻፴፩ ብር ።
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፳ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፫ ብር ።
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳ ብር ።
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፵፮ ብር።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፬ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፬ መ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፬ ፍራንክ
በአንድ ብር	፲ ሊሬ ፳ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ፳፭ ሳንቲም ነው
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፯ ብር ።

ሩግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚሀ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል ።

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው ።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፥በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፥ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቀባት ዘወትር ይገኛል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሂስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጉበርና አጉበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

Berliet



ቤርሊዮ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዮ አቶሞ ቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚአን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወኔ ፍል ወሀ መውረጃ ።

AMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኤዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳሀን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቀውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

ሶስተኛ ዓመት ፡ ቁጥር ፲፬
3 me ANNÉE № 14

ሐሙስ መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 7 AVRIL 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር
ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Diréсteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፺፱ ገጽ ተከታይ ።

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

፲፬ተኛ ክፍል ።

ዛሬ በኢትዮጵያ የቆመው ባንክ አፍ አቢሲኒያ ከቆመበት ቀን ጀምሮ እስከ ሃምሳ ዓመት ድረስ በኢትዮጵያ ሌላ ባንክ እንዳይቆም ውል ተቀብሏል ። ከዚህ ቀደም እንደ ተረዳነው ግን ማናቸውም ነገር በጥቂቶች ሰዎች እጅ ገብቶ ሞኖፖል ሲሆን ለሕዝብም ለመንግሥትም ጉዳት ነው። ለአጼ ምኒልክ አንድ ሰው መጥቶ በአገርዎ ከኔ በቀር ሌላ ሰው እንዳያርስ ወይም በቅሎ ገዝቶ እያከራየ እንዳይነግድ ወይም እኔን ሳይጠይቅ በየቤቱ ማንም ወጥ እየሠራ እንዳይበላ ፈቃድ ይስጡኝ ብሎ ለምንዋቸው ቢሆን የሚናገራቸው ቃል ምንም ቢያምር የሚሰጣቸው ተስፋ ምንም ትልቅ ቢሆን ያለ ጥርጥር ይቆጡት ነበር ።

አማላጅ ሆኖ ይህነን ቃል የነገራቸውንም ሹማቸውን ጉበልተህ መንግሥቴን ልትሸጥ አሰበህል ብለው ሳይቀጡት አይቀሩም ነበር ። የባንክ ሥራ ሞኖፖል እንዲሆን ግን የዕውቀት ባሕሪ በሌላቸው ሰዎች ቃል ተታለው አጼ ምኒልክ ፈቃድ ሰጡ። ያውም ለጥቂት ጊዜ ነው አይባል ለሃምሳ ዓመት ነው ። ሕዝቡም በሥራ ከሰለጠነ ዘንድ ያለባንክ እንዳይሆንለት ተመልክተንዋል ። ደጉን ንጉሥ አጼ ምኒልክን ግን ይህነን ሁሉ ነገር ያስረዳቸው ሰው የለም ። የባንክ ሥራ የገንዘብ ሥራ ነውና ፤ የሕዝብ ትዳር መሠረት እንደሆነ የታወቀ ነው ። ብር የማይገባበት ጉዳይ የለም ። ማናቸውንም ለኑሯችን የሚያስፈልገንን ሁሉ በሩብ ባላድ በተሙን በብር ገዝተን ነው ። ስለዚህም ይህ ተሙን ሩብ አላድ ብር እስኪገኝ ድረስ የሚደክመው ድካም ጥቂት ወይም ብዙ እንደሆነ ፤ ፩ባንክ እንዳወቀ እንዲለየው መንግሥት በውል መፍቀዱ ትልቅ ጉዳት ነው ። ሕዝቡ በመላው ብሩን የሚያስቀምጥበት ቦታ አንድ ብቻ እንዲሆን ቢደነባሳ ደግ ይሆናልን ባገሩም ውስጥ ካንዱ ወረዳ ወዳንዱ ወረዳ ብር ሲላክ መልክተኛው አንድ ብቻ እንዲሆን ቢደነገግ ይበጃልን ። የዚህንም ምላሽ በምሳሌ እናስረዳለን ።

ባንድ አገር ውስጥ ባላንጣ ተፎካካሪ የሌለው አንዳች ነገር ሲቆም ሕዝቡ ይጐዳበታል እንጂ አይጠቀምበትም ። ስለዚህም የጥይትንና የባሩድን ምሥጢር የሚያውቁ ሰዎች ጥቂቶች ብቻ ቢሆኑ ፤ የቀረውን ሰው ሁሉ ፈጅተው የዓለምን ሀብት ሁሉ ቀምተው ለብቻቸው ለመኖር ማሰባቸው አይቀርም ነበር ። በሌላውም ነገር ሁሉ እንደዚሁ ነው ። በያዘው ሥራ ባላንጣ እንዳይነሳበት እርግጡን ያወቀ ሰው ሁሉ ሌላን ሰው ደስ የሚያሰኝበት ወይም የሚጠቅምበትን መንገድ አይፈልግም ። ሀሳቡም ህልሙም ለጥቅሙ ብቻ ነው ። ሚዛን የማይዘናበለው በሁለቱም ጫፉ እኩል የሚከብድ ነገር ሲደረግበት ነው ። የሰው ባሕሪው ሁለት ነው ። አንዱ መልአካዊ ሁለተኛው ግን እንስሳዊ ይባላል ። ቀስቃሽ ካላገኘ ግን ሰው መልአካዊ ባሕሪን አይከተልም ። ወደእንስሳዊው ባሕሪው ያደላል። ለሰው አውራ ቀስቃሹ ግን ባላንጣ ነው ። ተፎካካሪ ባላንጣ ያለው ሰው ክፉ ሥራ ለመሥራት አይችልም ። ለባለጋራውም ቢሆን እንዳይሰነው ያውቃልና በደግነት ለማሸነፍ ይጣጣራል ። ገንዘብ ያለው ሰው አንድ ብቻውን ሲሆን ፤ ገንዘቡን ሲያበድር የፈለገውን ወለድ አምጡ ቢል ይሆንለታል ። የተጨነቀውም ሰው አበድረኝ ሊል ቢመጣበት አይራራለትም ። ይልቁንም የሰውዬውን መጨነቅ አይቶ ከፍ ያለ ወለድ ይፈልጋል ። ገንዘብ የሚያበድር ሌላ ባላንጣ ሲነሳበት ግን ተበዳሪዎቹ ወደባላንጣው እንዳይሄዱበት ርህሩህ ነው እንዲባል ይጣጣራል ። በተቸገሩትም ሰዎች ላይ መጨከኑን ይተዋል ። ባላጋራውም የሚቀበለው ወለድ ስንት እንደሆነ እየ

ጠየቀ ሰው ወደእርሱ እንዲመጣለት የሚቀበለውን ወለድ ያሳ ንሳል ዝቅ ያደርጋልም ። ገንዘብ የሚያበድሩት ባላንጣዎችም በብዙ ቍጥር የእያንዳንዱ ባላንጣ ባሕሪ እየተሻለ ይሄዳል ወለ ዱም ሁሉ በጣም ዝቅ ይላል ። ወለድም ዝቅ እያለ ሲሄድ ተበ ዳሪም ይበዛል ። ተበዳሪም ሲበዛ ፤ ባገርም ያለው ብር ሁሉ ሥራ አይፈታምና ሕዝብ ይጠቀምበታል ። ሕዝብም ሲጠቀም የመን ግሥት ኃይል እያደገ ይሄዳል ። ነገሩንም እንድንረዳው ቀጥሎ የተጻፈውን የሂሳብ መንገድ ስንጠረዥን እንመልከት ፤ እሱም አበዳሪው ሲበዛ የተበዳሪውም ቍጥር መብዛቱንና የወለዱን እያነሰ መሄድ ይገልጽልናል ።

ያበዳሪዎቹ ቍጥር	ከሽው ብር ወለድ የሚያጎድሉት ብር ቍጥር ።	ከሽው ብር የሚቀበሉት ብር የድርሻው ቍጥር	የተበዳሪዎች ሰዎች ቍጥር
፩	፲	፩፻	፪
፪	፳	፺	፬
፫	፴	፹	፰
፬	፵	፸	፲፮
፭	፶	፷	፴፪
፮	፷	፶	፷፬
፯	፸	፵	፻፳፰
፰	፹	፴	፪፻፶፮
፱	፺	፳	፭፻፲፪
፲		፲	ሺህ ፳፬

ይኸው በላይኛው የሂሳብ አካሄድ እንደምናየው ያበዳሪ ዎቹ ባሕሪ እየተሻለ የሚሄድ ወለድም ዝቅ የሚል ተበዳሪም የሚበዛ አበዳሪዎቹ ሲበዙ ነው ። ከዚህም የተነሣ ባገር ያለው ብር ሥራ አይፈታም ፤ አበዳሪ አንድ ሲሆን ግን ወለዱ ብዙ ስለሆነ ተበዳሪም እያነሰ ይሄዳል ፤ ባገሩም ያለው ብር ሥራ የሚፈታ ስለሆነ መንግሥትንም ይጎዳዋል በሌላውም የሕዝቡን ትዳር የሚነካ ነገር ሁሉእንደዚሁ ነው ። ሞኖፖል ለመንግሥ ትም ለሕዝብም ጉዳት ነው ። በያዘው ሥራ ባላንጣ እንዳይነ ሳበት እርግጡን ያወቀ ሰው ከጥቅሙ በቀር ሌላ አያስብም ። ለሕዝብም ክፉ መንገድ ሁኖ ሕዝብ እርስ በርሱ እንዳይራራና እንዳይረዳዳ ያደርጋል ። ስለዚህም ሞኖፖል የበዛበት አገር ቀጣፊና ሌባ ወንበዴም ይበዛበታል ። ሞኖፖልም ሁሉ የሚ ጎዳ ከሆነ ዘንድ ይልቁንም የባንክ ሥራ ሞኖፖል ሲሆን እጅግ ክፉ ነው ። አረቄና ጠጅ ሞኖፖል ሆኖ ያረቄውና የጠጁንይ ነት ለጤና የሚጎዳ ሲሆን በመላው ሕዝብ አይጎዳበትም የሚ ጎዳው ጠጭው ብቻ ነው ። የሐር ሞኖፖል ሲሆን የሚጎዳው ሐር ለባሹ ብቻ ነው ። ትንባኆም ሞኖፖል ሲሆን የሚጎዳው የትንባሆ ልማድ ያለበት ሰው ብቻ ነው ። እያንዳንዱ ሰው ትልቅም ቢሆን ትንሽም ቢሆን ፤ ሀብታምም ቢሆን ድሀም ቢሆን ለኑሮው የሚፈልገውን ነገር ሞኖፖል ማድረግ ግን በሕ ዝቡ ድኅነት በመንግሥትም ጉዳት እንዲ ወርድ እንደመፈለግ ያህል ነው ። እንግዲህ በማናቸውም አገር ከብር አብልጦ የሚ ፈለግ ነገር የለም ። ብር የለውጥ መሣሪያ ነው ። ገበሬ ቢያርስ ሽማኔም ቢሠራ ፤ ጸሐፊም ቢጽፍ ፈራጅ ሲፈርድ ቢውል ፤ ነጋዴ ቢነግድ ፤ ሁሉም የፈለጉትን ነገር የሚያገኙ ፤ ስለድካማቸው ዋጋ አስቀድመው ብር ከተቀበሉ በኋላ ነው ። ብር እስኪገኝ ድረስ ድካሙ ጥቂት የሚሆን ግን ወለዱ ሲያንስ ነው ። ወለ ዱም የሚያንስ አበዳሪዎቹ ብዙ ሲሆኑ ነው ። አበዳሪዎቹም የሚበዙ ሕዝቡ በሥራ ሲሰለጥን ነው ። ሕዝብም በሥራ የሚ ሠለጥን በሥርዓት ፊት እርስ በርሱ እኩል ሆኖ የሚበቃ አቅም ካገኘ ዘንድ ልቡ የመረጠውን ሥራ ለመሥራት ሲችል ነው ። ስለዚህም በኢትዮጵያ የባንኩም ሥራ ሞኖፖል በመሆኑ ለኢ ትዮጵያ ሕዝብ ትልቅ ጉዳት ነው ።

ዛሬ በኢትዮጵያ የቆመው ባንክ አፍ አቢሲኒያ ማህበረ ተኞቹ የውጭ ሰዎች ናቸውና የባንኩ ውል የተሰጠው በማይ ገባ እንደሆነ ሰው ሁሉ ተረድቶት በኢትዮጵያ ባንኩን ከልብ የተቀበለው ሰው የለም ። ስለዚህም የባንኩ አለቆች ከኢትዮ ጵያ መንግሥት ሹማምንት የሚበቃ እርዳታ እንዳያገኙ አው ቀውት ለኢትዮጵያ ሰው ሲያበድሩ እጅግ ተጠንቅቀው ነውና የሚበዛውን ገንዘባቸውን እየተበደሩ የሚጠቀሙበት የውጭ አገር ሰዎች ናቸው ። እነዚህም የውጭ አገር ሰዎች በተበደሩት ገንዘብ ነግደው ያገኙትን ትርፍ ገንዘብ ወዳገራቸው ይሰዳሉ እንጂ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም የሚሆን ሥራ አይሠሩበትም ።

የባንኩም ጌቶች የውጭ አገር ሰዎች ስለሆኑ ፤ የኢትዮ ጵያ ሕዝብ ባንኩን አያምኑትም ። ስለዚህም ገንዘቡን በባንክ የሚያስቀምጥ የኢትዮጵያ ሰው ጥቂት ነው ። ገንዘብን አደራ የሚያስቀምጥበት ሌላ ቦታ ስላጣ የሚበዛው የኢትዮጵያ ሰው ብሩን በማሰሮ እየከተተ ከመሬት በታች ይቀብረዋል ። በለገን ዘቦችም የኢትዮጵያ ሰዎች ተባብረው አንድ የረባ ባንክ አቁ መው በገንዘባቸው እንዳይሠሩበት የባንኩ ሥራ ሞኖፖል ሆን ዋልና ፈቃድ አያገኙም ። ቢያገኙም በማናቸውም ቲኒንሽ ምክ ንያት እንዳይወረሱ እየፈሩ ገንዘብ እንዳላቸው ቢገለጽ አይወ ዱም ።

ከጥቂት ዓመት በፊት ያገራችን ሹማምንት በመንግሥት ትእዛዝ ተሰብስበው አንድ የባንክ ዓይነት ማህበር አቆሙ። ማህበሩ ግን እስከዛሬ ድረስ የረባ ሥራ አልሠራም ። የረባ ሥራም አለመሥራቱ ምናልባት የኢትዮጵያ ሰው ለባንክ ሥራ የሚበቃ አእምሮ ስላጣ አይደለም ። ነገር ግን ማህበረተኞቹ ሹማምንት ስለሆኑ ነው እንጂ ። እነዚህ ማህበረተኞች የሆኑት ሹማምንቶች ማህበሩን ያቆሙት ስለሹመታቸው እንዳልሆነ በይ ገባቸው በመንግሥት ጉዳይ ሁሉ ባላጋራቸውን ለማጥቃት እን ደሚጥሩ ፤ እንዲሁም ለባንኩም ጉዳይ ለምክር በተሰበሰቡ ቍጥር እርስ በርሳቸው ከመነቃቀፍ ፤ አንዱ ያንዱን ሥራ ከማስነወር በቀር ሌላ የረባ ሥራ ለመሥራት አልሆነላቸውም ይልቁንም የባንኩ ጉዳይ ሲመከር አንዳንድ ጊዜ ልዑል አልጋ ወራሽ አብረው ስለተቀመጡ እያንዳንዱ ማህበረተኛ ብልሀ ተብሎ እን ዲመሰገንና ባላጋራውን እንዲያጠቃ ከሙግት በቀር ሌላ ለማ ህበሩ ሥራ የሚበጅ እውነተኛ ምክር አላመጣም ። ስለዚህም የባንኩ ሥራ እስከዛሬ ድረስ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሳይጠቅም መቅረቱ የሚገርም ነገር አይደለም ። ለወደፊትም ሳይጠቅም

ቢቀር አያስደንቅም ፡፡ ማናቸውም ማህበር ለያንዳንዱ ማህበረተኛና ለመላው ሕዝብ ጥቅም የሚሆን ማህበረተኞቹ ወደው ሲተባበሩ ነው እንጂ ፤ ንጉሡ ነገሥቱ የገቡበት ማህበር ነውና ሳንገባ ብንቀር እንነቀፋለን እያሉ ለግብር ይውጣ ነው እንጂ ሊተባበሩ አይደለም ፡፡ እንደዚህ ያሉትም ማህበረተኞች ተስማምተው አንዳች የረባ ሥራ ለመሥራት አይችሉም ። አይሳካላቸውም ። ለኢትዮጵያ መንግሥትም ሕዝቡ እየተባበረ የባንክ ሥራ እንዲያቆም ከፈለገ ዘንድ ፤ እንደዚህ ያለውን ማህበር ማቆሙን ትቶ ሕዝቡን በሥራ ቢያሰለጥን ይሻላል ፡፡ የሰውም ገንዘብ እንዲታፈር የተደላደለ ሥርዓት ያውጣ ፡፡ እሱ እራሱ ማህበረተኛ እየሆነ በያንዳንዱ ማህበር መግባቱን ትቶ ፤ ማህበር ሲቆም በንዴት ያለ ደምብ እንዲያድር በፍትሐ ነገሥት ለይቶ አውቆ ዜጎቹ የወደዱትን ሥራ ለመሥራት እንዲተባበሩ ሙሉ ፈቃድ ቢሰጥ ይሻላል ። ይህነንም ካደረገ በኋላ ፤ ከሕዝቡ ውስጥ አንድም ሰው ገንዘቡን ከመሬት በታች ሊቀብር አይወድም ወደባንክ አግብቶ እንዲወልድለት ወይም የተሻለ ሥራ እንዲሠራለት ይፈልጋል እንጂ ሕዝቡም በሥራ ሠልጥኖ እርካታ ፈአገኝ ባገሩ ውስጥ ያለው ገንዘብ ሥራ ይይዛልና ፤ መንግሥት የሚያገኘው ግብር ይበዛል ፤ በእንደዚህ ያለውም መንገድ የሚያገኘው ግብር ማህበረተኛ እየሆነ ከያንዳንዱ ማህበር ከሚያገኘው ትርፍ ሳይበልጥ አይቀርም መንግሥት ከሁሉ በላይ ነውና ይህነን በላይነቱን ትቶ ከዜጎቹ ጋራ በማህበረተኛነት መተባበር አይገባውም እንደዜህም ቢያደርግ አይጠቀምም ።

ዛሬ በኢትዮጵያ ደህና ባንክ ከላይም የተጠራው ባንክ አፍ አቢሲኒያ ብቻ ስለ ሆነ ፡፡ ይህም ባንክ አፍ አቢሲኒያ ለኢትዮጵያ ሰው ለማበደር የሚሠጋ ስለ ሆነ ፤ የኢትዮጵያ ሰዎች ገንዘባቸውን እየሸሸጉት ሥራ ፈትቶ ስለ ተቀበረ ዛሬ ባገራችን ብር ውድ ነው ። ስለዚህም ብር የሚበደር የኢትዮጵያ ሰው ወለድ ይበዛበታል ። ጭንቅ ከላገኘው በቀረ ሰርቼ አተርፋለሁ ሲል አይበደርም ፡፡

የኢትዮጵያም ሰው የሚበደረው ሲጨነቅ ብቻ ስለሆነ ብዙ የታመነ ተበዳሪ የለምና ገንዘባቸውን ሊያበድሩ የሚፈልጉ ሰዎች ቢኖሩ ፤ የሚያገኙት ጥቅሙ ጥቂት ነው ፡፡ ገንዘብ ያለው ሰው መቼም የታመነ ዋስ ለሌለው ሰው አያበድርም ። ገንዘብ የሌለው ሰው ደግሞ በቶሎ ዋስ አያገኝም ።የኢትዮጵያም ሕዝብ በሥራ ስላልሠለጠነ ፤ አበዳሪዎችም የሚፈልጉት ወለድ ብዙ ስለ ሆነ ። ድንገተኛ ችግር ካላገኘው በቀር ሠርቼ አተርፍበታለሁ ሲል የሚበደር ሰው በኢትዮጵያ የለም ፡፡ ይልቁንም ዛሬ በኢትዮጵያ ያለ ብር የሚበልጠው ሥራ ፈትቶ በመሬት ውስጥ ተቀብሮዋል ። እንዲሠራ ወደ ገበያ የሚወጣው ብር ግን ጥቂት ስለሆነ የሚገኝበትም ጥቅም አነሠ ፡፡

ከዚህም ምክንያት የተነሣ በኢትዮጵያ የቆመው ባንክ አፍ አቢሲኒያ ከቆመ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያገኘው ትርፍ ጥቂት ነው ። ለወደፊት ትልቅ ጥቅም ማግኘቱን ያጠራጥራል ። ባንክ የሚጠቅም የታመነ ተበዳሪ ሲበዛለት ነው ፡፡ የታመነም ተበዳሪ የሚበዛ ሕዝቡ በሥራ ሲሰለጥን ነው ፡፡ ሕዝብም በሥራ የሚሰለጥን ባገሩ ያለው ብር ወርቅ ሥራ ያልፈታ እንደሆነ ነው ። ባገርም ያለው ብር ሥራ የማይፈታ መላው ሕዝብ በሥርዓት ፊት እኩል ሆኖ ። እያንዳንዱ ሰው አቅም አገኝቶ ልቡ የመረጠውን ሥራ ሚሠራ የሕዝቡ ሀብት ያድጋል ፡፡ የሕዝቡ ሀብትም ካደገ ዘንድ ባንክ ይጠቅማል ፡፡ ስለዜህም የኢትዮጵያ ባንክ የሚፈልገው የገንዘብ ጥቅም ብቻ እንደሆነ ፤ ከሁሉ በፊት የባንኩ ሥራ ሞኖፖልነት ለቆ የኢትዮጵያ ሕዝቡ በሥራ እንዲሠለጥን እንደ ተቻለው መጠን መርዳት አለበት ፡፡ ይህን ካላደረገ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሥራ እንዲሠለጥን እንደ ተቻለው መጠን መርዳት አለበት ። ይህን ካላደረገ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ድህነት ላይለየው ነውና ፤ ባንኩም ለወደ ፊት የሚያገኘው ትርፍ አይበዛም ። ባንክ አፍ አቢሲኒያ ከቆመ ወዲህ ይኸው ፤ ፲ ዓመት ሊሆን ተቃርቧል ፡፡ የባንኩ ማህበረተኞች ግን እስከ ዛሬ ድረስ ለባንኩ ሥራ ከገቡት ገንዘብ አንድም ወለድ አልተቀበሉም የማህበሩም አማካሪዎች ባመት ለመቀበል በማህበሩ ደንብ የተፈቀደላቸውን ደምወዝ እስከ ዛሬ ድረስ አልተቀበሉም ። ነገሩም እንዴህ መሆኑ አያስገርምም ፡፡ ሕዝቡ በሥራ ባልሠለጠነ አገር ባንክም ቢቆም ትርፍ አያገኝም ። የባንክም ሥራ ፈጽሞ በሞኖፖል በሆነበት አገር ግን ሕዝቡ በሥራ አይሠለጥንም ።

የኢትዮጵያን አገር የመሰለ ሀብታም መሬት የትም ብንሄድ ብዙ አናገኝም ፡፡ ያገሩ ሕዝብ ሠልጥኖ እንደ ሚገባ ቢሠራ እንኳን አንድ ባንክ ሽ ባንኮችም ቢሆኑ ብዙ ትርፍ ያገኙበት ነበር ሕዝቡ በሥራ ካልሠለጠነ ግን እንኳን ብዙ ትርፍ እንዲአገባ ተብሎ የቆመው ባንክና ትንሽ ትርፍ ይበቃኛል የሚለው አንድ አጣሪም ሀሳቡ አይሳካለትም ፡፡

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት መጽሐፍ ነው።

መጋቢት ፱ ቀን በ፮ኛው ክፍል የተደረገ የትጋት ሥራ ።

አቶ ባይሳሴ ከሚባል ሰው ቤት ሌት ሌቦች በቅሎውን ሊሰርቁ ከቤቱ ሲገቡ ቢነቃባቸው ባለቤቱን በጩቤ ወግተውት ቢጮህ ዘበኞች ደርሰው ሌቦችን ተከታትለው አበራ እሚባል ዘበኛ ጠመንጃውን ጥይት አጕርሶ ፫ ጊዜ ተኩሶ ጥይቱ ቢከሽፍበት ሮጦ ሌባውን አጋድሞ በጠመንጃ ሰደፍ ከራሱ ላይ ቢመታው ጠመንጃው ከሰደፉ ላይ ተሰበረ ሌባውን ይዞ ወደ አለቃው አቅርቦ ለመስረቅ መሄዱን አምኖ ሌባው ዘብጥያ ገባ ይኸውም ዘበኛ ደስ የሚያሰኝ ሽልማት እንዲያገኝ የሚገባው ይመስለኛል ።

ሁለተኛ መጋቢት ፲፯ ቀን በ፬ተኛው ክፍል ይቶገ ማሚት ከሚባሉ መነኩሲት ቤት ፫ ሌቦች ግድግዳውን በሰንጢ ቆርጠው ገብተው ኖሮ በሳጥን ያስቀመጡትን እቃቸውን ሰርቀው ሲወጡ ከቤት ያለች አንዲት ሴት ብትጮህ ዘበኞች በፍጥነት ቢደርሱ ሁለተኛዋ አይሰማ ሞቱ እምትባል አሽከራቸው ከትንሽ ጕጆ ወጥታ ዘበኞቹን ምንም የለ ወደስፍራችሁ ተመለሱ እኛ እርስ በራሳችን ተጣልተን ነው እያለች ሌቦቹ እስቲርቁ በማታለል ስታነጋግራቸው አንደኛው ዘበኛ ሰው ሮጦ ከዚች ሴት ቤት ሲገባ አይቻለሁ ብሎ ቢገባ ከተሰረቀው እቃ ብርም ልብስም ከልጋላይ፡ አንደኛውንም ሌባ ከልጋ ውስጥ ተደብቆ

አገኘው ። ዘበኞቹም አይሰማ ሞቱ የምትባለውንና ሌባውን ከባሻ ወልደ ጊዮርጊስ ላይ አቅርበው ቢመረምሯቸው በጭሩ የተናገሩት ቃል ይህ ነው ። አይሰማ ሞቱ የምትባል እውነቱን ልናገር ባሉ ካሳ ይባላል እነዚህን ሌቦች ማታ ከፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ሰፈር ጠርቶ አረቂ ገዝቶ ሲጠጡ አምሽተው ሌሊት መስረቃቸው እርግጥ ነው ብላ ተናገረች ፤ ከቤቷ የተያዘ ሌባ ፈለቀ መኩሻ መስረቁን አምኖ ባልንጀሮቹ ካሉበት ስጠ ታንናከግን አስይዞ መስረቃቸውን አመኑ ። ዱብለና ጠጋዬ ለጊዜው አልተገኙም ፤ነገር ግን ተፈልገው ሳይያዙ አይቀሩም ።

ፈለቀ ከባሻ ደነቀ ላይ ቀርቦ የተናገረው ቃል አባቱ ባላ ምባራስ መኩሻ ይባላል አለ ። ከዚህ ቀደም ምን ሰርቀሃል ቢሉት በመስከረም ወር አዳ ከቀኛዝማች ዘረፉ መልከኝነት ፲፰ሰዎች ሆነን ከዚሁም ፭አችን ብረት ነበረንና የህል ጋዴ ከሰፈረበት እምስታችንም ፩፩ጥይት ተኩሰን ፬በቅሎ ፰አህያ ወስደን አፈ ርሳታ ሊወጣ ነው ቢሉኝ ሸሺቼ ወላሞ ወረድኩ አለ ። ስጠ ታና ዱባለ የብዙ ጊዜ ሌቦች ናቸው ፤ ከዚህ ቀደም አቃቂ ከፊ ሊዶሮቤት ሊሰርቁ ሄደው ቢነቁባቸው ተታኩሰው ዱባለ እጁን በጥይት ቆስሎ ተይዘው ከዘብጥያ ታስረው ይኖሩ ነበር ፤ የታሰ ሩበት ቀን ስለ በዛ አፈ ንጉሥ ከተማ ሁለተኛ እንዳታጠፉ አላፊ እሚሆናችሁ ዋስ ጠርታችሁ ተፈቱ ቢሉ ከችሎታቸው በፍጥ ነት ተነስቶ ብሩ የሚባል ሰው እኔ እዋሳለሁ ብሎ አስፈታቸው እነዚህ ሌቦች እስከሁን ለጌታ አያድሩ ነግደው አያተርፉ በየጊ ዜው በከተማ በሚሆነው ጥፋት ሁሉ እሚጠረጠሩ ናቸው ። ምናልባት ለዋሶቻቸው አከፋዮች ሳይሆኑ አይቀሩም በማለት ያ ስጠረጥራል ። በተለየ ስለተያዙ ለይቼ ጻፍኳቸው እንጂ በሰላይና በሌላ ምክንያት በዘበኛ እሚያዙ ብዙ ናቸው ። አሁንም እነዚህን ሌቦች ለመያዝ ዘበኞቹን ያነቃ የባለቤቶች መንቃት ነው መንግሥት በከተማ ዘበኛ ማቆሙ ለደካማው ረዳት ጥቅም እንዲሆን ነው ጥቅሙን ካላወቀ ጠቃሚውን ለማወቅ እንዴት ይችላል አንድ አንድ ሰዎች እንቅልፍ ወስዶአቸው ሌሊት ሳይሰሙ ሌባ ሰርቋቸው ጧት ተነስተው የተቆፈረ ቤታቸውን የጠፋቸው እቃ ባዩ ጊዜ ወደዳኞች ሄደው የለበስነው ሳይቀር ተሰርቀናልና አፈርሳታ ይውጣልን ይላሉ ።

አፈርሳታውም በቆመው ደምብ ይውጣ ተብሎ ይታዘዝና የተሰበሰበው ወይም ጠፋብኝ ተሰረቅሁ የሚለው ሰው በቀን ሰርቶ የሚያተርፈውን ጥቅሙን አጥቶ ፳ ፴ ቀን ተቀምጠው በቁስ በመስቀል ምለው አላየንም ብለው በየቤታቸው ይመለሳሉ ። ይኸ ሰው ልቡን ፈራጅ ቢያደርገው እሱ እራሱ ከቤቱ የገባውን ሰው ሳያየውና ሳያውቀው ሌሎች ከቤታቸው ተኝተው ያደሩ እንደምን ለማየት ይችላሉ ። ይኸንኑ ማለቴ በከተማው ሌባ ለማውጣት አፈርሳታ መታዘዝ ከተጀመረ ብዙ ጊዜ ነው የሕዝቡን በፀሐይ በዝናብ መጕዳት እንጂ ሌባው ተይዞ ጥፋተኛው ተቀጥቶ ለከተማው ጥቅም ባለማዩቴ ነው ።

በየነ።

የጃን ሜዳ የሽቅድድም ማኅበር ።

መጋቢት ፳፬ ቀን የፈረስ እሽቅድድም ሊደረግበት በቀጠሮ የታወቀ ቀን ስለ ነበረ በዚሁ ቀን ብዙ የኢትዮጵያ መኳንንትና የውጪ አገር መኳንንት ፈረሶች ተሰብስበው ነበረና ፤ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሰስት ሰዓት ሲሆን ወደ ጃን ሜዳ ሄደው በተሰናዳላቸው ስፍራ በተቀመጡ ጊዜ እሽቅድድሙ ተጀመረ ።

፩ኛ እሽቅድድም ።

የሜዳው ርቀት ፰፻ ሜትር ፤ የፈረሰኛው ክብደት ፷ ኪሎ ።

በዚሁ እሽቅድድም ስምንት ፈረሶች ገብተው ፤ መጀመሪያ የማድሙዋዜል የውብ ዳር ሚካኤል ብሩ ፈረስ ቀደመና ፤ ሁለተኛ የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፈረስ ፤ ሶስተኛ የሙሴ ኩራ ፈረስ ሆነ ።

፪ተኛ እሽቅድድም ።

የሜዳው ርቀት ሺ ፭፻ ሜትር ።

በዚሁ እሽቅድድም አራት ፈረሶች ገብተው ፤ መጀመሪያ የማዳም ቤንቲንክ ፈረስ ቀደመና ፤ ሁለተኛ የማዳም ዋይስ ፈረስ ሆነ ።

፫ተኛ እሽቅድድም ።

የሜዳው ርቀት ሺ ፬፻ ሜትር ።

በዚሁ እሽቅድድም አምስት ፈረሶች ገብተው ፤ መጀመሪያ የማዳሚዜል ፓፕ ፈረስ ቀደመና ፤ ሁለተኛ የልዑል ተፈሪ መኰንን ፈረስ ሆነ ።

፬ኛ ፤ እሽቅድድም ።

የሜዳው ርቀት ፪ሺ ሜትር ።

በዚሁ እሽቅድድም ስድስት ፈረሶች ገብተው መጀመሪያ የዶክቶር ሐስ ፈረስ ቀደመና ሁለተኛ የማዳም ኅስን ፈረስ ሆነ ።

፭ኛ ፤ እሽቅድድም ።

የሜዳው ርቀት ፪ሺ ሜትር ።

በዚሁ እሽቅድድም ሶስት ፈረሶች ገብተው መጀመሪያ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፈረስ ቀደመና ሁለተኛ የሙሴ ኩራ ፈረስ ሆነ ።

፮ኛ ፤ የኢትዮጵያውያኖች እሽቅድድም ።

የሜዳው ርቀት ሺ፬፻ ሜትር ።

በዚሁ እሽቅድድም መጀመሪያ የልዑል ተፈሪ መኰንን ፈረስ ቀደመና ሁለተኛ ያቶ ሚካኤል ብሩ ፈረስ ፤ ሶስተኛ የቃልብ ፈረስ ሆነ ።

፯ኛ ፤ እሽቅድድም ።

፫ሺ፬፻ ሜትር የዝላይ እሽቅድድም ።

በዚሁ እሽቅድድም አራት ፈረሶች ገብተው መጀመሪያ የልዑል ተፈሪ መኰንን ፈረስ ቀደመና ሁለተኛ የሙሴ ጋሊብ ፈረስ ሆነ ።

የሽቅድድሙ ሥርዓት እንደዚህ ሆኖ ከተፈጸመ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ወደ ግቢ ተመለሱ ። የሽቅድድሙንም አኳኋን ለመመልከት ተሰብስቦ የነበረው ሠራዊት ሁሉ ወደቤቱ ተመለሰ ።

በመጋቢት ፳፫ ቀን የሆነ የክብር ሹመትና ሽልማት ።

በመታመን መንግሥታቸውን ያገለገሉና ለወደፊትም የሚያገለግሉ የኃያላን መኳንንቶች ስምና የሹመትመዓርግ እኳኋን ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

፩ኛ በቅንነትና በእምነት ከብዙ ዘመን ጀምረው መንግሥትን ያገለገሉ ክቡር አፈ ንጉሥ ከተማ ጐላን ተሾሙ ።

፪ኛ ፤ ክቡር ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ ከክቡር አባታቸው ከራስ ወልዴ ጀምሮ መንግሥታቸውን በብዙ መታመን ስላገለገሉ ከምባታን ተሾሙ ።

፫ኛ ፡ ክቡር ደጃዝማች ሥዩም ሉል ሰገድ ከንታን ተሾሙ

፬ኛ ፡ ክቡር ደጃዝማች መሸሻ ከወንድ በላይ ጅሩን ፤ አሜቻን ተሾሙ ።

፭ኛ ፤ ክቡር ሊቀ መኳስ መንገሻ ውቤ ቡኖን ተሾሙ ።

፮ኛ ፤ ክቡር ልጅ አምባው ተክለ ማሸም ቀዎትን ተሾሙ ፤

፯ ፡ ክቡር ፊታውራሪ እርገጤ ከወሎ አውራጃ ከወረባቡ ውስጥ ተሾሙ ።

፰ኛ ፡ ቀኛ ዝማች ብሩ አንዳርጌ ከወሎ አውራጃ ከወረቃሉ ውስጥ ተሾሙ ።

ይህም ሹመታቸውና የሽልማት ማዕርጋቸው ለመንግሥት ቅኖችና የታመኑ አገልጋዮች መሆናቸውን ይገልጣል ። ለወደፊቱም በመታመንና በቅንነት ለመንግሥት አገልግሎታቸውን በትጋት እያሰፉና እያደሱ በመሔዳቸው ከነሱ በኋላ ለሚሾሙ ክቡራን መኳንንቶች ምልክት መሆናቸው አይጠረጠርም ።

የተሾሙበትን አገርም ፤ በየበኩላቸው ከመንግሥት በተቀበሉት ደንብና ሥርዓት በመጠበቅ ፤ ሕዝቡ ከፍ ወዳለው ዕውቀትና ሥልጣኔ እንዲደርስ ፃ'ኞቱ ስለሆነ ብርሃንና ሰላም ለክቡራን መኳንንቶች ደስታውን እየገለጠ ለከበረ ሹመታቸውና ለሽልማት ማዕርጋቸው ምሥጋናውን ከማቅረብ ጋራ ሹመት ያዳብር ይላል ።

ስለ መድኃኔ ዓለም በዓል አከባበር ።

መጋቢት ፳፯ ቀን የመድኃኔ ዓለም በዓል ስለነበረ ግርማዊት ንግሥተ ነግሥታት ዘውዲቱና የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ከነመኳንንቶቻቸው ወደ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ሄደው በዓሉን እንደሚገባ አክብረው ወደ ግቢ ተመለሱ ።

በተሌግራም የመጣ የውጭ አገር ወሬ ።

በርሊኖ ። ከኮሚኒስቲና በናሲዮናሊስቲ መካከል ብዙ ደምን እስተመፋሰስ ድረስ አምባጓሮ ሆኖዋል ። ፈታኞች ጠበንጃን መተኮስ ግድነት ስለሆነባቸው ፶ ያህል ሰው ቈስሎዋል።

የጀርመን ማተሚያ ላንዱም ለሌላውም ሳትል ዝም ብላ ማየት ምኞትዋ ስለ ነበረ በኢጣሊያና በዮጎዝላብ ግርግር ጥልቅነት ያህል ደስ እንዳላት ትገልጣለች ።

ኒዮ ዮርክ ። የጦር ወገን ክፍል ዘንድ ደፒነዶ የሰማይ ባቡር አለቃ አሁን በቅርብ ጊዜ ነው ኦርሊያንስ ወደሚባል ቦታ በሚደርስበት እንዲቀበሉትለመሄድ ፪ት የወታደሮች አይሮፕላኖችን አዝዋል ። በኢጣልያ መርከበተኞች ማህበር የቆመው የ፳ ሚሊዎን ብድር ሽክ ውል ከተዋዋሉበት ከጥቂት ሰአት ደቂቃ በኋላ ሥራው በመጀመሩ ትልቅ ሥራ ተደርጎዋል ።

ፐኪኖ ። የካንቶን ሠራዊቶች ሐሚክንግ የሚባል አገር ይዘዋል ተብሎ ይወራል ።

የኢጣሊያና የአ ላንድም የአሜሪክም የጀዎንም የሰ ግኝም ወገኖች ከእንግሊዝ ሠራዊቶች ጋራ ባንድነት ሁነው በሸንጋይ ዘንድ የዓለም መንግሥታት መሬት ያህል ለመጠበቅ አስተዳድረዋል ።

ሮማ ። ፋሺስቲንነት የተመሠረተበት ፳ተኛው ዓመት በዋለበት ቀን ዘንድ የሙሶሊኒ ጦርነትንም ስለ ጥቁር ቀሚስ ያህል የወጣው አዋጅም ስለ ፊት ጓራሪነት ሥራም እያስነሣ ሙሶሊኒ ጥቁር ቀሚስ መልበስ ማለት እጅግ ክብር ማለት መሆኑና ለወታደርነት ሥራ አንድነት የሚአደርግ ዋና ነገር መሆኑንም እያመለከተ በአሮጌው ዓለም የመፈታተን ሥራዎች ላይ በሚደረገው ዓመት በዓል መከበር የሊቶርዮ ቆንጆነት ስለ ፋሽስታዊት ኢጣሊያ መንግሥት በቀጥታ መሥራትና ውጊያ ማድረግ ትፈልጋለች ይላል ። ለነገ ጥዋት ፒያስ ፐፐሎ ከሚባል (ሜዳ ለጅዮ፣ አባንጓርዲስቲ የሚባሉ አዲስ የቆሙ ሠራዊት ክፍል ትልቅ መታዬት ይሆናል ።

ፓሪስ ። ዮርናል የሚባል ጋዜጥ እሮማ ወዳለ የሱ ተቀባባይ በጻፈውአርቲክሉ ዘንድ ፡ ኢጣሊያንና ፈረንሣዊንም ዲፕሎማቲክ ሥራና በንግድ ሥራ አንድነት ቢሆኑ ሠማንያ ሚሊዮን ላቲኖች በሥልጣን ያህል ከኤውሮጳ ሁሉ በበለጡ ነበር ይላል ።

ጆዋጆቶውን ። ደፒነያ የያዘ ሰንተማርያ የሚባል በራሪ ደማራራ ከሚባል አገር መጥቶ ወዲህ ወርዶዋል ።

ቶኪዮ ። በደቡታት ጉባዔ በሆነው እጅግ የባሰ ነገር ፕሬዚንና የፕሬዚዳንንም ምክትል ሥውር ገንዘብን ሠራዊትም አላችሁ ተብለው ተከሰው ዲሚሲዮንን አቅርበዋል ፡ ሥራችንን እንለቃለን ብለዋል ።

ዋሲንግቶን ። መሎን የሚባል የመንግሥት ወርቅ ገንዘብ መዝገብ ጸሐፊ ትእዛዝ ዘንድ ፐሬንቸቶውን የሚባል ጠቅላይ ፕሬዚዳን ለጻፈው ደብዳቤ መልስ ሲሰጥ የኤውሮጳውያንን ዕዳ መዳሰስ ለኢታኡኒ ጠቀሜታ የማይረባው ዋና ጉዳት የሚያመጣበት መሆኑ እያስረዳ አያስፈልግም ብሎዋል ።

ፓሪስ ። እንደ ማተን ጋዜጥ ዘንድ ወሬ የዮጎእዝላብ መንግሥት በአልባንያ ዳር መሬት ስለመሰለፋ ያህል እንዲመረመርበት የታዘዘውን ይሁን ብሎዋል ይባላል ።

እንደ ሌሎች ጋዜጥ ወሬ ግን ሬናሉት የሚባል ባለጦር ብረት መሣሪያ ፴ ሚሊዮን ፍራንክ ዋጋቸው ፴ ጋሪዎች ከፍራንስያ ወደ ዮጎእዝላብ ደርሰዋል ።

ሸንጋይ ። የካንቶን ሠራዊት ጠቅላይ ጀነራል በሩን እንዲገቡ በማክበር ፈቅዶ ከመንግሥታት እንደራሴዎች ጋራ ተነጋግሮዋል ።

ፐለባልያ ማንኪንግ የሚባል ፤ የሚሲዮናሪዮች (ካህናት) ቤቶችን ወሮ አባ ዱክት የሚባል የፈረንሣዊ ካህንንና አባ ማናራ የሚባል የኢጣልያ ካህንን ገድሎዋል ።

ፓሪስ ብሪያንድ እምኒሥትሮቹ ጉባኤ ዘንድ ፈረንሣዊ እሻንጋይ ባለው መሬት ያህል ክተት ብለዋል ። የተባለውን ወሬ አስዋሺቶ ዝም ብለን በማየት ፖለቲካችንን ይዘን እናቆ ያለን ብሎ ተናግሮዋል ።

ቡዳፐሳት ። (ሑንጋሪያ) በቅለን የጉባኤው ፕሬሲዳን ዘንድ በውጭ መንግሥታት ጉባኤዎች ሽምግልነት ሥራ ያለውን እኳሆን እያሥነሣ ፤ ሑንጋሪያ እራስዋን ሰላም የምታገኝበት መንገድ እንዲሁም የሑንጋሪያ ጠቀሜታ የሚገኝበት ከኢጣ ሊያ ስለሆነ ፤ በሚበልጥ ከኢጣሊያ ጋራ ሲሆን ፡ ሑንጋሪያ ከዓ ለም መንግሥታት ሁሉ ጋራ በፍቅር መኖር ነው አሳቦቿዋ ብሎዋል ።

ሎንድራ ዮኅዝላብ ። በአልባንያ ላይ ባደረገችው የጦርነት ሥራ ያህል ያለዓለም መንግሥታት ዘንድ ነገሩን ለመመርመር ስላልፈጠኑና ግድነት ስላላደረጉለት በእንግሊዝ መንግሥት አጋዥነት በባልግራድ መካከል እርቁን ይጀምራል ብለው የእ ንግሊዝ ጋዜጦች ያወራሉ ።

ሪኮፍየሚባል ሕዝብ ኮሚሲሮች ፕሬዚዳን ርሶቢትን ክፍል ሁሉ ሰብስቦ ፕሬዚዳንነቱ ባደረገው ጉባኤ ዘንድ የዓ ለም መንግሥታት ዘንድ ፤ ቺና እርስ በርስዋ ባሥነሣችው ተግባር በመግባታቸውና መሰኮብ እርስ በራሱ የሚያደርገውን አድማ እናጠፋለን ብለው ማሰባቸው በዓለም ሰላም ላይ የባሰ ጉዳት የሚያመጣ ነው ብሎ ተናግሮዋል ።

ሮማ ።ሚንሥትሮቹ ሁሉና ደፑታቶችም ስናተሮችም ሁሉ ማለት የመንግሥትም የሕዝብም ክፍል ሁሉ ተሰብስበው አብ ረው በነበሩበት ጊዜ የስናተር ሉዊጅ ሉዛቲ ሬሣን ተከብረዋል ።

ሬሣው የሉዛቲ ቤተሰዎች አሥከሬን ተቀብሮበት ወዳለ ወደ ፖደባ እንዲወስዱት ወደ ሌጋር ወስደውታል ።

ስናተሮች ስለፍርድ ያህል የሚያስፈልግ ገንዘብ ይርጋ ብሎዋል ። ጉባኤው የዲፕሎ ማቲክና የቈንስልነት ሥራ ስለማ ስተዳደር ያህል ለውጭ አገር ሥራና ለሕግ የሚያስፈልግ ገን ዘብ ግምትን ይርጋ ብሎዋል ።

ጂነብራ ።የዓለም መንግሥታት የሥራ አማካሪዎች ዘንድ ፋቲን በሚባል የፈረንሳዊ መልክተኛ ፕረዚዳንነት ስለእውቀት ሥራ ያህል ነባሪ ሺማግሎች እናቁም ብላ ኢጣሊያ ያቀረበች ውን ምኞት ይርጋ ብለዋል ።

የመርከቦች ወታደርነት ሥራ እ ዳወጣው ጽሕፈት ዘንድ አይድታንት ከምፓ ሶብራኖ የሚባል ሹመት ይዞ የነበረ ሮታ የሚባል ሥራውን ትቶታልና የሱን ምትክ ክንትራሜራልዮ ሞሪኖ የሚባል ተሾሞዋል ። አሚራልዮ ሮታ የአማራልዮ ዱኪ ምትክ የሰመርጂቢሊ ዲቢዚዮን አለቅነትን ተሾመዋል ።

ፕሬዚዳን ሙሶሊኒ ዘንድ የኢጣሊያ ስደተኞች ጠቀሜታ የሚወድ ስለሆነ እንዲኖሩና ሥራም እንዲያገኙ ከመንግሥት ዘንድ እያጋዘ ጁሺ የሚያህል የኢጣልያ ቤተ ሰዎች ሰብስቦ ያለው ካባሌር ፒያችንስ የሚባል የአርጂንቲና ማረስ ማህበር ፕሬዝዳንን በማክበር ተቀብሎ ተነጋግሮታል ።

ቡካርስት ። አትሬሽ ፈርዲናንድ ንጉሥ በድንገት ታሞ አብሶ ስለ ባሰበት ወደ ሲቺልያ ኢጣሊያ ይሄዳል ተብሎ የነ በረውን አሁን ቀርቶዋል ።

ቡዳፐሰት ። ሑንጋሪያ)የሑንጋሪያ ጋዜጦች ዘንድ ብትለን የሚኒስትሮች ፕሬሲዳን ቁምነገር ባለው ፖለቲክ ሥራ አሁን በቅርብ ወደሮማ ሊሄድነውናበ፬ ቀን ሚያዝያ እዚያ ይደርሳል እያሉ ያወራሉ ።

ሳንቲያጎ ቺላ አማሪካ የቺላ ኤጲስ ቆጶሳት ቤተክርስቲ ያን ከመንግሥት እንድትለያይ ይሁን በማለት እንደ ወጣው አዋጁ ልክ ለአምልኮ በቂ የሆነ ገንዘብ በያዓመት አውጡ ብለው ለካቶሊካውያን ሕዝብ አስታውቆቸዋል ። የቺላ ፈታሺ ነት ሥራ በሰሜን አሜሪካ አምባሳደር ላይ ለመነሣት ተሰብስ በው የነበሩ ጭፍራን አውቆባቸዋልና ብዙ አናርኪኮችን ይዘ ዋል ፡

ማስታወቂያ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰ ንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው ፤	፲፪ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፫ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር ።	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነርትጓሜው	፯ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትጓሜው ፤	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትጓሜው ።	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት ፤	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው ።	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ፡	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን ።	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ ።	አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ ።	አላድ
ያማሪኛ ፊደል ፡	ሩብ
አሳብና ምኞት ፡	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት ።	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር ።	፪መ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ፡	፩ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ።	፩ሩብ



በኤሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዜኒት የሚባል ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ከዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ፥ ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር ከሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር ተኩል ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፹ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፫ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ፫ ሩብ
በግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፩ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፩ ብር ።
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፻፴፩ ብር ።
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፳ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳ ብር ።
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳ ብር ።
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፶፭ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴ ብር ።
ቻዩ	፩ ነጥር	፲፩ መ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ እስከ ፲፭
በአንድ ብር	፲ ሊሬ እስከ ፲፰ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ፱ ሳንቲም እስከ ፹
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፭ ብር ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቀቅዎታል ።

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሂስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፤ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

Berliet



ቤርሊዮ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዮ አቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ከሜአን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋኛ እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

AMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፌልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፲፭
3 me ANNÉE № 15

ሐሙስ ሚያዝያ ፮ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 14 AVRIL 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ። Diréctеur	የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ደክፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ደሸጣል ።	Abonnements Ethiopie: Un an 5 Thalers Etranger: Un an 7 Thalers le numero 2 piastres

ስለ ኢየሩሳሌም ገዳም ።

ስለ ኢየሩሳሌም ነገር (ዴር ስልጣን) ግርማዊ አጤ ምኒልክ በዚህ ነገር ስንት እንደ ለፉ ስንትስ መታያያ ለሱጣልን አብድል ሃሚድ በደጃች መሸሻ ወርቄ እጅ በሃጂ አብዱላሂ አሊሳዲቅ እጅ ብቶ ኃይለ ማርያም ሰራብዮን እጅ እንደ ላኩና እንደ ደከሙበት እነራስ ናደውንም ስንት ጊዜ እንዳመላለሱ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የሚበዛው ሳያውቀው አይቀርም ። ይኸም መሆኑ ግብጾች የኢትዮጵያን ርስት አባቶቻችሁ ነን እያሉ ለመውሰድ ነው እንጂ የራሳቸው የሆነውን ቦታ እናስቀር በማለት አይደለም ። አባትነታቸውም የኢትዮጵያን ጥቅም እናስቀር በማለት ነው እንጂ ከሌላ ጸላት እናድናት በማለት አይደለም ነገር ግን በጎልጎታ ያሉት ቀኖች የግሪክና የካቶሊክ የአርመን የሶርያ ገዳማት ነገሩን ከሥር ጀምሮ ያውቃሉና እስከ ዛሬ ድረስ ግብጾች ከኢትዮጵያ ነጥቀው በወሰዱት መቅደስ ውስጥ እንዲቀድሱበት አልፈቀዱላቸውም ።

ለዚህም ምስክሩ አሁን በቅርቡ ልዑል አልጋ ወራሽ ወደ ሮፓ ሲሄዱ የዚህን የገዳም ነገር ማንሳታቸውንም አልተዉም ነበር ። የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ማኅበር ግን ማኅበሩ ለመመካከር አሁን ጊዜ አላገኘምና እግዚአብሔር ጉዳይዎን ሁሉ ፈጽሞ ከሚሄዱበት አገር በደህና ይመልስዎ ብለው መርቀው አቀባበላቸውንም አሳምረው ፤ ለጠየቁንም ጉዳይ ደስ የሚያሰኝ ምላሽ እንሰጣለን ብለው ሙሉ ተስፋ ሰጥተው ተሰነባበቱአቸው ። ልዑልነስ ከሄዱበት አገር የኢትዮጵያ አምላክ አቅሮ ደግሮ በደህና መለሳቸው ። ሲመለሱም ለዚሁ ጉዳይ ወደ ምድረ ግብጽ ሄደው ነበር ።ነገር ግን በቀድሞ ቃላቸው ደስ አላሰኙዋቸውም ።

በዚህ ሁሉ ነገር ግብጾች ኢትዮጵያን በማክበርና በወዳጅነት ዓይን እንዳልተመለከቷት ያስረዳል ፤ የቀሩት ገዳማት ኢትዮጵያን ከግብፆች አብልጠው ምን ያህል እንዲያከብሯትና እንዲወዷት ለመረዳት የኢየሩሳሌም የግሪክ ገዳም ፓትሪአርክ ስለ ልዑል አልጋ ወራሽ ክብር ሲሉ በጎልጎታ ውስጥ ለኢትዮጵያ ብለው የሰጡት መቅደስ የማይረሳ ምስክር ነው ።

ስለ ፍታንገሥታቸው ግብጾች ከጻፉት ፍታንገሥት አገራችን መጥቶ ምን ጠቀመን?ደኅና ልቡና ካለውና በልማድ ከሚፈርድ ዳኛስ ምን ያህል ይሻላል?እንኳን ለኢትዮጵያ ሊጠቅምና ከዓለም ነገሥታት ሕግ ያለያያት እሱ ነው።መንግሥት ሁሉ ባገር ውስጥ ያለውን ሕዝብ በሞላ ሲዳኝ ለኢትዮጵያ ይኸን የመሰለ ሥልጣን ከለከላት።ባገርዋ ተቀማጭ የሆነ የውጪ አገር ሰው ሁሉ እንደ ወገኑ የተለየ ዳኛ አለው ። የዚህ ምክንያት ምድር ነው ብለን ብንጠይቅ ምላሹን ከግብጽ የመጣው ፍታንገሥታችሁ በትክክል ባለመሆኑ ነው ይሉናል ።

በዚህ በኩል እንኳን የከበደ ሸክም ስለ ጫኑብን እስከ ዛሬ ድረስ ሕዝባችን እንደ አዘነ ይኖራል ። አሁን በቅርቡ ግን የኢትዮጵያ አልሚዎችና ጠባቂዎች የሆኑ ግርማዊት ንግሥታችንና ልዑል አልጋ ወራሻችን ተፈሪ መኰንን ይኸን ሸክም በዝግታ ለማቅለል ሲሉ ለሕዝባቸውና ለውጪ አገር ሰዎች በልዩ የቆመ ፍርድ ቤት አበጅተዋል።ይኸም ሥራ ወደ ፊት እየተስፋፋ እንዲሄድ አልጠራጠርም ፤

ክቡራን ወንድሞቼ ሆይ ይኸ ሁሉ ግፍ በናታችን በኢትዮጵያ ላይ እስከዛሬ ተሠራበት ። አሁን ግን ይህቺ ተበዳይ እናታችን እኛን ልጆቼዋን ይዛ ከባርነት ቀምበር ልውጣ እያለች ዓይኖቿን ወደ ብርሃን ጮራ እግሮቿን ወደሰላምንና መንገድ እየመራች ወደ ኋላችሁ አትመለሱብኝ አቅፋችሁ ደግፋችሁ ከብርሃን መከከል አስቀምጡኝ እያለች በእናት አንጀቷ ታለቅሳለች ፤ እኛ ደግሞ ፈቃድዋን ልንፈጽም የተዘጋጀን ልጆቹዋ አትዘኚ እናታችን ቀምበሩን ሰበርነው ጨለማም ሁለተኛ አያገኝሽም ። ባርነትም የለብሽም ብለን ልናጽናናትና ቃላችንንም ላና

ወላውልባት ይገባናልና አንድ ልብ ሆነንጥፋትዋን ተከላክለን ጥቅሟን እንፈልግ፡፡ፈቅጃለሁ ማለት አደረግሁ ማለት ነውና ልብ ከወላወለ የሚፈጸምና የሚደረግ ነገር የለም ፡፡

ዓለሙ መርሻ።

የ፻፮ ገጽ ተከታይ ።

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

፲፰ተኛ ክፍል ።

እውቀት የሌለው ሰው ፡ የዝሆንን ቁመትና መብረቅ ሲአይ የትልቅም ነጐድጓድ ጩኸት ሲሰማ የፈጣሪውን ሥራ ያደንቀዋል ፡፡ አስታዋይ የሆነ ሃይማኖተኛው ግን የንብና የጉንዳንን ትጋት የሥራቸውንም ትክክልነት የሥርዓታቸውን ማማር አይቶ ለዚህ ዓለም ፍጥረት ይገረማል ። ከመብረቅና ከነጐድጓዱ ኃይልም ይልቅ ንብና የጉንዳን ተአምር ለፈጣሪው የበለጠ ምስጋና ሁኖ ይታየዋል ።

እነሆም ሰሎሞንም በመጽሐፈ ምሳሌው ሁለት ጊዜ ያደንቃቸዋል ፡፡ ምሳሌ ምዕ ፮ ቍ ፮ ም ፴ ቍ ፳፫ ። እንዲሁም እውቀት የሌለው ሹም የመንግሥቱ ሀብት ከሐርና ከሻምፓኛ የሚነግው ግብር ሲበዛ ቢያይ ብዙ ሀብት የሚሰበስብ ይመስለዋል ። አስተዋይ የሆነ ሰው ግን መንግሥቱን ለመጥቀም ዓይኑን በሐርና በሻምፓኛ ላይ አይጥልም፡፡ሕዝብ ሁሉ የሚገዛውን ዕቃ አይቶ በዚያው ዕቃ ላይ ትንሽ ግብር ይጨምራል ። በዚሁም ለመንግሥት ትልቅ ጥቅም ያገኝበታል ፡፡

አሁን ለምሳሌ የኢትዮጵያ መንግሥት በየዓመቱ ከሐርና ከሥጋጃ የሚያገኘው ቀረጥ ጥቂት ነው ። ከቡጇዲድና ከብርድ ልብስ የሚገባለት ቀረጥ ግን ብዙ ነው ፡ ነገሥታት ሁሉ ጥቅማቸውን የሚፈልጉ ውድ ከሆነ ነገር አይደለም ፡፡ ሕዝብ ሁሉ ከሚፈልገው ከትንንሹ ዕቃ ሁሉ እንጂ ። ስለዚህም ሐርንና የኤሌክትሪክን ማብርያ ሰው ሁሉ እንደ ፈቀደው ሲሸጥ ሲለውጥ ጨውና ክብሪት ትምባሆም በብዙ ነገሥታት አገር ሞኖፖል ሆነው እናያለን ፡፡ እነዚህም ዕቃዎች ከሌላው ዕቃ ሁሉ ተመርጠው ሞኖፖል የሚሆኑበት ከሚገዟቸው ሰዎች ብዛት የተነሣ ለመንግሥት የሚገኝባቸው ጥቅም ተጠራቅሞ ብዙ ስለሆነ ነው ። ከብርና ከወርቅ አብልጦ የሚፈለግ ግን በማናቸውም አገር አይገኝም እያንዳንዱ ሰው ለኑሮው የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ በተሙን በሩብ ባላድ በብር ገዝቶ ነው ። ስለዚህም ብዙ ነገሥታት መጥፎ ብር እያተሙ እያወጡ ባገራቸውም ከርሱ በቀር በሌላ ብር ሕዝባቸው እንዳይገበያይ እያወጁ ደህና ብር የያዘ ሰው ሁሉ ብሩ በገበያ እንዳይሄድለት እያየ እንዲሸጥላቸው ሲያደርጉ እንደ ነበሩ የዓለም ታሪክ ይመሰክርልናል ። ውቡ ፊልጶስ የሚባል አንድ የፈረንሳዊ ንጉሥማ ከናካቴው ከነገሡ ጀምሮ እስኪሞት ድረስ ሕዝቡ የሚገበያይበትን የብር ዓይነት የለወጠ ከመቶ ጊዜ ይበልጣል ይላሉ ።

የብር ዓይነትም ከመለዋወጥ የተነሣ ሕዝብ የሚያገኘው ጉዳት ምን እንደሆነ እንዲረዳ አንባቢው ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል አስተውሎ ይመልከት ዛሬ በኢትዮጵያ ያለው ብር የነምሳውና ያጼ ምኒልክ ብር ነው ፡፡

እነሆ የነምሳውም ብር ክብደቱ ፳፰ ግራም ከ፮፻፳፰ አሥር ሺህኛ ግራም ነው ። በውስጡ ያለው ንጹሕ ብር ግን ፳፫ ግራም ከ፫፻፹፱ ሺህኛ ግራም ነው ። ስለዚህም በነምሳው ብር ውስጥ ያለው ብር ያልሆነ ነገር ፬ ግራም ፮ ሺ ፯፻፴፰ አሥር ሺህኛ ግራም ነው ፡፡ ያጼ ምኒልክም ብር እንደዚሁ ብር ትክክል ነው ይባላል ። ሁለቱም የብር አይነት በገበያ አይበላለጡም ።

እንግዴህ የኢትዮጵያ መንግሥት ለወደፊት እነዚህን ሁለቱ ቶችን የብር አይነት ሕዝቡ እንዳይገበያይባቸው ከልክሎ በውስጡ ፳፩ ግራም ፫፻፩ አሥር ሺህኛ ግራም ጥሩ ብር ያለበት ሌላ አዲስ የብር አይነት ቢያወጣ ። ብር የያዝክ ሰው ሁሉ ካሥር ብር አንድ ብር ፈሰስ ጥዬብሃለሁ እንደ ማለት ያህል ነው ። ስለምን ቢሉ ቀጥሎ የተጻፈው ቃል ያስረዳል ።

እንደዚህ ያለ አዋጅ ተነግሮ የዱሮው ብር በገበያ መሄዱ ሲቀር የዱሮውን ብር የያዘ ሰው ሁሉ መቼም ብሩን የሰበሰበው ዕቃ ሊገዛበት ነው እንጂ ሊቆረጥመው አይደለምና የያዘው በገበያ ሰው የማይቀበልለት ሲሆን ላዲሱ ብር ሊለውጠው ነው ፡፡ በዚሁም ምክንያት የዱሮው ብር ሁሉ ወደ መንግሥት ጓዳ ሊገባ ነው ። ይህም ሲሆንለት የኢትዮጵያ መንግሥት አሥር ብር ፳፩ ግራም ፫፻፩ አሥር ሺህኛ ግራም የሚከብድ ብር ሰጥቶ አሥር ብር ፳፫ ግራም ፫፻፹፱ ሺህኛ ግራም የሚከብድ ብር ሲገባለት ባሥሩ ብር አንድ ብር ትርፍ ሊያተርፍበት ነው ።

ከውጭ አገር የሚመጣው ዕቃ ሁሉ ግን የሚገዛው በኤሮፓ ነገሥታት ብር ሂሳብ ነውና የኤሮፓ ነጋዶች በአዲሱ ብር ውስጥ ያለው ጥሬ ብር በዱሮው ብር ውስጥ የነበረውን እንደማያህል ይገምቱታልና የዕቃቸውን ዋጋ ከፍ ሊያደርጉ ነው ።

የዱሮውን አሥር ብር ሲቀበሉበት የነበረውን ዕቃ ሁሉ ለአዲሱ ብር ሲሸጡት አሥራ አንድ ብር ሊፈልጉ ነው ። እህልና ሌላም በአገራችን የሚገኘው ነገር ሁሉ የሚሸጠውም ባላገር ብር የሚፈልገው መቼም አቡጇዲድ ወይም ሌላ ከውጭ አገር ተሰርቶ የመጣውን ዕቃ እንዲገዛበት ነውና የሚፈልገው ዕቃ መወደዱን ሲያይ እርሱም ከመሬቱ ያገኘውን እህልና ሌላውም ነገር ሁሉ ዋጋውን ካሥር አንድ ከፍ ሊያደርግ ነው ስለ ዚህ ብር የያዘ ሰው ዱሮ ለሥር ብር ሲሰጥበት የነበረውን ዕቃ ለመግዛት ሲፈልግ አሥራ አንድ ለመስጠት የግድ ሊሆንበት ነው ፡፡ ከባሕር ማዶ ነጋዴ የሚያመጣው ዕቃ ግን ስለ ተወደደ ትርፍ ብር አያገኝበትም ። አዲሱ ብር እንደ ዱሮ ብር ጥሩ ሳይሆን ቀርቶ ለሚያመጣው ዕቃ ስለ ተወደደበት ነው እንጂ ከባሕር ማዶ የመጣው ዕቃ ሁሉ ተወዶበት ከዱሮ የበለጠ ዋጋ መስጠት የግድ ስለ ሆነበት አይደለም ። ባላገሩም ቢሆን እህሉ ስለ ተወደደለት አንዳች ትርፍ አያገኝም ትርፉን ያገኘ መንግሥት ብቻ ነው ። ደግሞም ዋጋ ስለ ተጨመረባቸው ብሩ መጥፎ በመሆኑ እንደ ሆነ ነጋዴና ባላገር ዕቃ የያዙ አይጎዱም ፡፡ የሚጎዳ ዕቃ ስለተወደደ ብር የያዘ ሰው ብቻ ነው ።

በኢትዮጵያ ያለው ብር ሕዝቡ የሚገበያይበት ሀያ ሚሊዮን ይሆናል ተብሎ ስለተገመተ የኢትዮጵያ መንግሥት ድንገት ከላይ ባሳየነው ሂሳብ አዲስ ብር አውጥቶ በዱሮው ብር ሰውን እንዳይገበያይ ቢከለክል ባንድ ጊዜ ሁለት ሚሊዮን የሚ

ሆን ብር ያገኝ ነበር ። ማለት እንደፈረንሳዊ ንጉሥ ውብ ፊሊጶስ እየደጋገመ በያመቱ ቢለዋውጥ የኢትዮጵያ መንግሥትም ቢሆን ማድረጉ ይቻለው ነበር ሕዝቡ ግን በጣም ይጐዳበታል ። ነገር ግን እንደዚህ ያለው ሥራ ፈጽሞ የቅጥፈት ሥራ ነውና ከላይ የተጠራው የፈረንሳዊ ንጉሥም ቢሆን ሥራው መሰደቢያ ሆኖ በዓለም ታሪክ ላይ ተጻፈበት እንጂ አልተመሰገነበትም ።

ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደዚህ ያለውን ሥራ እንኳን ለመሥራቱ ማሰቡም አይገባውም ። ገንዘብ ከስፈለገው በእንደዚህ ያለ የቅጥፈት መንገድ ወይም ሥራ አውጥቶ ብር የያዙትን ዜጎቹን ሁሉ ከመጉዳት ። በግልጽ አገሌ ይህንን ያህል ገንዘብ አገባ ወይም አለው ተብሎ በእየ አንዳንዱ ዜጋው ላይ እንደ ሀብቱ መጠን ፈሰስ ቢጥልበት ይሻላል ። እያንዳንዱ ዜጋ የሚከፍለው ግብር እንደ ገንዘቡ ብዛት እንደ ሀብቱ መጠን ቢሆን ፍርድ ጐደለብኝ ብሎ የሚያዝን ሰው ከሕዝቡ ውስጥ ባልተገኘም ነበር ። አሁንም ለምሳሌ ዛሬ ገብረ ማርያም አቡጀዲድ እገዛለሁ ሲል አንድ ጋሻ መሬት ለወልደ ማርያም ሸጠለት በመንግሥቱ አዲስ ብር የወጣ እንደ ሆነ ገብረ ማርያም ስለ መሬቱ ዋጋ የተቀበለው ብር በገበያ የማይሄድለት ሆኖ ለአዲሱ ብር መለወጡ የግድ ይሆንበታል ። ገብረ ማርያም ሊገዛው የፈለገ አቡጀዲድ ግን አዲሱ ብር መጥፎ ስለሆነ ዋጋው ሊወደድበት ነው ። ነገሩ እንደዚህ ሲሆን ቀላዱን የገዛ ወልደማርያም ሳይነካ ቀላዱን የሸጠ ገብረማርያም ይጐዳል ። ስለዚህ በአንድ መንግሥት ውስጥ እንደዚህ ሆኖ አንዱ ዜጋ ሲጐዳ ሌላው ሳይነካ የቀረ እንደሆነ ፍትሕ ጐደለ ይባላል ።

ጸሐፊው የግድ ባይሆንበት ይህ ከላይ የተጻፈውን የቅጥፈት ሥራ በዚህ መጻፉ አይገባም ነበር ነገር ግን የሕዝብ አስተዳደር የሚባለውን መጽሐፍ ሲጽፍ እንደዚህ ያለ ማስረጃ በውስጡ ሳያሳይ ቢቀር መጽሐፉ ጐደሎ ይሆንበታል ። ደግሞም ጸሐፊው እንደ ሰማው ወሬ አንድ የውጭ ሰው ዛሬ በኢትዮጵያ ያለውን ብር እየ ከፈሉ ሁለት ብር ቢያደርጉት ይቻላል ብሎ ለኢትዮጵያ ሰዎች መክሩዋል አሉ ። እንደዚህ ያለውን ምክር ሰምቶ ፊት ባሳየነው ሂሳብ እንዳይሆንበት መጠንቀቅ ነው ።

የኢትዮጵያ መንግሥት የአንድ ቀጣፊ ምክር ሰምቶ ከላይ የተጻፈውን ስሕተት ቢያደርግ በቀሩት ነገሥታት ፊት ውርደት ይሆንበታልና ስለዚህ ከንደዚህ ያለው ምክር ይጠንቀቅበት ። በዛሬው አላድ ሩብ ተሙን ሲሸረፍ የሚያገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ጉዳት ይበቃዋል ። የዛሬው አላድ ሩብ ተሙን ሲታተም ለአንድ ብር ሁለት አላድ አራት ሩብ ፲፮ተሙን እየታሰበ ነበር ። ይህ ስለሆነ እነዚህ መሣሪያዎች ለአገራችን ገበያ እንደሚበቁ ሆነው አልተገኙም ። ደግሞም ብሩ ለሁለት አላድ ላራት ሩብ ለ፲፮ተሙን እንዲሸረፍ የኢትዮጵያ መንግሥት ምንስ ለሥርዐቱ ቢያውጅ አዋጁ አልረጋም ። እንደ ሥርዐቱ ፩ብር ፲፮ተሙን ብቻ ሊሸረፍ አይገባውም ነገር ግን ፳ተሙን የአንድ ብር ሀያኛ ነውና የኢትዮጵያ መንግሥት ፩ብር በ፲፮ተሙን ይሸረፍ ብሎ ሲያውጅ ብርህን ለተሙን የምትለውጥ ሰው ሁሉ በያንዳንዱ ብር አራት ተሙን ገብርልኝ እንደ ማለት ነው ። ግን ይመስገነው መንግሥታችን ይህንኑ አዋጅ አላጠነከረምና ሕዝቡም የተሙንን ርካሽነት ዱሮ ተረድቶት ብሩ በ፲፮ተሙን እስከ ፲፰ድረስ ሲለዋወጥ ይኖራል ። ተሙኑም የአገራችን ገበያ እንደሚፈልገው መጠን በብዙ ታትሞ ቢሆን ያለጥርጥር አንድ ብር ለሀያ ተሙን ይሸረፍ ነበር ። ነገር ግን እንደ አላዱና እንደ ሩቡ የታተመው ተሙን ጥቂት ነውና ያውም የሚበዛው አላድ ተሙን ሩብ ታትሞ የሚመጣልን ከፈረንሳዊ አገር ነውና ይኸነኑም ሳይቀር ቀጥሎ የተጻፈው እንደሚያሳየን ለአገራችን ትልቅ ጉዳት ነው ። የኢትዮጵያ ሕዝብ የትንንሾቹ የለውጥ መሣሪያዎችን ጣዕም ለምዶ ወድዋቸዋልና ሕዝቡም በጣም ድሐ ስለሆነ በአገሩ ውስጥ ከትልቁ የለውጥ መሣሪያ ይልቅ ትንንሹ የለውጥ መሣሪያ ይፈለጋል ። ዛሬ በድሬዳዋና በሐረር በአዲስ አበባም ገባዮች አስተውለን ብንመለከት ሕዝቡ እርስ በርሱ ሲገበያይ ወይም ሲገዛዛ የሚበልጠው ግዥው በተሙን ነው ።

ከዚያ በኋላ ቀጥሎ በሩብ በአላድ ነው ከፍ ያለውም በብር ። የኢትዮጵያ ሕዝብ የአገሩ ሀብት ጥቂት ስለ ሆነ ሙሉ ብር በቶሎ ለማግኘት አይሆንለትም ። ለኑሮው የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ የሚገዛበት ገበያ ሩቅ የሆነበት ሕዝብ ጉልበቱ ሁል ጊዜ ርካሽ ነው በእንደ ዜህ ያለ አገርም ሁለጊዜ፡ብር ይወደዳል ።

አሁን ለምሳሌ ። አንድ የአዲስ አበባ ጉራጌ ሰርቶ አንድ ሙሉ ብር እስቲያገኝ ድረስ የአራት ቀን ሥራ ይውልበታል አላድም እስኪያገኝ ድረስ ሁለት ቀን ። ሩብም እስኪያገኝ ድረስ አንድ ቀን ተሙን እስኪያገኝም ድረስ የሚሠራው ሁለት ሰዓት ያህል ነው ። እንግዴህ ከሙሉ ብር በቀር ሌላ የለውጥ መሣሪያ ባይኖር ሙሉውን ብር እስኪያገኝ ድረስ ጉራጌ አራት ቀን ሙሉ በራብ ይቸገር ነበረ ። ሙሉውን ብር ካገኘ በኋላ ሊከፍለው አይችልም ነበርናበሙሉው ብር ሽምብራን እንዲገዛበት የግድ ይሆንበታል።በሙሉው የሚገዛው ሽምብራም በዝቶበት በልቶም በቶሎ የማጨርሰው ነውና የሚጠብ ቅለት እያጣ ሽምብራውን ታቅፎ ሥራውን ትቶ ወይም ታጉሎ ይቀራል ። ወይም ደግሞ ሥራ እንዳይታጐል ከፈለገም ሽምብራውን የምትጠብቅ ሚስት ማግባት የግድ ይሆንበታል በዚሁ ምክንያት የተነሣ በላተኞቹ በዝተው በብር የተሸመተ ሽምብራ በጥቂቱ ቀን ያልቃል ጉራጌም ልፋቱና ሥራው ለሁለቱ ሆድ ብቻ ሆኖ ይቀር ነበር ጉራጌም ትርፍ አልባ ሆኖ ይቀር ነበር ። ተሙን ሳለ ግን ጉራጌው ከላይ እንዳየነው የመሳሰለ ችግር አያገኘውም ሽምብራውን የምትጠብቅለት ሚስትም ማግባት አያስፈልገውም ። ለዕለት ምግቡ የሚያስፈልገውን ያህል ሽምብራ በእኩለ ቀን ከሥራው ሲያርፍ በተሙን ሸምቶ ለምሳው የሚበቃው ያህል በልቶ የተረፈውን በጨርቁ ቋጥሮ በወገቡ ታጥቆት ወደ ሥራው ይመለሳል ።

ከሥራው የማይተጓጐል ስለ ሆነም በዕለት በዕለቱ እየሠራ በጊዜ ብዛት ጥቂት ብር አጠራቅሞ ወደ አገሩ ይመለሳል ። በሌላውም ነገር ቢሆን እንደዚሁ ነው ። ሕዝቡ ደሃ በሆነበት አገር ሁሉ ትልቁን የለውጥ መሣሪያ ከሚፈልገው

ይልቅ ትንሹን የለውጥ መሣሪያ የሚፈልገው ይበዛል ። የአንድ ድሃ ወታደር ሚስት ወደ ገበያ ብትሔድ ብሩን ለተሙን ቸርፋ በተሙን ሽንኩርት በተሙን ጨው በተሙን ቁንዶ በርበሬ በተሙን ጋዝ በቀለህ ክብሪት ገዝታ ለመመለስ ትችላለች ። አንድ ብር ሙሉ ይዛ ወደ ገበያ የምትሔድ ምናልባት እህል ለመሸመት ነው ። በድሃ ቤት እህል የሚሸመተው ግን ቢበዛ በወር አንድ ጊዜ ነው ። ማለት ነገሩ ሁሉ አጥብቀን ከመረመርነው በአዲስ አበባና በአውራጃው ሁሉ በሐረርጌ አውራጃም ያሉት ገበያዎች ሁሉ ከየለውጥ መሣሪያ ሁሉ እንደተሙን መወትር የሚፈልግ የለም ። ይህም ምክንያቱ ከህዝቡ የሚበዛው ድሐ ስለ ሆነ ነው ። የአንድ ድሐ ባላገር ሚስት የሚሸጥ ዕቃ ይዛ ወደ ገበያ ብትወጣ፥ የያዘችውም ዕቃ ምናልባት የተሙን ጕመን ወይም ሽንኩርት ወይም ዶሮ ወይም የተሙን ዳቦ ወይም ቆሎ እንደዚሁ የመሰለ ትንንሽ ነገር ይሆናል ፤አንዲት ላም ብትኖራት የአንድ ብር ቅቤ እስቲጠራቀምላት ድረስ ብዙ ቀን የሚያስፈልጋት ነውና ለእለት የሚሆነውን ትንንሹን ጉዳይዋን ለተሙን ትሸጣለች ። ተሙን ወደ ሌለባቸው የኢትዮጵያ አውራጆች በተሙን ፈንታ በጨው ወይም የጨው ግሚስ ወይም የጨው ኩርማን ብጥይት በቀለህ ከፍ ያለውም በሸማ ከብሩ ይልቅ በእያዚህ ያሉት ትንንሾች የለውጥ መሣሪያዎች ሲገበያዩ እናገኛቸዋለን ። እውነትም የዛሬውን ብር የሚያህል ትልቅ የለውጥ መሣሪያ ለእ[illegible]ደ ኢትዮጵያ ያለ አገር አይመችም ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይቀጥላል ።

ከኑጋድራስ ገብረ ሕይወት መጽሐፍ ነው።

የ፹፱ገጽ ተከታይ ።

አንድነት ያበረታል መለያየት ግን ያደክማል ።

ክቡር ዳዊትም እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪ እንደሆነ ሲአጠይቅ ። ዚአከ ውእቱ ሰማያት ወእንቲአከ ይእቲ ምድር ወዓለመኒ በምልዑ አንተ ሣረርከ ወይሴብሑ ለስምከ አለ መዝሙር ፹፰ ።

ዳግመኛም ፤ በክርስቶስ ታመንን በኋላ ሥልጣን አይገባቸውም የሚል ሰው ቢኖር ወይቤሉ ምንትኑዝ ዘይነብብ ጽርፈተ ። ወመኑ ይክል ኅዲገ ኃጢአት ብለው እንደ ተጠራጠሩት ሰዎች ያለ መሆኑን ይወቅ ማርቆስ ፫ ም ፯ ቁጥር ።

ክፍል ሁለተኛ እነሱን ይልቅ በብዙ ምክንያት ሹመት ይከለክላቸዋል ። በሀገሩ ቋንቋ የማይናገር እንዳይሾም ።

እፎ የአምኑ በዘኢይሰምዑ ወእፎኑ ይሰምዑ ዘኢሰበኩሙ እሚንሰ እምሰሚዕ ወሰሚዕ በቃለ እግዚአብሔር ይላል ጳውሎስ ሮሜ ሰዎች ም ፲ ቁ ፲፯ ።

ዳግመኛም ፡ ለቆሮንቶስ ሰዎች ወይእዜኒ አኃውየ እመ መጻእኩ ኀቤክሙ ወነበብኩ በነገረ በሐውርት አልብየ በቍዔት ዘእበቍዓክሙ ለእመ ኢተናገርኩክሙ ክሡተ ወገሀደ ፴ነ በሐማን ንሕነ ከማሁኬ አንትሙኒ ተአኃው ምስለ ዘመንፈስ ቅዱስ ኀሠ ከመ ትብዝኑ በዘይትሐነጽ ሕዝብ አለ ም ፲፬ ቁ ፲፰

፫፻ም በአንቀጸ ኤጲስ ቆጶሳት ኢይኩን ሊቀ ላዕለ ክርስቲያን ወኢይእመንዎ እንበለ ዘየአምር ሕጋጋቲሃ ወሥርዓታቲሃ ወቀኖናቲሃ ለሀገር ብለዋል ። ፲፯ ቁ ፲፬

ሶስተኛም እርስታችንን ኢየሩሳሌምን መውሰድ ጥል ሆኖ ይከለክላቸዋል ተሹመት አስቀድሞ እርቅ እንዲገባ ። ወለእመቦ ዘቦ ተስናን ምስለ ቢጹ ቅድመ ለይትዋቀስ በኀበ ቅዱሳን እመሰኬ አንትሙ ትኴንንዎሙ ለዓለም ኢይደልወክሙኑ ትኩንኑ ትሑተ ምኵናነ ይላል ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ፮ም ፫ ቁ

ዳግመኛም ፡ እመኒ አእመርኩ ነገረ ኵሉ ሰብእ ወነገረ ኵሉ በሐውርት ወነገረ ኵሉ መላእክት ወተፋቅሮ አልብየ ወለእመኒ ብየ ሃይማኖት እስከ አፈልስ አድባረ ከንቶ ከንኩ ይላል ፲፫ ም ፲፰ ቁጥር ።

ዳግመኛም በፊልጵስዩስ ። ወኢትግበሩ ኵሎ በተቃሕዎ ወኢ በአፍቅሮ ክብረ ከንቱ ዓለም ወኢትዘኃሩ ወኢትትዓበዩ ይላል ፪ ም ፪ ቁጥር ።

፫ቱ ፻ትም በአንቀጸ ኤጲስ ቆጶሳት ። ወለ እመ ኮነ ኤጲስ ቆጶስ ይደልዎ ከመ ይሰአል በዘይከውን ሰላም ላዕለ ክልአን ወይደልዎ ሎቱ ፈድፋደ ከመ ይኩን ዝንቱ በኀቤሁ ብለዋል ፲፪

ጥንትም በስንክሳር ስለ ጳጉሜን እርግማን በከንቱ እንዳይደርስ ይቤ እግዚእነ በወንጌል ሶበ በእክሙ ውስተ ቤት በሉ ሰላም ይኩን ለሰብእ ዝንቱ ቤት ለእመ ሀሎ ብእሲ ሰላም ይኅድር ሰላምክሙ ላዕሌሁ እመሰ ኢረከበ ዘይደልዎ ሰላምክሙ ይግባእ ኀቤክሙ እመሰ ኮነ ሰላም ይገብእ ኀበ ዘፈነዎ ሶበ ኢረከበ ዘይደልዎ ሰላም ከማሁ መርገምኒ ካዕበ ይትመየጥ ፈድፋደ ኀበ እሱር ለዘፈነዎ በዓመፃ ወኵሉ ዘይረግም በከንቱ ረገመ ነፍሶ ብለው ጽፈዋዋል በአንቀጸ ክህናት ፳፪ ።

ክፍል ፬ተኛ ማንም ክርስቲያን ሁሉ ታመነና ተተማረ በኋላ መምሕር እንዳያስፈልገው ጳውሎስ ወደ ገላትያ በጻፈው ክታቡ አሬት እንከ መርሃ ኮነተነ ለኀበ ክርስቶስ ከመ ንጽደቅ በአሚን ። ወሶበ መጽአት እንከ አሚን በክርስቶስ ኢንፈቅድ እንከ መርሃ እሰመ ኵልነ ውሉደ እግዚአብሔር ንሕነ በአሚን በኢየሱስ ክርስቶስ ይላል ፫ ም ፬ ቁ

ዳግመኛም ክርስቲያን ሁሉ በክብር ትክክል ነው ሲል ወኢይሜህር አሐዱ ለካልዑ ወኢይሜህር ብእሲ እኅዋሁ እንዘ ይብል አእምርዎ ለእግዚአብሔር እስመ ኵሎሙ ያአምሩኒ ንዑሶሙ ወዓቢዮሙ ይላል ለዕብራውያን በጻፈው ፰ ም ፲ ቁጥር ።

ቅዱስ ጴጥሮስም ናሁ እሰይም ውስተ ጽዮን ዕብነ ማዕዘንት ኅሬተ መክብርተ ወለእለሰ ይክህዱ ዕብን እንተ መነንዋ ነደቅት ወይእቲ ኮነት ውስተ ርእሰ ማዕዘንት አለ ።

ጌታም በማቴዎስ ወንጌል ወበሕቱ እብለክሙ ብዙኃን ይመጽኡ እምሥራቅ ወእምዕራብ ወይረፍቁ ምስለ አብርሃም ወይስሐቅ ወያዕቆብ በመንግሥተ ሰማያት ይላል ፰ም ፲፩ ቁጥር ። ዳግመኛም ፣ ፲፱ ቁጥር አልቦ ረድእ ዘየዓቢ እምሊቁ ወገብርኒ ዘየዓቢ እም እግዚኡ ብሎ መጠኑ ለረድእ ይኩን ከመ ሊቁ ወገብርኒ ይኩን ከመ እግዚኡ ብሎ አስተካከለ ።

ዳግመኛም ጸውአሙ ለገባዕት ሀቦሙ አስቦሙ እምደኃርት እስከ ቀደምት ወከማሁኬ ደኃርት ቅድመ ወቀደምት ድኅረ ብሎ የኋለኞችን አበለጠ ፳ ም ፱፪ ቁጥር ።

ዳግመኛም በኋላ የተማረና በኋላ የተወለደ በክርስቶስ ዘንድ እንዲወደድ በማርቆስ ወንጌል ኅድጉ ሕፃናተ ይምጽኡ ኀቤየ ወኢትከልእዎሙ እስመ ለዘከመ እሉ ይእቲ መንግሥተ እግዚአብሔር ወአንበርሙ ውስተ ሕፅኑ ወባረኮሙ ወወደየ እደዊሁ ዲቤሆሙ ይላል ። ፱ ምዕ፳፫ ቁጥር ።

ቀድሞ በመጠመቅም ብልጫ እንደሌለ ሲአጠይቅ ወብ ዙኃን ቀደምት ይከውኑ ደኃርተ ወደኃርትኒ ይገብኡ ቀድመ አለ ። ፳፱ ቁ

ደግሞም እግዚአብሔር ሁሉን አስተካክሎ ይገዛል ። ኢት ዮጵያም የሱ እንደሆነች ሲያስረዳ ወይኴንን እምባሕር እስከ ባሕር ወእምአፍላግ እስከ አጽናፈ ዓለም ብሎ ይገንዩቅድ ሜሁ ኢትዮጵያ አለ ፤ ክቡር ዳዊት መዝሙር ፷፯ ።

የኢትዮጵያንም ልጆች ተሁሉ አስተካክሎ እንዲአስባ ቸው ይታወቅ ዘንድ እዜክሮን ለረዓብ ወለባቢሎን እለ የአም ራኒ ብሎ ወናሁ ኢሎፍሊ ወጢሮስ ወሕዝበ ኢትዮጵያ እለ ተወልዱ በህየ ይላል ። መዝሙር ፹፮ ።

ጥዑመ ልሳን ።

የምስጋና ቃል ።

በዚህ ዓለም የሚሠራ ከስጦታ ወገን የሆነ ሥራ ብድር የሚያስፈልገው ከመሆኑ የተነሣ የሰጪ ስጦታ ሁሉ ከተቀባይ እጅ ብድርን ይፈልጋልና ፤ ብድርን መመለስ ለማይችል ተቀ ባይ የሚሰጥ ሰው ስሙ በተለይ ቸር ይባላል ። ቸር ነው የሚ ያሰኘውም ለስጦታው የሚበቃ ብድርን በሚገባ ሊመልሱለት የማይችሉ መሆናቸውን እያወቀ ድሆችን ልክ እንደ ሀብታሞች ጓደኞቹ መጠን አድርጎ በተዘጋጀ የስጦታ ማዕዱ ዙሪያ ሆነው እንዲመገቡ ርኅራኄውን ገልጾ ያሳየ እደሆነ ብቻ ነው እንጂ ብድሩን ሊመልሱለት የማይችሉ ድኆችን አስወግዶ ሀብታሞ ችን ብቻ ቢጋብዝ ቸር አያሰኘውም ። እነዚህም ሀብታሞች የሆኑ ወዳጆቹም ይህ የተጠሩበት ግብዣ ብድር የሚያስፈልገው መሆ ኑን ያውቃሉና ፤ ይህንን መጀመሪያ የጋበዛቸውን ሰውዬ መጋ በዝ ግድ የሚያስፈልግ ስለሆነባቸው የብድር ግብዣ አሰናድ ተው ለመጋበዝ ዋና ጥረት ያስፈልጋቸዋል ።

ከላይ እንደ ተናገረው ቸር በተባለው ሰውዬ ቤት ለምሳ የሚጠሩ ድኆች ግን አመስግኖ ከመመገብ በተቀር ለቸሩ ሰው ዬ የሚመልሱለት የስጦታ ብድር በትክክል እንደሌላቸው ፈ ጽመው ስለተረዱ፤እግዚአብሔር ይስጥልን እግዚአብሔር ይ ባርክልን የሚል ምስጋናቸውን ብቻ በፍጹም ልባቸው ያቀርባሉ እንጂ ፤ ከስጦታ ወገን የሚሆን ሌላ ነገርን ምንም ምን አያስ ቡም ። -

እኔም እንደዚሁ ሁሉ ዘለዓለማዊ ንጉሥ ክርስቶስ በታ መኑ ቸር አገልጋዩ ልዑል ተፈሪ መኰንን ርኅራኄ ያደረገ ልኝን የታላቅ ሥራውን ብድር እንደሚገባ መመለስ ይቅርና በትክክል ምስጋናውን ተናግሬ እንኳ የማልጨርሰው ስለሆን ኩ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል በብርሃንና ሰላም ወዳጆች ፊት አቅርቤ ዕፁብ ድንቅ እያልኩ ከመገረምናከመደነቅ በተ ቀር ሌላ ቃል ምንም ምን አላገኘሁም።

የማስጽፈውም ይህ ነው ። ገናናው የኢትዮጵያ መንግ ሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን የወገኖቻቸውን የሕ መምና የደዌ መከራቸውን እያዩ መታገሥ የማይሆንላቸው ሆኖ ፤ የኢትዮጵያ ብርሃን በሆነ ዕውቀታቸው መርምረው ዕውነተኛ ሐኪም ዶክቶር ሐነርን አስመጥተው ቤተ ሳይዳ በተባለው የሕ ክምና ቤት ካስቀመጧቸው ወዲህ ፤ በዶክቶር ሐነር እጅ የተ ደረገ የሕክምና ሥራ ወሬ እንደ ማለዳ ፀሐይ እየሞቀና እየደ መቀ ስለ ሔደ የብርሃኑ ጮራ በመላ ኢትዮጵያ አውራጆች ሁሉ ተዘርግቶ በጨለማ ደዌ ለነበሩ በሽተኞች የሚያበራ ከመ ሆኑ የተነሣ ትንሽ የብርሃኑ ብልጭታ ወሬ ታይቶኝ ከሀገሬ ከደብረ ሊባኖስ ቀጠባ ከምትባል ሰበካ ወዳዲስ አበባ ብመጣ እነዚሁኑ ከጨለማ ደዌ በዶክቶር ሐነር እጅ የዳኑትን በሽተ ኞች በሕይወት ጉዳና ሲወጡና ሲወርዱ በትክክል ለማየት በቃሁና እንደነሱው ሁሉ ወደ ቤተ ሳይዳ ገብቼ በዶክቶር ሐነር እጅ ለመታከም በምሉ ተስፋ እየተፀናናሁ ደፈርኩ ።

ጤነኞች ባለመድኃኒትን አይሹትም በሽተኞች እንጂእን ደሚባለው ሁሉ የበሽታዬ ልክ ታውቆኝ የነበርኩ በሽተኛ እኔም የታመኑ ፈዋሽ ዶክቶር ሐነርን ለመፈለግ ግድ ሆኖብኝ የነበረው የደዌዬ ምክንያትም ፤ ፈጣሪዬ ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአ ምሳሊነ ብሎ እንደ ፈጠረው ሰው ሁሉ መልክና ምሳሌ አድርጎ ከፈጠኝ በኋላ ፤ በዚህ ምክንያት ይመጣል ተብሎ ምክንያቱ የማ ይታወቅ ትርፍ አካል እንቅርት የሚባል ደዌ አንገቴን አንቆ አስጨንቆኝ ነበረና በዶክቶር ሐነር የሕክምና ብልሀትና ዕው ቀት የሚጠፋልኝ መሆኑን በፍጹም እምነት ስለተረዳሁት ነበረ ።

እንቅርት የሚባል በሽታዬን ካሳየኋቸው በኋላም እኒሁ ባለሙሉ እድል ዶክቶር ሐነር ከኔ አስቀድሞ ሀብታምና ድኃ በማይመርጥ አእምሯቸው አክመው ላዳኑዋቸው በሽተኞች ያደ ረጉት እንደነበረው ሥርዓታቸው ፤ ለኔም ደግሞ ለጕስቋላይቱ ድኃ እንደሚገባ ሥርዓትና ጥንቃቄ አድርገው ፤ እቤተ ሳይዳ በገባሁ ባራተኛ ቀኔ ይህንን ክፉ ባላጋራ ፤ አንገቴን አንቆ ይዞ ያስጨንቀኝ የነበረ እንቅርቴን በግድ ከንገቴ መንጥቀው (አው ጥተው)ጣሉልኝና ፤ ባከሙኝ አሥረኛ ቀን ደኅና ሁኜ ወደቤቴ ለመመለስ በቃሁ ።

ይህንንም ማስጻፌ የብርሌ አንገት በሚመስል አንገታ ቸው ላይ ይህ የጕስቍልና ምክንያት የሚሆን እንቅርት ስለወጣባ ቸው በውርደትና በኃዘን እንደኔ ሲጨነቁ ይኖሩ የነበረ በሀ ገሬ አውራጆች ያሉ ባለ እንቅርቶች ሁሉ ፤ በኔ ላይ የተደረገ የዶክቶር ሐነርን ግሩም ድንቅ ተብሎ የሚመሰገን የሕክምና ሥራ የተመለከቱና የሰሙ እንደሆነ ፤ ካያሉበት አገር ወደ ቤተ ሳይዳ እየመጡ ከመታከማቸው የተነሣ ምሉ ጤንነታቸውን ያገኙና በንድነት ሁነን የደኅንነታችን ምክንያት ለሆኑልን አልጋ ወራሻችን ሀብትና ጤና ከረጅም እድሜ ጋራ ስጥልን እያልን ወደ ፈጣሪያችን እንድንለምን ብዬ ነው እንጂ ፤ የዶ ክቶር ሐነርን ሥራ ተናግሮ በማመስገኑ ደስ የሚያሰኛቸውና ለድካማቸው ዋጋ የሚሆን እንደበትና ዕውቀት አለኝ ብዬ አይ ደለም ።

አስካለ ወልደ ገብርኤል ።

ሙሉ የደስታ ደስታ ።

መክብብ ፤ ለሁሉም ጊዜ አለው ያለው ቃል በጊዜው ሲደረግ እውነትም ለተመልካቹ ሁሉ በጣም ደስ ያሰኛል ። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ምንም እንኳ እግዚአብሔርበየጊዜው የሚሠራው የቸርነት ሥራ ብዙ ቢሆን ፤ በዛሬው ዓመት ውሥ ጥ ጥቂች ሰዎች በወሊድ ምክንያት ከዚህ ዓለም ወደ ወዲያ ኛው ዓለም አለፉ ማለትን እየ ሰማን ስለ ክብርት ወይዘሮ ተናኘ ወርቅ ተፈሪ ፡ የፊታውራሪ ደስታ ባለቤት እርግዝና ከብዙ ወዳጆቻቸውና የሚያውቋቸው ሰዎች ሁሉ ጋራ አብረን ስናዝን ና ስንጨነቅ ነበርን ።

ይልቁንም የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ጌታችን ልዑል ተፈሪ መኰንንና የልዕልት እመቤታችን ወይዘሮ መነን ፡ ደግሞም የክቡር ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው ኃዘንና ጭንቀት የበለጠ ስለሆነ በመዓልትና በሌሊት ወደ ፈጣሪያቸው ልመናቸውን ያቀርቡ እንደነበረ አይጠረጠርም ። እንደዚህ ከመ ሆኑ የተነሣም የለመኑትን የማይነሣ የነገሩትን የማይረሳ እርሀ ሩህ አባት እግዚአብሔር የጽኑ ኃዘናቸውን ወራት አሳልፎ ልዕ ልት ወይዘሮ ተናኘ ወርቅን ከተወለዱ በ፲፬ ዓመት ከ፪ ወር ከ፱ ቀን በወሊድ ምበንያት ወላዶች በሆኑ ሴቶች ላይ የሚሆነውን የምጥ ፃዕርና ጭንቀት ሳያሰማ በመጋቢት ፴ ቀን ዓርብ ከቀኑ በ፫ ሰዓት ተኩል ምጥ በጀመራቸው ባ፩ ሰዓት ተኩል በደኅና ለመገላገል አብቅቶ ዕልልታን የተጐናጸፈ ሙሉ ደስታን ስለ አሳያቸው ልዑል እግዚአብሔርን በብዙ ልናመሰግነው ይገባናል።

መዝሙር ። ፻፳፰ ቍጥር ፫ ሁሉን የሚችል አምላክ ልበ አምላክ በተባለ በነቢዩ በዳዊት አፍ ፤ ሚስትህ እንደ ፍሬያም የወይራ አረግ በቤትህ አጠገብ ፤ ልጆችህም እንደ ወይራ መን ትዮች በማዕድህ ዙሪያ ይሆናሉ ብሎ ወዳጆቹ ለሆኑ ሰዎች አዘጋጅቶ ያናገረውን የተስፋ ቃል ፡ ባለሙሉ ዕድል በሆኑ ልዕልት ወይዘሮ መነን ጀምሮ ፤ ደግሞ በተባረኩት ልዕልት ወይዘሮ ተናኘ ወርቅ የልጅ ልጆችህንም ታያለህ የሚለውን የደስታ ፍጻሜ ለማየት ስላበቃቸው የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንንን በተለየ የበለጠ ደስታ ለርስዎ ይገባል እያልን ለልዕልት ወይዘሮ መነንና ለልዕልት ወይዘሮ ተናኘ ወርቅ ለክቡር ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠውም እንኳ ደስ ያላችሁ ከማለት ጋራ የሽማግሎች አክሊል የልጅ ልጆች ናቸው ፤ የልጆችም ትምክሕት አባቶቻቸው ናቸው የሚ ለውን ቃል በማሳሰብ ደስታችንን እንገልጻለን ።

ያገር ውስጥ ወሬ።

በብረት መንገድ ስለ ሆነ አደጋ ።

ሚያዝያ ፬ቀን ከአዋሽ የተነሣው የፖስታ ባቡር ፬፻፶፰ ኪሎ ሜትር አቃቂ ጣቢያ ላይ ሲደርስ እንደ ተለመደው አርፎ ነበርና ለመሔድ የመነሣቱን ምልክት ባስጮኸ ጊዜያት ከወ ረዱት ሰዎች አንዱ እንደ ደንቡ በቶሎ ሳይወጣ ዘግይቶ ባቡሩ መሔድ ከጀመረ በኋላ እወጣለሁ ብሎ ሲንጠላጠል የባቡሩ ኃይል ጥሎት በሚያሳዝን መከራ ወድቆ ሞተ ።

ለወደ ፊት ፤ በባቡር ለሚሳፈሩ መንገደኞች ሁሉ እንደ ዚህ ያለ አደጋ እንዳያገኛቸው የተጻፈው ደንብ በመላው እጋ ሪው ላይ ይገኛልና ያንን እየ ተመለከቱ እንዲጠነቀቁ ብርሃንና ሰላም በብርቱ ትጋት ያስታውሳል ።

በቴሌግራም የመጣ የውጪ አገር ወሬ ።

ሮማ ፤የ፲፱፻፬ ዓመተምሕረት ክፍል የ፳ ዓመት ዕድሜ ወታደር ክተት በተባለ ጊዚ የጦር ሚኒሥትር ስለመሆኑ ያህል ፤ ሙሶ ሊኒ ወደ ሠራዊት አለቆች ሁሉ ወረቀትን ጽፎ በደስታና በሰ ላም እየተቀበሏችሁ በነዚህ ቅርብ ጊዜዎች አዲስ ወታደሮችን አቁሙ ብሎ አዝዞዋቸዋል ።

ማስታወቂያ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰ ንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው ፣	፲፪ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፫ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር ።	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነርትጓሜው	፯ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙእጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትጓሜው ፣	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትጓሜው ።	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት ፣	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው ።	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ፡	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን ።	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ ።	አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ ።	አላድ
ያማሪኛ ፊደል ፡	ሩብ
አሳብና ምኞት ፡	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት ።	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር ።	፪መ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ፡	፩ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ።	፩ሩብ

OMEGA



እጅግ ጥሩነቱ የተመሰከረለት ኦሜጋ ዐቢ የሚ ባል ባላንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ተኩል ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፰ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፹ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፩ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፪ ብር ።
:: ባለፈረስ	::	፻፴፪ ብር ።
:: ባለ ድመት ።		፻፳፮ ብር ።
:: ባለአህያ	::	፻፳፮ ብር ።
:: ባለሳቢ ግመል	::	፻፳፮ ብር ።
:: ባለአንበሳ	::	፻፵፩ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፩ ብር ተኩል።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፬ መ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ
በአንድ ብር	፱ ሊሬ እስከ ፰ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፴ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር ።

ሩግቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል ።

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሸቱ ፡ ለስዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና ከሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሄስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነቱ፡ ቢስኪሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።



ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ አቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሜኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ፡፡

AMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኤዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርበም ነጠላም ሸቶና ሎሲዮን ኦዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የኦዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተከሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፲፮
5 me ANNÉE № 16

ሐሙስ ሚያዝያ ፲፫ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 21 AVRIL 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር
ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Diréсteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ትምሕርት ማስታወሻ ።

በቀድሞ ዘመን በጐንደር መንግሥት የነበሩ ሊቃውንት የመጻሕፍትን ጉባዔያት ትርጓሜ ሲያስተምሩ አራት ክፍል አድርገውታል ። አራት ወገንም የተከፈሉ እሊህ ናቸው ። የብሉያት መጻሕፍት ፥ የሐዲሳት መጻሕፍት ፥ የሊቃውንት መጻሕፍት ፥ መጽሐፈ መነከሳት ናቸው ። እሊህንም በዝርዝር የተጻፉትን አራቱን ጉባዔያት መጻሕፍት አንድ ሰው የተማረ ቢሆን አራቱን ሁሉ አንድነት አድርጎ ለማስተማር አይፈቀድለትም ነበር ይባላል ። ጠያቂ ስለምን ምክንያት ቢል እንደ ዛሬ ዘመን የመጻሕፍትን ትርጓሜ አይጽፉትም ነበርና ትምርቱ ከቃል ወደ ቃል ስለሆነ ከቃሉ ብዛት ከትርጓሜው ስፋት የተነሣ ሥልቱ እንዳይለወጥ ብለው ነው እየተባለ ይነገራል ። ነገር ግን ከላይ ከቈጠርናቸው ከአራቱ ጉባዔያት መጻሕፍት አንደኛውን ክፍል ለማስተማር ይችላል ። ለቤተ ክርስቲያንም አለቅነት የሚሾም ሰው ጉባዔ ያወቀ በመጽሐፍ ምሥጢር የተራቀቀ ነው እንጂ እንዲያው ሳይማር ሳይመራመር በባለሟልነትና በገንዘቡ ኃይል አይሾምም ነበር ይሉናል ። ስለዚህ በአድባራቱ ሁሉ የተሾሙት አለቆች መጽሐፍ የተማሩ ጥበብ የመረመሩ ስለሆኑ ፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ባህል በብዙ ወገን እየተከናወነ እየተሻሻለም ተሠርቷል ። ይህም በዜማ መጻሕፍት በቅዳሴ በዝማሬ ፥ በመዋሥዕት ፤ በድጓ ፥ በምዕራፍ ይገኛል ። ዝማሜ ፥ መረግድ ጽፋት አደራረስ ሁሉ የወጣና የተጀመረ ያን ጊዜ ነው ይባላል ። ሊቃውንቱም በእንደዚህ ያለ ትጋት ሲኖሩ በአፄ ቴዎድሮስ ጊዜ የጐንደር ከተማ ሲቃጠል አብያተ ክርስቲያናት አብረው ተቃጥለዋል ። በዚህ ምክንያት ሊቃውንት ተሰደዋል የመጻሕፍትም ጉባዔ ትርጓሜ እያነሰ ሄዷል ፥ አቡሻክር የሚባለው የቍጥር መጽሐፍ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ትርጓሜው እንደጠፋ ቀርቷል ። ይህም አቡሻክር የሚባለው መጽሐፍ ዋና የሒሳብ ትምርት ነው ። በረቂቅ ተጽፎ ከአሪት ዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ወንጌል ያለውን መጽሐፍ ቅዱስ ያህላል ይላሉ ። እሱም ያን ጊዜ እንደጠፋ ቀርቷል ። ትምርቱም ለአራቱ ጉባዔ አምስተኛ ሆኖ የሚቈጠር ይህ ነበር ። ነገር ግን ንባቡ እያለ ትርጓሜው ነውና በሃገራችን የጠፋው ትርጓሜውን በዓረብ አለ ሲሉ ስለሰማን ፥ ከሃገራችን መርሀ ዕውር መጽሐፍ ከሚያውቁ ሊቃውንት ጋራ የአረብ ልሳን የሚያውቁ ወንድሞቻችን አንድነት እያሰማሙ ትርጓሜውን ያወጡታል ስንል ተስፋ እናደርጋለን ። አሁን ከአረብ ወደ ግዕዝ የተገለበጠው የአቡሻክር ትርጓሜው መጥፋቱ በአውራጃው ሁሉ በደንብ የቆመ የተማሪ ቤት ባለመኖሩ ነው ።

ሁለተኛም ሊቃውንቱ ለዓውደ ዓመት ለዘመን ለበዓላት ለአጽዋማት ማስታወቂያ ባጭር ቃል የወጣ መርሐ ዕውር መጽሐፍ ካለን ብለው ባያስቡበት ይሆናል ። ቢያስቡበትስ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ስንኳን የተጻፈውንና ያልተጻፈውን እንግዳ ድርሰት ያደርሳሉ። ከሁን በፊትም አንድ የጐንደር ሊቅ ድጓና ምዕራፍ በቃሉ ዘሩን ጽፎ በቃሉ ምልክቱን አመልክቶዋል ፤ አሁን ይህን ሁሉ ሐተታ ያመጣሁበት ምክንያት ዋናው ፍሬ ነገሩ ይህ ነው ። በዛሬ ዘመን ያለ ትውልድ በሥጋዊ ጥበብ እየሠለጠነ ስለ ሀገሩ ፍቅር እየተናደደ ሀገሩን መውደዱን ማንም አያጣውም ። በመንፈሳዊ በኩል ግን ዕገሌ ካህን አሕዛብ አገር ሂዶ አስተማረ ። ዕገሌ አለቃ ደቀ መዛሙርት አሳደረ ባለመባሉ የሃገራችንን ሊቃውንት ቅር ሳያሰኛቸው አይቀርም ። አስተማሪና ተማሪ በጉባዔ አለመገኘታቸው ለሕዝቡ በጣም ያሳዝናል ። ነቢዩ እንባቆም ተኀጕሉ አባግዕ እመብልዕ ወአልህምትኒ ኢይትረከቡ ውስተ ጎል ያለውን እናስብ ። ለሺ ፍልጥ ፥ ማሠሪያው ልጥ ፤ እንደሚሉ የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነውና በየአውራጃው ሁሉ የመንፈሳዊ ተማሪ ቤት ማቆም ያስ

ፈልገናል፤የተማሪ ቤት ለማቆምና ለመምሕራኑ ደሞዝና ቀለብ ችግር እንዳይሆን ማለስታወሻ ያልኩትን በብርሃን እገልጸዋለሁ በሰላምም እናገረዋለሁ ። በኢትዮጵያ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ቁጥራቸው ሰባ ሺ ሳይሆን አይቀርም ። በቁጥራቸው ልክ ቢመት በመቱ በአንድ በአንድ መቅደስ የገጸ በረከት ግብር ሁለት ሁለት ብር የሚያወጣ አውራጃ አለ፤አንዳንድ ብር የሚያወጣም አለ ። አላድ አላድም የሚያወጣ አለ ፣ ከዳኝነት ከውርርድ ፣ ከመቀጮ ከአዳፋኝ፣ ገንዘብ ጋራ ይህ ውጤታ ቢያንስ ቢያንስ ከሁለት መቶ ሺ ብር አያንስም በሚወጣበት ጊዜ በታመነ ሰው እየተሰበሰበ የመንግሥት ፈቃዱ ሆኖ ለተማሪ ቤት ማቆሚያ ቢሰጥ ለመንፈሳዊ ተማሪ ቤት ለሥራዊና ለአገልግሎቷ ለሊቃውንቶቿና ለደቀ መዛሙርቷ እንዲበቃ ያለጥርጥር እርግጥ ነው ፣ አሁን በዙሪያችን ያሉ አሕዛብ መንግሥታቸውን ሳያውቁ ይኖራሉ።ይህ መሆኑ ባይማሩ ነውና በኢትዮጵያ ግዛት አውራጃ ሁሉ የተማሪ ቤት የቆመ እንደሆነ እምልኮተ እግዚአብሔር እየሰፋ አምልኮተ ባዕድ እየጠፋ ይሄዳል፡፡የመንግሥታችን ኃይል ይበረታል።ትግሁ እንከ አኃውየ ጸልዩ ወሰአሉ ክመ ኢትበኡ ውስተ መንሱት እስመ መንፈስ ይፈቅድ ወሥጋ ይደክም ።

ሁለተኛው ማስታወሻ በሚመጣው እንዲታተም ተስፋ አደርጋለሁ ፣ በቀለ አበዩ ።

የ፫፻፺ ገጽ ተከታይ ።

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

እንባቢው ይህነኑ በጣም እንዲረዳው በአገራችንም ቢሆን የሀብታምና የድሀን ኑሮ ይመልከት ፤ እንድ ራስ ወይም ደጃዝማች አንዳች ነገር መግዛት ሲፈልግ በብዙ ብር እንጂ እንደ ድሀው በአላድ በሩብ በተሙን አይገዙም ፤ በሌሎች ሕዝቦችም ትዳር እንደዚሁ ነው ሀብታም የሆነ ሕዝብ የሚፈልገው የለውጥ መሣሪያ ትልቅ ነገር ነው ። ደሀ በሆነው ሕዝብ አገር ግን ትንሹ የለውጥ መሣሪያ ይፈልጋል ። ከእንደዚህ ያለው ምክንያት የተነሣ ይኸው ባገራችን እንደምናየው ሕዝቡ ከሙሉ ብር ይልቅ አላድ ሩብ ተሙን ስለአስፈለገው በገበያም በብዙ ስለተወደደና ስለ አስፈለገ የማያበቃም ስለሆነ ብሩን ሲሸርፍ ከሚገባው ዋጋ በላይ ይሰጥበታል፡ተሙንና እሩብ አላድ ስለተወደዱ ግን ለኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ ትልቅ ጉዳት ነው ፣ ስለ ምን ቢሉ ቀጥሎ የተጻፈውን አስተውለን ብናነበው ያስረዳናል ፤ ፊት እንደተናገርነው በአገራችን ያለው አላድ ሩብ ተሙን ወደ አገራችን የሚመጣው በነጋዴዎች በኩል ከውጭ አገር ነውና እንደዚሁ እነዚህ ነጋዶች ይህነን ትኒንሽ የለውጥ መሣሪያ በአገራችን መወደዱን አይተው ለብር ሲለውጡት ከፍ ያለ ዋጋ ይቀበሉበታል ፤ አንድ ነጋዴ በሺ ብር ተሙን ገዝቶ ወደአገራችን ቢያመጣውና ፲፮ ተሙን ለ፩ ብር ቢሸርፈው ፹ሺ ተሙን ያተርፍበታል በብር ቤትም ፸፻፶ ብር ያገኝበታል ፡፡ ማለት እንደ ሥርዓቱና እንደሚዛኑ ፩ ብር ፳ ተሙን መሸረፍ ይገባው ነበር፡ ይኸው ነጋዴም ተሙኑ የገዛው በ፩ ብር ፳ ተሙን ሂሳብ ነበረና የገዛው ስለዚህ ወደ አገራችን አምጥቶ ፩ ብር ለ፲፮ ተሙን ሲሸርፈው በእያንዳንዱ ብር ፬ ተሙን ያተርፍበታል እያንዳንዱ

የኢትዮጵያ ሰውም ፬፬ ተሙን ይገብርለታል የብሩ ትርፍም ወደ ውጭ አገር ይመለሳል፡፡ነጋዴው ብሩን በጥሬው ወደ አገሩ ባይመልሰው ቆዳና ቡን ወይም ሌላ ነገር በአገራችን የሚገኘውን ዕቃ ይገዛበታል ማለት ከውጭ አገር ሌላ ብር ሳያመጣ በሸረፋ ባገኘው ትርፍ የኢትዮጵያን ሕዝብ ድካም ወይም ጉልበት ይገዛበታል ።

ይኸነኑም ነገር አጥብቀን ከተመለከትነው የአገራችን ሕዝብ አላድና ሩብ ተሙን ለሚያወጡላቸው ሰዎች እንደሸርፉ ከፍታና ዝቅታ ከመቶው ብር ፲ና ፳ ብር ይገብርላቸዋል።አላዱና ሩቡ ተሙኑ ሁሉ በአገራችን የሚሠራ ቢሆን ግን ይህ ግብር ለመንግሥታችን በገባለት መንግሥቱም ለሠራተኞቹ በደመወዝ ምክንያት ሲያከፍለው ጥቅሙና ትርፉ አንድ ጊዜ ወደመንግሥት አንድ ጊዜም ወደሕዝቡ እየተመላለሰ ብሩ ከአገራችን ሳይወጣ በሕዝቡ እጅ ይቀር ነበር ጉዳትም ባልሆነበትም ነበር ።

መንግሥትም ሕዝቡን የሚለዋወጥበትን የለውጥ መሣሪያ ሁሉ ምንስ እርሱ ራሱ ቢያትም ፊት እንዳሰብነው ይህን ያሀል የሸረፋ ግብር ሊወስድ አይገባውም ። እንደዚህ ያለው ግን ብር ሊከፍል የሚገባውስ የሚሸርፈው ሰው ብቻ ነው ። መንግሥትም ግብሩን በሕዝቡ ላይ ሲጥል ፍርዱን አላጉዶለም የሚባለው በእያንዳንዱ ገባሩ እንደየሀብቱ መጠን ሲያከፍለው ነበር ። መንግሥት አንድ ብር በ፲፮ ተሙን ይሸረፍ ብሎ ማወጁ ደግሞ ሥራ እንዳልሠራ ይህነን ፊት ግልጽ ሆኖ የተጻፈውን እንቦ ነገሩን ከተረዳው ወዲያ አዋጁን ባለመርጋቱ አይቶ ደስ ሳይለው አይቀርም ። እእምሮ ያላቸው ነገሥታት ገንዘብ አትመው ሲያወጡ ከየሥራቸው ዋጋና ከሕዝቡ ግብር የሚወስዱት ባንድነት ታስበ ቢሆን ያንሳል እንጂ ከመቶ ፭ በላይ አይበልጥም ። እንግዴህ ይህ ከላይ ያነበብነውና ያየነው ብቻ አይደለም ጉዳቱ ማለት ብሩ በ፲፮ ተሙን ይሸረፍ ተብሎ የታወጀ ብቻ አይደለም ሌላ ጉዳት ደግሞ አለበት እንጂ ። ማለት ዛሬ የአዋጁ ቃል የተከሉት የኢትዮጵያ መንግሥት ግምጃ ቤትና የኢትዮጵያ ባንክ ብቻ ናቸው። በገበያው ግን ተሙኑ እንደተፈለገ መጠንና እንደጊዜው መወደድ ሁሉጊዜ ከፍና ዝቅ ይላል ።

እንግዴህ አንዳንድ ጊዜ ጉዳቱ የአገራችን መንግሥት ሠራተኛ ደመወዙን በብር ፈንታ ተሙን ፲፮ሸረፋ ሂሳብ ሲቀበል እንዳንድ ጊዜ በገበያው ሸረፋው ፲፯ና ፲፰ ሆኖ ያገኘዋል ። ሠራተኛው እንደዚህ ሆኖ ሲያገኘው ደመወዙን የሚቀበል ከመንግሥት ሲሆን ከሌላው ሰው ሁሉ በተለየ ከደመወዝ ከመቶ ፭ና ከመቶ ፲፩መገበሩ ነው ። ስለዚህ ከዚህ በላይ የተጻፈውን ነገርና ምክንያት ሁሉ እንዳየነውና እንዳስተዋልነው የኢትዮጵያ መንግሥት ሕዝቡ በሸረፋ እንዳይጎዳበት በመላው ሥልጣኑ ሊጥርበት ይገባዋል ። ይህነኑም ለመጣር ፈቃዱ ከሆነም አስቀድሞ ቀጥሎ የተጻፈውን ሰስት ነገር ያስፈልገዋል ።

መጀመርያ ሕዝቡ የሚገበያይበትን ትንንሹ የለውጥ መሣሪያ ሁሉ እያንዳንዱ ሕዝቡ የሚፈልገው ስንት እንደሆነ እየተመረመረ እንደሚበቃ ሆኖ ቢታተም መልካም ነው ። እያንዳንዱም ትንሹ የለውጥ መሣሪያ በብር ስንት እንዲሸረፍ መንግሥት ባለቤቱ ደንብ ለይቶ ሸረፋው ከፍና ዝቅ እንዳይል ቢጠብቅ መልካም ነው ።

ሁለተኛ ። ከመንግሥት በቀር ማንም ሰው አላድና ሩብ ተሙን በሂሳቡ እያሳተመ ከውጭ አገር እንዳያስመጣ ቢከለክል መልካም ነው ። የኢትዮጵያ መንግሥት ያቆመውን የብር ማተሚያ ወይም ፋብሪካ በየዓመቱ ለአገሩ ሕዝብ የሚበቃ ትንንሽ የለውጥ መሣሪያ ለማተም የማይቻለው እንደሆን ሲሆን ፋብሪካውን ያስፋው ያለዚያ ግን ለአገሩ ሕዝብ የሚበቃውን ያህልአላድና ሩብ ተሙን መንግሥት እራሱ እየተዋዋለ ከውጭ አገር የብር ማተምያ ፋብሪኮች እያሳተመ ቢያስመጣ መልካም ነው

ሶስተኛ ። በአንድ የመንግሥት አገር ሸረፋው ከፍና ዝቅ እንዳይል ዋናው ነገር ሕዝቡን በቶሎ እንዲገናኝ በሁሉ አገር ደህና ደህና መንገድ ማሰበጀት ነው ። ደህና መንገድ በሌለበት አገር ውስጥ ግን እያንዳንዱ ሰው የፈለገውን ነገር በቶሎ እንዳይገበያይበት የመንገዱ ጉርፍ እየከለከለው በእጁ ያገኘውን ሩብ ተሙን ብዙ ጊዜ ሥራ ፈቶ በእጁ ይቀመጣል የሚበዛው ትንንሹ የለውጥ መሣሪያ እንደዚሁ በያለበት ሥራ ሲፈታ መንግሥት ያወጀው አዋጅ ምንስ ቢጠበቅ የገበያው ሸረፋ ከፍና ዝቅ ማለቱ አይቀርም ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት መጽሐፍ ነው።

ስለ ሥልጣኔ ደረጃ መዓርግ ።

ለአንድ ሕዝብ ሥልጣኔ ብዙ ማለፊያ የከበረ የብዙ ዓመቶች የትእልፌተ እእላፋት ሕዝቦች ሥራ ነው ሕዝቦች ሁሉ በሥራና በትጋት ሊያኖሩትና ሊያሳድጉት መሬት የምትሰጠውን ሀብት ሁሉ በትምርት ማፍራቱን ሊያውቁበት በአእምሮና በበጐነት በሕይወታቸው ሁሉ ሊያሳድጉት ይገባቸዋል ።

የዓለም ሕዝቦች ሁሉ በማለፊያ ሊኖሩ ይወዳሉ ፤ ግን ይህ አኑዋዋር ሕዝቦች ሁሉ እንደምን እንደሆን አላወቁበትም ። አንድ አንድ ሕዝቦች ዛሬም እርሻ የማያውቁ አሉ ። በአደንና በአሣ ወጥመድ ፥ በዛፍ ፍሬ እየተመገቡ ቆዳ ለብሰው በመጥፎ የሳር ቤት ይኖራሉ ። አገራቸው ፍርያም ብዙ ውሆችና ምኔራል የብረት ዓይነት ሁሉ ያለበት ሳለ እንኳ ከዚህ ሁሉ ሀብት ስለ አላወቁበት እጅግ በሚያስደነግጥ ችግር ይኖራሉ ።

አንድ አንድ ሕዝቦች ግን በአገራቸው እንኳ ያልታደሉ ቢሆኑ በእውቀታቸውና በመሥራታቸው ተከባክበው እጅግ የተመቸ ኑሮ ይኖራሉ ፥ ከብቶችን ተጠንቅቀው እያረቡ ጠንክረው እያረሱ ማለፊያዎች አዳራሾችና መንገዶች እየሠሩ መሬት እየሰነጠቁ ምኔራል እያወጡ በሺ መዓዝን ጥቅማቸውን እያሰፉ ይኖራሉ ፥ ስለዚህ አንዳንድ ሕዝቦች መጨረሻው ደረጃ መዓርግ ደርሰዋል እስከማለት ይደፈራል ። አንዳንድ ሕዝቦች ግን በፊት በነበረው በኋለኛው መዓርግ ቁመዋል ።

እንደ ታሪኩ በየሰው የመሻሻልን የሥልጣኔ ደረጃ መዓርግ በአራት ይከፈላል ፥ የስልበጅ አሬሜኔ ኑሮ ፥ የዘላን እረኛ ኑሮ ፥ የገበሬ ኑሮ ፤ የኢንዱስትሪ ኑሮ ፤ ኢንዱስትሪ ማለት የሰው የሥፍራው ፍሬ ከፍጥረቱ ለውጦ ያቆመው ነው ። ለምሳሌ ከመሬት ውስጥ ሚኔራል ማውጣት ከእጸዋትና ጠጉር ልብስ ማድረግ ፤ ከፍጥረት ሁሉ መድኃኒት ማቃመም ፤ ከዚያ ወዲያ በመኪና እየሠሩ የሚያስፈልገውን በንግድ የተባለ መሣሪያ እየተለዋወጡ መኖር ነው ።

፩ኛ ደረጃ መዓርግ

የአረመኔ ኑሮ ከሥጋ ዘመዶቻቸው በተቀር እምነት የሌባቸውምና ከዓለም ሕዝብ ማሕበር ተለያይተው ፤ በዱር መኻከል በመጥፎ ቤት ይኖራሉ ። መሬቲቱ የምትሰጠው ማፍራቱን አያውቁትምና ፤ በአደን በዓሳ መጥመድ ወይም መሬቲቱ በምትሰጣቸው የዛፍ ፍሬ ይኖራሉ ። እኒህ የሚገኙበት አገር የሚበልጠው ፤ በበረዶው የማይቀልጥ አገርና ሙቀት በሚበዛበት አገር ነው ። እኒያ በሙቀት አገር ያሉ ሳይሠሩም አለችግር የእለት ምግብ ያገኛሉ ። እኒያ በበረዶም አገር የሚኖሩ ግን ለዕለት ምግባቸው እንኳ ይቸገራሉ ። እንግዲያስ የማይሠራ የሆነ ሕዝብ ሁሉ ሰልበጅ (ያልሠለጠነ) መሆኑን በዚሁ ምሳሌ አሳምሮ ያስረዳል ።

፪ኛ ደረጃ መዓርግ ።

የዘላኖች ኑሮ መጀመሪያ የሥልጣኔን ደረጃ መዓርግ ያመለክታል ። ዘላኖች ሕዝቦች ከየነገዳቸው ማሕበርተኝነት ገብተዋል ። እንስሶችን ማርባትና ማብዛት ተምረዋል ። ሥጋቸውንና ወተታቸውን እየተመገቡ ቈዳቸውንም ልብስና ድንኳን ማድረግ ይችላሉ ። ለእንስሶቻቸው መሠማሪያ ወደሚመች ሥፍራ መጓዝ ያውቃሉ ።

፫ኛ ደረጃ መዓርግ ።

ከዘላኖች በኋላ የገበሬነት ኑሮ ይከተላል ። ዛሬ የሚበልጡ የዓለም ሕዝቦች ከከብት ማርባት በላይ በእርሻ ይኖራሉ ። ግን እኒህ ገበሬዎች ሕዝቦች እንደ እየዕውቀታቸው ከፍና ዝቅ ያለ ብዙ ልዩነት ደረጃ አላቸው ። እኒያ ዝቅ ያሉ በቀላል መሣሪያ በብዙ ድካም ፍሬ ፃማቸውን ያገኛሉ ። እኒያ ከፍ ያሉ ግን የተሻለ መሣሪያ (መኪና) አበጅተው በትንሽ ድካምና በፍጥነት እርሻቸውን ያሰፋሉ ። ድንገት ለሚመጣባቸው አደጋ እንዲተጋገዙም ቤቶቻቸውን አቃርበው ሠርተው ይኖራሉ ። ስለዚህ ከሕዝብ ይልቅ ማኅበርተኝነታቸው እየተሻሻለ ይሄዳል ። ግን የሚያርሱት መሬት እንዳይርቅባቸው ትልቅ አገር (ከተማ) ሊያደርጉት አይችሉም ።

፬ኛ ደረጃ መዓርግ ።

ኢንዱስትሪ መጨረሻ ደረጃ ፤ ከሁሉ የበለጠ መዓርግ ሰው የደረሰበት የፍጥረት አፈራር መቻል ማለት የፍጥረት ገዢ መሆንን ያመለክታል ። ከዚህ ደረጃ መዓርግ የደረሱ ሕዝቦች በተሰናዳ መሣሪያ (መኪና) ቢያርሱ እንኳ ይበቃናል ብለው ደስ አላላቸውም ። የሚበልጥ ጥረታቸው ግን ከመሬት ውሥጥ እየቈፈሩ ብዙ የሚጠቅሙ ሚኔራል ማፍራት (ማውጣት) ነው ። በዘላንነትና ገበሬነት ላይ ኢንዱስትሪ የተጨመረበት እንደ ሆነ ከተሞች እያደጉ (እየበዙ) ይሄዳሉ ። በዓለም ሁሉ ብንመለከት ለኢንዱስትሪ እንዲመቻቸው ሲሉ ከተሞች የሚተከሉበትና እየሰፉ የሚሄዱበትም በባሕር ዳርና እንደ ጣና በወንዝ አጠገብ ነው እንጂ በፍሬያም አገርና ሚኔራል በሚወጣበት አገር አይደለም ። ስለዚህ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ በዚሁ ስፍራ እየተሰበሰቡ ትልልቆች ከተሞች እየሰሩ ይህነንም የኢንዱስትሪ

ሥራ በጣም ሊያሰሩ ይወዳሉ ። ይህ ኑሮ የሥልጣኔ መጨረሻ ደረጃ የሥልጣኔ አኑዋኑር ይባላል ። የኢንዱስትሪ ኑሮ ከሁሉ የበለጠች ከሆነች እኒያ በኋላ ቆመው የቀሩ ሕዝቦች ሊደር ሱብትና በትጋት ሊጣጣሩ ያስፈልጋቸዋል ይገባቸዋል ።

ግን ይህች ዓለም እንደ የያዘችው መሬት እንደ ስፋቷና እን ደሚኖሩባት ሕዝቦች ብዛት ልክ ብንመለከታት መሬቲቱ እንደ ሚገባት ያፈራች በጣም ትንሽና ጠባብ ነች ። ትንሽ ሳላች ደግሞ በጣም ትልቅ (ሰፊ ነች) ። እንዲሁም ከዚህ ኢንዱስ ትሪ የደረሱ ሰዎች እጅግ ጥቂቶች ናቸው ። ጥቂቶች ሁነው ደግሞ እጅግ ብዙዎች ናቸው ።

መሬቲቱ ትንሽ ሳለች ትልቅ ፥ ሕዝቦቹ ጥቂቶች ሳሉ ብዙ ዎች ያልኩበትን ምክንያት አንባቢው እንደምን ቢለኝ በዚሁ ስታቲስቲ ወይም ግብጦ ሊረዳው ይችላል ።

መሬቲቱ እንደሚገባት ያፈራች ትንሽ ነች ያልኩበት ፥ መሬቲቱ በሞላኝ ማለት ወኃ ከተሸፈነ ጋራ ስፋቷ ፭፻፲ ሚ ሊዮን ኪሎ ሜትር ካሬ ነች ። (ኪሎ ሜትር ካሬ ማለት በዓ ራት መአዘኑ ሺ ሺ ሜትር ወይም ፪ሺ ፪ሺ ክንድ ነው ።) ከዚሁ እስያ ፵፬ ሚሊዮን ኪ. ሜ ካ ፥ አሜሪካ ፵፫ ሚሊዮን ኪ. ሜ ካ ፥ አፍሪቃ ፴ ሚሊዮን ኪ. ሜ ካ ፥ ኤውሮፓ ፲ ሚ ሊዮን ፰፻፶ሺ ኪ. ሜ ካ ፥ አቴያንያ ፰ሚሊዮን ፱፻፶ሺ ኪ. ሚ ካ ፥ በዓለም ሁሉ ተዘርተው ያሉ ደሴቶች ፲፯ሚሊዮን ፪፻ሺ ኪ. ሜ ካ ፥ ድምሩ ፻፵፱ሚሊዮን ኪሎ ሜትር ካሬ ደረቅ መ ሬት ፥ ፫፻፷፩ሚሊዮን ኪሎ ሜትር ካሬ በባሕር የተሸፈነ መ ሬት መሆኑ ነው ።

ከዚች ፻፵፱ሚሊዮን ኪ. ሜ ካ ደረቅ መሬት እንደሚገ ባት ያፈራች ፥ ኤውሮፓ የምትባል ስፋቷ ፲ሚሊዮን ፰፻፶ሺ ኪ. ሜ ካ ፥ ከአሜሪካ ስታቲ ኡኒቲ (የአንድነት መንግሥታት) የምትባል ስፋቷ ፱ሚሊዮን ፫፻፸ሺ ኪ. ሜ ካ ፥ ከእስያ ጃፖን የምትባል አገር ስፋቷ ፮፻፹፪ሺ ኪ. ሜ ካ ፥ ድምሩ ፲፱ሚሊዮ ን ፱፻፪ሺ ኪ. ሜ ካ ፥ በተቀር ሌላው የቀረው ፻፳፱ሚሊዮን ፺፰ሺ ኪ. ሜ ካ እንደሚገባት አላፈራችም ።

ትልቅ ነች ያልኩበትም ከዚች የሚገኝ ፍሬ የጥቅም ሃ ብት ለሞላ ዓለም አልፎ ተርፏል ።

ኢንዱስትሪ የደረሱ ሰዎች ጥቂቶች ናቸው ያልኩበት ደግሞ በዓለም ያሉ ሰዎች በእስያ ፲፻ሚሊዮን ፥ በአውሮፓ ፬፻ ፸፫ሚሊዮን ፥ በአሜሪካ ፪፻፲፫ሚሊዮን ፥ በአፍሪካ ፻፴፱ሚሊዮ ን ፥ በአውስትራልያ (ኦችያንያ) ፱ሚሊዮን ፥ ድምራቸው ሺ፮፻ ፴፮ ሚሊዮን (ወይም ፩ምሊያርድ ፮፻፴፮ሚሊዮን ይሆናሉ ።

ከነዚህ ፬፻፸፫ሚሊዮን ኤውሮፖች ፥ ፻፳ሚሊዮን የኤው ሮፓ ዘሮች (ስታት ኡኒቲ) አሚሪካኖች ፥ ከእስያ ፹ሚሊዮ ጃፖኖች ፥ ድምራቸው ፮፻፸፫ሚሊዮን በተቀር ፥ ሌሎች የቀሩ ሺ፶፮ሚሊዮን (ወይም ፩ ሚሊያርድ ፶፮ ሚሊዮን)ሰዎች ገና አ ልደረሱባትም ።

ጥቂቶች ሳሉ ብዙዎች ያልኩበትን ምክንያት እኒህ ኢን ዱስትሪ የደረሱ ሰዎች በእውቀታቸው የዓለም ጌቶች ሁነው ያልገቡበት ሥራና የማይገኙበት ሥፍራ በማናቸውም ነገር ያ ልገዙት ፍጥረት አይገኝም ። አንድ ሁለት መንግሥታት ብቻ ባገባ ለአንባቢው ሳያስረዳው አይቀርም ስል እታመና ለሁ ።

አላንድ የምትባል መንግሥት ስፋቷ ፴፩ሺ፱፻፹፫ ኪሎ ሜትር ካሬ ሕዝብዋ ፰ሚሊዮን አገር በዓለም ካርታ ጅዖግራፊ አንጻር ስታያት እንደ አንድ ነጥብ ሁና ለማየትዋ እንኳ ታሽ ግራለች ። ከውጭ አገር ያለ ኰሎኒያዋ (ማለት በአሜሪካ ያለ በተቀር) የአላንድ ህንዶች የሚባሉ ደሴቶች ብቻ የመሬቱ ስፋት ፩ሚሊዮን ፰፻፷ሺ ኪሎ ሜትር ካሬ የሕዝቡ ብዛት ፷፩ ሚሊዮን ይሆናሉ ።

እንዲሁም እንግሊዝ የምትባል ደሴት አገር ፥ ስፋትዋ ፫፻፲፰ሽ ኪሎ ሜትር ካሬ የሕዝብዋ ብዛት ፵፯ሚሊዮን ፥ በዓለም ካርታ ጆዖግራፊ አንጻር ስታያት ከአንድ ነጥብ ምን ያህልም አትበልጥም ግን በኤኮኖምያና ፖለቲክ ዓለም በሞላ ትገዛዋለች እስከማለት ይደፈራል ። ኰሎኒያዋ (የቅኝ አገር) ብቻ የመሬቱ ስፋት ፴፩ሚሊዮን ኪሎ ሜትር ካሬ ፥ የሕዝቡ ብዛት ፬፻ሚሊዮን (ሩብ ዓለም) ይሆናል ።

አንባቢው ሊከራከር ከፈለገ ግን በዓለም ሁሉ ቢዘሩና ቢገዙም ጥቂቶች ሳሉ ብዝዎች ናቸው ያለውን የሚበቃ ማስረጃ አልሰጠም ሊል ይችላል ። ጥቂት ምሳሌ ብጨምረው ደግሞ አይከፋም ።

ህንድ የምትባል ከነዚያ መጀመርያዎች የሚቆጠሩ ፍርያም ሃብታም ወርቃማ የሆነች አገር ፥ ስፋትዋ ፬ሚሊዮን ፰፻ሽ ኪሎ ሜትር ካሬ ፥ የህዝብዋ ብዛት ፫፻፴፫ሚሊዮን (የዓለም አምስተኛ እጅ እዚያ ያሉ የሚገዙዋት ኢንዱስትሪ መዓርግ የደረሱ ሰዎች ምናልባት ከ፪፻ሽ (እንግሊዞች) አይበልጡም ይባላል። በዚሁ ሒሳብ ብንሔደው አንድ እንግሊዝ ስለ ሽ፮፻፹፰ ህንዶች መሆኑ (መቈጠሩ) ነው ።

ሁለተኛ ዘርያ ምሳሌ ደግሞ ፥ ያነን ከሁሉ ከፍ ያለ ደረጃ መዓረግ ደርሰዋል ተብሎ የሚጠራ ጀርመን የሚባል መንግ ሥት ፥ ከነዚያ ኢንዱስትሪ የደረሱ ጓደኞቹ በነጻጽረው ፥ አንድ ጀርመን ስለ ሁለት ሰዎች ተኩል ማለት ፪ጀርመኖች ስለ ፭ሰዎች ሊቈጠሩ ይችላሉ ። አንባቢው እንደምን ቢለኝ በዚሁ ስታቲስቲ ሳይረዳው አይቀርም ስል ተስፋ አደርጋለሁ ።

ዓለም ከተፈጠረ እስከ ዛሬ ድረስ በታሪክ ተሰምቶ የማይ ታወቅ ከ፳ዓመት በፊት ዓራት ዓመት (ሽ፱፻፲፬ ሽ፱፻፲፰ ዓ ም በኤውሮጳፖ ቊጥር) የነበረ ጦርነት ፥ ፸ሚሊዮን የሚያህል ፷፱ ሚሊዮን ፰፻፹፪ሺ ፬፻፹፫) አርበኞች ተጋጥመው ነበር ።

የጀርመን ወታደሮች ፲፫ ሚሊዮን ፪፻፶ሺ የሱ አጋዥ አውስትርያ ፱ሚሊዮን ወታደሮች ድምራቸው ፳፪ ሚሊዮን ፪፻፶ሺ ወታደሮች ባለጋሮቻቸው የመስኰብ ወታደሮች ፲፫ ሚሊዮን ፸ሺ የፈረንሳዊ ወታደሮች ፯ሚሊዮን ፱፻፴፫ሺ የእን ግሊዝ ወታደሮች ፳ሚሊዮን ፯፻፩ሺ የኢጣልያ ወታደሮች ፫ ሚ ሊዮን ፯፻፲፫ሺ የስታቲ ኡኒቲ ወታደሮች ፬ ሚሊዮን ፪፻፸፪ሺ ወታደሮች የቀሩ የሌሎች ነገሥታት ወታደሮች ደግሞ ማለት እንደነባ ልጅክና ጀፖን የመሰሉ ሁሉ ፱ሚሊዮን ፴፯ሺ ፬፻፹፫ ድምራቸው ፵፯ ሚሊዮን ፯፻፴፪ሺ ፬፻፹፫ ጋራ ተጋጠሙ ።

ከነዚህ የጀርመን ወታደሮች ፪ ሚሊዮን የሞቱት ፥ አካላ ቸው የጎደለ ፫ ሚሊዮን ፫፻፴፯ሺ ሲጠፋበት ፥ ያጠፋው ሃብት

ሁሉ (ማለት) መርከቦችና ከተሞች የታናናሾች መንግሥታት ወታደሮች የገደለባቸው ልክ በተርታ ለመጻፍ በጋዜጣ ይቅር ብመጻፍ ለመጻፍ እንኳ ረጅም ነውና፤ የ፫ የሚሆኑ ዋኖች ትልልቆች ጠላቶቹ የገደለባቸውና አካላቸውን ያጎደለባቸው ወታደሮች፤ የመስኮብ የሞቱት ፩ ሚሊዮን ፯፻ሺ፤ አካላቸው የጎደለ ፯፻፸፫ሺ ። የፈረንሳዊ ወታደሮች የሞቱት ፩ ሚሊዮን ፬፻ሺ፤ አካላቸው የጎደለ ፩ ሚሊዮን ፫፻ሺ ። የኢጣሊያ ወታደሮች የሞቱት ፯፻፶ሺ፤ አካላቸው የጎደለ ፯፻ሺ ። የእንግሊዝ ወታደሮች የሞቱት ፯፻፵፬ሺ አካላቸው የጎደለ ፱፻ሺ ። የስታቲኡኒቲ ወታደሮች የሞቱት ፷፰ሺ፡፡ አካላቸው የጎደለ ፻፶፯ሺ ። ሁሉም የሞቱት ድምራቸው ፬ ሚሊዮን ፮፻፷፪ሺ፤ አካላቸው የጎደለ ድምራቸው ፬ሚሊዮን ፻፴፱ሺ መሆኑ ነው ።

በዚሁ ሂሳብ ብንሄደው የጀርመን አንድ ወታደር ሲሞት ሁለት ተእኩል (ማለት) የጀርመን ፎች ወታደሮች ፫ የባላጋሮቻቸው ወታደሮች ገድለው ሞቱ፡፡እንዲሁም አንድ የጀርመን ወታደር አካላቱ ሲጎድል ሁለት ተእኩል ወታደሮች አካላታቸው አጎደለ ያልኩበት ምክንያት ይህ ነው ።

መጨረሻው ግን ጀርመን በጦርነት የማይቻል መሆኑን ከተረዱት ወዲያ ዓለም በሞላ አድማ መትቶ ከውጭ አገር ምግብ እንዳያገባ ከልክለው በራብ ስለአስጨነቁት እርቅ ለመን እንጂ በጦርነትስ ምንም ቢሆን ጀርመን አይሸነፍም ነበር ብለው የዓለም አዋቂዎች ሁሉ መስክረውለታል ።

በዚሁ ሂሳብ አንድ የጀርመን ሰው ስለ ሁለት ተእኩል እንግሊዞች (ማለት ኢንዱስትሪ መዓርግ ደረጃ የደረሱ) ከገመትነው ። እኒያ ለምሳሌ ያገቧቸው ህንዶች አንድ የጀርመን ሰው ስለ ፬ሺ፻፷፪ የህንድ ሰዎች መሆኑ (መቈጠሩ) ነው ።

እረ ምን ምን ብለነው ነው በመብዛት ቢሆንማ ጃፖንና ቺና ፫፻፶ ሚሊዮን ሕዝብ ያለበት ከ፴፪ ዓመት በፊት ሺ፷፻፺፬ ሺ፷፻፺፫ ዓ ም በአውሮፓ ቊጥር ለመስኩብ ፻፹ ሚሊዮን የሚያህል ሕዝብ ያለበትን ከ፷፪ ዓመት በፊት ሺ፱፻፬ ሺ፱፻፫ ዓ ም በኤው ቀ መቸ ያሸነፋቸው ነበረ ።

ክቡር አንባቢ ሆይ እንደሚገባት ያፈራች መሬቲቱ ትንሽ ሳለች ትልቅ በኢንዱ ስትሪ የደረሱ ሰዎች ጥቂቶች ሳሉ ብዙዎች ያልኩበትን ፡ አንተም አጥልቀህ ካሰብከው የሰጠሁህ መንገድ (ፕሮብሊም) ጭምር ሳትረዳው አትቀርም ይመስለኛል፤ እንዲህ በድፍረት መጻፌ ለማንቃቃት ስል ነው እንጂ እውነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ እስከ ዛሬ ድረስ የኢንዱስትሪን ጥቅም ያልተረዳው ሰው የሚገኝ አለ ብዬ አይደለም ። ግን ይፈልገዋል እንጂ ገና አልጀመረውም ። የኢትዮጵያ ልጆች ፈላጎች እንጂ ፈጻሞች አለመሆናችን እጅግ ያሳዝናል ።

የዘመኑ ሰው ሁሉም ያላግጥብናል ። ጀርመን የሚባል ሕዝብ እኮ ከዚህ ዓለም ሰው ሁሉ በእውቀቱ በላይ ሁኖ ያለ በፈጣጠሩ ከእምሳሉ ሰው በልጦ ወይም ልዩ ሁኖ ተፈጥሮ አይደለም ። ያሰባትን ሳይፈጽማት የማይቀር ስለ ሆነ ነው እንጂ እኛ ኢትዮጵያውያን ግን ዋናው አታላያችን ለሁሉ ነገር ቀስ ብለን እንደርሰዋለን በማለት ያህል እየዘነጋን ነው ይመስለኛል ። ያለነበት ሰዓት (ጊዜ) በዚህ ዓለም ካለ ሃብት ሁሉ እጅግ የከበረች እንደሆነች ፡ ከቶ ምንም አልተረዳነውም ። ዕፁብ ግሩም ነው በረጅም ቈይታ መሬቱ መሸብን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ ከሰው ሁሉ ትክክል ተፈጥረህ (ተወልደህ) ከዓለም ሰው ሁሉ በኋላ ድንክ ኍነህ ስትቀር ፡ እንዴት ብሎ እንቅልፍ ይወስድህ? የመልካም አኑአንዋር ይቅርና ፡ ከዓለም ሰው ሁሉ እናናቅህ ብቻ ልብህን በቅንዓት እሳት አያቃጥለውም? እረ ስንት አእላፋት ዓመት ትተኛለህ? ወንዶች ፍጡርን ሁሉ ለማዘዝ ደርሰው በመልካም አኑአኑዋር እየኖሩ ፡ አገራቸውን ጸጥ አድርገው ገዝተው በውጭ አገርም ጥቂቶች ብዙዎችን እየገዙ ምነው ከመኝታህ አትነቃ? ።

ሚከኤል ተሰማ ።

ማጽናኛ ።

በ፫ኛው ዓመት በ፻፵፫ ቁጥር ክቡር ነጋድራስ አፈ ወርቅ በአእምሮ የጻፉትን ቃል አይቼ እጅግ አዘንሁ ፡ አሁን እኮ ይህ ሁሉ ኃዘናቸው ላገራቸው ነው ፡ ሊቀ ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶስ አይበሉ የወንድማቸውንና ያገራቸውን ማዕርግ ለራሳቸውመሆኑን እኮ ስላወቁት ነው፤ ወይ በውቀት ያለ መከራ እንዴት ያሳዝናል። መቸም ሰው ካልተጨነቀ የሰው ያለህ ብሎ አይጮህም፡፡በጮኸም ጊዜ ፈሪ ፈሪው ቤቴን ዝጊልኝ ይላል ። ጐበዝ ጐበዙም መሣሪያውን ነጥቆ ጋሻውን አንግቦ አይዞህ ደርሼልሃለሁ ብሎ ያጽናናል፡፡እኔም በዚያው ልማድ ያለኝን መሳሪያ እርሳሴን ስዬ አይዞህ ደርሼልሃለሁ እያልሁ ትንሽ የርዳታ ቃል እጽፋለሁ ።

እኔ በግብጽ ፫ ወር ተቀምጬ ነበር ቀድሞ አበቶቼ የቤተ ክርስቲያናቸው ስራት እንደኛ ነው የቤተክርስቲያናችንም ስራት ከግብጽ የመጣ ነው እያሉ የሚያወሩልኝን ወሬ ሰምቼ ነበርና ይህኑ ነገር ለመረዳት ስል ሊቀ ጳጳሳት ቄርሎስ ካሉበት ከዋናው ቤተክርስቲያን አልለይም ነበር ።

በየውም እንደ ሰማይና ምድር የተራራቀ ሆነ የሚበልጡትንም አስሩን መለያያዎች በተራ ጽፌአቸዋለሁ ።

መጀመሪያ የጾም ነገር በሕዝቡ አይታወቅም ካህናቱ ብቻ በ፺ቱ አጽዋማት ሥጋና ቅቤ ወተት ሳይቀምሱ ይጾማሉ ። ግን በማናቸውም ጾም ዳቦና ሻይ ሳይቀምሱ ወደቤተክርስቲያን ለጸሎት አይገቡም ።

፪ኛ የኛ ፍትሐ ነገሥት ከቤተ ክርስቲያናቸው አይገባም ፍርድም በፈለጉ ጊዜ በቤተ መንግሥት ያለውን የሮፓን ፍትሐ ነገሥት ፈራጆች አምጥተው ያስፈርዳሉ የዕቡን እልአሳልንስ ፍትሐ ነገሥት እንኳን ሊፈርዱበት ይልቁንስ ሰው እንዳያይባቸው አፍረው ዕቃቤት ዘግተውበታል ይባላል ። እንግዲህ እንደታሰረ አውሬ በኛ ክርክር ጊዜ ይለቁት ይሆን በደህና ጊዜ መዝጋታቸው ጠቅሟቸዋል ።

፫ኛ ከልደትና ከፋሲካ በቀር በአል የላቸውም ።የሚያዝያ ማርቆስ ለት እንኳ ያከብሩታል ብዬ ወደ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ብሄድ ሳቁብኝ ።

፬ኛ ። በማናቸውም ጾም ቢሆን ቅዳሴአቸው ከ፪ ሰዓት አያልፍም ። ጾም አለመኖሩ በዚህ ይታወቃል ።

፭ኛ ፤ በጋብቻቸው ጊዜ የሚያደርጉትን ለመጻፍ ስላፈርሁ ለሚጠይቁን ሰዎች በቃል እነግራቸዋለሁ ። ትልቅ የጅ ጥበብ አለበት ።

፮ኛ ፤ ነጋድራስ አፈወርቅ እንዳሉት ትምባሆ አይለያቸውም

፯ኛ ፣ ላገራቸው እንጂ ለኛ ምንም አያስቡልንም ። ይህም ሊታወቅ በየ ቤተ ክርስቲያናቸው አጠገብ የእንግሊዝና የፈረንሳዊ ቋንቋ ተማሪ ቤት አሰርተው እያስተማሩ በመት በመት ብዙ ልጆች እየተመረጡ ወደ ዮንበርሲቲ ያልፋሉ ።

ሱዳንን እንኳ ከኛ አብልጠው ስለወደዱዋት ታላቅ የተማሪ ቤት አሰርተው የእንግሊዝና የፈረንሳዊ ቋንቋ ያስተምራሉ አሉ ። የሱዳንንም ጳጳስ ለተማሪ ቤቱ እርዳታ ገንዘብ ሲለምን ወደ ካይሮ መጥቶ አየሁት ።

ልኛማ እንኳንስ በገንዘባቸው ለልጆቻችን መማሪያ ብለው የተማሪ ቤት ሊአሰሩልን፤ደጉ ዳግማዊ ምኒልክ የሰሩልንንም የተማሪ ቤት ሞኖፖል አድርገውት ሌላም እንዳያስተምር ከልክለው ከ፰ ዓመት የሚበልጥ እናስተምራለን ብለው ልክ የሌለው ገንዘባችንን አጥፍተው ወደ ዩንበርሲቲ የሚአልፍ አንድ እንኳ ተማሪ አልተገኘም ።

እንግዴህ የመለየት ነገር ቅድሚያው የነሱ ነው ።

፰ኛ በመብል ነገር የምንለያይበት አለ ።

፱ኛ በስሚ ኢላሂ ብለው ይባርካሉ ፤ የኛ የተጠላበት በስመ እግዚአብሔር ብሎ በቤተ ክርስቲያን ቋንቋ በመባረኩ እንደሆነ

ያረብኛ ቋንቋ የሚአውቁ ያገራችን ቀዮች መነኮሳት አሉ የተጠላው መስማማት ከሆነ ባስተርጓሚ ሊናገሩ ይሻላል ይሆን? እነሱን በውቀት ያሳደጋቸውን መጥላታቸው ነጻነት ሲሹ አይደ ለምን ። ባገር ነገር ይሉንታ የለም ።

፲ኛየሚመጡት ጳጳሳት ሁሉ የቤተ ክርስቲያንን ነገርትተው ከቤተ መንግሥት ነገር እየገቡ ያልመጡበትን የመንግሥት ሥራ ይሠራሉ ፤ የዚህንም ታሪክ እንዳልጽፍ አንባቢን አሰለቻለሁ ብዬ ተወት አድርጌዋለሁ ። ሊቁንም የሰው ያለህ ያሰኛቸው ይህ ነው ምን ያድርጉ ። ምን ቸገረኝ ብለው ዝም እንዳይሉ ልባቸው ያገራቸውን ጉዳት ያውቃልና አላስተኛ አላቸው ።

አሳብ የሌላቸው ባገር የመጣ ግድ የለም ። በራሳችን ብቻ አይምጣ እንጂ የሚሉ ያገርን ጉዳት ጥቅም የማያውቁ ባልተካከለ ቦታ ተዘቅዝቀው ተኝተው እንቅልፍ የሚወስዳቸው ሰዎች እንዴት የታደሉ ናቸው ። ከዚህም በፊት ብዙ ሰዎች ስለ ሀገር ጥቅም የጻፍነውን የምክር ቃል አቶ ልማድ ይበጣጥሰዋል ብዬ እፈራለሁ ፤ ምንም የሕዝብ ምክር ባይሰማ ያ እንዲህ ያለው ሊቅ እንደ ኤርምያስ ስለ ሀገሩ ሲአለቅስ ምሾ ሲጠራ የሰው ያለህ ሲል ። ለልቅሶ ልድረስ ብዬ ነው እንጂ ምን አቅም ኑሮኝ እረዳለሁ ፤ ይልቁንስ ባዘገየኋችሁ ከንባቢዎች ይቅርታ እለምናለሁ ።

የብርሃንና ሰላም ወዳጅ ።

አስታዋሻችሁ ማኅተመ ወርቅ እሼቴ ።

ስለ ሆሣዕና በዓል አከባበር ።

የሆሣዕና በዓል ፤ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእዋለ አድግ ተቀምጦ ወደቤተ መቅደስ ሲገባ ሕዝቡም ሕፃናቱም ሽማግሎችም ልብሳቸውንና ቅጠል እያነጠፉ ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው ሆሣዕና በአርያም እያሉ ያመሰገኑበት ቀን ነው ። ሆሣዕና ማለትም እርዳ ቡሩክ ሁን ማቸነፍስጥ ማለት ነው ። በአርያም ማለትም በላይ(በሰማይ) ማለት ነው የክርስቶስ ወገንየሆንን ክርስቲያኖች ሁሉ ይህን የመድኃኒታችንን የክርስቶስን በዓል ። በየዓመቱ አምላካችንና ንጉሣችን መሆኑን አምነን መታሰቢያ አድርገን እናከብራዋለን የቀረውን ታሪክ በሁለተኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ክቡር አንባቢ ተመልከት ።

ስለ ጸሎተ ሐሙስ ።

ስለ ጸሎተ ሐሙስም ታሪክ በመጀመሪያው ዓመት ብርሃንና ሰላም ተመልከት ፤ ፍሬ ነገሩ ግን የሐዲስ ቁርባንን ምስጢርና የሐዋርያቶችን እግር በማጠቡ ትሕትናን ያስተማረበት ቀን ነው ። ይኸንን ምሳሌ ይዘው የኢትዮጵያ ሌቃውንት የጸሎተ ሐሙስ እግር ያጥባሉ ።

የጐርፍ አደጋ ።

ጂቡቲ ።

በሚያዝያ ሶስት ቀን በአምቡሊ በኩል ጎርፍ ከመንገድ ወጥቶ ወደ ከተማው ይልቁንም የባላገሩን መንደር አንድ ሜትር ያህል ገብቶት አጠፋው ፤ የሞተና የጠፋ ወደ አርባ ሰው ይገመታል ። አደጋ ያገኛቸውንም አላይኛው ከተማ አስጠልለዋቸዋል ። የሞተውም የሚቀበርበት ውሀ ስለሞላው ስፍራ አልተገኘም መዘዋወሪያ በጀልባ ነው ለጎርፍ መንገድ ወደ ጨው ማውጫው ትይዩ ቀደው ጨውን በጭራሽ አበላሽቶታል አምቡሊ የውሀውን ማውጫ መሂጃ አፍርሶታል ሥራ በያለበት ቆሟል

የውጪ አገር ወሬ ።

ሳንቲያጎ ቺለ የቺለ መንግሥት ገንዘብን ስለ መቈጠብ ያህል ከሎንድራ ላለው የቺለ ሌጋሲዮን ለማስቀረት ቈርጦታል።

ሪዮ ጃነይሮ ። ደበረሮስ የፖርትጋል መንገደኛ ወደ ፖርትጋል ልመለስ እንጂ ዓለም ሁሉ መዞር ይቀርብኝ ብሎ ቊርጡን ተናግሮዋል ።

አንጎራ ቱርክ የውጭ ጉዳይ ምኒስቲር የደፑታት ጉባኤ ጠይቀውት ሲመልስላቸው በቱርክና በባልካን መንግሥቶች መካከል ፈጽሞ ትክክል የሆነ ስምምነት ሁኖዋል የሆነ ሁኖ ግን ምናልባት ያላሰበችው አደጋ የተነሣበት እንደሆነ የቱርክ መንግሥት ተጠንቅቃ የሚያስፈልጋትን ይዛ መኖር ያስፈልጋታል ይላል ።

ሻንጋይ ፤ የኖርዲስታ ሠራዊቶች ፑክን የሚባል አገርን ይዘዋል ።

አዲስ የጃፓን መርከቦች ጭፍራ ደርሰዋል ተብሎ ይወራል ።

ቶኪዮ ። ጃፓን የሚያደላ ሠራዊትን አስከትቶ አዲስ የመርከቦች ጭፍሮች ወደ ቺና ሊሰድ ነው ተብሎ ይወራል ።

ቺንካይ (ከሚባል) ባሕር ፊሪቦት (የሚባል) ስለተገለበጠ ፪፻ ሰዎች እባሕር ተሰጥመዋል ።



የእጅ ዝኒት ሰዓት ።

በኤሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ከዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ተሩብ ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፰ ብር ተሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
በግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፭ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፵፫ ብር ።
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፻፵፭ ብር ።
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፳፫ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፫ ብር ።
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፴፫ ብር ።
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፶፭ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፵፩ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፬ መ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ
በአንድ ብር	፱ ሊሬ እስከ ፴ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፴፫ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፵፭ ብር ።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል ።

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳም ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።



የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድሬስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፣ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎች ና በያይነቱ ላሴተክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፣ ሽቱ ፣ ለስ ዮን ፣ አድኮሎኝ ፣ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፣ ካኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፣ ከፈይ ምንጣፍ ፣ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ እመለክ ታችኋለሁ ፣ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን ኦቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፣ ባለ አጉበርና አጉበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፣ መጫሚያ በያይነቱ፣ ወንበር በየዓይነቱ፣ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፣ ቢሲግሌት ፣ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፣ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፣ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

Berliet



ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ አቶሞ ቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ፡፡

AMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኔዲሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን ኦዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የኦዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሦስተኛ ዓመት ፡ ቁጥር ፲፯
3 me ANNÉE № 17

ሐሙስ ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 28 AVRIL 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé "Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ደረክተር
ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ደረክተሩ ያስታውቁ ።
Dirécteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ስቅለት በዓል አከባበር ።

ሚያዝያ ፲፬ ቀን በየአብያተ ክርስቲያናቱ ብዙ ክርስቲያኖች ተሰብስበው ኪርያላይሶን (እግዚአ መሐረነ ክርስቶስ) እያሉ ሲሰግዱና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኛ የተቀበለውን መከራ ስቅለቱንና ሞቱን ሲያስቡ ስለመከራውና ሞቱ የሚነግር የወንጌል ቃልም ሲሰሙ ዋሉ ። ካህናቱና ሊቃውንቱም በምሳሌ ሕዝቡ እንደሚረዳ እያደረጉ የጌታችንን ስቅለት ሲያሳዩ ዋሉ።እንደዚህ እየሆነ የስቅለት መታሰቢያ ሥራት ከተፈጸመ በኋላ በ፲፪ ሰዓት በጾምና በጸሎት በስግደትም ደክሞ የዋለው ሕዝብ ጉልበቱ እየተርገደገደ መራመድ ተስኖት በየአብያተ ክርስቲያናቱ በር ሲወጣ ለሚመለከተው ሰው በጣም ይገርማል ። ይህንም ጉልበት የሚያደክም ፡ ኃይል የሚከፍል ብርቱ ሥራ መሥራታቸው መድኃኒታችን ስለዓለም ቤዛ ኃጢአተኞችን ለማዳን ብርቱ መከራና ሥቃይ በመስቀል እንደ ተቀበለልን እኛም ጉልበታችንን በማድከም የጌታችንን መከራ እናስብ ብለው ይህን ሥራ መሥራታቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጽድቅንና ደግነትን ፈላጊዎች መሆናቸውን ይገልጻል ። ክርስቲያንነታቸውም የጸናና የበረታ እንደሆነ ያስረዳል ።

ደግሞ ሚያዝያ ፲፫ ቀን በየአብያተ ክርስቲያናቱ ያሉ ቀሳውስትና ዲያቆናት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው መስቀል ዘውቀጤማ ተሸክመው ቃጭል እያቃጨሉ በየቤቱ እየዞሩ (ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ትንሣኤሁ አግሃደ) በመስቀሉ ሰላምን አደረገ ትንሣኤውንም ገለጠ እያሉ ለሰው ሁሉ ቀጤማ እየሰጡ የትንሣኤውን ምሥራች ነገሩት ሰውም ሁሉ ቀጤማውን በደስታ ተቀብሎ ከሁለት እየሰነጠቀ በራሱ ላይ አስሮ በየቤቱና በየመንገዱ ሲታይ ዋለ ።

የመድኃኔ ዓለም ካህናት ወደ ልዑል ግቢ ቀጤማ ለመስጠት በገቡ ጊዜ ደብተራ አሥራት የተቀኘው ቅኔ ።

ሥላሴ ።

በነቂሀ ወበንዋም ።
ምኒልክ አዳም እንዘ ይሄሉ።
ኃይለ ሥላሴ ዘዮም ለኵሉ ከመ አሜሃ ተከሥተ ።
እስመ ነሥአ እምገበ መንግሥቱ አሐደ መንግሥተ ።
ወእምኔሁ ለሐኰ አስካለ ማርያም ብእሲተ ፤
ወእሙ ተወክፈት መራኁተ ።
ወለተ ጊዮርጊስ ፀሐይ ቀጸበቶ ግብተ ።
ለዘገብረ አበይተ ኃይላተ ።

ደግሞ ስለትንሣኤ ክብር በስምንቱ ቀን ሁሉ ገበያ ክልክል ስለሆነ በዚሁ ቀን ለፋሲካ በዓል የሚያስፈልገውን ለመግዛት ወደገበያ የሚሄደውና የሚመለሰው ከብዛቱ የተነሣ መንገዱ ጠቦትኑ ይጋፋ ነበር ፡ ይልቁንም ለአውቶሞቢል ነጂዎች ወዲህና ወዲያ ለማለት ያስቸግራቸው ነበር ።

ስለ ትንሣኤ በዓል አከባበር ።

የቀዳሚ ሥዑር ማታ ከሌሊቱ በ፩ ሰዓት ሰው ሁሉ በየክፍሉ ወደ አለው ቤተ ክርስቲያን በተሰበሰበ ጊዜ ካህናቱ እንደ ልማዳቸው የትንሣኤውን አደራረስ ሲያደርሱ አደሩ ። በቅዱስ ጊዮርጊስቤተ ክርስቲያንም የትንሣኤን በዓል ለማክበር ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ ነበር ። የውጭ አገር ሰዎችም የበዓሉን አከባበርና የካህናቱን ያደራረስ ሥርዓት ለማየት መጥተው ነበር ። ክቡር መልአከ ገነት ወልደ ሐናም ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ፍጹም ፍቅር ስለ አላቸው ፤ ያደራረሱ ሥርዓት በትክክል አምሮ እንዲፈጸም ካህናቱን በጥንቃቄ ይመለከቷቸው ነበር ። እውነትም ከመልአከ ገነት ወልደ ሐና ትጋትና

ያገልግሎት ናፍቆት ከመኖራቸው የተነሣ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት አገልግሎትና ያደራረስ ሥርዓታቸው ከአብያተ ክርስቲያናቱ ሁሉ ከፍ ያለና የበለጠ ፡ የተመሰገነም ሆኖአል ። ኅብረታቸውና አንድነታቸውም ፍጹም ያገልግሎት ፍቅር እንዳላቸው ያስረዳል ።

በየአብያተ ክርስቲያናቱ ሁሉ አደራረሱ ተፈጽሞ ከቅዳሴ በኋላ ከሌሊቱ በ፲ ሰዓት ስለ ትንሣኤ በዓል መታሰቢያ በቤተ መንግሥቱ ፯ ጊዜ መድፍ ተተከሰ ። ከዚህ በኋላ ሰው ሁሉ የደስታ በዓል አድርጎ ዋለ ። ብርሃንና ሰላም ለክቡራን ወዳጆቹ ሁሉ እንኳን ብርሃነ ትንሣኤውን ያሳያችሁ እያለ ደስታውን ይገልጻል ።

የ፻፳፫ ገጽ ተከታይ ።

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

፲፯ተኛ ክፍል ።

ከዚህ ቀደም እንዳየነው ብርና ወርቅ ሳይለመድ ሰው በከብትና በጨው ሲለዋወጥ ሳለ ፤ ከብቱ ሲከሳበት ወይም በበሽታ ሲሞትበት ጨውም በውሀና በዝናም ሲሟሟበት ሊለውጥባቸው ብሎ ለገዛቸው ሰው ብዙ ጉዳት ነበረበት ። ከዚያ በኋላ ቀጥሎ ብረትና መዳብ የለውጥ መሣሪያዎች ሆኑ ። ነገር ግን እነዚህም ቢሆኑ አንዳንድ ጊዜ ዋጋቸው ዝቅ ብሎ ሸክማቸው ግን ከባድና በአንድ ሌሊት እርጥበትም ሲዝጉ ለዘወትር የለውጥ መሣሪያ ሆነው ሊኖሩ የማይመች ሆነው ተገኙ ከነዚህ በኋላ ቀጥለው ብርና ወርቅ የለውጥ መሣሪያዎች ሆነው በዓለሙ ሁሉ የታወቁ ሆኑ ።

ከምድር ውስጥ የሚገኘው ብር ከወርቁ ይበዛል ። ወድያውም ብር ለመልቀም የሚደክመው ድካም ያንሳል ። ስለዚህም ከወርቁ ብር በጣም ይረክሳልና በየዓመቱ እንደተገኘው ብር ብዛት መጠን የብር ወጋ ዘዋትር ከፍና ዝቅ ይላል ። በምድር ውስጥ የሚገኘው ወርቅ ጥቂት ስለሆነና ለመልቀሙም የሚያደክመው ድካም ብዙ ስለ ሆነ የወርቅ ዋጋ እንደብሩ በቶሎ ከፍና ዝቅ አይልም ። የለውጥ መሣሪያቸው ብር የሆነ ሕዝቦች ይህ የብር ዋጋ ዘወትር ከፍና ዝቅ በማለቱ በብዙ ይጐዳቸዋል ።

አሁን ለምሳሌ አንድ ነጋዴ የሆነ ሰው ብር በተወደደበት ጊዜ በእጁ የነበረውን ቆዳ ለሽህ ብር ቢሸጠው የሚሸጠው ቆዳ አቡጀዲድን ለመግዛት ነበር ። ነገር ግን ገና አቡጀዲድ ሳይገዛ ብሩ ቢረክስ በሽህ ብር ሊገዛው አስቦ የነበር አቡጀዲ በሽሁ ላይ መቶ ብር ጨምሮ ለመግዛት ግድ ይሆንበታል ። ስለዚህ ያ ነጋዴ በሽህ ብር ብቻ ሊገዛው የነበረ ዕቃ የብር ዋጋ ስለረከሰ በሽሁ ላይ ጨምሮ ሲገዛው መቶ ብር መክሰሩ ነው ። በቀሩት ሕዝብ ትዳር እንደዚሁ ነው ። የኢትዮጵያ ሕዝብ በየዓመቱ የሚሸጠው ዕቃ ዋጋ ግምቱ ወደ ፳ ሚሊዮን ብር ይሆናል ። በዚሁም ገንዘብ በየዓመቱ ከውጭ አገር ዕቃ ይገዛበታል ። እንግዴህ በአንድ ድንገተኛ ምክንያት የብር ዋጋ ከመቶ ፳ ዝቅ ባለ ቁጥር ዱሮ በ፳ ሚሊዮን ብር ሲገዛው የነበረ የውጭ አገር ዕቃ ሁሉ በብር ዋጋ ቢታሰብ ብሩ ከመቶ ፳ ከፍ ባለበት ጊዜ ከ፳ሚሊዮን ብር ፬፻፺ሺህ ብር ያስጨምራልና በዚሁ ምክንያት የተነሣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ ዓመት ብቻ ወደ ፬፻፺ሺህ ብር ያህል ይከስራል ።

ስለዚህ ብዙ ነገሥታት የብር ዋጋ በየዓመቱ ከፍና ዝቅ ሲል ሕዝባቸው እንደሚጐዳ ተረድተውት በአገራቸው ውስጥ ሰው ሁሉ በወርቅ ሒሳብ እንዲለዋወጥ ደምብ ደነቡ ። እንደዚህ ብለው በደነቡት ነገሥታት አገር ውስጥ የብር ወይም የመዳብ ገንዘብ ቢኖር የወርቁ ወኪል እየሆነ ሥራውን ይሠራል እንጅ እንደ ዋጋው እያወጣ አይዶለም ። ይህንን ስለአልነ አንባቢው እንዲረዳ ቀጥሎ የተጻፈውን አስተውሎ ያንብብ ።

በ፲፰፻፲፯ ዓመተ ምሕረት በሰኔ ፳፪ ቀን የእንግሊዝ መንግሥት እንደ አወጀው ደምብ በአገሩ ውስጥ ሰው ሁሉ ሲገበያይ የዕቃውን ዋጋ የሚለክበት የለውጥ መሳሪያ ፓውንድ አስተርሊንግ ወይም ጅኔ የሚባል ወርቅ ነው ። የዚህ የጅኔ ሚዛን ፯ግራም ፺፰ሺህ፹፻፳ መቶ ሺህኛ ግራም ነው ።
በውስጡ ያለው ጥሩ ወርቅ ግን ፯ ግራም ፴፪ ሺ ፬፻፴፱ መቶ ሺህኛ ግራም ነው ። ስለዚኅ በጅኒው ውስጥ እንዲጠነክር ተብሎ ከወርቁ ጋራ የተደባለቀው መዳብ ፹፯ ሺ ፯፻፹፯ መቶ ሺህኛ ግራም ነው ። እንግዲህ ባጭሩ ብናመለክት በየአንዳንዱ የእንግሊዝ ጅኔ ውስጥ ፲፩ እጅ ጥሩ ወርቅ ፩ እጅ መዳብ አለበት ። ጅኔውም ሲሰራ ክፍሉ ፡ ፩ ጅኔ ፪ ጅኔ ፭ ጅኔ አኩሌታ ጅኔ እየሆነ ይታተማል ። ከ ፩ ጅኔ አኩሌታ ያነሰ የወርቅ ገንዘብ ለማተም ግን ወርቁ እያነሰ የማይመች ስለ ሆነ ሌላ የብርና የመዳብ ተበጀ ።

ጅኔው በሀያ ክፍል ተከፍሎ እያንዳንዱም ሀያኛ ክፍል ሽሌንግ ይባላል ። ነገር ግን የወርቅ ሽለንግ ከማነሱ የተነሣ እንኳን ለማተም በእጅም ለመያዝ አይመችምና የዚሁ ትንሹ ወርቅ ምስል እንዲሆን ተብሎ የብር ሽለንግ ታተመ ። ስለዚህ ዛሬ በእንግሊዝ አገር አንዱ ጅኔ ለ፳ የብር ሽለንግ ቢለወጥ ሽለንጉ የወርቁ ወኪል እንዲሆን ስለ ተደነበ ነው እንጂ በሀያው ሽለንግ ውስጥ ያለው ጥሬ ብር በእውነት አንድ ጅኔ የሚያወጣ ሁኖ አይዶለም ። የብሩ ሽሊንግ ምልክት ብቻ ነው ብርም መሆኑ ቀርቶ መዳብ ወይም ነሐስ ሆኖ ቢሆን ያው ነው ። ሰውም በእነዚሁ ገንዘብ ሲለዋወጥ ከ፵ ሽሊንግ በላይ ወርቅ እንጂ ብር እንዳይቀበል ሥርዓት ተበጅቶለታልና ስለዚህ በእንግሊዝአገር አንዱን ሰው ከሌላው ሰው በማናቸው ምክንያት የሚቀበለው ገንዘብ ቢኖረው በብር ከ፵ ሽሊንግ የበለጠ መቀበል የግድ የለበትም ። ሽሌንግም ሲታተም ፳ ሽሊንግ ፪ ተኩል ሽሌንግ ፪ ሽሌንግ ፩ ሽሌንግ አኩል ሽሊንግ የሽሊንግ ፫ ኛ የሽሊንግ ፬ ኛ የሽሊንግ ፯ ኛ የሽሊንግ ፲፪ ኛ እንደዜሁ እየተከፋፈለ ይታተማል በ ፲፪ኛ የሽሊንግ ክፍል ውስጥ ያለው ጥሩ ብር ግን በጣም አነሰ ለመያዙ የማይመች ስለ ሆነ ወኪል እንዲሆነው ተብሎ የቆርቆሮ ዓይነት አንድ ገንዘብ ለምስል ታተመ ።

ስሙም ፔኒ ይባላል ። ፔኒውም ፩ ፔኒ አኩል ፔኒ ሩብ ፔኒ እየሆነ ይታተማል ። ፲፪ ፔኒ ሽሊንግ ይለውጣልና ማንም ሰው ከዚሁ ፔኒ ከተባለው የቆርቆሮ ገንዘብ ከ፩ ሽሊንግ ዋጋ በላይ በግድ መቀበል የለበትም ።

በጀርመንም አገር እንደዚሁ ነው ፡ ሰው ሁሉ ዕቃ ሲገዛዛ መተሳሰቢያው በወርቅ ነው ። በዚያው አገር ያለውም የብርና

የነሐስ ገንዘብ ሁሉ ለምልክት ብቻ ነው ። የጀርመን አገር ገንዘብ ማርክ ይባላል ።ከየአንዳንዱ ኪሎ ግራም ጥሩ ወርቅ ፪ሺህ ፯መቶ ፺ አንድ ማርክ ይታተማል ። ማርኩም ሲታተም ፳ ማርክ ፲ ማርክ ፭ ማርክ እየሆነ ነው ። ሲታተምም ፱እጅ ጥሩ ወርቅ ፩እጅ መዳብ እየሆነ ነው ።

ከ፭ ማርክ በታች ግን ወርቁ አንሶ ለማተም የማይመች ስለ ሆነ ምስል እንዲሆነው ተብሎ ከያንዳንዱ ኪሎ ግራም ጥሩ ብር ፪ መቶ ሆኖ ይታተማል ። ይህም ምስል የሆነው የብር ገንዘብ ፭ ማርክ ፪ ማርክ ፩ ማርክ እኩል ማርክ የማርክ ፭ትያ ክፍል እየሆነ ይታተማል ። ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው ከሌላው ሰው የሚቀበለው ገንዘብ ቢኖረው ከ፳ ማርክ በላይ በወርቅ እንጂ በብር መቀበል የግድ የለበትም ። ብር ለሆነው ገንዘብ የለውጥ መሣሪያ ወኪል እንዲሆን የማርክ አምስተኛ አሥረኛ ሀያኛ ክፍል ተብሎ ነሐስ የማርክ አምስተኛ የማርክ መቶኛ ተብሎም የቆርቆሮ ገንዘብ ይታተማል ነሐስና ቆርቆሮ የሆነውን ገንዘብ ሁሉ ግን ሰው የሚቀበለው እስከ አንድ ማርክ ብቻ ነው ። ከዚያ በላይ ግን በብር እንጂ በነሐስና በቆርቆሮ የግድ መቀበል የለበትም ።

እነሆ በላይ እንደተጻፈው እንደምናየው የእንግሊዝ መንግሥትና የጀርመን መንግሥት በአገራቸው ውስጥ ሰው በገንዘብ ሲለዋወጥ የለውጥ መሣሪያ ወርቅ እንደሆነ ደንብተውታል ። ከወርቅ በቀር የለውጥ መሣሪያ የብርና የነሐስ የመዳብና የቆርቆሮም የወርቅ ወኪል ሆኖ አስተሳስቦ ሂሳቡ ሲሞላ ወርቅ እንዲያሰጥ ነው እንጂእርሱ ራሱ እንደ ወርቅናእንደብር ዋጋ ሊያወጣ አይደለም ፡፡

እንግዴህ ፊት እንዳልነው እያንዳንዱ ሽህ ግራም ጥሩብር ፪ሽህ የብር ማርክ ይታተማል ። በያንዳንዱ የብር ማርክ በውስጡ ያለው ጥሩ ብር አምስት ግራም ብቻ ነው ። በአጼምኒልክ ብር ውስጥ ያለው ጥሩ ብር ግን ከ፳ ግራም ይበልጣል ። ስለ ዚህ ማርክ እንደ እውነተኛ ዋጋው የሚሸረፍ ቢሆን ለየአንዳንዱ የአጼ ምኒልክ ብር ከ፬ ማርክ ተኩል በላይ ይደርሰው ነበር ዛሬ ግን የአጼ ምኒልክ አንዱ ብር እጅግ ቢበዛ ለ፪ ማርክ ብቻ ይሸረፋል ። እንደዜህ የሆነበት ምክንያት የአጼምኒልክ ብር በገበያ ያለው ዋጋ የሚያወጣ በውስጡ ስላለው ጥሩ ብር ነው ማርክ ግን የወርቅ ወኪል ነውና ፳ሲሞላ ፯ግራም ሽህ ፮፻፹፭ አሥር ሽህኛ ግራም ለሚከብድ ጥሩ ወርቅ የሚለወጥ ስለሆነ ነው።ሽልንግም እንደዜሁ በአጼ ምኒልክ ብር ሲለወጥ ፪ ሽልንግ ለ፩ ብር እየሆነ ነው ። በውሥጡ እንዳለው ጥሩ ብር ሚዛን ቢሆን ግን ለየአንዳንዱ የአጼ ምኒልክ ብር ፬ ሽልንግ ተኩል ሊሰጡበት ይገባ ነበር ። ይህንን ስለ አልነ አንባቢው እንዲህ ይጠይቅ ይሆናል ። በእየአንዳንዱ ማርክ ውሥጥ ያለው ጥሩ ብር ጥቂት ከሆነ ስለምን ከፍ ያለ ዋጋ ይሰጥበታል። የዜህ ጥያቄ ምላሽ ግን እንዴህ ነው ። የብሩን ማርክ እያተመ የሚያወጣ የጀርመን መንግሥት ራሱ ነው ። ይህም የጀርመን መንግሥት በአዋጁ ፳ የብር ማርክ ይዞ ለሚመጣ ሰው በፈለገው ጊዜ ፯ ግራም ሺ ፮፻፹፭ አሥር ሺህኛ ግራም በሚዛኑ የሚከብድ ጥሩ ወርቅ ከመንግሥት ግምጃ ቤት እንዲቀበል እዋሳለሁ ብለዋል ። ስለዚህ የጀርመን መንግሥት ስለ ተዋሰ እያንዳንዱ የብር ማርክ የሚቀበል ሰው ፳ ማርክ ሲሞላለት ወርቅ እንዲቀበል ያውቃልና የብር ማርክ በገበያ ዋጋ ሲያወጣ ስለ ወርቅ እየታሰበ ነው ። እንደዜሁም በጀርመን አገር ውሥጥ ያለው የነሐስና የቆርቆሮ ገንዘብ እያተመ የሚያወጣ የጀርመን መንግሥት ነውና ይህንን የነሐስና የቆርቆሮ ገንዘብ የሚቀበል ሰው ሂሳቡ ሲሞላለት የብር ማርክ ወይም የወርቅ እንዲሰጠው የጀርመን መንግሥት ተውሰዋል ።

ስለዚህ በጀርመን አገር ያለው የብርና የነሐስ የቆርቆሮም ያለውን መሣሪያ ዕቃ ሲገዛዘበት ዋጋው ዝቅና ከፍ የሚል ወርቅ ሲረክስ ነው እንጂ የወርቅ ዋጋ ከፍና ዝቅ ካላለ ዋጋው አይነቃነቅም ። ይህም የሆነበት ምክንያቱ ወርቅ እሰጣለሁ ብሎ የጀርመን መንግሥት ተውስዋል እያለ ሰው ሁሉ ስለ አመነ ነው ።

የእንግሊዝ መንግሥትም ደንብ እንደዚሁ ነው። መንግሥት ራሱ እያተመ ለሚያወጣው የብርና የነሐስ የቆርቆሮም ገንዘብ የእንግሊዝ መንግሥት ተውስዋል ። ፳ የብር ሽሊንግ ይዞ ወደ የመንግሥት ግምጃ ቤት የሚሄድ ሰው ሁሉ ጆኔ የሚባል ወርቅ በውስጡ ፯ ግራም ፴፪ ሽህ ፪፻፴፱ መቶ ሺህና ግራም ሚዛኑ የሚከብድ ጥሩ ወርቅ ያለውን ገንዘብ ይቀበላል ። ፲፪ የቆርቆሮ ፔኒ ይዞም ቢሄድ የመንግሥቱ ግምጃ ቤት አንድ የብር ሽልንግ ይሰጠዋል ። ስለዚህ የእንግሊዝ መንግሥት ከመታመኑ የተነሣ እያንዳንዱ ሰው የብር ሽልንግ ወይም ቆርቆሮ ፔኒ ሲቀበል እንደ ወርቅ ይቆጥረዋል ።

ስለዚህ በእንግሊዝና በጀርመን አገር ሰው ሁሉ ሲገዛ የሚተሳሰብበት በወርቅ ነውና ከምድር የሚገኘው ወርቅ ጥቂት ሆኖ የወርቅ ዋጋ የማይንቀሳቀስ ስለ ሆነ ሰው ሁሉ የሚለዋወጥበት የለውጥ መሣሪያ ከመርከሱ የተነሣ ሕዝቦቻቸው አይጐዱባቸውም ።

ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግሥትም ቢሆን ሕዝቡ እንዳይጐዳበት ቢፈልግ የአገሩን ሕዝብ የሚተሳሰብበት የለውጥ መሣሪያ ወርቅ እንደ ሆነ ቢጥርበት መልካም ነበር ። ይህነኑ ለመጣር ፈቃዱ እንደ ሆነ እንዴት ያለ ደምብ ለማውጣት እንደሚገባው ለይተን በዜህ መጽሐፍ ውስጥ ለመናገር ጊዜ አይሰጠንም ። ደግሞም የደምብ አውጪዎች ሥራ ነውና የሕዝብ አስተዳደር በሚባለው መጽሐፍ ውስጥ ቢገባ ትክክለኛ ቦታው አይደለም ። የአገራችን መንግሥት በአገሩ የለውጥ መሣሪያ መሠረቱ ወርቅ እንዲሆን ቢፈልግ ከአንዳቸው የኤሮፓ ነገሥታት የገንዘብ ፍትሐ ነገሥት አስመጥቶና አስተርጕሞ መንገዱን አይቶ ላገሩ የሚመቸው የገንዘብን ደምብ ማውጣት ይችላል ።

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት መጽሐፍ ነው።

ምክር ሠናይት ለኵሉ ዘይገብራ ።
ዘሰ አፍቀራ ለዓመፃ ጸልአ ነፍሶ ።

የኢትዮጵያ መኳንንትና ካህናት ወታደሮች ሆይ ብርሃንና ሰላም የላከኝን መልክት እንደተሰጠኝ ያህል እመክራችሁ

ዘንድ ሕሊናዬን አሳስቦኛልና በብርሃን እንድትመለከቱት በማ ክበር እለምናችኋለሁ ። ሁለተኛ ዓመት ቍጥር ፺፩ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ በ፩፻፩ ገጽ በመጀመሪያ ዓምድ በ፲፯ኛው መስመር ለኢትዮጵያ መኳንንት ለዕለት ጥቅም ብሎ ሁሉም የኔ ይሁን ሁሉንም እኔ ልሥራ ማለት ይቅር ብላችሁ ንገሩ ለኢ ትዮጵያ ክህናት መንፈሳዊ ሥራን ትታችሁ ለዕለት ጥቅም ስትሉ በዓለማዊ ሥራ መግባታችሁ ይቅር ብላችሁ ንገሩ ለኢ ትዮጵያም ወታደር ባላገር ቢጠፋ እኔን ምንቸገረኝ ብሎ ድኃን ማጕላላት ይቅር ብላችሁ ንገሩ ብሎ ሰይፍ በሆነ ቃሉ ቢያዘኝ ነው እንጂ ጌቶቼን ለመምከር ደፍሬ አደለሁምና በደስታ እን ድትቀበሉኝ ደግሜ ደጋግሜ እለምናችኋለሁ ። ለምሳሌ እንደ ምታውቁ ላንድ ሰው ብዙ አካላት አለው ። እርሳቸውም እጅ ፥ እግር ፥ ዓይን አፍንጫ ፥ ጆሮ ፥ አፍ ፥ ናቸው ። እነዚህ አሁን የጠ ራናቸው አካላትም እግዚአብሔር በሰጣቸው ስፍራ ሁነው ህጉን ሳይተላለፉ ለያንዳንዳችን እንደሚያገለግሉን ሁሉን እናውቃለን እውነት ነው እጅ ከእግር ሥራ ገብ ቼየእግር ሥራ ልሥራ አይልም ። እንዲሁም እግር ከፍ ባለው ቦታ ሁኜ የእጅ ሥራ ልሥራ አይልም እንዲህም ዓይን ማየቱን ትቶ በፍንጫ ሥራ ገብቸ እሸታለሁ አይልም እንዲሁም ጆሮ በአፍ ሥራ ውስጥ ገብቼ እበላለሁ አይልም ። ይልቁንስ እግዚአብሔር ከሰጣቸው ስፍራ ሁነው ላንድ አካል በንድነት ያገለግላሉ እንጂ እንግድ ያስ ያንድ ሰው አካላት እየመናፈያቸው ሁነው ሕጉን ሳይተ ላለፉ በጥንቃቄ የሚሰሩ ከሆነ እኛም የኢትዮጵያ መኳንንትና የኢትዮጵያ ክህናት እንዲሁም የኢትዮጵያ ወታደሮች ሕጉን ሳንተላለፍ ደንበሩን ሳናፈርስ መንግሥታችን በወጣልን ደምብ ቁመን በሥራችን ልንመሰገን ይገባናል ። ደግሞ ለምሳሌ አንድ ልንገራችሁ በንብ ቤት ሶስት ዓይነት ሠራተኞች አሉ ይባላል ። ማለት አንደኛው ክፍል የመንግሥት ዘበኛ ። ሁለተኛ የአበባ መልክ ለይቶ የመንግሥቱን ጥቅም የሚሰበስብ ሶስተኛው ከማረ መልክ ወህ ተሸክሞ በቍርና በህሩር የሚያገለግል ነው (መልካም ደምብ) እሊህም ትንንሾች ትሎች በየስራቸው ቁመው በስምምነት ስለ ሠሩ ሁሌ ጊዜ በንብ ቤት ሀብትና ክብረት አያ ቋርጥም ነገር ግን ጠያቂ ከሁሉ የሚያንሱ ሳሉ ከሁሉ የበለጠ ሀብትና ክብረት በንብ ቤት መገኘቱ ምክንያቱ ምን ይሆን ብሎ ይጠይቅ ይሆናል ። ይኸውም ሁላችን እደምናውቀ አንድነት መስማማት ተብሎ ይተረጐማል ።

አሁን ግን እንደዚህ ያለ መልክም ምሳሌ ተከት ለን ብንሄድ ነው መንግሥታችንና ሕዝባችን የሚበለጽግ እ ንጂ በመተላለፍና ለኔ ይመቸኝ አይደለምና ተመክሪዎች ተጠ ንቀቁ እስተውሉም ። ፩ኛ መኳንንቶች ሆይ መንግሥት ሹሞ ሽልሞ ግዛት በሰጣቸሁ ጊዜ እናንተም እንደሚገባችሁ ለመንግ ሥት ልትታዘዙ እንዲሁም የሕዝብ ቀምበር ልታቀሉ ይገባችኋል እንጂ ካለሥራችሁ ገብታችሁ ሠራተኞችን ማስጨነቅ ይቅርብ ችሁ ይኸውም ለሰሚው ግራ ነው ፤

፪ተኛ የኢትዮጵያ ክህናትም የኢትዮጵያ መንግሥት ቀላ ድና የከተማ ቤት ሰጥቶ ያስከበራችሁ ቤተ እግዚአብሔርን እየገለገላችሁ መንፈሳዊ ሥራ ልትሰሩ ነውና ከማይገባችሁ ስራ ገብታችሁ ለዕለት ጥቅም ስትሉ ወይበ ለብሳችሁ መስቀ ልና ጭራ አንግታችሁ ፯ ክንድ ሸሽ ጠምጥማችሁ የሰው ጠላ እያጣጣማችሁ ባልተማረ ሕዝብ ጆሮ የእለት ጥቅም ስትሉ የጠላት ፖሎቲካ መናገር አይገባችሁም ይሄውም መንፈሳዊ ሥራ አደለምና ውርደት ያመጣባችኋል ። ፫ኛ የኢትዮጵያ ወታደሮችም የተቀበላችሁትን ብረት የመንግሥት ዘበኞች ሁና ችሁ ስታበቁ የመንግሥት ጠላት ልትከላከሉበት ነው እንጂ ባገ ር ሰው መሸ አዳር አደለምና በባላገር ቤት ገብታችሁ ሙክት እረዱ እርጎ ገምጥሉ ። ንብ በርብሩ ። እንጀራ ጋግሩ እያላችሁ ባልና ምሽት እያስጨነቃችሁ እነሱ ቀምሰውት የማያውቁ ምግቡ በመጋበዛችሁ ለሰሚ ጆሮ ደንቆታልና ይሄውም እንደ ምታውቁ የዘበኛ ሥራ አደለም።ስለዚህ ወታደሮች ልትጠነቀ ቁበት ይገባችኋል ። አለበዚያስ ለመዓት ዝግጁ ናችሁ ። ፬ተኛ ባገር ውስጥ የምትኖሩ የከተማ ሰዎች መንግሥት በከተማ ውስጥ ያስቀመጣችሁ ለናንተ አትርፋችሁ ስታበቁ የቤቱ ክራ ይና የወር ግብር ልትሰጡት ነውጂ ለኪሣራ አደለምና ከዘራ ይዛችሁ ግራ ለብሳችሁ አውለኝና ጠበቃ እየሆናችሁ የሰራተ ኞችን ገንዘብ መውሰድ አይገባችሁም ። ስለዚህ በከተማ ውስጥ ለምትኖሩ ሰዎች መጠንቀቅ በግድ ያስፈልጋችኋል ። ስራ በመሥራት ፈንታም ፖሎቲካ የሚባል የለት ጥቅም የጥንት ጉዳት ንግድ አስፍታችኋልና ሸያጩ እንዳያከስራችሁ ተጠን ቀቁ አሁን ግን ብርሃንና ሰላም የሚባል ጋዜጣ ጠሊቅ ሀሳ ቡን ገልጦ ያባትነቱን ያህል ከመከራችሁ በኋላ ምክሩን ጥሳ ችሁ ህጉን አፍርሳችሁ የተገኛችሁ እንደሆን ሀላፊነቱ በራ ሳችሁ ላይ ነው ። የኢትዮጵያ መንግሥት ግን አስቀድሞ ብር ሃንና ሰላም ስላስታወቀ ምንም ሀላፊነት የለበትም ፡፡ ይላል የብርሃንና ሰላም መልክተኛ ። ተማሩ ረምሃ አድዋ ።

በየጁ የሚሆነው የወፉ ውጊያ ።

ከአዲስ አበባ ተነሥቼ ወደ ዓድዋ ስሔድ ሳለሁ በየጁ ያየሁት የሕዝባችን ጉዳት ቀጥሎ እንደሚነገረው ነው ።

የጁ በሚባል አገር በደረስን ጊዜ አንዲት በጣም ያማ ረች ሥፍራ ሠፈር አደረግን ። ከዚህም በኋላ ምሳችንን በልተን ሽርሽር ለመዞር ወደ ወንዙ አቀናንና አንድ ሰውዬ በጣም የገረጣና ሰውነቱ የቈሰለ በወንዙ ሲታጠብ አገኘነው ። እኛም ለመጠጋት ፈራነው ። ነገር ግን ከትንሽ ጊዜ በኋላ ስለ ቍስሉ ነገር ጥያቄ ጀመርን ። እርሱም መለሰና እንዲህ አለን ። ባገራ ችን ውስጥ ክፉ ደንብ አለብን ፤ እርሱም ወፉ ውጊያ የሚ ባል ፡ ማለት በመካከላችን አንድ ወንዝ አድርገን ስናበቃ ዘመ ዳችንም ቢሆን ከወንዝ ወዲያ ማዶ እና ከወንዝ ወዲህ ማዶ ሆነን ስንዋጋ እንውላለን፡ከዚህም የተነሣ ብዙ ሰዎች ይሞታሉ። እኔም የምታዩኝ ቍስሉ የወፉ ነው አለን ። ይኸ ሁሉ ሲሆን ንግግሩ ከሕመሙ የተነሣ በጣም የደከመ ነበረና እኛም ቀረብ ብለን እርሱን መጠየቅ ጀመርን።እርሱም መለሰና ይኸን ውጊያ ከተውነው ሶስት ዘመን ከሆነን በኋላ ወንድ ልጅ የሆነ ሁሉ የሶስት ዘመን ግብር አምጡ ብለው አገረ ገዢው ያዙን ። እኛም የአገሩ ሰው ሁሉ በማለዳ ተነሣንና ወደ ቤታቸው የሚ ቻለንን እህላችንንና እንጨታችንን ተሸክመን ሄድንና አቤቱ

ታችነን እንጮህ ጀመር ። ከአቤቱታችንም የተነሣ የሰሚ ጆሮ ይደነቁር ነበር ። ከዚህም በኋላ አንድ ሰውዬ ወደኛ መጣና ምን ተበድላችኋል ብሎ ጠየቀን ። እኛም እንደሚያውቁት ጌታዬ ይኸንን የወፍ ውጊያ ተተውነው ሶስት ዘመን ሆኖናል ። አሁን ግን ባመቱ ቁጥር ሶስት ሶስት ብር ቀረጥ ይክፈለኝ ብለው ስላዘዙን የጌታችንን ምሕረታ እንለምናለን ብለን የመጣንበት ስለዚህ ነው እያልን ስናመለክተው ጌቶቹ ወጡ ። እኛም እግዚአብሔር ያሳይዎ ጌታዬ ትላንትና ጭቃ ሹማችን እንዳስታወቀን ስለ ወፍ ውጊያ የሶስት ዓመት ግብር እያንዳንዳችሁ ፫ ፫ ብር አምጡ ብሎናልና እኛም ሳንዋጋ ስለምን እንከፍላለን ብለን የመጣንበት ስለዚህ ነው ጌታዬ አልናቸው ።

መልስ እርግጥ ነው የሶስት ዓመት ግብር መዝገቤን ባየው የወፍ ውጊያ ገቢ ገንዘብ ስለሌለ እንዲገባ ብዬ ያዘዝኩት ስለዚህ ነው አሉ ። ይህን ሲናገሩ እንዳልተማርን ተስፋ ቆረጥን ስለሆነ ግን ድኃ ጉጉ ነውና ጌታዬ ምነው የምሕረት ቃልዎን እንለምናለን አልናቸው እሳቸውም ወደግራና ቀኝ ተገላምጠው አጋፋሪን ጥራ ማነህ አንተ የኔ አሉ እነሥራ ፈት በፍጥነት አጋፋሪ አይምሬ ብለው በጠሩ ጊዜ እሱም አቤቱታውን በፍጥነት አቀረበ ጌቶችም እንዲህ አሉት ምነው ታሰጨቀጭቀኛለህ ወዲያ አታባርርልኝም ወይ አሉት እሱም ፈጣን ነበረና ይኸነን በተናገሩት ጊዜ የቁጣ ብትሩን አወረደብን እኛም ሸሽን ብሩቅ ስንሄድ ሳለ አቶ አጋፋሪ አይምሬ ጠሩን እኛም የተማርን መስሎን በሩጫ ቀረብን ጌቶችም መለሱና ሰማችሁ ግብሬን አልተውም እኔ አትዋጉ ብዬ አልከለከልኋችሁ ገንዘቤን እያንዳንዳችሁ ሶስት ፫ ብር የሶስት ዓመት እስከ ሁለት ቀን ያላገባችሁ እንደሆነ ባጠፌታ ትከፍላላችሁ አሉን እኛም የሚገባንን ከፈልን ሁለተኛ ደግሞ የማርና የፈሰስ የጦም ቆሎ አምጡ ብለው አስጨንቀውናል ሶስተኛም ደግሞ እርሰን እህላችንን ሸጠን እንዳንሰጣቸው ለነሱ ቤት ስንሰራና ሌላም ያዘዙንን ነገር ሁሉ ስናደርግ ጊዜው ይተላለፍብናል ይኸን ሁሉ ተበድለናል የምንሄድበት ብናጣ ነው እንጂ እኛስ በጣም ተጨንቀናል ስለውጊያው ነገር ። ደግሞ ያለ ምክንያት ከምንከፍል እየተዋጋን እንክፈል ብለን የቀረውን ልማዳችነን ጀመርን እያለ ሲያጫውተኝ ጊዜው ስለመሸ እኛም ወደሰፈራችንተመለስን ከቡራን እንባቢዎች ሆይ አገረገዢው ሕዝቡ በንደዚህ ያለ መጥፎ ሥራ ሲሰሩ ዝም ብለው ግብራቸውን ከመብላት ሕዝቡን በአዋጅ ቢያስከለክሉት ለመንግሥት ትልቅ ጠቀሜታ ነበር ሕዝቡ ግን ጥፋት መሆኑን አውቆ የተፈሪ ብርሃን ስለጠነከረ ያለ መምሕር ወደዕውቀት ጎዳና ገብቶ ሲጓዝ ሳለ እጅግ የበረታ የሲሚንቶ አጥር እያጠሩና የብርሃኑን ውጋጋን እየከለከሉት ሕዝቡ በጨለማ መከከል ይጋጫል እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብስ ከዱሮውም ጀምሮ ታዛጋኝና መንግሥቱን አክባሪ እንደሆነ በብርሃንና ሰላም ተረድቶነዋል ።

ደግሞ የትግሬ መንገድ ስፋቱ አንድ ሜትር የማይሆን ዳርና ዳሩ የጫካው ብዛት የሚያስፈራና ጋሬጣው የሚጎጠጥ ስለ ሆነ በጣም ያሳዝናል ። አገረ ገዞዎች ከድኃ ብር ለመሰብሰብና በግዛታቸው ላይ ቀረጥ ለማብዛት ነውጂ ለመንግሥት ጠቀሜታ አለማድረጋቸው በዚህ ይታወቃል አንድ የሺ አለቃ በግዛቱ ላይ አራት ስፍራ ላይ ቀረጥ እየወሰደ ደግሞ መንገዱን ሳያስጠርገው ስለ ደን ብዛት ቀመኛ እየበዛ ነጋዴዎች እየነጠቀ ስላስቸገረና ስለ መንገዱ መጥበብ ብዛት የሚሰበርም ዕቃ እየተሰበረባቸው ትርፉን በቀረጥና በኪሳራ ሲጨርሱ ጊዜ በመክሰብ ፈንታ ከሳሮት ሁኖ ቀረ ። ክቡራን አገረ ገዞዎች ሆይ የመንግሥት አዋጅ የምትጠብቁና የምታከብሩ እንደሆናችሁ እናውቃለን ። ስለ ሆነ ግን አራት ስፍራ ላይ ተማቆም ሶስቱን ተውት መንገዱም ጫካ ተሚበዛበት ብታስጠርጉት ደግሞ ከድኃ ገንዘብ ሶስት እጅ ተመቀበል ሁለቱን እጅ ብትተው ለመንግሥታችንና ለህዝቡ ጠቀሜታ ነበር ነገር ግን እናንተን የምመክርበት እውቀት የለኝምና ለወደፊቱ ለኢትዮጵያ መንግሥትና ህዝብ እንደሚመች አድርጋችሁ እንድትሰሩ ስንል በተስፋ እንጠብቃለን

ጥሩነህ ካብትህ ይመር

የከተማ ወሬ ።

ሚያዝያ ፲፮ ቀን በአዲስ አበባ የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ውሥጥ ቀጨኔ በሚባል ሰፈር የተደረገ እጅግ የሚያሳዝን እንግዳ ነገር ከዚህ ቀጥለን እንጽፋለን ።

አቶ ገብረ ሥላሴ የሚባል ሰውዬ በከተማ ኑዋሪ ስለሆነ ያጋፋሪ ሣህሌን ቤት ተከራይቶ ሚስት አግብቶ ታናሽ ወንድሙንም ከሀገሩ አስመጥቶ ይኖር ነበረና ፤ በዚኅ መካከል በእግዚአብሔር ዳኛ ባልጋ ቁራኛ ተይዞ ተኝቶ ሳለ ፤ ይኸው ከሀገሩ ያስመጣው ታናሽ ወንድሙ የወንድሜን ገንዘብ እወስዳለሁ ብሎ ጠብ እንሥቶ ሣጥን ከፍቶ ገንዘቡን ሊወስድ ወደሣጥኑ በቀረበ ጊዜ ፤ ያቶ ገብረ ሥላሴ ሚስት ወንድምህ ታሞ ሳለ እንዴት ገንዘቡን ለመውሰድ ትፈልጋለህ እኔስ ቢሆን የባሌን ገንዘብ ባሌ በውቃቢዬ ቢተርፍልኝ አስታምምበታለሁ ፤ ቢሞትብኝም ቁርባኑን አስቄርብበታለሁ እንጂ መች እሰጥሀና ትወስደዋለህ እያለች ስትተናነቅ የሚያይልባት ቢሆን አንድ አሽከር ነበርና ሂደህ ዘበኛ ጠርተህልኝ ና ብላው ሂዶ ጠርቶ እስኪመለስ በባሏ ጠመንጃ ተኵሶ ገደላት ። ያም ዘበኞች ሊጠራ ሂዶ የነበረ አሽከር ተመልሶ በመጣ ጊዜ እሱንም ደግሞ ሊገድለው ጠብ መንጃውን አጉርሶ አፈ ሙዙን ቢያሳየው እንደገና ሸሽቶ አመለጠ ።

የ ጠመንጃውን ጩኸት ከጐረቤት አንዴት ሴትዮ ሰምታ ኖሮ በድንጋጤ ብትደርስ ይህችኑ በጥይት የሞተችውን ሴት የባሩዱ ነበልባል ከልብስዋ ተያይዞ ሲያቃጥላትና ፤ ይሞታል ተብሎ ይጠበቅ የነበረው ባሏም ምሳሌ በሌለው ድንጋጤ አእምሮውን አጥቶ ራቁቱን ቁሞ አገኘቻቸውና እሳቱን በውሀ እንዳጠፋችው ሰው ደረሰላት ።

ከዚህ በኋላም ገዳዩን ወደ ባሻ አየለ ቤት ሲገባ ሰዎች አይተውት ኖሮ የባሻ አየለ ቤት በዘበኛ ተከበበና ገዳዩ ተይዞ ወደ ግራዝማች ሣህሌ ወስደው ቢመረምሩት መግደሉን አምኖ እውህኒ ገባ ።

በባቡር መሳፈር

ሚያዝያ ፲፱ ቀን ብዙ በባቡር ተሳፍረው ከሚሄዱት ሰዎች ጋር ፤ በበርሊን ከተማ ያለ የኡልሽታይን ኮፓንያ ጋዜጣ ጸሐፊ ሙሴ ኩርት ሉቢንስኪ የተባሉ ሰው ነበሩ ። ይህ ኩፓንያ ፎሲሸ ፀይቱንግ ። በርሊነር ፀይቱንግ አም ሚትግ ። በርሊነር ሞርገን ፖስት የተባሉ ፫ ዋኖች ጋዜጦች አሉት ። ከነዚህ ሌላ ደግሞ በየሳምንቱና በየወሩ የሚወጡ ፴ ጋዜጦች አሉት በየቀኑ የሚታተሙት የጋዜጦች ቁጥር ሶስት ሚልዮን ተኩል ነው ፤ ሙሴ ኩርት ሉበንስኪ ወደኢትዮጵያ ከመጡን አንድ ወር ይባልጣል በዚሁም ወር በአሩሲ እስከ ዟይ ባህር ድረስ ዙረው አይተዋል ፤ ዛሬም ጨርጨርና ሐረርን ለማየት ወርደዋል ።

ሙሴ ኩርት ሉቢንስኪ ከኢትዮጵያ ወደሐገራቸው በተመለሱ ጊዜ ስለኢትዮጵያ ሳይጽፉ አይቀሩምና የጻፉትን ጋዜጣ አይተን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እናመለክታለን ስንል ተስፋ አለን ።

ያገር ውስጥ ወሬ ።

መጋቢት ፱ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ከሌቱ በ፩ ሰዓት የአቡነ ገሪማ ቤት ክርስቲያን ከተሠራ ሺ ፫፻፳፯ ዘመን የሆነው አጼ ገብረ መስቀል ያሠሩት ተቃጠለ ። እኛ ግን ትልቅ ጉዳትን ስለ ሆነ ለማየት ሄደን ነበረና ሕዝቡ በትልቅ ኀዘን ሲላቀስ አገኘነው ። ደግሞ በምን ምክንያት እንደ ተቃጠለ ካህናቶቹን ብንጠይቃቸው ያቃጠለውንስ አላወቅነውም ፤ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመስለናል አሉኝ ሌሊት ስለሆነ በቤተ ክርስቲያኑ የነበረው አርባ አራት የሚሆን ታቦት በግራኝ ጊዜ ከሌላ ስፍራ እያሸሹ ያገቡት ነበረና እሱም ተቃጠለ ። ጥሩነህ ክብትህ ይመር።

በቴሌግራም የመጣ ቃል ።
የውጪ አገር ወሬ ።

ሮማ ። እራስ ተፈሪ ያበሻ ገጋር በመንግሥት መዓረግ ኀብኘተውት የነበረውን ለመመለስ ዱክ አብሩሲ ለሚመጣው ግንቦት ከመርከብ እጅቡቲ ወርደው በምድር ባቡር በኩል ወደ አዲስ አበባ ይገባሉ ።

ጀኖባ ። ሳንታ ማርያ ሁለተኛ የተባለው አዲስ አረዮፕላን ዘንድ ፖሳለበ የሚባል ሰው ነድቶት በመብረር ወዲህ ደርሶዋልና መኪናውን ተፈታትቶ ደዊልዮ ከሚባል መርከብ ላይ ተጭኖ ለደፒነዶ እንዲረከብ በዚሁ ወር ፳ ቀን ወደ ኒዮ ዮርክ ለመሄድ ይነሣል ።

ሊዮንዮ ። ፍራንሳይ ። የፈረንሣዊ ሶሲያልስት ከግራና ከል ቀናና ከኮሚኒሲቲ ክፍል ጋራ ስምምነት ለማድረግ ያህል ያደረጉት ፳፩ኛው ጉባኤ ተመርቆዋል ።

ብሩክስለስ ። ሞንስ በሚባል አገር በኩል ካለው መዓድን ሥራ በሆነው የመፈንዳት አደጋ ፴ ሠራተኞች ሙቶዋል ብዙዎችም ቈስለዋል ። ንግሥት ጉልየልሚና የደረሰውን የድንገት አደጋ ለማየት እቦታው ሂደዋል ።

ሳንቲያጎ ። ቺለ የመንግሥትና ገንዘብ እጅ ለማድረግ ያህል በደለኞች ሁነው የተገኙ የመንግሥት ሚኒሥትሮችንና ሠራተኞችንም እንዲደበደቡና ህይወታቸው ሙሉ ወህኒ እንደፈረደባቸው አድርጉ ብሎ መንግሥት ወደጉባኤ ደብዳቤ ልኮዋል

የመንግሥት ወሬዎች ዘንድ፤ አሁን በቅርብ ከተነሣው የምድር መንቀጥቀጥ ብዙ ሰው ሙተዋል ብዙ ጉዳትም ሁኖዋል የተባለውን ወሬ ያስዋሸዋል ።

ሳንፍራንቸስኮ ። ከሊፎርኒያ ዶፒንዶና ጓደኞቹ በደስታ ፩ ቀን እዚህ ሰንብተው ወደ ዋሲንግቶን ለመሄድ ተነሥተዋልና እዚያ በደረሱ ጊዜ ፕሬዚዳንን ኩሊድጅ በማክበር ተቀብለው ይነጋገራቸዋል ።

ማስታወቂያ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፯ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው ፤	፲፪ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፫ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር ።	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነርትጓሜው	፯ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ዋራዙእጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትጓሜው ፤	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትጓሜው ።	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት ፤	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው ።	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ፤	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን ።	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ ።	አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ ።	አላድ
ያማሪኛ ፊደል ፤	ሩብ
አሳብና ምኞት ፤	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት ።	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር ።	፪መ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ፤	፩ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ።	፩ሩብ



የእጅ ዝኒት ሰዓት ።

በኤሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ከዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ተሩብ ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፳ ብር ተሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ፫ ሩብ ።
ሳም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር ።
የገዘሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፲፯ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ብር
የወ ላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
በግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፭ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፯ ብር ።
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፻፴፭ ብር ።
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፳፯ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፰ ብር ።
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፯ ብር ።
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፵፭ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፩ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፬ መ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ
በአንድ ብር	፱ ሊሬ እስከ ፴ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፴፯ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፭ ብር ።

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል ።

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

ሩግቢ

RUGBY



የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድሪስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፣ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሸቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፊታውራሪ ዶሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሄስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጉበርና አጉበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፡ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ ሲኒ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።



ቤርሊዮ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዮ አቶሞ ቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ፡፡

AMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኔዲሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሸቶና ሎሲዮን ኦዶክለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የኦዶክለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተከሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ። የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቆውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፲፰
3 me ANNÉE № 18

ሐሙስ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 5 MAI 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ደረክተር ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ደረክተሩ ያስታውቁ ። Diréctеur	የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፊደን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።	Abonnements Ethiopie — Un an 5 Thalers Etranger — Un an 7 Thalers le numero 2 piastres

የልዑል ዱክ ዴ ዓብሩስ ወደ ኢትዮጵያ አመጣጥ ።

ልዑል ዱክ ዴዝአብሩስ በግንቦት ፱ ቀን አዲስ አበባ ሊገቡ ነው ። ስለዚህም በትልቁ ቤተ መንግሥትና በልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ ቤቱም ቅጥሩም መንገዱም ሁሉ ይታደሳል ።

በከተማውም ውስጥ ያለው ዋና ዋናው መንገድ ሁሉ ይታደሳል ። በየመንገዱም ዳር ቤት ያላቸው ሰዎች ሁሉ ቤታቸውን እንዲያድሱና ንጹሕ እንዲያደርጉ በማዘጋጃ ቤት ታዟል ።

ደግሞ ልዑል ዱክ ዴዝአብሩስ ወደ አዲስ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ለማየት ይወርዳሉ ተብሏልና ስለዚህ እስከ አዲስ ዓለም ያለው መንገድ ለአውቶሞቢል እንዲመች ሁኖ መታደስ ጀምረዋል ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ይህንኑ የሚታደሰውን መንገድ ለማየት ሁለት ጊዜ ወደ አዲስ ዓለም እየወረዱ ተመልሰዋል ።

የልዑል አልጋ ወራሽ አባት ልዑል ራስ መኰንን ከ፲፰፻፹፪ ዓ ም ወደ ኢጣልያ አገር በሄዱ ጊዜ እጅግ ያማረ አቀባበል ተደርጎላቸው ነበር ይባላል ። ደግሞ በ፲፱፻፲፮ ዓ ም ልዑል ተፈሪ መኰንን ወደ ኢጣልያ አገር ሄደው ሳሉ የኢጣልያ ንጉሥ ግርማዊ ቢክቶር አማኑኤል እስከ ባቡር ማቆሚያ ወርደው በትልቅ መዓርግና ክብር ደስ አሰኝተው እንደተቀበሏቸው ብላታ ኅሩይ በጻፉት ደስታና ክብር በሚባለው በልዑል ተፈሪ መኰንን የአውሮፓ መንገድ ታሪክ አንብበን ተረድተነዋል ።

አሁንም ልዑል ዴዝ ዱክአብሩስ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ልዑል ተፈሪ መኰንን በሁለት መንግሥቶች መካከል ያለውን ፍቅር ለማስፋትና ለማጽናት ወደ ኢጣልያን አገር እንደ ሔዱ ግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል በሁለቱ መንግሥቶች ያለውን ፍቅር እንዲሰፋና እንዲጸና ፈቃዳቸው ስለሆነ አጐታቸውን ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩስን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የወዳጅነት መጐብኘት ብድር እንዲመልሱ አደረጉ ።

ልዑል ዱክ ዴዝአብሩስ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት የተመረጡበት በደግነታቸውና በሥራቸው መልካምነት የተመሰገኑ በመሆናቸውም ነው እንጂ የግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል አጎት በመሆናቸው ብቻ አይደለም

ደግሞ ምንም እንኳ የሠሩትን ሥራ በሙሉ ለመጻፍ ባይቻል በኢጣልያ ቋንቋ ተጽፎ ወደ አማርኛ ከተገለበጠው ታሪካቸው ባጭሩ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን አትመን እንገልጣለን ።

የግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ ኡምቤርቶ ወንድም ልዑል ፕሪንስ አሜዴኦ ሹመታቸው አውስታ በሚሉት አገር ዱክ ተብለው ነበር ፤ ከእርሳቸው ልጆች አንዱ ስማቸው ሉይጂ ነውና ሲወለዱ በንጉሥ ኡምበርቶ ፈቃድ አብሩሲ በሚሉት አገር ዱክ ተብለው ከተወለዱ ጀምረው ተሾሙ ፤ አብሩሲ የሚሉት ሮማ አጠገብ ያለው ሰፊ አገር ነውና የአብሩሲ ሕዝብ ጀግና የአብሩሲ አገር መልካም ስለሆነ የሀገሩን ስም ብርቱና ውብ አብሩሲ ብለው በምሳሌ አወጡለት ፤ በዚሁም በከበረ አገር ላይ ልዑል ዱክ ተሾሙ ። ንጉሥ ኡምበርቶ እኚህን የወንድማቸውን ልጅ የአብሩሲን ዱክ እጅግ ይወዱ ነበርና የአብሩሲን ዱክ በቤተ መንግሥታቸው አሳደጓቸው የአብሩሲ ዱክ ገና በልጅነት ሳሉ የባሕር መርከብ ትምህርትና ከባሕር ወዲያ ተሻግረው የዓለምን አገር ሁሉ ማየትና መልመድ ጥልቅ ምኞት ስለነበራቸው ከንጉሥ ኡምበርቶ ፈቃድ ለምነው የባሕርና የጦር መርከቦች ትምርት በሚያስተምሩበት ትምሕርት ቤት ገቡ ።

ከትምሕርት ቤት ሳሉ የትምሕርት ቤት አለቆች ጥበባቸውን ልቡናቸውንና ጀግንነታቸውን ሲያዩ ደንግጠው ተደንቀው ሲያመሰግኑዋቸው ሲመርቀዋቸውና ሲያከብሯቸው ነበር ። ምንም የግርማዊ የንጉሥ ኡምበርቶ የወንድማቸው ልጅ ቢሆኑ

የባሕርን ትምሕርት እንደሚፈልገው ዜጋ ሁሉ እንደዜጎቻቸው አምስት ዓመት ሙሉ ጠንቅቀው አስተውለው ከተማሩ በኋላ መጀመሪያውን የጦር መርከብ ማዕርግ ጋርዲያማሪና የሚሉትን ተቀብለው ተሾሙ ። እንዲህ የሚመስሉ ትልቅ መኰንን ይልቁንም ከንጉሥ ወንድም የተወለዱ ፕርንስ ለኔ የማይገባኝ ትልቅ መዓርግ የለምና ተትልቆች መዓርጎች ትልቁን ይስጡኝ ብለው ቢለምኑ ከተወለዱበት ቀን ጀምሮ የዱክን ሹመት የሾሙዋቸው ግርማዊ ንጉሥ ኡምበርቶ የሚፈልጉትን መዓርግ ሳይሰጧቸው አይቀሩም ነበር ። ዳሩ ግን አምስት ዓመት ሙሉ የባሕርን መርከብ ትምሕርት ተምረው ለሕዝባቸው የትምሕርትን መንገድ እንዳሳዩ አሁንም የሚገባቸውንና የማይገባቸውን ሹመት ለማግኘት መንግሥት የሰጣቸውን መዓርግ ነቅፈው ፖለቲካንና ምክርን ሥርተው የሚኖሩ ሰዎች በዓለም ሁሉ ሲበዙ አይተው ሹመትን ማግኘት በማይገባ ስስትና በማይገባ ንፍገት አይሆንም በትምሕርት ነው እንጂ ብለው ለዜጎቹ የቀና መንገድን ለማሳየት ምንም ዱክ ቢሆኑ ምንም የንጉሥ ዘር ቢሆኑ ዜጎቻቸው ትምህርታቸውን ሲጨርሱ የሚቀበሉትን መዓርግ ከአጎታቸው ከግርማዊ ንጉሥ ኡምበርቶ ለምነው ይህንን መዓርግ እንደ ዜጎቻቸው ተሾሙ ።

ጋርዲያማሪና ከተባሉ በኋላ መቸም ለጦር መርከብ መልመድ ከባሕር ላይ ቅርብና ሩቅ አገር መሄድና መዛወር ያስፈልጋል በስፑቺ በሚሉት መርከብ ላይ ተልከው ወደ ደቡብ አሜሪካ አጠገብ ወዳለው ባሕር ሔዱ እርሳቸው ገና በደቡብ አሜሪካ ሳሉ እጅግ የተወደዱና የተመሰገኑ አባታቸው ልዑል ፕርንስ አሜዲኦ በእግዚአብሔር ፈቃድ ብርቱ በሽታ ወደቀባቸውና ሞቱ ። የአብሩሲ ዱክ ወደ ኢጣልያን አገር ተመልሰው ከወንድማቸው ጋራ የልዑል ፕርንስ አመዲኦን ተዝካር አውጥተው በሌላ መርከብ ላይ በዓለም ሁሉ ለመዛወር ተነሡ በዓለሙ ሲዛወሩ ተኢጣልያ ወደ ሱማሌ አገር ሞቅዲሾ ተሞቅዲሾ ተመልሰው ወደ ቱርክ አገር ወደ አስያ ሚኖሬ ተዚያ ደግሞ ወደ ኢጣልያ ወደ አሜሪካ ወደ ጃፖን ወደ ሕንድ አገር ሲሄዱና ሲመለሱ በባሕር አጠገብ ያለውን አገር ሁሉ አምላክ የፈጠረውን ዓለም ሁሉ አይተውና ለምደው በባሕር መርከብ አለቆች ውስጥ የተከበሩና የተመሰገኑ ሆኑ ።

ከአሜሪካ ሰሜን ያለው ሰፊ አገር አላስካ ይባላል ። ሰው ከሚኖርበት አገር ሁሉ እሱ ይበርዳል እሱ ይቀዘቅዛል ። እንኳንስ የሌላ አገር ሕዝብ ብርድ የለመዱ መስኮቦች በዚህ ቀዝቃዛ በረዶ በሚፈላበት አገር መኖር አይቻለንም ብለው አገሩን ለአሜሪካ መንግሥት በገንዘብ ሼጠው ነበር ። በዚያው አላስካ በሚባል አገር ትልቅ ተራራ አለና መቸም ተዓለም ሁሉ ደጋ ተራራ ብርዳም አገር ነው ቆላውም ወንዙም ስለ ብርዱ የሰው መኖር ያልተቻለበት የዚያው አላስካ የሚባል አገር ተራራውና ደጋው እንኳንስ ለሰው ለአውሬና ለአስሳም የሚያስፈራና የሚስደነግጥ ሆነ ። የዚህን የአላስካን ተራራ ስም የኤልያስ ተራራ ብለው ስም አወጡለት የቅዱስ ኤልያስ ተራራ ማለት ነቢይ ኤልያስ የወጣበትንና ተራራው ራስ ላይ ደርሶ ወደ ሰማይ ሲዓርግ የበረረበትን ተራራ ዳገት ማስመሰላቸው ነው ። ይህንን ክፉ ተራራ ሰው እንኳንስ ለመውጣት ለመቅረብ አይደፍርም ነበርና ልዑል የአብሩሲ ዱክ ወደ አሜሪካ ሲሄዱ የዚያውን የሚያስፈራውን ተራራ ወሬ ሰምተው ይኸውም የቅዱስ ኤልያስ ተራራ ከሚባለው ላይ እስተ ራሱ እኔ እወጣለሁ ብለው ተናገሩ እንዲህ ሲናገሩ ሕዝብ ሁሉ ደንግጦ ለልዑል ሕይወታቸው ፈርቶ ከዚያ ከሚያስፈራው ተራራ ዘንድ እንዳይሄዱ ምንም ቢለምናቸው ሰው ወጥቶበት ከማያውቅ ቦታ ላይ መውጣትና ሰው ደፍሮት ከማያውቅ ነገር ላይ መድፈር ለኛ ለነገሥታት ዘር የሚገባን ነውና የቅዱስ ኤልያስ ተራራ ከሚባለው ላይ እወጣለሁ ብለው ወደ አላስካ ተሻገሩ ። አላስካ ደርሰው ምንም ተሰማይ የወረደው በረዶና ተመሬት ላይ የነበረው በረዶ ሲደበለቅና ሲያስጨንቅ ምንም ገደልና የሚያስፈራ ዳገት መውጣታቸው ሲያስቸግር እስተ ቅዱስ ኤልያስ ተራራ ራስ ወጥተው የጀግንነታቸው ምልክት እንደሆነ የመንግሥታቸውን የኢጣልያን ባንዲራ ተክሉበት ከአላስካ ተመልሰው አገራቸው ሲደርሱ በትልቅ ደስታና ክብር ተቀበልዋቸው ።

ደግሞ የሰሜን ፖሎ ወደ ሚሉት ቦታ መሄድ አሰቡ ። የሰሜን ፖሎ ማለት የምድር አኳኋን እንደ ኳስ ነውና ከላይ ወደ ሰሜን ያለው ራስ የሰሜን ፖሎ ይባላል ከታች ወደ ደቡብ ያለው ራስ የደቡብ ፖሎ ይባላል ። የሰሜን ፖሎ የሚያስደነግጥ ቦታ ነው በሰሜን ፖሎ ዓመቱ ሁለት ቀን ብቻ ነው ሁለት ቀን ማለት ፀሐይም ሳይገባ ሌሊትም ሳይጨልም ስድስት ወር ሙሉ ብርሃን ነው ደግሞ በሚከተሉት ስድስት ወር ፀሐይ አይወጣም ቀን አያበራም ስድስት ወር ሙሉ ጨለማ ነው ወደዚያው ግሩም አገር ብዙ ሰዎች ሄደው ነበር ግን አንድም ሰው እስተ ፖሎ ቦታ ሄዶ አይታወቅም ነበር ። ስለምን ብላችሁ ብትጠይቁ የፖሎ አገር መሬት አይደለም የበረዶ ባሕር ነውና ስለብርዱ ስለ ባህሩ ደግሞ ሌላ አገር ታይቶ የማይታወቅ ስለዚያ አውሬ ስለሚበዛበትና ስለ ስድስት ወር ሙሉ ጨለማው አለ ቀን ስለ ስድስት ወር ሙሉ ቀን አለሌሊት ስለዚህ ሁሉ ይህንን አገር ደፍሮ የሄደው ሰው ሞትን ታልፈለገ ሳይቀርብ ተሩቁ ወደ አገሩ ይመለስ ነበር ። የአብሩሲ ዱክ ግን ወደ ሰሜን ፖሎ ለመሄድ ቆርጠው ተግርማዊ ንጉሥ ኡምበርቶ ፈቃድ ለምነው የተለየ መርከብ አሰናድተው ተነሡ ። የበረዶ ባሕር በሚጀመርበት ቦታ ሲደርሱ ተመርከባቸው ወርደው በረዶ የለመዱ የተለዩ ውሾች በሚስቡት ጋሪ ላይ ዕቃቸውን አስጭነው ወደ ፖሎ በረዶ ውስጥ ተጓዙ ። ተሰው ሁሉ ይልቅ ወደ ፖሎ እቀርባለሁ ብለው ተናገሩ የቀድሞ የሮማ ቄሳሮች ወደ ፊት መሄድ ያስፈልጋል እንጂ በሕይወት መኖር አያስፈልግም ብለው እንደ ተናገሩ የአብሩሲ ዱክ በረዶውን አውሬውን ጥልቅ ጨለማውን ደፍረው ገፍተው ሰው ደርሶበት ከማይታወቅ ቦታ ተፖሎ ቅርብ ለቅርብ ደረሱና ስማቸውን በዓለም ሁሉ አስከበሩና አስመሰገኑ ። ተሰሜን ፖሎ ወደ አገራቸው ወደ ኢጣልያን ሲመለሱ የአጎታቸውን የግርማዊ የንጉሥ ኡምበርቶ የሞታቸውን ወሬ ሰምተው እጅግ አዘኑ ደግሞ ግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል ነግሡና ያአብሩሲ ዱክ ሁለት ዓመት ኢጣልያ አገር ተቀመጡ ።

ኋላ ደግሞ እንደ ገና ተነሥተው ግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል ግዛው ንዳው ብለው በሰጡአቸው መርከብ ላይ ሁነው ዓለሙን ሁሉ ባሕሩን ሁሉ እየዞሩ እያዩ ሶስት ዓመት ሙሉ ተባሕር እስተባሕር ተሽግረው ኖሩ በእንግሊዝ ቅኝ አገር ክንያ በሚሉት አገር ትልቅ ተራራ አለ በአፍሪቃ ካሉት ተራሮች ሁሉ ይህው የኬንያ አገር ተራራ ቁመቱ ይረዝማል የተራራውም ስም ሩባንዞሪ ይባላል እሰማይ ላይ የሚደርስ ስለሚመስል የዚህ ተራራ ስም በጠገቡ በሚኖሩት ሻንቅሎች ቋንቋ የደመናዎች ተራራ ይባላል የቅዱስ ኤልያስን ተራራ እንደወጡ ወደሰሜን ፖሎ እንደ ሄዱ አሁንም ይኸው በአፍሪቃ ውስጥ የሚበልጠውን የደመኖችን ተራራ መውጣት ልዑል የአብሩሲ ዱክ አሰቡ ይኸውም አሳባቸው ለስማቸውና ለአገራቸው ለኢጣልያ ስም አጠራርና ክብር ብቻ እንዲፈልጉ ብለው አይደለም በዚያው በማይታወቅ በታ ላይ ሄደው ያገሩን አኳኋን እንደ ትምህርቱ ሕግ ተመልክተው የዓለምን ትምህርት ለማስፋት ብለው ነው እንጂ ስለዚህ በግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል ፈቃድ ወደ ክንያ አገር ሄዱ ። እዚያ ደርሰው መቼም አገሩ የክፉዎች ሻንቅሎች አገር ነው እንኳንስ ጨካኞችና ሞኞች ባላገሮች አገሩን የሚገዙት እንግሊዞችም ሲደነቁ ልዑል የአብሩሲ ዱክ እስተሩባንዞሪ እስተ ደመኖች ተራራ ራስ ላይ ወጥተው ተአፍሪቃ ተራሮች ሁሉ ከፍ የሚለውን የተራራውን ራስ የንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል ተራራ ብለው ስም አወጡለት ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ያስራትና የእርሻ ማሻሻል

ስለ ሀገራችን ስለ ኢትዮጵያ መንግሥት ጠቀሜታ የሚሆንለትን አገዛዝ ለብርሃንና ሰላም በተቻለኝ እርዳታ የን አክፍላለሁ ይህነኑም ያነሳሳኝ በብርሃንና ሰላም ስለ ሀገራቸው ብለው የሚደክሙና የሚአስቡ ክቡራን የኢትዮጵያ ልጆች ኢትዮጵያ የምትሰፋበትንና ኃይል የሚሰጣትን በማናቸው ነገር ማሻሻል የምታገኝበትንና የምትድንበትን ስለተናገሩ በዚህ ነገር ሐሳባቸው እጅግ ደስ ስላለኝ ነው ። እንግዲህም እንዲህ ከሆነ እስቲ ያስራት ነገር እንመልከት ኢትዮጵያ መንግሥት ከቆመበት ጀምሮ አሁን ድረስ የሀል አስራት ቀርቶ በቀምበር ፳ብር ቢቀበል ስንት ገንዘብ ሊሆን ይታወቃል ። እጅግ ጠቀሜታ ነበር ገንዘብ ስለበዛ የሚመጣን ችግር እንዲአቸንፈው የታወቀ ነው ፫ኛም የኢትዮጵያ መንግሥት እርሱም ተጠቅሞ ሕዝቡም ይጠቀሙበት ነበር ማለት እስቲ ይታሰብ ባመት የሚያገኘውን ገንዘብ ወይም ከ፲ሚሊዮን ሕዝብ ወይም ከ፺ሚሊዮን ሕዝብ በቀምበር ፪፫ብር ሲከፈል ታ፲ሚሊዮን ፳ሚሊዮን ብር አያገኝም እስቲ ፲ሩስ ይቅር ከ፺ሚሊዮን ፲፬ሚሊዮ ንብር አያገኝም ። የሀል አስራት ባመት ቢታሰብ እንደዚሕ ይሆን አይመስለኝም እህል በያይነቱ ቢከተት በስብሶና ነቅዞ ተጕሳቁሎ ቀረ እንጂ ምንጠቀመ ፬ኛም ሕዝቡ ይጠቀምበታል ያልኩት እስቲ በዚህ እሕል ምክንያት ድኃውን የሚጎዳበትንና የሚከስርበትን እንይ አስራት በደረሰ ጊዜ ይህኑ የሚሰበስቡ ጸሐፊና ዳኛ ደምበኛ የሚባሉ ባንድ ድሀ ቤት ሲያድሩ ሰላሳ እንጀራ ፪ገምቦ ጠጅ ፪ገምቦ ጠላ ፪ ድስት ወጥ እራታቸውን ግብዝ ይሰጣል በዚህም ብዙ መጓደድና መቀጮ አለበት ምኝታ አልተመቸንም እግራችነን አልታጠብንም ለእግራችን ቅቤ አምጣ ይሉታል ይህን በመሰለ መቻያ ሲያዳፉትለ፲ቁና እህል ብለው እንደምን ይጠቀማል ባመት ጠፍቶ ማለቱ ከቄጥር መጕደሉ ለመንግሥቱ ጥቅም መሆኑ ነወይ እንዲሁ ለራሱና ለሕዝቡ ጠቀሜታውን ያስብ ይመስለኛል ።

፫ኛም ፤ በኢትዮጵያ መንግሥት ውስጥ ያሉ መኳንንቶችና ሹማምንቶች በዚህ ድኃ ነገር ሰንፈው ይኖራሉ ። ለራሳቸው ማሳረስና ማስነገድ ይመስል እኛ ከድኃችን ያመት ግብራችንን ፤ ያመት አሥራታችንን ፤ የወር ጨዋችንን ታገኘነው ገባር ከተቀበልን ምን አለብን ስለ ማለት ነው ። ግብሩና የወር ጨዉ ቀርቶ አሥራቱ ብር ቢሆን እነሱስ ስንት በተጠቀሙ ፤ ለራሳቸውስ እንዴት በተጉ ፤ እርሻ ተግተው የሚበቃቸውን ያሀል ቢያርሱና ቢያሳርሡ ፪ንግድ እንዲሆንላቸው የታወቀ ነው ። ከ ገባራቸው ያመት አሥራት ሒሳብ ብር ሲያጠራቅሙ ባንድ በኩል እነሱ ሲያሳርሱ ለመግዛትና ለመሸጥ ይመቻቸው ይመስለኛል ። በዚህም ነገር የኢትዮጵያ መንግሥት መኳንንቶቹንና የሻለቆቹን በማናቸውም ሥራ ለሾማቸው ምኒሥትሮቹ ወታደሩን እስተ መሣሪያው አደንድኖና አወፍሮ ለመያዝ ይችላል ።

፬ኛም ፡ የእህል አሥራት ስለ ቀረ በእህል ወገን መንግሥቱም ይጐዳል ሕዝቡም ይጐዳል ይራባል እንዳይባል መንግሥቱስ የእርሻ ምኒሥትሩን ታትጋውና የሚመቸውን መሣሪያውን ታቀረበለት ታርሶ አያጠግብም አያተርፍም የሚል አለ ። ሕዝቡስ የእህል አሥራት ሲበላ የነበረው የብር ቀለብ ቢሰጡት ሸምቶና ነግዶ አያተርፍም አይጠግብም ይሆን ። ባላገሩስ እንዲህ ከሆነ ከጕዳት አልዳነም እንዳይል ያለ ሐሳብ እርሻውን አርሶ የበቃውን ይዞ ትርፉን ቢያቀናውና ቢነግድበት ጠቀሜታ አላገኝበትም ይላል ፤ አይመስለኝም ። የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ ፤ እኔ ከእናንተ እበልጣለሁ ብዬ አይደለም ። ይህን ሐሳብ መዘርጋቴ ፤ በጐደለ ሞልታችሁ ፤ በዘበው አቃንታችሁ ለሀገራችሁ ጥቅም እንድታሻሽሉት ስለ ማለት ብዬ ነው እንጂ አሁንም ቃሉ ስላልተካከለ ፤ አማሪኛው ስላልቀና ይቅርታችሁን እለምናለሁ ።

ደጃዝማች በላይ አሊ ሚ ።

መልስ ።

አቶ ማኅተመ ወርቅን ስለ ጠየቃቸው ቀይ ጐበዝ ፡፡

አቶ ማኅተመ ወርቅ ምላሹን አጥተውት አይደለም ዘመድ መፈለጋቸው ግን ሰው ሁሉ ከግብጽ በወጡ ጊዜ እንዲል ነው እንጂ ይህም አሳብ የብልህ አሳብ ነው ።

የኢትዮጵያ ሰዎች ከግብጽ እጅ የወጡ መች ነው ተመልሰውስ ወደምድረ ግብጽ የወረዱ መች ነው የሚል የዚህን ታሪክ የማያውቅ ሰው አለ አይመስለኝም ፤ ዳሩ ግን ታሪኩን በጭሩ ብጽፈው አያጐዳም ይመስለኛል ። ይህ ታሪክ በኢትዮጵያ ክብረ ነገሥትና ገድለ ተክለሃይማኖት አለ በፈረንጆችም አሁንም ታሪኩ እንደተከታዩ ነው የቀዳማዊ ምኒልክ የልጅ

ልጅ ድል ነዓድ በነገሠ በ፱፻፳ ዓ ም መንግሥት ከእስራኤላ
ውያን ከቀዳማዊ ምኒልክ ልጆች ወጥታ ለነገደ ዛጓ ፫፻፴፫
ዓመት ሙሉ ተሰጠች ። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ለእስራኤላ
ውያን ለኢትዮጵያ ሰዎች መንግሥታቸውንና ጵጵስናቸውን
አንድነት ባንድ ቀን መለሰላቸው ፤ የኢትዮጵያውን ሰው አቡነ
ተክለ ሃይማኖትን ከሌዊ ወገን የተወለደውን ይኩኖ አምላክን
ቀብተህ አንግሠው ብሎ ከእግዚአብሔር የተላከው መልአክ
በራእይ ተገልጾ ነገራቸው ፤ እርሳቸውም ይኵኖ አምላክን ቀብ
ተው አነገሡት ። ከእግዚአብሔር የተሾሙ ሊቀ ጳጳስ ሁነው
የኢትዮጵያ ሰዎች ግን ከእግዚአብሔር የተሾሙትን ያገራቸ
ውን ከህናት የተክለሃይማኖትን ልጆች ንቀው ተመልሰው
ጵጵስና ለማምጣት ብዙ ገንዘብ ይዘው ወደግብጽ አገር ዬወ
ርዱ ጀመር ። ለአጼ ይኩኖ አምላክ ግን ፲፭ ዓመት ሲገዙ
ሌላ ጳጳስ አልነበራቸውም ከአቡነ ተክለሃይማኖት በቀር ከአ
ቡነ ተክለ ሃይማኖት በኋላም ብዙ የበቁ ለጵጵስና የሚገቡ
መነከሳት እያሉ የኢትዮጵያ ሰዎች የግብጽን ሰው ሊያመጡ
ወደዱ ።

የኢትዮጵያም ሰዎች እንዲሁ በአጼ ይኩኖ አምላክ ጊዜ
በአቡነ ተክለ ሃይማኖት እግዚአብሔር የሰራላቸውን ሥራ ረስተ
ውት ሌላ ጳጳስ አመጡ ከግብጽ ሀገር በገዛ ወርቃቸው ላመ
ጡት ሰው ተገዙ በፈቃዳቸው የግብጽ ባሮች ሁነው ለመኖር
አሁንም እኛ የኢትዮጵያ ሰዎች በጣም ደስ የሚለን የእግዚ
አብሔርንም ኃይሉን የምናውቅ ከግብጽ ሁለተኛ በወጣን ጊዜ
ነው እንጂ በቀረውስ ደስም አይለን ቤተ ክርስቲያናችን ነጻነት
ካላገኘች አሁንም ለዚህ መሣሪያ ይሆን መወድስ አስከትላለሁ ።

በመልዕልተ ክህነ አሮን ሊቀ ክህናት ።
በአምሳለ እሳት ነደት ለእግዚአብሔር መዓቱ ።
ለአምላክ ግብጽ ምስል አምጣነ ፈጠሮ ውእቱ ።
እምወርቀ ዘአስተጋብኡ እስራኤል እሙንቱ ።
ወሕዝበ እስራኤል ያዕትቱ ።
ዕብነ ጽማዊ ዘቆመ ለእግዚአብሔር በፍኖቱ ።
ለሕዝቅያስኒ ንጉሥነ፤ መዋዕለ እድሜ መንግሥቱ ።
ፈጺሞ ከመ ኢኃልቀ ይትዓወቀ በትእምርቱ ።
ይግበእ ድኅረ፤ ኀበ ሰብአ ቤቱ ።
ለተክለ ሃይማኖት ፀሐየ ጽድቅ ሚመተ ጳጳሳት ጽላሎቱ ።

ዘእንግዳ ደስታ

ስለ በቀለ አበዬ መልስ ።

ወንድሜ ሆይ ያገር ልጅ መልስ እየተመላለሰ በጋዜጣ
ሲጨዋወት መልካም ምግብ ከወንድም ጋራ በፍቅር እንደ
መጋበዝ ለልብ ደስ ያሰኛልና ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል
በደስታ እንድታነብልኝ በማክበር እለምንሃለሁ ። ሥጋዊ ትም
ርት እየተማሩ ስለ ሀገሩ መናደድ ማንም አያጣውም ትላለህ
ስለ ሀገር መናደድንና መሞትን ካላጣኸው ክቡር ነጋድራስ
አፈወርቅ ስለ ሀገራቸው የሰው ያለህ ብለው ሲጮሁ አንተን
መሳይ ጀግና እንዴት ሳትረዳ ቀረህ ። ከሀገራችን ጳጳስ እናውጣ
የማለታችን አሳብ መንፈሳዊ አልመሰለህምን ንባቡ ሥጋዊ
ቢመስልህ ትርጓሜው መንፈሳዊ ነው ። ተሸፋፍኖ ቢተኙ ገልጦ
የሚወጋ ጌታ አለ ። ነገሩን ልብህ እየተረዳው ለምን በከህኑ
ብቻ ትፈርዳለህ በመምሕሩስ አትፈርድም አትፍረዱ ይፈረድ
ባችኋል እንዳለው ነው ። ክህኑን ወደ አሕዛብ አገር ገብተህ
አስተምር ብሎ የሚያዘውን ሹሙን መቼ አጣኸው ። ቀድሞ
ነበር እንጂ እንዲህ ብሎ መምከር ። አሁን የት ይገኛል መሆን
ያቡን አሽከር ። ሐዋርያትን ሁሩ ወመሐሩ ብሎ የላካቸው ሰማ
ያዊ አባታችን አይደለምን ፤ ከግብጽ ጳጳስ አናወጣም ማለታ
ችን፤እንዲሁ አንተ እንደጻፍከል ከግብፅ የመጡ ጳጳሳት ሁሉ
ለሀገራቸው ጥቅም እንጂ ለኢትዮጵያ ጥቅም ሲሉ እንኳን
የተማሪ ቤት በገንዘባቸው ማቆምና በአሕዛብ አገር ያለውን
ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ላሽከር ማደሪ አደረጉት እንጂ ለእንዳ
ንት ላለ ክህን መቼ ሾሙት ፤ አሁንም ምሣር በዛፎች ስር ላይ
ተቀምጦአል ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬን የማያፈራ ይቆረጣል
ወደ እሳትም ይጨመራል ። እነሆ የኢትዮጵያ ዛፎች መልካም
የጵጵስናን ፍሬ የግብጽ አዕዋፍ ሲበሉት የኖሩትን የማታፈሩ
ከሆናችሁ እንደ እሳት ወደሚአቃጥል ንዴት ትጨምራላችሁ
አብድ ይነውም ጊዜ ማዕረር ጊዜ ገሚድ በጽሐ ቃለ ማዕነቀ
ተሰምዓ በውስተ ምድርነ እንዳለው የዕውቀት ማዕረር ጊዜአ
ችን ደርሶአልና እንደ ሰነፍ በአዝመራ ወራት አታንቀላፉ
ያዝመራችን ጊዜ በከንቱ ካለፈ ኢትዮጵያ መራቧ አይጠረጠ
ርም የኢትዮጵያ ሽማግሎች ለምን ዝም አላችሁ ሲሆን በሀ
ገራችሁ ቤተ ክህነት ነጻ እንድትሆን እዘኑ ምከሩ ሳይሆንም
በመካከል ገብታችሁ አስታራቂ ሁኑ ፤ነገር ግን ከኢትዮጵያ ጳጳስ
እናውጣ ማለታችን ግብጾችን አያስቀይምም እነሱ አባቶቻችን
ናቸውና እኛ ልጆቻቸው በአዕምሮ ስንፋፋ ደስታ ይገባቸ
ዋል እንጂ ብልህ ልጅ እናትና አባቱን ደስ ያሰኛል መምሕ
ርም ስለተማሪው ዕውቀት እጅግ ደስ ይለዋል ተማሪም ከመም
ሕሩ የበለጠ ይሆናል ከመምሕሩ ይሻል ደቀ መዝሙሩ ይባላልና
ቅዱስ ዳዊትም ወእምኵሎሙ እለ መሐሩኒ ጠበብኩ ብሏል ።

ኃይሌ ሮባ ።

የጥያቄ መልሶች መልስ ።

ፆኸውና ፊታውራሪ አርአያ በቁ ፴ እንደጻፉት ። በግዕዝ
ድምፃቸው አንድ ሁኖ መልካቸው ልዩ ልዩ የሆነ ፊደላት አሉ
በዱሮ ኢትዮጵያ ቋንቋ እንደ ልዩ መልካቸው ልዩ ልዩ ድምፅ
ሳይኖራቸው አይቀርም፤ የዱሮ ሊቃውንትም የሚገቡበት ሥፍራ
ያውቁታል ጨርሰውም የሚያውቁት ጥቂቶች ሳይሆኑ አይቀ
ሩም በማሪኛ ውስጥም እነዚህ ልዩ ልዩ መልክ ሆነው በድምጽ
የማይለያዩ በግዕዝ እንዳሉ ገብተዋል ። ብዙ ሰዎችም በድምፅ
ስላልተለያዩላቸው የትኛው ፊደል እንደ ሚገባ አያውቁምና
እየ ተጠራጠሩ ይጽፋሉ የፊደላቱን አገባብ ስላአጡትም ባንድ
ዶብዳቤ ላይ ላንዱ ቃል ድምፃቸው አንድ ከሆነ ሁለት ዓይነት
ፊደላት ሊጽፉ ይችላሉ ። ፊደላቱ መልካቸው ተለያይቶ በድ
ምጽ ካልተለያዩ ለሚጽፍ ሰው ያስቸግረዋል ።

ፊታውራሪ አርአያ በ፳፱ተኛው መስመር መልሳቸውን
ይጀምራሉ ። እንደ ምን ትለኝ እንደሆነ ድምጻቸውና መልካ

ቸው በግዕዝና በራብዕ ይታወቃል፡ድምፃቸው ከመልካቸው ቢገጥም ራብዕ ግዕዝ ይለያቸዋል ። ሁሉ የሚገኘው በግሡ ነውና ግሡ ቢመጣ በጐን በጐኑ የፊደሉን መልክ እጽፋለሁ ከዚህ በኋላ ሁሉም በግሡ ይታወቃል፤ ሲሉ መልሳቸውን በግሡ መምጣት ይጨርሱታል ግሡ ግን እግር እንደ ሌለውና ሰው ካልጻፈው አለመገኘቱን ዘንግተውታል መሰለኝ ።

ጠያቂው አጠያየቁ ዛሬ በምንነጋገርባቸው ባማረኛ ፊደላችን ውስጥ ባሉት ከግዕዝ በመላው መጥተው የሚያስቸግሩትንና ያለጥቅም ጊዜና የሌለንን ወረቀትና ቀለም መጨረሻ የሚሆኑትን ትርፍ ፊደላት ለማስመርመር ነበር እንጂ በግዕዝ ደብዳቤ ቢጽፍ (ስንጽፍ)ያስቸገሩትና አገባባቸውን ያጣባቸው ይሆን አይመስልም ።

ያማሪኛ ቋንቋ ከግዕዝ የወጣ ቢሆን እጅግ እንደተለዋወጠ እንደሚራራቅም ማንም ያውቀዋል ። ያ የግዕዝ ቋንቋ ባማሪኛ እንደተለወጠ እንደዚሁ ፊደላቱም ሥራቸው አንድ ሆኖ መለዋወጥና ማነስ ወይም መጨመር በንግግሩ ዓይነት በግድ የሚያስፈልግ ነው ። አሁንም ቢሆን ከግዕዝ አማሪኛ እንደተለየ ለግዕዝ የሚያስፈልጉትን ፊደላት ለግዕዝ ቋንቋ ላማሪኛ የሚያስፈልጉትን ላማሪኛ መለየት ነው እንጂ ያሮጌውን ቋንቋ ፊደላትና ያዲሱን አንድ ላይ ስርፋ ለማጣበብና ለማደነጋገር ለምን እንከብታለን ። አያቶቻችንና አባቶቻችን ብልሐት ቢያንሳቸውና እርስ በርሳቸው ስምም ሳይኖራቸው በመቅረቱ ፊደላቱን መርጠው መክረው ተማክረው ሳይዙ እንዲያው እንዳሉ የግዕዝን ፊደላት የሚያስፈልጉአቸውንም አዲስ ፊደላት ጨመሩባቸው እንጂ እንደሚገባ የደነገጓቸው አይመስለኝም ።

ፊታውራሪ አርአያ የሰጡትን መልስ ከነምሳሌው ብንመለከተው ለግዕዝ ቋንቋ እንጂ ላማሪኛ የሚጠቅም የለበትም ። ምንም የጥያቄውን ቃል ባላየው የሳቸው መልስ እንዲህ ይላል ባማሪኛ ውስጥም እኒህ ልዩ ልዩ መልክ ሁነው በድምጽ የማይለዩ በግዕዝ እንዳሉ ገብተዋል ይላልና ጠያቂው የጠየቀው በውነት ባማሪኛ ፊደል የተነሳ እንደሆነ ያስረዳል ። አማሪኛና ግዕዝ የተለያዩ ቋንቋ ናቸው እንጂ አንድ ቋንቋ ሆነው ባንድ ዓይነት ፊደል ብቻ የሚጻፉ አይደሉም ። ባማሪኛ አንዲት ደብዳቤ ወይም መጽሐፍ ለመጻፍ ብንፈልግ እነ ሸ ቸ ኘ ዠ ጀ ጨ ያስፈልጉናል ። በግዕዝ ግና እጅግ ጭራሽም አያስፈልጉም ። እነ ሐመሩ ሐ ብዙኃኑ ኃ ንጉሡ ሠ ዓይኑ ዓ ፀሐዩ ፀ አራቱ ፊደላት ቈ ኰ ጐ ጐ ደግሞም ሌሎች ለግዕዝ የሚጠቀሙ ላማሪኛ በብላሽ የሚያውኩ በፊደላቱ መካከል አሉ እነ ሃ ኣ ዩ ጺ ለነዚህ ሁሉ እኛ ስርፋቸውን ካልሰጠናቸው ማወካቸው አይቀርም ። ማለት ለግዕዝ የሚጠቀሙትን ለግዝ ላማሪኛ የሚጠቀሙንን ላማሪኛ መስጠት ነው ። ጌታም በማቴዎስ ወንጌልም ፳፪ ቁ ፲፯ ፈሪሳውያን ንገረንም ምን ይመስልሃል፤ ይገባልን ለቄሳር ግብር መስጠት ወይስ አይደለም ? ቢሉት በቍ ፳፩ አላቸው ። እንኪያስ የቄሳርን ለቄሳር ስጡ የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር ስጡ ሲል ያስረዳናልና የግዕዝን ፊደላት ለግዕዝ ያማሪኛን ላማሪኛ በመስጠት ጥቅማችንን እንኳ ባናስበው በግድ የሚያስፈልገን ይመስላል ።

ፊታውራሪ አርአያ ከሰጡት መልስ ውስጥ ባማሪኛ ፊደል በኩል ምንም ጥቅምና ምክር ያገኘንበት የለም ። ቢሆንም አሮጌውን ቋንቋችንን እንዳንዘነጋ የሚያስታውስ ትልቅ ምክራቸውን ሰጥተዋል ። ማን ሊሰማቸው ይሆን እንጂ ? በዚህ በዱሮው ቋንቋችንና መጻሕፍቶቻችን ጥበቦቻችን ሊአስቡበት የሚገባቸው ጳጳሱና ሊቃውንቱ ነበሩ የኛ ጳጳስ የምናውቃቸው የውጭ አገር ሰው ስለሆኑ እንኳን ላሮጌው ቋንቋችንና ዛሬ የምንነጋገርበትን «ሊያስተምሩበት የሚገባቸውን» ቋንቋችንን እንኳ እጅግ እንደማያስቡበት ሁላችን የምናየው ነው ።

ሌሎቹም ያገራችን ምሁራን ቀሳውስት እሳቸውን እየተከተሉ ለካህናት ያልታዘዘላቸውን ንዋይ ሲሰበስቡ ይኖራሉ እንጂ የቤተክርስቲያናችንን ቋንቋና ብልሃት ለማስፋትና ባገራቸው ውስጥ ያለውን አረመኔ ለማስተማርና ለማጥመቅ እንኳ አያስቡም ። የግሪካውያን ካህናቶች ይሁኑ የሮማውያን እንደኛው የዱሮ ቋንቋቸውን ለቤተ ክህነት ሰጥተዋል ። እነሱም ይኸንን ቋንቋ በቅጡ ሳያውቁ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት አይበቁም ጳጳሱና ሊቃውንቱ ካዲሱ ቋንቋ ይበልጥ አሮጌውን ነው የሚአውቁት ። የኔ አገር ጳጳሶችና ሊቃውንቶች እንኳን ቋንቋውን አውቀው ሊነጋገሩበትና በዚያ ቋንቋ የተጻፉትን መጻሕፍቶች አንብበ መተርጐም የሚችሉ እጅግ አይገኙም ። ቀሳውስት የሚባሉትስ በጥቅሉ ማንበብም አይችሉ ይመስለኛል ። አንዳንዶች እንዳሉ እንዳይቀየሙብኝ እለምናለሁ ። እኔም በትንሽ እውቀቴ በማርቆስ ወንበር ለተቀመጡት ብጹዕ እጨጌአችንና ለመምሕራኑ ፊታውራሪ አርአያ ያስታወሱትን እንዲአስቡበት ብሩህ ልቡናቸውን አሳስባለሁ ። በዚህ ወገን ካህናቶች ሊያስቡበት የተገባቸው ነው እንጂ መንግሥትን የሚያስፈልግ ነገር የለበትም፤ቢሆንም መንግሥት የማይገባበት ነገር ከቶ የለም ። አሮጌዎቹን መጻሕፍቶች ከዱር ከገደሉ ኢያሰበሰባችሁ ብታሳትሙና ፀሐይ ብታሞቁት የዱሮውን ቋንቋና ብልሐት ብታስለምዱ ኢየዞራችሁ አህዛቦችን በክርስቶስ ስም ብታስተምሩና ብታጠምቁ ለናንተ የዘለዓለም ክብረት ላገራችሁ ትልቅነት እንደ ተሰጣችሁ እናንተ ከኔ ይበልጥ እንድታውቁት አውቃለሁ ። ይኸንንም ክብረት ለማግኘት እንዳታደርጉ አውቃለሁና ቢሆንም ባይሆንም በጠባብ እውቀቴ አስታውሳችኋለሁ ። ብርሃንና ሰላም ነገር ስላረዘምኩ እንዳትሰለቸኝ እየለመንኩ ወደ ጀመርኩት የፊደላት ነገር እመለሳለሁ ።

ትንሹ ተማሪ በውጪ አገር ያለው መ ሥ ወ ።

ከዚህ የቀረው በሚከተለው ቁጥር ይታተማል ።

ያገር ውስጥ ወሬ ።

ጅሩ በሚባለው አገር የሚያልፈውን ነጋዴ የገንዘብ ጥፋት ያስፈራዋል። ከብትም ይሠረቅበታል እየተባለ ሲወራ ሰምተን ነበር ። አሁን ግን የጅሩ ሕዝብ የሚያስመሰግነውን ቁም ነገር ጀምሯል ። ከዛሬ ሁለት ወር በፊት ያገሩ ሽማግሎች ተሰብስበው እንግዴህ ዘወትር ባፈርሳታ ስንጨነቅ ከመኖርና ያዳፋኝ የሹም ራት እየተባለ ገንዘባችንን ስንጨርስ ከመኖር ክፉ አድራጊውን አጥፍተን አገራችንን ብንጠብቅ ይሻላል ብለው መክረው ጕልማሳ ጕልማሳውን መርጠው ዘበኛ

አቆሙ ። እንዲህም የተደረገው ጅሁር በሚባለው ስፍራና በል ዑል አልጋ ወራሽ ጉልት በዲላሞ ነው ። እነዚህም በሀገር ፈቃድ የተመረጡ የሀገር ዘበኞች ዘመድ ወዳጅ ብለው እን ዳይለዩ አባት ልጁን ፡ ወንድም ወንድሙን እንዳይለቅ በጽኑ መሀላና ግዝት ተወሳስነዋል ። ሌሊቱንም ሁሉ በየቦታው እየ ዞሩ ከሌሊቱ ፩ሰዓት በኋላ ማናቸውንም ሰው ወዲያ ወዲህ ሲል ካገኙት አሥረው አምስት ብር ይቀበሉታል ። ሌላም ክፉ ሥራ ሲያደርግ ቢያገኙት አሥረው ወደ ሕዝብ ሹማምንቶች ያደርሱ ታል ። ደመ ወዝም የሚያገኙ ከሕዝቡ ላይ ነው ። የሆነ ሁኖ ጅሩ ሌባን ለማጥፋት ትጣጣራለች ። ከመሸ በኋላም ከቤቱ ለመ ውጣት የሚደፍር የለም ።

እኔም የሥርዓታቸው መጽናት እስደነቀኝና እረ ይህን ሐሳብ የጀመራችሁበት ምክንያቱ ምንድነው ብዬ አንዱን ሽማ ግሌ ብጠይቀው ዋ ልጄ ሆይ በኔ ዕድሜ እንኳ አፈርሳታ እየ ተባለ ስንቀጠቀጥ ከመቶ ጊዜ ይበልጣል ። በያንዳንዱም ጊዜ ፫፫ ፬፬ ወስሳታ መውጣቱና መያዙ አልቀረም ። ዳኑ ግን የሚሄ ደው ወደ ዳኞች ቤት ነውና ሠርቶ ቀምቶ ያጠራቀመውን ያለ የሌለውን ገንዘብ ለዳኛው ያሸክመውና በሰምንቱ ያገሩን ዘፈን እየዘፈነ ከተፍ ይላል ። ባላገርም ባየው ጊዜ ንይኑ ቀጠል ይመስልና ልቡ ዱጭ ዱጭ ይልበታል ። ቤቱን ያቃጥለዋል ፤ ከብቱን ይዘርፈዋል በማለትም በመንልትና በሌሊት ዕረፍት አጥቶ ይኖራል ። በእንደዚህ ያለ ምክንያት እውነት መናገር ለባላገር አይቀናውም ነበር ።

አሁን ግን ጠቡ ከልቀረልን እኛው እየያዝን እንቀጣው ብለን ነዋ ልጄ አለኝና ወደ፡፡ሥራው ሄደ ይህን የመሰለ ሥራ በየገሩ ሁሉ ቢለመድ ለመንግሥታችን ትልቅ እርዳታ በሆነ ነበር ። የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።

የከች ገጋር ባዲስ አበባ መግባት ።

መሐራጃ ድራጅ ሚርዛ መሐራው ሹሪ ኬንጋርጂ ሱዋይ በሕዲር የተባሉ የከች አገር (በሀንድ) ገጋር በሚያዝያ ፳፯ ቀን በ፲፩ ሰዓት አዲስ አበባ ገቡ ። ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ያገር ግዛት ሚንስትርና ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ከብዙ መ ኳንንትና ሠራዊት ጋራ ብዙ ሀንዳውያንና የውጭ አገር ሰዎ ች በክብር ተቀበሏቸው ።

ካገራቸው ከተነሱ አንድ ወር ይሆናል በተሀራ በተባለ አገር ፲ ቀን ያህል አደን አድነው አጋዘንና እንዲሁ የመሰለ እንስሳ ገደሉ ። በአዲስ አበባ አራት ቀን ያህል ቆይተው በአሩሲ በኩል ሒደው በበርበር አልፈው ወደ አገራቸው ይመለሳሉ ። ብርሃንና ሰላም እንኳን ደኅና ገቡ ይላል ።

በቴሌግራም የመጣ የውጭ አገር ወሬ ።

ሮማ ፣ ዱካ ዴዝ አብሩሲ ከጋስፓሪኒ የኤርትራ ገዢና ከጓሪልያ ባለ ሙሉ ሥልጣን ምኒሥትር ። ከዱካ ፍራኚቶ የመ ንግሥት ቢትወደድ ። ከማሉዘርዲ የመርከብ ሹም (ካፒታን) ከዲ ቹቲስ ቆንሲል እንደራሴ ጋራ ሚያዝያ ፲፯ቀን (ኣብሪል ፳፭ቀን) ቬኔስያ በተባለ የቤተ መንግሥት መርከብ እንደ መንግሥት መዓርግ ሆኖ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ተፈሪ መኰ ንንን ለመጐብኘት ወደ ኢትዮጵያ ለመሄድ ተነሣ ።

Rome— Le Duc des Abruzzes accompagné de M.Gasparini, gouverneur de l'Erithrie; de M.Guariglia, Ministre Plénipotentiaire; du Duc Fragnito, Maitre des cérémonies de S.M.le Roi, du capitaine de frégate Malusardi et du vice Consul de Ciutis s'embarquest aujourd'hui à Naples á bord du navire Royal Venezia á destination d'Abyssinie pour rendre visite officielle au Régent Tafari-Makonnen.

ከታይምስ ጋዜጣ የተገለበጠ ።
የባሪ ነጻነት ማህበር አደጋ(በበርማ) ።

የበርማ አገረ ገዢ ስር ሐርኩት በትለር ፤ በምድር ሕንድ እንደራሴ በኩል ቀጥሎ የተጻፈውን በቴሌ ግራም ወደ ሎንዶን አሳለፈ ። የባሮ ነጻ ማህበር ባገኘው አደጋ ከእንግሊዝ ሹማም ንት አንድ ጀግና ካፒቴን ። አንድ አጋን ሲንገ የተባለ ህንዲ ፈረሰኛ ከነተከታዩ ሞተ ። ሶስት ሰዎች ቆሰሉ ፤ አንድ ቱርጁማ ን የሄደበት ሳይታወቅ በዋለው ቀረ ብሎ ለምድረ ሕንድ እንደ ራሴ እየዘነ ከስታወቀ በኋላ ስልክ ስለ ተበጠሰ ያደጋውን ንሽ ልንሰማው እስካሁን አልቻልንም እንጂ የሚበቃ ጦር ልከናል ። በናጋ ኰረፍታዎች አውራጃ በስተምዕራብ ዳግመኛ ጦር ተልኮዋል ፤ በሁክዋንግ ሸለቆ አውራጃ ባለፈው ዓመት አያል ሽህ ባሮች ነጻ ወጡ ፤ የበርማን አገር ባሮች ነጻ ለማውጣት ሲል እንግሊዝ ይህን ያህል ለሰው ልጅ የተከላከለበት ወደፊት በታሪክ ተጽፎ ይኖራል ። በካችንና በናጋ ወረዳ መካከል ፤ ባለፈው ዓመት የዘመተው ጦር 3,445 ባሮች ከባርነት ነጻ አውጥቶ ፤ ባሁኑ ዓመት ባሮቹ ደስ ብሏቸው በየቤታቸው ተቀምጠው ተገኙ ። ያሁኑ ዘማች ደግሞ ጉዞውን ወደ ሰሜን እያቃና ስለሄደ ፤ እስካሁን አንድ ነጭ ባልደረሰበት ስፍራ በከፉው ነጋስ በተባለ ከተማ አልፎ ሄደ ። አገሬው በየስፍራው ፤ በያውራጃው ፤ ታጥቆ ተሰልፎ በየበረቱ ውስጥ ደፍጦ፡በዙሪያው ስፍራው ሁሉ ወጥመድ ብቻ ሁኖ ይታያል።ሌሊት ወንድ ወንዱ ጠመንጃውን ታቅፎ ይተኛል።

የከቲት ፲፭ ይህ ወሬ በተሰማበት ቀን በሑኮንግ ሸለቆ ወረዳ በደሉ(የስፍራ ስም)፤ሁኑ ዘማች ደርሶ ፤ ሰው ከሚተላለ ቅበት ስፍራ ከመግባቱ በፊት ስንቅ ለማደራጀት ቆይቷል ይባ ላል ። በዚህም ዘመቻ ፭ሺ ያህል ባሮች ከባርነት ነጻ እ[illegible]ዲወጡ ተስፋ ተደርጓል ። በጥር ወር ፩ የካቺን ከተሰበሰበበት ጉባኤ ስር ሐርኩት በትለር (የበርማ አገረ ገዢ)ቀጥሎ የተጻፈውን ተናገረ ። የእንግሊዝ መንግሥት ሕግጋት እስከ ፍጻሜው የማ ይለወጥ የጸና ነው ። ባይሆን የኪሳራችሁን ግምት ተመንግሥት ትጠይቃላችሁ እንጂ ። ከእንግዴህ ወዲህ ። ባሮ በገር ውስጥ መሼጥና መለወጥ ። ስለ ዕዳ ማስገምገም ። በጋብቻ ውስጥ ስለ ገንዘብ መቀጠር ፤ ወይም በክፍያ ለመውሰድ በጽኑ ክልክል ነው ። በዚያ አገር የደህና ባሮ ዋጋ ፬፻ ሩቢያ (፲፭፻)ወይም በዓጕሽ ይለወጣል ።



በኤሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ከዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ተኩል ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፹፩ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፺ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፭ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፭ ብር ።
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፻፴፫ ብር ።
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፳፯ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፰ ብር ።
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፰ ብር ።
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፵፫ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፬ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፬ መ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፭ ፍራንክ	፯
በአንድ ብር	፳ ሊሬ እስከ ፯ ሳንቲም	
በአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፴፩ ሳንቲም	
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር ተ፫ ሩብ ።	

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል ።

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

ሩግ ቢ





የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው ።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዴልፊአ በቦስቶን በማድራስ፥በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፥ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆ የአጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመከከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፌታውራሪ ጴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሂስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

Berliet



ቤርሊዮ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዮ አቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

AMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኤዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶክለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የኦዶክለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፈልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተከሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ። የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፲፱
3 me ANNÉE № 19

ሐሙስ ግንቦት ፬ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 12 MAI 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር
ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Diréecteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የልዑል ዱክ ዴዝአብሩስ ወደ ኢትዮጵያ አመጣጥ ።

የ፮፴፱ ገጽ ተከታይ ።

ተዚያ ተመልሰው ባሬስ የሚሉት የታላቅ መርከብ ሹመት ተሾሙ ኋላ ግን የኢጣልያና የሰሜን አሜሪካ መንግሥት ወዳጅነትን ለማጥናትና ለማስፋት ብለው ግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል የአሜሪካንን ፕሬ ሲዳንት ለመጐብኘት የአብሩሲን ዱክ ወደ አሜሪካ ላኩ ተኢጣልያ ንጉሥ ዘር የተወለዱ ፕሪ ንስ ወደኛ ይመጣሉ ብለው የአሜሪካ ሕዝቦች ደስ ሲላቸው ንጉሥና የኢጣልያ ሕዝብ ሁሉ ተማናቸውም ትልቅ መኰንን የሚወደዱና የሚፈቀሩ የአብሩሲ ዱክ ተልከውልናል እያሉ ሲያወሩ የኢጣልያና የአሜሪካ ትልቅ የወዳጅነት ምልክት እንደ ሆነ አወቁ ። ስላዚህ መቸም ተዓለም ሁሉ የአሜሪካ ሰዎች ባለ ጸጎች ናቸው በሚያስደነግጥና በሚያስደንቅ ክብር የአብ ሩሲን ዱክ ተቀበሉ። የአሜሪካና የኢጣልያን ወዳጅነት ተዚያው የአብሩሲ ዱክ ወደ አሜሪካ ተደረሱበት ቀን ጀምሮ እየጠነከረ እየጠና ሄደ ። ጦር የተነሣ ጊዜ አሜሪካና ኢጣልያ አብረው ተዋጉ ፣ ጦርነት የተጨረሰ ጊዜ የዓለም ሁሉ መንግሥቶች በጦርነት ጊዜ በተበደሩት ገንዘብ ከአሜሪካ መንግሥት ጋራ ሲከራከሩ የአሜሪካና የኢጣልያን ወዳጅነት ተመልክተው የአ ሜሪካ መንግሥት አለቆችና የኢጣልያ መንግሥት መልክተ ኞች አለመከራከር አለ መዘግየት አብረው ተስማምተው ውል ተዋዋሉ ።

የህንድ አገር ደቡብ ቆላ ሰሜኑ ደጋ ነው። ተዚያው ደጋ አገር ወዲያ ከራኮሩምና ሂማላያ የሚሏቸው ረጂም ተራሮች አሉ ከራኮሩም ተራራ አገርና ህንድ አገር መካከል ሁኖ ወደ ቺና ቆላ ወደ ህንድ ቆላ ፈሳሾች ወንዞች ይለያያል ። ተዓለሙ ሁሉ የሚረዝሙ ተራሮች ከራኮሩምና ሂማላያ ስለሆኑ ስማቸውን የዓለም ጣራ ብለው አወጡ ። በሚያስፈራ በቅዱስ ኤልያስ ተራራና ተአፍሪቃ ውስጥ በሚረዝም በሬብንዞሬ በዱመኖች ተራ ራላይ በጅግንነታቸው ስማቸውን የተከሉ ፣ ልዑል የአብሩሲ ዱክ ወደ ዓለም ጣራ ወደ ከራኮሩም ሊሄዱ ተመኙ ። ከሕንድ አገር ደርሰው እንግሊዞችና ሕንዶች በደስታ ተቀበሏቸው ። ኋላ ደግሞ የምድር ባቡር እስተሚደርስበት ቦታ በምድር ባቡር ሄደው ተዚያ ወዲያ እንደ ሕንዶች ሥርዓት በለማዳ ዝሆን ላይ ተቀምጠው ሲጓዙ ተተራራው ስር ደረሱ ፤ ከደረሱ በኋላ እርሳቸውና ተከታዮቻቸው ተራራውን መውጣት ጀመሩ ። የተራራው ርዝመት ሰባት ሺህ ሜትር ከባሕር በላይ ነውና እስከዚያው ቀን ድረስ ሰው ከባሕር በላይ ወጥቶ አምስት ሺህ ሜትር አልፎ አይታወቅም ነበር ። ከአምስት ሺህ ሜትር በላይ መውጣት የሚከለክለው ምክንያት እዚያ ላይ አየሩ ቀላል እየሆነ የሰውን ሳምባ በጣም አይገባም ፤ የሰውን ልብ እንደ ሩጫ ያስኬደዋልና ሰውነቱን ሁሉ ያንድላል ። ዳሩ ግን ልዑል የአብሩሲ ዱክ ወደ ከራኮሩም ተራራ ሳይወጡ በፊት ከተመሰ ገኑ ሐኪሞች ጋራ ተማክረው የተለየ መድኃኒት ተቀብለው በምክርና በብልሓት በትምሕርት መሄዳቸውን አቅንተው አንድ አንድ ተከታዮቻቸው መውጣት ያልተቻላቸው ከመንገድ ላይ ሲቀሩ እርሳቸው እስተከራኮሩም ተራራ ራስ ደርሰውና የሕንድ አገር ወንዞችና የቺና ወንዞች መለያያቸውን ተሰው ሁሉ በፊት አግኝተው ተመልክተው ለዓለም ሁሉ አዋቂዎች በትምሕርታ ቸው አሳዩ ። ይህንን ሲያደርጉ ስማቸው ተሕንዶች ዘንድ እጅግ የከበሩና የተመሰገኑ ሆኑ ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ስለ ትሪፖሊ ግዛት የኢጣልያ መንግሥ ት ከቱርክ መንግሥት ጋራ ጦርነት ይዋጋ ጀመረ ። ጦርነት የተጀመረ ጊዜ ግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል አንዱን የመርከቦቹን ጦር ወገን ለአብሩሲ ዱክ ሰጥተው የኛ ጦር ወደ ትሪፖሊ ሲሻገር የቱርክ መንግሥት የጦር መርከቦች እንዳይ

መጡብን አንተ በሰጠሁህ መርከቦች ቱርክን ከልክል ብለው አዘዟቸው ። ልዑል የአብሩሲ ዱክ ከነመርከቦቻቸው አዲሪያ ቲክ በሚሉት ባሕር መውጫ ሂደው የቱርክ መርከቦች ከጠረፋቸው ወደ ውጭ እንዳይወጡ ይከለክሉ ጀመሩ ።

ልዑል ዱክ ዴግ አብሩስ ።

እዚያ ላይ ሳሉ የቱርክን መርከቦች ፕሬቤዛ በሚሉት ቦታ ላይ አግኝተው ተዋግተው ቱርክን ድል አደረጉና መርከቦችን አሰጠሙ። የቱርክ ጦርነት ሲጨረስ ሶስት ዓመት ሙሉ እርቅና ሰላም ሆነ ኋላ ግን የዓለም ጦርነት የተባለው ተጀመረ ። ይኸው ትልቅ ጦርነት ሲነሣ ልዑል የአብሩሲ ዱክ አሚራልዮ የሚሉትን መዓርግ ተቀብለው ተኢጣልያ የጦር መርከቦች ሁሉ ላይ ተሾሙ ። ተአውስትሪያ ጋራ ሲዋጉ ያደረጉት ግሩምና ድንቅ ነገር በዓለም ታሪክ ለዘለዓለም ተጽፎ አለ ። አንዱን ብቻ እንድናስታውስ የሴርቢያ ጦር ታሪክ እዚህ ቀጥለን እንናገራለን ። የሴርቢያ ንጉሠ ግርማዊ ጴጥሮስ ካውስትርያ ጦር ጋራ ተዋግተው ድል ሆኑ ። ስለዚህ የሴርቢያ አገር ሁሉ በአውስትሪያዎች እጅ ተያዘና ንጉሥ ጴጥሮስ ተቀረላቸው ጦር ጋራ ወደ ባሕር ጠረፍ ሸሹ ። ንጉሥ ጴጥሮስ ተነጦራቸው ከባሕር ዳር አጠገብ አመለጡ ብለው ሰላዮች ሲያወሩ የሴርቢያን ጦር ጭራሽ ለማጥፋትና ንጉሥ ጴጥሮስን ለመያዝ የአውስትርያ ንጉሠ ነገሥት ብዙ ጦር ወደባሕር ዳር ሰደዱ ። ያንጊዜ በሴርቢያ ጦር መካከል ክፉ በሽታ ወድቆባቸው ነበርና ንጉሥ ጴጥሮስ ራሳቸው ታመሙ ። ስለዚህ ከትልቅ ከአውስትሪያ ጦር እንደ ገና መዋጋት አይቻላቸውም ነበርና የሴርቢያ ጦር ነገር የሚያስጨንቅ ሆነ ። ልዑል የአብሩሲ ዱክ ይህነን ሰምተው የሴርቢያ ንጉሥ ጴጥሮስ የኢጣልያ ንግሥት የግርማዊት እሌኒን እኅት አግብተው ነበርና ኢጣልያና ሴርብያ አብረው ከአውስትሪያ ጋራ ተዋግተው ስለነበሩ የሴርቢያ ጦር በአውስትሪያዎች ኃይል እንዳያልቅ ተመርከቦቻቸው ሁሉ ንጉሥ ጴጥሮስ ወደነበሩበት ባሕር ዳር ቀርበው ጦሩንና ንጉሡን ወደ ኢጣልያ ለመውሰድ አሰቡ ። ይኸው አሳባቸው ምንም ድንቅ ጀግናነታቸውንና ድፍረታቸውን ቢያስረዳ የሚያስቸግር ነበረ ። ስለምን ማለት እዚያ በሕር ዳር አጠገብ የአውስትሪያ የጦር መርከቦች ተሰብስበው ነበርና የሴርብያ ጦር በኢጣልያ መርከቦች ላይ ሲወጣ ወይም ኋላ የኢጣልያ መርከቦች የሴርቢያን ጦር ይዘው ሲሄዱ ካውስትሪያ መርከቦች መዋጋት ጭንቅና ችግር ይሆን ነበር ። የሴርብያን ጦር ለማደንና ለመያዝ የሚያስተውሉና የሚሰሩ የመርከብ አለቆች እንደምን አድርገው በዚያው ጊዜ ካውስትሪያ ትልቆች መርከቦች ጋራ መዋጋት ለማሰብና የሚያስፈልገውን ለማዘዝ ይቻላቸው ነበር ።

እንደዚህ ብለው አንዳንድ ሰዎች ሲጠራጠሩ የአብሩሲ ዱክ ተነመርከቦቻቸው ባሕርን ተሻገሩ የመርከቦችን አንድ ወገን ንጉሥ ጴጥሮስ ወደነበሩበት ጠረፍ ሰደዱ ሌላውን ወገን ይዘው እርሳቸው ራሳቸው የአውስትሪያንመርከቦች ለመከልከል ሒዱ ከአውስትሪያ መርከቦች ጋራ ዱራሶ በሚሉት ቦታ አጠገብ ተገናኝተው አውስትሪያን ድል አደረጉና ሁለት መርከቦችን አሰጠሙ ፡ደግሞ የመርከቦቻቸው ሌላው ወገን የሴርብያን ጦርና ንጉሥ ጴጥሮስን ለመያዝ ከባሕር ዳር ቀርበው የአውስትሪያን ጦር በመድፋቸው መትተው ሲያባርሩ ሴርብዮችን ሁሉ ተነንጉሣቸው ተዚያ ቦታ አውጥተው ይዘው ወደኢጣልያ አመጡ ፡ልዑል የአብሩሲ ዱክ እንደህ አድርገው የሴርብያን ንጉሥ አዳኑ ። በጦርነት ጊዜ ያደረጉት ልዩ ልዩውን ነገር ብንጽፍ ታሪካቸው አያልቅም ነበር ። ስለ ዚህ ከብዙ በጥቂቱ ከፍለን እላይ ያለውን ጽፈናል ። ጦርነት ከተጨረሰ ወዲያ ልዑል የአብሩሲ ዱክ ወደሱማሌ አገር ሂደው ለሕዝባቸው ጥቅም እዚያ ቆላ ጥጥ ለመትከል እንዳሰቡ የታወቀ ነው ፤ በዚያው ክፉ ወባ በሞላበት ቆላ የአብሩሲ ዱክ ያደረጉትን ሥራ ሰው ሁሉ ሰምቶዋል ፡ ቀድሞ ስለ በሽታውና ስለ ጨካኞች ሱማሎች የውጭ አገር ሰው ተቀምጦበት የማይታወቅ ዱር ጫካ አገር አሁን በርሳቸው ፈቃድ እርሻ የሚበዛበት ፍሬ የሚመላበት አገር ሆነ ፤ እኒህን ያህል ፕሪንስ በዓለም ሁሉ እንዲህ የተወደዱና የተመሰገኑ ትልቅ መኰንን ዛሬ በግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል ፈቃድ ወደትልቂቱ ኢት

ዮጵያ ተላኩ የልዑል የአብሩሲ ዱክ ወደኢትዮጵያ መምጣት የኢትዮጵያንና የኢጣልያንን ወዳጅነት እያሰፋ እያጠና እያጠነከረ ለዘለዓለም ይኖራል ።

የ፻፵፮ ገጽ ተከታይ ።

የሁለተኛው መልስ መልስ ።

እስቲ የክቡር አቶ መኰንን ኢያቄምን መልስ ቍ ፴፫ እንመልከት ፤ እነዚያኑን ፊደላት ሊቃውንቱ እንዲመክሩበትና እንዲያከናውኑት መባሉ ንግግራቸው በዘመን ብዛት ይፋለስ እንጂ አስቀድሞ የተመከረበትውና የተከናወኑ አይደለምን ፡ ደግሞ ከነዚህ አንዱን መያዝ ይሻላልን ፡ ወይስ የሁሉም ስፍራ ስፍራቸውን ለይቶ ማወቅ ምንስ ቢፋለሱ በድምፅ አንድ ይሁኑ እንጂ በምስጢር ይለዩ የለምን ፡ በዚያውስ ላይ በውጭ አገር ፊደላት በድምፅ አንድ ሁነው በጸጻፍ በምስጢር የሚለዩ ከብዙ ሥርፋ ላይ ያሉ አይደለምን ሲል የእብራይስጥንና የሮማውያንን ፊደላት እጅግ ሳይመረምር የማይመስለትን ምሳሌ ሰጥቶናል ። በድምፅ አንድ ይሁኑ እንጂ በምስጢር ይለዩ የለምን ያለው በግዕዝ እርግጥ ነው በማርኛ ግን ልክ አይደለም ሁላችን የምናውቀው ምሳሌ እንኳ የማያስፈልግን ነው ። የሮማውያንን ንግግሮች ሁሉ አንድ ላይ ከተው የያዙትን ፊደላት ብታውቅ ፳፭ ናቸው የግዕዝ ወይም ያማርኛ ፴፫ ናቸው ያውም ግዕዝ ግዕዙን ቆጥረን አረቢኛ የሚባሉትንም ድርብ ፊደሎች ኋ ቧ ፲፬ የሚሆኑትም ቀርተው ፴፫ በ፯ ብታበዛቸው በጥቂቱ ከ፪፻፴ የሚበልጡ እግር እጃቸው ተለዋውጠ ታገኛቸዋለህ ምንም መሰረታቸውን ፴፫ቱን ቢያውቅ የኢትዮጵያን ፊደል አውቃለሁ ሊል አይችልም ፤ ፪፻፴ዎቹን ካላወቀ በተቀር ፤ አንተ እንደ ሰጠኸን ምሳሌዎች ፳፭ አይነት ብቻ አይደሉም ፪፻፴ ናቸው እንጂ ፤ እንኳን አትቀንሱ አክሉባቸው ለሚል ምሳሌህና በዝተዋልና ቀንሱላቸው ለሚል ምሳሌ እንኳ ቢሆን እጅግ ያነሱ ናቸው ። ደግሞ በሮማኖች ፪ ኢ. (IY) ፪ ገ (GJ) ፪ ከ (KQ) ፪ ሰ (CS) አሉየምትላቸውን እስቲ ተመልከት ፡ በሮማውያን ፪ ኢ.ኢ. ወይም ፫ ኢ.ኢ.ኢ. ባንድ ንግግር ለመጻፍ ያስፈልጋሉና ስለዚህ አንዱን አይተህ ኢ. ሁለት ጊዜ ከመጻፍ ሲሉ ለሁለት ኢ. የሚቆጠር (y) አወጡለት ስሙንም በተለየ ኢፖሴሎ (Jpslon) ወይም ኤ ግሬክ (i grec) ነው ፤ ፪ ገ የምትላቸው ሮማውያን ፡ (ኢጣልያን) አንዱን ብቻ (C) ለገ ለጀ አድርገው ይዘውታል ። ፈረንሳዊዎች ብቻ ከእና ኢ. ሲገጥም ለዠ አድርገው ይዘዋል አንደኛውንም (J) ፈረንሳዊዎች አስፍተው ያዙት እንጂ ላቲኖች (ሮማኖች) ጉዳይ አላገቡትም ነበር ፪ ከ ያልካቸው (K) በላቴንም የለ ይኸንንም የውጪ አገር ስም ለመጻፊያ ሲሉ ፈረንሳዊዎች የያዙት ነው ፪ሰ ያልካቸው (c) ይኸኛው ያንተ ነው እንጂ ሮማኖችስ ለ (ቸ) ለ ከ ለ (ሽ) ነበር የደነገጉት ስሙም በሮማኖች ላቴኖች ቸ ነው ፈረንሳዊዎችም ለ (ከ) ለ (ሽ) ነበር የሚያደርጉት ፡ ቋንቋቸው ከሮማውያን እንደ ተለየ እንደዚሁ ፊደላቱን ከሮማውያን ደንብ ለይተው በንዳንድ ስርፋ ልውጥ ስም ስላአወጡላቸው በንዳንድ ስርፋ ፈረንሳዊዎች ሰ አሏት ልክ እንደ አማርኛ ፊደላት ድርብና ትርፍ ቢመስሉህ ነው እንጂ የሮማውያን የእብራይስጥም ፊደላቶች አንዱ አይነት ፊደል (ቀለም) ለ፫ አራት አይነት ድምፅ መጥቀሟን በቅጡ የምታውቅ ብትሆን ሁለት ፫ አይነት ፊደላት ላንድ አይነት ድምፅ ያገለግላሉ ስትል እንኳን ልትመስላቸው በልብህም ባላሰብካቸውም ነበር ።

አቶ መኰንን ከጻፍክልን መልስ ውስጥ ለኔ እንደሚመስለኝ አንዲት የምትጠቅም ምክር እናገኝበታለን እሷውም በማርኛ የምታስፈልገን የማጥበቅ ምልክት ብቻ ነች ። ብዙህ ስሞችና ንግግሮች በማጥበቅና በማላላት የተነሳ ምሥጢራቸው ስውር የሚሉን አሉ ። አለቃ ገብረ ሐና የሚባሉ ሰውዬ አንዱ ባላገር (ናን) አላልቶ ቢጠራቸው አጥብቀኝ አጥብቀኝ ፡ አጥብቀኝ ሲሉ ጮኹበት ይባላል ። ይኸ መሆኑ ለፊደላችን ደንብና ማዕርግ ባይኖራቸው ነውና የማያስፈልጉትን ከመሰብሰብ የሚያስፈልጉትን መመልከት ይሻላል ።

አቶ መኰንን አባት ያጠፋው ልጁን ያለፋው ። የሚለውን ምሳሌ ሳያውቁ ፡ አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀውን ብቻ ያውቅ ኖሯልና በ፳፫ መስመር አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው እንዲሉ ፡ አስቀድሞ የነበረውን ፊደል ከጠፋና ከተፋለሰ ዛሬ የተጻፈው ነገር ሁሉ ለኋላ ልጆች አለመታወቁን ማስተዋል ነው ይላል ። ከቶ ያቶ መኰንን ኢያቄምን ምሳሌ ሳያውቅ ቀርቶ ይሆን የዚህ ዓለም ፍጥረት ሁሉ ቋንቋውንና ጽሕፈቱን ፡ ብልሐቱን ፡ እንዲህ የለዋወጠውና ያጠራው ያሳመረው ? ሌላው ሁሉ ይቅርና የኛስ አባቶች የግዕዝን ቋንቋ ወደ አማሪኛ የለወጡት አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው የሚለውን ምሳሌ ሳያውቁ ቀርተው ይሆን? እጅግ ምሳሌዎችን መከተል ማብዛት እራስን መጉዳት እንዳይሆንብን ።

በዱሮዎቹ አባቶቻችን ዘመን የተጻፈው ጽሕፈት ዛሬ ባለመታወቁ ያጐደለን ጉድለትና ጉዳት በውነት ልክና ስፍር የሌለው ፡ ከልባችን የማይወጣ ነው ። ይኸውም መሆኑ ባባቶቻችን እርስ በርሳቸው ባለመስማማትና ሁላቸው በየፊታቸው የሚገባቸውን ሥራ ባለመሥራታቸው ነው ። ማለት ባገር ስምም ከሌለ ዘንዳ እንኳን የትምሕርት ብልሀትና ፤ የሚበላው እህል የሚለብሰው ልብስ ይጠፋል ። (ጠፍቶማል) ሕዝብም የሚገባውን ሥራ ፤ ክህን የክህነቱን ፤ ወታደር የወታደርነቱን ፡ ነጋዴ የንግዱን ፤ ገበሬ የግብርናውን ፡ ሠራተኛ የሞያውን ፡ ሁሉም በየፊቱ የያዘውን ሳያጠራ በዝብርቅርቅ ኖሯልና (ይኖራልና) ነው ። ይልቁንም እመጀመሪያው መልስ እንዳልኩት ፡ የኢትዮጵያ እውቀትና ብልሀት ትምሕርት ሁሉ የጠፋው በጳጳሶቻችን የውጭ አገር ክህን መሆንና የየሊቃውቱን መጻሕፍቶቻችንና እውቀቶቻችንን ከመሰብሰብ ይልቅ ገንዘብ ማጨቅ ከመውደዳቸው የተነሳ ፡ ግማሹን እየሸጡ በውጭ አገር በተኑት ። ግማሹንም በእውቀቱ ማነስ ጥጋብ የገፋውን ወንድማቸውንና እሕዞቦችን ሲሸሹ በየዋሻው እንደቀበሩት ቀረ እንጂ ፤ ቋንቋችን ስለተለወጠ የጠፋን ነገር ያለ እንዳይመስላችሁ ።

አቶ መኰንን በመጨረሻው መስመሮች የጠቀሰልንን ጥቅስ እስቲ እንመልከተው ፤ (ራዕይ ም ፳፪ ቁ ፲፰ እመ ወሰከ ዲቤሁ ይዌስክ እግዚአብሔር ላዕሌሁ መቅሰፍተ ፡ ወእመኒ

አሰሰለ እምውስተ ቃለ ዝንቱ መጽሐፍ ያሴስል እግዚአብሔር ክፍሎ እምዕፀ ሕይወት ወእምነ ሀገር ቅድስት) ያለው ይደርስብን ይመስለኛል ሲል መልሱን ይጨርሳል ። እረ ጉድ ፥ እረ ጉድ ፥ ማን ይሆን ከሃይማኖታችን መጽሐፍ (ከመጽሐፍ ቅዱስ) እንቀንስ ወይም እንጨምር ያለውና ይኸንን የጠቀሰልን ? ወይስ የግዕዝን ፊደላት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አይተሀቸው ይሆን ? የዚህን አጠቃቀስ ምሥጢር ተችሎህ ለተማሪው እንድትገልጽልኝ ክቡር ፊቃድክን እለምናለሁ ።? (እንባቢዎች ግን ም ፳፪ ቁ ፲፰ ፲፱ ተመልከቱ) ።

ትንሹ ተማሪ በውጪ አገር ያለው መ ሥ ወ ።

መልስ ።

ብርሃንና ሰላም ሶስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፯ ገጽ ፻፷፩ ስለጸፍኩት ቃል በዚሁ ዓመት በቁጥር ፲፰ ገጽ ፻፵ ክቡር ኃይሌ ሮባ የመለሰው መልስና ሀሣቤን ለመቃወም ያሳሠበውን ምክንያት በቀጥታ መንገድ ብመረምረው አንድም ፍሬ ነገር አጣሁበት እናንተም ወንድሞቻችን የኢትዮጵያ ልጆች ነገሩን መርምራችሁ እንደተረዳችሁት የታወቀ ነው ። እኔ መጀመሪያ ጋዜጣውን የጻፍኩት ምክንያት ስለ አራት ነገር ነው ። ፩ኛ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ስለአቡሻኽር ትርጓሜ ነው ። ፪ኛ ስለ ሊቃውንቱና ስለ ካህናቱ ትምርታቸው እንደሚሰፋ ማስታወሻ ነው ። ፫ኛ መንግሥት ለጳጳሳቱ አበል አድርጎ የሠጠው የገጽ በረከት ገንዘብ ለተማሪ ቤት ማቆሚያና ለመምህራኑና ለደቀ መዛሙሩቱም ደሞዝና ቀለብ እንዲሆን ማሳሠቢያ ነው ። ፬ኛ በሥጋዊ በኵል ያሉ ወንድሞቻችን ስለ ሃገራቸው ፍቅር እየተናደዱ ሃገራቸውን መውደዳቸውን ማንም አያጣውም ያልኩት የኢትዮጵያ ኃያላን ጠላት ዕርቅ አፍርሶ ድንበር ጥሶ ቢመጣ ስለ ቅድስት ሃገራቸው ሰማዕትነት ተቀብለው ደማቸውን አፍሰው ጠላታቸውን አጥፍተው ይኖራሉ ማለትን ያስረዳል ። ክቡር ኃይሌሮባ ግን ለሃገሬ ጥቅም ስል የጻፍኩትን ሀሳብ አገር የሚነካ ሊቃውንት የጐዳ አስመስሎ በማያውቀው በግዕዝ ቋንቋም በብርሃንና ሰላም አሳትሞ አየሁ የኢትዮጵያ ብልሆች በእንደዚህ ያለ ቃል ይታለሉና ይቃወሙኛል ብዬ አልጠራጠርም እንከርዳድና ስንዴውን ፍሬና ገለባውን ለይተው በእውቀት ሰፌድ እንዲያጠሩ ጥሩት አምናለሁ ይልቅስ በማታውቀው ቋንቋ በግዕዝ በመጻፍሕና ደገኛውን ሀሣብ ለውጠህ ክፉ ምሳሌ በመተርጐምህ ለሕሊና ቀለት ለልቡና ጥፋት ያሰኛል ። የክፋትና ተንየኮል መምህር መሆንም በመጽሐፍ ተከልክሏል መዝሙር ፵፱ ወለኃጥአሰ ይቤሎ እግዚአብሔር ለምንት ለከ ትነግር ሕግየ ወትነሥእ በአፉከ ሥርዓትየ አንተሰ ፀላዕከ ተግሣጽየ ወአግባዕከ ድኅሬከ ቃልየ እመኒ ርኢከ ሠራቂ ትረውፅ ምስሌሁ ወረሰይከ መክፈልትከ ምስለ ዘማውያን በኋላ ይኸም ቃል ሌላ እንዳይመስልህ ልንገርህ ሳትጠበቁ ሳትጠነቀቁ ሳትማሩ ሳትመምሩ ሰው አትምከሩ ማለት ነው ። ሰሎሞንም በምሳሌው ምዕ ፳፪ ቁ ፫ አስተዋይ ሰው ክፉ አይቶ ተሸሸገ አእምሮ የሌላቸው ግን ዘለው ገቡ (ተጐዱም) ይላል ይህን ልተውና ወደ ቀደመው ነገሬ ልመለስ እኒ ጋዜጣ የጻፍኩበት ምክንያት ከላይ እንደ ተባለው ለኢትዮጵያ ተማሪ ቤትና ለሊቃውንቱ ጥቅም ነው እንጂ የጳጳሳትን ምርጫ ነገር የሚያነሣ ከአርእስቱ እስከ ኅዳጉ በጻፍኩት ጋዜጣ ውስጥ አንዳች አይገኝም አንተ ግን ከገራችን ጳጳስ ለመሾም ብናስብ የመቃወም መልስ ጻፊብን እያልክ የሀሠት ወሬህን ታንቈረቍራለህ እኔ ከመምህራኖቼ ከኢትዮጵያ ሊቃውንትና ከሕዝቡ ፈቃድ የተለየ ሌላ ሀሣብ እንደሌለኝ ማንም ሰው ያውቃል ክቡር ኃጋደራስ አፈወርቅም እራሳቸው ይመሠክራሉ ሲጨሁ ሳትረዳ ለምን ቀረህ ትለኛለህ የኢትዮጵያ ተማሪ ቤት እንዲቆምና መምህራኑ ደሞዝና ቀለብ የሚያገኙበትን መንገድ በብርሃን መምራት ወደ ጨኸቱ ቦታ ለመሄድ አልመሰለህም ።

በመንፈሳዊ በኩል ዕገሌ ከሀን ነው አሕዛብ አገር ሄዶ አስተማረ ባለ መባሉ ያገራችንን ሊቃውንት ቅር ሣያሰኝ አይቀርም ያልኩት ፥ ዝልፎ ለጠቢብ ከመ ይፄስክ ጥበበ እያሉ ሲነግሩኝ ነበርና ካህናቱ ትጉሃን ሆነው በየ አውራጃው የተማሪ ቤት አቁመው ቃለ እግዚአብሔር እየሰበኩ በዙሪያችን ያሉትን አሕዛብ ከአምልኮተ ጣኦት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ከወበዴነት ወደ ሕገ ሥርዓት እንዲመልሱዋቸውና መንግሥታቸውን ለማገልገል አገራቸውን ለመጥቀም እንዲያበቁቸው ሕሊናቸውን ለማነቃቃትና ለማፋጠን ብዬ ነው እንጂ ጉባዔያቸውን ለመቃወም እንዳልተጻፈ ከንተ በቀር ሁሉም ተረድቶታል ። ሁለተኛ የአቡን አሽከር መሆን አይገኝም ትለኛለህ ካሁን በፊትም ቢሆን መቸም ዜጋ የሆነ ሁሉ የመንግሥቱን ፈቃድና ትእዛዝ መተላለፍ አይገባውምና እኛ በጃንሆይ በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ልዑል እራስ መኰንን ለአቡን አገልጋዮች ሁኑ ብለው ስለ አዘዙን ይህን ያህል ዘመን በቅን አገለገልን ። አሁንም ግርማዊት ንግሥት ሐጼጌ ዘውዲቱና ልዑል ተፈሪ መኰንን በሠጡን ባልደረባ ውስጥ መንግሥታችንን እንረዳለን ። አስቀድሞ ነበር እንጂ መምከር ላልከው ማናቸውም ነገር ቢሆን የሚሆንበትና የሚከናወንበት ጊዜ አለው መክ ምዕ ፫ ቁ ፩ ለሁሉ ዘመን አለው ከሰማይ በታችም ላለው ነገር ሁሉ ጊዜ አለው ቁ ፯ ለዝምታ ጊዜ አለው ለነገርም ጊዜ አለው ይላል ። ዳዊትም ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር ብሏል ጌታችን በዮሐንስ ወንጌል ምዕ ፪ ቁ ፬ ዓዲ ኢበጽሐ ጊዜየ ብሏል ክቡር ኃይሌ ሮባም ጊዜ ገሚድ በጽሐ ቃለ ማዕነቅ ተሰምዓ በውስተ ምድርነ ብለህ ጠቅሰሀል ። እኔም ስለዚህ ለጊዜው የሚያስፈልገውን በጊዜው ተናገርኩ ነገር ግን በግዕዝ ቋንቋ አብዝተህ ስለጻፍክልኝ የኢትዮጵያ ሊቅ ያሬድ ፈያታዊ ዘየማን መኑ መሀረከ ወመኑ ነገረከ ከመ ታእምር ዘንተ ብሎ የአንክሮ ቃል እንደዘመረ እኔም ለእውቀትህ ጥልቅ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ለወደፊቱም እርሳሴን ቀርጬ ወረቀቴን አሰናድቼ እቆያለሁ ፥ እንግዴህ ነገር ቢያበዙት በአህያ አይጫንም ምሳ ምዕ ፲፩ ቁ ፩ ሴብ ሚዛን በእግዚአብሔር ዘንድ የተፀላ ነው እውነት ሚዛን ግን ፈቃዱ ነው ብሏልና እግዚአብሔርን የምትፈሩ ጽድቅ የምትናገሩ የብርሃንና ሰላም ወዳጆች በእውነተኛው የልብ ሚዛን ነገሩን መዝናቿሁ እንድትፈጽሙትና እንድትቆርጡትም ተስፋ አደርጋለሁ ።

ኢትዮጵያዊ በቀለ አበዬ ።

ስለ እመቤታችን ልደት በዓልና ።

የቅዱስ ራጉኤል በዓል መታሰቢያ

ግንቦት ፩ ቀን የመቤታችን ማርያም ልደቷና የቅዱስ ራጉኤል በዓል አንድነት ስለ ዋለ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በብዙ ሠራዊት መኳንንት ታጅበው እንጦጦ ከራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ወጥተው ነበሩ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ራስ ተፈሪ መኰንንም ባንድነት ወጥተው ቅዳሴውን አስቀድሰው ታቦት ወጣና ዑደት ታውደና ካህናቱ በማሬ ምሥጋና ኢያቄም ወለዳ ዳዊት ዘመዳ እያሉ አመስግነው ሲጨርሱ ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ለበዓሉ የሚገባውን ትምርትና ተግሣጽ ባማረ በጣፈጠ ቃል እንዲህ ብለው ሰበኩ፤ ቃሉም ቀጥሎ የተጻፈው ነው ። የዛሬ በዓል ያባታችን ያዳም ተስፋ የተፈጸመበት ነው አባታችን አዳም ብበድለው እንደፈረደብኝ ደግሞ ማረኝ ብለው ይምረኛል ብሎ ንስሐ ቢገባ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ብሎ ተስፋ ሰጥቶት ነበርና እመቤታችን ሕጉን ጠብቀው ከሚኖሩ ከኢያቄምና ከሐና የተወለደችበት ቀን መታሰቢያ ነው ፤ ስለዚህ ሊቁ ዳዊት ዘመዷ ኢያቄም አባቷ ብሎ አመሰገነ ፤ እኛም በዚህ ቀን የመቤታችንና የመልአኩ መታሰቢያ ቀን ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን ተሰበሰብን መሰብሰባችን ግን ክርስቲያን ለመባል ብቻ አይደለም፤ የተቻለው ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ ያልተቻለው እምነ ቤተ ክርስቲያን ይዞ ለነዳያን መጽውቶ ሊሔድ ነው እንጂ እንዲያው ክርስቲያን ነው ይበሉኝ ለመባል አይደለም ፤ ሥጋውን ደሙ ካልተቀበልን ሕጉን ካፈረስን ቅዱሳን ያማልዱናል ማለት ከንቱ አሳብ ነው ። ይህን ባናደርግ ቅዱሳን ሊቀጡን የተሰናዱ ናቸው ። አሁን የንጉሥ አሽከር የጌታውን ጠላትና ዓመፀኛውን ሊቀጣ ተሹሞ ይጠብቃል እንጂ ዝም ይለዋልን ? የሚያማልዱበት ጊዜ አለ ፤ ባለማወቅና በስሕተት ሕጉን ያፈረሰ ወደ ፈጣሪው በንስሐ ተመልሶ ቢያለቅስ ቅዱሳን ርኅሩሐን ናቸውና ይረዱታል ብለው ብዙ ተግሣፅ ከተናገሩ በኋላ እንደ አባትነታቸው ሕዝቡን ባርከው ጸሎት አድርገው ሕዝቡ በደስታ ተሰናበተ ።

የከተማ ወሬ ።

ሚያዝያ ፳፱ ቀን ከማታው ፲፪ ሰዓት በትልቁ በአውራጃው መንገድ ብዙ ሠራዊት በየክፍሉ ሁኖ ጠርብ ጠርቡን እየያዘ ሎጋውሽበ ብሎ እየጮኸ ሲያልፍ ዘበኞቹን አልታገድም ብሎ አቀቶዋቸው መንገደኛውን ሁሉ ሲያስቸግር አመሸ ። ጩኸቱን ሰምተን ነገሩን ብንጠይቅ በአቶ ፋሲካ ቤት ግብር ተጠርቶ ሲበላና ሲጠጣ የዋለ ሠራዊት ነው አሉን ።ቀርበን ነገሩን ብንመለከት ሁሉም ሰክሮ ነበር ። አንዳንዱ አእምሮዋቸው ጨርሰው ያላጡ የተሸነፉ ባልንጀሮቻቸውን እየደገፉ ይዘው ይሄዱ ነበር። እያሌ ትልልቆች ሰዎች በበቅሎ ተቀምጠው ርከብ መርገጥ ዛብ መጨበጥ አቅቶዋቸው ነፋስ እንደ ሚያወዛውዘው መቃ ሁሉ ከከርቻው ወደ ቀኝና ወደ ግራ እየተወዛወዙ ለሚደግፏቸው ሰዎች ሲያስቸግሩ ላይታው ያስደንቃል ። አንዳንድ ሰዎችም ጨርሶ እንደ ደረቀ ግንድ ሁነው ለሳንሳ እየተሸከምዋቸው ይሄዱ ነበር ። አንዱ ሰውየም ከጉምሩክ በታች ባለው መንገድ በተነጠፈ ድንጋይ ላይ እንደ ሞተ ሆኖ ወድቆ ደርቆ የሚያነሳው ታጥቶ ወንድሙ የተባለ ዘበኛ በአጠገቡ ቁሞ ነበረ። የአቶ ፋሲካ የለጋሥነታቸውና የሲሳዩ ብዛት እጅግ አድርጎ አስደነቀን ግሩም ነው ። ግን ሰውነታቸውን አጥተው እንደ ግንድ ደርቀው ለሳንሳ ሰው ተሸክምዋቸው ይሄዱ የነበሩና የሚአነሳቸው አጥተው በየመንገዱ ወድቀው የቀሩ እምባጓሮ አንስተውም የተፈነከቱትን በማየት በጣም አዘንን ።

ሰው በለጋስነቱ ብዙ መብልና መጠጥ ቢያቀርብ የተጠራ ሰው ልኩን አውቆ እስኪጠግብ ድረስ መብላት እስኪረካ ድረስ መጠጣት ይገባዋል እንጂ ከልክ አልፎ በመብላትና በመጠጣት አእምሮውን አጥቶ ላይታው እስኪያስቀይም ድረስ መበላሸት አይገባውም ።

መብልና መጠጥ ጤናችንን እንድንጠብቅ በሕይወት እንድንኖር ተሰጠን እንጂ ጤና አጥተን ህይወታችንን ልናበላሽበት እንዳልተሰጠን ማሰብ ይገባናል ።

ልኩን አለማወቅ ከእንስሳ መብስ እንደሆነ ማንም አያጣውም። ማር ይስሐቅም ወእምከመ ረከብከ ለመዓር ብላዕ እምኔሁ በዓቅም ሥሩዕ ። ከመ ኢትቁዕ በጊዜ ጽጋብ ፤ ማር ብታገኝ በመጠን ተመገብ ። አብዝተህ ተመግበህ እንዳይወጣብህ ብሏል ና ከልክ አንለፍ ።

ስለ ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ቤት ግብር

ግንቦት ፪ ቀን ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ጭፍራቸውን የከተማው ዘበኛና ብዙ ወዳጆቻቸው መኳንንትና የውጭ አገር ሰዎችም ሰብስበው ትልቅ ግብር አድርገው ሲጋብዙ ዋሉ ።

የስርዓቱ ማማርና የሲሳዩ ብዛት እጅግ ግሩም ነበረ ። በግብሩ የተጋበዘ ሰው ሁሉም እጅግ ደስ ብሎት ክቡር ከንቲባ ነሲቡን እያመሰገነ ሄደ ።

የውጭ አገር ወሬ ።

የሶቢየት አድማ (በቻይና) ።

"የሶቢየት ሕዝብ ባቀረበው ነገር ፤ የቻይናን አኳሆን ለማሻሻል ሲል የዓለም ማሕበር በጉባዔ የመከረው ቃል የተጻፈበት የጉዳይ ወረቀት ሁሉ ፤ እኩሉም በጋዝ ተነክሮ ፤ እኩሉም በሰት ተቃጥሎ ከሌላ ሰነድ ጋራ ተቃጥሎ ፤ በሶቢየት ብጥብጥ ውስጥ ተገኘ ። በነዚህም የጉዳይ ወረቀቶች ፤ ከተጻፈው ውስጥ ቻይናን በመሳሪያና በገንዘብ ፤ ሌላ ሕዝብ እንዳይረዳት ። የውጭ አገር ጠላት ወሬ የሚሰብክና ፤ እርዳታ የሚከለክል ጦር ቢሰድ ለቻይና የሚያስፈራ ይሆናል የሚል ቃል ነው ።

ደግሞም የውጭ አገር ወታደርና መርከብ ከገራቸው እንዲወጣ ለመጠየቅና በነሱም ላይ የጦር አድማ አስነስቶ የካንኳንን መንግሥት በበጎ ስም ለማስጠራት የተመከረ ቃል በውስጡ አለበት ። በቻይና የሚሆነውን ሁሉ ወሬ እየጻፉ ለየሌጋሲዮኑ ፤ ያውም አብልጠ ለጃፖን ሊጋሲዮን ወሬ ስለሚያቀብሉ ሰላዮች የተጻፈም በውስጡ ተገኘ ።

ከታይምስ የተገለበጠ ።

በታላቁ የአውሮጳ ጦርነት ምክንያት የእንግሊዝ ሕዝብ ማነስና መብዛት ።

ስለ እንግልጣርና ስለ ዌልስ ሕዝብ ብዛትና ማነስ ከሚያስ ረዳው መዝገብ በ፲፱፻፳፩ ዓመት የተገለበጠው በጋዜታ ታትሞ የሕዝቡ ቁጥር ፴፯ ሚሊዮን ፰፻፹፯ሺ ፯፻፺፱ ሆነ ከዚህ ከተቆ ጠረው ውስጥ ፲፰ ሚሊዮን ፸፭ሺ ፪፻፴፱ ሴቶች ፲፱ ሚሊዮን ፹፻፲፩ሺ ፬፻፹ ወንዶች ናቸው ። ለ፯፻ ሰዎች ሺ፯፻፱ ካሬ ሚትር ያህል ስፍራ እንደሚደርስ በሂሳብ ታውቆ የሕዝቡ ብዛት ከሌላ አገር ሕዝብ ስለበለጠ እስታስቲክ እንዲወጣ የግድ አስፈለገ ። ስለ ብዛትና ማነስ በሚያስረዳው መዝገብ እንደ ተጻፈ ፣ ካለፈው ዘመናት ሁሉ ይልቅ በሺ፱፻፲፩ና በሺ፱፻፳፩ ዓመት መካከል ከተወለደው የሚያድገው ጥቂት ነበር ። የዚህም ዋናው ምክን ያቱ ፤ ወጣቱና ታዳጊው ፣ ሁሉ በታላቁ የአውሮጳ ጦርነት ስላለቀ ነው ። ከተቆጠረው ሕዝብ ከሞተ ሰማኒያው በከተማ ኑዋሪ ነው ። ዋና ከተሞች ቁጥራቸው ፺፯ ይሁን እንጂ በያንዳንዱ ከተማ ከ፻ሺ ሕዝብ በላይ አለ ። ባልታወቀው ታናናሽ ከተማ የታዳጊው ቁጥር ስለ በዛ ፣ እንዲሁም ከተማው እየሰፋ እስከ ፻ሺ ሳይቀርብ አይቀርም ከዚህ በኋላ ፻ሺ ህዝብ እየበዛና እስከ ልጅ ልጅ እየተ ባዛ የሚያስቸግር አበዛዝ ሳይሆን አይቀርም ። በሌንክ ሳየርና በዮርክ ሻየር ያሉ ሰራተኞችና ኑዋሪዎች የማነስና የማደጋቸው ልክ ካለፈው ዓመት ባሁኑ ዓመት ደህና ሁኖ ይታወቃል በሥራ ላይ ያሉ በመዝገብ ስማቸው የተጻፈ ቁጥራቸው ፲፯ ሚሊዮን ፻፸፰ሺ፺ ነው ወንዶቹ ፲፪ ሚሊዮን ፻፲፪ሺ ፯፻፲፰ ሴቶች ፭ ሚሊ ዮን ፰፩ሺ ፫፻፴፪ ናቸው ። ከሕዝቡ ከመቶ ፴፱ኙ በፋብሪካ ውስጥ ሥራ ሰርቶ አዳሪ ነው ከመቶ ፲፫ ሼቅጦ ጽፎ አዳሪ ነው ከመቶ ፲፪ቱ በራሱ አዳሪ ሆቴልና ታላላቅ ሱቅ ያለው ነው ።

ስለ ጥቂት የውጭ ሰዎች ።

ባገር ውስጥ ስለ ተወለደውና በዜግነት የገባው የውጭ አገር ሰው በ፻ ሺ ሕዝብ ውስጥ ፯፻፯ ይገኝ የነበረ ፣ እያደረ እያነሰ በመሄዱ ከሺ ፱፻፲፩ ዓመት እስከ ሺ ፱፻፳፩ ዓመት መካከል በ፻ ሺ ሕዝብ ውስጥ ፯፻፪ ብቻ መገኘቱን አመዛዝኖ እስታቲስትኩ ያሳያል ። የጀርመን ሕዝብ ቍጥሩ ፶፫ ሺ ፫፻ ፳፱ የነበረው ፲፱ ሺ ፫፻ ፶፰ ብቻ ተገኘ ። እንደዚሁም በአውሮጳ የ ነበረው ሕዝብ ሁሉ ቍጥሩ በጣም እየጐደለ ሄደ ። ቢገኙም የቤልጅግ አገር ሰዎች ከስንት አንድ የነበሩ ከሺ ፱፻ ፲፩ ዓ መት እስከ ሺ ፱፻ ፳፩ ዓመት ከ፬ ሺ ፯፻ ፶፯ ቍጥር እጥፍ ሁነው ቍጥራቸው ፱ ሺ ፯፻ ፹፩ ሆኑ ከአሜሪካም በላይ በላዩ የሚገባው ዝብ ቍጥሩ የዛሬ አስር ዓመት ፲፫ ሺ ፯፻ ፴፯ የነ በረው ዛሬ ፲፱ ሺ ፻ ፸፩ ሆኑዋል ። ከውጭ አገር ሰዎች ከእ ኩሌታው ቍጥር የሚበልጡ በሎንዶን ያሉ ናቸው ። በስቴፔኒ ወረዳ ያሉት ቍጥራቸው የዚያን ሲሶ ይሆናል ፣ ወጣቱም በዕድሜ ቆይቶ አለማደጉ ፣ ምስክሩና ምክንያቱ ጦርነቱ ነው ። ጉልማሶች በሕጻንነት መቀሰፋቸውና የሴትና የወንድ ሕጻን ብዙ ባለመ ኖሩ ለሚመጣው ትውልድ በታሪክ የሚወጋ ነው ። በሕጻንነት በቅጽበት መቀሰፋቸው ምንም ተስፋ የሌለው ነገር ቢሆን በ ነሱ ምትክ ድርስ ጉልማሶች ስማቸውን በመዝገብ አጻፉ ።

ደግሞም ስለ ወንድና ሴት ብዛትና ማነስን ያመጣ ምክ ንያቱ ጦርነቱ ስለሆነ በሺ፱፻፲፩ በቍጥር የሴቱ ብልጫ ከወ ንዱ ፩ ሚሊዮን ፪፻ሺ የነበረ አሁን ፩ ሚሊዮን ፯፻ሺ ሆነ ። ለጋብቻ ዕድሜ ከደረሰው ሕዝብ መካከል ወንዱ ለሴቱ አይደ ርስም ። ፴ና ፴፭ ዓመት ዕድሜ ከሆኑት መካከል ሴትና ወንድ ቢመዛዘን ፩ሺ ወንድ ፩ሺ ፬፻፹ ሴት ይደርሰዋል ። ከወንዱ ሴቱ በብዛት የመዘነበት ፩ኛው ዋና ምክንያት የሴቶች ዕድሜ ከወንዶች ዕድሜ ስለበረከተ ነው ።

ማስታወቂያ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰ ንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው ፣	፲፪ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፫ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር ።	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነርትጓሜው	፯ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትጓሜው ፣	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትጓርሜው ።	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት ፤	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው ።	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ፣	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን ።	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ ።	አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ ።	አላድ
ያማሪኛ ፊደል ፣	ሩብ
አሳብና ምኞት ፣	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት ።	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር ።	፪መ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ፣	፩ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ።	፩ሩብ

OMEGA



እጅግ ጥሩነቱ የተመሠከረለት ኦሚጋ በቢ የሚባል ባላንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲግ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፳ ብር ተኩል ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፹፭ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፩ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኩረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኩረጃ	፲፭ ብር
አቡጀዲ መንጸር	፩ ኩረጃ	፻፴፭ ብር ።
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፻፴፭ ብር ።
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፳፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፰ ብር ።
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፰ ብር ።
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፵፭ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፩ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፩ መ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ
በአንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ ፰ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፴ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፭ ብር ተ፪ ሩብ ።

ሩግቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚ ወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመረለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል ።

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

የዘህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፥ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆ የነ ጂ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ካኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመከከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሂስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፤ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

Berliet



ቤርሊዮ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዮ አቶሞ ቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚአን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

AMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶከለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶከለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፡ ቁጥር ፳
3 me ANNÉE № 20

ሐሙስ ግንቦት ፲፩ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 19 MAI 1927.

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ። Diréctеur	የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ስፈስገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።	Abonnements Ethiopie Un an 5 Thalers Etranger Un an 7 Thalers le numero 2 piastres

ስለ ልዑል ዱክ ዴዝአብሩስ አቀባበል መሰናዳት።

ግንቦት ፰ና ፱ ቀን የኢትዮጵያ መኳንንቶች በየቦታቸው ሁነው የጭፍሮቻቸውን ሰልፍ ሲያዩና ሲያስተካክሉ ዋሉ ፤የኢትዮጵያና የኢጣልያ ሰንደቅ ዓላማም በየመንገዱ ዳር ግራና ቀኝ እየሆነ ተተከለ ። በየበሩና በየድልድዩም ቅስት እየተበጀ በልዩ ልዩ ጌጥ አምሮ ተሠራ ። በቅስቱ ላይም የግርማዊ አጼ ምኒልክና የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት የልዑል አልጋ ወራሽም ፎቶግራፍ ተደርጎበታል ። ላቀባበሉ የሚሆን ማስታወቂያም በአማሪኛና በፈረንሳዊ ታትሞ ለየመኳንንቱ ተሰጠ ማስታወቂያውም ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው።

አዲስ አበባ ግንቦት ፡ ፰ ፡ ፱ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮ ፡ ቀን ። ፲፱፻፲፱ ዓመት ምሕ

ስለ ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ አቀባበል ማስታወቂያ

በግንቦት ፰ ቀን ፤ ጂቡቲ ይገባሉ ። በጂቡቲ ላይ ባለ ማዕርግ የሆነ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚልከው መኰንን ይቀበላቸዋል። በዚያውም ቀን በልዩ ባቡር ከጂቡቲ ተነስተው ወደ ድሬዳዋ ይወጣሉ ። ከኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት አልፈው ደወሌ ላይ ሲደርሱ የክብር አቀባበል ይደረግላቸዋል ። ወደማታ ባ፲፩ ሰዓት ድሬ ዳዋ ይገባሉ ። በባቡር መቋሚያ አንድ ባለ ማዕርግ መኰንን ይቀበላቸዋል ። ከዚያም ወደ ቤተ መንግሥቱ ገብተው ያድራሉ ።

በግንቦት ፱ ቀን ፡ ጧት ከድሬ ዳዋ ተነስተው አዋሽ ባ፲፩ ሰዓት ይገባሉ ። በዚያም አንድ ባለ ማዕርግ መኰንን ይቀበላቸዋል ። እዚያው አድረው በግንቦት ፲ ቀን ከሌሊቱ ፲፩ ሰዓት ከአዋሽ ተነስተው በ፱ሰዓት አዲስ አበባ ይገባሉ ። ከባቡር ሲወርዱ ልዑል አልጋ ወራሽ ይቀበሏቸዋል ። ወዲያውም መኳንንቶቹን በየተራ ያስተዋውቋቸዋል ። ልዑል ዱክም በበኩላቸው መኳንንቶቻቸውን ከልዑል አልጋ ወራሽ ያስተዋውቃሉ ። ከዚህም በኋላ ወደ ቤተ መንግሥት ገብተው ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ይቀበሏቸዋል።ከቤተ መንግሥት ለማረፊያ ወደ ተዘጋጀላቸው ወደ ልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ ይሄዳሉ ። ማታም ልዑል አልጋ ወራሽ እንግዶቹን ራት ይጋብዛሉ ።

በግንቦት ፲፩ ቀን ፡ ከጧቱ በ፫ ሰዓት ተኩል የውጭ አገር የዲፕሎማቲክ ሰዎች ወደ ልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ እየመጡ ከልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ጋራ ይገናኛሉ።በ፬ት ሰዓት ወደ ቤተ መንግሥት ገብተው የዳግማዊ ምኒልክን መታሰቢያ ቤት ይጐበኛሉ ። በ፭ ሰዓት የዳግማዊ ምኒልክን ትምሕርት ቤት ይጐበኛሉ ። በ፮ ሰዓት ከዱክ ጋራ የመጡ መኳንንቶችና የኢትዮጵያ ትልልቆች መኳንንቶች ስለ ዱክ ዴዝ አብሩዝ ክብር በቤተ መንግሥቱ ምሳ ይጋበዛሉ። ባ፲ ሰዓት የዳግማዊ ምኒልክን ሆፒታል ይጎበኛሉ ። በ፲፩ ሰዓት የኢጣልያ ሌጋሲዮንን ለመጐብኘት ይሄዳሉ ።

ግንቦት ፲፪ ቀን፡ በ፬ ሰዓት የቅዱስ ጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን ይጎበኛሉ ። በ፭ ሰዓት ቤተ ሳይዳ ሆፒታል ዘተፈሪ መኰንንን ይጎበኛሉ።ወደማታ በ፱ ሰዓት የልዑል አልጋ ወራሽን ትምሕርት ቤት ይጐበኛሉ። ማታ በሁለት ሰዓት ልዑል አልጋ ወራሽ ከዱክጋራ የመጡትን መኳንንቶችና የኢትዮጵያን ትልልቆች መኳንንቶችን ስለ ዱክ ዴዝ አብሩዝ ክብር ራት ይጋብዛሉ ።

ግንቦት ፲፫ ቀን፡ ከ፫ ሰዓት እስከ ፯ ሰዓት ትልቅ ሰልፍ ያያሉ በ፯ ሰዓት የኢጣልያ ሌጋሲዮን ስለ ዱክ ዴዝ አብሩዝ ክብር ምሳ ይጋብዛል።ከምሳ በኋላ እረፍት ያደርጋሉ ማታ በሁለት ሰዓት ልዑል አልጋ ወራሽ ስለዱክ ዴዝ

አብሩዝ ክብር የውጭ አገር የዲፕሎማቲክ ሰዎችንና የኢትዮጵያ ትልልቆች መኳንንቶችን ራት ይጋብዛሉ።

ግንቦት ፲፬ ቀን ፤ በ፩ሰዓት ተኩል ተነስተው ልዑል አልጋ ወራሽና ዱክ ወደዲስ ዓለም ይወርዳሉ።በ፭ ሰዓት በሆሎታ ወንዝ የቆመውን የወፍጮ መዘውር አይተው በ፯ ሰዓት በገነት ከተማ ምሳ ይጋበዛሉ ። ከእኩል ቀን በኋላ ሽር ሽር ይወጣሉ ። ተመልሰው በገነት ያድራሉ

ግንቦት ፲፭ ቀን፤ ከገነት ከተማ ባ፩ ሰዓት ተነስተው ባ፬ ሰዓት ተመልሰው አዲስ አበባ ይገባሉ ። ወደ ማታ ባ፲ ሰዓት ወደ እንጦጦ ማርያም ወጥተው ቤተ ክርስቲያኑና የአቴጌን መታሰቢያ ይጐበኛሉ ። ማታ ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ጋራ ወደ ማዘጋጃ ቤት ይሄዳሉ ። የአዲስ አበባ ከንቲባም ስለ ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ክብር የውጭ አገር ዲፕሎማቲክ ሰዎችንና የኢትዮጵያን ትልልቆች መኳንንቶችን እራት ይጋብዛሉ። ደግሞ አዲስ አበባ ከሚኖሩ ከውጭ አገርና ከኢትዮጵያ ትልልቆች ሰዎች ከራት በኋላ እየመጡ ከዱክ ጋራ እንዲተዋወቁ ይጠራሉ ።

ግንቦት ፲፮ቀን ፡ ከ፫ሰዓት እስከ ፯ሰዓት በጃን ሜዳ የፈረስ እሽቅድድም ያያሉ በ፯ ሰዓት ፤ ከውጭ አገር የዲፕሎማቲክ ሰዎችና ከኢትዮጵያ ትልቆች መኳንንቶች ጋራ ዱክ ዴዝ አብሩዝ በቤተ መንግሥት ምሳ ይጋበዛሉ ። በ፲ ሰዓት የኢጣልያ ሌጋሲዮን ስለዱክ ዴዝ አብሩዝ ክብር ግርማዊት ንግሥትንና ልዑል አልጋ ወራሽን ትልልቆችንም የኢትዮጵያ መኳንንቶች ሻይ ይጋብዛል ማታ ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ የኢትዮጵያን መኳንንትና የውጭ አገር ዲፕሎማቲክ ሰዎች ራት ይጋብዛሉ።ከዚህ በኋላ የአፈሴሉ ቀን ይጨረሳል ።

ከኢጣልያ መንግሥት የሚመጡ የኢትዮጵያ መንግሥት እንግዶች ስማቸውና ማዕርጋቸው ቀጥሎ የተጻፈው ነው

፩ኛ ፡ ልዑል ፕሬንስ ሉዊጂ አሜዴ ደ ሳቦያ ዱክ ዴዝ አብሩዝ
፪ኛ ፤ ክቡር ያዕቆብ ጋስፓሬኒ የኤርትርያ ገዥ ።
፫ኛ ፤ ክቡር ሩፋኤል ጓሪሊያ ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር
፬ኛ ፤ ክቡር ሞንታልቶ ማሲሞ ዱክ ደ ፍራጊኖ የግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ የቤተ መንግሥቱ የበዓል አሰናጂ ።
፭ኛ ፡ ኮማንዳ ማሉሳርዲ የግርማዊ ኢጣልያ ንጉሥ በቤትም በመንገድም ረዳት ።
፮ኛ ፡ ባሮን ይቺኡቲሳ የግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ ቢስ ቆንስል
፯ኛ ፡ ሊዩትና ደቤሶ ኮንት ካፓኔ ።
፰ኛ ፤ ኮማንዳ አርናቲ የቤሲኒያ የጦር መርከብ አዛዥ ።
፱ኛ ፤ ሊዩትና ኰሎኒል በዚል ።
፲ኛ ፡ ካፒቴን ይ ማርያ ።
፲፩ኛ ፡ ከባሊዮር ራብ የኤርትራ አገር ገዥ ዋና ጸሐፊ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ከኢጣልያ መንግሥት ለመጡ እንግዶች ባልደረቦች ያደረጉላቸው መኳንንቶች ስም ።

፩ኛ ፤ ክቡር ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው የፈረስ ዘበኞች አለቃ
፪ኛ ፤ ክቡር ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የመንግሥት አማካሪ

Addis-Abeba, les 16, 17, 18, 19, 20, 21, 22, 23, 24, Mai 1927

PROGRAMME DE LA VISITE

de
SON ALESS OYALE
LE PRINCE AMEDEO DES AVOIE
Duc des ABRUZZES

16 Mai Arrivée à Djibouti et rèception par un dignitaire de la cour lmpériale d,Ethiopie.
Départ pour Dire-Daoua par train spécial.
Aprés avoir traversé une partie du térritoire Ethiopien, SON ALTESSE ROYALE Le Duc des ABRUZZES sera officiellement reçu à Dawoullé par un dignitaire de la cour lmpériale.
Arrivée à Diré-Daua 5 h. du soir,
Réception par un dignitaire de la cour Impériale.
S. A. R. Le Duc des ABRUZZES sera logé au palais du Gouvernement.

17 Mai Départ de Diré-Daoua le matin. Arrivée à Aouache à 5 h. s. Réception par un dignitaire de la cour Impériale.

18 Mai Départ de l,Aouache à 5 h m. Arrivée à Addis-Abeba à 3 h s.
SON ALTESSE IMPERIALE TEFERI MAKONNEN se rendra à la gare pour recevoir S. A R. Le Duc des ABRUZZES.
Présentations officielles.
Réception par SA MAJESTE L'IMPERATRICE au Palais Impérial.
Aprés la réception, S. A. R. Le Duc des ARUZZES se rendra au palais privé de S. A. I. TEFERI MAKONNEN où il séjournera jusqu'à son départ.
Le soir, dîner intime offert au palais de S. A. I. TEFERI MAKONNEN en l'honneur de S. A. R. Le Duc des ABRUZZES et de sa suite.

19 Mai A 9:30 h m. Réception au palais de S. A. I. TEFERI MAKONNEN du corps diplomatique par S. A. R. Le Duc des ABRUZZES
A 10 h m. Visite au palais Impérial du Mausolée de S. M. l'Empereur MENELICK II.
A 11 h. Visite de l'école MENELICK II.
A 12 h. Dejeuner au palais Impérial en l'honneur de S. A. R. Le Duc des ABRUZZES et de sa suite.

Les grands chefs Ethiopiens y seront invit és.
A 4 h s. Visite de l'hôpital MENELICK II
A 5 h s. Visite à la Légation Royale d'Italie.

20 Mai A 10 h. m Visite de la cathédrale St. Georges.
A 11 h m. Visite de l'hôpital de S. A. I. TEFERI MAKONNEN, « Le bété Saïda »
A 3 h s. Visite de l'école TEFERI MAKONNEN.
A 8h s. Diner offert à S. A. R. Le Duc des ABRUZZES et à sa suite, au palais de S. A. I. TEFERI MAKONNEN Les Grands dignitaires de la cour Impériale y seront invités.

21 Mai De 9 h m. à 12 h m. S. A. R. Le Duc des ABRUZZES assistera à une revue des troupes.
A 1 h s. Dejeuner en l'honneur de S. A. R. Le Duc des ABRUZZES, à La Lègation Royale d'Italie.
A 8 h s. Dîner au palais de S. A. I. TEFERI MAKONNEN en l'honneur de S. A. R. Le Duc des ABRUZZES.
Le corps diplomatique, ainsi que les grands chefs de l'Empire y assisteront.

22 Mai Excursion à Addis-Alèm. Dèpart d'Addis-Abeba à 7: 30 h m. A 11 h. Visite à la minoterie d'Holotta.
A 12 h m. Dejeuner à Guènnet. Après midi Promenade et Retour à Guénnet où L. L, A. A. passeront la nuit.

23 Mai Départ de Guénnetà 7 h m. Arrivée à Addis-Abeba à 10 h m. A 4 h s. Visite de l'Eglise Ste Marie et du tombeau de S. M. l'Impératrice Taitou, sur le Mont Antotto. Le soir dîner offert à l'Hôtel de Ville par Son Exc. Le Kantiba d'Addis-Abeba en l'honneur de S. A. R. Le Duc des ABRUZZES. Le corps diplomatique et les grands chefs Ethiopiens y assisteront. aprés le diner Rèception des notabilités Europeennes et Ethiopieennes.

24 Mai De 9 h m. à 12 h m. Courses de chevaux à Djan Méda A 1 h s. Grand dejeuner au palais Impèrial en l'honneur de S. A. R. Le Duc des ABRUZZES, auquel assisteront sa suite, Les membres du corps diplomatique et les grands chefs de l'Empire.
A 4. h. s. Thé offert par la Lègation Royale d'Italie en l'hönneur de S. A. R. Le Duc des ABRUZZES.
Y Assisteront S. M. L'IMPERATRICE, S. A. I. TEFERI MAKONNEN, et les Grands dignitaires de L'Empire Le soir Dîner à La Lègation Royale d'Italie offert Par S. A. R. Le Duc des ABRUZZES en l'honneur des grands chefs Ethiopiens et Le corps diplomatique. La Visite officielle prend fin le 24au soir.

SERVIE D'HONNEUR

Attachè à Son Altesse Royale Le Duc des ABRUZZES.
Fitaourari Dèssita Damto. General de Cavalerie
Blatta Hrouy. Conseiller de l'Empire.

Suite de Son ltesse Royale
Le Prince MEDEO DI SVOiA
Duc des ABRUZZES
Son Exc.Che valier grand croix JCOPO GASPRINI.
Gonverneur de la colonie de l,Erythrée.
Grand officier *RAFFAELE* GUARIGLIA.
Ministre Plénipotentiaire.
MONTLTO MSSIMO.
Duca di Fragnito
Maitre des cérémonies de S. M. Le Roi d,Italie.
Commandant MALUSARDI.
ide de camp de S. M. Le Roi d,Italie.
Baron de CIUTIIS.
Vice Consul de S. M. Le Roi d'Italie.
LeL ieutenant de vaisseau Comte F. CAPPONI
Officier d'ordonnance de S A. R. Le Duc des ABRUZZES
Le Capitaine de vaisseau de VACSELLO ORNATTI
Commandant la R. N. VENEZIA
Le lieutenant Colonel BoSELLI
Le Capitaine de MARIA
Cavalier RAVA
Sécrétaire général de S. Exc, Le Gouverneur de L'ERYTHREE

የ፻፵፰ ገጽ ተከታይ ።

መልስ ።

ሐምሌ ፪ቀን በቁጥር ፴በገጽ ፪፻፴፤ የተጻፈው ጥያቄ ላይ ደርሰኝ መልሶቹ ደርሰውኝ መርምሬ የጥያቄውንም አኳሆን ተረድቼ የሚገባውን የሚያስፈልገውን መልስ ልስጥ ስል የሚከተለውን እጽፋለሁ አባቶቻችን ለግዕዝ የተሰናዱትን ፊደላት እንዳሉ መያዛቸው የታወቀ ነው ከዚህ ከግዕዝ ፊደል ያማርኛ ፊደላችንን ለይተን አርመን አስተከክለን መያዝ የሚያስ ፈልገን እንዲሁ እስከዛሬ ብዙህ ሰዎች ሳይረዱት ይቀሩ አይመስለኝም ቢሆንም ያልተረዱት ወገኖች በጣም ይበዛሉና ያንኑ የዱሮውን እንይዛለን ሲሉ ሳይሞግዱ (ሳያውኩ) አይቀሩም እኔ ግን ለሀገርና ለመኒግሥት የሚጠቅም የመሰለኝ ሁሉ በጆርናል ልናስታውቅ ነጻ የሰጡንን ል አ ወራሻችንንና ንግሥታችንን በአድሚ ያሰንብትልን እያልኩ የሚጠቅም የመሰለኝን መልስ እጽፋለሁ ።

ከዓለም ፊደሳት ሁሉ በረጅምነትና በሰፊነት የቀረ የኛ ፊደል ቻብ ነው ወረቀትና ቀለም እንደ ሚቻግረኝ ሂሣብና ቢሆን ከዓለም ፊደላት ሁሉ ይበልጥ አጭር መሆን የተገባው ነበር።

ምንይሆናል ብዙህ ሰነፎች ወንድሞቼ ከሁን በፊት የተጻፉት መጻሕፍቶችና መዝገቦች ለሚመጡት ልጆቻችን ሳይታወቁ ይቀራሉ ኢያሉ ያስፈራራሉና የሚያስበውም የለ እኔም አላስበውም ቶሚመጡትስ ልጆቻችን እንዴት የኛ አያቶችና አባቶች በዓለም የሌለውን እረጅም ፊደልና አጭር ቋንቋ አቆዩን ሲሉ በእኛና ባባቶቻችን አባት ያጠፋው ልጁን ያለፋው እየተረከሁ አጭር መንገዶ መፈለጋቸው የሚያይቀር አይመስለኝም ። አሁንም ቢሆን ፊደሎቻችን እጅግ የበዙና የተደራረቡ አንዱ ካንዱ የሚመሳሰሉ ናቸውና ድርቦቹ ቀለሞች ብቻ ስለተነሱባቸው ካማርኛ ቋንቋ የሚሳሳቱ መጻሕፍቶችና መዝገቦች አይገኙም ፊደላችን ቢጠራ ቋንቋችን የሚለውጥ አይደለም አይሆንም እንጂ ፊደላችን እንደሚገባው የሚያጥርልን ቢሆን በጥቂት ጊዜ በትንሽ ቦታ ያሰፉት መጻሕፍቶች ሁሉ ሊገለበጡ የግዕዙቹም አምረው በፍጥነት ሊተ ረጕሙልን ይቻል ነበር ፊደላችን ጠርቶ ታርሞ ያማርኛ ቋንቋችን እንዳለው እንደ ነበረው እየተጣራና እየሰፋ ይሄዳል እንጂ አንዳንዶች እንደሚመስላቸው ተፋልሶ ንግግሩ የሚለውጥ አይደለምና ሊያምርና ሊሰፋ የሚይዙት ፊደሎች በልክ ቢሆኑ ነበር መልካሙ አሁንም እውቀታቸው የሰፋ የኢትዮጵያ ልጆች መርምረው እልኩ ቢያገቡት የሚያስፈልገን ነበር ። አሁን ቢሆን ያማርኛ ፊደል አሐዝ ነጥብ ከግዕዝ ፊደላት ተለይቶ ከውጪ አገርም አንዲት ነጥብ እንኳ ሳይቀር እንደሚከተለው ቢሆንልን እጅግ መልክም መስሎ በትንሹዋ እውቀቴ ይታየኛል።

ከውጪ አገር አንዳች ነገር በጽሕፈታችንና በንግግራችን መበደርና መዋስ አያስፈልገንም ቢሆንልንስ እኛ ከልክ ያለፉ ፊደላት ያሉን ብናበድር ያምርብን ነበር ። ቋንቋውን በውጭ አገር ፊደላትና ቋንቋ ለማስፋት የሚፈልግ ቃል አናገኝምና ነው እንጂ ።

የሚያስቸግሩንን ሁሉ ባበደርን ነበር ። ከእንግዴህ ወዲህ የውጪ ፊደልና ቋንቋ አለመበደርን እንፈልግ በፊደላችን ውስጥ ያሉትን ትርፎች ሁሉ ብድር በሚሰደን ስፍራ እናግባቸው በኛ አገር ላልተለመደው አዲስ ንግግርና የእቃ ስም ተማሪዎችና ጸሐፊዎች አዲስ ንግግርና ስም ባማርኛ ፊደል ማውጣት ይገባናል ያስፈልገናልም የቋንቋ መሠሪያና መወለጃ ከተማሪ ቤትና ከመስሪያ ቤት እንደሁ እናስብ ባገራችን ለማይሠራው እቃና መሳሪያ ያገራችን ነጋዴዎችና የየጉምሩክችን ጸሐፊዎች ሰራተኞች ስም ስሙን ባማርኛ ያውጡ እንጂ እንዴት የራሳችንን ቋነቋ ማስፋት ትተን የሰው አገር ቋንቋና ስም ባገራችን እናሰልጥን? አንዳንድ አዲስ ንግግርና ስም በፊደላችን እንዴት ማውጣት ይቸግረናል? ይኸ የማይሆንልን ቢሆን ምንም ሕዝባችን ሰለጠነ ቋንቋችን ሰፋ ሊባል አይቻልም። ሕዝቡም ቋንቋው ጠፋ ተሰወረ ማለት ነው እንጂ ። ቋንቋችንን ማስፋት ትተን ያዲስ ንግግርና የእቃ ስም ከውጪ ከተበደርን በጊዜ ብዛት ያማርኛ ቋንቋ ይኸ እጅግ የሰፋ ቋንቋ እንዲያጠልቃትና እንዲያጠፉት ዛሬ እናስብ ። አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀውን ትተን አባት ያጠፋው ልጁን ያለፋውን እያሰብን ለኛ ያይደል ላገራችንና ለልጆቻችን የሚበጃቸውን እንስራ ። እናስብ ።

ኢትዮጵያውያን ቋንቋን መበደር እንደ ጀመርን እንደዚሁ ከውጪ ሰዎች እየተጋባን እንደ ሌሎች አገሮች ዘራችንን ለማጥፋት ትውልድ መደረብ ጀምረናል ። ይኸኛው ዋና የኢትዮጵያ ጉዳት እንደሁ የሚአስተውል ሰው ሳይረዳው አይቀርም ይኸ ታላቅ ጥፋት በገንዘብ ፈላጊ ሴቶችና ተምረናል ብለህ ነን እያሉ በሚወጡ (አጉል የሚኰሩ) ኩራተኞች ወንድሞቻችን ፊት ይታየኛል ። ዘር ማጥፋትን ተምረው እንደሁ እንጂ አገር ማልማትን የተማሩ አይመስሉም ። አገርን ለማሰልጠንና ለመርዳት ትልቅና የታወቀች ለማድረግ የተማሩስ ሰዎች ቢሆኑ ለዘራቸው ማልሚያ እንጂ ማጥፊያ ባልሰሩ ። ያገራቸውን ቆቱ እያገቡ ባስተማሩ ባሰለጠኑ ነበር ። ዘራችንንና ቋንቋችንን እንደ ማፋሰት የውጪ አገር ትውልድና ቋንቋ ላገራችን ብናሰፋ እውቀታችን መስፋቱ ቀርቶ ውርደታችንና ድንቁርናችን ሰፋ ማለት ነውና እስቲ ሁላችን እናስብበት ።

ባማርኛ ቋንቋ የማይጠቅሙት ትርፍ ፊደላት ይቅሩና ከሌሎቹም ቀንሶ ልክ የሚያገባቸው ብልሀ ቢገኝ መልክም ነበር ። ሮሜ ም ፲፫ ቁ ፯ ለሁሉም እያንዳንዱ የሚገባውን ስጡ ። ግብር ለሚገባው ግብሩን ካስር አንድ ለሚገባው ካስር አንዱን ፍርሐት ለሚገባው ፍርሐቱን ክብር ለሚገባው ክብሩን እያለ ያስረዳናል እንግዴህ ለግዕዝ የሚገባውን ለግዕዝ እንስጥ ላማርኛ የሚገባውን ላማርኛ እንስጥ ። ስል ። በትንሹዋ እውቀቴ ላማርኛ የሚያስፈልጉንን ፊደላት ፡አሐዝ፡ ነጥብ ፡ሰይቼ ጽፌ የብርሃንና ሰላም ወዳጆችና የአኒምሮ ጓደኞች እንድትመረምሩአቸው ስል አቀርብላችሁ አለሁ ።

ከግዕዝ የተለየ ያማርኛ ፊደል ።

ለመረዳት በየ ቁጥሩ እስር እንመልከት ፡፡

፩ኛ ሀ ሁ ሂ (ሀ) ሄ ህ ሆ ። ፪ኛ (የማጥበቅ ምልክት) ለ ሉ ሊ ላ ሌ ል ሎ ። መ ሙ ሚ ማ ሜ ም ሞ ። ረ ሩ ሪ ራ ሬ ር ሮ ። ሰ ሱ ሲ ሳ ሴ ስ ሶ ። ሸ ሹ (ሸ) ሻ ሼ ሽ ሾ ። ቀ ቁ ቂ ቃ ቄ ቅ ቆ ። ፫ኛ በ ቡ ቢ ባ ቤ ብ ቦ ። ተ ቱ ቲ ታ ቴ ት ቶ ። ቸ ቹ (ቺ) ቻ ቼ ች ቾ ። ነ ኑ ኒ ና ኔ ን ኖ ። ኘ ኙ (ኚ) ኛ ኜ ኝ ኞ ። አ ኡ ኢ (አ) ኤ እ ኦ ። ከ ኩ ኪ ካ ኬ ክ ኮ ። ወ (ው) ዊ ዋ ዌ ው ዎ ። ዘ ዙ ዚ ዛ ዜ ዝ ዞ ። ዠ ዡ (ዢ) ዣ ዤ ዥ ዦ ። የ ዩ (ዪ) ያ ዬ ይ ዮ ። ደ ዱ ዲ ዳ ዴ ድ ዶ ። ጀ ጁ ጂ (ጀ) ጃ ጄ ጅ ጆ ። ገ ጉ ጊ ጋ ጌ ግ ጎ ። ጠ ጡ ጢ ጣ ጤ ጥ ጦ ። ጨ ጩ (ጭ) ጫ(ጨ) ጭ ጮ ። ጸ ጹ አያስፈልግም ጺ ጻ ጼ ጽ ጾ ። ጸ ጹ ጺ አያስፈልግም ጻ ጼ ጽ ጾ ። ፈ ፉ ፊ ፋ ፌ ፍ ፎ ። ፐ ፑ ፒ ፓ ፔ ፕ ፖ ።

ቋ ኋ ኳ ጓ ።

ኋ ሟ ሯ ሷ ቧ ቷ ቿ ዟ ዷ ጧ ጯ ፏ እነዚህ ሁለት ሶስት ቀለማትን ከተው ይይዛሉና እጅግ የሚጠቅሙ ናቸው ። ሆነውም በእጅ ጽህፈት መኪና ለማግባት አያስፈልጉም በምሳሌ ። ኩዋኩዋቴ ፤ ኳኳቴ ፤ ዝቁዋላ ፤ ዝቋላ ፤ ሁዋላ ፤ ኋላ ፤ ባልዋን ፤ ባሏን ፤ ነግሮ አል ፤ ነግሯል ፤ መኩሪያ ፤ መኵሪ ፤ ፉአ ፉአ ፉአፉአቴ ፤ ፏፏቴ እንዴህ ኢየሆኑ ለጊዜና ለቦታ እረዳታ ናቸውና የሚያሰፉቸው ቢገኝ እጅግ መልካም ነበር ።

ትኝሹ ተማሪ በውጪ አገር ያለው መ ሥ ወ ።

ስለ ልዑል ዱክ ዴግ አብሩዝ አቀባበል ።

አስቀድሞ በማስታወቂያ እንደ ተነገረ ግንቦት ፲ ቀን በ፱ ሰዓት ከቤተ መንግሥቱ እስከ ባቡር ማረፊያ ድረስ ሠራዊቱ ሁሉ በለቃ በለቃው ግራና ቀኝ እየሆነ ሰንደቅ አላማውን እየያዘ ተሰለፈ ። በዚሁ ሰዓት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሰልፉን እያዩ ከቤተ መንግሥቱ ወደ ባቡር ማረፊያ ወርደው ባቡሩ እስቲመጣ ድረስ ለልዑል ዱክ ዴግ አብሩዝ መቀበያ በተሰናዳው ድንኳን ተቀመጡ ።

ከዚህ በኋላ ባቡሩ ገብና ከድንኳኑ አጠገብ ሲቆም ሙዚቀኞች የሰላምታ ሙዚቃ አዜሙ ። ወዲያውም ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ልዑል ዱክ ዴግ አብሩዝን በሰላምታ ተቀበሏቸው ። ልዑል ዱክ ዴግ አብሩዝም ከባቡር ማረፊያ ተሰልፎ ሰላምታ ለሰጠ ወታደር እየዞሩ ሰላምታ ሰጥተው ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ጋር ወደ ድንኳኑ ገቡ ። ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም የኢትዮጵያን ትልልቆች መኳንንቶችን እንዳንዳቸውን እያቀረቡ ከልዑል ዱክ ዴግ አብሩዝ ጋር አስተዋወቋቸው ። ልዑል ዱክም በበኩላቸው አብረዋቸው የመጡትን የጣሊያን መኳንንቶችን ከልዑል አልጋ ወራሽ ጋር አስተዋወቁ ፡ ልዑል ዱክ ዴግ አብሩዝ ከባቡር ሲወርዱ ጀምሮ መድፉ ይነጉድ ነበር ። ከድንኳኑ ውስጥም ጥቂት ዕረፍት ከሆነ በኋላ ልዑል ዱክ ዴግ አብሩዝ ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በስተቀኝ በተለየ አውቶሞቢል ተቀመጡ ። አብረዋቸው የመጡ የኢጣልያ መኳንንቶችም ከኢትዮጵያ መኳንንቶች ጋር በየማዕርጋቸው በተሰናዳላቸው አውቶሞቢል ሁነው ጉዞ ተጀመረ ። ነጭ ልብስ የለበሰ ፈረሰኛ ። ቀጥሎ ሰማያዊ የለበሰ መትረየስ አንጋች ዘበኛ ከአውቶሞቢሉ ፊት በሰልፍ ይሄድ ነበር ። ካውቶሞቢሉ በኋላም ያንበሳ አንፋሮ ያሰረ ያንበሳ ጐፈር የደረበ ጋሻና ጦሩን እየያዘ ፈረሰኛ በሰልፍ ይሄድ ነበር ።

ልዑል ዱክ ዴግ አብሩዝም መኪታ መስሎ ግራና ቀኝ ለተሰለፈው ወታደር ሰላምታ እየሰጡ ከቤተ መንግሥቱ ደርሰው ካውቶሞቢል ወረዱና ከቤተ መንግሥቱ ገብተው ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የተገባ ሰላምታ ሰጥተው የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ግርማዊት ንግሥት ሆይ

ግርማዊ ንጉሣችን ቢክቶር አማኑኤል የአርሳቸውን የልብ የወዳጅነት ሰላምታ ለግርማዊ ሰውነትዎ እንዳቀርብ ስለ አዘዙኝ በጣም ደስ ብሎኛል ። ተቀድሞ ዘመን ጀምሮ የተመሠረተው የኢጣልያና የኢትዮጵያ የሁለቱ ትልቅ ቤተ መንግሥቶች ፍቅር ልዑል አልጋ ወራሽና እንደ ራሴ ተፈሪ መኰንን በኛ በኢጣልያ አገር በመጡ ጊዜ በእርግጥ ለዓለም ሁሉ ተገለጠ በዚያውም ጊዜ የኢጣልያ ቤተ መንግሥት መኳንንቶችም ሕዝብም ሁሉ ለኢትዮጵያ መንግሥት ጥልቅ የልብ ወዳጅነት እንዳላቸው አሳዩ።

አሁን ደግሞ ግርማዊ ሰውነትዎ ልዑል አልጋ ወራሽም የኢትዮጵያ መኳንንቶችም ሕዝብም ሁሉ አዲስ አበባ ላይ ለደረስነው ለእኛ ለራሳችን መልክሙን ደስ የሚያሰኘውን አቀባበል ስለ አደረጉልን የተካከለ የፍቅር ምልክት መሆኑን አስበን እጅግ ደስ ብሎናል ።

የግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል መንግሥት በብልሁ በጠቅላይ ሚኒስትር በክቡር ሙሶሊኒ ፈቃድ በፖለቲክ ነገር ሁሉ አለውልውል በቀና መንገድ ስለመሄድ በዚህ ዓለም ክፍል የሁለቱ ትልልቆች አገሮቻችን ጥቅም ለማስፋት የሚስፈልገው ነገር የኢጣልያና የኢትዮጵያ ወዳጅነት መሆኑ ተረድቷል

ከጥንት ጀምሮ ስለ አለው ስለ የክብረት ታሪክዋ የተከበረችው ልዕልት ኢትዮጵያ አሁን በሥልጣኔ መንገድ ፈጥና ወደ ፊት ስትሄድ ታይታ ኢጣልያ በትልቅ ደስታ ታመሰግናለች ።

በዳዊትና በሰሎሞን ልጅ በግርማዊ በአባትዎ በጃንሆይ ዙፋን ላይ በነገሡ በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ መንግሥትና በአዋቂው በልዑል አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንን ትእዛዝ የበለጠውን ልማትና በረከትን ኢትዮጵያ ስታገኝ የሁለታችን መንግሥት ፍቅር እየጠነከረ እንደሚሄድ ጥርጣሬ የለውም። ይልቁንስ ኢትዮጵያና ሁለቱ አገሮቻችን ኤርትራና ሱማሌ ብዙ የንግድ ጠቀሜታ እንዳላቸው የሚያስፈልግ የወዳጅነት ማስሪያ እየሰፋ ይሄዳል ።

ዛሬም ደስ የሚያሰኘው መገናኘታችን የኢጣልያና የኢትዮጵያ የልባቸውን ሀሳብና የሁለቱን መንግሥቶች ትክክለኛ ጥቅም ደስ አሰኝቶ የሚያጠናውንና ስለ ዓለም ሁሉ ሰላም ብርቱ አጋዥ ሆኖ የሚረባውን ፖለቲካ ያስረዳል ።

ለዚህ ለደጉ ሥራ ተአልፍና አልፍ ዓመት ጀምሮ ለሁለታችን ቤተ መንግሥቶች የፈቀደላቸውን እርዳታ አምላክ ያድርግልን ።

ስለዚህ ለግርማዊ ሰውነትዎ የሚገባውን ሰላምታና የልባችንን ምኞት አቅርበን ለግርማዊትነትዎ ለልዑል አልጋ ወራሽና ለቤተ መንግሥትዎ ሁሉ ጤናና እድሜ ለልዕልት ኢትዮጵያ ልማትና በረከት እንዲሰጥ እንለምናለን ብለው ልዑል ዱክ ዴግ አብሩዝ ንግግራቸውን በጨረሱ ጊዜ ደግሞ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የሚከተለውን ቃል ተናገሩ።

ልዑል ሆይ

በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በእኔ በመላ ኢትዮጵያም ስም ሆኜ እዚህ አገር በደህና ለመግባትዎ የማቀርብዎን የወዳጅነት ምኞት ልዕልናዎ ይቀበል ዘንድ እለምናለሁ።

ግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል ፈቃዳቸው ሁኖ ከብዙ ዘመን አስቀድሞ ታሪኩ ገናናነት ካለው ከቤተ ዘመዳቸው ውስጥ ልዑልነትዎን መርጠው ግርማዊትን ለማየት በመላካቸው በተለየ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ልብ በደስታ ተነክቷል ።

የልዑልነትዎም አመጣጥ የነዚህን የሁለቱን ቀዳማውያን መንግሥቶች ሕዝብ በፍቅር የሚያስተሳስር ስለሆነ ለዘለዓለም የወዳጅነት መታሰቢያ ሁኖልን ይኖራል ።

ኢትዮጵያ ለልዕልናዎ ስታደርግ በግርማዊ ንጉሥ ለተመሰለ ሰውነትዎ የምታደርገው አቀባበል ምንም በውበት ኢጣ

ልያ ለእኔ ለራሴ ያደረገችውን የሚያስደንቅ አቀባበል ባይተካከለው ለፍቅራዊ ሐሳባችን የተገለጸ ምስክርና የሁለቱን አገርች ጥቅም ማስፋት ለደስታ እንዲሆን የሚያስፈልገውን መልካም የስምምነት ፍቅር በኢትዮጵያና በኢጣልያ መከከል ለማጽናትና አጠንክሮም ለመያዝ ጥልቅ ሐሳባችን እንደሆነ በእውነቱ የሚያረጋግጥ ነው ።

የልዑልነትዎም ወደኢትዮጵያ መምጣት ግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል እንደኛው ባንድ ዓይነት የፍቅር ምኞት የሁለታችንም አገሮች ሕዝብ በፍጹም ስምምነት እንዲኖሩ ማሰባቸውን ያነረግጥልናል ።

ግርማዊ ንጉሥንና ግርማዊት ንግሥቲቱን ልዕልናዎንም የንጉሡን ቤተ ዘመድና በክቡር ሙሴ ሙሰሊኒ ታላቅ ዕውቀት እየገነነ የሚሔደውን የኢጣልያንን መንግሥት እንዲጠብቅና እንዲባርክ እግዚአብሔርን እንለምናለን ። ደግሞ በደስታ እንዲኖሩና ወዳጃችን የሆነች ኢጣልያ ሐብትዋ እየበዛ እንዲሄድ የበለጠ ታላቅ ምኞታችንን እናደርጋለን ብለው ጨረሱ።

በዚህም መከከል ፳፩ ጊዜ መድፍ ተተኩሶ ልክ ፲፩ ሰዓት ሲሆን ሰልፉ እንደፊተኛው ሆኖ ከቤተ መንግሥቱ ወደ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ግቢ ጉዞ ተጀመረ ። ከቤተ መንግሥቱ እስከልዑል ግቢም ግራና ቀኝ ወታደር ተሰልፎ ነበር ልዑል ዱክም እንደፊተኛው ለተሰለፈው ወታደር ሰላምታእየሰጡብልዑል ግቢ ወደተዘጋጀላቸው ማረፊያ ቤት ገቡ

የሰው ብዛት የሰልፉ ማማር ላየው ብርቅ ለሰማው ድንቅ ነው ።

ብርሂንና ሰላም ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝንና ተከታዮቻቸው የኢጣልያ መኳንንቶችን እንኳን ደህና ገባችሁ እያለ መልከም ምኞቱን ከደስታው ጋር ይገልጻል ።

መልስ

በላ ልበልህ መሠረቱን የአእምሮ ሥራቱን የብርሃንና ሰላም ዕራቱን ። ፈሰስ ከምበል ያርገው የተፈሪን ጠላቱን ።

ወይኩን ቃልከሙ ፩ደ እመኒ እወ እወ ወእመኒ አልቦ አልቦ ፤ እውነቱን እውነት ሐሰቱን ሐሰት በማለት ቃላችሁ ፩ድ ይሁ[illegible] ሲል ነው ። ደጅ አጋፋሪው በቀለ አቦዬ ሆይ በ፫ተኛው ዓመት ብርሃንና ሰላም ቁጥር ፲፰ ስለጻፍኩልህ መልስ ባ፲፱ነኛው ቁጥር መልስ ስትሰጠኝ ከጻፍከው ሁሉ አንድም ፍሬ ነገር አላገኘሁበትም አልከኝ ። ፍሬና ገለባ መለየት ቢቸግርህ ነው እንጂ የጻፍኩልህስ ሁሉም ፍሬ እንደሆነ የብርሃን ልጆች ተረድተውታል ።

ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ አቡሻክር የጻፍከው ጅብን ሲወጉ በአህያ ይጠጉ እንዲሉ ፤ አቡሻክር ፈላጊ መስለህ የዓረብ መምሕር ምርጫ ትፈልጋለህ ። በአቡሻክር መጥፋት የምትቆረቆር ከሆንህስ ብትማርም ብታስተምርም ቀድሞ የዓረብ ልሳን አልቸገረኸም ነበር ፡ ይልቁንም ዛሬ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ለሀገራቸው ነጻነት ምክራቸውን ስላበረቱና ሚሥጢራቸውን ስላገኘኸው ተቆርቋሪ መስለህ ምሥጢር ተከፍለህ ለወገኖችህ ለማውራት የፈለግህ ትመስላለህ ። ባ፲፮ ቁጥር የጻፍከው ጋዜጣ በመንፈሳዊ በኩል ዕገሌ ካህን አሕዛብ አገር ገብቶ ያስተማረ የለም ብለህ የኢትዮጵያን ካህናት በመላው ሰደብካቸው ። አሁን እኔ ለምን ሰደብህ ብዬ በብርሃን ብጠይቅህ ዝልፎ ለጠቢብ ያለውን ሰምቼ ነው እንጂ ጉባዔያቸውን ለመቃወም አይደለም ብለህ ቃልህን አሳበልኸው ። እመኒ እወ እወ ያልኩህ ለዚህ ነው ። መዝለፍስ ቢሉህ ባንተ እንደበት የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሊሰደቡ ይቻላልን ይህም ታላቅ ድፍረት ነው ። የኢትዮጵያን ልጆች መንቃታቸውን ስታከስስ በዛሬ ዘመን ያለ ትውልድ በሥጋዊ ጥበብ እየሰለጠነ ስለ ሀገሩ መናደድን ማንም አያጣውም ብለህ ስለ ሀገራቸው ነጻነት በመንፈሳዊ የጻፉትን ጋዜጣ እንቅፋት ሆንኸበትና መልሰህ ስለሀገራቸው ሰማዕትነት ይቀበላሉ ማለት ነው ብለህ በውዳሴ ከንቱ ትሸነግላቸዋለሁ ።

ደግሞ የኢትዮጵያ ሊቃውንት የሚሾሙ በጉቦ ነው መምህራኑም ለደቀ መዛሙራት አብልተውና አጠጥተው አሳደሩ ሲሉ አልሰማሁም ትለናለህ ለጉባዔው እንደሆነ ቀድሞም እነመምሕር አካለ ወልድ እነ አለቃ ወልደ ጊዮርጊስ እሌህን የመሰሉ ሁሉ ገንዘባቸውን እያበሉና እያለበሱ ያስተምሩ ነበሩ ዛሬም እነ አለቃ ኀሩይ እነመምህር ደስታ እያበሉና እያለበሱ ያስተምራሉ ከአድባራቱ አለቆችም ቢሆን አንተ በጉቦ በገንዘባቸው ኃይል ተሾሙ ስትል ሰማንህ እንጂ እኛስ ዕገሌ አለቃ በጉቦ ተሾመ ሲሉን አልሰማንም የቀድሞ ወዳጅህ ጉቦ ጥሎህ ሸሸልና አየነፍ) ትዘከረዋለህ ።

የከፋት የተንኮል መምሕር ሆንክ ትለኛለህ መምሕራኑን በንፍገት የተሾሙትን አለቆች በገንዘባቸው ኃይል ነው እያልኸ በርቀት ስትሰድብና ስታማ ስለ ሰማሁህ ተንኮልህን ገለጥኩብህ እንጂ የከፋት መምር አይደለሁም ።

ፈያታዊ ዘየማን መኑ መሐረከ ወመኑ ነገረከ ከመ ታእምር ዘንተ እያልህ ባልተማርከው ግዕዝ ቋንቋ ጻፍህ ትለኛለህ ፈያታይ ዘየማን እንደተማረና ከአባቱ ቀድሞ ገነት እንደገባ ማን በነገርህ አልሰማህምን ።

እኔስ ፈያታይ ዘየማን ስላልከኝ ፋንታ ነቢያተ ኢሐሠሥኩ ወሐዋርያተ ኢተለውኩ አላ ብርሃንና ሰላሞ ቀጸበተኒ ዕበ ርኢኩ አመንኩ ተፈሪ መኰንን መድኃኒተ ኰነኒ እላለሁ አልኩህ ይልቁንስ ያልተማረው ረቂቅ ቀማኛ ፈያታይ ዘጸጋም አ[illegible]ተ ነህ እኔም የፊተኛውን ጋዜጣ የጻፍኩበት ምክንያት በነገሬ አላወቁብኝም እንዳትል ነው ። ክቡር አጋፋሪ በቀለ ሆይ ፩ድ ወታደር እንዴህ አለ ሁለት ጊዜ ባላሁ ከዚህ ቤት ገብቼ ፊትም በወራሬ ዛሬም ተመርቼ አለ ይባላል ።

በፊት ያገርህን ልጆዎች ዓባይን የሚአኸል በረሃ ተሻግረው ሲመጡ ለዕንግድነት በመቀበል ፋንታ ነግደ ኰንኩ ብሏልና ብለህ ባለሙሉ ስል ጣን ነህና እንደ ቸርነትህ መጠን በቀጨም ስትጋብዛቸው ኖርህና ዛሬ ደግሞ ለሊቃውንቱ ጥቅም ነው እንጅ የጳጳሳትን ነገር አልጻፍኩም እያልክ በሸንጋላ መላስህ ትደልለናለህ ።

የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ ከዚህ በላይ የተጻፈውን ቃል መርምራችሁ ባልረታ ባልበረታ ቢጠፉ ስደዱኝ ቢለማ ፍረዱኝ ሲል ይሚገታል የብርሃን ተማሪ ለሀገሩ ተቈርቋሪ ። ኃይሌ ሮባ

OMEGA



እጅግ ጥሩነቱ የተመሠከረለት ኦሚጋ በቢ የሚባል ባላንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲግ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ እኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ተኩል ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፪፻፸ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፭ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፪፻፳ ብር ።
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፪፻፳ ብር ።
፡፡ ባለ ድመት ።		፪፻፹፫ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፪፻፺፭ ብር ።
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፪፻፹፭ ብር ።
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፪፻፷፭ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፬ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፬ መ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ
በአንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ ፰ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፴ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፰ ብር ተ፪ ሩብ ።

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚ ወጣ ኃያልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ በንዚን የማፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቀቀዎታል ።

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

ሩግ
ቢ

RUGBY

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፡በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆ የኒ ጠነበ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለሰዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ካኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና ኀሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን ኦቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላሸው ፣ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣል ።

Berliet



ቤርሊዮ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዮ አቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

ARMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶክለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶክለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ኮዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ ቢጋዝ የሚነድ ምድጃ ስንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፳፩
3 me ANNÉE №. 21

ሐሙስ ግንቦት ፲፰ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 26 MAI 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲረክተር
ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።
Diréсteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ።
የዳግማዊ ምኒልክን ተማሪ ቤት እንደጐበኙ ።

ግንቦት ፲፮ ቀን ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ የዳግማዊ ምኒልክን መታሰቢያ ቤት ጐብኝተው ከተመለሱ በኋላ በ፫ ሰዓት የዳግማዊ ምኒልክን ተማሪ ቤት ለማየት ወደ ተማሪ ቤቱ በፈረሰኞች ታጅበው መጡና አስተማሪዎቹ ተማሪዎችን አሰልፈው ባማረ አቀባበል ተቀበሏቸው ። ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ከነ ተከታዮቻቸው በተማሪ ቤቱ በር በቆሙ ጊዜም ተማሪዎቹ በሙዚቃ እየተመሩ የሚከተለውን መዝሙር አሳምረው በመዘመራቸው ደስ አሰኙዋቸው ። መዝሙሩም ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

፩ ። ኢትዮጵያ እጅግ ታላቅ ፥
በዓለም ላይ በስተምሥራቅ ፥
ዝናሽ ብዙ የሚአስደንቅ ፤
ይጠብቅሽ አምላክ ጽድቅ ፥

፪ ። ኮረብቶችሽ ተራሮችሽ ፤
ፍሬያት አዝለው አስጊጠውሽ ፥
ምንጮችሽ ወንዛወንዞችሽ ፥
ሁል ጊዜ ሰምሰም እያደረጓሽ ፥

፫ ። ቡሩካን ሕዝብ ልጆችሽ ፥
እየገነኑ እያበቡልሽ ፤
የኛ ሐገር ውብት በናደሽ ፥
ደስ ደስናል ለልጆችሽ፥

፬ ። አሁንም ደኸው እናታችን ፥
ለሶስት ቀለም ባንዲራችን ፥
ለነጻነት ገንዘባችን ፥
ለማገልገል ምኞት አለን ፥

፭ ። ለዘውዴቱ ለተፈሪ ፥
እድሜን አድልልን ፈጣሪ ፥
ኢትዮጵያ የኛ አኩሪ ።
በደስታ ዘላለም ኑሪ ።

ከበቀለ ሀብተ ሚካኤል ።

ከዚህ በኋላ ተማሪዎቹ በየ ክፍላቸው ገቡና በየ ክፍሉ እየዞሩ ትምሕርት ቤቱንና ተማሪዎቹን አይተው ሔዱ ።

ስለ ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ የልዑል አልጋ ። ወራሽ ተፈሪ መኰንንን ተማሪ ቤት ማየት ።

ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ወደ ተማሪ ቤቱ ሲጐበኙ የሚደረገው አገባብ አስቀድሞ ተሰናድቶ ታትሞ ነበር እንደዚሁም የጨወታው አኳሆን ባጭሩና መዝሙሩ ታትሞ በየ ሰዉ እጅ ተሰጥቶ ነበረ ቃሉም ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው ።

አ ገ ባ ብ ።

ክቡራን እንግዶች ሲመጡ የጋሪባልዲ መዝሙር የልዑል አልጋ ወራሽ ሙዚቀኞች እየመሩቸው ልጆቹ ይዘምሩታል ።

ተማሪዎቹን በየክፍላቸው ማየት ።

የመጻሕፍት ቤት ማየት ።

የጅምናስቲክ ሰልፍ ማየት ።

የመብልና የመኝታ ቤት ማየት ።

ክቡራን እንግዶች ከተማሪዎቹ ጋራ ሥዕል ይነሣሉ ።

በሽማ መሥሪያ ቤት የሽማኔ ሥራ የሚማሩ ልጆች ሲሠሩ ማየት ።

በአናጢነት ሥራ ቤት የአናጢ ሥራ የሚማሩ ልጆች ሲሰሩ ማየት ።

ለማረፊያ በተሰናዳው ቤት የሻይ ግብዣና የተያትር ጨዋታ ።

አንድ ተማሪ ከፈረንሳዊ ክፍል ያጠናውን ይናገራል ።

መዝሙር ።

፩ኛ ፥ የኢትዮጵያ ብርሃን ።

ዘላለም ያኑርልን ።
የነፃነት አምባችንን ።
አምላክ ይጠብቅልን ።

ለሶስት ቀለሞች ዕናት ።
ላገር ለሕዝባችን ልማት ።

እውቀት እውነት ሊነግሡብን ።
ተፈሪን ያኑርልን ።
፬ኛ ። የተ መ ት ቤ ተማሮች ።
ለሠራታችን ሶስት ቀለሞች ።
ክብር መሆን በሕይወት በሞት ።
ነው የኛ ዋናው ምኞት ።
ለሶስት ቀለሞች ፅናት ።
ላገር ለሕዝባችን ልማት ።
እውቀት እውነት ሊነግሡብን ።
ተፈሪን ያኑርልን ።
አንድ ተማሪ ከእንግሊዝ ክፍል ያጠናውን ይናገራል ።

መዝሙር ።

፩ኛ ፡ ለኢትዮጵያ እናታችን
ለነፃነት ትምክሕታችን ።
ለሰንደቅ ዓላማ ሠራታችን ።
እንምላለን መታመናችን ።
፪ኛ ፡ ንግሥተ ነገሥታት ግርማዊት ።
ጠብቅ አምላክ ዳዊት ።
ልዑል የኢ. መ አ ወ ተፈሪ ።
ጠብቅ የዓለም ፈጣሪ ።
፫ኛ ፉከራችን ብርሃን አርነት ።
ዓላማችን ፍርድ ቅንነት ።
መሣሪያችን ጥበብ ትምህርት ብልሃት ።
ምሽጋችን እግዜርን ፍርሃት ።
የተማሪ ቤቱ ሹም ንግግር ።

PROGRAMME

Arrivée de S. A. l'Hote Royal
Hymne de Garibaldi chanté par les éléves avec accompagnement de la musique de S. A
Inspection des éléves dans les classes.
Visite de la Bibliothéque.
Exercices dc gymnastique par les éléves.
Visite du Rèfectoire et du Dortoir.
Photographie des "Hôtes" et des éléves.
Visite de la filature·
Visite de la menuiserie.
Thé dan sla salle de réceptions scène théâ trale.
Morceaux de récitation par un éléve de la section française après la bataille
Le laboureur et ses enfants
Le loup et l'agneau.
Chants
Morceaux de récitation par un éléve de la section anglaise. "A mather's love"
Chants
Discours de M. L'Administrateur

ግንቦት ፲፪ ቀን ልዑል ዱክ ዴገ አብሩዝ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን ተማሪ ቤት ለመጐብኘት በ፱ ሰዓት በፈረሰኛ ታጅበው በመጡ ጊዜ የተማሪ ቤቱ ዋና ሹም ክቡር ሐኪም ወርቅነህ ከአስተማሪዎቹ ጋራ ተማሪዎቹን አሰልፈው በማረ ሰልፍ ተቀበልዋቸውና ተማሪዎቹ በኢጣልያ ቋንቋ አንድ መዝሙር ዘመሩላቸው ። ዘምረው ሰላምታ ሰጥተው ሲያበቁ ተማሪዎቹ በየ ክፍላቸው ገቡና ልዑል ዱክ ዴገ አብሩዝና ተከታዮቻቸው በየ ክፍሉ እየገቡ ትምሕርት ቤቱንና ተማሪዎቹን አዩ አስተማሪዎቹም በየ ክፍላቸው አንዳዱ ከተማሪዎች ከተማሩት ነገር ይጠያይቋቸውና በመላለሳቸው ደስ ያሰኙ ነበር ። ከዚህ በኋላ ደግሞ የሽማ ስራ ተማሪዎችና የአናጢነት ተማሪዎች አይተው ሲያበቁ ለሻይ ግብዣና ለጨዋታ በተ ሰናዳው ቤት ገቡና በሻይ ግብዣ ጊዜ ከተማሪዎቹ እየተነሱ ደስ የሚያሰኝ ጨዋታ ቴአትር አሳዩ

የቴአትሮውን አኳኋን በጭሩ ማስረጃ ።
በጨዋታው ውስጥ ያሉ ሰዎች ።

ዮሐንስ ።
፪ት ባለ ዳዎች ።
የመንገድ ጓደኛ ።
አሮጊት ሴት ።
ጨዋታ የሚያሳይ ሰው ።
ንጉሥ ።
የንጉሡ ሴት ልጅ ።
አስማተኛ ።
ተከታይ ገረዶች ።

መጀመሪ ጨዋታ ።

ሁለት በገንዘብ ዕዳ የገቡ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ጓሮ አካፋና ዶማ ይዘው መቃብር ሲቆፍሩ ፣ ዮሐንስ በጀርባው ኰረጆውን አንግቶ ድንገቱን ደርሶ እንደ ደከመው ሰው እየተ ንገደገደ ሲቀመጥ ፣ በገንዘብ ዕዳ የገቡት ሰዎች ሥራቸውን ተወተ አድርገው የመጣበትን ምክንያት ከጠየቁት በኋላ እንደ ገና ሥራ ይይዛሉ።ያን ጊዜ ዮሐንስ የሰው መቃብር አትቆፍሩ በቅድሚያ እግዚአብሔር ትኰነናላችሁ ቢላቸው ገንዘባችንን ሳይከፍል ስለሞተ በሕይወቱ ደልቶት በጊዜ ሞቱ እንዴት ያር ፋል ፣ ከሞተ ገንዘባችንን እንኳን በናገኝ እንደ ውሻ ሬሳውን አውጥተን ጥለን ቁጭታችንን እንወጣለን ቢሉት ያለኝ ገንዘቤ ፺ ብር ብቻ ነውና የሰውዬውን ሬሳ ላትነኩ ቃል ገብታችሁ ውሰዱ ብሎ ቆጥሮ ይሰጣቸዋል።፪ቱም በገንዘቡ ዕዳ የገቡ ሰዎች ሟቹ የወሰደብን ፴ ብር ብቻ ነበር አሁን ግን ፺ ብር በማግኘታችን ደህና ዕድል ገጠመን እያሉ ዘወር ብለው ከተሾከሾኩ በኋላ ከዮሐንስ ተሰነባብተው ይለያያሉ ፣ ዮሐንስ የመቃብሩን አፈር ሲመልስ ደክሞት አንገቱን ደፍቶ ከእጆቹ መካከል አቀርቅሮ ማረፍ ከተቀመጠበት የመንገድ ጓደኛ ገብቶ ወደ እምትሄድበት ሁሉ ልከተልህ ጓደኛህ ልሁን ብሎ ምሳውን አብረው ሲጋበዙ እንጨት ተሸካሚ አሮጊት እገባለሁ ስትል እንጨት ጠልፎ ጥ

ሏት የመንገድ ጓደኛ ቁስሉን በመድኃኒት ሲያድንላት ይታያል።ቀጥሎ ጨዋታ የሚያሳይ ሰው ጐራዴ ታጥቆ አሽንጉሊት ይዞ ይታያል ከዚህ በኋላ ንጉሡና የንጉሥ ሴት ልጅ በገረዶቿ ታጅባ ይገቡና ወደ ግርዶሽ ተመልሰው ለመሄድ ሲንጉራደዱ ይታያሉ ። ዮሐንስም የንጉሡን ልጅ ለማጨት ራሱ ሂዶ ንጉሡን ለመጠየቅ ይገለገላል ።

፪ኛ ጨዋታ ።

በቤተ መንግሥት ጓሮ ወደ ማታ ።

ዮሐንስና የመንገድ ጓደኛ ወደቤተ መንግሥቱ አብረው ሂደው፣የመንገድ ጓደኛ ደጁን በጁ ቋ ቋ አድርጐ በመታ ጊዜ ንጉሡ ብቅ ብሎ ምን ሁናችሁ መጥታችኋል ቢላቸው ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ልጅዎን እንዲድሩልኝ ጥያቄዬን አቀርባለሁ ሲል ዮሐንስ ይለምናል ንጉሡም በመገረም ቃል ልጄ ለምትጠይቅህ በትክክል መልስ ካላገኘህ እንገትህን ትሰየፋለህ ከመለስህ ግን ልጄን ታገባለህ ብሎ የፈለገችውን እንድትጠይቅ ጠርቶ ካጋጠማት በኋላ ወደ ስፍራው ይመለሳል ። የንጉሡም ልጅ የፈለገችውን ጠይቃ ለመልሱ ጊዜ ሰጥታው ስትመለስ በስተ ጀርባዋ የመንገድ ጓደኛ በዘንግ ሲወጋት አንድ አስማተኛ የገጠማትን በጠየቃት ጊዜ አንድ ሰው የልቤን ሃሳብ ሊነግረኝ ለነገ ቀጥሬዋለሁ ትላለች በቅርብ የሚገኝልሽ ሃሳብ ጫማና ሹራብሽ ነውና ሃሳብሽን በዚሁ ወስንሽ አሣርፊ ካላት በኋላ ተሰናብታው ትሄዳለች ያን ጊዜውን የመንገድ ጓደኛ አስማተኛውን በሰይፍ ሰይፎ ከተጋደመበት ጽሕሙንና ጠጉሩን ቆርጦ በመሐረም ጫፍ ሲቋጥር ይታያል።

፫ኛ ጨዋታ ።

ዮሐንስና የመንገድ ጓደኛ በማግሥቱ ወደቤተ መንግሥቱ ፉጨት እያፏጩ ይገባሉ ። የመንገድ ጓደኛ ዮሐንስን እንዲህ ሲል ይመክረዋል ። በሕልሜ አይቻለሁና ሀሳቧን የጠየቀችህ እንደሆን፡መጀመሪ ያሰብሽው ጫማሽ ነው ።

፪ኛ የጅ ሹራብሽ ነው በልና በ፫ኛው ምንም ሳትናገር በመሐረሙ ጫፍ የተቋጠረውን ፈትተህ አሳያት ። ንጉሡና የንጉሡ ልጅ በሰራዊት ታጅበው ገብተው ከተቀመጡበት መጀመሻውንና ሁለተኛውን ሀሣብ በነገሬት ጊዜ ደስታና እልልታ ሁኖ ልታገባው ተስማምተው ።

፫ኛውን ሀሣቤን ንገረኝ ትለዋለች ። ዮሐንስም እንደ ተመከረው በመሐረም የተቋጠረውን ያስማተኛውን ጽህምና ጠጉር ፈትቶ ሲያሳያት ዓይንዋን ሸፍና በጭካኔው ተንገፍግፋ ትጠላዋለች። ይህን ጊዜ ዮሐንስ ወደ መንገድ ጓደኛ ቀረብ ብሎ የተጠላበትን ምክንያት ሲያዋየው በዘንግ ምታት ትወድህም አለች ብሎ ከሮጊቷ የወሰደውን የጭራሮ ዘንግ ይሰጠዋል ። ዮሐንስም እንደ ተመከረ በዘንግ የንጉሡን ልጅ ቢመታት ያለ ልክ ታፈቅረውና ራሱን ስትስመው ይታያል ።የመንገድ ጓደኛ ዕዳዬን ከከፈልሁህ ፣ ከእንግዴህ ወዲህ አሰናብተኝና ልሂድ እያለ ዮሐንስን ይጐተጉታል ። ዮሐንስም በመገረም ፣ ምን ዕዳ አለ ብህ ፣ ከዚህ ሁሉ ሀብት የነከርሽኝ አንተ ነህና አብረን እንኑር አትሂድ ቢለው ፣ ከመቃብር የሰውዬውን ሬሳ ቆፍሮ አወጣለሁ ሲል ፤ ብር ያስከፈለህን ያን ክፉ ሰው ታውቀዋለህን? ያ ሰው እኔ ነኝ ብሎት ከሰው መካከል ሹልክ ብሎ ሲሄድ ዮሐንስ ሲፈልግ ፣ በመካከል መጋረጃ ሲወድቅ የጨዋታው ፍጻሜ ይሆናል ።

ዘገብረ ሠናየ ኢያሱኡል ዐሰዐ ።

ክቡር ሐኪም ወርቅነህም የሚከተለውን ንግግር ተናገሩ ።

ልዑል ሆይ ።

በዛሬ መጐብኘትዎ ስላደረጉልን ክብር በዚህ ተማሪ ቤት አስተማሪዎችና ተማሪዎች ስም ሆኜ ምሥጋናዬን ለማቅረብ እለምናለሁ ።

ተማሪ ቤታችን ከተከፈተ ሁለት ዓመቱ ብቻ ስለሆነ የሚያኮራ የተፈጸመ የሥራን አይመስለኝም ። ስለሆነ ግን በዚሁ በጭሩ ዘመን ውስጥ የተመላላሾቹ ተማሪዎች ቁጥር ከ፴፪ – ፺ የነዋሪዎቹም ተማሪዎች ቁጥር እስከ ፹፫ እንደደረሰ ብናስተውል ከዚህም ቀደም ንባብና ጽሕፈት የማያውቁ የነበሩት አያሌዎች ልጆች አሁን ሁለቱንም እንዳወቁ ብናስታውስ ። ይልቁንም ዓይነተኛ ነገር የሆነ የበለጠ እውቀትን ለማግኘት ምኞት እንዳደረባቸውና ከነሱም ብዙዎቹ ወደዚህ ተማሪ ቤት በመምጣት አካሄዳቸውን እንዳሳመሩ ብንመለከት ፣ ይህን ተማሪ ቤት በታላቅ ለጋስነት ያቆሙ ልዑል አልጋ ወራሽ ካገራችን ባንዱ ክፍል መልካም አገልግሎት አገልግለዋል ለማለት በሚገባ ይችላሉ ። የትምርት ቤቶች መከፈትና ተማሪዎችን ወደ ውጪ አገር ለትምርት መላክ ፣ የሴቶች ልጆች ትምርት ቤትም ሊከፈት መታሰቡ መንግሥታችን ዜጎቹን በጣም የሚያስፈልግ መሆኑን ተረድቶ የሥልጣኔን መንገድ እንደተከተለ ያስረዳናል ።

የልዕልናዎ አገራችንን መጐብኘት ስለ ኢትዮጵያ ልማትና ደኅንነት በተለየ የልዕልናዎ ፣ በጠቅላላም ትልቅ የኢጣልያንን ሕዝብ ምኞት ይገልጻልና በዝግታ በሰላም ወደ ሥልጣኔና ወደ ብርሃን እንድንገፋ እንዲረዳንና እንዲያደፋፍረን ፣ ለወደፊትም ይህ የወዳጅነት ዓይነተኛ ምኞት እያደገ እንደ ሚሄድ ፍጹም ተስፋ አለን ።

ልዕልናዎን እንደገና እያመሰገንን ጤናና እድሜ እንመኝልዎታለን ብለው ጨረሱ።

ልዑል ዱክ ከተከታዮቻቸው ጋራ ለመሔድ በተነሱ ጊዜም የኢትዮጵያ ብርሃን የሚል ከአቶ ኤፍሬም የተገጠመ መዝሙር በሙዚቃ እየ ተመሩ ዘመሩ መዝሙሩም እጅግ በመድመቁና በማማሩ የሰሚዎቹን ልብ ነካ።

ከዚህ በኋላ ልዑል ዱክ ከተከታዮቻቸው ጋራ ወደ ሰፈራቸው ተመለሱ ።

የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት መሰናዳትና የተማሪዎቹ መሰልጠን እጅግ ደስ አሰኝቶ ዋና ሹሙና አስተማሪዎቹን የሚያስመሰግን ሆኖ ታየ ። በሁሉም ነገር እያደገ እንዲሔድ ሙሉ ተስፋ አለን ።

ሰልፍን ስለ ማየት ።

ግንቦት ፲፫ ቀን ትልቅ ሰልፍ ይታያል ተብሎ በማስታወቂያው እንደ ተነገረ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሰልፉን ለመመልከት እንደሚመጡ ሆኖ

በተደለደለ ከፍተኛ ቦታ ላይ ከፍል ውሀ ሜዳ ዳር ተተክሎ ወደ ተሰናዳው ድንኳን ገብተው ከክቡራን መኳንንቶቻቸው ጋር በተቀመጡ ጊዜ ወደዚያው ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ከተከታዮቻቸው ጋር መጥተው በተሰናዳላቸው ሥፍራ ገብተው ተቀመጡ ። የከተማውም ሰው የሰልፉን አኳኋን ለማየት እንዲመቸው በሜዳው ዙሯ ያለውን ጉብ እየተሽቀዳደመ ሲይዝ ከብዛቱ የተነሣ እርስ በርሱ ይጋፋ ነበር ።

ከዚህ በኋላ የሰልፉ ጊዜ ደረሰና ይህንኑ ሰልፉን ለማየት የተከማቸውን ሰው አጋፋሪዎችና ዘበኞች ከዳር ቁሞ እንዲያይ ቦታ ቦታውን አስያዙት ። በድንኳኑ በርም ዋናው ሰንደቅ ዓላማ ተተክሎ እየተውለበለበ ሲያሸበርቅ በታየ ጊዜ ልብን ደስ ያሰኝ ነበር ።

ከዚህም ሁሉ በኋላ ለሰልፍ የተዘጋጀው ሰልፈኛ ወታደር ባለቃ ባለቃው ሆኖ ተራ ተራውን እየጠበቀ በማረ ሥርዓት ተሰልፎ ሰንደቅ ዓላማውን እየያዘ ፡ የአንበሳ ጐፈሩን እየለበሰ ፡ ፈረሰኛ እየመራው ፡ ፈረሰኛውና እግረኛው ሰልፉን ማሳየት ጀመረና ፡ ጀግና ጀግናው ወታደር ከሰልፉ መኻከል ተነጥሎ ጋሻውን እያርገበገበ ፡ ጦሩን እየሰበቀ ፡ ጐራዴውን እየመዘዘ ፡ ጠመንጃውን በመደገን እየተንበረከከ ድንኳኑ ተተክሎበት ወደ ነበረው ጉብ ዳገቱን ወጥቶ ከድንኳኑ በር ቀርቦ የጀግንነቱን ሞያ በመቁጠር እንደ አንበሳ እየዘለለና እየፈነጨ ያንበሳ ደቦል መስሎ ሲፎክር በታየ ጊዜ ያፈጣጠኑና ያቀለጣጠፉ ፡ ያረማመዱና የሰውነቱ ማማር ፡ የብርታቱና የጥንካሬው ነገር በጣም የሚያስደንቅና የሚያንቀጠቅጥ ነበር ።

እንደዚህም ሁኖ የብዙ ብዙ ሠራዊት ካለፈ በኋላ የክቡር ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው ሠራዊት ፈረስ ዘበኛ እንደ ነፋስ የሚፋጠን ፈረስ ፈረሱን እየተቀመጠ ያንበሳ ጐፈሩን ለብሶ ፡ ጋሻውን አንግቦ ፣ ጠመንጃውን አንግቶ ፡ ጦሩን እሰየበቀ በየ ደንቡ ሁኖ ተሰልፎ ሲያልፍ የብዛቱና ያኳሁኑ ነገር እጅግ እድርጎ አስደነቀ ። ክቡር ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠውም ሠራዊታቸው እስኪያልፍ ድረስ ባማረ ፈረስ ተቀምጠው በሥርዓት እንዲያልፍ ትእዛዝ እየሰጡ ይመለከቱት ነበር ።

ይህም ከሆነ በኋላ እንደዚሁ ሆኖ ብዙ ሠራዊት በያለቃ በያለቃው ሰልፉን በሚያስደንቅና በሚያበገርም አኳኋን እያሳየ ተሰልፎ ካለፈ በኋላ ደኅና አድርጎ ሰልፍ የተማረው የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዘበኛ ግራዝማች ገብረ ዮሐንስ ባማረ ነጭ ፈረስ ተቀምጠው እየመሩት ሙዚቃ እያስመታ በደረሰ ጊዜ ሜዳውን አናወጠው ። የተመልካቹንም ዓይን ሁሉ ከማማሩ የተነሣ አለመለመው ። ይልቁንም በድንኳኑ ትይዩ እሜዳው መኻከል ቆሞ የሰላምታ ሙዚቃ እየ ተነፋለትና እየ ተመታለት ሰላምታ በሰጠ ጊዜ ልዑል አልጋ ወራሽና ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ከመኳንንቱ ጋራ ተነሥተው ሰላምታ ሰጡትና ከፍልወሀ ሜዳ ዙሪያ አንስቶ እስከ ከተማው መኻከል ጭብጨባው ቀለጠ ።

ደግሞ እንደገና እንደዚሁ ሁኖ አምሮ ሰልፉ ሲታይ በማስታወቂያ የተነገረው ሰልፉ ሊታይበት የተወሰነው ሰዓት ተላለፈና ሰባት ሰዓት ተዡል ሲሆን ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ከተከታዮቻቸው ጋራ ልዑል አልጋ ወራሽን ተሰናብተው በቀጠሮ ተዘጋጅቶ ይጠባበቃቸው ወደ ነበረው ቦታ ተመለሱ ። ስለ ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ክብር ከተሰበሰበው ሠራዊትም ፤ ሰዓቱ ስለ ተላለፈ ከብዛቱ የተነሣ ሰልፉ ሳይታይለት ተርፎ ቀረ ።

ይህንንም የሰልፉን ማማርና የሠራዊቱን ብዛት በሜዳው ዙሪያ ቆሞ ይመለከት የነበረው ሰው ሁሉ ፡ ባዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ያለው ወታደር ብቻ እየ ተከፈለ ወጥቶ እንደዚህ አድርጎ የበዛ ከቶ በዳር አገር ያለው ወታደር በመላው ክተት ተብሎ ተሰብስቦ ቢሆንማ ምን ስፍራ ይበቃው ኖሯል እንዴትስ ሆኖ ተሰልፎ ይታይ ነበር ግሩም ድንቅ እያለ ፈጣሪውን በማመስገን ሲደነቅ ፈጽሞ ደስ ያሰኝ ነበር ።

እውነትም የሚገርምና የሚያስደንቅነገር ነው።በአዲስ አበባ ዙሪያ ባሉ አውራጆች ያለ ወታደርማ በመላ ካተሰበሰበ የፍልወሀ ሜዳ እንዴት አድርጎ ይበቃው ነበር ። ባዲስ አበባ ዙሪያ ያለ ወታደርን ተሰብስቦ ይችላል ማለት ይቅርና ፤ የሁለት እራሶች አገር ወታደር ባንድ አይቅር ከተሰበሰበ አይችልም ነበር ።

እንደዚህ ሆኖ ሰልፉ ከታየ በኋላም ሠራዊቱ ሁሉ ወደ ቤቱና ወደ ሰፈሩ ደስ ደስ እያለው ተመለሰ ።

ልዑል ዱክ ዴዝአብሩዝ
አዲስ ዓለምን ከተማ እንደ ጐበኙ ።

ግንቦት ፲፩ ቀን በ፪ ሰዓት ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝና ተከታዮቻቸው ከልዑል አልጋ ወራሽ ጋራ ካዲስ አበባ ተነሥተው ወደ አዲስ ዓለም ከተማ ሄዱና ሲጐበኙ ውለው በ፲ ሰዓት ተመልሰው አዲስ አበባ ገቡ ። ከማታው ፪ ሰዓት በፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው ቤት ራት ተጋበዙ ።

ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ
የአዲስ አበባን ማዘጋጃ ቤት እንደጎበኙ ።

ግንቦት ፲፫ ቀን ከማታው ባ፬ ሰዓት ተኩል ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝና ተከታዮቻቸው ከልዑል አልጋ ወራሽ ጋራ ወደ ማዘጋጃ ቤት ሄዱና ግራዝማች ማህሌ ዘበኞች አሰልፈው በክብር ተቀበሏቸው ። ክቡር ከንቲባ ነሲቡም ማዘጋጃ ቤቱን ውጭውንና ግቢውን በሰንደቅ አላማና በኤሌትሪክ መብራት አስጊጠው ግሩም በሆነ አቀባበል ተቀበሏቸው ። ወደዚያውም ስለ ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ክብር በማዘጋጃ ቤት ራት ተጋበዙ ።

ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ
በጃን ሜዳ የፈረስ እሽቅድድም ለማየት እንደ ሄዱ ።

ግንቦት ፲፯ ቀን ከጡዋቱ በ፫ ሰዓት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከነመኳንንቶቻቸው ፤ ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝም ከነተከታዮቻቸው የፈረሶቹን እሽቅድድም ለማየት እንደሚመች ሆኖ አምሮ ወደ ተሰናዳው ቦታ ደርሰው በተቀመጡ ጊዜ ከዚህ ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ቃል ሆኖ የፈረሱ እሽቅድድም ተጀመረ ።

መጀመሪያ እሽቅድድም ።

አንደኛ ፤ የሙሴ ክራ ፈረስ ቀደመና ዋንጫና ፵ ብር ፤ ሁለተኛ ፤ የሙሴ ማክሊን ፈረስ ሆነና ፴ ብር ፤ ሶስተኛ የሙሴ ፓፕ ፈረስ ሆነና ፲ ብር ተቀበሉ ።

ሁለተኛ እሽቅድድም ።

አንደኛ የልዑል አልጋ ወራሽ ፈረስ ቀደመና ዋንጫ ፵ ብር ሁለተኛ የዶክቶር ሐስ ፈረስ ሆነና ፴ ብር ተቀበሉ ሶስተኛ ፡ የሙሴ ዴስኬ ሞንትቢላንድ ሆነ ።

ሶስተኛ እሽቅድድም ።

አንደኛ ፡ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፈረስ ቀደመ ። ሁለተኛ የማድሙዋዜል የውብ ዳር ብሩ ፈረስ ። ሶስተኛ ፡ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፈረስ ሆነ ።

አራተኛ እሽቅድድም ።

አንደኛ ፡ የማዳም ዋይስ ፈረስ ፡ ሁለተኛ የሙሴ ቤንቲንክ ፈረስ ፡ ሶስተኛ ፡ የሙሴ ዲሴሞንተቤላርድ ፈረስ ሆነ ።

አምስተኛ እሽቅድድም ።

አንደኛ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ቀደመ። ሁለተኛ ፡ የማድማዜል የውብ ዳር ብሩ ፈረስ ፡ ሶስተኛ የልዑል አልጋ ወራሽ ፈረስ ሆነ ።

ስድስተኛ እሽቅድድም።

አንደኛ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፈረስ ቀደመና ዋንጫና ፶ ብር ፡ ሁለተኛ የሙሴ ቤንቲክ ፈረስ ሆነና ፴ ብር ተቀበሉ ። ሶስተኛ የሙሴ ቤንቲንክ ፈረስ ሆነ ።

ሰባተኛ የእንጦጦ እሽቅድድም ።

አንደኛ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፈረስ ቀደመ ፡ ሁለተኛ ያቶ ሚካኤል ብሩ ፈረስ ሆነ ።

ስምንተኛ የዝላይ እሽቅድድም ።

አንደኛ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ቀደመና ዋንጫና ፶ ብር ፡ ሁለተኛ የሙሴ ክሬ ፈረስ ሆነና ፵ ብር ፡ ሶስተኛ የዶክቶር ሐስ ፈረስ ሆነና ፴ ብር ተቀበሉ ፡

ከዚህ በኋላ ይህ ከዚህ በላይ የተነገረው ስጦታ ሁሉ በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፊት ቀረበና ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ አንድ አንዱን እያነሱ ስጦታውን ሊቀበሉ ተዘጋጅተው ለነበሩት ሰዎች ሰጡ ።

እንደዚህ ሁኖ አምሮ የሽቅድድሙ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላም ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል የኢ መ አ ወ ተፈሪ መኰንን ከክቡራን መኳንንታቸው ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝም ከተከታዮቻቸው ጋራ ባማረ አጀብ ወደ ቤተ መንግሥቱ ገብተው ስለ ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ክብር ትልቅ ግብር የደስታ ግብዣ ተጋበዙ ።

ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ
ከአዲስ አበባ ወደ አገራቸው ለመሔድ እንደተነሱ ።

ግንቦት ፲፯ ቀን ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ከአዲስ አበባ ወደ አገራቸው ለመሔድ መነሣታቸው በእርግጥ ስለ ታወቀ የውጭ አገር ሚንስትሮችና ቆንስሎች ነጋዴዎችም ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝን ለመሸኘት ወደ ባቡር መቆሚያ ወረዱ ። የልዑል አልጋ ወራሽ መትረየስ ዘበኞችና የአዲስ አበባ ከተማ ዘበኞችም በባቡሩ መቆሚያ ተሰልፈው ይጠባበቁ ነበር ፡ ልዑል አልጋ ወራሽም ከብዙ መኳንንቶች ጋራ ወደ ባቡሩ መቆሚያ ወርደው እንግዶቹን ለመሸኘት ተተክሎ በነበረው ድንኳን ገብተው ተቀመጡ ፡

ከዚህ በኋላም ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ከነተከታዮቻቸው ከባቡሩ መቆሚያ ደርሰው ልዑል አልጋ ወራሽ ካሉበት ድንኳን ገብተው ጥቂት እንዳረፉ ባቡሩ የሚነሣበት ጊዜ ስለ ደረሰ ከልዑል አልጋ ወራሽና እዚያ ከነበሩ መኳንንቶች ሁሉ ተሰናብተው ልዩ ሆኖ ወደ ተሰናዳላቸው ባቡር ገቡ ፤ ባቡሩም ለመሔድ በተነሣ ጊዜ ተሰልፎ የነበረው ወታደር የሰላምታ ጥሩንባ እያስነፋ ሰላምታ ሰጠ ፡

ብርሃንና ሰላም ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝን ከነተከታዮቻቸው በደህና አገራችሁ ለመግባት ያብቃችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ያቀርባል ።

የ፻፷፯ ገጽ ተከታይ ።

፩ኛ ፡ ያማርኛ ቁጥሮች ወይም አኀዞች ።

፩ (1) ፪ (2) ፫ (3) ፬ (4) ፭ (5) ፮ (6) ፯ (7) ፰ (8) ፱ (9 ፩0 (10) ፲፩ (11) ፲፪ (12) እንደዚህ አካሂድ ቢሄዱልን እጅግ መልካምና ለሒሳብ ልክ እንደ ዓረብ ማለት እንደ ኤውሮፖች ቁጥር ይሆንልን ነበር ። በተረፈ አራተኛውን ቁጥር አስር እን መልከት ።

፪ኛ ፤ ነጥቦች ።

በፍጥነት በችኰላ ሲጻፍ አንዱ ንግግር ካንደኛው እንዳ ይደበለቅ እንደ ተለመደው እንደ ግዕዝ በእጅ ጽሕፈት ቢገቡ አይከፉም ። በእጅ መኪና ሆነ በማኅተም ጽሕፈት ጊዜ መጨረሻ ናቸውና ብርሃንና ሰላም እንዳስተማረን ይሁኑ ። በሌላው ረገድም ብድር ከመሄድ የራሳችንን ማቃናት ይበልጣል ። ኤውሮፖች የዓረብን ቁጥር በመበደራቸው ስንት ይናደዱ ይመስላችኋል? እነሱስ ቢቸግራቸው ነው ። እኛ ግን ማሰናዳት ቢያቅተን ይሆንብናል እንጂ ችግርስ የለብንም ።

ማስረጃ።

፩ደኛ ፡ ሁለት ጊዜ የሚደጋገሙትንና ላማርኛ የማያስ ፈልጉትን አውጥቼ በነሱ ቦታ የሚገቡትን ለማሳየት ስል በዝርዝር መዕከል ጽፌአቸዋለሁ በመማርያ ፊደል ውስጥ ግን እንዴህ አይጻፉም ።

፪ተኛ ፡ መጥበቅ የሚገባው ቀለም ላይ የማጥበቅ ምልክት [.) (የማጥበቅ ምልክት) ውልብ [ስሚ] እናድርግ በምሳሌ ጅማ ያገር ስም ጅማ የሰው ስም ያ ችግኛችን ጅብ ብሎ ወጣ ያ ችግኛችን ጅብ ብሎ ወጣ ። ከፊተኛው እጅብ (ችፍግ) ይላል ከኋለኛው ግን ጅብ (ዢብ ይመስላል እንደዚሁ ብዙ ስምና ነገር አሉ ።

፫ተኛ ፡ የውጭ አገር ስሞች በዜች ቀለም የሚጻፉትን ስንተረጉም Vበ ከበላይ ይህቺን መስመር እናድርግ ምሳሌ Vittorio ቢቶሪአ Victor ቢክቶር ።

፬ተኛ በግዕዝ ቁጥር ከላይና ከታች የሚሰረዙት ሰረዞች አያስፈልጉንም ፫ ፮ ፯ ከ(ገ) ከ(ጌ) ከ(ጊ) የሚደነጋገሩ የሚሳሳቱ አይመስለን አሀዝ የሚገባበት ንግግር በተከታዉና በመጭው

ይለያል ይታወቃል የግእዝን ፩ ላማርኛ አዲስ ቁጥር ምንም (ባዶ ዜሮ) ለሚባል ከንድ ፩ ቁጥር በፊት ለሚገኝ እናድርጋት አኑ ዓን ላማርኛ አራት (፬) ቁጥር እናግባ ። የግዕዝን ቁጥሮች ለግ ዝና ። ለዘመን ለማእርግ ለተርታ ለማለት ፩ደኛ ፪ተኛ ፡ ፫ተኛ ፬ተኛ ኢያልን ከመጻፍ ተኛን ኢየተውን ፩ ፪ ፫ ፬ ኢያደረ ግን እናስለምዳቸው ። አለበለዚያ የግእዝ ቁጥር ላማርኛ እጅ ግም አይመቹም ።

፫ኛ ፤ ነጥብ የሚስያደንቅ ሆኖ ከነገር መጨረሻ ሲሆን የሚያስደንቅ ጥያቄ ሲሆን ፯ኛ ፊደላቱን ከለየሁ ወዲህ በነዚህ በደነባኋቸው ፊደሎች ብቻ ነውና የጻፍኩት አንዳንዶች እንደ ሚመስላቸው ትርፎቹ ቀለማት ስለወጡ ንግግራችን ተሳስቶ ምስጢሩ ይሰወራችሁ እንደሁ እስቲ አስተውሉ ።

እኔ እውቀቴ ያነሰ ትንሽ ደንቆሮ እንደሚገባ እመድባለሁ ብዬ አይደለም እነሳሴ እነሳሴስ ድርቦቹን እንተው ለማለትና እውቀታቸው የሰፋ ብልሆችን ቀስቅሼ እንደሚመችና ጊዜና ገንዘብ ጨራሽ እንደማይሆን ። እጥር ምጥን አድርገው ። ነገ ተነገ ወዲያ ሳይሉ ባዲሱ ቋንቋችን (ባማርኛ) ልክ እንዲደነግጉልን ልቀስቅስ ስል ነው ። ይህ የማይሆንልን ቢሆን ። አሁን እንደ ጻፍኩት ልክ ለመማርያ እንዲመች ከየምሳሌው ጭምር በመዝገቡ ጽፌ እንዳሳትመው የብርሃንና ሰላምን ወዳጆች ምክርና ቃል እጠብቃለሁ ፊደላችን አምሮ እልኩ ከደረሰ በኋላ ብርሃንና ሰላም ፪ ዓመት ቁጥር ፴ በገጽ ፪፻፫ ኢትዮጵያዊው ተማሪ የጻፈልንን የስልጣኔ አረዳትና መሪ እንደሚለው ቋንቋችንን ሁሉ ባንድ መጽሀፍ መሰብሰብና በክቡሴር የሚባለውን መጽሐፍ ማሳተም ያስፈልገናል ። ፊደላችን ሳይታረም ቋንቋችንንና ባገራችን የሚገኙትን እንስሶች አትክልቶች ያገር ክፍል ስሞች እነዚህን የመሰሉ ነገሮች ሁሉ ባንድ ላይ ከቶ የሚይዘው ትልቅ መጽሐፍ እንዲታተም ለብርሃንና ሰላም ወዳጆችና ለአእምሮ ጓደኞች አመለክታለሁ ። ምርመራ ።

እስቲ ያማርኛ ፊደል ቢረዝምና ቢሰፋ ምን እንድንጐዳ ቢያጥርና በልክ ቢሆን ምን እድንጠቅም እንመርምር ፤ ብርሃንና ሰ እንዳይሰለቸኝ ስል ባጭሩ እጽፋለሁና እንባቢዎች አርዝሙት ቋንቋችን የሚመደብበት ፊደል ቢበዛ ያንን ሁሉ ዝብዝብ ለማወቅ (ለመማር) ብዙ ጊዜ ያስፈልገናል በነዚያ ሁሉ ቀለማት መጽሐፍ ሆነ ሌላ ጉዳይ ለመጻፊያ ብዙ ጊዜና ሰፊ ወረቀት ብዙ ቀለም ያስጨርሰናል የውጭ አገር ሰዎች ብዛቱን አይተው ይሸሹሉ እንጅ ኢየተማሩት ቋንቋችን በየትም የታወቀ አይሆንልንም ከሁሉ ይበልጥ ለህዝብና ላገር የማስታወቂያ ጉዳይና ጁርናል ሆነ ሌላም ነገር ሁሉ በቶሎ በፍጥነት ታትሞ ሊወጣልን አይቻልም ። ፊደል ለቃሚዎች ሀመሩ (ሐ)ንጉሱ ሠ አይኑ ዐ ጃሮውኸ ኢያሉ ሲመርጡ ሲያማርጡ ሲያነሱ ሲጥሉ ጊዜው ያልፋል።

በእጅ ጽሕፈት መኪና ፊደሎቻችን መግባታቸውን ይቀርና ዞረንም መኪናውን ለማየት የማይቻለን ነው ። ይኸ እክልና ጉዳት ሁሉ እንዳያገኘን ብናደርግ ብዙ የጊዜና የገንዘብ የጥቅም ትርፍ እንድናገኝ ሁላችን እናስብ ።

እስቲ የዓለምን ታሪክ እንመልከት ።

የመጀመሪያ ጽህፈት ስእል ብጤ ነበር እሱውም እንደ እንስሳ እንደ አትክልት እንደ ዕቃ አይነት ስዕል እንደ ተገኘ ይመስላል አይመስልም ሳይባል ይጫር ነበር ። እነዚህም ስእሎች ከጥቂት ዕቃና እንስሳ ማመልከት በተቀር የማይጠቅሙ ነበሩ ከዚህ በኋላ እነዚሁኑ ስእሎች ከፋፍለው አብዝተው አንዳንድ ሀሳብ ንግግር እንዲያመለክቱ ደነገጓቸው በምሳሌ መሄድ ሲሉ የሚራመድ እግር ብጤ አየሁ ሲል የተከፈተ አይን ያየው ሰው ቢሆን የሰው ብጤ መሳል ሌላውንም ነገር እንደዚሁ ኢየጫሩ ከብዙው ሁለት ሶስቱ ሀሳባቸው ይታወቅላቸው ጀመር ፤ ከዚህ በኋላ ሰው ኢየበዛ ንግግሩ ኢየሰፋ ሲሄድ መክረው ያለውን ግግር ሁሉ የሚይዙ ልክና ቁጥር የሌላቸው ምልክቶች ሰሩ (ጻፉ) እነዚያን ሁሉ ምልክቶች ማንበብና መጻፍ የሚያውቅ ሰው ገና እኑን በማጥናት እራሳቸው ይሸብት ነበር ። ይኸ ሁሉ ሲሆን እነዚህ ምልክቶች መልክ እንጅ የንግግር ድምጽ የላቸውም ። ከዚህ በኋላ (ግብጾች የሰውን ቃል ድምጽ ንግግር ኢያደመጡ አንዳድ ምልክት አወጡ እንዴህ አድርገው በሲል አንድ ምልክት ቡ ሲል ሌላ ከበ የማይቀርብ ምልክት ቢ ሲል እንደዚህ ከ ቡ የራቀ ለሌሎቹም ፊደላት ሁሉ ልዩ ልዩ የሆነ ምልክቶች እጅግ የበዙ አወጡ ። እነዚህን እጅግ የማይቀራረቡ ፊደሎች ሁሉ እስቲ ያጠኑ ብዙ ዘመን ያስፈልጋቸው ነበር ይላል ።

ትንሹ ተማሪ በውጭ አገር ያለው ። መ ሥ ወ ።

የውጭ አገር ወሬ ፤ የሶቢየት እድማ በቻይና ።

በሶቢየትና በቻይና መካከል ስላለው አድማ የተተረጐሙ ደብዳቤዎች ከብዙ ፎቶግራፍ ጋራ ተይዘው ጋዜጣ አታሚዎች እንዲመረምሩና የምርማሬውን ፍጻሜ እንዲያስታውቁ ተጠይቀዋል ። በምርምር ጊዜ በረቂቁ ላይ ስማቸውን የፈረሙት በልታወቁ ደብዳቤዎች ስለ መገኘታቸው እርግጥነት በማናቸውም ጥያቄ አያስፈልገንም ። የተያዙትም ደብዳቤዎች ፈጽመው የሚናገሩት የአድማ ሥራ መሆኑን ፤ የሶቢየት መንግሥት ከሕዝቡ ገንዘብ አዋቶ የጦር መሣሪያ እየ ገዛ ለቻይና መስደዱ በፖለቲካ አካሄድና ወታደር አርጋንዜሽን ለሚረዱ ሁሉ ደመወዝ መስጠቱ እርግጠኛ ምስክር ሆነ ። ከተያዙት ደብዳቤዎች መካከል ባንደኛው ላይ ምስጢር ነው የሚል ቃል ከጻተፈበት ውስጥ ለቻይና ወታደር የተላከው የጦር መሣሪያ ቁጥር ተጽፎ መገኘቱም እይነተኛ ማስረጃ ነው ። የመሣሪያውም ቁጥር ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው ። ፳፬ መድፍ ። ፯ መትረየስ ፤ ፳ ፩ ሺ ፬፻ ፫ መስኮብ ጠበንጃ ፤ ፬ሺ ሌላ ዓይነት የጃፓን ጠበንጃ ፤ ፳ ፪ሺ ቦምብ እንደ ድማሚት የሚፈነዳ) ፲ ፰ ምሊዮን መስኮብ ጥይት ፤ ፪ ምሊዮን የጀርመን ጥይት ፤ እኩል ምሊዮን የጃፓን ጥይት ። ፲ሺ ድግን መትረየስ ትርፍ መሣሪያ ጭምር ፤ በዚሁም ምስጢር ነው በሚለው ደብዳቤ ውስጥ ከግርጌው ማመልከቻ ተጽፎበታል ማመልከቻውም እንዲህ ነው ፤ በታኅሣሥ ፲ ፱ ፻ ፳ ፫ ዓ ም ለቻይና ወታደሮች ከመስኮብ አገር ገና የሚላክ የጦር መሣሪያ ቁጥር ፳ ፫ ሺ ጠበንጃ፤ ፴፪ ሚሊዮን ጥይት ፤ ፻፴ መትረየስ ፤ ፵፪ መድፍ ፤ ፵፬ ሺ ቦምብ ፤ ፲ ፱ ሺ ድግን መትረየስ ፤ ፫ ሺ ጐራዴ ፤ ፲ ሺ በሽታ የሚገል ብትን መርዝ ፤ ፫ ሺ ማስክ (ብትኑ መርዝ ወደ አንጫ እንዳይገባ የሚከለክል መሣሪያ) አስር ነበልባል ወርዋሪ ብረት ፤ ፮ አውሮጵላን ሌላም ትንንሽ መሣሪያ ተጽፎበታል ።

የእጅ ዝኒት ሰዓት



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሠከረለት ዝኒት የሚባል ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲግ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፰ ብር ተ፫ ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፹፪ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፩ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፮ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፩ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፩ ብር ።
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፻፴፬ ብር ።
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፳፫ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፯ ብር ።
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፰ ብር ።
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፶፩ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፪ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፫ ሩብ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፳፭
በአንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ ፳፭ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፭ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚ ወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል ።

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ግልጸ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል ቡተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

የዘ ህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፡ ሸቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኵታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፌታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሄስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፤ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፤ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

Berliet



ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ አቶሞ ቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንክራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ።

ARMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሸቶና ሎሲዮን አዶክለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሸቶና የአዶክለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ክዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፳፪
3 me ANNÉE № 22

ሐሙስ ግንቦት ፳፭ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ.ም
JEUDI 2 JUIN 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix ".

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲረክተር
ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።
Diréctеur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፊደን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

በልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ የተደረገ ሙሉ ግብር ።

በግንቦት ፲፰ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ፡ ፳፪ ቀን ሙሉ ግብር ሁኖ በከተማ የሚኖርና እንግዳ ወታደር ባለቃ ባለቃውና በየደንቡ እየተጠራ በልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ የደስታ ግብር ተጋበዘ ።

የግብሩለትም ልዑል አልጋ ወራሽ ከነመኳንንቶቻቸው በዳራቹ ከመቀመጣቸው አስቀድሞ አዛዦች የሚያስፈልገውን ምግብና መጠጥ በያይነቱ አዘጋጅተው ከመጠባበቃቸው የተነሣ ከላይ በተነገሩት ቀኖች መኳንንት መኳንንቱ እንደ ማዕርጋቸው በመጋረጃው ውስጥ ገብተው ከተጋበዙ በኋላ ፡ መጋረጃው ይገለጥና እጋፋሪዎቹ ሠራዊቱን ሁሉ በደንብ በደንቡ እስገብ ተውት የተዘጋጀለትን መብልና መጠጥ ደስ ደስ እያለው ሲጋበዝና ፡ ጀግና ጀግናውም የጀግንነቱን ሥራ እየቆጠረ ሲፎክር ልብ አድርጎ ሰሰማውና አስተውሎ ለተመለከተው እጅግ አድርጎ ያስደንቅ ነበር ።

ይህም ሁሉ ሲሆን በግብሩ ሲበላና ሲጠጣ የዋለው ሠራዊት እድሜ ለንግሥታችን እድሜ ለአልጋ ወራሻችን እያለ ልዑል እግዚአብሔርን ያመሰግን ነበር ።

የሁለት ክፉ ጠባዮች መሻሻል በወለጋ ፡ አንደኛ ስለ ሌባና ቀጣፊ ።

እንደሌላው አገር ሁሉ በወለጋም ሌባና ቀጣፊ በብዙ ይገኝበታል ነገር ግን የዘንድሮው ኑሮውና ያምናው ከዚያም በፊት የነበረው ኑሮው በጣም ልዩ ሆኖበታል ያምናው ወይም ከዚያ በፊት ያልሁት ኑሮው በጣም የተመቸ ነበር እንደምን ቢሉ አንዱ ሌባ የሚኖርበት ባንዱ አገረ ገዥ ውስጥ ይሆንና ያንዱም ሌባ መኖሮ በሁለተኛው አገረ ገዥ ይሆናል አንዱ ሌባ ከገሩ የሠረቀውን ላም ይሁን በሬ ፈረስ ይሁን በቅሎ ሌላም ነገር ሁሉ ከሌላ አገር ለመጣው ሌባ አሳልፎ ሰጥቶ ያ የብዙውን ዋጋ በጥቂት ዋጋ ሸጦ ለውጦ መካፈል የሁለቱ ሌቦች ልማዳቸው ነው እንደዚህም የሚያደርጉ ሌቦች ባገር የታወቁ ናቸው ሥራቸውም ኩራጁ ይባላል ትርጓሜውም የሰረቁትን ነገር የባለ ብዙውን ዋጋ ነገር በጥቂት ዋጋ መሸጥ ማለት ነው ደግሞም በውስጣቸው የሚታዘዙ ደዘህ ብረሮች አሉ እንዲህ እየተባበሩ ሴትኛ አዳሪንና ደሀ ገበርን ያገርንም ሽማግሌ ሲያሰዝኑ ይኖራሉ። ባላገርም ሰው ቀን ሲሰራ ውሎ ሌት እነሱን በመጠበቅ እንቅልፉን አጥቶ ሲያድር በማግሥቱ ለለት ሥራው የሰነፈ ይሆናል ከዚህ በላይም እንዳልሁት ባገር የታወቁ ናቻው ና ቀን ደሀና ሰዎች መስለው አምስቱ ምስክር አንዱ ከሳሽ ሆነው የደሃን ገንዘብ ሲሆን በመርታት አለዚያም በግልግል ሲቀሙ ይታያሉ ወየው ጉድ ማን ደፍሮ አንተ ሌባነህ አንተ ሸፍጭ ነህ ይበላቸው? ደህው እንዳይላቸው ያልረታ እንደሁ ከሰውን የረታ እንደሁ በቀሉን ይፈራል። ዳኛው እንዳይላቸው ከልተረቱ ከልተመቱ ከነጭራው ከልያዝሽው ይባላል የሌላውን አገር አላውቅም እንጂ የወለጋ ሌባና ሸፍጭ ይህ ሁሉ ምክንያት ቀርቶበት ጉድ ፈልቶበታል ዘንድሮ ክቡር ደጃዝማች ብሩ የወለጋና የአውራጃዋ ገዥ በየከተት ወደ አዲስ አባባ ሲጓዙ ለየባላባቱና ለተውት እንደራሴያቸው መልክም ደምብ ሰጥተው ሄዱ ደምቡም ባጭሩ እንዲህ ነው ። ባላባትም ደሃም መልከኛም በምትኖርበት አገር በየወረዳህ ውስጥ የሚጠረጠር እንኳ ሌባና ቀጣፊ ያየህ እንደሆነ ለፊትአውራሪ ጥላዬ ንግረህ ተይዞ እኔ እስክመለስ ድረስ ታስሮ ይቀመጥ እርታም የለብህ ቢሉት ደህውም ባላባቱም ከደስታው የተነሣ ተዛለለ ።ሌባና ቀጣፊም ይኸን በሰማ ጊዜ ተስፋው ተቆርጦ እንግዲህ ሌት ሰርቀን ቀን ከልሞገትን ምን አለፋን እርሻና ንግድ ይሻለናል ያለ ይመስላል

ለዚህም ምስክሩ ከየካቲት ወር አንስቶ እስከ ዛሬ ባገር ያለው ሰላምና የከብት አለመጥፋት ነው ሌባ በያዙላቸው ጊዜ እርታልኝ ለሚሉ ዳኞች እነሆ ምሳሌው ከዚህ አለ ፣ የማይገባ መሆኑንም መግለጫ ባገርጉደጉድሁ ነበር ነገር ግን ክቡር ደጃዝማች ብሩ ያደረጉት መግለጫ ሆኖ ይታያል ፡፡

፪ተኛ ። በወለጋ የሚኖሩ የባላገሩ ጉበዛዝትና ቆነጃጅት በጣም ዘፈን በመውደዳቸው አገር ይታወክ ነበረ ። ይኸም ዘፈናቸው የሚደረገው ከምሽቱ ጀምሮ እስከ ፯ትና ፰ ሰዓት ከሌሊቱ ነው ፡፡ ይልቁንም የታጨች ልጃገረድ ባገር ያለች እንደ ሆነ የመዳሯዋ ቀን ወሩ ሲገባ ባባቷ ደጅ ስታስጨፍር ስትጨፍር እንቅልፍም የላት ወደዚያም የሚጉርፈው ጉረምሳ ጭሬውንና ጨቤውን የከረረ ጉመዱን እየያዘ ሲሄድ ለሰልፍ የተጠራ ወታደር ይመስላል ። ግን ከዘፈኑ ቦታ ደርሶ ዘፈኑ ሲጀመር መልከ ቀና ልጃገረድ እስክስታ ምታውቅ በመካከል ቁማ አንደዬ ላንዱ አንደዬ ለሌላው ስታለክልክ በድንገት አቶ ቀናት በሰይጣን ምክር ተሞልተው ከተፍይሉ እመካከል ይደባለቁና ምነው ለኔ ምነው ለኔ እንጂ ያበብሉና ያን ተሰልፎ የመጣ ጉረምሳ በፋጭና በጉመድ በጨቤ ያከታክቱታል እዚያም የሚሞተው ይሞታል የቀረውም ጣቱን ጆሮውን ከነፈሩን ዓይኑን ጥርሱን ያጣና የማይረባ ይሆናል ። በዚህ ምክንያት ባመት የሚሞተውንና የሚቆስለውን ብንገመተው በጭሩ በወለጋ ከምስት መቶ አያንስም በየዓመቱ ይኸን ያህል ሰው ሲበላሽ ላገር ጉድለት መሆኑን ማን ይስተዋል ፡፡ ግን ክቡር ደጃዝማች ብሩ ይህ የጉረምሳ መሰብሰብና መዝፈን ላገር ጉዳት መሆኑ ታይቷቸው ይህ ዘፈን እንዳይደረግ ባገር ክልክል አደረጉ ያገርም ሽማግሌ ደስ አለው ጉረምሳውም ደስ ሳይለው አይቀርም መመታትም ቢሸሽም በቆነጃጅት መነወር ስለ ቀረለት የቆነጃጅቱ ግና ያጠራጥራል ፡፡

ዛሬ አንድ ጨኸት ባገር አይሰማም በጨቤም የሞተ አላየንም በዚህ ምክንያት የሚቆስል ቁስለኛ ወደሆፒታል እለት እለት ሲመጣ ይታይ ነበር ። ዛሬ ግን በሽታ ካቆሰለው በቀር ሰው ያቆሰለው ሲመጣ አላየንም ። በዚህም ነገር ደስ ብሎናል ይህንንም ልማድ ለማስቀረት የሚጥሩ ሰዎች ብዙ ነበሩ ። ግን ክቡር ደጃዝማች ብሩ ስለፈጸሙት ምስጋና ይገባቸዋል ይህም ጽፈት የማቆላመጥ ነገር እንደሌለበት እግዚአብሔር ምስክሬ ነው ። ሰላምን የምፈልግ ሰው ነኝና ሰላምን የሚፈልጉ ሰዎች እንዲሰሙት ጽፌያለሁ ። ደግሞም በየአውራጃው ያሉ አገረ ገዦች ሁሉ እንዲህ ያለውን እሮጌ ልማድ ቢያሽሉት አገራቸው ያለችግር እንድትኖር ይረዳቸዋል ። ሰው ሲፋጅና ሰላም ሲያጣ እያሚገቱ ከተረታው ዳኝነት ከረታው የረች ከማለት ክፋውን ጠባይ ካገር እያጠፉ የድኃው ግብሩ ይበቃ ነበር ከመልካም ሽቱ መልካም ስም ይሻላል የተባለውን ማሰብ ነው ።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።

ይድረስ ከክቡር በጅሮንድ ነጋድራስ ዘለቀ ፣
የንግድና የገንዘብ ሚኒስትር ።

በዚህ ስምንት ቀን ጤና አጥቼ ከሰው ተለይቼ ከቤት ከመቆል የተነሣ ለወጭ ገንዘብ ብቻ ስትፈርም የምትውለው ትዝ አለኝ የጓዳውንም የገቢ ምንጭ ባስታውሰው የወጭው መብዛት የገቢውም ምንጭ ከማነሱ መበርከቱ ። በኤልያስ ጊዜ የበረከተውን የመበለቷን የዘይት ማሠሮ ይመስለኛል ፣ እግዚአብሔር በሰጠህ ሥልጣን የያዝከው ሥራ እጅግ ሰፊ የኢትዮጵያ ትዳር ነውና የገቢ ምንጭ የሚቆፍሩ ረዳቶች በየአውራጃው ብታቆም የመንግሥታችን ክብረት ከሌሎች መንግሥት ክብረት አያንስም ፣ ሕዝባችን ሥራ የሚመራው እያጣ ባገሩ ውስጥ ያለውን ሥራ ትቶ ትዳሩንና ሲሳዩን እየረገጠ ወደባዕድ አገር እንጀራ ፍለጋ እየሄደ ገሚሱ በጦር ገሚሱ በበሽታ ያልቃል ። ከሄደበትም አገር ከጥቃት የሚያድነው የለም ገንዘብም ይዞ ቢመለስ ተካፋዩ ብዙ ነው ። ለባላገሩ ያንድነት የግብር ደምብ እንዲሁም ለነጋዴው በየበሩ የማይጉላላበት የቀረጥ ደምብ ቢወሰን ከዘመድ ወደባዕድ አገር ከገነት ወደ እሳት አይሰደድም ነበር ፣ ዳግመኛ ላገር ማልሚያ ተስፋ የርሻና የንግድ ማስፊያ ተብሎ የቆመው ማኅበር ብንከባከበውና ሥራ ብንይዝበት በቅርቡ የሥራ ምንጭ ይበዛልን ነበር ። ይልቁንም የግብርና የመንገድና የድልድይ የጅ ብልሐት ሥራ ብናበዛ ያለው ከቤት ውሎ ካገራችን በሚወጣው የንግድ ዕቃ ገቢውን ያመነጭልናል ፣ የወዲያ አገር ተረት የሮም ከተማ ባንድ ጌዜ አልተሠራም ይባላል ፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት ለምቶ ስሙ ተጠርቶ የነበረው ከተማ እስከ ዛሬ ድረስ ሲሠራ ይኖራል ፣ በኛም አገር በበረኃችን ላይ ብዙ ጥጥና ልዩ ልዩ ዓይነት አታክልት የሚያለማው ውሀ በብላሽ ሲፈስ ይኖራል ። ከእንጦጦ ጀምሮ እስከ ወረኢሉ ያለ ሜዳ መንገደኛ ቢደክመው የሚያርፍበት ዛፍ አያገኝም በዚህ ውስጥም ያሉ ተራሮች ጥንት ደን ጫካ ኑረው በዘመን ብዛት ተመንጥረው ስለ ዕለት ጥቅም ሲሉ የዘለዓለም ጉዳት አመጡ ፣ ደን ቢኖር መሬቱንም ጎርፍ አይጣላውም ። ሣሩም ለቤት ክዳን ለከብት ምግብ ይሆን ነበር እንጨቱም ከቤት ሥራ የተረፈው ማገዶ ሁኖ በያዓመቱ ለመሬት ስበት የሚያስፈልገውን የከብት ፍግ ከመማገድ ያድነው ነበር መምሕርና ንጉሥ አንድ ጊዜ መንገድ ያመለክታል ሕዝቡ ቢከተል በጥቂት ቀን ዳር እስከ ዳር ይለማ ነበር ፡፡ ትልቁ አብነታችን ጃንሆይ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ያለሙት የባሕር ዛፍ አይከሌብቱስ የተባለው እሱ ባይኖር አዲስ አበባ ያለ ሕዝብ ሁሉ እሀል ቀምሶ አያድርም ነበር ፡፡ ጃንሆይ ከዚህ ጀምሮ በገዙት አገር ሁሉ በየመንገዱ ዳርና ዳሩን እንዲተከል አስጀምረው ነበር ። በወዲያ አገር በየመንገዱ ባቡር በሚሄድበት ሁሉ ዳርና ዳሩን ዛፍ ይተከሉበታል ፡፡ መንገደኛ ይኸን እያየ አገር እንዲመርቅ ነው ፡፡

በሀገራችንም ከድሬ ዳዋ በላይ እስከ አዲስ አበባ ድረስ በመንገዱ ቀኝና ግራ ዛፍና አታክልት ቢተከል ለመንገደኛ ላይኑ ማረፊያ ለሚተክለውም ጥቅም ይሆን ነበር ። የሥራውን ፊደል ሀ ሁ ብለን ጀምረናል እግዚአብሔር ዕውቀቱን ትጋቱን ትእግሥቱን ሰጥቶ ሆ ለማለት ያብቃን ፡፡

ከንቲባ ገብሩ ።

የ፫፻፷፮ ገጽ ተከታይ ።

እስቲ የዓለምን ታሪክ እንመርምር ።

የኛ የኢትዮጵያውያን ፊደል እዚህ ከደረሰ በኋላ አንድ ጊዜ ብቻ ተደንግጎ የቀረ ይመስላል ። እንዴት ብትሉኝ ልዩ ልዩ አይነት ምልክት ብቻ አላቸው እንዳይባል አንዳንድ ምልክት መደብ አድርገው ካንዱ ብዙዎች እንዲቀርቡ አደረጓቸው ለምሳሌ ብበቢባ በ መደብ ሆኖ ቡ በ ቢ ባ እንደዚህ እግር እጅ ጅራት የሚመስሉ ምልክት ሰጥተው ተውልን በዚያውም ላይ የዱሮው ንግግር እጅግ ያልተጣራና ያልሰመረ ነበርና ብዙ ድርብና ትርፍ ቀለማት አስፈለጋቸው አያቶቻችንና አባቶቻችንም እረፍት በማጣታቸው እንደሌሎች ህዝቦች ከልክ አላገቧቸውም ። በምሳሌ ግብጾች በዚያ በትልቁ ስልጥንናቸው ዘመን በነዚያ አእዋፍ ዓሳ ፡፡ በሚመስለው ጽህፈታቸው አልነበረም ያን ሁሉ ብልሃትና እውቀት መድህኒት ሲጽፉ የነበረው አሁን የታል የትሄደ ህዝቡ ለወጠው ወይስ እሱው አውቆ ተለጣ ይህን ብል ፊደላችንን እንለውጥ የምል አይምሰላችሁ እኔ ግን በልክ እናድርግ ነውየምላችሁ ፤ ከኛ ውስጥ እንኳን መክሮ ተማክሮ እልክ ናግበ የሚልና ትርፎቹን እንተው የሚል ሰው እንኳ የዱሮዎቹን ሊቃውንት ይፈራል መሰለኝ እንጂ እጅግየማያስፈልጉትንና ባንድ በሁለት ነገር ብቻ የሚገቡትን ፊደላት ሁሉ ኢየለየ ከልኩ የሚያገባቸው ብልህ ሰውስ ጠፍቶ አይስመለኝም ፡፡

ብርሃንና ሰላም ባትሰለቸኝ እስቲ የጀመርነውን ታሪክ እንመልከት እነዚያ የዱሮ ሰዎች አንድ የተከናወነ ጽህፈት ፊደል እጅግ ይ... ያስቡ ነበር ። በእስያ ከሊባኖስ ተራራ ጥግ በሰሮያ በሚ... ባሕር ወገን ፊኒስ የምትባል ያገር ክፍል ነበረች የዛሬው ፓለስቲና በሚባለው አገር ክፍል ውስጥ ነች በዚ የነበሩ ሰዎች ከጌታ ልደት በፊት በ፪ሺ ፲፫ ዓመት በኤወሮፖች ቁጥር ከግብጾች የተቀበሉትን የመጀመሪያ ፊደል አስበው አስተክክለው አሻሽለው የዷፉና ለሌላው ህዝብ ሁሉ ትልቅ እውቀት የሰጡ ፊኒሳውያን ናቸው ። ከፊኒሳዎች ግብጾች ግሪኮች እንደገና ተቀብለው አርመው አስተካክለው እንደ ቋንቋቸው ለይተው ያዙአቸው ። ከነዚህ ኢታሊዎች ከኢታሊዎች ሮማኖች ከሮማኖች በአውሮፓ የሰፈረው ሕዝብ ሁሉ ወስዶ እንደ ንግግሩ አሳምሮ አሳጥሮ ፳፮ ዓይነት ልዩ መልክ ብቻ ያሉአቸውን ፊደላት ይዘው የሚያስፈልጋቸውን ንግግር ሁሉ ፳፮ ፊደላት ብቻ እየጻፉ ይኖራሉ ። (ይኸንን መጻፌ ታሪኩን ለማሳወቅ ስል ነው እ'ንጂ የኛ ፊደል እንደነሱ ይሁን ስል አይደለም ከልኩ ዓለመድረሱ ነው እንጂ የኛ ፊደል ከነሱ የበለጠ መልክም አካሄድ አለው)። እነዚህ ፳፮ እንኳ በዙ ሲሉ ፫ ፺፬ቱን የቀነሱላቸው አሉ ። ይኸ እንኳ እንደ ኃሳባቸው ያልደረሰ ቢሆን ለነዚሁ ፊደላት ሌላ አጻጻፍና ደንብ አውጥተው በጥቂት ጊዜ በትንሽ ስፍራ ብዙ ጉዳይ ለመጻፍ ችለዋል ። ይኸውም ጽሕፈት ስትኖግራፊ ይባላል ። ማንም እንደበታም ፈጣኝ ሰባኪ የሚናገረው (የሚሰብከው) ንግግር ሁሉ አንድ ሳትቀር በፍጥነት ሲናገር ተከትለውት ለመጻፍ ይቻላል ። በፍጥነት ስለመጻፉ ባንዲት ደቂታ ፺፰፬ ቃል (ነገር) ይጻፋል ። በታ ባለመያዙ በተራ ጽሕፈት በአራት ገጽ የሚጻፈውን ንግግር በስተኖግራፊ አንድ ገጽ ብቻ ይበቃዋል ። የተራው ጽሕፈት እንደሁ ባንድ ደቂቃ ዓ፬ ቃል ብቻ ነው ለመጻፍ የሚቻለው ፡፡ ይህ ሁሉ ብልሐት እንደኛ እንዳባቶቻችን አርጌውን ብልሀትና ድንቁርና ይዘን እንሞታለን በማለታቸው እንዳልሆነእባካችሁ እንረዳ እንመልከት

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ

የዚህን የፊደላችንን አገባብ በሁለቱ ጁርናል ማሳተሚ ንባብ የቻሉ ጁርናል የሚመለከቱ ብልህ ሰዎች ሁሉ እንዲያስቡበትና ቢፈቅዱ እንዲይዙት ባይፈቅዱ የተሻለ ደንብ እንዲያወጡለት ስል ነው እንጂ አንብበው ዝም እንዲሉ አይደለም መጻፌ ፤ አሁንም ቢሆን ከሰው ስህተት ክብረት ዝገት አይታጣምና ትንሹ ወንድማችሁ (ልጃችሁ) የተሳሳተውን እያስተካከላችሁ እንድትመለከቱልኝ እለምናችኋለሁ ።

ትንሹ ተማሪ በውጭ አገር ያለው መ ወ ሥ ።

የከተማ ወሬ ።

ግንቦት ፳፫ ቀን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ደብረ ሊባኖስ ወደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ለጠበል ባማረ አውቶ ሞቢል ተቀምጠው ብዙ መኳንንቶችም በአውቶ ሞቢል በአውቶ ሞቢላቸው ተቀምጠው ተከትለዋቸው ሔዱ ፡፡

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም ሸኝተዋቸው ማታ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ ፡፡

ግርማዊት ንግሥታችን ወደሄዱበት አገር በደህና ደርሰው በደህና ይመለሱልን እያልን ትልቅ ምኞታችንን እናቀርባለን

ያገር ውስጥ ወሬ ።

መስቀል ተሰላጢን ፡፡

በሸማግሌዎች አማርኛ መስቀል ተሰላጢን ተብሎ ሲወጋ እየሰማሁ ሕገ ትሩፋትና ሕገ ርትዕ እንዴት ባንድነት ሊቀላቀሉ ይቻላል ብዬ ትርጓሜው ሲቸግረኝ ይኖር ነበር ። አሁን ግን በዓይኔ አየሁ ።

ግንቦት ፳፫ ቀን ከሐዋሽ ወደ አዲስ አበባ በሚገባው በቡር ተሳፍረን ስንመጣ ዱከም ላይ አንድ ቄስ ካንድ ወታደር ጋራ ይጨቃጨቁ ነበር ፤ ምክንያቱንም ብጠይቅ ባልናሚስት ሲፋቱ እሳቸው ለሴቲቱ ዋስ ሆነው ነበርና አሁን ታግቻለሁ ብለው ከነገረ ፈጂዋ ጋራ መጣላታቸው ነው አሉኝ ። ፳ ደቂቃ ያህል ከተጨቃጨቁም በኋላ ለሐሙስ እግት እንድታመጣ ገዝቼሃለሁ አሉት ። በዚህ ጊዜ ከሕዝቡ ግማሹ ይስቃል ግማሹ ያደንቃል ፤ የዋሁ ወታደርም ተምበርክኮ ይለምን ነበር ፤ እንደኔስ ዋናዩቱን አቀርባለሁ ብሎ ቢሄድ ባልተ ጨቃጨቁትም ነበር ።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ

የውጭ አገር ሰዎች ስለ ኢትዮጵያ የሚጽፉት ቃላት። ከርሚንሐም ዊክሊ ፖስት ከተባለ ጋዜጣ የተተረጐመ ።

By C. F. REY. F. R. G. S.
(Comander of the order of Ethiopia.)

የኢትዮጵያ መንግሥት ኰማንደር ኦፍ ዲ ኦርደር ኦፍ ኢትዮጵያ የሚል የማዕርግ ንሽን የሰጠው ከሲ ኤፍ ሬይ ኤፍ አር ጅ ኤስ ስለዛሬው የኢትዮጵያን ትጋት የተጻፈ ።

ከአፍሪቃ ታላላቅ ነገሥታት ሁሉ በስልጣኔ እርምጃ ወደ ኋላ የቀረች ኢትዮጵያ በቅርብ ጊዜ ጉዞዋን አቅንታ ወደ ፊት ስትሄድ በሩቅ እንደ ብርሃን ውጋጋን የምትታይ ትመስላለች። የዓለም ነገሥታት የጥቅም ውል ሊዋዋሏት ተጭነዋታል ።የዓባይን ውሃ ጉድብ ከጣና ባሕር የሱዳንን የጥጥ አዝመራ በመስኖ ለማጠጣት ከኢትዮጵያ ጋር እንግሊዝ ውል ለመዋዋልና የውሐውን ጥቅም ለራሱ ለማስለጠን ሕሊናው በንቃት ይናፍቃል ። ኢጣልያም ወደ ጠረፍ ግዛቷ የሚያገናኝ ማሕል ለማሕል ለምድር ባቡር የብረት ሐዲድ ለማንጠፍ ትፈቅዳለች ። ነገር ግን ኢትዮጵያ የሊግ ደ ናሲዮን ማኅበረተኛ ስለሆነች ስለምትገደድበት ጥያቄ ሁሉ ጨኸቷ በጉባዔው ይታያል ። የኢትዮጵያ ሃይማኖት ያረጀ ስለሆነ ሕዝቧ በድንቁርና ወደ ኋላ እየተጐተተ የበሬ መሸጥና መለወጥ ይኸንም የመሰለ ክፉ ልማድ አይጠፋትም ። ኢትዮጵያ መጀመሪ እንደዚህ የመሰሰለውን ያገር ልማድ ልታፈቀርና ልትገስ በሰጠችው የተስፋ ቃል ወደ ሊግ ዳናሲዮን መግባት ተፈቀደላት ። ስለዚህ በኢትዮጵያ ከገር ወዳገር የሚዘወር ሰው ፣ ያሁን ትውልድ ስልጣኔ እንዴት እንደነገሠ ማየት ይችላል ። ከውጭ አገር ነገሥታት ጋራ የምድር ባቡር ስላገናኛት ወደ ዋናዋ ከተማ ብዙ ሰው መግባት ጀምሯል ። በሺ ፱፻፳፬ ዓ ም በፈረንጆች ቁጥር የልዑል አልጋ ወራሽና ፳፥የሚያህሉ መኳንንት አውሮጳን በመጐብኘታቸው ፤ የምዕራብን እቃ ወደ አገራቸው ለማግባት የነበረው የቆየ ምኞት ተፈጸመ ።

የአውቶሞቢል መግባት ባዲስ አበባ ።

ሁሉም ከአውሮፓ ሲመለሱ በቁጥራቸው ልክ አቶ መቢል ገዝተው ስለመጡ ባዲስ አሻንጉሊቶች ለመጫወት እንዲችሉ በዋናዋ ከተማና በዙሪያዋ መንገድ ለመስራት በትጋት ጀመሩ ። አሁን ልዩ ልዩ አቶመቢሎች ቁጥራቸው ፪፻ የሚቀርብ ፣ አንዳንዱ ፈጽሞ ያልተማረ የኢትዮጵያዊ ነጅ የፍጥነት ልክ ሳይወስን ወይም በመንገድና በዳሩ አንዳንድ የሚያሰናክል ነገር ተጠንቅቆ ሳይመለከት እየነዳ አቶ መቢሎች በቶሎ ተሰባሪ ሳይሆኑ አይቀርም ይመስለኛል ። የተሰናከሉትንም ለመጠገንና ላስቲኩን ለማስለወጥ ፋብቱሩ ያንገፈግፋል ፈረሱን በቅሎውን አህያውን ላሙን በጉን ሕዝቡ አስከታትሎ እየነዳ ወደ ገበያ ሲገባ አቶሞቢል በደረሰ ጊዜ መንገዱ ተዘግቶ መተላለፊያ ሲጠፋ ነጅው ጡሩምባውን በነፋ ጊዜ የተጫናች በቅሎ ደምብራ ጭነቷን ስታዝረከርክ በመካከል ብዙ ሰው አለመጻጡና አለመሞቱ የሚገርም ነው ። ዋናዋ ከተማ አዲስ አበባ አልፎ የደንጊያ ቤት ይታይበት ነበር እንጅ ጭፍቅፍቅ ያለች መንደር ሆና በውስጧ ነዋሪ ፰ ሺ ሕዝብ ብቻ ነበር ። በሺ ፰፻፺፮ ዓ ም ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ ከጣሊያን ዘመቻ ምላሽ ከተማዋን ቆርቁረው ዲስ አበባ ብለው ሰየሟት ትርጓሜው አዲስ የሆነ አበባ ማለት ነው የከተማዋ አቀማመጥ ፰ሺ ፊት ወደላይ ከባሕር ከፍ ያለ ስለሆነ ዓመቱን ሙሉ አዲስ አበባ ደስ የሚአሰኝ የሕይወት አየር ትጠጣለች ።ከተማዋም በባሕር ዛፍ ተሞልታ መሐል ለመሐል ሁለት አፍላጋት (ወንዞች) ይከፍሏታል ። ከከተማዋና ከሊጋሲዮኖች መካከል የፈረስ መሽቀዳደሚያና ፣ የፖሎ መጫወቻ በደምብ አብጅተዋል የሊጋሲዮኖች ርቀት ከከተማዋ አራት ማይል ይሆናል ።

ለከተማው ስልጣኔ ያላቸው የሕይወት ውሃና የከተማ ጥዳት ስራ ቤት ቢአቆሙ ከሁኑ ይበልጥ ደስ ያሰኝ ነበር ። ወንዱም ሴቱም ከመናኛ ጨርቅ የተሰፋ ሱሪና እጀጠባብ ለብሰው ስለኰት ምትክ ቀን በላይ የሚደርቡት ማታ ማታ ለብሰውት የሚያድሩ ሼማ የሚባል ከነጭ ጥጥ የተሰራ አላቸው ከባለጠጋዎች በቀር ተራው ሕዝብ ሲሄድም፡በከብት ሲወጣ ጫማ አይለብስም ።

ብርንዶ ሥጋ በላተኞች

ምግባቸው እጅግም ያህል አያኰራ ዳቧቸው ዘንጋዳ ከሚመስል ጤፍ ከሚሉት ተጋግሮ ከበርበሬ የተሰራ የኽክ ወጥ ፤ በቀረበ ጊዜ ይልቁንም ኤሮጳዊ ለመዋጥ ቢፈትን የበርበሬው ትኩሳት ጉሮሮውን ያመዋል ። ዋናው ምግባቸው ትኩስ ታርዶ ብርንዶ የሚሉት እርጥብ የበሬ ሥጋ ነው ። የቤተ መንግሥት ግብር የሆነ ጊዜ ፲፭ሺ ሕዝብ ቀርቦ ሲበላ አይቼ የሚገርም ነገር አጋጥሞኛል ። ፍም የመሰለ ታናሽ ሁለት ሰዎች በመሎጊያ ተሸክመው ወደ ሰደቃው ሲቀርቡ ሥጋ ቤቱ ጉማጅ ጉማጅ እየቆረጠ እያንዳንዱ አፉ እንደቻለ ባፍ በፉ ያጐርሰዋል ። በላተኞቹም ያን ትልቅ ጉማጅ ሥጋ ከፋቸው አውጥተው አንዱን ጫፍ በፋቸው ነክሰው ከታች ወደ ላይ በቢለዋ ሲቆርጡ አረዘም ያለ አፍንጫ ላለው በጣም ፣ ስፈራዋል ። ይኸን አይቶ ደግሞ በልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ ለአውሮጳውያን መኳንንት ግብር በሆነ ጊዜ ገበታው በንጹህ ጨርቅ ተዘርግቶ ስለ ከበሬታ ምግብ በወርቅ ፤ በብር ፣ በሺህላ ሳህን ሲቀርብ ማዬት ያስገርማል ።

በገቢያውም የሚያስደንቅ ያጋጥማል አውቶሞቢሎችና ቢስኪሌቶች ሲተላለፉ የነሱ ማደንቆር አንሶ በየሱቁ የስፌት መኪና ሲንገጫገጭ ሰምተን እልፍ ስንል እስከ ብዙ ቀን ለመቀጣጫ ከዛፍ ላይ የተሰቀለ ሰው እናያለን ። ፍትሐነገሥታቸው ከሙሴ ሕግ ግልባጭ አይን ባይን ጥርስ በጥርስ የገደለ በጠላቶቹ እጅ ተሰጥቶ ይሙት የሚል ነው ፤

በገንዘብ ዕዳ ስለ ሚያዙ ፤

ዋና የሚገርም ነገር ሁለት ሰዎች በሰንሰለት ተቆራኝተው በሰላም እየተጫወቱ ሲሄዱ ነው አንዱ አበዳሪ ሌላው ተበዳሪ ወይም በገንዘብ ተጣልተው ከሳሽና ተከሳሽ ይሆናሉ ፣ ደምብ

ቸው የሚለው የተበደረ ይከፈል ነውና በማይረባው ትኒሽ ነገር ሰውን መከሰስ ይቻላል፡ኢትዮጳውያን ጭቅጭቅና ሙግት የሚወዱ ዘወትር በመንገድ ዳኛ አውጥተው እየተካሰሱ ብጐጆ ውስጥ ተጠየቅ ሲሉ የሚውሉ ስለሆኑ ይኸ ሊሆን ዘንድ ያስፈልጋል ። በከተማው መካከል ይልቁንም በገቢያ ውስጥ ያልተሰራበት በዶ ስፍራ ስራ ፈቶ ሳይሰራበት ይኖራል፡ በዚህም ስፍራ ከሁድ በቀር ኢትዮጳውያን ሲቸረችሩ ሲነግዱ ይታያሉ ፡ ወደ ከተማው በሚያገባው መንገድ ሁሉ አጋሰሱ አህያው ሳር ወይም ገንቦ ወይም ኩበት ተጭኖ በቁሎች ከዳር አገር ቆዳ ይዘው እንጨት እህል በስልቻ ማር በስልቻ ቅቤ በኬሻ በርበሬ ብዙ ዶሮች እግራቸውን ታስረው ተዘቅዝቀው ተጭነውና ጋላ ጦር ይዞ ጐራዴውን በወገቡ ሼብ አርጐ ከብቶቹን እያቀጣጠነ ወደ ከተማ ሲያጓተለትል ሴቶቹ እንዳህያ ጭነት ተሸክመው ሲገቡ ይታያል ፡ ከገቢያው ሲደርሱ ወደ ልዩ ልዩ ገበያ ገብተው ጭነታቸውን ከራገፉ በኋላ በመሬት ትኒሽ ጨርቅ አንጥፈው በዚያ ላይ እቃውን ይዘረግፉና እስኪሸጥ ድረስ እነዚህ የተገጠቡ ከብቶች ቆመው ጻሐይ ያንቃቃቸዋል በቁሎ አህያ ፍየል በግ ዶሮ የሚሸጡበት በተለዩ ገቢያ አለ ፡ የፈረስ ገቢያ ግን በተለዬ ተከተማው ውጭ በስምንት ቀን አንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚቆመው ። ከመንገድ አንድ ወገን በተለየ የአቡጀዲድ ተራ ነው በያውራጃው ገበሮችና ባላገሮች ጥጡን እየፈለቀቁና እየነደፉ ይፈትሉና ለሼማኔ ሰጥተው ሼማ እያሰሩ ይለብሳሉ ሼማኔውም ጥንት ዘመን በአሪት እንደ ነበረው ዓይነት መሳሪውን ይዞ እግሮቹን በጉድጓድ ከቶ ሲሰራ ይታያል ።

ሶለ ገንዘብ ።

የመገበያያቸው የማሪያ ቴሬዛ ብር ነው፡ አንዱ ሁለት ሺሊንግ ይሆናል ፡ ካዲስ አበባ ውጭ ሕዝቡ ከብር በቀር ሌላ ዓይነት ገንዘብ አይቀበልም የወረቀት ገንዘብና ፋክቱር ስላል ተለመደ ለማናቸውም ዕቃ ብር ተሼክሞ ሂዶ መክፈል ነው ማስረጃ በምዕራብ ኢትዮጵያ ቡን ለመግዛት መጀመሯ ባዲስ አበባ ብር ገዝቶ ወንበዴ እንዳያስፈራ ባቡጀዲድ ውስጥ ተጠቅልሎ ያንድ ወር መንገድ ሰዶ ነው የሚከፈል ራቅ ባለው ትኒንሽ አገር እስከሁን ድረስ ዋናው መገበያያ አሞሌ ጨው ነው ባንድ ብር ፫ መንዲስ ጨው ይገዛል ባንድ አሞሌ አንድ ዶሮ ወይም ፲፪ እስከ ፳ እንቍላል ይገዛበታል ።

ባንድ ስፍራ ጓዜ ጠፍቶኝ ስንከራተት፡መሽቶ ለበቅሎዬ ማደሯ ስል ፪ ጥይት ከፍዬ አሳድሯለሁ ። በእንደዚህ ያለ ሁሉ በድንቁርና ምንም ወደ ኋላ ስለተጐተተች ኢትዮጵያ ቀስ ቀስ እያለች መንቃት ይዛለች ። ወደፊትም ያሁኑን ትውልድ ሥልጣኔ እየተከተለች እንድትሄድ ተስፋ አለኝ ። ከባሕር ጠረፍ እስከ ዋናዋ ከተማ የተሠራው የምድር ባቡርና በዋናዋ ከተማ ያለው መንገድ የሩቁን በቅርቡ ስላከናወነ ሕዝቡ በሆነው ተረድቶት ነገሩ ገብቶታል ። አገረ ገዢዎችም በከተማቸውና በያውራጃው ያዲስ አበባን ከተማ መንገድ አይቶ በዚያ ዓይነት እንዲሠሩ በተስፋ እንጠብቃለን ።

ከዚያ በኋላ ሁለቱም ገዢዎቿ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሁኑን ትውልድ የአውሮፓን ሥልጣኔ ተከትለው ሕዝቧ የሚጐዳበትን ጎዘን ታልከፈሉላት አገራቸውን ገናና መንግሥት ማድረግና ማሳደግ አይቻልም ።

ከዚህ በላይ የተጻፈው የኢትዮጵያ ነቀፌታ ተርጉመን ማተማችን ብልሆች የኢትዮጵያ ልጆች እንዲያውቁትና ምላሽ እንዲሰጡበት ነው ። ስለዚህ ነገር የተሰናዳና የተከናወነ ምላሽ ጽፎ ላመጣ ሰው በደስታ እናትምለታለን ።

የውጭ አገር ሰው በኢትዮጵያ ስለ ባሮ ነጻነት
የጻፈው ወሬ ካሜሪካ ጋዜታ የተተረጐመ ።
ከጀክ ቦም የተጻፈ.

የኢትዮጵያን ባሮ ነጻ ለማውጣት አሜሪካንንና ኤሮፓውያንን የተጠሩበት በታሪክ ተጽፎ ይኖራል ። ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በሚከተለው ትክክል ቃላት ልመናቸውን ዛሬ አቀረቡ ። የኢትዮጵያ መንግሥት በሃገሯ ስለሚሆነው የባሮ ነገር ታላቁን ተስፋ ለማወቅ ትችል ዘንድ ፡ አገሩን ለማሻሻልና ፡ ባሮ ነጻነት ተቀብሎ እየተቀጠረ ፡ እንዲኖር የሚረዱ አሜሪካንንና ኤሮፓውያንን ትጠራለች ። ለዚህ ሥራ አላፊነትና ትጋት ላላቸው ሰዎች ኃሳብ ማስፈጸሚያ ፡ በገንዘብ ረገድ አንዳች ችግር እንዳያገኛቸው እርዳታ እንሰጣለን ። የኢትዮጵያን ታሪክ ከሕጻንነቱ የሚያውቅ ያህ ልማድ ከታላቁ ምኒልክ ጀምሮ በንግሥተ አዜብ በኢትዮጵያ ንግሥት ፡ ዘመነ መንግሥት ተያይዞ የመጣ እርምጃ መሆኑን አይስቱትም ። ይኸም እርግጠኛ ታሪክ መሆኑን ነገሩን ከማስተዋልና ካጻጻፉ ይገኛል ። የኢትዮጵያ መንግሥት ባሮን ነጻ ለማውጣት በማሰቧ ሰውን መሸጥና መለወጥ ኃጢአት እንደ ሆነ ከብዙ ዘመን ጀምራ ተረድታለች ። ሰውን መሸጥ ነውርነቱ በዘመን ብዛት ስለተለወጠ የኢትዮጵያ መንግሥት በነገሩ ወደ ፊት ልትገፋ ስለፈቀደች በባርነት የተወለዱት ሁሉ ነጻነትን ተቀብለው እንደ ሕዝቡ ደልቷቸው ሊኖሩ ደምብ ተሰጥቷል ።

ስለ አትክልት ።

በመንግሥት ውስጥ ያሉ አገረ ገዦዎችና ፡ መንግሥት ተስማምተው ነገሩን ከቆረጡ በኋላ ይህ ሀሳብ በቶሎ ይፈጸማል ። የሥራው አካሔድ ቀጥሎ እንደተጻፈው ይሆናል ።

አስቀድሞ በኢትዮጵያ ቡን ፡ ላስቲክ ፡ ፍሬና ሌላም የመሬት ሲሳይ የሚተከልና ፡ የቀንድ ከብት በግ ፈረስ መሬት ተከራይቶ የሚያረባ ከውጭ አገር ሰው ማምጣት ያስፈልጋል ።

እንደዚህ ቢሆን ባሮች ሁሉ በሥራው ውስጥ በደሞዝ እየተቀጠሩ የደሞዛቸውን እኩሌታ ለጌታቸው እየከፈሉ የተገዙበትን ገንዘብ አፍርተው ነጻነታቸውን እስኪያገኙ ድረስ ሌላውን የደሞዝ እኩሌታ ለመንግሥት ያስይዛሉ ። እንደሚያገኙት መጠን ታስቦ የተገዙበትን ከፍለው የሚጨርሱት እስከ ፳ዓመት ይሆናል ። ነገር ግን ከጥንት የቆየውን ልማድ በቶሎ ለማስቀረት ሲባል ያውም በአፍሪካ ባንድ ጊዜ ባሮች ሁሉ ነጻ ቢወጡ የሚበዙት እርነት ከወጡ በኋላ ስራ አጥተው ተስፋ አልባ አሜሪካኖችና አውሮጳውያን እንደሚያስቡት ፡ በየመንገዱ ወድቀው

ይቀራሉ ። ይልቁንም ማደሯና ስራ ካጡ ሰው መግደልና መቀማት ይጀምራሉ ። አሜሪካ ለኢትዮጵያ የምታደርገው ውለታ አሁን የታሰበውን ስራ በቶሎ ማቆም ነው እንጂ በስራው እጅ መጫን አያስፈልግም ። የውጭ ሰው ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ አገሩን ለማሻሻልና ይሄን የታሰበውን ሥራ አቁሞ በሥራው ውስጥ ባሮችን ቀጥሮ ነጻ እንዲወጡ ቢረዳ የኢትዮጵያ መንግሥት ሊፈቅድለት የተዘጋጀ ነው ።

ስለ ጠቅላላው ሃሳብ ።

ይህን ስራ አስቦ ባላፊነት ለመሥራት ለፈለገ ሁሉ በስራው ችግር ልዑል የኢ መ አል ወ ተፈሪ መኰንን እርዳታ ይሰጣሉ ። ደግሞም በኢትዮጵያ ያሉ ባሮች ነጻ እንዲወጡ የኢትዮጵያ መንግሥት ከልብ መፍቀዱን ይህ ብቻ ያስረዳል የዚህን ነገር መርምሮ ከሩቅ በቅርቡ ለማወቅ ልዑል ራሳቸው የባሯ መሺጥና መለወጥ አፍሪካ ሲፈጠር አብሮ የበቀለ ልማድ ነው ብለው የተናገሩትን ቃል ማስተዋል ነው ። ኢትዮጵያ በመንግሥቷ ኃይል ራሷን ችላ መኖሯ ታላቅ ለመሆን የተሻለውን መንገድ ትጋበት እንደሚሉት አሜሪካን (ተረት) የመንግሥቷንና የሕዝቧን ችሎት ተግታ አሳየች ። ብዙ ርስት ያላቸው ሰዎች አገረ ገገዎች ፡ ከታላቅ ዘር ተወላጆች ሁሉ መቶ ፡ አንዳንድ ጊዜም ሺህ የሚያህሉ ባሮች አሏቸው ። ልዑል የኢ መ አ ወ ተፈሪ መኰንንና መንግሥታቸው በአውሮጳ ስለሚላላኩት የዲፕሎማ ስራ በማናቸውም እርዳታ እንዲያገኙ ተስፋ ተደርጎ ሌላው ቀርቶ አውሮ ፕላን እስካሁን ድረስ በአገራቸው እንዳይበር ሕዝቡም ከለከለ የባሯ መሺጥና መለወጥ በኢትዮጵያ ጉዳቱን ከዚህ ከሉነው በቀር ሕዝቡ አላስተዋለውም ።

ለደህና ኑሮ የማይጥር ነገሩን ሁሉ ባልሆነው እኳኋን ሳይጠነቀቅ የሚተው ገንዘብ ለሚገዛው ባሯ የሚጓጓ የድሮው ባሯ ሻጭ ባሁኑ ትውልድ ስልጣኔ በኢትዮጵያ ውስጥ ይገኛል ቢባል ጭራሽ ለነገሩ እምነት አናደርግም ። በኢትዮጵያ አንድ ራስ መቶ ባሮች እያሉት እርሻ አያሳረሰ ጥቅም ለማርባት ሀሳብ የለውም ፡ የሚያሳርሰውም ለራሱ ለወታደሩ ለባሮቹ ለለት ምግብ የሚበቃው ያህል ነው ያውም ቢሆን ትጋት ሳያደርግ በብዙ ቸልተኝነት ነው እንግዲህ ከቸልተኝነት የተነሳ የሚወለው ችግር ገንዘብ በማትረፍ ፈንታ ባሮቹን የሚየለብስበት ገንዘብ እየቆረቆረው የሀሳብ ሸክም ይጫነዋል ። ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በገራቸው ባሯ ነጻ እንዲያገኝ የተጉበትና እርዳታ የፈለጉበት ይህን ይህን አይተው ከጉዳት በቀር ትርፍ አለመኖሩን አስተውለው ነው ።

ደስ ስላላቸው ባሮች ።

የባሮችን ጠባይ መርምሮ ላወቀው ሰው ባሯ ነጻነት ተቀብሎ ራሱን ከሚችል በሰው ሀሳብ በባርነት ለመኖር ወደው ደስ ብሏቸው የሚኖሩ ብዙ አሉ ፡ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አ ወ ተፈሪ መኰንንም በተሰጠው ደምብ ውስጥ በባርነት የተወለዱ ሁሉ ቢፈቅዱ ነጻነትን ተቀብለው እንደ ሕዝቡ ደልቷቸው ሊኖሩ ደምብ ሰጥቻለሁ ባሉበት ቢፈቅዱ ማለታቸው ፈቅደው አርነትን አይቀበሉም በማለት ተጠራጥረው ይመስላል ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የዓለምን ታሪክ ነገሥት አጥብቀው መርማሪ ናቸው ። ታሪክ ከመመልከት የተነሳ በዩናይቲድ እስቴት ቀድሞ ዘመን ከጦርነት በኋላ አሜሪካኖች ባሮችን አናስጠጋም ብለው የከለከሉበትንና ከሰሜን አፍሪቃ ጋር ትልቅ ጦርነት የሆነበትን መርምረው ባሮችን ሁሉ ነጻ በቶሎ ቢያወጡ አሜሪካንን እንደ ገጠመው ብጥብጥ ባገራቸው እንዳይሆን ለማድረግ ባንድፊት ይሄም ያሳስባቸዋል ይህን ሁሉ በረቂቅ ዕውቀት የከተማው ሰው እንዲያስተውልና ካላንድ መሰናከል ባሯ ነጻ ለማውጣት ያሰቡትን ታላቅ ሀሳብ እግዚአብሔር ቢአስፈጽማቸው ለኢትዮጵያም ለባሮችም ለባለባሮችም የተስማማ ኑሮ ይሆን ነበር ።

ማስታወቂያ ።

የክቡር ዶክተር ሐነር ሰለግ ውሻ ልጅ እግር በጀርባው ላይ ዳማ ያለበት ሰለግ ውሻ ያገኘው ሰው እዚህ ቤተ ሳይዳ ሆስፒታል ድረስ ቢአመጣ እንደሚገባው ዋጋ ይቀበላል ከጠፋም አምስት ቀን ሆኖታል ግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓመት ።

ማስታወቂያ ።

ታላቅ የቲአትር ጨዋታ ያደርጋል ጨዋታውም ታላቅ ቁም ነገር ያለበትና ለሰውነት ደስ የሚአሰኝ ነውና አገራችሁን ወዳጆች ወይዛዝርና መኳንንት ሁሉ በደስታ ትመጣላችሁ ስንል ከግሌዝ ቤት ድረስ በ፰ ሰዓት በክብር እንጠብቃለን በዚህም በጨዋታው የሚገኘው ገንዘብ እናት አባት ለሌላቸው ለድኃ ልጆችና ነፃ ለወጡ ባሮች ተማሪ ቤት ነውና የሚሆነው ምንም እንኳ ጨዋታው ለዓይን ሥጋ ደስ የሚአሰኝ ቢሆን ገንዘባችሁን የምትሰጡበት ምክንያት መንፈሳዊ ስለሆነ የነፍስ የሥጋ ጥቅም መሆኑን በማክበር እናመለክታለን ።

አጭር ማስታወሻ ።

ማየት መመልከት ላገር ይበጃል ።
ገንዘብና እቃ ቢበደሩ በቀን ብዛት ይከፈላል ።
ቋንቋ ግን በጊዜ ብዛት ያገርን ቋንቋ ያጠፋል ።
ዬሰው ቋንቋ ከመበደር የራስን ማስፋት ይበልጣል ።
የውጭ ስልጡን ከማግባት ያለሚስት መኖር ይሻላል ።
ያገርልጅ አግብቶ ማሰልጠን እንዴት ያምራል እንዴትስ ያስመሰግናል ።
ይህ ዘረኛነት ብሎ ከመሰደብ ያድናል ። ልብ ያለው ያመለክታል ።
እንደሱ ያለ ሰው እጅግ አገሩን ያስከብራል ።
ያ የዱሮን እንያዝ የሚሉትን ደርሰው ይመስሏችሁአል ።
በዚህ ወገን ገንዘብ አሸንፎአቸው ተኝተዋል ።
ብልሁ ግን የዛሬንና የጥንቱን ጊዜ መርምሮአል ።
እንደ አሜሪካ እንዳአውስታራሊያ ህዝብ ዘራችን እንዳጠፋ ያውቃል ።
በብልህ ጆሮ ጥቂት ነገር ይበቃል ።
በመልካም እርሻ ጥቂት ዘር ያጠግባል ።

መ ሥ ወ ።

OMEGA



እጅግ ጥሩነቱ የተመሠከረለት ዖሜጋ ቦቢ የሚባል ባለአንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲግ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፳ ብር ተ፫ ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፬ ብር ተኩል።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ሩ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፱ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፰ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፯ ብር ።
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፻፴፮ ብር ።
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፳፫ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፴፫ ብር ።
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፴፬ ብር ።
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፺፩ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፫ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፫ ሩብ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፬ ፍራንክ	፲፮
በአንድ ብር	፳ ሊሬ እስከ ፳ ሳንቲም	
በአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፲ ሳንቲም	
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር	

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል ።

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳም ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

ሩ ግ ቢ

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፥በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፥ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቀበት ዘወትር ይገኛል ።



ማስታወቂያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፣ ሽቱ ፣ ለስዮን ፣ አድኮሎኝ ፣ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፣ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፣ የአልጋ ልብስ ፣ ከፈይ ምንጣፍ ፣ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፣ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማስታወቂያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፊታውራሪ ዩፌሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሄስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማስታወቂያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፣ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፣ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነቱ፡ ቢሲግሌት ፣ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረትና ለአንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላሸው ፣ ፋኑስ በየዓይነቱ ፣ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፣ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

Berliet



ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ አቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

ARMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኒዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ የሶርትርያስ ቢት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮሎኝ አምባሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮሎኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ስንና ብርት ሳሀን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ። የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፥ ቁጥር ፳፫
3 me ANNÉE № 23

ሐሙስ ሰኔ ፱ ቀን ፤ ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 9 JUIN 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen , Héritier du trône d' Ethiopie , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጺሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ክቡር ሐኪም ወርቅነህ የፍቅርና የአገልግሎት ማኅበር አለቃ ።

ስለ ፍቅርና አገልግሎት ማኅበር ።

ግንቦት ፳፰ ቀን የፍቅርና ያገልግሎት ማኅበር ስለ ድሆችና ነጻ የወጡ ባሮች ተማሪ ቤት እርዳታ በግራንድ ሆቴል የቴአትር ጨዋታ ለማሳየት ክቡራን ወይዛዝርንና መኳንንትን የውጭ አገር ሰዎችንም ጠርቶ ነበር ሕዝቡ ለማየት እየቸኰለ በስምንት ሰዓት ተሰበሰበ ።

ለሀገራችን ወይዛዝር በሥልጣኔ መንገድ መልካም አርአያ የሚሆኑ ክብርት ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅም ለማኅበሩ የሚያስፈልገውን ዕቃ እያዘጋጁ ያቀርቡ ነበር ፤

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በደረሱ ጊዜም መጋረጃው ተገለጠና ክቡር ሐኪም ወርቅነህ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

የተወደዳችሁና የተከበራችሁ ጌቶቻችን ሆይ ።

ባለፈው ዓመት ማኅበራችን ነጻ ለወጡ ባሮችና ለድሆች ልጆች ተማሪ ቤት ሊሠራ መጀመሩን ቢያስታውቃችሁ የሥራውን መልካምነት በቅን ልቡናችሁ አስባችሁ የችግሩ ተካፋዮች በመሆናችሁ ዘላለም ከልባችን የማይጠፋ ጥልቅ ውለታ ስላደረጋችሁልን ገናናውን ስማችሁን በዚች በተከበረች ቀን ልንጠራው ስለ ወደድን ከዚህ ቀጥሎ ይነበባል ብለው በተናገሩ ጊዜ ።

ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ ባለፈው ዓመት ለተማሪ ቤቱ እርዳታ የሰጡትን ፤ ሰዎች ስም ከዚህ በታች እንደ ተጻፈው አነበበ ።

ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ	፪ሺ ብር
ልዑል አልጋ ወራሽ ተ፡ መ፡	፬ሺ፪፻፶ ብር
ልዕልት ወይዘሮ መነን	፫፻ ብር
ክቡር ደጃዝማች አባውቃው	፫፻፳፭ ብ፡
ክቡር አቶ ተሰማ እሸቴ ።	፫፻ ብር
ክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ ።	፪፻፲ ብር
ክቡር ከንቲባ ነሲቡ	፪፻፳ ብር
ክቡር ራስ ኀይሉ ።	፪፻ ብር
ክብርት ወይዘሮ ተናኘ ወርቅ	፪፻ ብር
ክቡር ፊታውራሪ ዓምዴ	፻ ብር
ክቡር ብላታ ኅሩይ	፻ ብር

ክቡር ቀኛዝማች ታደሰ ገነሜ	፻	ብር
ክቡር ሊቀ መኳስ መኰንን	፻	ብር
ክቡር አቶ ተድላ	፭	ብር
ክቡር ነጋድራስ አስታጥቄ	፳፭	ብር
ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ገ እ	፳	ብር
ክቡር አፈንጉሥ ከተማ	፶	ብር
ክብርት ወይዘሮ አጥቂለሽ	፶	ብር
ክቡር ፊታውራሪ ደስታ ተሰማ	፴	ብር
ክብርት ወይዘሮ በለጥሻቸው	፴	ብር
ክቡር ቀኛዝማች አምባቸው	፴	ብር
ክቡር አቶ ሚካኤል ብሩ	፲፭	ብር
ክቡር ቀኛዝማች ይመር	፲፭	ብር
ክቡር ራምሴስ ተስፋ ጊዮርጊስ	፲፭	ብር
ክቡር ደጃች መስፍን	፲	ብር
ክቡር አቶ በላቸው	፲	ብር
ክቡር አሕመድ ማላህ	፲	ብር
ክቡር ሙሴ ሚናስ	፲፪	ብር
ክቡር አቶ መኰንን ሀ ወ	፲፭	ብር
ክቡር አቶ ኤፍሬም	፲፮	ብር
ክቡር ቀኛዝማች ወልደ ማርያም	፲	ብር
ክቡር አቶ በቀለ ኪሮስ	፲	ብር
ክቡር ፊታውራሪ ኪዳነማርያም	፲	ብር
ክቡር አለቃ ኀሩይ	፲	ብር
ሙሴ ፓናዮታቴስ	፲	ብር
ስሙ ሊገለጽ ያልወደደ ፩ ደግ ኢትዮጵያዊ	፲	ብር
ክቡር አቶ ተክላ ሚካኤል	፳	ብር
ክቡር አቶ ኃይሌ	፳	ብር
ክቡር አሳላፊ ካሣዬ	፪	ብር
ክቡር አቶ አስፋው ኪዳነ ወልድ	፪	ብር
ክቡር ሙሴ ሐሻዱሪያን	፭	ብር
ክቡር አቶ ሀብተ ሥላሴ	፭	ብር
ክብርት ሲስተር ሜሪ	፭	ብር
ክቡር ሙሴ አስተማቲ	፭	ብር
ክቡር ፊታውራሪ ባንተ ይርጉ	፩	ብር
ክቡር አቶ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት	፩	ብር
ክቡር አቶ ተክለ ማርያም ካሣሁን	፫	ብር

ከዚህ በኋላ አቶ ምቀኝነት የቀስት ምልክት አድርጎ ስለ ተሰበሰበው ሰው ቅናት ይዞት እያጉመተመተ መጥቶ ወደ ሰዉ ሲመለከት የመተባበርና ያንድነት ወዳጅ የሆነ ጀግና እየሮከረ ሰይፉን መዞ ሎሬሳ ለብሶ ዝናር ታጥቆ ጠበንጃውን በግራ እጁ ይዞ መጥቶ አንገቱን ብሎ ገደለው ከጌታው ዘንድ ሄዶ ፎክሮ ሰለባውን ጣለና ጫማ ሳመ ወዲያው በግጥም ምቀኝነት እንዳ ይጎዳቸው እንዲጠነቀቁ ለሕዝቡ ተናገረና ተጨበጨበለት ግጥሙም እንደሚከተለው ነው ።

ፉከራ ።
ማኅበሩ አንደኛ ላገሩ ልርዳ ባይ ።
ፊቱን ሳይዞር ምቀኝነትን ገዳይ ።
የኢትዮጵያ ልጆች ።
ነና ወጣት ጉልማሶች ።
የተማመኑ ወንድሞች ።
ላባታቸው አገልጋዮች ።
ለናታቸው አሳቢዎች ።
ቤታቸውን ጠባቂዎች ።
ለወደ ፊት ባለ ተስፎች ።
የቅንነት ፊታውራሪዎች ።
የ ውነተኛ ባልንጀሮች ።
አንድነትን አክባሪዎች ።
ምክርንም አስተዋዮች ፡
ፍቅርንም አዋቂዎች ።
የኢትዮጵያ ልጆች ።
ይህንን ሰላልኩኝ እጅግ ደስ ደበሰን
ጎዛችን ብዙ ነው ገናን ገናን አለን ።

ልጅ በድሉ ዮሴፍ ይህን ጨዋታ በማሳመሩ ሰው ሁሉ አደነቀለት ይህን አንብቦ ሲጨርስ ተጨበጨበና መጋረጃው ተጣለ ።

በ፪ተኛው ጨዋታ መጋረጃው ተገለጠና ማኅበሩ ለትምርት የሰበሰባቸው ልጆች ተሰልፈው በየደረታቸው ላይ መለዮአቸውን አድርገው ሰንደቅ አላማ ይዘው ቆሙ ከመካከላቸውም አንዱ የሚከተለውን ቃል አነበበ

የነጻ ልጆች ምስጋና መንግሥቱንና ማህበሩን
በስደት ሲያወጡን ከቀድሞ አገራችን ።
ለይተው ሲወስዱን ከናት ከባታችን ።
እንገዛ ነበር በውድ በግዳችን ።
አሁን ግን አይተውት መከራ ግፋችን ።
ፍቅር አገልግሎት የኛ ረዳታችን ።
ከተፈሪ በታ ተሰራ ቤታችን ።
ከዚህ አደረሰን መልካሙ እድላችን ።
በፍቅር ለቀቁን ለጋስ ጌቶቻችን
እኛም እናገልግል ስለ ይሉኝታችን ።
ቀድሞ በግድ ነበር አሁን በውዳችን ።
የነጻነትን ክብር ስለ ማግኘታችን ።
እድሜአቸውን ያርዝም ለየጌቶቻችን ።

ሁለተኛውም ልጅ የሚከታለውን አነበበ ።

እናት አባታችን ዘመዳችን ሁሉ ።
ካይናቸው ስላጡን በጣም ሲዋልሉ ።
ታዳጊ ነውና ክርስቶስ ለሁሉ ።
መልካም አምበ ሠርተው ላገራቸው ሲሉ ።
ፍቅር አገልግሎት ለኛ ያስባሉ ።
ወንድሞቼ ሁሉ በጣም እልል በሉ ።
ሁሉም እልል እልል እንበል ሁላችን ባንድነት ።
በዘውዲቱ መንግሥት በተፈሪ ስልጣን አገኘን ነጻነት ።
እልል እልል እልል ሳገር እናገልግል እንዳንኰበልል ።
የመጨረሻውን ቃል ሁሉም ባንድነት ሲናገሩት የሰው ልብ በርኅራኄ ተነካ። ወዲያው ተጨበጨበና መጋረጃው ተጣለ።

ኢትዮጵያና ልጆቿ የልጅ ልመና የአባት አሳብ ስለሚለው ከሜዲ በሁለተኛው ዓመ ብርሃንና ሰላም ቁጥር ፳፪ ተመልከት ።

የዛሬው የኢትዮጵያ መንግሥት መኳንንትና ሕዝብም
የትምህርት ፍቅር እንደ ተሰማው ።

የተማረ ልጅ፡ አባክህ ጌታዬ ወሬ ልጠይቅህ ።
ማያንስ ኬምስትሪ ደግሞም ጀግራፊ ምን አለማወቅህ ።
ሒሳብ አሪትሜቲክ አልጀብራ ጆምትሪ አለመመርመርህ ።
ላንተም ብቻ አይደለ ጉዳት ነው ላገርህ ።
ይህን ሁሉ ነገር ስላለመማርህ ።
አንተ ተቀምጠህ ለባዕድ ያልፋል ክብርህ ።

ብልህ መኰንን አረ እውነትህን ነው ነገሩ ገብቶኛል ።
ይህስ ያልከው ነገር በጣም ቆጭቶኛል።
አለመማራችን በጣም ያሳዝናል ።
ባለመሥራታችን ማንም ይንቀናል ።
ስለዚህ ሁላችን ተባብረን በንድ ቃል ።
ስንፍና ኩራትን አውጥተን እንጣል ።
የተማረ ልጅ ፡ ጌታዬ ዛሬ እርስዎን እንዲህ እንደ ጻጸተዎ ።
በቅጡ ያስረዱ ለመላው ሕዝብዎ ።
የርስዎ ጊዜ አልፎአል በድል በሑብትዎ ።
ነገር ግን ያስቡ ለልጅ ልጆችዎ ።
ጥበብን ይማሩ ዛሬ ሳሉ እርስዎ ።
እሱ ያውቃልና እእምሮ ለብዎ ።
ብልህ መኰንን ፡ እንኳን የኔን ልጆች ሳላስተምር ልቀር ።
ሴቱንና ወንዱን ሕጻናቱን ከገር ።
ሁሉንም ሰብስቤ አንድም ልጅ ሳላስቀር ።
በጣም እጥራለሁ ለትምርት ነገር ።
በዚህ ይገለጻል ንጉሥ መውደድ አገር ።
ኋላም ይቆጠራል ከታላቅ ቁም ነገር ።
የተማረ ልጅ፡እናንት ካሰባችሁ በሙሉ ልባችሁ ።
ሊታገለግሉ ለውድ አገራችሁ ።
ጉልበታችሁ ኃያል ሚሊዮን ከብታችሁ ።
ለሌላም ይተርፋል እንኳን ለልጃችሁ ።
ስንኳን ተማሪ ቤት መርከብ በሰራችሁ ።
ሁላችሁ ሳትሆኑ ያውም አንዳ አንዳችሁ ።
ብልህ መኰንን ፡ እስከ ዛሬም ድረስ ዝም ማለታችን ።
ስንፊከበር ነው አንዳችን ካንዳችን ።
አሁን ግን ጸጽቶን ይኸው ስንፍናችን ።
ለትምርት ማስፋት ተነሳን ሁላችን ።
ለዚህ የማይረዳ ከመከከላችን ።
በላጋራ ሆነው ለነጻነታችን ።
የተማረ ልጅ ፡ እንዲህ ካሰባችሁ እላንት መኳንንቶች ።
የትም ተከፈቱ የተማሪ ቤቶች ።
በጥበብ ያድጋሉ ብዙ ሕጻናቶች ።
በፈተናም ጊዜ ተመርጠው አዋቆች ፤
ዩንቤርስቲ ሔደው ይባላሉ ሊቆች ፤
ስማችሁ ይጠራል የኢትዮጵያ ጌቶች ።
ብልህ መኰንን ፤ አሁን አንተ ከኛ በጣም ሕጻን ነህ ፤
ካዋቂ ይበልጣል ጥልቁ ሐሳብህ ፤
ለመንግሥትህና ለውድ አገርህ ።
በጣም ትረዳለህ ስለ መማርህ።
እንዲህ አናገርህ መልከሙ እውቀትህ ፤
ባይደረግ እንኳን ካንተ ወጣልህ ፤
ብዙ አስረድተሃል ጸጸትም የለህ ።
ቶሎ አልሆነ ብለህ ወንድሜ አይክፋህ ፤
ነገርህን ሁሉ ሰው እስቲቀበልህ ፤
ችሎታ አታግባበት ለማስታወስህ ፤
ገልጸህ ብትናገር ለሀገርህና ለወገኖችህ ።
ኋላ ይወዱሃል ዛሬ ቢጣሉህ ።

የተማረ ልጅ ፡ እንኳን እርስዎ እንዲህ እያጸናኑኝ ።
ዱሮውን ላገሬ ይሉኝታም የለኝ ።
ሁሉን እነግራለሁ እንደሚታየኝ ።
በገሬ ላለግም ግዝት አለብኝ ።
እርስዎ እንዲህ አሁን ቢያመሰግኑኝ ።
ሰነፎች ግን አሉ የሚቀየሙኝ ።
ብልህ መኰንን ፤ ማንም አይቀየም እውነት ብትናገር ።
መርዳት ይገባናል ሁላችንም ላገር ።
በስንፍና ብዛት ሳይደረግ ቢቀር ።
ቆይቶ ይቆጨናል ወደ ኋላ ስንቀር ።
የኢትዮጵያ ሰዎች እንዲህ ስንፋቀር ።
በልጆች ቅናትን ይዘን እንዳንቀር ።
ሊቅ ፤ ትንሽ ልውቀሳችሁ እናንት መኳንንት ።
ዛሬ ለልጃችሁ የምታደርጉት ።
በመብል በመጠጥ በሳቅ በጨዋታ ማሳደግ ከቤት ።
ጥቂትም ከፍ ሲል ብዙ ጭፍራ መስጠት ማዕርግ ሹመት።
ፈረስና በቅሎ እምቢልታ ነጋሪት ደግሞ አገር ግዛት ።
ይህ ሁሉ ተገኘ አላንድ ልፋት ።
ከጥንቱ አልተማረ ትንሽ ትምህርት ።
በልቡ ያድራሉ እነ አቶ ትእቢት ።
ከርሱ ይርቃሉ ትህትና ትእግሥት ።
ርህራኄ የለው ድሃ ማጉላላት ።
በዚህ በክፋቱ ሰው ሲአለቅስበት ።
በቶሎ ይመጣል የእግዚአብሔር መቅሰፍት ።
መኳንንት ሁሉ ፡ አሁን ሊቁ ያሉት አይደለም ሐሰት ።
እንዲህ እንደሚሉት ይሆናል እውነት ።
ጉልማሶች ሲሾሙ ሳይማሩ ፊት ።
ድሆችን ማጉላላት በግፍ በጭንቀት ።
ስለዚህ ወደ ፊት ደምብ እናርግለት ።
ሰባት ዓመት እድሜ ያሉ ሕፃናት ።
ተመልምለው ይግቡ ከተማሪ ቤት ።
ይህን እማያደርጉ እናትና አባት ።
ወህኒ ይታሰሩ ፲፰ዓመት ።
ገንዘባቸውንም ለተማሪ ቤት ።
በዚያ ይማራሉ እኒያ ሕፃናት ።
በንዲህ ያል ይሰፋል ጥበብ ትምህርት ።
የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉ ፡ የመኳንንቱን ቃል በጣም እን
ወዳለን ።
ልጆቻችንንም እናስተምራለን ።
ከገንዘባችንም አሥራት እንሰጣለን ።
ለሀገር ለመንግሥት በጣም እንረዳለን ።
ለገንዘባችንም ምንም ስስት የለን ።
በልጆቻችን እጅ ኋላ እናገኛለን ።
ንጉሥ ፤ የጥበብን ጥቅም እናንት ካወቃችሁ ።
ልጆች ለማሥተማር ካሰበ ልባችሁ ።
ለሁሉም ረዳት እኔ አለሁላችሁ ።
በጣም ፈቃዴ ነው ። አዋጅ ይውጣላችሁ ።

የመንግሥት አዋጅ አዋጅ አዋጅ አዋጅ ።
ልጅ የወለድ'ክ ሁሉ ወንድም ወይ ሴት ።
አምጥተህ አስተምር ከተማሪ ቤት ።
እንዲህ እየሰማህ ዝም ብትል አንተ ።
ቶሎ ይደርስሐል ሁለት ጉዳት ።
፩ኛው የልጅህ ድቁርናነት ።
፪ተኛው ደግሞ እንደ ቅድሙ ደምብ ታላቅ እስራት ።
ስለዚህ ቶሎ በል እርዳ ለትምርት ።
ለቸገረህ ሁሉ እኔ አለሁ መንግሥት ።
ይህ ስራ እንዲፈጸም ያዙ ልኝ ጸሎት ።
በነገሩ አስቡ በፍምጹ ትጋት ።
አምላክ ቢፈጽመው ይህንን ምኞት ።
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ፍጹም ሕያው ናት ።

ብርሃንና ጨለማ ።

ብርሃን ፤ ልጆች እልል በሉ ደስም ይበላችሁ ።
ለናንተ ላበራ ያው መጣሁላችሁ ፡
እንግዲህ ባንድ ይሁን ልቤና ልባችሁ ፡
ምን ጊዜም ምን ጊዜም እንዳልለያችሁ ፡
ባከላችሁ ጽላት ጻፉኝ ከልባችሁ ፡
መንገዴን ጠብቁ እንደ ሕሊናችሁ ፡
ጨለማ ፡ ይህ ቀጣፊ አታላይ በየት ዞሮ መጣ ፡
ብዙ ቀኑ ነበር ካገሬ ከወጣ ፡
በምን አመጣብኝ እወይ ያምላክ ቁጣ ፡
በሄድኩበት ሁሉ እሱ እኔን ሊያሳጣ ፡
፫፻ ዘመን የያዝኩትን በጣ ።
ምን ቢሆን አለቀም ነፍሴ ሳትወጣ ፡
ብርሃን ፤ አንት ባለጌ እረኛ ምን ትሳደባለህ ።
አቅምህን የማታውቅ ይሉኝታ የሌለህ ፡
ለምን ተኔ ጋራ ትወዳደራለህ ።
ፊት እንኳን ብትኰራ ተራ ነበረህ ፡
ዛሬ ግን ኤሌትሪክ ጭፍራዬ ነጥቆ አባረረህ ፡
ጨለማ ፤ ስድብስ ከመጣህ መታለልህን ልርታ ፡
አንድ ቀን አትውል ከጨዋ ከጌታ ፡
ፍቅርህ ከልጆች ነው ከማያውቅ ይሉኝታ ፡
እነሱን ለመስደብ በሳቅ በጨዋታ ።
ከቶ በምን ይሆን ኃይልህ የበረታ ።
ግፋችንን ይየው የፈጠረን ጌታ ።
ብርሃን ፤ አንት ዕውር ደንቆሮ ከቶ የታውቃለህ ።
እንዲያው በአፍ ድፍረት ትሳደባለህ ።
የዚህን መላውን እኔ ልንገርህ ።
እንጨትን ብትቆርጠው ለጋውን መርጠህ ።
ለሥራ ይገባል በያስፈለገህ ፡
ቀና ጉበጥ ይላል እንደ ፈቃድህ ፡
ግን ትልቅ ግንድ ቢሆን ቶሎ አይቆረጥ ።
ለሥራ የማይመች በቁም በቅምጥ ፡
ትልቁም ከስፍራው እንዳይናወጥ ፡
እንዲያው ለጥላችን ላድባር ይቀመጥ ፡
ለጋ ለጋውን መልምሉ በቅጥ ።
ከኔ ቤት ይመጣል አብሮኝ ሊቀመጥ ።
ጨለማ ፡ አንተን ካስፈለገህ ለጋ ለጋውን ።
ለኔ ልቀቅልኝ ዛፍና ግንዱን ፡
በጫፉ በስሩ ልዝጋ መንገዱን ፡
እንዲህ ተከፋፍለን ያስፈለገንን ፡
ሥራችን እንስራ በፈቃዳችን ፡
በዚህ ይታወቃል ድካም ኃይላችን ፡
ብርሃን ፡ ያንተ ግን አሳብህ በዚህ ይታወቃል ።
ሕዝቦችን ለመከፈል ልብ ያፈራርቃል ፡
ያንተማ ተንኰልህ መቼ በትኒሽ ያልቃል ፡
መንገዱን ለመዝጋት ልብህ ይንቀቃል ፡
አሁን ግን ላንተ ያገኘነው መላ ፡
ይህ ክፉ ስብከትህ ባገሩ ሳይሞላ ፡
አባትና ልጁን ትኒሽ ትልቁን ሁሉን ሳታጣላ ፡
እግሮችህን ሰብሮ በተማሪ ዱላ ፡
እጆችህን አስሮ የሬጥኝ የኋላ ፡
ከገደል መጣል ነው እንደ ጠላ አተላ ።
ጨለማ ፡ ባንድ ወገን ሲአስቡህ የዋህ ትመስላለህ ።
አሁን ግን በኔላይ የጭከና ነገር ትፈርድብኛለህ ።
የጎረምሳ ነገር ትነጋገራለህ ።
ሕፃን አይደለህም መቼ ይሉኝ ትላለህ ፡
በዚህ በመላስህ ትደበደባለህ ፡
ብርሃን ፡ አሁን እኔና አንተን ምን ያነዛንዛል ።
ሰው ከልቡ መርጦ ደህናውን ይይዛል ።
የዚያን ጊዜ አንተ ጨለማህ ይርቃል ።
የኔ ግን አበባ በጣም ይፈነዳል ፡
ላይንም ደስ ያሰኛል የብርሃን የጸዳል ።
በኔ የሚመካ በጣም ይጓደዳል ፡
ከደስታም ጋራ ብዙ ልጅ ይወልዳል ።
ከኔ ብርሃን አይቶ በውቀት ያስድጋል ።
የቤቱን ደስታ ዘወትር ያጸናል ፡
የፍዳም ቅጣት ከጭራ ይቀጥናል ፡
የሕዝቡ አበባይ ተፈሪ ይሆናል ፡
በእንዲህ ያለ መንገድ አገር ይቀናል ።
ስለ ሰካራም በሁለተኛው አመት ብርሃንና ሰላም ቁጥር
፳፫ገጽ ፪፻፰ ተመልከት ።

ትጉና ሰነፍ

ትጉ ፡ ልጆቼ ተነሱ ለሥራ እንዘጋጅ ።
ራሳችን ከልቻልን አናገኝም ወዳጅ ።
ሰነፍ ፡ ሥራ ሥራ እያልህ ሁሉን አሰቀቅኸው ።
አርፈህ ከልበላኸው ምኑን ተጠቀምኸው ።
ትጉ ፡ ከንቅልፍ ምን ይገኛል ወይስ ከጨዋታ ።
ጥበብ ያለውና ሠርቶ የበላ ነው ያለው ከበሬታ ፡
ሰነፍ ፡ አንት ዋሾ ቀጣፊ ለምን ትዋሻለህ ።
ሠርቶ የበላ ነው ከበርቴ ትላለህ ፤

ትጉ ፡፡ እውነቱ ነውና የማይሠራ የለም፤
እንኳን ሰውና እሱ መድኃኔ ዓለም ፤
ሰነፍ ፡ አንተ ተው እባክህ ሐሰት ቃል አታውራ ፡፡
እግዜር ምን ቸግሮት ያልከውን ቢሠራ ፡፡
ትጉ ፡፡ መጽሐፍ ላሳይህ ስነ ፍጥረትን ፡
በቀዳሚ ገብረ ሰማየ ወምድረ ብሎ እሚለውን ፡፡
ሰነፍ ፡ አወይ ያንተ ነገር ትለው የማታጣ ፡፡
የምድሩን ሳይጨርስ ከሰማይ ላይ ወጣ ፡
ትጉ ፡፡ አላነበብህ ይሆን የመጽሐፍ ቃሉን ፡
ተሰርዓ በሰማይ ተሰርዓ በምድር ብሎ ያለውን ፡፡
ሰነፍ ፡ የሰማይስ ሥራ በምድር አለ ታልከኝ ፡
ዘላለም ልኖር ነው ምንም እንዳይነካኝ ፡፡
ትጉ ፡፡ አንተ ልጅ ምን ትናገራለህ ነገሩን ሳታውቅ ፡
እንስሳ ይመስል አንተ መች ታውቃለህ ኩነኔና ጽድቅ ፡፡

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ቁጥር ይታተማል ፡፡

ከዚህ በኋላ ክቡር ሐኪም ወርቅነህ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ፡፡

ልዑል ሆይ

ክቡራን ወይዛዝርና ጌቶች

ዛሬ ይህን የቴአትር ጨዋታ ለማየት ስለመጣችሁልን በፍቅርና አገልግሎት ማኅበር ስም ሆኜ ከልብ የሆነ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ ፡፡ ይህም ጨዋታ የተደረገበትን ዋና አሳብ እናንተ ታውቁታላችሁ ምክንያቱም እናት አባት ለሌላቸው ድሆች ልጆችና ነፃ ለወጡ ልጆች ተማሪ ቤት አሁን ደግሞ ጥቂት ገንዘብ እንድናገኝ ነው ፡፡

ከዚህ ቀድሞ ቴአትር አድርገን በነበርን ጊዜ ልበ ሰፊዎችና ለጋሶች ጌቶቻችን ለተማሪ ቤቱ ማቋሚያ ፲ሺ ያህል ብር እርዳታ ሰጡን በዚህ እርዳታ ፳፬ የሚያህሉ ልጆች ሰብስበን እናሳድጋለን የእጅ ሥራም እናስተምራቸዋለን እስከሁን ድረስ ስለ ቦታ ችግር ተማሪ ቤቱ አልቆመልንም ነበር አሁን ግን በልዑል አልጋ ወራሽ ቸርነት ከሁዳዳቸው ላይ አንድ ማለፊያ ቦታ ስላገኘን ድንጋይ አስፈልጠን የተማሪ ቤቱን ሥራ ጀምረናልና በቅርብ ጊዜ የቤቱ ሥራ እንዲፈጸም ተስፋ እናደርጋለን ነገር ግን ካገኘነው ገዘንብ እስከሁን ድረስ ለልጆቹ ማሳደጊያና ለሌላም ከግራ ወጥቶለት አሁን በእጃችን ያለው ገንዘብ ፰ሺ ያህል ስለሆነ ለወደፊቱ ለልጆቹ ማሳደጊያና ለቤቱም መሥሪያ አይበቃምና ፡ አሁን ይህን ጨዋታ ማድረጋችን ከናንተ ከጌቶቻችንና ከመቤቶቻችን እርዳታ እንዲጨመር ብለን ነው ፡፡

ባለፈው ጊዜ እኛን በጣም ደስ ያሰኘን ነገር አምስት ሴት ወይዘሮች ለዚህ ሥራችን ማለፊያ እርዳታ ስለ ሰጡን ነው ፡፡ ይህም ያልተለመደ ነገር ነው ይኸ ያልተለመደ ነገር መሆኑ እኔ እንደሚመስለኝ ጥፋቱ የኛ የወንዶች ነው ፡፡ ለመንግሥትና ለሕዝብ እርዳታ በሚሆን ነገር ሁሉ የሴቶች ሥራ አይደለም እያልን ብንነግራቸውና ብንከለክላቸው ነው እነዚህም እርዳታ ያደረጉልን ሴት ወይዘሮች ልዕልት ወይዘሮ መነን ክብርት ወይዘር በለጥሻቸው ክብርት ወይዘሮ አስቴር ክብርት ወይዘሮ ተናኘ ወርቅ ክብርት ወይዘር አጥቁሌሽ ናቸው ፡፡

ፀኛ ፡ ለኔ እንደሚመስለኝ ከመከልከላችን የተነሣ ሴቶችም በሕዝብ ሥራ ስማቸው በገሃድ በመታወቁ ያፍሩ ይሆናል ፡፡ የሆነ ሆኖ እናት አባት ለሌላቸው ልጆች ተማሪ ቤት በመቆሙ ሴቶች በጣም ደስ ብሏቸው ይሆናል ፡፡ ርህራኄና አዛኝነት ከወንዶች ይልቅ በሴቶች የሚጸና ስለ ሆነ በእንደዚህ ያለ ሥራ ሁሉ በጣም ደስ ብሏቸው ይረዳሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን ፡፡

ከዚህ ቀደም እንዳስታወቅሁት አሁንም ሁለተኛ አስታውቃለሁ ፡፡ ለዚህ ተማሪ ቤት እርዳታ ገንዘብ የሰጡ ሰዎች ሁሉ መቼም ቢፈልጉ ሂሳቡን ለማየት ይችላሉ ፡፡

ደግሞ በውነተኛ ፍቅር አገራቸውን የሚወዱ ወይዛዝርና መኳንንት ከማኅበራችን ቢገቡ በደስታ ልንቀበላቸው የተዘጋጀን ነን ፡፡

ክቡራን መኳንንትና ወይዛዝር ሆይ ፡ ዛሬ ለዚህ ጉባዔያችን ስለ መጣችሁልን በጣም እናመሰግናለን ፡፡ በችኰላ ስለ ሠራነው ባጠፋነውም ሁሉ ይቅርታ እንድታደርጉልን እንለምናችኋለን ፡፡

ለግርማዊት ንግሥታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን እግዚአብሔር ዕድሜና ጤና ይስጥልን ብለን እንለምናለን ፡፡

አሜን ፡፡

ከዚህ በኋላ ሰስት ሴቶችና አንድ ወንድ እየዘመሩ ዘፈናቸውን አሳዩና ተጨበጨበላቸው ፡፡

ጨዋታውን ከጨረሱ በኋላ ስለ ማሕበሩ እርዳታ ሐራጅ ተደረገና ሰዉደስ ደስ እያለው በግዢ ስም ብዙ ገንዘብ ሰጠ ከዚያ በኋላ በዚያ የነበረ ሰው ሁሉ ሻይ ተጋበዘና ማሕበሩን እያመሰገነ ወጣ ፡፡

ጨዋታውን ሁሉ ሰዎቹ በጣም ስለ ሰለጠኑበት እንደሚደረግ አስመስለው አደረጉት እንጂ አላፈሩበትም ስለዚህ የሚያስቀው ከልክ አልፎ ያስቅ ነበር የሚያሳዝነውም ነገር ልብ አድርጎ ለተመለከተው አጥብቆ ያሳዝን ነበር ፡፡

ስለ ትጋታቸውና በሃገራቸው ፍቅር ተናደው ይሉኝታ ሳይፈሩ የሚደረገውን ነገር ሁሉ ገልጠው በማሳየታቸው ክቡር ሐኪም ወርቅነህና ማኅበሩን ሕዝቡ ሁሉ አመሰገናቸው ፡፡

ነጻ ለወጡ ልጆች ተማሪ ቤት እርዳታቸውን እንሰጣለን ብለው ያስታወቁ ሰዎች ቁጥርና የሰጡት ገንዘብ ልክ በሚከተለው ቁጥር ይታተማል

የከተማ ወሬ ፡፡

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንና ክቡር ራስ ጉግሣ አርዓያ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን ትምሕርት ቤት እንደጐበኙ፡

ግንቦት ፳፬ ቀን በ፲ ሰዓት ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንና ክቡር ራስ ጉግሣ አርአያን ተማሪ ቤቱን ለማየት መጡ ፡፡ ክቡር ሐኪም ወርቅነህ ከተማሪ ቤቱ በር ተቀብሏቸውና በየክፍሉ እያገቡ ሲያሳዩ አስተማሪዎቹ ተማሪዎቻቸውን በልዑል ፊት እየጠየቁ የትምሕርታቸውን ልክ ፈተኑ ተማሪዎቹም የተማሩትንና ያወቁትን ትምሕርት በትክክል በመ

የመንግሥት አዋጅ አዋጅ አዋጅ አዋጅ ።
ልጅ የወለድኽ ሁሉ ወንድም ወይ ሴት ።
አምጥተህ አስተምር ከተማሪ ቤት ።
እንዲህ እየሰማህ ዝም ብትል አንት ።
ቶሎ ይደርስሐል ሁለት ጉዳት ።
፩ኛው የልጅህ ድቁርናነት ።
፪ተኛው ደግሞ እንደ ቅድሙ ደምብ ታላቅ እስራት ።
ስለዚህ ቶሎ በል እርዳ ለትምርት ።
ለቸገረህ ሁሉ እኔ አለሁ መንግሥት ።
ይህ ስራ እንዲፈጸም ያዙ ልኝ ጸሎት ።
በነገሩ አስቡ በፍፃጼ ትጋት ።
አምላክ ቢፈጽመው ይህንን ምኞት ።
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ፍጹም ሕያው ናት ።

ብርሃንና ጨለማ ።

ብርሃን ፤ ልጆች እልል በሉ ደስም ይበላችሁ ።
ለናንተ ላበራ ያው መጣሁላችሁ ፣
እንግዲህ ባንድ ይሁን ልቤና ልባችሁ ፣
ምን ጊዜም ምን ጊዜም እንዳልለያችሁ ፣
በካላችሁ ጽላት ጻፉኝ ከልባችሁ ፣
መንገዴን ጠብቁ እንደ ሕሊናችሁ ፣
ጨለማ ፣ ይህ ቀጣፊ አታላይ በየት ዞሮ መጣ ፣
ብዙ ቀኑ ነበር ካገሬ ከወጣ ፣
በምን አመጣብኝ እወይ ያምላክ ቁጣ ፣
በሄድኩበት ሁሉ እሱ እኔን ሊያሳጣ ፣
፫፻ ዘመን የያዝኩትን በጣ ።
ምን ቢሆን አለቅም ነፍሴ ሳትወጣ ፣
ብርሃን ፤ አንተ ባለጌ አረኛ ምን ትሳደባለህ ።
አቅምህን የማታውቅ ይሉኻታ የሌለህ ፣
ለምን ተኔ ጋራ ትወዳደራለህ ።
ፊት እንኳን ብትኰራ ተራ ነበረህ ፣
ዛሬ ግን ኤሌትሪክ ጭፍራዬ ነጥቆ አባረረህ ፣
ጨለማ ፤ ስድብስ ካመጣህ መታለልህን ልርታ ፣
አንድ ቀን አትውል ከጨዋ ከጌታ ፣
ፍቅርህ ከልጆች ነው ከማያውቅ ይሉኝታ ፣
እነሱን ለመስደብ በሳቅ በጨዋታ ።
ክቶ በምን ይሆን ኃይልህ የበረታ ።
ግፉችንን ይየው የፈጠረን ጌታ ።
ብርሃን ፤ አንት ዕውር ደንቆሮ ክቶ የታውቃለህ ።
እንዲያው በአፍ ድፍረት ትሳደባለህ ።
የዚህን መላውን እኔ ልንገርህ ።
እንጨትን ብትቆርጠው ለጋውን መርጠህ ።
ለሥራ ይገባል በያስፈለገህ ፣
ቀና ጉበጥ ይላል እንደ ፈቃድህ ፣
ግን ትልቅ ግንድ ቢሆን ቶሎ አይቆረጥ ።
ለሥራ የማይመች በቁም በቅምጥ ፣
ትልቁም ከስፍራው እንዳይናወጥ ፣
እንዲያው ለጥላችን ሳድባር ይቀመጥ ፣
ለጋ ለጋውን መልምሉ በቅጥ ።
ከኔ ቤት ይመጣል አብሮኝ ሊቀመጥ ።
ጨለማ ፣ አንተን ካስፈለገህ ለጋ ለጋውን ።
ለኔ ልቀቅልኝ ዛፍና ግንዱን ፣
በጫፉ በስሩ ልዝጋ መንገዱን ፣
እንዲህ ተከፋፍለን ያስፈለገንን ፣
ሥራችን እንስራ በፈቃዳችን ፣
በዚህ ይታወቃል ድካም ኃይላችን ፣
ብርሃን ፣ ያንተ ግን አሳብህ በዚህ ይታወቃል ።
ሕዝቦችን ለመከፋፈል ልብ ያፈራርቃል ፣
ያንተማ ተንኰልህ መች በትኒሽ ያልቃል ፣
መንገዱን ለመዝጋት ልብህ ይነቃቃል ፣
አሁን ግን ላንተ ያገኘነው መላ ፣
ይህ ክፉ ስብከትህ ባገሩ ሳይሞላ ፣
አባትና ልጁን ትኒሽ ትልቁን ሁሉን ሳታጣላ ፣
እግሮችህን ሰብሮ በተማሪ ዱላ ፣
እጆችህን አስሮ የፊጥኝ የኋላ ፣
ከገደል መጣል ነው እንደ ጠላ አተላ ።
ጨለማ ፣ ባንድ ወገን ሲአስቡህ የዋህ ትመስላለህ ።
አሁን ግን በኔላይ የጭከና ነገር ትፈርድብኛለህ ።
የጎረምሳ ነገር ትነጋገራለህ ።
ሕፃን አይደለህም መች ይሉኝ ትላለህ ፣
በዚህ በመላስህ ትደበደባለህ ፣
ብርሃን ፣ አሁን እኔና አንተን ምን ያነዛንዛል ።
ሰው ከልቡ መርጦ ደህናውን ይይዛል ።
የዚያን ጊዜ አንተ ጨለማህ ዩርቃል ።
የኔ ግን አበባ በጣም ይፈነዳል ፣
ላይንም ደስ ያሰኛል የብርሃን የጸዳል ።
በኔ የሚመካ በጣም ይጓደዳል ፣
ከደስታም ጋራ ብዙ ልጅ ይወልዳል ።
ከኔ ብርሃን አይቶ በውቀት ያሳድጋል ።
የቤቱን ደስታ ዘወትር ያጸናል ፤
የፍዳም ቅጣት ከጭራ ይቀጥናል ፣
የሕዝቡ አባባይ ተፈሪ ይሆናል ፣
በእንዲህ ያለ መንገድ አገር ይቀናል ።
ስለ ሰከራም በሁለተኛው አመት ብርሃንና ሰላም ቁጥር ፳፫ገጽ ፻፹፰ ተመልከት ።

ትጉና ሰነፍ

ትጉ ፣ ልጆቼ ተነሱ ለሥራ እንዘጋጅ ።
ራሳችን ከልቻልን አናገኝም ወዳጅ ።
ሰነፍ ፣ ሥራ ሥራ እያልህ ሁሉን አስቀቅኸው ።
አርፈህ ካልበላኸው ምኑን ተጠቀምኸው ።
ትጉ ፣ ከንቅልፍ ምን ይገኛል ወይስ ከጨዋታ ።
ጥበብ ያለውና ሠርቶ የበላ ነው ያለው ከበሬታ ፣
ሰነፍ ፣ አንተ ዋሾ ቀጣፊ ለምን ትዋሻለህ ።
ሠርቶ የበላነው ከበርቴ ትላለህ ፤

ትጉ ፡፡ እውነቴ ነውና የማይሠራ የለም፣
እንኳን ሰውና እሱ መድኃኔ ዓለም ፤
ሰነፍ ፡ አንተ ተው እባክህ ሐሰት ቃል አታውራ ፡፡
እግዜር ምን ቸግሮት ያልከውን ቢሠራ ፡፡
ትጉ ፡፡ መጽሐፍ ላሳይህ ስነ ፍጥረትን ፤
በቀዳሚ ገብረ ሰማየ ወምድረ ብሎ እሚለውን ፡፡
ሰነፍ ፡ አወይ ያንተ ነገር ትለው የማታጣ ፡፡
የምድሩን ሳይጨርስ ከሰማይ ላይ ወጣ ፤
ትጉ ፡፡ አላነበብህ ይሆን የመጽሐፍ ቃሉን ፤
ተሰርዓ በሰማይ ተሰርዓ በምድር ብሎ ያለውን ፡፡
ሰነፍ ፡ የሰማይስ ሥራ በምድር አለ ታልከኝ ፤
ዘላለም ልኖር ነው ምንም እንዳይነካኝ ፡፡
ትጉ ፡፡ አንተ ልጅ ምን ትናገራለህ ነገሩን ሳታውቅ ፤
እንስሳ ይመስል አንተ መች ታውቃለህ ኩነኔና ጽድቅ ፡፡

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ቁጥር ይታተማል ፡፡

ከዚህ በኋላ ክቡር ሐኪም ወርቅነህ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ፡፡

ልዑል ሆይ

ክቡራን ወይዛዝርና ጌቶች

ዛሬ ይህን የቴአትር ጨዋታ ለማየት ስለመጣችሁልን በፍቅርና አገልግሎት ማኅበር ስም ሆኜ ከልብ የሆነ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ ፡፡ ይህም ጨዋታ የተደረገበትን ዋና አሳብ እናንተ ታውቁታላችሁ ምክንያቱም እናት አባት ለሌላቸው ድሆች ልጆችና ነፃ ለወጡ ልጆች ተማሪ ቤት አሁን ደግሞ ጥቂት ገንዘብ እንድናገኝ ነው ፡፡

ከዚህ ቀድሞ ቴአትር አድርገን በነበርን ጊዜ ልበ ሰፊዎችና ለጋሶች ጌቶቻችን ለተማሪ ቤቱ ማቋሚያ ፲ሺ ያህል ብር እርዳታ ሰጡን በዚህ እርዳታ ፳፬ የሚያህሉ ልጆች ሰብሰበን እናሳድጋለን የእጅ ሥራም እናስተምራቸዋለን እስካሁን ድረስ ስለ ቦታ ችግር ተማሪ ቤቱ አልቆመልንም ነበር አሁን ግን በልዑል አልጋ ወራሽ ቸርነት ከሁዳዳቸው ላይ አንድ ማለፊያ ቦታ ስላገኘን ድንጋይ አስፈልጠን የተማሪ ቤቱን ሥራ ጀምረናልና በቅርብ ጊዜ የቤቱ ሥራ እንዲፈጸም ተስፋ እናደርጋለን ነገር ግን ካገኘነው ገዘንብ እስካሁን ድረስ ለልጆቹ ማሳደጊያና ለሌላም ከሥራ ወጥቶለት አሁን በእጃችን ያለው ገንዘብ ፰ሺ ያህል ስለሆነ ለወደፊቱ ለልጆቹ ማሳደጊያና ለቤቱም መሥሪያ አይበቃምና ፤ አሁን ይህን ጨዋታ ማድረጋችን ከናንተ ከጌቶቻችንና ከመቤቶቻችን እርዳታ እንዲጨመር ብለን ነው ፡፡

ባለፈው ጊዜ እኛን በጣም ደስ ያሰኘን ነገር አምስት ሴት ወይዘሮች ለዚህ ሥራችን ማለፊያ እርዳታ ስለ ሰጡን ነው ፡፡ ይህም ያልተለመደ ነገር ነው ይኸ ያልተለመደ ነገር መሆኑ እኔ እንደሚመስለኝ ጥፋቱ የኛ የወንዶች ነው ፡፡ ለመንግሥትና ለሕዝብ እርዳታ በሚሆን ነገር ሁሉ የሴቶች ሥራ አይደለም እያልን ብንነግራቸውና ብንከለክላቸው ነው እነዚህም እርዳታ ያደረጉልን ሴት ወይዘሮች ልዕልት ወይዘሮ መነን ክብርት ወይዘር በለጥሻቸው ክብርት ወይዘሮ አስቴር ክብርት ወይዘሮ ተናኘወርቅ ክብርት ወይዘሮ አጥቂለሽ ናቸው ፡፡

ፀኛ ፤ ለኔ እንደሚመስለኝ ከመከልከላችን የተነሣ ሴቶችም በሕዝብ ሥራ ስማቸው በገሃድ በመታወቁ ያፍሩ ይሆናል ፡፡ የሆነ ሆኖ እናት አባት ለሌላቸው ልጆች ተማሪ ቤት በመቆሙ ሴቶች በጣም ደስ ብሏቸው ይሆናል ፡፡ ርህራኄና አዛኝነት ከወንዶች ይልቅ በሴቶች የሚጸና ስለ ሆነ በእንደዚህ ያለ ሥራ ሁሉ በጣም ደስ ብሏቸው ይረዳሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን ፡፡

ከዚህ ቀደም እንዳስታወቅሁት አሁንም ሁለተኛ አስታውቃለሁ ፡፡ ለዚህ ተማሪ ቤት እርዳታ ገንዘብ የሰጡ ሰዎች ሁሉ መቼም ቢፈልጉ ሂሳቡን ለማየት ይችላሉ ፡፡

ደግሞ በውነተኛ ፍቅር አገራቸውን የሚወዱ ወይዛዝርና መኳንንት ከማኅበራችን ቢገቡ በደስታ ልንቀበላቸው የተዘጋጀን ነን ፡፡

ክቡራን መኳንንትና ወይዛዝር ሆይ ፤ ዛሬ ለዚህ ጉባዔ ያችን ስለ መጣችሁልን በጣም እናመሰግናለን ፡፡ በችኰላ ስለ ሠራነው ባጠፋነውም ሁሉ ይቅርታ እንድታደርጉልን እንለምናችኋለን ፡፡

ለግርማዊት ንግሥታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን እግዚአብሔር ዕድሜና ጤና ይስጥልን ብለን እንለምናለን ፡፡

አሜን ፡፡

ከዚህ በኋላ ሶስት ሴቶችና አንድ ወንድ እየዘመሩ ዘፈናቸውን አሳዩና ተጨበጨበላቸው ፡፡

ጨዋታውን ከጨረሱ በኋላ ስለ ማሕበሩ እርዳታ ሐራጅ ተደረገና ሰዉ ደስ ደስ እያለው በግገር ስም ብዙ ገንዘብ ሰጠ ከዚያ በኋላ በዚያ የነበረ ሰው ሁሉ ሻይ ተጋበዘና ማሕበሩን እያመሰገነ ወጣ ፡፡

ጨዋታውን ሁሉ ሰዎቹ በጣም ስለ ሰለጠኑበት እንደሚደረግ አስመስለው አደረጉት እንጂ አላፈሩበትም ስለዚህ የሚያስቀው ከልክ አልፎ ያስቅ ነበር የሚያሳዝነውም ነገር ልብ አድርጎ ለተመለከተው አጥብቆ ያሳዝን ነበር ፡፡

ስለ ትጋታቸውና በሃገራቸው ፍቅር ተናደው ይሉኝታ ሳይፈሩ የሚደረገውን ነገር ሁሉ ገልጠው በማሳየታቸው ክቡር ሐኪም ወርቅነህና ማኅበሩን ሕዝቡ ሁሉ አመሰገናቸው ፡፡

ነጻ ለወጡ ልጆች ተማሪ ቤት እርዳታቸውን እንሰጣለን ብለው ያስታወቁ ሰዎች ቁጥርና የሰጡት ገንዘብ ልክ በሚከተለው ቁጥር ይታተማል

የከተማ ወሬ ፡፡

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንና ክቡር ራስ ጉግሣ አርዓያ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን ትምሕርት ቤት እንደጐበኙ፡

ግንቦት ፳፱ ቀን ባ፲ ሰዓት ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንና ክቡር ራስ ጉግሣ አርአያን ተማሪ ቤቱን ለማየት መጡ ፡፡ ክቡር ሐኪም ወርቅነህ ከተማሪ ቤቱ በር ተቀበሏቸውና በየክፍሉ እያገቡ ሲያሳዩ አስተማሪዎቹ ተማሪዎቻቸውን በልዑል ፊት እየጠየቁ የትምሕርታቸውን ልክ ፈተኑ ተማሪዎቹም የተማሩትንና ያወቁትን ትምሕርት በትክክል በሙ

መለሳቸውና በመሰልጠናቸው ልዑል አልጋ ወራሽንና ክቡር ራስ ጉግሣን አብረዋቸው የነበሩትንም ሰዎች ሁሉ ደስ አሰኙዋቸው።

ከዚህ በኋላ ተማሪዎቹ የሚያድሩበትን ቤት ከምድር ቤቱ እስተ ፎቁ አዩ ። ወዲያው ደግሞ የእንጨት ሥራና የሸማ ሥራ የሚማሩ ተማሪዎችን አዩና ሥራቸውን አይተው ደስ ባሏቸው ቻይ በተሰናዳበት ቤት ገብተው ቻይ ሲጋበዙ ተማሪዎቹ እጅግ ደስ የሚያሰኝ የቴአትር ጨዋታ ተጫወቱ ።

ከዚያ ወጥተውም ተማሪዎቹ (የጅም ናስቲክ) የሰውነት ማንቀሳቀስ ትምሕርት ከተማሪ ቤቱ በውጪ ባለው ሜዳ አሳምረው አሳዩና የጅምናስቲክ ማየት በተፈጸመ ጊዜ ክቡር ራስ ጉግሣ በአስተማሪዎቹና በተማሪዎቹ በተማሪ ቤቱ አኳኋንም እጅግ አድርገው ደስ ስላላቸው ለተማሪ ቤቱ እርዳታ አምስት መቶ ብር ሰጡ ።

፲፪ ሰዓት ሲሆን ልዑል አልጋ ወራሽና ክቡር ራስ ጉግሣ በየአውቶሞቢላቸው ተቀምጠው ወደ ቤታቸው ተመለሱ ።

ክቡር ራስ ጉግሣ አርአያ በንጹሕ ልቡና በብዙ ትሕትና የመንግሥት አገልጋይ የድሃ ረዳት እንደሆኑ በማወቁ ሰው ሁሉ ያመሰግናቸዋል ። ግን ወደ ሀገራቸው በደኅና ይመልሳቸው እንጂ በግዛታቸው ውስጥ የልዑል ተፈሪ መኰንን አብነት ተከትለው ትልቅ ተማሪ ቤት በማቆም በበታቻቸው ላሉ መኳንንት መልክም መሪ ፡ በጎረቤታቸው ላሉ ገዢዎች መልክም አርአያ እንዲሆኑ ተስፋ እናደርጋለን ።

የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ከደብረ ሊባኖስ ወደ አዲስ አበባ መመለስ ።

የተወደዱ ንግሥታችን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በደብረ ሊባኖስ ለጠበል ሄደው ሰንብተው ነበርና ሰኔ ፩ቀን በ፲፩ ሰዓት አዲስ አበባ ገቡ ። ልዑል አልጋ ወራሽና ክቡራን መኳንንቶቻቸው የከተማው ሰው ሁሉ በታላቅ ደስታ ተቀበሉዋቸው ።



ግርማዊት ሆይ እንኳን ደኅና ገቡልን እያለ ብርሃንና ሰላም ደስታውን ይገልጻል ፡፡

የውጭ አገር ወሬ

ስለ ባርነት

የባሪያ መሸጥና መለወጥ ከሚሪከ ጠርነት ወዲህ ጭራሽ በመቅረቱ ፈንታ በዓለም ላይ እየበዛ ሄደ የምድረ ግብጽን ፒራሚድ (ከጫፉ ቁብብ ያለ ያሸዋ ተራራ) በግድ ታስረው እንደ ሰሩት ሰዎች ብዙ ሴትና ወንድ ሕጻናት ጭምር የሚያንገፈግፍ ፍዳ እየቻሉ ይኖራሉ ።

በአፍሪቃ በፖርቱጊስ ቅኝ አገር ፖርቱጊስ አንጎላ በተባለው ባሮች ለስም ነጻነትን ስላገኙ በባርነት ጽኑ ስራ እንዲሰሩ የግድ ተደርጓል በስሐራ ምድረ በዳ በማረቆ በላይብሪያ በሱማሌ ጠረፍና ራቅም ብሎ በኰኰ ደሴቶች ባሮችን እየያዙ ስለ ንግድ ጉዳይ የሚሸጡ ሰዎች ብዙ አሉ ።

በአንጎላ ባሮች ስለ ሚቀበሉት ፍዳና ሰቃይ ።

እስካሁን ድረስ በኔፓል አገር በባርነት የሚኖሩ ፶፩ሺ ባሮች ነበሩ ደሞዝ አልባ በባርነት የሚሰሩ ባሮች በበርማም አገር እስካሁን አሉ ፕሮፌሶር ሮስ የተባለ አንድ የአሜሪካን መላክተኛ በአንጎላ ባሮች የሚቀበሉትን ፍዳና ስቃይ ለመመርመር ሂዶ በዚያ በደንቆሮ አገር ያየውንና የምርማሬውን ፍጻሚ ለጊ ደ ናሲዮን አቀረበ

ባሮቹም በመጐዳት ምክንያት ከስተው ስለ ነበረ እስራ አንዱ በመንገድ ሞቱ ሴሎችም ሬሳውን ለመቅበር ስለ ተከለከሉ ላሞራ ጥለዋቸው ሄዱ ሴቶቹ ልጆቻቸውን በጀርባቸው አዝለው ከዚያ በላይ በራሳቸው ከበድ ሸሀል ዕቃ ተሸክመው አየኋቸው እነዚህም ባሮች በጭከኔ ብዙ ጊዜ ተገርፈዋል አንድ የመንደር ቱኪ (ሹም) የጆቹን መሐል ተገርፎ ሁለቱም እጆቹ ቆርጥ ብለው አብጠው በማግሥቱ ከሐብስ ቤት ወጥቶ ደማ ይዞ እንዲቆፍር በግድ ታዞ ደማውን መያዝ ተስኖት ባውራጣቱና በጣቶቹ መሐል ጨብጦ ችጋር አድክሞት አየሁ አሁን በቅርብ ቀን የባሪያ መሺጥና መለወጥ እንዲቀር በበርማም አገር ተጀምሯል «የበርማ አገር የጦር አለቃ ቃብጢያን ባሪን ከስድስት ወታደሮች ጋር የባሮቹን አገር ገብተው ሲጐበኙ ባሮቹ ቀን ደህና ተቀበለዋቸው ማታ ግን ሊያርዱዋቸው ፈተኑ የበርማ አገር ባሪያ ዋጋው ፪፻ ሩብያ ነው ወይም በ፰ ጐሽ አንድ ባሪያ ይለወጣል እስካሁን ይህን ልማድ በቶሎ ለማስተው አልተቻለም በማሴይ አውራጃ ሰው መሸጥ የጭካኔ እንደሆነ ሳይረዱ እናትና አባት ልጆቻቸውን በሕጻንነታቸው ይሸጣሉ እነዚህም የተሼጡ ሕጻናት በገዥዎቻቸው እጅ እንደ ቤት ዕቃ በባርነት ይኖራሉ በሖንግ ኰንም ይኸን የመሰለ የጭካኔ ሥራ እስካሁን አይጠፋም ፡



በአውሮጳ አገር አሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሠከረለት ዝኒት የሚባል ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፰ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ተኩል።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፹፭ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር ተሩብ
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፱ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፫ ብር ተሩብ
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፯ ብር ተኩሉ
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፻፴፯ ብር ።
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፸፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፲ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፸፰ ብር
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፺፬ ብር ።
ቡክር	፩ ጁኒያ	፴፪ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፫ ሩብ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፲፫
በአንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ ፶
በአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፲፯ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል ።

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኰምፓንያ" ብቻ ነው ።

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፡በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ካኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኵታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመከከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሂስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረትና ለአንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላሸው ፡ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።



ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ አቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

ARMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኤዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ስንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቆውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

ዕስተኛ ዓመት ፣ ቁጥር ፳፬
5 me ANNÉE № 24

ሐሙስ ሰኔ ፱ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 16 JUIN 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé "Lumière et Paix".

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ብርሃንና ሰላም ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ሕዝባቸውን በሰላም ለማኖር የተኛውንም ልብ ለመቀስቀስ ብርንሃና ሰላም የሚባል አዲስ መሪ ተከሉ ። እኒህ ብርሃንና ሰላም የተባሉ እንደ ሁለት እንቍ የከበሩ ቃላት ከትልቅ እስከ ትንሽ ሊነቅፋቸው አይችልም ። ስለ ምን ብርሃንና ሰላም ያገር ድምቂያ ነው ፡ ብርሃንና ሰላም ለመንግሥት ኃይልና ክብር ነው ይህም ይታወቅ ዘንድ ብርሃን ከሌለበት ሥፍራ ሰላም አይገኝም ብርሃን ከልፈለጉት እሱ ራሱ መጥቶ የጨለመውን ልብ አያበራም ። በዚሁ ዘመን ያለን አዲሶቹ የኢትዮጵያ ሕዝብሳ ትልቁ ትንሹ ብርሃን ፈጽሞ በገራትን እንዲደምቅ ምን ሥራ ሰራን ለጥቅም የሚሆን ሥራችንስ ወዴት አለ ብርሃንና ሰላም ብሎስ በመናገር ብቻ ምን ጥቅም አገኘን ይኸንንም ነገር በጣም ለመረመረው የኢትዮጵያን ሕዝብ አንጀት የሚበጥስ ነው ማለት መሪና ተመሪ ሁላችን ተኝተናል በዓለምም ሁሉ እንደኛ የተመቸው ሰው ያለ አይመስለንም እንቅልፋም በጣም ጣፍጦናልና ከኛ አንድ ስንኳ ከመኝታው ለመነሳት እጁን የሚያንቀሳቅስ አይገኝም ከላይኛውም ደረጃ ወደ ታችኛው ወድቀን ከወደቅንበትም ቦታ ተኝተናልና ይኸን ጊዜ እባካችሁ እንነሳ ብሎ የሚያስብ የለም ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ ሀብት አልነደለብንም ሕዝባችንም ልብ የሌለው ሆኖ አይደለም የሕዝባችንንስ ልብ ስንኳንስ ያልሰለጠኑት በጣም የሰለጠኑትም ሰዎች ይደነቁበታል ። ነገር ግን ሕዝባችን እንደ ሰለጠኑት ይሆን ዘንድ ሥርዓት ጎድሎብናል ይልቁን ሁሉን ማድረግ ከሚቻላቸው ጌቶቻችን መሸተትና መትጋት ጎድሎብናል ። የኔ ወገን ወንድሞቼ አሁንስ ከመኝታችን የምንነቃበት ጊዜ ደርሱዋል ምድር ነግቶ ፀሐይ ወጥቶ ሰራተኛ ሁሉ በየሥራው ተበተኖአልና በብርሃንና ሰላም ያነበብነውን ሥራ በመሥራት ልንፈጽመው ይገባናል ። በእምነት ተጣጥረን ያረጀውን የኢትዮጵያን ልብ እንደገና አድሰን በሾለ ብርዕ ያገራችንን ፍቅር መልሰን መላልሰን ልንጽፍበት ይገባል ። እናንተም አገረ ገዢዎች ችሎትና ኃይል የናንተ ነው ነገ ልንሰራው የሚገባንም ፈቃድ ከጃችሁ ነውና የሚሻለውን መንገድ አሳዩን ።

ከልዕልናችሁና ከማዕርጋችሁ እየቀነሳችሁ ኢትዮጵያን እናታችሁን አክብሯት ከሃብታችሁም አካፍሏት በከንቱ ያለፈ ጊዜ ተመልሰው ቢፈልጉት አይገኝም አስራ ሁለት ሰዓትም ካለፈ በኋላ ፀሐይ ትገባለችና የሚሰራበት ሥራ የለም ፡፡ ግን የዚያን ጊዜ ከተወደችውና በስንፍናችን ምክንያት በፈረሰችው ነጻነታችን በታች ሆነን ማልቀስ ነው የዚያን ጊዜ ያባቶቻችንን ትዕቢት አስበን ፊታችንን በኃፍረት እንሸፍናለን ሰውነታችንን ደህና ነን በማለት እናታልል ፡፡

ይህንንም ከሚያነቡ ሰዎች አንዱ እኛ ደንቆሮች አይደለንም የሰለጠኑ ሰዎች የለበሱትን ሁሉ እንለብሳለን ይል ይሆናል ። ይህንም መልስ የድንቁርናችን አይነተኛ ምስክር ነው ፡፡ ዝንጀሮም ያየችውን ሁሉ ታደርጋለችና በዚሁ የተማረች ናት የሚላት የለም ስለምን ያየችውን አስመስላ መሥራት አማይቻላት ቢሆን ነው ።

አሁንም የጥፋትና የሀልፈት ደወል እንደውላለን ተነሡ ተነሡ ወንድሞቼ ሆይ ተነሡ አገራችንን የሚጎዳው ምክንያት ዋናው አይነተኛው ብርሃንን ከማጣት የተነሣ ነው ፡፡

ትንሹ ልጃችሁ ጥሩነህ ክብትህ ይመር አድዋ

የ፻፹፯ ገጽ ።

ሰነፍ ፡ ደግሞ አንተ ሰው ሆነህ ሰውን ትሰድባለህ

ራስህን ለመቻል ባሬ ትሆናለህ ፡
ዘወትር በሥራ ትቀጠቀጣለህ ፡
ለመኝታህ እንኳን ትንሽ እረፍት የለህ ።

እንዳንተ እንዲሆኑ ሰው ታባብላለህ
ሰውን ሳታበላሽ እግዚር በገደለህ

ትጉ ፡ እኔ ምን ባልኩ ነው ሥርቼ ብበላ የምትረግመኝ ፡
ሰሎምን በምሳሌ ቀድሞ ባይነግረኝ ፡
ለሰነፍ እንደስንፍናው አትመልስለት ብሎ ባይለኝ
አዋርድህ ነበር ምንም አትርፈኝ ።
ዳሩ ግን ሌላ ሰው ደግሞ እንዳታምኝ ፡
እጠብቅሃለሁ በግራም በቀኝ ፡

ሰነፍ ፡ አንተም ባትጠብቅ እኔም ግድ የለኝ ፡
እንቅልፌን አስትቶ ምን አባከነኝ ።
እንኳን እኔ ልዞር ያንተ ሲገርመኝ ፡
ይሰብካል ብለህ ነው የጠረጠርከኝ
አውቆ የያዘውን ከመረቅህልኝ ፡
ዙሬ አንዳላስተምር ግዝት ያርግብኝ

ትጉ ፡ አንተ በምን እንዲህ እንቅልፍ ትወዳለህ ፡
ከቶ አልሰማህ ይሆን ሰሎሞን እንዳለህ
እንቅልፍ ስትዘራ ረሀብ ታጭዳለህ ፡
በመከርም ወራት በጣም ትተኛለህ ።
ስለ ስንፍናህም ድሀ ትሆናለህ ።
ከባልንጀሮችህም ዝቅ ዝቅ ትላለህ ፡

ሰነፍ ፡ የናንተ ጌትነት ምን ያደርግልኛል ፡
ጌትነት ስ ባገኝ እንቅልፍ ይሻለኛል ፡
ጉኔ እስኪላጥ ድረስ ግድም ያደርገኛል ፤
ግን ክብር በሆነሁኝ ይወዘወዘኛል
እሱን በማጠንጠን ድቅቅ ያደርገኛል ፡

መንፈሳዊ እርዳታ

ግንቦት ፳፰ ቀን የፍቅርና ያገልግሎት ማኅበር ስለ ድሆች ልጆች ተማሪ ቤት እርዳታ ለማግኘት ቴአትር ባደረጉበት ቀን እርዳታ የሰጡ ሰዎች ከዚህ በታች የተጻፉት ናቸው ።

ክቡር አቶ ፋሲካ	፻፳	ብር
ክቡር ነጋድራስ ታፈሰ	፻፩	ብር
ክቡር ልጅ ኃይለ ማርያም ገሠሠ	፶፭	ብር
ክቡር አፈ ንጉሥ ከተማ	፶	ብር
ክቡር ሙሴ ፓይላክ	፶	ብር
ክቡር አቶ በቀለ ኪሮስ	፴	ብር
ክቡር ቀኛዝማች አምባቸው	፴፭	ብር
ክቡር ልጅ በዛብህ ስለሺ	፲፭	ብር
ክቡር አቶ አስፋው ኪዳነ ወልድ	፲፭	ብር
ክቡር ግራዝማች ይገዙ	፲	ብር
ክቡር አቶ ተክለ ማርያም	፲	ብር
ክቡር ፊታውራሪ ገብረ ማርያም	፯	ብር
ክቡር ሙሴ ሐሻዱሪ ን	፯	ብር
ክቡር ፊታውራሪ በየነ በቃቢል	፭	ብር
ክቡር አቶ ሞገስ ደስታ	፭	ብር
ክቡር አቶ ኪዳኔ በልሁ	፭	ብር
ክቡር አቶ ወንድማገኘሁ ወልደ ዮሐንስ	፭	ብር
ክቡር አቶ ዓለማየሁ ወንድማገኘሁ	፭	ብር
ክቡር ሙሴ ጋኖታኪስ	፬	ብር
ክብርት ወይዘሮ አዜብ ያሬድ	፫	ብር
ክቡር ሙሴ አክቢዲስ ክናጂያ	፫	ብር
ክቡር አቶ ያሬድ	፪	ብር
ክቡር ሙሴ ዜዲያን	፪	ብር

ጥቂቱን ዕቃ በብዙ ዋጋ እየገዙ በዕቃ ግዢ ምክንያት (እርዳ የሰጡ ሰዎች ።)

ክቡር ራስ ኃይሉ	፩፻፳	ብር
ክቡር ራስ ጉግሳ	፩፻፭	ብር
ክቡር ደጃዝማች ሥዩም	፻፶፭	ብር
ክቡር ሙሴ ጎርጎርዮስ	፻፶	ብር
ክቡር ልጅ መንገሻ ወልደ ጊዮርጊስ	፻፶፪	ብር
ክቡር አቶ በላቸው	፻	ብር
ክቡር ልጅ ፍቅረ ሥላሴ ከተማ	፹፭	ብር
ክቡር ፊታውራሪ ገብረ ማርያም	፷፪	ብር
ክቡር አቶ ወልደ ጻድቅ አስረስ	፷	ብር
ክቡር ብላታ ጎሩይ	፷	ብር
ክቡር አቶ ተሰማ እሼቴ	፳፭	ብር
ክቡር ሊቀ መኳስ መንገሻ	፳	ብር
ክቡር አቶ ብርሃነ ማርቆስ	፳	ብር
ክቡር ፊታውራሪ ኃይሌ ወልደ ሩፌ	፶	ብር
ክቡር ሙሴ ጳውሎስ	፶	ብር
ክቡር አቶ ኤፍሬም ተወልደ መድኅን	፴	ብር
ክቡር አቶ ተስፋዬ ተገኝ	፴	ብር
ክቡር አቶ አርአዶም	፴፯	ብር
ክቡር አቶ ተፈራ ወርቅ	፴፪	ብር
ክቡር አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ	፴	ብር
ክቡር አቶ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት	፳፭	ብር
ክቡር አቶ ታደሰ መሸሻ	፳	ብር
ክቡር ነጋድራስ አስታጥቄ	፳	ብር
ክቡር አሕመድ ማላህ	፳	ብር
ክቡር አቶ በቀለ ማሀሌ	፳	ብር
ክቡር ነጋድራስ ወልደየስ	፳	ብር
ክቡር ሙሴ ቶማስኒ	፳	ብር
ክቡር ሙሴ ሚናስ	፳	ብር
ክቡር ቀኛዝማች ይመር	፲	ብር
ክብርት መዳም ሚናስ	፲	ብር
ክቡር ፊታውራሪ ቀነዓ	፯	ብር
ክቡር ሙሴ ማርቲኒ	፭	ብር

ድምር ፬ሺ ፭፻፷፩ ብር

ደግሞ አምና በተደረገው ቴአትር እንደዚህ እንደዛሬ ሁሉ አገራቸውን የሚወዱ ክቡራን ጌቶቻችን እርዳታ እንሰጣለን ብለው ቃላቸውን አሳልፈውልን ነበርና የተከበረ ስማቸውን በሚመጣው ጋዜጣ ጽፈን እናስታውሳለን ።

የሰው ልጅ ዘር ንቀት ።

ከማየትና ከመስማት ወይም ከማንበብ ብዙ ነገር ይገኛል እንደሚሉ እኔም ያየሁትንና ያነበብኩትን በዚህ ባለሁበት አገር በቀን በቀኑ የሚደረገውን ነገር ባጭሩ ሳይበዛ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ልጽፍላችሁ ፈቀድሁ ይኸው እንኩ ስሙኝ እስቲ ትንሽ ታሪክ ላውጋችሁ የሰው ልጅ ዘር ንቀትን ።

ይኸው ከሀገራችን ከወጣን ፬ ዓመት ሆነን በ፲፱፻፲፪ ዓመተ ምሕረት አሜሪካን አገር ደረስን መቼም ሰው ካልቆየና ታልተማረ ሁሉን ነገር በቶሎ መርምሮ ለማወቅ አይችልምና እኛም እንደዜሁ ፊት እንደ ደረስን በጣም ነገሩን ሁሉ መርምረን አላወቅነውም ነበር ። ነገር ግን አሁን ሁሉንም ነገር መርምረን ስለ አገኘነው ልዩነትን ሁሉ በሰው ልጅ ዘር ላይ ።

፩ኛ ፤ በአሜሪካን አገር ሁለት ዓይነቶች ሕዝቦች ይኖራሉ እነዚህም ሁለት ሕዝቦች ያልኳቸው ነጮችና ጥቁሮች ናቸው ።

፪ኛ ፤ እነዚህም ጥቁሮች ከደቡብ አፍሪካ ነው የመጡት በባርነት ተሸጠው የመጡበትም ጊዜ ከ፫፻፶ ዓመት በልጧቸዋል የመጡትም በእንግሊዝ እጅ ነው ። ቁጥራቸውም ፳ ይሆን ነበር ይህ የእንግሊዝ ሰው እነዚህን ባሮች ወደ ደቡብ አሜሪካ ወስዶ ሸጣቸው ከዚህም በኋላ ዘራቸው እየበዛ ሄደ ዛሬ የጥቁሮቹ ቍጥር ፲፪ ሚሊዮን ሆኑዋል ። ነገር ግን የሰሜኑ አሜሪካ ተደቡቡ አሜሪካ ጋር ተዋግቶ ጥቁሮችን ዓርነት አወጣቸው ። በዚያን ጊዜም ፕሬዝዳንቱ አብርሃም ሊንከን ይባል ነበር የዚህ ፕሬዝዳንት ስም በዓለም ሁሉ የታወቀ ነው ።

ከዚህ በኋላ ጥቁሮች ወደ ምዕራብና ወደ ሰሜን ወደ ምሥራቅም ተበታተኑ እስከ አሁን በደቡብ የሚኖሩት ጥቁሮች በጣም ነጻነት የላቸውም ነጮች ግፍ ይውሉባቸዋል በሰሜንና በምዕራብ በምሥራቅ የሚኖሩት ጥቁሮች ትንሽ ነጻነት አላቸው ይኸውም ዓርነት ከወጡ ስልሳ አራት ዓመት ሆኖአቸዋል ። ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው የዘር ንቀት ባጭሩ ያስታውቃችኋል።

፫ኛ ፡ የነጮች አኗኗር እጅግ ከፍ ያለ ነው ከጥቁሮች ነጮች ሁሉን የፈለጋቸውን ነገር ለማድረግ ይችላሉ ሁሉ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል ።

፬ኛ ፡ የጥቁሮች አኗኗር ግን እጅግ ያሳዝናል ሕይወታቸውን ሁሉ ደስ ሳይላቸው ይኖራል ልክ እንደ ድመትና እንደ ውሻ ነው አኳሁናቸው ነጮች ጥቁሮችን በሙሉ ዓይን ለማየት እጅግ ያለመጠን ይጸየፏቸዋል ።

፭ኛ ፡ በሁሉ ከተማ ብዙ ብዙ ዓይነት የቲያትር ጨዋታ ያሳያሉ ደግሞም እጅግ ባለውቀቶች የሆኑ ሰዎች በትልልቅ አደራሽ ቤት ንግግር ያደርጋሉ በዚህም መልካም ቲያትር ቤት ጥቁር አያስገቡም በዚህም ንግግር በሚደረግበት ቤት ጥቁር አያስገቡም ።

፮ኛ የተማሩም ጥቁሮች አሉ ሐኪም የሆኑ ሕግም ያወቁ እናም አስተማሪዎች የሆኑ እነኝህ ሰዎች ሥራ በሚፈቱበት የዕረፍት ጊዜ ባላቸው ወደ ትልቅ ሆቴል ሄዶ ወይም ወደ ትልቁ ቲያተር ቤት ሄደው ለፈንጠዝያ ይህቺን የርዕፈታቸውን ጊዚያት እንደማሳለፍ ከዚያው ከሚኖሩበት ቁጭ ብለው ይውላሉ ወይም በመንገድ ይንከላወሳሉ ይኸንን ሁሉ ማድረጋቸው ነጮቹ ወደ ትልልቁ ስፍራ እንዲገቡ አይፈቅዱላቸውም ጥቁር አለፍ ባለ ቁጥር ነጮች እንዲህ ይላሉ እየው ያን ወዳራ ሽንቅላ አለፈ ይላሉ ኔግር ይሉታል ይህ ትርጓሜው በጣም ያነሰ ወደ ታች የሆነ ሰው ማለት ነው ።

፯ኛ፡ደግሞም ነጭ ጥቁር የገደለ እንደሁ ዳኛውም ፈራጆቹም ቀኑን ከነገ ከዛሬ ይሉና ያቆዩታል ተራው ሲደርስ እችሎት ይቀርባል ይጠይቁታልም ይመረምሩታልም ይኸንን ከደረጉ በኋላ እንዲህ ይላሉ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ እወህኒ ይቀመጥ ቀጥለው እንዲህ ይላሉ ይፀን ሁለት ዓመት አመሉ የመረ እንደሁ የወህኒውን ስራት የጠበቀ እንደሁ አድርግ ያሉት ያደረገ እንደሁ ከሁለት ዓመት በኋላ ይወጣል ብለው ነገሩን ያደለድሉለታል የዚያ የጥቁር ሰው ደም ግን እንደ ውሻ ደም ፈሶ ይቀራል ።

፰ኛ ፡ ነገር ግን ጥቁር ነጭን የገደለ እንደሁ እንደ ውጋት ያጣድፉታል ወዲያው በቶሎ ብለው ወደችሎት ያቀርቡታል ቀጥለው ወደ ወህኒ ያገቡታል እወህኒ ውስጥ ሁለት ወር ወይም ሶስት ወር ያቆዩታል ከዚህ በኋላ ይሰቅሉታል ።

፱ኛ ፡ በተማሪ ቤት ብዙህ ብልህ የሆኑ የጥቁሮች ልጆች አሉ ከፍ ባለው ተማሪ ቤትም የሚማሩ በኮለጅና በዩኒቬርስቲ የሚማሩ ከነጮች ልጆች ጋራ ሴቶች ልጆችና ወዶንች ልጆች የተማሪ ቤት ሲዘጋ ሥራ ይፈልጋሉ ተማሪ ቤታቸውን ከሣራ እንዲከፍሉ ። ሥራም ባገኙ ጊዜ ሰው ወደ ማያቸው ስፍራ ሥራ ይሰጧቸዋል እድፍ የሆነ ሥራ መስኮት ማጠብ ወይም መሬት ተንበርክኮ በቡርሽ ማጠብ ጥቁሮቹም ሴቶች ልጆች እንዲሁ እንደዚህ ያለውን ሥራ እየሠሩ ይኖራሉ ።

፲ኛ የነጮች ልጆች የሆኑ እንደሁ ብልህም ቢሆኑ ብልህም ባይሆኑ ጥሩን ሥራ ያገኛሉ የአፊስ ሥራ ወይም ዕቃ መሸጥ እንዲሁም ሴቶቹ ልጆች ያማረውን ሥራ ያገኛሉ ።

፲፩ኛ ሥራ በተወደደ ጊዜ የጥቁር ልጆች ሥራ ለማግኘት አይችሉም ከአንድ አንዱም ስፍራ አንድ ጥቁር እስከ ብዙ ዓመት ሥራ ሲሰራ ከኖረበት ስፍራ ሥራ ውድ ሲሆን ያን ጥቁር ያወጡና ለነጭ ሰው ይሰጡታል ይህም እርስ በርሳቸው መተጋገዛቸውን ያሳያል ።

፲፪ኛ እንግዲህ እነኚህ ጥቁሮች ነጻነታቸው ምን አደረገላቸው ባሉበት ከተማ የሚሆነውን ነገር የሚደረገውን ሁናቴ ካላየ እንዲያው በጋዜጣ ላይ ማንበብ ትላንትና ማታ ግሩም የሆነ ንግግር በትልቁ አደራሽ ውስጥ ተደረገ የሚል ወሬ በጋዜጣ ላይ ያያሉ መቼም ጋዜጣው ለጥቁርም ለነጭም ይታተማል በዚህ ላይ ልዩነት የለም ነገር ግን ብዙ ጥቁሮች ገንዘብ ያላቸው አሉ ደስ ሳይላቸው ይኖራሉ ገንዘባቸውን እንኳ ለማጥፋት ቢፈልጉ ወደ ትልቅ ሆቴል አያስገቧቸውም ።

፲፫ኛ ደግሞም በዚህ ላይ እምን ላይ ቆመሽ እግዜርን ታሚያለሽ እንደ ሚሉ ጥቍሮች የውጭ አገር ሰውን ሲጣሉ ከነጮቹ ይብሳሉ ይመስላቸዋል እነሱ ከፍ ያሉ ከውጭ አገር ሰዎች የዛሬን ብተው ያዘርዝረኝ የሚሉ ተረት ባገራችን ሺማግሌዎች ሲተረክ እሰማ ነበር ። እንደዚሁ ጥቍሮች ምንም ቢማሩ ተመልሰው ወደ ኋላ ነው የሚአስቡት አህያ ከመዱ ዘመድ ከዘመዱ እንደ

ሚሉ እነኚህ የተማሩት ጥቍሮች ከምናምንቴው ሰው ጋራ ማህበር ማድረግ ይወዳሉ ደህና ከተማረው ከውጭ አገር ሰው ጋራ የሚያደርጉት ።

፲፬ ኛ ደግሞ ሌላ ልዩነት አለ እጅግ ለሰሚ የሚያስደንቅ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው በጥቍሮች መሐከል ብዙ ዲቃላዎች አሉ ከነጭ የተያበለቁ መልካቸው የነጣ ነው እነኚህ ወደ ትልቁ ቲያትር ቤትና ወደ ትልቁ አዳራሽ እንደ ነጭ ያልፉሉ መቸም እበር ላይ ቆሞ ዘርህ ምንድነው ብሎ የሚጠይቅ የለም መልኩ ከነጣ የትም ስፍራ ለመግባት ይችላል ። ግን ከነጮች ጋራ ማኅበር ለመግባት አይችልም ምክንያቱም ይህ ነው ፥ዘር ይጠየቃል እማህበር ውስጥ ለመግባት ። የተያበለቁበትም በመሐከለኛው አሜሪካ ነው እነኚህ መልካቸው የነጣ ጥቍሮች ወይም ዲቃሎች በጣም የጠቆሩት ይጠላሉ ወደ ሱቅ ይሄዱና በነጮች መደብር የሚያውቁትን ጥቁር ያዩ እንደሆን እንዳላየ አይተው ያልፉታል ።

ምክንያቱም ይህ ነው ነጭ የሚመስለው ዲቃላ ያንን በጣም የጠቆረውን ያነጋገረ እንደሁ ነጮቹ አየው ያነጭ ከነሰ ጥቁር ጋር ይነጋገራል ብለው እንዳይሰድቡት ነው ነጮች ግን ያ ዲቃላ የጥቁር ዘር መሆኑን አያውቁም ። ነጮች ደግሞ እንድ ባህሬ አለባቸው ከጥቁሩ አብልጠው ዲቃላውን በጣም ይጠላሉ ።

፲፭ኛ አንድ የእንግሊዝ ሰው አሜሪካን ለማየት መጣና አገሩን ዞሮ አየና ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ ሀገሩ ሲመለስ እን ዴህ ብሎ በጋዜጣ ላይ ጻፈ የአሜሪካን አገር እጅግ መልክም ነው ነገር ለአሜሪካ ነጮች እጅግ አዝናለሁ አለ በአንድ አገር ከጥቁር ጋር በመኖራቸው ሕይወታቸውን በጣም ደስ ሳይላቸው ይኖራሉ ተሎ ደህና ዋሉ አለ።

ዘውዴ በየነ ።

ስለ ወለጋ ወረዳ አኳሆን ።

ባለፈው ሳምንት የክቡር ደጃዝማች ብሩን ግዛት አኳሆን እንደ ጻፍነው በጎረቤቶቹ ያሉትን አገሮች አስተዳደር እንጽፋ ለን ። የክቡር ደጃዝማች መኰንን ደምሰው ዱሮ ባአገራቸው ሌባ ሰልጥኖ የነበረውን ዛሬ ሌባ ከግዛታቸው ጭራሽ አጥፍተ ዋል። አገሩንም በሌብነት ፈንታ ቡን መትከልና እርሻ በማረስ አሰለጠኑት ፍርዳቸው ትክክል ስለ ሆነ ወታደር ባላገርን አማረ ጋላውን ለማጥቃት አይችልምና ሁሉም በስምም ስራውን ይሰራል ። ደጃዝማችም ቡን ማስተከልና እርሻ ማሳረስ የዘወ ትር ስራቸው ነውና ባላገሩ እሳቸውን እያየ ይበረታል ከዚህም ሌላ ባላገሩ በስራው እንዲበረታ ብለው ቡኑን እርሻውን ሂደው እያዩለት አመስግነው በቸገረው ነገር እርዳታ ይሰጡታል ከደግ ነታቸው የተነሣ ዛሬ ግዛታቸው በብልጥግና ከፍ ከፍ እያለ ይሄዳል ። ከሁሉም ደስ የሚአሰኝ ነገር ለባገላሩ ያወጡለት ደንብ ነው በድሮ ዘመን መልከኛው በጥቂት ትእዛዝ ምክንያት እየዞረ በገባሩ ቤት እያደረ በመስተንግዶ ሲአስቸግረው አድሮ በነጋው የጠም አዳሬ አምጣ እያለ ሲአስቸግረው ይኖር የነበረውን ዛሬ አንድም መልከኛ ትእዛዝም ቢኖር ሲአዝ ውሎቱ ቤት ገብቶ ያድራል እንጂ በገባር ቤት እንዳያድር በስራት ከልክለዋል እንደ ክቡር ደጃዝማች መኰንን ያለ ገጋር ቢበዛ ላገራችን ሰላም ይሆናል በማለት ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች መግለጼ ነው እንጂ የከንቱ ምስጋና አይምሰላችሁ ይኸን የሚጠራጠር እን ዳለ እንደኔ እየዞረ ሊአይ ያስፈልገዋል ።

፪ ኛ ደግሞ የክቡር ደጃዝማች ሃብተ ማርያም ግዛት መል ክም ነው ። ነገር ግን በዚያ አገር ያየሁት ሁለት ነገር ያሳዝነኛል። ፩ኛ በዚያ አገር ዝሆን ወይም ጎሽ ገሎ መጨፈር እንደ ትልቅ ማዕርግ ይቆጠራልና በዚህ የተነሣ በየ ዓመቱ በረሀ እየወረዱ የሚአልቁት ሰዎች ብዙዎች ናቸው ። አሁን በቅርቡ በዚያ ከተማ ሳልፍ ያየሁት ነገር ይገርመኛል በአንድ ስፍራ ሴቶችና ልጃገ ረዶች ፅዩቀፉ ከልክ ያለፉ ሠራዊቶች ሲጨፍሩና ሲንጫጩ አይቼ ነገሩን ብጠይቅ አንድ ሰው ጎሽ ገሎ ነው ቢሉኝ ለዚህ ለማ ይረባ ነገር ይኸን ያህል ሠራዊት በመሰብሰቡና ያገር እስተ ዛሬ ጎሽ ወይም ዝሆን መግደል ያልረባ ስራ መሆኑን ሳይረዳው በመ ቅረቱ አዝኜ አልፌ ሄድኩኝ ። ፪ ኛ በዚያ አገር ሌባ አለ ልክ ሰልጥኖአል የሰውን በቅሎ ወይም በሬ እየሰረቀ ተመልሶ ባለቤቱን በቅሎህን አሳይሃለሁ ብሎ ለከብቱን አምሎ መልሶ በኩል ዋጋ ይሸጥለታል በለ ከብቱም አዲስ ከብት በምሉ ዋጋ ከመግዛት ለዳኛ ጨኸ በአፈርሳታ ከመልፋት ይሻለኛል ሲል የገዛ ከብቱን ይገዛል ይኸንንም ነገር አንድ የወሎ ነጋዴ ቡን ለመግዛት በዚያ ከተማ ሰንብቶ ወደ አገሩ ሲመለስ እኔ ወደ አዲ ስ አበባ ስወጣ አብረን ስንጓዝ አጫወተኝና አራት አጋሰሶች ጠፍተውበት ዱጋ ከሚባለው አገር በ ፹ ብር እንደ ገዛቸው ነገረኝ ክቡር ደጃዝማች ሃብተ ማርያም ሁለቱን ክፉ ልማዶች በቶሎ ከአገራቸው እንዲአጠፉት በተስፋ እንጠብቃለን

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።

ታሪክ ።

አንድ ጊዜ ሁለት የእንግሊዝ መኳንንት በፈረንሳይ አገር ላቤል ወደሚባለው ታልቅ ከተማ ነፋስ ለመለወጥ ሄዱ ይባ ላል ከነዚህም መኳንንት አንደኛው የፈረንሳዊ ቋንቋ አያውቅ ም ነበርና በማናቸውም ነገር ያለ ቋንቋ እንዳይሳካለት አስቦ እጅግ ያለ መጠን ተስፋ ቆረጠ ሁለተኛው ግን የጀርመን መምሕር በትምሕርት ቤት ያስጠናውን የፈረንሳይ ቃላት ተማ ምኖ በዲክሺዮናሬ (መዝገበ ቃላት) እርዳታ እራሱን እንዲች ልተስፋ አደረገ እነዚህም መኳንንት ከግራ እንዳያበዙ ስለ ተጠነቀቁ ሁለት ሰው የሚያስተኛ አልጋ ያለበት አንድ ክፍል ቤት ተከራይተው በሆቴል ተቀመጡ ። ጊዜያቱም የብርድ ወራ ት ነበረና ሙቀት ስለ መፈለግ በየክፍሉ እሳት ይነድ ነበር ፤

ሁለቱም የእንግሊዝ መኳንንት እንዳገሩ ልማድ ወደ ማታ የጤና ነፋስ ለመለወጥ ወደ ወንዝ ዳር ለመሄድ ተዘጋጁ ነገር ግን አንደኛው ደክሞኛል ብሎ ለመቅረት አሰበና ብቻውን እንዳይሆን ባልንጀራው የሆቴሉን አሽከር ጠርቶ እሳቱን ጠብ ቅ እንዲለው ባልንጀራውን ለመነው ። ያም ባልንጀራው ወደ ደጅ ወጥቶ ዲክሺነሬውን ከኪሱ አወጣና እየተመለከተ ከዚህ በታች የተጻፉትን ቃላት መተርጐም ጀመረ ።

ዶንት ሌት ማይፋ የር እሳቴን እንዳትለቅ ይኸን ከተ ረጎመ በኋላ አሽከሩን ጠርቶ ነ ሌሴ ፓ ሞን ፋ አለው ፋ ማለት

እብድ ነው ትርጓሜው ፈ ግን አሳት ማለት ነው አሽ ከሩም በፍጥነት ትእዛዙን ሰምቶ እየተደነቀ ለሆቴሉ አዛዥ ከነዚህ ከሁለቱ መኳንንት አንዱ እብድ ነው መሰለኝ ባልንጀ ራው ወደ ሽርሽር ሲሄድ እኔን ጠርቶ እብዴን ጠብቅ አለኝ ብሎ ነገረው ፤ የሆቴሉም አዛዥ እብድ በሆቴል ሲገባ የሚ ያስፈራ መሆኑን አውቆ ለዕቃውም ፍራቻ ለራሱም መዳኛ ሲል እየሮጠ ወደ ፎቅ ወጣና ደጁን ወደ ኋላ ቆለፈበት ያም ሰው አትቆልፍ እያለ በእንግሊዝ ይለፈልፍ ጀመረ ነገር ግን አፉን ባለማወቃቸው ከእብድ ቆጥረውት ዕውነትም እብዷል እንዴት እናድርግ እያሉ መላ ያወጡ ይጥሉ ጀመር በመጨረሻ ግን ያ መኰንን ተቆጣና ሥራው ደጁን ለመክፈት በጁ መምታ ትና ዕቃውን አንዱን ካንዱ ጋራ ማጋጨት መስበር ሆነ ይኸን በሰሙ ጊዜ በመጨነቅ ወደ ዘበኛ አለቃ ነገሩን አመልክተው ደጁን አስከፍተው እጁን አሲዘውት ከሄዱ በኋላ ጥቂት ቆይቶ ባልንጀራው ደረሰ ፡፡ የሆቴሉም አዛዥ በፈረንሳዊ የወንድመን ሆኔታ ቢነግረው አልሰማው ስላለ እጁን ጎትቶ ወደ ታሠረበት ማረፊያ ቤት ወስዶ አሳየው ። ከባልንጀራውም ጠይቆ የሆነውን ነገር ከተረዳ በኋላ ዲክሺኦሪውን ተኪሱ አውጥቶ ቃላት እያየ ዕብድ አይደለም አሳስቼ ነው ፍቱልኝ ብሎ ለመናቸው ። እን ርሱም ቃል የስህተት መሆኑን ተረድተው ፈትተው ሰደዱት ይባ ላል ። እንባቢ ሆይ ይህ ሁሉ ቋንቋ ካለመማር የተነሳ ነውና ቋን ቋን ለመማር አትቦዝን ።

ስመኝ ።

ስለ ሙሴ ሐና ቤይ ሳሌብ ዕረፍት ።

የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ዲሬክተር የነበሩ ሙሴ ሐና ቤይ ሳሌብ በአርባ አምስት ዘመናቸው ሰኔ ፯ ቀን በሰ ባት ሰዓት ተኩል ዓረፉ ።

በሰኔ ፯ ቀን በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ ። በቀብሩ ጊዜም ልዑል የኢ መ አ ወ ተፈሪ መኰንንና ብዙ መኳንንቶች የውጭ አገር ሰዎችም ነበሩ ። የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ተማሪዎችም የሐዘን ምልክት አድርገው ወደ ልቅሶ መጥተው ነበር ።

ብርሃናንና ሰላም ለሙሴ ሐና ባለቤትና ለልጆቻቸው ለዘመዶቻቸው ሁሉም እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

ስለ መረዳዳት ።

ይድረስ ለከበራችሁና ለተመሰገናችሁ ክቡራን የኢትዮጵያ ልጆች ብርሃንና ሰላም ከሚባል ከልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ በፍቅርና በንድነት ምስ ተጠርተን በትልቁ ግብዥ ከተዋወቅን ጀምሮ እስካሁን ድረስ ለጤናችሁ እንደምን ናችሁ እኔ ግን አለ ናፍቆታችሁ በቀር እግዚአብሔር ይመስገን ደኅናነኝ ።

አሁን ግን ጌቶቸ ሆይ ሁላችሁ እንደምታውቁ ብርሃንና ሰላም ከሚባል ከልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ በመዠመሪያ ዓመ ትና በሁለተኛ ዓመት ሐሙስ ሐሙስ በሁለት ሰዓት እየተጠ ራን የምንበላው የነበረ የልብ ዝግንና የራስ አልጫ ደሞ የ ምንጠጣው የነበረ የኃይል ወተት እንኳንስ ለበላውና ላሸተተው ሁሉ ያጠግብ ነበር አሁን ግን በሶስተኛ ዓመት የልዑል ግቢ እንደ ቀድሞ ሳለ ምግብ በማነሱ ወጥ በመለስለሱ መጠጥ በመቀ ነሱ ሰው እንደ ልማድ ለለመደ ሰው ጨንቆታል ነገር ግን ለኔ እንደሚመስለኝ ብርሃንና ሰላም የሚባል የልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ ከቀድሞ ዛሬ ይሰፋል ወጥ ቤቶቹም ሁሉ ከቀድሞ ዛሬ ይሠራሉ እንጀራ ጋጋሪዎቹም ከቀድሞ ዛሬ ያፈጥናሉ እላለሁ ስለሆነ ግን የግቢ ሰው ምንም ሥራውን ቢያፈጥን ያገር ቤት ሰው እንደያይነቱ በበቅሎ ጭኖ እከተማ ካላገባ ምግቡ እያነሰ ወጡ እየለሰለሰ መጠጡ እየተቀነሰ እንደሚሄድ ጥርጥር የለበትም ። ነገር ግን አንድ ብልህ ጠያቂ እንዲህማ ከሆነ አንድ ያገር ቤት ሰው አንተ አይደለህም ምነው በያይ ነቱ ጭነህ አታገባ ብሎ የጠየቀኝ እንደሆነ ዝም ከማለት በቀ በር ለተክክል ሀሳቡ መልስ አላገኝበትም ። አሁን ግን ብርሃንና ሰላም የምንጽፍ ሁላችን ፍሬውን ከጐተራ ልብ ኢያቀዳን ከል ዑል ግቢ እናቀና እንጂ የቤቱ ሠራተኞች ብቻ አስበው ይም ሉት ማለት አያስፈልገንም ። አሁን ግን ስለዚህ ሁሉ መሪ ነትንና ተፈሪነትን ለልዑል አልጋ ወራሻችን ስለ ሆነ በእው ቀት ደረጃ ወጥተን ማጨብጨብ ይገባናል ። አሜን ይሁን

ተማሩ ረምሃ ዓድዋ ።

ደሴ አውራጃ ወሎ የትምሕርት ቤት ማቆም ማስፈለጉን ማስታወቅ ።

ወሎ ከግራኝ አንሥቶ እስከ አፄ ዮሐንስ መንግሥት አብ ያተ ክርስቲያኑ ጠፍቶ በጨለማ ይኖር ነበር አፄ ዮሐንስ ግን ከጨለማ ወደ ብርሃን ማዝለቅ ጀምረውት ነበረ ዛሬ ብርሃን በተ ቀረው አገር በኢትዮጵያ ጨርሶ ሲበራ የወሎ ሕዝብ አለመ ማሩና አለመሰልጠኑ ከሥልጣኔ መንገድ እርቆ በመኖሩ እጅግ ያጸጸታል ።

፩ኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ሰዎች እንዴት ሰሙ በልክ
ከግራኝ እስካሁን ዓለም ሲታወክ
ምሉ ድንቁርና በልብ ሲሰብክ
ወንድም በወንድሙ በቅናት ማወክ
በጨለማ መሄድ በዱር መደበክ
መሥረቅን መግደልን አድርገው አምላክ
ሐበሻ በድርቡሽ እጅ ሊማረክ
ቤዛ ለዓለም ሆነ ዮሐንስ ቡሩክ
የዓለም መሠረቱ ወጥቶ ምኒልክ
ሁሉንም ባባቱ አስኬደው በልክ
በመንግሥቱ ሁሉ አንድ ሰው ሳያውክ

ለምኒልክ ንጉሥ ሲረዳው አምላክ
የኢትዮጵያ ብርሃን ወጥቶ እልትሪክ
ተፈሪ ቄርሎስ የዓለም ምስማክ
የኢትዮጵያን ልጆች ወደውጭ መላክ
ይምላ ሐሳብዎ ልብዎ አይታወክ
ብርሃን እንድናገኝ በሰአቱ ልክ
ጀመረልን ሰላም ቢረዳን አምላክ
ብርሃንና ሰላም አውጥቶ መላላክ ።
ድንቁርና ገብቶ ልብ እንዳያውክ ።
ብልሁ ሰሎሞን ተአምላክ ቢላላክ ፤
እውቀትና ሐብትን ሰጠው አለልክ ፤

፪ተኛ ፤

ስለ ኢትዮጵያ አምላክ እረድቶዎ ።
ብርሃንና ሰላም ቢገባ አገርዎ ።
ትንሹም ትልቁም ሕዝቡም መረቀዎ ፤
ደንቆሮውን ሁሉ ስለ ማንሳትዎ ።
የሰሎሞን እውቀት ገብቶ እልቡናዎ ።
ተፈሪ ቄርሎስ ይምላእ ሐሳብዎ ፤
የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉም ተጉልዎ ።
እውቀት ለመፈለግ ተሯሯጡልዎ ፤
አገሩን ለማጽናት ተነሣ ሕዝብዎ ፤
ብርሃንና ሰላም ይብዛ በገርዎ ፤
ከግራኝ እስካሁን ጠፍቶ ሀገርዎ ።
በጨለማ ሲኖር ተዘግቶ ሰዎዎ ፤
ብርሃንና ሰላም ከፈተልዎ ፤
ተፈሪ ጌታዬ ደስ ይበልዎ ፤
የሐበሻ ልጆች ሰለጠኑልዎ ፤
አውሮፓዊ ሁሉ አደነቀልዎ ።
ከኢትዮጵያ ሁሉ ወሎ ቀርቶልዎ ፤
ብርሃንና ሰላም አላገኘልዎ ፤
ይኖራል በጥንቱ ተዘግቶልዎ ፤
እንዴት እንዴት ወሎ ትደንቁር ሕዝብዎ ፤
ይከፈት ትምሕርት ቤት እንመርቀዎ ፤
ሺማግሌዎቹም እንዲአስቡልዎ ።
ወበከመ ይምሕር አብ ውሉዶ እንዳለልዎ ፤
ብርሃን ይገለጥ ወሎ ይሰልጥንልዎ ፤
ወሎ ለምለሟ አገር እንድትቀናልዎ ።
ያስቧት ጌታዬ በብሩህ ልብዎ ፤
እጅግ ጥቅም አላት እምትረዳዎ ፤
በውል ሲመሰከር ከእግዚአብሔር ሀብትዎ ፤
በትክክል አርጎ አምላክ ቢቀባዎ ፤
አጋሚዶ ሁሉ ከዓለም ጠፋልዎ ፤

፫ተኛ ።

ትንሽ ወንድማችሁ ስሙኝ ልንገራችሁ ፤
በደካማ እውቀቴ እማስታውቃችሁ ።
ብርሃንና ሰላም ይፈልግ ልባችሁ ፤
ተፋጠኑ ለእውቀት እርዱ ላገራችሁ ።
ሁሉ አደነቀ ስለ ትጋታችሁ ።
በጣም ተፋቀሩ ባንድ ልብ ሆናችሁ ።
አይቸግርም እውቀት ተተዋደዳችሁ ።
ለመንሥት ከሆነ ጥኑ ሐሳባችሁ ።
ቁማችሁ በውል ቃል በቃል ኪዳናችሁ ።
ለኢትዮጵያ አስቡ እንዲሆንላችሁ ።
ብርሃንና ሰላም ወጥቶ ባገራችሁ ።
አስቡ ለአበሻ ጠቅል ሳለላችሁ ።

ገብረ ሕይወት መሸሻ ዘብሔረ ተሁለ ደሬ ።

ከዚህ የቀረው በሚከተለው ቁጥር ይታተማል ።

የውጭ አገር ወሬ

ስለ ተማሪ ቤቶች እርዳታ በአሜሪካ

ጠቀሜታ ስላለው ሥራ እርዳታ ፵፪ ሚሊዮን ፩፻፶፰ ሺ ፰፫ ወይም ፵፪ ሚሊዮን ፩፻፷፰ ሺ ፯፻ የሚያህል የአሜሪካን ብር ለተማሪ ቤቶች ማቆሚያ ያስፈልጋል ሲል ፤ ኤድዋርድ ኤፍ ሐል የተባለ የአሜሪካን አማካሪ የተናገረውን ቃል እንደሚከተለው ነው ።

በአሜሪካን አገር አያል ተማሪ ቤቶች ለመሥራት ፕሮግራሙ ተዘጋጅቷልና ከመንግሥት እርዳታ ጋራ ይህን የበጎ ሥራ ለመሥራት ኃሳባችን ቢከናወን ፤ እስከ ሁለተኛው ትውልድ ድረስ ልጆቻችን ተማሪ ቤቶች ለማቆም ሳይደክሙ ከዚሁ አሁን ከሚሠሩት ቤቶች ተርፎ ለእብዶችና ለባለጤኖች ሆፒታል ይሆናል ። የአሜሪካን መንግሥት የወር ገቢ ገንዘብ ከልዩ ልዩ የሥራ ክንፍ የሚቀበለው የመኪና ግብር ብቻ የወር ገቢ ፬፻፰ ፭ ሺ የሜሪካን ብር ነው ። ከዚህም ቀደም እንዳመለከትነው በኒዮ ሐብንና በቦስቶን ያሉ ስለ ስልጣኔ እድገት የቆሙ ማኅበሮች በዚህ ነገር ሳይረዱን አይቀሩም ። የአሜሪካን መንግሥት የወር ገቢ ገንዘብ ከግብርና ይህን ከመሳሰለ በቅርብ ግምት በጠቅላላው ፴፩ ሚሊዮን ፱ሺ ፫፻ ብር እንዲገኝ አይጠረጠርም

ያገር ደምብ አፍርሳ አረቄ ስለ ጠጣች ሴት በአሜሪካ ።

በአሜሪካን ከተማ በዋናው ፍርድ ቤት አንዲት ሴት ኢባ ኰሎስኪ የተባለች ደምብ አፍርሳ አረቄ ስትጠጣ ተይዛ በዳኛ ፊት ቀርባ ስለ መቀጮ ፻፶ የአሜሪካን ብር ከፍላ የ፴ ቀን እስራት ተፈረደባት ።

ኤስፔራንቱ

በዱጎስላብ ስለ ምድር ባቡር ሥራ የኤስፔራንቱ ማግባት በ፳፩ ማረስ ፲፱፻፳፯ ታላቅ ትእዛዝ (ጀ ደ ነምራ ፯ ሺ ፸፩ ፱፻ ፳፯) የሴርብያ መንግሥት የንግድ ሚኒስትር ክርአትና ስላብ ለኤስፔራንቱ እንደ ረጂ ቋንቋ ለጽሕፈት ብሎ ቁርጥ ስም ሰጠ ። ማስታወቂያውም ለመንገደኞች በድጎስላብ በመንግሥቶች ባጎን ውስጥ ደረሰ ።

ኤስፔራንቱ ለሕዝብ ሁሉ እንዲሆን ተብሎ ታስቦ የወጣ ቋንቋ ነው ። በዚህም ቋንቋ ብዙ መጻሕፍት ተጽፈዋል ።

የእጅ ዝኒት ሰትዓ



በአውሮጳ አገር አሚሠራው ስዓት ሁሉ መብለጡ የተመ ሠከረለት ዝኒት የሚባል ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፰ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር ተሩብ
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር ሩብ ምላሽ
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፱ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፫ ብር ተሩብ
አቡጀዲ መነጸር	፩ ኮረጃ	፻፴፮ ብር ተኩሉ
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፻፴፮ ብር ።
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፳፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፲ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፰ ብር
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፵፬ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴ ብር ። ፴
ቻይ	፩ ነጥር	፫ ሩብ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፳
በአንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ ፱
ባአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፲፰ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፩ ብር

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠንቀቀዎታል ።

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድሬስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቀባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሴላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ ቡተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፌታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

Berliet



ቤርሊዮ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዮ አቶሞ ቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

ARMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠበበ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶክለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የኦዶክለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተከሻ ብሩሽቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አኳን ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፳፭
3 me ANNÉE № 25

ሐሙስ ሰኔ ፲፮ ቀን ፤ ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 23 JUIN 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በአገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ለመንግሥትና ለሕዝብ ጥቅም ።

ሌሎች መንግሥቶች እንደሚያደርጉት እንደ ተገባ የኢትዮጵያ መንግሥት እስከ ዛሬ ለራሱና ላገሩ ጥቅም መኖፖል አድርጎ የሚነግድበት በገሩ በጣም የሚፈለግ ዕቃ የለም ። ይልቁንም የሚጠቅሙት እየመሰለው ለራሱ መኖፖል ማድረግ የሚገባውን ዕቃዎች ለውጭ አገር ሰዎች በመኖፖል የሰጣቸው ብዙ ነገሮች አሉ ። እንደ ባንክ ፤ እንደ ትንባሆ ፤ ምን ይሆናል ፤ አሁን ካለፈ ወዲያ የራሱንና የሕዝቡን ጉዳት ሳይረዳው የቀረ አይመስለንምና ለወደ ፊቱ በመኖፖል ውል የንግድ ሥራ ሆነ ሌላ እንዳይሰጥ እንመኛለን ። ሌላው ይቅርና አንድ ያገሩ አመለኛ ድኃ በገዛ ምድሩ ላይ ያለ ኪምርኰፍ ፈቃድ የሚያስፈልገውን ትንባሆ ሊተክል ነፃነት የለውም ፤ አይችልም ። ለመሸጥም ገበያ ቢያወጣ የያዘውን ተነጥቆ መቀጫ መክፈል አለበት ።

ያለፈው አለፈ ፤ ለወደ ፊቱ እንደዚህ ያለ የሕዝቡን ነፃነት የሚቃወም ውል መንግሥታችን በይዋዋል መልካም ነው ። ላገር መጥቀሚያና ለመንግሥታችን ማክበሪያ እንዲሆኑ የሚከተሉትን ዕቃዎች በእሱው እጅ መኖፖል ቢያደርግ አያሌ ጥቅም ለሕዝቡና ላገሩ ይከማቻል ። እነዚህ ብዙ ትርፍ ለመንግሥታችን ፤ አያሌ ጥቅም ለሕዝባችን እየሰጡ አገራችንን የሚያስከብሩ ሆነው የታዩኝ ዕቃዎች አቡጀዴ ፤ ፈትል ፤ ድርና ማግ አሸቦ ፤ ሳሙናና ሻማ ናቸው ። እራሴን ላክብር ሕዝቤን ልጥቀም ቢልና ትርፉ እንዳያንስበት ቢያስብ ጥጡ በገሩ ተርፏልና የሚበቁ ያቡጀዲድና የፈትል ፋብሪካዎች ማቆም ያስፈልገዋል ።

አሸቦን ግን ከጅቡቲ ባሕር እያስጣራ ማስመጣት የሚያቅተው አይደለም ። ለሳሙናና ሻማም የሚያልቀው እንስሳ ልክ የለውምና የሚያስፈልጉትን መኪናዎች ያስተክል ።

እነዚህን አራት ዕቃዎች እንደሚከተለው አስደርጎ እንደሚበቁን ከገራችን ቢያሠራቸውና በየከተማው ነጋድራስ እጅ እያከፋለ በደንብ ቢያሸጣቸው የራሱ ጥቅም ልክ የሌለው ሆኖ ለሕዝቡ ብዙኅ ፋይዳ በፈየደለት ነበር ። የኔ አገር መኳንንትና ሕዝቦች ዳተኝነትና ቀጠሮ ማብዛት ካቶ ንፍገት ጋር ከዘራችን የወረዱብን ሆነው እንደሁ እንጃ? የማይለቁን መሆናቸውን ብርሃንና ሰላም ተረድቶ በብዙ ምሳሌና ምክር ይዋጋቸዋል ። በስንተኛው ቁጥር እንደሁ አላስታውሰውም እንጂ ። ሰነፎች ለነገ ከሚሉት ምግብ ለነገ የሚሉትን ሥራና ደንብ ያበዛሉ ሲል አንብቤ ነበር ።

እእምሮው ያነሰ መኰንን በግፍ ብዙ ይበድላል ።
ንፍገትን ግን የሚጠላ ብዙ ዘመን ይኖራል ።
በለስን የሚጠብቅ ፍሬውን ይበላል ።
ጌታውን የጠበቀ ክብር ያገኛል ።
ከብቱን በብልሀት የሚበትን ሰው አለ ፤
አብዝቶ ይጨመርለታል ፤
ያለ ጥቅም የሚነፍግ ሰው አለ ፤
ይደኸያልም ፤
እያለ ሰሎሞንም በምሳሌው ያስረዳናል ፤

ጌታም ስጡ እንዲሰጣችሁ ብሎን ነበር ። ለጊዜው ገንዘብ ማውጣታችሁ ብቻ ነውና የሚታያችሁ እስቲ ከበታቻችሁ ያለውን ገበሬ ዘር አውጥቶ አበታተን አስቡት? ፤ እንደዚህ ገበሬ ጥቅሙ ለናንት ለመኳንንቶች የሚበዛ መሆኑን የምትረዱ እንኳ ቢሆን በፍጥነት እነዚህን ፋብሪካዎች እንድታቆሙልን የታወቀ ነውና እስከዚያ ድረስ መንግሥታችን በተለየ ከውጪ አገር እያስገዛ ቢያስመጣ ብዙ ጥቅም እንዳለው የሚያስተውል ሰው ይረዳዋል ። በዚሁም ጊዜያት መካከል የውጭ አገር ነጋዴዎች ሆኑ ያገራችን እነሱውም የሉ ። አቡጀዴ ፤ ፈትል ፤ ሳሙናና ሻማ ከእ

ንግዴህ ወዲያ ወዳገራችን ለንግድ እንዳታስመጡ ከሁን በፊት ያመጣችሁትንም ሸጣችሁ ጨርሱ ሲል ቀኑን ለክቶ ማወጅ ያስፈልገዋል ። እሱ ግን ያዋጁ ቀን ሳይደርስ ቀደም ብሎ እነ ዚህን ሸቀጦች አስመጥቶ በየከተማው እንደሚበቃው ማደላ ደል ይገባዋል ። መቼም በታወቀው ዳተኝነት ቀኑ ገና ነው ሲል ማስመጣቱን ቢያዘገይ ወዮልን ፡፡ የገበያ ነገር ሊረገዋ አይቻ ልምና፤ሸቃጮቹ ቀደም ብለው ይጨርሱና እስር የሚተከው ሸቀጥ ይታጣና ሕዝቡ ይቸገራል ፤ ይጨነቃል ። አገራችን እን ድትጠቀም መንግሥታችን እንዲከብር ያልነው ነገር ወደ ችግ ርና ጭንቅ ሲዞር እጅግ የሚያሳዝን ይሆንብናል።ሕዝቡ የሚ ቸገርና የሚጨነቅ መንግሥት የነዚህ ሕዝቦች መንግሥት ነኝ ማለት አይገባውም። መንግሥት ማለት ለሕዝቡ ጥቅምና ለራሱ ብርታት የሚያስብ ነው ። ሕዝቡ የሚጠቀም ከሆነ መንግሥቱ ከበረ በረታ ማለት ነው ። የሕዝብ ጥቅም ለመንግሥቱ ብር ታት እንደ ሆነ ሊቆች ይመሰክራሉ ። ደንቆሮዎችም ያያሉ ። ሕዝቡ የከበረ መንግሥት ዓለሙን ሲያንቀጠቅጠው እኛም እና ያለንና እበካችሁ ለመረዳዳት አያውከን ። ነጋድራስ ገብረ ሕይ ወትም ያንድ መንግሥት ሕዝብ ቢደኸይ (ቢቸገር) የዚያኛው ስር መነቃነቁ ነው ሲል መክሮን ሄዷል ። እንግዴህ መንግሥት ማለት መኳንንቶች ሕዝባችሁን ለመጥቀም ተነሡና ብዙን ብልሐት ከማያስፈልጉ ዕቃዎች የተነሣ እንኳ ለባዕዶች የም ናፈሰውን ገንዘብና ጉልበት እስቲ አስቀሩልን ።

እኔ ወደ ውጪ አገር ከወጣሁ ብዙ ጊዜ ሆኖኛልና በኢ ትዮጵያ ስንት ኩረጃ አቡጀዴ ፤ ስንት ወረቀት ፈትል ፤ ስንት ጆንያ አሸቦ ፤ ስንት ደርዘን ሳሙናና ሻማ ባመት ባመቱ ከውጭ እንዲመጣና ስንት ገንዘባችንና ጉልበታችን በነዚህ እንኳ እን ዲጠፋ ገቢውንና ወጭውን ብር በልክ ለማስረዳት ስለማይቻ ለኝ የብርሃንና ሰላም ወዳጅ የሆነ የጉምሩክ ሠራተኛ እንደሚ ከተሉት ምሳሌዎች ሁሉን ጠንቅቆ ቢያስታውቀን እራስና እን ጉል ጆሮና ልብ ያሉን ሰዎች በነዚህ እንኳ ያለብንን ጉዳት ሳንረዳው እንቀርም ። እስከዚያውም ድረስ በራስ ግምት እሳ ንሰን ያሰብነውን እንኳ ብንመለከት ስንት እንደ ተጐዳን እንደ ምንጐዳ ባጭሩ ልንረዳው እንችላለን ።

ስለ አቡጀዴ ።

ያቡጀዴን ልብስ ለመሥራት የሚያስፈልግ ዋናው ነገር ጥጥ እንደ ሆነ ማንም ያውቀዋል ። ጥጡን ኢትዮጵያ እንደ ፈለግነው ያህል እንድትሰጥ እንኳን ለእኛና በሩቅ ላሉ ወለል ብሎ ይታ ያል ። ጥጡ ባገራችን እያለ ምነው መንግሥታችን ያቡጀዴን መኪና አስመጥቶ ጥጡ በየሞላበት አገራችን ክፍል ዋና ከተ ሞች ለማቆም ምን ይቸግረዋል ። የሥራ ብዛትና ለየራሳቸው ጥቅም እንጂ ላገራቸው ጥቅም የሚያስታውሱት አማካሪዎች ቸልተኝነት የተነሣ ይመስለኛል እንጂ መንግሥታቸውን የሚያ ቸግረው ቢሆን ብልሐት በፈለጉበት ነበር ።

አሁንም ቢሆን እነዚህን መኪናዎች አስመጥቶ በመነፓል ሊነግድበት አቡጀዴን ቢያሰራ ብዙ ጥቅምና ትርፍ እንዲያገኝ ከኛ ይበልጥ ለሱ የሚታየው ነው ። ባእድ ነጋዴ ከልክ ያለፈ ዋጋውን እየቆለለ ተቸጋሪ ድኃውን ከሚያስጨንቀው ባዳናቸው ነበር ። ይኸ ልክ የሌለው ትርፍ በልክ ሆኖ እመንግሥታችን ጓዳ ቢገባ ብዙ ጥቅም ለኛው በተገኘበት ወደ ውጪ አገር ከሚሄድ ለመንግሥቱ ቢገባለት ተመልሶ ለሕዝቡ የሚረዳ መሆኑን አገሩ ባልሳተውም ነበር ።

ስለ አሸቦ ።

ላገሬ የሚያስፈልጋትን ያህል አሸቦ ኢያስጣራሁ ለመው ሰድ አስቤአለሁና ጥቂት የማጣሪያ ቦታ ስጠኝ ሲል መንግሥ ታችን የፈረንሣዊን መንግሥት ቢለምነው ጥቂት ቦታና የባሕ ሩን ውሐ የሚነፍገው አይሆንም ። የማይፈቅድለት ቢሆን እንኳ በታውን ተከራይቶ ኢያስጣራ ቢያስመጣ ብዙ ጥቅም እንድናገኝ ሞኝ እንኳ አይስተውም ።

በፍቅር ወይም በኪራይ አስፈቅዶ የሚበቁ ሰራተኞችና የማጣሪያ መኪናዎች አሰናድቶ የሚያስፈልገንን ያህል ቢያስመ ጣ መጀመሪያ መንግሥት ብዙ ትርፍ በገኘ ። ሁለተኛ ሕዝቡ እጅግ በተጠቀመ መንግሥት ማለት የብዙ ልጆች አባት ማ ለት እንደሁ መረዳቱን (ማወቁን) በገለጸ ነበር ። የፈረንሣዊ መንግሥት በቸሮታ ሆነ በኪራይ ቦታውንና ባሕሩን የማይፈ ቅድለት ቢሆን ግን የተጣራውን አሸቦ በቀላል ዋጋ እጅቡቲ ኢያስገዛ ወደየከተማው አስመጥቶ በየነጋድራሱ እጅ በቀላል ዋጋ እንዲሸጥ እንዳገሩ ቅርበትና እንደ መንገዱ አኳኋን የመ ሸጫውን ደንብ ጭምር ቢሰጣቸው መንግሥት ብዙ ጥቅም አግኝቶ ለሕዝቡም አሁን ከሚገዛበት ዋጋ ብዙ ባነሰለት ነበ ር ። የሚቸረችሩም ኢትዮጵያዊ ከውጪ አገር ነጋዴ በከ ባድ ዋጋ ከመግዛት ከየነጋድራሱ በቀላል ዋጋ ጆንያውን ኢየ ገዛ የተገባ ትርፉን በገኘበት ። ባእድ ጥቅሙን ብቻ እያየ ያ ለልክ የሚያስወጣውን የኢትዮጵያ ገንዘብ ለየሌላው ጉዳይ በሆ ነላት ነበር ።

በዚህ መነፓል አሻሻጭ ከሸቦ ከሚያገኘው ትርፍ ላይ የውጪ አገር ነጋዴዎች የሚያወጡለትን የቀረጥና የኩቴ ገ ንዘቡን አንሥቶ የሚቀረውን ትርፍ በየራስ ከተማው አሸቦ ው በሚሸጥበት የሆፒታል ማሰሪያና የድውዮች ወንድሞቻች ን መርጃ ቢያስደርገው የበቃ ገንዘብ እንኳ ባይገኝ ብዙ የሚ ረዳ በተጠራቀመ ነበር ።

ስለ ፈትል ሳሙናና ሻማ ።

መንግሥት ማለት ያገሪቱና የሕዝቡ ሁሉ አሳዳሪ አባት እንደሁ ሁላችን (እናውቀ) እናውቃለንም ። እንግዲያስ መንግ ሥት የብዙህ ሺ ልጆች አባት ማለት ነዋ ፤ አገር ማለትም የነዚህ ልጆች (ሕዝቦች) ሁሉ መፈጠሪያና መኖሪያ እንደ ሆነች የሚስተው ሰው የለም እንግዲያውስ አገር ማለት በቁሙ ሆነ በሙቱ ሕዝቡን ታቅፋ ኢየመገበች የምታኖር እንጀት (ማሕ ጸን) ነቻ ።

አባት ጥሮ ግሮ ልጆቹን እንደሚያሳድግ መልካምም መ ንግሥት ሕዝቡን ከመከራ ለመጠበቅና ከችግር ለማዳን ይለፋ ል ይጥርማል እናት በቀይ ደሟ አጽንታ በነጩ አበርትታ ል ጆቿን እንደምታሳድግ አገርም ያለመሰልቸት ፍሬዋን ነፋሷን ጮማዋን ኢየመገበችን በብዙ አይነት ደሟ ኢያረካችን በቁማ ችን ሆነ በሙታችን ታቅፋ ታኖረናለች ።

አሁንም ቢሆን ልጆች ላባቶቻችን የምንገባውን ውለታ ያህል ለመንግሥታችንም መክፈል በውድ ባይሆን በግድ የተገባን ነው (ነበር) እንግዲህ ያገርንና የእምዬን አንድነት ከተረዳን ለእናታችን የምንገባውን ላገራችን መገባት እንዳለብን እንረዳ ፣ ይልቁንም ይህቺኛዋ የዘለዓለም ማሕጸናችን ነችና ከዚያኛዋ ይበልጥ እንገባታለን እናቱን መውደድ የማያውቅ አገሩን መውደድ አይችልም ። አገሩን የሚወድ እናቱን አፍቃሪ ነው አባቱን የማይወድ መንግሥቱን ይጠላል ። መንግሥቱን የሚከድ ያባቱ ገዳይ ነው ፡ ነፍሱን የማይወድ ከፈጣሪው ይርቃል ሥጋውን ብቻ የሚወድ ከሁሉ (ከሰው ከእግዜር) ርቆ ይወድቃል ።

መንግሥት ማለት የብዙ ሺህ ልጆች አባት መሆኑን ተረድተናል እናውቅማለንና እስቲ ይኽ አባት ማን እንደሆን እንመልከት በየትም አገር መንግሥት ማለት አንድ ሰው ብቻ አይደለም ያገሩ ሕዝብ ሁሉ ነው እንጂ ። ይልቁንም መንግሥት ማለት እነዚያ ለሕዝቡና ላገሪቱ ኢያሰቡ ያነዋወር ደንብና ስርዓት ሊሰጡ ከሕዝቡ የተመረጡ ሰዎች ባንድነት ይመስላሉ ። ከነዚሁም አንድ ዋና አሳዳሪ ንጉሥ ይመርጣል ስለሆነ መንግሥት ማለት መላው ሕዝብና አገሪቱ ናቸው ።

አገራቸውን ለመጠበቅና ሕዝባቸውን ለመጥቀም በተለየ ግብርና አበል ከሕዝቡ ሊቀበሉ ማእረግ የተሰጣቸው ብዙ መኳንንቶች አሉን ፡ አገራቸውን ለመጠበቅ እንዳልሰነፉ እንዳይሰንፉም የዓለም ታሪክ ሁሉ ይመሰክርላቸዋል ፡ ለመጥቀም ግን እንዳልደረሱ ከየታሪኩ ተርፎ ያለሙ ሕዝብ ሲያፈዝባቸው ይታያል እነዚህም መኳንንቶች አንዱን ጥሎ ተው አንደኛው እንደ ጉዶለባቸው አይተው ፡ እንደ ራስ እንደ ደጃዝማች እንደ ፊታውራሪ ያለ ማእረግ ያላቸው ትልልቆቹ ከበርቴዎች እንኳ ለዚህ ክብረትና ትልቅነት ላበቃቸው አባታቸውና መንግሥታቸው ዘለዓለም ታቀፉ ለምታኖራቸው እናታቸው በዚህ ትንሽ ነገር ቢረዷቸው ቢጠሯቸው የጐደለው ያለም ማፈሪያ የሆነበትን በሞሉ ነበር ። ሌላ እንኳ የማከብዳቸው ቢሆን በየራስ ከተማቸው ፡ የፈትል ፡ የሳሙናና ሻማ ፡ ፋብሪካ አቁመው ለብዙህ ክብረት ላበቃቸው መንግሥት መኖፖል ስራ ቢሰጡ ከሚጐድሉት አንዱን ሞሉ ማለት ነበር ፡ አባት እንደሚያሳድግ ልጆች ጥረ ፣ ግረን መጠር እንዳለብን እናስብ ፡ ከትንሾቹ በፊት ትልልቆቹ እንደሆኑ አባት እናትን መጠር የሚጀምሩ ከኔ ከትንሹ ይበልጥ እነሱ ያውቃሉ ፡ እንግዲህ እናትና አባት ማለት አገርና መንግሥት እንደ ሆኑ መረዳታቸውን በጧጠራቸው ተገልጾልን ትንንቹም በፍጥነት በተከተልናቸው ነበር ብዙ ክብረትና ጌትነት ለሰጧቸው አገርና መንግሥት ጥቅም ቢፈልጉ ከዚያ ከእርጉም ንፍ ገት ርቀው አንዳንድ ፋብሪካ አቁመው ላገር ጥቅም መኖፖል ቢሰጡ ለዘለዓለም የሚኖር ሐውልታ በሕይወታቸው ሳሉ ማቆማቸው ነው እንጂ ለመንግሥት መርዳታቸው ብቻ ሆኖ ባልቀረ ነበር ።

ስለ ሐውልትነታቸው እነዚህ ፋብሪካዎችና በነሱ የሚሰሩ ዕቃዎች የፋብሪካውን ተከታይ መኰንን ስምና ምልክት የታተመባቸው ዘለዓለም ስምና ምልክታቸው ሳይለወጡ ኢየተጠሩባቸው ለልጅ ልጅ ኢየተላለፉ በኢትዮጵያና በዓለም ታሪክ ከሌላው ሥራቸው ይበልጥ ተቀርጸው ባበሩ ነበር እንጂ በመንግሥቱ እንደ ሚረሳ አስከፊና ነፍስ አውጪ ግብር ብዙ ገንዘብ አጥፍተው ባልቀሩ ነበር ።

የኔ አገር መኳንቶች ላሳደጋቸው መንግሥትና ለተፈጠሩባት አገር ጥቅም ከጉልበ ቶችው እንጂ ከገንዘባቸው በደስታ ከፍለው ይረዱስ አይመስለኝም ። አንብበው እንዳላነበቡ ሰምተው እንዳል ሰሙ አያድርጋቸውና በነዚህ ፋብሪካ የሚያወጡት ገንዘብ የሚቆጯቸው ቢሆን በየፋብሪካው የሚሰራው ፈትል ሳሙናና ሻማ እንደ ደነቡ በመኖፖል መንግሥት እያሸጠ ያወጡትን ገንዘብ ከትርፉ ላይ ቢከፍላቸው ከሁለት አመት ይበልጥ ባልቆየባቸው ነበር መኪናውን ለማቆም ግን እንደ ኢትዮጵያውያን ቸልተኝነት ብዙ አመት እንዳይበቃን ሁላችን እናውቃለን ።

ክቡራን መኳንንቶች ሆይ ። መንግሥታችን ለሌላው ጉዳይ ሁሉ ገንዘብ እንዲቸግረውና ብዙ ሊሰራ የጀመረው ሥራ ሁሉ እንዳልተዳረሰለት ከኔ ይበልጥ ክቡርነታችሁ ያውቃልና እስቲ በነዚህ ባዲስ ሥራ እንኳን እርዱት ። ብንረዳ ኢትዮጵያን የሚቸግራት የለም ። የሚረዳን ሕዝብ እግዚአብሔር እንዲረዳ ታውቃላችሁና እባካችሁ እንረዳ እንረዳ እንረዳ ።

ምንም ቢሆን መንግሥታችን ከውጪ አገር መንግሥት ሆን ከበርቴ ገንዘብ መበደር በማናቸውም ጉዳይ አያስፈልገውየማይገባው ነውና ። ባገሩ ያለው ገንዘብ ያወጣጥና ያገባብ ደንብ ኤኰኖሚ (ቁጥብ) የሌለው የባእድም ገንዘብ ቢያመጣ ወጪው ብቻ በዝቶ ያላንድ ጥቅም በከኖ እንዲያልቅ የታወቀ ነውና ስለዚህ ያተርፉል የተባለው ብድር የሚያጠፉ ሆኖ ይገኛልና ይጠንቀቅ ። ያሜሪካው ሊቅ ፍራንክሊን ያለውን እናስብ እዳ የሚገባ ሰው ነጻነቱን ለቆ ስሺ ጻጻታ የሚሰናጻ ነው ። ምንኛ መልክም ያለእረፊት መተኛት ። ባለእዳ ሁኖ ጥዋት ከመነሳት እያለ ያገሩን ሕዝብ ይመክር ነበር ።

ምሳሌም ባለጸጋ ድሖችን ይገዛል ። ተበዳሪም ያበዳሪ ባሮ ነው ሲል እንመለከታለንና ከብድር ባርነት እንራቅ ። ስለዚህ ሌላው ክብረታችን ሁሉ ይቆይና እስቲ ብዙ ብልሐት በማያስፈልጉን በጥጥና በጨው ሥራ ብቻ ከገራችን የሚወጣውን ገንዘብ ብናስቀር ኢትዮጵያ ስንት ጥቅም እንደምታገኝ ለሁላችን በርቶ ይታያልና እነዚህ ያገር ጠባቂና ጠቃሚ የተባሉ ትልልቅ ከበርቴዎች በእውነት ላገራቸው ጥቅምና ፡ ለመንግሥታቸው ክብረት ለነጻቸው ጉልበት ፈልገው ቢረዱ ከነዚህ እቃዎች (ፈትል ሳሙና ሻማ) ከሚገኘው ትርፍ የቀረጡና የከኰቱው ለመንግሥት ተነስቶ የሚተርፈው ፋብሪካው በየቆመበት ከተማ ለመንገድ ማሰሪያ የሚሆን ቢሆን አያሌ ጥቅም ነበረው ።

ከዚህ የቀረው በሚከተለው ቁጥር ይታተማል ።

ይድረስ ከክቡር

ለኢትዮጵያውያን የሰልጣኔ ትምርት ቤት እርዳታ ገንዘብ

አዘጋጅ ዲረክተር ።

ሰላምና ጤና ለርስዎ ይሁን በያሌው ጤናዎን እንዴት አሉ

ክቡር ወንድሜ ሆይ ።

ላገራችን ጥቅም ለወንድሞቻችን ማሰልጠኛ የሚሆኑ የተማሪ ቤቶች እንድንተክል አስበው ክቡር ፊታውራሪ ዴሬሳ ።

ኢትዮጵያውያንን ሁሉ ለጠሩበት ተማሪ ቤቶች እርዳታ ነፍሴ እንደምትወደው እራሴ እንደምታስበው በብዙው ለመርዳት የማልችል ድሀ ተማሪ ብሆን ባሉኝ በሚኖሩኝ ክብረቴ በመ ጻሕፍቶቼ ቁጥር ፩ ፩ መሐለቅ በያመቱ ላዋጣ የተሰናዳሁ መሆ ኔን በፊርማዬ አስረዳለሁ አሁንም ባሉኝ መጻሕፍቶቼ ቁጥር ቀጥዬ ሂሣብ አዋጥቼ ፺፫ ሊሬ ሰድጄልዎታለሁና ያቅሚን ያህል ሥራ እዲያስያዟት እለምንዎታለሁ ። ደህና ይሁኑ ።

ኢትዮጵያ ለዘላዓለም ትኑር ።

፲፱፻፲፱ ዓ ም ግንቦት ፯ ቀን ፡

ትንሹ ወንድምዎ ተማሪው መ ሥ ወ።

የሀገርን መውደድ ምልክት ።

የፍቅርና የአገልግሎት የሥራውን ውበትና ያረማመዱን መልክምነት ስመለከት ሳለሁ ወንድም ወንድሙን አይንቀውም የሚኅዳና የሚጠቀመንን ለይተን አውቀን ከቶ አቅም አጥቼ ለማሕበሩ እርታም ባላደርግ የሀገሬ ጥቅም መሆኑን ስለተረዳ ሁት ከዚህ ሰዓት ወዲያ እስከ ኢትዮጵያ የበለጠች ልትሆን ነው ብዬ የደስታ አክሊል ሕሊናዬን ስለከበበው ይህችን ለመ ጻፍ ተገደድሁ የወንድማማችነትና ያንድነት ሰባኪው መምሕ ራችን ብርሃንና ሰላም በየጊዜው የሚያስተምረን መሰረት ብር ሃን ከጭለማ ሁከት (ጠብ) ከሰላም የሚያገናኝ ደምበር የላቸ ውም።ዳሩ ግን ማናቸውም ሕዝብና መንግሥት ለጨለማ ያልተገዛ የለም በዘመን ብዛት ነጻነቱን እያገኘ የብርሃን ተከታታይ ሆነ እንጂ ስለሆነ ባንድ ወገን ጭለማ ግዛቱን ቢለቅ በሌላ በኩል በሰው ልጆች ልብ ርስቱን ያሰፋል የሆነ ሆኖ የጭለማ ተንኮል ፈጽሞ ከሀገሩ የነተቀለለት መንግሥት ይገኝ አይመስልም ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ እስካሁን ድረስ ጭለማና ብርሃን ግራና ቀኝ ሲፎካከሩ ይታያሉ ፪ንተቃራኒዎች ይዞ የሚዛገም ሕዝብማ ለኑሮው ማናቸውን ይመርጥ ይሆን ብርሃንና ሰላም ንስ ከሕዝብ ወገን የሚጠላ ያለ አይመስለኝም ይልቁንም በኢ ትዮጵያ ልጆች ዘንድ በዛሬው ወራት ጭለማ የተናቀች ሁና ከቅድስት ሀገራችን እንደ ይሁዲት መንግሥት ለመፍለስ ቀር ባለች የይሁዲት መንግሥት ማለትም አጼ አንበሳ ወዴ ዘ[illegible] ዓመተ ምሕረት በሞተ ጊዜ አንዲት አይሁዲት የማክዳን ዘ[illegible] አጠፋለሁ የኔ ዘር በማክዳ ፋንታ መንግሥቱን ይይዛል ስትል መኳንንቱን ሁሉ አስገደለች ፩ ልጅ ብቻ ደልነአድ የሚባል አመለጠ ቄሶችና ንጸ.ሐን መነከሳት የክርስቲያን ሰው ዘር አይጥፋ ብለው የኢትዮጵያን ተስፋ ደልነአድን ከኃጢአተኞች ሰይፍ አዳኑት ከልጁ ጋራ ወደ ሸዋ ተሰደደ በሀገረ ተጉለት ደበቁት እዚያው እርሱም መንገሥ ዠመረ ልጆቹም ፩፻፱፲፰ ዓመተ ምሕረት ድረስ በተጉለት ነገሡ ። ይህችም ይሁዲት የክርስቲ ያንን ሃይማኖት ጠልታ ሕዝቡን በአይሁድ ሕግ ለማሳደር ፈለ ገች እሷም ፵ ዓመት ነገሠች ከርሷ በኋላም ፭ነገሥታት የስዋ ዘሮች የክርስቲያንን ሃይማኖት ለማጥፋት ፈለጉ ግን ክርስቲያ ኖች በረቱና የአይሁድን ዘር ከአልጋ ጣሉት የሚል ታሪክ እየ ሁና እንግዲያውማ ድል ማድረግ የአባቶቻችን ልማድ ከሆነ በኛም ጊዜ የድንቁርና ድል መሆን አያስገርምም እምቤቲቱ ኢትዮጵያም ለአሁን የሚያስፈልጋትን ሁነታ አውቃ ተፈሪ መኰንን የሚባል ልጇዋን የሊቅነት ማዕረግ ሰጥታ በያውራጃዋ የትምሕርት ኃኪሞች እንዲያጸድቁላት ታተጋጋለች ታማኙ ልጇዋም ልዑል ተፈሪ መኰንን ሕዝባቸውን ወደ ሥልጣኔ ደረጃ ለመሳብ ያንቃቃሉ ንጹሕ ልብፍጠርልኝ ያለውን ዳዊት አይንግን የተቢትና የስንፍናን ልብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይነቀልለት ለምለ ሚቱን ሀገራችን ትኑር ከታላቁ የሥልጣኔ ደረጃ ያደርሳት አሜን ።

ብርሃንና ሰላም የቀናው መንገድ ስንኳን ዓይናማውን ስውር የሚያስኬ፡፡ ብርሃንና ሰላም የውቀቱ መሪያችን፡ የምግብህ መጣፈጥ ገባ ከጥንታችን ።

ብርሃንና ሰላም የውነት መስካሪያችን ተሚጋች ሆነልን ለነጻነታችን ።

እየለ ገዳ ዘብሔረ ወግዳ ።

ኑሮን ከማሻሻል ስለሚነሳ ጉዳት

ማለት አንድ ቀን ላገሬ አዲስ ዓለም ከተማ እዛወራለሁ ስል በሌት ሙቀት በቀን ላቦት የሚሰጠኝ ድንቁርና የሚባል የወትሮ ልብሴ ችላ ብዬ ጥበብ የተባለ አዲሱን ኩታ በመነን የተሠራ ለብሼ ወይዘሮ ማሰብን ተከትዬ እውቀት በተባለ በተፈሪ ጐዳና ስሄድ ሳለሁ የቀድሞ ኑሮዬን የሚያውቁ ያገሬ ሰዎች በሩቅ ሳለሁ ተመልክተው አዩኝና እንዲህ ብለው ተማከሩ ይህ ሰውዬ ድንቁርና የሚባል የወትሮ ልብሱን ትቶ ቀጭን ከለበሰ ጥበብ አምሮታልና እንግደለው ብለው ጥይት ሐሰታቸ ውን አጉርሰው ተመልክተው ቢተኩሱ እውነትም ጆሮዬን መቱኝ ። ነገር ግን በሚያስፈራ ጐዳና ብንሮጥ ሩጠን እናመል ጥምና ሲሉ ፡ ስሕተት በሚባል በግራው ጐዳና ሩጠው አመለጡ ዳሩ ግን ያገሩ አየር እንደተስማማቸው አውቂያለሁና ጆሮዬን ክድን አድርጌ እቤቴ ሄጄ ሳበቃ እረፍት ከሚባል አልጋዬ ወጥቼ ጋደም አልኩኝ ። ስለሆነ ግን የመታኝ ጥይት ባንድ ጆሮዬ ገብቶ በንዱ ስላልወጣልኝ በጉሮሮዬ ውስጥ እየተመላ ለሰ አላስበላ አላስጠጣ አላስቀምጥ አላስተኛ እያለ በጣም እየ ወዘወዘኝ ስጠበብ ስጨነቅ ሳለሁ ፡ ብርሃንና ሰላም የሚባል የቅ ርብ ቀን ወዳጄ አመልክቼን እንጂ ሳንቃውን ክፍት አድርጎ ገባና እውነትም ቢዳስስኝ ለካ ሰውነቴ ሁሉ ደም ቋጥሮ ነገር ግን ብርሃንና ሰላም የሚባል የቅርብ ቀን ወዳጄ ረቂቅ ብልህ አዛኝ ርኅሩኅ ነውና አረሳሳዋለሁ ሲል በገናውን ቃኘና እንዲህ ብሎ ያጫውተኝ ጀመረ ።

እንዴት ነሽ ኢትዮጵያ የሀበሻ መንግሥት
ተኝተሽ ነበረ ብዙ ቀን ሌሊት
እንግዲህ ተነሽ ሩጪ ወደ ፊት
ብርሃንና ሰላም ሳለልሽ መብራት
ልጅሽ ተፈሪ ነው የወንዶች አባት
ብርሃንና ሰላም በጣም ተጀነነ
ጫማውን ረገጠና ጥበብ ተከደነ
ጠላ ሲያጣ ኑሮ ጠጅ ተለመነ

ምስርም እምቢ አለና ከሥጋው ዘገነ
ተፈሪ ነውና ሁላችን ፈራን

ብርሃንና ሰላም ምንኛ ተዋበ
ጨለማና ክፋት እየሰበሰበ
በብርሃን ጥይቱ ወርዶ ደበደበ
መምሕር አወጣና ልጆች አስረከበ
አበታችን ብሎ አያቱን ሰደበ

ብርሃንና ሰላም ምንኛ ተጋፋ
ወደ ፊቱ ሄደ አገሩን አሰፋ
የኛ ድንቁርና አውቆ ሊያጠፋ
መኪና ያለህም ተፈሪ አይነት ስፋ
ጥበብ እንጂ ነው በጁ የሚሰፋ

ብርሃንና ሰላም ሁለቱ ጓደኛ
ጨለማን ለመግደል ሁነውት ደመኛ
ጨለማም ሞታሉ ባላባት ርስተኛ
ድንቁርናም ገባ ታርቆ እንደኛ
አመሉን ትቶ ያረቂ ወልፈኛ

ብርሃንና ሰላም ደግ ነገር ለመደ
ኢትዮጵያን ገባ እየተራመደ
ድምበራችን አለ ገመድ ተጋመደ
ጨለማውም ሞተ ብርሃን ተወለደ
ጨለማ ገዳይ ሰላም በፈረደ

ብርሃንና ሰላም በጣም ገሰገሱ
ኢትዮጵያ ገቡ ጫካውን እየጣሱ
ምድሩን ጨረሱና ባሕሩ ዳር ደረሱ
መረብ ቢኖር ግና ዓሣ በጠበሱ
መርከብም ታጣና በግር ተመለሱ

ብርሃንና ሰላም የዓለም መብራት
ላቶ ተንኮል ልማድ ይዘው በሸንጎ ሥራት
ውርድን አሳይተው ሰጋር በቅሎ ሳይሉ ይለፍ ረቱት
እንግሁኝ አለ ሙግት ሲያልቅበት
ፍርድ ይብቃ ሆነ ለባላባት ርስት
ብርሃንና ሰላም ምን ጊዜ አደገ
ለዲቁና በቅቶ ቅስና ፈለገ
ክህነት መች ይታጣል አእምሮ ካደገ
ጳጳሱም ከገር ነው ልብ ላደረገ

በጕሮው ውስጥ ገብቶ ርሳስ ተጋድሞ
ወይ ያልሰማ ጕሮ ሰው ያጣላል ደግሞ ፤
ያልዋጠ ጕረሮስ ምኑን አጣጥሞ
አቶ ተንኮል ሞተ ሐሳቡን ፈጽሞ ፤

ተንኮል ሞተ ነገር ተከተተ ብለህ በል እያለ ደወል በሆነ ቃሉ እያጫወተኝ ንበቡና ምሥጢሩን ትርጉሙን እየሰማሁ ማስተዋል ስጀምር ሳለሁ እነደግነት ፤ እነየዋህነት ፤ እነያገር ፍቅር እነ ቸርነት ፤ እነመረዳዳት ፣ እነአንድነት ፤ እነመተጋገዝ ፣ እነስምምነት ፡፡ እነመተዛዘን እነቅንነት ፣ የሚባሉ ወዳጆቼ ለካ ሰምተው በረው ደረሱብኝ ፡፡ እኔም ከፍትፍቱ ፊቱ ነውና ፊታቸውን ትመለከትሁ ጊዜ የግቢ ዘበኞች እንደሆኑ ለይቼ አወቅሁ ብርሃንና ሰላምም የበገናውን ግጥም ተወት አደረገና መቸም ለወዳጅ የሚደበቅ የለም ሁሉንም አጫወታቸው ፤ እነደግነትም ያለፈውንና የሚመጣውን ሁሉ በግልጥ አጫወቱት ፣ ለሰሚ ጕሮዬም እውነትን በመስማት ደስ ብሎታልና በውስጡ የነበረ የሐሰት ጥይት ወደቀለት አሁ ግን እግዚአብሔር ይመስገን የጕሮዬ በሽታ ቀለል ብሎኝ ጤናማ ነኝና ለመስማት አልዘገይም ለመብላትም እምቢ አልልም ፡፡ ተማኑ ሮምሃ ዓድዋ

የውጭ አገር ወሬ ፤

የኬሜል ፓሻ ጋብቻ ከምንቴኖራግዊ ልጅ አገረድ ጋር ሎንዶን ግንቦት ፲፫ ቀን፡

የቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳንት (ሰብሳቢ ሹም) ኬሜል ፓሻ ፡፡ ከምታምር ምን ቴኖግራዊ ልጅ አገረድ ፲፰ ዓመት እድሜ ከሆናት ጋር በቶሎ ሊጋባ የጋብቻ ውል አስሯል ሲል ከቤልግራድ የተላከቴሌግራም ዴሊ ኒዮስ ለተባለ ጋዜጣ ዛሬ አስታወቀ፡

ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፡፡

የተወደዱ አንታችን ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ በኢትዮጵያ በሰነበቱበት ጊዜ ከግርማዊነትዎ የተደረገላቸውን አቀባበል እርሳቸው ራሳቸው ነገሩን፡፡እንዴህ ያለው የግርማዊነትዎ የፍቅር ሐሳብ የሚገልጽ አድርጎት ከግርማዊነትዎ ማግኘታችን የግርማዊነትዎን የፍቅር ሐሳብ ያስረግጥልናል አጥብቆም ደስ እንዳለን ለግርማዊነትዎ እንገልጻለን ፡፡

ቢቶሪዮ አማኑኤል ፡፡

ለልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ፡፡ ተፈሪ መኰንን ፡፡

ሮማ ፡፡

የተወደዱ አንታችን ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ በመልክታቸው ጊዜ ልዕልናዎና የኢት ዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ያደረጉላቸውን የፍቅር አቀባበል እርሳቸው ራሳቸው ነገሩን ፡፡ በሁለቱ አገሮቻችን የሚሆ ን በጣም የሚናፈቀው የጠቀሜታ መስማማት እንዲጸና እያመነ ጥልቅ ምሥጋናችንን ለልዕልናዎ እናቀርባለን ፡፡ የፍቅር ሐሳባችንነ እየ ገለጥን ለልዕልናዎ እናቀርባለን ፡፡ ቢቶሪዮ አማኑኤል ፡፡

ለልዑል አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንን ፡፡

እኔ ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ከኢትዮጵያ ወደ ሮማ በገባሁ ጊዜ ለግርማዊ የኢጣልያን ንጉሥና ለክቡር ሙሶሊኒ ለኢጣልያን መንሥት ጠቅላይ አለቃ በኢትዮጵያ የልዑልነትዎና የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝቡ እኔ በኢትዮጵያ በነበርኩ ጊዜ ለኔና ከኔ ጋራ አብረው ለነበሩት ሚሲዮን ያደረጉት መልካም አቀባበል አስታውቄያቸዋለሁ ፡፡ ግርማዊ ንጉሥና ክቡር ሙሴ ሙሶሊኒ ሚሲዮኖችን በሁለቱ ትልልቅ ሃገሮቻችን መካከል የዝምድና ማሠሪያን ለማጥበቅ ምክንያት ስለ ሆነ እጅግ ደስ አላቸው ፡፡ እኔ እራሴ በኢትዮጵያ ያገኘሁትን መልካም አቀባበል የማይረሳ መታሰቢያ ሆኖ በልቤ ይኖራል ፡፡ ልዑልነትዎ ጥልቅ የሆነ ምሥጋናዬን የኔና ከኔ ጋራ የመጡትን ሰዎች ከልብ የሆነ የወዳጅነታችንን እንዲቀበሉልኝ እለምነዎታለሁ ፡፡ ሉጂ ዲ ሳቦያ ፡፡

ለልዑል የኢትዮጵያ መ አ ወራሽና እንደራሴ ተ መ ሮማ ።

የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ለልዑል ዱክ ድዝአብ ሩዝና አብሮዋቸው ለተላኩ የኢጣልያ መላክተኞች በኢትዮጵያ አገር በሰነበቱበት ጊዜ ስለ አደረጉላቸው ትልቅ የፍቅር አቀባበል ልዕልናዎን አመሰግናለሁ እንዲህ ያለ አቀባበል በኢትዮጵያና ሀኢጣልያ አገር ያለውን መስማማት የእውነተኛ ፍቅር መሆኑ ሙሉ እምነት ይሰጠኛል ።

ደግሞ ለወደ ፊቱ ለሁለት ትልልቅ መንግሥት የንግድና የጠቀሜታ መስማማት ለዘወትር በጣም እየጸናና እየሰፋ እንዲሔድ መጥቀሙን ሙሉ እምነት ይሰጠኛል ። ይህ የፍቅር ሐሳቤን አገላለጥ ልዕልናዎ በደስታ እንዲቀበለው ልዕልናዎን እለምናለሁ ።

ሙሶሊኒ።

ለግርማዊትንግሥት ዘውዲቱ ።

ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩስ ከኢት ዮጵያ ዛሬ በሮማ ስገባ ለግርማዊ ለኢጣልያን ንጉሥ በኢትዮጵያ ሳለሁ ስለ ተደረገልኝ መልካም አቀባበል አስታውቄ እጅግ ደስ አላቸው ምሥጋናዬንና ጥልቅ የሆነ ማክበሬን ግርማዊትነትዎ እንዲቀበሉኝ እለምናለሁ ። ሉጂ ዲሳበያ ።

ለግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል ።

የተወደዱ አጎትዎ ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ከአዲስ አበባ ከተመለሱ በኋላ በደህና ወደ ሮማ ደርሰው ከግርማዊነትዎ ጋራ መገናኘታቸውን ብንሰማ እጅግ ደስ ብሎናል እርሳቸውም በሁለቱ መንግሥቶች መካከል ያለውን ወዳጅነት ለማጽናት ስለ ሆነ ለዘላለም የማይረሳ መታሰቢያ ሆኖልን ይኖራል ሰኔ ፲፩ ቀን ፲፱፻፲፮ ዓመተ ምሕረት ።

ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ።

ለግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል ።

የተወደዱ አጐትዎ ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ በሁለቱ መንግሥቶች መካከል ያለውን ወዳጅነት አብዝቶ ለመግለጥና ለማጽናት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ለዘለዓለም መታሰቢያ ሆኖ የሚኖር ፍቅራቸውንና ደግነታቸውን ካሳዩን በኋላ በደኅና ወደ ሮማ ተመልሰው ከግርማዊነትዎ ጋራ መገናኘታቸውን ስለ ሰማን እጅግ ደስ ብሎናል ።

ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ከእኛ ጋራ የቆዩበት ቀኑ ምንም እንኳ ጥቂት ቢሆን በዚሁ በጥቂቱ ቀን ለኛ የገለጡልን ፍቅራቸውንና ደግነታቸውን አይተን እኔ ወደ ሮማ በመጣሁ ጊዜ ግርማዊነትዎ ያሳዩኝን ፍቅርዎንና ደግነትዎን አሳሰበኝ ።

አሁንም በልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ አመጣጥ የተገለጠው የሁለቱ መንግሥቶች ወዳጅነት ለብዙ ዘመን ጸንቶ እንዲኖር የልቤን ምኞት ለግርማዊነትዎ አቀርባለሁ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ

ተፈሪ መኰንን ።

ለክቡር ሲኞር ሙሶሊኒ ።

ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የሁለቱን መንግሥቶች ወዳጅነት አጽንተው ፍቅራቸውንና ደግነታቸውን ካሳዩን በኋላ ተመልሰው በደህና ወደ ሮማ መድረሳቸውን ስለ ሰማን እጅግ ደስ ብሎናል ።

ደግሞ የኢጣልያ መንግሥት ትልቅነትን ከደግነት ጋራ አስተባብረው የያዙትን የንጉሡን አጐት ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝንና ሌሎችንም መልክተኞች መርጦ መላኩ የወዳጅነቱን ምልክት ለማሳየት እንደ ሆነ ተረድተነዋል ።

ይህም የልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ አመጣጥ ወደ ፊት የሁለቱ መንግሥቶች ሕዝብ ወዳጅነት እንዲሰፋና እንዲበዛ ዋና ምክንያት መሆኑ አይጠረጠርም ።

ይኸውም ወዳጅነታችንና ፍቅራችን ለዘለዓለም ጸንቶ እንዲኖር የልባችን ምኞት መሆኑን እንዲቀበሉን እለምናለሁ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ

ተፈሪ መኰንን ።

ልዑል ሉጂ ዲ ሳበያ ዱክ፹ዴዝ አብሩዝ ።

ልዑልነትዎ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ለዘላለም የማይረሳ ፍቅርዎንና ደግነትዎን ካሳዩን በኋላ ወደ ሮማ በደህና ተመልሰው ከግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤልና ከመንግሥቱ ጠቅላይ አለቃ ክቡር ሙሴ ሙሶሊኒ ከሕዝቡም ጋራ መገናኘትዎን ስለሰማን እጅግ ደስ ብሎናል ።

ደግሞ የልዑልነትዎ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት የሁለቱን መንግሥቶች የፍቅር ማሠሪያ ለማጥበቅ እንደሆነ ለእኛ አስረድተው የእኛም ሀሳብ ወዳጅነታችንን ለማጽናት መሆኑን ለግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤልና ለመንግሥቱ ጠቅላይ አለቃ ለክቡር ሙሴ ሙሶሊኒ ለሕዝቡም ሁሉ አስረድተው ስለ ነገሩልን እጅግ እናመሰግንዎታለን ።

አሁንም ለልዑልነትዎና ልዑልነትዎን ተከትለው ለመጡ ሚሲዮኖች ሁሉ የምናቀርበውን ከልብ የሆነ ምስጋናችንን እንዲቀበሉን በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ስምና በራሴም ስም እለምንዎታለሁ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ

ተፈሪ መኰንን ።

ማስታወቂያ

፲፱፻፲፮ ዓመተ ምሕረት ሰኔ ፱ ቀን እኔ ፊታውራሪ ግፋወሰን ማህተሜ ተሰርቆ ጠፍቶብኛልና እስከ ሰኔ ፳ ቀን ድረስ አግኝቶ ያመጣልኝን ሰው እሸልማለሁ ከእንግዴህ ወዲያ አትሞ ቢያመጣ አላፊም አልሆን ውልም አይረጋብኝም ከሰኔ ፱ ቀን ወዲህ ማህተሜም የጠፋውም ከነኮርጆው ነው ደግሞ እንድናስ ማሰር ጠመንጃ ጨምሮ ነው የጠፋው ሰኔ ፲፪ ቀን ፲፱፻፲፮ ዓመተ ምሕረት ።

OMEGA



እጅግ ጥሩነቱ የተመሰከረለት ኦሜጋ በቢ የሚባል ባለ አ[illegible]በሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፰ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር ተሩብ
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር ሩብ ምላሽ
የበግ ቆዳ	፩ ክረጃ	፱ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ክረጃ	፲፰ ብር ተሩብ
አቡጀዲ መነጽር	፩ ክረጃ	፻፴፰ ብር ተኩሉ
:: ባለፈረስ	::	፻፴፯ ብር ።
:: ባለ ድመት ።		፻፳፰ ብር ።
:: ባለአህያ	::	፻፲ ብር
:: ባለሳቢ ግመል	::	፻፳፰ ብር
:: ባለአንበሳ	::	፻፵፬ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፫ ሩብ

ስለ ምንዛሪ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፳፯
በአንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ ፺፰
ባአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፰ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፰ ብር

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል ።

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሰያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

ሩግቢ

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ[illegible]ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና ሕሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሳ መኖቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሂስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ማጥን በየዓይነቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረትና ለአንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።



ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቀኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ አቶሞቢል በአንጨት የሚሄድ ከሚኦን በጠንከራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፎል ቤት መውረጃ ።

ARMENAK ZAMANIAN
AGENT GÉNÉRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኦዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶከለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የኦዶከለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ። የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፡ ቁጥር ፳፮ 3 me ANNÉE № 26	ሐሙስ ሰኔ ፳፫ ቀን ፣ ፲፱፻፲፱ ዓ ም ። JEUDI 30 JUIN 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé "Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሰምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስተድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፺፰ገጽ ተከታይ

ለመንግሥትና ለሕዝብ ጥቅም ።

አስረጂ ሰንጠረጋር ።

እላይ እንደ ለመንኩት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ሰራተኛ ሁሉን መርምሮ እርግጠኛ ልኩን እንደሚከተለው አድርጎ ለብርሃንና ሰላም እስቲገልጥ ድረስ ስንት ኩረጃ አቡጀዴ ስንት ወረቀት ፈትል ስንት ጆንያ አሸቦ ስንት ደርዘን ሳሙናና ሻማ እንዲገቡና በስንት እንዲሸጡ እውነተኛ ልኩን ባልጽፍ እሳንሸን በገመትነው ከብዙው ጥቂቱን ጉዳታችንን በሚከተሉት ሰንጠረዦች ልንረዳ እንችላለን ።

የኢትዮጵያን ሕዝብ ገንዘብ ወደ ውጪ አወጣጥ ልክ
በጥቂቱ አስረጂ ።

የአቡጀዴው ዓይነት	ስንት ኩረጃ እንደሚሸጥ	ባንድ ወር ውስጥ ገቢና ወጪ	
		የተሸጠ ኩረጃ	ስንት ብር እንድናወጣ
ባለ ሳቢ ግመል	፻፳፬	፹፻፫	፴፫ሺ.፱፻፺፱
ባለ አንበሳ	፻፶	፹፻፬	፴፫ሺ.፯፻
ባለሰይጣን ስዕ	፻፺፭	፹፻፺፫	፴፬ሺ.፱፻፳፫
ባለ መንጥር	፻፺፬	፹፻፺፫	፴፬ሺ.፱፻፳፱
ባለ ድመት	፻፴፭	፫፻	፶ሺ.፭፻
ባለ ፈረስ	፻፴፫	፫፻፳፬	፶፰ሺ.፬፻፲፱
ባለ አህያ	፻፳፫	፬፻	፶፱ሺ.፱፻
የወር ድምር		፱ሺ.፯	፱፻፷፰ሺ.፭፻፳፱
ያመቱ ጥቅል ድምር		፳፬ሺ.፬፻፲፬ኮረጃ፲ጣቃ	፫ሚ.፫፻፹፰ሺ.፯፻፹፫

ይኸ ግን አሳንሰን እንዳሰብነው ካዲስ አበባ ጉምሩክ እየወጣ በሸዋ ያለው ሕዝብ ብቻ የሚከፍለው ነው ።

ይኸውም ሲሆን በዋጋው ብዛትና በድህነት ክብደት ተይዘው ያለ እጀጥባብ የሚሄዱ ብዙ ወንድሞቻችንን እናያለን ፣

በሌሎቹም የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚያስፈልገውን አቡጀዴ እንደሚከተለው ልንገምተው እንችላለን ፣ በሐረር አውራጃ ያለው ሕዝብ ጭራሽ የፈትል ነገር የማያውቅ ስለ ሆነ ብዙ አቡጀዲ የሚያስፈልገው ነው ይኸውም ቢሆን ሕዝቡ ጥቂት ነው ከዚሁም እራቆቱን ሐጅ ቆቱ ሞልቶአልና ስለ ዚህ ከሸዋው እራት እጅ የሚያንስ ኩረጃ አቡጀዲ ያስፈልገው ይሆናል ለዚሁም መግገ የሸዋው ሕዝብ ከሚያወጣው ገንዘብ አራት እጅ ያነሰ ብር ከድሬ ደዋና ከዘይላ ከእንግሊዝ ሱማሌ ለሚመጣላቸው ፮ሺ.፪፻ ኩረጃ ከ፯ ጣቃ ፳፻፺፯ሺ.፻፳፭ ብር ፲፬ መሐለቅ ጥጡ ባገራቸው ሳለ ባመት ባመቱ ይኸን ያህል ገንዘብ ይገብራሉ ።

በኤርትርያ በኩልና በሱዳን በኩል የሚገባው ጨርቅ ጥጥ እንደሌላው አገር ትግሬን አማራ ሰይንትን ጎንደሬንና ጎጃሜን ያለብሳል ጎጃሜና ጎንደሬዎች እጅግም በፈትል የተመሰገኑ ቢሆኑ ሴቶቹ ከእራሳቸው ተርፈው ከጋቢ በተቀር ለወንዶቹ ለማልበስ አልተቻላቸውም በነዚሁም አገሮች መለስ ብዙ በድህነትና ባለመሰልጠን እራቁታቸውን የሚሄዱ አሉና ሕዝቡም አነስ ያለ ነውና ከሸዋው ሁለት እጅ ያነሰ ያስፈልጋቸው ይመስላል ማለት ፲፪ ሺ. ፪፻፯ ኩረጃ ከ፰ ጣቃ ለማግኘት ላቶ በዕድጨክኝ ፩ ሚሊዮን ፯፻፺፬ ሺ. ፫፻፺፩ ብር ከ፱ መሐለቅ መስጠት ያስፈልጋቸዋል ።

የቀሩት በእንግሊዝ ቅኝ አገሮች ወገን ላሉት የኢትዮጵያ ክፍሎች ። ወለጋ ፣ አመያ ፣ ከፋ ከጉጃም በመለስ እስከ ውጋዴን (ሐረር አውራጃ) ድረስ የተዘረጋው ዳራገር ምንም አገሩ ሰፊ ቢሆን ሕዝቡ ጥቂት ነው ። ከነዚሁም እንደነከፋ ውላሞ ፣ አመያ የሚፈትሉ አሉ በነዚሁም ላይ ከሸዋ ብዙ የባሕር ጨርቅ ይወርድላቸዋል ። ደግሞም ያልሰለጠኑ እራቁታቸ

ውን የሚሄዱ ብዙ ሕዝቦች አሉብቸውና ከሸዋው ሶኮት እጅ ያነሰ አድርገን ልንገምተው እንችላለንና ለ፳ሺ ፻፴፰ ኲረጃ ከ፬ ጣቃ አቡጀዴ በገዛ ጥጣቸው ተሰርቶ በእንግሊዝ ቅኝ አገር ኢየገባላቸው ሊገዙ ፩ ሚሊዮን ፻፳፱ሺ፩፻፺፬ ብር ከ፱ መሐለቅ መስጠት ያስፈልጋቸዋል ።

ኢትዮጵያ የጥጡን ስትሰጠን ባለመማርና ባለማሰብ ልጆቿ በአቡጀዲድ ብቻ ባሬቱ ማዕዘን የምናስገብሬትን ገንዘብ በዚህ ሰንጠረዢ እንመልከት ።

	ኲረጃ ።	ብ ር ።	መ
በሸዋ መለስ	፳፬ሺ ፬፻፲፬	፫ሚ ፫፻፹፲ሺ ፯፻፹፫	
በትግሬ መለስ	፲፪ሺ ፪፻፯ ከ፩ ጣቃ	፩ሚ ፯፻፺፱ሺ ፫፻፺፬	፱
በወለጋ ጸሬገር መለስ	፳ሺ ፻፴፰ ከ፬ ,,	፩ ሚ ፻፳፱ሺ ፩፻፺፬	፱
በሐረር መለስ	፯ሺ ፻፫ ከ፯ ,, ,,	፳፻፶፯ሺ ፻፺፩	፲፬
ጥቅል ድምር	፶ሺ፳፻፰፩ ኲረዳ ከ፲፯ ጣቃ	፯ሚ ፶፱ሺ ፱፻፳፩ ብር	

ከዚህ ከ፯ሚሊዮን ፶፱ሺ፱፻፳፩ ብር ለቀረጥና ላገልጋይ የኢትዮጵያ ልጅ የውጭ ሰውዬ የሚያወጣው ፶ሺ፫፻ ብር ያህል ብናነሳ ባጭሩ (አሳንሰን) እንጻሰብነው በቡጀዲ ብቻ ባመት ባመቱ ካገራችን የሚወጣው ገንዘባችን ከ፯ሚሊዮን ፱ሺ፬፻፳፩ የሚ በልጥ ነውና እበክችሁ ትንሽ ትልቁ ተመልከቱት አስቡበት ስል እለምናችኋለሁ ።

እንዳቡጀዲው አስተሳሰብ በቀሩት ዕቃዎች የምንከስረውን ለማወቅ አሳንሰን ያሰብነውን ለክቡራን አንባቢዎች ማቅረብ የተገባኝ የሚያስፈልገኝ ነውና ያገራችንን ጥቅም የምትፈልጉ እንድትረዱኝ ተከተሉኝ ።

፩ኛ

በኢትዮጵያ ብዙ ፈታዮች እንደነበሩ የታወቀ ነው አሁን ቢሆን እነዚያ ፈታዮች ደዋሪዎች የሆኑ ልጆች ብቻ ወልደዋል ማዳወር እንጂ መፍተል የሚያውቁ ጭራሽ የጠፉ ይመስላል ። ለነዚህ ደዋሪዎች ብዙ የሚደውሩትና የሚያደሩት ፈትል እንደሚያስፈልጋቸው የሰሙ ጥጥ የሌለው አገር ፈታዮች ትምርትና ማሰብ በሚባል ሐይል ። መፍተልን ለብረት እንጨቱ አስተምረው በሚያስደንቅ ብልሐት ብረት እንጨቱን ። ንፋስ ውሀውን የሌላቸው ጥጥ ኢያስፈተሉ ጥጡ ከሞላቸው ከፈታዮች ልጆች ፣ ከደዋሪዎች እህቶቻችን በያመቱ ፪ ሚ ፫፻፴ሺ፳፻፸ ብር በፈትል ሰበብ ያስገብሩአቸዋል ።

፪ተኛ ፣

ኢትዮጵያ ባለም ካለው ሲሳይ የጐደላት አንድ ነገር እንደ ሌለ ያለም ሊቃውንቶችና ጥበበኞች መስክረውላታል ምን ይሆናል ልጆችዋ እውቀትና ሥራ የማንወድ የማንስማማ ሰነፎች ነንና እግዚአብሔር የሰጠንን ክብረት ልንጠቀምበት አጥብቀን አልፈለግንምና ነው እንጂ የጨው ኲረብታ እንደሚያስደንቅ ተራራ ባገራችን ተጋድሞ እናየዋለን ፣ የተሰናዳ ጐዳናና የተሰናዳ የጭነት መኪናዎች (ባቡር) በያገራችን ክፍሎች ባይኖሩን ነው እንጂ እንኳን ለኛና ውጭ አገር ሄዶ ብዙ ገንዘብ የሚልክልን ጨው ነበር ። የብረት ሆነ የእንጨት መንገድ እኛ ስለሌለን የብረት መንገድ ያላቸው ሰዎች ከጅቡቲ ባሕር ኢያፈሱ አምጥተው ከ፩ሚ ፻፺፰ሺ ብር የበለጠ ገንዘብ ባመት ባመቱ ሲቀሙብን ይታየኛል ኢትዮጵያውያን ሆይ በነዚህ በቀላል በቀላሉቹ ጉዳታችን አስበን ብልሐቱን ካልፈለግን በየትልልቁ ብናስብ መቼ እመጨረሻው እንደርሳለን? በይ የማይዘልፈረስ ወንዝ ዘሎ ይድናል እንደማለት ይመስላልና ብዙ ብልሐትና ብዙ ችግር በሌለበት ሁሉ እኛ እራሳችንን እንቻል ስል ጥንና ማለት በገሩ ባለው እቃ እራስን መቻል ነው ፤

፫ተኛ ።

እንዶድ የሚባል የሚያስገርም ሳሙና እናታችን ብትሰጠን እኛ በእጅ ብልሐት አሳምረን በሁሉ ስፍራ እንዲያገለግለን እንደነ የጥበብ ሳሙናዎች አላደረግነውምና ነው እንጂ ጥበብን ፈልገን ይዘን ቢሆን ከውጪ አገር ከቶ ምንም ባላስፈለገን ነበር ይኸም የጥበብ ሳሙና ከወንድሙ ከቶ ሻማ ጋራ የእንስሳ ስብ እንጂ እጅግም ሌላ ነገር እንዳያስፈልጉ ታውቃላችሁ ሳሙና ለጤናችን ሆነ ለጥዳታችን እጅግ የሚያስፈልግን ነበር ዛሬ ሕዝባችን እጅግ ያልሰለጠነ በመሆኑ ብዙ ሳሙናና ውሀ የማይፈጅ ሆኖ ብዙ ገንዘብ ባያወጣበት ነው እንጂ ። የጤናን አቆጣጠብ ሲማር «ሲሰለጥን» አያሌ ገንዘብ እንዲያወጣበት እጅግ የሰለጠኑትን ሕዝቦች አኑዋኑር የሚያይ ሰው ሳይረዳው አይቀርም ከውጪ አገር ከሚመጣውና ባገራችንም ከሚሰራው ጭምር ፳፻ሺ ብር ለሳሙና ሻጭ ለባዕድ በያመቱ ሳንገብር አልቀረንም ።

፬ተኛ

ሻማ ኤሌትሪክ ፓሉት አገልግሎቱ በሌሎች አገር ቢያንስ ኤሌትሪክ ለሌለው ለኛ አገር ሕዝብ በጣም የሚያስፈልግን ነው ይልቁንም ለየቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎት ስለዚህ ከ፳፻ሺ ብር የበለጠ እንፈጅበታለን ።

መኪናውን ከማስመጣት በቀር ባገራችን ለመስራት ብዙ ብልሐት ለማያስፈልጉን ነገሮች መንግሥታችን መንገል እንዲያደርጋቸው በመለከትነው እቃዎች ኢትዮጵያ በያመቱ የምትከስረውን ገንዘብ ከብዙው በጥቂቱ የታሰበውን ግብጦ ጥቅል ድምር ላገራቸው ጠቃሚ መኳንንቶች እናሳስባለን ።

መ ሥ ወ ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ከጃፓን መንግሥት ጋራ የንግድና የወዳጅነት ውል መዋዋል ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ከክርስቶስ ልደት በፊትና ከክርስቶስም ልደት በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ወደ ሮማ ወደ ግሪክና ወደ ፓርቱጊዝ ወደ ምስርም ምድረ ግብጽ እየተላላከ የወዳጅነት መገናኘት እንደ ነበረው የታወቀ ነው ።

ነገር ግን በ፲፭፻፲፭ ዓ ም በዓፄ ልብነ ድንግል ዘመን በተነሣው በመሐመድ ግራኝ ምክንያት የኢትዮጵያን ዙሪያ እስላሞችና አረማውያን ስለ ያዙት የኢትዮጵያ መንግሥት የመላላኪያ መንገድ በለማግኘቱ ከውጭ አገር መንግሥቶች ጋራ ሳይገናኝ ቆይቶ ነበርና በአፄ ቴዎድሮስና በአፄ ዮሐንስ ዘመን እንደ ገና መላላክ ተጀመረ። በጃንሆይ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን

ግን በኢትዮጵያ ዙሩያ ብዙ የባሕር መንገድ ስለ ተከፈተ የኢትዮጵያ መንግሥት ከትልልቆቹ የአውሮጳ መንግሥቶች ጋራ የንግድና የወዳጅነት የሌላም የልዩ ልዩ ዓይነት ውል ተዋዋለ ።

አሁን ደግሞ ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት በእውቀትና በጥበብ ወደ ፊት እንድትሄድ ማሰባቸውና ሥራ መጀመራቸው በዓለም ላይ ስለ ተሰማ ከቀድሞው የዓለም ክፍል ከእስያ እጅግ የራቀው የጃፓን ንጉሠ ነገሥት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ የንግድና የወዳጅነት ውል ለመዋዋጃ ሚኒስቲሩንና ቆንስሉን ወደ ኢትዮጵያ ላከ ። ሚኒስቲሩና ቆንስሉም አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በራሳቸው ስም ሆነው በሰኔ ፲፭ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ውሉን ተጻጽፈው ተፈርሞ ለጃፓን ንጉሠ ነገሥት መላክተኛው አስረከቡት ።

ይኸውም ውል ትልቅ የወዳጅነት ሥራ ስለ ሆነ ልዑል አልጋ ወራሽ የጃፓኑን ሚኒስቲር ከኢትዮጵያ መኳንንት ጋራ ራት ጋበዙት ሚኒስቲሩም በማግሥቱ ልዑል አልጋ ወራሽን ከመኳንንቶቻቸው ጋራ ራት ጋበዘ ከዚህም በኋላ በሰኔ ፲፱ በባቡር ተሳፍሮ ወደ ሀገሩ ተመለሰ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ወዳጆቹ ሲበዙለት ንግዱ እየሰፋ ሕዝቡ መበልጠጋቸው አይጠርጠርም ሕዝቡም ሲበለጥጉ መንግሥቱ ኃይሉና መታመኑ ጸንቶ ይኖራል

ስለ ሀገር ልማት ።

ስለ ሀገራችን ልማት የምትጣጣሩ ክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ ቀጥየ የጻፍኩትን እንድትመለከቱልኝ ስል አስቀድሜ ይቅርታችሁን እለምናለሁ ።

ከእግዚአብሔር በታች ለድኃ ጠባቂው መንግሥት ቀጥሎም መኳንንቶች ናቸው መንግሥትም ድኃ እንዳይጐዳ አገር እንደይጠፋ መኳንንቶችን ጠብቁ ብሎ በየአውራጃው ይሾማቸዋል ለመንግሥትም ኃይሉ መኳንንቱና ሕዝቡ ነው መኳንንቶችም ከሰው በልጠው አምረው ከብረው መታየታቸው በሕዝብ ላይ ነው ።ጌታችን ኢየሱስክርስቶስ ሐዋርያትቶችን ሑሩ ወመሐሩ ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም ብሎ ሥልጣን ሰጥቶ ሲልካቸው በዚህ ዓለም የወንድሞቻችሁን ጥቅም እንጂ የራሳችሁን ጥቅም አታስቡ ለናንተስ ጥቅማችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያስብላችኋል ብሎ እንዳዘዛቸው መጻሕፍት ይነግሩናል ነገርግን እነኝህ ከላይ በየአውራጃው መንግሥት ድኃን ጠብቁ ብሎ ይሾማቸዋል ያልናቸው መኳንንቶች መንግሥት ወስኖ በሰጣቸው ሕግ ሥርዓት ላይ ሕዝባቸው የሚበለጥግበትን መንግሥታቸው የሚጠቅምበትን የሥራመንገድ እየፈለጉ ተስማምተው መስራት ትተው የራሳቸውን የዕለት ጥቅም ብቻየሚመለከቱ ይመስላሉ ። ነጋዴ ካንድ ሀገር ወደ አንድ ሀገር የንግድ ዕቃ ለማስተላለፍ የፈለገ እንደሆነ የዳኛ ጦር እልፍ ነው ባንዱ ቢስት ባንዱ ይወጋል እንደሚሉ በየአንዳንድ ሀገር ገጀ ግዛት ላይ ፩፫ ኬላ እየተሰራ ካንዱ ቢስት አንዱ ያዘው እሰረው ፍታው እየተባባሉ ትርፉ ጨርሶ እ- ስማሉን እስከሚአጐድል ያስጨንቁታል ይህንም ማድረግ ነጋዴን አትነግድ ብሎ በዋጅ መከልከል ይመስላል ምናልባት ነጋዴ በንግዱ መንግሥትን ወይም ሀገረ ገጀን አይጠቅምም የሚል ቢኖር ብዙ መንግሥቶች ንግድን አስፍተው በደምብ በማስተላለፋቸው እንዴት እየባለጠጉ እሻግሮ ይመልከት ደግሞም እዚሁ እቅርቡ በሀገራችን ውስጥ እንደ ሐርር አውራጃ ከመሰለው ሁሉ በንግድ ብቻ ከሚገኘው ሐብት መንግሥታችን ምን ያህል እንደሚረዳ ይመርምር ገበሬና ዘላንም ቢሆኑ መከራቸው ከነጋዴ ባይበዛ አያንስም እነኝህም ሁለቱ በስራቸው ከሚያገኙት ሐብት እንደ ነጋዴ ግብራቸውን ለመንግሥትም ሆነ ወይም ለሀገረ ገገሮች መስጠታቸው አይቀርም እንግዲህ መንግሥት በየአውራጃው የሚሾማቸው ሀገረ ገገሮች የነኝህን የሰስቱን ሰራተኞች ጥቅም ካልጠበቁ መንግሥትም መኳንንትም ወታደርም ጥቅማቸውን አጡ ማለትነው መቸም በሀገራችን ያለ ዋና ሥራ ይኸው ፫ቱ ብቻ ይመስለኛል ነጋዴ ነግዶ ካልተረፈ ገበሬ አርሶ ካልጠገበ ዘላን ከብት አርብቶ ጥቅም ካላገኘበት ሁለቱም ባንድነት በሐብታቸው እየተረዳዱ ሀገራቸውን መንግሥታቸውን በመጥቀም ፈንታ በድኅነታቸው እየተሰደዱ የባዕድ ሕዝብ ተራወጅ መዘባበቻ እየሆኑ ይኖራሉ ።

ይቤ በላይነህ ገብረ ሥላሴ

ስለ መረዳዳት ።

በሶስተኛው ዓመት ቁጥር ፳፬ ገጽ ፪፻፶፱ የብርሃንና ሰላምን ድግስ በመደገስ እንድንረዳዳ ላሳሰቡን ለክቡር ተማኑሮምሃ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቅርቤ በድንቁርና መጋዘ (ጢሰኝነት) ከመረትሁት ምርት በቲንሽ ቀለም ቁና ሰፍሬ በስስ አቁማዳ ወረቀት ቋጥሬ በደካማ በቅሎ ብርዕ ጭኜ መልከም ኃሳብ የሚባል ቆርቋሪዬን አስቤ ተስፋ የሚባል ነጋዲዬን አሰናድቼ ከበር ቁሜ አለሁና እርዳታዬ ምንም ማኅበረተኞችን የምያጠግብ ባይሆን ፡ ለልጆቹ ሰርግ የደገሰ ብርሃንና ሰላም ንጉሥ አከናውኖ ለመናገር ለሠርግ የሚሆን ጥበብልብስ ሳትለብስ ለምን ገባህ ብሎ ፡ ወደ የጭለማ ዳርቻ ተስፋ መቁረጥ አውጥቶ የልቡና እጅ እግሬን በስንፍናሰንሰለት አስሮ ጥርስ ማፋጨት ቅናት ካለበት ቦታ እንዳይጥለኝ በእውቀት የምታገለግሉት መላልሳችሁ እንድትለምኑት እማልዳችኋለሁ ። ብርሃንና ሰላም አባት ፡ ልጆቹን ሠርቶ ቀጥቶ እንዲያኖር ልጆቹም በሠራላቸው ሥራት ባስተማራቸው ትምሕርት እንደፀኑ መላው ዓለም ተረድቶታል ነገር ግን በጥቂት ዘመን ፈጽሞ አልሰለጠነ ብሎ ለማማት በጣም ያስቸግራል ። ስንኳንስ ፍጡርና ሁሉን በቅጽበት ማድረግ የሚቻለው አምላክ ዓለምን ሲፈጥር ባንድ ጊዜ አልፈጠረውም በየዕለቱ በየሰዓቱ ፈጥሮታል እንጂ ዳግመኛ ዩኅን የመሰለ በየጊዜው የሠራው ብዙ ምስክር አለ ። ዳሩ ግን ይህን ምስክር መቁጠር አያስፈልገንም ። የሚያሸንስ ሕዝባችንን በፍጥነት ማስተማር ነው ። እስኪ አሁን በመላ ኢትዮጵያ ይቅርና ባንዲት ከተማ ብቻ ስንት ሥራ ፈቶች ሕፃናት እንዳሉ እናስብ እነሱም ከመንገድ ዳር እየተሰበሰቡ ሲላፉ ወጭ ወራጁን አላፊ አግዳሚውን ሲያስቸግሩ ይኖራሉ ። ለነዚህም አንድ ሥርዓት ቢሠራ ለመንግሥታችን የከበደ ነገር መስሎ እንደማይታየው አምናለሁ ሥርዓቱንም ከዚህ አስከትዬ እጽፋለሁ

በሃገራችን ከቀድሞ ጀምሮ የጭራ ብር እየተባለ ክብት ያለው ሰው ሁሉ በየአገባቡ የተሠራለትን ቀረጥ ለመንግሥት ይከፍላል ። ይህም ክብት እግዚአብሔር በቸርነቱ ለፍጥረቱ ያበቀለውን ሣር በልቶ ውሀ ጠጥቶ ይኖራል እንጂ ሰው ከደከመበት አንዳች ለልብሴ ለጉርሴ አምጡ ብሎ የሚያስቸግርበት ነገር የለውም ። በዚህም ላይ የሰው ተገዢ ሆኖ ፈቃዱን ፈፅሞለት ይኖራል እንጂ ሰሙን ሲያውክ አልሰማንም አላየንም። እንግዴህ እንዴህ ሲሆን እነዚህ ሥራ ፈትተው ማነንም ሲሰድቡና ሲደበድቡ የሚኖሩ የሕፃናት አባት እናቶችን ልጅ ባለህ ቀረጥ አውጣ ብለው ሊያስገድዱዋቸው እንደ ምን የተገባ ይሆን ለእናት ላባታቸውስ ልጆቻቸው ሰው በሰደቡ በገደሉ በደበደቡ ቁጥር ካሳ የነፍስ ዋጋ መቀጫ አምጡ እየተባሉ ልጆቻቸው መከራ ወድቆባቸው እያዘኑ ከሚሰጡት ገንዘብ ይልቅ ከትምሕርት ቤት በሕይወት እያዩዋቸው በደስታ ገንዘባቸውን ቢሰጡ የማይሻላቸውን ነው ። እስመ ርቱዕ ዘኒ የሐርስ እንዘ ይሴፎ ምርካበ የሐርስ ፤ ወዘኒ ያከይድ እንዘ ይሴፎ ምርካበ ያከይድ ። ወእመሰ ንሕነ ዘራዕነ ለክሙ ዘመንፈስ ቅዱስ ዐቢይኑ ውእቱ ሰበ ንሕነ ነዓርር ለክሙ ዘሥጋ ሰብአ እንዲል ። ፩ቆሮ ፱ ፲-፲፩ ። ገበሬ በክረምት በጭቃ መከራውን እየተቀበለ ማረሱ መዝራቱ ኋላ በመከር ጊዜ ጥቂቱ ብዙ ሆኖልኝ በደስታ እመገበዋለሁ ብሎ አይደለምን ፤ መንግሥትስ ሕዝቡ ሥርዓቱን አፍርሶ በተገኘ ጊዜ ባጠፋው ጥፋት መጠን ቅጣቱን እንዲቀበል ሲያዝዝ የማይራራ ሲሆን አስቀድሞ ባለ ማወቅ እንዳያጠፋ የሚማርበት ገንዘብ አምጣ ብሎ ቢያስገድደው ከጭካኔ ይቆጠርበታልን ። በከንቱማ ርኅራኄ የሚገባ ከሆን ሠርቆ ቀምቶ ደብድቦ ገድሎ ሲገኝ ምነው አበጀህ ብሎ አይምረው አሁንስ ከዚህ ሁሉ መከራ እንድትድን የምትማርበት ገንዘብ አውጣ ብሎ ማስገደድ ምን ከጭካኔ ይቆጠራል ፤ ለኔ እንደሚመስለኝ ልጅ ባለህ ይህን ያህል ገንዘብ አውጣ ብሎ መንግሥት እንደ ፈቀደ ቀረጥ ማስወጣት ለከፈለውም ገንዘብ የደረሰኝ ሰጥቶ ልጁን ከትምርት ቤት ማግባት ከዚህ በኋላ ልጁ ስራ ፈቶ የተገኘ እንደ ሆነ መቀጫ ማስከፈል ይሻላል ላባቶቻቸውም ልጆቻቸው ሥራ ፈተው በየሰዓቱ መብል መጠጥ በየዕለቱ ልብስ ጌጥ አምጡ ብለዋቸው ገንዘባቸውን ባጥቂት ቀን በከንቱ ከሚጨርሱ ልጆቻቸው ሥራ ይዘው ገንዘባቸው ለብዙ ቀን በቁም ነገር ቢሆን እንዲሻላቸው አያጠራጥርም ። እኔስ አንድ ነገር ይገርመኛል ሰው ሁሉ ገንዘቡን በወለድ ሲያበድር እንደሱ ያለ ያልታመነ ጓደኛውን ዋስ እየቀጠረ ለማይረባ ብር ወለድ ሲሰጥ መንግሥት እኔ ልዋስና ገንዘባችሁን ለብዙ ወለድ ላበድርላችሁ ቢል እምቢ የሚለው መንግሥቱን ጠርጥሮት ነውን ወይስ ከመንግሥት ባለ ዕዳነት ባንድ ቀን ችግር የሚጠፋ ንብረት ያለው የድኃው ባለእዳነት ይሻላል ብሎ ነው ።

የስንፍናችን መጀመሪያ የሀገራችን ሰው ሁሉን ነገር መንግሥት ያውቃል ብሎ ሀሳቡን ሁሉ በመንግሥት ላይ ይጥላል መንግሥት ያለ ሕዝብ ምን መሥራት ይችላል ። ይህነንም ስለጻፍሁ ብዙ የሚነቀፈኝ ሰው እንዳለ ተረድቻለሁ (ስለምን) ይህን የመሰለ ቃል የጻፉ እንደኔ ያሉ ድኆች ናቸው እንጂ ከባለፀጎች ወገን አንዳቸው ስንኳ አልጻፉምና ። ነገር ግን ብርሃንና ሰላምን የመሰለ መዓዛ ቃሉ ልብ የሚመስጥ ምግብ ሲደገስ ባለማይዎች ሊረዱ ይገባቸው ነበር አለመርዳታቸው ግን መጀመሯ የሚፈረድ በነሱ ስለሆነ ነው በነሱ መጀመሯ የሚፈረድባቸው ስለምን ነው ብሎ የሚጠይቀኝ ሰው ቢኖር እንደኔ ያለ ድኃ ሲደግስ ባይጣፍጥለት ባይኖረው ነው ተብሎ ይታዘንለታል እንጂ አይነቀፍም እኒያ ግን ድግሳቸው ቢጠፋ ሁሉ አይነት አቃቂር ሳላቸው የወደደ ይመገብ የጠላ ይተው ብለው ያጠፉት ይመስላልና ስለዚህ ነው ብዬ እመልስለታለሁ ። የሆነ ሁኖ በሆድ ውስጥ አጥንት ሁኖ ከቀረ ጽንስ የጨነገፈ ይሻላል (ልጁ ቢሞት እናቲቱ ትድናለችና) ስለዚህ ምንም ባይደረግ እየተናገራችሁት ይቅር እንጂ ላይደረግ ምን አደከመን ብላችሁ ቸል እንዳትሉ የብርሃንና ሰላም አሰናጂዎችን ሁሉ ደግሜ ደግሜ እማልዳችኋለሁ።

ከዚህ አስከትዬ ቲንሽ ምስጋና አቀርባለሁ ።

(ሥላሴ)

ፈጠረኒ ኃይለ ሥላሴ ትቤ ጥበብ መርዓተ ቤቱ ከመ እኩን አነ መቅድመ ተግባሩ መንግሥት ።

ኢትኃድር ብሒቱ ውስተ ነፍስ ምይንት ።

ወርእሳ ተዌድስ አኮኑ በብዝኃ ብርሃኑ ትፍሥሕት ።

ያሰስል ለነ ግብረ ጽልመት ።

ኃይለ ሥላሴ ዘመጽአ እምዘርዓ ዳዊት ።

ሰላመ ይጸጉ ለነገሥት ለአሕዛብ ወለበሐውርት ።

አረረም መረረ ማኅበሬን ከፈልኩ እንደሚሉ ሁሉ መስተንግዶ ቃሉ አልተካከለምና ። (ሙሴ ልቡናዬ) አሳብ ዓይኔ ባሳሳበት ። ንግግር እጄ ባዳላበት (ከ) ለሊቅ (ከ) ለአፈ ሊቅ ማሩኝ ሲል ከፊታችሁ ወድቆ ይቅርታችሁን ይለምናል ።

ሞገስ ዓምደ ሚካኤል ።

ከንቅልፍ ስለ መንቃት ።

በሶስተኛው ዓመት ቁጥር ፳፱ ብርሃንና ሰላም በደስታ (ወይም በናፍቆት) ከመጀመሯው እስከ መጨረሻው እያነበብሁ ስመለከት በጣም ልብ ብዬ አእምሮዬን የጣልሁበት ቃል ያቶ ጥሩነህ ክብትህ ይመርና ያቶ ዘውዴ በየነ ንግግር ነበር ። የነዚህ የሁለቱ ወንድማማች አሳብ ልቤን በኃዘን ሰብሮኝ (አድክሞኝ) አሁን ካሁን ትሰጠኝ ብሎ የናቱን ጡት እንደናፈቀ ልጅ ሁኜ ራሴን በሁለት ጉልበቴ ውስጥ አምቄ ስተክዝ በስተደጅ ሰው መጥቶ ያለሁበትን ቤት መዝጊያ ኳ ኳ አደረገው ። እኔም እንደሀገሩ ልማድ ከተቀመጥሁበት ስፍራ ቶሎ ብድግ አልሁና ደጃፉን ብቅ ብዬ በስተ ደጅ የመጣውን እንግዳ እቤት እንዲገባ ለመንሁት ። በስተውጭ የመጣው እንግዳም እቤት ገብና በተቀመጠበት ወንበር ሁኖ ትክዜዬን ይመለከት ጀመር ፤ የኔም ኀዘን አፍአዊ ያይደለ ውስጣዊ ነበርና የመጣበትን ነገር እጠይቀው ዘንድ አልተቻለኝም ብቻ እኔም ሳልጠይቀው እርሱም ሳይነግረኝ አምስት ደቂቃ ያህል ቄይታ አደረግን ከስድስተኛው ደቂቃ በኋላም በስተደጅ የመጣው እንግዳ «ም

ነው ወንድሜ በጣም ተክዝሃል ? በሚል ጥያቄው ከባድ በሆነ ኀዘን የተደቆሰውን ልቤን ቀሰቀሰው ፡ እኔም ለጊዜው ሌላ መልስ ልሰጠው አልቻልሁም ። ብቻ ቶሎ ብዬ ብርሃንና ሰላም የሚ ባል ስልጡን መላክተኛ አንስቼ ከመጀመሪያው ይዤ አንብለት ጀመርሁ ። መላልሼ እያነበብሁ ያስረዳሁት ቃልም ከ፪ኛ፫ ገጽ የሚገኝ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ቃል ነው ። በዚ ሁም ዘመን ያለን የኢትዮጵያ ሕዝብሳ ከትልቅ እስከ ትንሽ ድረስ ብርሃን ፈጽሞ ባገራችን እንዲደምቅ ሰላምም እንዲበዛ ምን ሥራ ሠራን ? ለጥቅም የሚሆን ሥራችንስ ወዴት አለ ? ብርሃንና ሰላም ብሎ በመናገር ብቻስ ምን ረብ አገኘን ? ይህነ ንም ጥያቄ ብንመረምረው የውስጥ አንጀታችንን የሚበጥስ ነው ማለት መሪና ተመሪ ሁላችን ተኝተናል ። በዓለምም ከለ ሁሉ እንደኛ የተመቸው ሰው ያለ አይመስለንም ። እንቅልፉም በጣም ጣፍጦናልና አንድ ስንኳ ከኛ ከመኝታው ለመነሳት ሰውነቱን ያንቀሳቀሰ የለም ፤ ከላይኛው ደረጃ ወደ ታችኛው ደረጃ አዘቅዝቀን ወድቀን ከወደቅንበትም በታ ተኝተናል ። አሁንም እባካችሁ ወንድሞቼ እንነሳ ብሎ የሚያስብ የለም ። እስተሚል ቃል ድረስ መላልሼ አነበብሁለት ። ከዚያ በኋላም ተከታዩን እያነበብሁለት ወረድሁና «አሁንም ያንቀላፋውን ህዋሳታችን የሚያነቃቃ ደወል እንደውላለን ። «ተነሡ ተነሡ» ወንድሞቼ ሆይ «ተነሡ አገራችንን የሚጐዳ ምክንያት ዋና እይነተኛው ብርሃንን ከማጣት የተነሣ ነው» ፡ ከሚል መስመር ደርሼ ያንደኛውን አሳብ ጨርሼ የሁለተኛውን አነብለት ጀመርሁ

የሁለተኛውም አሳብ በገጽ ፪፻፲፬ በመጀመሪያው ዓምድ ባንደኛው መስመር የሚገኘውን «የሰው ልጅ ዘር ንቀት» ከሚ ለው አንስቶ ስሙ እስካለበት ድረስ የአሜሪካን ጥቁሮች የሚያገኙትን ግፍ ሳነብለት «የነጮች ልጆች ብልህም ቢሆኑ ብልህም ባይሆኑ የጠዳውን ሥራ ያገኛሉ ። ያውም የኦፌስ ሥራ የጥቁር ልጆች ግን ሥራ በተወደደ ጊዜስ ተነክቶቼው ሥራ ለማገኘት አይችሉም ። ሌላስ ይቅርና አንድ ጥቁር ሰው ብዙ ዓመት ሲሠራበት ከነበረ ስፍራ ሥራ ሲወደድ ሠራተኛ ሲበዛ ያን ጥቁር ሰው ያስወጡና ሥራውን ለነጭ ይሰጡታል ። ይህ ም ነገር እርስ በርሳቸው መተጋገዛቸውን ያሳያል ። ከሚለው መስመር ደርሼ አስሬ ሁለተኛው ክፍል ልጀምር ስል አብሮኝ የተቀመጠው ሰውዬ ትንሽ አረፍ በል ላጫውትህ አለና ቀጥሎ ያለውን አጭር ቃል ነገረኝ ። እላንተ አሜሪካ ላይ በሚሠራው ሥራ ታዝናላችሁ እኔ ግን እኛ ድረስ እንዳይመጣ እስጠነቅቃለሁ አለና ነገሩን ባጭሩ ተወት አደረገው ። እንደ ምን ብለው ዘበ እዝን ሰሚዓ ለይስማዕ አለኝ ። ከዚያ በኋላ እኔም ጋዜጣውን አንብቤ ጨረስሁና እርሱም ተነስቶ እቤቱ ሄደ ።

ክቡራን ጌቶቼና ወንድሞቼ ሆይ አቶ ጥሩነህ ካብትህ ይመር መሪና ተመሪ ሁላችን ተኝተናል ብሎ በርሳስና በወረቀት መላ ክተኛ ሲቀሰቅሰን ጊዜ ልብ ብሎ ለሰማው ሰው ይህ በጣም የሚያነቃቃ ቃል ነው ፤ መሪ ስል በየወረዳው ያሉ የሥራ አለ ቆች ማለቱ ነው ። ተመሪ ሲልም በነሱ እግር ሁነን የምንሠራ ሠራቶኞችን ነውና ፡ አሁንም ሁላችን ባንድነት የወንድማችንን የፍቅር ቃል ብርሃንና ሰላም ከተባለ መላክተኛው በፍጥነት ተቀብለን ቶሎ ከከባድ እንቅልፋችን ነቅተን አይቴ ብሔሩ ለጥበብ ወአይቴ ማህደሩ ወበአይቴ ይትረከብ አሰረ ፍኖታ እያ ልን ሥራ ፍለጋ እንሂድ ። አይሆንም አይሆንም የተመቼ ጊዜ ካለፈ በኋላ ባለፈው ጊዜያችን ብንጸጸት ነፋስን እንደመ ጨበጥ ያህል ነው ።

ፍስሐ ወልደ ሚካኤል



ክቡር ልጅ ፍቅረ ሥላሴ ከተማ
የኢ መ አ ወ ተፈሪ መኰንንን ማተሚያ ቤት እንደጐበኙ

ሰኔ ፲፫ ቀን ክቡር ልጅ ፍቅረ ሥላሴ ከተማ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን ማተሚያ ቤትና መጻሕፍት ቤት አይተው በሥራው ሁሉ ደስ ብሎዋቸው አመስግነው የአምሳ ብር መጻሕፍት ገዝተው ሔዱ ። ማተሚያ ቤትንና መጻሕፍት ቤት ን ለማየት መምጣታቸውና መጻሕፍት መግዛታቸው የዕውቀት ወዳጅ መሆናቸውን ያስረዳል ።

ብርሃንና ሰላም እንደዚሁ ለመሰሉ ዕውቀት ፈላጊዎች ወዳጆቹ ምስጋናውን ከማቅረብ አይቦዝንምና ክቡር ልጅ ፍቅረ ሥላሴን በጣም ያመሰግናቸዋል ።

የክቡር ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው ልጅ
ክርስትና መነሣት

ሰኔ ፲፱ ቀን ከሌሊቱ በ፲ ሰዓት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥ ታትና ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ከብዙ ክቡራን መኳንንትና ሠራዊት ጋራ ወደ ገብርኤል ቤተ ክርስቲ ያን ሄዱ ። ክቡር ፊታውራሪ ደስታና ክብርት ወይዘሮ ተናኘ ወርቅም ልጃቸውን ክርስትና ለማስነሣት በገብርኤል ቤተ ክር ስቲያን ገቡ ። ልጂቷን ክርስትና ያነሱም ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ናቸው ።

የክርስትናው ሥርዓት ተፈጽሞ ከተቀደሰ በኋላም ፍስሐ ለማ የተባለ ደብተራ የሚከተለውን ቅኔ ተቀኘ ።

ክብር ይእቲ ።

ከዋክብተ ሰማይ አእሩግ መንንዎ ለዘቀዳማዊ ልማድ ።
እንዘ ይእኀዙ ምድረ እስመ ተንሥኡ ለወልድ

በሃገራችን ከቀድሞ ጀምሮ ‹ጭራ ብር እየተባለ ከብት ያለው ሰው ሁሉ በየአገባቡ የተሠራለትን ቀረጥ ለመንግሥት ይከፍላል ። ይህም ከብት እግዚአብሔር በቸርነቱ ለፍጥረቱ ያበቀለውን ሣር በልቶ ውሀ ጠጥቶ ይኖራል እንጂ ሰው ከደከመበት አንዳች ለልብሴ ለጉርሴ አምጡ ብሎ የሚያስቸግርበት ነገር የለውም ። በዚህም ላይ የሰው ተገዢ ሆኖ ፈቃዱን ፈጽምለት ይኖራል እንጂ ሰውን ሲያውክ አልሰማንም አላየንም ። እንግዴህ እንዴህ ሲሆን እነዚህ ሥራ ፈትተው ማነንም ሲሰድቡና ሲደበድቡ የሚኖሩ የሕፃናት አባት እናቶችን ልጅ ባለህ ቀረጥ አውጣ ብለው ሊያስገድዱዋቸው እንደ ምን የተገባ ይሆን ለእናት ላባታቸውስ ልጆቻቸው ሰው በሰደቡ በገደሉ በደበደቡ ቁጥር ካሳ የነፍስ ዋጋ መቀጫ አምጡ እየተባሉ ልጆቻቸው መከራ ወድቆባቸው እያዘኑ ከሚሰጡት ገንዘብ ይልቅ ከትምሕርት ቤት በሕይወት እያዩዋቸው በደስታ ገንዘባቸውን ቢሰጡ የማይሻላቸውን ነው ። እስመ ርቱዕ ዘኒ የሐርስ እንዘ ይሴፎ ምርከቦ የሐርስ ፤ ወዘኒ ያከይድ እንዘ ይሴፎ ምርከቦ ያከይድ ። ወእመሰ ንሕነ ዘራዕነ ለክሙ ዘመንፈስ ቅዱስ ዐቢይኑ ውእቱ ሶበ ንሕነ ነዓርር ለክሙ ዘሥጋ ሰብእ እንዲል ። ፩ቆሮ ፱ ፲ ፲፩ ። ገበሬ በክረምት በጭቃ መከራውን እየተቀበለ ማረሱ መዝራቱ ኋላ በመከር ጊዜ ጥቂቱ ብዙ ሆኖልኝ በደስታ እመገበዋለሁ ብሎ አይደለምን ፤ መንግሥትስ ሕዝቡ ሥርዓቱን አፍርሶ በተገኘ ጊዜ ባጠፋው ጥፋት መጠን ቅጣቱን እንዲቀበል ሲያዝዝ የማይራራ ሲሆን አስቀድሞ ባለ ማወቅ እንዳያጠፉ የሚማርበት ገንዘብ አምጣ ብሎ ቢያስገድደው ከጭካኔ ይቆጠርበታልን ። በከንቱማ ርኅራኄ የሚገባ ከሆነ ሠርቶ ቀምቶ ደብድቦ ገድሎ ሲገኝ ምነው አበጀህ ብሎ አይምረው አሁንስ ከዚህ ሁሉ መከራ እንድትድን የምትማርበት ገንዘብ አውጣ ብሎ ማስገደድ ምን ከጭካኔ ይቆጠራል ፤ ለኔ እንደሚመስለኝ ልጅ ባለህ ይህን ያህል ገንዘብ አውጣ ብሎ መንግሥት እንደ ፈቀደ ቀረጥ ማስወጣት ለከፈለውም ገንዘብ የደረሰኝ ሰጥቶ ልጁን ከትምርት ቤት ማግባት ከዚህ በኋላ ልጁ ስራ ፈቶ የተገኘ እንደ ሆነ መቀጫ ማስከፈል ይሻላል ላባቶቻቸውም ልጆቻቸው ሥራ ፈተው በየሰዓቱ መብል መጠጥ በየዕለቱ ልብስ ጌጥ አምጡ ብለዋቸው ገንዘባቸውን ባጥቂት ቀን በከንቱ ከሚጨርሱ ልጆቻቸው ሥራ ይዘው ገንዘባቸው ለብዙ ቀን በቁም ነገር ቢሆን እንዲሻላቸው አያጠራጥርም ። እኔስ አንድ ነገር ይገርመኛል ሰው ሁሉ ገንዘቡን በወለድ ሲያበድር እንደሱ ያለ ያልታመነ ጓደኛውን ዋስ እየቀጠረ ለማይረባ ብር ወለድ ሲሰጥ መንግሥት እኔ ልዋስና ገንዘባችሁን ለብዙ ወለድ ላበድርላችሁ ቢል እምቢ የሚለው መንግሥቱን ጠርጥሮት ነውን ወይስ ከመንግሥት ባለ ዕዳነት ባንድ ቀን ችግር የሚጠፋ ንብረት ያለው የድኃው ባለእዳነት ይሻላል ብሎ ነው ።

የስንፍናችን መጀመሪያ የሀገራችን ሰው ሁሉን ነገር መንግሥት ያውቃል ብሎ ሀሳቡን ሁሉ በመንግሥት ላይ ይጥላል መንግሥት ያለ ሕዝብ ምን መሥራት ይችላል ። ይህነንም ስለጻፍሁ ብዙ የሚነቀፈኝ ሰው እንዳለ ተረድቻለሁ (ስለምን) ይህን የመሰለ ቃል የጻፉ እንደኔ ያሉ ድኖች ናቸው እንጂ ከባለፀጎች ወገን አንዳቸው ስንኳ አልጻፉምና ። ነገር ግን ብርሃንና ሰላምን የመሰለ መዓዛ ቃሉ ልብ የሚመስጥ ምግብ ሲደገስ ባለሚይዎች ሊረዱ ይገባቸው ነበር አለመርዳታቸው ግን መጀመሪያ የሚፈረድ በነሱ ስለሆነ ነው በነሱ መጀመሪያ የሚፈረድባቸው ስለምን ነው ብሎ የሚጠይቀኝ ሰው ቢኖር እንደኔ ያለ ድኃ ሲደግስ ባይጣፍጥለት ባይኖረው ነው ተብሎ ይታዘንለታል እንጂ አይነቀፍም እኒያ ግን ድግሳቸው ቢጠፋ ሁሉ አይነት አቃቂር ሳላቸው የወደደ ይመገብ የጠላ ይተው ብለው ያጠፉት ይመስላልና ስለዚህ ነው ብዬ እመልስለታለሁ ። የሆነ ሁኖ በሆድ ውስጥ አጥንት ሁኖ ከቀረ ጽንስ የጨነገፈ ይሻላል (ልጁ ቢሞት እናቲቱ ትድናለችና) ስለዚህ ምንም ባይደረግ እየተናገራችሁት ይቅር እንጂ ላይደረግ ምን አደከመን ብላችሁ ቸል እንዳትሉ የብርሃንና ሰላም አሰናጂዎችን ሁሉ ደግሜ ደግሜ እማልዳችኋለሁ።

ከዚህ አስከትዬ ቲንሽ ምስጋና አቀርባለሁ ።

(ሥላሴ)

ፈጠረኒ ኃይለ ሥላሴ ትቤ ጥበብ መርዓተ ቤቱ ከመ እኩን አነ መቅድመ ተግባሩ መንግሥት ።

ኢተኃድር ባሕቱ ውስተ ነፍስ ምይንት ።

ወርእሳ ትዌድስ አኮኑ በብዝኃ ብርሃኑ ትፍሥሕት ።

ያሰስል ለነ ግብረ ጽልመት ።

ኃይለ ሥላሴ ዘመጽአ እምዘርዓ ዳዊት ።

ሰላመ ይጺጉ ለነገሥት ለአሕዛብ ወለበሐውርት ።

አረረም መረረ ማኅበሬን ከፈልኩ እንደሚሉ ሁሉ መስተንግዶ ቃሉ አልተካከለምና ። (ሙሴ ልቡናዬ) አሳብ ዓይኔ ባሳሳበት ። ንግግር እጄ ባዳላበት (ከ) ለሊቅ (ከ) ለአፈ ሊቅ ማሩኝ ሲል ከፊታችሁ ወድቆ ይቅርታችሁን ይለምናል ።

ሞገስ ዓምደ ሚከኤል ።

ከንቅልፍ ስለ መንቃት ።

በሶስተኛው ዓመት ቁጥር ፳፬ ብርሃንና ሰላም በደስታ (ወይም በናፍቆት) ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው እያነበብሁ ስመለከት በጣም ልብ ብዬ አእምሮዬን የጣልሁበት ቃል ያቶ ጥሩነህ ከብትህ ይመርና ያቶ ዘውዴ በየነ ንግግር ነበር ። የነዚህ የሁለቱ ወንድማማች አሳብ ልቤን በኃዘን ሰብሮኝ (አድክሞኝ) አሁን ካሁን ትሰጠኝ ብሎ የናቱን ጡት እንደናፈቀ ልጅ ሁኜ ራሴን በሁለት ጉልበቴ ውስጥ አምቄ ስተክዝ በስተደጅ ሰው መጥቶ ያለሁበትን ቤት መዝጊያ ኳ ኳ አደረገው ። እኔም እንደሀገሩ ልማድ ከተቀመጥሁበት ስፍራ ቶሎ ብድግ አልሁና ደጃፉን ብቅ ብዬ በስተ ደጅ የመጣውን እንግዳ አቤት እንዲገባ ለመንሁት ። በስተውጭ የመጣው እንግዳም አቤት ገባና በተቀመጠበት ወንበር ሁኖ ትካዜዬን ይመለከት ጀመር ፤ የኔም ኀዘን አፍአዊ ያይደለ ውስጣዊ ነበርና የመጣበትን ነገር እጠይቀው ዘንድ አልተቻለኝም ብቻ እኔም ሳልጠይቀው እርሱም ሳይነግረኝ አምስት ደቂቃ ያህል ቈይታ አደረግን ከስድስተኛው ደቂቃ በኋላም በስተደጅ የመጣው እንግዳ ‹ም

እለተ ዓርብሰ የዋህ ዘኢኅደረ ለባዕድ
መንጦላዕተ ጽልመት ገብረ እንዘ ይሰቲ ጽዋዓ ሞቱ ዋህድ

እጣነ ሞገር

አክለ ደቂቅ ዮሐንስ ለዘአጥመቆ እሳት ።
ሰመዮ ብርሃነ ውስተ ጽልመት
ወእምድኅረ ተጠምቀ በረከሙ እንዘ ቅውማን አርድዕት
በአንብሮተ እድ ለሕፃናት
እስመ ለእሉ ይእቲ ዘመንግሥተ ሰማይ እረፍት
ወተሰብረ በኃይለ መዋኢ እፀ ሲኦል ብርት

አሠረ ንጉሥ

ለአብርሃም አብ ኃይለ ሥላሴ ምሉዓ ጥበብ ወሀብት
ወሀቦ ሞገስ ወግርማ በቅድመ ኵሉ ፍጥረት
ወበውስተ እዝና ቤተ መንግሥት
አሰከለ ማርያም ትሰምዕ ድምፀ መላእክት
እንዘ ይብሉ በዓቢይ ስብሐት

ከዚህ በኋላ ግርማዊት ንግሥት ነገሥታትና ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በክቡራን መኳንንቶቻቸው ታጅበው ወደ ቤተ መንግሥት ገቡ ።

ክቡር ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠውም ስለ ክርስትናው ደስታ በቤታቸው ትልቅ ግብር አሰናድተው ነበርና መኳንንቱና ሠራዊቱ በልዑል ፊት የደስታ ምሳ ሲጋበዝ ዋለ ።

በግብዣውም ጊዜ ክቡር ነጋድራስ ደስታ ከዚህ በታች የተጻፈውን ቃል ተናገሩ ፡፡

አሁን በዚህ በምረቃዬ ሁለት ቃሎች እናገራለሁ ወደ ክርስትና የተጠራንበትን የእግዚአብሔርን ቃል ስለ ኢትዮጵያ ስለ መልካሚቱ ቆንጆ ራቁትነት ።

መጀመሪያ

ኒቆዲሞስ የአይሁድ መምሕር በሌት በውሀ ውስጥ ወደ ደህንነት የሚአደርስ መንገድ አገኘ በዚህ መንገድ የሚሔዱ ሁሉ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወራሾች ለዘላለም የማይጠፉ መሆናቸውን ክርስቶስ እርግጥነቱን ነገረው ፡፡ እኔም የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ ለዘላለም አይጠፉም ማነው ከጆ እይነጥቃቸውም ዮ ወ ፲ ፳፱ ፡
በክርስትና የሚገኝ ተስፋ አታውቁምን ሥጋችሁ የመንፈስ ቅዱስ መቅደስ እንደሆነ ፩ ቆሮ ፯ ፲፱ እግዚአብሔርን ደስ ታሰኙ ዘንድ የእግዚአብሔር ይህ ነው መቅደሳችሁ ከዝሙት ትርቁ ዘንድ እግዚአብሔር ለርኩሰት አልጸራንምና ለቅድስና እንጂ ክቡር ፊታውራሪ ደስታ በንጽሕና የእግዚአብሔርን ተስፋ ስለ ጠበቁ ለልዑል አልጋ ወራሽ ልጅ ሊሆኑ ተመረጡ እላንተ ደግሞ ቅዱሳን ሁኑ በሥራችሁ ሁሉ የተመረጠ የመንግሥ ትና የክህነት ወገን ናችሁ የተቀደሰች ዘር የተመረጠ ሕዝብ ከጨለማ ወደ ብርሃን ተጸርታችኋል ማንም የእግዚአብሔር ቃል የሚጠብቅ ሞትን አያይም ለዘላለም ዮሐ ፰ ፶፩ ።

ይህነን ከዚህ በላይ የተነገረውን ተስፋ ለማግኘት እንሩጥ እንቅጻደም ወደ እግዚአብሔር ትእዛዝ መፍጠን ወደ ፍቅር መሮጥ የዘላለም ደህንነት ነው እግዚአብሔር ፍቅር ነው በፍቅር የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔር ፍቅር ነው ዮ ፩ ፬ ፡

፪ኛ ስለ ኢትዮጵያ ራቁትነት ቆንጆዋ እናታችን ራቁቷን ቁማ ምነው እናፋርም ምድር ራቁቷን ስትሆን የሰው ልጆች እራቁታቸውን ይሆናሉ ምድር ጠም ስታድር የሰው ልጆች ጠም አዳሪ ይሆናሉ እኛም ምድራችንን ባዶ ብናደርጋት መንገደኛ ዓይኑን ጣለባት ኢትዮጵያ አሁን ባዶ አይደለችም የሚል የለም እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁለት የተሻለ ስጦታ ሰጣቸው ምድርን እንዲበሉና በመልካም ሥራት እንዲሔዱ ሥራትና ምድር የሌለው ሕዝብ መሆን እጅግ ያስፈራል ይህ ከስውና ከእግዚአብሔር የተወለደችው ሕፃን እንድታድግ ኢትዮጵያም በሥራት መንገድ እንድትሔድ ምድሯንም ፍሬ አማ እንድታደርግ ተስፋ አድርጌ ብርጭቆየን እጠጣለሁ ።

የከተማ ወሬ ፤

ሰኔ ፲፯ ቀን ከሌሊቱ በ፯ ሰዓት ከወይዘሮ ስኂን ቤት ወደ ላይ ባለው የሚስዮን ተማሪ ቤት አንድ ሌባ በድጅኖ መስኮት ሰብሮ ገብቶ መብራት አብርቶ ሁለት ጥሩ ሱፍ ብርድ ልብስና ሁለት እጀ ጠባብ ሁለት መጋረጃ ካወጣ በኋላ ሌባው ከቤት ሳለ አንጐናፍር የተባለ የሚስዮን ዘበኛ በውጭ ሁኖ ቢተኩስ በረሽ ደረቱንና ጆሮ ግንዱን አቁስሎት ከቤት ወድቆ ተገኘ

እስከ ዛሬም ሌባው እንደ ቆሰለ እጃን ሚዳ በባሻ ወልደ ጊዮርጊስ እጅ ተይዞ ታስሮዋል ሰንፎ ነው ሰርቆት የገባ እንጂ ሰርቶ ቢበላ ይልቅ በተሻለው ነበር። ወንድሞቹም አራት ሁነው እርሱን ሊጠይቁ መጥተው ተያዙ ከወንድሞቹ እጅ ትንሽ ድጅኖ ስለት ያለውና የሳንቃ ቁልፍ አብሮ ተያዘ የሌባውም ወንድም ስሙ ይማሙ ይባላል ፡፡

የውጭ አገር ወሬ

ከኒዮ ሐብን ኵንግሬስ የተተረጐመ

ስለ ከዋክብት አዋቂዎች (ኤስትሮኖመስ)

የከዋክብት አዋቂዎች እውቀታቸው የተወሰነ ነው የኦክስፎርድ ዮኒቬርሲቲ ዲሬክተር ዶክቶር ተርነር የከዋክብትን ኀብረት የተማረና አሁንም በተማረው ላይ እየቀጸለ የሚሄድ የከዋክብት ፍጥረት እናውቃለን የሚሉ ሁሉ እውቀታቸው ከባሕር አንድ ነጠብጣብ ውሀ የማፍሰስ ያህል ይመዘዘናል አለ ። ለጥቆም ሚዳው ወሰን የሌለው ስለ ሆነ ስለ ሰማይ ከዋክብት የምናውቀው ጥቂት ነው ብሎ የሚከተለውን ምሳሌ አስረዳ፤ እስከሁን ድረስ የከዋክብትን ትምሕርት የመረመረው ሌላው ቀርቶ ያንድ ከከብ ታሪክ ከስር እስከ ጫፍ ሊያውቁ አልቻሉም ቴሌስኮፕ የሚባለው ሙኪና በገሃድ እንዲያሳይ እናምናለን በዚህም መኪና እርዳታ የከዋክብትን ትምሕርት እስከ ጫፍ መርምሮ ቢያውቅ እንኳን ትኒሽ እንዲረዳው አይጠረጠርም

ማስታወቂያ ፡፡

ኀሐ ጽባሕ የሚባል መጽሐፍ ዋጋው ፫ ብር ነው



እጅግ ጥሩነቱ የተመሰከረለት አሜጋ በቢ የሚባል ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፫ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፰ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፯ ብር ተኩል
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፻፴፰ ብር ተኩል
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፳፫ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፲ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፫ ብር
ባለአንበሳ	፡፡	፻፵፬ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፫ ሩብ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፲፯
በአንድ ብር	፫ ሊሬ እስከ ፴
በአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፲፪ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፰ ብር

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

ሩግቢ

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፣ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዮን አቶመቢል የፌታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሄስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጉበርና አጉበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

Berliet



ቤርሊዮ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዮ አቶሞ ቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

ARMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Póur l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶከለኝ አምቦሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶከለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፳፯
3 me ANNÉE № 27

ሐሙስ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 7 JUIL 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፪፻፪ገጽ ተከታይ

ለመንግሥትና ለሕዝብ ጥቅም።

አስረጅ ሰንጠረዣ

የዕቃው ዓይነት	ወጪው ብር ።
ላቡጀዲ ፤	፯ሚ ፱፻፩፻፳፭
ለፈትል ፤	፪ሚ ፫፻፺፰፻፳፻፸
ሳሽቦ ፤	፩ሚ ፻፺፫፻
ለሻማና ሳሙና ፤	፩ሚ ፫፻፻

ጥቅል ድምሩ ፲፪ሚሊዮን ፶፫፻፫፻፴፭ ብር ።

እረ ኢትዮጵያ በያመቱ ይህን ያህል ብር ለውጭ አገር ሰው ባራቱ እቃዎች ብቻ የምትገብር ከሆነች ያላት ገንዘብ ሁሉ በጥቂት ዘመን እውጭ አገር ሄዶ ባዶ እጅዋን ምነው ያልቀረች? ሲል የኔ ብጤ ሳይጠይቀኝ አይቀርም ይሆናል ። እሱውም የገንዘብን ሥራና ጥቅሙን መዋያውን እንዴት እንደምን እንደሆነ ካንዱ እጅ ወዳንዱ እየተዛወረ እንዲኖር አጥብቆ ባያውቅ ነውና ለማወቅ ቢፈልግ የነጋደራስ ገብረ ሕይወትን መጽሐፍ ምዕራፍ ፰ ፱ ፲ አጥብቆ ይመልከት ። በተረፈም እነዚህ የውጪ አገር ነጋዴዎች በንግድ ሆነ በሌላ ካገራችን የሚያከማቹትን ገንዘባችንን በቅጣጫው ወዳገራቸው አይሰዱትም ካገራቸው ገንዘብ አስመጥተው መግዛት የተገባቸውን የሚያስፈልጋቸውን ቆዳ ፤ ቡና ፣ ሰም ፣ የዝሖን ጥርስ ጥጥ ፣ እንደዚሁ ያሉትን ሁሉ ካገራችን በቀላል ዋጋ በገዛ ብራችን ገዝተው ወዳገራቸው ይሰዳሉ ። ባገራቸው የማይገኙ ስለሆኑ ብዙ ትርፍ ይዝቁባቸዋል ። ያ ከኛ በጨርቅና በሌላ እቃ የተገኘው ትርፍና ዋናው አገራቸው ከሚሸጠው ከሚሸጡት እቃችን ላይ ተነስቶ አገራቸው ባንክ ይገባል ። ከሁለተኛው ፋይዳ (ካገራችን እቃ ላይ) ካገራቸው በተገኘው ትርፍ እንደገና አቡጀዲድና ፈትልን ለኛ የሚያስፈልጉንን የባሕር እቃዎች ከሚሰሩበት ፋብሪካ ቤቶች በቀላል ዋጋ ገዝተው ይኸንን በቆዳ በቡን ጉብ የመለሱልንን ብራችንን ሊወስዱብን ከኛ እቃ ላይ በተገኘው ትርፍ ሊቸረችሩብን ይመጡልናል (እንደዚህ ስለሆነ ብራችን በውጪ አገር ሰው እጅ ኢየሆነ ያገራችን ሰው ባዶ እጁን ያጨበጭባል) እንደዚህ ኢየሆነ ከኛው እቃ ሽያጭ የሚገኘው ትርፍ ገንዘብ ባመት ባመቱ ዋና ሆኖ እቃ ኢየተገዛበት ሶስተኛ ሊነግድብን ይመጣል ። እነዚያ መጀመሪያ ለንግድ ሲሉ ወደ ኢትዮጵያ እቃ ይዘውበት የመጡት ዋና ገንዘባቸው የነበረው ብር ባመቱ ከነትርፉ እባንክ ገብቶ ኢየወለደ በትርፍ ትርፎቹ የተገኙትን ፋይዶችና የትርፍ ትርፎች ያዝዛል አሁን ባገራችን እንዲህ ከብረው የምናያቸው ነጋዴዎች ሁሉ ስንት እቃ ይዘው ኢትዮጵያ እንደገቡ እስቲ አስቡት ሁላችሁ ኢትዮጵያውያን ።

እንግዲህ የኢትዮጵያ መንግሥትና መኳንንት ላገራቸው ጥቅም ለሕዝባቸው ክብረት ለነጻቸው ጉልበት ከልብ የሚጥሩ ቢሆኑ በነዚህ በአራቱ እቃዎች ወደ ውጪ የሚወጣብንን ፲፪ ሚሊዮን ፶፫፻፫፻፴፭ ብራችንን እንኳ አስቀርተው ለሕዝባቸው መነጋገጃ ቢያደርጉ ገንዘብ ካለ ለጉልበት መንገድ አለ ነውና የኢትዮጵያን ጥቅም ልክ እኔ ከነሱ ይበልጥ አውቄ ልዘረዝርላቸው አላስብም ሆኖም ለነዚህ ሁለት ቃሎች ፈቃዳቸውን እለምናለሁ ።

መጀመሪያ እራቁቱን የሚሄደው ሕዝባቸው በቀላል ዋጋ ይለብሳል ፤ ሁለተኛ ስራ ፈት አውደልዳይ ወሮ በላ ሁሉ በየፋብሪካው ስራ ያገኛል ፣ ጠቅላይ አገራችን እውቀትና ጉልበት ትጨምራለች ጉልበት ማለት እውቀትና ክብረት ናቸው እውቀት ካለ ገንዘብ አለ ገንዘብ ካለ ጉልበትና ለማግኘት መንገድ አለ ነውና ክቡር ፈቃዳቸው ሆኖ ያለቸልታ ቢያስቡባቸው በማ

ለት ለብርሃን ልቡኖቻቸው አመለክታለሁ ። ሌላም እርዳታ (እስታዋሽ) እንዳገኝ ተስፋ አደርጋለሁ ።

፲፪ ሚሊዮን ፺፫ሺ፫፻፸፫ ብር ብቻ ባገራችን ብንነግድበት ለኢትዮጵያ ምን ክብረት ነች ቢል መኳንንቶችን ይጠራራል የሚል ሰው አይጠፋም ይመስለኛልና ፲፪ ሚሊዮን ፺፫ሺ ብራችንን ብቻ ማስቀረት እንዳልሆነ ጥቅማችን ሳስረዳው እፈልጋለሁና እነሆ ይመልከት ፤ በገዛ ገንዘባችን ከኛው ላይ ይገዙዋአቸው ለነበረው ለሚያስፈልጉዋቸው ፤ ለቆዳ ፤ ለቡን ለሰም ፤ መግዣ የውጪ አገር ነጋዴዎች በገራቸው ስለሚአተርፉቸው ትርፍ ሲሉ በያመቱ ፲፪ ሚሊዮን ብር ወይም ያ፲፪ ሚሊዮን ብር እቃ ሊያመጡ የግድ ይሆንባቸዋል ። እንደዚህ ሊሆን ኢትዮጵያን መንግሥቷ የንግድ አገባብ ማወቅ ከገሩ የማይገኘውን እቃ ካገሩ በሚገኘው መለወጡ ይገለጣል ። ስለዚህ ለኢትዮጵያ ከውጪ ገቢዋ በያመቱ ፲፪ ሚሊዮን ፺፫ሺ፫፻፸፫ ብር ሆኖ ከገሩዋ ላቡጀዲድ ይወጣ ከነበረው ጋር ኤኮኖምያ (ቁጥብ) የምታደርገው ገንዘብ በያመቱ ፳፬ ሚሊዮን ፺ ሺ ፯፻፵፮ ብርና በየስራው አያሌ ሕዝቦቿን ማሰልጠን እንድታገኝ ግልጽ ነው ። አባት እናት ለልጆቻቸው ልጆችም ለወላጆቻቸው ካላሰቡ ማን ያስብላቸዋል እንደ ተባለ እንደዚሁ አገርና መንግሥት ለሕዝቦቻቸው ሕዝቦችም ላገራችንና ለመንግሥታችን ካላሰብን ማን ይመጣልናል? አሁንም ቢሆን መንግሥት ላገሪቱና ለሕዝቦቹ ። ሕዝቦቹም ላገራቸውና ለመንግሥታቸው ኢያስቡ ይጠቅም የመሰላቸውን ምክርና ስራ ከነምሳሌው መስጠት የተገባቸው የሚያስፈልጋቸው ነውና የድሐ የደንቆሮ ምክር ነው ኢያልን ከመናቅ የተነሳ ብዙ የመንግሥትና ያገር ጥቅም እንዲቀርብን እያሰብን ምክር አቅራቢዎቹን በድሕነትና በእውቀታቸው ማነስ ከማቆሸሽ ይልቅ ደግ ደጉንና የሚጠቅመውን ከማይጠቅመው ምክር) መሀከል እየለየን በቶሎ በቶሎ ስራ ማስያዝ ነበር መልካሙ ፤ ብንወዝፈው ከከፉ ቀን የሚያድነን እህል አይደለም የስራና የስራት አወጣጥ ድልብ የለውም ፤ ምሳሌ ምክር በሰው ልብ እንደ ጠሊቅ ውሃ ነው አእምሮ ያለው ሰው ይቀዳዋል ሲል ይመክረናልና እንቀዳ በሰነፍ ጆሮ አንዳች አትናገር የነገርከውን ጥበብ ያፌዝ ብሀል የሚለውንም እናስብ ።

በመልካም መኖር የቻሉ ሕዝቦች አገራቸውን የሚያሰፉት ሕዝባቸውን ያሰለጠኑት ከሕዝቡ አንዳንዱ የሚሰጡዋቸውን ያልተቃናውን ምክር ኢያቃኑ ኢያሰፉ ኢያሳመሩ ኢያለሙ ነው እንጂ እንዲያው ኢየዳሰሱ በማለፍ አይዶለም ።

በ፪ተኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ቁጥ ፴፱ ገጽ ፫፻፰ ለሕዝ ማሰልጠኛ ገንዘብ ድሖ እንዳይጠቃ እንደ ድሕነቱ ካብታም እንዳይታማ እንደነብቱ የሚያስቀጣቸው ሆኖ ቢታየኝ ባ፭ አገባብ ያወጣጥ ደንብ በመንግሥት ቢታዘዝ ሕዝቡ ሳይጐዳ የሚበቃ ገንዘብ የሚያገኝበት ነው ስል ጽፌ ነበር ። ምክርና ሥራን ከነምሳሌው መስጠት የተገባ ነው ። ስላልኩ ምሳሌውን ዛሬ በመስጠቴ ይቅርታችሁን እለምናለሁ ። ምንም በውጪ አገር ሰው እጅ የማድር ገንዘብ የሌለው ተቸጋሪ ተማሪ ሆኜ አስተማሪዎቼ ከሚሰጡኝ ከምማርባቸው መጻሕፍቶቼ በተቀር እርስት ቦታ ቤት ከብት ገንዘብና ብረት ባይኖረኝ በኪስ በሚሄዱ ባሉኝ በሚኖሩኝ ከብቶች በመጻሕፍቶቼ ቁጥር ስለ ወንድሞቼ ማሰልጠኛ ስላገሬ ጥቅም ስል ወተቷን ያጠጣችን የውቀት ላሜን መጽሐፌን ቢሆን ኢየሸጥኩ በያመቱ ባንዳንዱ መጽሐፍ ፩ ፩ መሐለቅ ላወጣ የተሰናዳሁ ነኝ ፤ አሁንም ባሉኝ መጻሕፍቶቼ ልክ ከራሴ ጭምር ስለ ፹፪ መሐለቅ ሂሳብ ፶፭ ሊሬ ሰድጃለሁ ። ለወደፊቱም በፊርማዬ አመሰክራለሁ ።

እራሳችንን እንድንችል አገራችንን እናከብር ፤ መንግሥታችንን እንርዳ ስል በጻፍኩላችሁ ቃላት ስህተት ብታገኙ አርሙ ችሁ ብርሃንና ሰላምን ለማይመለከቱ መኳንንቶች ሆኑ ድሆች ወንድሞቻችን ሁሉ እንድታስታውሱልኝ በብርሃን የምትሄዱትን የሰላም ልጆች በውጪ አገር ሆኜ እለምናችኋለሁ ትንሹ ተማሪ ።

መ ሥ ወ

ምስጋና

የሕዝቡን ሕይወት ለወደዱ ጌታችን

በመጽሐፍም እንደ አነበብነው እኛም እንደ እምናየው የከብት ባለቤት ለከብቶቹ ጠባቂ እረኛ ያደርግላቸዋል ይኸውም እረኛ መንጎቹን በሥራት መጠበቅ አለበት ያለበለዚያ የማይችል ከሆነ ሳይጠፉና ሳያልቁበት አልችልም ብሎ ለባለ ቤቱ ማስረከብ ይሻለዋል ሳያስረክብ በስንፍና አውሬ ወይንም ሌባ ቢያጠፋቸው ለከብቱ ሁሉ አላፊ ሆኖ ከፋይ መሆኑ አይጠረጠርም ጌታችንም ለሐዋርያት በጎቼን ጠብቁ ማለቱ በመንፈሳዊም ሆነ በዓለማዊ መንገድ መሪ እንዲሆኑን ነው እንጂ ይህ ትእዛዝ በሐዋርያት ብቻ ተወስኖ እንዲቀር አይደለም መንግሥትም ሥራዩንና ሕዝቤን ጠብቅ ብሎ ሹም ሽልሞ ማስቀመጡ ዝም ብሎ እንዲቀመጥ አልነበረም የሕዝቡን ጉዳትና የሥራውን አካሄድ እየተመለከተ በቀጥ እንዲያደርግ የማይችለውንም ለመንግሥት እያመለከተ እያደላደለ እንዲሠራ ነው እንጅ ።

እኛም የድሬ ደዋ ሠራተኞች ይህን ያህል ዘመን ሙሉ በዚህ በተቃጠለ በረሃ እየተቀቀልን ለመንግሥት አገልጋዮች ሆነን መኖራችንን ማንም አይስተው በዚሁም አገር በኖርንበት ዘመን ሁሉ ከበሽታ እንዳልተለየን ሁሉ ያውቃል ስለ ዚሁም ጉዳታችን ሁሉ መንግሥት ለሰጠን አለቆቻችን በበሽታ አልቀን መንግሥታችን አንድ ሐኪም እንዲያደርግልን ንገሩልን እያልን ማመልከታችንን ዘወትር አልተውንም ነገር ግን ልመናችን ባለቆቻችን በኩል ሊፈጸምልን አልቻለም ከዚህም በኋላ ተስፋችንን እስከ መቍረጥ ደረስን ዳሩ ግን ምክር መልካም ነውና ሁላችን በንድነት ሁነን መክረን ለልዑል ጌታችን ጉዳታችንን በወረቀት አስታወቅን ። ልዑል ጌታችንም ወረቀቱን በላከነው በስምንተኛው ቀን ሙሉ ተስፋ ያለው መልስ ሰጡን ቃሉም የጠየቃችሁት ጥያቄ የሚገባችሁን ነውና ይፈጸምላችኋል የሚል ነው ባለቆቻችን በኩል ያን ያህል ዘመን ደክመን ያልሆነው ባንዲት ወረቀት ቃል በስምንት ቀን መፈጸሙ እጅግ ደነቀን ደስታችንም ከሕይወታችን የበለጠ ሆነ ሐኪሙንም ሳይቆይ በፍጥነት ልከውልን እንደ ልባችን እንታከማለን ለወደፊቱ ብዙኅ ዘመናት ረጋርም ወራት የምንታከመው ቀርቶ ከመጣ

እስከ አሁን የታከምነውና ያገኘነው ጤና ገንዘባችንም እቤት የዋለውን ለጌታችን ዋጋ ቢታሰብ ምን ያህል በበቃው ለሕዝባቸውስ ሰግተው በፍጥነት እንዲፈጸምለት ማድረጋቸው በምን ሚዛን ይመዘናል ። እኛ ግን ለልዑል ጌታችን የሚበቃ ምስጋናና ዋጋ እናገኝምና የማይጠፋውን ርስትና ሕይወት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያገኙ በፍጹም ልባችን እንለምናለን ልመናችንም ሐሳባችን እንደማይለያቸው ለማወቅ ነው እንጂ በሥራቸውና በግብራቸው ሁሉን ከሚችልና ከሚመዝን ንጉሥ ዋጋ እንደሚያገኙ አይጠረጠርም ነገር ግን የጌታችን ቸርነት አይታይም ይህንን ያህል ዘመን በየአለቆቻችን በኩል ስንደክም የኖርነውን ማሰብ ነው እንጂ ለሕዝባቸው አያስቡም እንዳይባል በሁሉ ቦታ ይመሰክርላቸዋል እንግዴህ ተሹሞ መቀመጡ ምን ሊሠራ ነው? ከሕዝቡስ በላይ ሌላው ሥራ ይበልጣል በማለት ነውን ወይንስ ልዑል እሺ አይሉም ብሎ ለማመካኘት ነውን ይህ እንዳይሆን ማናቸውንም አይነት ሥራ ሁሉ ሠሪው ሰው ነው ለሥራው ሁሉ መሣርያው ሰው ከሆነ ከሁሉ አስቀድሞ ለሰው ማሰብ እንዲገባ አይጠረጠርም ልዑልም እሺ አይሉም ብሎ እንዳያመካኝ ያን ያህል ዘመን የለፋንበትን በስምንት ቀን በማግኘታችን ይመሰክርበታል ለወደፊቱም በሹመት ላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ እንዲገነዘቡት ተስፋ እናደርጋለን ።

ልዑል ሆይ ልዕልናዎን ዘለዓለም ያኑርልን

የድሬ ዳዋ ሕዝብና ሠራተኞች ።

ከእንቅልፍ ስለ መንቃት ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ መኳንንቶቻችን አዲስ አበባ ሁነው ከዲስ አበባ ውጭ የሚሰራውን ሥራ እጅግ አያዩትም ይሆናል ። ደግሞም በሥራ ብዛት አንዳንዱን ነገር ይዘነጉታልና እኛም አሽከር ጌታውን እንደሚያመለክት ሁሉ ከሁን ቀደም በብርሃንና ሰላም ብናስታውስ ደጉ አሳባችን የክፉ አሳብ መስሎ ስለ ተቈጠረብንና ስለ ተቀየሙን እንግዲህስ መጻፉን ይቅርብን ብለን ትተነው ነበር ይህም የሚበቃ ትምርት ከለማግኘት የተነሳ ነው እንጂ እንደሚገባ የተማሩ ሰዎችስ ላገራቸው የሚጠቅም መስሎ የታያቸውን ነገር እስከ ዕለተ ሞታቸው ብዙ ችግርና ጭንቅ እየተሸከሙ ይሰራሉ እንጂ ሰውን ፈርተው አሳባቸውን አያቋርጡም ። እኔ ግን ፍራት በተባለው አሳብ ተማርኬ መበሳጨች በተባለው ሞዶሻም ራሴን ተቀጥቅጬ እንክትክት ብየ ሁለተኛ ቀን እንደማልነሳ ሁኜ ነበር ። እንዲሁም ብዙ ሰዎች ለመታከም እስከማይቻላቸው ድረስ ልባቸው የቆሰሉ አይታጡም ይሆናል ፣ ስለ ሆነም ሕይወት ፈጽማ ከሥጋ ካልተለየች መንቀሳቀስ አይቀርምና አቶ ጥሩነህ ክብትሀይመር ተነሱ ተነሱ ወንድሞቼ ሆይ ተነሱ ብለው በጻፉት ቃል ተንቀሳቅሼ ኑሬ ደግሞ አቶ ሞገስ አምደ ሚካኤል በ፫ኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ቁጥር ፳፮ ግሩም የሆነ ልዩ ልዩ ነገር ተናግሮ ሲያበቃ አመጨረሻው የሆነ ሁኖ በሆድ ውስጥ አጥንት ሁኖ ከቀረ ጽንስ የጨነገፈ ይሻላል ልጁ ቢሞት እናቱ ትድናለችና ስለዚህ ምንም ባይደረግ እየተናገራችሁት ይቅር እንጂ ላይደረግ ምን አደከመን ብላችሁ ችላ እንዳትሉ ደግሜ ደግሜ እማልዳችኋለሁ ብሎ የጻፈውን ባነብ ፈጽሜ ተነሳሳሁና ይህን ለመጻፍ ተበረታታሁ አቶ ዘውዴ በየነ በብርሃንና ሰላም ቁጥር ፳፬ የሰው ልጅ ዘር ንቀት ብሎ የጻፈውን ቃል በጣም የሚያሳዝን ነው ። ስለ ሆነ ግን እኔም የዓለም አኳሆን ገና በቅጡ ሳላወቅ ሁም ነበርና በዚሁ የሰው ልጅ ዘር ንቀት የተነሳ በልዩ ልዩ አገር ለባላገሮቹ እንዴት ያለ የውርደትና የንቀት ሥራ እንደሚሰራባቸው በብርሃንና ሰላም አምርሬ ጽፌ ነበር ። ብስጭቴም ከልክ ያለፈ ነበር አሁን በየው ብመለከተው ግን ሰው ሁሉ እንደየመጠኑ የሰው ልጅ ዘር እንደሚናቅ የተፈጥሯችን ባሕርይ መሆኑን ተረድቸው ባፈጣጠራችን አኳሆን በጣም እደነቃለሁ አንዱ የብርሃንና ሰላም ማሕበረተኛ አቶ ዘውዴ በየነ ሌላስ ይቅርና አንድ ጥቁር ሰው ብዙ ዓመት ሲሰራበት ከነበረ ሥፍራ ሥራ ሲወደድ ሰራተኛ ሲበዛ ያን ጥቁር ሰው ያስወጡና ስራውን ለነጭ ይሰጡታል ። ይህም ነገር እርስበርሳቸው መተጋገዛቸውን ያሳያል ብሎ የተጻፈውን ቃል ጠቅሶ ደግሞ ፩ ጓደኛው እናንተ አሜሪካ ላይ በሚሰራ ሥራ ታዝናላችሁ እኔ ግን እኛ ድረስ እንዳይመጣ እስጠነቅቃለሁ ብሎ ያጫወተውን ጽሮት አንብብሁትና ላቶ ዘውዴ በየነ የማጽናናት መልስ ልጽፍለት ወደድኩ ።

ክቡር ወንድሜ አቶ ዘውዴ ሆይ ፡፡ በዚሁ የሰው ልጅ ዘር ንቀት በጣም እንደምታዝንና እንደምትበሳጭ ባጻጻፍህ ተረድቸዋለሁ ፡፡ ማዘኑ የተገባ ነው መበሳጨቱን ግን እንድትተወው እመክርሃለሁ ። ተወው ብየ መምከሬም ከመበሳጨት የተነሳ ሕይወትህን ሳታደክም ትምርትህን ፈጽመህ አገርህ እንድትገባና እንድትረዳ ስለተመኘሁልህ ነው ፡፡ መቸም ሰዎች በኛ ላይ የሚሠሩብንን ካልሆነ እኛ ለጓደኞቻችን (ቢጽ) የምንሠራባቸውን ዘወር ብለን እንድናየው ባኅርያችን አይፈቅድልንም እንጂ በመልክ የተለያዩ ሰዎችስ ይቅሩና መልካችን አንድ የሆነው እንኳ መናናቅና መለያየት ሥራችን ሁኑዋል። ስለዚህ ማድላት በተፈጥሯችን ውስጥ አለ እንግዲህ ምን ይደረግ ሌላስ ይቅርና እናት እንኳ የገዛ ልጆችዋን ሁሉ ትክክል አታያቸውም እንግዲህ በመጥፎው ባህርያችን እያለቀስን አጠር ሲል እንቅልፍን ረዘም ሲል ሞትን ላዘጋጀልን አምላክ እናመሰግናለን። ጊዜ አላፊ ነውና ደስታ ብታገኝ በመጠን ደስ ይበልህ። ሐዘንም ብታገኝ በልክ እዘን ጊዜ አላፊ ነውና ።

ኪዳነ ማርያም አበራ ።

ሰውና ሥራ

፩ ሰው በሥራ ላይ

ብርሃንና ሰላም በብዙ ስፍራ የመጻሕፍትን ቃል እንደሚያስታውሰን በዓለም ያለ ልዩ ልዩ ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር ለያንዳንዱ ላዳም ልጅ እንዳቅሙ መጠን አካፍሎታል ፩ ቆሮ ም ፲፪ ቁ ፬ ሮሜ ም ፲፪ ቁ ፮ ነገር ግን ደግሞ ከዚያ ከተሰጠው ሥራም ይፈለግበታል ማቴ ም ፳፭ ቁ ፲፬ ፩ ቆሮ ም ፬ ቁ ፪ ስለዚህም በማናቸውም ሥራ ላይ የሚሾም ሰው ሥራውን የሚገዛ ከሆነ በሥራው ውስጥ ያሉትን ደግሞ ይገዛልና የሥራውን አኳኋን በሚታይና በሚዳሰስ ለመግለጥ ሳይጣጣር በእግዚአብ

ሑርና በሰው ፊት የሚከፍለውን ዕዳውን ተረድቶ አስቀድሞ በሕሊናው ውስጥ ገብቶ የተሰጠውን ሥራ ለማቸነፍ መቻሉን በጣም መመርመር ያስፈልገዋል ።

ሥራ ለራሱ በዩናችን የሚታይ በጃችንም የሚዳሰስ ግዙፍ አካል ያለው ቢመስል ውስጥ ሕዋሳታችንን የሚያስለች ክብርቱ ፍቃዳችን ጋራም የሚዋጋ የሞቀው ያ ሕሊናችንም ምኞት ለማድከምና ለማቀዝቀዝ የሚታገል የሐኬትና የቀቢጸ ተስፋ የሥሥትና የምቀኝነት የሆነ ረቂቅ መንፈስ እንዳለው እያንዳንዳችን በሰውነታችን ልንረዳው እንችላለን ስለዚህ ከሥራ የሚገኘው ትርፍ ሁሉ ፍጻሜው እንኳ ለጥቅም ቢሆን ለጊዜው ሥራ ለሠራተኛው ብርቱ ወደረኛ ነው ።

ይህ ሁሉ ግን እየደረሰባቸው ሹመታቸውና ሥልጣናቸውን በሥራ ላይ የገለጡ ያለፉና ያሉ ብዙ የዓለም ሰዎች ታሪካቸውን ብናነብ የበቃ ምስክር እንድናገኝ ጥርጣሬ የለውም እንግዴህ የስንፍናውን ዓይን በዕውቀቱ መብራት አብርቶ የተሰጠውን ሥራ በትክክል ለመሥራትና ለማሠራት ከበቃ የበረታ ሥራም ቢሆን ሊገዛለት ይችላል በዚያውም መብራት የብዙዎችን ስንፍና ይገልጣል የሥጋ መብራት ዓይን ነው ዓይንህም ጽሩ ብትሆን ሥጋህ ሁሉ የበራ ይሆናል ማቴ ም ፮ ቁ ፳፪ ።

ለምሳሌ ለብዙ ሥራ የሚሆን መኪና መኪናውን ለመሥራትና ለመማር ብዙ ጊዜ ይወስዳል መኪናውን ግን ከሠሩትና ከተማሩት በኋላ መኪናውን ለማሠራት ቀላል ነገር ነው እንዴሁም ሰው ለተሰጠው ሥራ የውቀቱን መኪና ከሰናዳ ጨርቅ ለብሶ ያሰናዳውን ወርቅ ለብሶ ሊያስኬደው ይችላል ለጊዜው እንኳ እንደ ሐሳቡ ልክ በብዙ ዕንቅፋት ምክንያት ሥራው ባይሳካለት ለጊዜው የቀረውን በጊዜው ሊፈጽመው ይሆንለታል

እንዴህም በሆነ አረማመድ በሥራ የሚገኝ ሰው በሥራ ላይ ቁሟል ወይም ተሹሙዋል ለማለት ደፍሮ ለመናገር ይመቻል የዚህ ሰውዬ በታም ለማወቅ ቢያስፈልገን ክቡር ፊታውራሪ ዴሬሳ በብርሃንና ሰላም በ፫ኛው ዓመት ፰ኛ ቁ በገጽ ፶፱ የጻፉትን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው እየደጋገምን ብናነበው እናገኘዋለን ።

፪ኛ ፡ ሥራ በሰው ላይ ።

ሰው የሥራውን ማስተካከል ግድነት ሳይኖረው ለሹመቱና ለንጀራው ብቻ ኢየጓጓ በማያውቀውና ባልሰለጠነበት ሥራ ተሹሟል የተባለ ጊዜ እገሌ ሥራው በላይ ተሹሞበታል ለማለት አንጂ በሥራ ላይ ተሹሟል አያሰኝም ፤

መቸስ ይህ እንዲህ ያለው ምኞት ሥረ ነገሩ ከሥሥት የበቀለ ይመስላልና እንግዲህ ሥሥት የሐጢአት እናት ናት እንዳለ አንድ የቀድሞ ዘመን የዕርዕ ፊሎሶፍ ሥሥትም ራስህን መውደድን ወይም ለኔ ይመቸኝን ደግሞ ትወልዳለች ለኔ ይመቸኝም ከሀገርን መውደድ ጋራ ትወዳደራለች ለዚህም ለማስረዳት የሚከተሉትን ቃላት ብቻ አመለክታለሁ እንጂ ትርጓሜ አያስፈልግም ለኔ ይመቸኝ ብቻ ሐሳቡ የሆነ ሰው የራሱን ወዳጅ መሆኑ ግልጥ ነገር ነው ራሱን ብቻ ከወደደ ግን ሀገሩንና ጌታውን ንጉሡን ለመክድ በቀላል ነገር እንዲታለል ጥርጥር የለውም በሥሥት ወጽመድ ወድቀውም ፍጻሜያትው ለጥፋት የሆኑ ሰዎች የሚከተሉትን ለምስክር ብንጠራ ይበቁናል ግኻዝ በንዕማን ገንዘብ ይሁዳ በአይሁድ ገንዘብ ሐናንያና ሰጲራም በገዛ ገንዘባቸው ተታለው ከጌቶቻቸውና ከሀገራቸው መለየታቸውን ያስረዳናል አቤሴሎምም ያባቱን ሹመት ያለ ጊዜው ፈለገው መጽ ነገ ክልእ ።

አዳም ዓባታችን በዚያ በተሰጠው ጸጋ ደስ ብሎት በቃኝ ማለትንም በጨመረበት ኑሮ በሞ ፤ ዕዳ አይወድቅም ነበር አሪ ዘፍም ፫ ቍ ፲፯ ያምላኩን ክብር በመመኘቱ ግን የቆጡን አውርድ ብላ የብብትዋን ጣለች ሆነበት ከሥሥት ያገኘው ፍሬም ይኸው ለልጆቹ ተጋባ ።

ከዚህ በላይ እንዳመለከትነው ሕዝባችን የሚበልጠው ኢያንዳንዱ ለራሱ ሹመት ባገኘሁና እንጀራ በወጣልኝ ባይነው እንጂ የተሰጠውን ሥራ በትክክል ሠርቶ ሲያበቃ ለሀገሩና ለንጉሡ ጥቅም መሆኑን የተረዳው ሰው በጣም ጥቂት ነው ። ከዚህ ምኞት ውስጥ ለሚኖረው ሰውም ያውልህ ሹመቱ ያውልህ እንጀራው የሚል ድምጽ የሰማ ጊዜ ጅብ ባጥንት የተማገረ በቍዳ የታሰረ ቤት አለ ቢሉት የት ነው ሳይል ገስግሰ እንደሚባል የሥራውን ክብደት ወጽመድ መሆኑን ሳያስተውል እየዘለለ ጥልቅ ይልና በማያውቀው ሥራ ገብቶ ይንፈራገጣል ጉዳቱም ለራሱ ብቻ አይሆንም ለሥራውም ጭምር እንጂ

ለንደዚህ ያለ ሰው ሰሎሞን እንዲህ ሲል ይመክረዋል ሰውነትህ ቢሳሳ በጕሮሮህ ላይ ካራ አኑርም የሐሰት እንጀራ ነውና የጣፈጠ መብሉ አይመርህ ምሳ ም ፳፫ ቍ ፪

ብዙ ጊዜም ከንደዚህ ያለው ሰው ውስጥ በሥራ ሠልጥነው ከሥራ በላይ የሆኑ ሠራተኞች ይገኛሉ ነገር ግን ቅድም እንዳልነው ሰውዬው ከሠራተኞቹ በላይነቱን እንጂ የሥራውን በላይነት የለውምና የሥራውን ግድነት በለመመልከቱ ደጅ ያልጠናችሁኝ ያልተከተላችሁኝም ሲል ሠራተኞቹን ቢያጕላላ ሠራተኞችም ደጅ ጥናቱና መከተሉ የሥራው ወደረኛ መሆኑን አውቀው ወደ ስራው ያደሉ ጊዜ ትንንቁ እዚህ ላይ ይሆናል እንግዴህ እኒን ያልታደሉ ሠራተኞች በላይ ድንቀናርና በታች ዕውቀት ጨቍነው እንዲያስጨንቋቸው የተሰማው ሰው አይስተውም ነገር ግን አንድ የብርሃንና ሰላም ወዳጅ ከዚህ ቀደም በዕውቀት ያለ መከራ ሔል አስታውቆናልና የዕውቀት ሰዎች ስለ ሀገራቸው ቢጨነቁ አያስደንቅም

ክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ በትንሹ ዕውቀቴ ይህን ለመጻፍ ያስደፈረኝ የጌታችንን የልዑል የኢ መ አ ወ ተ መ ሐሳብን ኢየተከተላችሁ በልዩ ልዩ ምክር ኢትዮጵያ ሀገራችሁን ለማነቃቃትና ወደ ሥልጣኔው ደረጃ ለማድረስ ስትፋጠኑ ለዚሁ መልካሙ ምኞታችሁ ግን ተቃዋሞች ከሆኑት የሚያውቀውን ሥራ መሥራት ሐፍረት ኢየመሰለው በማያውቀውና ባልሠለጠነበት ሥራ ላይ ደርሶ እሾማለሁና እዛለሁ የሚል ሰው እንደኛው የሥራችሁን ዕንቅፋት እንደ ሆነ መስሎ ቢታዬኝ የልፋታችሁና የደጉ ሐሳባችሁንም ምቀኛ እኔም በተቻለኝ በፊታችሁ ለማስጣት ነው እንጂ እላንትን ለመምከርና የረሳችሁትንም ለማስታወስ አቅም ኑሮኝ አይደደለም ቢመስላችሁም ይቅርታችሁን እለምናለሁ ። ፍቃዳችሁ ቢሆን ግን ደግሞ

አንድ ነገር መድኃኒታችን የጠየቀውን ጥያቄ የወንጌልን ቃል ላስታውስ እለምናችኋለሁ ማን ሰው ነው ከናንት ልጁ እንጀራ ቢለምነው ደንጊያን ይሰጠዋል አሣ ቢለምነው እባብን ይሰጠዋል ማቴ ም ፯ ቍ ፱ ይህ ምን ሊያመለክተን ይችላል።

ሺቃ መኰንን ።

የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ትምሕርት ቤት ተማሪዎች በዕውቀት የበለጡ የበለጡት እንደ ተሸለሙ ።

ሰኔ ፳፯ ቀን በ፱ሰዓት ክቡራን የኢትዮጵያ መኳንንቶችና የውጭ አገር ሚንስትሮችና ወይዛዝርም በትምሕርት የበለጡትን ተማሪዎች ከልዑል አልጋ ወራሽ ስጦታ ሲቀበሉ ለማየት ተጠርተው ነበርና በተጠሩበት ሰዓት ወደ ትምሕርት ቤቱ ተሰበሰቡ ። ልዑል አልጋ ወራሽ በትምሕርት ቤቱ ሲገቡ የሰላምታ ሙዚቃ ተነፋና ተማሪዎቹ ተሰልፈው ቈይተው እጅ ነሡ ። ከዚህ በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽና ትምሕርት ቤቱን ለማየት የመጡ ሁሉ እየዞሩ መጀመሪያ የተማሪዎቹን መኝታና መብሊያ ቤት አዩ ። የሸማ ሥራ የሚማሩትንም ልጆች መኪናውን ሁሉ ሲያወዛውዙትና አሳምረው ሲሠሩ አይተው እጅግ ደስ አላቸው ። ወዲያውም የእንጨት ሥራ የሚማሩትን ልጆች ለማየት ወደ አናጢ ቤት ገቡና ልጆቹ ሥራቸውን አሳይተው ሲያበቁ የኢትዮጵያን መዝሙር በትግርኛ ዘምረው ለልዑልና አብረዋቸው ለነበሩ ሰዎች ሁሉ ደስ አሰኙዋቸው ። መዝሙሩም በማሪኛ ተርጕመነው ይኸው የሚከተለው ነው ።

፩ ኢትዮጵያ ሃገራችንን
እንወዳታለን
በዓለም በሞላዋ
ለኛስ የለም እንደርስዋ
ከአምላክ የተቀበልናት
እናታችን ናት

፪ ኢትዮጵያ ሃገራችን
በእውነት ርስታችን
ጀግኖችዋ የሞቱላት
ደማቸው የፈሰሰባት
እጅግ የደከሙላትን
እናከብራታለን

፫ በኢትዮጵያችንም
ይሁንልን ሰላም
ሙቀትዋ ብርሃንዋ
ግሩም ነውና የርስዋ
ተራሮችዋም ከፍ ያሉ
አምባ ይሆናሉ

ከዚህ በኋላም ልጆቹ ስጦታ ሊቀበሉበት ወደ ተሰናዳው ቤት ገቡና መኳንንትና ወይዛዝር ሁሉ በየመዓርጋቸው ተቀመጡ ። ወዲያውም የትምሕርት ቤቱ ዋና ሹም ክቡር ሐኪም ወርቅነህ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ልዑል ሆይ

ክቡራን መኳንንትና ወይዛዝሮች በትምህርት ለበለጡ ተማሪዎች ሽልማት በሚሰጥበት በዚህ ቀን መጥታችሁ እኛን ማክበራችሁ ታላቅ ደግነት ነው ። ከናንተ ብዙዎቹ እንደምታውቁት ይህ ተማሪ ቤት ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም በተከፈተ ጊዜ ፴ ልጆች ነበሩ ። የመኝታ ቤቱ ሥራ ፈጽሞ ሳያልቅ ስለቀረ ልጆች የሚማሩት እየተመላለሱ ነበር ። ቀስ ቀስ እያለ ግን የተማሪዎቹ ቁጥር እያደገ ስለሄደ በሰኔ ወር ስንዘጋ ፹፱ ያህሉ እያደሩ የሚማሩና ፳፱ እየተመላለሱ የሚማሩ ተማሪዎች ነበሩን ይኸም የኢትዮጵያ ወጣቶች የአውሮፓን ስልጣኔ እንደሚወዱና እንደሚናፍቁ ይመሰክራል ። ልጆቹም እየበዙ ሲሄዱ ቦታ ይጠብ ጀመርና በዚህ ምክንያት አስተማሪዎችም ስላነሱን እንግሊዝ የሚማሩበትን ክፍል ከ፰ ወደ ፫ ክፍል ልናሳንሰው ግድ ሆነብን ። ነገር ግን በዱሮው ቤት ላይ ሌላ እንደጨመርን ተመልክታችሁ ይሆናል ። ከልጆቹም ተምረው በማስተማር እንዲረዱ ፲፪ የሚያህሉ ልጆች ወደ ቤይሩት ተልከዋል ። ፯ቱ ወደ አሜሪካኖች ተማሪ ቤት ፭ቱ ወደ ፈረንሳዊ ተማሪ ቤት ከነዚሁ አንዳንዱ ወንድሞቻቸውን ለማስተማር እንዲረዱ ለአስተማሪነት የበቁ ሆነው ቶሎ እንዲመለሱልን ተስፋ እናደርጋለን ።

የገንዘብ አኳኋናችን ደስ የሚያሰኝ መሆኑን ለመናገር ደስ ይለኛል ። ባለፉት ዓመታት በጎ ከሚያስቡልን ወዳጆቻችን እርዳታ ተቀብለናል ፡

በዚህ ዓመት ውስጥ በትምህርት ላይ የሸማኔ ሥራና ያናጢ ሥራ ፪ የሥራ ትምህርት ቤቶች ተከፍተዋል የሸማኔ ሥራ ትምህርት ቤት ከእንግሊዝ አገር በመጣ ፰ መኪና ከአስመራ በመጣ ፫ መኪና ናቸው የሚማሩት ። የሸማ ሥራ የሚማሩ ፲ ልጆች አሉ የአናጢነት ሥራ የሚማሩ ደግሞ ፲፩ ልጆች አሉ በተማሪ ቤቱ ከተማሩ ልጆች አንዱ ፲፭ ያህል ብር በወር ደመወዝ እያገኘ በከተማ ውስጥ ሥራ አግኝቶ ይሰራል ። እኚህ ሥራ የሚማሩ ልጆች ሥራቸውን ሲጨርሱ ማታ ማታ የሂሣብና የእንግሊዝ ቋንቋ ትምህርት ይማራሉ ላስተማሪዎቹ ባለፉት ዓመታቶች መልካም ሥራ ስለ ሠሩ እውነተኛ ምስጋናየን አቀርብላቸዋለሁ ።

ላስተዳዳሪነት ረዳቶችም የሚበልጡት በሥራቸው ስለተጉ አመሰግናቸዋለሁ ።

ተማሪ ቤታችን ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ

የገንዘባችን ገቢ

፻፳፫ሺ ፫፻፵፰ ብር ፳ ተሙን ፩ ቤሳ

ያስተማሪዎችና ሰራተኞች ደመወዝ	፴ ሺ ፻፶፳፮ ብር ፫ መሐለቅ	፺፩ሺ ፱፻፵፬ ብር ፲መ ፩ ቤሳ
ለተማሪዎች ምግብና ልብስ ለቤት ጉዳይ	፳፩ሺ ፳፱ ፱ ፡ ፲፩ ፡	
አዲስ ለተሰሩት ቤቶችና በምድረ ግቢ	፴፰ሺ ፯፻፷፭ ፡ ፳ ፡	
ለተሰራው ሥራ ሁሉ በልዩ ልዩ ምክንያት ለተማሪቤት ጉዳይ	፱ ሺ ፳፱ ፡ ፯ ፡	

አሁን በሳጥን ቀሪ ገንዘባችን ፴፫ሺ ፩፻-፯ ብር ፲፩ መ ፩ ቤሳ

ቀጥሎም በትምሕርት የበለጡት ልጆች በየስማቸው እየተጠሩ ልዩ ልዩ የሽልማት ስጦታና በልዑል አልጋ ወራሽ መልክ የተቀረፀ የወርቅ ሜዳይ በልዑል አልጋ ወራሽ እጅ ይቀበሉ ነበር ። በተቀበሉም ቁጥር ጭብጨባው ይቀልጥ ነበር ። ደግሞ የፖስታና የቴሌግራፍ ዲሬክተር ክቡር አቶ ብርሃነ ማርቆስ ፡ ጕበና ለተባለው በፈረንሳዊ አንደኛ ለሆነው ልጅ የወርቅ ሰዓት ፡ ናደው ለተባለ በእንግሊዝ አንደኛ ለሆነው ልጅም የወርቅ ብርዕ ሰጧቸው ። ይህም ከተፈጸመ በኋላ የሻይ ግብዣ ተደረገ ። ከሻይ በኋላም ልዑል አልጋ ወራሽ የሸማ ሥራና የዕንጨት ሥራ ለሚማሩ ልጆች ስለ ትጋታቸው ስጦታ ሰጧቸው ፤ በዚያን ጊዜ ከተማሪዎቹ አንዳንዱ እየተነሡ በፈረንሳዊና በእንግሊዝ ያጠኑትን ቃል ሲናገሩ ሰዉን ሁሉ ደስ አሰኙት ። ደግሞ ፯ልጆች ተነሥተው ምሥጢረ ሥላሴን እየተቀበሉ

በማርኛ አሳምረው ደገሙትና ከነሱ አንድ ልጅ የሚከተለውን ንግግር ተናግሮ ሲጨርስ በጣም ተጨበጨበለት ።

እግዚአብሔር አስቀድሞ ብዙ ጊዜ በልዩ ልዩ ዓይነትም ላባቶቻችን በነቢያት አፍ ከተናገረ በኋላ እርሱ በዚህ በኋላኛው ዘመን ዘልጁ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ዓለሙንም የፈጠረው ነገረን ። ከዚህም በኋላ በሐዋርያት በሊቃውንት በመምሕራን አድሮ አስተማረን ፡ ምድርን ያለ መምሕራን ያልተዋት እግዚአብሔር ዛሬም በዘመናችን ለከበረች ኢትዮጵያ ልጆች ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱን አንግሦ አብያተ ክርስቲ ናት ታደሱልን ሃይማኖተ ወንጌል ሰፋልን ።

ደግሞ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንንንአሥነስቶ ያባቶቻችን ትርጓሜ መጻሕፍት እንዳይፋለሱ ልጆችም በአእምሮ እንዲጐለምሱ መጻሕፍትን ከነትርጓሜያቸው በትጋትና በውቀት ስላሳተሟቸው ወንጌል ከሁሉ ደጅ ደርሶ ይነገራል ። ዛሬ በሀገራችን ሃይማኖተ ወንጌል እሰፋ እሰፋ ድንቁርና እጠፋ እጠፋ ብላለችና ለሁለቱ ዓይኖቻችን ብርሃናት ለግርማዊት ንግሥታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን ረጅም ዕድሜ ይስጥልን ። ክቡራን ጌቶቻችን ሆይ በዚች ቀን በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ያለን ልጆቻችሁን ለመጐብኘት ስለ መጣችሁ ክብር ምስጋና ለናንተ ይሁን ።

ከዚህ በኋላም ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ደስ የሚያሰኝ ንግግር ተናገሩና ፫ጊዜ ተጨበጨበ ።

በሀገራችን በኢትዮጵያ በቀድሞ ዘመን አንዳንድ ሰዎች በትጋታቸው ወደ ውጭ አገር እየሔዱ ምንም አንዳንድ ቋንቋ እያወቁ ቢመጡ ባገራችን ውስጥ የቋንቋ ትምህርት ቤት ባለመቆሙ በቋንቋ ነገር ብዙ ችግር ነበር በኋላ ግን ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ ለኢትዮጵያ የውጭ አገር ቋንቋ የሚያውቁ ብዙ ልጆች እንዲያስፈልጋት ስለተረዱት የውጭ አገር ቋንቋ ትምምርት ቤት አቁመው ብዙ ልጆች እንዲማሩ አደረጉ ።

እኔም ይህን የውጭ አገር ቋንቋ ትምህርት ቤት ማቆሜ ለኢትዮጵያ ትልቅ ጥቅም መሆኑን ስለ ተረዳሁት ነው ። ይህም የትምህርት ቤት ሲቆም ሠላሳ ልጆች ብቻ ነበሩና አሁን በሁለት ዓመት እስከ ፪፻ የሚያህሉ ልጆች እንዲማሩበት መሆኑ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ስለ ሆነ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ በዚህም ትጋት እስከ አምስት ዓመት አንድ ሺ የሚያህሉ ልጆች ሰይማሩበት አይቀሩም ።

ደግሞ ለዚህ ትምሕርት ቤት እርዳታ ገንዘባቸውን የሰጡትን ሰውች ሁሉ አመሰግናለሁ ወደፊትም የትምሕርትን ጥቅምነት እያወቁ በየግዛታቸው የትምሕርት ቤት እንዲያቆሙትስሩ አደርጋለሁ ።

የትምሕርት ቤቱንም ዋና አድሚኒስትራቶር ሀኪም ወርቅነህንና አስተማሪዎቹን ሁሉ አመሰግናለሁ ።

ደግሞ ተማሪዎቹ ሁሉ ትምህርታቸውን ጨርሰው በእድሜ ቆይተው አገራቸውን ለማገልገል እንዲ በቁ እመኛለሁ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ እድሜና ጤና እንዲሰጣቸው ለሀገራችን ሰላምና በረከት እንዲሆን እግዚአብሔርን ለምናለሁ ብለው ጨረሱ

ቀጥሎም ልጆቹ የቴአትር ጨዋታ ተጫውተው ሰዉን ሁሉ ደስ አሰኙት ይህ ሁሉ ሲሆን ተማሪዎቹ በሙዚቃ እየተመሩ አያሌ መዝሙር ይዘምሩ ነበር ፡

በትምህርት ቤቱ አኳኋን ደስ ብሎዋቸው ክቡር ደጃዝማች ብሩ ፲ ወቄት ወርቅ ለተማሪ ቤት ወረቀትና ቀለም መግዣ እርዳታ እንዲሆን ። ፲ ጥገት ላም ለልጆች ወተት የሚሰጡ ፱ ወላድ በግ የሚረቡ ። ፫ ጥምድ ሀሬ የትምሀርት ቤቱን አት



ክቡር ደጃዝማች ብሩ የወለጋና የአቢጋር ግራብ አውራጃ ገገር ።

ክልት መሬት የሚያርሱ ሰጡ ። ከዚህ በፊትም ለትምህርት ቤቱ እርዳታ ሰጥተዋል ።ክቡር ደጃዝማች ብሩ እንዲህ አድርገው ለትምህርት ቤት ለግሰው መስጠታቸው የዕውቀትና የስልጣኔ ወዳጅ መሆናቸውን ያስረግጣል ። ዱክ ዴዝ አብሩስ ሺ ብር በክቡር ሙሴ ኰራ እጅ በዚሁ ቀን ሰጡ ።

ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ፪፻ ብር ሰጡ ።

ክቡር ደጃዝማች አባ ሻውል ፶ ብር ሰጡ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለትምህርት ቤት ዋና ሹም ሐኪም ወርቅነህና ላስተማሪዎቹ ስለ ትጋታቸውና ስለ ሥራቸው ማከናወን ማመስገናቸውና ለተማሪዎቹ የተገባቸውን ልዩ ልዩ ስጦታ በመስጠት ደስ ማሰኘታቸው በትጋታቸው ትጋት እንዲጨምሩና ኢትዮጵያ በዕውቀት የጐለመሱ ልጆች አግኝታ እንድትበረታ ሙሉ ጥረታቸውን ያስረዳናል።ለልዑል ተፈሪ መኰንን ዕድሜ ሰጥቶ አገ

ራችንን ሰላም ያደርግልን እንጂ የኢትዮጵያ ብርሃን እንዲደም ቅ ሙሉ እምነት አለን።

ብርሃንና ሰላም በሥራቸውትጋትና መከናወን ለተመሰገኑ ክቡር ሐኪም ወርቅነህ የትምህርት ቤቱ ዋና ሹምና ለክቡራን አስተማሪዎች ምስጋና ያቀርብላቸዋል ። በትምህርት በመብለጣቸው የተሸለሙት ተማሪዎችም ሲሚመጣው ዘመን የበለጠ ትጋት አሳይተው የበለጠ ምስጋና እንዲያገኙ እየተመኘ እንኳን ደስ አላችሁ ይላል ።ልክ ፲፪ ሰዓት ሲሆን ስርዓቱ ተፈጸመና ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ከመኳንንቶቻቸው ጋራ ተነሥተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ ።

ስለ ድሆች ትምህርተ ቤት ።

የአዲስአበባ ከተማ ማዘጋጃ ሆት የድሆች ልጆች የሚማሩበት የትምህርት ቤት ለመስራት ከ፱ ዓመት ጀምሮ ከከተማው ሕዝብ ጥቂት ጥቂት የእርዳታ ገንዘብ ማጠራቀም ጀምሯል አሁንም ባለፈው በግንቦት ወር ልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ ከኢጣሊየ ወደ አዲስ አበባ መጥተው የማዘጋጃ ቤትን በጐበኙ ጊዜ ለነዚሁ ለድሆች ልጆች ትምህርት ቤት ሥራ እርዳታ ፫ሺ ብር ሰጥተዋል

የአለም ነገሥታትና መሳፍንት የሌላውን አገር ለመጐብኘት በሄዱ ጊዜ ለትምህርት ቤትና ለሆፒታል የእርዳታ ገንዘብ መስጠታቸው እጅግ ያስመሰግናቸዋል ።

የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ወደፊት ለድሆች ልጆች ትምህርት ቤት የሚበቃ ገንዘብ አግኝቶ ለዚሁ ትምህርት ቤት መሰሯ የሚሆን ቦታ ፈልጎ ሥራውን በቶሎ እንዲጀምር ተስፋ እናደርጋለን ።

የእጅ ሰዓት ዝኒት ፤



እጅግ ጥሩነቱ የተመሰከረለት አሚጋ በቢ የሚባል ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን !! በ፡፣ ፣ ፃ ቃ ፅ

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

ሩግ
ቢ

RUGBY

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፊታውራሪ ዴፌሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሂስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፣ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ማጥን በየዓይ ነቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፣ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

ለውነተኞች ኢትዮጵያውያን ማስታወሻ ።

በፈረንሳይ ቅኝ አገር ወሰንና በእንግሊዝም እንደቆመው ጉምሩክ ሁሉ ኢትዮጵያ በማናቸው አይነት ወሰን የሌለው ጥቅም የምታገኝበት ነውና በአድዋ ከተማ ላይ ለሐገሩ ሺአለቆች የሚ ገባቸውን ጥቅም ማትነክ በሥራት ተተክክሎ ሊቆም ያለውን ጉምሩክ በፍጥነት ማቆም ያስፈልጋታል የዚሁ ነገር ጥቅም የሚ ያስረዳ በስራት ጽፌን አዘጋጅተናልና መረዳት የሚገባው ሁኖ ከተረዳውም ይህ ነገር እንዲፈጸም ሊረዳ የሚችል ሰው ይህን ለጻፈ ሰው ጠይቆ ጥቅሙን በዝርዝር ሊያውቀው ይችላል ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።

አራዶም ዕቅቡ

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ክቡራን የኢትዮጵያ መኳንንትና የውጪ አገር ሰዎችም የፍቅርና ያአገልግሎት ማኅበር ነፃነት ለተፈቀደላቸው ባሮችና አባት እናት ለሌላቸው ድሆች ልጆች ስለቆመው የእጅ ሥራ ተማሪ ቤት እርዳታ እንሰጣለን ያላችሁትን ችሮታችሁን እኔ አሁን ለጊዜው ወደ መንገድ የምሄድ ስለሆነ ገንዘቡ በልጅ ብርሃ ነ ሥላሴ አበየሬ እጅ ተሰብስበ እንዲቆየኝ ተስፋ እያደረግሁ ለሱ እንድትሰጡልኝ በማክበር አስታውቃችኋለሁ ።

የፍቅርና አገልግሎት ማኅበር አለቃ ።
ሐኪም ወርቅነህ

ARMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኔዲሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፳፰
3 me ANNÉE № 28

ሐሙስ ሐምሌ ፯ ቀን ፤ ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 14 JUIL 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ሕዝብ አስተዳደር

የኢትዮጵያ መግሥት ከጥንት ከመሠረት ከብዙ ዓመታት በፊት ጀምራ ብርቱ በዓለም ሁሉ የታወቀች እንደነበረች ብዙ የዓለም ታሪክ ይነገርላታል ። ደግሞም ከዚህ ጋራ ለጊዜው የሚያስፈልግ የሕዝብ አስተዳደር እንደነበራት ብዙ ታሪኮች ይነግሩናል ። ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የቆየውን ታሪክ ብንመለከት ኢትዮጵያ በዙሪያዋ ካሉ ጠላቶቿ ጋራ ስትዋጋና ስትከራከር እንደ ነበረ ማንም ሊረዳው ይችላል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ መንግሥት ከጀመረ አንስቶ እስከ አያሌ ዘመናት ድረስ እንደ ጊዜው በኀይል በእውቀት ፤ በጥበብም ከጎረቤቶቹ ሳይሰንፍ ዘመናቱን አሳለፈ ። ነገር ግን በኋላኛው ዘመን ኢትዮጵያ እውቀትንና ጥበብን ትቶ ኀይልና ብርታት የሚባሉትን መሣሪ ብቻ ይዞ ይኖር ጀመር የዚህም ምክንያት በላይ እንዳመለከትነው በዙሪያዋ ባሉ ጠላቶች ሁከት ዕረፍትና ሰላም ስላጣ ከጠላቶቹ ጋራ ለመቃወም እንዲመቸው ሲል ሕዝቡን ሁሉ በመላው የኀይል ብልሀት ብቻ ያስተምራቸው ጀመር ። በዚህም ብርታቱ አገሩን ለባዕድ ሳያሳልፍ እስከ ዛሬ ድረስ ነጻነቱን ስለጠበቀ ኀይሉንና ጥንካሬውን አይቶ ዓለም በመላው ያደንቃል ነገር ግን የኢትዮጵያ መንግሥት በዛሬው ጊዜ ያረጀውን የዱሮ ብልሀትና ጥበብን ብቻ ይዞ ለመኖር አይቻለውምና ላሁኑ ዘመን የኢትዮጵያ መንግሥት ሊያቆመው ግድ የሚያስፈልገው ሕግና ሥርዓት ብዙ ነው ከዚሁም ጥቂት ጽፈን እናመለክታለን ። አሁን ጽፈን ለማስታወስ የምንደፍር አርእስት ነገሮች እነዚህ ናቸው እነዚህም ያስተዳደር አኳኋን በምስት ይከፈላሉ የገበሬ የነጋዴ የወታደር የካህን ፤ የመኳንንት አስተዳደር ናቸው ። እነዚህ ባምስት የመደብናቸው ክፍሎች ጥቅማቸውና ፍሬያቸው ልዩ ልዩ ቢመስል የዚህም የዚያም ጥረት ተረዳድተው መንግሥታቸውን ለመጥቀም ብቻ ነው ። ስለዚህም የመንግሥት ሕይወቱ ብርታቱ ኀይሉ ተብለው ይጠራሉ ። መንግሥትም ለነዚህ ክፍሎች ለያንዳንዱ ሊፈጽምላቸው የሚገባውን ከዚህ ቀጥለን እናመለክታለን ። የኢትዮጵያ መንግሥት የተደላደለ የሕዝቡ ማስተዳደሪያ ደምብ የለውም ለማለት እንደፍርም ። ነገር ግን ደግሞ እንደዚህ ያለውን ተስፋ ይዘን ለመድፈር እንችላለን አንድ ድኃ ልጅ የተቸገረ ላባቱ ወይም ለናቱ ለንጉሡ ወይም ለጌታው የሚፈልገውን ነገር ሲለምን አይፈራም አያፍርምም እነዚህ እንደ ማይቆጡትና እንደማይጠሉትም ያውቃልና ሳይፈራ አጥብቆ ይለምናል እስኪፈጽሙለት ድረስ ። ስለዚህ እኛ በዚች አገር የተወለድን ልጆች የናታችንን ጥቃትዋንና ውርደትዋን የድሆችዋን መከራና ስደት እያየን ዝም ብለን ለመታገስ አይቻለንም አገዛዝ ከፍቶባቸው የሚወዱዋትን አገራቸውን ትተው ወደ ባዕድ አገር እየሄዱ ስለሚያልቁ ወንድሞቻችን ምክንያት እናታችን ኢትዮጵያ ግርማዋ የሚሆናት ድኃዋ እየተዋት ስለሄደ እናዝናለን ። እነዚህ ወንድሞቻችን ደግ የሕዝብ አስተዳደር ኑሮዋቸው ቢሆን አገራቸውን ጥለው አይሄዱም ነበር ስለዚህ ለከበሩ ጌቶች እንደመሰለኝ ማስታወሻ ይሆናል ብዬ ያሰብኩትን ቃል አመለክታለሁ ።

ከዚህም የሚበልጥ አዲስ ደምብና ስርዓት ለሕዝባቸው በፍጥነት እንዲያወጡለት ተስፋ እናደርጋለን ።

ስለ ገበሬ አስተዳደር ፤

ገበሬ የሚባል ክፍል የራሱ ለሆነ መንግሥት ኀይሉ ብርታቱ ሕይወቱ ስለሆነ መንግሥት ሊፈጽምለት የሚገባው ይህ ነው ። መጀመርያ ገበሬ በሚኖርበት አገር ከሚያገኘው የምድሩ ፍሬ ሁሉ ባመት አንድ ጊዜ ብቻ ተከብትም ተሀል ከሚያገኘው ሁሉ ከስር አንድ ለመንግሥት ሊያመጣ ይገባል

መንግሥትም አሥራቱን የሚቀበሉለት የታመኑ ደህና ደህና ሠራተኞችና ጸሐፊዎች መሾም ያስፈልገዋል ስለዚህ መንግሥት ይህ ድኃ ለፍቶ ከሚያገኘው የድካሙ ፍሬ አስራት ቢቀበልና በትክክልም ቢገዛለት ገቢው ጥቅሙ ያንስ አይመስለኝም ። ነገር ግን ለድኃውም ከሚያገኘው የምድሩ ፍሬ ቢሰጥ ተመችቶት በኖረ በደረጃ ሀብትም ባገኘ ነበር መንግሥትም ድኃው ስለ በለጠገለት ሀብት ባገኘ ፡ ገቢውም በበዛለት ነበር ነገር ግን መንግሥት ድኃ የማያገኘውን ግብር አምጣ ቢለው አይሠራውምና አገር ለቆ ይሄዳል እንጂ ሊያገኝ አይችልም ስለዚህ መንግሥት ባገሩ ድኃው ሊበለጥግለት የፈለገ እንደሆነ በድሀው ያለውን ዕንቅፋት ሁሉ ታገር አጥፍቶ በደግ አገዛዝ እየጠበቀ ሕዝቡን እንዲመራ ይገባል ። ሁለተኛ ይህ ድኃ ገበሬ ባመት ባመት አዲስ ስርዓትና ደምብ እየገባለት እንዲሰለጥንና እንዲሁም መንግሥት በያገሩ መንገድና ድልድይ ሊሠራለት ያስፈልጋል ። ሶስተኛ ይህ ድኃ ገበሬ ባገሩ እንዲበለጥግና ብዙ ገቢ ገንዘብ ሊያገኝ ቢፈልግ ባዶ ያለ መሬት እያየ መሬት ላልያዘና ርስትም ለሌለው ድኃ የሚበቃውን ያህል ሰጥቶ ፬ ወይም ፫ ዓመት እስኪደረጅ መርዳት ነው ። አራተኛ ድኃው ገበሬ ለሙግት ለነገር ሲል ሥራውን ፈትቶ እየመጣ አቤት እንዳይል ትክክለኛ ዳኛ ፈጣሪውንና ንጉሡን የሚፈራ መማለጃ የማይቀበል የሚበቃ ቀለብና ማደሪያ ያለው ሊሾምለት ይገባል ድኃው መጥቶ በጌቶቹ ፊት አቤት እያለ በመጮህ እንኳን ጌቶቹን ይቅርና ለሚሰማውም ሰው በጣም ያሰቅቃል ። ነገር ግን ከዚህ ይበልጥ አስር ጊዜ ድኃው ሥቃይ እንዳለበትና ሥራውንና ምሽቱን ልጆቹን ቤቱን ትቶ ስለመጣ እሱም በረሃብና በብርድ መንፈቅ ዓመት ምሉ ሲቀመጥ በጣም እንደሚጨነቅ ጥርጥር የለውም ። አምስተኛ መንግሥት ለድኃው ገበሬ ከውጭ አገር የሚገዛው ዕቃ ሁሉ ባገሩ ተርፎ እንዲሸጥለት ማድረግ ይገባል ደግሞም ባገሩ ውስጥ የገንዘብ ምንዛሬ ከትንሹ እስከ ትልቁ ያለውን የገንዘብ ለውጥ ያለ ችግር እንዲያገኝ ያስፈልገዋል አለዚያ ግን የገንዘብ መለዋወጫ የሌለው ሕዝብ እየጠፋ እንጂ እየለማ እንዳይሄድ የታወቀ ነው ይህም መብል አግኝቶ የሚጎርስበት እንዳጣ ያህል ነው ሕዝብ ለሚኖርበት አገር ጌጥ ሽልማትዋ ነውና ስለዚህ ሽልማት ከልጸዳና ከልተጌጸ ሊያምር አይችልም ስለዚህ ለድኃ ይህን በሚመስል ከዚህም በሚሻል አስተዳደር ቢጠብቁት ለመንግሥትና ለህዝቡ ትልቅ ሀብት እንዲያመጣ ማንም ሊረዳው ይችላል ።

ስለ ነጋዴ አስተዳደር ።

ነጋዴ የተባለ ክፍል ካገሩ በያይነቱ ዕቃ እየወሰደ ወደ ሌላ አገር የሚሸጥና እንዲሁ ከሌላ አገር ልዩ ልዩ ዕቃ እያመጣ የሚሸጥ ነው ፡ ይህን ድኃ ነጋዴ የመንግሥትና የሕዝብን ጥቅምና ሀብት የሚያቀባብል ረድኤት የመላው ፈጣን መላክተኛ መርከብ ብለን እንጠራዋለን ፡ በዚህ መካከል መንግሥት ከወረጃና ከወጪው ብዙ ገቢ ቀረጥ ያገኝበታል እንዲሁ ነጋዴው ከሚያመላልሰው ዕቃ ሁሉ የድካሙን ፍሬ ብዙ ትርፍ ያገኛል ። ሕዝቡም ሀብት ያገኛል ይሠለጥናልም ነገር ግን ይህ ድኃ ነጋዴ መጀመሪያ መንግሥት የተደላደለ የቀረጥ ደምብ አቁሞ ቀረጡን በትክክል የሚቀበሉት የተማሩና በሥራም የሰለጠኑ ሂሣብ ያወቁ ጸሐፊዎችና ሠራተኞች መሾም ያስፈልገዋል ይህም ባዲስ አበባና በሐረር አውራጃ ብቻ ሳይሆን በመላዋ ኢትዮጵያ አገር በርና ኬላ ባለበት ሁሉ ማቆም ነው እንጂ የሁለት አገር ገቢ ከኢትዮጵያ በሥሩ መእዛን እየሄደ ለባእድ አገር ጥቅም ብቻ ለሚሆን ገንዘባችን መጠኛ ሊሆነን አይችልም ። ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደዚህ ያለውን ጉዳት ተመልክቶ በያገሩና በየበሩ የተደላደለ የቀረጥ ደንብ በቶሎ ቢያቆምበት በነዚህ በሁለቱ አገሮች ባዲስ አበባና በሐረር አውራጃ ከሚያገኘው ገንዘብ ይልቅ መቶ ዕጽፍ እንደሚያገኝ ጥርጥር የለበትም ። ስለዚህ መንግሥት በላይ እንዳመለከትሁት አዲስ ሕግ ለሕዝቡ ቢፈጥርለት አገር በለማ ሕዝብም በሰለጠነ መንግሥትም በተጠቀመ ነበር ። ነገር ግን ይህ ድኃ ነጋዴ ባገራችን በኢትዮጵያ የተተካከለ የቀረጥ ደምብ ስላልተበጀለት ለመንግሥት ብዙ ቀረጥ አይገባለትም ምክንያቱም ከዚህ በሚከተለው ምሳሌ እንገልጻለን ። አንድ ነጋዴ መቶ አጋሰስ ጭኖ ለንግድ ቢነሣ አስቀድሞ በያገሩ ብዙ ኬላ አለና በየበሩ ለቀራጮቹ ሲከፍል የጫነውን እኩሌታ ያህል መክፈሉ አይቀርም ። ሁለተኛም ባለፈው ኬላ ቁጥር በረኛው አቁሞ ቀረጡን እስኪቀበለው ድረስ ብዙ ጊዜ ይቆያልና ክብደቱ ሰማንያ የሚያህል ኪሎ የተጫኑ አጋሰሶች በገጣባው ጀርባ ላይ ተገትረው ሲውሉ የክብደቱና የቁስሉ ሥቃይ ስላስጨነቃቸው እህ እህ እያሉ ይጮኻሉ ለነጋዴውም ብዙ ስቃይ ይሰማዋል ጨካኙ በረኛ ግን ይህ ሁሉ መጨነቅና ስቃይ በልቡ አይገባምና አይሰማውም በዚሁም መካከል ካጋሰሶቹ አምስት ወይም ስድስት ይሞቱና ለነጋዴው የባሰ ጭንቅ ይሆንበታል ኪሳራውም ይበዛል ይህም ዋና የመንግሥት ኪሣራ ነው ።

ስለ ወታደር አስተዳደር

ወታደር የተባለ ክፍል የመንግሥት ኃይል ኩራት የሕዝብ ጠባቂ ተብሎ ይጠራል ፡ ስለዚህ መንግሥት ለወታደር ትክክለኛ ደምብ ሠርቶ ትምህርትና ዘብ መጠበቅ በጣም ጠንቅቆ እንዲማርና እንዲሰለጥን ያስፈልገዋል እንዲሁም በጣም የሠለጠኑና የወታደር ደምብ ጠንቅቀው ያወቁ አለቆች መሾም ያስፈልገዋል ። ላንድ ወታደር የሚበቃው የወር ቀለብ ያመት ልብስ የሚቀመጥበት ቤት አንድ ጠመንጃ አምሳ ጥይት አንድ በጠመንጃው አፈሙዝ የሚሰካው ሰይፍ (ሳንጃ) ከመንግሥት ሊያገኝ ይገባዋል ። ወታደርም በታዘዘበት ሥራ ሁሉ ፈጥኖ ተግቶ አለቃው ያዘዘውን መፈጸም ግድ አለበት እነዚህም ወታደሮች በዋናዋ ከተማ ባዲስ አበባ ብቻ ሣይሆን በመለዋ ኢትዮጵያ አገር ከተማና ገጠር ነው እንጂ ። ይህም ወታደር የመንግሥቱን ደምብ ጠንቅቆ መጠበቅና ከዚያም ላንዳያልፍ ከዚያም እንዳያጎድል ደምቡን በትክክል መፈጸም ይገባዋል የተማረና የሠለጠነ የመንግሥቱንም ሕግ የሚጠብቅ ወታደር ያለው አገር መንግምቱ ይከበራል ሕዝቡም ይታፈራል ነገር ግን እንደ ቀድሞው ያለ የወታደር አስተዳደር ለኢትዮጵያ መንግሥት አይጠቅምም የኢትዮጵያ ጀግናው ወታደር በደምብ ሊያድር የተገባው ነው ነገር ግን የኢዮጵያ መንግሥት ወታደሮቹን በትክክል ሊያሣ

ድር ቢፈልግ አስቀድሞ ለመላው አገርና ከተማ የሚያስፈልግ
ወታደር ደሞዝ ሰጥቶ በልክ ማሰደር ነው በዚህም አገልጋይ
የሆነና የማያገለግለውን ወታደር በታወቀ አገር በደህና በተጠ
በቀ፡ሽፍታ ወንበዴ ሽፉጭ ቀማፊም ካገር በጠፉ፡ሕዝብ በለማ
ሰላምም ባገኘ ነበር ፡ እንግዲህ ለዚህ ሁሉ አደራጂው መንግ
ሥት ብቻ ነው ባዲስ አበባ ያለ ሕዝብ ከብዛት የተነሣ መተ
ላለፊያ መንገድ ሲጠፋ ሰው አገሩን እየተወ ቢመጣ ነው እንጂ
መንግሥት ሥራ አውጥቶ በየክፍሉ ቢወሥ ነው ሕዝቡ ይጠ
ቀም መንግሥቱም ይመሰገን ነበር ።

ስለ ካህን አስተዳደር ።

ካህን የተባለ ወገን በእግዚአብሔርና በሰው መኻከል ሁኖ
ሰውን ከእግዚአብሔር ጋራ የሚያስታርቅ እንዲሁም የእግዚአ
ብሔርን ሕጉንና ትእዛዙን የሚያስተምር ነው ። ነገር ግን ባገ
ራችን በኢትዮጵያ ለካህን የተመደበ የተተከከለ ማደሪያ የለ
ንም ያገራችን ካህን ግን የተወሰነ ማደሪያ ሣይኖረው ሕግ እን
ዳይፈርስ ሃይማኖት እንዳይጠፋ ዘለዓለም እንደተጋ ይኖራል በዚ
ህም በዓለም ሲደነቅለት ይኖራል፡ነገር ግን የኢትዮጵያ መንግ
ሥት በካህን ስም የሚያወጣው ገንዘብ እንኳን በኢትዮጵያ ላለ
ካህን ለሌላም ይበቃል ። ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግሥት ባገሩ
ሕዝቡ እንዲሰለጥን ትምህርት እንዲሰፋ ሃይማኖት እንዲጸና
የፈለገ እንደሆነ ለመላዋ ኢትዮጵያ አብያት ክርስቲያን የሚበቁ
ካህናት በደሞዝ አሳድሮ ሕዝቡን መጻሕፍትን እያስጠኑ የሃማ
ይኖትን እውቀት እንዲማር ማድረግ ነው ። ሕዝቡም ባገሩ ቋንቋ
በግእዝና ባማርኛ ንባብና ጽሕፈት ከትርጓሜው ጋራ ተምሮ
ከጨረሰ በኋላ እንዲሁም ልዩ ልዩ ቋንቋና ጥበብ እንዲማር ያስፈ
ልገዋል ኢትዮጵያ እንደዚህ ሁና ብትማር በጥቂት ዓመታት ትሰለ
ጥን ነበር ሕዝባችን እንደዚህ በጣም ሳይማር ፈጣሪውን የሚ
ያምነውና የሚፈራው ይልቅ ቢማርና ቢሰለጥን እንዴት አብ
ልጦ በወደደውና በታዘዘለት ነበር እንደዚህ ተግቶ ላገሩና
ለተመሰገነች ሃይማኖቱ ሕይወቱን ለውጦ ነጻነቱን መጠበቁ
እጅግ ይገርማል ስለዚህ መንግሥት በላይ እንዳመለከትነው
ለካህን አዲስ የሚበጅ ደምብ አቁሞ ሕዝቡ እንዲማር ያስፈ
ልጋል ።

ስለ መኳንንት አስተዳደር ።

የኢትዮጵያ መኳንንት ከጥቂቶቹ በቀር ደግ ስርዓትና ማስ
ተዳደርያ ደምብ ስለሌላቸው በኑሮዋቸው ደስ ብለዋቸው የሚ
ኖሩ ብዙ አናይም ፤ ደግሞ ለራሱ ጉዳት ለሕዝቡ ጥፋት ለመን
ግሥቱም ኪሣራ እንጅ የተጠቀመ መኳንንት ጥቂት ብቻ ሳይ
ሆን አይቀርም ነገር ግን የዚህን አኳኋን አጥብቀን ብንመረ
ምር መድኃኒት ይገኝለት ይመስለኛል የመኳንንቶቻችን ጉዳት
የሕዝባችን ጥፋት እጅግ ያሣዝናል ስለዚህ መንግሥት ንብረ
ታቸው የተሻለ እንዲያደርግላቸው ተስፋ እናደርጋለን ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ከዚህ በላይ ጽፌ ያመለከትሁ
ትን ያልታረመና ያልተተከከለ ሐሳብ አይታችሁ እንዳትከፋብኝ
የትሕትና ልመናዬን አቀርባለሁ ይህን ሁሉ ያስለፈለፈኝ ጉዳት
ስለተሰማኝ ነውና ስለዚህ ክቡራን ጌቶቻችን በሰፊው እውቀታ
ችሁ እንዲተጉበትና እንዲያስቡበት ስል ነው ።

ይግዛው ጎሹ ።

ስለ ክቡር ደጃዝማማች ኃብተ ማርያም ግዛት ለተጻፈው ቃል መልስ ፡

አንድ የብርሃን ሰላም ተላላኪ በክቡር ደጃዝማች ኃብተ
ማርያም ላይ የሐሰት ቀንበር ስለ ጫነባቸው ቢአሳዝነኝ ከዚህ
በታች የተጻፈውን ቃል እንዲአትሙልኝ ስለ ማክበር እለም
ናለሁ የክርስቲያን ልብ ሚዛን መሆኑን ልብ ያድርጉት ስለ
ክቡር የብርሃን ሰላም ተላላኪ መልስ ክቡር ደጃዝማች ኃብተ
ማርያም በግዛታቸው ውስጥ የፈረንሳዊ የትምህርት ቤት ስለ
ማቆማቸውና ብዙህ ልጆች አስተምረው ስላሰለጡኑ እንኳንስ
ባሉበት አገር ይቅርና ለኢትዮጵያ መንግሥት ሁሉ ያስተማሯ
ቸው ልጆች በውቀት እንዲረዱን ተስፋ ነበረን፡አሁን ግን አን
ድ የብርሃን ሰላም ተላላኪ ነኝ የሚል ሰው በደጃዝማች ኃብተ
ማርያም አገር ላይ የሌብነት ስልጣኔና ስራ የዝሆንና የጐሽ
መግደል ይደረጋል ብሎ የምቀኝነት ወሬ ስለ አውራ ብዙ የሚ
አሳዝን ነው አንተስ ይኸነን የቅንአት ወሬ መጻፍህ መጽሐፍ
ስትደግም ከእለታት አንድ ቀን እስመ በቅንአትስ ኢይትረከብ
ጸጋ እግዚአሔር ያለውን ተመልከተህ አታውቅምን በክቡር
ደጃዝማች ኃብተማርያም ገብረ እግዚአብሔር አገር ላይ የነጋ
ዴና የድንገተኛ ሰው ለከብቱ መሳፈሪ ቤትና ሽቦ ተሰርቶ እራ
ቱን ተጋብዞ ከብቱንም በሚገባ ሕግ ያለ ዋጋ አድሮና በአልፍ
ተሸኝቶ በደስታ ወደ ሚፈልገው ቦታ መሄዱን የሚያውቁ
ሰዎች ሁሉ እንዴት ይስቁብህ ይሆን በጣም አዘን ኩልህ ምክር
እንዳላካፍልህ ስምህ ጠፋብኝ ማን ብየ ልምከርህ ለወደፊት ስም
ህን ንገረኝ አደራህ ወዳጄ ሆይ፡ፎተኛ ስለ ዝሆንና ጐሽ መሞት
አንተን ምን ያሳዝንሃል ስለዝሆን ነገር የጻፍከው ንግሥተ አዜብ
ለጠቢብ ሰሎሞን ያቀረበችውን ነገር ከጢሮስ ከሲዶና የመጣው
አምኃ የዝሆን ጥርስ ከማን እንደ መጣ ስለሞን አትመለከትም
ከሰማይ ያላንድ ውርዝው ነኄ በተቀር ለአዳም የታዘዘው ምን
ግብር ይቀርብናል እነሆ ተመልከተው የእስክድር ተማሪዎች የተ
ዋኒ ደራሲዎች ያሉትን እስራኤል መሰሉ ቀታሌ ኃያል ነኄ እስመ
በርእሶሙ ገብሩ እንተ ዘድንግል ጽጌ ሰሎሞንም ቤተ መንግ
ሥቱ ወይም ቤተ መቅደሱ የተሰራው በዝሆን ጥርስ ይባላል
ይህ የሆነው ዝሆኑ ሂዶ ነው ወይስ ሞቶ ነው ይህን ተመልከ
ትልኝ የዝሆን ጥርስ ዋጋ ማውጣቱንና ቀረጡ ለመንግሥት እን
ደሚጠቅም አልሰማህምን የጐሽንስ ቀንድ ዋንጫ ተሰርቶ ጠጅ
እንኳን ብታጣ ጉሽ እንኳ ጠጥተህበት አታውቅምን ይልቅ ከዚህ
ከቅናት ወሬ እምተናግሮ ይሂይስ አርምሞ ያለውን ብትማር ይሻ
ልህ ይመስለኛል ደግሞ በመጨረሻው የሚአስቅ ጨዋታ ተጫ
ውቶ መለያየት መልካም ነውና አንተን እራስህን ጭምር የሚ
አስቅ አንድ ጉባኤ ቃና ልስጥህ ስምህን አስበህ ተመልከተው
ዋህድ ሰብእ በላዕለ እግዚእ ቀንአ አምጣነ ግብሩ ቀሊል ወማህ
በረ እግዚእ ዘጸልአ ይልሃል አኃዱ ኢትዮጵያዊ ዘአልቦ ጽልሁት
ውስተ ልቡ ይላል አሁንም የብርሃን ሰላም አንባቢዎች ሆይ

ከብረት ዝገት ከሰው ስህተት አይጠፋምና ይቅርታችሁን እንድት አደርጉልኝ ስል በማክበር እለምናለሁ

ታናሽ ወድንማችሁ ቀኛዝማች መርሻ ታ ።

የድሬዳዋ ሕዝብና ሠራተኞች ስለ ጻፉት ምስጋና እነውተኛ መልስ።

ሽማግሌ ሲተርት አለ ባለ ቤቱ አይነድም እሳቱ ይላል ። እንዲሁም ያገራችን ሹማምትና አለቆች በተሾሙበት ሕዝብና ወታደር ሠራተኛ ጉዳቱን የሚጠብቁና ጥቅሙን የሚያስቡ እጅግ ብዙ አይደሉም ። እስቲ እንዲያው እንኳን ሕዝቡ በን ድነት ተሰብስበውና ተስማምተው ሲያመለክቱና ሲደክሙ ይህ ንን አስቦ ለማድረግ እንኳን እየተመረጡ የተሾሙትና ማንም ደንቆሮ አይስተውም ነበረ ። ይሁንና እነዚህስ ያወቁ የሰለጡ ደግሞ ባገራቸው ሥስታ በትክክል የቆመ ስለ ሆነ ጉዳያቸው በቶሎ ታውቆ ተፈጸመላቸው ። መቼም በኢትዮጵያ ያለ ሕዝብ በጥቃቱና በመበደሉ የሚጠብቀውና ተስፋው መንግሥት ነው፤ ኬላ እንኳ ለማለፍ እየቸገረው በየአገሩ የሚያለቅስና እዚሁ እከተማ መጥቶ በችግር ላይ ችግር እየተጨመረበት የሚኖር ስንት ይሆን ምን ያህልስ ዓመት የተቀመጠ ይገኛል? ይህ ሁሉ ካመልካችና ከስታዋሽ ጥፋት ነው እንጂ ልዑልማ ለሕዝባቸው ምን ጊዜስ አጃቸውን እንደ ዘረጉና ዓይናቸው ችግረኛና የተ በደለ እንደ ፈለገ አይደለምን ፣ ብርሃንና ሰላም በሰስተኛው ዓመት በ፳፯ ቁጥር በ፪፻፲፪ገጽ ሻቃ መኰንን ሰው የሥራውን ማስተካከል ግድነት ሳይኖረው ለሹመቱና ለእንጀራው ብቻ እየጓጓ በማያውቀውና ባልሠለጠነበት ሥራ ተሹሟል ስላሉ እውነትም እንደዚሁ ሁሉም ሹመት የሚፈልገው የተሾመ ውም የራስ የራሱን ጥቅም ብቻ ይፈልጋል እንጂ ላገራቸው አገልግለው ፡ መንግሥታቸውን ረድተው ፡ ሥራቸውን አከናው ሠራተኞቻቸውን ሕዝብና ወታደራቸውን በትክክል ጠብቀው የሚኖሩ ጥቂቶች ይኖሩ ይሆናል፤በተረፈ ሌላውማ እሱ እንደ ማሰጠትና እንደ መጥቀም ያንኑ የተሾመበትን ሕዝብና ሠራ ተኛ እጅ ይጠብቃል ። ይህም ትልቅ ጉድ ነው ።

እረ እኔስ የገረመኝ አንድ ነገር ነው ፣ እነዚህ የድሬዳዋ ሕዝብና ሠራተኞች ብዙ ቀንና ብዙ ጊዜ ባለቆቻችን በኩል ደከምን ይላሉ ፤ አሁን በቀጥታ ጌታቸው ሲፈጽሙላቸው እንደ ምን ያለ ቁጭት ይገባቸው ይሆን ዕድሜ ለተፈሪ እንጂ ይህ ሁሉ ግፍ ቀርቶ የሰው ልጅ ሰው የሚሆንበት ጊዜ ደርሷል ። ግን ረዳት ስለሌላቸውና ብቻቸውን በመድከማቸው ማዘን ይገ ባናል እንጂ በተረፈስ በሙሉ አፋችን ለመጥራት ቅር ይለን እንደ ነበረ እንደ ጐረቤቶችዋ ትክክል ሆና በሙሉ ልባችን ኢትዮጵያ ለመባል ደረሰች ፡ እኛም ልጆችዋ ተስማምተንና ሠልጥነን እናታችንን አገልግለን ለማስመስገን ያብቃን አሜን ፤

እንጀራዋ ብዙ እናትህ ሐበሻ።
መሶብ እያነሳት መብሊያ አጥታ ስትሻ፡
አሁን ልትሰፋ ነው ለከታ ብንት ጋሻ ፡
ደኅ ኢትዮጵያ ደስ ይበልሽ ኩሪ፡
ያንቺ ልጅ ብቻ ነው የታጠቀ ሱሪ፡
ጥበብን ተምረሽ ኩታሽንም ሥሪ፡
ጠባብ ቀሚስሽን ያስፋልሽ ተፈሪ

ኢትዮጵያ

ወልዳ እንዳልወለደች ሲለኝ ወገንተኛ
መሰንበት ደግ ነው አገኘሁ እረኛ
የእግዚአብሔር ቸርነት ይገርማል ምንኛ
ኢየሱስ ክርስቶስ ፍርድህ እውነተኛ
አቁመው ተፈሪን አርፌ እንድተኛ

ብርሃንና ሰላም

ዕድሜውን እንለምን እንዳንሆን እቡን
የተፈሪን ዕውቀት አስተውሉ ሐሳቡን
እንዳይገባን ተኰላ አጥብቆ ጉድቡን
ብቻውን ደክሞ ነው የሚያግደን ሕዝቡ፣

የሺጥላ ማሬ ።

ስለ ላይኛውና ታችኛው ደረጃ

በ፫ኛ ዓመት ፳፬ ቁጥር ፪፻፳፫ ገጽ በመጀመሪያው ዓምድ በ፳ኛ መስመር አቶ ጥሩነህ ካብትህ ይመር ያድዋ ቴሌግራ ፊስታ ባገረ ገዢዎችና ለኢትዮጵያ ወጣቶች በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ እንዲህ ሲሉ ይመክሩናል ይዘልፉናልም ።

በዚሁ ዘመን ያለን አዲሶቹ የኢትዮጵያ ልጆች ትልቁ ትንሹ ብርሃን ባገራችንፈጽሞ እንዲደምቅ ምን ሥራ ሠራን? ለጥቅም የሚሆንሥራችን ስ ወዴት አለ ? ብርሃንና ሰላም ብሎ በመናገር ብቻስ ምን ጥቅም አገኘን ? ይህነንም ነገር በጣም ለመረመረው የኢትዮጵያ ሕዝብ አንጀት የሚበጥስ ነው ማለት መሪና ተመሪ ሁላችን ተኝተናል።በዓለምም ሁሉ እንደኛ የተመ ቸው ሰው ያለ አይመስለንም እንቅልፋም በጣም ጣፍጦናልና ከኛ አንድ ስንኳ ከመኝታው ለመነሣት እጁን የሚያንቀሳቅስ አይገኝም ከላይኛውም ደረጃ ወደ ታችኛው ደረጃ ወድቀን ከወደቅንበትም ቦታ ተኝተናልና ይህን ጊዜ እባካችሁ እንነሣ ብሎ የሚያስብ የለም ሲሉ በመሪዎችና በተመሪዎች መካከል ትልቅ የጥፋት መዶሻ ጣሉብን ተጥሎም አልቀረ ብዙ አዋቂ ዎችን ሰባበረ አሁን ግን ለሰባራችን ምን ዓይነት መድኃኒት እናገኝበት ይሆን ? ከላይኛውም ደረጃ ወደ ታችኛው ደረጃ ወድቀን የማንነሣ ከሆነ አሮጌውን ባህርይ ተወት አድርገን ተጋግዞ መውጣት ነው እንጂ ሌላ መድኃኒት የለውም አሁን ግን የኢትዮጵያ አገረ ገዦዎችና ወጣቶች ሆይ እያደሩ ቀኁል ቀኁል የተባለው ተረት በኛ ላይ ደርሷልና እባካችሁ ይህን ጊዜ እንነሣና ደረጃውን ለመውጣት እንራመድ ደረጃውን እንወጣ ለን ስንል ቀኁልቀኁል የሚመልሰን ድንጋይ ቢኖር ግን እርሱ አሮጌ ባሕርይ ነውና አዲሱን መያዝ ነው ማለት ባባቶቻችን ጀምሮ ስለ ተረገጠ አርጅቶ ስለቱ ረግፏልና ጫማ አያስኬድ ምና ስለዚህ በሱ ፈንታ አዲስ የተወቀረ ድንጋይ እየመረጡ የሰነፈውን ሁሉ ማስበጀት ነው አለበለዚያስ የምድር ብረት ሳይዘረጉ ባቡርን እንደመጉተት ያህል ይመስላል ። ክቡራን አገረ ገዢዎችና የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ ግርማዊት ሰላም

ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሻችን ከንድተው ሰንዝረው የሰጡንን የእውቀት ደረጃም ብዙ እንደሆነ ታውቁታላችሁ ለዚሁም በሰላሳ ዓመት እስከላይኛው ደረጃ ልንዘልቀው ፈርማ አድርገን ነበር ፤ አሁን ግን እንኳንስ በሰላሳ ዓመትና በመቶ ዓመት የምንዘልቀው አይመስለኝም ፡ ለዚሁም ማስረጃ ደረጃው ከተበጀና ከተሠራ ሶስት ዓመት ሁኖታል ፤ ነገር ግን በሶስት ዓመት ሙሉ ከላይ የሚወርድ እንጂ ወደላይ የሚወጣ ሰው አላየንም ፡ አሁን ግን ለዚሁ ደረጃ በቶሎ ለመውጣት ለሠራተኞች ብዙ ገንዘብ ያስፈልጋልና አገረ ገዢዎችና መኳንንቶች ሁሉ ከልዕልናችሁና ከማዕርጋችሁ እየቀነሳችሁ ኢትዮጵያ እናታችሁን እርዷት አከፍሏትም የኢትዮጵያ ወጣቶችም ኢትዮጵያ አገራችን በሕይወታችንና በሞታችን የዘለዓለም ርስታችን ናትና እባካችሁ እንርዳት እንደግፋትም መቼም የተሸከመች ማህጸን ምንም ቢከፋትና ቢቸግራት በልጆችዋ ላይ ልትራገም አያስችላትም እንጂ ኢትዮጵያ እናታችን የበደልናትን በደል ይህን ያህል ተብሎ ሊገመት አይቻልም ፡ ስለሆነ ግን ኢትዮጵያ እናታችን ሁሉንም መርማሪ ነችና ድሆቹን ልጆችዋን ተወት አድርጋ ድርብ በሚለብሱና ጫማ በሚጎርሱ በሀብታሞቹ ልጆችዋ ላይ በተለየ ባገረ ገዢዎችና በሽለቆች ጠሊቅ የሆነ ኀዘኑዋን እያቀረበች በየደጃፋችሁ ትጮሀለች ስለዚህ አገረ ገጋዮችና መኳንንቶች ሁሉ እንደየችሎታችሁ መጠን እየያዛችሁ ከኢትዮጵያ እናታችሁ የይቅርታ ምርቃን እንድትቀበሉ በቶሎ ታረቁ አሁንም የጥፋትና የሕልፈት ደወል እየተደወለ ተነሡ ተነሡ የሚል የደወሉ ድምጽ እየበረታ ሄዷልና እባካችሁ ይህን ጊዜ እንነሣ አገራችንን የሚጐዳው ዋናው ዓይነተኛው ብርሃንን ከማጣት የተነሣ ነውና ተነሡ ተነሡ ተነሡ እያለ ከበርቲዎቹን ይቀሰቅሳል ።

ሁለተኛም በሶስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፮ በ፪፻፩ ገጽ በሁለተኛው ዓምድ በመጀመሪያው መስመር ብርሃንና ሰላምን የመሰለ መዓዛ ቃሉ ልብ የሚመስጥ ምግብ ሲደግስ ባለሚያዎቹ ሊረዱ ይገባቸው ነበር ። አለመርዳታቸው ግን መጀመሪያ የሚፈረድ በነሱ ላይ ስለሆነ ነው ፤ በነሱ መጀመሪያ የሚፈረድባቸው ስለ ምን ነው ብሎ የሚጠይቀኝ ሰው ቢኖር ግን እንደኔ ያለ ድሀ ሲደግስ ባይጣፍጥለት ባይኖረው ነው ተብሎ ይታዘንለታል ፡ አይነቀፍም እነዚያ ግን ድግሳቸው ቢጠፋ ሁሉ ዓይነት አቃቂር ሳላቸው የወደደ ይመገብ የጠላ ይተው ብለው ያጠፉት ይመስላልና ስለዚህ ነው ብዬ እመልስለታለሁ ብለው ክቡር ሞገስ ዓምደ ሚክኤል በብርሃን አስታወቁን ። እውነትም ብንመረምረው ኢትዮጵያ እናታችን ድሆቹን ልጆቹዋን ተወት አድርጋ ከበርቴዎችን በግልጽ ስታማ ትታያለች ። ነገር ግን ኢትዮጵያ እናታችን ለጊዜው ደስ አይላትም እንጂ ለወደፊቱ ሳያልፍላት ይቀራል ተብሎ ምንም አይጠረጠርም ። እንግዲያስ አገረ ገዢዎችና መኳንንቶች ሆይ ኢትዮጵያ እናታችን በቶሎ እንደሚያልፍላት የማንጠረጥር ከሆነ ይህን ጊዜ እንነሣና ከኢትዮጵያ እናታችን የወርቅ ኒሻን ተሸልመን ስማችንን በነዋሪ ሀውልት እናስጽፈው ከመልካም ሽቱ መልካም ስም ነውና ። ነገር ግን ኢትዮጵያ እናታችን በኛ ዘመን ጊዜ ከላይ ወደታች ወርዳ የወደቀች እንደሆነ ዬ ዬ ዬ በነዚያ ሰዎች ዘመን ኢትዮጵያ አገራችን ከላይ ወደታች ወደቀች የሚል ጽሕፈት በሀውልቱ ላይ አይጠፋምና ገሀነም እሳት ይፈረድብናል ። ስለዚህ ከመጥፎው መልካሙን ከጭለማ ብርሃኑን እየመረጥን ይህን ጊዜ እንነሣና አገራችንን እንርዳት ስል በኢትዮጵያውያን አፍ ሆኜ አሳስባችኋለሁ ።

ተማኑ ሮምሃ አድዋ

ስለ መረዳዳት ።

የብርሃንና የሰላም ወገኖች ወንድሞቻችን ብዙ ጊዜ ተእንቅልፍ የመንቃትን ነገር ቢአስታውሱኝ ትዝ የሚሉኝን ሶስቱን ዋኖቹን የእንቅልፍ ወዳጆች ለመጻፍ ብዕሬን አነሳሁ ። እኒህንም በተራ ጽፌአቸዋለሁ ፤

አንዱ በማናቸውም ስፍራ ቦቀኑ ብርሃን ሳለ ይተኛና ተነስ እባክህ አልመሼም ያለፈውም ሌሊት አልፏል ብለው የቀሰቀሱት እንደሆነ (እ) እያለ እየተነጠራራ እንደማይሰማ ተኝቶ ጊዜውን ያሳልፍና የሚቀሰቅሱት ሰዎች ከሄዱ ወዲያ ይነሳል ተኝተህ አነገሌ መጥተው ነበር አልነሳ ብለህ ሳይገናኙህ ሄዱ ያሉት እንደሆነ እሰማ ነበር እኮ እገሌ እንዲህ አለ አንተም እንዲህ አልህ ብሎ ምልክቱ፥ ይናገራል ።

ሁለተኛው እንቅልፉ እስኪአልፍለት ድረስ ወድቆ ቢእገላብጡት ቢነቀንቁት ምንም አይሰማም ፤

ሶስተኛው በተኛ ጊዜ ተእንቅልፉ መጣፈጥ የተነሳ ስራ የያዙትንና የሚነጋገሩትን ሁሉ አትጩሁብኝ ብሎ ያስወጣል የሚወደው ልጁ እንኳን አባባዬ ያለው እንደሆነ ይዘሽልኝ ውጪ ብሎ ከባለቤቲቱ ጋራ ይጣላል

ግን ሁለተኛው በጊዜ ብዛት ይነሳ ይሆናልና ቢቀሰቅሱት ደግ ነው ሶስተኛውም ውሀ ቢአፈሱበት ምናልባት ይነቃ ይሆናልና አትስነፉ ቀስቅሱት የመጀመሪያውን ግን እየሰማ የተኛ ነውና ለመቀስቀስ አታስቡ

የተኛውን ሁሉ ለመቀስቀስ የምትጣጣሩ ሰዎች በመጀመሪያው ሰውዬ እንዳትደክሙ አስጠነቅቃችኋለሁ

የብርሃንና ሰላም ወዳጅ ማኅተመ ወርቅ እሼቴ

የእሳት አደጋ

ጂቡቲ በሰኔ ፳ና ፳፩ ቀን መንደር ጆዲድ ከሚባለው የባላገር መንደር ፲፬ ቤት አንድም ዕቃ ሳይተርፍ በጭራሽ ተቃጠለ ይኸን መንደር በያመቱ የእሳት አደጋ ስለሚአገኘው ምክንያቱ ይመረመራል

የውጭ አገር ወሬ

ስለ ኢትዮጵያ ጥቅም መሻሻል ፣

ሙሴ ቢሐይድን ስለአሜሪካንግድ አኳሆንከጻፈውራፖርዝርዝር ውስጥ አንደኛው ገጽ እንዲህ ይላል ከፍሪቃ ውስጥ

እንዳሉት ፍሬን ያዘሉ አገሮች የመሰለች ለስልጣኔ ናፍቆት ሳላት ያረማመድ ትጋት ያልሞከረች ከብዙ ዘመናት ድረስ ሳት ታወቅ ትኖር የነበረች ለምለም ኢትዮጵያ በቅርብ ጊዜያት ስለ ጥቅሟ መሻሻል ባሳየችው እድገት የኑሮዋን አኳሆን ታር ም ዘንድ እንደነቃች እምነት ይሰጣል ያገሪቱ አቀማመጥ ለሰ ውነት በመስማማቱም እነሆ በዙሪያዋ ካሉት ጐረቤቶቿ ከአ ፍሪቃ ቅኝ አገሮች ሁሉ አንድም አምሳያ የላት ። ኢትዮጵያ በራሱ አዳሪ ነጻ መንግሥት እንዳላት የዓለም ነገሥታት በ፲፱፻ ፲፮ ዓ ም በሮማይስጥ ቁጥር አውቀውላትና ዳግም በ፲፱፻፳፰ ባልጋ ወራሹዋ ብርታት ማኅበረተኛቸው ሁና በማናቸውም እንደ መትጋት ሁሉ ዋና የጥቅም ከፍታዋ የተስፋፋ በውጭ አገር ሰዎች ነው ። የፍራንኮ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያና ፈረንሳዊ የምድር ባቡር ከፈረንሳዊ ግዛት ጂቡቲ ጠረፍ ከሚመላለሰው በቀር እስከሁን ሌላ የምድር ባቡር አልተዘረጋም ። ይኸም ፈጽሞ በፈረንሳዊዎች እጅ ነው በከተማ ኑዋሪ ግሪኮችና አር መኖች ከውጭ አገር የሚገባውን የንግድ ዕቃ እየጻፉ ያስመ ጣሉ ሌላው ቀርቶ የማሪያ ትሬዛ ብር ከአውስትሪያ ለመገበያያ የሚመጣው በውጭ አገር ወኪሎች ነው ፤

ስለ እጅብት ሱዳን ያበይን ወንዝ እጅ አድርጎ የጣናን ባሕር ጐድበ የውሐውን ጥቅም ለራሱ ለማሰልጠን ሲል እን ግሊዝ የተነሣበት ጣሊያንም በደቡብና በሰሜን ያሉትን ቅኝ አገሮቹዋን ኤርትራንና ሶማሌ ሌንድን ለማገናኘት ስትል በኢ ትዮጵያ መኻል ለመኻል ሰንጥቃ የምድር ባቡር ለመዘርጋት ያሳሰባት ፍሬው ምክንያት የኢትዮጵያ መንግሥት ሳይፈቅድ አይቀርም በማለት የተስፋ ምኞት ስለ ተደረገ ነው ። እነዚህ ንም ሁለት ምኞቶች ለመፈጸም ከኢትዮጵያ መንግሥት አስ ቀድሞ ፈቃድ ከተገኘ በኋላ ስለ አገሪቱ ኢትዮጵያ ጥቅም ማደግ የሰብ ዘንድ ያስገድዳዋል ።

በሌላው የንግድ ስፍራ ወይም በአባይ በኩል በከብትና በሌላም እርዳታ የንግድ ዕቃና ሸቀጥ ለመስደድ እጅግ የሚ ዘገይና ችግር ስለ ሆነ የሚበዛው ያገር ውስጥ ንግድ በፈረን ሳዊ ባቡር እየተጫነ ይሄዳል ። በዚህም በኩል የሚገባውና የሚ ወጣው የንግድ ሲሳይ በ፲፱፻፳፬ ዓ ም ገቢው ፲፰ ሺ ፯፻፺፫ ሜትሪክ ቶንስ ወጪው ፳፫ ሺ ፯፻፹፯ ቶንስ ሆነ ።
በ፲፱፻፲፬ ዓ ም የወጭ ብዛት ከገቢው ሁለት እጅ ሲበልጥ የገቢው ብዛቱ ምንም ሳይለወጥ ቆየ የሆነ ሆኖ ከ፲፱፻፳፬ ዓ ም ፊት ገቢው ይኸን ያህል አላነሰም ነበር ፤ በጂቡቲ የሚሄ ደው ወጭ ሰም ቆዳ ቡን የበግ ቆዳ የፍየል ሌጦ እህል የዝ ሆን ጥርስ ይኸን ይኸን የመሳሰለ ነው ከውጭ አገር ገቢው አንድ አንድ ጊዜ የሚገበያዩበት አሞሌ ጨው ሕዝቡ የሚለ ብሱት ጨርቃ ጨርቅ ጋዝ ሱካር ብረታ ብረት ባጋሰስ ለሚ ጫነው ጭነት መጠቅለያ ጆንያ ነው ።

በጋሚቤላ የሚሄደው ንግድ ብዙ ስለ ሚፈይድ ከጅቡቲ ንግድ ጋራ ብዛትና ጥቅምን ለማመዛዘን ያውካል በሺ፱፻፳፬ ዓም በጋሚቤላ ወጭው ንግድ ፪፻፳፪ሺ የግብጽ ጊኒ ገቢው ንግድ ፩፻፲፩ሺ (የግብጽ) ጊኒ ሆነ ። ወጭው ቡንና ሰም ነው ። ገቢው ግን ጨርቃ ጨርቅ ጨው ሌላም የሱዳን ዕቃ ነው ። የኢትዮ ጵያ ሐብት እስከሁን ሳይነካ ይኖራል ። የዚህም ምክንያቱ ስራ ስላልተለመደ ነው ። ማርና ቡን በየዱሩ ይገኛል ፲፱፻፲፫ ዓ ም ዘን ጋዳ በብዙ ማረስና ማምረት ተደምሯል (ላስቲክ ከሰል መዳብ ብር ዲኝ ። የጨው ባሩድ ሚካ ወርቅ ዲኝ ሳይቆፈሩ ይኖራሉ እንጅ በኢትዮጵያ በጣም ስለ ሚገኘው እነሆ ኢትዮጵያ ፍሬን ሁሉ ያንዠረበበች ድንግል መሬት ነች ፤ የሚፈልገውን ማዕድን ሁሉ ያረገዘች ለምለም ኢትዮጵያ ይኸን ያህል ሐብት ስላላት የጥቅም ማሻሻል ጉዞ ብትደምር ሲሳዮዋ ለዓለም ሁሉ በቂ ነው እንግዲያስ ጥቅሟን ለማሻሻል ዋና ነገር መንገድ በያውራጃዋ መስራትና የምድር ባቡሩን ኖል በጣም ማሳነስ ነው ። ኢጣሊያ ለምጥዋ መንገድ የምድር ባቡር እንድትዘረጋ እንግሊዝ ለበር በራ ንግድ የባቡር መንገድ እንዲሰሩ የታሰበው ምኞት ለኢ ትዮጵያ ስፋትና ልማት እንዲረዳ አይጠረጠርም ።

ለውነተኞች ኢትዮጵያውያን

ማስታወሻ ።

በፈረንሳይ ቅኝ አገር ወሰኑና በእንግሊዝም እንደቆመው ጉምሩክ ሁሉ ኢትዮጵያ በማናቸው አይነት ወሰን የሌለው ጥቅም የምታገኝበት ነውና በአድዋ ከተማ ላይ ለሐገሩ ሺአለቆች የሚ ገባቸውን ጥቅም ሣትነካ በሥርዓት ተተካክሎ ሊቆም ያለውን ጉምሩክ በፍጥነት ማቆም ያስፈልጋታል የዚሁ ነገር ጥቅም የሚ ያስረዳ በስርዓት ጽፈን አዘጋጅተናልና መረዳት የሚገባው ሁኖ ከተረዳውም ይህ ነገር እንዲፈጸም ሊረዳ የሚችል ሰው ይህን ለጻፈ ሰው ጠይቆ ጥቅሙን በዝርዝር ሊያውቀው ይችላል ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።

አራዶም ዕቁቡ

የኢትዮጵያ መንግሥት የርሻ ሚኒስቴር

የከብት ሕክምና ሥራ

(አዲስ አበባ)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

የርሻ ሚኒስቴር አዲስ አበባ አራዳ ላይ እንጨት ተራ አጠገብ ማናቸውንም ዓይነት የከብት በሽታ ማከሚያ (የከብት ሐኪም ቤት) ማቆሙን ለሕዝብ ያስታውቃል ፤ በዚህም በከብት ሐኪም ቤት ከእሁድና ከዓመት በዓል በተቀር ሁል ጊዜ ከጧቱ ከሁለት ሰዓት አንሥቶ እስከ ሰባት ሰዓት ድረስ ከብቱ የታ መመበት ሰው ሁሉ እየመጣ ሊያሳክም ይችላል ። ደግሞ ልዩ ልዩ ለሆነ የከብት በሽታ መድኃኒት እያሰናዳ ካዲስ አበባ ከተማ እርቀው ለሚኖሩ ሰዎች ይሸጣል ። የሚጋባ የከብት በሽታ በተነሣ ጊዜም በሽታው እንዳይተላለፍ የክትባት መድኃኒት ያደርጋል ። የታመሙትንም ከብቶች እንደሚያስፈልግ እያደረገ በቀላል ዋጋ ያሳክማል ።

OMEGA



እጅግ ጥሩነቱ የተመሰከረለት ኦሜጋ በቢ የሚባል ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፷ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ።
የገዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፭ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፯ ብር ተኩል
፡፡ ባለፈረስ	፡፡	፻፴፭ ብር ተኩል
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፳፷ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፰ ብር
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፺፬ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፫ ሩብ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፲፭
በአንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ ፱፭
ባአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፲፭ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፭ ብር

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

ሩግቢ

RUGBY

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድሪስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፣ ሽቱ ፣ ለስዮን ፣ አድከሎኝ ፣ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፣ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፣ ከፈይ ምንጣፍ ፣ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና ከሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፣ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬስ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፣ ባለ አጎበርና አጎበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፣ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነቱ፡ ቢሲግሌት ፣ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላሸው ፣ ፋኑስ በየዓይነቱ ፣ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፣ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

Berliet



ቤርሊዮ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዮ አቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ

ARMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l 'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን ኦዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የኦዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ ፤ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፳፱
3 me ANNÉE № 29

ሐሙስ ሐምሌ ፲፬ ቀን ፤ ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 21 JUIL 1927

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen , Héritier du trône d' Ethiopie , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ስፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piástres

ስለ መንግሥት ጉዳት ።

በኢትዮጵያ የመኳንንቱና የወይዛዝሮቹ ርስትና ጉልታቸው ምናልባት ባልሳሳት በግምት አንድ መቶ ሺ የጋሻ ምድር የሆነ እንደሆን ያንዱ ጋሻ ምድር ባመት ግብሩ አስራምስት ብር ሲሆን በመቶው ሺ የጋሻ ምድር አስራ አምስት መቶ ሺ ብር ማለት አንድ ሚሊዎን ተኩል ካንድ ዓመት ግብር ገቢ ለመንግሥት ይቀርበታል ። ከዚሁም ከመቶው ሺ የጋሻ ምድር ከሥሩ ጋሻ አንደኛው ነውና የሚታረሰው እንኳን እርሳቸው አሳርሰው ለመንግሥት ጥቅም ያሥራት እህል ማግባታቸው ይቅርና ከቶውንም እነዚያ መከረኞች ድሆች ከምስለኔና ከዱግ እየታገሉ አርሰው ካገቡት ያሥራት እህል ምድራችንን እናቀናበት እያሉ እህሉን ከጐተራ ብሩን ከግምጃ ቤት እየተጻረጉ ቀለብተኛውንና ደመወዘተኛውን ሲያውኩት ሲያስጨንቁት ይኖራሉ ።

ስለ ሕዝቡ ጉዳት ።

ሕዝቡ መቸም እንደ ጭቃ ተረግጦ እንደ ገል ተቀጥቅጦ ነውና አኗዋዋሩ ከዚሁ ከጭንቅ ኑሮው ውስጥ እንዳይወጣ ተብሎ ላንድ ጋሻ ምድር ያመት ግብሩ አሥራ አምስት ብር በዛበት እንደምን ይቻላል ተብለበት ላንድ ጋሻ ምድር (ሙሉ ቀላድ) አሥራ አምስት ብር በዛበት ከተባለማ ከታረሰና ከተሰራ ዘንዳ ባንዱ ጋሻ ምድር ላይ መቶ ታምሳ ዳውላ እህል ሲገኝበት ከሥሩ ጋሻ ምድር ላይ አንድ ሺ ከምስት መቶ ዳውላ እህል መገኘቱን ተሳስቶ ይሆናላ አልተሳሳተ እንደሆነ በመላው ዓለም ያለው ሕዝብ ሁሉ ነፃነቱን አግኝቶ የየራሱን መንግሥት በጥበብና በሀብት መስርቶ የችግርና የጭንቅ ቀምበሩን ከንገቱ ሰብሮ ጥሎ ሲኖር እንግዲያውስ ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር የኢትዮጵያን ሕዝብ ብቻ በመልኩ አልፈጠረውም ማለት ይሻል እንደ ሆን ነዋ ተፈጥሯል እንጂ የሚባልለት እንደሆነ ያ ድኃ ሞቱ በቀረበ ጊዜ ጀምሮት የነበረውን ሥራ ሳይፈጽመው ስለ ቀረ ለልጁ አደራውን አጠንክሮ ቢነግረው ልጁ ያባቱን ምክር ተከትሎ ሥራውን ፈጽሞ ብዙ ጥቅምን እንዳገኘ አይተናልና ይልቅ የጅግ ቸርና ለጋስ አባትዎ ያጼ ምኒልክ አሳብዎና ምኞትዎ ተጀምሮ እንደማይቀር በጭንቅና በችግር ገመድ የታነቀ ሕዝብዎ ፍጹም እምነት አለው ፡፡ ስንኳንስ ስለ ኢትዮጵያ ጥቅምና ነፃነት ግርማዊ አባትዎ የጀመሩት ሥራ ሊቀርና ያንድ ምስኪን አሳቡና ምኞቱ በልጁ እንደሚፈጸም የታወቀ አይደለምን መኳንንቱም እርስታችን ነው እያሉ የሚያወሩት እየለማ እየታረሰ በሆነ መልካም ነበር እንዲያው ጆሮ ቀለቡን ሲሰፈር ይኖርና በቀን ብዛት ዳዋ ለብሶ እሾህ ጐርሶ አውሬ ተንተርሶ የሽፍታ መቃጠሯ ሁኖ ይኖራል አይሰሩበት ወይም ለሚሰራ አይሰጡት ፡፡

የሕዝቡንም ጉዳትና ችግር ካሥሩ አንዱን እጅ እንኳ ከጻፍነው ሰው መሆንን ባላስፈለገም ነበር ። እነሆ የኢትዮጵያ መከረኛ ድኃ በስተ ምሥራቅ እንኰበር ይፋትና ተጕለት ቡልጋና ሞረት በጥቅሉ መካከል አገር የተባለ ሁሉ የመጫሚያ እላቂ በምታህል ባንዲት ጋሻ ምድር ከሶስቱ ሥራ ሲሶ አንዱን ለመልከኛ ወይም ለሻለቃ ከመት እስከመት ይሰራል የእጅ ሥራውንም እንደዚሁ እጅ ሥራ ማለት ከግዝት በዐል በተቀር ነው ደግሞ የድኃው ፋንታዎች ከሚባሉቱ ከሁለቶቹ ሥራዎች አንዱን ለወረዳ ምስለኔ አንዱን ለዱግ ይሰራል የዚህማ የድኃ ጎጆ ባንድ ጠገግ እግር ተወርች ታስሮ የተቀመጠ ጊዜና ፤ መገናኘት እስከስፈታው ድረስ ። ወይ ምንጃር ሆይ እንደ ምን ባለ ኀዘንና ልቅሶ ከዚያ ከጭንቅ ኑሮው ውስጥ ወጣ እንኳን ቸር እግዚአብሔር አወጣው ሰሎሞን ለሁሉም ጊዜ አለው ብሏልና ተሥፋ አይቈረጥም ። ደግሞ ባንዱ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ አምስት ጊዜ ጭነትን ጭኖ መሄድ አለበት ያምስት ጊዜ ጭነቱ ዝርዝሩ ይህ ነው ፡፡

ሶስት ጊዜ ለመልከኛ አምስት አምስት ቁና እህል እየ ፈጨ ዱቄቱን ጭኖ ። አራተኛ ማርን ጭኖ አምስተኛ ለመንግሥት አሥራት ባወጣሽ ዱቄት ይጭናል ለመልከኛ ዱቄትን ጭኖ አዲስ አበበ በደረሰ ጊዜ ተጭኖ የመጣው ዱቄት ገና ከህያው ጀርባ ላይ ሳይ..ርድ እንኳን መጣህልኝ ነገ በማለዳ አዋሽ ከቀላዶ ሄደህ ፩ ጭነት ጤፍ ጭነህልኝ እንድትመጣ ይ ባላል ይህ መከረኛ ድኃ ደምን እያነባ እያለቀሰ ምነው ጌታዬ ሆይ ዛሬ እኮ አገራችን ያገዳ እህል አዝመራ ነው ዝናሙ ሳ ይነሣ ካልደረስኩ ጭራሽ መሰደዴ ነው እያለ ይጮሃል ይለ ፈለልፋል ግን ማን ይሰማዋል ፡ ከዚህ በኋላ እንደ ኢዮብ የ ተወለደበትን ቀን እየረገመ ወደ ታዘዘበት አገር ሄዶ ይደርሳል ከዚያ ደግሞ ይኸው እድሉ ቀድሞ ቈይቶታልና ከመልከኛው ቀላድ ላይ ያለው ምስለኔ የጌቶቹ የመኝታ ቤት ፈርሷልና በዚህ ሰሞን የቤቱን ሥራ ረድተኸኝ ትሄዳለህ ይለው ቤቱን ሲያሰራው ሰንብቶ እንዲጭን የታዘዘውን እህል ጭኖ አዲስ አበባ በደረሰ ጊዜ እንደ ገና ጭነህ ያመጣህውን እህል በመዘውር አስፈጭተህ አምጣና ፊት ያመጣህውንም ዱቄት አንድነት አሰፍረህ ትሄዳለህ ተብሎ ሳለ በመካከሉ ስንቁ አልቄ በታልና ተዝሎ ፡ ዝክር ወደአለበት ለቅልውጥ ሲዞር ሲንከራተት በየከተማው ተስቦ ወይም የሆድ በሽታ ተቅማጥ ዘርፎ ይመጣና እንደ አሮጌ ውሻ ከመልከኛው አጥር ሥር ያህያውን ፋንድያ ተንተርሶ ሲያጣጥር ሲንገላታ ይሰነብትና ከሃሌ ኩሉ አምላክ ነፍሱን ከሥጋው በለየት ጊዜ የመልከኛው ሎሌ ዎች በሁለት እንጨት አጣብቀው ወስደው ወደ አንድ ጉድባ አስጠግተው ጫር ጫር አድርገው ይቀብሩታል አህያውንማ ገና ታሞ ሳለ ሌባ አጠናቆለታል ወደ ዚያው ከመልከኛው አ ቅራቢያ ካሉቱ ከጐረቤቶቹ አንዲቱ ሴት እትዬ ዛሬ ከሰፈራችሁ ሬሳ ሲወጣ አየሁ ማነው የሞተው ብላ ከመልከኛው ሥ ራ ቤቶች አንድኛዩቱን የጠየቀቻት እንደሆነ እባክሽ ተዩኝ እቴ ሆይ ሰውም አይዶል ገበር ነው ትላታለች ይህች ሴትዮ ምንም ለምፀት ብትናገር እንደ ሰው ሁና ስላላየችው የዚህ የገበር ኑሮውን መሰከረችለት ሊባልና እኔም ከሞት ወደሕይወት ተሸገረ እንጂ አልሞተም ማለትን እደፍራለሁ ። ወደዚያው እገሌ የሚባል የኔ ገበር ሞቷልና ፊት የነበረበትን ዳፈንና ግብር የመሬቱን ያዋጅ መንገሾ በቶሎ ላክልኝ ይልና ይኸው መልከኛ ወደ ምስለኔው ይልካል ምስለኔው በዚሁ መልክት የሟቹን ሚስትና ልጅ ካረዳቸው በኋላ በዚህ ላይ የተጻፈውን አምጭ ክፈዩ ብሎ ባስጨነቃት ጊዜ ይህቺ ሴትዮ እንደዚህ ብላ አለቀሰች ።

ድኃ ቢሞት ደግነው በጌቶቹ ፋንታ ፤
ከመከራ በቀር ላያገኝ ደስታ ፡
ሳይወር ፈረሰኛ ሳይተኩስ ነፍጠኛ ፣
ካጥር ስር ቀናቸው የኛማ መልከኛ ።
አዋጅ መነገሩ ልገብርሁ ነወይ ።
ዳፈን መጠየቂ ልከፍልሁስ ነወይ ፡
ጠይቆት ካጥርሁ ያለው እሱ ነበር ፡
ክልክሉ ብዙ ነው በየወረዳችን ።

ዋ ያማር ዋ ያማር ያልታጨደ እንደሆን ። እያለች ስልትና ቃና ባለው ዜማ እያለቀሰች እያነባች ላርባ ቁርባኑ ስሙን ልታስጠራበት ለጠበል ለጠዲቅ ከዘመድ ቲንሽ ገንዘብ ተበድራ ቁርባኑን ታስቆርብና የመልከኛው ዳፈን ስላልተከፈለ ላት እንደሌባ ተሰርቃ ተሸሽጋ ይህን የመከራና የችግር መፍለቂያ ጎጆና ምድር ትታ ልጅዋን አዝላ እብስ ጥርግ ትልና የፈታይ የፈጪይ እያለች እንጀራ ማውታ ልጅዋን ለማሳደግ ከ ንዱ አገር ወዳንዱ አገር ስትዞር ስትንከራተት ስትንገላታ ደግሞ ልጅዋ በችጋርና በስደት ብዛት ይሞትባታል ፡ ከዚህማ ወዲያ በየማርገጃው ላይ ያምርባታል አስከትለኝ አብሮ አድጌ እስከ ትለኝ ልጄ ልጄ እያለች እየተቀጠቀጠች ደግሞ በግጥም ሙሾን እንደዚህ ታማሻለች ።

ልጅ አሳድግበት አባት የሌለውን ፡
አግኝቻለሁ ቀብቅብ እባካችሁ ዘሩን ፡
አባትና ልጁ የሄዱት በምክር ፡
ቢያስመርራቸው ነው የመልከኛው ግብር ፡
መቅረት ካልተወራስ ይሻላል መቃብር ።
ይኸ ድሀ ድሀው ገበር የሚሉቱ ፡
ከየት አገር ይሆን የፈለቀበቱ ፡
ሳላስታምም ባሌን ሞተልሽ ብለውኝ ።
ሳላሳድግ ልጄን ምስለኔው አበሮኝ ፡
ወዲያው ልጄ ሞቶ ከፈኑ ቸግሮኝ ፡
የሚሄድበቱ መላው ቅጡ ጠፍቶኝ ።

ገበር ሰውም አይደል ነው አሉ መሰለኝ ፡ እንደዚህ እያለች እስከ ጊዜ ሞቷ በሐዘን መልሕቅ ተይዛ ትኖራለች ፣ እንግዲህ ልጅ ባባቱ ፋንታ ተተክቶ ያባቱን ርስትና ምድር ካላረሰና ካልቆፈረ ለመንግሥት ህብቱና ጥቅሙ ከወዴት አገር ሊመጣለት ነው ፡ አራሽ ገበሬውም ሳል እንደያዘው ድመት እያደር መመንመኑ አለወግ አለ አገባብ መገዛት ቢበዛበት ነው እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ እርሻ ቁፋሮ አያውቅም ሊባል አይቃጣም ።

እንግዲህ ይህ መከረኛ ድኃ ባንዲት ጋሻ ምድር ይህን ያህል መከራና ጭንቅ ከደረሰበት ሁለትና ሶስት መቶ ወይም አንድ ሺ የጋሻ ምድር ያላቸው መኳንንት መልከሚቱን እናት እንተ ታውኅዝ ሀሊብ ወመዓረ የተባለችውን ኢትዮጵያን አይንዋን ሸፍነው ክብርዋን ሸሽገው ጥፋቷንና ውርደቷን መውደዳቸው ሐሰት አይባልም ለማለት ምን ይከለክለናል ፡ እንግዲያውማ ከዚህ በላይ ስለ እሱዋ የተጻፈውን እንዳይደርስባት ከወደዱማ እነሆ ከ፲፱፻፱ ዓመት ወዲህ ታላቁ አፄ ምኒልክ ስለ ምድር ግብር ነፃነት ጀምረውት የነበረውን ልንፈጽመው ይገባናል ብለው መኳንንቱ ሁሉ ተሰብስበው ላንድ ጋሻ ምድር ባንድ ዓመት ግብሩ ይህን ያህል ገንዘብ ይሁንለት በማለት ይውጣ ይውረድ እያሉ ሲመከከሩ ከማካሪዎቹ አንደኛው ይልቅ እኛ ከመፋጀት ከድኃው በእያውራጃው ዋና ዋና ሰዎችን አስጠርተን የሕዝቡን አሳብና አኳኋን ብንጠይቃቸው አይሻልምን ብሎ

ቢናገር መልካም ነው ። ይጠሩ ተባለና ከያውራጃው ምክር አዋቂዎች መንግሥታቸውን አክባሪዎች ሀገራቸውን በፍጹም ዋዳጆች ተመርጠው ቢጠሩ ጆሮዋቸውን ወደ አዲስ አበባ ቀቀረው ያዳምጡ ነበርና በቅጽበት ከተፍ አሉ ወደዚያው እንደ መጡ ወደ ምክር ቤት ተጠርተው ገቡ ፡ ጥያቄ የጉልበት ጉልበት ግብር ቀርቶላቸው ባንድ ዓመት ባንድ ጋሻ ምድር ስንት ብር ልታወጡ ይሆንላችኋል ብለው ቢጠይቋቸው ፡ ምላሽ የጉልበት ግብር ፈጽሞ ቀርቶልን በየራሳችን ላይ አዛዥነትን ካገኘን ባንድ ዓመት ባንድ ጋሻ ምድር ይህን ያህል ብር ልናወጣ ይሆንልናል ብለው መኳንንቱ ከደነገጉት ከወሰኑት በላይ ሁለት ብር አብልጠው ጨምረው ተናገሩ ፤ ያውም ባንድ ዓመት ውስጥ ሶስት ጊዜ የጉልበት ግብር (ሥራ) እየሰራንላችሁ ማለትን ጨምረው ፪ተኛ ጥያቄ የጉልበት ግብርስ ፈጽሞ ይቅር ተብሏል ባይሆን ሶስት ጊዜ በምትሰሩልን ፈንታ ሶስት ሩብ ብትሰጡሳ ቢሏቸው በሶስት ጊዜ ስራ ሶስት ሩብ ብንሰጥ ምንም ባልተጐዳን ነበር ። ነገር ግን አይሆንም ማለት ማዘዝን የለመደ ሰው ልማድህን ባንድ ጊዜ ተው ቢሉት አይሆንለትም ከበሽታ ሁሉ ልማድ ትበረታለች እንደ እሚባል በማለት እነዚህ የማይረቱ ተሟጋቾች መንገዱን በዘጉባቸው ጊዜ እነሞት አይፈሬ ባይን ጥቅሻ በከንፈር ንክሻ ነገሩስ መልካም ነበር።አፄ ምኒልክ ያቈሙትን ሀውልት መንቀል ይሆንብናል እንጅ ተባለና ለመንግሥት ማገልገላቸው ለድኃው ማዘናቸው እስከዚህ ድረስ ሆነና ጉባዔው ተፈትቶ ደግሞ በሌላ ጊዜ ነገሩን ወስነን ጨርሰን እናስታውቃችኋለን መባልን ተሸከሙና በረኀብ አኰርባጅ ሲገረፉ ሰንብተው እኒህ እድለቢሶች ወደ መከረኛዪቱ ጎጆዋቸው ተመለሱ ።

እሽ ይሁን ነገሩስ መልካም ነበር ። አፄ ምኒልክ ያቆሙትን ሀውልት መንቀል ይሆንብናል እንጅ አይደለም የተባለው ለድኃው ነጻነት መሰናከያው ይህ እሆነበት ነፍስዎን ይማርና አፄ ምኒልክስ ከብዙ ዘመን በፊት በድኃው ራስ ላይ ተዘፍዝፎ ይኖር የነበረውን ጭንቅና ጉዳት ከራሱ ላይ አውርደው ጥለውታል ቁጥራቸውም ከብዙው በጥቂቱ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ነው ። ፩ኛ በማናቸውም ነገር ሰውን ሰው የገደለ እንደሆነ የገዳዩ ዘመድ እስከ ሰባት ትውልድ ይወረስ ይነቀል ነበር ። ፪ተኛ ልጅ የሌለው ሰው መካን የሞተ እንደሆን አገረ ገዥ ይወረሰው ነበር ። ፫ተኛ ገባር ባንድ ወር ለመልከኛ አንድ ዳውላ እህል ያስፈጭ ነበር ።

፬ኛ ፡ ይኸው ገባር ሙክት ቢያሰባ ፡ ጤፍ ስንዴና ማር ቢኖረው ሩቅ ካለ ዘመዱ ያውም የካህን ምድር ካለው ዘመዱ እያሸሸ ያስቀምጥ ነበር ። አለዚያስ አሁን የተነገሩቱ ከቤቱ የተገኙማ እንደሆን ይሞት በቃ ያስፈርዱበታል ።

፭ኛ ፤ በገባር ምድር ላይ ፈሳሽ ውሀ ወይም ምንጭ ቢኖር መስኖ አግብቶ አታክልትን መትከል አይችልም ነበረ ። አንዳንድ ሰዎች ሥራ በመውደድ ወይም በስሕተት አታክልትን የተከሉ እንደሆን በትንሽ ሰበብና ምክንያት ይከሰሱና ምድራቸውን ይወረሱ (ይነቀሉ) ነበር ።

፮ኛ ፤ ባለ ምድርና ባለ ርስት የሆነ ሰው ችግርና መከራ ድንገት ይደርስበትና ምድሩን የሸጠ እንደ ሆነ ከምድሩ ዋጋ እጥሌታውን ከፍሎ ባላባት (አገረ ገዢው) ይወስድበት ነበር ።

፯ኛ ፡ የመንግሥት ወህኒ የእሥር ቤት የሚጠብቅ ሜታ የሚባል ብዙ ባለ ምድር አለ ። የፊ አለቃው የገበታ ቤት ሹም ነው ፡ ፡ እሥር በሚጠብቅበት ወር በወር ተራው ከእሥር ቤት አንድ እሥር የጠፋ እንደ ሆን ተረኛው ሁሉ መላ ንብረቱን ከነ ምድሩ ይወረስ (ይነቀል) ነበር ።

በዚህስ አሳብ አይግባችሁ ፤ ከብዙ ዘመን በፊት ተመሥርቶ የነበረውንና እጅግ ለሚሰማ ጆሮ ያስከፋ የነበረውን ጭንቅና መከራ እጥሌታውን ከመሠረቱ እያፈለሱ ነቃቅለው ጥለውታል ። ምነው የናንተ ጉዳይ በታሰባችሁ ጊዜ ጃንሆይን እከ እንደዚህ ያለውን ጉዳይ አንድ ቀን ብለምናቸው በፊታውራሪ እገሌ ቀላጤነት ይሁንልህ ብለውኝ ነበር በማለት አሳባችሁን በቅጽበት ታከናውናላችሁ ። የኛ የድሆቹ ጥቅም ከእንቅልፉ በተንቀሣቀሰ ጊዜ ልክ እንደ ማቱሳላ ዕድሜ ይረዝማል ። ይህንም የጉልበት ግብር ነፃነት ጃንሆይ እራስዎ ተግተው አስበውበት እንደ ነበሩ በሁላችሁ ዘንድ የተረዳ ነው ። ለዚህስ ነገር ለምሳሌ አንድ ተረት ቢነገር አይከፋም ። አንድ ሰውዬ ገብቶ በት ከማያውቅ ቤት ገብቶ ሳለ የቤቱ ጌታ መጥቶ ከዜህ ቀደም በኔ ቤት መጥተህ አታውቅ ዛሬ ምን እግር ጣለህ ብሎ ቢጠይቀው ውሀ ቢጠማኝ እሳት እሞቅ መጣሁ ብሎ መለሰለት እንደሚባለው ተረት ሆነ እንጂ ሌላ መንገድ ይገኛልም አይመስለኝ ።

ለብርሃን ወሰላም ይህን መናገሬ ፡
እንዲደርስ እንዲላክ ለሸዋ ሀገሬ ፡ (ለነ ሞት አይፈሬ)
ታንጹዋል ተሠርቷል የኔስ መቃብሬ ፡
ምን ያስቸግራል የድኃ መቃብር ፡
በትንሽ እንክሴ አድርጎ ጫር ጫር ፡
መለስ ማድረግ ነው ሁለት ላዳን አፈር ፡
እርም እንዳይሆናቸው አይደል የነሱ ዘር ፡

መታደልና ችሎት ለመኳንንቱ ፤ ችግርና ዕውቀት ለድሆቹ ስለ ሆነ መንገዱ የወለፈንድ ጠማማ ሆነ እንጂ እንግዲያውማ የመንግሥት አማካሪዎች ለከተው አመዛዝነው ከወሰኑት በላይ ይልቅ ከያውራጃው በምርጥ ተጠርተው የመጡት ድሆች መኳንንቱ ከወሰኑትና ከደነገጉት በላይ ሁለት ብር ጨምረው ደግሞ ባንዳንድ ዓመት ውስጥ ሶስት ጊዜ የጉልበት ሥራ እንሥራላቸው ማለታቸው ለመንግሥትና ለሕዝብ ተመዛዛኝ ጥቅም ነበረ እንጂ እንደ ዳሎታ ሚዛን ባንድ ወገን ብቻ አልነበረም ጥቅሙ ።

ዓስበ ፤

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ስለ ክቡር ሐኪም ወርቅነህ ወደ ውጭ አገር መሄድ የተደረገው የፍቅር ግብዣ

ሐምሌ ፱ ቀን በ፲ ሰዓት የፍቅርና አገልግሎት ማኅበር ስለ ክቡር ሐኪም ወርቅነህ ክብር በሙሴ ግሌዝ ሆቴል የሻይ ግብዣ አሰናድቶ ነበርና ማኅበረተኞቹ ሁሉ በተቀጠረው ሰዓት ተሰበሰቡ ። ክቡር ሐኪም ወርቅነህና ክብርት ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ በደረሱ ጊዜም ፒያኖና ልዩ ልዩ ዓይነት ድምጽ ያለው

ክበሮ ባማረ ዜማ ይመታ ጀመር ። ወዲያውም ሰው ሁሉ ለሻይ ግብዣ በተሰናዳው ቤት ገባ የሻይ ግብዣ ሲጀመር ክብርት ሲስተር መሬ የክቡር ሐኪም ዶርቅነህን ልጆች ይዘው ደረሱና የሻይ ግብዣ በሙሉ ደስታ ተፈጸመ ። በሻምፓኝ ጊዜም ክቡር ልጅ ውብሸት ወልደ ዮሐንስ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ክቡር አባታችን ሆይ ።

ምንም ከአይናችን ሊለዩን ፈቃዳችን ባይሆንና የርስዎ ናፍቆት ቢይዘን መቼም ሁላችንንም እያንዳንዳችን ለመንግሥታችን እንድናገለግልና እንድንታዘዝ ግዴታ መሆኑን ስለ አወቅነውና ስለተረዳነው የልባችንን ኀዘን ያጽናናል ስለዚህ ዛሬ ከመሄድዎ በፊት ይህችን ታናሽ ግብዣችንን በማክበር እናቀርባለን ክቡር ሆይ ይህቺን የኛን የልጆችዎን ግብዣ አክብረው ስለ መጡልን በእኔና በማህበሩ ስም ሆኜ አመሰግናለሁ ።

ይልቁንም ይህንን የክቡር አባታችን ስንብት ለማየት ተጠርተው ፈቃዳቸው ሆኖ መጥተው አብረውን ያሉትን እንግዶቻችንን የፍቅሩና ያገልግሎት ማህበር ምሥጋናቸውን በጣም ያጋንናል ።

ደግሞ ወንድማችን ልጅ መሥፍን ቀለመ ወርቅም ተመርጦ ከርስዎ ከአባቱ ጋራ በሄዱ በጣም ደስ ብሎናል እርስዎን አባቱን እንዲረዳና መንግሥቱን በፍጹም ልቡ እንዲአገለግል ሙሉ ተስፋ እናደርጋለን ።

ልዑል እግዚአብሔር በደህና እንዲመልሳችሁ ህፃናቱንም አሳባቸውን ፈጽሞ በደህና መልሶ መንግሥታቸውን አገልጋይ አባት እናታቸውን ጠዋሪ ያድርጋቸው ስንል ሙሉ ምኞታችንን እናቀርባለን ብለው በፈጸሙ ጊዜም ተጨበጨበ።

ከዚህ በኋላም ክቡር ሐኪም ወርቅነህ

የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ክቡራን ወንድሞቼ ሆይ

የውነተኛ የመንፈሣዊ ወንድምነታችሁንና ፍቅር ለመግለጽ አስባችሁ ይህን የናፍቆት መታሰቢያ ማድረጋችሁ እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ ያለውን የወንጌል ቃል እንደፈጸማችሁና የማህበሩንም ምልክት ቃል እንደጠበቃችሁ ያስረዳል ማለት የማህበሩ ስም ፍቅርና አገልግሎት ነውና ይልቁንም ለወደ ፊት ምሳሌ የሚሆን ከልብ የማይጠፋ ውለታ ስላደረጋችሁ የመላ ኢትዮጵያን ወጣቶች ሀሊና ያነቃቃል ስል ታላቅ ተስፋ አደርጋለሁ።የማህበር ወድሞቼንና በዚህ አብረውን ያሉትን ወይዛዝርና መኳንንት ሁሉ በሰላምና በጤና አቆይቶ ለቅድስት አገራችን ለኢትዮጵያ በረከት ሰጥቶ መንግሥታችንን አስፍቶ በሰላም ያግጠመን ስል ያባትነትና የወንድምነት ምርቃቴን አቀርባለሁ ብለው በጨረሹ ጊዜ ረጅም ጭብጨባ ተጨበጨበ ።

ወዲያውም ክቡር ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ክቡራን እመቤቶቸና ጌቶቼ ወንድሞቸም ሆይ

በርሀሩሁ አባታችን ትጋትና በለጋሱ አልጋ ወራሻችን ቸርነት እኔ ወንድማችሁ ከክቡርአባታችን ጋራ ለመሄድ ስለተፈቀደልኝ ለልዑል አልጋ ወራሽና ለታላቁ አባታችን ለክቡር ኃኪም ወርቅነህ ጥልቅ ምሥጋናዬን አቅርቤ ክቡራን እመቤቶቼንና ጌቶቼ ፥ ወንድሞቼንም በሰላም ያገናኝን ስል የናፍቆት ስንብቴን ሰጥቼ በደህና የመመለስ ምኞቴን አቀርባለሁ ብለው በጨረሱ ጊዜ ተጨበጨበ።

ይልቁንም ክቡር ልጅ በድሉ በግንቦት ፳፰ ቀን የተደረገውን ከሜዲአስበው ያው እንደፈራሁት ልጄ አፈረንጅ አገር ሊሄድ ነውና ልጅህን በደህና ይመልስልህ ብላችሁ እዘኑልኝ ብለው እንደ ማልቀስ ሲሉ ጊዜ እዚያ የነበረውን ሰው ሁሉ በሳቅ ፈቱት ። የልጅ ልመና ያባት ሐሳብ ስለሚለው ከሜዲ ሁለተኛው ዓመት ብርሃንና ሰላም ቁጥር ፳፪ ተመልከት ።

እውነትም በክቡር ሐኪም ወርቅነህ የማህበሩ አለቃና በማህበረተኞቹ መካከል የነበረውን ያባትነትና የልጅነት ፍቅር ማየት በዚያ ከነበረው ከሚጣፍጠው መብልና መጠጥ ይልቅ ልብን ደስ የሚያሰኝ ነገር ነበር ።

ክቡር ሙሴ እንድርያስ ከዋድያ ማህበሩ ጠርተዋቸው ነበርና የማህበሩን ፍቅርና መስማማት አይተው ደስ ብሏቸው እያመሰገኑ ሄዱ ።

መኑ ጠቢብ ዘየአቅበ ለዝ

ካደረ የማይለይ ሀብትን ከተሰጠ የማይነሣ እውቀትን ገንዘብ እናደርግ ዘንድ የከበደውን አቃልለህ ፡ የጠመመውን አቅንተህ ፣ የጐደለውን መልተህ ፡ ደገኛውን ትእዛዝ (ደምብ) በብርሃንና ሰላም ስጠን ። የሰው ውሳጣዊ አእምሮው የሚታነጽበትንና አፍአዊ ግብሩ (ሥራው) የሚገለጸበትን መርምሮ ያወቀና የተረዳ እንዴት ያለ እድለኛ ነው ። እኔስ ስንኳን ይህን ልመረምርና ወደፊትም ያየሁትንና የሰማሁትን ልጽፍ ስላለፈው ያዩ ላላዩ ፡ የሰሙ ላልሰሙ ፡ የነበሩ ላልነበሩ ፤ እንዳይነግሩ አደራ ስል ነበር ። ምንም ዳዊት ኢትፍርሆ ለሰብእ ሰበ ይብእል ያለው ቢያግዘኝ ሰሎሞን ጥበቡ ለነዳይ ምኑን ውእቱ ባለው ተረትቼ እስካሁን ቆይቻለሁ ። ጥበብም ሀብታምና ድሀም በትል ከሁሉም ያፈቀራትን ብታከብር ሰው (ሕዝብ) የሚቀበለው ደጃዝማች እገሌ በግዛታቸው ቀድሞ የነበረ ክፉ ልማድ አስቀሩ።ስለሀገራቸውና ስለሕዝባቸውም እንዲህ ያለ የርኅራኄ ሥራ መልካም ደምብ፡ አቆሙ ሲባል ለጊዜው ተስፋ ይሆናል ፡፡ ያሁን ሕዝብ እንደቀድሞ አይመስለኝም ፤ በቃል ሰልጥኑዋል ። እኛ ግን ባይቀበሉንም አይቻለንም በየነው በሰማነውም ሁሉ ዝም እንል ዘንድ ጊዜውን ያጠብቅ እንጂ እነሆ ካገረ ገዦዎች ፍርድን የጠነቀቁ ጉቡን እጅ መንሻን የናቁ ሕዝብ ሥራ እንዳይፈታ እንዳይጉላላ እንዳይበሳጭ እንዳይመረር ዳኞችን እየተከተለ አቤት አቤት እንዳይል በሥርዓት የጠበቁ ብንፈልግ እናገኛለን ደግሞም እግዚአብሔርን የማይፈሩ ሰውንም የማያፍሩ በዘመድ በወዳጅ ባማላጅ በጓዳጅ ጉቦ እየተቀበሉ ፍርድ የሚያጐድሉ ደሀ የሚበድሉ በተሾሙበትም ሕዝብ ግብር እያፀኑ ካባት ከናቱ ከወንድም ከእህቱ ካገሩ ከምድሩ እየተሰደደ ወደባዕድ ሀገር የሚሄድም ይኖር ይሆናል ። መልካም ገዢ ለሀገሩና ለሕዝቡ ዋስና ጠበቃ መሆኑን አውቆ ድሆቹም እንደሱ ሰው መሆናቸ

ውን አስተውሎ የተቻለውን የርኅራኄ ሥራ ቢሠራላቸው
በሰውም በእግዚአብሔርም ዘንድ የተወደደ ይሆናል ። ያየውን
ወንድሙን ያልወደደ ያላየውን እግዚአብሔርን ይወድ ዘንድ
እንዴት ይችላል ይላል ሐዋርያ ። በ፫ተኛ ዓ በ፳፯ ቁ በ፱፻ ፲፪ ገጽ
ሺቃ መኰንን የጻፉትን ስመለከት እንግዴህ እኒህ ያልታደሉ
ሠራተኞች በላይ ድንቁርና በታች እውቀት ጨቁነው እንዲያስ
ጨንቋቸው የተሰማው ሰው አይስተውም ከሚለው ስደርስ
አንድ የቀድሞ መኰንን የተናገረው ትዝ አለኝ ። ነገሩም ይህ
ነው ። የቤቱን አዛዥ ፲፭ ዳውላ ጤፍ ከጎተራ አውጥተህ
ለገባሮች ሰጥተህ አስፈጭ ብሎ አዘዘው ። እንዳዘዘውም አስፈ
ጨና ቢሰፍረው ፲፱ ዳውላ ሆነ ። ምን ያህል ሆነ ብሎ ቢጠይ
ቀው ፲፱ ዳውላ ሆነ ጌታዬ አለው ። ጌትዮውም እረ ግና ጤፍም
ጉደለ በለሆሣሥ ይህን ነገር ገብስ እንዳይሰማ አለው
ይባላል ።

አሁንስ በዚህ ነገር ምን ያልተነካ ይገኛል ነገር ግን ገብስ
እንዳይሰማ ፡ስላንድ ሹም ከተሾመ እስካሁን ዕረፍት ሳይደረግ
ደክሞ ያለማውን ለመጻፍ ምኞት አለኝ ሲራክ ኀባዕ ነገረክ እስከ
ትረክብ ጊዜሁ ብሏልና ጥቂት ጊዜ እቆያለሁ መንግሥት በእ
ውቀታቸውና በመታመናቸው በትጋታቸውና በቅንነታቸው
መርጠ የሾማቸውማ ሹማምት በሥራቸው ጥራት በድካማቸው
ብዛት መንግሥታችንን አክብረው አገራችንን ጠብቀው በውስ
ጣቸው ያሉትን ሠራተኞች አመስግነው አምረው ይታያሉ ።
ጥቂቶች ሰነፎች ግን ብልሁን ተንኮለኛ አስተዋዩን ነገረኛ ትሁ
ቱን ትዕቢተኛ ዝምተኛውን ግፈኛ እያስመሰሉ ለባለዘመኖች
በየቤታቸው እየዞሩ አስቀድመው ያመለክቷቸዋል ። እነዚያም
እስኪ እነየው እንመርምረው ከቃሉ እናግኘው ሳይሉ ነገራ
ቸውን ተቀብለው እውነት ማድረግ ምን ሐሳብ እንደሆነ ልና
ውቅ አልቻልንም ፤ አሁን በሰው ዘንድ የተሰወረ ቢሆን በእ
ግዚአብሔር ዘንድ የተገለጸ ነውና ዕድል ተርታቸውን ጽዋ
ፋንታቸውን ያን ክፉ በታ ሳያደርግላቸው አይቀርም ። ከሁሉ
በፊት ለሕዝቡ የሚያስፈልገው በጎ ሥራ በከተማ ሥራ ፈት
ሁኖ እንዳይጉላላና እንዳይቸግር በትንሽ ደጅ ጥናት በትንሽ
ነገር ዓመት ፪ዓመት እንዳይቀመጥ ዶሮ ብትታመም ፍሪዳ ጣሉ
ላ፣ የሚሉት እንዳይደርስበት ትንሽ ሲፈልግ ያለውን እንዳይጨ
ርስ የቆመ ደምብ የሚሠሩበት ለየሹማምቱ መስጠት ያስፈል
ጋል በተረፈ ድሀ ሁኖ ላየው ብዙ ያበሳጫል እነሆ አንድ ሰው
አራት መኳንንት ደጁ ሲጠና ፪ዓመት ከመንፈቅ ሆነው ሁሉም
እናስደርግልሃለን ይሉታል እንጂ አንችልም አይሉትም እንግ
ዲህ ጭራሽ ሳይነግሩለት የቀሩ እንደሆነ ምን ያስብ ይሆን? አንድ
ያገሬ የቡልጋ ልጅ በገና እየደረደረ ያጽናናኝ ዠመረ በግጥም
ዜማው ልዩ ነበረ ማዕዜ እበጽሕ ወእሬኢ ገጸ ለአምላኪየ ተ መ
የቀድሞ ሰዎች ደጎና ሄዱ፡ሳያሩ ሳይነዱ፡ያሁኖቹ ግን ተቃጠሉ
እንውጣ እንውጣ እያሉ፡እሳት ሐሳብን ጠቅል፡በጥበብ በኃይል።
ጌታዬ ሆይ ልንገርህ፡ድሆች አይቁሙ ከደጅህ፡ደሆችን ጥራቸው
አቅራቢም የላቸው።የቀን ከሥር አንድ አውጣልን። ለኛስ ማን
አለን፡ድሆችህን አትርሳ፡እንዳያገኝህ ወቀሳ፡ለድሆችህ ሰጠን፡አም
ላክ አንተን፡ከንተ በቀር ለማዳን። ማንንም አናምን ። ቸር ኖላዊ
ነበረ ። ስለበዛን ተቸገረ ። አንለያይ በጉችህ ። ግዛን ጠቅለህ ።
(ልዩ) መስማት ይሰማሉ ። አያስተውሉም አሉ ። ብርሃንና ሰላም
ተፈሪ ነው ቃሉ ። አክሊለ ደጀን ዘብሔረ ቡልጋ

አገርንለማልማት ገገር ለሕዝቡ መራራትና ማሰልጠን እንዲገባው

መጀመሪያ ክፍል እውነተኛ ባላባትና ዕውቀትም ርኅራ
ኄም ያለው ሰው ገገር በሆነ ጊዜ ሕዝቡ ደስ ይላቸዋል ።
ስለምን ቢሉ አባት ለልጆቹ እንዲያስብ ለሚገዛው አገር ተጨ
ንቆ ተጠንቅቆ ያስብላቸዋልና ። ባላባት ያልሆነና ዕውቀት ርኅ
ራኄም የሌለው ሰው ግን ገገር በሆነ ጊዜ እንደ እንጀራ አባት
ጨካኝ ይሆንባቸዋል ። የእንጀራ አባት የእንጀራ ልጆቹ ጥቂት
ቢበሉ ብዙ ብዙ ቢሠሩ ጥቂት እየመሰለው ብትርና ቁጣ ያበዛ
ባቸዋል ። እንደዚህም ሁሉ እሱም አገር ከማጥፋትና ሕዝብን
ከመበደል ለራሱ ጥቅም ብቻ ከማሰብ በቀር ሌላ ሥራ የለውም
ገገር ሁኖ ፍርድ ማወቅ ድኃን መደገፍና መጠበቅ ነው ። ድኃ
የእግዚአብሔር ቍስሉ ነውና ። ዳግመኛም በልቡናዬ ዕውቀት
ንና ርኅራኄንም አሳድርብኝ ብሎ አምላክን መለመን ነው።

ሁለተኛ ክፍል የወረዳ ሹም ምስለኔ እንደራሴ የሽለቃ
የተባሉቱ ገንዘብ እናጠራቅማለን እያሉ ድኃውን ያስመርሩ
ታል ። ትልቁ ገገር መበደሉን አይሰማም ። አገር ጥሎ ይሄዳል
እንዲህ እየተበደለ ብዙ ድኃ አገሩን እየጣለ ይሄዳል ። አውሬ ወም
በዴ ወደ በሽታ ይገለዋል ። ልጅ ሳይተካ ይቀራል ። ወይም ተሰዶ
በሰው አገር ለምዶ ይቀራል ። እንዲህ ሲሆን ጊዜ በመልማት
ፈንታ አገሩ ይፈታል ። ብዙ ገንዘብ ይገኝበት የነበረ ገንዘብስ
ይቅርና ከሰው ተለይቶ ደን ሆኖ ይቀራል ፤

ከዚህ ሁሉ ለማዳን በየአውራጃውና በየሽለቃው አገር
ሁሉ መንግሥት ደሞዝ ሰጥቶ ተመልካቾች ማኖር ነው ፤ እኒህም
ተቋጣሮች ናቸው እንዲህ ቢሆን አገሩ ይለማል ሕዝቡ ይበዛል
ብዙ ገንዘብ ለመንግሥት ይገባል ገዥ ሲፈርድላቸውና ሲራራ
ላቸው ጊዜ ደስ ይላቸዋል መንግሥታቸውንና አገራቸውን ይወ
ዳሉ ስለሀገራቸውም ይሞታሉ ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታ
ችን የሱስ ክርስቶስ ስለኛ መሞቱና መከራ መቀበሉ ፍቅርንና
ርኅራኄን ሲያስተምረን ነው ፤ እኛም እንግዴህ ስለሀገራችን በፍ
ቅር ማሰብና መሞት ይገባናል አለዚያ ለዘመዱና ላገሩ የሚያ
ስብ ከሐዲያን የከፋ አረመኔ ነው ይባላል ለማንም ሰዎች ቢያ
ኖሩት እንዳች የሚሹ የሚበጀውንም ባያስብላቸው ይልቁንም
ለቤተ ሰዎቹ ሁሉ ሃይማኖቱን የካደ ከማያምኑትም የከፋ ነው
፩ ጢሞቴዎስ ፭፰ ይህ ሁሉ የሚለውን ተመልክተን ስለ ሀገ
ራችን መንግሥትና ሕዝብ በየአቅማችን ማሰብና ማገልገል ይገ
ባናል አለዚያስ ቀን ስንበላ ውለን ሌት ተኝተን ብናድር ይህን
ሁሉ ሳናስብ እንደ እንስሳት መሆናችን ነው ከሞቱትም መቄ
ጠራችን ነው ከቶም እነዚያ ይሻሉናል ዘሞተሰ አዕረፈ ተብሏ
ልና ንጉሥ ቢሞት ንጉሥ ይተካል መንግሥት ቢጠፋ ግን
አውሬ እንደሌላቸው ንብ መሆን ነው ። ያልተማረ ሕዝብ ግን
ንጉሥና መንግሥት ፩ ይመስለዋል ንጉሥ ማለት የሕዝብ ወይም
የማኅበር አለቃ ማለት ነው መንግሥት ማለት የሕዝብ ማኅበር
ማለት ነው ።

የሆነም ሁኖ የሕዝቡን ማኅበር ወይም የሕዝቡን ጉባኤ የሚጠቀልልና ፩ድ የሚያደርግ ማለት ነው። አዋቆችና ፈላስፎች መሐንድሶችም ሊቃውንትና የሕዝቡ መምሕራንም ስለዚህ የሰውን ወገን በ፱ ይከፍሉታል ፤እንዲህ እያሉ፡ ፩ዲቱ ሕዝብ ልባም ናት የታመነችም ናት ቁም ነገርንም ትወዳለች ምንም ቢሆን አትፈራም ደህና ሥርዓትም አላት ትጠብቀው ማለች ስለዚህ የእግዚአብሔርን በረከት በሃይማኖት ተቀብላ በደግነትና በትምህርትም በእውቀትና በብልሃትም ታድጋለች አገሩዋንም አቅንታ የሰውን አገር ትወርሳለች መንግሥቷም ለዘላለም አይንቀሳቀስም። ሌላይቱ ሕዝብ ግን የሚወለዱትንና የሚሞቱትን ሰዎች አትጽፍም ሹማምንቶቿንም ገንዘባቸውን እንዳይጠፋባቸው በመዝገብ እየጻፉ ያስቀምጣሉ እንጂ የትውልድ መጻሕፍት አይጠብቁም ስለዚህ አገርዋ ልብ የላትም ሐሰትም የምትወድ ፈሪም ናት አልታመነችም በጎ ነገርም አይገኝባትም በጨለማ መንፈስ ተሸፍና እርስ በርስዋ እየተፋጀች በወሸላከነትና በምቀኝነት ሁና እውቀትና ብልሃት ሳትሰራ ትጠፋለች ብለው በመጽሐፋቸው ታሪክ ጽፈውታል። ስለዚህ እኛ ከማነኛይቱ ወገን ነን እያሉ ሁሉም እያንዳንዱ ልቡናውን ይመርምር አሁን እኛ በሀገራችን የሆነውን ታሪክ የምንጽፍና የምንጠብቅ ብንሆን በጨለማ መንፈስ ባልተያዝንም ነበር ።

ከኛ በኋላ የነበሩ ዓለም ሁሉ ፊንቃ ባልተኛንም ነበር ። እንዲህ ሲሆን ጊዜ መኳንንቱ ከንጉሡ ንጉሡ ከመኳንንቱ ከወታደሩ ወታደሩ ከባላገሩ ፩ አካል ፩ አምሳል ሁነው ተስማምተው ልጆች አባታቸውን እንዲወዱና ለአባታቸው እንዲታዘዙ ለንጉሡ እየታዘዙ የንጉሣችን ዕድሜያቸውን አርዝምልን ብለው እምላክን እየለመኑ በፍቅር ይኖራሉ ይኸም ሊታወቅ ቅዱሳት መጻሕፍትና የዓለም ታሪክ ብናነብ ወላጆች ለልጆቻቸው ነገሥታት ለሕዝባቸው የሚያደርጉላቸውን ነገር ትክክል ሁኖ እናገኝዋለን

አ ኢ

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ቁጥር ይታተማል ።

ቢያና ፡ ባልበ ከመንግሥት መኳንንቶችና ከኢጣልያኖች ተሰናብቶ በአሬዮፕላን በኩል እሮማ ተነስቱአል ።

ሶፊያ ፡ብሮፍ የሚባል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አካሜራ ዴፑታቶ ስለውጭ አገር ፓሊትክ ሲነጋገር የቡልጋርያ ምኞት ከመንግሥቶቹ ጋራ እየተስማማች እምነት ለማግኘትና ደግሞም በዓለም መንግሥቶች ማህበር እንደሌሎቹ መንግሥት ተስተክክላ ለመንግሥትዋና ለስምዋ መልካም ስም እንድታገኝ እንደሆነ ገልጡአል ። ሩሲያን እውጭ አገር ይልቁንም በቡልጋርያ ግርግር ለማስነሳት ብቻ ሐሳብዋ ስለሆነ ፤ እንደገና ከሱዋ ጋራ የዲፕሎማቲክ ሥራ ለማድረግ አስቸጋሪ መሆኑን አመልክቱአል ። ጦርም እንዲቈጠር ተብሎ የነበረ አሁን ግን መንግሥቶች ይህን ሐሳብ ስላስቀሩት ለነዚህ የበለጠ ምስጋናውን አቅርብዋል ።

ኒዩ ዮርክ ፤ የፎርድ ኢንዱስትሪያ እየሰፋ መሄዱንና ደግሞም ስለ አይሁድ ሕዝብ የሚያሳይ ዴባረኒ ኢንዲፔንዴንት የሚባል ጋዜጥ ላወራው ወሬ አሁንም የአሜሪክ ጋዜጦች ደጋግመው ያወሩታል ።

የፊተኛ ሳንታማሪያ በራሪ ስብርባር እሬዕቤልት ባሕር ዘንድ ተቃጥሎ የነበረ ፍራንኪኒ የሚባል ኢጣልያ አባሕር አግኝቶት በማውሬቲያኖ የሚባል መርከብ በኩል ወደ ኢጣልያ አገር ተልኳል ።

ሮማ፡ ሚክሎኮፑሎስና ካፉንደሪስ የሚባሉ የግሪክ ምኒስትሮች ትላንትና ማታ ሮማ ገብተዋል ።

ቶሪኖ ፡ የኢጣልያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ከየመን ለመጡ መልክተኞች በቆይታ ተነጋግረው ወደ ማታው አብረዋቸው የወታደሮች ስፍራና የበላገሮቹም ኢስቲቱቶ አይተዋል።

ዱብሊኖ ፡ ያልታወቁ ሶስት ሰዎች አሂጂንስ ለሚባል የአርላንድ ምኒስትር በሽጉጥ ተኩሰውበት ጥቂት ቆይቶ ሙቷል።

ሞስኮ ፡ ቡአች በሚባል የእንግሊዝ ወኪል ተመርተው ፳፫ሰዎች ስለ እንግሊዝ በሰላይነት ታምተው መያዛቸው ኡፊሴል ጋዜጥ ያወራል ።

ሮማ ፤ ሚካሎኮፑሎስና ካፉንደሪስ የሚባሉ የግሪክ ምኒስትሮች ማታ እቢላ ቶርሎኒያ ሂደው ከፕሬሲደን ሙሶሊኒ ጋራ ረጅም ጊዚያት ተነጋገረዋል

ለእውነተኞች ኢትዮጵያውያን ማስታወሻ

በፈረንሳይ ቅኝ አገር ወሰንና በእንግሊዝም እንደቆመው ጉምሩክ ሁሉ ኢትዮጵያ በማናቸው አይነት ወሰን የሌለው ጥቅም የምታገኝበት ነውና በአድዋ ከተማ ላይ ለሐገሩ ሺአለቆች የሚገባቸውን ጥቅም ሣትነካ በሥርዓት ተተካክሎ ሊቆም ያለውን ጉምሩክ በፍጥነት ማቆም ያስፈልጋታል። የዚሁ ነገር ጥቅም የሚያስረዳ በስርዓት ጽፌን አዘጋጅተናልና መረዳት የሚገባው ሁኖ ከተረዳውም ይህ ነገር እንዲፈጸም ሊረዳ የሚችል ሰው ይህን ለጻፈ ሰው ጠይቆ ጥቅሙን በዝርዝር ሊያውቀው ይችላል

ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም

እራዶም ዕቁቡ

የኢትዮጵያ መንግሥት የርሻ ሚኒስቴር
የከብት ሕክምና ሥራ
(አዲስ አበባ)
ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

የርሻ ሚኒስቴር አዲስ አበባ እራዳ ላይ እንጨት ተራ አጠገብ ማናቸውንም ዓይነት የከብት በሽታ ማከሚያ (የከብት ሐኪም ቤት) ማቆሙን ለሕዝብ ያስታውቃል በዚህም በከብት ሐኪም ቤት ከእሁድና ከዓመት በዓል በተቀር ሁል ጊዜ ከጧቱ ከሁለት ሰዓት እንሥቶ እስከ ሰባት ሰዓት ድረስ ከብቱ የታመመበት ሰው ሁሉ እየመጣ ሊያሳክም ይችላል ። ደግሞ ልዩ ልዩ ለሆነ የከብት በሽታ መድኃኒት እያሰናዳ ካዲስ አበባ ከተማ እርቀው ለሚኖሩ ሰዎች ይሸጣል የሚጋባ የከብት በሽታ በተነሣ ጊዜም በሽታው እንዳይተላለፍ የክትባት መድኃኒት ያደርጋል ። የታመሙትንም ከብቶች እንደሚያስፈልግ እያደረገ በቀላል ዋጋ ያሳክማል ።



እጅግ ጥሩነቱ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ተሩብ ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፰ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ ።
ም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፪፺ ብር ።
በሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተኩል
ነወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተሩብ
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፱ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፫ ብር
አቡጀዲ መነጸር	፩ ኮረጃ	፪፴ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፪፴፰ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፪፳፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፪፱ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፪፳፫ ብር
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፪፺፩ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፰ ብር ።
ሻይ	፩ ነጥር	፲፩ መ

ስለ ምንዛሬ

በአንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፫
በአንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ ፰
በአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፳፪ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፮ ብር

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

ሩግቢ

RUGBY

የዘህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ፣በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፈታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሄስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

Berliet



ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ አቶሞ ቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ

ARMENAK ZAMANIAN
AGENT GÈNÈRAL
Pour l 'Abyssinie et Djibouti

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ኩዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፴
3 me ANNÉE № 30

ሐሙስ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፤ ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 28 JUIL 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ቢገዛ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በዕውቀት የበለጡ የበለጡት እንደ ተሸለሙ ።

ሐምሌ ፲፬ ቀን በ፱ ሰዓት የኢትዮጵያ መኳንንቶችና የውጭ አገር ሚኒስትሮች ወይዛዝርም በትምህርት የበለጡትን ተማሪዎች ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ከልዑል የኢ መ አ ወ ተፈሪ መኰንን ስጦታ ሲቀበሉ ለማየት ተጠርተው ነበርና በተጠሩበት ሰዓት በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተሰበሰቡ ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ እስኪመጡ ድረስም ልዑል የኢ መ አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሥራውን የሚያሰናዱ ሁሉ በሥርዓት ሥራቸውን አከናውነው እንዲጠባበቁ አደረጉ ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት በደረሱ ጊዜም የሰላምታ ሙዚቃ ተነፋ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽ ከቡራን መኳንንትና ወይዛዝርም ከተሰናዳላቸው ቦታ በተቀመጡ ጊዜ ተማሪዎቹ የኢትዮጵያን መዝሙር ባማረ ዜማ ዘመሩ ።

ከዚህ በኋላ ስጦታ መስጠት ተጀመረና በትምህርት የበለጡ ልጆች በየስማቸው እየተጠሩ ልዩ ልዩ የሽልማት ስጦታና በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት መልክ የታተመ የወርቅ ሜዳይ ተቀበሉ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገ ታት ዘውዲቱ ።

በተቀበሉም ቀኑጥር ጭብጨባው ይቀልጥ ነበር። በእንግሊዝ መጀመሪያ ሆኖ የመጀመሪያ ስጦታ የተቀበለ ተምሳስ የተባለ ተማሪ ነው ።

በፈረንሳዊ መጀመሪያ ሆኖ የመጀመሪያ ስጦታ የተቀበለ ደግሞ ግዛው ነው ። ስጦታ መስጠት ከተፈጸመ

በኋላ መጋረጃው ተገለጠና ከልጆቹ አንዳንድ እየተነሱ ባማ ርኛ በእንግሊዝና በፈረንሳዊ ደስ ደስ የሚያሰኝ ንግግር ተና ግረው ባነጋገራቸው መሰልጠን ሰውን ሁሉ ደስ አሰኙት ።

ቀጥሎም አምስት ልጆች በፈረንሳዊ ቋንቋ ብዙ ጨዋታ ተጫወቱና ተጨበጨበላቸው ። ወዲያውም ተማሪዎቹ ተሰብስ በው ስለ ግርማዊት ንግሥት መዝሙር ዘመሩ ።

ከዚህ በኋላ ቀይና ጥቁር የለበሰ በሰይጣን ምሳሌ ሆኖ ሲፎ ክር አንድ እርሱን የመሰለ ከርሱ የበረታ መጥቶ ፎከረና አስ ደነገጠው ። ቆይተውም ሁለቱ ተስማምተው በንድነት ሄዱ ። ያለባበሳቸውና ያኳሁናቸው ነገር በዚያ ለነበረ ሰው እጅግ አስ ገረመው ።

ሁለተኛ መጋረጃ በተገለጠ ጊዜም አንድ ሽማግሌ ከተኛ በት አልጋ እየሳለ ተነሥቶ ሰይጣን አጣልቶ ሊበታትናቸው ስለ ፈለገ ፍቅር ስላጡ አምስት ልጆቹ ከሽምግልና ድካምኛተ ነሣ እየተንቀጠቀጠ ሲጸልይና ዳዊት ሲደግም ታየ ። ልጆቹንም አስጠርቶ ስለ መጣላታቸው ገሥጾ መክሮ ዘንጎችን ባንድነት አሥሮ ሊሰብሯቸው እንዲሞክሩ አዘዘና ሳይሆንላቸው ሲቀር ጊዜ ሽማግሌ አባታቸው ማሠሪያቸውን ፈቶ ዘንጎቹን ባንዳ ንድ እየነጠሉ እንዲሰብሯቸው ስልጆቹ ሰጣቸውና ሰበብረው ጣሏቸው ። ልጆቹን በፍቅር ማሠሪያ ታሥረው አንድነታቸውን ቢያጸኑ ማንም ሊጐዳቸውና ሊያቸንፋቸው እንደማችይል ፤ፍቅር ቢያጡና የፍቅር ማሠሪያቸው ቢፈታ ግን ኀይላቸው እንዲ ደክምና ጉዳት እንዲያገኛቸው አስታወቃቸውና በፍቅር እን ዲኖሩ መከራቸው ። ልጆቹም ተስማምተው በፍቅር እንዲኖሩ ላባታቸው ቃል ሰጡትና ፤ በሴት ምሳሌ ሁና ለመጣችው ለወ ይዘሮ ፍቅር አደራ በሰጣቸው ጊዜ በጣም ተጨበጨበ ።

ይህም ሲፈጸም ልጆቹ ተሰብስበው አስገዶም ኃይለ ማር ያም የተባለ ግሩም የሆነ ድምፅ ያለው ልጅ እየመራቸው ስለ ልዑል ተፈሪ መኰንን እየተቀባበሉ መዝሙር በመዘመራቸው የሰዉን ልብ አንቀሳቀሱት ።

ቀጥሎ አቶ በቀለ ሀብተ ሚካኤል የሚከተለውን
ንግግር ተናገሩ ።

ልዕልት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን

ክቡራን ጌቶች እመቤቶች ።

እንደ ተማሪ ቤቶች ደምብ የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ስለክረምቱ ዕረፍት የሚዘጋ ስለሆነ ለተማሪዎቹ ፈተና አድ ርገን ልዑላን ጌቶቻችን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን መጥተው የተማሪዎቹን ትምህርታቸውንና ተማሪ ቤታችንን እንዲያዩልን አመልክተን የመምጣታቸውን ፈቃድ ስላገኘን ደስ ብሎን እላንትም ክቡራን ጌቶቻችን አብራችሁ እንድትመጡ ልን አስታውቀናችሁ ልክ በፈለግናችሁ ሰዓት ጥሪአችንን ፈቅዳ ችሁ መምጣታችሁ እጅግ ደስ ብሎናል ።

በዚሁ አሁን ባሳየናችሁ ጫወታ ውስጥ ያልተካከለ ነገር ብታገኙበት ፍጹም ይቅርታችሁን ለምነን ለወደፊቱ ደስ የሚ ያሰኛችሁን እንድናደራጅ ተስፋ እንሰጣለን ።

ክቡር ደጃዝማች ብሩም ለዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት እርዳታ ለወረቀትና ለቀለም መግዣ አስር ወቄት ወርቅ ለተ ማሪዎች ለብርዝ ሐያ ጉንዶ ማር ለተማሮች ለዳቦ የሚሆን ሰላሳ አምስት ዳውላ ዱቄት ለዚሁ ማብሰያ መቶ ሸክም እን ጨት እርዳታ ስለሰጡ ከልባችን እናመሰግናቸዋለን ።

ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ዕድሜ ለኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

በመጨረሻው የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ግሩም የሆነ ብዙ ምክ ያለው መን ፈሳዊና ሥጋዊ ትምህርትን የሚሰጥ ቃል ተናገሩ ። ይህንኑም የው ጭ አገር ሰዎች እንዲሰሙት ተብሎ ክቡር አቶ ብርሃነ ማር ቆስ የጽስጣና የቴሌግራፍ ዲሬክተር በፈረንሳዊ ተርጉመው ተናገሩት ፡፡ ቃሉም የሚከተለው ነው ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ።

አገራችን ኢትዮጵያ ከቀድሞ ጀምሮ ራስዋን የቻለች ነጻ መንግሥት መሆኗዋ ምንም በዓለም የታወቀ ቢሆን የዓለም መን ግሥቶች ጓደኛ ሆና ፲፱፻፲፩ ዓመተ ምሕረት ከማህበሩ ገብታ ማህበረተኛነቷን ገልጻለችና ይኸን ጓደኛነቷን ለማጽናት የትም ህርት ቤቶች ማብዛት እንዲያስፈልጋት የሁላችንም ልብ ተረድ ቶታል ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክም እንደ ሀገራችን ልማድ ብዙ ዘመን ገዝተው ከኖሩ በኋላ ከውጭ አገር መንግሥቶች ጋራ የሚያገናኝ ሥራ ሲጀመር የሀገራችን ትምህርት ብቻ እንዳይበ

ቃና እነርሱንም መምሰል እንዲያስፈልግ ስለ አወቁ ለውጭ አገር ቋንቋ ለጊዜው ይህን ተማሪ ቤት አቆሙ ። ለመኳንንቱና ለሕዝቡም ምሳሌ ለመሆን ተወላጆቻቸውንና ዘመዶቻቸውን በቤተ መንግሥት ያሳደጓቸውን ልጆች ሁሉ ወደዚህ ትምህርት ቤት እንዲገቡ አደረጉ ይህች ተማሪ ቤት ስትመሰረት በመጀመሪያ ከሉት ልጆች አንዱ እኔው ራሴ ነበርሁ።የኢትዮጵያም ልጆች ትምህርት ወዳጆችና ራሳቸውም ለትምህርት የተከፈተ መሆኑን ማንም አይጠራጠርም ይህንንም የሚያስረዳ ነገር በየጊዜው እየመረጥን ወደ ውጭ አገር ከሰደድናቸው ልጆች በቀር ከባት ከናታቸው እየኰበለሉ በፈቃዳቸው ለትምህርት ወደ ውጭ አገር የሔዱ ብዙ ልጆች ይገኛሉ ። በዚሁም በሀገራችን ውስጥ በፈቃዳቸው በጥረትና በትጋት እየተማሩ ለመንግሥታቸው አገልጋይ ለመሆን የደረሱ ብዙ ናቸው ። ደግሞ ከባላገርም ከከተማም በፈቃዳቸው እየመጡ እንግሊዝ የሚሉ ብዙ ስለሆኑ ወደ ፊት በየስፍራው የትምህርት ቤት በዝቶ ቢማሩ ለራሳቸው ጥቅም ነው ለመንግሥታችንም ኩራት ላባት ለናታቸውም ደስታ ይሆናል ያልተማረ አባትና እናቱን እንዲረግም የተማረ አባት እናቱን እንዲመርቅ ይህ ለማንም አይሰወርም።ደግሞ የሀገራችንን ትምህርት ባማርኛና በግዕዝ መማር ትልቅ ጥቅም ያለበት ነውና መኳንንቱ ሁሉ በየግዛታቸው የንባብና የጽሕፈት ትምህርት ቤት እያሰሩ እንዲያስተምሩና ወደ ውጭ አገር ለተሰናዳው ትምህርት የተማሩት እንዲመጡ ያስፈልጋል ። ይኸንንም ደንብ ማቆማችን የሀገራችንን ትምህርት ሳይማር የውጭ አገር ዕውቀት እማራለሁ ማለት በድቡሽት ላይ ቤት እንደሰራው ሰው ምሳሌ ለመሆን ነው ።

አሁን እንኳ ቀደምም ብሎ በእኛው ዘመን እነሐኪም ወርቅነህ እነ ነጋድራስ አፈወርቅ እነ ብላታ ኅሩይ እነ ከንቲባ ገብሩ እነ አለቃ ታዬ እናቶ ወልደ ማርያም ከነዚህም በቀር ብዙዎቹ እንደ አምድ ሆነው መንግሥታችንን ለማገልገል መድረሳቸው አስቀድመው የሀገራችንን የኢትዮጵያን ትምህርት ስለ ተማሩ ነው እንጅ እየተጉና እየጣሩ በተማሩት በውጭ አገር ቋንቋ ብቻ አይደለም ፤

በዚህ በተማሪ ቤት ላላችሁ ተማሪዎች የምሰጣችሁ ምክር ለአባት እጥፍ ደስታ የሚሆንለት የልጅ ልጅ ማየት ነውና እግዚአብሔር በተፈጥሮ እንደሰጣችሁ እድላችሁ በምታገኙት ዕውቀት አስተማሪ እንድትሆኑና ለመንግሥቱ አገልጋይና ሠራተኛ የዕለት ጥቅም ብቻ ፈላጊ እንዳትሆኑ እለምናችኋለሁ ፤

የሚበቃ ዕውቀት እንድታገኙ ብትተጉና ብትጥሩ ብትማሩ የሚንቋችሁ ያከብሩዋችኋል የሚጠሏችሁ ይወዷችኋል ከብራችሁም የበዛ ሆኖ ደስ እንዲላችሁ አስተውሉ

መምሕራኑም ሕጻናቱም እስከ ዛሬ ባለው ድካማችሁ እናመሰግናችኋለን ።

ግርማዊት ንግሥት ሆይ ።

በኢትዮጵያ ላሉት ተማሪ ቤቶች ሁሉ እናት ለሁሉም ልጆቿ ነውና የምታስበው ሁሉንም እየሔዱ ቢጐበኙ ደስ ይላቸዋል ። ኢትዮጵያም ከፍ ወዳለው ወደ ሥልጣኔ ደረጃ ብትደርስ የመንግሥቱ እድገትና ከፍታ ጥቅማችን ነውና ማስታወስ የሚገባኝ ነው ።

እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ሀብትና ልማት ለንግሥትም ረጅም ዕድሜ እንዲሰጥ ሁሉን ለማድረግ የሚችል እግዚአብሔር ይኸን ምኞቴን እንዲፈጽምልኝ እለምናለሁ ።

በግርማዊት ንግሥትና በኔም በራሴ ስም የውጭ አገር መልክተኞችንና ክቡራን መኳንንቶችንና ወይዛዝሮችንም ሁሉ ይህን የትምህርት ቤት በአል ለማክበር ስለ መጣችሁ አመሰግናችኋለሁ ብለው በጨረሱ ጊዜ ሶስት ጊዜ ተጨበጨበ።

ከዚህ በኋላ የቻይ ግብዣ ተደረገና ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ባማረ ዓጀብ ወደ ቤተ መንግሥት ተመለሱ ። ሰዉ ሁሉም ደስ ደስ እያለው ሔደ ።

Bien que l'indépendance de l'ethiopie, neutre pays, soit connue de l'univers entier, indépendance dont les origines remontent aux époques les plus reculées, elle a manifesté en 1923 le désir d'entrer dans la société des Nations comme membre de cette famille des peuples. Nous somme tous convaincus de la nécessité de créer des écoles afin de faire apprécier davantage le concours que notre pays pourra appôrter à cette grande oeuvre humanitaire.

Sa Majesté l'Empereur MENELIK aprés avoir gouverné longtemps notre pays dans le cadre de ses coutumes s'est rendu compte, dès les premiers jours de contact de son pays avec l'étranger, de l'insuffisance de l'instructiôn locale et Il a pensé à doter notre pays des institutions scolaires, et c'est précisémént dans cette noble idée qu'IL a créé cette première école où les langues étrangères ont commencé á être enseignées. Pour donner l'exemple aux Chefs et au peuple Il a mis, Lui le premier, dans cette école les enfants de sa Famille et les enfants élevés à la Cour Imperiale. Je suis fier d'être un des premiers éléves de cette école

Perssonne ne doute de la vivacité d'esperit des enfants de l'Ethiopie ni de leur ardente passion pour les études. A l'appui de cette affirmation, je puis proclamer qu'en dehors des enfants que nous envoyons à l'étranger pour s'instruire. après avoir fait une sèlection parmi les plus intelligents, il se trouve des enfants qui, s'èchappant à la tendresse de leurs parents vont à l'étrnger pour y charcher à satisfaiare leurs nobles aspirations. Nombreux sont ceux qui par un trvail intelligent et tenace sont parvenus à un degré tel qu'ils sont aujourd'hui à même de servir leur patrie.

Un grand nombre d'enfants venant des provinces ou habitant la Capitale sollicitent avec une touchante insistance d'entrer dans les écoles animés du seul désir de s'insitruire; il faut donc ouvrir beaucup d'è coles où l'instruction que ces enfants recevront sera avant tout dans leur i. tèrêt personnel et ensuite deviendra un sujet de fierté pour notre Gouvernement et la joie et le bonheur pour leurs parents.

Il ne faut pas s'étonner si les enfants qui reçoivent une instruction benissent leurs parents et eeux qui en ont été privés les maudissent.

Comme c'est un grand avantage de connaitre la langue maternelle et le gheuze, il est absolument nécessaire que les Chefs aient á coeur de crèer des ècoles dans leurs pays respectifs pour donner aux enfants l'aliment de l'esprit afin de les mieux preparer á recevoir l'instruction ètrangère, car il est indèniable que pour ètudier les sciences étrangères il est indispensable de se perfectionner dans sa langue maternelle, autrement ce serait construire une maison sur du sable.

Je citerai en passant quelques exemples qui sont de nos jours: le D Martin Workeneuh, le Négadras Afe Work, le Belatta Herouy. le Kantiba Cabrou. l'Aléka Tayi, Ato Wolde Mariam etc, etc... s'ils sont arrivés á servir notre Gouvernement ce n'est pas leurs connaissances des langues étrangères, qu'ils ont acquises à force d'un travail persévérant. mais c'est parce qu'ils avaient étudiè d'abord leur propre langue.

Le conseil que je vais donner aux élèves de cette ècole est celui-ci: "La joie d'un grand père est de voir ses petits enfants; votre joie sera celle d'enseigner á votre tour aux plus pétits que vous dans les limites de l'intelligence dont la providence vous gratifiera; Je vous prie de ne jamais rechercher l'intèrêt Passager et si à force de zéle et d'un persévérant labeur vous finissez par acquérir une instruction suffidante ceux qui vous dèdaignent vous respecteront, ceux qui vous haïssent vous aimeront; efforcez vous de regarder toujours vers plus haut."

Nous remercions les professeurs de toutes leurs peines, et les éleves de leurs assiduitè.

M A J E S T E

La mère pense et chèrie avec une ègale affection tous ses enfants; aussi me permettrai-je de rappeler respectueusement á votre Majèsteque si ELLE daigne honorer de ses Augustes visites les enfants des écoles ceux-ci en seront encouragés et la Ethiopie pourra atteindre le plus haut degré de le civilisation.

J'adresse au Tout-puissant les plus ferventes priéres d'accorder à l'Ethiopie le bonheur et la prospérité et à votre Majesté, longue vie. Je le prié d'exaucer ces voeux les pluss ardents.

Au nom de Sa Majesté et en Mon nom personnel je remercie Messieurs les Membres du Corps Diplomatique, les Dames et les Messieurs que out bien voulu honorer de leur prćsence cette fête scolaire

---

የ፪፻፳፯ ገጽ ተከታይ ።

ስለ መንግሥት ወታደር ጉዳት ።

ሕዝቡ ነጻነቱን ካገኘ ዘንድ የወታደሩ ጥቅም ከዚህ ጋራ የግድ ይሳሳብና ድኃ ወታደር የጉልበቱን ዋጋ ያገኛል ማለት ምናልባት በዳር አገር ሁለትና ሶስት ገባሮች እንዳሉት እነሱን እንደ ድኩላ በእያገሩ ከማባረር ያርፍና ከሕዝቡ ላይ ስለ ጉልበት ግብር ከሚወጣው ገንዘብ ያመት ደመወዙን የጉልበቱን ዋጋ በቀጥታ እየተቀበለ መንግሥት ያዘዘውን ስራ በትክክል እየሰራ በያስታ ይኖራል ። ቀለብ በመስፈር የሚኖሩ ሰዎችም በየወሩ ከሶስቱ ባለጉልበታሞች ጋራ መታገል ይቀርላቸዋል ሶስቱ ባለጉልበታሞች የወረዳ ምስለኔ ያሥራት እህል ጸሐፊ ጕተራ ጠባቂ ናቸው እነሱም ሁለት ዓይነቶች ሚዛኖች አሏቸው አንደኛው አሥራት ሰፋሪውን ሁለተኛው ቀለብ ተሰፋሪውን የሚጐዱባቸው ማለት ከህዝቡ ላይ ያሥራቱን እህል ሲቀበሉት በትልቅ ቁና ላዳን ነው ስለ ኢትዮጵያ ደሙን በሚያፈስላት ለወታደሩ በቲንሽ ቁና እርባ ቁልቢጥ ሎሌ በትን እየሰጡት የጭንቅ ኑሮን ይኖራል ።

እነዚህ ሶስቱ ባለ ጉልበታሞች አረማመዳቸውን አሳምረዋልና አይሽሩም እንደ መንዝ ርስት ተተክለውበት ይኖራሉ ።

ደግሞ ስለደመወዝና ቀለብ አሰናከዩቹን ከረጅሙ ባጭሩ ማስታወቂያ ። መንግሥት እንደ አገልግሎቱና እንደ ቸርነቱ መጠን ለወታደር ቀለብና ደመወዝ መስጠት አይቀረውም ዳሩ ግን ክምሳ አለቃው ቱኪ ዱግ ጀምሮ እስከ የሺ አምበሉ አለበት ስፍራ ደርሶ ደጅ ለመጥናት ዳገቱና አቀበቱ ስለ ራቀበት ይህ ከመንግሥት የተቀበለው ቀለብና ደመወዝ ከዳገቱ እኩሌታ ሲደርስ ያልቅበትና እንደገና ከምሳ አለቃው በወለድ ገንዘቡን ይበደርና ዳገቱን ጨርሶ ወጥቶ ከሺ አምበሉ ይገናኝና ያችን የተበደራትን ገንዘብ ሲሰጥ ወንድሜ ሆይ አሁን ምን አለፋህ ምን አሳሰበህ ያንተን አገልግሎትህንና ልፋትህን አጥቼው እኮ አይደለም እግዚአብሔር ባይልልህ ነው እንጂ ገና እኛ ሳንፈጠር አይደለም ለዚህ ለመንግሥት ማገልገል የጀመርከው እኔ እንኳ የመንግሥት ሥራ እየበዛብኝ ባላስታውስህ ያምሳ የመቶ አለቃህ ያንተኑ ጉዳትና መጉላላት ዘወትር ይነግሩኛል አሁንም ይኸውና ወደ ፊት የቀለብና የደመወዝ ማደጊያ መጻፍ ተጀምሯልና በየ ዳር አገርም ገባር ይቈጠር ተብሏልና ከሁለቱ

ምንም ቢሆን አንደኛውን ወገን አታጣምና አይዞህ አትደናገጥ ስለ ስጦታህም እግዜር ይስጥልኝ መባልንና ከንቱ ተስፋውን ብሽማው ሙሉ ታቅፎ ተደብሎ ወደ ቤቱ ይመለሳል። ያ የገባር መቄጠርና የደመወዝ መቀበያ በደረሰ ጊዜ ከደመወዙ ጋራ ዓይን ላይን ሳይተያዩ ወትሮ ለባለ ዕዳ ታልፋለች ገባሮቹም ለባለ ብዙ ብር ይሰጣሉ ስለ ዚህ ድሀ ወታደር በተስፋ ገመድ ታንቆ ብረጅም እንጨት ምኞት ላይ ተንጠልጥሎ ሲወዛወዝ ይኖራል ።

እነሆ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በኢትዮጵያ ራስ ከተማዋ አዲስ አበባ ላይ ለመላዋ ኢትዮጵያ ብርሃኑን እንዲያበራላት ታላቅ ፋኖስን የትምርት ቤት አቁመውላታል ይህ ፋኖስ ዘይት ያስፈልገዋልና ለዘይቱ ዋጋ ሕግን እንዲያሰጠው ይልቅ ከእያውራጃው ስለ ግብር ነጻነት ተብሎ ተጠርቶው የመጡት ድኆች እንደ ተናገሩት ከጉልበት ግብር ነጻ ሁነን መንግሥት የወሰነልንን ገንዘብ ከሰጠን በላይ ደግሞ በንዳንድ ዓመት ውስጥ ሶስት ቀን የጉልበት ሥራ እንስራላችሁ ብለዋልና ስለ ሶስት ቀን ሥራ በየጋሻው ቁጥር አንድ አንድ ሩብ ተጨምሮ የወጣ እንደሆን ይህነን ሩብ ወደ ትምርት ቤት ማግባት ነው ከዚህ ወዲያ ይህ ፋኖስ በሕግ የተሰጠውን ዘይት በገንዘብ አግኝቷልና ያለ ማቋረጥ ሲያበራ ይኖራል ፡ ኢትዮጵያም ኢትዮጵያ ሁና ትኖራለች አለዚያስ ሰውን መልከም ፈቃዱ ባነሳሳው ጊዜ ገንዘቡን ሊቸር ሊሰጥ ይሆንለታል ነገር ግን ይህ እንደ መንኰራኩር ተዘዋዋሪ ፈቃድ ደግሞ መከልከልን ይችላልና ሕግን በሕግ አሻሽሎ አበጅቶ የተጀመረውና ወደ ፊት የሚጀመረውም ሥራ እየገፋ እየተጋፋ እንዲሄድ ጽኑ ተስፋ እናደርጋለን የመልከሚቱ እናት ኢትዮጵያ ልጆቿዋም ከጨለማ ጉድጓድ ወጥተው ላይን የራቀውን ሊያዩ ላሳብ የረቀቀውን ሊሰሩ ይችላሉ ፡

ያገኘ እንደሆን ሕዝቡ ነጻነትን ።
ትበርህ እምፀሐይ ኢትዮጵያችን

ደግሞ መሐል ሸዋ ወቀሳዋንና መሬር ሐዘኑዋን ከረጅም ተራራ ላይ ቁማ ድምፁዋን ከፍ ዘለግ አድርጋ እየጮኸች ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን በግጥም ሙሾዋን እንደዚህ ታሞሻለች ።

ከሁለት መቶ ዘመን የሚበልጥ ለፍቼ ፤
ለዚሁ ምሥክር እኔ መች አጥቼ ፤
ጥንት ያነገሥኋቸው አብዬ ከብስቴ ፡
በስተ ምሥራቅ በኩል አንኰበር ማጀቴ ፡
አሁን ለወደ ፊት ይኸ ነው ምኞቴ ፡
የጉበት (ል) ነጻነት በየወገኖቼ ፡
ቡልጋ ተጕለት ሞረት ይፋት መርሀ ቤቴ ፡
ሥጋዬ ወትሮ አልፆ ቁሜአለሁ ባጥንቴ ፡
ወደ ፀሐይ መግቢያ ለማቅናት አስፍቼ
እስቲ ይታያችሁ ይህ ሁሉ ጥረቴ
ነጻነት ትጡረኝ በዚያችው በርስቴ
ትቤ መሀል ሸዋ የመኩሯ እናቴ
እንዲህ ጨኼ አቤት አቤት ብዬ ጌቶቼ ካልሰሙኝ
ለቅድስት ሥላሴ መሄዴ ነው ይግባኝ

ዓስቤ ኃይሉ ዘብሔረ አንኰበር ፡

ስለ መርሻ ታ፣
የአሽሙር ንግግር መልስ ።

ይድረስ ከክቡር የብርሃንና ሰላም ድሬክቴር ይህ ቃል እንዲታተምልኝ በማክበር እለምናለሁ።ስለ ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያም አገር አስተዳደር ሌባ እንደ ሰለጠነ ዝሆን ገሎ ጕሽ ገሎ ሕዝብ ተሰብስቦ በመጨፈሩ ባለፈው ሳምንት የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ስለ አሳተመው መልስ መርሻ የሚባል የክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያም አሽከር እኔ በጋዜታ ደጃዝማች ሀብተ ማርያምን የሰደብኩ አስመስሎ በአግባ ስሜን ጽፎ የስድብ ጋዜታ ስለ ጻፈብኝ መልስ በትህትና ትንሽ መልስ እሰጣለሁ ።

ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያምን የአገሬን ገዢ እንዳልሰደብኩ ከላይም እግዚአብሔር ከታችም የልዑል ማተሚያ ቤት ድሬክቴር ያውቀዋል ፡፡ ግን እኔ የስድብ መልስ ብሰጥህ ያው አንተኑ መከተል ይሆናል እንጂ ለዘለዓለም ማስታወሻ አድርገህ የምትኖረውን እጽፍልህ ነበር።እኔ ግኔ ለምን እሳደባለሁ ብልግና ይሆንብኛል ስል በማክበር ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እገልጻለሁ ዘአልበ ጽልሁት ውስተ ልበናየ ወአነ ቀናኢ ለኢትዮጵያ ብሔርየ ፊታውራሪ ቀነዓ ፡፡

ፊ ቀነዓ

የከተማ ወሬ ፡ የዘበኞች ትጋት ።

ዓለሙና ተፈሪ የሚባሉ ሽፍቶች ሰው ሲገሉና ሲቀሙ ይኖሩ ነበር፣እነዚሁም ሺፍቶች ሳይታወቅባቸው ቀን ደህና ሰው እየመሰሉ ለሊት ነጋዴ ከሰፈረበት እያሰለሉ ሲቀሙ ነጋዴውም ገንዘቤን አላስቀማም ብሎ ቢበረታባቸው በጥይት እየገደሉ ቢሰንፋላቸው ጭፍሮቻቸውን አስይዘው እጁን ለኋሊት ከዛፍ ላይ አስረው ያለገንዘቡን ቀምተው እንደታሰረ ትተው እየሄዱ በነጋ ጊዜ ጩኸቱን የባላገሩ ሰዎች ሰምተ ው ተሰብስበው በደሉን ሲነግራቸው ከየት አገር የመጣ ሺፍታ ይሆን እያሉ ከታሰረበት ፈተው ነጋዴውም ብዙ ዘመን የደከመበትን ገንዘብ በትርና እስራት አትርፎ በአንድ ቀን አጥቶ ይቀር ነበር ። ያም ነጋዴ ላገረገጋገው መቀማቱን ይጮህና በተቀማበት አገር ያለ ሕዝብ አውጫጭኝ ይውጣ ተብሎ ይታዘዝና ሕዝቡ ሥራ ፈቶ ብዙ ቀን ይጉላላና ይቸገር ነበር ፡ አሁን ግን ባላፈው በሰኔ ወር ውስጥ እነዚሁ ሽፍቶች አቃቂ ነጋዴ ከሰፈረበት ጠመንጃ ተኩሰው ፩ገድለው አንድ አቁስለው ገንዘባቸውን ዘርፈው እውነተኛው አምላክ ሲገልጥ በጭለማ የሆነውን ሁሉ ወደብርሃን ሳያወጣው አይቀርምና ጥቂት እልፍ ብለው በቀሙት ገንዘብ ተጣልተው የገዛ ጓደኛቸውን ንጉርና ዘለቀ የሚባሉትን በሽጉጥ መትተው ሁለቱንም ገደልን ብለው መሳሪያቸውን ይዘው ሄዱ ንጉር የሚባለው ሞቶ ዘለቀ የሚባለው በ፪ ጥይት ቆስሎ ነበረና ከቆሰለበት ስፍራ እየተንፏቀቀ መጥቶ ለከተማ ዘበኛ አሊቃ ለግራዝማች ማህሌ ነግሮ ባወቀበት ቤታቸውን ከፊታውራሪ አብተጊዮርጊስ ሰፈር አሳይቶ ተፈሪና አበበ ጉርሙ የሚባሉትን አሲዞ እነዚሁም ከባሻ ደነቀ ላይ ቀርበው ቢመረመሩ ሽፍታነታቸውን አምነው ከኛ ጋራ የሚሰሩ ብዙ ሰዎች አሉ ብለው ሌሎቹንም ስማቸውን በዝርዝር አጽፈው አስታወቁ እነዚሁንም ሽፍቶች ስማ

ቸውን በሰሙ ጊዜ ግራዝማች ማህሌ የታመኑ ዘበኞቻቸውንና ሌሎችም የምሥጢር ሰላዮች በያሉበት እንዲያዙ በትጋት አዘው ፳፮ ሽፍቶች እስከ ሁለት ቀን ተይዘው እንደፊተኞቹ ልክ ሽፍትነታቸውን አምነው በሽፍትነት የሰሩትን ሥራ ከብዙ በጥቂቱ በቃላቸው ያመኑት ከዚህ ቅጥሎ የተጻፈው ነው አቀማመጣችን በከተማ ሌሊት በየዘመዳችን ቤት ተጠግተን ነው ቀን ቀን ግን ወይዘሮ ጽጌ የሚባሉ ሴትኛ አዳሪ አሉ ጐፈሬአችንን አሳምረን ከሾላው ስር ተሰብስበን ቤታቸው ቅርብ ነውና ብቅ ብለው ሲያዩን ሙሽራ ተቀባይ መስለው ምንጣፍ አንጥፈው ብርሌብርጭቆ ለቀልቁ እያሉ አሽከሮቻቸውን ሲያስቸግሩ ከደጅ እቤት ብቅ ጥልቅ ሲሉ ይቆዩናል እኛም ስጋችንን ለስለት ነፍሳችንን ለእሳት የለወጥንበት ቤታችን እርስታችን ነውና አንተ ቀደም አንተ ቀደም ሳንባባል ተሽቀዳደመን የእኩል ቤታችን ነውና እንደደረስን እንቀመጣለን ከጐጃም ማር ከተጣለው ጠጅ አምጭላቸው ይባላል አራት አራቱን ቀንድበን በአምስተኛው አዝማሪ ጥሩ ይባልና የሰንጎ ምት ይመታል ።

ሰንጎ ሰንጎ ተው ሰንጎ መገን ፡፡
ገበሬ አረሰ ከርሞ ሊበላ ፡፡
ነጋዴ ሚኒ ትርፉን ሊበላ ፡፡
ያለሙ ፈረስ ሳለ ጩልሌው ።
አፍ ተደረሰ ደርሶ እሚቀማው ።
ጨለማ ለብሶ ንጉሥ ሳይሰማው ፡፡

ሲል ከዚያ ለፉከራው ዘበኛ እንዳይሰማን ሹልክ ሹልክ ልክ ብለን ተጠቃቅሰን ከጐድጓዳ ስፍራ ተሰብስበን ተፏክረን ነጋዴ ከሰፈረበት በሰላይ ደርሰን እንደተቻለን ተኩሰን የጫነውን ገንዘቡን የበቅሎ አጋሰሱን መሳሪያ ልብሱን ገፈን ወለኔ የሚባል ያባቶቻችን ግዛት አለ ጣቃውን በቅሎውን ሸጠን ያገኘነውን ገንዘብ ተካፍለን ባ፭ተኛው ቀን አዲስ አበባ ከወይዘሮ ጽጌ ቤት ምንጣፉ እንዳማረ ጠጁ እንደተንቆረቆረ የሚገባ የዘማች ሰላምታችንን አቅርበን በዱቤ የጠጣነውን ጠጅ እንደ ሂሳባችን ተሳስበን የተረፈውን ለወደፊቱ ይሁንልን ብለን የየድርሻችንን ገንዘብ አስረክበን ጠጃችንን እንጠጣለን አለ ፡፡ ደግሞ ነጋዴ ቀማን የሚሉበት ስፍራ ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው አቃቂ መሳፈሻ አዳ ወረዳ ድኩም ከወንዙ መሳፈሻ ቢሾፍቱ ከጨፌው የካ በሾላ በኩል ከመሳፈሻው አራሽ የገበሬውን ቤት አቃጥለን ባለቤቱን ገድለን ዘረፍንበት ያሉት አዳ በአንበ ወረዳ ነው ከዚሁም አዳ የአዶ ገበያ ሹም አቶ አየለ የሚባለውን የሚስቱ ወንድም ይልማ ሻውል የሚባል ጓደኛችን ባባቴ እርስት ተጣልቶኛልና መጥታችሁ ግደሉልኝ ካብታም ነውና ገንዘብ ታገኛላችሁ እኔም ዋጋችሁን እሰጣችኋለሁ ብሎ ለምኖን ይልማም ከኛ ጋራ መሳሪያውን ታጥቆ በወቀው መንገድ እየቀደመ መርቶ ቤቱን አቃጥለን እሱን ሚስቱን አሽከሩን ገድለን ገንዘቡን ዘርፈን ተመለስን አሉ ። ከዚህ በኋላ ይልማ ሲያታልል የኀዘን ልብስ ለብሶ አዳ ከቤቱ ተቀምጦ ኖሮ አቶ ኤፍሬም የሚባል የዘበኞች የ፶ አለቃ አዳ ወርዶ ይልማን ይዞ በ፪ተኛው ቀን ደረሰ የሐገሩ ሰውም ቤቱ በመቃጠሉ ነጋዴ በመዘረፉ በአውጫጭኙ ተጨንቆ ነበርና የከተማ ዘበኞች አዳ ወርደው ሽፍታ በመያዛቸው መንግሥቱን እያመሰገነ በልልታና በደስታ ተቀበላቸው ይባላል ። ይልማም ቢጠየቅ ጓደኞቹ እንደተናገሩት ቃል አመነ ከዚህ በኋላ ከልዑል አልጋ ወራሽ ችሎት ቀርበው ቢጠየቁ መግደል መቀማታቸውን አምነው የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ተቀጡ ።

ነገር ግን ምንም ሰው ኃጢአት ቢሠራ ጊዜ ሞቱ ሲደርስ መጸጸት አይቀርምና እንደኛው ሲሳይ አሻግሬ የሚባለው ወደ ፍርድ ሥፍራ ሲወስዱት ተሰብስበው በግራና በቀኝ የሚያዩትን እያየ ወንድሞቼ ሆይ የኔ አይድረስባችሁ ፤ እኔ የአባት ምክር አልሰማ ብዬ ነው ከእንግዴህ ወዲህ ለሚወለዱ ልጆች በኔ የደረሰውን መከራ ንገሯቸው ። የአባታቸውን ምክር እንዳይንቁ እንዲህ ያለ ፍርድ እንዳይፈረድባቸው እያለ በሚያሳዝን ቃል እየተናገረ ነፍሱ ከሥጋው ወደምትለይበት ሥፍራ ደረሰ ይባላል ። ከነዚሁም የተረፉ ሽፍቶች ከአዲስ አበባ ሸሽተው ወለኔ ከሚባለው ከተማ ተቀምጠዋል ይባላል እነዚሁም በልዑል አልጋ ወራሽ ቃል ተፈልገው እንዲያዙ ለየአገረ ገዢዎቹ ብርቱ ትእዛዝ አልፏል ማለትን ሰምተናል ፡፡ ግን እነዚሁ ሽፍቶች ተይዘው ተቀማን ተዘረፍን የሚሉ ነጋዴዎች የሰላም ጊዜ አግኝተው መንግሥታቸውን አመስግነው እንዲኖሩ ተስፋ እናደርጋለን ፡፡ ይልቁንም በ፫ኛው ዓመት ብርሃንና ሰላም በቁጥር ፳፰ በ፪፻፲፰ ገጽ ስለ ወታደር አስተዳደር አቶ ይግዛው ጐሹ እንደጻፉት ቃል ቢፈጸም እንደዚህ ለተጨነቀው አገር ሁሉ ወስላታና ቀጣፊ ጠፍቶ ሕዝቡ ለመንግሥቱ ዕድሜ ላገሩ ልምላሜ እየለመነ እንዴት ደስታው ይበዛለት ይሆን ስል ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች ባለችን ትንሽ ዕውቀቴ በማክበር አመለክታለሁ ።

በየነ መሸሻ ፡፡

በባቡር መሳፈር ፤

ሐምሌ ፲፯ ቀን ክቡር ብላታ ኅሩይ ወደ ኤውሮጳ የምትሄድ ልጃቸውን ለመሸኘት በባቡር ተሳፈሩ ። ክቡር ብላታ ኅሩይ ሲሳፈሩ ለመሸኘትም ብዙ መኳንንትና ወይዛዝር ተሰብስበው ነበር ። ሐምሌ ፲፱ ቀን ተመልሰው አዲስ አበባ ገቡ ፡፡

የክቡር ሐኪም ወርቅነህ ፤ ወደ ውጭ አገር መሔድ ።

ሐምሌ ፲፰ ቀን ክቡር ሐኪም ወርቅነህ ልጆቻቸውን ይዘው ወደ ኤውሮጳ እንዲሔዱ ተነሡና እርሳቸውን ለመሸኘት ብዙ መኳንንትና ወይዛዝር እባቡር ማረፊያ ድረስ ተሰበሰበ ። ክቡር ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅም አብረው ወደ ውጭ አገር ሔዱ እነሱን ለመሸኘት ደግሞ ብዙ ሰው ከየጣብያው እንዲመለስ አብሮ ተሳፈረ ።

ብርሃንና ሰላም ክቡር ሐኪም ወርቅነህንና ክቡር ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅን ጉዳያቸውን አስፈጽሞ እግዚአብሔር አምላክ በደህና ወዳገራቸው እንዲመልሳቸው ይመኝላቸዋል ። ወደ ትምህርት ቤት የተላኩ ልጆችም አምላክ ትምሕርታቸውን በደህና አስፈጽሞ ላገራቸው ጥቅም እንዲያበቃቸው እንመኝላቸዋለን ፤

የጅ ዝኒት ሰዓት ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሁሉ ሰዓት መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ተሩብ ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፰ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ ።
ም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፲፯ ብር ።
የ በሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር ተሩብ
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፱ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፫ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፲፭ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፴፰ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፳፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፱ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፫ ብር
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፵፬ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፰ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፬ መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፲፫
አንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ ፰፫
ባአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፳፫ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፯ ብር

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ፤የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው ።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ክች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና ኸሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሰ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሂስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

Berliet



ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ አቶሞ ቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚአን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ

ኤን ቤ ኤዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቀውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አዲጋ ወልሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፩
3 me ANNÉE № 31

ሐሙስ ሐምሌ ፳፰ ቀን ፤ ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 4 AOUT 1927

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen , Héritier du trône d' Ethiopie , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ስፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፲፪ገጽ ተከታይ ።

አገርን ለማልማት ነገር ለሕዝቡ መራራትና ማሰልጠን እንዲገባው

የተከፈተ ቤት ቢገኝ ማናቸውም ሰው ገብቶ ከዚያ የተገኘውን ገንዘብ ቢወስድ የሚያስጥለው የለም ይህም እንደዚህ ነው ለዚህ ሁሉ ልክ አብጅቶ በየስራው ጸንቶ ለመኖር ሕዝብን ማንቃት ነበር አገር መውደድ ነው።አገሩን የሚወድ ሰው በሰማያዊ ርስት መኖርን የሚወድ ነው መውደድም በቃል ብቻ አይደለም በተቻለ ስራ ሁሉ ለሕዝብ ጥቅም የሚሆን ስራ ማሰራት አገርንም ለሌላ መንግሥት ከመገዛት ማዳን ነው።ይህነን ያደረገ ሰው ቢሞትም እንዳልሞተ ያህል ነው ስሙ በሐውልትና በደንጊያ ተቀርጾ በደግነት ሲጠራ ይኖራልና ስለዚህ በእውቀት ከሰለጠኑ መንግሥታት ተዋውሎ የስራ ሁሉ መሥሪያና መኪኖች ፋብሪካ ስራውንም ሁሉ በያይነቱ የሚሰሩ ብልሆችና አዋቆች መሐንድሶችም አምጥቶ የእጅ ስራና የመጻሕፍትም ቋንቋ በያይነቱ የሚማሩበት ተማሪ ቤት ከፍቶ በየአውራጃው ማቆም ነው ከ፯ ዓመት ጀምሮ እስከ ፳ እስከ ፳፭ ዓመት የሆናቸውን ልጆች ሁሉ እየሰበሰቡ ትምርትን ሁሉ በያይነቱ ማስተማር ነው በእውቀት ከሰለጠኑ መንግሥታት አገር ያሉ ሰዎችስ በልጅነታቸው እግዚአብሔርን መፍራትና አገራቸውን መውደድ ስለተማሩ አለ ንጉሥ በጉባዔ ምክር እየተስማሙ ሬፑብሊክ የሚባል ስም አውጥተው አገራቸውን ገዝተው የሰው አገርንም ይገዛሉ።ንጉሥ ያላቸውም ዴፑታቲ ምኒስትሬ ሰናቶሬ የሚባሉ ከ፭፻ የሚበዙ ፈላስፎችና አዋቆች ሊቃውንትም አማካሮችም አሉና ተጠንቅቀው ተጠበበው ቃል በቃል እየተረጐሙት ለአገራቸው የሚጠቅም ሕግና ወግ ደንግገው የጻፉትን መጽሐፍ ማኅተማቸውን (ፊርማ) እንዲጽፉለት ወደ ንጉሣቸው ያመጡታል ንጉሣቸውም አንብበው አትመው በዓለም ሁሉ እንዲዘረጋ ወደ ማኅተም ቤት ሰደው ሚልዮኖች መጻሕፍትን ያደርጉታል ሕዝባቸውም ሁሉ ይህንን መጽሐፍ እያየ የመንግሥቱን ምሥጢርና ፍርድ ጣዕምንም ሌላም ሁሉ ያውቃል ከ፲፬፻፶፬ ዓመተ ምሕረት ዠምረው እስከ አሁን ድረስ የኤውሮፓ ነገሥ ታት እያንዳንዳቸው ሠራዊታቸውን ወትሮ ተሰናድተው መጠባበቅ ዠመሩ የጦርንም ሥርዓት እግረኞች ፈረሰኞች መድፈኞችንም መርከበኞችንም በሰልፍ ሥርዓት እንዲታዘዙና እንዲዋጉ አዘዙ ሕዝቡም እውቀትን እየጨመረ ሄደና በ፲፬፻፶፱ ዓ ም የመጻሕፍት ማኅተም የሰውን ልብ ቶሎ የሚገልጽ ተገኘ በ፲፫፻፴፩ ዓ ም የባሩድ ብልሃት ተገኘ በ፲፬፻፺፪ ዓ ም አሜሪካ የምትባል አገር ነቢያት በሱባዔ ሐዋርያትም በስብከት ያልጻፏትን በክርስቶስ ፎሎ ኮሎምቦ ተገለጸች እንዲሁ አውስትራልያም የኤውሮፓ ሕዝብ በዚህ ዘመን ምክር ሠናይ ለኩሉ ዘይገብራ ብለው ከንጉሥ ጋራ እየተማከሩ አክባሮች የተባሉትን አዋቆች ሊቃውንት የሚደነግጉ መርጠው አስቀመጡ አዲስ ሥርዓትን እየጨመሩ አደጉ የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥትንም መታደስ አሰናዱ ሕዝባቸውም ሁሉ በደስታና በጸጥታ አለፍርሃት አለጥርጥርም በዕረፍት እስከ ዛሬ ተቀመጠ በኛ አገር ግን ይህንን ብርሃን ስንኳንስ ባገራችን ሊገኝ መኖሩንና አለመኖሩን ለይቶ የሚያውቀው የለም ነበር ።

በአፄ ምኒልክ ጊዜ ግን ከአውሮፖች እየተዋዋሉ ሥሩልኝ አድርጉልኝ እያሉ ስልክ አዘርግተው ተሌግራፍ ተሌፎንም የምድር ባቡርም ጶስጣም ከርታም ጶስጣልም ቴምብርም ብርም አላድም ሩብም ተሙንም መሐልቅም (ግርሺ) አመጡልን ነገር ግን ይህንን ሁሉ በአድርጉልኝ ስሩልኝ በባዕድ ሕዝብ ነውና የሚሠራው የልመናን ገንዘብ ይመስላል ስለዚህ የሕዝብና የሹማምንቶች ዓይነ ልቡናቸውን ይከፈት እንጂ ይህንን በአድርጉልኝ ስሩልኝ የተጀመረው የቀን ንጋት ነውና የትምርት ቤት አው

ርቶ በየአውራጃው ሁሉ ያሉትን የመንግሥት ተስሩ የሚሆኑትን ሕፃናት አሰብስቦ እንደ አውሮፓ ሥርዓት ቢማሩ እኒህ ያልናቸውን መኪናዎች አምጥቶ ስራ ቢሠራ ተማሮችም ከአውሮፓውያን መምሕሮቻቸው ሰምተው የተማሩበትን ብልሃትና እውቀት ፍልስፍናም ጥበብን የእጅ ሥራን በማኅተም እየታተመ መጻሕፍታቸውን ሰው ሁሉ ዕለት ዕለት ቢሰማው በሀገራችን ያለ የቀን ጨለማ በፀሐይ ብርሃን ይሸሽ ነበር የእኩል ቀን ብርሃንም በሀገራችን ላይ ዘሩኑን ተክሎ ጸላቶቻችንን የነበልባል ቀስቱን ገትሮ ይዋጋልን ነበር ፡፡ ይህ ቢሆን ለንጉሣችንና ለሕዝባችን በኢሳይያስ ቃል የተነገረው ትንቢት ይሆናል መንፈሥህን ለተራብ ብታፈስና ብትራራም የተጨነቀችውንም ነፍስ ብታጸግብ ብርሃንህ በጨለማ ይወጣል ጨለማህም እንደ ቀትር ይሆናል ኢሳይያስ ፶፰ ፲ ።

ስለዚህ ከሁሉ በላይ ፫ቱን ነገር አጥብቆ መያዝ ይገባዋል፤ ፫ቱም እኒህ ናቸው ከሁሉ በላይ አብልጦ እግዚአብሔርን መውደድና መፍራት ነው፡፡እግዚአብሔር ፤ አምላካችሁ እንዳስተማራችሁ ያዘዛት ትእዛዝ ሕግም ፍርድም ይህች ናት እግዚአብሔር አምላክህን ትፈራ ዘንድ ትእዛዙንም ትጠብቅ ዘንድ ዕድሜህና ዘመንህ ይረዝምልህ ዘንድ ስማ ፳ኤል ሆይ እግዚአብሔር አካችን ፩ እግዚአሔር ነው አንተም እግዚአብሔር አምላክህን ውደድ በልብህ ሁሉ በነፍስህ ሁሉ በኃይልህ ሁሉ ኦሪት ዘዳግም ምዕ ፮ ቍጥር ከ፩ ፫ ፪ኛም ባልንጀራን እንደራስ ትክክል አድርጎ መውደድና ማክበር ነው ወንድምህን በልብህ አትጽላውገር ግን ባልንጀራህን ገሥጸው በርሱ ምክንያት ኃጢአት እንዳ ይሆንብህ፡፡አትበቀል ከወገኖችህም ከማንም ቂም አትያዝ ነገር ግን ባልንጀራህን ውደድ እንደራስህ ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ ፲፱ ቍጥር ከ፲፯ ፲፰፡፫ተኛ ከሰውነት ይልቅ አገርን መውደድ ነው ወላጅ እናት ናትና እርሱዋን መንግሥቷንና ባንዲራዋንም ንጉሥዋንም የማይወድ ከዲያብሎስ የከፋ የከረፋ ነውና እሱን ጠላት ማድረግ ነው አለዚያስ ለዘመዱና ላገሩ የማያስብ ከከሐዲ የከፋ አረመኔ ነው ይባላል ለማንም ሰዎች ቢኖሩት አንዳች የሚሹትን የሚበጃቸውንም ባያስብላቸው ይልቁንም ለቤት ሰዎቹ ሁሉ ሃይማኖቱንም የካደ ከሚያምኑትም የከፋ ነው ፩ ጢሞቴ ዎስ ፭ ፰ ።

አ ኢ. ።

ሰላም ብርሃን መሪ ለኢትዮጵያ ፍቅር ።

እነሆ ለአገሩ እንደ ሙሴ ምልክት የሚጥር ብልሐተኛ ብርሃንና ሰላም ብሎ የእውቀትን ምንጭ ለልጆቹ አዘጋጅቶልናል ። አስተዋይና ቅንነት ወደአለበት ሥፍራ ከዚያ የእውቀት ብርሃን ትመነጫለች ። እኛም ኢትዮጵያውን በሞላነው ። በ፩ ልባችን ብርሃኑን እየጠጣን እናታችንም ጸጋዋን ታለብሰናለች ከአባቱም ከዳዊት የተቀበለው ቸር ጠባቂ በኢትዮጵያ ባንዲራ ወሰን ከወሰን በጥበብ ለማስፋት ልጆቹን ለእውቀት እሚያስተውል እውነተኛ የተባለው ነው ። እንደዚሁም ልጆችዋን በእውቀት እየመሠረቱ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም መታሰቢያ እንድትኖርለት የሚጠብቀን ሆኖ ከሰሎሞን ልሳን ለእውነተኞች ጸፋጭ የሆነ ነው ።

፪ተኛ ።

ረቂቁን እውቀት ተቀብለው አገራቸውን እየጠበቁ የሚመክቱ ገር ልቦች በጥበብ ለማልማትና ለማስፋት ለኢትዮጵያ ለትምህርት ትሁቶች የሆኑት ናቸው ። እነዚህ እግዚአብሔርን የፈሩበት አገራቸውን ከልብ ያገለገሉበት ክብራቸው እንደ ቤት ክርስቲያን ዕጣን ጢስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት የቀረበች በዙሯዋም እንደ መላእክት ዜማ የከበረችም ሆና የኢትዮጵያን ብርሃን እየአበበች ታፈራለች ። ለመንሥታቸውም አገልግሎት የሚመኙ ትሁቶችና ትምህርትን ለአገራቸው ልጆች የሚገልጹ ቡሩኮች በጌቶቻቸው ዘንድ እንደ ሰማይ ከዋክብት አሁን አሁን እያደመቁ የኢትዮጵያን ክብር እየመሰረቱ ከዘሩ ናቸው በታች የእውቀት ብርሃን ለማድረስ የሚአቀርቡት ናቸው ። የኢትዮጵያን ክብር በእውቀት ለማስፋት ሁሉም በ፩ነት በጥበብ አውቀው እንዲአገለግሏት ስብሐት ለእግዚአብሔር እየቀደሱ ኢትዮጵያን እሚጠብቋት ናቸው ።

፫ተኛ ።

ኃጢአት መሪ እርግማንን ትጠብቃለች ።

የክፉት ጭንቅላቶች መርዛቸውን ለመትከል በአፋቸው አዛኝ እረዳትም እንደመሆን እየተነፈሱ ለሰውም ፊት ሲያዩ አንገታው እንደመነዠሴ መልክ ለብሰው በአፋቸው የሚአስቱ ናቸው ። ልባቸውን ግን በዕባብ ገለባ ታብቀው እንደይሁዳ ለመሣም እየፈጠኑ የሚቸኩሉ ናቸው ። ጥቅም እየጣመቻቸው ራሳቸውን ቀና ቀና እያሉ የመርዝ መንገድ እየዘሩ ለተንኮል የሚደፍጡ ናቸው የርግቦችንም ፍሬ እያረገፉ በብርሃን እናዳይሺቱ በተንኮለኞች ልጓም ተይዘው በአየዳረው መከከል ወድቀው ወደላይ እያንጋጠጡ ከተንኮለኞች የሚሰውራቸውን ይለምናሉ ። የክፉተኞችም የሐሰት መንገድ እየጠቀመቻቸው እንደውቀት የሚቆጥሩት ናቸው ። እነዚያ ጥቅማቸውን ለብሰው በገዛ ሰውነታቸው እየተልከሰከሱ የክርዳዱን ፍሬ እየዘሩ የሚያመርቱት ናቸው ።

ለሃገሩ የሚደክመው ሁሉ።ለጥቅማቸው ከሚአስቱት ተንኮለኞች እፍ መሬቅ ነው ።

፬ኛ ፤

ለሰው እሚያስፈልገው የሥጋችንን ሞት አለመፍራት ነው

መፍራት የእግዚአብሔርን ቍጣ ነው እንጂ ።

መፍራት ክፋትንና የነፋሳችንን ጥፋት ነው እንጂ ።

መፍራት ማታለልንና የኃጢአትን ምንጭ መከተል ነው እንጂ ።

መፍራት ወግን መሺጥና የገሃንመ እሳትን ለቅሶ ነው እንጂ ለገንዘብ ፍቅር ሲሉ ሕግን ለገበያ ለውጠ በኃጢአት መከናነብ የይሁዳን ክረጢት አቅፈው የሚማፀኑበት ናቸው ። ንጹሕነትንና የዋህነትን በመፍራታቸው ንብረታቸው ለገንዘብ ሺጠው በገንዘብ ሲመኩ ወደ ሺመቱበት ጠማማ ቍልቍለት በዲያብሎስ እጅ በሰሩበት ኃጢአት መቅረት አለባቸው ።

፫ኛ

ተንኮል ። በልባቸው እየጻፈች የእባቦች እሾህ አጥምደው እያዘነጉ በስውር ይመነጥቃሉ ። ፈጽመው ለማጥፋት እስኪጨርሱ ድረስ ለማታለልና ለማውደም የእግዚአብሔርን ቁጣ እስኪቀበሉ ማንገስ ይተዋሉ ደብርዳሉስ ተብሎ አይባልም ። በዚህም በዚያም ደጃፎችን ዘግተው እሙኖችን አድክመው መረባቸውን ለቀቅ ለቀቅ እያደረጉ ስልቻቻቸውን እያሰሩ እንደ አረሀ ሼንበቆ በመለመጥ ዳንኬራቸውን ይረግጣሉ በጥጋብ ገንፍለው ለሚስሩት ተንኮል የሚአጨበጭቡት ናቸው ። ክንዳቸውንም ዘርግተው ከብረት ኃይል አጠንክረው የአድማቸው ብዛት እየሰነዘሩ በየክፍሉ አንድ አምሣል ሆነው እንደ ድርና ማግ ተግባብተው ከሩቅ እየተጠቃቀሱ እንደ ባቢሎን ጊዜ ሰዎች እየአመሳቀሉ ያምቧቸው ጀመር እንደአሣ ጂራት በተገኙበት ተንኮል ለመያዝ የሚሟልጡት ናቸው ።

፬ኛ ።

ዓመፃን ተሸክመው እሁድ እሁድም እንዳይሁዳ ለቅስፈት ስንዴውንና ወይኑን ለሰው ይምሰል ሲሉ ለመቀበል የሚቀድመው ሁሉ የስይጣንን በር ለመክፈት ኃጢአት ጠማምነታቸው አፍጥና ወደሳት ለቅሶ ትመራቸዋለች ። ሼንጋዮች አታላዮች ምልክተኞች ስለሆኑ አንድም ሰው በስራቸው ዓመፃ አይስታቸውም ።

ወዮላቸው ሥጋ በሥጋቸው በመንዝር ተስማምተው እንደሰዶም እርኩሳትን ያጸኑ በኃጢአት መከናነብ ተዘጋጅተው የእግዚአብሔርን ቍጣ እርግማን የሚጠብቁት ናቸው ሰኔ ፳ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም

ታደሠ ኃይለ ሚካኤል

ማድነቅ ።

ብዙ ጊዜ ለምክርና ለተግሣጽ ለመንፈሳዊና ለሥጋዊ ትምሕርት እንዲሆነን የተጻፈውን እያነበብን ጉድ ነው ግሩም ነው እያልን እናዳንቃለን ይልቁንም በ፳፱ና ፴ ቁጥር ብርሃንና ሰላም አቶ ዓስበ የጻፉትን ቃላት አንብበው ብዙ ሰዎች ሲያደንቁና የሃሳቡን አካሄድ ሲያመሰግኑ ሰምተናል ፤ እውነትም ያገሩን ጉዳት ተመልክተው ላገር ጉዳት የሚሆነውን ነገር ሁሉ እንደቀር ገልጠው በመናገራቸው ሊመሰገኑ ይገባቸዋል ፤ ላገር በረከትና ጥቅም ሊሆን ያመለከቱት ሁሉ ቢፈጸም መልካም ነው ፤ ነገር ግን ከዚህ በፊት እንደሰማነውና እንዳየነው በማድነቅና በመገረም ነገሩ ቢያልፍ ተነግሮ እንዳልተነገረ ተሰምቶ እንዳልተሰማ ታውቆ እንልተደረገ ባክኖ ቢቀር በሽቱ ጊዜ አመዳይ እንደነካው ስንዴ አለ ፍሬና አለ ትርፍ ሆኖ መቅረቱ አይጠረጠርም ፤ ከቡራን አንባቢዎች ሆይ ይኸነን ሁሉ ነገር ላላገኘውና ትንሽ መስማት (ማንስ)ለሌላው ሰው ቢነግሩት ምንም አይገባውም አያስተውለም እንጂ እንዴት ተጠዋሬ ጠዋሪውን እንዲህ ሲሆን ዝምብሎ ያስተውለዋል ? የሚጫነው አህያና የሚጭነው ገበር በከንቱ ሲጠፉ አስጫኝና በላተኛው አለማስታዋሉ አጥልቶ ላየው ሰው ከባትና እናት ሞትይህ እንዲያሳዝን ጥርጣሬ የለበትም ፤ በሌላ አገርና ዓለም የሚሞተው ምክንያቱ ምን እንደሆን የገደለው እስከ ማይታጠቅ ቀርቶ ሰውን ያህል ያውም እንደእጅና እንደ እግር አገሌና አገሊት ምነው አይወልዱ ይህ አገርና መንደርሣ ምነው አይፋፋ ምክንያቱ ምንድነው ተብሎ ይመረመራል፣ምርመራውም ምክንያቱ እስኪገኝ እስኪታወቅ ድረስ ነው።ሰው ቀርቶ የሚያርሰው በሬና የምትታለበው የምትረባውም ላም በግና ፍየል በከንቱ አለ እውቀትና ብልሃት አይታረዱም አይሞቱም እንዲሁም ዛፍና ቅጠላ ቅጠል የሚረባውና የሚጠቀመው እንዲያው በከንቱ አይቆረጡም ተጠዋሪ ጠዋሪውን አለመውደዱ ለጁና ለእግሩ አለማሰቡና ሆድ ለሆዱ አለመንሰፍሰፉ በጣም ይገርማል ስለ ዚህ የሆድ ነገር ሆድ ይበላል የተባለ ተረት ከዚህ ላይ ከንቱ ሆኖ ታየኝ እግዚአብሔርም ለእስራኤል እንዲህ ይላል የጠላትህን አህያ ከጭነቱ በታች ወድቆ ብታገኘው ትተኸው አትሂድ ዋ የራሳችንን ወንድምና ወዳጅ ከብትም እንዲህ ስናደርገው ያየ ምን ይለን ይሆን?እስካሁን ድረስ በተሰራው ሁሉ ካሁን በፊት አስታዋሽና መልክተኛ ስላልነበረ ሆነ፡፡ለወደፊቱ ቢሆን ግን ሳይጀመር የተፈጸመ ነገር የለምና ብርሃንና ሰላም ተላላኪና አስታዋሽ ሆኖ እግዚአብሔር ደግሞ ዕድሜና ጤንነት ለንግሥተ ነገሥታታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን ሰጥቶ የተጀመረ ሊፈጸምልን የተረሳ ሊታወስልን የጐደለ ሁሉ እንዲሞላልን ቀድሞ ከነበረ ጉዳታችን የሚመጣ ጥቅማችን እንዲበዛና እንዲትረፈረፍ ተስፋ አደርጋለሁ ፤

ዋስ ይሁን ንጉሤ፡

የተሻለውን መንገድ ስለ መያዝ ።

ግራዝማች ድንቁርና የሚባሉ የጥንት ባላባት ወይዘሮ ድርቅናን ተወላጅ አግብተው ብዙ ልጆች ወልደው አፋጁ በሚባል ከተማ ይቀመጡ ነበር የልጆቹም ስም ከዚህ ቀጥሉ እንደ ተጻፈው ነው ። ትዕቢት ቅንዓት ምቀኝነት ሐሰት ሐኬት ስስት ናቸው ። ትዕቢትና ቅንዓት ጌታ አዳር ሂደው በወታደር ደምብ አገር ላይ ተሰርተው ጭዋ ሁነው ተቀምጠዋል ምቀኝነትም ለማዳ አውሬ ነውና ሰዎችን በሥውር እየነጠቀ ይወስዳል ሕዝቅኤል ፲፱ ፯ ። ሐሰትም ጠማማ ነውና መንደር ለመንደር እየዘረ ፀብ ይዘራል ምሳሌ ፮ ፲፬ ። ሐኬትና ስስትም ግብዞች በዘንተኞች ናቸውና ካፋፍ ላይ ተቀምጠው የበረታውን እናሳልፍ የደከመውን እናሳርፍ እያሉ ወደ ሥልጣኔ የሚተላለፋትን ሰዎች አስቸግረዋል ማቴ ፳፫ ፲፫ ። ለነዚህ ስድስት ወንድማማች ሎሌ ሁኜ ሳገለግላቸው የምኖር እኔ ነኝና ችግር የሚባል ድርጎ አውጥተውልኝ አንድ ቀንስ እንኳ ጐድሎብኝ አያውቅም እንዲህ ሁኜ ብዙ ዘመን ስኖር ከዕለታት አንድ ቀን እግረ መንገዴን ሳልፍ ትሕትና ፍቅር የሚባሉ ደጋግ ሰዎች ብርሃንና ሰላም ዘርግተው ሲያነቡ አገኘኋቸው ፤ ቃሉም ከሁለተኛ ዓመት ቍጥር ፫ አቶ መክብብ ደስታ የጻፉት ቃል ነው ። ማለት ወዳጅ የተባለ ፈጣሪና ሃይማኖት መንግሥትና ሕዝብ ነው፤ወጽመድ የተባለ ድንቍርና ነው መንግሥት ሲፋቀር አንድነት ይገኛል ኃይል ይበረታል ፍቅር ሲቀዘቅዝ አንድነትም አይገኝ ወጽመዱም አይለቅ ከሚል ሲደርሱ ወንድሞቼ ሆይ ዝግ አርጋችሁ እስቲ ደጋግሙት እንዲህ ያለውን ቃል ሰምቶ አላውቅም አልኳቸውና እነሱም ዝግ አርገው

ቢደጋግሙት ነገሩ ደነቀኝና ሳወጣ ሳወርድ—ድንገት ብርሃን ከሰማይ በራ በሰውነቱ ላይም ወደቀ ድምፅም ሰማሁ ስፈራ ስንቀጠቀጥ አንተ ማነህ አልኩት ፡ ፅንባቆም ፫ ፬ አንተ የም ታባርረኝ እኔ ቅንነት ነኝ ስሜም ብርሃንና ሰላም ይባላል አለኝ አቤቱ ምን ትሻለህ አደርግ ዘንድ አልኩት ፡ ብርሃንና ሰላምም ተነሣ ወደ አዲስ ዓለም ከተማ ሂድ ከዚያም ትሰማለህ ታደ ርገው ዘንድ የሚገባህን አለኝ ፡ ከኔ ጋር የነበሩ ሰዎች ግን ተደነቁ ከድንጋጤ የተነሣ ዓይኔ አያይም ነበርና ወደ አዲስ ዓ ለም ከተማ መርተው አገቡኝ ወይመርሆ ፍኖተ እንተ ኀረየ ነፍሱሂ ውስተ ሠናይ ተኀድር ። ወዲያውም እከተማው እን ደ ገባሁ ከዓይኔ እንደ ቅርፍት ያለ ወደቀልኝና አየሁ ። ወተ ሥዕአ እምአዕይንቲሁ ከመ ዘማሬት ወርእየ ሶቤሃ ፤ ከዚህ በኋላ ከጌታየ አእምሮ ተምሬ ለክህነት በቃሁና የሥጋየ ቍራጭ ያጥንቴ ፍላጭ ኢትዮጵያዊ ጳጳስ ባርኮ እስኪ ሰጠኝ ድረስ በተስፋ እጠብቃለሁ ፡ ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ባልተ ከናወነ እውቀቴ ጽፌዋለሁና የተማማተ ቃል ቢገኝበት ይቅር ታችሁን እለምናለሁ ።

መወድስ ። አበ ሕዋሳት አዳም ሕሊና ዚአየ ።
ዘይትዓፀፍ ዘልፈ ዓፅፈ አእምሮ ብርሃናዊ ።
በሰሚዓ ምክሩ ጠዋይ ለፀላዒ ሠናይ አርዌ ።
ተዓርቀ እምዓጽፈ አእምሮ ወለብሰ ድንፃዌ ።
ወአኀዘ እምአሜሃ ወንጌለ መከራ ኀዘነ ከመ ይስብክ በጽማዌ ።
አመ ወጽአሂ በእድሜሁ ትእዛዘ ቄሣር ምንዛዌ ፡፡
ድንግለ ምኒልክ ኢትዮጵያ ብርሃንና ሰላም ሰማያዌ ።
በድንግልና ወለደት ከመ ይኩኖ ቤዛዌ ።
ለአዳም ሕሊናየ ዘኮነ መሬታዌ ። በላይ ሃጐስ አድዋ ።

ክቡራን የኢትዮጵያ አገረ ገዢዎች ሆይ

ካንድ ወር ተኩል በፊት ፉሪ በሚባለው አገር አንዲት የግሪክ ሴት ያገባ የእንግሊዝ ዜጋ አንድ የሣር ጎጆው ቢቃጠ ልበት ካይሮን በሚባል በወሬ ወረቀት በፈረንጅ ቁጥር ፲፰ ሜይ (ግንቦት) ፲፱፻፳፯ ዓመት የራይተር የስልክ ቃል በዓለ ም ሁሉ በወሬ ወረቀት ታትሞ ታየ ቃሉም ይህ ነው ።

የስልክ ቃል ትርጓሜ

ጆሩናል ካይሮን ፲፰ ሜይ ፲፱፻፳፯ ዓመት

የራይተር የስልክ ቃል

ከሕዝብ መማክርት ቤት ሚስተር ኤሊስ ዲቪስ ። የእን ግሊዝ ዜጋ በሀበሻ የሚኖር አብን የሚባል ወምበዴ ጥሎበት ጥል አንሽውን መንግሥት አለመቅጣቱን አስታወቀ ፤ የውጭ ጉዳይ ምኒስትር እንዲህ ሲሉ መለሱ ። መላልሰውም ሥርዓት ቢፈልጉ ፍሬ ያጡበት ሁኖ የእንግሊዝን ዜጋ አጥፊዎች ወ ምበዴዎች በተገለጠ ጥግ ሁነው በሀበሻ እየኖሩ የብርታንያ መንግሥት ነገሩን በትልቅ ንቃቱ ተከትሎ ከሚገባ ፍርድ ለ መድረስ የሚያስፈልገውን ልክ ያበጃል። በሀገራችን ተረት ጌታ እንደ ነገሩት በቅሎ እንዳሠገሩት እንደሚሉ ። በዓለም ቃላቸ ው የተደመጠ ካያት ከቅድም አያታቸው የተከበሩ የታላቅ ብርታንያ የውጭ ጉዳይ ምኒስቴር ወሬ ቢሰሙ እውነት መስ ኋቸው ለኛ ውርደት ለወዳጆቻችን ኃፍረት የሚሆን ቃል በዓ ለም ሁሉ አሰሙ ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ከጥንት ጀምሮ እስከሁን የአብር ሃም ልጅ መሆኑ ሊታወቅ የመጣውን ሁሉ እንግዳ በፍቅር መቀ በል ልማዱ ነው ። ይልቁንም ከሕዝብ ማህበር ከገባን ወዲህ እንኳን የውጭ አገር ሰዎች እነሱን ተጠግተው የመጡ ያገ ራችን ሰዎች የማይገባ ቢሰሩ ስለነሱ ፍቅር ብለው ይታገሱዋ ቸዋል ። በሥርዓትና በዘበኛ ብርታት የተጠበቀው ሌላው አገር እንኳ ከዓለም ጦርነት ወዲህ ሽፍታና ወምበዴ ሰልጥኖበታል ። በኛም አገር ቤት የሚቃጠልበት ምክንያቱ ብዙ ነው ።

አንዱ ከቤተ ሰብ ነው ። መብራት ሲያበሩ እንጀራ ሲጋ ገር ወጥ ሲሰራ ። ሁለተኛ ሐጂ አህመድ የሚባል ዓረብ ከጃን ሆይ ስሳ ሺ ብር ተበድሮ የሚከፍለው ቢያጣ ቤቱን አቃጥሎ ገንዘቤም መዝገቤም ተቃጠለብኝ አድራጊውን አውጡልኝ አለ ።

ሶስተኛ በጋለሞታ ሴት የተገናኘ ሰው እስዋን ያገባውን ሰው ቤት ስለ ቅንዓት ያቃጥላል ።

አራተኛ ወዳጅ ከወዳጁ እንዲቀያየም ተንኮለኛ በወርቅ እየተገዛ ቤት ያቃጥላል እንዲህ እንዲህ ያለውን በደለኛ ከተ ገኘለት የኢትዮጵያ መንግሥት እየመረመረ ለመቅጣት ይጥራል። ክንቲባ ገብሩ ።

Honorables Gouverneurs de, Provinces Ethiopienne

Il y a environ un mois et demi ,un ressortis- sant britannique du nom de OWEN ,habitant á Fouri et marié à une femme de nationalité grecque avait eu sa toucoule incendieé. Cette nouvelle a été pu bliée par le journal "KAIRON" en date du 18 mai 1927 à la suite dúne communication des télégrammes Reuter et a parue ensuite dans toute la presse mondiale.

Le texte était ainsi conçu :

Traduxtion du Télégramme.

Journal KAIRON 18 mai 1927

Télégramme Reuter.

" A la chambre des Communes Mr. Ellis Davies attira l'attention sur l'attaque dirigée par des brigan ds contre le sujet britannique OWEN ,domicilié en Abyssinie et dont les coupables n'auraient pas été punis par le Gouvernement.

En réponse le Ministre des Affaires Etrangères déclara que des démarches répetées ont été faites en faveur de Mr; OWEN et n'ont eu aucun résultat et que le Gouvernement Britannique suit avec gran de attention l'asile visible dont joussent en Abys- sinie les assassins dé sujets britanniques et qu'il ne manquera pas de prendre les mesures nécessaires pour obtenir justice.

Il y a chez nous un proverbe qui dit: " Le mulet trotte de la manière dont on le fait trotter et le maitre agit suivant ce qu'on lui dit.

Honorable depuis ses ancêtres et dont les paroles ont de l'estime dans le monde ,le ministre des Affaires Etrangères de la Grande Bretagne, 'sur la base de racontars 'a cependant fait entendre dans le monde entier des paroles deshonorantes pour nous et qui sont de nature à porter ombrage à nous amis.

Le Peuple Ethiopien digne de son Père ABREHAM a' depuis les temps les plus reculés .réserve son accuil cordial et hospitalier à tous les étrangers arrivant dans son pays.

Depuis que nous faisons partie de la Société des Nations et bien avont déja ,non seulement les étrangers, mais aussi les gens de notre race, jouissant de la protection étrangère sont traités amica lement et avec indulgence lors même qu,ils commettent des fautes.

Depuis la Grande Guerre ,les voleurs et les ban dits ont pu augmenter le nombre de leurs mauvai ses actions .même dans des pays où la police, grâce à son organisation complète est à même de faire régner un ordre parfait.

Chez nous, les incendies proviennent de causes noumbreuses et différentes.

1°. Par les ménages. En allumant les lampes, ,en préparant les aliments ,la cuisine.

2°. A titre d'exemple. Un arabe du nom de Hadji AHMED avait emprunté une somme-de 60.000 Thalers au Trésor de l'Empereur. Se voyant dans l'impossibilité de rembourser ,il incendia sa maison et demanda la recherche du coupable disant que ses documents et son argent avaient été détruits.

3°. Des personnes qui se querellent pour des raisons d'ordre passionnel. Si une femme se marie avec l'un ,le prétendant évincé par jalousie va mettre le feu à la maisson.

4°. Parfois aussi des malfaiteurs achetés avec de l'argent incendient des maisons pour semer la discorde entre des amis.

Le Gouvernement Ethiopien dans chaque cas porté à sa connaissance a toujours fait tout ce qui était nécessaire pour parvenir à l'arrestation des coupables et des punitions très sévères ont toujours été infligées à ceux dont la culpabilité a été démontrée par l'enquête

Cantiba GABROU

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ።

የኢትዮጵያ መታደስና የሥልጣኔ ደረጃ መውጣት።

ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ፡ ከነገሡና ልዑል ተፈሪ መኰንን አልጋ ወራሽና እንደራሴ ከሆኑ ጀምሮ እስከሁን ድረስ በየጊዜው የቀድሞው አሮጌ ልማድ ባዲሱ በአውሮጳ ልማድ እየታደሰ መሔዱን የኢትዮጵያ ወዳጆች የሆኑ ሁሉ ያለ ጥርጥር ይናገራሉ ። ምናልባት የኢትዮጵያን መታደስ በፋቸው ለመናገር የማይወዱ አንዳንድ ሰዎች ቢኖሩ እንኳ በልባቸው እንዳወቁትና እንደ ተረዱት ጥርጥር የለበትም ። ይልቁንም ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አውሮጳን ጎብኝተው ከተመለሱ ወዲህ ብዙ ነገር እንደ ታደሰ አስተዋይ ልብ ያለው ሰው ሁሉ ይመሰክራል ።

አሁን ባለፈው በሰኔ ወር እንኳ ለኢትዮጵያ ወዳጆች እጅግ ደስ የሚያሰኝ፤ መንግሥታችንን የሚያስመሰግንና ሕዝቡን የሚጠቅም በተለየ የወንጀለኞች ቅጣት ፍርድ ቤት ከነ ደንቡ አቍመው ለዚሁ የሚሆኑ ዳኞች መምረጣቸውና ደንብ መስጠታቸው ኢትዮጵያ አንድ የሥልጣኔ ደረጃ መውጣትዋን ያስረዳናል ።

ለዚሁም ፍርድ ቤት ከተሰጠው ደንብ ውስጥ ፍሬ ነገሩን ብቻ ባጭሩ አውጥተን ለኢትዮጵያ ወዳጆች ሁሉ እናስረዳለን ።

በዚህ ፍርድ ቤት ለፍርድና ለምርምር የሚቀርቡ ወንጀለኞች ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ናቸው ።

፩ኛ ፤ ነፍስ ገዳይ ። ሽፍታ ወንበዴ ። ሌባ ። በንጉሡና በመንግሥቱ ላይ ክፉ ሥራ የሚሠራ የመንግሥቱን ሥራና ገንዘብ በድፍረት የሚያጠፋ ለዳኛ ወይም ለአለቃው የማይታዘዝ እምቢተኛ አዋጅ አፍራሽ። ቤት አቃጣይ በተንኮል ሌላ ሰው የሚጠፋበትን ሥራ የሚሠራ ነው ።

ከዚህ በላይ ከተቆጠረው ወንጀል በቀር ማንም ሰው ቢሆን ዋስ ቢያገኝ ዋስ ጠርቶ ፥ ዋስ ባያገኝ ርስቱን ቤቱን እንደ ዋስ አድርጎ ነገሩን ይነጋገራል እንጂ እጁ ተይዞ ወደ ቅጣት ፍርድ ቤት አይቀርብም ።

፪ኛ ፡ ማንም ሰው ቢሆን በማይገባ የታሠረ እንደ ሆነ በማይገባ መታሠሩ ተመርምሮ ከታወቀ በኋላ ካሣ ይቀበላል ።

፫ኛ ፡ ቅጣቱ በገንዘብ መክፈል የሆነ ወንጀለኛ እስቲፈ ረድበት ድረስ የታሠረበት ቀን ሁሉ ተቆጥሮ ከገንዘቡ ይገ ድልለታል ። በእሥራትም የሚቀጣ የሆነ እንደ ሆነ እጁ ከተ ያዘበት ቀን ጀምሮ እስኪፈረድበት ድረስ የነበረው ቀን ከቅ ጣቱ ቀን ውስጥ ገብቶ ይቆጠርለታል ።

፬ኛ ፡ ምስክሮች ወይም በጽሕፈት የሆነ ነገር ከሩቅ አገር እስቲመጣ የሚቆይ ነገር ካልሆነ በቀር ወንጀለኛው ወደ ቅጣት ፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ እስከ ፲፭ቀን ፍርዱን ይቀበላል ።

፭ኛ ፡ የመታሠር ቅጣት የሚፈረድበት ወንጀለኛ የሚታ ሠርበት የወሩ ልክ ተቆርጦ ከሶስት ላይ በትክክል ተጽፎ አ- ንዱ በወንጀል ቅጣት ፍርድ ቤት ። ሁለተኛው በወንጀለኛው ወይም በዘመዶቹ እጅ ። ሶስተኛው በሚታሠርበት ሹም እጅ ይቀመጣል ። ቀኑም ሲደርስ ተፈትቶ ይለቀቃል ። ከተቆረጠው ቀን በላይ ታሥሮ የተቀመጠ እንደ ሆነ ካሣ ይቀበላል ።

፮ኛ ፡ በዚህ በወንጀል ቅጣት ፍርድ ቤት የሚፈርዱ ዳ ኞች በእስራት የሆነ እንደ ሆነ ካንድ ወር እስከ ፯ ወር በገን ዘብ የሆነ እንደ ሆነ ካሥር ብር እስከ መቶ ብር ቅጣት ለመ ፍረድ ተፈቅዶላቸዋል ።

ከዚህ በላይ ቅጣት የሚፈረድበት ወንጀለኛ የተገኘ እን ደ ሆነ ግን ነገሩን እስከ መጨረሻው መርምረው የመረመሩ በትን መዝገብ ጨምረው ወደ ችሎት እያቀረቡ የሚገባ ቅጣት ይፈረድበታል ።

ነፍስ ገዳይም ቢሆን ነገሩን ሁሉ እስከ ሚቻላቸው መር ምረው የመረመሩበትን መዝገብ ጨምረው ለፍርድ ወደ ች ሎት ያቀርባሉ ።

የቀረውም የቅጣት ፍርድ ቤት ደንብ በዝርር ተጽፎ ለዳኞቹ መሰጠቱን ሰምተናል ።

፯ኛ ፡ ዳኞቹም አሁን ለጊዜው አምስት ስለ ሆኑ ፍርዱ የሚረጋው በበለጡት ወገን ነው እንጂ አራቱ የተስማሙበ ትን አንዱ ሊያፈርሰው ። ሶስቱም የተስማሙበትን ሁለቱ ሊያ ፈርሱት አይችሉም ።

፰ኛ ፡ በየወሩ መጨረሻ ቅጣት የተፈረደባቸውን የወንጀ ለኞችን ቁጥር በዝርዝርና በድምር ስማቸውንና የወንጀላቸውን ዓይነት ባጭሩ እየጻፉ ለልዑል አልጋ ወራሽ ያስታውቃሉ ።

ኢትዮጵያ አገራችን ይህን የሥልጣኔ ደረጃ ስትወጣ በዓይናችን ለማየት ላበቃን ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቀር ባለን ።

ስለ ሕዝብና መንግሥት አስተዳደር ደንብ ማሻሻል ።

ካሁን ቀደም ብዙ የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ለገበሬ ያመት ግብር ቢቀልለት ለነጋዴ መንገድ ቢበርግለት ግምሩክም ቢሠ ራለት ለካህን ለወታደርም ሌላ የተሻለ ደንብ ቢቆምለት መን ግሥታችን ብርቱ የተፈራ ሕዝባችን የተከበረ ባለጸጋ አገራችን ለምለም የጠዳ በሆነልን ነበር ብለው በጣም በሚመሰገን አጻጻፍ ጽፈዋል እውነትም ከመት ወዳመት የጐደለውን እየሞሉ የጠመ መውን እያቀኑ የሕዝብና መንግሥት አስተዳደር ደንብ ቢያሻ ሽሉት ለሕዝብ እንዲረዳና ለመንግሥት እንዲጠቅም ጥርጥር የለበትም፡ስለሆነ ግን የሕዝብና መንግሥት አስተዳደር ደንብ ካ ደፈውና ልፍትፍት ብሎ ከተበላሸው ወረቀት ወደሌላ የሰው እጅ ወዳልነካው ንጹሕ ወረቀት አዛውረው እንደሚያሳድሱት ልክ እነዚያ ደንቡን የሚያስተካክሉ ሰዎችም በዚያው መጠን የያንዳ ንዳቸውን ልብ ከጠማማ ወደቅንነት ከክፋት ወደየዋህነት ከተን ኰል ወደገርነት ከጭከና ወደርህራሄ ካልመለሱት ያነን ደንብ ሺ ጊዜ እንኳ ሲገለባብጡት ቢውሉ ገና እነሱ አዲስ ባሕርይ ለብሰው አልታደሱምና ስለክፋታቸው ምክንያት በሰው ደም የተነከረ ልብስ ለብሰው ያቀኑትን ደንብ ሕዝብና መንግሥት ሊረዳ አይችልም ብዬ ለመጻፍ እደፍራለሁ ። ነገር ግን እነሱ ራሳቸው አፍአዊ ጠባያቸው ያይደለ ውሣጣዊ ሕሊናቸውን ቀድ ሰው ከፉ ሠርተውብናል ከፉ እንስራባቸው ሳይሉ በንጹሕ ልብ በቅንነት ያስተካከሉት እንደሆን እነሱን በሰላም አሳልፎ ልጆ ቻቸውንና የልጅ ልጆቻቸውን ሁከት አልባ በጸጥታ ያሳልፍላ ቸዋል ።

ፍሥሐ ወልደ ሚካኤል ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ያዲስ አበባ የእህል ገባያ ።

የበጋ ሸመታ ።

፩ ዳውላ (ሰማንያ ኪሎ)		ስንዴ	፭ ብር
፩ ,,		ገብስ	፬ ብርታላድ
፩ ,,		ጤፍ	፯ ብር

ያሁን ሸመታ

፩ ,,		ስንዴ	፲፩ ብር
፩ ,,		ጤፍ	፲፭ ብር
፩ ,,		ገብስ	፳ ብር

፻ ኪሎ	የስንዴ	ዱቄት	፩ኛ	፳፰ ብር
፻ ,,	,,	,,	፪ኛ	፳፯ ብር
፻ ,,	,,	,,	፫ኛ	፳፫ ብር
፻ ,,	,,	,,	፬ኛ	፳፭ ብር
፻ ,,	,,	,,	፭ኛ	፲፩ ብር

በባቡር መሳፈር ።

ሐምሌ ፳፬ቀን ክቡር ደጃዝማች ብሩ ወደ ፓሪስ ለመሔድ በባቡር ተሳፈሩ።ክቡር ደጃዝማች ብሩ የብርሃንና ሰላም ወዳጅ ሲነሱ ለመሸኘት ብዙ መኳንንትና ሠራዊት እባቡሩ ማረፊያ ድረስ ተሰብስቦ ነበረ። ክቡር ደጃዝማች ብሩ ከሔዱበት አገር ወደአገራቸው በደህና እንዲመለሱ እንመኝላቸዋለን ።

ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ያገር ግዛት ሚኒስትር ወደ አሩሲ ወደ ግዛታቸው ለመሔድ ሐምሌ ፳፬ቀን በባቡር ተሳፈሩ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሁሉ ሰዓት መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ።
ምን	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፭ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፭ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፭ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፴፱ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፳፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፲ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፯ ብር
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፵፬ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፰ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፬ መ

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፲፭
አንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ ፱
ባንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፺ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፭ ብር

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ራግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው።

ራግቢ

RUGBY

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልክም ብርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻው ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

COGNAC SaE&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬምርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

Berliet



ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቀኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ አቶሞ ቢልና በእንጨት የሚሄድ ከሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ኤን ቤ ኔዳሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጆጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ብርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ እምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ። የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤኔስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፪
3 me ANNÉE № 32

ሐሙስ ነሐሴ ፰ ቀን ፤ ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 14 AOUT 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadairé paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።	የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ደከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ደሸጣል ።	Abonnements Ethiopie: Un an 5 Thalers Etranger: Un an 7 Thalers le numero 2 piastres

ዓመፃን አርቆ ጥበብን ስለ መቀበል ።

ኢትዮጵያ ከልጆቿ አለመስማማት የተነሣ ረዳት በማጣቷ የጥበብ ረኃብተኛ ሆና ትኖር ነበር ፡ ምንም እንኳን ቢሆን የተራብ ሳይበላ ፡ የታረዘ ሳይለብስ እንደማይቀር ሁሉ የልጆችዋ በፍቅር መተሣሰር ዕውቀት የፍቅር ፍቅርም የዕውቀት እንደ ሆነ ሁሉ መሪአቸውን ልዑልን አድርገው እናታቸውን በዕውቀት ያጐናጽፏታል የማለት ሙሉ ተስፋ አለኝ ። ይኸንንም ያስረዳኝ የብርሃንና ሰላም ወንድማማቾች የሚሻልን ለመፈለግ የጻፉት ቃል ነው ፡ ከጭለማ ብርሃን ከጠብ ሰላም እንደሚሻል እናውቃለን አድርገነው ባናውቅ እንኳን ስለዚህ ወንድሞቼ ከ ጻፉት የሚሻለውን እየተቀበልን በብርሃንና በሰላም እንኑር ።

አንዲት ትንሽ ተረት ፍቅር ስለሌላቸው ስለድኃዎች ።

ባንዲት ጉድጓድ ውስጥ ቁጥራቸው የበዛ ፡ ፍቅር የሌላቸው ብዙ ጉንዳኖች ይኖሩ ነበር ። ክህያ የዋለ ጥጃ እርግጫ ተምሮ ይመጣል እንደሚባል አንዳንድ ደኅናዎች ቢኖሩ አያሠሯቸውም ነበርና እንደሌሎቹ ሆነው ቆዩ ፤ ለዚሁ ለኑሯቸው የሚሆን ለዕለት ነበር እንጂ ለሚመጣው አላሰቡም ነበር ፡ በድንገት ክረምት ገባ ረኃብም ሆነ እንኳን ረኃብ ተጨምሮ ፊትም ቢሆን ፍቅርና ርኅራኄ የሌላቸው ናቸው ። ኃይል ያለው ድኃውን እየቀማ በላ ድኃው በረኃብ አለቀ ክረምቱም አለፈ ። ከተረፉት አንዱ ድኃ ወደ አውራው ሂዶ ባለፈው ክረምት በግዛቱ ውስጥ የሆነውን ዓመፃ ነገረው ስለ አገዛዙም ወቀሰው አውራም ይኸንን በሰማ ጊዜ አዝኖ በሱ ስም ሆኖ በጐደለው እንዲሞላ ለተበደለ ሥራት እንዲያይና ቀማኛውንም እንዲቀጣ አንዱን እንደራሴው አደረገው ፡፡

መልክተኛውም ይህነን ማዕረግ ካገኘ በኋላ ያ ዓመፃ ሁሉ የተነሣበትን ምክንያት ለማወቅ ፈለገ ከተቀሙትም ድኃዎች በትቲር የሰበሰበውን ተቀምቶ የነበር አንድ ትንሽ ጉንዳን ነበርና የሆነውን ሁኔታ ጠይቆት ቀማኛውንም እንዲቀጣለት ስሙን ይነግረው ዘንድ ተስፋ ሰጠው ፡፡ እሱ ግን ኃዘኑ እንደታወቀለት ባወቀ ጊዜ ጌታዬ ሆይ ይኸስ ከሆነ በሀሌ መንጠቅ ሳይሆን የተበደልሁበት ሌላ ምክንያት አለ እሱውም ይህ ነው

አባቴ ለሚመጣው የሚያስብ የተራበ የሚያበላ የደከመ የሚያሳርፍ ትጉ ባለጸጋ ነበር በዚሁ ስራውና ኑሮው ተመቅኝተው በክረምት ውሐ የማይደርስበት አፈሯ ለስላሳ የነበር ቦታ ነበረችውና እስዋን ለመውሰድ ባለጸጋ ጎረቤቱ ከነመልቲ ባልንጀራው ተነሳበት በኃጢአትም አስከሰሰው ታሰረም መልቲውም ለቀሀ ታልሔድክለት ከነነፍስህ እንኳን የሚያስፈራህ ነው ብሎ አስፈራራው አባቴ ግን ብርቱ ስለነበረ ስራቱን ለማመልከት ብቻ ነበር እንጂ ይኸንን ሁሉ አልፈራም ነበር ጌታ ነበርና በራፉን ለመግባት የንጉሡ በረኛ ቢከለክለው የስንዴ ቅንጣት ሰጥቶ መጀመሪያውን በር ገባ ፤ ሁለተኛውንም ቢከለክል በተረፈችው ላይ ኩርማን ጨምሮ ሰጠና ገባ እዚያም ባላጋራዎቹ ባዩት ጊዜ እውነቱ ይገለጽብናል ብለው ወደ አውራው ሳይደርስ የወትሮ ወንድማማችነታችን ይሻላልና በዚሁ ጭቅጭቅ ያለኝን በስንቅ ጨርሻለሁና ክረምቱን የሚያወጣኝ ያህል ስጠኝና እንታረቅ አለው ፡ አባቴም ከጠብ ሰላም ይሻላል ብሎ ከነበረው አምስት መቶ ቅንጣት ሲሶውን ሰጥቶ ታረቀ በሁለተኛውም ዓመት አባቴ አረፈ እንዳባቴ እንኳ ባልሆን እናቴ ታጽናናኝ ስለነበረች ደህና በሰላም እኖር ነበር ። ችሎታ እንደሌለኝ አውቆ ያው የባቴ ጠላት መሬትህን ሽጥልኝ አለዋለሁ አንተ ግን ከባቱ ጋር ስንታረቅ እስከ ሕይወቱ ሊበላ ከዚያ በኋላ ሊለቅልኝ ውል አለን ብለህ ከሰሰው ተባብለው ከሰውኝ ሁለት ዓመቴ ነው የበራፍ መግቢያ ስለሌለኝ በግፍ ሺጩ ወይም ተቀምቼ በመቅረቴ እረግቼ ነበር እስካሁን ያልታሰበውን አውራችን ይኸንን ስላደረገልን እግዚአብሔር ይመስገን ፡፡

አሁንም ስራቱን ታይልኝ ዘድን ፈቃድህ ይሁን አለው ባላጋራዎቹም አቀረበለት ነገሩንም መርምሮ ደባ እንደሆነ አወቀ በግፍ ስራ ያስፈቱበት ቀን ታስቦ ለደህው የሚገበውን ሰጥተው የሚገባቸውንም ቀጣት ለመቀበል ተፈረደባቸው ።

ከዚያም በኋላ ድራጐቶቹን ሲጨርስ ወደአውራው ተመልሶ እሱም ያደረገውን በግዛቱም ውስጥ የተደረገውን ሲደረግም የቆዬውን አመለከተው አውራም በተደረገው አዝኖ ሹም ባደረገው ደስ ብሎት የፍርድ ቤት ሲሰራ መልካም ዳኞችም ሊያስቀምጥበት አሰበ ። ተደረገም ብዙ ዓመቶችም በጭለማ ወህኒ የታሰሩ ብርሃንን አዩ ተፈትተውም በሰላም ኖሩ ።

እንደዚሁ ሁሉ ምቀኝነትን ትተን ሰላምን በመከከላችን ብርሃንን በአክሊላችን ላይ አድርገን ወደ እውቀት ከተማ እንግባ ።

ልዑል ጌታችንን አክሊላችንን
ለእውቀት ፈላጊዎች ለመመኪያችን
ፍላጐቱን ሁሉ አምላክ ያርግልን

ክፍሌ ዕርገቱ

ስለ አንድ መንገደኛ ።

ብርሃንና ሰላም የሚባል ህጻን ተወልዶ በዓለሙ ሁሉ ስሙ ታወቀ ከታወቀም በኋላ በስምንት ቀኑ ለኢትዮጵያ ልጆች መምሕር ሆኖ ጥቅም ያለው ፍሬውን ለመመገብ ጀምሮ ነበረና ስለ ሆነ ግን ምግቡን ብዙ ሰዎች አልተመገቡትም አለ መመገባቸው ገንዘብ ስላጡ ነው እንጂ የብርሃንና ሰላም ምግብ ከማር ከወተት ሁለት እንጅ መጣፈጡን ሳይሰሙት አይቀርም የኸንን ማለቱ ባንድ ሰፌ አገር አውራጃ አንድ ሰውዬ ስሙም አቶ ምቀኝነት የሚባል ክፉ ሰው የዳጉሳ ቂጣ እየበላ ያላንድ ሥራ ሲዞር ይውላል ፤ ባላገሮቹ በተሰበሰቡበት አንድ ትልቅ ሰው ብርሃንና ሰላም ሲያነብላቸው በትእግሥት ሲሰሙ ነበረና ንባቡም ከተፈጸመ በኋላ እርስ በርሳቸው እንዲህ ብለው ተማከሩ ይኸ ምቀኝነት የሚባል ሰውዬ ጥቅም የሌለው ምክር ሲሰጠንና ሲያታልለን ነው የሚውል እንጂ ጠቀሜታ ያለውስ ነገር ከርሱ አላገኘንም አሁንም ለዘመዶቻችንና ለባላገሮቹ እንዳያጠፋቸውና እንዳያታልላቸው ይኸንን ሰውዬ ከገራችን እናጥፋ ብለው አንድነት በሚባል ዱላ ይመቱት ጀመረ ። እርሱም ከጩኸቱ የተነሣ ሰው ደረሰለትና አስጣለው አሁን ለጊዜው ሰው ቢያድነው ለወደፊት አንድነት የሚባል ዱላ ከተነሳ ሳይጠፋ አያርፍም ብለን ተስፋ እናደርጋለን ። ይህም ሰውዬ አገሩን ትቶ ከሰው አገር መዞሩና ያልተስማማውን ምግብ ተመግቦ በመኖሩና ስራ ፈት በመምሰሉ ምን ይመስላችሁ ይሆን ? አሁን እኛም ተምረናል የምንል ሰዎች ለሥራ ወደ ውጭ ሒዱ ሲሉን ትልቅ መከራ የመጣብን እየመሰለን ተከተማ መለየትን አንወድምና ለወደፊቱ ግን አገር መዞርና መሰለል እንደሚያስፈልገን ስል አስጠነቅቃለሁ ። ማለት እንደምንሰማው የውጭ አገር ሰዎች ለመንግሥታቸውና ለሀገራቸው ፍቅር ሲሉ በበረሃ ብዙ ጊዜ እየተጓዱ ብንሞትም እንሙት እያሉ በጨካኞች ህዝብ መሀከል በመቀመጣቸውና ያማራቸውን ነገር ሳይበሉና ሳይለብሱ ለሀገራቸው ጠቀሜታ እንሰራለን ሲሉ በዚያው ስፍራ ሞተው ይቀራሉ ፤

እኛም እንደዚሁ ሁሉ ላገራችን ጠቀሜታ እንሥራ ፤

ጥሩ ነህ ከብትህ ይመር

ስለ ወላሞ ሥርዓት

መንግሥትና እግዚአብሔር ለሕዝቡ አዛኝ ስለ ሆነ ባላገርና ነጋዴ እንደይበደል ክቡር ደጃዝማች ይገዙን ኅዳር ፳፩ ቀን በወላሞ አገር ሾማቸው ለዚሁም የተቀባው መንግሥት ሲሰጥ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሲያመለክት በውስልትና የሰለጠኑ ብዙ ሌቦች ነበሩና ያለ መጠን የሚበድል ሥራ ሠርተው ነበር ።ስለሆነ ጥፋታቸው ሁሉ በሙሉ ባይጻፍ በ፡-ር ቃል በኋላፊው ዘመን ይልቁንም የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ቤተ ክርስቲያን አቃጥለው ለደብሩ አቅኚ የነበሩ መምሬ አፍራሳ የሚባሉትን ቄስ ቤታቸውን አቃጥላው እሳቸውን ገድለው የቀሩትም አለቁ ። ዋናው ሌባ ስሜ የሚባለው ተይዞ ታስሮ አመለጠ ። ሁለተኛም ተይዞ አምልጦ ነበርና ክቡር ዳጃዝማች ይገዙ የተሾሙለት ተይዞ በጥብቅ ታሥሮ አዲስ አበባ አወጥተውት ወህኒ መግባቱ ያስረዳል ።

ሁለተኛ ።

በሀገር ግዛታቸው ከገቡ በኋላ የሥርዓታቸውን ሕግ ቀጥሎ የተጻፈው ያመለክታል ። ሀገሩ እንዲተከከል ቤት አቃጣይ ሌባና ቀጣፊ እንዲጠፋ የድኃውን መበደል ጠልተው የመንግሥቱን ጥቅም ስለፈለጉ ወልሞ የሚባለውን ቅጠልና ዘርጭ እምቡዋይን አጠፉ ። መንገዱንም ጥረግ በከተማው ላለ ወንዙንም ሁሉ ድልድይ አሠራ ብለው አዋጅ ነግረው እያስጠረጉ ከተማውን አዘጋጁት ።

፫ተኛ ።

በሀገር ላይ እየወሳለተ የሚኖር ሌባን እየያዘ ያመጣልኝን ሰው እሸልማለሁ ብለው በየአውራጃውም አሽከሮቻቸውን እየላኩ የተያዘውም እየተያዘ ያመለጠውንም በየወሰናቸው ላሉት አገረ ገዥዎች እያስታወቁ አስይዘውታል ።

፬ተኛ

እንኳስ ብር ወድቆ አግኝቶ ብር አገኘሁ ብሎ ሊሰጥና ቤቱንም ሰ ገብቶ ከነመሳሪው ልብስ ሳይቀር ገፎ ይወስድ ነበር ። አሁን ግን ሀገር እንደገገርው ነውና አንድ ሰውየ ብር ወድቆ አገኘሁ ብሎ ክቡር ደጃዝማች ይገዙ ባስቻሉበት አምጥቶ ቢሰጥ ነገሩን በጥንከሬ መርምረው የብሩ ባለቤት ተገኝቶ እውነቱ ከወጣ በኋላ ብሩን ለባለቤቱ አሰጥተው አገኘሁ ብሎ ላመጣው ሰው ስለ እውነተኛነቱ ባለመደበቁ ፲ብር ሰጡት ። ከዚህ በኋላ ግን ብዙ ገንዘብ አገኘን እያሉ መቁጠሮና ጭራ ሳይቀር አደባባይ እያወጡ ባለቤቱ እያገኘ ወሰደ ። እንዲህ እየሆነ በእውነተኛ መንገድ ለሚሄድ ሥልጣኔ ጀምሯል ።

፭ተኛ

ነገር ግን ካሁን ቀደም ሌባ ቤቱን እያቃጠለ አብትዬውን እየገደለ ሚስቶቹንና ልጆቹን እየወሰደ ሕዝቡ ተቸግሮ ገሚ

ሱም እየፈራ ያበቱን ርስት እየለቀቀ ገሚሱም እየኰበለለ ብዙው ምድር አዳሪ ሁኖ ይኖር ነበር ። ግን ሥርዓቱ ከተተከከለለት የተሰደደው እየተመለሰ እየገባ ደግሞ ላማራውም የጠፉ ምድር በመንግሥት ፈቃድ ቀላድ እየተጣለ ወደፊት ሐሰተኛ ጠፍቶለት እንቅልፍ ወስዶት ከደረ እንደ ሸዋ ብዙ እርሻ እያረሰና አትክልት እየተከለ ሌላ ሥራ ሳይመለከት በመልካም ሥርዓት ሰልጥኖ ሀገሩ ይለማል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ። ግን በየአውራጃውም ያሉት አገረ ገዢዎች እንደዚሁ ተግተው ወስላታ ቢያጠፉ እጅግ መልካም ነበር ።

አሳምነው ።

ስለ መንፈሳዊና ሥጋዊ ጤናነት ።

ጤና እጅግ እንደከበረ ሀብት ነው ስለዚህ እንዳይጠፉብን እንጠብቀው በኃጢአታቸውና ቸል ብለው በለመጠንቀቃቸው በሽተኞች ሁነው የሚቀሩ ብዙዎች ናቸው ፤ በጕብዝናቸው ጊዜ በክፉ ምኞት ስተው ባደረጉት ጠንቅ አሁን የሚሰቀዩና የሚጨነቁ በደዌ የሚማቀቁ እየባቡ የሚኖሩ ስንት ሽማግሎች አሉ ።

በትንሽ ምክንያት ሞት ይደርስብናል ። በደማችን ትንሽ መርዝ ሲሰርጽ እንለታለን ደማችን በአካላችን ሁሉ እንዳይዘራ መከልከያ ቢገኝ ጀንዝዘን እንሞታለን ። መንፈሳዊ ሕይወታችን ከሚጐዳበት ነገር ሁሉ እንጠንቀቅ የሚያሰንፍ በሽታ አለ ካንዱ ወዳንዱ የሚያልፍ በሽታም ደግሞ ሞልቷል ። መንፈሳዊ በሽታ ወደኛ የሚያልፍበት በክፉ ሰው ምሳሌና አነጋገር ነው ።የሚገባብን ደግሞ ይልቁንም መንፈሳዊ ሓይላችን ሲደክም ጊዜ ነው ፤ በሽታውን ለመቃወም ኃይል ሊሆንልን በአምላክ ቃል በተዘጋጀልን መንፈሳዊ ምግብ እንጐልብትና ክፉውን እንሻረው እናሸንፈውም ።

በትንሽ ቍስል ኃይላችን ይጠፉብናል ሕሊናችን በኃጢአት ቈስሎ ሳለ መንፈሳዊ ድፍረት አጥተን እንቀራለን ከሁሉ ይልቅ ማስተዋልና የማያልፍ የአምላክ ሰላም ቢያድርብን ግን ዕለት ዕለት በጽድቅ ለመሔድና በደስታ ለመኖር አዲስ ኃይል እናገኝ ነበርን

በቍጣ ስናኰርፍ ክፉ የሚያቈስል ቃል ከአፋችን ሲያፈትልክብን ጤናችን ይጐዳበታል ከሙሉ ሳምንት ሥራ ይልቅ በቍጣ የምንናደድበት ጊዜ ያደክመናል ቍጣ እንደ መርዝ ሁኖ በደማችን ይገባል

እየመላለሱ በባልንጀሮቻቸው ላይ የሚተርቡና የሚዘባበቱ በሌሎችም የሚከሩ በትንሽ ነገር የሚቀየሙ በትዕቢት የሚናገሩ ሰዎች በሽታ የሚያድርባቸው ናቸው እንጂ ። ሙሉ ጤና የላቸውም።ልባችን ሲመረር ሰውነታችን ይበሳጫል ። መንፈሳችን ሲጐለብትና ጤና ሲኖረው ሰውነታችን ደግሞ ብዙ ጊዜ በጤና ይጠበቃል ። አምላክን በጽድቅ ለማገልገል ሁለተንናችን ብናቀርብለት እርሱ ከሚጐዳን ይጠብቀናል የመንፈሳችንና የሰውነታችን ጤና እየበረታ ይሔዳል ብሎ አንድ ሊቅ ይመክራል ። ልዑል ተፈሪ መኰንንም የሕዝብ ጥቅሙ መንፈሳዊና ሥጋዊ ጤንነት ቢያገኝ ነው በማለት ለመንፈሳዊ ጤንነት የሚበጀው ትምህርት ቤት አቁመው ሕዝባቸውን ይረዳሉ ሥጋዊ ጤንነት እንዲያገኝና የሕዝባቸው ሕይወት እንዲጠበቅ ሆስፒታል አቁመው በብዙ ኪሳራ እንዲታከም አድርገዋል ። እሆስፒታሉ እየታከሙ ከብዙ ብርቱ ዓይነት በሽታ የዳኑም ብዙ ናቸው ። ተፈሪ መኰንን ዕድሜ ያስጥልን እንጅ አገራችን መንፈሳዊና ሥጋዊ ጤንነት እንድታገኝ ሙሉ ተስፋ አለን ።

ጠንቋይን ስለ መጥላትና ስለ መናቅ ።

አሩሲ ጕጕ በሚባል አገር ሺባሽ የምትባል አጋንንት ወጥታ የኢትዮጵያን ሕዝብ እያሳተች ትኖር ነበር። ያጋንንትነቷም ምልክት ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

መጀመሪያ እሷ ቤት ስለት ተስሎ የሚገባው ሕዝብ ከ፯ ሺህና ከ፰ አያንስም ይኸውም ሕዝብ ሁሉ ሲመጣ ከቤቷ በታች ኮሶ ባንኮላ የሚባል ዳገት በታች አንድ ወንዝ አለ ስሙንም የኃጢአት ማጠቢያ ብለው ሰይመውታል በዚሁ ወንዝ ልብሱንና ገላውን አጥቦ ይውልና ከዚያ ተነሥቶ ወደ ሱዋ ቤት ሲመጣ ከትልቁ ከጃንሆይ ግቢ እንስቶ እልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ ያህል ሲቃረብ ስግደት ይጀምራል ። ይህ ግን መሳለሚያው ነው እቤቷ ደጃፍ ከፊት በሯ ያነሣ እመስጊዱ ድረስ ባፉ መሬት እየሣመ ይገባል ።

ሁለተኛም ከዚሁ ከኃጢአት ማጠቢያ ተብሎ ከተሰየመው ወንዝ አንሥቶ ይኸነኑ ኮሶ ባንኮላ የሚባላውን ዳገት በንብርክኬ ወጥቼ እመስጊድ እገባለሁ እያለ እየተሣለ በንብርክኩ ይወጣል ።

ሶስተኛም በመስጊዱ ቡና ጠጥቶ የሚወጣና የሚገባው ሰው ይርገጠኝ ብዬ ተስያለሁ ብሎ ከፊት በሩ ላይ በደረቱ ለጥ ብሎ ይተኛና የሚገባውና የሚወጣው ሰው ሁሉ በሁለት እግሩ ጀርባውን እየረገጠው ያልፋል ።

አራተኛም ፣ እንደውሻ እየጮኩ እገባለሁ እያለ እየተሣለ እንደውሻ ኃው ኃው እያለ እየጮኸ ይገባል ።

አምስተኛ ፣ በቀንበር ተጠምጄ እገባለሁ እያለ በቀምበር እንደ እንስሳ ተጠምዶ ይገባል፣

ስድስተኛም ከፊት በሯ አንሥቶ እስለት ማግቢያው ድረስ መኳንንትም ወታደርም ባላገርም ሁሉ ቢሆን በርኖስ ለብሶ ለመግባት አይሆንም የቤቱንም ጣሯና ግድግዳ አሻቅቦ የተመለከተ ዓይኑ ይጠፋል እየተባለ በዓይኑ አንድ ቦታ ቁልቁል ምድሩዋን ሲመለከት ከዓይኑ የሚፈሰው እንባ ምድሯን ያርሣታል።

ሰባተኛም ከባሌ እባብ ተስያለሁ ብሎ በቅል ውስጥ አድርጎ ቅቤ እያላሰ ይዞ መጣ ይኸውም እባብ ሰልጥኖ ቤት ለቤት እየሄደ በጅራቱ ሲኒ ለሰው ያቀብላል በክፉቱም እትልቁ ቤት የመጣውን ይነክሰዋል እየተባለ ይወራል ። ስምንተኛም ከዋድላ ባንድ ዘለላ ሰንበሌጥ ተስያለሁ ብሎ ይዞ መጥቶ ያነን ሰንበሌጥ ተቀብላ ከቤት ግድግዳ ላይ ሻጡት ያም ደረቅ ሰንበሌጥ እንደገና ለምልሞ በቀለ ከዚሁም ሰንበሌጥ እየቀጠፉ የታመመውን ሰው ሲመቱበት ይድናልእየተባለ ይወራል ።

ዘጠኛኛም ከላሥታ ቅዱስ ላሊበላ ሴት ዝንጀሮና ወንድ ዝንጀሮ ተስያለሁ ብሎ ይዞ መጣ እነዚሁም ሁለት ዝንጀሮዎች

አሁንም ስራቱን ታይልኝ ዘድን ፈቃድህ ይሁን አለው· በላጋራዎቹም አቀረበለት ነገሩንም መርምሮ ደባ እንደሆነ አወቀ በግፍ ስራ ያስፈቱበት ቀን ታስቦ ለደህው የሚገበውን ሰጥተው የሚገባቸውንም ቅጣት ለመቀበል ተፈረደባቸው ።

ከዚያም በኋላ ድራጐቶቹን ሲጨርስ ወደአውራው ተመ ልሶ እሱም ያደረገውን በግዛቹም ውስጥ የተደረገውን ሲደረ ግም የቆዬውን አመለከተው አውራም በተደረገው አዝኖ ሹም ባደረገው ደስ ብሎት የፍርድ ቤት ሊሰራ መልከም ዳኞችም ሊያስቀምጥበት አሰበ ። ተደረገም ብዙ ዓመቶችም በጭለማ ወህኒ የታሰሩ ብርሃንን አዩ ተፈትተውም በሰላም ኖሩ ።

እንደዚሁ ሁሉ ምቀኝነትን ትተን ሰላምን በመካከላችን ብርሃንን በአክሊላችን ላይ አድርገን ወደ እውቀት ከተማ እንግባ ።

ልዑል ጌታችንን አክሊላችንን
ለእውቀት ፈላጊዎች ለመመኪያችን
ፍላጐቱን ሁሉ አምላክ ያርግልን

ክፍሌ ዕርገቱ

ስለ አንድ መንገደኛ ።

ብርሃንና ሰላም የሚባል ህጻን ተወልዶ በዓለሙ ሁሉ ስሙ ታወቀ ከታወቀም በኋላ በስምንት ቀኑ ለኢትዮጵያ ልጆ ች መምሕር ሆኖ ጥቅም ያለው ፍሬውን ለመመገብ ጀምሮ ነበረና ስለ ሆነ ግን ምግቡን ብዙ ሰዎች አልተመገቡትም አለ መመገባቸው ገንዘብ ስላጡ ነው እንጂ የብርሃንና ሰላም ምግ ብ ከማር ከወተት ሁለት እንጅ መጣፈጡን ሳይሰሙት አይቀ ርም የኸንን ማለቴ ባንድ ሰፌ አገር አውራጃ አንድ ሰውዬ ስሙም አቶ ምቀኝነት የሚባል ክፉ ሰው የዳጉሳ ቂጣ እየበላ ያላንድ ሥራ ሲዘር ይውላል ፤ ባላገሮቹ በተሰበሰቡበት አንድ ትልቅ ሰው ብርሃንና ሰላም ሲያነብላቸው በትእግሥት ሲሰሙ ነበረና ንባቡም ከተፈጸመ በኋላ እርስ በ ርሳቸው እንዲህ ብለው ተማከሩ ይኸ ምቀኝነት የሚባል ሰው ዬ ጥቅም የሌለው ምክር ሲሰጠንና ሲያታልለን ነው የሚው ል እንጂ ጠቀሜታ ያለውስ ነገር ከርሱ አላገኘንም አሁንም ለዘመዶቻችንና ለባላገሮቹ እንዳያጠፋቸውና እንዳያታልላቸው ይኸንን ሰውዬ ከገራችን እናጥፋ ብለው አንድነት በሚባል ዱላ ይመቱት ጀመረ ። እርሱም ከጩኸቱ የተነሣ ሰው ደረሰ ለትና አስጣለው አሁን ለጊዜው ሰው ቢያድነው ለወደፊት አንድነት የሚባል ዱላ ከተነሳ ሳይጠፋ አያርፍም ብለን ተስፋ እናደርጋለን ። ይህም ሰውዬ አገሩን ትቶ ከሰው አገር መዞ ሩና ያልተስማማውን ምግብ ተመግቦ በመኖሩና ስራ ፈት በ መምሰሉ ምን ይመስላችሁ ይሆን ? አሁን እኛም ተምረናል የምንል ሰዎች ለሥራ ወደ ውጭ ሒዱ ሲሉን ትልቅ መከራ የመጣብን እየመሰለን ተከተማ መለየትን አንወድምና ለወደፊ ቱ ግን አገር መዞርና መሰለል እንደሚያስፈልገን ስል አስጠነቅቃ ለሁ ። ማለት እንደምንሰማው የውጭ አገር ሰዎች ለመንግሥ ታቸውና ለሀገራቸው ፍቅር ሲሉ በበረሃ ብዙ ጊዜ እየተንዱ ብንሞትም እንሙት እያሉ በጨካኞች ህዝብ መሀከል በመቀ መጣቸውና ያማራቸውን ነገር ሳይበሉና ሳይለብሱ ለሀገራቸው ጠቀሜታ እንሰራለን ሲሉ በዚያው ስፍራ ሞተው ይቀራሉ ፤

እኛም እንደዚሁ ሁሉ ላገራችን ጠቀሜታ እንሥራ ፤

ጥሩ ነህ ካብትህ ይመር

ስለ ወላሞ ሥርዓት

መንግሥትና እግዚአብሔር ለሕዝቡ አዛኝ ስለ ሆነ ባላገ ርና ነጋዴ እንደይበደል ክቡር ደጃዝማች ይገዙን ኅደር ፳፩ ቀን በወላሞ አገር ሾማቸው ለዚሁም የተቀባው መንግሥት ሲሰጥ የእ ግዚአብሔር ፈቃዱ ሲያመለክት በውስልትና የሰለጠኑ ብዙ ሌቦ ች ነበሩና ያለ መጠን የሚበድል ሥራ ሠርተው ነበር ።ስለሆነጥፋ ታቸው ሁሉ በሙሉ ባይጻፍ በ፡-ር ቃል በኃላፊው ዘመን ይልቁ ንም የአቡን ተክለ ሃይማኖትን ቤተ ክርስቲያን አቃጥለው ለደብሩ አቅኚ የነበሩ መምሬ አፍራሳ የሚባሉትን ቄስ ቤታቸውን አቃ ጥላው እሳቸውን ገድለው የቀሩትም አለቁ ። ዋናው ሌባ ስሜ የ ሚባለው ተዩዘ ታስሮ አመለጠ ። ሁለተኛም ተይዘ አምልጦ ነበ ርና ክቡር ዳጃዝማች ይገዙ የተሾሙለት ተይዘ በጥብቅ ታ ሥሮ አዲስ አበባ አወጥተውት ወህኒ መግባቱ ያስረዳል ።

ሁለተኛ ።

በሀገር ኀዛታቸው ከገቡ በኋላ የሥርዓታቸውን ሕግ ቀ ጥሎ የተጻፈው ያመለክታል ። ሀገሩ እንዲተከከል ቤት አቃጣይ ሌባና ቀጣፊ እንዲጠፉ የድኃውን መበደል ጠልተው የመን ግሥቱን ጥቅም ስለፈለጉ ወልሞ የሚባለውን ቅጠልና ዘርጭ እምቡዋይን አጠፉ ። መንገዱንም ጥረግ በከተማው ላለ ወንዙ ንም ሁሉ ድልድዩ አሠሬ ብለው አዋጅ ነግረው እያስጠረጉ ከተማውን አዘጋጁት ።

፫ተኛ ።

በሀገር ላይ እየወሳለተ የሚኖር ሌባን እየያዘ ያመጣ ልኝን ሰው እሸልማለሁ ብለው በየአውራጃውም አሽከሮቻቸ ውን እየላኩ የተያዘውም እየተያዘ ያመለጠውንም በየወሰና ቸው ላሉት አገረ ገዦዎች እያስታወቁ አስይዘውታል ።

፬ተኛ

እንኳስ ብር ወድቆ አግኝቶ ብር አገኘሁ ብሎ ሊሰጥና ቤቱ ንምሶ ገብቶ ከነመሳሪው ልብስ ሳይቀር ገፎ ይወስድ ነበር ። አሁን ግን ሀገር እንደገዢው ነውና አንድ ሰውየ ብር ወድቆ አገኘሁ ብሎ ክቡር ደጃዝማች ይገዙ ባስቻሉበት አምጥቶ ቢሰጥ ነገሩን በጥንካሬ መርምረው የብሩ ባለቤት ተገኝቶ እውነቱ ከወጣ በኋላ ብሩን ለባለቤቱ አሰጥተው አገኘሁ ብሎ ላመጣው ሰው ስለ እውነተኛነቱ ባለመደበቁ ፲ ብር ሰጡት ። ከዚህ በኋላ ግን ብዙ ገንዘብ አገኘን እያሉ መቁጠሪና ጭራ ሳይቀር አደባ ባይ እያወጡ ባለቤቱ እያገኘ ወሰደ ። እንዲህ እየሆነ በእውነ ተኛ መንገድ ለሚሄድ ሥልጣኔ ጀምሯል ።

፭ተኛ

ነገር ግን ካሁን ቀደም ሌባ ቤቱን እያቃጠለ አብተዬውን እየገደለ ሚስቶቹንና ልጆቹን እየወሰደ ሕዝቡ ተቸግሮ ገሚ

ሱም እየፈራ ያባቱን ርስት እየለቀቀ ገሚሱም እየኰበለለ ብዙው ምድር እዳሪ ሁኖ ይኖር ነበር ። ግን ሥርዓቱ ከተተካከለለት የተሰደደው እየተመለሰ እየገባ ደግሞ ላማራውም የጠፉ ምድር በመንግሥት ፈቃድ ቀላድ እየተጣለ ወደፊት ሐሰተኛ ጠፍቶለት እንቅልፍ ወስዶት ከደረ እንደ ሸዋ ብዙ እርሻ እያረሰና አትክልት እየተከለ ሌላ ሥራ ሳይመለከት በመልካም ሥርዓት ሰልጥኖ ሀገሩ ይለማል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ። ግን በየአውራጃውም ያሉት አገረ ገገርዎች እንደዚሁ ተግተው ወስላታ ቢያጠፉ እጅግ መልካም ነበር ።

አሳምነው ።

ስለ መንፈሳዊና ሥጋዊ ጤናነት ።

ጤና እጅግ እንደከበረ ሀብት ነው ስለዚህ እንዳይጠፉብን እንጠብቀው በኃጢአታቸውና ቸል ብለው ባለመጠንቀቃቸው በሽተኞች ሁነው የሚቀሩ ብዙዎች ናቸው ፤ በጕብዝናቸው ጊዜ በክፉ ምኞት ስተው ባደረጉት ጠንቅ አሁን የሚሳቀዩና የሚጨነቁ በደዌ የሚማቀቁ እየባቡ የሚኖሩ ስንት ሽማግሎች አሉ ።

በትንሽ ምክንያት ሞት ይደርስብናል ። በደማችን ትንሽ መርዝ ሲሰርጽ እንለታለን ደማችን በአከላችን ሁሉ እንዳይዘራ መከልከያ ቢገኝ ጀንዝዘን እንሞታለን ። መንፈሳዊ ሕይወታችን ከሚጐዳበት ነገር ሁሉ እንጠንቀቅ የሚያሰንፍ በሽታ አለ ካንዱ ወዳንዱ የሚያልፍ በሽታም ደግሞ ሞልቷል ። መንፈሳዊ በሽታ ወደኛ የሚያልፍበት በክፉ ሰው ምሳሌና አነጋገር ነው ።የሚገባብን ደግሞ ይልቁንም መንፈሳዊ ሓይላችን ሲደከም ጊዜ ነው ፤ በሽታውን ለመቃወም ኃይል ሊሆነን በአምላክ ቃል በተዘጋጀልን መንፈሳዊ ምግብ እንጐልብትና ክፉውን እንሻረው እናሸንፈውም ።

በትንሽ ቍስል ኃይላችን ይጠፋብናል ሕሊናችን በኃጢአት ቈስሎ ሳለ መንፈሳዊ ድፍረት አጥተን እንቀራለን ከሁሉ ይልቅ ማስተዋልና የማያልፍ የአምላክ ሰላም ቢያድርብን ግን ዕለት ዕለት በጽድቅ ለመሔድና በደስታ ለመኖር አዲስ ኃይል እናገኝ ነበርን

በቍጣ ስናኰርፍ ክፉ የሚያቈስል ቃል ከአፋችን ሲያፈተልክብን ጤናችን ይጐዳበታል ከሙሉ ሳምንት ሥራ ይልቅ በቍጣ የምንናደድበት ጊዜ ያደክመናል ቍጣ እንደ መርዝ ሁኖ በደማችን ይገባል

እየመላለሱ በባልንጀሮቻቸው ላይ የሚተርቡና የሚዘባበቱ በሌሎችም የሚኰሩ በትንሽ ነገር የሚቀየሙ በትዕቢት የሚናገሩ ሰዎች በሽታ የሚያድርባቸው ናቸው እንጂ ። ሙሉ ጤና የላቸውም።ልባችን ሲመረር ሰውነታችን ይበሳጫል ። መንፈሳችን ሲጕለብትና ጤና ሲኖረው ሰውነታችን ደግሞ ብዙ ጊዜ በጤና ይጠበቃል ። አምላክን በጽድቅ ለማገልገል ሁለተንናችን ብናቀርብለት እርሱ ከሚጐዳን ይጠብቀናል የመንፈሳችንና የሰውነታችን ጤና እየበረታ ይሔዳል ብሎ አንድ ሊቅ ይመክራል ። ልዑል ተፈሪ መኰንንም የሕዝብ ጥቅሙ መንፈሳዊና ሥጋዊ ጤንነት ቢያገኝ ነው ብማለት ለመንፈሳዊ ጤንንት የሚበጀው ትምህርት ቤት አቁመው ሕዝባቸውን ይረዳሉ ሥጋዊ ጤንነት እንዲያገኙና የሕዝባቸው ሕይወት እንዲጠበቅ ሆስፒታል አቁመው በብዙ ኪሳራ እንዲታከም አድርገዋል ። እሆስፒታሉ እየታከሙ ከብዙ ብርቱ ዓይነት በሽታ የዳኑም ብዙ ናቸው ። ተፈሪ መኰንን ዕድሜ ያስጥልን እንጂ አገራችን መንፈሳዊና ሥጋዊ ጤንነት እንድታገኝ ሙሉ ተስፋ አለን ።

ጠንቋይን ስለ መጥላትና ስለ መናቅ ።

አሩሲ ጉጉ በሚባል አገር ሺባሽ የምትባል አጋንንት ወጥታ የኢትዮጵያን ሕዝብ እያሳተች ትኖር ነበር። ያጋንንትነቷም ምልክት ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

መጀመሪያ እፀ ቤት ስለት ተስሎ የሚገባው ሕዝብ ከጂሺህና ከጅ አያንስም ይኸውም ሕዝብ ሁሉ ሲመጣ ከቤቷ በታች ክሶ በንከላ የሚባል ዳገት በታች አንድ ወንዝ አለ ስሙንም የኃጢአት ማጠቢያ ብለው ሰይመውታል በዚሁ ወንዝ ልብሱንና ገላውን አጥቦ ይውልና ከዚያ ተነሥቶ ወደ ሱዋ ቤት ሲመጣ ከትልቁ ከጃንሆይ ግቢ አንስቶ እልፁል አልጋ ወራሽ ግቢ ያህል ሲቃረብ ስግደት ይጀምራል ። ይህ ግን መሳለሚያው ነው እቤቷ ደጃፍ ከፊት በሯ ያነሣ እመስ ጊዱ ድረስ ባፉ መሬት እየሣመ ይገባል ።

ሁለተኛም ከዚሁ ከኃጢአት ማጠቢያ ተብሎ ከተሰየመው ወንዝ አንሥቶ ይኸነኑ ክሶ በንከላ የሚባላውን ዳገት በንብርክኬ ወጥቼ እመስጊድ እገባለሁ እያለ እየተሣለ በንብርክኩ ይወጣል ።

ሶስተኛም በመስጊዱ ቡና ጠጥቶ የሚወጣና የሚገባው ሰው ይርገጠኝ ብዬ ተስያለሁ ብሎ ከፊት በሩ ላይ በደረቱ ለጥ ብሎ ይተኛና የሚገባውና የሚወጣው ሰው ሁሉ በሁለት እግሩ ጀርባውን እየረገጠው ያልፋል ።

አራተኛም ፡ እንደውሻ እየጮኩ እገባለሁ እያለ እየተሣለ እንደውሻ ኃው ኃው እያለ እየጮኸ ይገባል ።

አምስተኛ ፤ በቀንበር ተጠምጄ እገባለሁ እያለ በቀምበር እንደ እንስሳ ተጠምዶ ይገባል፡

ስድስተኛም ከፊት በሯ አንሥቶ እስለት ማግቢያው ድረስ መኳንንትም ወታደርም ባላገርም ሁሉ ቢሆን በርኖስ ለብሶ ለመግባት አይሆንም የቤቱንም ጣሯና ግድግዳ አሻቅቦ የተመለከተ ዓይኑ ይጠፋል እየተባለ በዓይኑ አንድ ቦታ ቁልቁል ምድሩዋን ሲመለከት ከዓይኑ የሚፈሰው እንባ ምድሯን ያርሣታል።

ሰባተኛም ከባሌ እባብ ተስያለሁ ብሎ በቅል ውስጥ አድርጎ ቅቤ እያላሰ ይዞ መጣ ይኸውም እባብ ሰልጥኖ ቤት ለቤት እየሄደ በጅራቱ ሲኒ ለሰው ያቀብላል በክፋቱም እትልቁ ቤት የመጣውን ይነክሰዋል እየተባለ ይወራል ። ስምንተኛም ከዋድላ ባንድ ዘለላ ሰንበሌጥ ተስያለሁ ብሎ ይዞ መጥቶ ያነን ሰንበሌጥ ተቀብላ ከቤት ግድግዳ ላይ ሻጡት ያም ደረቅ ሰንበሌጥ እንደገና ለምልሞ በቀለ ከዚሁም ሰንበሌጥ እየቀጠፉ የታመመውን ሰው ሲመቱበት ይድናልእየተባለ ይወራል ።

ዘጠኛኛም ከላሥታ ቅዱስ ላሊበላ ሴት ዝንጀሮና ወንድ ዝንጀሮ ተስያለሁ ብሎ ይዞ መጣ እነዚሁም ሁለት ዝንጀሮዎች

ሰው ወልደው ያም የተወለደው ሰው በዚሁ በሷ ቤት ሲያገለግል ይኖራል እየተባለ ይወራል ።

አስረኛም አንድ በቀሎ ከሐረር ሰው ስለት ተሥሎ ከነእቃዋ ጭኖ ቢለቃት አሩሲ ድረስ ሰው ሣይስባት ሰተት ብላ መጣች እየተባለ ይወራል ።

አሥራ አንደኛም እረከቦት ሲወጣ እመስጊድ ቡና በጀርባዬ ላይ ሆኖ ይቀዳብኝ ብዬ ተስያለሁ ይልና ቡናው ሲፈላ ሄዶ በደረቱ ለጥ ብሎ ከህዝቡ ፊት ይተኛል ቡናውም የሚጣደው በትልቅ ጋን ነው ያሁሉ በጋን የተፈላው ቡና እስቲያልቅ ድረስ በጀበና እየተቀዳ በሰውዬው ጀርባ ላይ አስቀምጦ ቡናው እየተቀዳ ለህዝቡ ይታደላል ።

አሥራ ሁለተኛም በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ያለው ህዝብ ሁሉ መጀመሯ ለሷ የሰገደው ሁሉ እሳት በገል ይጭርና እጣን ያጤስና ባሩሲዋ እመቤት በትልቁ ቤት መጀን በሜቴ ከረማ መጀን በደህና አውለህ አሣድረን ይላል እንጂ በግልጽ ስሟን ሺባሽ ብሎ የሚጠራት ሰው አይገኝም ። ህዝቡም ፈጣሪውን ትቶ በሷ ሲያመልክ ይኖራል ።

ይህ ሁሉ በርግጥ የሆነ የሷ ቤት ሥራ ነው ደግሞም ብዙ ዓይነት በጆሮ ለመስማት የሚገርም ሁሉ ሞልቷል ። ሁሉን እንዳልጽፈው ጊዜው ይረዝማል ስለማለት ተውሁት ይህ ሁሉ ነገር የህዝብ መጉጃ ያጋንንት መጥቀሚያ ሥራ ነው እንጂ የዉነተኛው ምሕረት ከእግዚአብሔር እጅ አልፎ አይደለም ።

ይኸንኑም ምክንያት ለመጻፍ ያሣሠበኝ እንደዚህ ነው አባቴ ክቡር ፊታውራሪ አቤቤ አሩሲ ከቆላው አገራቸው ሥራ ለማሥራት ወርደው በወባ በሽታ ህመም ምክንያት ቢሞቱ ከሱዋ ጋራ ጥቂት ጥል ነበራቸውና እንዲህ ብላ ወረቀት ጻፈችላቸው ።

ይድረስ ለክቡር ፊታውራሪ አበቤ ይኸንን የተጣላንበትን ነገር ስለትልቁ ቤት ብለው ይተውኝ እኔ ነኝ እንጂ ጠቃሚዎ ሌላ የሚጠቅምዎ የለም ብላ ወረቀቱን በሰም ጧፍ ጠቅላ ብትልክባቸው ለሱዋ ወረቀት መልስ እንዲህ ብለው ጻፉላት ።

ይድረስ ከጋንንት ማደሯ ሺባሽ የተጣላንበትን ነገር ትልቁን ቤት ፈርተህ ተወኝ ብለሽ የጻፍሺልኝ ወረቀት ደረሰኝ ለትልቁ ቤትሽም አንድ ክብሪት ይበቃዋል ደግሞስ አለኔ ጠቃሚ የለህም ብለሽ የላክሽብኝ መንግሥቱን ጥኑ ሰላም ከደረገው አርሺ ብበላ ለጉሮሮዬ አንድ እንጀራና አንድ ብርሌ ጠጅ አላጣም ደግሞ ጠቃሚ አንድ ክርስቶስና መንግሥትው አንቺም ሕዝቡን ሁሉ እያሳትሽ በምትመኪበት ከትልቁ ቤትሽ በምትሠሪው ሥራሽ ተፋርጂ ብትነቀይሽንብራ ቆርጥሚ ወኃ ጠጥቼ ብኖር ለኔ ጥቅሜ ይህ ነበር ። ያንቺን ከዚህ አገር መነቀል ሣያሣዬኝ እግዚአብሔር በሞት መንገድ አይጥራኝ ብለው ጻፉላት ። ከዚህም በኋላ እንዲሁ እያሉ ሲያዝኑ በመንግሥት ፈቃድ ከብቷም ተወርሶ እርስቷም ተነቅሎ በሱዋም ቤት የቅዱስ ሚካኤል ታቦት ተተክሎ እሱዋም አርያ ከሚባል አገር ተቀምጣለች እያሌ ሰው አሁን እንኳን በሱዋ መሳሉን አልተወውም።

ደግሞ አባቴ ከሷ ጋራ የተጣሉበት ነገር ይህ እሷየያዘችው ሥራ ከዚህ ቀደም በጆሮ ተሰምቶ የማይታወቅና ከክርስቶስ መንገድ በጣም ስለተራራቀ ከልክ ያለፈ የክህደት ሥራ ስለሆነ ነው ደግሞስ ይህ በስለት ከሷ ቤት የሚሰበሰብ ህዝብ ሁሉ። የሚበዛው ክርስቲያን ነው ገሚሱም ሥጋ ወደሙ የተቀበሉ ሰዎች ናቸው የሷ ሃይማኖት እስልምና ነው

ደግሞስ ክርስቲያን ሆኖ ሥጋ ወደሙ ተቀብሎ በጾም በጸሎት ተጠምዶ ፈጣሪውን መለመኑን ትቶ ለእስላም መስገድና ከሷ ቤት እህልና ውኃ ተቀብሎ መመገብ ይገበዋልን)

ደግሞስ ማዳንና መግደል ያላንድ ዓምላክ እንደማይቻል ልቡ እያወቀው ለስዋ መስገዱ በጣም ይገርማል ሁለተኛም እስዋ ከዳነችና ከገደለች ሕዝቡ የፈቀደውን የልብ ምኞት ሁሉ ፈጻሚና አድራጊ ተሆነች መጀመሯ ልጅዋን ከሞት ማዳን አይበልጠውምን ሁለተኛም እስዋ እራስዋ በሣልና በውጋት በቁርጥማት ትቀጠቀጣለች ።ከዚህ መዳንና ህዝቡን ከዚያ በኋላ መጥቀም አይበልጠውምን

ይሁን ደግሞ እስዋ የክርስቶስ ፍጥረት ነች እንደኛው ሞትንና መከራን በራስዋ ተሸክማ ለምትኖር እንዴት ፈጣሪውን ትቶ ለፍጡር ይሰግዳል ስለዚህ ኤርምያስ ም ፩ ቁ ፲፮ እንዲህ ይላል በፍርዱም በላዬቸው እነግራለሁ ስለክፋታቸው ሁሉ እኔን ስለተውኝ ለንግዶችም አማልክት ዕጣን አጠኑ ለጃቸውም ሥራ ሰገዱ ሁለተኛም ኤር ም ፪ ቁ ፲፫ እንዲህ ይላል ሕዝቤ ሁለት ክፋት አድርገዋልና ። እኔን የሕያውን ውኃ ምንጭ ተውኝ ለራሳቸው ጉድጓድ ቆፈሩ የተቀደዱ ጉድጓድ ውኃ ይይዙ ዘንድ የማይችሉ ።

አባቴም ክቡር ፊታውራሪ አበቤ ተስዋ ተፋርጂ አንገቴን ለሥራት ጀርባዬን ለግስፋት ሰጥቼ ብሞትም በስዋ ነገር እንዳንድ ሰማዕታት እቆጠራለሁ እያሉ ሲመኙ የሰውና የእግዚአብሔር ሃሣብ በጣም እጅግ የተራራቀ ነው ። ሰው ሆኖ ከሞት መቅረት የለምና ከአባታችን ከአዳም ከቆዬን ልማድ በተወለዱ ፺፯ ዓመታቸው አሩሲ ዲማ ከሚባል አገር አረፉ ስለዚህ እሳቸው በህመም ምክንያት ቢሞቁ አሁን ባገር የሚወራው ፊታውራሪ አበቤ ከሜየቴ ከወይዘሮ ሽባሺ ከትልቁ ቤት ተጋጭተው ነው የሞቱት በሳቸው መጀን ይበላል ።

ደግሞ እኔም ባለፈው የከቲት ፲ ቀን ትንሽ ጉዳይ አግኝቶኝ በፈረስ ሆኜ ከከተማው ቤቴ ወደ የካው ቤቴ ደርሼ በቶሎ ለመመለስ ሃሣብ ነበረኝና ፈረስ ተጭኖልኝ ገና ከቤት ወጥቼ እርካብ ቆንጥጬ ከፈረሱ ላይ እጠጣለሁ ስል ከወደኋላዬ ድድቅ መሳይ ነበረና ፈረሱ ወደኋላው ሲያፈገፍግ በገዛ ኃይሉ በጀርባው ተገልብጦ ፈረሱ ብቻውን ወደቀ።

እኔም ወደዚያው በዚሁ ፈረስ ተቀምጬ እዚሁ አሰብሁት እየካው ቤቴ ደረስሁ በማግሥቱ እንደዘመኑ ህመም ራስ ምታትና ውጋት ይዞኝ ስምንት ቀን ታምሜ ብተኛ አባቱ ከትልቁ ቤት ተጣልቶ ሞተ ከሳቸው የተጣላ ሰው ምን ዘር ይተርፋዋል አሁንም ልጁ ከፈረስ ወድቆ ተሰብብሮ ሊሞት ነው እየተባለ ተወራ እኔም ለፍጥረቱ የሚራራ ቸር መሐሪው አምላክ እንደ ሰው አፍ ሳያደርገኝ ከበሽታዬ በጥቂት ቀን ምሮ

ኝ ይኸው በከተማው እሄዳለሁ ደግሞ በትንሹ በግጥም አድርጌ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች አቀርባለሁ ።

የፈጣሪ ሥሙን አጥብቃችሁ ጥሩ ። ሺባሽን አጠፋ ት ነቀላት ከሥሩ ። አባሮ ሰደዳት እንዳትቆም በምድሩ። እናንት አዋቂዎች በጣሙ ምከሩ ፤ አስመስለው ነገር ለ ንጉሥ ቢነግሩ ። ይሁን ያለ እንደሆን ይጠፋል ፍጡሩ የልጅ ነገር ብላችሁ ሐሜትን አታውሩ ። እኔ ነግሬ አለሁ በጣሙ ጠንክሩ ፤ ለአምልኮ ባዕዲማ እኔ አብስ ነበር ። ትውልዴም ጋላ ነው ትምህርት ባልማር ። እንኳን እገላለሁ ብላ ለሕዝብ ስትፎክር።እንሠግድ ነበረ ለንጨትና ማር ፤ አሁን አገኘሁት አውቄ ምግባር ። ለክ የሱ ነንወይ ያንድ ፡ ዓምላክ ፡ ፍጡር ፡ እስከሁን ፡ ለፋሁኝ ። ልቤ ፡ እስቲታክ ት ፡ አረፍኩኝ አሁንስ አገኘሁ ንብረት ። ብርሃንና ሰላም የእውቀት መሠረት ፡ እናግሮኝ የልቤን ብሞትም ልሙት ፡ የጥ ቃት የተንከል መሆኑን እሥቤ ። ይኸንን ቃል ጻፍሁት ልጅ ተፈራ አቤቤ፡

የ፲፱፻፳፯ ተከታይ ።

ስለ መንግሥትና ሕዝብ አስተዳደር ደንብ ማሻሻል ፤

የተቀናና የተተከከለ ደንብ አውጥቶ የወጣውንም ደንብ በፍጥነት አስቀድሞ የሥራ አለቅነትና ያገር ግዛትነት መዓርግ ላላቸው ሰዎች ትእዛዙን አጥንተው እንዲጠብቁትና እንዲ ጠብቁበት መስጠት ቀጥሎም በነሱ እግር ሆነው ለሚሠሩ ሹፍ ሮች ማደል ይገባል ፤ ከሰጧቸው በኋላም ያንን ትክክል ሁኖ የቆ መውን ደንብ እንዳይተላለፉ መንግሥት ወይም የመንግሥት አማካሪ የሆነ ቀይና ጥቁር ረጅምና አጭር ሃብታምና ድኃ ብሎ ሳይመርጥ ትክክለኞች ሃይማኖት ያላቸው እግዚአብሔርን የሚ ፈሩ መንግሥታቸውን የሚያከብሩ ገሮች ትእግሥተኞች ቶሎ የማይቈጡ አድልዎን የሚጠሉ በትምርት የበሰሉ ባውቀት የጐ ለመሱ ትምርታቸውም የቋንቋ ትምርት ብቻ ሳይሆን ባገራ ቸው ትምርት ጠሊቅ በሆነ አሰለጣጠን የሰለጠኑ ከገሩ ውስጥ መርጦ ተጠባባቂዎች ሊሾምላቸው ግድ ያስፈልገዋል ። እንዲህ ክልሆነ ግን ሕዝብና መንግሥት ኦስተቃቅፎ ሳያንቃቅፍ ሊያ ስተዳድር በብዙ አዋቂዎች አስመርምሮ ያወጣውን ያገባብ ደንብ በየሥራ ቤቱና በየግምጃ ቤቱ ታጥፎ ተቀምጦ ሳለ እንበሳ ወይፈን ወይፈኑን ነምር ምክት ምክቱን ቀበሮም ጥቦት ጥቦቱን ሲያደቁ አገሪቷን ሲያመዘብሩ ዓመታቱም ከመ ጽላሎት ያል ፋል ። ዋ ዋ እንዲህ ጉበዝ ጉበዙን ብልህ ብልሁን አስተዋይ አስተዋዩን እላይኛው መስመር ላይ በተመለከተው ከጠማማ ፍጥረት ራስ በፈለቀው የጥፋት ፑለቲክ እንክትክት ጥፍትፍት እቅቅ ድቅቅ ብሎ ያለውን ጨርሶ ተመርሮ ካገር የጠፋ እንደሆን አያድርስ አያድርስ ። እንኳን ለተወለዱበት አገር ላልተዛመዱ በት ለባዕድ አገርም ቢሆን አያድርስ ።

ምሳሌ ባንድ ተማሪ ቤት ውስጥ ከሰዓት ወደሰዓት ከቀን ወደቀን ተማሪዎችን አጥንተው ሊሰለጥኑበት የቀረበላቸው መጻ ሕፍት መላልሳችሁ በጣም ይህንን አጥኑትና በዚያው ተፈትና ችሁ በፈተና ቀን ሳትወድቁ የወጣችሁ እንደሆን ከዚህ የበለጠ መጻሕፍት ተመርጦ ይለወጥላችኋል ። ማለት ቀርቶ የገበታውን ማማርና ሽልማት የጥራዙ አጠነካከርና የቀለሙ አቀባብ የወረ ቀቱ ንጣትና አወፋፈር አይተው ከጠገቡ በኋላ ፍሬና ገለባውን ለይተው ሳያውቁት መጻሕፍቱን መቶ ጊዜ ቢለዋውጡላቸው በተማሪ ቤቱ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ምን ተጠቀሙ ። ጊዜያቸ ውን በከንቱ አጠፉ እንጂ አልተጠቀሙም ልንል እንችላለን ።

እንግዲያስ በቤተ መንግሥትም ቢሆን አስቀድሞ የወጣ ውን ደንብ ተጠንቶ ሳይፈጸም ተራ ሕዝብ ሁሉም አይቶ ተመ ልክቶ የጥቅሙን ነገር እንደሆነ ሳይረዳው ደንብ አስተካከሊ ዎችን ብቻ ተሰብስበው ብዙ ጊዜ ቢያስተካከሉት ባገሩ ውስጥ ያለ ሕዝብ አይቶ ስላላጠናው መንግሥትና ሕዝብን ሊያስተዳድር አገርን ሊያሰለጥን አይችልም ፤ ስለምን ብሎ የሚጠይቅ ቢገኝ ቀጥሎ በተጻፈው ቃል አረስዳዋለሁ ።

የሕዝብና መንግሥት አስተዳዳር ደንብ የንጉሥ ምሳሌ ነው ። ንጉሥ ባገሩ ውስጥ የሚኖር ሕዝብ ሁሉ እንደሚያው ቀ ። የቤተ መንግሥትንም ደንብ የሕዝብ አስተዳዳሪ ስለሆነ በግልጽ ሰው ሁሉ ሊያውቀው ሊጠብቀውም ነው የሚገባ እን ዲህ ካልሆነ ግን ተደንብቶ ሳለ እንዳልተደነባ ያህል ነው ስል ባለችኝ በጠባብ ዕውቀቴ በብርሃን አንብበው በሰላም ለሚተረ ጉሙ የመሰለኝን በጭሩ እገልጽላቸዋለሁ ።

ፍሥሐ ወልደ ሚከኤል ።

በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በበላይ እልቅና የተደረገው ኮንሴር ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በእሁድ ቀን በ፩ ነሐሴ ከኩለ ቀን በኋላ በ፲ ሰዓት ክቡር ፊታውራሪ ዓምዴና ክቡር ፊታውራሪ ደስታ ተከትለዋቸው ከኮንሴሩ ቦታ በመጡና ከአውቶሞቢል በወረዱ ጊዜ ሙዚቃው የተፈሪ መኰንን ማ ርሻ መምታት ጀመረ ።

የአርመን ሕዝብ የማህበር አለቆችና ብፁዕ አባ ዮሴፍ በታላቅ ክብር ተቀብለው ልዑል በሳሎኑ ውስጥ በገቡ ጊዜ ከ፬፻ የሚበልጡ ሰዎች ተነስተው በታላቅ ደስታ አጨበጨቡ ላቸው ከዚህ በኋላ ለልዑል በተሰናዳላቸው በልዩ ቦታ ግራና ቀኝ የውጭ አገር መንግሥታት ክቡራን ሚኒስትሮችና ወይዛ ዝሮች መሐከል ተቀመጡ በማናቸውም ነገር ኮንሴሩ በትክክ ል በሚገባ ሆኖ በደስታ ከተፈጸመ በኋላ በ፲፪ ሰዓት ተኩል ብፁዕ አባ ዮሴፍ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል ተናገሩ ።

ልዑል ጌታዬ ሆይ ።

ክቡራኖች ሆይ ፤

እመቤቶቼና ጌቶቼ ።

የአርመኖች ሁሉ የበላይ ብፁዕ ፓትሪአርክ ሐዋርያዊ መልክተኛ በመሆኔና በኢትዮጵያም ያሉትን የአርመን ሕዝብ በመንፈሳዊ ሥራ ጠባቂ በመሆኔ በአዲስ አበባ ነዋሪ ስለሆኑ ት አርመኖች ሁሉ ከኢትዮጵያ መንግሥት ስላገኙት መልካም ጥበቃ ጥልቅ የሆነ ምስጋናቸውን ለልዑልነትዎ አቀርብ ዘንድ ከሁሉ አስቀድሞ የሚገባኝ ሥራ ነው ።

በአዲስ አበባ ላለው የአርመኖች ትምሕርት ቤት ጥቅም እንዲሆን በልዑልነትዎ መልካም ጥበቃ ጥላ በተዘጋጀው በዓል መጥተው ስለአከበሩን ጥልቅ የሆነ የማክበር ምስጋናችንን ለልዑልነትዎ እንዳቀርብ የአሳባቸው አስተርጓሚ እንድሆን ይፍቀዱልኝ ።

ልዑል ጌታዬ ሆይ ፥

ደግነትና ርኅራኄ የዘወትር ልማድዎ ስለሆነ ይህ መልካም ሥራ የከበረ ልብዎን ስለነካውና በዚህ በዓል መጥተው ስለአከበሩን የተማሪዎቻችንን ምስጋና ቅዱስ ዳዊት በሕፃናትና በሚጠቡ ልጆች አፍ ከፍጹም ጥልቅ ልቦናቸው በሚወጣው ምስጋና አመሰግንሃለሁ በሚለው ቃል እባርክልዎታለሁ፡

ለኢትዮጵያ ትልቅነትና ልማት መልካም ኑሮ እንዲሆን ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለልዑል አልጋ ወራሽ ለቤተ ሰባቸውም እረጅም እድሜና ተድላን ክብርንም እንዲሠጣቸው እግዚአብሔርን እለምናለሁ

ደግሞ ከውጭ መንግሥታት ወደ ኢትዮጵያ ተልከው የመጡት የከበሩ መልክተኞች መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ ወደ በዓሉ መጥተው ስለአከበሩን የአርመኖችን ሁሉ ጥልቅ የሆነ ምስጋናችንን አቀርብ ዘንድ የሚገባኝ ሥራ ነው

በዚህ በዓል በመሰብሰባቸው ክብር ያደረጉልንንና በዓለም እንዲያምር ያደረጉልንንም ሰዎች ሁሉ አመሰግናለሁ

ከዚህ በኋላ ለአንድ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ሕዝቡ ሁሉ ተነሥቶ የኢትዮጵያ ኢምን ዜማ በሙዚቃ ሲመታ ሳለ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ወደ ግቢ ተመለሱ

Traduction de l'adresse ci-dessus lue par le rev. Pere Garabédian, délégué apostolique.

Monseigneur

Excellences

Mesdames, Messieurs.

En ma qualité de délégué apostolique de sa sainteté le Patriarche suprême de tous les Armeniens et Pasteur spritual des Armeniens d,Ethiopie' je considére comme l'un de mes premiers devoirs de présenter à votre Altesse Impériale et Royale, l, expréssion de la profonde gratitude de la communauté Armenienne pour la protéction bienveillante qu, elle jouit sous les auspices du Gouvernement Imperial Ethiopien.

Je me fais l'intérpréte de notre sentiment commun, en adressant à Votre Altesse Impériale et Royale, nos trés profonds et réspectueux remerciments pour le haut patronage qu'elle a bien voulue accorder à cette fête organisés au prófit de l'école nationale Armenienne d'Addis-Abeba.

Monseigneur

Pouisque votre Altesse Impériale et Royale a bien voulue suivant son habituelle bienveillance, et suivant les traditions de l'Empire, cette oeuvre de bienfaisance qui touche de si prés au noble coeur de votre Altesse Impériale, je me permets de me faire l'intérpréte de nos éléves pour répéter à votre Altesse avec Sain, David, ces paroles qui sont réstées célébres " Par la bouche des petits enfants je vous bénis des paroles qui emanent du trés " profond de leur coeur,, "

Je pric Dieu pour qu,il veuille accorder grandeur, prospérité, et bien etre à la noble Ethiopie, á Sa Majésté L'Impératrice Zeouditou à votre Altesset et à la famille Impériale.

Je me fais egalment un devoir de présenter les plus vifs remrciments de la Communauté Armenienne à LL. EE. MM. les representants des Puissances accréditées auprés du Gouvernement Imperial Ethiopien, d'avoir, bien voulu par leur présence, rehausser l'éclatde cette fête·

Je remercie egalement tous ceux qui ont bien voulu honorer de leur présence cette fête et tous ceux qui ont contrbué á son succés.

የሚገባ ሥራ ።

አምላክ ለያንዳንዳችን የምንሠራው ሥራችንን አመለከተን የማይሠራ ለግሞ እያዘጠዘጠ የሚኖር የገዛ እንጀራውን የማይበላ ወንበዴ ነው ። ቅዱስ ጳውሎስም የማይሠራ አይብላ ብሏል ።

አንድ ያማርኛ መጽሐፍ ስላንድ ሰው ሲተርክ እንዲህ ይላል፥ አቶ እገሌ ከመብላትና ከመጠጣት ከመጫወትና ከመሳቅ ከተድላና ከደስታ በቀር ምንም አያውቅም ነበር ። ስለዚህ አንድ ሰው የእገሌን ጌትነት ከመንገድ ላይ ወድቆም ባገኘው አላነሣውም ብሎ ተናገረ ሲል ይተርካል ።

እንደርሱ የመሰሉ መብላትና መሳቅ ብቻ የሚወዱ ስለምንድር ወደዚች ዓለም መጡ ያለ ሥራ እውነተኛ ደስታ የለም ያለሥራ እውነተኛ ክብረት የለም ። ባሮ ቀጣት ፈርቶ ይሠራል ሥራ ሁሉ በደስታ እንጂ በግድ ያለፈቃድ እንደ ባሮ ሥራ አይሁን ። አባቱን የሚወድ ልጅ ያባቱን ፈቃድ ሊፈጽም ብሎ የታዘዘውን ሥራ በደስታ ያደርጋል ።

ለነፍስና ለሥጋ የሚያስፈልግ ሁሉ በምሕረቱ ለሰጠን ለሚያስብልን ለአምላክ በሥራችን እናገልግል በሥራችን ዕረፍትና ደስታ ጉልበትም የሚያድለን የማያልፍ ደሞዝ ለታመኑ ሠራተኞች የሚሰጣቸውን እያሰብን ላባታችን ፈቃድ በስራችን የሚገባ መሥዋዕት እናቅርብለት ።

ዓለም እንይ



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሁሉ ሰዓት መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፴ ብር ፲ መሐ ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ ።
ም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፫ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፫ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፴፱ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፳፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፲ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፰ ብር
፡፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፵፩ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፰ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፬ መ

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፲፰
አንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ ፱
ባአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፲፰ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚሁ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ግልጹ ሰያስረዳም ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

ሩግ ቢ

RUGBY

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፣ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቂ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፤ ሽቱ ፤ ለስ ዮን ፤ አድከሎኝ ፤ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፤ ካኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፤ ከፈይ ምንጣፍ ፤ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና ኾሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፤ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፌታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤኼስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፤ ባለ አጉበርና አጉበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፤ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፤ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፤ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፤ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክስል የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

Berliet



ቤርሊዮ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዮ አቶሞ ቢልና በእንጨት የሚሄድ ከሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሲ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

ኤን ቤ ኤዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተከሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳሀን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ። የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሦስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፭
3 me ANNÉE №. 35

ሐሙስ ነሐሴ ፲፪ ቀን ፤ ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 19 AOUT 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen , Héritier du trône d' Ethiopie , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊትሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ብፁዕና ቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ዕረፍት ።

አቡነ ቄርሎስ የእስክንድርያና የኖብያ የኢትዮጵያም ፓትርያርክ በተወለዱ በመቶ አምስት ፣ በእስክንድርያ በመንበረ ማርቆስ በተቀመጡ በአምሳ አምስት ዓመት ሐምሌ ፴ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓመተ ምሕረት አረፉ ።

አቡነ ቄርሎስ ከቅዱስ ማርቆስ ጀምሮ ፻፲፪ኛ ናቸው ቄርሎስ በመባል በስም ግን ፭ኛ ናቸው ። የአቡነ ቄርሎስም ዕረፍት በካይሮና በምድረ ግብጽ ሁሉ ከተሰማ በኋላ በእስክንድርያ በመንበረ ማርቆስ የአቡነ ቄርሎስ ወኪል ሆነው የተቀመጡት የመኖፍያ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ዮሐንስ ለግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቴሌግራም አሳለፉ ።

የግብጾች የእስክንድርያ ፓትርያርክ ብፁዕ ቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ዛሬ ጧት መሞታቸውን በታላቅ ኀዘን እናስታውቃለን ።

ፊርማ የእስክንድርያ አባ ዮሐንስ ።

ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽ የአቡነ ቄርሎስን ዕረፍት የሚያስታውቅ ቴሌግራም በደረሳቸው ጊዜ እጅግ አድርገው አዘኑ ። ወዲያውም በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያን ሁሉ ፍታት እንዲደረግላቸው አዘዙ ። ለአቡነ ዮሐንስም ቴሌግራም ምላሽ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል በቴሌግራም አሳለፉ ።

የላኩልንን ቴሌግራም በታላቅ ኀዘን ተቀበልን የብፁዕና ቅዱስ አባታችን የአቡነ ቄርሎስ ዕረፍት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትልቅ ኀዘናችን ነው ። በየአብያተ ክርስቲያናቱም ሁሉ ለፓትርያርክነታቸው የሚገባ ፍታት እንዲደረግ አዘናል ።

ፊርማ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ተፈሪ መኰንን ።

ከዚህም በኋላ ክቡር እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በአዲስ አበባ በያድባራቱ ያሉት ካህናት መስቀልና ጥና እየያዙ ልብሰ ተክህኖ እየለበሱ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ድረስ እየመጡ በነሐሴ ፫ ቀን ዕሁድ ፍታት እንዲፈቱ ለየአድባራቱ አለቆች አስታወቁ ።

በዚሁ ቀን በማለዳ ልዑል አልጋ ወራሽ የኢትዮጵያ ትልልቅ መኳንንቶች ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ቅዳሴ አስቀደሱ ። ከቅዳሴም በኋላ የፍታት ጸሎት ተጀመረ ስለ ካህናቱም ብዛት የቅኔ ማኅሌቱ የማይበቃቸው ስለሆነ በቅኔ ማኅሌቱ ዙሪያ በየክፍሉ ሆነው ይፈቱ ጀመር ።

የውጭ አገሮች የዲፕሎማቲክ ሰዎች ሁሉ ስለ አቡነ ቄርሎስ ዕረፍት የኢትዮጵያን መንግሥት ሕዝብ ለማስተዛዘን እቤተ ክርስቲያን ድረስ መጥተው ነበር ።

አራት ሰዓትም ከሆነ በኋላ ፍታቱ ተጨረሰና ስለ አቡነ ቄርሎስ ዕረፍት ክብር ፲፪ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ።

አቡነ ቄርሎስ ለእስክንድርያ ፓትር ያርክነት ሳይመረጡ ለኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሆነው እንዲመጡ ተመርጠው ነበር ። ነገር ግን እግዚአብሔር ለታላቁ ማዕርግ ለፓትረያርክነት እንዲመረጡ ፈቃዱ ሆኖ ነበርና ባልተገለጠ ምክንያት እርሳቸው ቀርተው አቡነ አትናቴዎስ ተመርጠው ወደኢትጵያ መጡ ፤ ከጥቂትም ጊዜ በኋላ የእስክንድርያው ፓትርያርክ አረፉና አቡነ ቄርሎስ ተመርጠው በመንበረ ማርቆስ ተቀመጡ ።

አቡነ ቄርሎስ ትሑትና ርኅሩኅ ከሁሉ ጋራ ተፋቃሪ ነበሩ እንኳን ክርስቲያኖቹ እስላሞቹም ቢሆኑ እንደ አባት ያዩዋቸውና ያከብሩዋቸው ነበር ።

አቡነ ቄርሎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ ወኖብያ ወኢትዮጵያ ።

በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ዮሐንስ ዘመን አቡነ ጴጥሮስንና አቡነ ማቴዎስን አቡነ ሉቃስንና አቡነ ማርቆስን ጳጳስነት ሾመው ወደ ኢትዮጵያ የሰደዱ አቡነ ቄርሎስ ናቸው። አፄ ዮሐንስም አቡነ ቄርሎስ ደግ ሰው መሆናቸውንና የኢትዮጵያን መንግሥት ማክበራቸውን ሕዝቡንም መውደዳቸውን በሰሙ ጊዜ እርሳቸው በሚጭኑት ዘውድ ዓይነት የወርቅ አክሊል አሰርተው ወደ ካይሮ ድረስ ሰደዱላቸው ። አቡነ ቄርሎስም ያንን አክሊል ደፍተው በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በገቡ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ እያዩ በኢትዮጵያና በግብጾች መከከል ያለውን የሃይማኖት ወዳጅነት እጅግ አድርገው አደነቁ ይባላል ።

አቡነ ቄርሎስ በተወለዱ በ፺፱ ዓመት ፓትርያርክነት ከተሾሙ ፶ ዓመት ሆኖ ነበር ። ይህንም የአምሳ ዓመት መፈጸሚያ ቀን እንደ ብሉይ ኪዳን ሥርዓት የኢዮቤልዩ በዓል አድርገውበት ነበር ። በዚሁም ቀን በምድረ ግብጽ አውራጃ አቡነ ቄርሎስ የሾሟቸው ፲ ጳጳሳት ወደ ካይሮ መጥተው ነበር ። ደግሞ በካይሮ ከተማ የሚኖሩ የክርስቲያን ወገኖች የግሪክ የአርመን የሶርያ የእንግሊዝ የአሜሪካ የጀርመን የቤተ ክርስቲያኖች አለቆች ሁሉ መጥተው ነበር ። ከእስላሞቹም ወገን ሁለት እጅግ የተማሩ ሺሆች መጥተው ነበር ። በነዚህም ላይ የቤተ መንግሥቱ ሚኒስትሮችና ባላባቶች ሁሉ ምንም እስላሞች እንኳ ቢሆኑ መጥተው ካይሮ ባለው በቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን ቅዳሴ አስቀድሰው የአቡነ ቄርሎስን በዓል አከበሩ ይህም ሁሉ ደግነታቸውንና ከሁሉ ጋራ መፋቀራቸውን ይመሰክርላቸዋል ።

አቡነ ቄርሎስ ከሁሉ ጋራ ይፋቀሩ ነበር ስለተባለ ከሁሉም ይልቅ ከኢትዮጵያ ሰዎች ጋራ ያላቸው ፍቅር እጅግ ጽኑ ነበር ።

ይህንኑም የሚያስረዳ ነገር በቤታቸው ያሉት የእልፍኝ አሽከሩም አጋፋሪውም አሳላፊውም፡በረኛውም፡ቡን አቅራቢውም እነዚህ ሁሉ የኢትዮጵያ ሰዎች ናቸው ።

በድንገትም የኢትዮጵያ ሰው በሱዳን በረሃ ዞሮ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሔድ ካይሮ በደረሰ ጊዜ ምግብም የማደሪያ ቤትም እንዳይቸገር አድርገው ያዞሉታል ።

በ፲፱፻፲፮ ዓ ም ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አውሮጳን ለመጐብኘት በሔዱ ጊዜ አስቀድሞ ኢየሩሳሌምንና የኢትዮጵያን የኦርቶዶክስ ሃይማኖት አባት አቡነ ቄርሎስን ማየት ይገባኛል ብለው ከኢየሩሳሌም ወደካይሮ ሔደው ነበር ከኢትዮጵያም ሲነሡ ወደ አቡነ ቄርሎስ መድረሳቸውን በእርግጥ ስለአወቁት በጥሩ ወርቅና በፈርጥ ያጌጠ አክሊል ፤ ከባ ላንቃ ከነ መደረቢያው ፡ ባለወርቅ ጥልፍ ከፈይ ሱሪ ፡ እጀ ሰፊ የሐር ቀሚስ ፡ ያረንጓዴ ሐር ሀባዬ ። የወርቅ መስቀልና የወርቅ መቋሚያ ይዘውላቸው ሔደው ነበርና አቡነ ቄርሎስ ስለ ሽምግልናቸውና ስለ ድካማቸው ይህን ሁሉ ለብሰው ለመቀመጥና ለመታየት የማይችሉ ቢሆኑ ባጠገባቸው የቆሙ ሰዎች ልዑል አልጋ ወራሽ ያመጡልዎ ሽልማት ሁሉ በጠረጴዛ ላይተደርድሮ ሰው ሁሉ እየገባ ይየው እንጂ እርስዎ የለበሱት እንደሆነ እጅግ ይደክማሉ ብለው መከሩዋቸው።እርሳቸው ግን ድካሜ እስከ ሞት የሚያደርሰኝ እንኳ ቢሆ ን ከልጆቼ ዘንድ የመጣልኝን ሽልማት ለብሼ ሳልመርቃቸው አልቀርም ብለው ሽልማቱን ሁሉ ለብሰው የወርቅ አክሊሉን ደፍተው ይጠብቁ ጀመር ።

ልዑል አልጋ ወራሽም ከተከታዮቻቸው ከመኳንንቶች ጋራ በገቡ ጊዜ በታላቅ ደስታ ተቀበሏቸው ጸሎትና ቡራኬም

አደረጉላቸው ። ከቡራኬውም በኋላ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።

እጅግ የተወደዳችሁ ልጆቼ ሆይ እኔ በመንበረ ማርቆስ ከተቀመጥሁ ጀምሮ ፈቃዴና ምኞቴ ሁሉ ኢትዮጵያንና የተ ወደዱ ሕዝቡዋን ለማየት ነበር ፤ ነገር ግን የሚያገናኘን የባ ቡር መንገድ ባለመኖሩ ምኞቴ ሳይፈጸምልኝ ቀረ ። በኋላም የባቡር መንገድ በተሰራ ጊዜ እድሜዬ ስለ በዛና ስለ አረጀሁ ረጅም መንገድ ለመሄድ የማልችል ሆኜ ቀረሁ ፤ ስለ ሆነም በፍቅርና በጸሎት በቡራኬ ከናንተ አልተለየሁም ፤ ዛሬ ግን እና ንተን በማየት አሳቤና ምኞቴ ስለ ተፈጸመልኝ በአርያም ያለ ውን ጌታ አመሰግናለሁ ።

ልጆቼ ሆይ የምኰራባችሁ በእናንተ ነውና በአርያም ያለው ጌታ እንዲጠብቃችሁ ቀንና ሌሊት በጸሎቴ እለምናለሁ

ባለፈው ዓመት የተባረኩት ልጃቹን ልዕልት ወይዘሮ መነን ወደ እኛ በመምጣታቸው ደስ ባለን ጊዜ እርስዎም መጥተው ለሀገራችን ክብር ይሆናሉ ብለን ተመኝተን ነበርና አሁን ዛሬ መምጣትዎ ለወንድሞቻችን ለግብጾች ታላቅ ደስታ እየጨመረ ሔደ ።

ዓይኖቼ ልዑልነትዎንና አብረው የመጡትን ራሶችን መ ኳንንቶች አይተው ምኞቼ ከተፈጸመበት ከዚህ ቀን ስለ ደረ ስሁ ለአምላክ ምስጋና አቀርባለሁ ብለው ንግግራቸውን ጨረሱ ።

በዚህም አነጋገር ልዑል አልጋወራሽና መኳንንቱ እጅግ ደስ አላቸው ነገር ግን በሽምግልና መድከማቸውን አይተው ሁሉም አዘኑ ። ይህንም ሁሉ መጻፋችን አቡነ ቄርሎስ የኢትዮጵያን ሰዎች ከሌሎቹ ከሃይማኖት ልጆቻቸው ሁሉ አብልጠው ይወ ድዋቸው እንደ ነበረ ገልጠን ለማስረዳት ያህል ነውንጂ መል ክም ስራቸውን ሁሉ ጽፈን ለመጨረስ አይደለም ።

አሁንም ልዑል እግዚአብሔር በእውቀቱ ብዛትና በጥበቡ ጥልቅነት እንደ አቡነ ቄርሎስ ደግነትና ርኅሩኅነት ፍቅርና ትሕ ትና ያለው የኢትዮጵያ ፍቅር ያደረበት ፓትርያርክ መርጦ በመንበረ ማርቆስ እንዲያስቀምጥልን ልመናችንን በፊቱ እና ቀርባለን ።

ብርሃንና ሰላም የአቡነ ቄርሎስን የሃይማኖት ልጆቻቸ ውን የእስክንድርያንና የኖብያን የኢትዮጵያንም ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

ማመልከቻ ።

ይድረስ ለክቡር ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ከዚህ በታች የጻ ፍኳትን ሐሣቤን እንድታትምልኝ በማክበር እለምንሃለሁ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓመት ብልሁ ሞገስ ዓምደ ሚካኤል በብርሃ ንና ሰላም ጋዜጣ በሆድ ውስጥ አጥንት ሆኖ ከቀረ ጽንስ የጨ ነገፈ ይሻላል ልጁ ቢሞት እናቱ ትድናለችና ስለዚህ ምንም ባይደረግ እየተናገራችሁት ይቅር እንጂ ላይደረግ ምን አደከ መን ብላችሁ ቸል እንዳትሉ ። ያሉትን ቃል ከዕለታት ፩ ቀን እሰው ቤት ሐጂ ጋዜጣ ስመለከት አገኘሁት እኔም ምክሩ እልቤ ቢገባ ክርኔን እጉልበቴ ላይ አስደግፌ እራሴን በመዳፌ ይገር ፭ ደቂቃ ያህል ዝም ብዬ ቆየሁ የቤቱ ባለቤት ምነው ልጄ ምን ቃል በጋዜጣችን ውስጥ አግኝተህ ተከዝህ አሉኝ እኔም እንዲህ ብዬ መለስኩላቸው ጨዎች ሲተርቱ ሰው የሆ ዱን አሳብ የነገሩት እንደሁ የከረከሩት ያህል ይስቃል ሲሉ ሰምቼ ነበር ለኔም ብልሁ ሞገስ ዓምደ ሚካኤል የሆዴን አሳብ ቢነግሩኝ ነው አልኋቸው እሆድህ ምን ኖሯል አሉኝ ። እኔም ከሁለት ወር በፊት ሁለት ሐሳቦች አስቤ ሳልጽፋቸው ቀርቼ ነበር እላይ እንደተጻፈው ቃል ሊሆንብኝም እንደሁ እንጃ ፤ ብቻ ዬን ስቀመጥም ስሔድም በመንፈቀ ሌሊትም ትዝ እያለኝ ከራሴ ወደልቤ እየወረደ እየወጣ አስቸግሮኛል አልኳቸው ምን ይሻልሐል አሉኝ አሁንማ መድኃኒቱን ሞገስ ዓምደ ሚካ ኤል ነግረውኝ ቢደረግም ባይደረግም ልናገረውና ይቅር አልኋ ቸው እሳቸውም እግዚአብሔር ይርዳህ ብለውኝ ተሰነባበትን ። አሣቤም ከዚህ አስከትዬ የጻፍኩት ነው ።

ይድረስ ለክብርት አዲስ አበባ ጉሙሩክ ። ለክቡር ለአቶ ገብረ እግዚአብሔር የጉሙሩኩን ስራና የዙሪያውን በር ደግ ሞም የባላገሮችን ገበያዎችና ኬላዎች በልክ ስለ አስኬዱልን ታላቅ ምስጋና ይገባዎታል አዲስ አበባ እጉሙሩኩ ውስጥ ፩ የዘገዬ ሥራ አለና በቶሎ እንድታከናውኑልን በማክበር እማ ሥብዎታለሁ የዘገዬውም ሥራ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው አዲስ አበባ ጉሙሩክ ያበሻ እቃ ማስቀመጫና የሚዛን ቤቱ ዙሪያውን ተገንብቶ ልክ እንደሸቀጥ ቤቱ መቁለፍ ያስፈልገ ዋል ቁልፉንም የያዘ ሰው ለዘበኞች አስረክቦ እውጭ እንዲያ ድር ይገባዋል ሌላውን ሁሉ እኔ እጽፈም ዘንድ አይገባኝም ሌሊት ሌሊት ማር ይፈራል እሁድ በየሳምንቱ ሠራተኞች ሲወጡ ጭር ሲል በሩ ሲዘጋ ማር ይፈራል ያለውም በስልቻ ነው የታሠረውም በቁቻ ነው ሌሎችም ያገራችን ሸቀጦች አሉ ጭር ሲል የሚፈሩ ስለ ፈሪዎች እቃዎች ይህ ቤት በፍጥነት መሠራት የግድ ያስፈልገዋል ለወደፊት ግን እንደ ሸቀጥ ቤት ማዕርግ ያደርጉልናል ስንል ተስፋ አለን ።

ሁለተኛ ፤

ይድረስ ማዘጋጃ ቤት ለክቡራን ሹማምንቶች አዲስ አበ ባን የህል ተራን ገበያ ጭቃውንና መጥበቡን እንድትገቡበት ልን በማክበር አማስባችኋለሁ ይልቁንም ቅዳሜ በየሣምንቱ ከመጥበቡና ከጭቃው የተነሣ አሮጊቶች እናቶቻችንና እርጉ ዞች እህቶቻችን ታውከው ይውላሉ እህል ተሸክመው ያመጡ ልን እንስሶች በርግጫና በጡጫ በዱላም ሲደበደቡ ይውላሉ ገበሬዎችም ሲረጋገጡና ስልቻ መጫኛቸው ሲጠፋ ይውላልና በመጠን እንድታደርጉልን መጀመሪያ የህል ተራ ማጥዳትና በልክ ማድረግ ይገባል ፤ አቶ ሞቢል ከጮሬ ከአዳ እህል አያ መጣም አቶሞቢል ከጉማና ከጌራ ማር አያመጣም አቶሞቢል ከሲዳሞና ከጅማ ቡን አያመጣም እንስሶች የሚሰሩልንን አቶ ሞቢሎች አይሠሩልንምና የእንስሶች ጥፍር እጭቃ ውስጥ ተሸ ጉጦ እንዳይውል ድንጋይ ማንጠፍ የግድ ነው ። ለገበሬዎችም በክፍል በክፍላቸው ተራውን እንዲቀመጡ ከብቶቻቸውንም

እሬታቸው ተራውን እንዲያስሩ ያደርጉልናል ስንል ተስፋ እና ደርጋለን ።

ለብርሃንና ሰላም የምታገለግሉ ጌቶቼ ሆይ ከዚህ በላይ የጻፍሁትን ያልታረመ ቃሌን በሰላም እንድትቀበሉኝ በትሕትና እለምናችኋለሁ ። ጥበብን ለሰሎሞን መርቆ የሰጠ እግዚአብሔር እንዲሁ ለናንተም ጥበብን ይግለጽላችሁ ። አሜን ።

ወንድማገኘሁ አበይ ።

ከተማሪ ቤት ስለ እሚቀሩ ልጆች ።

ባገራችን እተማሪ ቤት ያልገቡ ልጆች ጥቂቶች ናቸው ። እተማሪ ቤትም ቀርተው የሚማሩ ጥቂቶች ናቸው ። ሰው ተፈጥሮ በዓለም ላይ ሲኖር ባለጠጋ ወይም ድኃ ነው ። እተማሪ ቤት ለመማር የሚመጡ የባለጸጋ ልጆችና የድኃ ልጆች አራት አምስት ወር ተምረው ከዚያ በኋላ ትተው ይሄዳሉ እንጂ ከጥቂቶች ልጆች በቀር እተማሪ ቤት ለመቆየትና ሥራ ለመያዝ የደረሰ ልጅ የለም እተማሪ ቤት ሶስት አራት ወር ያህል ገብቶ ያልሞከረ ልጅ ያለ አይመስለኝም ። የዚህ ምክንያቱ እንደኔ አሳብ ሁለት ይመስለኛል። አንደኛው ምክንያት መጀመሪያ የባለጸጋ ልጆች እተማሪ ቤት ሔደው ሲማሩ ይውሉና ማታ እቤታቸው ሲገቡ አባቱ ልጄ ዛሬ ምን ምን ስትማር ዋልክና መጣህ ይልና ይጠይቀዋል ። ልጁም አባቱ የማያውቀውን ቋንቋ ያሰማዋል መቼም ትምህርት ለኋላው ይጠቅመዋል እንጂ ለትንሽ ልጅ ለጊዜው ትምህርትና ቀጣት ያስመርረዋል አባቱም የኋላው ክሞት በቀር የማያስቀረው ጥበብን ልጄ ሊያገኝልኝ ነው ብሎ ስለ ማሰብ ፋንታ የልጁን መበሳጨት አይቶ እኔ ምን አባቱ አያቴና አባቴ እንራስ እከሌ እነደጃዝማች እከሌ በትርጁማንነት አልበሉ እያለ ሲያስብ ደግሞም የሱን ባልንጀራ ልጆች ከመንግሥት ይጠጉና ባለ ሟል ሆነው ሲላላኩና ሲጫወቱ ያያል ያሥ የዚህ ባለጸጋ ልጅ ጌቶቹ በተማሪ ቤት በኩል ሲያልፉ ባልንጀራው የጌቶቹን በቅሎ አሙን ዘለብ ይዞ ከጌቶቹ እየተጫወተ ሲሔድ ወይም እግቢ እየጠና ሲልኩት ያይና እኔ እንግዴህ ተምሬ ሳድግ እንደገና ደጅ ጠንቼ ሥራ እስታገኝና ባለሟል እስክሆን ይኸ ባልንጀራዬ አሁን ከንጉሥ ተጠግቶ ሊሾም ሊሸለም ነው ሲል ያባቱና የልጁ አሳብ እዚህ ላይ ይገጥምና አንድ ቀን አባትና ልጅ ጨዋታ ሲያነሱ ልጄ እኔ ምን አባቱ ባትማር የነ እገሌ ልጆች ከጌቶች ባለሟል ናቸው ። ለከሌም በቅሎ ለከሌም ፈረስ ሰጡት አንተ ግን እተማሪ ቤት ውለህ ማታ ስትመለሰ ደብተር ብጤ በጅህ አንጠልጥለህ ከመምጣት በቀር ምንም አላገኘህ ይልቅስ የኔ ያባትህ ገንዘብ እንኳን ላንተ ለማንም ይተርፋልና ይኸን የፈረንጅ ጭቅጭቅ ተውና፥ ጌቶቹን ደጅ ጥና ይለዋል ። ፪ተኛ የድሆች ልጆች ከተማሪ ቤት የሚወጡበት ምክንያት ደግሞ ያንድ ድኃ ልጅ እተማሪ ቤት ገብቶ አራት አምስት ወር እንደ ተማረ የዚያ የልጅ አባት ወታደርም እንደሆነ ጌታውን ሲያጅብ ይውልና ነጋዴም እንደሆነ ሲነግድ ይውልና ማታ ከልጁ ጋራ እቤታቸው ሲጫወቱ አባቱ ልጁን እንዲህ ይለዋል ልጄ እኔ ስነግድ ስለፋ እውልና ማታ አንተ ስትመለስ አንተ ደብተር ብጤ አንጠልጥለህ ይዘህ ትመጣለህ ከስራው ከምኑ አታግዘኝ የነ እከሌ ልጆች ሲነግዱ ውለው እሩብ ተሙን አትርፈው አባቶቻቸውን ያግዛሉ ለራሳቸውም ልብሳቸውንና ሆዳቸውን ችለዋል ።እኔ እየለፋሁ አንተን አበላለሁ አንተ የለት እራት የሚሆን ነገር አታመጣልኝ እያለ የኋላውን ጥቅም ሳያስብ ልጁን ያደክመዋል ። ልጁም ባልንጀሮቹ እገበያ ውስጥ ሲያላግጡ ሲጫወቱ ሲቸረችሩ እያየ እንደ ባልንጀሮቹ ጊዜውን በጫዋታ ለማሳለፍ መቸም ልጅ ይመኛልና ያባትና የልጁ አሳብ እዚህ ይገጥምና ልጁ ተምሮ ለኋላው አባቱንም እንዳይረዳው እራሱንም እንዳይችል ሌባ ቀጣፊ አድርጎት ይቀራል ። ለዚህ የሚሻለው ነገር የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ታውቁታላችሁና ለኔ ለትንሹ ወንድማችሁ እንድትገልጹልኝ እለምናችኋለሁ ።

ትንሽ በር ።

በራሱ ዕውቀት ዓለሞችን ሁሉ ፈጥሮ ሰውንም ፈጥሮ ከሁሉ የበለጠ ዕውቀት ለሰው የሰጠ እግዚአብሔር በማያልቅ አዲስ ምስጋና ለዘለዓለም ይመስገንና በሱ ትእዛዝ ይህችን ትንሽ በር እሰራለሁ ስለ አገሬ ሰው ። ሞኙ ሰው ሌላው እንዳይሄድባት ይዘጋታል ብልህ ግን ሰው ሁሉ እንዲሄድባት ያሰፋታል ያገሬ ልጅ ሆይ በዚች ትንሽ በር የተጻፈውን ቃል አስተውለህ ምስጢሩን ተመልከት የምሥጢሩ ዓይነትም ይህ ነው ። ምን ያንቀላፋኃል ሺ፱፻፳፱ ዓመት የተኛኸው ይበቃኃል ። ከመኝታህ ተነስ ። ወደዕውቀት ገሥግሥ ። ውጭ ወጥተህ በገንዘብህ ገዢ አታምጣ ። በገርህ ሰው ሳታጣ ። የውጭ ሰው አትመን ፡ እንግዳህ አዋቂ ሁን ፡ ከውጭ አዛዥ ናዛዥ አታምጣ ፡ ራስህ ነፃ ውጣ እነዚህን አስር ቃላት የመሰለ ነው የምስጢሩ ዓይነት ። የናቴ የኢትዮጵያ ልጅ ሆይ ። በመጻሕፍት ያለ እንዳልጽፍልህ ሁሉንም ታውቀዋለህና ከሰው የሰማሁትንና ያገኘሁትን በትንሽ በር እንድጽፍልህ ፈቃድህ ይሁን ። ይህችን ትንሽ እንደምን አገኘሃት ብትለኝ ለወንድሜ አልሰውርምና ልንገርህ ፤ ኢየሩሳሌም ሁኜ ወደሀገሬ ወደኢትዮጵያ ስመለከት አቶ ብልጤ የሚባል ሰው ከባድ ሸክም አስጭኖ ወደኢትዮጵያ ሲጓዝ ታየኝ እኔም እስቲ ልጠይቀው ብዬ መንገድ ስጀምር ዙሪያው ገደል ሲሆን በዚች ትንሽ በር ሾለክሁና እንደ ሸዬ ሩጬ ደረስኩበት ። እንዴት ዋልህ ጌታው ብልጤ ይኸን ከባድ ሸክም ጭነት ወዴት ትወስደዋለህ ወዴትስ ታራግፈዋለህ አልሁት ። እሱም በስተኋላው ስደርስበት ጊዜ የፖለቲክ ሰው መሰልሁትና ይህን ቃል መለሰልኝ ። ዛሩ ከጐመራ ውኃው ከጠራ እህሉ ካፈራ ሰው ከገራ ኢትዮጵያ ወስጄ አራግፈዋለሁ አለኝ ። ሌባና ወንበዴ እንዳይወስድብህ ተጠንቀቅ ብለው እኔም የፈለግሁት ይህን ነው ይውሰዱት ቢለኝ ይህ ነገር ምን ይሆን ብዬ ጌታዬ የስጠኝ መነጽር የተሸፈነውን ሁሉ ያሳያልና የድናሚት የመድፍ የመትረየስ የጠመንጃ የሽጉጥ የጥይት ዓይነት የሰይፍ የጐራዴ የጩቤ የካራ ዓይነት የጦር የቀስት የመጋዝ የፋስ የመጥረቢያ የገዘሞ ዓይነት እነዚህን የመሰሉ ልዩ ልዩ ዓይነቶች አየሁ ወተት ቅቤ ማር ሱካር የመሰሉም አሉት ላፍ ጣፍጠው ልናፉ

የሆድ በሽታ የሚሆኑ ፤ የወርቅ የብር ዓይነቶች የሚብለጨለጩ ማንካ ሹካ ሰሐን አሉት ከመብል ጋራ ወደ አፍ ገብተው ብሽታ የሚሆኑ ይልቁንም ጥሩ አረቄ የመሰሉ መርዞች ብዙ ዓይነት አየሁ ፡፡ ይህን አየሁና በድንጋጤ ስንቀጠቀጥ ጌታው አቶ ብልጤ እንደ አንተ ያሉ ሰዎች ካንተ በኋላ ይመጡ ይሆን ብለው አዎን ይመጣሉ ተነሥተዋል እኔ በነሱ ዓይን ሰነፍ ነኝ ጭንቀታቸውም ከጭንቱ ይከብዳል አሉኝ ፡፡ ስማቸው ማን ማን ይባላሉ ብለው እግዜር የለም ኩነኔ የለም ንጉሥ ገዳይ ወርቅ ለብቻየ ይባላሉ እነሱን የመሰሉ ሌሎችም አሉ አለኝ ። በል ደህና ዋል በአምሳያህ አትጨክን አልሁትና ተሰፋ ቆርጬ ወይ አገሬ ወይ አገሬ እያልኁ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሼ በክርስ ቶስ መስቀል እግር ወደቅሁ ። ገሩ ወንድሜ ሆይ አንተ ግን ልትመልሰው ትችል እንደሆነ ደህን ጊዜ ተጠናከር ያለዚያ ግን በትንሽ በር ውጣና መዳኛህን ፈልግ ።

አባ ገብርኤል ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ማመልከቻ፣

የኢትዮጵያ መንግሥት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለመንግሥታቸውና ለመ ኳንንቶቻቸው ለሕዝባቸው ለሀገራቸው ሲሉ ወደፊት ለሚጫ ነን የድንቁርና ጉዳት አስበው መርምረው አማካሪዎች ከአውሮፓ ነገሥታት ጋራ ትምሕርትና ሥልጣኔ ንግድና መተባለፍ እንድናገኝ ብለን አስበናልና ከፋም እንደሆነ መልካምም እንደ ሆነ ምከሩ ቢሉ እንደሰማነው መልስ ከጥቂት ሰዎች በቀር ሁሉ በንድ ቃል ወደ ማኅበርነቱም እንግባ ስልጣኔም እንከተል ፡ ልጆ ቻችንንም በትምህርት እናበርታ ተብሎ በዚህ ተወስኖ ተፈረመ ኢትዮጵያም በዚህ ምክር አልጋ ወራሹን ሰዳ ከዓለም ነገሥ ታት ጋራ የዕውቀት ዝምድና ልትካፈል ማህበርነት ገባች ። እውቀት እንኳ ዛሬ ቢጐድልባት ከሳአል መንግሥት በፊት አስ ቀድሞ የነበረ የጀግንነት ባንዴራዋን እስታሁን አለ ትምሕርት በድፍረት ሳትወድቅ በመቆየቷ ብዙህ ታሪክ አዋቆች መሰከሩ ላት ። ልጁዋም አፄ ቴዎድሮስ የዓውሮፓን ስልጣኔ መመስረታ ቸው በቅርቡ ተወሳሳት ። ደጉ አፄ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥትም በልባቸው አስበው የተማሩ ሰዎችም ጠይቀው የአውሮፓን ስር አት ለመከተልና ለመፈጸም ቆርጠው እንደተነሱላት በዚሁ መሐከል የድንገት በሽታ ኃሳባቸውን አጓደለው ። ተፋጥነው በጊዜያቸው ያቆሙትን ስራ በአዲስ አበባ ገልጸን እንጽፋለን። መጀመሪያ ጉምሩክ ፖስታ ስልክ ማዘጋጃ ፈረንሳዊና እንግሊዝ ቋንቋ በመልካቸው የተሰራ ብር አላድ ሩብ ተሙን ቤሳ አስራ ሁለት ምኒስትሮች የእንጨት ፋብሪካ ሆቴል የከተማ ዘበኛ ይህ የቆመ ስራ እየሰፋ ይሄዳል እንጂ አልጐደለም መንግሥ ትም ለሚአስፈልገው ጉዳዩን ለንግዱና ለሂሳቡ ተቀዳሚ መሠ ረት ሆኖ ወደትልቁ ደረጃ ስበ ይመራዋል እንጂ አልከፋውም አሁንም ልዑል አልጋ ወራሽ የጃንሆይን ውጣኔ ባለመሰልቸት ለመፈጸም ተነስተዋል ። ልባቸውንና ክንዳቸውን የኢትዮጵያ አምላክ ያበርታልን ፡፡

ልዑል ሆይ በሕዝቡ ጥፋትና ክፋት አይዘኑ ፡ ሀሳብዎም አይቈረጥ ፤ ያልተማረ ሕዝብና ሙጫ ልጅ ጠቀሚታውንና ጠ ቃሚውን ንጉሥ ለይቶ ለማወቅ አይችልምና አይሰልቹት በድ ካምዎ እንደጀመሩት ስለ ድንቁርና ባርነት በንዳንድ አፍ እሚ ታለምባት ያለ ነጻ ሲያወጧት በኽር ልጅዎ ኢትዮጵያ ናት ። ደግሞ ለዚህ ለሚያልፈው ዓለም ለኋላ ትውልድ የሚ ቈይ ነገር ቢሠሩላት እያደርም እስከሉም ድረስ ደስ ያሰኛል በብርታትና በትጋት እንዲሰፉና እንዲቆም ያስባሉም ይሠራ ሉም እያለ እእምሮኛ ሁሉ አመስግኖ ዙፋንም ለዘለዓለም ሕ ያው ይሁን ይላል ፤ እኔ አጥብቆ ደስ ያለኝ ቅናትና ምቀኝነት ማጣላት ወዳጅ መሥሰል አራቱ ቀጣፊዎች በካህናትና ከዱሮ መኳንንት አፍ የሚባል ጫካ በረሀ ከአባታችን ሰፈር በታች ተደብቀው የሚኒስትር መክዶናልድም ጤንነት እየጠያየቁ ብዙ ጊዜ ቢነሱ ሥራቸው ታውቆ እነዚህ ሰዎች ባለማሰብ የተነሣ መንግሥታችንን ለማስነፍና አገራችንን ለባዕድ ለማስመቸት ዋጋ የበሉ ይመስላሉ ብለው ቢሰየሙ አሳባቸው ተቈርጦ እ ራዳ ገብተው ወሬኛና አቃጣሪ ሁነዋል ብለው ሠርቶ መብ ላትና አገርን መውደድ ቢያሚውቱኝ ሰላም ለባንዲራዬ ብዬ እጅ ነሣሁ ፤ እነሱን ከንቲባው መርምሮ ካገር ወደውጭ አገር ወህኒ ቢያሳርፋቸው መልካም ይመስለኛል ።

አሁን ግን ልዑል አልጋ ወራሽ በማናቸውም ነገር ኢ ትዮጵያ ነፋስ እንዳይገባበት ዘወትር እንደታጠቁ መኖራቸውን የዓለም ጋዜጣ ያመሰግናቸዋል ። ደግሞ ለኢትዮጵያ መሪዎች ነን የሚሉ የስልጣኔ ባለተስፋዎች ሁሉ ደስ የሚል ልዑል አውሮጳ ሄደው ከመጡ ወዲህ ትምህርት ቤት ፡ መንገድ ፡ ዘ በኛ በሚያስደንቅ ቆመ ቢሉን ለቀረው ነገር ሊፈመድና ወደ ፊት ሊገሠግስ ነው ብለን ተስፋ እናደጋጋለን ።

ልዑል ሆይ ለሥልጣኔ ደረጃ ለማውጣት ያለ አሳብዎ ሰ ላም ለዛሬ እንደሌለዎ ተረድተነዋል ። ለወደፊቱ ግን ካላስተካከ ሉት ለምለሚቱ አገርዎ ኢትዮጵያ በድካምዎ የዘለዓለም ነጻ ነቷን ይመሠርታሉ ። ለልዕልናዎና ለልጆችዎ ግን ቀድሞ ከነበሩ ነገሥታት የሚበልጥ እየተወሳ የሚኖር በዓለም የማይ ረሳ ስም ይተክላሉ ፤ በ፲፱፻፲፮ ዓመት እንኳ ከልዑልነትዎ ብዛት የተነሣ ንግሥተ አዜብ ማክዳ ሌሎች ነገሥታት ጀምረውት የቀረ የኤሮጳ ስልጣኔና የእግዚአብሔርን ስፋት ልዑል አልጋ ወራሽ ተሻግረው አስፋፍተው በመምጣትዎ ደስ ያሰኛል መሳፍንቶችዎንም አስከበሩ ፡፡ የሰለጠኑ የዓለም ነገሥታትን እዩ ። ልዑል ባዩት የዓለም ስልጣኔና ዕውቀት በመዘርጋት አሳብ መሳፍንቶቹ በሚገዙት አውራጃ ሊያግዟቸው ነው ብለን ተ ስፋ ነበረን ፡ እንኳን እነሱ ሊተውት ከዚህ የቈዩት አገረ ገዦ ዎች በየከተማው በገንዘባቸው ትምህርት ሊዘረጉ ተስፋ ነበረን አሁን ሁሉ ቀርቶ ብንሰማ አንድ አንድ ተማሪ ቤት በየከተ ማው ይቅርና በግዛታቸው ፩ አላቆሙም ቢሉኝ ምኞቴ ሁሉ ተስፋ ቆረጠ መንግሥታችንም እጅግ ያስለቅሳል ከሚገዙት አገር የሚወጣ ግብር ሲሶ ለነሱ ሲሶ ለወርዋሪ ሲሶ ለመንግ

ሥት ካላገቡ ወይ ተማሪ ቤት ካላቆሙ እርዳታቸው ለመቼ ቀን ይሆን ብየ አሳቤ ሁሉ ተበተነ ። የሚገርምስ አውሮፓን አይተው የመጡት መኳንንት አለማቆማቸው ያሳዝናል ለወደፊት ከሚጻፍ የግርማዊት ንግሥትና የልዑል አልጋ ወራሽ ስም ታሪክ መጽሐፍ የስልጣኔ መሰረት መታጣታቸው እነሱ አሳዘኑኝ ትል ከማይተላ ነቀዝ ከማይነቅዝ ቦታ መዝገባችሁን አኑሩ የተባለው ሁለተኛ ማዕርግ የማይጠፉ የዓለም ደስታ የሚታይበት ይኸ ይመስለኛል ። ገንዘብ ሱቅ በሬ ላም ርስት አትክልት መንግሥት እስታሉ ነው እንጂ ሕዝብ ዓይን ታልከፈተ መንግሥት ነዋሪ ሕግ ከልመሰረተ ፍሬ የለውም ።መኳንንትና ባለጠጎችም ልምክራችሁ ለመንግሥትህና ላገርህ ቀዋሚ ነገር ስምህን የሚያስጠራ ታላደረግህለት ከሞት በኋላ ገንዘብ መተረቻና መጫወቻ መሆኑ ከዚህ ቀደም ያለፉት ሰዎችገንዘብ ያስረዳናል።የኢትዮጵያ መሳፍንት መኳንንትከብታሞች ነጋሮች ነጋዴዎች አራሾች ሆይገንዘባችሁ በመሬት ተቀብሮ ንዳ ቤት የሚባል አንዳንድ የደሓ ልጅ በልቶት ከሚቀር ገንዘባችሁን የትምሕርት ቤት ፋብሪካ ኩፓንያ እያደረጋችሁ ብታቆሙት ለዘለዓለም የማይጠፋ ወለድ እየሆነ ለልጆች የሚጠር ይሆናል ። ቀኛዝማች አስረስ ተሰማ ።

በብረት መንገድ ስለሆነ አደጋ ።

ነሐሴ ፱ ቀን ከሞጆ ወደ አዲስ አበባ በሚወጣው በስኞ ባቡር አንድ ሰው ተሳፍሮ ሲመጣ አዲስ አበባ ለጋር ለመድረስ ፳፪ ሚትር የሚሆን ሲቀረው ወድቆ ባቡር ድጦት በሚያሳዝን መከራ ሞተ ወደፊት ባቡር ለሚሳፈሩ መንገደኞች ሁሉ እንደዚህ ያለ አደጋ እንዳያገኛቸው እንዲጠነቀቁ ብርሃንና ሰላም ያስታውሳል ።

የመንግሥትና የሀገር ፍቅር ማጠንከር የተገባ ነው ።

የመንግሥት ፍቅር ማጠንከር መንግሥት ሕዝቡ እንዲበለጥግና በሥልጣኔ እንዲኖር አገር ሰላም እንዲሆን በየአውራጃውና በየበሩ ላቆማቸው አገር ገዦዎች የሕዝብ ጉዳት የሚሆነውን አጠንክሮ አዋጁን ለሹሞች ያማልፋል ሕዝብ ከመንግሥት ያለፈለትን በሰላምና በጸጥታ መኖርን አገር ማፍቀርና ለመንግሥት በጠንከረ ቃል መርዳትን ከአገር ገዦው መቀበል አለበት ለዚኸውም ከዚች ዓለም እስከወዲያኛው መታሰቢያ የሆኑ ወሮታቸው በቶሎ የማይከፈል የኢትዮጵያ ብርሃን ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አገራቸው ከትዮጵያ ምንም የትሕምርት ወምበር ቢዘረጋበትና ሕዝቧ በስንት ሚሊዮን ቢታሰብ አብዛኛው በሥርዓት አለማደጉንና በትሕምርት አለመጐልመሱን ስለ ተረዱት ከሁን ቀደም በሐረር አውራጃ ሕዝብ በሥረዓት እንዲሰለጥንና እንዲ ጠነክር በሰላም እንዲኖር በትምርት እንዲጐለምስ እንደ ደነገጉት በሙሉ ኢትዮጵያ ሕዝባቸው እንቅፋት የለሌበት ጥርጊያ መንገድ እንዲተላለፍ በሰፊው ድልድይ እንዲሸጋገር ወደስልጣኔው ደረጃ እንዲደርስና እንዲበለጥግ በትምሕርት እንዲጐለምስ በብዙ ትጋትና ድካም ያቆሙልንን የትምሕርት ቤትና የስልጣኔ መንገድ ወደፊትም በየጊዜው እንደሚያስቡልን ሕግና ደምብ ተቀባይ የምንሆን ትጉሕ እንጂ ቸልታ ንቃት እንጂ እንቅልፍ የሌለን ለኢትዮጵያ ብርሃን ለልዑል አልጋ ወራሽ ለተፈሪ መኰንን አጋዥና ረዳት እንድንሆን መንግሥት ይስፋ ኢትዮጵያ ትጠንክር ።

የሀገር ፍቀር ቸርና ርኅሩኂቱ ኢትዮጵያ ለደስታሽ ወሰን የሌለው ከአያሌ ጊዜ ጀምሮ ሕዝብሽ ከትሕምርት እንዲራቀና ስልጣኔ እንደተመኘ መኖሩ የተረገጠ ነው ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር የተባልሽ እጅሽን በእግዚአብሔር ፊት እንደዘረጋሽ እኛም ወሰን የሌለው የሐሳብ ምኞታችንን በትልቅ ምስጋናችን ማቅረብ ይገባናል የምስጋና ምግብ ገባችሽ ከኢትዮጵያ ብርሃን ከልዑል አልጋ ወራሽ ከተፈሪ መኰንን ቤት በጥልቅ የተዘረጋውን እንመግባለን ሕዝብ በሙሉ ቢበለጥግ ነው እንጂ የበለጠገውን ከበቅሎ ሲወርድ ዕርካብ ቢይዙለት ከተቀመጠበት ሲነሣ በርኖስ ቢያራግፉለት ባርኔጣ ቢያቀብሉት የተወለዳትን ቢያገቡለት የወለደውን ቢያነሱለት ለርሥቱ ወኪል ቢሆኑት በአብቻ በጋብቻ በጡት በማር ቢሉት እወደድ ባይ ጥቅም ነገር ያለበት ሳይመስልምያ ከንቱ ድካም ነውና በሥራ ላይ ቢደክሙና ቢተጉ ነው እንጂ በተለምዶ ከመሰልጠን መንግሥት በሙሉ ሐሳቡ ያቆመውን የስረዓት ስልጣኔ ተቀብሎ በሥራ ላይ መድከም ይበልጣል ከበደ አየለ ።

ማስታወቂያ ።

የመንግሥት ሠራተኞች የሆኑ የኢትዮጵያ ወጣት ልጆች እውቀታቸውን በግድ እያሰፉ መሄድ የሚያስፈልግ ስለመሰላቸው ሥራቸውን ከጨረሱ በኋላ እርስ በራሳቸው እየተሰበሰቡ የሚማሩበት ቤት ከነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፲፱ ፡ ዓ ም ጀምረው "ሠረቀ ብርሃን" ብለው የሰየሙት አንድ የተማሪ ቤት ማቆማቸውን በሥራ ላይ ላሉ ወንድሞቻቸው ያስታውቃሉ ። የትምህርቱም ጊዜያት ከእኩለ ቀን በኋላ በ፲ ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ ፩ሰዓት ድረስ ነው ፤ በዚሁም የትምህርት ቤት የሚሰጠው ትምሕርት ለጊዜው ግዕዝና አማርኛ የፈረንሣዊ ቋንቋ ደግሞም ቁጥር ነው ፤ ነገሩን በትክክል ለመረዳትና እትምህርት ቤቱ ለመግባት የሚፈልጉ ሰዎች ወደ አቶ መታፈሪያ ወልዴ ዘንድ እየመጡ ለመጠየቅ ይችላሉ ። ቤቱም ከራስ መኰንን ድልድይ ዘላይ ነው ።

(ሠረቀ ብርሃን)

A V I S

Les jeunes gens Ethiopiens , fonctionnaires du Gouvernement , ont l'honneur de porter à la connaissance de leurs camarades que,ayant vu la nécessité de développer leur capacité intellectuelle , ils ont fondé , à partir du 7 Août 1927 , une école sous la désignation de " LA LUMIERE SORT " où ils se réuniront entre eux aprés leur travail . Les heures des cours sont fixées de 4 heures jusqu'à 7 heures du soir .

Les études qu'on donne pour le moment sont le gueuëz , l'amarigna , le français et le calcul .

Pour tout renseignement complémentaire s'adresser à Atto Mettaferia Weldé à côté du pont Ras Mekonnen.

La Lumière sort .

የእጅ ሰዓት ዝኒት



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሁሉ ሰዓት መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ፲ መሐ ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት ።	፱ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፮ ብር ።
ዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
በሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፭ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፭ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፭ ብር ተኩል
አቡጀዲ መንጸር	፩ ኮረጃ	፻፴፭ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፴፱ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፳፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፲ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፰ ብር
፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፵፩ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፰ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፩ መ

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲፱ ፍራንክ ፲፰
አንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ ፱
በአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፲፰ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፭ ብር

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚሀ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን [illegible]

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

ሩግቢ

RUGBY

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድሪስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ኳኬ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዮን አቶመቢል የፊታውራሪ ዶሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፤ ባለ አጉበርና አጉበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፤ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሽው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፤ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

COGNAC S. E. A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክስል የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

Berliet



ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ አቶሞ ቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

ኤን ቤ ኤዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጆጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶክለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶክለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት ጎልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፡ ቁጥር ፴፬
3 me ANNÉE № 34

ሐሙስ ነሐሴ ፲፱ ቀን ፡ ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 25 AOUT 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፊለን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ጥያቄና ታሪክ

በኋላ ለቀረች መንግሥት መንግሥቷና ሕዝቧ እንዲያድጉ ምን ያስፈልጋታል? ነፃነት ያላቸው ፳፯ የሚያህሉ መንግሥታት በዓለም አሉ በስልጣኔ ከነሱ ወደኋላ ያስቀሯት ምንድነው? ከፍ የሚያደርግ እውቀት እንድታገኝ ትምርት የተባለ መሳርያ እንደሚገባ ሁኖ እንዳይሰፋ የዘጋው ማን ነው ። ለዚህ ጥያቄ አስተካክሎ የሚመልስ የብርሃንና ሰላም ልጅ እጅግ የተመሰገነ ብልህ ሰው ውነ ።

ብልሁ ፈታውራሪ ደሬሳ የጻፉት ሁሉ ልብ የሚነካ ነውና ከምርጦች ቃሎቻቸው ይልቁን ከመመኘት እገሌ ነው ብላችሁ ብትገልጡት በየሥራው ኃላፊነት ሹም የሚሉትን ቃሎች እጅግ ይቀሰቅሳሉ ። በዓለም እንዳሉ ጓደኞቹ ዋናው ፈሪጁ ብርሃንና ሰላም ነው ። ግን ለኃያላኖቹ ሲሾሙና ሲሸለሙ መልካም ምኞቱን ያቀርብላቸዋል ፡ ሲታመሙና ሲሞቱ ያጥናናቸዋል ። አሁን ልጅ ስለሆነ ይሆናል እንጂ ለወደፊቱ እንደሚፈርድባቸው ጥርጥር የለበትም ። በገነኑ አገር የገነኑ ስሞችና ጋዜጦች በተቀር ፡ ሕዝቡስ ቀምበሩን ወደ ሹሞቹ እንደ መጣል ያደርጋል ። ግን በኋላ ለቀሩት መንግሥታት ነገራውቹ እጅግ ያስደንቃል ። ሎሌው ሲነቃ ጌታው ይተኛል ።

እኔ የታየኝን ያህል እንዳልፈርድ ገና ልጅ ነኝና አይገባኝም ። ግን ታሪክ መመርመር ለሁሉ ይበጃል ። እንዳሉት ብልሁ ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ፡ ሥጋችን አለ ዓይን ፡ አእምሮዋችን አለ ታሪክ ፡ ሁል ጊዜ ጨለማ ናቸውና ደግ ቢሆን ወይም ክፉ ለመከተል አለ ታሪክ እውነተኛ ሚዛን የለም ። ስለዚህ የሚገባውና የሚሆነውን ትልልቆች በብሩህ ልቡናችሁ አጥርታችሁ ልትፈርዱት ለማነቃቃት ስል ስለዚህ አካሂድ የዓለም አስተማሪዎች (መሪዎች) የሆኑትን የሁለት መንግሥታት ታሪክ በጣም አጭር ረድፍ ጽፌ ለክቡራን ብርሃንና ሰላም ወዳጆችና አንባቢዎች ልልክላችሁ አሰብኩ ።

ሰው በዚህ ዓለም ሲፈጠር በአንድ ገዢ ተመርቶ እንዲገዛ ተመድቧል ። የአኳኋኑ ደረጃ መሰላል ግን በየነገዱ ብዙ ልዩነት አለው ። ሕዝቡ ዓይኑን ሲያነቃም በየጊዜው ይለዋወጣል ። እንደታሪኩ ዋኖቹ የአገዛዝ አኳኋን ፫ ጊዜ ተለዋውጧል ። ፩ኛ የአሶሉቶ መንግሥት ንጉሡ እንደፈቀደው የሚያደርግ ፪ኛ ፌውዳለ (ጉልት) (ስልጣን በከበርቴ ልጅ) ነበር ይህ ሥራ ከዓለም በሞላ በእስያ የሚገኙ ፮ ትንንሾች መንግሥታት አፍጋኒስታ ሄጂያድ አሲር አማን ዬመን የሚባሉ እስላሞችና ስያም የሚባል ቡዲስቲ ብቻ እስከዛሬ ድረስ ቆይቶዋል ተብሎ በታሪክ እንደተጻፈ አለ ።

ከዚህ በላይ የተጻፉ ሁለቱ ሕጎች መንግሥት አያሳድጉ ለሕዝቡ አይጠቅሙ ፡ ለማናቸውም ትልቅ ጉዳት ፡ ጭርሱን ፈጽመው ወደ ኮሎኒያ የባዕድ ተገዢ ለመሆን የሚጥሩ መሆናቸውን ለአንዳንድ ብልሆች ሕዝቦች ተገለጡላቸው ለጊዜው አሳባቸውን በጋዜጣና በዲስኩር (ስብከት) እያደረጉ ለሕዝባቸው ማካፈል ምሉ ነፃነት ቢያጡ እንኳ ማኅበር እየሆኑ ከብዙ መከራ ጋራ በብዙ ልዩ ልዩ ብልሃትና ረቂቅ ፖሊቲክ ተጣጥረው የመንግሥታቸውን አኳኋን እስከ መለወጥ ደረሱ ።

መጀመሪያ የዓለም መምሕር ፡

ከሁሉ በፊት የእንግሊዝ ሕዝብ መንግሥት ማለት የአንድ ዓይነት ሕዝብ ማህበር ክብረታቸው የማህበሩ አለቃ የደማቸው ምልክት ሰንደቅ ዓላማ መሆኑን ተረዱትና ሁሉ በትክክል አብረው ባቆሙት ሕግ እንዲገዙ ፈልገው በሺ ፩፻፲፭ ዓ ም (ኤው ቀ) በእንግሊዝ አገር ብዙ ሁውከት ተነስቶ ነበር ። ያን ጊዜ በእንግሊዝ መንግሥት ጆባኒ ሴንሳ ቴራ ዮሐንስ አለ መሬት

የሚባል ንጉሥ ነበርና ፣ የሕዝቡን ሁከት እንዲያበርድ አሰባ በቸውን ተቀበለ ። ከዚያ ወዲያ ሕዝቡ ኰስቲቱሲዮኒ የሚባል መንግሥት አቆሙ ። (ኰስቲቱሲዮኔ ማለት የአሶሉቶና የጉልት መንግሥት ሥራቱን የሚያጠብ የስልጣኑን ፍርድ የሚቃወም የበላገሮቹን ነፃነት ሥራት የሚዋስ ሕግ ነው) ለዚሁ ሥራ ፓርላሚንቶ የሚባል ቤተ መንግሥት አቁመው በሁለት ካሜራ ከፈሉት አንዱ ለዴፑታቲ የተባሉ የሕዝብ እንደራሴዎች ሁለተኛው የሴናቶሬ የተባሉ በትልቅ ሞያቸው የተመረጡት ለማናቸውም ሥራ ነገር ሁሉ በትክክል እያስኬዱ የሚፈጽሙና ሕግ የሚያቆሙ አደረጉ በአእምሮ በመታመን በመቻል የበለጡትን መርጠው የመንግሥታቸው እንደራሴዎች ሚኒስትሮች ሹመው ጋቢኔቶ የሚባል ቤተ መንግሥት አቆሙ ። እንደገና ከተመረጡት የተመረጠ የመንግሥት አለቃ ጠቅላይ ሚኒስትር ሾሙ ማናቸውም ሥራ በነዚሁ ሹማምንት ካለቀ ወዲያ ንጉሡ ይፈርማል ። የከበርቴ ልጅም በአእምሮው (እውቀት) ካልተመረጠ (መንግሥት የቆረጠለት ደመወዝ ይበላ እንደሆን ነው እንጂ) በማይችለው በመንግሥት ሥራ ገብቶ ሊያበላሽ አይችልም ። ግን ትንሽ እንደቆዩ ብዙ ነገሥታቶች ይህንን ሕግ ደምስሰው የአሶሉቶ ስራት ሊመልሱ ሞከሩ ። ይልቁን ቀዳማዊ ንጉሥ ካርሎ ከሕዝቡ ብዙ ተቃውሞ ነበርና በሺ ፮፻፵፱ ዓ ም ኤው ቊ ለሞት ፈርደው አሳልፈው ሰጡት ። ዳግማዊ ንጉሥ ካርሎና ዳግማዊ ንጉሥ ያዕቆብም እንደዚሁ ሞከሩትና ሳይሆንላቸው ቀረ ፫ኛ ጉሌልም ሲነግሥ ግን ከሕዝቡ ፈቃድ እንዳይወጣ የሕዝቡ ነፃነት ያቆሙትን የፓርላሚንቶ ሕግ እንዲያከብር በፊት ምሎ ነገሠ ይህ ንጉሥ የደግነት ሥራው በጣም አደገ ። ስሙም ብዙ ገነነ ። ከዚያ ወዲያ እንግሊዝ ከዓለም መንግሥታት ሁሉ መጀመሪያ ደረጃ መንግሥት ሆነ ። ሕዝቡም ከልክ ያለፈ በለጠገ ። ነገሥታቱም ከሁሉ ነገሥታት ከፍ ያሉ የእንግሊዝ ደምም ከሁሉ የከበረና የታፈረ ሆነ ። በዓለም አንጻር እንደ ውድማ የማታህል ደሴት ስትሆን የዓለም ሲሶ ልትሆን ትንሽ የጐደለባትን መንግሥት ለመግዛት በቃ (ማለት ዛሬ ቢለዩም አሜሪካ ስታቲ ኡኒቲ እንግሊዞች መሆናቸው አልቀረም) ነገሥታቱም ከሕዝቡ በአንድነት የተመሰረቱ ስለሆኑ ጃፖን በተቀር ዘውዱን ከልጅ ልጃቸው ያሶፈ ከነሱ የሚበልጥ ሌላ የሚገኝ አይመስለኝም ።

ሁለተኛ የዓለም መምሕር ።

የፈረንሳዊ መንግሥት በ፲፯ መቶኛ ዓ ም እርሻው ኢንዱስትሪና ንግዱ ኤኮኖምያውና ፖለቲኩ ሰፍቶ በህንድና በአሜሪካ ብዙ ትልልቆች ኰሎኒዮች አድርጎ ነበር ። ግን ብዙ ጊዜ ሳይቈይ ባራተኛ ንጉሥ ኤንሪን (ሺ፭፻፹፫ - ሺ፮፻፲ ዓ ም) በ፲፫ኛ ንጉሥ ሉዊጂ (ሺ፮፻፲ - ሺ፮፻፵፫ ዓ ም) በ፲፬ኛ ንጉሥ ሉዊጅ (ሺ፮፻፵፫ - ሺ፯፻፲፭ ዓ ም ኤው ቁ) ብዙ ተለዋወጠ ከበርቴዎችና ካህናቶቹ በአሶሉቶና ጉልት አገዛዝ ጊዜ ብዙ ተመቻቸው ፣ ሥልጣን ሁሉ ተሰብስቦ ወደ እጃቸው ገባ ሕዝቡ ለከበርቴውና ለካህናቱ ማሳደርያ የሚከፈለው የነበረ ግብር ሲበዛ መንግሥት እየሰነፈ ሊሄድ ጀመረ በ፲፯ኛና በ፲፰ኛ መቶኛ ዓ ም ግብሩ በጣም እያደገ ሄደ ፣ ሶስተኛው መንግሥት የተባለው ወረዳው ገባር ሕዝብ ቀምበሩ በጣም ሲከብደው ከከበርቴ መንግትና ከቤተ ክህነት መንግሥት ጋራ በጥልቅ ተጣላ ፣ ይልቁንም በእኩሌታው በ፲፰ መቶኛ ዓ ም ፲፮ኛ ንጉሥ ሉዊጂ ለቤተ መንሥት ይወጣ የነበረ ገንዘብ ከልክ አሳልፈው የከበርቴ ልጅ በሆነ ሁሉ ደመወዝ አወጣለት ሕዝቡ በዕውቀት የበሰለ ፣ የእንግሊዝ እንፍሉዌንስም ተሰምቶት ነበርና (የነሱን መንገድ ለመከተል) ከባለሥልጣኖቹ ጋራ (በሺ፯፻፹፱ ዓም ኤው ቁ ነፃነት እርነት ፣ ትክክልነት ፣ ወንድማማችነት ፣ በሚሉት የማይሞቱ ቃሎች ስም ሪቮሉሲዮን አነሳ በዜሁ ጦርነት ውስጥ የሴቶቹ ሳይቀር ብዙ ደም ፈሰሰ ። ሮላንድ የምትባል ሴት ወደምትደበደብበት ስፍራ ስትደርስ እንዲህ ብላ አደነቀች ወይ ነፃነት በአንቺ ስም ስንት በደልና ግፍን ዓመጽ ሊደረግ ነው ። ፲፮ኛ ንጉሥ ልዊጂ ሳይቀር ከነቤተዘመዶቹ በሺ፯፻፺፫ ዓም ኤው ቊ ፈርደው ገደሉት ። በየቀኑ የሰው ደም እንደወኃ ይጐርፍ ነበር ግን የእግዚአብሔር ስራ ድንቅ ነውና ፣ አንድ አርበኛ ወታደር በናፓርተ የሚባል ባለ ትልቅ አእምሮ ፣ ለጊዜው አገሩን ቀጥ አድርጎ ያዘው ግን እሱም ኰንስል ተብሎ ከተሾመ ከ፱ ዓመት በኋላ ፣ ሊገድሉት በቃጡት ሰዎች አመኃኝቶ በተንኰል አድርጎ ፣ ቀዳማዊ ናፓሌዎን ተብሎ ነገሠ ። ስልጣንም ለዘመዶቹና ወገኖቹ ብቻ ሰጣቸው ። (እርያ ታጥባ በጭቃ ትገባለች ፣ ውሻ ትፋትዋን ተመልሳ ትበላዋለች እንደሚሉት ምሳሌ ደረሰቸው ።) ግን እውነት ናፖሌዎን የማይሞት ቁምነገር ሰርተዋል ። የባላገሮቹ ትክክልነት ፣ የአገር አውራጃዎች አስተዳደር መሻሻል ፣ ኢንዱስትሪ ፣ ንግድ እርሻ ማስፋት ፍትሐ ነገሥት አውጥቶ ማሳተም ባንክ መትከል ለሕዝብ ትምህርት ቤት ማቆም መንገድ ማውጣት የአገሩን የክርስትና ሃይማኖት (የካቶሊካውያን ቤተ ክርስቲያን) መዘርጋት እንደዚህ የመሳሰሉ ሌሎች ብዙ ስራዎችም ሠራ ስለሆነም በፊት እንዳመለከትኩት እንደነ እንግሊዞች በሕዝቡ ስላልተመሠረተ ለጊዜው ቢያብብና በሞላ ዓለም እንደፀሐይ ቢታይ በኋላ ለዘሩ አልተመቻቸውም የፈረንሳዊ መንግሥት ከሺ፯፻፺፪ ዓም (ኤው ቊ) ፫ ጊዜ የሬፑብሊክ ፣ ፫ ጊዜ የመናርኪክ (የንጉሥ) አገዛዝ እየሆነ ተለዋወጠ ። ከሺ፰፻፸፭ ዓ ም (ኤው ቊ) ወዲህ ግን ፣ በሬፑብሊክ ዴሞክራቲክ ስልጣን በሕዝብ እጅ አገዛዝ ሁኖ ቀጥ ብሎ በእውቀት የበለጠ እየተመረጠ እስከ ፯ ዓመት ድረስ የሚሾም ፕሬሲዴንት አድገው ምናልባት እንኳ ትንንሽ ልዩነት ቢኖርበት በፊት እንዳመለከትኩት መሰረቱን እንደ እንግሊዞች አገዛዝ አደረጉት ።

የፈረንሳዊ ሪቮሉሲዮን ለመላ ዓለም ነው እንጂ ለኤውሮፓ መንግሥታት ብቻ አይደለም ሥራቱና የአገዛዙን ደምብ የለወጠው ፣ ደግሞ ቀጥሎ ለተጻፉ መንግሥታት ከፍ ባለ መዓርግ ደረጃ አደረሳቸው ፣ ያልተከተሉት ግን እኩሌታቸው መንግሥታቸው ወረዳ ፣ ሕዝባቸው ድኃ ሁነው ቀሩ ። እኩሌታቸው አሁን ለመከተል ጀመሩ ለምሳሌ ትናንት በመስኮብ የነበረ መዓትና ፣ ዛሬ በቺና ያለ መከራ ሁላችን እናውቀዋለን ። እኩሌታቸው ጭርሱን ነፃነታቸውን አጠፉ ። አንድ አንድ ብርቶች ግን በስንት መስዋዕት ነፃነታቸውን አስመልሰው ለዚሁ ፫ኛ መንገድ ተከትለው ማለፍያ ይራመዳሉ ሁሉ ቀርቶ ትርኮች እንኳ ያነን የማይነቀነቅ ትልቅ ብረት የልምድ ቀምበራቸው ጥለው ፣ ዛሬ

ጥዋት ተነስተው የደረሱበትን ደረጃ መዓርግ ለዓለም በሞላ አስደንቆታል ኢጣልያ እንኳ አሁን ሶቻሊስቲ ኮሙኒስቲ ፡ ማሶኖርያ ፤ ፋሺሽቲ እየተባሉ የወገን ስምና በትንንሽ ነገር ቢለያዩ እንኳ መሰረታቸውስ ያው ዴሞክራቲክ መንግሥት የተባለ አገዛዝ ነው ። በዚሁ ዓለም ነፃነት ያላቸው መንግሥታት ፡ የሁለቱን መንግሥታት የተከተሉትን ፷፰ መንግሥታት አከፋፈል ፡ በሚከተለው ስታትስቲ እንደተጻፈ ነው ።

ሞናርኪክ ዴሞክራቲክ	ሬፑብልክ ዴሞክ	ሞናርኪክ ዴሞክራቲክ	ሬፑብ ዴሞክራቲክ
ኤውሮፓ		አሜሪክ	
እንግሊዝ	ፈረንሳዊ		ስታቷ ኡኒቷ
ስፓኝ	ጀርመን		ሜሲክ
ኢጣልያ	ስቢጸራ		ኒካራጉዋይ
ሞናኮ	አንዶራ		ፓናማ
ሉሴንቡርግ	ፖርቶጋሎ		ጉዋቴማላ
ቤልጂክ	አውስትርያ		ሆንዱራስ
ኦላንድ	ቸኮሰለባኪያ		ሳን ሳልባዶር
ሮማንያ	ኡንጌሪያ		ኮስታሪክ
ይጉስ ላብያ	ግሪክ		ብራሲላ
ቡልጋርያ	አልባንያ		አርጀንቲና
ስበጽያ	ሞስኮብ		ቺለ
ኖርበጂያ	ፖሎኒያ		ኮሎምብያ
ዳኒማርክ	ኤስቶንያ		በንጹዌላ
ኢስላንደ	ሊቶንያ		ኡሩጉዋይ
ሊክሕቴ ንስተ	ሊቱዋንያ		ፓራጉዋይ
ይን	ፊላንዲያ		ቦልብያ
ድምር ፲፫	ዶሚንጎ		ፔሩ
	ሳን ማሪኖ		ኤኳቶር
	ኡክራይና		ኩባ
	ሜመል		ሃዪቲ
	ደንዚክ		ድምር ፳
	ድምር ፳፩		

ሞናርኪክ ዴሞክራቲክ	ሬፑብሊክ ዴሞክራቲክ
እስያ	
ጃፖን	ቺና
ፔርሲያ	አርመንያ
ኩሩዴስታን	ቱርክ
ሜሶፖታሚያ	አርዘበይጀን
ኔፓል	ጆርጂያ
ድምር ፭	ኩባን
	ቴሬክ ድምር ፯
አፍሪቃ	
ግብጽ	ሊበርያ

ጠቅላይ ድምር ፳፩ ሞናርኪክ ዴሞክራቲክ ፡ ፵፱ ሬፑብሊክ ዴሞክራቲክ መሆኑ ነው ።

የዛሬ የዓለም መንግሥታት ሁሉ ፡ እንደቀድሞ አሳባቸውና አእምሮዋቸው በአንድ ጠባብ ሐሳብ የተዘጋ አይደለም ። የማይረባ ኑሮዋቸውና አሮጌ ልምዳቸውን በጥልቅ ለዋውጠውታል መሬት በፍጥነት የሚዞሩ መሰሪያዎች በመፍጠራቸው አዲስ ነገር ለማየትና ለመያዝ ቀናቸው ፤ ቀድሞ ወሬዎችና ጥበቦች ቀስ ብለው የሚዞረጉ የነበር ፡ ዛሬ በጥቂቶች ደቂቆች ስልኮች ቴሌግራሮች ፡ ጋዜጦች ፡ ከሁሉ መአዝኖች ዓለም ሰብስበው አምጥተው በአንድ አፍታ ይነዙታል ዛሬ የሚፈጥሩዋቸውን አዲሶች እውቀቶችና ጥበቦች አዲሶች መዝገቦችና የኢንዱስትሬፍሬዎች እጅግ በሚያስደንቅ ፍጥነት ይቀበሉታል ። ቀድሞ ብዙ መቶ ዓመቶች የሚያስፈልጉት የነበሩ ሥራዎች ፡ ዛሬ በጥቂቶች ዓመቶች ፡ በጥቂቶች ወራቶችና ሳምንቶች ይፈጸሙታል ። የዛሬ ሕይወት ከድሮ ብዙ የተለየች ሁና በብዙ ምቾት በልጥጋለች ። አሁንም ገና በአዲሶች ትውልዶች ተስፋ ያደርጋሉ እንጂ የኑሮን መሻሻል ፡ ትክክል ሁና በሁሉ መልክ ልትገባ የሚበቃ እውቀት አልተገኘም ይላሉ ።

የነዚህን ወግና ሥልጣኔ ተቃውሞ የማይቀበል መንግሥት ወዮለት ለስም ነፃነኝ ቢልም ነፃነቱ ከምንም አይቈጠርም የነሱን መንገድ ይዞ ካልገሰገሰ እስከመቸም ነፃነት የለም ።

በውቢቱ ዓለም የሚገባው ሥራ ሊፈጸም ፡ የተተከከለ የስልጣኔ ሥራ በጠነከረ ትምርት እንዲያድግ የሚያስፈልግ ደስታና ክብርም በፍቅር እንዲፈጸም ተስፋ እናደርጋለን ።

ሚከኤል ተሰማ

መልስ ።

ብርሃንና ሰላም በ፪ኛ ዓ ቁጥር ፵፺ አገረ ገዢዎች መኳንንቶች አገራቸው እንዲለማ ሕዝባቸው እንዲሠለጥንና እንዲበለጥግ እንደሚወዱ እርግጥ ነገር ነው ሲል ይመሰክራል ፡ ለዚሁ ግን ምን ማድረግ እንዲገባቸው ጠይቆ ፡ የጥያቄውን መልስ በምሉ ተስፋ ይጠብቃል ።

ብርሃንና ሰላም በዚሁ ቁጥር አገረ ገዢዎች ሕዝባቸውን የሚያስማማ ምክር ለመግለጥ ሶስት የበረቱ ቃላት ሊያሳስበን ይወዳል ።

፩ኛ ከብርሃንና ሰላም የተሰወረ የለምና አገረ ገዢዎች መኳንንቶች አገራቸው እንዲለማ ሕዝባቸው እንዲሠለጥንና እንዲበለጥግ እርግጥ ምኞታቸው መሆኑን ያስረዳናል ።

፪ኛ አገረ ገዢዎች አገራቸው እንዲለማ ሕዝባቸው እንዲሠለጥንና እንዲበለጥግ መመኘት ብቻ እንደማይበቃቸው ሲያስረዳንም ምን ማድረግ ይገባቸዋል ሲል ጥንቁቅ ጥያቄ ይጠይቃል

፫ኛ ፡ ይህነኑ ጥያቄ መጠየቁም ከጥልቅ ሐሳቡ እንደ ሆነ ሲያመለክተንም የጥያቄውን መልስ በምሉ ተስፋ ይጠብቃል ፤

ለዚህም የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ከዚህ ቀደም የሚበቃውን መልስ እንዳቀረቡ በልዩ ልዩ ሥፍራ ተመልክተናል ነገር ግን እጌሌ ከኔ በፊት አስቀድሞ መልከከሙን ቃል ተናግሮታልና አፈን መከራት አይገባኝም የማይባል ስለሆነ እኔም የጥያቄውን መልስ ያቅሜን ያህል ለብርሃንና ሰላም እንዳቀርብ ፍቃዳችሁ ይብን ስል በማክበር እለምናለሁ ፤

የብዙ ቤተ ሰዎችና የብዙ ከብት ጌታ ጠቀሜታውን አውቆ ቤተ ሰዎቹና አሽከሮቹ ከብቱም ለርሱ ያለውንም ሁሉ የጠገበና ያማረ ፣ የሰባና የደነደነ ፣ ሊሆኑለት ቢወድ ምኞቱ ክፉ አይመስልም ፡፡ አገረ ገዢዎችም በደኸየና በደረቀ አገር የተሾሙ ጊዜ በገዛ ቤታቸው ሳይቀር ድህነትና ችግር እንዲሸ ቀዳደምላቸው ተረድተው አገራቸውና ግዛታቸው እንዲለማና እንዲበለጥግ መውደዳቸው ወይም መመኘታቸው ደግ ኃሳብ ነው ። ሐዋርያው ግን እንዲህ ይላል ፣ ወንድም ወይም እህት አራቄታቸውን ቢሆኑ የዕለት እንጀራቸውንም የሚሹ አንዱም ከላንት ቢላቸው በደህና ሂዱ ይሙቃችሁ ጽገቡም ሥጋቸው የሚሻውን ግን ካልሰጧቸው ፣ ምን ይጠቅማል ያዕ ም ፪ ቍ ፲፮

የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ከኔ በሚበልጥ ሳይመለከቱት ይቀራሉ ብዬ ሳልጠረጥር ምኞት ተጀምሮ ካልተፈጸመ ምኞት ሁኖ መቅረቱ ነውና የምኞት መጨረሻ እንዴት ሊሆን እንዲገባው ሲያስተምሩን ልዑል ጌታዬ የተናገሩትን ቃል አስታውሳለሁ፤

የቅዱስ ጳውሎስ የፍቅር ሐዋርያ ተከታይ የሆኑት የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፲፱፻፲፩ ዓ ም አደን ደርሰው ድሬ ደዋ በተመለሱ ጊዜ ከዚያ ለነበሩ መኳንንትና ሕዝብ እንዲህ የሚል የተስፋና የምኞት ቃል ሰበኩላቸው ።

የኔ ኃሳብና ምኞት ፍቅር ዘርቼ ፍሬውን ለመልቀም ነውና ሳትቸኩሉ ዝም ብላችሁ ከተመለከታችሁ የተናገርኩትን መመርመር ትችላላችሁ።(የልዑል ተፈሪ መኰንን የአደን መንገዳቸውን አኳኋን እይ) ይህ ተስፋና ምኞት ግን እንኳንስ እንደተናገሩት ሊቀር ከቶም አልዘገየም ። ይኸው ዋና የፍቅራቸው መግለጫ የድንቁርና ጠላት የድህነትና የችግር ወደረኛ የሆነ የፍቅር ዘር የሚዘሩበትን እርሻ ደኑን አስመንጥረው ድንጋዩን አስቆፍረው በ፲፱፻፲፯ ዓ ም ያሠሩትን ተማሪ ቤት የዘሩ ወራት ደረሰና ፣ ሞተውን ሕሊና የሚያንቀሳቅስ ሕያው በሆነና ፍቅር በሞላው ቃላቸው እንዲህ እያሉ ዘሩን መዝራት ጀመሩ ። አገሬን እወዳለሁ ማለት ያፍ ልማድ ነው ፣ አገሩን የሚወድ ፍቅሩን አውጥቶ በሚሠራው ሥራ ላይ ሲያሳይ ነው የሚታወቀው ፣ ብርሃንና ሰላም መጀመሪያ ቁጥር ፲፱ እይ መቸስ በበረከት የዘራ በበረከት ያጭዳል ነውና በበረከት የዘሩትን የፍቅር ዘር እንደተመኙት ሆነላቸው ፣ በመልካም ምድር የወደቀ ዘር ያደገ የለማም ፍሬ አፍርቶ አንዱም ሰላሳ ሁለተኛውም ስልሳ ሶስተኛውም መቶ እንደ ሰጠ ማር ም ፬ ቍ ፰፤

ከሰላሣ እስከ መቶ ሰማንያ የሚያህሉ ተማሮች ለምልመው አብበው አፍርተውቸው ፍሬውን ለመልቀም ደረሱና ደስደስ እያላቸው መከሩን ለማየት ለተሰበሰቡት አገረ ገዢዎች መኳንንት እንዲህየሚል ቃል ተናገሩ ይህን የውጭ አገር ቋንቋ ትምህርት ቤት ማቆሜ ለኢትዮጵያ ትልቅ ጥቅም መሆኑን ስለ ተረዳሁት ነው ይህም ትምህርት ቤት ሲቆም ሰላሳ ልጆች ብቻ ነበሩ አሁን በሁለት ዓመት ፱ የሚያህሉ ልጆች እንዲማሩበት መሆኑ ደስ የሚያሰኝ ስለ ሆነ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ይህንንም ብለው ብቻ አልጨረሱም አገረ ገዢዎችንም ደግሞ በተለየ የትምህርትን ጥቅምነት እያወቁ በየግዛታቸው ትምህርት ቤትን እስኪያቆሙ በተስፋ እንዲጠብቋቸው ያስታውቋቸዋል እንጂ ብርሃንና ሰላም ፫ኛ ዓ ቍ ፳፫ እይ እንግዲህ ብርሃንና ሰላም አገረ ገዦዎቹን አገራቸው እንደለማ ሕዝባቸው እንዲሠለጥንና እንዲበለጥግ እነደ ሚወዱ ጥርጥሬ የለበትም ሲል በድፍረት የመሰከረላቸውን ምስክር ከዚህ በላይ የተጻፈውን የልዑልን ፈቃድና ምኞት ፣ የምኞታቸውንም አፈጻጸም አይተው ካልተማሩና ካላደረጉ እንደሚወዱ ማለት በሐሳብ ውስጥ ያለ የምኞት አገባብ ነውና ፤ እንዲያው ላይደረግ እንደሚወዱ ቢባልላቸው ሕዝባቸው ምንም አይጠቀምበትም ። ሁለተኛም ወዳጆቻቸውና እማኞቻቸውን ብርሃንና ሰላምን ሐሰተኛ ያደርጉታል ሶስተኛም የኢ መ አ ወ ል ተ መ ዕዝራ ልቡን አዘጋጅቷልና የእግዚአብሔርን ሕግ ለመመርመር ለማድረግም ፤ ትእዛዙንና ፍርዱን በእስራኤል ላይ ያስተምር ዘንድ ዕዝ ም ፯ ቍ ፲ እንደ ተባለ ማድረግን ጭምር እያሳዩ ፣ ስለዚህ እለምናችኋለሁ እኔን እንድትመስሉ ፩ቆሮ ም ፬ ቍ ፲፮ ኢያሉም በተስፋ ሲጠብቁ ምኞታቸውና ማድረጋቸውን የሚከተል ሲጠፉ ጊዜ ትእዛዝን መተላለፍ ነውና ፤ ምን ትሻላችሁ በበትርን ልምጣባችሁ ወይም በፍቅርና በየውሀት ፩ቆ ም ፬ ቍ ፳፩ የሚል ኃይለቃል ጥያቄ ሳይመጣ ፡፡ አገረ ገዦዎች አገራቸው እንዲለማ ሕዝባቸው እንዲሰለጥንና እንዲበለጥግ በእውነት ፈቃዳቸው ከሆነ ብርሃንና ሰላም የልዑል ጌታቸውን አደራረግ በፍጥነት እንዲከተሉ እንጂ በምኞት ብቻ እንዳይቀሩ ያስጠነቅቃቸዋል ከ፲፱፻፲፯ ዓ ምሕረት ጀምሮ ብርሃንና ሰላም የሚበልጠው ትምህርቱና ምክሩ ስለ ሀገረ ገዦዎች መኳንንትና ስለ ሕዝብ ስለትምህርት ቤቶችና ስለ ልዩ ልዩ ሥልጣኔ አኳኋን ነውና ለዚሁ ብርሃንና ሰላም ፫ዓ ምሉ ካስተማረው ትምህርት የሚሻል መልስ ለማቅረብ ሐሳቤ አይፈቅድልኝም ፣ ነገር ግን አንድ ነገር ብቻ ላስታውስ እወዳለሁ ፣ አገረ ገዦዎች መኳንንቶቻችን ዳዊትን መድገም ያዘወትሩና የነፍሳቸውን ረድኤት የሚሹ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ብፁ ናቸው ለማለት በደፈርሁ ፤ ስለዚህ እንደ ቀድሞ ዘመን መኳንንት ጻፍልኝ አንብብልኝ ተርጉምልኝ ባዮች እጅግ አይደሉምና ሥጋ ከነፍስ ከተለየ በኋላ ሕያው ሆኖ ለመኖር የማይቻል ስለሆነ ለነፍስና ለሥጋ የሚሆነውን ምክርና ተግሣጽ ያለበት ብርሃንና ሰላምንም ደግሞ እንደማንም ጋዜጣ ሳይቆጥሩት ማንበቡን ቢያዘወትሩ በልዩ ልዩ ትምሕርት ላይ አገራቸው እንዲለማ ሕዝባቸው እንዲሠለጥንና እንዲበለጥግ ምን ማድረግ እንዲገባቸው በትክክል ይገልጥላቸው ነበር ።

ጽሕፈትን ከማንበብ የሚገኝ ፍሬ እጅግ ብዙ ስለሆነ መጻሕፍትን ማንበብ የህዋሳት አውድማ ይባላል ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ትምሕርት የሆኑ ክቡራን አገረ ገዦዎች መኳንንቶቻችን አገራቸው እንዲለማ ሕዝባቸው እንዲሠለጥንና እንዲበለጥግ እንደሚወዱ ብርሃንና ሰላም የመሠከረላቸውን ምስክር ቀላል እንዳይመሥላቸው በጣም ትልቅ ነውና የኔ እንዳላቸው የኛ ብለው እንዲገነዘቡትና ትምሕርቱን ከጀመረበት ቀን ጀምረው እንዲመለከቱት ክቡር ፈቃዳቸው እንዲሆን እየለመንሁ ፣ ሜን እልላቸዋለሁ ፡፡

ብርሃንና ሰላም ይህነኑ ጥያቄ ጠይቆ ችላ ሳይል መልሱን በምሉ ተስፋ መጠበቁ የጠየቀው ጥያቄ አገረ ገዦዎችና ሕዝቡን የሚያስማማ ጥልቅ ሐሳብ ስለሆነና ይህ የተፈጸመ ጊዜ ለኢትዮጵያ ዋና የሥልጣኔዋ ምልክት መሆኑን ሲያስረዳ ነው እንግዴህ ስለ ሕዝብና የሕዝብ ጠባቆች አኳኋን ፫ዓመት ያህል እያለፈ ያስተማረውን የድካሙን ፍሬ ለመልቀም የትምህርት ፈተና ያደረገ ይመስላል ስለዚህ ብርሃንና ሰላምን ያህል መምሕር ለጥቅማችን ያቆሙልን የትምሕርቱ (ኤግዛሚኔሽን) ፈተና ዋናው ጠቅላይ ጌታችን የኢ. መ አ ወ ተ መ በብርሃንና ሰላም ውስጥ ካለው ምስጋናና ምረቃ አብልጨ ለማቅረብ ሐሳቤ ያነሰ ስለሆነ ብርሃንና ሰላም ያመሰገናቸውን ምስጋናና ምረቃ ፡፡ልዑልነትዎ ሲደርስ ኢትዮጵያ ወደ ፍጹም ብርሃን ደረሰች ማለት ነውና አዎን አሜን ይሁንልን ።

ዕድሜና ጤና ለግርማዊት ንግሥታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን ፤ ኢትዮጵያ ዘለዓለም ትኑር ።

ሻቃ መኰንን

ይህቺን ዓለም የሚከብዳት ድንቁርና ብቻ ነው ብሏል
የግሪክ ፈላስፋን ።

የጥበብ ጌጥ ደግነት የድንቁርና መጥፎነት ክፋት ናቸው ይላሉ ብዙ ሌሎች አዋቂዎች። ደግሞ ሰው በተፈጥሮ ባህርዩ ሕግን ሊከተል የተገደደ ነው እገሌ መልካም ነው እገሌ ክፉ ነው እያሉ ሰውን ለማመስገንና ለመስደብ እንደምን እንችላለን? ። የሰው ልጅ ሆኖ ፈጽሞም ጠቢብ ፈጽሞም ደንቆሮ የሆነ ይገኝ አይመስለኝም ። ደግሞየማየት የመስማት የማሰብ እድል ላለው ሰው ያለፈውን ዘመን ሰው ታሪክ እየመረመረ ባሁኑ ዘመን የሚሠራውን ነገር እያየ የሚመጣውን ዘመን አኳኋን እያሰበ የሰው ልጅ ፍጥረትም ይመስለው ይሆን? ። ፍጥረታችን ከንቱ ነው እንዳንል በሐሳባችን የተራቀቅን ዘለዓለማዊ ፍጥረቶች ነን። በፋችን ሙሉ ፍጹም መልክም ፍጥረቶች ነን እንዳንል እንኳንስ የደንቆሮችና ብልህ የተባሉትንም ሰዎች ሥራ ሲአዩት እጅግ የምናጸጽት ፍጥረቶች ነን ። ሰሎሞን የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው አለ እግዚአብሔርን መፍራት ያዘዘውን ሕግ ተጠንቅቆ መጠበቅ ነው ትልቅ ድንቁርና እግዚአብሔርን አለመፍራት ነው እግዚአብሔርንም አለመፍራት ሕጉን ተጠንቅቆ አለመጠበቅ ነው አባቶታችንም ሲተርቱ ደግ ለራሱ ክፉ ለራሱ ይላሉ ደግ መሆንም ክፉ መሆንም ምንም ለራስ ቢሆን ደግ ሰው እራሱን ደስ አሰኝቶ መሰሎቹንም ደስ ያሰኛል ክፉ ሰውም እንደዚሁ እራሱንም በድሎ ሰውንም ይበድላል ፡፡ቅዱስ መጽሐፍም እንደሚአስተምረን ደግነት ሕይወትን ስትሰጠን ክፋት ደግሞ ሞትን ትሰጠናለች ። ልቦና ለሰጠው ሰውማ ደግነት ሕይወት ስትሰጠን ክፋት ደግሞ ሞትን ሳትሰጠን ጊዜ እንደ ሕይወትስ ደስ የሚል እንደሞትስ የሚጠላ ምን ይገኛል የሰው ልጅ ተብሎ ከደግነት በቀር ክፉነትን እንኳንስ አንደኛዋ አመሉ ሊአደርጋትና ስሙአንስ ሊአውቀው ይወድ ነበር ነገር ግን የሰው ልጆች ስንባል ደግነትና ክፋትን እንደምን ለይተን እናውቃቸዋለን? ላንዱ የደግነት ሥራ የሚመስለው ላንዱ የክፋት ሥራ ይመስለዋል ። ላንዱም የክፋት ሥራ የሚመስለው ላንዱ ደግሞ ደግ ሥራ መስሎ ይታየዋል ። ባለፈው ዘመን ደግ ተብሎ የተሠራው በኛ ዘመን ክፉ መስሎ ይታያል ባለፈው ዘመን የተሰራውን ክፉ ነው የምንለውን ዛሬ ደግሞ እኛ መልሰን እንሰራዋለን ነገ ግን ባለፈው ዘመን አባቶቻችን እያወቁም ይሁን ሳያውቁ የሠሩትን ሥራ እኛ ክፉ መሆኑን እያወቅነው በዚሁም እየተጸጸትንበት እንደገና እኛ መልሰን ሥንሠራው ጊዜ የምን ይባላል ። የብልህነት እንዳይባል ብልህ የሆነ ሰው ክፋትን ሥራ ቢሠራ ብልህ ሊባል አይገባውም ብልህ ከሆነ ሞትን የምታመጣ ነገር ሊወድ አይችልምና በድንቁርና እንዳይባል የሚሠራው ሥራ ክፉ መሆኑን ተረድቶታልና ። እነሆ የሰው ፍጥረቱ ጎደሎ ይመስላል ምሉ ፍጥረት ሊባሉ የሚቻሉም እንስሶች ይመስላሉ ። የሰውም ክብረቱ ጎደሎ ፍጥረቱን በውቀቱ እያሙአላ ዝቅ ብሎ ካለበት ደረጃ ዕለት ዕለት ከፍ ከፍ ወደሚለው ደረጃ እያወጣ በመሄዱ ነው ። ይህ ሁሉ ሲሆን የሰው ልጅ ሲባል በዚች ዓለም የሚኖሩበት ጊዜ ፈጽማ ትንሽ ነች ይህቺኑ ትንሽ ጊዜውን የተቻለውን ያህል እየጣረ ለቁምነገር ካልዋላት ምንጊዜ ትልቅ ሥራ ሠርቶ ዝቅ ያለ ማዕረጉን ከፍ ወዳለው ማዕረግ ሊአደርሰው ይቻላል።

የሰው ልጅ ሲባል ጥበብን እንደ እህል ውኃ መፈለግ ይገባዋል ጥበብ ደግሞ ለፈለጋት ያለቺው ኑሮዋ ከኛው ጋራ ነውና መገኛዋ እሩቅ አይደለም ግን ላልፈላጋት ሰው በከንቱ ልትገኝ አትችልም። ድንቁርና ኑሮዋ ከኛ ጋራ ነው እሱአንም ለማግኘት ሮፍቶ መፈለግ አያስገድድም ድንቁርናን ከወደዱአት አውቃ ትመጣለች እንኳንስ ወደዋት ሳይወዱአት ሳይፈልጉአት ቅልብልብነቱአ ወሰን የለውምና ግድ ውደዱኝ ፈልጉኝ ስትል ትመጣለች ። የሰው ልጅ በባህርዩ በውቀት የተመሠረተ ፍጥረት እየሆነ ጥበብ መልክም ጌጡን ጥሎ ድንቁርና የውርደት ጌጡን ቢለብስ ይወዳል ። ግን የሰው ልጅ ምንም ባህርዩ እውቀት የተሰጠው ፍጥረት ቢሆን የባህርይ እውቀቱን በትምህርት ቤት ካልገራት የባህርይ እውቀቱን ድንቁርና እያሸነፈች ከሞት ማድረሱአ ውል ውል የለውም። ይህንም ለመሰለ ነገር ማስረጃ ብዙህ ምክር ሞልቱአል ከዚሁም አንድ ሁለቱን ሳይበዛ በጥቂቱ እናመለክታለን ። ትምህርት የተማረ ሰው ከሐሳቡ ጋራ መጫወት የለመደ ክፉና በጎን እውነትንና ሐሰትን ነገር በሐሳቡ እያመዛዘነ መፍረድ የሚችል ሰው ፤ ሰው በጁ ለሠራው ጣዖት መስገድ ከቶ አይሆንለትም ብቻ ካለመማር የተነሳ እንኳንስ ሌላ ሰው የሠራውን ይቅርና እሱው እራሱ ጭቃውን ጠፍጥፎ ብረቱን አቅልጦ ላሠራው ስዕል የፈጠረኝ ይህ ብሎ ይሰግድለታል ። ልጅነታቸውን በትምህርት ቤት የፈጁ ብዙህ ጥበብ ያወቁ ሰዎች ደግሞ መሰሎቻቸውን አዋርደው እራሳቸውን አክብረው የሚታዩበትን ነገር አጥብቀው ይፈልጋሉ ይህንም የመሰለ ሥራ የሚሠሩ በሥጋዊ መንገድ ብቻ ያሉ ሰዎች አይደለም በመንፈሳዊም መንገድ እንሄዳን የሚሉ ሁሉ ናቸው እንጂ ። መክብብም ብሏል ሁሉን አየሁት ሁሉም ከንቱ ነው ፡፡ ዳዊትንም ሰው ለከንቱ ፈጠርከው ብሏል ። እውነትም የሰው ፍጥረት እንዴት አያሳዝንም እንዴት ከንቱ መስሎ አይታይም ፤ ሰው ደግሞ ሆን ክፉ ከሞት አያል

ፍም እንደ ክርስቲያኖች መንገድ ደግ የሠራ የዘለዓለም ደስታ ወረሰ ፤ ክፉ የሠራም የዘለዓለም ስቃይን ይቀበላል ። ደግ ሠርቶ ደስታ ያገኘ እማረ ፡ ግን ክፉ ሠርቶ የዘለዓለም ለቅሶን የሚቀበል ደግሞ እንዴት የከበደ ኀዘን ይሆን ለሰው ልጅ፡ ይህንም ማለት በሰው ልጅ ኅሳብ ያለውን መከራ መናገሬ ነው እንጂ እውነተኛውን ነገር ለውቀቱ ለደግነቱ ወሰን የሌለው ዘለዓለማዊው አምላክ አይደለም አዋቂው ሰው ከናቱ ማህጸን ሲወጣ ክፉና በጎን ሳይለይ ማለት አእምሮ ሳያውቅ ይወለዳል ፡ እድሜውን ያረዘመለት እንደሆነ አእምሮ ካለማወቅ ወደ ማወቅ ደርሶ ከዚያም አልፎ እንደገና ወደ ልጅነት ባሕርዩ ተመልሶ በሽምግልና ብዛት ዝጋርቶ አእምሮውን አጥቶ ማለት ክፉና በጎን መለየት አቅቶት ይሞታል ።

የሰው ልጅ ሕፃን ሆኖ አእምሮ ባለማወቁ የሚጸየፈው አንድም የለም ሰው ሽምግሎ ሲዝጋር ምንም ቢሆን ሰው ሳያስይም አይቀርም ማለት ለሰው ልጅ ተወልዶ ከህፃንነት እነፍስ ማወቅ ከነፍስ ማወቅ ተመልሶ ወደ ነፍስ አለማወቅ ደርሶ እስኪሞት ልብ ብሎ ለተመለከተው ሶስት አይነት ትምህርት እናገኝበታለን ከዚህም የምናገኛቸውን ትምህርቶችሁሉም እንደሐሳቡና እንደመሰለው እንዲመረምራቸው ክቡራን አንባቢዎቼን ይቅርታ ለምኜ አልፋለሁ

የሰው ልጅ ጥበብን ስለምን ይፈልጋታል ምን ታደርግለታለች የዚህን መልስ የብርሃንና ሰላም ወዳጆች አስተካክለው ይጽፉልኛል በማለት ትልቅ ተስፋ አድርጌ ለነሱ አደራ ሰጥቻቸዋለሁ

ልሻን ወርቅ

ስለ ሹም ሽር ።

በነሐሴ ፲፮ ቀን ክቡር ፊታውራሪ አረጋይ አፈ ንጉሥ ተብለው የፍርድ ሚንስቴርነት ተሾሙ ። ክቡር ደጃዝማች አሰፋ ሉል ሰገድ–ማጂንና ጉልድያን ተሾሙ ። ክቡር ከንቲባ ማተቤ የፊታውራሪ አረጋይ የነበረውን ወንበርነት ተሾሙ ፡ ክቡር ብላታ ኅሩይ ወልደሥላሴ ብላቴንጌታ ተብለው የውጭ ጉዳይ ዲርክተርነት ተሾሙ ። ክቡር ቀኛዝማች ሞላ የከንቲባ ማተቤን ወንበርነት ተሾሙ ። ክቡር ቀኛዝማች ፋርቾ የቀኛዝማች ኃይሌ የነበረውን ወንበርነት ተሾሙ ። ክቡር ቀኛዝማች ባንት ይዋሉ የቀኛዝማች ሞላ የነበረውን ወንበርነት ተሾሙ ። ክቡር ግራዝማች ይገዙ የቀኛዝማች ፋርቾ የነበረውን ወንበርነት ተሾሙ ። ክቡር ባላምባራስ ቸርነት የባላምባራስ ኃይሌ ኪዳነ ቃል የነበረውን ወንበርነት ተሾሙ ፡ ክቡር አቶ ተሰማ የግራዝማች ይገዙ የነበረውን ወንበርነት ተሾሙ። ክቡር አቶ ዳዲ የባላምባራስ ቸርነት የነበረውን ወንበርነት ተሾሙ ። ክቡር ቀኛዝማች ኃይሌ ባላምባራስነት ተሾሙ ።

ብርሃንና ሰላም አዲስ ሹመትና መዓረግ ላገኙ መኳንንት እንኳን ደስ ያላችሁ እያለ የደስታ ምኞቱን ይገልጻል ።

ስለ ክብርት ወይዘሮ እታለማሁ ዕረፍት ።

ክብርት ወይዘሮ እታለማሁ ።

ክብርት ወይዘሮ እታለማሁ የክቡር አቶ ገብረ እግዚአብሔር ባለቤት በ፲፰፻፺፬ ሰኔ ፲፪ ቀን በሐረር ከተማ ተወልደው በተወለዱ በ፳፯ ዓመታቸው በነሐሴ ፲፯ ቀን ፲፱፻፲፱ ከሌሊቱ በአምስት ሰዓት ተኩል ዓርፈው በጴጥሮስና ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ ።

ብርሃንና ሰላም ለክቡር አቶ ገብረ እግዚአብሔርና ለወንድማቸው ለክቡር አቶ በየነ ለዘመዶቻቸውና ለወዳጆቻቸው ሁሉም እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

ማስታወቂያ

ከኔ ከሀብተ ሥላሴ ሎተሪ የገዛችሁ ሰዎች ለጊዜው የሚገዛ ስላልተገኘ ቀኑ ተለውጧል የቀኑም ልክ በሚመጣው ሐሙስ ይቆረጣል ብዬ አስታውቃችኋለሁ ።

ሀብተ ሥላሴ ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሁሉ ሰዓት መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የሚባል ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ፲ መሐ ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፰ ብር ፫ ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር ።
የ ዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
የ በሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ፫ ሩብ
የ ወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር ፫ ሩብ
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲፩ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲ ፮ ብር ፫ ሩብ
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፱ ብር
፡፡ ባለሰይጣን ፡፡		፻፵፬ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፴፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ ፡፡		፻፲፰ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል ፡፡		፻፳፰ ብር
፡ ባለአንበሳ ፡፡		፻፵፬ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፰ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፫
አንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ ፱
ባንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፴ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፯ ብር

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል ብቶለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

ሩግቢ

RUGBY

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው ።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዳልፊአ በቦስቶን በማድራስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፥ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዩን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጂሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን ኦቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሄስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፤ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሽው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፤ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክስል የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

Berliet



ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ ኦቶሞ ቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የማድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት ‑ አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፭
3 me ANNÉE № 35

ሐሙስ ነሐሴ ፳፮ ቀን ፤ ፲፱፻፲፱ ዓ ም ፤
JEUDI 1 SEPTEMBRE 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix."

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ብርሃንና ሰላም ፤ ቀሰቀሰው አዕብ ።

የብርሃንና ሰላም ወዳጆች በሞቀ አሳባቸው ስለ ቀሰቀሱን ትንሽ ለመጻፍ አሰብኩ ። ወዳጆችሁ ብርሃንና ሰላም ከከፍታ እየወጣ ከሜዳ እየሮጠ ከከተማም ከሀገር ቤትም እየዞረ ፡ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ለኢትዮጵያ ስማ ስማ እያለ ሲጠራ እንሰማለን እንዲህ እያለ ፡ ብርሃን ሳላችሁ በብርሃን እመኑ ። የሰላም ልጆች እንድትሆኑ ። ገንዘባችሁን ለእውቀት መዝኑ ። ከባዕድ እጅ እንዳትወድቁ ከጨከኑ ።

እንደዚህ እያለ ሲናገር ስንሰማው ቆይተን መንፈቀ ሌሊት ሲሆን እንቅልፍ ሸለብ አደረገኝ ፤ በሕልሜ ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽ ከሚኒስትሮቹ ጋራ ሁነው ለናታችን ኢትዮጵያ ከዓለም መንግሥታት የሚያስተካክላት ነገር በፍጥነት ልንሠራላት ይገባናል ብለው ሲነጋገሩ የሰማሁ መሰለኝ ። ኢትዮጵያ በመካከላቸው ከተፍ አለችና ለሁላችሁ የሚሆን ምክር ልስጣችሁ አለቻቸው ።

ልጆቼ ሆይ በፍቅር ተቃቀፉ ። በምክር ተደጋገፉ ። እንዳትጠብ ርስታችሁን አስፋፉ ። የእውቀት ብርሃን እስቲገባ አትረፉ ። ብላ ስትመክራቸው ቆይታ ፡ በተለይ ለሚኒስትሮቹ ልምከራችሁ አለቻቸው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ሁኖ ለሚወደው ደቀ መዝሙር እናቱን አደራ ብሎ ሰጠው ። ያ ደቀ መዝሙሩም የጌታውን ፈቃድ ፈጸመ ። እንደዚሁም ሁሉ ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽ የሚከብደኝንም ቀምበር እንድታቀሉልኝ አደራ ብለው በአዋጅ ሰጧችሁ ።

፩ኛ ፤ በመንፈሳዊ ነገር ከባድ ቀምበር አውልቃችሁ እንድትጥሉልኝ እጄን ዘርግቼ እጠብቃለሁ ።

፪ኛ ፤ በየሹመታችሁ የሚነካ ነገር በፍጥነት እንድታደረጁት ብዙ ተስፋ አለኝ ። የስልክና የፖስታ ሚኒስትርም በያውራጃው ስልክና ፖስታ ያስተክል ። ይልቁንም በትግሬ አውራጃ ፤ በአጋሜ ፤ በመዝብር ፤ በዓድዋ ፡ በአክሱም ፤ በሽሬ ፡ በወልቃይት ፤ በእንደዚህ የመሰለ ሁሉ ስልክ ሊተከልበት ፡ ፖስታ ሊመላለስበት ፤ እንዲያስፈልግ ይሰወርብህ ብዬ አልጠረጥርም ።

፫ኛ ፤ የጦር ሚኒስትር በሙሉ ኢትዮጵያ ያለ ብረት ተነጥዬት ፡ ሠራዊቱ ከነመኳንንቱ ቆጥረህ በያውራጃው የሚገባ ምስጋና ፤ ለክፉ ቀን የሚሆን ስንቅ ፤ ለማበጀት አትዘንጋው ። መቶ ሺ የሚሆን ሠራዊትም እድሜው ከ፳ እስከ ፴ ዓመት የሆነውን ወጣት ሰልፍ አስተምረህ ፡ የቆላውን ፡ የደጋውን ፡ አየር አስለምደህ በገራቸው ፍቅር የተቃጠሉ ሲጠሯቸው አቤት ሲያዟቸው ወዴት ፡ የሚሉ አዝጋጅተህ መኖር ይገባሃል አለችው ከ፴ እስከ ፵ እድሜ ያለው ጀግናም ፡ ብረቱ ቀልቀል ሳይሆን በያለቃው ተለይቶ ተቆጥሮ በሶስት ወር ሰልፉ እየታየ አዲስ አበባ መጥቶ ሊታይ አይደለም ። ከጦር ሚኒስትሩ የተሾሙት ፡ ሰልፍ የተማሩ ዞረው እንዲያዩና ላነሰው አክለው ፡ ለበዛው አጉድለው ፡ በያገሩ ክፍል ያለ ብረት እንዲያውቁት በጦር ምንስቴር የሚታዘዝ ሠራዊትም ከመንግሥት የዓመት ቀለብ ሊወጣለት ግድ ነው ። በሚኒስቴሩ ታዞ የዓመት ቀለብ ያልወጣለት ወታደር ግን በክፉ ቀን ክተት ያሉት እንደሆነ በፍጥነት ሊረዳ አይችልም ። ከመቶ ሺ ወታደርም በሞላው አገርህ እየለዋወጥህ አስቀምጣቸው ። ቤታቸውንም በየክፍሉ ይሥሩ ። ከእርሻ ፡ ከንግድም ፡ አይግቡ ። ቢሠሩም ለመንግሥት የሚሆን ነው ። ከ፵ እድሜ በላይ የሆኑት ግን በወር ተራ ሰልፍ እየተማሩ የመንግሥ ሞያ እየፈጸሙ ቢያርሱ ቢነግዱ ደግ ነው ። ብላ ስትመክረው ሰማሁ ።

፬ኛ ፡ ለሀገር ሚኒስቴርም እንዲህ ብላ መከረችው ፡ ልጄ ሆይ ቢሆንልህ አገሬን ሁሉ ዞረህ አይተህ ለሀገሬ የሚበጅ ነገር አድርግለት አለዚያ መቶ የሚሆኑ እውቀት ያላቸው ያገር

ልጆች በሞላው አገሬ ዞረው አይተው ጉዳቱና ጠቀሜታውን አስተውለው ጠፍ መሬት የሆነውንም እንዲለማ እያደረጉ ከብት ለማርባት የተመቸ አገርና እህል የሚበዛበት አገር በገብያ እንዲገናኙ እያደረጉ ፤ ለባላገርም እንደ እያሀገሩ ሀብት እየመዘኑ ከሻለቆቹ እየተማከሩ ባመት የሚከፈለውን ግብር እንደጊዜው ይሁን ። ከሚዘራበት ወራት ጀምሮ እስከ እህል መግባት ድረስ በመሬት የሆነ ነገር ይከልከል ። አራሹና ነጋዴ ወታደሩም በጽፈት ይለይ ሥራ የሆነም በደሞዘኛ እንጂ በባላገር አይሠራ ከዚህ ቀደም በባላገር የተሠራ ቤት አምሮ ሰው ሲቀመጥበት አላየሁምና ለወደፊቱ ይቅር ። ጠፍ መሬት ባለበት እንደ ሽሬና ወልቃይት አዘቦ ሌላም ይሆን የመሰለ አገርም ፤ እህል የሚሆን እህል አታክልት የሚሆን አትክልት ፤ ጥጥ የሚሆን ጥጥ በደሞዘኛ እያሳረስክ ሰዉ እንዲወጣለት አድርግ። እህልና ጥጥ የበዛ እንደሆነ ወርቅ መብዛቱን እወቀው ። አገሩን ፤ መንግሥቱን ፤ አባት እናቱን ፤ ሚስቱን ፤ ልጆቹን ፤ እየተወ ፤ ከሰው አገር እየሄደ ባመት ቢያንስ ቢያንስ ፴ና ፵ ሺ ወጣት ኀበዝ ጢስ ሁኖ የሚቀረው አያሳዝንህም ። ለእርሻ ማሰልጠኛ የሚሆን ሁለት መቶ ሺ ብር ብታወጣ ደግሞ ራሱን ችሎ ባምስት ዓመት አራት መቶ ሺ ብር ያላገኘህ እንደሆነ ምላሴ በጩርቅ ሥራው ። በእውቀት የሚመሩትም ፬ የሚሆኑ በትምህርት የበሰሉ ዲሬክተሮች ያገር ልጆች ያስፈልጋል ።

፫ኛ ፤ ለገንዘብ ምንስትርም እንዲህ ስትለው ሰማሁ በውራጃው ሁሉ ገቢ ወጪውን እንዲታወቅ አድርግ በየሻለቃው የገባ ወርቅም ከበዛው ቀንሰህ ላነሰው አክለህ አስተዳድራቸው ። በየከተማው የመንግሥት ግምጃ ቤት አሰርተህ ከገቢ ወርቅ ካስር አንድ ከዚያ ግምጃ ቤት አግባ ። ለመንግሥት ሰራተኞች ከዚያ ደሞዛቸውን ትሰጣቸዋለህ ። ደግሞ በየከተማው እንግዳ የሚያርፍበት ቤት ታሠራለህ በየከተማው አንድ የቋንቋ መምሕርና ሁለት ያማርኛ መምሕራን አሳድር ። ለአብያተ ክርስቲያናትና ለድልድይ ለምድር ባቡር መስሪያ ቢሆንም ከዚያ ግምጃ ቤት ይሆናል ሕዝቡም የመንግሥት ግምጃ ቤት እያዬ ተስፋው እየበዛ ይሄድ ነበር ። አሁን ግን አንዳንድ ገንዘብ ያላቸው የመንግሥት ሰዎች ከውጭ አገር ሰው አደራ ሲያስቀምጡ ሲያዩዋቸው ጥርጣሬ ይይዘዋልና በመንግሥቱ ሊታመን አይችልም ግምጃ ቤት ቁሞ በስርዓት ተዘጋጅቶ ሲያየው ግን አደራ የሚያስቀምጥም በእምነት ባስቀመጠ እርሻ አለማለሁ አታክልት አተክላለሁ መኪና አወጣለሁ ላለ ሰው በዋስ እየሆነ ይበደርና ይሠራ ነበር ። ሥራ የበዛ እንደሆነ ገቢ ገንዘብ ለመንግሥት ይበዛለታል ከተማውም እየለማ ይሄዳል ።

፬ኛ ፤ ለንግድ ሚኒስትርም ቀጥላ እንዲህ አለችው ። ልጄ ሆይ ልብ ለሁሉ አባል ሥጋ እየመነጨ እንዲመግበው ፤ አንተ ደግሞ ለሁላቸው ልጆቼ በደጋ በቈላ ያሉትን በንግድ እንዲገናኙ እያደረግህ በቀረጥ በየመንገዱ እንዳይጉላሉ የተደላደለ ስርዓት አውጥተህ ቀማኛ ሽፍታ በሚያስፈራ አገርም ደህና ጠባቂዎች አስቀምጠህ ገደል የሆነ እንዲደለደል ሜካ የሆ እንዲጻረግ አድርግ በየበሩም የተደላደለ ጉምሩክ አቁም እንነግዳለን ለሚሉ የውጭ አገር ሰዎችም አገርህን የማይጐዳ ውል እየተዋዋልክ ተቀበላቸው ይልቁንም የፋብሪካ ሥራ እናመጣለን ያሉ ይግቡ ፤ ያገርህ ልጆች ቤት ሰርተው እንዲያከራዩ ግድ በላቸው ። ገንዘብ ለሸገረው ማበደርም አይከፋም ካገርህ የሚወጣ እቃና ከውጭ አገር የሚመጣ እቃ ሲበዛ ገቢ ለመንግሥት ሊበዛ ነው ለዚህ የሚረዱህም እውቀትና ሕዝባቸውን መውደድ ያለባቸው ሰዎች ሹምበት በሶስት ዓመት አደራጀው ፤ ይህን በፍጥነት የፈጸምከው እንደሆን አለማው አሰፋው የሚሉት የቅጽል ስም እሰጥሃለሁ ።

፭ኛ ፤ ለእርሻ ምንስትርም እንዲህ ስትለው ሰማሁ ። ከዚህ ልጆቼን የማሳድግበት ሥራዊቴን የምቀበልበት ሌላ ጥበብ እንዳልነበረኝ ከእርሻ በቀር አንተ ታውቃለህ ። አሁንም የሚታረሰው አገር በስርዓት ሁኖ እንዲታረስ አታክልትም እንዲተከል ለባላገርም ትልልቅ የሆነ ዛፍ በስርዓት እንዲያሳድግ ያሳደገውም ለራሱ ጥቅም እንዲሆነው በአዋጅ ማስታወቅ በወንዝ ዳርና በሜካ ያለውም በመንግሥት እጅ ሁኖ በወረቀት እንዲቈረጥ ይህን በፍጥነት ያላደረግህ እንደሆን ከሶስት ዓመት ወዲያ ለቤት መስሪያ የሚሆን እንጨት የሚገኝ አይመስለኝም ዛፉ ተቈርጦ ያለቀ እንደሆን ደግሞ ሊቃውንት እንደሚሉት የክረምትም ዝናም እያነሰ ይሄዳል ውሀው ይደርቃል በትግሬ በኩል ዛፍ የሆነ እየተቈረጠ አልቋል ። የክረምትም ዝናም እያነሰ ሄዷል ፤ ስለዚህም ላገረ ገገሮቹ በፍጥነት አስታውሰህ ትልቅ የሆነ ዛፍ እንዲያድግ ካላደረግኸው አገሩ ይጐዳል ውሀውም ይደርቃል ። መስክ የሆነ ሁሉ የባሕር ዛፍ ይተከልበት በየከተማው ዙሪያ እንዲሁ ይሁን ።

፮ኛ ፤ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትርም እንዲህ ያለችው መሰለኝ ልጄ ሆይ ለውጭ አገር ሰዎች ከትልልቆቹ መንግሥትና ከታናናሾቹ መንግሥት በትሕትናና በፍቅር እየተነጋገርህ ላገርህ ጥቅም የሚሆን ነገር እየተስማማህ በፍቅር ኑር አገሬን በሚያሰለጥናት ነገር ተጋደል ንግድ እናገባለን ትምህርት እናስተምራለን ላሉ ሰዎች ስፍራ ስጣቸው ልጆቼ የሚስተማሩበት መጻሕፍትም አሳትመህ ስጣቸው በኤዛሜ ቀንም በትምህርት ለቀደሙ ልጆች ከመንግሥት አስፈቅደህ ስጦታ እንዲያገኙ አድርጋቸው ቆንስሎች በምታስቀምጥበት አገርም በምክር ለተወሰኑ አለመጉደል ነው እግዚአብሔር ይርዳህ ብዬ ጸሎቴን አቀርብልሃለሁ ።

፯ኛ ፤ ለመንፈሳዊ ምኒስትርም ለብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ደሞ እንዲህ ስትላቸው ሰማሁ ። ልጄ ሆይ በግርማዊት ንግሥትና በልዑል አልጋ ወራሽ ባጤ ሁነህ የአገርህ ልጆች የጠራ ውሀ በብሉይ በሐዲስ ያለውን እንድታጠጣቸው ስርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በብሉይና በሐዲስ ከመጽሐፈ ሊቃውንት የሚስማማውን እያየህ ለመላው አገሬ የሚሆን ቀኖና አውጣለት ። ስለ ምንኩስና ስለ አጽዋማት ስለ በዓላት ስለ ቁርባን ስለ ቃል ኪዳን ስለ ክህነትና ዲቁና ስለ ተዝካርና ዝክር ስለ ምጽዋትና ስለ አምኃ ስለ ድኖች ምግብና ስለ ትምህርት ግን ልጆቼ በጣም ተጐድተዋልና ከነገሥታትና ከምንስትሮች ተማክረህ በቶሎ በየአውራጃው ሁሉ ከ፫ ዓመት እስከ ፲ ዓመት ልጅ የሆነ ሁሉ ክህን በውግዘት ንጉሥ በአዋጅ የኔ ወገን

ናተባለ ሁሉ በዓመት ያገሩ ንባብና ጽሑፈት እንዲያውቅ ማፋጠን ነው በትልቅ ገዳማትና ከተሞች ግን በደሞዝ የተቀጠሩ መምህራን ስርዓተ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልግ ስርዓትን ከሊቃውንት ተማክረህ አሳትመህ በመላው አገሬ ላከበት ገዳማትና አድባራትም ቄጥረህ በመዝገብ አግባ ንዋዬ ቅድሳትም መጻሕፍቱም በቤተ ክርስቲያኑ የሚያገለግሉትም በመዝገብ ይግባ ። ብዙ ከአገሬ መጻሕፍት ከሰው አገር እየተሸጠ አልቋል የውጭ አገር ሰዎች ሆኑ በዙሪያየ ያሉት እስላሞቹ ሳይቀሩ ያልተቃና ስርዓቴን እያዩ ያላግጡብኛል ። አንድ የብርሃንና ሰላም ተማሪ እስላምና የውጭ አገር ሰዎች ከሐረርጌ እስከ ጋምቤላ ትምህርታቸው እየሰፉ እነደሄዷ ጽፎ ነበር ። ከጎጃምና ካዲስ አበባ ወዲህ የውጭ አገር ሰዎች ብዙ ያልገቡበት ስለ ሆነ ያገሬ ትምሕርት እያነሰ የሄደ እንደሆን ሌሎች ይገቡበታል የሕዝብ ልብ ይከፈላል ሕዝብ አምልኮተ ፈጣሪ በጣም ሳይገባው የኤውሮጳ ሥልጣኔ የገባው እንደሆነ ደግሞ ሃይማኖት ወደ መናቅ ይደርሳል ። ስለዚህ ሳይቃጠል በቅጠል ነው ለዚህ ነገር ማስረጃ የመስኮብና የእስጳኛ ሕዝብ እንዴት እንዳደረጉ አዋቂዎችን መጠየቅ ነው በፈረንሳዊ አገርና በኢጣልያ አገር ብዙ ሰዎች ፈጣሪያቸውን ወደ መስደብ የደረሱ አሉ ፡ ምክንያቱም በካህናቱ ስንፍና ሥራ ፈት ጽዝቶ ሠራተኛ አንቦ ስላገሩ የሚሙክት ጥቂት ስለ ሆነ (ፈረንሳዊ ጀርመን ኢጣልያ ነምሳ) ጠላት አዋቂታቸው ነበር ። ጠላቶቻቸውን ድል ታደረጉ በኋላ ግን የሚሊታሪ ወገን የሆኑት ቤተ ክርስቲያን ከነአምልኮቱ ቤተ ክህነት ከነስርዓቱ የናቁ አሉ ። በዚህ ነገር አስተውለህ ሕዝቤ አምልኮቱን ሊያከብርና በፍፁነት የተደላደለ ስርዓት አውጥተህ አገሬን አስተምርልኝ ከዚህ ቀደም ግብጻውያን ልጆቼን ያስተምሩልኝ ብዬ ወርቄን አፍስሼ ልጆቼን አስገድዬ ታቦታቴን ገንዘብ እንዲገበላቸው ብለው የሱማሌና የአረሚ መሳለቂያ አድርገውት የነበረ ጊዜ ይበቃኛል ልጄ ሆይ አታሳፍረኝ እኔም በጸሎቴ ወደ አምላኬ እጄን መዘርጋት አላፍርም በሬት የነበርሁትም ወደ ኋላ መሆኔ በጣም ያሳዝነኛል ብላ ንልፍ አለችና ጸሎት በምትይዝበት ዋሻ ሄዳ ገባች ። ምንክቴሮችም በየፋንታ ምክርዋን ሲሰሙ ቆይተው ቢሆን አብልጠን አለበለዚያ እናታችን ከመከረችን ነገር በሁለት ዓመት ያልፈጸምነው እንደሆን ሰው ሁሉ ይናቀን ብለው ከግርማዊት ንግሥትና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተመርቀው እጅና እጅ ተያይዘው ከግቢ ሲወጡ ያዩኋቸው ይመስለኝ ነበር ።

ከቡራን ምንስትሮች ሆይ ይህን ትንሽ ማስታወሻ ስለጻፍኩ ከድፍረት እንዳትቆጥሩብኝ ይቅርታችሁን እለምናለሁ ።

ጐ ጐ ዘእምናዴር ።

፪፻፵፯ ገጽ ተከታይ ።

ትንሽ በር

በገናየን ልስራ የሚያምር፣እኖራለሁና ከሰው አገር ፣ ይጠቅም የለሞይ ጥሩ ግብር፣ብዙ ልጅ ወልዳለች ሳባገር፣ብልሆች ተሰብስቡ ሞኝ ይቅር፣ልንገራችሁ እኔ ጥሩ ምክር፣ገና ሳይመጣብን የላይ በቡር፣ባለክንፍ ነው የሚበር፣በመድፍ ገሞራ የሚሰብር፣አባት ገድሎ እናት የማይምር፣መሬት ከጨበጠ ባፍ ፍቅር፣ስንዝር ብትር አይሰጥ መቃብር፣የዚህ መዳኒቱ ምን ያምር፣ዋጋ አያስፈልግ አንድንም ብር፣ አንድነት መምከር ነው በጥሩ ፍቅር፣የብርሃን የሰላም ሁኖ ማኅበር፣ደግሞ አዳምጡኝ አንድ ምክር አድጋችኋልና ሞግዚት ይቅር የበቃ የነቃ ሞልቶ መምር ሩቅ ደክሞ ማምጣት ትልቅ ነውር ይደነቅ የለምወይ ዳር አገር ።

ኢትዮጵያ እናቴ የሰው መጀመርያ ለወርቅ ዝምታኽ የለውም መስፈርያ እስቲ ቀና ብለሽ ተመልከች ግፍ ያአንቺ ፤ የመሰሉ ግብጽና ሶርያ ደግሞ እንደነሱ ደጉ አርማንያ ቀጽራቸው ተንዶ ሆነ መሰማርያ ። ፍሬያቸውን በላው አንበጣ ደንብያ፣ይህን አይታሽ ባንቺም ባሊያ፣አጥብቀሽ እሪበይ ገነት ኢትዮጵያ፣አሰማሩብሽ ጠጦችና እሾያ፣ለዚህ መዳኒቱ ላመልክትሽ ነያ፣ብርሃንና ሰላም ካወጡት ገበያ፣ከዚያ ያገናኘንና አግዜር ኬንያ፣ጥሩ ቅጥር መከረሽ መዝጋት ነው ደንጊያ ።

ብርሃንና ሰላም እንዴት ዋላችሁ ዕውነተኛው ብርሃን ይኑር በሁላችሁ ። ብዬ እባርካለሁ ድኩም አሮጌያችሁ አረጀሁ ደከመኝ ልናዘዝላችሁ አርነት ውጣልኝ ከመገዛታችሁ ። በገዛ ዳቧችሁ ልብ ልቡን ያጣችሁ ። ለእነግዲሁ ልቡና ይስጣችሁ ፣ ብርሃንና ሰላም ምሰሉ ሁላችሁ ።

ብድግ በል ብድግ በል ሐበሻ ተነሳ ። ይኼ ምኝታችን አልተመቸምሳ ።ቀበሮ ይነጥቃል ይሰብራል አንበሳ ። ተኝቶ መብላትስ ይሆናል ነቀርሳ ። አሁን ስራ እንስራ እንንቀሳቀስ። አሟች ኃል ብለው ሳያወጡን ቀሳ ። ሥርቶ ለበላ ሰው የለውም ወቀሳ ለብርሃንወሰላም ስለሆነ ጎሳ ።

ብርሃንና ሰላም ምስለ ማዕምር ወሊቅ ። አርጎው ሊተ አና ቅዱ ጽድቅ ። እባዕ ውለቴቶን እንዳስብ ጥልቅ ። ስለአገሬ የአዜብ ምሥራቅ ። ያለ አገር የለም መደላቀቅ ። ብርሃን ሳለ ተነሡ ደቂቅ ዕውቀት እንግዛ በጣም ያውቅ ። የዕውቀት ገበያ መቸውም አያልቅ ። ለልጆቻችን እንዲሆነን ስንቅ ። እኛም በነሱ እንድን መርቅ ።

ናሁ ይትባረኩ ትውልደ ጻድቃን ። ብሎ የነገረን ዳዊት መኰንን ። ወልዶልናልና ሰሎሞን ብርሃን በብርሃን እንስራ ሳያልፍ ዘመን ። ብርሃን አበራና ሰላሙን ሰጠን ይህ ጠቅል ተፈሪ ቃኘው መኰንን ። ተነሱ ተነሡ እንስራ ሲለን ብልህ ይሸከመው። ሞኝ ሞኝውን ። ስለ ምን የሚል ይመልከት ጉንዳን ። ተሸክሞ ሲሄድ የደከመውን ። እኔም እንደ ጊዜ ልናገር ዘፈን ። ብርሃን ወለደልን ምሥራቅ መኰንን ። ያቤሚሌክ ምኝታ ምን አስደነቀን የኛ አይበዛምወይ ከስሳ ዘመን ። ሺዘጠኝ መቶ ዝም ብለን ተኛን ።

ይህ ተፈሪ ሰው የለውም አመል ። ጓዝ ብዙ ነው ተውት ይደልድል ።አባቱ የቃኘው እሱ ይጠቅል እድሉ ነው እንጅ ምንከ ይበል ፤ ከላይ የመጣ ነው ከዳዊት ደወል ፣ ትንቢት ተናገረ እውነት የሚመስል ፤ ሁላችሁ ዝም በሉ እኔ ሆይ ልበል አርፈን እንቀመጥ በገነት አምሳል ብርሃንና ሰላም ስንከታተል

ኢትዮጵያ ዕድልት ወለተ ሥላሴ

ዜና ጽርየትኪ በጽሐ እስከነ አድማስ ጎር

ፀዳልኪ ፀደሰ መልዕልተ ኩሉ ፍጡር

እስመ አንቲ ትጸድሊ አምጸዳለ ነሐርይ ዘውስተ ባሕር
ምንተ ይትፌቀር ዘዓቀበ ኪ በንጽሕ እንበለ አበሳ ወነውር
ወጽድቀ ይትአወይ ምሥብዒተ መንግሥት ወክብር
ዓዲ ከመ ፀሐይ ይቀውም ዲበ ምድር
ኃይለ ሥላሴ ቀነተ ለፈጽሞ ዝንቱ ምግባር
ጽድልት ኢትዮጵያ አሠረ ዚአሁ ከመ ትሑር
አባ ገብርኤል ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

አቶ ወንድማገኘሁ ዓባይ ለጻፈው ማመልከቻ መልስ ።

አዲስ አበባ ጉምሩክ ውስጥ ፩ የዘገየ ሥራ አለና በቶሎ እን ድታከናውኑልን በማክበር አሣሥብዎታለሁ ። የዘገየውም ሥራ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ። አዲስ አበባ ጉምሩክ የአበሻ እቃ ማስቀመጫ የሚዛን ቤት ዙሪያውን ተገንብቶ ልክ እንደ ሽቀጥ ቤት መቆለፍ ያስፈልገዋል ። ቁልፉንም የያዘ ሰው ለዘ በኞች አስረክቦ እውጭ እንዲያድር ይገባዋል ። ሌላውን ሁሉ እኔ እጽፍም ዘንድ አይገባኝም ለሊት ለሊት ማር ይፈራል እህድ የሰምገቱ ሁሪተኛኝ ሲጠጡ ጭር ሲል በሩ ሲዘጋ ማር ይፈራል ለተባለው ።

መጀመሪ እስከ ዛሬ ድረስ ለማርና ለቅቤ ደግሞ ለየአንዳ ንዱ ዕቃ ማረፊያ ዙሪያውን የተገነባ ትርፍ ቤት ያለመሠራቱ የሽቀጥ ሥራ ከባቡር መቋሚያ ላይ እንዲፈጸምና ዕቃውም ወደ ከተማ በቀጥታ እንዲገባ ነገሩ ከተቆረጠና ሽቀጡም የሚ አርፍበት ቤትና የጽሕፈት ቤትም እንዲሠራ ለሥራ ሚኒሥትር ትእዛዝ ከተሰጠ አያሌ ጊዜ ሆነው ። ለዚሁም ሥራ የሚሆ ኑት ቤቶች አንዳንዶቹ ተሠርተው አንዳንዶቹም በጅምር ርቀተው እንዳንዶችም በአሳብ ብቻ ስለቆዩ የጉምሩክ ሹማምቶች አሳባ ችን ታገደ።በተቀር ለማያስፈልግ ሥራ ሁለት ጊዜ ገንዘብ በከ ንቱ እንዳይወጣ የሽቀጥ ሥራ ከባቡር መቋሚያ ሲሆን ከአገር አገር ውስጥ የሚነገድበትን ዕቃ የሽቀጥ መቀመጫ ከነበረው ቤት ውስጥ ልናገባው ነበር ።

ሁለተኛ ቤቱም ዙሪያውን ቢገነባ ቁልፍ ያገርም እንደ ሽቀጥ ቤት ቢደረግለት የማርን ፍራቻ የሚያስጥለው ነገር የለም ስለምን ማለት ሽቀጥ የሚቀመጥበት ቤት ዙሪያውን ግንብ እያለው በቁልፍ እየተዘጋ ሽቀጥም ብዙ ጊዜ ፈርቷል ነገር ግን ያስፈራሩት ሰዎች በአስፈራሩት ቁጥር ክሰውን በሚ ዛኑ ክሰዋል ። ማርም ከጋን ገብቶ ኋደኛውን ጌሾ አግኝቶ በቀ ሉን እስኪወጣ ድረስ እንደሌላው ዕቃ ሁሉ ፍራት አይለየው ምና ፈርቶም ቢገኝ ስለ ፍራቱ ጠበቂ የሆኑት ሰዎች ለፈራበት ክሰዋል ። ለማር መፍራት ምሽግ የሚያስጥለውና በትክክል የማ ይመሰክርለት ስለሆነ አስፈራሪዎችም ቢኖሩ ለአስፈራሩበት ምስክር እንዲያገኝ ብለን ማር ከጉምሩክ በገባ ጊዜ ነጋዴው ለዘበኛ ሲአስረክብ አስቀድሞ አስመዝኖ ያስረክባል ። በሚአ አወጣበት ጊዜ ሚዛኑ ከፊተኛው ሚዛን ቢጐል በጐደለው ልክ ነጋዴው ያኔውን ይከፈላል ። ይህ ደንብ መደረጉን ልጅ ወንድ ማገኘሁ ዓባይ አልሰማም መስሎኛልና ለወደፊት እንዲያውቀው ይሁን ።

ደግሞ በባሕርዩ ማስፈራራት የሚመኝ ሰውና በንጉሥ ሕግ ላይ የሚሸፍትን ሰው እንዳያስፈራራና እንዳይሸፍት አስቀ ድሞ ለመከልከል አይቻልም በአስፈራራና በሸፈተ ጊዜ እንዳ ያመልጥ አሰቀድሞ አስቦ መያዣ መንገድ ይደረግለታል እንጂ የሹምም ሥልጣኑ ከዚህ ድረስ ነው ።

ሰስተኛ በጉምሩክ ያለው መጋዚን ሁሉ ለቡናና ለቆዳ ማኖሪያ የማይበቃ ቢሆን እኩሌታው ከሽቀጥ ቤት እንዲቀመጥ ሆኑዋል ደግሞ ከባቡር መቋሚያ እንዲሠራ የተባለው ቤት ሣይሠራ ቢቆይ ከአገር ውስጥ ለሚመጣው ዕቃ ማረፊያ ሌላ ቤት መስራት ተጀምሯል ። ቢሆንም ከሚዛን በቀር ምሽግና ቁልፍ የሚያስፈራሩትን ጠረኞች ከሥራቸውና ከአሳባቸው አልወሰናቸውም ። ለዚህም ምሽግና ቁልፍ ማርንም ወይም ሌላውንም ዕቃ እንዳይፈራ እንደምን አይከለከልም ብሎ የሚ ጠራጠር ሰው ቢኖር ወደኔ ይምጣና አስረዳዋለሁ በተቀር ማስ ረጃውን ነገር ሁሉ በወረቀት ለመጻፍ የማኅተምን ቤት ሠራ ተኞች ሌላ ሥራ እንዳይሠሩ ሥራ ማስፈታት እኔም ለቀረው ሥራ የማገኘውን ጊዜውን በዚህ ብቻ እንዳላሳልፈው ለማለት ነው ።

የአዲስ አበባ ጉምሩክ ።

ይድረስ ከክቡር ከንቲባ ነሲቡ ።
ልጄ ወዳጄ ሆይ ።

ከተማችን እየሰፋ ወስላታው እየበዛ ሂድዋልና ደክመህ እንዳልደከምህ ሰርተህ እንዳልሰራ እንዳትሆን በንቃት እንድት ኖር ከዚህ ቀደም በኔ የደረሰብኝን ነገር ባስታውቅህ አብነት ይሆ ንሃል ስል ጻፍኩልህ ።

እንደዛሬ የሰው አገር ሰው ሳይበዛ ጥቂቶቹ እንኳ እጅግ ያስቸግሩ ነበር አንድ የሰው አገር እንግዳ ተከሰሰና ከሹመት ቤት ሆኜ ባስጠራው ባርኔጣውን ሳያወልቅ ከራሱ ላይ እንደ ደፋ ሁለት እጁን ተኪሱ እንደ ሽጐጠ መጥቶ ከፊቴ ቆመ እንዳገ ርህ ልማድ በሥርዓት ቁምና ሳነጋግርህ ብላው በሥርዓት ከኖ ርሁ ባርኔጣ ከወለቅሁ ከገሬ ምን ያመጣኝ ነበር ብሎ መለሰልኝ ከቶም ዛሬማ ከዓለም ጦርነት ወዲህ ወይትነሥኡ ሕዝብ ዲበ ሕ ዝብ ወነገሥት ላዕለ ነገሥት እንዳለ ወንጌል ሕዝቡ በመንግሥቱ ላይ መነሣቱ ሥርቆቱም ቅሚያውም መብዛቱ እጅግ ያሳዝናል የወዲያ አገር ሥርቆት በጨርቅ በቀንድ ከብት በጋማ ከብት እንዲህ በቀላሉ አይደለም ገንዘቡን እስተ መዝገቡ ነው የሚያወ ድመውት ። አንድ ነጋዴ ሰው የስልሳ ሺ ብር ቡን ሼጠላቸው ገንዘብ እስኪመጣ ፈርማ ያዘህ ቆይ ብለው ሰጡት በሚከፍሉ በት ቀን ፈርማቸውን ይዞ ቢሄድ ተቀብለው ፮ ሰዓት ደርሰዋል ከምሳ በኋላ እንሰጥሃለን ብለው ገብተው ቀደው ጥለው ገንዘ ብም የለብን ብለው ሸፍጠው ውለውት ቀሩ ሲሉ ሰማሁ ። እን ዲህ ያለው ሥራ በመዝገቡ ቢመረመር ከወዴት እንደ መጣ ልኩ ይታወቅ ነበር ። አሁንም ወደ ፊት ስራና ገንዘብ ጌታም የሌለው ሰው በምን ምክንያት እየከበረ እንደሚኖር ገንዘብም ከዚያ በፊት መኖሩን አለመኖሩን ያገር ሰውና የውጪ ሰው ሳይመረጥ ፀሊጋሲዎኖች እርዳታ መርምሮ በልክ ማስተዳደር ለሹመትህ ማዕርግ መጠኑ ነው ። ከንቲባ ገብሩ ።

ስለሚያከስር ጨዋታ ።

ይድረስ ለክቡር ብርሃንና ሰላም ዲሬክተር የማክበር ሰላምታዬን አቀርብዎታለሁ ።ወንድሜ ሆይ እኔ ምንም የውጭ አገር ሰው ብሆን ብዙ ጊዜ የኢትዮጵያን እንጀራ ስለበላሁ አንድ የሚያሳዝን ነገር አይቼ ልጽፍልዎ ግድ ሆነብኝ ይህነኑም ብብርሃንና ሰላም እንዲታተምልኝ ሙሉ ተስፋ አድርጌ እለምንዎታለሁ ቃሉም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ።

ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ መንግሥት ስንኳን የገዛ ዜጋውን የውጭ አገር ሰው እንኳ ይህን የከሳራ ጨወታ እንዳይጫወቱ ከልክሎ ነበር ነገር ግን አንድ አንድ ስራ ፈቶች እየተደበቁ መጫወታቸውን አልተውም ። አሁን ግን ይህን የማይረባ የከሳራ ጨወታ የኢትዮጵያ ሹማምንቶች መንግሥቱ መርጦ በየአንድ አንድ ክፍል ስራ ላይ ያቆማቸው ስራቸውን በማስፋት ፈንታ የራስ መኰንን ቡና ሆቴል በሚባለው ቤት ሌሊት እየገቡ ሲጫወቱና ሲከስሩ ያድራሉ ። እነሱን ለመሰለ ሰው ይህ የከሳራ ጨወታ ትልቅ ነውር ነው ይልቁንም ከዘንድሮው ፋሲካ ወዲህ እየባሰ ሄደ ። ምናልባት ይህን ነገር ሀሰት ነው የሚል ቢኖር ክቡር ከንቲባ በታመኑ ሰላዮቻቸው ሳያውቋቸው የሚቀሩ አይመስለኝም እኔ ግን ስማቸውን መጥራት አያስፈልገምና ለወደፊቱ ግን ይህ የማይረባ ስራ ቢቀር ይሻላል ። ◦

የእውነተኛ ክርስቲያን መንገድ ።

የወገኖቼ ጥፋት ያሳዘነው የሀገሩ ፍቅር የተሳለበት ወጣቱ ኢትዮጵያዊ በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉት ቀጣፎችና አታላዮች ላይ የተማማጸ ቀስቱን ወርውሯል ነፍሳቸውን ለክርስቶስ ለሚያስገዙ ሰዎች መልከም ምሰሌ ነፍስን እልል የሚያሰኝ ድንቅ አነጋገሩ ከፍጹም ልብ የሚታመን ብርሃንና ሰላም ፫ኛ ዓ ፴፪ ቁ ፪፻፶፪ ገጽ ክርስቲያን ሆኖ የክርስቶስን ሥጋና ደሙን ተቀብሎ በጾም በጸሎት ተጸምዶ ፈጣሪውን፣መለመኑን ትቶ ለእስላም መንገድ ይገባዋልን ? የሚል ጥያቄ ከክቡር ተፈራ አበቤ የተጻፈ የብርሃንን ወገኖች በትጋት ይቀሰቅሳል ። ክርስቲያን ሆኖ ለዚህ የማይረዳ የለምና የብርሃንና የጭለማ መንግሥት መኖራቸውን አእምሮ ያለው ቀርቶ አእምሮ የሌለውም ለይቶ ማወቁ ጥርጣሬም የለበት ዓለም ከተፈጠረ አንስቶ እስከ ፲፱፻፳፫ ዘመናት ድረስ አሕዛብ በመላቸው በየነገዳቸው ልዩ ልዩ አማልክት መፍጠር በጠማማ ጠባያቸው እንደነበረባቸውም የተረገጠ ነው ። እንዚያውም የቀድሞ ጣዖታት በየሥፍራውና በዓለም ሁሉ እስከሁኑ ትውልድ ይገኛሉ ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ የአዳምን ልጆች በወንጌሉ ብርሃን ካደሰን ወዲህ ቢሆን ሞሐመድ የወደደውን እምነት መሰረተ እንጂ ሌላ በጉልህ የታወቀ የሃይማኖት አባት አልተገኘም ነበርና እንግዲህ ፪ኛ ሃይማኖት አሩሲ ከጉጉ ወረዳ መስራች ከተገኘች በሀገራችን አንድ የጭለማ ደረጃ ቆመ ለማለት እንችላለን በለሆን የኢትዮጵያ ልጆች ከትምሕርት ምንጭ ባለመጠጣታቸው የተነሳ አንዳንዶቹ ቢስቱም የሐሰት ስብከት ከለልባቸው እንዳይቀበሉ የታመነ ነው ። ወደፊትም በትንሣኤው የሚቀበሉትን ፍርድ፤አስበው የማያድን በይን ጣዖት ከማምለክ ወደፈጣሪያቸው ዓይነ ልቡናቸውን አቃንተው በንስሐ ነጽተው ከቸር ጠባቂ ርኅሩህ ንጉሣችን መድኃኒ ዓለም እርቅ በመለመን ይቅርታ እንዲያገኙ ዕድላቸው ይምራቸው ። የኢትዮጵያ ልጅ ሆኖ ክርስቲያንነቱ በሊቃውንት ሁሉ ሲነገር አምልኮተ ባዕድ በልቡ እንቁላል የሰራበት ከሆነ የታለ ክርስቲያንነቱ እስኪ የማን ገንዘብ ለመባል ይሆን ጥረቱ ፩ሎሌ ለ፪ ጌታ አይታዘዝምና እናስብ ።የእግዚአብሔር ወገን ያልሆነ ሁሉ በሞት ፍርድ በታች ሆኖ ወደ ዘለዓለም መቃብር ይወርዳል ምድራዊ በሕርዩ በሞት ይጠፋል በበጉነት ፍጻሜ መታደስ ፊውሳችን ነውና ሽባሽ ለምትባል ፍጥረት የምትሰግዱ ወንድሞቻችን እንግዶች መጣተኞች አይዶላችሁም የቅዱሳን ወገን እንጂ የሚለውን ሊያስተምሩ የተመረጡ ቄስና መምሕራን ሁሉ የእግዚአብሔር ነገር በነቢዩ በሕዝቅኤል የተባለው ይደርስባቸዋል ። አንተ የሰው ልጅ ሆይ እኔ ለእሥራኤል ቤት ተመልካች አድርጌ ሾምኩህ ከፊ የምትሰማውን ነገር ሁሉን በትእዛዜ ትነግራቸው ዘንድ ። እኔም ዓመፀኛውን አንተ ዓመፀኛ ሆይ ሞት ትሞታለህ ስል አንተም ይህነን ነገሬን ባትነግረው አመፀኛ በአመፃው ይገስጽ ዘንድ ዓመጸኛስ በአመጸው ምክንያት ይሞታል ደሙን ግን ከጅህ እፈልጋለሁ ነገር ግን አመፀኛውን ከክፋቱ እንዲመለስ ገስጽሽው ከክፋቱ ባይመለስ እርሱ ስለኃጢአቱ ይሞታል አንተ ግን ነፍስህን አዳንክ ፴፫ ፰ ፱ ይላልና ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግብረገብነት ርስቱ ስለሆነ ያስተማሩትን የማይረሳ ነውና መምሕራኑ አበርትተው ቢያስተምሩት አስማተኛና ቃላቱኛን ጠንቋይንም መንገድ ዘወር ብሎ ማየት ሥራው አልነበረም ። የሀገራችን ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ነገር የተቀበለች ክርኩስት ሥራ ሁሉ የተለየች በክርስቶስ ቃል የተመሰረተች በክርስቶስም ቃል በአሕዛብ መሐከል እንደብሩህ ብርሃን የበራችናትና የሰይጣናትን ደጆች ሁሉ ድል መንሳትን ይስጠን የክርስቶስ ጥበቡና ፍቅሩ አይወስንም የልጆቹን ነፍስወደ ጥፋት አይወስዳትም ። ለአዳምና ሔዋን እግዚአብሔር በገነት ተስፋ ሰጥቷቸው እንደነበረ ከሴት ዘር የእባብን ራስ የሚቀጠቅጥ እንዲመጣ እንዲሁም ባልዐላችን ፍለጋ በግሥገሣ የሚከተሉ ኢትዮጵያውያን የአስማተኛና ቃልቻን መንፈስ ለመቀጥቀጥ እንዲበረቱ የውነተኛ መንፈሱን ይስጥልን ። ክቡር ተፈራ አበቤ ሆይ ላንተ ያልሆነ ለብልሁ አዋቂው አባትህ እውነተኛው ጌታና ንጉሥ ። አከብራለሁ እንጂ እኔ የዚህን ዓለም የጋኔን ማደርያ አላውቅም በማለታቸው በውነተኞች ክርስቲያኖች ዘንድ እጅግ ይመሰገናሉ ። አንተም ይህነን የዲያብሎስ መርዝ ሐሰት የሕዝብ መውጊያ ጻፍፈህ በብርሃንና ሰላም ስለ መግለጽህ የኬቤል ካህናት ጣዖትዋን በሰረገላ አድርገው ባዞርዋት ጊዜ የመንገድ አላፎች ሁሉ የኬቤል ሰረገላ ሲያልፍ በጉልበታቸው ሲሰግዱ አንድ ጀግና ብቻውን ቁሞ ቀርቶ ወደሹም ወስደው አንተ ክርስቲያን ነህን ስለምን አትሰግድላትም ለጣዖቷ ብለው ቢጠይቁት እኔ ክርስቲያን ነኝ በሰማይ ለሚገዛው እውነተኛው አምላክ እሰግዳለሁ ለዚህች ጣዖት አልሰግድም ብትፈቅዱልኝ ሳልፈራ እቀጠቅጣታለሁ እንዳለው መሆንህ አይጠረጠርም ። በውነት አንድ አምላክ ብቻ አለና እሱን ብቻ እናምልክ እርሱም የነገሥታት ንጉሥ የአሕዛብ ጌታ የሚሆን ። እየለ ገዳ ።

ንው ደቂቅ ወስምዑኒ። ፈሪሃ እግዚአብሔር እምሀርክሙ።

ማስታወቂያ

በነሐሴ ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፱ ገጽ በወጣው ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ የመንግሥት ሠራተኞች የሆኑ የኢትዮጵያ ወጣት ልጆች ሠረቀ ብርሃን ብለው የሠየሙት ተማሪ ቤት አቋመዋል ብለን አስታውቀን ነበርና ይኸንኑ ተማሪ ቤት ስለሀገራቸው ስለኢትዮጵያ ፍቅርና አገልግሎት የመሠረቱትን ሰዎች ከዚህ በታች እንደተጻፈው በዝርዝር ስማቸውን እንገልጻለን ።

፩ኛ የክቡር ፕሬዚዳን ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል የጽሕፈትና የእርሻ ምኒስትር

፪ኛ ዋና ፕሬዚዳን ክቡር ልጅ ኤፍሬም ማሀለ ጊዮርጊስ

፫ኛ አቶ መታፈሪ ወልዴ

፬ኛ ልጅ ለማ ወልደ ገብርኤል

፭ኛ አቶ ጸጋዬ ገብረ ጻድቅ

፮ኛ አቶ በላቸው ይመሩ

፯ኛ አቶ ጽጌ ወልደ ጻድቅ

፰ኛ አቶ ወልደ ሰማያት

፱ኛ ልጅ ብርሃኑ ሥላሴ አባየሬ

፲ኛ አቶ ወዳጆ አሊ

፲፩ኛ ልጅ ኃይሉ ወልደ መስቀል

፲፪ኛ አቶ ወልደየስ ወልዴ

እንዲሁም ደግሞ የሀገርን ፍቅር የምትሰብከው ትልቂቱ የፍቅርና አገልግሎት ማኅበር በዚህ ማኅበር ውስጥ የአገልግሎቷን ሥራ ለማስፋት አንደኛ ማኅበር ሆናለች ።

ክቡራን ጌቶቻችንና እመቤቶቻችን ደግሞም ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ሆይ ከዚህ በላይ እንደአስታወቅነው ለጊዜው በሥራ ላይ የተቀመጡ ወንድሞቻችን በቀን ለመማር ስለስራቸው ብዛት ጊዜ ስለማያገኙ ግርማዊት ንግሥታችንና ልዑል አልጋ ወራሻችን ፥ ተማምነን ይህን ተማሪ ቤት ከምሽቱ ባስር ሰዓት ተከፍቶ እስከ ሌሊቱ ፭ሰዓት ድረስ እርስ በርሳችን የምንማማርበት መክፈታችን ለሀገር ፍቅርና ለታላቁ መንግሥታችን አገልግሎት ነው እንጂ እውነትም ለንግድና ለመዋዌ አካሄድ አይደለም ።

ስለዚሁ ስለመልካሙ አካሄድ ክቡራን ጌቶቻችንና እመቤቶቻችን ደግሞም ክቡራን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ሆይ እናታችን ኢትዮጵያ ምንም ከዚህ ቀደም የሚበቃ እውቀት ኖሯት ነጻነቷን እስከ ዛሬ ብትጠብቅና ፈጣሪዋን እየለመነች በመልካምም አስተዳደግ ልጆቿን ብታሳድግ ዕውቀት የማትጠግብ ናትና ወደፊት ሀገራችን ወደታላቁ እውቀት እየገፋች እንድትሄድ እናንተ ለናታችሁ ታዛዥ የሆናችሁ ምሩቅ ኢትዮጵያውያን እንደምትወዱ አውቀን ይህም ተማሪ ቤት ለሁላችንም ክብርና ማዕርግ ነውና እንደሚቻላችሁ ለሠረቀ ብርሃን ተማሪ ቤት እንድትረዱ በታላቅ አክብሮት እንለምናችኋለን ።

ሠረቀ ብርሃን በኢትዮጵያ

ከእንቅልፍ ስለ መንቃት

ክቡራን ወንድሞቼ ጌቶቼ የብርሃንና ሰላም ወዳጆች የምትሆኑ ለሁላችሁም ለየራሳችሁ የከበረ ሰላምታ አቀርባለሁ ።

እንቅልፍ ይዞኝኖሮ ሳልሰማ ነገሩን ፡ ዕወቁኝ ለማለት መቻልሁ አሁን ፡ ከእንቅልፌ ነቅቼ በስተውለው ጊዜያቱን ፡ ቀሪውጥቂት ሆን ዕኩል ሰዓት ሊሆን ፡በኩል ሰዓትማ ምሳ ተሰናድቶ መብላት መጠጣት ነው በየቤቱ ገብቶ ። ኢትዮጵያ እናቴ ዛሬ ተመሪ ፡ በሰው አገር ዕቃ ስትንቀባረሪ። ይልቅ ይሻልሻል ራስሽ ተፈሪ ። በቀጭኑ ፈትልሽ ጥበብ ኩታ አሰሪ ፡ ጥበብ ኩታ ለብሰሽ እንቺማ ብትኰሪ ፡ ሁሉም ይፈራሻል ለራስሽ ብትከብሪ ሐሰት እንዳይመስልሽ ነገሩን ዕወቂው ፡ ይፈራ የለምወይ ከገኘ ወዲያ ሰው ። እኔ ብናገረው ዳሩ ምን ያደርጋል ፡ ውስጥ ለውስጥ ገብተው ይበጠቡጡሻል ፡ መብላት የት ታውቂአለሽ መደገስ ነው እንጂ ። በመሶብ አቅርበሽ ስትንጐራደጂ ። እየተባበሉ ና ብላ ና ጆርጂ ፡ ልቅም አርገው በሉት በይ እስቲ ይኸውልሽ በይ ተናደጂ ፡ እንቺማ ብትሰሚኝ እኔ እንደ ምመክርሽ ። ለኑሮሽ ዕወቂ ራስሽ ይሻላል ተፈሪ በቤትሽ ፡ የቤትንሰው ሳይፈራሽ ው‥ው መች ይፈራል ፡ አመልሽን ጠይቶ ከቤትሽ ይገባል ፡ መመራመር አታውቅ ሁል ጊዜ ደግነት ። ሥራ አልሠራህ ብላ መቄጣት የለባት ። ኩፍ ብሎ ውሎ ገባ ብሎ ከቤት ። መሶብ ከፊት አርጎ እስኪጠግቡ መብላት ፡ የናታችን አመልሁል ጊዜ እንደዚህ ነው ፡ ብለው ይነግሩታል ለዚያ ለውጭው ሰው ፤

ቤት ነብረቱን ትቶ የደከመበትን ፡ ወደ እንቺው ይሮጣል ሲሰማ ዝናሽን ፡ ያራቱን ወር መንገድ ይገባል ባንድ ቀን ፡

ነገሩን አስበሽ አትመራመሪ ፡ ደግነትሽን አይቶ እግዚአብሔር ፈጣሪ ። ወንድ ልጅ ሰጥቶሻል እንግዲህ ተፈሪ ፡ እንኳ ለሐገሩ እንኳን ለንብረቱ ለሰው ተቋጣሪ ፡ አገሩን ይወዳል አትጠራጠሪ ፡ ሆድሽን አስፍተሽ እሱኑ አምነሽ ኑሪ ፡

ወንድሙ ተሸበሩ። ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል



የእጅ ሰዓት ዝኒት

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሁሉ ሰዓት መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ፲ መሐ ።
ያሲዳሞ ቡና	፩	፳ ብር ፫ ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፮ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር ፫ሩብ
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲፩ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፫ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፵፫ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፮ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፴፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፲፯ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፬ ብር
፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፵፫ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፰ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፫
አንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ ፱
ፍአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፴፫ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፮ ብር

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻ ነው ።

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፡በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፣ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ ኦድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ካኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደ ገሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና ነሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን ኦቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሰ መኖቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጉበርና አጉበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፤ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፤ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክስል የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

Berliet



ቤርሊዬ ኦቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርለ ዬ አቶሞ ቢልና በእንጨት የሚሄድ ከሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

ኤን ቤ ኢዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማስፈያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን ኦዶኮሎኝ አምባሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የኦዶኮሎኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ክዳ ከውያ የልብስ መተኰሻ ብርጭቆ በያይነቱ ቢጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳሀን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፣ ቁጥር ፴፮
3 me ANNÉE № 36

ሐሙስ ጳጉሜ ፫ ቀን ፣ ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 8 SEPTEMBRE 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ በመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር በመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ቢገዛ አረስን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የኢትዮጵያ ጭንቀት ።

የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ አየሁ ።

(እንበቆም ፫ ፯ ።)

ነቢዩ በዚህ ቃል ኢትዮጵያ ጭንቀት እንዳላት ይናገራል ። እርሱም በእግዚአብሔር መንፈስ ተተንፍሶ ይህን ያስታውቃል ነገሩም ሕልም ወይም የዋዛ ነገር አይደለም ነቢዩ በርግጥ ያየው ነገር ነው ። ወደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወት አጥልቆ ለማየት ከእግዚአብሔር ዘንድ የትንቢት ጸጋ ተሰጠው ። ስለዚህ የኢትዮጵያን ኑሮ ከሩቅ ሊያየው ቻለ ።

ኢትዮጵያ ማን መሆንዋን ጥያቄ አያስፈልግም ፣ ያች እጅዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የተባለላት ሕዝብ ናትና (መዝ ፷፯ ፣ ፴፩ ፣ ሰፎ ፣ ፫ ፣ ፲ ፣) ድንኳኖችም በርሳቸው የሚኖሩትን ያመለክታል ። ስለዚህ አለ አንዳች ጥርጣሬ ፣ በኢትዮጵያ መሬት የሚቀመጡትን ሕዝቧን ያስባል ። ከሁሉ የሚበልጠው ጥያቄ ግን ፣ ይህ የኢትዮጵያ ጭንቀት ነቢዩ ያየው በምንና በምን መሆኑን መጠየቅ ነው ።

ነቢዩ ያየው ከእግዚአብሔር ሆኖ ስላየው ራእዩ እጅግ እውነተኛ የሆነ ራእይ ነው ። አሁንም ወደ ሕዝባችን ሕይወት በእውነት ማየት ለመቻል ፣ ነቢዩ በሚያየው መንገድ ብቻ ነው እንጂ በሌላው መንገድ የሕዝባችንን ሕይወት እንደሚገባ ልናይ አንችልም ። እንዲሁም መድኃኒቱ እርሱ በሚያመለከተው መንገድ ብቻ ይገኛል ። ስለዚሁ ነው የትንቢት ቃል የተሰጠን ፣ በርሱ የሕዝባችን አኑዋዋርና ፈውሱን ለማወቅ ።

ጭንቀትና ሐዘን እንዲያው በከንቱ አይመርዱም ። የተፈጥሮው ደምብ ይህን ያስታውቀናል ። የታመመና በንዳች ነገር የተጐዳ የደከመና የተራበ ደግሞም በመንፈሱ ውስጥ የተናወጠ ይጨነቃል ። የሥጋና የመንፈስም ጭንቀት አለ ። እያንዳንዱ በተለየ በሚደርሰው ነገር በሕይወቱ ይጨነቃል ሕዝቦችም እየጭንቀታቸው ይወርድባቸዋል ። ዳሩ ግን የሆነው ቢሆን ለያንዳንዱ ከጭንቀት የሚያደርሰው የገዛ ራሱ ሕይወት ነው ። ለሁሉ ፍጥረት ብዕዕናውን ለማሰልጠን ወይም ወደ ጭንቀት ለመድረስ እየምክንያቱ አለው ። ደምቡም ለሁሉ አንድ ነው ። አሁን በጭንቀት በኩል ያሉትን ዓይነተኞች ምክንያቶች ከዚህ በጭሩ ላመለክት እሻለሁ ።

ከሁሉ አስቀድሞ የሕዝባችን ጭንቀት የሚበዛው ከውስጥ ከሕዝባችን ሕይወት ማኸል ነው እንጂ ከውጭ አይደለም እንግዲህ ሕዝባችንን ለማዳን ብንሻ የውስጡ ሕይወትን መፈወስ ያስፈልጋል ። በሕዝቡ ታሪክ እንደሚታወቅ ሕዝብንና ወገኖችን የሚጐዳቸው የገዛ ሕይወታቸው ነው ፣ ስለዚህ ኢትዮጵያ ልትኖር ብንፈልግ የሕይወታችንን መሰረቶች በቶሎ ልናድስ ይገባናል ።

፩ኛው የጭንቀት መሰረት ኃጢአት ነው ፣

ለጭንቀትና ለጥፋት ከኃጢአት በቀር ምን ምክንያትና መሰረት አለበት ይህንንስ ነገር ማን ሊክደው ይችላል ። የሕዝብ ሕይወት በኃጢአትና በልዩ ልዩ ዓመፃ ከተበላሸ በኋላ ሕዝብ ያን ጊዜ ነው ጥፋቱ ። ሌላ መጀመሪያ የጥፋትና የጭንቀት መሰረት ሆኖ የሚታወቅ ነገር የለም ። ያበዓለም ላሉ ሕዝብ ለትምሕርትና ለጥንቃቄ የተጻፈው በመጽሐፍ ቅዱስ ያለ የአሕዛብ ይልቁንም የእሥራኤል ሕዝብ ታሪክ ይመሰክራል ። (ምሳ ፫ ፣ ፲፪ ፣ ምዕ ፬ ፣ ፩ ፣ ፫ም ፣ ፮ ፣ ፩ ፣ ፲ ፣) ይህንንም ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱስን በጽኑ መመርመር ይገባል ፣ ለዚህ ለአምላካዊው እውነተኛ ነገር ደግሞ የሕዝብ ሕይወትና የዓለሙ ታሪክ ያጠብቀዋል ። በኃጢአትና በድንቁርና የወደቀ ሕዝብ ወደ ሥልጣኔ የደረሰ ከቶ አልታየም ፣ በሁሉ ዘመን

ኃጢአት የሕዝብና የሥልጣኔ አጥፊ ነው ፡፡ እንግዲህ ኃጢአት
ሊጠፋ ዓይነተኛው ፈውሱ ምንድር ነው ኃጢአትን የሚቃ
ወም ሕዝብን ከእግዚአብሔር ቍጣና ከጭንቀታቸው ሊያድን
የሚችል መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ፤ ሌላው መልከም ነገር
የሚባል ያለ እንደሆን ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ፍሬ ነው ፤ በርሱ
ብቻ ነው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ወይም የሚያሳዝ
ነው የሚያስቈጣውም ለመለየት የሚቻል ፡፡ እንዲህ ከሆነ
ከሁሉ በፊት መጽሐፍ ቅዱስን በአገራችን በጣም እንዲወደ
ድና እንዲከብር እንዲዘረጋም ግድ ያሻል ፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ
መሰልጠን በኢትዮጵያ እንዳይሆን የሚቃወሙ ያሉ እንደሆን
ከዚህ ነገር የበለጠ በእውነት ኢትዮጵያን ይረዳታል ይጠቅማ
ታል የሚሉበትን ምንና ምን ነገር ሊያመለክቷት ይችላሉ ፡፡

ኢትዮጵያ እስከ አሁን ተጠብቃ የኖረችው እንኳ በመጽ
ሐፍ ቅዱስ ረድኤት ነው ፡፡ እግዚአብሔር በአይሁድነት ዘመንና
በዚሁ በክርስትናው ዘመን መጀመሪያም ከሌሎች ሕዝብ አስቀ
ድሞ የኢትዮጵያን ሕዝብ በቸርነቱ ጐብኝቷል ፡፡ ሌሎች አሕ
ዛብ በአረሚነት ጨለማ ሲንከባለሉ ሳሉ የቃሉን ብርሃን ወደ
ኢትዮጵያ ሰደደ ነቢዩ ኢሳይያስ ኢትዮጵያን ለማስተማር ዘረ
(ኢሳ ፳ ፥ ፫ ፡ ፬ ፤) እንዲሁም ወንጌል ወደ ኢትዮጵያ መግባት
የጀመረበት ዘመን ብናስብ የሚገርም ነው ፡፡ ወንጌል በይሁዳ
ሕዝብ በተሰበከበት ዘመን የክርስቶስ ሃይማኖት ወደ ኢትዮ
ጵያ መግባት ጀመረ ፡፡ (ግ ሐዋ ፰ ፥ ፳፮ ፡ ፵ ፡) እንዲሁም በዘመነ
እሥራኤል ከአይሁድ ሕዝብ መካከል የአብርሃምንና የዳዊትን
ሕያው አምላክ በፍጹም ልባቸው ያመለኩት አንድ አንድ ደገ
ኞች የትዮጵያ ልጆች ይገኙ ነበር ፡፡ (ኤር ፴፰ ፡ ፯ ፥ ፲፫ ፡፡) ዛሬ
ም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የነኝህን ኩቴ ቢከተል ኢትዮጵያ
እጅግ በተጠቀመች ፡፡

ደግሞም የኢትዮጵያ ነገሥታት ደገኞች እንደ ነበሩ
ልናስብ ይገባናል ፡፡ ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ጥበብ ለመመር
መር ወደ ኢየሩሳሌም ከትልቅ የሀብት ጓዝ እንደመጣች ሁሉ
የሚያውቀው ነው ፡፡ ከሰሎሞንም ከዓይነተኞች ወይም ከመጀመ
ሪዎች ጥበቡ እግዚአብሔርን መፍራት ነበር ፤ ንግሥቲቱም
ይህን ነገር እንደተማረች ለንጉሡ ለሰሎሞን በመለሰችለት ቃል
ይታወቃል ፡፡ እንዲሁም ንግሥት ሕንደኬ የእግዚአብሔር የሕ
ያው አምላክ ዕውቀት ፊት እንዳገኘች ኋላም የክርስቶስ ወን
ጌልን በሹመኛዋ በኩል እንዳገኘች ለማለት የሚያስደፍር ነገር
ነው ፡፡ የክርስትናውን ሃይማኖት ባንዱ በእግዚአብሔር የነበረ
ለትን አምልኮ ደስ የሚያሰኛት ሆኖቢሆን ከገንዘቧ ሁሉ ባልሾመ
ችውም ሰውየውበመንግሥቷ የገንዘብሚኒስትር ነበርናበዚህ አ
ምልኮው ግን አንዳች አልጠላችለትም ሀስ ባዩሆንወደ ኢየሩሳ
ሌም ለእግዚአብሔር ሊሰግድ ፈቃድ ባልሰጠችውም ፡፡ ስለዚህ
ደግነቷ በሁሉ ነገር ይገለጣል ፡፡ እንዲህ ብሎም የክርስትናው
ሃይማኖት በነገሥታቱ ውድ በኢትዮጵያ ሊዘረጋ ጀመረ ፡፡

ከዚህ በኋላ በነ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ተብሎ የተጠራ
የወንጌልን እውነተኛ ብርሃን በኢትዮጵያ ላይ አበራ ፡፡ የአትና
ትዮስ የቄርሎስ የዮሐንስ አፈወርቅ የሌሎችም የወንጌል ሰብ
ከት የያዙ መጻሕፍት በአገሬ ተዘረጉ፤ ሰዎችን ለእውነተኛውና
ለተቀደሰው የሃይማኖት ሕይወት የሚያስተምሩና የሚመክሩ

ዳሩ ግን በምንም በምንም ብሎ በኋለኛው ዘመን የወንጌ
ል ብርሃን እንደ ተፈለገው ሆኖ አላበራም ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ
ለማግኘት ቸገረ ስለዚህ እውነተኛው ዕውቀት አነሰ አረሚነ
ትና እስልምና በመኻልና በዙሪያ ሆኖ አስጨንቀ ሰላምም በጦ
ርና በሌላው ምክንያት ጠፋ ፡፡ ይህ ሳይቀር ግን ስለዚያ ስላ
ለው ስለ ክርስትናው ሃይማኖት ኢትዮጵያ በነፃነት ተጠብቃ
ትኖራለች ፡፡ በአፍሪቃ የዓለም ክፍል ካለው ሕዝብና መንግሥ
ታት በራሷ ኃይል ነፃነቷን ይዛ ያለች የኢትዮጵያ መንግሥት
ናት ፡፡ ይህም በሌላው ምሕረት አይዶለም እግዚአብሔር በራሷ
እንድትቆም ኃይል ሰጥቷታል ምስጢሩም የክርስትና ሕዝብ
ቅሬታ ስለሆነች ገናም እግዚአብሔር በምሕረቱ ዓይን ያያ
ትና ይጠብቃት ስላለ ነው ፤

አሁንሳ እግዚአብሔር እንዳይቈጣብን ነቢዩ ያየውንም
ጭንቀት እንዳያጠፉን ምን ልናደርግ ይገባናል ? የፊተኛው
መልስ ይህ ብቻ ይሆናል ፤ እንደ ቀደሙት አያቶቻችን የእግ
ዚአብሔርን ቃል በሕዝባችን ሕይወት እንዲሰለጥን ማድረግ
ኃጢአትንና ዓመፃን እንዲቀነስ ትምሕርት ዕውቀት አእምሮ
በጎንም ማስተዋል ሁሉ እንዲዘረጋ ማድረግ ነው ፡፡ ከመጽሐፍ
ቅዱስ ሊማር የማያስፈልገው እንዲህ ያለ የበቃ አዋቂ ከቶ
የለም ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኘውም ዕውቀት ሌላ
የበለጠ የለም ፤ ስለዚሁ ካህናቶቻችን ቄሶቻችን ሕዝባችን ለማ
ስተማር የሕዝባችንንም ጠቀሜት ምንድር መሆኑን ለመመር
መር ቢተጉ ምንኛ ብፁዕ ዘመን ይሄው ዕዳ ግን ኃይል ባላ
ቸው ቢወዱ መልካሙን ነገር ለማድረግ ችሎት ባለባቸው በት
ልልቆቹ ይወድቃል ይህ የሕዝባችን ጭንቀትና መሻት እያን
ዳንዱ ኢትዮጵያዊ እንደ የራሱ አድርጎ ሊመረምረውና ሊማ
ረው ይገባዋል ዛሬ የእንቅልፍና የምኝታ ዘመን ሊሆን አይ
ችልም ሌሎች ሕዝብ በብዙ ትጋትና ኃይል ኑሮዋቸውን
ሊያሻሽሉ ዘወትር እንዲህ ሲሰሩ ሳሉ አብሮ እሽቅድድም
ያስፈልጋል ፡፡

፪ና ፡ ከኢትዮጵያ ጭንቀት ልጆቿ ሥራ የማይወዱ ስለ ሆነ ነው ፡፡

ሥራ የማይወድ ሕዝብ እንዴት ሊሠለጥን ይችላል እን
ግዲህ ሥራ አለመውደድ በሕዝቡ ሕይወት ሲታይ ይህ የጭ
ንቀትና የመከራ የሞትም ፈታውራሪ መሆኑ እጅግ የተረዳ
ነገር ነው ፡፡ እያንዳንዱ በገዛ ሥራውና በገዛ ቤቱ ታካችነት
ቢያሳይ ምንም እንኳ ለገዛ ጠቀሜቱ የሚደርስ ቢሆን የሕዝ
ቡን ሕይወት ይጐዳል ፡፡ ታካችነት ሥራን አለመውደድ ለሕዝ
ብና ለመንግሥት ጠቀሜት በሚሆን ነገር ደግሞ ስንቱን ጉዳ
ት ያመጣል በዚህ በአገራችን ገና ሥራና የሥራ ጥቅም አል
ታወቀም ያወቁት ያሉም እንደሆን እጅግ ጥቂቶች ናቸው ፤
ሥራ ለሚወድና ለሚሠራ ሰው እንደ ጉራጌ ነው ይባላል ፡፡
እውነትን ሊፈርድ የሚወድ ያለ እንደሆን ግን የከተማው ሕይ
ወት አለጉራጌ ፈጽሞ በሞተ የሥራ ሕይወት በርሳቸው በኩል
ብቻ ይንቀሳቀሳል እንዲሁም ከውጭ በሚመጡት ሰዎች የስራ
ሕይወት ይታያል ፡ ሥራቸውን እየሠሩ ቤታቸውን ሰተት ብለ

ው የሚገቡቱ ሊመሰገኑ ይገባቸዋል ። ክብራቸውም ሊታይላ
ቸውና ሊመሰከርላቸው ስለዚህ ጕራጌዎች ለሕዝቡ ሕይወት
ጨው ናቸው እንጂ ንቀት የሚገባቸው ሰዎች አይዶሉም ።
እርሳቸውን በመስደብ ግን ተሳዳቢው የሥራ ጠላት መሆኑን
በገዛ ራሱ ይመሰክራል ። ሥራን እንደ ነውር እየቈጠሩ የጨዋ
ልጅነኝ እያሉ ሥራ የማይገኝበትን እንጀራ በደጅ ጥናት ለማ
ደን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉ ለስርቆትና ለማታለል ለመግደል
ለቅምያ ብቻ ለማድባት ግድ ይሆንባቸዋል ፡፡

በሕዝብ መካከል ለሥራ ብቻ የተፈረደባቸው አንድ ወ
ገን የሆኑት የሰዎች ክፍል የለም አገሌና አገሊት እንጂ እኔ
ልሠራ አይገባኝም ሊል የሚገባው የለም ይህን ማለት ይቅርና
ሥራ እጅግ ክቡር ነገር እንደሆነ እንጂ እንደ ነውረኛ ነገርና
እንደሚያሳፍር አድጎ በሕይወቱ ሊያሳይ አይገባውም በሥራ
ቸውና በምሳሌያቸው በሥራ ማሰናከያ የሆኑትን ሰዎች ብቻ
ስድብ ይገባቸዋል ፡ የተገባ ሥራ መሥራት ከማይለወጠው
ከአምላክ ደምብ የገባ ነው ፤ ስለዚህ እንደ ሌሎቹ ኃጢአት
ሥራ የማይወዱ ሰዎች ወደ ዘለዓለም ስድብ ይደርሳሉ (ዳን ፲፪ ፪

መኳንንቶችና ትልልቆች ሰዎች ወይዛዝሮች እመቤቶ
ችም ሁላቸው ሊሠሩ ሥራ ሠሪዎችንም ማፋጠንና ማበርታት
ይገባቸዋል ። በቀድሞ በሮማውያን ዘመን ሳይቀር አያሌ ከሕ
ዝቡ ትልልቆች የእጅ ሥራን እጅግ ይወዱ ነበር ፤ በጊዜው
መንግሥታቸውን ያገለግላሉ ቤታቸው ከገቡ ደግሞ የአታክ
ልት ሥራ የእርሻ ሥራ በገዛ እጃቸው ይሠሩ ነበር ።

አንድ ዘመን የሮማ መንግሥት ጋሊ በተባሉ ሕዝብእጅግ
ችግር አገኘች የሮማ ሰዎችም ቺነቺናቱስ ወደተባለ ጀግና ሰው
ረድኤቱን ይለምኑ ዘንድ መልእክተኞቻቸውን ላኩበት የተላኩ
ትም ቺንቺናቱስ በገዛ እጁ መሬቱን ሲያርስ ቆያቸው ፡፡ እር
ሻውን ትቶም ወደጦር ሄደ ጠላቶችንም አሸነፈ ። ከዚያ በኋ
ላም ስራውን በፈጸመ ጊዜ እንደገና ወደ እርሻው ማረስ ተመ
ለሰ ፡፡ እንግዲህ ስራን እየጠሉና እንደነውር እያዩት እንዴት
አድርገው አገራቸውን ይጠቅምዋታል ፤ አንዱ ከኢትዮጵያ
ትልቅ ጭንቀት እንሆ ስራ የአሠራሩም መንገድ ገና አል
ታወቀም ። አያሌ ሲሰሩ ሳሉ ነጠላቸው እጃቸውን እያለበሰ
ችግር ይሆንባቸዋል ፡፡ ስለዚህ በፍጥነትና በትክክልነት ከመስ
ራት ከነጠላቸው ወይ ከሸማቸው ሲታገሉ ይውላሉ ፡፡

ስራን መስራት ማወቅ ብቻም አይበቃም ፡፡ ስራውን የሚ
ከናወንበት መንገድ መምረጥም ይገባል ፡፡ በሁሉ ነገር መታ
ደስ ያስፈልጋል ፡፡ የተሻለውን ነገር ማድረግ እንጂ የለመድ
ኩትን አለቅም ማለት ወዴት ያደርሳል ፤ እያንዳንዱ በተመደ
በለት ስራ በብዙ ትጋትና ፍጥነት በየስራው ሊንቀሳቀስ ይገባል
ስራ ከፍጥረቶች ሁሉ ልንማረው እንችላለን ፡፡ ዛፎችና አታ
ክልት በነፋስ ሲወዘወዙ ይታያሉ ሕይወታቸውንም ያስታው
ቃሉ ። ገብረ ጕንዳን ለሚመጣው በማሰብ ያህል በስራቸው ወዲህና
ወዲያ ይራወጣሉ ፡፡ እንዲሁም ሌሎች ፍጥረታት በተፈጥሮ የተ
ሰጣቸውን ስራ በትጋት ይፈጽማሉ ፡፡ ፍጥረታት ለከንቱ አል
ተፈጠሩም ፤ በእግዚአብሔር ከንቱነት የለምና ። የእግዚአብ
ሔር ሕያውነትና በስራ መያዙን በስራቸው ይመሰክራሉ ፡፡ ጌታ
ችን እንዳለ ፤ አባቴ እስከ አሁን ይሰራል ፡፡ (ዮሐ ፭ ፤ ፲፯)እግ
ዚአብሔር በሀኬት አይውልም ፤ ስለዚህም የእግዚአብሔር ልዩ
ልዩ ፍጥረቶች እያንዳንዳቸው በተፈጥሮአቸው የተደነባላቸውን
ስራ ይፈጽማሉ ፡፡ ስለዚህ ሕዝባችን እንደሚገባው ስራ ምን
መሆኑን ባያውቅ ፤ ትልቅ የሚያጠፋ ጭንቀት አለበት ፤ እንግ
ዲህስ ሕዝባችንን ለማዳን ብነወድ እያንዳንዳችን ባለንበት
ስራን መውደዳችንን እንግለጥ ፤ እርስ በራሳችንም ምሳሌ እን
ሁን የማይንቀሳቀስ ደንጊያ ነው ፤ ሕይወት ያለው ግን በስራው
ሊንቀሳቀስ ይገባዋል ። ዕ ገ

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

የሮዐል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ልጅ ወይዘሮ የሺ እመቤት ።

ትርጓሜ

አንዲት የኢትዮጵያ ፕሬንሴስ ወዳውሮፓ ለትምህርት ትሄዳለች

ጂቡቲ በ፳፯ቀን ከ አልሃራም ጋዜታ መልክተኛ ።

ጂቡቲ የተለየ ባቡር ከ፪ሳሎን ጋሪዎች ጋር ዛሬ ጠዋት
ደረሰ ፤ በውስጡም ፕሬንሴስ የሺ እመቤት የኢ መ አ ወ
ልዑል ተፈሪ መኰንን ልጅ ነበረችበት ፤ ከሷም ጋር እህቷና
የእህቷ ባል ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው ደግሞ ዶክተር ማር
ቲን ከሚስታቸው ጋር ነበሩ ። ፕሬንሴስ የሺ እመቤት ገና ልጅ
እድሜዋ ፲፯ዓመት ያላት የረቀቀችና በጣም ብልህ ነች ። ዛሬውኑ
ከዶክተር ማርቲንና ከማዳም ማርቲን ጋር ፓርቶስ በሚባል መር
ከብ ይሳፈራሉ ፤ የቀሩት መልክተኞች ወዳዲስ አበባ ይመለሳሉ።

የሺ እመቤት ማለት ከሺ ሰው በላይ ሆና የምታዝ ማለት
ነው ። ፕሬንሴስ ሆይ የዘመዶችዎን ቤተ መንግሥትና ያባትዎ
ትልቅነትና ክብር ያለበትን አዲስ አበባን ለምን ጥለው መጡ
ከተወደዱትስ ዘመዶችዎና ከወንድሞችዎና ከእህትዎችዎ ለም

ንደርቃሉ የዚህስ የሚአደክመው የ፰፻ኪሎ ሜትር ሌትና ቀን መንገድዎ ምን ይሆን ምክንያቱ ዛሬ ማታስ ተሳፍረው ጭቅ ጭቁን የደመናን ጭለማ የቀይ ባሕርን ሙቀት ወደሚአገኙዎት ሲሄዱ ወዴት ይሆን የሚደርሱበት ብዬ ጠየቅኋቸው ።

(የፕሬንሲስ ምላሽ) እከምብሪድጋር እሄዳለሁ ከዚያም እስ ከእድገቴ የትልቆች ደረጃ ድረስ ትምህርቴን እቀበላለሁ የመን ገዴም ምክንያትና ፈቃዴ ይኸ ነው ። ይኸ መሆኑ የኛ የኢ ትዮጵያ ፕሬንስና ፕሬንሲሶች አስቀድመን በትምህርት ከልቀ ደምን ለኢትዮጵያስልጣኔ ሌላ ምንም ተስፋ የሚሆነን የለም ለትልቆችና ለቴንሾች አንዲት ምሳሌ እንድሆን ነው አባቴ የፈለገውና ስለዚህ ትእዛዙን ተቀብዬ አገሬን ትቼ ስመጣ የመ ንገዱን ድካም ፡ ብርድና ሙቀትን አልፈራም ።

አባቴ ሲማር ሲአስተምር በትምርህት ከሠለጠኑትም ጋር ሲኖር ስልጣኔንና የኢትዮጵያ ልጆች ሰልጥነው እንዲረዱት ማስፈለጉን ስለተረዳ ነው አለችኝ ።

(ስመልስላት) ወየው ጉድ እንዴት ያለ የከበረና ብርቱ የሆነ አሳብ ነው ፤ ነገር ግን እመቤቴ ፕሬንሲስ ሆይ በአየር መለዋወጥ ይልቁነም ስለእንግሊዝ አገር ብርድ ሕይወትዎንም ሆነ በጤናዎ ምክንያት ሁሉ ደግሞ ከዛሬው ዘመን ሰዎች ተጠ ንቃቂ እንዲሆኑ ፤ ትምህርትዎን ይማሩ አመልዎ ደህና እንዲ ሆንና እንዲጠነቀቁ ፤ ለሁሉ ሰውና ለድሆችም ደግ እንዲሆኑ ትዕቢተኛ እንዳይሆኑ ፤ ወዳገርዎም በጤና ተመልሰው ላገርዎ ልጆች ምሳሌ እንዲሆኑ ብዬ አልኳቸው ።

እናንተን የኢትዮጵያ ወዳጆች አመስግኜ ይኸቹ የኢት ዮጵያ ፕሬንሲስ የምትሄድበትን መልከሙን አሳቧን ፈጽማ መ መለሷን እንድትአምኑ ይሁን ።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፮ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም

ከእንቅልፍ ስለመንቃት ።

፩፻፳፰ ገጽ ተከታይ ።

ኢትዮጵያ ትበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር ብሎ ዳዊት ንጉሥ የተናገረውን ቃል እነሆ ሁላችሁ ብትመለከቱትና ብት አስቡትም ። ኢትዮጵያ ያላየችውን ከማየት ያጣችውን ከማግ ኘት ያልተሠራውን ከመሥራት ራሷን ከፍ ከፍ ከማድረግ በቀር ዝቅ ዝቅ የሚአደርግ ነገር ምንም አላገኛትም ይልቁንም ከት ልቁ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከ ንግሥተ ነገ ሥታት ዘውዲቱና በልዑል አልጋ ወራሻቸው ተፈሪ መኰንን ዘመን ሰው ሁሉ ለራሱ የሚበላውን የሚጠጣውን የሚለብሰ ውን ማየት ይቅርና የምድሪቱን ማማርና የሥራውን መተካከል ብንአየው ገደሉን አፍርሰው ሜዳ ፤ ፈረፈሩን ደልድለው ደረጃ በየሐሳባችን እንደልባችን መንጐጃ ። በእግር እንኳ ሳይሆን በአቶሞቢል በባቡር በእግራችንም ብንሔድ እንኳ ጭቃ አይነ ካን ለንቅፋት አይመታን በየሥራችን ውለን ዕድሜ ለንግሥ ታችን ዕድሜ ላልጋ ወራሻችን እያልን በደኅና ወደ ቤታችን የምንገባ ስለ ሆነ እኔም ባለኝ አቅሜ ይህነን አስቤ ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት የሚለውን ንባብ ወደ ኋላዬ አስቀ ርቼ ወዳርትዓ አገሪነ ውስተ ፍኖተ ሰላም ከሚለው ተነስቼ ፍለ ጋዬም ለይኩን ብርሃኑ ለእግዚአብሔር አምላክነ ላዕሌነ እስከ ሚለው ለመድረስ ነው ከዚህም ሌላ አሳቤን እጽፋለሁ ልዑል ጌታዬ በቀድሞ ዘመን የነበረውን ግፍና መከራ መርምረው አስበው እስረኛውን ሁሉ ከብዛቱ የተነሣ ደግሞም በርስትም በገንዘብም የተጣላ ሰው ሁሉ በአፈ ንጉሡና በወምበሮቹ ላይ የሚነጋገር ስለ ሆነ የታሰረ ሰው ሁሉ በቶሎ ቀርቦ ነገሩ የማ ይጨረስ ነበርና ። እገሩ ቤቱ ነብረቱ እየራቀበት ስንቁን የሚ አቀብለው ዘመድ እያጣ ጠላቱን እፋርደዋለሁ ብሎ ያስር ቀን ወይም ያስራ አምስት ወይም የሀያ ቀን የሚሆን መንገድ ተቈ ራኝቶ ከመጣ በኋላ ወደ ችሎት የሚቀርበው በአፈ ንጉሡና በወምበሮቹ ላይ ስለሆነ ከሕዝቡ ብዛት የተነሳ በቶሎ ቀርቦ ነገሩ አይጨረስም ነበር ።

መኰንን ዘበርቱዕ ይኄንን ወኢያደሉ ለገጽ የተባሉ ልዑል ጌታዬ የሕዝባቸው ደም በከንቱ እየፈሰሰ በመቅረቱና ሕዝብ ም በሕዝብ ላይ ጨካኝ እጁን በማንሣቱ ተደገፎ እሞታለሁ ብሎ በለማሰቡ አዝነው ፤ ዓመፀኞች ለሆኑ ሰዎች ሁሉ በቶሎ ቀርበው መመርመሪያ የዳኝነት ቤት በሰኔ ፲፯ አቁመዋል ከተ መረመረም በኋላ እስከ አስራምስት ቀን ድረስ ነገሩ እንዲፈጸም እስረኛው የሚቀመጥበት ቤት ተሰርቷል ይኸውም በራስ ቢት ወደድ ተሰማ ግቢ በነበረው ቦታ ነው ፤ ለዚሁም ሥራ የተመ ረጡ ወአንከርዎን ሞገሰ ቃሉ ወጣዕመ ነገሩ ወማዕማዕ አፉሁ የተባሉ ። ሁለተኛም የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል የተባሉ ክቡ ር ደጃዝማች መስፍን በቀኝና በግራቸው ተመርጠው የተቀ መጡ ፤ እምከመ ሀለው ፪ቱ ወሰለስቱ እሄሉ እነ ማዕከሌሆሙ ብሎ ጌታ የተናገረላቸው ክቡር አቶ ወንዴ ፤ ክቡር አለቃ ዳኜ ክቡ አለቃ ሠርፁ ፤ ክቡር አቶ ተሰማ በልሁ እነዚህ ነገሩን መር ምረው በቶሎ እንዲፈጸምና ባለ ደምም ወደ ሥራው እንዲሄድ የሰውን ሕይወት ያጠፋውም ወደ መጨረሻው ነገር ወደ ሞት እንዲሄድ የመረመሩትን ቃል ትጉህ ዘኢይነውም በተባለው በአቶ በቀለ ዛማኔል እጅና በዝቅተኞቹ በአቶ ተፈሪ ይገቶ በአ ቶ ወንድሙ ተሸበሩ እጅ ተጽፎ ከልዑል ችሎት እስረኛው ቀርቦ የመዝገቡ ቃል ተነቦ ፍርዱ በፍትሐ ነገሥት እንዲፈጸ ም አድርገዋል ። ይኸውም ኃሳባቸው ለሕዝብ መራራትና አገርን ለማስልጠን እንደሆነ ያስረዳናል ።

ወንድሙ ተሸበሩ

የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ያደ/ጉት የቴአትር ጨወታ ።

በሐምሌ ፲፱ ቀን የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎ ች ትምርትቤቱ በተዘጋበት ቀን በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና በልዑል አልጋ ወራሽን ተፈሪ መኰንን በብዙ መኳንንትና ወይዛ ዝር ፊት ደስ የሚያሰኝ የቴአትር ጨወታ አሳይተው ነበርና ጨ ወታው ለሕዝብ የሚጠቅም ትምህርት የሚሰጥ ስለሆነ ሕዝቡ እንዲየየው ተብሎ በነሐሴ ፳፮ ቀን በግሴዝ ሆቴል ጨወታው ተደገመ ። ጨወታውን ለማየትም ልዑል የኢ መ አ ወ ተፈሪ መኰንንና ልዕልት ወይዘሮ መነን ክቡራን መኳንንትና ብዙ ሌላ ሕዝብ ተሰብስበ ነበር ።ጨወታው አምሮ ከታየ በኋላም ስለትም ሀርት ቤቱ በትጋት የሚያሠራና የሚያስብ ክቡር አቶ በቀለ ሀብ ተ ሚካኤል የሚከተለውን ቃል ተናገረ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን

ልዕልት ወይዘሮ መነን

ክቡራን የኢትዮጵያ አርበኞች መኳንንቶች ወይዛዝሮች የዛሬውን በዓላችንን አክብራችሁ በመምጣታችሁ ልክ የሌለው ደስታ ተሰምቶን እናመሰግናችኋለን ። ይህች የብርሃን ጊዜአችን የኢትዮጵያን ሕፃናት ሁሉ ወደ ትምሕርት መሪ የመሆን እጣዋ ደርሶላት የታደለች በመሆንዋ እጅግ ደስ ያሰኛል ።

የትምህርት መሪነቷንም እነሆ የኢትዮጵያ ልጆች በሥልጣኔ መንገድ ለመሄድ ፈቅደው በአረማመዳቸውና በሚሠሩት ሥራ በማናቸውም የሚአከናውኑት ሐሳብ ሁሉ ያሳይላታል

ይልቁንም ለኢትዮጵያ ለክብሯና ለደስታዋ በሰፊ.ው. አሳቢ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ለማናቸውም ነገር ሁሉ ላገር ጥቅምንና ትርፍን ክብርንም እንደ መስተዋት ገልጦ የሚአሳይ ትምህርት እንደሆነ አውቀው ለኢትዮጵያ ከሚደክሙላት ከብዙዎቹ ነገሮች ሁሉ ዓይነተኛው ትግልዎ የትምህርት ቤቶችን ማበራታትና የኢትዮጵያንሕፃናት በትምህርት እንዲበረቱ ለማነቃቃት እንደሆነ የዓለም ጆሮ በትክክል አድምጦ ሒሊናው ተረድቶታል ።

ልዕልናዎ በ፲፱፻፲፬ ዓመተ ምሕረት የዳግማዊ ምኒልክን ተማሪ ቤት ለመጐብኘት መጥተው ለተማሪዎቹ ከበላበት አልተወለድንም በገንዘብ አልከበርን ወይም አልበዛንም ብላችሁ አትዘኑ ትምህርቱን ሳይመረር እስከመጨረሻው የደረሰ ሰውይኸንን ሁለቱን ማዕርግ ያገኛል ። ሰሎሞን ከዕንቁ ጥበብ ትበልጣለች ያለውን ተመልከቱ ከለማወቅ ነጻነትን አገር መውደድን ባለማወቅ ማፈርን የሚፍቁ እውቀትና ፍቅር ናቸውና እውቀትን ፍቅርን ለማግኘት እስከሚቻላችሁ ጣሩ ብለው የሰጡአቸው ጣፋጭ ምክርዎ የኢትዮጵያን ሕፃናት ሁሉ ልብ የሚነክና ለትምህርት እንዲተጉ የሚአነቃቃቸው ሆኖ ምንም ከዚህ ከሐገራቸው ተምረው ለጊዜው ለሚአስፈልግ አገልግሎት እንዲደርሱና እንጀራን እንዲአተርፉ ቢታወቃቸው ከዕንቁ የምትበልጥ ጥበብ እየታሰበቻቸው እንደልዑል ምኞትና ሐሳብ ከፍ ወዳለው ወደእውቀት ደረጃ እስከመጨረሻው ደርሰው ላገራቸውና ለመንግሥታቸው ተመስጋኞች አመስጋኞች አገልጋዮች መሆንን እየተመኙ ከገራቸው ከባቶች ከናቶቻቸው ከዘመዶቻቸው ተነጥለው በየጊዜው እየመነኑ በውጭ አገሮች በኤውሮፓ በሜሪካ በምስር በሌሎችም አገሮች የሔዱ ወንድሞቻችን ከልዕልናዎ ቸርነትና ለጋስነት የመላው እርዳታ እያገኙ እውቀትን ለማትረፍ በያሉበት ይጥራሉ አንድ አንዱም ወንድሞቻችን እንደዚሁ ስለትምሕርት እውቀትን ስለመፈለግ ሕይወታቸውን ያሳለፉ አሉ ።

ይህ የመስከብን ንጉሠ ነገሥት የተላቁ ጴጥሮስን የሚመስል የልዑል የማይረሳ ደግ አድራጎትዎና ሐሳብዎ ሁሉ በታሪክ ተጌጦ ለዘላለም ወደፊት ለሚመጣው ትውልድ እንዲኖርልዎ ጥርጥር የለበትም

አሁንም የዳዊት የሰሎሞን አምላክ ግርማዊት ንግሥታችንን ዘውዲቱ ምኒልክን ጠብቆ የልዑልን እድሜዎን አርዝሞ ለውዲቱ አገራችን ለለምለም ኢትዮጵያ ያዘጋጁላትን መልካም አሳብዎን ሁሉ እንዲአስፈጽምዎ ስለልጆቿም ክብር የሚደክሙትን ድካም ሁሉ የድካምዎን ዋጋ ለወደፊቱ በቡርሃን አገዛዝዎ ለሰፊው መንግሥትዎ የኢትዮጵያ ልጆች በእውቀት አገልግሎታቸው እንዲከፍልዎ በፍጹም ልባችን እንመኛለን ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

በቀለ ሀብተ ሚካኤል

A SON ALTESSE IMPERIALE TAFARI MAKONNEN

Hériter du Trone d'Ethiopie,

A SON ALTESSE LA PRINCESSE MANEN,

Aux Honerables Chefs, Dignitaires et Dames,

Nous vous remercions d'avoir bien voulu honorer de votre présence, qui nous cause la joie la plus vive, notre féte de ce jour. Il est heureux que l'époque lumineuse actuelle ait éte choisie pour guider la Jeunesse Ethopienne dans la voie du développement intellectuel.

Ce développemment est démontré par les progrès dans la voie de la civilisation et par l'activité de la Jeunesse Ethiopienne. Le monde entier a compris que Votre Altesse Impériale, qui se proccupe si largement de la renommée et du bonheur de l'Ethiopie, S'est rendue compte que c'est de l'instruction que découlent l'honneur, l'interêt et les avantages. Aussi, de tous les efforts qu'Elle fait pour la prospérité du pays, le principal est d'encourager les écoles afin de développer les facultés intellectuelles de la jeunesse Ethiopienne.

Lorsque Votre Altesse Imperiale est venue, en l'année 1914, visiter l'Ecole Ménélick II, Elle a declarée aux éleves qu' il ne fallait pas être affligé du fait de ne pas appartenir à une famil le noble ou riche, car celui qui, saus se décourager 'aura poursuivi ses études jusqu'à la fin peut s'élever jusqu'à ces dux conditions. Songez à ce qu'a dit Salomon "la scince est plus precieuse que les joyaux" l'etait d' ignorance de la patrie étant une cause de honte, efforcez-vous donc de rechercher le seul moyen de l'effacer c'est-à-dire daspirer toujours à la connaissance et à l'union.

Les excellents avis que vous leur avez ainsi donnés, touchèrent le coeur des jeunes Ethiopiens et les encouragèrent à devenir studieux. Bien qu'ils sachent que l'instruction qu'ils peuvent recevoir ici leur suffit momentanèment pour gagner leur vie en servant leur pays, ils serappelérent toujours que „l'instruction est plus précieuse que les joyaux" et, désireux

de suivre le conseil exprimé par Votre Altesse impériale d'arriver au plus haut degré de la connaissance afin de devenir des serviteurs, dignes de louanges, de leur pays et de leur gouvernement, ils quittent leur Patrie et leurs proches et se rendent à l'étranger, en Europe en Amérique, en Egypte et dans d'autres pays. Grâce à la bonté et à la générosité de Votre Altesse Impériale nos frères qui ont obtenu Son aide, s'efforcent là où ils sont, d'acquérir les connaissances les plus étendues.

Certains d'entre eux ont sacrifié leur vie pour acquérir la science. Vous pouvez être assurée ALTESSE que ces bienfaits et cette sollicitude qui sont comparables à ceux du Tzar de Russie PIERRE le Grand, seront enregistrés dans l'Histoire pour toujours et demeureront, pour la prospérité le témoignage le plus éclatant de votre gloire.

Nous faisons des voeux, du plus profond de nos coeurs pour que le Dieu de David et de Salomon veuille bien portéger notre Impèratrice S. M. ZAOUDITOU MENELICK et donner une longue vie à Votre Altesse Impériale afin de Lui permettre d'acomplir les précieux projets qu'Elle a élaborés pour la prospérité de notre cher Payis. Nous souhaitons également que les enfants de l'Ethiopie vous témoignent leur gratitude par les services et le concours éclairé qu'ils vous apporteront en retour des efforts que vous avez faits pour eux.

Vive l'Ethiopie.

ማስታወቂያ ።

በነሐሴ ፲፪ ቀን ፩፻፲፪ ገጽ በወጣው ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ የመንግሥት ሠራተኞች የሆኑ የኢትዮጵያ ወጣት ልጆች ሠረቀ ብርሃን ብለው የሠየሙት ተማሪ ቤት አቋመዋል ብለን አስታውቀን ነበርና ይኸነኑ ተማሪ ቤት ስለሀገራቸው ስለኢትዮጵያ ፍቅርና አገልግሎት የመሠረቱትን ሰዎች ከዚህ በታች እንደተጻፈው በዝርዝር ስማቸውን እንገልጻለን ።

፩ኛ የክቡር ፕሬዚዳን ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል የጽሕፈትና የአርሻ ምኒስትር

፪ኛ ዋና ፕሬዚዳን ክቡር ልጅ ኤፍሬም ማህለ ጊዮርጊስ

፫ኛ አቶ መታፈሪ ወልዴ

፬ኛ ልጅ ለማ ወልደ ገብ ኤል

፭ኛ አቶ ጸጋዬ ገብረ ጻድቅ

፮ኛ አቶ በላቸው ይመሩ

፯ኛ አቶ ጽጌ ወልደ ጻድቅ

፰ኛ አቶ ወልደ ሰማያት

፱ኛ ልጅ ብርሃነ ሥላሴ አባየሬ

፲ኛ አቶ ወዳጆ አሊ

፲፩ኛ ልጅ ኃይሌ ወልደ መስቀል

፲፪ኛ አቶ ወልደየስ ወልዴ

እንዲሁም ደግሞ የሀገርን ፍቅር የምትሰብከው ትልቂቱ የፍቅርና አገልግሎት ማኅበር በዚህ ማኅበር ውስጥ የአገልግሎቷን ሥራ ለማስፋት አንደኛ ማኅበር ሆናለች ።

ክቡራን ጌቶቻችንና እመቤቶቻችን ደግሞም ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ሆይ ከዚህ በላይ እንዳአስታወቅነው ለጊዜው በሥራ ላይ የተቀመጡ ወንድሞቻችን በቀን ለመማር ስለስራቸው ብዛት ጊዜ ስለማያገኙ ግርማዊት ንግሥታችንና ልዑል አልጋ ወራሻችንን ተማምነን ይህን ተማሪ ቤት ከምሽቱ ባስር ሰዓት ተከፍቶ እስከ ሌሊቱ ፩ሰዓት ድረስ እርስ በርሳችን የምንማማርበት መከፈታችን ለሀገር ፍቅርና ለታላቁ መንግሥታችን አገልግሎት ነው እንጂ እውነትም ለንግድና ለመጥፎ አካሄድ አይደለም ።

ንዑ ደቂቅየ ወስምዑኒ ። ፈሪሃ እግዚአብሔር እምህርክሙ ።

ስለዚሁ ስለመልካሙ አካሄድ ክቡራን ጌቶቻችንና እመቤቶቻችን ደግሞም ክቡራን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ሆይ እናታችን ኢትዮጵያ ምንም ከዚህ ቀደም የሚበቃ እውቀት ኖሯት ነጻነቷን እስከ ዛሬ ብትጠብቅና ፈጣሪዋን እየለመነች በመልካምም አስተዳደግ ልጆቿን ብታሳድግ ዕውቀት የማትጠገብ ናትና ወደፊት ሀገራችን ወደታላቁ እውቀት እየገፋች እንድትሄድ እናንተ ለናታችሁ ታዛጋ የሆናችሁ ምሩቆች ኢትዮጵያውያን እንደምትወዱ አውቀን ይህም ተማሪ ቤት ለሁላችንም ክብርና ማዕርግ ነውና እንደሚቻላችሁ ለሠረቀ ብርሃን ተማሪ ቤት እንድትረዱ በታላቅ አክብሮት እንለምናችኋለን ።

ሠረቀ ብርሃን በኢትዮጵያ።

በአውሮጳ አገር ሚከሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት ሚየባል ባለፈረስ ስዓት ከሴሙ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር ፲ መሐ ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፳ ብር ፫ ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፱ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፮ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር ፫ሩብ
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጇ	፲፩ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጇ	፲፫ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጇ	፻፵፫ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፮ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፴፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፲፯ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፱ ብር
፡ ባለአንበሳ	፡፡	፻፵፫ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፰ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፱ መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፱ ፍራንክ ፫
ነ'ያ ብር	፳ ሊሬ እስከ ፶
ባአንድ ጊኒ	፲ ብር እስከ ፴፫ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፮ ብር

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቀቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።



ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሸቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ካኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በየይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን ባያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመክከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክስል የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኩፍ ሱቅ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

በማስታወቂያ ያወጣሁት ሎተሪ ወረቀቱ በተባለው ቀን ሳይሸጥ ስለቀረ ቀኑ በጥቅምት ፭ ቀን ፲፱፻፳ ከኩለቀን በኋላ በ፱ጠኝ ሰዓት መለወጡን አስታውቃለሁ ። ቦታውም በከዚኖ አዲስ አበባ ስቴሊዮ ቴዎፌሎ ቤት ነው ። ሎተሪ የገዙ ሁሉም ልዩ ልዩ ጨዋታ ያያሉ ።

ሃብተሥላሴ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሴላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፊታውራሪ ዱሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሄስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ቤርሊዬ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቀኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ አቶሞ ቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዘማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጉብርና አጉብር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፤ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ማጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፤ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምባሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ። የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፯
3 me ANNÉE № 37

ሐሙስ መስከረም ፭ ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 15 SEPTEM BRE 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen , Héritier du trône d' Ethiopie , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ቅዱስ ሩፋኤል በዓል አከባበር ፤

ጳጉሜን ፫ ቀን ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከክቡራን መኳንንቶች ጋራ ባማረ አጀብ ወደ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን ሄደው በዓሉን አክብረው ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመለሱ ።

በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ግቢም ባመት ባመቱ እንደተለመደው ለሊቃውንቱና ለካህናቱ ለተማሪውም ሁሉ ትልቅ ግብር ተደርጎ ሊቃውንቱና ካህናቱ ተማሪውም ሁሉ በልዑል ፊት የደስታ ምሳ ሲጋበዙ ውሎ ለልዑል አልጋ ወራሽ ዕድሜ እየለመነ እግዚአብሔርንም እያመሰገነ እየቤቱ ሄደ ።

በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የተደረገ የቸርነት ሥራ ።

ጳጉሜን ፬ቀን በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ግቢ ለድኃው ሁሉ ምጽዋት እንደሚሰጥ አውቆ ድኃ የሆነ ሁሉ ተሰበሰበና በተራ በተራው እየተጠራ ገንዘብ የሚያስፈልገው ገንዘብ ልብስ ለሚያስፈልገው ልብስ ከብት የሚያስፈልገው ከብት እየተቀበለ ልዑል አልጋ ወራሽንና ልዕልት ወይዘሮ መነንን እያመሰገነ ሔደ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንና ልዕልት ወይዘሮ መነን እንደዚህ ያለውን የደግነት ሥራ የሚያዘወትሩ ናቸው ። ለድኃ የሚሰጥ ለእግዚአብሔር ያበድራል የተባለውን ቃል ፈጽመዋልና ይህን ብድራቸውን እግዚአብሔር እንዲመልስላቸው የታመነ ነገር ነው ።

ምጽዋቱ እንደሚያስፈልገው እያዩ ይሰጡ የነበረም መምህር ኃይለ ማርያም ናቸው ።

ስለ ቅዱስ ዮሐንስ በዓል አከባበር ።

መስከረም ፩ ቀን ሰኞ ከሌሊቱ በ፲፪ ሰዓት ያዲስ ዓመት መጀመሪያ ምስራች ሰባት ጊዜ መድፍ ተተኰሰና የከተማው ሰው ሁሉ አበባ አበባውን ይዞ እየወዳጁ ቤት እየሔደ እንኳን ከዘመነ ሉቃስ ወደ ዘመነ ዮሐንስ ያሸጋገራችሁ እያለ የደስታ ምርቃት ሲመራረቅ ዋለ ። ያለፈውን ዓመት በደህንነት ያሳለፈልንና ያስፈጸመን አምላክ ይኸን አዲሱን ዓመት በሰላም እንደያስፈጽመን እንለምናለን ።

ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘው ዲቱ ። ዕድሜ ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ኃይልና ጽናት በኢትዮጵያ ይሁን ስንል እንለምናለን ።

ባሕረ ሐሳብ ።

በኢትዮጵያውያን ቍጥር በ፲፱፻፳ ዓ ም በዘበነ ዮሐንስ ዕለቱ ሰኞ ይውላል ። በዚሁም ዘመን ፱ ወንበር ይወጣል ። ፳፩ መጥቅ ፱ አበቅቴ ይሆናል ። ፩ ሕፀጽ ፩ መዓልት ፱ አበቅቴ ቢያጋጥሙት ፲፩ ይሆናል ፲፩ ሌሊት ፲፰ ጨረቃ ሆኖ ያድራል ። የጾም መግቢያንና መውጫን ለማወቅ የሚከተለውን ቃል ተመልከት ።

ጥር ፳፰ ቀን ነነዌ ።
የካቲት ፲፪ ቀን ዓቢይ ጾም ።
መጋቢት ፱ ቀን ደብረ ዘይት ።
መጋቢት ፴ ቀን ሆሣዕና ።
ሚያዝያ ፫ ቀን ስቅለት ።
ሚያዝያ ፭ ቀን ትንሣኤ ።
ግንቦት ፩ ቀን ረክበ ካህናት ።
ግንቦት ፲፬ ቀን ዕርገት ።
ግንቦት ፳፬ ቀን ጰራቅሊጦስ ።

ግንቦት ፳፮ ቀን ጾመ ሐዋርያት ።

ግንቦት ፳፱ ቀን ጾመ ድኅነት ረቡዕና ዓርብ ።

ይህንንም ጾም ለመጾምና ለየክፍሬ በዓሉ በደህና እንዲያደርሰን በትጉህ ልቡና እግዚአብሔርን እንለምን ። እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ለዘለዓለም በነፃነት ያኑራት ። ይህች ፡ ትንሽ ዕውቀቴን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች አከፍላለሁ ።

ቄስ ጸሐፊ ገብረጻድቅ ።

፪፻፺፫ ገጽ ተከታይ ።

የኢትዮጵያ ጭንቀት ።

፫ኛ፡ ከኢትዮጵያ ጭንቀት ፡ ያገር ፍቅርና (ፓትሪዮቲስም) የሕዝቡ አንድነት ገና እንደሚገባው ስላልታወቀ ነው ።

እያንዳዱ ራሱን ይወዳል ፤ የራሱንም ጠቀሜታ ብቻ ይሻል የራሱን ብቻ በመፈለጉ ደግሞ የባልንጀራውን በሚቻለው መንገድ ሊጎዳ ወይም ሊያጠፋ ይፈልጋል ፡ እንዲሁም ትጋቱና ዕውቀቱ ከዚህ ብቻ ይጠቀለላል ፡ እኔን ይመቸኝ እንጂ የሌላውን ምን አግዶኝ ። እንዲህ ያለ አመጸኛና መጥፎ አሳብ በሕዝቡ ሲበዛ እንዴት ያለ ጠቀሜታ ለኢትዮጵያ ይሆንላታል ፡ እንዲሁም ወገንና ወገን ለራሱ ብቻ ሲያስብ ራሱን ብቻም ሲያበላልጥ ቢኖር ኢትዮጵያ እንዴት ትሆናለች ፡ አንዲት ከተማ ወይም መንደር ተለይታ የራሷን ብቻ ስታስብ ምን ጥቅም ይሆንላታል እርስዋስ ለብቻዋ ምንን ማድረግ ይቻላታል የኢ. ዮጵያ ሕዝብ በፍጥረቱ አንድ ሕዝብ ነው ። አንድነቱ ግን አልታወቀም ፡ ስለዚህ አንዱን ወገን ጉዳት ሲያገኘው ሁለተኛው ወገን ጉዳቱ ወደርሱ እንደማይደርስ ሆኖ ይሰመዋል እርስ በርስዋ የተለያዩች መንግሥት ወይም ሕዝብ አትጸናም ጦርነት ሕዝብን ወደ አንድነት ሊያገባው አይችልም ጦር ፀብን ለማድረግ ደምንም ለማፍሰስ ብቻ ኃይል አለው አገሩን መሬቱንም ሊገዛ ይችላል የሕዝብን ልብና ፈቃድን ግን ከቶ ሊገዛ አይቻለውም ስለዚህ ከዚህ ሁሉ ጋር ሕዝቡ ተራርቆና ተለያይቶ ብቻ ይኖራል ሕዝቡን የሚገዛው የአገሩ ፍቅር በያንድአንዱ ሲሰርጽበት የአንድነቱንም ዕውቀትን ሲያገኝ ብቻ ነው

እንግዴህ አንዱ ከሕዝባችን ትልቅ ጉዳት ሊያመጣ የሚችል ከዚህ ላይ ነው ያለ ። ሁሉ እንዳንድ ሰው ሆኖ በአንድነትና በፍቅር ገመድ ሊተሳሰር ያስፈልጋል ከመንግሥቱም የሚገኘው ጠቀሜታ ለያንዳንዱ ወገን በትክክልነት እንደአገሩ መሻት ሊከፈል ግድ ያስፈልጋል ሕዝብ ከሕዝብ ጋር ሊተቃቀፍ አንድ ወገን አንድ ቋንቋ አንድ ደም እንደሆን አጥብቆ ሊረዳው ይገባል ጠላት ከሁሉ የበለጠ የሚጠቀምበት ነገር ከሕዝባችን ድካም ወይም ጉደሎነት እንደዚሁ ነገር የለም ተስፋው ሁሉ በዚህ ብቻ ታስርዋል ይህ ማለትም የኢትዮጵያ ሰው አንድነቱን አያውቅም በዚህ ግድ የለውም አንዳች አያስብም በማለት ነው ። ብዙች እንዲህ ይላሉ እንግዴህ እውነተኛው የአገር ፍቅር የኢትዮጵያም ደም አንድ እንዲሆን ወገንለወገንም እጅግ እንዲቀራረብ እንዲተዋወቅ እንዲተማመንም ማድረግ በዚህም ሁልጊዜ መስራት እንዲህ ያለው ስራ በዚህ እኰል ያለውን የኢትዮጵያን ጭንቀት እንደመዶሻ ቀጥቅጦ ከንቱ ያደርገዋል

፬ኛ፡ ከኢትዮጵያ ጭንቀት እጅግ የታመኑ የመንግሥት፡ አገልጋዮች ያነስዋት ስለሆነ ነው ።

ብዙች አገልጋዮች እንዳሉዋት እርግጥ ነው የታመኑቱ አገልጋዮች ግን እጅግ ጥቂቶች ናቸው እኒህ ጥቂቶችን ለማየት ግን ስንት ብዙ ደስ ያሰኛል ያያቸውና ያወቃቸው እውነተኛውንም አገልግሎት የሚወድ አዬ እንዲህ ያሉ አገልጋዮች ምነው በበዙ ሳይል አይቀርም ።

እንደነዚህም ያሉ የመንግሥትና የሕዝብ ሹማምንት በሕዝባችን ቢበዙ ስንት ጥቅም በሆነልን ። ከዚህ የነህምያ ሕይወትና ስራን ዘርዝሮ ለመግለጥ ይረዝማልና ፡ ከመንግሥት አገልግሎት የሕዝብ መሪዎች የሆኑትን ፤ የነህምያን መጽሐፍ አጥብቀው እንዲያነቡት እለምናቸዋለሁ ። በስራቸው ሕዝባቸው እንዲሠለጥንና እንዲጠቀምበት የሚያስቡቱ ስንት ያህል ይሆናሉ እኒህ ያልታመኑ አገልጋዮችሳ ምንድር ነው አውራ ግድፈታቸው ። በጉቦ መቀበል ነዋ ። ነህምያ ግን እንዲህ አላደረገም የሰውን ገንዘብ ይቅርና ፡ ከመንግሥት የታዘዘለትን ድርጎ እንኳን ለሕዝቡ እንዳይከብድ ብሎ ተወው ። ምነው እግዚአብሔርን ይፈራ ነበርና (እይ ነህ ፭ ፡ ፩ ፲፱)

ጉቦ በእግዚአብሔር ሕግ በጽኑ ትእዛዝ ተከልክሎዋል የተባቀዩን ዓይን የሚያሳውር በመሆኑ ። ሁላቸውም ጉቦ የተቀበሉ ሰዎች ቅኑን ነገር ከጠማማው ሊለዩ አይችሉም ነበር ። እንግዲህ አንድ አገልጋይ ጉቦ ቢወድ ፤ መንፈሳዊ ዓይኖች ብርሃንን ማጥፋት ነው እንግዲያስ እንዴት አድርጎ በሥራው ሕዝቡን ሊመራ ይቻለዋል ዕውር ዕውርን ቢመራ ፡ ሁለቱ ከገደል ይወድቃሉ ። እነኝህን ሰዎች ዮሐንስ መጥምቅ እንዲህ አድርጎ ይገሥጻቸዋል ። ደመወዛችሁ ይብቃችሁ ደመዎዝ ያነሡባቸው ለመንግሥት ሊያመለክቱ ይገባቸዋል ። መንግሥት ብመጥፎ ሥራቸው እንጅ ፡ በተገባው ደመወዛቸው አይጎዳም ። ስለዚህ ይህ ገንዘብ መውደድ ሕዝብን ያጠፋል ። ገንዘብ ወዳጆች ደግሞ መጨረሻቸው የዘለዓለም ጥፋት ነው ። በዚሁ ነገር የመጣ ቅዱሳት መጻሕፍት ሲገልጹ ፡ ገንዘብ መውደድ ፡ የጥፋት ሥር መሆኑን ይገልጣሉ ።

ዕ ገ

መልስ

ክቡር የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ዲሬክተር

ሙሴ አቤን በኔ የተነሣ ወደ ኩሪዬ ዴቲዮፒ ደብዳቤ ልከው ታትሞላቸው አያለሁ ።

ሙሴ አቤን በዚሁ ደብዳቤ ሕዝቡን በኔ ላይ ሊያስነሱ ፈልገው እያሉ ያለ ስሜ ስም ይቀቡኛል ፤ ስሜን የሚያስከፋ ቃል በጋዜጣ ሲወጣብኝ ዝም ብየ ማየትና በምር ስሞታ ሳልናገር መቀመጥ ደብዳቤውንም ለጻፉት ሰው ያመጡብኝ ቃል እውነት የሌለበት መሆኑን ሳላሳያቸው መተው አይሆንልኝም ።

እኔ ጽፌው የነበረ ቃል ሁሉ የበረ ነገሩ ዋና ማሰሪያው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ፤ በሙሴ አቤን የተነሳውን ነገር እውነተኛው መደቡን ማሲያዝ ፤ የተቃጠለበት ምክንያቱ ሳይታወቅ በቀረው በሙሴ አቤን ጎጆ የተነሳ ምን አለብኝ ብሎ እንደ

ልቡ የእንግሊዝን ዜጋ በኢትዮጵያ የገደሉት ሰዎች ሳይቀጡ ቀሩ ። እያለ የሚያበከውን የእንግሊዝን ጋዜጣ ታውቆቧል በማለት ስፍራ ስፍራውን ማስያዝ ። ይህ ነው እንጂ እኔ ሙሴ አቤንን ሕዝብ እንዲጣላቸው ያደረግሁበት ምንም የለኝ ። ሙሴ አቤን በመጣባቸው አደጋ በፍጹም ልቤ ነው አዝኘ ያለሁ ። ግን ደግሞ የእንግሊዝ ዜጋ በኢትዮጵያ አገር ተከራይቶት ሲኖር የነበረው ቤት እሳት ከተበላስ ምክንያቱን አስታውቄን እያሉ በእንግሊዝ የምክር ቤት ያሉት አማካሪዎች ይህን ያህል ከመ ጠየቅና ጋዜጣውም አያይዞ በኢትዮጵያ ላይ መንግሥትን የሚ ያነክክና የተጠላ ቃል በጋዜጣ ከማውጣት የሚያደርስ እንዳልነ በረ ነገሩ አድላዊ ያይደለ ሁሉ ፍርዱ ከኔ የተለየ እንዳይደለ ጥርጥር አላገባበትም ።

በሙሴ አቤን ደብዳቤ ከንቲባ ገብሩ በብርሃንና ሰላም ስለ ጻፉት ደግሞ የስሞታ ቃል አለበት ። እኔ ግን በከቲንባ ገብሩ ደብዳቤ ምንም የለሁበትምና ቢፈቅዱ እርሳቸው ራሳቸው ይመ ልሱ ብየ ትቸላቸዋለሁ ።

ዶ ኤ ዋይስ ጽንጌር ።

Dr Erich Weinzinger

ሥራን ለመውደድና ስንፍናን ለመናቅ ።

ሰው የተወለደው ለመንቀሳቀስ ነገርን ሁሉ ለመመርመር ምን እንደሆነ ለማወቅ ምንምን እንዲያደርግና ወዴት እን ደሚሄድ ነው ስለዚህ ባለጠጋም ድኃም ሳይቀር ያለስንፍና መሥ ራት ይገባቸዋል ። ሥራ ለነፍሳዊና ለሥጋዊ ይበጃል መጀመሪ የመታወክን ሕመም ያድናል ሁለተኛ የስንፍናን ። ሥራ ዋና የኃዘን መድኃኒት ነው ለሰውም የጤና ምንጭ ኃብት ለሕ ዝብም ትልቅነትና ልምላሜ ነው ። ሥራ ያከብራል ስንፍና ያዋ ርዳል ። ማለት ስንፍና ሰውንና ሕዝብን ወደ ባርነት ይመራ ቸዋል። ሥራ ግን ብርታትንና ነጻነትን ይሰጣቸዋል እንዲሁ ሥራ ያበልጥጋል ። በግንባራችን ላብ ያገኘነው መናኛ እንጀራ ከሰ ውነት ይሰማማል በሐሰት የተገዛው ነጭ እንጀራ ግን እንደ አመድ ተለውጦ ከጕሮሮ አያልፍም ማናቸውንም ቀን ሳትሰሩ በት እንድነገር አትመልከቱት ደግሞ ለኛ ዋናው ነገር ጊዜ እንደሆነ አሳቡ እንደጊዜ ካመለጠ አይመለስም ፥ ሥራ ጥጋብን ደስታን ክበሬታን ያመጣል ሥራና ድካም የመጀመሪያ መሰረት የሕዝብ ጉልበቶች ናቸው ግን ስንፍናና ችልታ (መዘንጋት) ወደ ባርነት ያደርሳሉ ። ሥራ ሁሉ ክበሬታ አለው እንደዚሁም ጠቀሜታ አለው ። በጣም የሚጣፍጠው እንጀራና ደስ የሚል ምቾት በራስ ላብ የተገኘ ነው ፥ ምንም የማይሰራ ምንም አይ ደለም ደግሞ ምንም ለመሆን አይችል ፥ ሥራ እውከትን ስን ፍናን ድህነትን ያርቃል ፥ ሰው ማናቸውንም ሥራ ቢይዝ በል ጅነቱ ወራት ማረፊያው በአካል ሰውነቱ ጊዜ ምርኩዝ በሽ መገለ ጊዜ መከሬ ይሆናል ። በጣም የሚሰራ ኃብታም ነው ። ግን ማነንም ሥራ የሚያውቅ ሁሉ እዳን አይፈራም በረሐብም አይሞት ። ረሐብ በሰራተኛ ቤት በር ትቆማለች ግን ልትገባ አትደፍርም ። ስለዚህ ሁሉም ሰው በእጅና በራሱ (በሐሳብ) መሥራት ይገባቸዋል ፥ በእውቀትና በሥራ ማናቸውም ነገር የበለጠ ዋጋ ያወጣል ፤ በርግጥ ሥራ የሰው ሕይወት ነው ቅዱስ ጳውሎስ የማይሰራ አይብላ ብሎዋል ፤ ሐዋርያውም በጁ ሥራና በሰው ሸክም ያለመሆኑ ደስ ይለው ነበር ፤ ያንድ ቀን ስንፍና ከስምንት ቀን ሥራ ያደክማል ።

እኔም ይህን ቃል መጻፍ ያሳሰበኝ ለብርሃንና ሰላም አን ባቢዎች የእውቀት ምክር ኖሮኝ አይደለም ነገር ግን ሥራ ያከብራል ስንፍና ያዋርዳል እላይ እንደተባለው ሥራን ወደን አገራችንን እንድናገለግላት ነው ።

አበበ በላቸው ።

ስለ ሃገር አኳኋን

ብርሃንና ሰላም ገልጾ ስለ ነገረን ደስ የሚል ቃሉን ያስ ረዳናል እኛም የተቻለንን እንረዳዋለን። ብርሃን ማለት እንደ ጥር ጊያ ጐዳና የተከናወነ ማለት ነው ባሸዋ በኖራና በድንጋይ መሰ ረት እንደ ተሰራባቸው ። ዳግመኛም ሰላም ማለት አገዛዝና መግዛት አንዋዋርና አረማመድ ነው ከዚህም በላይ እንደ ተባ ለው ጥርጊያ ጐዳና በመሰረት ድንጋይና አሸዋ በኖራ የተሰራ የተባለ ያገር ፍቅርና አንድነት ልጆችን ለትምህርት ቤት ማግ ባት መንግሥትን መርዳት አስተዳደርን ማወቅ ነው አገዛዝና መግዛት አንዋርና አረማመድ ማለት መጀመሪያ መንግሥት የተ ሻለውን ደንብ በየአመቱ መለወጥ ለነጋዴ ለወታደር ለባላገርና ለቤተ ክህነት ቀንበር እየቀለለት ሥርዓቱንና ህጉን ማሻሻል ዳግ መኛም ህዝቡ ባላገር እንደሚገባው ምድሩን ማረስ አስራት በኩራት ሳይጐድልበት ለመንግሥት መርዳት ነጋዴም እንደ ሚገባ ቀረጡን ማስቀረጥ ቀሳውስትም ቤተ ክህነቱን እንደሚ ገባው ማገልገል ወታደርም በተሰጠው ስራ ሃገሩ መንግሥቱን ማገልገል እንደዚህ ቢሆን መንግሥትም ህጉንና አስተዳደሩን በያመቱ ያሻሽልላቸዋል መንግሥትና ህዝብ ነጋዴና ገበሬ ወታ ደርና ቤተ ክህነትም ተባብረው ቢተሳሰቡ ይህ የከበረው መን ግሥታችን ምንኛ ከፍ ከፍ ባለ ነበር ። አንዳንድ እንኳ ሰዎች ምንም እንኳ ችግር ቢበዛባቸው ህዋሳታቸው ለመንግሥታቸው ጥቅምና ትርፍ የሚሆኑትን ያስባሉ ይኸውም በሕጻንነት ያገር ፍቅርን በመማራቸው ነው ይልቁንም ከየቤታችን ለገዛ እራሳ ችን ጉዳት የሆነብንን እናገራለሁ ። አንድ ሰው ተነስቶ ከባላ ገር ውስጥ ወደ ሌላ አገር ይሄዳል ስራ ሰርቶ ጥሮ ግሮ ደክሞ ብዙ ገንዘብ ያከማቻል ጥንት የነበረባቸው ዘመዶቹም ማግኘ ቱን ይሰማሉ እንጠይቀውም ይሉና ሰላሳ አርባ ሆነው ወዳለ በት አገር ይሄዳሉ ወዳለበትም ቦታ ይደርሳሉ ፈጥኖ ብቅ ብሎም ይቀበላቸዋል የተቻለውም ቢሆን ፍሪዳውን ያርድላቸዋል ደግ ሰም ይሆናል ዝቅ ያለው ግን ሙክቱን ድግሱም እንደ መጠኑ ያድራሉም ባለቤቱም ተነስቶ በማለዳ ወደ ስራው ይሄዳል እነ ሱም እቤት ድግሳቸውን ሲበሉ ሲጠጡም ይውላሉ ባለቤቱ ማታም ከስራ ይገባል እንእያ እንደምን ውላችኋል ይላል ወደ ቤትም ደጃፍ ሲደርስ እግዚአብሔር ይመስገን ልጄ ምን ጠፍቶ ይሉታል ።

እንደዚሁም ሲሆን ወር ሁለት ወር ይሆናቸዋል አንዲት ቀን እንኳን ስራ አይሠሩለትም ሰርኩንም ድግስ ነው በዚሁም

ምክንያት ገንዘቡም ያልቃል ሚስቱም ሲቸግራት የወትሮ ልማዳችው ድግሱ ይቀርባቸዋል ባለቤቱም እንደ ተለመደው እሥራውሎ ማታ ይገባል አሁንም እነእያ እንዴት ውላችኋል ይላቸዋልን እነሱም ምን ደህና እንውላለን ሚስትህ ዘመዶቿን እንጂ እኛን ጠልታን ይሉታል ። ምሳቸውን አልበሉም ወይ ብሎ ይጠይቃታል። ገንዘብ ስላለቀብኝ የሚበላውም ስለጠፋ ምሳቸውንም አልበሉ ትለዋለች ዘመዶቼ ቢበሉት ይልና ይደበድባታል ወደ ዳኛም ይሄዳሉ በዚሁም ነገር ይፋቱማል ዘመዶቹም ሰርቶ እሚአበላቸው ያጣሉ አይ ችጋር ሊፈጀን ነው ወደ ሃገራችን እንግባ ብለው ለመሄድም ይነሳሉ ገንዘብ የበሬ መግዣ የማረሻ ያባትህንም መሬት የምንገብረው አጥተን በግብር ተይዟል ይሉታል እሱ ግን ገንዘቡን በነሱ ድግስ ጨርሷልና ወደብድርም ይሄዳል ብድርም ያጣል ገንዘብ አጣሁ ይላቸዋል እነሱም መቼ ገንዘብ አጥቶ ነው ሳጥኑ እንጅ እንዳይጉድል ነው ይሉትና የጥንት ፍቅራቸውን ትተው ቂም የሚባል ሐሳባቸውን በሆዳቸው ይዘው እሱን ሲያጡ ወደሃገራቸው ይገባሉ እሱ ግን ከገንዘቡም ሳይሆን ከሚስቱም ሳይሆን ከዘመዶቹም ሳይሆን እንዲያው በከንቱ እድህነቱ ይመለሳል ለሃገራችን ግን ፩ኛው ጉዳት የሚሆን የዘመድ ተሰሪ ነው ከሚሰሩት የማይሰሩት በላተኞች መብለጣችውም ስለዚህ ነው ይልቁንም እኛ አንድ ባለጸጋ በሃገራችን ቢኖር የሱን ዓይን ዓይን ብናየው እሱን ከማደህየት በተቀር ምን ምን ጥቅም ይገኝበታል ። ጥረን ግረን ሥራ ሠርተን እንደሱ ብንሆን ይሻል ነበር እንጂ ።

የሱን እጅ ብናየው አይሆን ለልጅ ልጅ ።
እኛው ጥረን ግረን ብናተርፍ ነው እንጅ ።
የሰው ገንዘብ መዝረፍ ያሰኛል ቀላጅ ።
በፊትህ ወዝ ብላ እንድ ትደረጅ ።
ጥንቱንም ለአዳም ተነግሯል አዋጅ ።
እርጅና ሳይመጣ መጣጣር ነው እንጅ ።
ከደከሙ ወዲያ አንድ የለም ወዳጅ ።
አሁን በልጅነት ይሻል ነበር እንጅ ።

ድሬ ደዋ ትምህርት ቤት ካሉት የብርሃንና ሰላም ናፋቂዎች አንዱ ።

በቀለ ዘለቀ ።

ሠረቀ ብርሃን በኢትዮጵያ ፤

ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ልጆች ማሕበር በኢትዮጵያ ውስጥ ፍጹም ብርሃን እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህነን የፍቅርና ያገልግሎት ማሕበር ተማሪ ቤታቸው የስሙ ፍሬ ሠረቀ ብርሃን በኢትዮጵያ ብለው ሰየሙት ። ሠረቀ ብርሃን በኢትዮጵያ ማለትም ተፈሪ ብርሃን በኢትዮጵያ ወጣ ማለት ነው ። ስለዚህ ኢትዮጵያ እንደዚህ ያለ ምሳሌ አድርጋ በሶስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፭ ፴፮ ፎቶግራፍ የተነሣችበት ምክንያት እንዴት እንደሆነ እንደተሰጠኝ የሀል ንባቡን ከነ ትርጓሜው አገልጾላችሁ ዘንድ ሕሊናዬን አሳሰበኛልና በሚከተለው መስመር ተመልከቱ ፤

፩ኛ ፣ ኢትዮጵያ አገራችን ንዑ ደቂቅየ ወስምዑኒ ፈሪሃ እግዚአብሔር እምህርክሙ ብላ ልጆቿን በመጥራቷ ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምራ ፈሪሃ እግዚአብሔርን አብልጣ እንደምትወድ ያስረዳል ።

፪ኛ የኢትዮጵያ ልጆችም የናታቸውን ድምጽ በሰሙ ጊዜ ተሎ ብለው ከናታቸው ብብት በመቅረባቸው ከሁሉ በፊት አስቀድመው ፈሪሃ እግዚአብሔርን መማር እንደሚመርጡ ያስረዳል ማለት የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ተብሏልና ።

፫ኛ ፣ የብርሃን ተማሪዎች በተሰበሰቡ ጊዜ ሠረቀ ብርሃን ለራትዓን በውስተ ጽልመት መሐሪ ወመስተሣህል እግዚአብሔር በጨለማ ውስጥ ለሚኖሩ ቅኖች ሰዎች ተፈሪ ብርሃን ወጣላቸው ። ምነው እግዚአብሔር መሐሪ ይቅር ባይ ነውና ብርሃን ወጣላቸው ብላ ባስተማረቻቸው ጊዜ የደስታ ጭብጨባቸውን እንዳቀረቡላት ያሳያል ።

፬ኛ ፡ ኢትዮጵያ አገራችን ዘውዲቱን በፀሐይ ምሳሌ አድርጋ በራሷ ላይ በማድረጓ ኢትዮጵያ በቀድሞ ዘመን ዝምራዋን የቻለች መንግሥት ናት ተብሎ ይተረጐማል ።

፭ኛ ፡ በኢትዮጵያ አንገት የወርቅ ማተብ መስሎ የሚታዬውን የስልጣኔ አበባ ሐረግ ወይን ዘምኒልክ እስከለ ማርያም ዘዘውዲቱ ተብሎ በሁለት ይፈታል ።

፮ኛ ፡ ኢትዮጵያ ከመከከላቸው ግርማዊት ንግሥታችን በስተ ቀኝ የኢትዮጵያ ቀኝ እጅዋን ይዘው ልዑል አልጋ ወራሻችን በስተ ግራ የኢትዮጵያ ግራ እጅዋን ይዘው ተስተካክለው ተደጋግፈው ልክ በመቆማቸው ሶስትነት በዓከላት በመንግሥት አንድነት ተዋህዶተ ቃል ኃይል ይሰጣል ተብሎ ዘይቤ ሁኖ ይተረጎማል ።

፯ኛ ፡ ኢትዮጵያ አገራችን በግርማዊት ንግሥታችንና በልዑል አልጋ ወራሻችን አጋዥነት ከነደዚህ ያለ መልክም ምሳሌ ደረሰች ስል በብርሃን ተቀበላችሁ በሰላም ለምታነቡ ሰዎች አሳስባችኋለሁ ። አሁን ግን ሠረቀ ብርሃን በኢትዮጵያ የምትባል ተማሪ ቤት የአገልግሎቷን ሥራ በማስፋቷ አንደኛ መሕበር ሁናለች በሠረቀ ብርሃን ተማሪ ቤት የሚማሩ የመንግሥት ሠራተኞችና ተማሪዎችም አሁን ለጊዜው አምስ ስድስት ናቸው አንድ ስንኳ አኔ ራሴ ነኝ ስለዚህ በዚያ የሚማሩ ተማሪዎች አስለማጠናቸውና አቀለማጠፋቸው ምን ጊዜ እንደሚያጠኑ አይታወቅም ሳስተዋይ ልብ ያስደንቃል ለወደፊቱም ይህ ተማሪ ቤት በግርማዊት ንግሥታችና በልዑል አልጋ ወራሻችን በመኳንንቶቻችንና በወጣቶቻችን ረዳትነት ክፍ ከፍ አያለች እንድትሄድ ጥርጥር የለበትም የኢትዮጵያ ሊቃውንትና ወይዛዝሮችም ለዚሁ ለተመሠረተችው አዲስ ተማሪ ቤት በሙሉ ፈቃዳችሁ እንድትረዷት ማንም አይስተውም ። ለንግዴሁ ኢትዮጵያ አገራችን ማሕበር እየሆንን ገንዘብ እየሰበሰብን ተማሪ ቤት እያቆምን መምሕራንም የተመረጡ የኢትዮጵያ ሰዎች እያደረግን በያውራጃው ሁሉ ያገራችንን ልጆች በገዛጃችን ካላስተማርናቸው ከውጭ አገር ሰዎች ብቻ ተምረው አይጠቀሙምና ለዚህ ሀሳብ አትስነፉ ጠንክሩም ። አሁን ግን ያቅሜን ያህል ለሠረቀ ብርሃን ተማሪ ቤት እርዳታዬን ፫ብር ሰጥቻለሁና እነሱ እንዳትሉኝ ይቅርታችሁን እለምናለሁ ። ተማኑሮምሃ ዘዓድዋ ።

ወደ ኢትዮጵያ ክርስቲያኖች

የኢትዮጵያ ነጻነት በሃይማኖት ልትለማ ነው ። ወይም በሃይማኖት ልትጠፋ ነው ። ከቡራን አባቶቼ ሆይ ብዙ ጊዜ ልጽፍላችሁ እየጀመርኩ ለመፈጸሚያ ጊዜ እያነሰኝ ሃሳቤ ሳይደርሳችሁ ብዙ ጊዜ ቀርቷል አሁን ልጽፍላችሁ ያነሳሳኝ አንድ ሰውዬ ያሳተመውን ቃል ስላነበብኩ ባጭር ቃል ዋና ነገር ላስታውሳችሁ ቆረጥኩ ይህ ሰውዬ የጻፈው ቃል እንደሚከተለው ነው ።

የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች በቤተ ክርርስቲያናቸው ክርስቲያን ያልሆነ ሰው አያስገቡም አረመኔዎች ሂደው ወደ ቤተ ክርስቲያናችሁ ገብተን ያምላካችሁን ቃል እንስማ ብለው ቢለምኑዋቸው አንተ ወደቤተ ክርስቲያን ለመግባትና የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት አይገባህም አንተ ኢትዮጵያዊ አይደለህም አናስገባህም ብለው ከልክለው ከቤተ ምድራፍ ይመልሱታል ። ቸር ቢሆኑ ግን ከደጃፍ ቁሞ መሬት ስሞ ቤተ ክርስቲያኑን ተሳልሞ እንዲሄድ ያመለክቱታል ይላል ። ይህ ነገር ለኔ እውነት አይመስለኝም ። በሃገሬ ሁኔ ይህ ልማድ መኖሩን ሰምቼ አላውቅም ጋላ ሆነ አማራ ወላሞ ሆነ ሻንቅላ እስላም ሆነ አይሁድ ሎሌ ሆነ ጌታ የእግዚአብሔር ቃል ለሰው ልጆች ሁሉ እኩል ይሰበካል እንጂ እንዴት እንደትንሽ ስጋዊ ነገር ወገን ይለይበታል ፤ ይኸነንም አድርገን ቢሆን ክርስቲያኖች ነን ብለን ራሳችንን ለመቁጠር መቸ ይገባን ነበር የጠፋትን ሊፈልግ አልነበረም የመጣውን ደግሞ ቀጥሎ እንዲህ ይላል ፤ በየጳር አገሩም በኢትዮጵያ አውራጃዎች ሁሉ ሂደው ለመኖርና የእግዚአብሔርን ቃል ለመስበክ የእግዚአብሔርንም ፍቅር ለሕዝቡ ለማስተማር ሞክረውትም አያውቁ ወደፊትም ሊሞክሩት እያሰቡ ያደርጉታል ተብሎም ለመጠርጠር ተስፋ የለም ይላል ።

ከዚህ አስቀድሞ የኢትዮጵያ መምሕራን እየዞሩ ማስተማራቸው እርግጥ ነው ። ነገር ግን በኢትዮጵያ ዙሪያ ያሉት አረመኒዎች የክርስቲያን ሃይማኖታችንን ለመቃወም አዘውትረው ስለተጣጣሩ ብዙ ዘመን የሚያስፈልግ ስለሆነ ነው እንጂ እውነት ስንፍና እና ምቀኝነት አሸንፎን እንዳልነበረ የዓለም ታሪክ ይመሰክርልናል ። ግን ያለፈውስ አለፈ እረ ለወደፊት እንደዚኸው ዝም ብለን ይህ ሰውዬ እንደተናገረው ልንኖር ነው ምነው ከቡራን አባቶቼ እንዴት የክርስቶስን ፍቅር ከአረመኒዎቹ ተጉድተው ከሚኖሩት ወንድሞቻችን ሰውራችሁት ትኖሩ ? ምነው ጌታ ወርዶ ተዋርዶ የድንግሊቱን ሥጋ ለብሶ ሰው ሁኖ በመካከላችን የኖረው ፍቅርን ሊያስተምረን አልነበረምን ጋላ ሱማሌ እስላም አረመኔ በክርስቶስ ወንድማችን ሊሆን አይገባውምን ሰው ለወንድሙ መልካም መስራት መፍቀዱ የታወቀ ነው ወንድምነቱን እየሄዳችሁ ብታስተምሩት ለኢትዮጵያ ረዳት ለመሆን መጣሩ ይቀራልን ። ባለፈው ወራት ብዙ ሱማሌዎች ከኤውሮፓ መጥተዋል ማለት ስሰማ ጊዜ መቼም የሰው አገር ያለ ሰው ያገሩን ሰው ለማየት ይናፍቃልና እስቲ ሂጄ ልያቸው ብዬ ወደሰፈሩበት ቦታ ሂጄ አየኋቸውና ከወዴት ነው የመጣችሁት ብዬ እየጠየቅሁ ብዙ ተነጋግረን ብዙዎቹም አዲስ አበባና ሀረርጌ እየተመላለሱ በንግድና በገባርነት በኢትዮጵያ መኖራቸውን ነገሩኝ ብዙዎቹም ጅጅን በሚባለው ከተማ መኖራቸውን አጫወቱኝ ።

ብዙ ነገር እነሱም እኔን ጠየቁኝ እነሱ ያሉበት ቦታ በጣም የተናቀና ቁሸሽ የሆነ ቦታ ነበርና እዚያ ድረስ ሂጄ ሳያቸው በማሰቤም ተደነቁ ያረፉበትም ቤት አንድ እውነተኛ የእግዚአብሔር ወዳጅ የሆነ ሰው ቤት ነበር ። ይኸውም ሰውዬ እየሰራ በሚያገኘው ገንዘብ እያጠራቀመ መግቢያ የቸገራቸውን ድሆችና እንግዶች እየሰበሰበ ሲያበላና ሲያጠጣ ማረፊያ እየሰጠ ሲያስተናብር የሚኖር ሰውዬ ነበር ። ይኸንኑም ሁሉ የሚያደርግላቸው ያለዋጋ ነው ። ከዚኸውም ከሰውዬ ስንነጋገር አኗኗናቸውንና ችግራቸውን እያጫወተኝ በጣም አሳዘነኝ ።ከዚህ በኋላ ወደ ሱማሌዎች ስመለስ እንደዚህ ብዬ ጠየቅኋቸው ፤

አሁን ዓለም አላፊ መሆንዋን እያወቃችሁ ምን ቸገረ ብላችሁ በለው አገር እንዲህ በመጉላላት ትኖራላችሁ ምነው አገራችሁ ገብታችሁ እያረሳችሁና እየነገዳችሁ ብትኖሩ አይሻላችሁምና ብዬ ጠየቅኋቸው ። መቼም የሱማሌ ስልጡን ተከራክሬ በችኮላ ለመናገር ዝግጁ መሆኑን ታውቃላችሁና ሁሉም ምላሽ ለመስጠት ተሻሙ ። ግን አንደኛው እጅግ ስለባሰበትና ሰውነቱ ስለተነካ ከተቀመጠበት ብድግ አለና ጓደኞቹን ፈቃድ ለመነ ወንድሞቼ እባካችሁ አንድ ቃል ቀድሚያችሁ ልናገርና ይህ ጉበዝ ምላሽ ከሰጠኝ በኋላ ተራችሁን እለቃለሁ አለ ።ጓደኞቹም ድምጣቸውን አጠፉለት ከዚያ በኋላ እንዲህ ብሎ ጠየቀኝ ።

የኔ አባትና እናት የኖሩት በኢትዮጵያ ግዛት በጅጅጋ በታች ነበር ብዙ ላም አርቢዎች ነበሩ እኔ ትንሽ ሳለሁ ሃበሾች መጡና አባቴን ገድለው እናቴን ማርከው ላሞቻችንን ዘርፈው ሄዱ ያነን ጊዜ ሸሽቼ አምልጬ ወደ ባሕር መርከበኝነት መጣሁ ። አሁን ጊዜ አልመች እያለ የሰው አገር ሰልችቶኛል ግን የሰው አገር ቢሰለቸኝ ወደማንኛው አገሬ ተመልሼ ልግባ እስቲ ለዚህ ምላሽ ስጠኝ ሱማሊዎችን ማን ከኢትዮጵያ ይቆጥረናል እረተወኝ ኢትዮጵያ ሃገራችን አይደለም እኛ ሃገር የለንም እኛ እግዚአብሔር የጠላን ሕዝቦች ነን ብሎ ዕንባ አሸነፈውና ነገሩን ሳይጨርስ ተቀመጠ በዚያን ጊዜ በጓደኞቹም ዓይን እንባ መልቶባቸው ባየሁ ጊዜ ሰውነቴ በጣም አዘነ ።ከዚህ በኋላ ከመቀመጫዬ ተነስቼ ወዳጆቼ የምናገረውን በትዕግሥት ሥሙኝና ወደ ሥራዬ ልሂድ ብዬ የሚከተለውን ቃል ተናገርኩ ።

መልአኩ በያን

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

በስንፍና ስለሚያልቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ

ይድረስ ለአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት

ከአዲስ አበባ ከ፲ እስከ ፳ ጊዜ በሚበልጡ ከተሞች ውስጥ (በመኪናዎች መንቀሳቀስ ሥራዎችና ከብዙ ዓመቶች በኋላ ሳት ብሎ እየቆየ በነፋስ የሚመጣ በሽታ በተቀር) በየቀኑ በአዲስ አበባ የሚያልቀውን ሕዝብ ያህል በበሽታ ምክንያት አይሞትም ። ብርሃንና ሰላም በቅን እንዳመለከተው በአዲስ

አበባ ብዙ ሐኪሞች አሉና ፡ ለሕዝባችን በየቀኑ ስለሚጨርሰው ያለ በሽታ እያሳተሙ ይገልጡት ይሆናል ። እያልኩ ተጠብቄ ባጣ በባእድ አገር ይቅርና ፤ በሀገራቸውም ሥራ እንዳያጡ (አንዳንድ ደጎች ካልሆኑ የሚበልጡትስ) ቀስ ቀስ እያሉ ነው እንጂ ዘጥንቃቄ አያከሙም የሚሉት ወሬ እውነት እንዳይሆን አጠራጠረኝ ። እለ ክርሰሙ ያመልኩ ተስፋ ከቆረጥኩ ወዲያ ሰው የያዘውን ከወረወረ ፈሪ አይባልም ። እንደሚሉት ምሳሌ ይህችን አጭር ማስታወሻ ልጽፍ አሰብኩ ።

ለከተማ ነዋሪ ሰው አባቱና እናቱ ማዘጋጃ ቤት ነውና ወላጅ ልጆቹን እንዲያሳድግና እንዲያስብ ማዘጋጃ ቤትም እንዲሁ ማድረግ በከተማ ተቀማጮች ሕዝቦችም እንደ ልጅ ላባቱ በፍቅርና በፈቃዳቸው ሊታዘዙትና በሚቻላቸው ነገር ሁሉ ሊያግዙት ይገባቸዋል ።

በውጪ አገር እንደተመለከትኩት የማዘጋጃ ቤት ትልልቆች ዋነኞች ሥራዎች ፳ ናቸው ፩ኛ ። የሚጠጣ ጥሩ ወኃ ወደ ከተማ ማግባት ፪ኛ ሊበላ በከተማ የሚታረደውን ከብት በሽታ እንዳይኖረው መፈተሽ ፫ኛ ፤ መንገድ መሥራትና ከተማን ማጥዳት ፬ኛ፤የሌሊትን ማብሪ ሉቹ ኢሌክትሪክ መትከል ፭ኛ ሕዝቡን በፍጥነት መመላለሻ ትራም(እንደ ባቡር ዓይነት በከተማ ውስጥ የሚመላለስ) መዘርጋት ፮ኛ ለከተማ ድሆች በሽተኞች ሆፒታል መሥራት ፯ኛ ኤሌሜንታሪ የተባለ ሕዝብ ሁሉ እስከ ፫ ዓመት ንባብና ጽሕፈት በግድ የሚማርበት ማቆም ፡ ፰ኛ ጉዋርዲያ ቺቪካ የሚባሉ ዘበኞች ከተማ ጠባቂዎች ማሳደር ።

እንደዚህ ያሉ ትልልቆች ሥራዎች ሲያቆም ገንዘብ የማይበቃው እንደሆነ በከተማ በሚኖር ሰው እዳ ሊጥል ይችላል። ለሀገሩ ጥቅም ስለሆነ መንግሥቱም አለ ወለድ ወይም ወለዱ በጣም አሳንሶ ያበድረዋል ። ሥራው ካለቀ ወዲያ ግን ሶስቱ ትልልቆች (ወኃ ሉቺ ኤሌክትሪክ ትራም) እየራሳቸው ችለው ያድራሉ እንጂ ከማዘጋጃ ቤት እርዳታ አንድ ተሙንም አይፈልጉም።ማዘጋጃ ቤትም ትርፍ አንድ ቤሳ አይወስድም ። ከተማው እየሰፋ ሲሄድ ሥራውን ለመጨመር ወይም አንድ መኪናን የተበላሸ እንደሆነ ሲያበጅ ሕዝቡ በሚጠጣው ወኃ በሚያበራው ኤሌክትሪክና በሚቀመጠው ትራም ፤ ክራዩን በዛ አድርገ ይከፍላል ። የሚያስፈልግ አዲስ ወጪ የሌለበት ጊዜ ግን በጣም ትንሽ ለሠራተኞችና ለመኪናዎች መንቀሳቀሻ የሚያስፈልጋቸውን(የሚበቃቸው) ብቻ ለክቶ ይከፍላል ።የቀሩ ፭ ሥራዎች ደግሞ ክሕዝቡ በከተማ የሚሐፋ የሆነ የማዘጋጃ ቤት (ቀረጥ) ገቢ ያስተዳድረዋል ።

ሕዝቡ የሚጠጣው ወኃ ከከተማው ብዙ ኪሎ ሜትር የራቀ ስፍራ ሂዶ ፲ ሜትር የሚሆን ጥልቀት ቆፍረው ፲ ሜትር ሳይደርስ የሚገኝ ወሀ ከመሬት በላይ ያለ እድፍ የሚስብ ስለሆነ ብዙ ሚክሮቦች (ትንንሽ ትሎች) በሽታ የሚያመጡ ወደ ምንጩ እንዳይደባለቅ በጉድጓድ ልክ ትልልቆች የብረት ቧምቧ አግብተው አጣብቀውታል ። መቶም ከ፲ ሜትር ጥልቀት በታች በሁሉ መሬት አሸዋ ነው ያለ ይህነን በአሸዋ ተመርቶ የሚሄድ ወሀ በጣም የጠራ ለሕይወት የተሰጠ ነው ። ያንን የተቆፈረ ጉድጓድ ማስተንፈሻ ሲያገኝ ወሀው ፈንድቶ እስከ ፻ ሜትር የሚሆን ወደ ላይ ይደርሳል ። ከዚያ ወሀ የሚስብ ቧምቧ አግብተው ያወጡትና ሰው ሊያተላልፍ የሚችሉ ትልልቆች ቧምቧች በመሬት ውስጥ ለውስጥ እንደተቀበሩ እስከ ከተማው ከደረሱ በትንሾች ቧምቧዎች በየቤቱ ያከፍሉታል ።

መታጠቢያ እየሆነ የሚጠፋ ወሀም ከሰገራቸው መገናኛ ቧምቧ አድርገውበታልና ፡ በመሬት ተቀብሮ ውስጥ ለውስጥ ይዞት የከተማውን እጣቢ እድፍንም ጨማምሮ ጠራርጎ ወደ ትልቅ ፈሳሽ ወንዝ ያገባዋል ። የከተማ ነዋሪ ሰውም እየቤቱ ውስጥ ወይም በየዙሪያ ቤቱ ለከተማ ጠራጊዎች ሰዎች በተደነባላቸው ስፍራ ሳያስረክብ ጉድፍ (እድፍ) የተገኘበት እንደሆነ መቀጮ ይከፍላል ። እንዲህ ብሎ በጣም ከጠዳ በሽታ ከከተማው ይጠፋል ። ሕዝቡም ከሚሞተው የሚወለደው ሲበልጥ እየበዛ ይሄዳል ።

በሽታን የሚያመጣውና የሚያጠፋው በዝርዝር ለይቶ ለማስታወቅ ብዙ ትልልቆች መጻሕፍት ያስፈልጋል ። ስለሆነም የማንም (የትኛውም) በሽታ መሰረቶች ሚክሮቦች (በግሪክ ቋንቋ ትንንሽ ፍጥረቶች) የሚባሉ ትንንሾች ትሎች እልቆ የሌላቸው በወሀ በደመና በአየር ትእልፊት አእላፋት የሚገኙ እንደሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብም አይስተውም ይመስለኛል ። በሚክሮስኮፒዮ የሚባል መስተዋት በአንድ ነጥብ ወሀ እስከ ፵፪ ሚሊዮን ይቆጠራሉ ።

ብልሆች ሕዝቦች ግን ፤ ከነዚህ ሚሊዮኖች ጠላቶች መዋጋት አውቀውባቸዋል ፤ በነፋስ እንዳይመጡ ከተማውን አጥድተው ፤ በደም እንዳይጋቡ በሽተኛውን ከብት አስወግደው ፤ (የጤናማውን ቢሆንም ሲበሉት በእሳት ቀቅለው) በዝምብ ፤ በቁንጫ በትኋን እንዳይተላለፉም ፤ ከተማው ሲጠዳ ድምጥማጣቸውን አጥፍተው ፤ በውኃ እንደይሳቡም ፤ በብረት ዘግተው ድል መተዋቸዋል ።

እኛ ኢትዮጵያውያን ግን፡እንደቸልተኝነታችን መጠን ከተሞቻችን እንደ ፈረንጅ አገር ትልልቆች ፤ መሬታችን ሁሉም እንደነሱ ጭቅጭቅ ብሎ ሰው የሰፈረበት ቢሆን ፤ ባንደዬ ባለቅን ነበር በአዲስ አበባ በየመረባው ውስጥ ሰገራና የሚጠጣ ጉድጓድ ውኃ አይቶ ፡ ባንደዬ አለማለቃችንን ከቶ የውቢቱ አገራችንን ጤናማ አየር ምንኛ መታደላችን ነው ። የሆን ሁኖ እስከ ጊዜው ድረስ ወኃውን አፍልቶ እንደገና አብርዶ መጠጣት ፤ ይልቁን ለአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝባችን በጣም የሚያስፈልገው ነው ።

ባለችኝ አቅሜ ለሕዝቤ ለጤናና የድህንነት ምኞት እርዳታ ስል ፡ የአገሬን መዘጋጃ ቤት ከአሁን በፊት አውጥቶ በቆመው ደምብ በላይ አጋዥ ሊሆነው ፤ የፈረንጆች መዘጋጀ ቤት ደምብም የሚያስፈልገው መሆንን ባውቅ ፤ ለጊዜው የሚያስፈልግን በጭሩ አዋጥቼ ገልብጬ ልልክለት በምሉ ፍቃዴ የተዘጋጀሁ ነኝ ።

ሚካኤል ተሰማ

OMEGA



በአውሮጳ አገር ሚከሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት ሚየባል ባለፈረስ ስዓት ከሴሙ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ፲ መሐ ።
የሲዳሞ ቡና	፩	፰ ብር ፫ ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ፫ ሩብ ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር ።
የ ዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፮ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር ፫ሩብ
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲፩ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲ ፫ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፵፫ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፮ ብር
፡፡ ባለ ድመት ፡፡		፻፴፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፲፮ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል ፡፡		፻፳፬ ብር
ባለአ ንበሳ	፡፡	፻፵፫ ብር ።
ሱካር	፩ ጆኒያ	፳፰ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፰ ፍራንክ ተ፶ ሳንቲም
አንድ ብር	፲፩ ሊሬ እስከ ፺፫ ሳቲንም
በአንድ ጊኒ	፲፩ ብር እስከ ፴፫ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፮ ብር

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፣ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ክች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት አመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምሬው ሰላሳ አራት ነው ።

COGNAC S.E.A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክስል የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

በማስታወቂያ ያወጣሁት ሎተሪ ወረቀቱ በተባለው ቀን ሳይሸጥ ስለቀረ ቀኑ በጥቅምት ፳ ቀን ፲፱፻፳ ከኩለቀን በኋላ በዘጠኝ ሰዓት መለወጡን አስታውቃለሁ ። ቦታውም በካዚኖ አዲስ አበባ ስቴሊዮ ቴዎፊሉ ቤት ነው ። ሎተሪ የገዙ ሁሉም ልዩ ልዩ ጨዋታ ያያሉ ።

ሃብተሥላሴ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሄስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ቤርሊዮ አቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዮ አቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሜኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እንደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አላጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፰
3 me ANNÉE №. 38

ሐሙስ መስከረም ፲፩ ቀን፡ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 22 SEPTEM BRE 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ቢገዛ ስፈስገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፪፻፺፫ ገጽ ተከታይ ።

ወደ ኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ።

አሁን ወንድማችሁ አብደል አሊ የተናገረው ቃል የሁላችሁንም ልብ እንደነካው ታውቆኛል በውኑ የኔም ልብ እንደናንተው ተነክቶአል ግን እነሆ አዲስ ምስጢር ልንገራችሁ የዛሬ ይቱ ኢትዮጵያችን እንደወትሮዋ አትምሰላችሁ። እንደወትሮ ጨካኝነታችን ቀርቷል እንደወትሮ እርስ በራሳችን ለመጋደል መፈለጋችንም ቀርቷል ። የኢትዮጵያ ሰዎች ሃሳብና ምኞት በሰላምና በፍቅር ተገዳድፈው ነጻነታቸውን ከጥፋት ለማዳን መጣጣር ሆኖአል መንግሥታችንም ለሕዝቡ አጥብቆ ማሰብ ጀምሯል ይህ ሱማሌ ነው ይህ ጋላ ነው ይህ ሻንቅላ ነው ይህ ወላሞ ነው ማለት ቀርቷል በኢትዮጵያ መንግሥት ለሚኖር ድሃ የኢትዮጵያ ነጻነት ነጻነቱ ነች የኢትዮጵያ ክብር ክብረቱ ነች እያለ ማስተማር ጀምሮአል ዛሬ ሃይማኖታችሁንና ወገናችሁን የሚጠይቃችሁ የለም ኢትዮጵያውያን ነን ካላችሁ ለኢትዮጵያውያኖች የሚሰጠው እርዳታ ሁሉ ይሰጣችኋል ወዳጆቼ ሆይ የወትሮውን ጨካኝነትና አውሬውን ባህሪያችንን እያሰባችሁ ሃገራችሁን ጠልታችሁ በስደት ለመኖር አትቃለሉ እስቲ ተመልከቱት እዚህ ጥቁር በማይከብርበት አገር አገር እንደሌለው ለምን በስደት ትኖራላችሁ አባቶቻችሁ አገራችሁ ግቡ ዛሬ አገራችሁ ብትገቡ ስራ ለምዳችኋል ንግድ ለምዳችኋል ስለዚህ በጥቂት ጊዜ ጌቶች ለመሆን ትበቁና በደስታ ትኖራላችሁ ። አባቶቻችሁ የወትሮውን ባህሪያችንን እርሱትና አዲሱን ባህሪያችንን ሞክሩት አሁን ወንድሞቼ የምላችሁ ከንግግሬ ነው እንጂ ከንጉቴ አይምሰላችሁ እንደዚሁም ኢትዮጵያ በመላ ትቀበላችኋለች ብየ ፈጻምኩና ለመሄድ ልሰናበታቸው ስጀምር በደስታ ተሳከሩና እውነት እንደናታቸው ልጅ አዩኝ የሃገሬን ሰው መናፈቁንም ስለተረዱት በጣም አዘኑ ይልቁንም የተናገርኩት ነገር አዲስ ስለሆነባቸው እየተገረሙ የሚበቃ ገንዘብ ስናገኝ ወደሃገራችን እንገባለን ግን ያንተን ስምና አድራሻ ስጠን ብለው ያዙኝ የኔ ስምና አድራሻ ምንም አይረባችሁም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ወዳጃችሁ ይሆናል ግን እግር ጥሎአችሁ አዲስ አበባ የመጣችሁ እንደሆን አልዑል ተፈሪ መኰንን ግቢ ሂዳችሁ ያልጋ ወራሽ አሽከር እገሌ የአገሌን ልጅ እንፈልጋለን ብትሉ የሚያሳያችሁ ታጡ አይመስለኝም ብዬ ተሰናብቻቸው ወደ ስራዬ ሄድኩ ።

ክቡራን አባቶቼ ሆይ አሁን ይኸንን ሁሉ ነገር መጻፌ ይህ የሰው አገር ሰው ውሸት የተናገረ መስሎአችሁ እንዳትከራከሩት ብዬ ነው እንጂ ሌላ ፍሬ አለበት ብዬ አይደለም ሕዝባችንን ወንድሞቻችንን ክደናቸው መኖራችን አይጠረጠርም ።

እንግዴህ ይኸነን ሰውዬ እውነተኛ አድርጋችሁት ልትቀሩ ይሆንን በየዳር አገሮቻቸው ሂደው የእግዚአብሔርን ፍቅር ያስተምራሉ ተብሎ ተስፋ የለም ብሎ ተናግሯል።ይህ ነገር እውነቱሆኖ ይቅርን ወይስ መምሕራኖቻችን ዛሬ እየተነሳችሁ ወደ የዳር አገሩ እየሄዳችሁ ባረመኔዎች ወንድሞቻችን መካከል እየኖራችሁ የእግዚአብሔርን ፍቅር እያስተማራችሁ ለኢትዮጵያ ረዳቶች ታደርጓቸው ይሆን ?

ይህ ሰውዬ ይኸነን ሁሉ ከጻፈ በኋላ ነገሩን እንዲህ ይፈጽማል እኛ የሰለጠን ነው ክርስቲያኖች በነኝህ በኢትዮጵያ የዳር አገሮች እየገባን ወንጌልን ካልሰበክን እነኝህ አረመኔዎች ክፉ ስራቸውን ለመተው ነፍስ አውቀው አይችሉም ኢትዮጵያን የሚረዳ የእግዚአብሔርን ፍቅር ማወቅ ነው ሕዝቦችዋ በፍቅር በተሳሰሩ ጊዜ ነፃነቷ ከመከራ ትድናለች ይላል ። ግን እውነተኛው ኢትዮጵያውያን ሆይ ይህ የዋህ የሰው አገር ሰው የሚነገረውን እንመርምር ። ይህ የሰው አገር ሰው በኢትዮጵያ አረመ

ኒዎች መከከል ገብቶ በበረሃ ለመስበክ ሲመኝ እነኝህ አእምሮ የሌላቸው አረመኒዎች የገደሉት እንደሆን ለኢትዮጵያ መንግ ሥት ትላቅ ጉዳት ይሆንበታል ። ይህ አዲስ ነገር አይደለም ያለፈውን የዓለም ታሪክ ስንመለከት ወደፊት የሚወጣውን በቀጥታ ለማየት እንችላለን ። እነሆ በጣም እርቀን ሳንሄድ የጀርመን መንግሥት አንድ ጊዜ ያደረገውን እንመልከት ።

አንድ ጊዜ ሁለት ጀርመኖች እንደዚሁ እንዳሁኑ ሰውዬ ቻይና የሚባለውን አገር ጉበኙና የዚያ አገር ሕዝብ አረመኔ መሆኑን በተረዱ ጊዜ በዚህ ሕዝብ መከከል ገብተው ወንጌልን ለመስበክ ፈቀዱ ። ገብተው ጥቂት ዘመን እንዳስተማሩ አእምሮ ያነሳቸው ባላገሮች አገኙዋቸውና ሁለቱንም ሰባኪዎች ገደሏቸ ው ። የጀርመንም መንግሥት ዜናቸ ያላገባብ መገደላቸውን በሰማ ጊዜ ደማቸውን ሲፈልግ የጦር መርከብና ወታደር ልክ አገሩን ሊያስወጋ ተሰለፈ ። በዚሁም አመጣጥ ለባላገሩ ስላስፈ ራው አንድ ወረዳ አገር ለደም ዋጋ ከፍለው ጦርነቱን አስቀሩ ፤ በሁለት ሰዎች ደም ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ ወደ ባርነት ገባ ። እነዚህ ሰባኪዎች ባላገሮች ሁነው በነበር ባንባጓሮ ድንገት ነፍ ሳቸውን ቢያጡ ለመንግሥትና ለሕዝብ የሚያስቸግር ነገር አይመጣበትም ነበር ። ስለዚህ የሰው አገሮችን ሰዎች አእምሮ ወደሌላቸው ወንድሞቻችን መከከል እየሄዱ እንዲያስተምሩ ከማድረግ ይልቅ እኛው ራሳችን እየሄድን ብናስተምራቸው በነፍስም በሥጋም የሚጠቅም ነገር ይሆናል ። ስለዚህ ኢትዮ ጵያ ተነስታ ቆማ የኢትዮጵያን ካህናቶችና ክርስቲያኖች ትለም ናለችና ልመናዋን እንድትሰሙ አስታውሳለሁ ።

ብዙ ካህናቶችና ደብተራዎች ልባቸው ወንጌልን ማስተ ማር ሲፈቅድ ድሆች ነን ለማስተማር አንችልም ገንዘብ የለንም እያሉ ያመካኙ ይሆናል ። ክቡሩን ወንድሞቼ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብረቱን ትቶ ድህነትን ገንዘብ አድርጐ አልነበረም አሕዛብን ያስተማረው ? በገንዘብ የሚሠራው ዋናው ሥራ አይ ደለም መንፈሳዊ ያለ ገንዘብ ይሠራል ። እነሆ አራአያነታችሁ ብቻ ነው አሕዛብን ለማስተማር የሚችል ።

በአረመኔዎች መከከል እየሄዳችሁ ቤታችሁን እየሰራችሁ ሕፃናቶቻችሁ ከሕጻኖቻቸው ሚስቶቻችሁ ከሚስቶቻቸው እናንተ ከሰዎቹ ወዳጅ ጓደኛ ሁናችሁ ኑሩ ። አናንዋራችሁን እንደ ክ ርስቶስ አናንዋር አድርጋችሁ ኑሩ ። የክርስቶስ አናንዋር እን ዴት ነበር ? ክርስቶስ ዘወትርም ለጐረቤቶቹ ነበር እንጂ ለ ራሱ ሲያስብ ተገኝቶ አያውቅም ነበር ። ክርስቶስ እገሌ ጠላ ቴነው ብሎ ክፉ ሲያስብ ክፉ ሲናገር ተሰምቶ አይታወቅም ነበር ። ሌላው ቀርቶ በመስቀል ላይ ሰቅለው ሲያቧልቱበት ሲሰማቸው አባቴ ሆይ እነኚህ የዋኾች የሚያደርጉትን አያው ቁምና ይቅርታህን ስጣቸው ብሎ ጸለየ ። ተክርስቶስ አንደበት አንድ እንኳ ቃል የሰውን ልጅ የምታስቀይም ወጥታ ታውቃ ለች የሚል የለም ። ጐረቤቶቹ ሲያዝኑ ሃዘናቸውን ይካፈል ነበር ። ጐረቤቶቹን ደስ ሲላቸው ደስታቸውን ይካፈል ነበር ይኸውም ሰውን ደስ ለማሰኘትና ፍቅሩን ለማግለጽ ነበር ።

ክርስቶስ በዚች ዓለም ኑሮ ይህችን አናንዋር ያስተማረው እንዲህ አድርጐ በደግነትና በፍቅር ለመኖር አይቻልም እያ ልን እየዋሸን በክፋት እንዳንኖር ነበር ። ዛሬም እኛ ኢትዮጵ ያዊያኖች ይህን ትምህርቱን ፈጽመን የረሳነው እንመስላለን ። እስቲ አልፎ አልፎ የሚጻፈውን የክፋትና የጭካኔ ንግግር በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ እንኳ የሚደርሰውን እናስብ እጅግ ያስደንቃል እንዴት ሰው ሥራ ፈትቶ የሰው ሃሳብ ለመቃወ ምና በሰው ልብ ቅያሜንና ጨካኝነትን ጠላትነትን ለመፍጠር ፍሬ የማይገኝበትን ነገር የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ እገሌ ባለፈው ሳምት በጻፈው ነገር አትታለሉ እያለ ግራ ያገ ባል ። አባቶቼ ሆይ ተነሱ ፍቅርን አስተምሩ ጠላትነት ይጥፋ

በብርሃንና ሰላም ውስጥ የሚጽፉን ጥቂቶች የሚገስጽ የመሰለ ቃል መጨመሬ እንደ እነ አስታጥቄ ወልደማኔልና እንደነ ክቡር ደስታ ምትኬ በብዙ ወርቅ የማይገኝ ሃሳብ ጥቂ ቶችን የሚያስቀይም ለብዙዎች የሚረዳውን አይነት መልክም ሃሳብ የናቅሁ መስሎአችሁ በከንቱ እንዳትቀየሙብኝ የምለው እንዲገባችሁ አጥልቃችሁ እንድታስቡት እመኛለሁ ።

በሩቅ ሆኖ የሚመለከታችሁ አንድ ተማሪ መልአኩ በያን ።

የዘመን ዮሐንስ ሐዲሱን እንቁጣጣሽ ለብርሃንና ሰላም ልጆች ።

በአለፈው ጊዜ ብዙዎች የብርሃንና ሰላም ልጆች ለአገራ ቸው ነጻነት መጠበቅና ስልጣኔ ለማግኘት ብዙ ማድረጉ የሚ ገባውን ትልልቅ ነገር ሲጽፉ ነበረ አሁን ብናስበው እነዚህን ትልልቅ ነገሮች ማሰብና መስራት የትልልቆች ሰዎች ስራ ነው አሁንስ እኛ ከሕዝብ ወገን የጐደለንን ነገር ብንጽፍ መልካም ነው ። እኛ ሕዝብ ለማድረጉ የምንችለውን ሳናደርግ እኛ የማ ንችለውን ለምን አልተሰራም ብለን ብንጽፍ ሕሊናችን እዬወ ቀሰን አስቸገረን የኢትዮጵያ ህዝብ የአገራችን ነጻነት እንዲከ በርና እንዲታፈር ሰልጣኔ ወደ አገራችን እንዲገባ እኛም እን ድንጠቀም ማድረጉ የሚገባንን በክፍል ጽፌአለሁ ። መጀመ ሯው ነገር ላንዱ ወንድማችን ምቀኛ መሆን ትተን መረዳዳት ነው ። መረዳዳት ማለትም ገንዘብ መስጠት ለሚገባው ለስጋ ወንድም በገንዘብም በምክርም መርዳት ደግሞም ለእውነተኛ ወዳጅ በምክርም በስራ ጉዳይም የሚቻልን ያህል በእውነት መርዳት ለቀረውም ለኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ ለሁሉ ሰው ገን ዘብ መስጠትና ጊዜ አጥፍቶ በስራ ጉዳይ መርዳት የማይቻል ነውና መርዳቱ እንኳ ቢቀር ለስራውና ለጉዳዩ እንቅፋትና ምቀኛ አለመሆን ነው ። ይኸንንም የኋለኛውን ቃል ማድረ ግና በህዝብ ጉዳይ እንቅፋት ምቀኛ አለመሆን ወገን ለይቶ በትውልድ በጋብቻ በክርስትና ወይም በሃይማኖት ወገንነት ወይም በማህበረተኛነት አይደለም ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ነው እንጂ ። ከኔ በቀር ወይም የኔ ወገን ወይም የኔ ማህበር ካል ሆነ ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለምን ሰርቶ ይጠቀማል ለምን ያገኛል ወይም በማዕርግ ለምን ከፍ ይላል ብሎ የሚመቀኝና የህዝቡን ጉዳይ የሚቃወም የኢትዮጵያ ጉዳይ ደመኛዋ መሆ ኑን ልቡ ይታዘበው ደግሞ አርሽ ነግጅ ሰርቶ ወይም መንግ ሥት አገልግሎ በመስራትና በመበርታት ልብለጥ ልቅደም የሚል ሰው ምቀኛ አይባልም ትጉ ይባላል።ደግሞ በራሱ ሥራ ተግቶ ጠንክሮ ሰርቶ ስራውን መልካም በማድረግና በስራውና

በትጋቱ በመቅደም ፈንታ የሌለውን ሰው ስራ እንቅፋትና መሰናክል ሁኜ እኔ ልቅደም የሚል ሰው ምቀኛና ያገሩ ጠላት ነው ምቀኝነትን መተው ማለት ደግሞ ይኸንን ጆርናል አንብበን እውነት እኮ ሰው ሁሉ ምቀኝነትና በሰው መዋልን አብዝቶታል ብሎ በሌላው ፈርዶ በዚያው ደቂቃ ውስጥ በአንዱ ተንኮል ማሰብና ካንድ ምቀኛ ጋራ ለምቀኝነት ማሾክሾክ አይደለም በፊት የሌላውን ጉዳይ ለማሰናከል ታጥቆ በተነሣው ሃሳብህ በሱ መፍረድና መከልከል ነው ።

ሁለተኛው ባንተና በሌሎቹ መሐከል የሚሆነውን ጉዳይ በህሊናህ መርምረህ ማንንም ፈራጅ ሳትፈልግ በእውነትና በትክክል ኦንተው ፍረደው ለሌሎቹ የሚገባቸን በጉልበት ወይም በእውቀት ለራስህ አድልዎ በማድረግ ልውሰድ ብለህ አትመኝ በትክክል ሂድ ይኸም ባህርይ የሚገኘው ጨርሶ በሰለጠነ ሕዝብ ነው ። ወይም ደግሞ የስልጣኔን በህርይ ባልጀመረ በገራም ሕዝብ ዘንድ ነው ። ደግሞ ሁሉም የኔ ይሁን ሁሉንም ልውሰደው ሌላው ሰው ይቅርበት ብሎ መሰሰትና ገንዘብን እንደ አምላክ አድርጎ በገንዘብ ማምለክ ያገርን ነጻነት በገንዘብ መለወጥ ለገንዘብ ብሎ ስም የሚያጠፋ ነገር መስራት ከእውቀት ገንዘብን መውደድ እነዚህ የሚገኙት ደግሞ ገራምነትን የቀድሞ በህርይ ትቶ ለስልጣኔ ሳይደርስ በዚህ መሐከል ባለው ሕዝብ ዘንድ ነው ። ብዙም አገሮች ሕዝቦች በባዕድ እጅ ወድቀው ነጻነታቸውን አጥተው በባርነት የሚገዙ በዚህ መሐከል ሳሉ የወደቁ ናቸው ይኸም ውድቀት የመጣው ገንዘብን መፈለግ ከሶስት ነገር በኋላ መሆኑን ሳይረዱት ነው እነዚህም ሶስት ነገሮች ሕይወት ያገር ነጻነት መልካም ስም እነዚህ ናቸው ገንዘብ ከነዚህ በኋላ ትፈለጋለች ። አሁንም ደግሞ ማንም ኢትዮጵያዊ የሆኑ ሰዎች ከትልቅ እስከ ትንሽ ይኸን ነገር ማወቅ ያስፈልገናል እውነት ነው ገንዘብን በትጋት መፈለግ ያስፈልገናል የሆነ ሆኖ ግን እነዚህን ሶስት መሰረት አክብሮ ገንዘብን መፈለግ ከነዚህ በኋላ ነው ። እነዚህን ሶስቱን ሳንጠብቅ በገንዘብ አምልከን የገንዘብን መንገድ ብቻ ብንከተል ወየው ለነጻነታችን ያሳዝናል ። ትልልቁን ስራ ግን ለማድረጉ የሚችሉት ትልልቆች እንዲያስቡትና እንዲጽፉት ተነሱ እንድንሰማ በትልቁ እመኛለሁ ፤ ይኸን ያልኩበትንም በትንሽ ምሳሌ ላመልክት አሁን ከዚህ አንድ ጆኒያ በቆሎ በስምንት ብር ይሸመታል ያውም በሞጆና በውልንጭት ባቡር መንገድ ስለተሰራ ነው ። ከዚህ እንዲህ ሲሆን ወለጋ ከብርብር አንድ ጆኒያ በቆሎ በሶስት ተሙን ይሸመታል ለዚያውም የሚፈልገው ሰው ጠፍቶ በምድር ይፈሳል የኛው እህል ከዚህ ከስር ቀን መንገድ ባቡር በማጣት እህላችን ከምድር ሲፈስ ዘንድሮ ከህንድ አገር ባቡርና መርከብ ስላለ ብዙ ጆኒያ ስንዴ ከዓመት መንገድ መጥቶ አዲስ አበባ ተሸመተ ። ይኸን ጊዜ ወየው ባቡር በኖረ ለባላገሮቹም ብዙ ጥቅም ላዲሳበባም ብዙ ጥጋብ ይሆን ነበረ ብዬ እኔ ብመኝ ጥቅሙ ምንድር ነው ለማድረጉ አቅም የለኝምና ምኞቴ እዚህ ድረስ ነው ። ደግሞም አንዳንድ ጊዜ ለማድረጉ የሚቻለውን ትንንሽ ነገር ብንጽፍ አይከፋም እንዳንድ የማይረባና የማይጠቅም ልማድ ባገር ውስጥ የነበረውን ብንተው መልካም ነው ከነሱም አንዱ በመንገድ ሲገናኙ ለመከባበር ብሎ ከበቅሎ መውረድ ነው ፤ አንዱ ሰው በእግር ቢሄድ አንዱም በበቅሎ ቢሄድ ይኸ አንድ ነው ሁሉም ለጉዳያቸው ነው የሚሄዱ እንጂ በእግር የሚሄደውን ለመናቅ አይደለም ይኸነኑም የማይረባ ነገር መሆኑን አይተን አንዱ በእግር አንዱ በበቅሎ ስንሄድ ብንገናኝ እንዳንወርድ ከብዙ ሰዎች ጋራ ውል አድርገናል ። ይኸ ከንቱ ድካም እንዲቀርልን ይኸን ማለታችን ደግሞ ከበቅሎና ከሰው ድካም ይልቅ ሰው ለጉዳዩ ለቀጠሮ ቸኩሎ ሲሄድ ሀያ ሰው በመንገድ አግኝቶ ሀያ ጊዜ ቢወርድ ሀያ ደቂቃ ጊዜ ያልፍበታል ። ይልቁንም ወደባቡር የሚሄድ ሰው ባቡር የሄደበት እንደሆነ ከመንገዱ ይተጓጎላል ይኸም ባቡር ደግሞ ዛሬ በሳምንት ሁለት ጊዜ ወደ ጅቡቴ የሚሄድ ስለሆነ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ከኢትዮጵያ አውራጆች ሁሉ በቀን ሃምሳ ጊዜ መቶ ጊዜ ባቡር የሚመጣበት ጊዜ ይመጣል ስለዚህ ታአሁኑ ጀምረን ብናስብበት መልካም ነው ፤ አሁንም እንኳ በከተማው አቶ መቢል በዝቷል ፤ በየስፍራው ለመውረድና ለመቆም ያስቸግረ ሆኖአል ስለዚህ ነው ይኸን ማለታች ግን የመንግሥት ሹሞች ለሆኑት ለትልልቆች ባለማዕረጎች እንወርዳለን ። ደግሞም ከህዝቡም ወገን ቢሆ[illegible] ይኸ ነገር አልገባቸው ብሎ መከበር የቀረባቸው ለሚመስላቸውና የዚህን ዓይነት መከበር ለሚፈልጉ ሰዎች ሹሞችም ላልሆኑ ባልንጀሮቻችን እንወርድላቸዋለን ይኸ ድካም መቅረቱ ግን እውቀት ላለው ሰው ለሁሉም የጋራ ነው ።

ፊ ደሬሳ

ስለ ከተማ መንገድ ።

ክቡር ከንቲባ ነሲቡ የከተማው መንገድ በሥራም በጥዳትም የተከናወነ እንዲሆን ሲሉ ሥራውን በትጋት መጀመራቸውና ከቀድሞ ይበልጥ ማሻሻላቸው ያለጥርጥር እንደ ፀሐይ የተገለጠ ነው ። ሌላው ሁሉ የበጐ ሥራቸው ሳይደመር መንገድ ለሕዝቡ ማሠራታቸው ምንም ለጊዜው ጥቅሙን አንዳንድ ሰዎች ባያውቁት ። እስከ አሁን በተሠሩት መንገዶች ሁሉ እሩቁን ቅርብ ጭቃውን ደረቅ ከማድረግ ያደረሱ እሳቸው እንደሆኑ እነሆ ሥራቸው ሊመሰክር ይችላል ። ማዘጋጃ ቤት መንገድ ለመሥራት በፈለገ ጊዜ በዋጋ እንዳይበለጥ ሃሳቡን በወረቀት ጽፎ ማስታወቂያ በየመንገዱ እየለጠፈ ፤ በጨረታ ዋጋ ላሳነሰ ይሰጣል ፤ እንጅ ወዳጅ ጠላት ደሃ ኃብታም አይለይም ። ይኸውም ተጫርቶ ሥራውን የተቀበለ ሰው በማናቸውም የሚያስፈልገውን ጥንቃቄ ካላደረገ ነገሩ ተመርምሮ መቀጮ ይወድቅበታል ።

ክቡራን የመንገድ ሥራ ተቋራጮች ሆይ ይህ ሁሉ የተተከከለ ደምብ መቆሙን ስታውቁ አስር ሽህ ብር የሚያወጣውን ያጣሪ ስፈሩን መንገድ ሙሴ ሚናስ ባምስት ሽህ ብር ተቋርጠ የኃብታሙን ቦታ ሳይነካ ፤ በመንገዱ ምክንያት የደሃ የደሃውን ቦታ እያሰፋ አርባና አምሳ ሽህ ብር ደንጊያውን አራዳ ላይ ሊሸጥ ይስማማል እያላችሁ ታማላችሁ ይባላል ሙሴ ሚናስ

ደንጊያውን አራዳ ላይ አውርዶ እየሸጠ ሊጠቀምበት ቢያስብ ይህ የቆመው ማዘጋጃ ቤት መንግሥቱን በእምነት ከሚያገለግሉ ወጣቶች አንዱን ተቈጣሪነት ሊሾምበት ይችላል ፡፡ በዚህስ ለምን ይከፋችኋል ላንድ ለሙሴ ሚናስ ሲል መንግሥት ድኃውን እንዳይበድል እያወቃችሁ ሕዝቡን ከትንሽ እስከ ትልቅ አስተካክሎ ስለሚጠብቅ ከቍጥር አንድ ቢጐድልበት አይወድም ። ዳግም ሙሴ ሚናስ የደሃውን አፈርሳለሁ የኃብታሙን እሰራለሁ ብሎ በሥራው የተዋዋለ ይመስል ከሊጋባ ወዳጄ ቤት በላይና አሁን ከተሠራው ተማሪ ቤት ግርጌ ቤት ሲያሠራ እኔም እግረ መንገዴን ስሄድ አይቼ በድሮው ወሰን ልክ ስለምን ይሰራል ብዬ ብጠይቅ ከወይዘሮ አሰለፈች ቤት በላይ የመንገዱ ስፋት ፭ ሜትር ይሁን ተብሏል እየተባለ በከተማ ይወራል አሉኝ ፡፡ የዚህንም ምክንያት ለጊዜው እኔ ምንም ለማስረዳት ስላልቻልኩኝ ከማዘን በቀር ሙሴ ሚናስ በብርሃንና ሰላም በቀጥታው ሊያስረዳችሁ የተዘጋጀ መሆኑን ማንም አይስተው ሁለተኛ ከቅርብ ቀን በፊት እንደ ሰማሁት ከወይዘሮ አሰለፈች ቤት በላይ በሚሊዮን ጉራጌ የብዙ ደሃ ቤቶችና አጥሮች እያስፈረሰ ሲያስለቅስና መራራ ኃዘን ሲያዝኑበት አይቼ ይምሰል አይምሰል የጠይብ እጅ ከከሰል እንደሚሉት ሁሉ ያየተወራው ከደረሰ ዘንድ ለመጠየቅ የማያስፈልግ መሆኑን አውቄ ወደ ተግባሬ ሄድሁ ፡፡ ከሰው ስህተት ከብረት ዝገት አይጠፋም እንደሚሉት ድንገት እሱስ ቢያጠፋ ለጊዜው ያው በብዙ ድካም የሰራችሁት ቤታችሁ በመፍረሱና በክረምት የምትያርሱበት በማጣታችሁ ታዝኑ ይሆናል እንጂ መንገዱንማ አንዳንድ ላይ ለሐብታሙ አስር ሜትር አንዳንድ ላይ ለዳሃው ፳ ሜትር ሊሰፋ አይቻልም ፡፡ እንኳንስ ይህ ብዙ ከብት የማያልፍበት መንገድ ሌላ ሌላው የነጋዴ መንገድ ፳ ሜትር ነው ሲሉ ከለዛሬም አይተንና ሰምተን እናውቅምና ከራዳ እስከ ወይዘሮ አሰለፈች ቤት ድረስ አስር ሜትር ከዚያ በላይ የድንጊያውና የደሃው ቦታ ፳ ሜትር የሚሰፋ ከሆነ እውነትም ደንጊያውን ሊሼጥ ነው ከመባል ሙሴ ሚናስን ያድነው፡፡እኔም አህያ የለኝ ከጅብ አልጣላ እንደሚሉት ቦታ የለኝ ከወዳጄ ከሙሴ ሚናስ አልጣላ እንዲያው ለነገሩ የኃብታም ሳይፈርስ እኛን እስከ እልፍኞችን ቤትና አጥራችንን በሚሊዮን ጉራጌ ጠነጠነው እያላችሁ በመንግሥት ብታዝኑ ጉዳታችሁን ክቡር ከንቲባ እንዲያዩላችሁ እየተሰማኝ ነውና በዚህ ውስጥ ያልሰማሁት የተዘነጋ እንዳለ ይቅርታችሁን እለምናለሁ ።

ስመኝ መኰንን

በመስከረም ፲፮ ቀን ፲፱፻፳፯ ዓ ም በ፩ ሰዓት ከምሽቱ ከአስመራ የተላከ ቴሌግራም።

ልዑል እምልዑላን ተፈሪ መኰንን

አርሺሜድ የሚባለው የጦር መርከብ የኢትዮጵያ መላክተኞች ለዱክ ዴዝ አብሩዝ በኋለኛው ግንቦት ስለመጡበት መታሰቢያ ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የሚልኩትን ስጦታ የያዘ ከጂቡቲ መጥቶ ዛሬ ምጽዋ ደረሰ፣ ዱክ ዴዝ አብሩዝ ማዚኒ በሚባለው መርከብ ትላንት ከኢጣሊያ ሶማሌ የመጡት መላክተኞቹን ዋናው ፊታውራሪ ደስታ የሆኑበትን በክብር ተቀበሉ ። ፊታውራሪ ደስታ ለልዑል ዱክ ዴዝ አብሩዝ በእጅ የተጻፈ የግርማዊት ንግሥትንና የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ደብዳቤ ሰጥተው ታላቆቹን ስጦታ አንድ በወርቅ የተጠለፈ ሙሉ የከብት ዕቃ አንድ ጐራዴ አንድ ጋሻና አንድ የወርቅ ጦር ፣ ሁለት አንበሶች አንድ ግሩም የሆነ የአንበሳ ቆዳ ሰጧቸው ።

ወዲያው ይህን ከሰጡ በኋላ ፊታውራሪ ደስታ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።

ልዑል ሆይ

ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከልዕልናቸው ከንጉሡ ቤተ ዘመዶች ማህል ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ግርማዊ የኢጣልያን ንጉሥ ስለጐበኙበት ብድር ለመመለስ እርስዎ ስለ ተመረጡ በሁለቱ አገራችን መካከል ያለውን ወዳጅነት ይበልጥ ለማጥበቅ እንደሆነ በፍጹም ተረድተነዋል ።

ልዑል ሆይ በኛ ዘንድ መልካም የሆነ መምጣትዎ እንደምን ያለ ታላቅ ደስታ እንደሆነንና እርስዎም ሥጋቶችን አጥፊ ሁነው የሰላም መልክተኛ መሆንዎን በመመልከት በኢትዮጵያ ልብ ላይ እውነተኛ ፍቅር መቀረጹን ባለማቋረጥ ያስታውሳሉ ስል እምናለሁ ፡፡

ልዕልናዎ ኢትዮጵያን በጐበኙ ጊዜ ከእርስዎ ሳልለይ በመሰንበቴ በጣም ደስ ብሎኝ አሁን ደግሞ ወደ ልዕልናዎ ለመምጣት በመታዘዜ ስለ አገኘሁት ክብር ይበልጥ ደስ ይለኛል ። ይህ በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ወዳጅነት ለሁለቱ አገሮች መገናኛ ልማት ረዳት ነው ስል ፍጹም እምነት አለኝ ።

ልዑል ሆይ

እንደታዘዝሁት ከፍተኛ ትእዛዝ የግርማዊት ንግሥትንና የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የፍቅርና የወዳጅነት ሰላምታ ለልዕልናዎ ሳቀርብ ስለ ወዳጅነታቸው ምስክር የሚሆኑ እነዚህን ቃናናሾች መታሰቢያዎች እንዲቀበሉ እለምንዎታለሁ እንደ አገራችን ልማድ የተሠሩትን እነዚህን ዕቃዎች ምንም የእኛን ኃሳብ ለማስረዳት የማይበቁና ያነሱ ቢሆኑ ለልዕልናዎ በመልካም ፈቃዱ እንዲቀበሏቸው በማክበር እለምንዎ ዘንድ እደፍራለሁ ፡፡

ልዑል ዴዝ አብሩዝም ቀጥሎ በተጻፈው ቃል መለሱ ።

ክቡር ሆይ ።

አሁን ያቀረቡልኝን እጅግ የሚያምሩ ቃሎች በየነፍሳችን ውስጥ መልካም ስሜታ እንዲያገኙ አረጋግጥዎ ዘንድ ደስ ይለኛል ። አዲስ አበባን ስለ መጐብኘታችን መታሰቢያ ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በመልካም ፈቃዳቸው ለላኩልን መታሰቢያዎች በጥልቅ እናመሰግናለን እነዚህ ስጦታዎች መጀመሪ ከንጉሥ ዘንድ የመጡ በመሆናቸው ሁለተኛም እንደሚያምሩ ሁነው በመሥራታቸው ሶስተኛም በግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽ ለታላቁ ለኢጣልያ ነገሥታት ቤተ ዘመድ ፣ ለክቡር ሙሴ ሙሶሊኒ መንግሥትና ለኢጣሊያ ለመላው ሕዝቡ የወዳጅነት ታላቅ ምስክር እንዲሆኑ በሰቡት ከፍተኛ አሳብ ምክንያት ዋናነታቸውን በተለይ እንገምተዋለሁ ።

ለንጉሡ ቤተ ዘመድ የታማኝነት ምሳሌውን የሚሰጥ፣ ብኢትዮጵያም በሰነበትኩ ጊዜ ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን እጅግ ብሙረና በጣፈጠ አቀባበል ሲያስነብቱኝ ወኪላቸው የሆነ ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው ይህን የወደጅነት አሳብ ገላጭ በመሆኑ አጥብቆ በተለየ ደስ ይለኛል ።

ክቡር ሆይ አዲስ አበባን በመጐበኘቱ ጊዜ የተረጋገጡትን እነዚህን መልካም አሳቦች ለግርማዊት ንግሥትንና ለልዑል አልጋ ወራሽ እንዲያደርሱልኝ እለምንዎታለሁ። በነዚህም መልካም አሳቦች ላይ ዛሬ የተደረገው የወደጅነት መግለጫ ሲጨመርበት በሁለቱ አገሮች መካከል እየጸና ለሚሄደው ፍቅር ታላቅ ማረጋጋጫ ሆኑ ።

በኢትዮጵያና በኢጣሊያ በሁለቱ አገሮቻችንን የጠበቀውን ፍቅር መጽናቱን በዚች መሰብሰብ ተረድቼው ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ጤንነትና ለኢትዮጵያ መንግሥት ገናንነት እገልጻለሁ ብለው ጨረሱ ።

በዚሁም ምክንያት ምጥዋ ላይ የደመቀች በዓል ሆኖ የከበረ ብሩህ መሰብሰብ ሆነ ከኩለቀን በኋላ ከመንግሥቱ አዳራሽ መሰብሰብ ሆኖ የግዛት ሹማምንቶችና የጦር ሹማምንቶች ተዘጋጅተው ትልልቆች የኤርትራ ሹማምንቶች ተገናኙ ።

ከምጥዋ ጠረፍ ደስ የሚያሰኝ የመርከብ መረወጥ ነበር ከዚህም በኋላ የልዑል ዱክ ያዲስ አበባ ጉዞ ሲኒ ማቶ ግራፍ ሆነ ይህ ከሆነ በኋላ እንጥብርቅ ሆኖ ከተማዋ በርታ የጠረፉወሀ ብሩህነት ይታይ ነበር ክሪስፒና ማሲኒ የጦር መርከቦችም አዳራሽም በብርሃን አጊጦ መሻገር ሆነ ከቀሩትም ሹማምንቶች ከተሰበሰቡት ጋራ የጅቡቲው ቆንስል አቶ ክብረትና ፊታውራሪ ቢራራ ከዚህ በዓል አብረው ነበሩ ። ሌላም ሹም ደጃዝማች ተድላ አባ ጉበንም ወዳገራቸው ለመሄድ ከዚያው ነበሩ ። ይህ ቀን እንደምስክር ሆኖ የኢትዮጵያንና የኢጣልያንን የጸና ፍቅር የሚመሰክር ይሆናል ።

ስለ የርሻና የመሥሬ ሚኒስቴር ቤት ምረቃ ።

መስከረም ፰ ቀን ከእኩለቀን በኋላ ባስር ሰዓት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል የኢ. መ አ ወ ተፈሪ መኰንን ከክቡራን መኳንንቶቻቸው ጋራ የርሻና የመሥሬን ቤት ለመመረቅ ከቤተ መንግሥቱ ተነስተው የርሻና የመሥሬን ጽሕፈት ቤት እንዲሆን አምሮ በተሰናዳው ስፍራ ገቡ ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል የኢ. መ አ ወ ተፈሪ መኰንን የጽሕፈት ቤቱን ሁሉ በየክፍሉ ዞረው አይተው ካበቁ በኋላ አምሮ በተሰናዳው ድንኳን ገቡና ሻምፓኝ ተጋበዙ ። በሻፓኝ ጊዜም ክቡር አቶ መኰንን የርሻና የመሥሬ ቤት ዲሬክተር በሚኒስተሩ በክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደመስቀልና በሠራተኞቹ ስም የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ዛሬ በዓላችንን ለማክበር ከክቡራን ሚኒስችሮትዎና መኳንንቶችዎ ጋራ በዚች ባሁኑ ሰዓት ስለገቡኙን ። ለደስታችን ዳካ ለክብራችን ወሰን የለውም ስለዚሁም በሚኒስትሩ በክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ስም ። ደግሞ በርሻና በመሥሬ ሚኒስቴር ሠራተኞችና በኔም በራሴ ስም ሆኜ ጥልቅ ምስጋናችንን አቀርብለዎ ዘንድ ውድ ፈቃድዎ እንዲሆን እለምናለሁ ። ይህቹ የዛሬይቱ ውድ የሆነች የመጐብኘትዎ ቀን ለኛ ለርሻና ለመሥሬ ሚኒስቴር ሠራተኞችዎ ክብር የተጐናጸፈች ጌጣችንና ወደፊትም የሥራ ትጋታችንና ኃይላችን ትሆናለች ።

እነሆ በዘመናችን የኢትዮጵያ ዕድሏ ተገለጠ ። ካሁን ቀድሞ እናታችን ኢትዮጵያ ልጆቿን የምታሳድግበት ብዙ ልዩ ልዩ ሀብት ሲኖራት የሚያስተዳድርላትና ገልጦ የሚያውቅላት ሰው አጥታ ተሸፍና ስትኖር ። ግርማዊት ንግሥትና ልዕልናዎ በመታደልዋ በሕዝቧ ላይ የብርሃን ጨረር ዘርግተው ልጆቿ እርስ በራሳቸው ተያይተው በከንቱ የተሸፈነውን የኑሮአቸውን ባሕርይ እንደ መስተዋት ገልጌው ስላዩ ። አይተውም ስለ ተጸጸቱበት ይኸውም በያለበት የሥራቸውን እርምጃ ማሳየት ጀምረዋል ። እርሻና የመሥሬ ሚኒስቴር ሠራተኞች ለምለሚቱ ሀገራችን ኢትዮጵያ በምግብም በልብስም ቢሆን ልጆቿን የባዕድ እጅ ሳታሳይ የምታሳድርበት የነፃነት ኩራቷን የምትጠብቅበት ከሌላው ልዩ ልዩ ሥራዋ የገነነ ። አይነተኛ ሥራዋ ከብት ማርባትና የርሻ ሥራ መሆኑ ጠልቆ ስለተሰማን ግርማዊነትዎን ተማምነን ተፈሪ ክንድዎን ተመርኩዘን ይኸው የሥራችንን መልካም ጉዞ ወደ ፊታችን አቅንተን ለመሄድ ፍጹም ምኞታችን መሆኑን በትህትና እንገልጻለን የሥራችንንም አረማመድ የሚያሳይ ከሥራችን ውጥኖች ውስጥ ጥቂቶች በጭሩ አመለክትዎ ዘንድ እነሆ እጀምራለሁ ።

(፩ኛ)ሀገራችን ኢትዮጵያ መጀመሪያ ሀብቷ የርሻ ሥራ ስለሆነ ጥቅሙን አመዛዝኖ በያውራጃው ያለውን ባላገር በርሻ ሥራ ላይ የሚገኘውን ጥቅምና ጉዳት አመዛዝኖ በየጊዜው የሚያመለክተው ። ደግሞም ስለ ሕዝቡም ጥቅም ለየጊዜው ያስተዳደር ደምብ እያወጣ የሚላላክበት የርሻ ሚኒስቴር በያውራጃው የሥራ ቤት ማቆም ጀምሯል ።

(፪ኛ)የኢትዮጵያ ሀብቷ የከብት ማርባት ሥራ ስለሆነ የከብት ጤና ጠባቂ ባለመኖሩ እንደ መርባቱ ብዛት ። ታማሚውና ሟቹ በዚያው ልክ በመሆኑ ለዚሁ አደጋ አፍራሽና ጤና ጠባቂ የሚሆን የርሻ ሚኒስቴር የከብት ሀኪም አቁሟል ።

(፫ኛ)በማናቸውም አገርና መንግሥት ቢሆን የጀመረ እንጂ የጨረሰ የለምና እንደዚሁም መጀመሪያ የኢትዮጵያ የሥልጣኔ በር ከፋችና የእውቀት መሪ ሆናችሁ በመጀመራችሁ ጀምራችሁም የደከማችሁበትን ፍሬ ለማየት ከታላቁ እግዚአብሔር እድል ስለተሰጣችሁ ይህን ቸርነት ላደረገልን እግዚአብሔር ዋጋና ምስጋና አናገኝለትም ።

ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ፡ ላልጋ ወራሻቸው ልዑል ተፈሪ መኰንን እረጅም እድሜና ጤንነትን ይስጥልን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑርልን ። ብለው በጨሱ ጊዜ ጭብጨባው ቀለጠ ።

የርሻና የመሥሪያ፪ ቤት ሚኒስቴር ዲሬክተር ክቡር አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ ።

ከዚህ በኋላም የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን የሚከተለውን ንግግር ተናገሩ።

በግርማዊት ንግሥትና በኔም በራሴ ስም ሆኜ ምስጋናዬን አቀርብላችኋለሁ ። ምኒስቴር ማለት ምሳሌው አካል ማለት ነው ። ከካል ውስጥ አንዱ የዛለ እንደሆነ የቀሩትም ህዋሳቶቹ ሁሉ እንደ ሚበዝኑ እንደዚሁም የቀሩት ምኒስቴር ቤቶች በትጋት ሥራቸውን ካልሰሩ፤ያንዱ ምኒስቴር ሥራ ብቻ በቂ አይሆንም የውጭ ጉዳይ ምንስቴር በመቆሙ ደስ ብሎን፤ አሁን ደግሞ ይህ የምኒስቴር ቤት በመከፈቱ እጅግ መልካም ሆነ።የኢትዮጵያ ዋና ሃብቷም የርሻ ሥራና ከብት ማርባት መሆኑ እርግጥ ነውና፤እናተ የርሻና የመስሪያ ምኒስቴር ሥራ አስኪያጆችና ሠራተኞች እንዳሁኑ ውጥናችሁ ባላችሁ አቅም ሳትበዝኑ ሀገራችሁን እንድትረዱና መንግምታችሁን እንድታገለግሉ ይሁን ብለው በጨረሱ ጊዜ ከግቢ እስከውጭው ጭብጨባው ቀለጠ ።

ከዚህ በኋላ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አብረዋቸው ከነበሩ ክቡራን መኳንቶቻቸው ጋራ ተነሥተው ሔዱ ።

መስከረም ፱ ቀን ከእኩለ ቀን በኋላም ደግሞ የርሻና የመሥሪ ሚኒስትርና ዲረክተሩ የርሻና የመሥሪ ሚኒስቴርን እንዲመርቁ አያሌ መኳንንቶችንና የየሥራው አለቆችን የውጭ አገር ሰዎች የኢ. መንግሥት አገልጋዮችንም ጠርተው ነበርና ከሻይ ግብዣ በኋላ በሸምፓኝ ጊዜ ሚንስትሩ ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደመስቀል በሠራተኞቹ ስም የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ክቡራን መኳንንቶች ሆይ

የዛሬ በዓላችንን አክብራችሁ የርሻና የመስሪያ ሚኒስቴርን ለመመረቅ ስለ ተሰበሰባችሁ የዘለዓለም መታሰቢያችንና የዘወትር ደስታችን በመሆኑ በራሴ ስምና በርሻና በመስሪያ ሚኒስቴር ሠራተኞች ስም አመሰግናችኋለሁ ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ስለ ሃይማኖቷ ከረማውያን ጋራ ስትዋጋ የሥልጣኔ መንገዷ ታውኮባት ሳለች ነቢዩ እንደ ተናገረው እጆቿን ወደ ታላቁ እግዚአብሔር ዘርግታ ልመናዋን ስላቀረበች የዕድል ዕጣዋ ደርሶ ታላቁ ዳግማዊ ምኒልክ የመሠረቱትን ሥራ ለማስፈጸም ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱንና አልጋ ወራሻቸውን ልዑል ተፈሪ መኰንንን አስነሳላት ይኸው እንደምናያቸው ልዩ ልዩ የሥራ ቤቶች ቆሙ ። ይኸውም የኢትዮጵያ ዕድል ተብሎ ይጠራል ።

የጽሕፈትና የርሻ ሚኒስትር ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ።

ሰው እዚህ ዓለም መጥቶ ለመኖሩና ቆይቶም ለመሄዱ ለተከታዩ ትውልድ ማስረጃ የሚሆነው አንድ የሥራ ምልክት ትቶ ካልሄደ ነበር ለማለት እንዴት ይቻላል ? ሰው እዚህ ዓለ

ም ሊኖር በተፈቀደለት ጊዜ ለስሙ መታሰቢያ የሚሆነውን አንድ ሥራ ካላደረገ ስንኳንስ ብዙ ጊዜ የተለየንን ዛሬም እንኳ በህይወቱም ሳለ ቢሆን አንዳንድ ሰው ለመኖሩ ፣ሚያስታውስ ለት ሥራ ባለ መሥራቱ ሳለ እንደሌለ ሆኖ ይኖራል ። ስለዚህ ሁላችንም በያለንበት የተቻለንን ያህል እየሰራን መንግሥታችንን ብናገለግል ለራሳችንም ክብር ለመንግሥታችንም ኩራት መሆኑ አይጠረጠርም ።

እግዚአብሔር ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለአልጋ ወራሻቸው ለልዑል ተፈሪ መኰንን ረጅም ዕድሜና ጤንነት ይስጥልን ኢትዮጵያ ዘለዓለም ትኑርልን ።

ወዲያውም ክቡር ዶክቶር ሬኖ የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ሐኪም በኢትዮጵያ የእርሻ ሥራ እንዲሰለጥን በእርሻና በከብት ማርባት የበለጡት የበለጡትን እየሸለሙ ለዚህ ሥራ እንዲያተጋቱ ለሚኒስትሩና ለዲሬክተሩ የጀመሩትን ሥራ ተከናውኖ እዲፈጸምላቸው እየተመኙ ለኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ደስ በሚያሰኝ ምርቃት መርቀው ነገራቸውን ጨረሱ ።

ከእውነተኛ የኢትዮጵያ ብልጥግና ምንጭ የርሻና የከብት ማርባት አንዱ መሆኑን ስላወቀ ብርሃንና ሰላም እርሻና ከብት ማርባት ባገራችን ሰልጥኖ ላገሩ ተርፎ ለውጭውም ትርፉን ለማካፈል እስኪበቃ ድረስ እንዲሆን እየተመኘ ለዚሁ ሥራ ለማከናወኑና ለማስፋቱ ታጥቀው ለቆሙ ለሚኒስትሩ ለክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀልና ለዲሬክተሩ ለክቡር አቶ መኰንን ሃብተ ወልድ ለሠራተኞቹም ሁሉ ልምላሜውን ያሳየን አምላክ ፍሬውን ያሳየን እያለ መልካም ምኞቱን አቅርቦ እንኳን ደስ ያላችሁ ይላል ።

የእጅ ሰዓት ዝኒት



በአውሮጳ አገር ሚከሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለፈረስ ስዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሰያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል"አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ"ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅበት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ኬኬ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለከ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሄስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፤ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክስል የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ትእዛዝ

ሙሴ እንድርያ ከዋዲያ በደጃች ዓለማየሁ ወራሽነታቸው ከደጃች ብርቄ ስለሚፈልጉት ገንዘብ የደጃች ብርቄን ወራሾች ብዙ ጊዜ አስፈልገን ስላጣናቸው የሙሴ ከዋዲያን ገንዘብ ከ ፋይ ሰው ስላጣን የደጃች ብርቄ በታ በቁጥር የተጻፈው በጥ ቅምት ፱ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም በሐራጅ እንዲሸጥ አዝዘናል የሙሴ ከዋዲያንን ገንዘብ እከፍላለሁ በታችን አይሸጥ የሚል ሰው ከ ዚህ ቀን በፊት መምጣት ያስፈልገዋል ይህነን ቃል የጸሐፊዎች አለቃ አቶ ቀጣው ጋዜጣ እንዲጻፍ የድርግ ማስታወቂያም እን ዲለጠፍ ያድርግ ብለን አዝዘናል ጳጉሜ ፬ቀን ፲፱፻፱ ዓመት ፈርማ የነጋድራስ አፈወቅ ።

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርክሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፱
3 me ANNÉE № 39

ሐሙስ መስከረም ፲፰ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 29 SEPTEMBRE 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen , Héritier du trône d' Ethiopie , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ያስታውቁ ።	የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ስፈልግ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።	Abonnements Ethiopie Un an 5 Thalers Etranger Un an 7 Thalers le numero 2 piastres

ስለ እንቁጣጣሽ ምስጋና ።

መቼም አራቱ ወንጌላውያን የዘመን ማገጃና የክርስቲያን ደስታ መሆናቸውን ዓለም ሁሉ የሚያውቀው ስለሆነ ለሀገሬ ልጆች ለወጣቶችና ላባቶቼም በየክፍሉ ምስጋናዬን ስለእንቁጣጣሹ ልሰጣቸው ወድጃለሁና ጆሮ ያለው ቢሰማኝ ለደስታዬ ፍጻሜ አላገኘለትም ። እነሆ የእንቁጣጣሼን ክንፒሊማ (ምስጋና) ጀመርሁ ።

ስለ ንግሥታችን ።

የነግሥታት ልጅ ዘውዲቱ ። ስምሽ ተጠርቷል በብርቱ ። አይታሰብም ጽናቱ ። የጠላታችን ክፋቱ ። የኢትዮጵያ ዘሪቱ ። ባሕር ከፋች ነሽ በሪቱ ።

መክፈቻ አንች ነሽ የባሕር ። ዘውዲቱ ንግሥት በምር ፤ ተፈሪ ልጅሽ ባይኖር ፤ ያባትሽ ድሐ በክብር ፤ ዬት ይኖርልሽ ነበር ፤ እንዳታደርገኝ አፈር ፤ አምላክ ሰማይ ወምድር ፤ እንዳታሳዩኝ አስቀር ፤ የኢትዮጵያን ችግር ፤

ዋ ብሎ ቢሄድ አሞራ ፤ ያባ ዳኛው ልጅ አትፈራ ፤ ሊቀማ ጠላት ቢከራ ፤ ተፈሪው ልጅሽ አስቀራ ፤

የሕዝቡ ሁሉ ፈጣሪ ፤ እድሜ ይስጥልኝ ለተፈሪ መንፈስ ቅዱስ ሆይ ብረሪ ፤ የምስራቹን ንገሪ ፤ ተወልዷልና ተፈሪ ፤ ኢትዮጵያን አክባሪ ።

መቼ ሞተና መኰንን ፤ ተክቶልናል ተፈሪን ፤ ጉዘው በዛና ቀረን ፤ ጠቅል ተፈሪን አፈራን ።

ስለ ኢትዮጵያ ጀግኖችና አርበኞች ።

ለሀገራችን ለናታችን እንዳገሰላች ላስጋችሁ ብዬ ልለምናችሁና ወረታዋን እናቅርብላት ።

በየክፍላችን እንበርታ ፤ ጥለኛችንን እንርታ ። እናቀርባለን ይቅርታ ። ለኢትዮጵያ ክረብታ ። መንገድሽ ይሁን ቀጥታ ።

ስለ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንቶች ፤

እሹ ጥንካሬ ብርታት ። ጉዳናውንም አቅኑት ፤ ትምህርታችሁን አስፉት ። ይጨመርበት ጸሎት ፤ ዛሬ ነውና ብርታት ፤ ሳይል ጠያቂው ጉተት ፤ ትምህርታችሁን አጽኑት ፤ ብርያ እንድሆን በእርቀት ፤ እብነ እል ዓሳል ጽሮት ፤ እንውጣ ስንል አርነት ፤ ከእስክንድርያ ሰራዊት ። ክርክር ሳይቀር ስርአት ፤ ተዘጋጅታችሁ ቆዩት ።

ክቡራን ሊቃውንቶቻችን ሆይ ስንኳን ለዘመነ ዮሐንስ አደረሳችሁ የመጻሕፍቶቻችሁን ምዕራፍና ቁጥሩን እንዳትዘነጉትና በእልባት እንድት አቆዩት በታላቅ ተስፋ እናስባችኋለን ።

ስለገበሬዎች ምስጋና ።

የት ኬደ ሳይል አሽከሬ ፤ ነጭ የሚአመርተው ገበሬ ፤ ጥቁር ጤፍ አትበል ነጋዴ ፤ ነጭህን ብላ ዘመዴ ። ግፉም እክ ነው ብርታት ፤ ኃይል ገበሬው መሰረት ።

ክቡራን ገበሬዎች የወታደርና የካህን የደጅ ጠኚና የነጋዴም መሰረቶች ሆይ ስንኳን ለዘመነ ዮሐንስ ለመድረስ ያበቃችሁ ብለን እናመስግናችሁ ።

የሥልጣኔውም መዝሙር በኔ ሐሳብ እንደዚህ ይመስለኛል ። መጀመሪያ የገንዘብ ወጭን ሳትመለከቱት በያውራጃችሁ የትምህርት ቤትን ማቆም ነው ።

፪ተኛም ሲቢሊዛሲዮን ማለት የእውቀትን ስልጣኔ ለማስፋት ያለ መሰልቸት ነው ። ፫ተኛም የሥራ ብልሐትን ለማቆም ፋብሪካን በያይነቱ በየጠረጳችሁ ማብዛት ነው

፬ተኛም ዜጎቻችሁን መልካም አገዛዝ ማለት ትክክለኛነት ነው ። ፭ተኛም በቀጥታና በሙሉ ልብ ለሀገር ማሰብ መልካም ነው ። ፮ተኛም በየግዛታችሁ ውስጥ የሰለጠኑትን

የወጣቶችን የእውቀት መሪነታቸውንና የጊዜውን አካሄድ የስልጣኔውን ጉዳናቸውን ማስፋት በጣም ጥሩ ነው። ብዙውንም እንዳልጽፈው ብርሃንና ሰላም በሌላ በኩል ስራውን እንዳይፈታብኝ እሰጋለሁኝ ። እግዴህ ጌቶቼ ሆይ እኔ ያለሁም የሌለሁም የማልታወቅ አንድ ድሐችሁ ለክቡርነታችሁ መጻፌ ሐሳብ የሚባለው ትልቁ ሽክም ቀንና ሌሊት እንቅልፍ ስለነሳኝ እርሳሴንና ወረቀቴን አነሳሁ ። የእውቀት መሰረት በጥራሮትከሚአውቁት በስተቀር የትምህርት ቤት መሆኑን ተረድታችሁታልና የዳግማዊ ምኒልክ የልዑል ተፈሪ መኰንን የትምህርት ቤት ብቻ ሳትመለከቱት በዝግጁ ሐሳባችሁ በያውራጃችሁ የተማሪ ቤትን ለመክፈት መጣጣራችሁን እንለምናችኋለን ።

ደነቀ ተክለ ጊዮርጊስ ።

ለወይዛዝሮች እንቁጣጣሽ ።

ይድረስ ለክቡራን የሃገሬ ወይዛዝሮች ለክብራችሁ የሚገባ ሰላምታዎቼን አቀርባለሁ ። ከዚህም በታች ለናንተ ጥቅም የመሰሉኝን ቃሎች አመለክታችኋለሁ ፈቃዳችሁ ቢሆን ።የትምህርት ቤታችን ስለእረፍት ጊዜ ስለተዘጋ ባለፈው ዓመት መከር ወዳጄን ብርሃንና ሰላምን መሪ አድርጌ ማስተዋል የሚባሉ መነጽሮቼን ባይኖቼ ዘርግቼ ወደ ጅቡቲ ለሺርሺር ሂጄ ነበር እዚያም አንድ የውጭ አገር ሰው ወዳጅ አገኘሁና የውጭን አገር ወይዛዝሮች ስልጣኔ ነገረኝ ቃሉም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ። አንድ ባለጸጋ ጓደኛውን ለሻይ ከነባለቤቱ ጋብዟቸውነበር ያም የተጠራ ሰውዬ የግብዣውን መጥሮ ተቀብሎ አግብቶ ሳለ ከሥራ ብዛት ቀጠሮውን እረስቶት ኖሮ የተቃጠሩበት ጊዚያት ኑስ ሰዓት ሲቀረው ቀጠሮውን አስታወሰና ከነሚስቱ በፍጥነት ልብሳቸውን ይለውጡ ጀመር ያኔውኑም ልብሳቸውን ለዋውጠው ሲጨርሱ ሴትዮዋ ጸጉሯን ታበጥር ጀመር ጸጉሯም ከእርዝማኔው የተነሣ በቶሎ አልከናወንላት ስላለ እሷም እንደዚህ አለች በልብስ አለባበስ ባካሄድ በነጋገርም ከባሌ አልሰነፍኩም ነገር ግን በጠጉሬ ብዛት የተነሣ ከባሌ ወደኋላ ልቀር ሆን እኔስ ጸጉሬን እንደ ባሌ ባሳንሰው ምን አለብኝ ብላ ያኔውኑ ጸጉሯን ቆርጣ ወደ ቀጠሮዋ ሄደች።ደግሞም የሃገሯ ወይዛዝሮች ሁሉ ይህ የሷ ሃሳብ መልካም መሆኑን ስለተረዱት ጸጉራቸውን በልክ እየቋጠሩ ይቆርጡ ጀመር ይኸውም (ሞድ)ለሃገር ልማድ ሆኖ እስከ ዛሬ አለ ብሎ ይህችን መልካም የስልጣኔ አኳኋን ስላጫወተኝ እኔም ይኸንን በሰማሁ ጊዜ ይህቺን የስልጣኔ አኳኋን ለመቤቶችና ለእህቶቼ ቢሰሙት መልካም ነበር ስል ላሳስባችሁ ጻፍኩላችሁ ።

የሃገሬ ወይዛዝሮች እናቶቼና እኅቶቼ ሆይ ።

ይህቺ ወይዘሮ ለሃገሯ ስልጣኔ በመሰላት ነገር ስላሰበች ባሃገሯ ስሟ እንደ ሃውልት ስለተተከለና ይህቺ ወይዘሮ የጀመረችልን የስልጣኔ መንገድ መልካም ነው እንደተባለች ሁሉ እናንተም ምነው ወደ እውቀት አትጣጣሩም ይኸውም እውቀት ለናንተ በመላው ዓለም የክብር ስም ይሆናችሁ ነበር በትጋት ቡቃስቡብት ።

፭ኛ መልክ የላችሁ እንዳይባል ቁንጆ ነው መልካችሁ እመቤቶቼ ሆይ እንዳሸንጉሊትና እንደ በሺተኛ ፊታችሁንና እራሳችሁን ለምን ትሸፍናላችሁ ። ይልቅስ እንደ ጎረቤቶቻችሁና እንደ ባልንጀሮቻችሁ በግልጽ ብትሄዱ የሚያሙአችሁ ጠላቶቻችሁና ጐረቤቶቻችሁ ምንኛ ባፈሩ ። ተወላጆቻችሁ የሃገር ልጆች ምንኛ በኰሩባችሁና ደስም ባላቸው ።

፮ኛ አንዳንድ ጊዜም ከጐበሩና ከመጋረጃው ወጥታችሁ እንደ ጐረቤቶቻችሁ በየአታክልታችሁና በየግቢአችሁ ውስጥ ያለውን ስራና አኳኋን በየጊዜው ብትመለከቱትና ብትፈቅዱት መልካም ነበር ።

፯ኛ ፡ ቀሚሳችሁን አጠር አጠር አድርጋችሁ ብትታጠቁት ውብ ነው ይኸውም ዘርፈፍ አድርጎ መታጠቅ መንገድ ስትሄዱና ሺርሺር ስታደርጉ ለመራመድ እየከለከላችሁ እንቅፋት የሚሆንባችሁ ይመስለኛል። ከሰውነታችሁስ አትርፋችሁ ልብሳችሁ መንገድ እየጠረገና አዋራ እያነሳ ሲሄድ ምን ጥቅም ያለው ይመስላችኋል።በሰለጠኑ ሰዎች ፊትም ከትምህርት ጉድለት ነው ይህ አለባበስ እያሉ ይቀልዱባችኋል ።

፰ኛ ፡ ገረዶቻችሁን እንደ ማስፈተል አሽከሮቻችሁን እንደ ማሳረስ ሥራችሁን እንደ መጐብኘት ሁሉ ሥራፈትነት ወዳችሁ ሥራን ጠልታችሁ ደጅ ጥናት እንሄዳለን በቅሎ ጫኑ አሽከሮቻችንም ተከተሉን እያላችሁ ሳይቸግራችሁ አቀብና ቁልቁል ማለታችሁ ያሳዝናል ። የሴት አራሽ የወንድ አስፈታይ ሁለቱም ያለሥራቸው ነው እያሉ ሽማግሌዎች እንደሚተርቱት ሁሉ ይኸውም ስንፍና እባሎቻችሁ ላይ መሆኑ እርግጥ ነው፣ ባሎቻችሁ ፊት ባያሳዩአችሁና ባይፈቅዱላችሁ ይኸንን የመሰለ ሃሳብ ስታስቡ ፊት ቢነሱዋችሁና ቢገስጹዋችሁ መች ሥራፈት በቅሎአችሁን እያስጫናችሁ ችግረኞች አሽከሮቻችሁን መቼ ታለፉቸው ነበር ። ይኸውም ስንፍና ለባሎቻችሁ ስም ማስጠፎ ነው ።

፱ኛ ፡ የሃገሬ ወይዛዝሮች እመቤቶቼ ሆይ ሰውነታችሁንም አነቃቂ ሥራችንም ጐብኙ የጅ ሥራ ተማሩ ደጅ ጥናትንና አጅብን ናቁ ብልሃትንም አስቡ የናንተ ደጅ ጥናትም እባሎቻችሁ ድረስ ይሁን ለናንተ ሰጭ ነሻችሁ ባሎቻችሁ ናቸውና የባሎቻችሁን ፈቃድ ከፈጸማችሁ ለናንተ ዋናው ደጅ ጥናት ይህ ነው በርታ ብላችሁ ሰውነታችሁን እያነቃቃችሁ እፍረትንና ይሉኝታን ንቃችሁ በሥራና በዕውቀት ላይ እንደ ደጅ ጥናቱ ብትጣጣሩ ምንኛ በተወደዳችሁና በተከበራችሁ ነበር ። እመቤቶቼ ሆይ ከ፲፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ሕጻናት ልጆቻችሁንና ወንድሞቻችሁን የተራመዱትን አረማመድ፣ እስቲ ተልመከቱት አሁን ጥቂት በናንተ በኩል ብንመለከት አንድም ዕውቀትን የሚያስብና የሚመለከት ስለሌለ በጣም ያሳዝናል ። ክቡራን የሀገሬ ወይዛዝሮች በጠፉም እርማችሁ በጐደለም ሞልታችሁ በተሰጣችሁ አእምሮአችሁ እንድትመለከቱት ስል አሳስባችኋለሁ ።

ያገሬ ወይዘሮ አስቡ መክብብን እዩ ምሳሌን፣ እሱ ያስረዳችኋል የዕውቀቱን ብርሃን፣ ይሉኝታን አስንቆ ጥበብ መማርን መጽሐፍ ነውና ቅዱስ መሪአችን፣ ጠንክር በርታ ብሎ እው

ቀት መማርን፤ ይህ ነው መልካም ነገር የሚያስጠራ ስም፥ በርቱና ተማሩ የሀገር ፍቅርን፣ ብዬ እናገራለሁ ለናንተ ክብሩን፣ ብትወዱም ብትጠሉም አንብቡ ይሄን ።

በቀለ ዘለቀ ።

የሚያስደንቅ ጫወታ

አንድ ቀን ማታ ከቶ ሃሳብ ጋር በመንገድ ውስጥ ሽር ሽር ስናደርግ ከጫወታ የተነሣ ትንሽ ገንዘብ ነበራቸውና በዚህ በገንዘቤ ምን ላድርግበት እያሉ ምክር ይጠይቁኝ ጀመር እኔም ስለ ገንዘብዎስ የሚጠቅም ነገር ምን ላድርገው ስላሉኝ ምክሬን ልስጠዎት አልኳቸውና ከሁሉ ነገር ስም ይበልጣልና ስምዎ ለዘለዓም ተተክሎ እንዲኖር ለሃገርዎ ጠቀሜታ የሚሆን መታሰቢያ የፈለጉትን ቢያደርጉ የሚሻል ይመስለኛል ይልቁንም የትምህርት ቤት ። በዚህ ጊዜ ምክሬ ልባቸውን የነካው ይመስለኛል ። (እህ እህ እህ) ብለው ሳቁ ። አንተስ የደላህ ነህ ስለምን ትቀልዳለህ እኔስ ይህ የሚያተርፍህ ዕቃ ነውና ብትገዛውም ጠቀሚታ ታገኛለህ የምትለኝ መስሎኝ ነበር ሥራየንም እያወቀው በንግድ እንደምቀመጥና የበቃ ትዳር ስንኳ እንደሌለኝ ለኔ መኖሪ ጕጆ የሌለኝ ትምሕርት ቤት አቁም ብለህ ትመክረኛለህን ? ይልቁንስ ይኸነን ምክርህን በዓመት እስከ ፱፻፲ ብር ለሚያገኙት ምክራቸው አሉኝ ። በዚህ ጊዜ አጥብቄ ደነገጥኩኝ ከንግግራቸውም ይቅርና እኔስ በጦር እንደ ተመታ ሆንኩኝና ይኸንን ንግግር እስቲ ይመልሱት አልኳቸው በፊት እንደተናገሩት ሁለተኛ መለሱት እኔም ገረመኝና እነዚህን የመሰሉ ጌቶች በሃገራችን እያሉ እውነትም ለአምላካችን ምስጋና ይገባዋል ይልቁንስ እኔስ ልመክራቸው መች ይቻለኛል ትንሽ የሃሳቤን ልፈትፍት እንጂ እውነትም እነዚህን የመሰሉ ሃብታሞች እያሉ ለሃገራቸው ስንት ጠቀሜታ ይሰሩ ነበር የእውቀትስ ምንጭ እንደምን በፈለቀ ማለት ስማቸውስ እስከ ዘላለም እንደ ብረት ምሰሶ ጸንቶ ይኖር ነበር ። አንድ አንድ ሰዎች በአውሮፓ መታሰቢያ ለሃገራቸው ከብዙ ዘመን በፊት ያቆሙትን የሃገራቸው ሕዝብ ስማቸውን እያነሱ ሲያመሰግኑአቸው እንሰማለን ። እነዚህን የመሰሉ ሃብታም በሃገራችን ካሉ ትልቅ ደስታ ነውና ስማቸውን እባክዎ ይንገሩኝ አልኳቸው ስማቸውንስ አሁን ለጊዜው አላስታውስምና በሌላ ጊዜ እነግርሃለሁ አሉኝ ። እኔም ስማቸውን ባይነግሩኝ በትንሹ የደስታ ምልክት ስለነገሩኝ አሁን የቆምኩበት መሬት አልበቃ ብሎኛል እነዚህም ጌቶቹ ከሁን በፊት ሳያስቡ አይቀርም ይመስለኛል ። አሁንም ያጫወቱኝን በብርሃንና ሰላም ለማሳተም ተስፋ አለኝና አሁንም ያልናቸው ጌቶቹ ሳያነቡት አይቀርምና ያለጥርጥ ከሐብታቸው አክፍለው ለወንድሞቻቸው ለኢትዮጵያ ልጆች የትምህርት ቤት እንዲያቆሙላቸውና ሌላም የበለጠ ሐሳብ እንዲያደርጉ በደስታ እየጓጓሁ የኢትዮጵያ አምላክ ይጠብቃቸው ለማለት ያብቃኝ እያልኩ እመኛለሁኝ ።

ትንሹ ልጃችሁ ጥሩነህ ከ

ስለ ሀገር ፍቅር

በዓይኔ ያየሁትና በታሪክ የሰማሁት

ብርሃንና ሰላም በጧት ታጥቆ ተነስቶ ያገሬን ልጆች የራባችሁ ላጥግባችሁ የተጠማችሁ ላረካችሁ የት አላችሁ እያለ የተበታተኑትን በጎቹን ሊፈልግ ክንፉን እንደዘረጋ እየበረረ ዓለሙን ሲዋኝ እንደ ልማዱ እኔ ባለሁበት ስፍራ ከተፍ አለ ለካ ከዚያው በሁለተኛው ዓመት ቁጥር ፴፰ ገጽ ፫፻፪ ባለዘመኖቹን ከሌላ ጓደኛው ተበድሮ ከነስእላቸው አግብተዋቸው ኑሮ እኔ ገና ሰላምታ ሳልሰጠው አንድ ተማሪ ከጓደኛዬ ነጥቆ አይቶ ወሬውን በተማሪ ቤቱ ባንድ ጊዜ ነዛው ። መቸም ካባቱ ስንፍና በተቀር ሌላውን የሚያወራለት ሰው የለውምና ተማሪዎቹ በአንድነት ተነስተው አባትህም እስከዚህ ደፍሮ ሊያሳትም ቻለ ወይ እያሉ ለመናገር የማያምር ብዙ ጸያፍና ውርደት እጅግ የሚያሳዝንና የሚያጋድል መዓት አፈሰሱበት ። እዚያ ልትፋረድ ነጥቀን ወደ ማተሚያ ቤታችን እንልክሃለን፣ አለዚያ እንበጫጭቅሃለን ብለው ትግል ተነሱበትና እኔም ከወዳጄ ጋራ የሆንኩ ልሁን ብዬ ለጊዜው በቡጢ በሰልኩ እንጂ ሳይሆንላቸው ቀረ ። ንዴቱ እስከ አለቀየው ጭምር ደርሶ ነበርና አያነበብኩ ተረጎምኩላቸው ። ነጻነት ለዘለዓለም ይኑር ይህንንም እግዚአብሔር ይመስገን ። ለአንባቢው እንደያሰለች ይህ ባጭሩ ይብቃና፣ ነገርን ነገር ያመጣዋል አፈርን ድግር ያመጣዋል እንደሚሉት ምሳሌ ከነዚሁ ልጆች ጥልቅ የሆነ ብዙ የተቃጠለ መንፈስ የሀገር ፍቅርና ቅናት በተመለከትኩ ጊዜ እንዲሁም ከአንድ ትንሽ ልጅ መልካምና እውነት የሆነ የተፈጸመ ሥራ በብዙ ቋንቋ የታተመ ታሪክ ለክቡራን ብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ጽፌ ልልክላችሁ አሳሰበኝ ።

ትንሽ ልጅ አገሩን ወዳጅ

አንድ ዘዋሪ መርከብ ከአንድ አገር ተነስቶ ወደ ሌላ አገር ሲጓዝ በዚያው መርከብ የብዙ ልዩ ልዩ አገር ሰዎች ነበሩ ። ከነዚያ ውስጥ አንድ የ፲፩ ዓመት ልጅም መጥፎ ጨርቅ የለበሰ እንደ አንድ እንስሳ ገዳም ሁል ጊዜ ብቻውን ነበር ። ሁሉም በመጥፎ ዓይን ያዩት ነበር ። በመጥፎ ዓይን ሊያዩት እውነታቸው ነው ። ከሁለት ዓመት በፊት እናቱና አባቱ ገበሬዎች ለአንድ ሰው ገባያ ለገባያ እየዞረ ጨዋታ ለሚያሳይ የማኅበር አለቃ ሸጡት ። ጌታው ብዙ ልዩ ልዩ ዓይነት ጨዋታ (መዝለል መውጣት ቡጢ እርግጫ የመሰለ) ና፣ ራብ መቻል ከስተማረው ወዲያ በብዙ ራብና ኩርኩም አገር ላገር ሲያዞረው በአንድ ፖርቶ (መርከብ የሚቆምበት ስፍራ) ሲደርስ መከራው እጅግ በዝቶ ብትሩንና ራቡን መቻል አቅቶት ከዚያ ከጨከኝ ጌታው ሸሽቶ የሚረዳው እንደሆን ሊጠይቀው ወደ ቆንስሉ ሄደ ።

ቆንስሉም ወዲያው ወደ ከተማ ዘበኛ አለቃ (ከንቲባ) ወደነዚያ እንደ እንስሳ የሸጡት ዘመዶቹ እንዲልከው ወረቀት ጽፎ ሰጥቶት በቶሎ በዚያው መርከብ አሳፈረው ምስኪኑ ልጅ በሽተኛና ጨርቃማ ነበር ። በሁለተኛ መዓርግ አንድ ክፍል ሰጥተውት ሁሉ ቢያዩት ጥቂቶችም ቢጠያይቁት የሚጠሉትና የሚንቁት መስሎት ምንም አይመልስላቸውም ነበር፤ ደጋግ

መው እየጠያየቁና እየመታቱ ዕረፍት በማስጣታቸውም አሳዘኑትና አስቈጡት ፡ እንደምንም ብለው ከነዚያ ፫መንገደኞች ሊያነጋግሩት ቻሉ ። እሱም ባልጠራ (በተደበላለቀ)ቋንቋ ታሪኩን አወራላቸው እንያ መንገደኞች ያገሩ ሰዎች እንኳ ባይሆኑ ትንሽ በርህራሄ ትንሽም በመጠጥ ሞቅ ብሎዋቸው ነበረና ፡ ነገሩ ገባቸው ። ሌላ ነገር ሊያወራላቸውም እያቧላለቱ እየኰራኰሩ ገንዘብ ስጡት በዚያ አደራሽ ሌሎች ሰዎች ቢገቡ ደግሞ ለነሱ ለማሰዬት እንደገና ገንዘቡን በጠረጴዛው እያንጨጨ ይህንንም ውሰድ ይህንንን ውሰድ እያሉ ጨመሩለት ፡ ልጁም በትህትና ቃል ያስነብትልኝ እያለ እየተቀበለ ወደኪሱ ከትቶ ከዚያው ርጉ ፊቱና ተወደጅ ፍግግታው ወደ ጓሮው (እልፍኝ)ወጥቶ መጋረጃውን ገረድ አድርጎ ፡ እየተከዘ ሁነታውን ሁሉ በርጋታ ሊያስተነትንና ሊያስብ ጀመረ በነዚያ ሁለት ዓመት በሰበሰባቸው ገንዘቦችመልካም እንጀራ ገዝቶ ሊበላና ወደ ከተማውም ሲደርስ ሁለት ዓመት ሙሉ ለብሶት የሚኖረውን ጨርቅ ጥሎ አንድ ኮት ሊገዛበት ። ወይ ደግሞ ወደነዚያ አባቱና እናቱ ብዶ እጁን ከመግባት ፡ ትንሽ በርህራሄ እንኳ ቢቀበሉት ይዘላቸው ሊገባ በቻለ ። ለሱ እንያ ገንዘቦች ትንሽ ዕድል ነበሩ። ደስ ብሎት ይህነን እያሰበ ከጓረው በመጋረጀው ውስጥ ተቀምጦ ሳለ ፡ ሰስቱ መንገደኞች ደግሞ በሁለተኛው መዓርግ በሚበላበት አደራሽ በደረጃው መኻከል ተቀምጠው እየጠጡ የመዘራቸውንና ያዩትን አገር ሁሉ ያወጉ ጀመር ። ከንግግር ንግግር የተነሳ ወደዚያን ምስኪን ልጅ አገር ደረሱና ። አንዱ የሆቴላቸውን ሌላው የባቡር መንገዳቸውን አመረሩ ኋላ ሁሉን ፡ነድነት ሁነው በብዙ መጥፎነታቸው ንግግሩን አፋፉሙት አንዱ ከዚያ ይልቅ ወደ ፖሎሱድ (ዘለዓለም በረዶው የማይቀልጥ አገር)መዛወር መረጠ ። ግን ንግግሩን ሳይጨርስ ገንዘቡን እንደ አውሎ ነፋስ በፊታቸው እየወረወረ ፡ በጠረጴዛውና በምድር ቤቱ ሁሉ እየተንከባላለ ብሩን በፊታቸው በተነላቸው ሁሉም በብዙ ቍጣ ተነስተው ወደ ላይ ቢመለከቱ እንደገና ደግሞ ገንዘቡን እየጨበጠ በፊታቸው ረጨባቸው ። ከብዙ ንዴት መጋረጃውን ቀላ አድርጎ በደጅ አፉ ቁሞ በንቀት ቃል ብራችሁን ውሰዱት ። እኔ አገሬን ከሚሰድብ የልመና ገንዘብ አልቀበልም ። አልፈልገውም አላቸው ።

ተ ሚ ።

የአዳኞች መከራ በኢታንግ አውራጃ ።

በዚህ ዓለም ሰዎች ሥራቸውና መኖሪያቸው ልዩ ልዩ ሳለ ሐሳባቸው በብዙ ነገር ሲጋጠም ለተመለከተው ሰው በጣም ያስገርማል።አንዳንዶች ሰዎች በያሉበት ሆነው መልካምን ነገር ለማድረግና ሰውን ለመርዳት ሲያስቡ ይታያሉ አንዳንዶችም ፈጽመው ሲረዱና ሲያደርጉ ይገኛሉ ። አንዳንዶችም በየሄዱበት አገር ሁሉ ያዩትንና የሰሙትን ነገር እየጻፉ የሰውን አእምሮ ለማንቃት ያመለክታሉ ። አንዳንዶችም የሰሙትንና ያዩትን አእምሮ የሚያነቃውን ነገር ከሌሎች ሊከፈሉት አይወዱም የቀናትም ከቶ አያስቡትም ። በያገሩም ያዩትንና የሰሙትን እርግጠኛ ነገር እየጻፉ ለሚያሰሙ ሰዎች ምስጋና አላቸው ።

ማነው አዲስ አበባ ሆኖ የወለጋን የከፋን የወላሞን የጎፋን የማጅን የቦረናን የሲዳሞን የሐረርን አኳኋን ለመስማት የማይወድ ። ወይስ ማነው በነዚህ አገሮች ሁኖ የሸዋን የጐጃምን የትግሬን የወሎን አኳኋን ለመስማት የማይናፍቅ ። ይህን ለመስማት የማይወድ ሰው ቢኖር ኢትዮጵያዊ አይባልም ።

በብርሃንና ሰላም በ፳፩ኛው ቁጥር ፪፻፸፫ኛው ገጽ አንድ የብርሃንና ሰላም ተላላኪ "ስለ ወለጋ ወረዳ አኳኋን" ሲጽፍ እንዲህ ይላል "የክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ግዛት መልካም ነው ። ነገር ግን በዚያ አገር ያየሁት ሁለት ነገር ያሳዝነኛል ፩ኛ በዚያ አገር ዝሆን ወይም ጎሽ ገድሎ መጨፈር እንደ ትልቅ ማዕርግ ይቆጠራልና በዚህ የተነሣ በያመቱ በረሃ እየወረዱ የሚያልቁ ሰዎች ብዙ ናቸው" ብሎ ነገሩን ያሳጥራል ነገር ግን በምን ምክንያት ይሆን ብዙ ሰዎች የሚያልቁት ብሎ ለሚመራመር ሰው ምክንያቱን መግለጥ የተገባ ነውና ነገርህን መግቢያ በማድረጌ እንዳትቀየም እለምንሃለሁ ።

ለዝሆንና ለጎሽ አደን ብለው ወደበረሃ የሚወርዱትን ሰዎች ፫ት ዓይነት መከራ አለባቸው ። የዚህ አገር አዳኝ እንደ ሌላው አገር አዳኝ ለሰውነቱ አይጠነቀቅም ። እነዚህም ፫መከራዎች ራብ ፡ ንዳድ ፡ ሽንቅላ አዳኙ ወደበረሃ ሲወርድ የሚይዘው ስንቅ ላንድ ሳምንት አይበቃውም ። ጥቂትም በርበሬና ጨው የያዘ እንደሆነ እበረሃው ሲደርስ ሽንቅላ ይጨርስበታል ፡ ምክንያቱም እንዲህ ነው ከበረሃው ሲደርስ ሂዶ ከሽንቅላው ቆሮደጅ ይሰፍራል ። አዳኝና የሚያድንበት መሳሪያ ለማግኘት ይስማማል ገና ተስማምቶ አደን ሳይጀምር ይዘት የወረደው በርበሬና በሶ በሽንቅላ ቅምሻ ያልቃል ። እነዚህም ሽንቅሎች ክፋታቸውና ተንኮላቸው በጣም የበዛ ነው የብልጠትም መንገድ አላቸው በመጀመሪ አንዱ ሽንቅላ ይመጣና ዘመድ እንሁን አደን እረዳችኋለሁ በማለት የተቀመመች በርበሬና በሶ ይቀምሳል እንደገና አንዱን ሂዶ ይዞ ይመጣና የንጉሥ ዘር ነው ከኔ እሱ ይበረታል ለርሱም የወዳጅነት ሥራ ሥሩለት እያለ ሲለፈልፍ ይቆነጥሩለታል ፡ ሽንቅላ ጣፋጭ ነገር ሲያይ ጥንብ እንዳየ አሞራ ነውና አንዱ ካንዱ በኋላ እየመጣ ያዳኙን ትንሽ ስንቅ ሙልጭ ያደርጋታል አንዳንዱም ሞገደኛ አልሰጥም ብሎ ያንገራገረ እንደሆን ንፉግ ነው ተብሎ ያሳድሙና በስድብም በማስፈራራትም እንደውሻ ያደርጉታል ። ግን ስንቁን ከጨረሰ በኋላ ራብ ሲጠናበት ቦቤ የሚባል እህል ማሽላ የሚመስል ይገኛልና ያ ተወግጦ ካሣ ጋራ ተገንፍቶ ይበላል አዳኙም ገንዘብ እንዳለው ያንኑ እየገዛ ይበላል ያውም የሚገዛው በውድ ነው ። እንዲህ ያለው ያልተለመደው መብል ለሆድ አልስማማ እያለ አደኑ ቦታ ሳይደርስ ታሞ በተቅማጥ የሚሞት አለ ፡ ከቆሮውም ተስማምቶ የሚአድንበትንና አዳኙን ይዞ ከሄደ በኋላ ሽንቅላው እንደለመሆን ነው ። እንጂ ልቀደም ልቆይ ማለት የለም ፡ ጥቂትም ከቃሉ ዝንፍ ካሉ ተቆጥቶ ወደ ሰፈር መመለስ ነው ፤ አውሬም ሲገኝ ሽንቅላው አስቀድሞ ይመታል እንጅ አዳኝ መተኰስ የለበትም ፤ ምክንያቱም እንዲህ ነው ፤ አዳኝ ከሽንቅላ ጋራ ሂዶ አንድ ጐሽ የሞተ እንደሆነ ያ ሽንቅላ የሚያገኘው ኪራይ ፮ ብር አዳኙ የለበሰውን ሱሪ ሸማ እጀጠባብ በወገቡ ያለቺው

ን ሁሉ ገፎ የጐሽ ጭንቅላትና ማርጣ አሸክሞ ወደ ሰፈር መመ
ለስ ነው ። ይህ እንደይቀርበት ሲል ከደጋ የወረደውን አዳኝ
ይስታል በማለት ይጠራጠርና ሽንቅላ በመጀመሯ እንደ ልምዱ
ብንድ ጥይትም ቢጥል አዳኝ ማርጣን ወስዶ ያለውን መገፈፍ
ነው ፣ እንደንዱም ሕሊናው ወቅሶት አንተ ገለህ አልፈልግም
ያለው እንደሁ ስድብም ዱላም ተቀብሎ እሰፈር ሲደርስ ወደ
ሌላ ያባርሩታል ። እሽም ያለ ይዞ አገሩ ሲገባ የብርሃንና ሰላም
ተላላኪ እንዳየውና እንዳዘነበት ይጨፍሩበታል ።

ሁለተኛው በዚህ መከራ ፣ በረሃ ውስጥ የሚያድኑ ሰዎች
በሚጠጡት ውኃና በማያድሩበት በታ አለመጠንቀቅ ወባ ትይ
ዛቸዋለች ሳያድኑም የሚሞቱት አሉ ። እቤታቸውም ከገቡ
የሚሞቱት ብዙ ናቸው ከሞትም የዳኑት ወባዋን የሚቃወም
ትክክለኛ መድኃኒት ከኃኪሞች መቀበል ስላልወደዱ ወይም
ስለ አላወቁ ኩኪ መጅ የተባለውን የወባ ጠንቅ በጣፊያቸው
ተሸክመው ስንኩሎች ሆነው ይቀራሉ ። በመጨረሻው አስጊ
ዜያታቸው ይሞታሉ ።

፫ኛው መከራ በጣም ያልተለመደ እንግዳ ነገር ነው
አሁን በቅርቡ በመጋቢት ወር ፲፱ የሚሆን አዳኝ ሳይወርድ
አልቀረም ከነዚህም ምን ያህሉ እንደ ተመለሰ ልኩን ለመጻፍ
ችግር ነው ።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።

ይድረስ ከክቡር ወዳጄ ከከንቲባ ገብሩ

በ፴፫ኛው ቁጥር ነሐሴ ፲፯ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም በታተመው
ጋዜታ ላይ የጻፉልኝን የምክር ቃል አየሁት ፤ ለዚሁም የም
ሰጥዎት መልስ ቀጥሎ ያለው ነው ። በከተማ ውስጥ በቀድሞ
ጊዜና በሁኑ ጊዜ ያለውን የስርቆት ነገር የዘበኝነት ሥራ አስ
ተዳደር በመዝገቡ ላይ አይቶ ያመዛዝነዋል ፤ ስለዚህ ከብዙ
ዓመት በፊት የቀድሞው ስርቆት ብዛት በነበረ ጊዜ የሚያዙት
ሌቦች እጅግ ያነሱ ነበሩ ። ባሁኑ ጊዜ ግን የሚያዙትና በእስ
ራት ቤት ያሉት ሌቦች ተጠራቅመው ከዘብጥያ ውስጥ ታስረው
ያሉት በዝተዋልና በዚህ ምክንያት የስርቆት ነገር እያደር ከማ
ነሱ በቀር በዝቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

እኔ ግን በእውነት እነግረዎታለሁ አሁን በጻፉት ጋዜታ
ላይ በከተማ ውስጥ ወስላታ በዛ ብለው የጻፉትን ቃል የዘበኝነት
ሥራ አስተዳደር የማይመስል አድርጎ ፈጽሞ ይቃወመዋል ።

ለዚሁም ምስክር በጣም በሚበዛ የከተማው ሰው ሲሆን
ይችላልና ማለት በገበያም ውስጥ ቀድሞ ይደረግ የነበረውን
የስርቆት ነገር ማንም እንደሚያውቀው አሁንም ደግሞ በጣም
አልፎ አልፎ ያውም አንዳንድ ጊዜ ከገባያው ውጪ የተደረገ
የስርቆት ነገር ይሰማ እንደሆነ እንጂ በተቀረ ያለጥርጥር ሁሉም
በሰላም ይኖራል ። እኔ እንደማስበው ግን የዘበኝነትን ያጠባበቅ
ሥራ ምስጋና ያጠፋ ሰው በከተማ ውስጥ ያለ አይመስለኝም ።

በሌላውም ስፍራ ደግሞ በከተማ ውስጥ የሌብነት ሥራ
በጣም መጉደሉንና እያደርም መሻሻሉን በየክፍሉ ያለው ነዋሪ
ሕዝብ በግልጽ እያወራ ምሥጋናውን ሲያቀርብልን እንሰማ
ለን ይልቁንም ደግሞ ከዚህ ቀደም የዘበኝነት ጥበቃ ሥራ
በትጋትና በሚገባ ስለተደረገ እንዲሁም ወስላቶችን እንዳይቀ
ናቸው አድርጎ የዘበኝነት ሥራ አስተዳደር ነቅቶ ስለ ጠበቃ
ቸው ብርሃንና ሰላም ባያሌ ቁጥር በታተመው ጋዜታው አረ
ጋግጦ አመስግኖታል ። ስለዚህ ይህን አሁን እርስዎ የወረወሩ
ትን የወስላቶች ወሬ የእውነትን መሠረት የያዘ አድርገን አል
ቆጠርነውምና ይነከናል ብለን ምንም ቢሆን ልንሰጋበትና ልና
ፍርበትም አንችልም ። ዳሩ ግን ለወደፊት ለሥራችን የሚያተጋ
ጉዳይና ምክር አስበው የጻፉልን ጊዜ ተራቅቀውና በሚገባ አስ
ተውለው እውነተኛውን የሥራ ጉድለት ይጻፉልን እንጂ የደ
ግነት ምክርዎንስ በደስታ ተቀብለን እስከተቻለን ድረስ ሥራች
ንን ለማቃናት በርግጥ የምንጥርበት እንሆናለን ።

ክቡር ወዳጄ ሆይ ፤ ለማንበብ አይሰልቹብኝና ቀጥሎ ደግሞ
ከእርስዎ ዘንድ የማጠራው አንድ ነገር አለ ። በዚሁ በማመል
ከቻዎ ላይ ወደ መጨረሻው የጻፉልኝን ቃል እንዳየሁት ይህ
ያሉት ነገር በውጪ አገርና ወይም በዚሁ አገር የተደረገ
መሆኑን ለይቶ አያስረዳም እንጂ አንድ ነጋዴ ሰው የ፳ሺ ብር
ቡን ሸጠና ገንዘብ እስኪመጣ ድረስ ፊርማ ይዘህ ቆይ ብለው
ሰጥተውት ቆይቶ በሚከፍሉበት ቀን ፊርማቸውን ይዞ ቢሄድ
ተቀብለው አሁን ፮ ሰዓት ደርሷልና ከምሳ በኋላ እንሰጥሃለን
ብለው ገብተው ቀደው ጥለው ገንዘብም የለብን አሉትና ሸፍ
ጠውት ቀሩ ሲሉ ሰማሁ ብሎ ይላል ። እኔ ግን ፈቃድዎ
ቢሆን አሁን ለዚህ ጉዳይ የምጠይቅዎት ሶስት ነገር ብቻ ነው ።
የዳኛ ምርምር መቼም ጫፉን ካገኘ ሥሩን እስኪያገኝ ድረስ
መንገዱን አይለቅምና መጀመሪያ እርስዎ እንደሰሙት ይህ የተ
ደረገው የማታለል ሥራ በርግጥ በዚህ ከተማ ውስጥ የሆነ መ
ሆኑን ለማወቅ ። በዚህ አገር ያልተደረገ መሆኑን ፈጽሜ ስረዳ
ው ግን ከዚህ በታች ያለው ጥያቄ ቃል አያስፈልገኝም ። ይህነንም
መጻፌ እንደጥቅስዎ ቃል በመጀመሯው ላይ ያለውን ሲመለ
ከቱት በወዲያ አገር የተደረገ አስመስሎ ያሳያል ። በመጨረ
ሻው ላይ የተያያዘውን ሲመለከቱት ግን በዚህ አገር ላይ የተ
ደረገ ያስመስላልና ላለአዋቂ ሰው እንዳይመስል እንዲለይ ብዬ
ነው እንጂ በኔ እንኳ በኩል ስመለከተው እጅግም ግራ ገብቶኝ
አይደለም ።

ሁለተኛ ይህ ተደረገ ሲሉ ሰማሁ ያሉት የማታለል ነገር
የተደረገው በዚህ ከተማ ውስጥ እንደሆነ ግን ከኚህ ለርስዎ ከ
ወሩት ሰዎች ውስጥ ይህ ሰወዬ የስልሣ ሺ ብር ቡን መሸጡ
ንና ሸጦም ፊርማ መቀበሉን ያዩና ያስረገጡ ሰዎች እንዳሉ
ነገሩንና ስፍራውን ሊመሩኝ እንዲችሉ ቢያደርጓቸው ስል እ
ጠይቅዎታለሁ ፤ ሶስተኛም ብሩን በሚቀበልበት ጊዜ ባለ ቡኑ ሰው
ዬ እገጋሮዎቹ ቤት ሄዶ ገንዘቤን ስጡኝ ሲላቸው በምሳ አመካ
ኝተው ገብተው ፊርማውን ሲቀዱ ያየውን ሰው በወገንም እ
ንደሰሙት ቃል እንዲገልጹልኝ ነው ዳሩ ግን በኔ ወገን ሳስበ
ው ይኸ ነገር በጣም ይገርመኛል ይህ ሰውዬ በንደዚህ ያለ ሥ
ራ የተታለለው በየትም አገር የሆነ ቢሆን እንዴት ያለ ጭራ
ሽ ሞኝ ሰው ነው ።

ማለት ይህን ያህል ገንዘብ በዛሬው ዘመን ሰው ላይ ጥሎ
ገንዘቡን ሳይቀበል ፊርማውን እጅ የሚያገባ ?

በውነት ይኸ ሰው በዚህ ዓይነት የስህተት መንገድ ተታሎ ገንዘቡን ካጣ ብቻ ዳኛ በቸርነቱ እስከሚቻለው ድረስ ይመረምርለታል እንጂ ሰውዬውስ ገንዘቡን ጠልቶ አውቆ እንደጣለ ያለ ነውና አእምሮ በሌላቸው ተርታ ቁጥር ይገባል ፡፡ ይህንንም ጥያቄ ወደርስዎ መልሼ መጻፌ የስልጣው ሺ ገንዘብ ጌታ በገዛ ስህተቱ ተታሎ ገንዘቡን ስላጣ በኔ ዳኝነት በኩል መጥቶ እስካሁን ድረስ ያልጮኸልኝና ወሬውንም ያልነገረኝ ስለሆነ ስለዚህ ከሰማሁበት ስፍራ ክርስዎ ወገን የነገሩን ሁኔታ አጣርቼ የተቻለኝን ያህል እንድመረምርለት ብዬ ነውና መልሼ በማስቸገሬ አይፍረዱብኝ ስል እለምንዎታለሁ ፡፡

ከንቲባ ነሲቡ ዛማኤል ።

ስለ መስቀል በዓል አከባበር ።

መስከረም ፲፯ ቀን የመስቀል በዓል ዋዜማ ነበረና በዚሁ ቀን የአዲስ አበባ ሰው ሁሉ የመስቀልን በዓል ለማክበር ከጧት ጀምሮ የመስቀሉን አበባ እያሰናዳ በደስታ አጊጦ ይጠባበቅ ነበር ። ከስድስት ሰዓት በኋላም ሕዝቡ ሁሉ በዓሉን ስለ ማክበር ሰልፍ ወደሚደረግበት ቦታ ይጓዝ ጀመር ።

ስፍራውም እቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ድንጋይ በተነጠፈበትና አምሮ በተሰናዳው ሥፍራ ላይ ነበረ ፡፡ በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ጥግ ውብ የሆነ አዳራሽ ድንኳን ተተክሎ በውስጡ ልዩ ልዩ ዓይነት የሆነ ያማረ ያማረ ምንጣፍ ተነጥፎበት ነበር ፡፡ በድንኳኑ በር ግራና ቀኝ ሰንደቅ ዓላማ ይውለበለብ ነበር ፡ ደመራውም እሜዳው መከከል ተተክሎ በወርቅ መጐናጸፊያ ተጐናጽፎ ፰ ሰዓት ሲሆን ብጹዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ መጡ ። ወዲያውም የየአድባራቱ ካህናትና ሊቃውንት የመዓርግ ልብሳቸውን እየለበሱ ቀሳውስቱና ዲያቆናቱም መስቀልና ጥና እየያዙ መጥተው በደመራው አንጨት አጠገብ ቆሙ ።

ስምንት ሰዓት ተኩል ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን መጡና ከድንኳኑ ውስጥ አምሮ በተሰናዳው ክፍ ባለ ቦታ ተቀመጡ ። በቀኝ በኩል የውጭ አገር መኳንንቶች በየመዓርጋቸው ተቀመጡ ። በግራ በኩል ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስና የኢትዮጵያ መኳንንት ተቀምጠው ነበር ።

ከዚህ በኋላ ደመራውን ከበው የቆሙ የየደብሩ ካህናት የሚገባውን ሥርዓት አድርሰው ወንጌል ተነበበ ቀጥለው ፴፪ኪ ግዚአታ አድርሰው ደመራውን ፫ጊዜ ዞረው ገለል ሲሉ ልዑል አልጋ ወራሽ ከነመኳንንቶቻቸው ፫ጊዜ ዞሩና ተመልሰው ከነበሩበት ቦታ ተቀመጡ ። ይህ ሁሉ ሲደረግ ፎቶግራፍ አንሺዎች ቶሎ ቶሎ ለማንሳት ይጣደፉ ነበር ።

ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን የንጉሥ ሠራዊት ተሰልፎ የመስቀል አበባ የተጐነጐነበት የደመራ እንጨት ይዞ እዮሀ እያለ የያዘውን እንጨትም እድምሩ ላይ እየጣለ ሰልፉን እያሳየ በየተራውና በየደምቡ አለፈ ።

ቀጥሎ የከተማ ዘበኞች ግራዝማች ማህሌ ባማረ ፈረስ ተቀምጠው እየመሩዋቸው ሙዚቃ እየተነፋ ሰልፉን ማሳየት ጀመረ ዘበኛው ሰልፉን አሳይቶ እስቲጨርስም ሙዚቀኞቹ እሜዳው መከከል ሁነው ሙዚቃ ይመቱ ነበር ፡፡ በመጨረሻም ክቡር ከንቲባ ነሲቡና ክቡር ነጋድራስ አስታጥቄ እንደ ኤውሮጳ መኳንንቶች አለባበስ የሰልፍ ልብስ ለብሰው የመዘጋ ቤት ጸሐፊዎችን አስከትለው በሥርዓት ሰልፋቸውን አሳይተው በልዑል ፊት ሰላምታቸውን ሰጥተው ባለፉ ጊዜ እጅግ ያስ አሰኙ ይልቁንም ክቡር ከንቲባ ነሲቡ የኢትዮጵያን ልጆች ሙዚቃ ተምረው ራሳቸውን ችለው ሙዚቃ በስርዓት እንዲነፉ ማድረጋቸው እጅግ መልካም ነው ።

ከዘበኛው በኋላ ብዙ ሠራዊት ሰልፉን እያሳየ አለፈ ። በዚሁ መከከል የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በስርዓት ለብሰው ሰንደቅ ሰንደቅ አላማቸውን ይዘው እየዘመሩ አምረው ታዩ ። ከዚህ በኋላም በየተራው ብዙ ሠራዊት አለፈና ቀጥሎ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሠራዊት በየደምቡ ሰልፉን እያሳየ አለፈ ። በመጨረሻውም በስርዓት የሰልፍ ትምርት የተማረ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሠራዊት ሰማያዊ ኮት የለበሰ መትረየስ አንጋች ፈረስ ዘበኛ መርቶት እሜዳው በገባ ጊዜ መዚቃው ሲነፋና ሠራዊቱ እሜዳው ገብቶ እየተደራረበ ተሰልፎ ሜዳውን ባስጨነቀው ጊዜ ላይታው አስደነቀ ። እሜዳው ተገርግሮ ቁሞ መዚቃ እየተነፋ በክቡር ግራዝማች ገብረ ዮሐንስ ትእዛዝ ሰላምታ በሰጠ ጊዜም የተሰበሰበው ሰው ሁሉ የደስታውን ምልክት ለማሳየት ጭብጨባውን አቀለጠው ።

ልክ ፲፩ ሰዓት ሲሆን ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ተነሡና በወርቅ እቃ በተንቆጠቈጡ በቅሎ ተቀምጠው በክቡራን መኳንንቶቻቸው ታጅበው ወደ ቤተ መንግሥቱ ገቡ ።

ብርሃንና ሰላም ብርሃን መስቀሉን በደኅና ለማሳየት ያበቃንን አምላክ እያመሰገነ ፡ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ለኢትዮጵያ መኳንንትና ሠራዊት ለሕዝቡም ሁሉ ነዋሪ ደስታና ሰላም እየተመኘ እንኳን ብርሃን መስቀሉን ያሳያችሁ ይላል ።

የውጭ ወሬ ።

ጀኖባ (ኢጣልያ)፡፡ ከመንደቶረ ኡምብርቶ ፓጂ የሚባል የከፒተንፏሌቴ ጻሐፌ ትእዛዝ የነበረ ሰው ተይዞዋል ።

ፓሪስ

የሬፒብሊክ መንግሥት ማኅበር ድግስን ደግሰሁበት ሚለራንድ የረፒብልኩ ፕሬዚዳን የነበረ ሲናገር የሶቪት መንግሥት እፓሪስ ባለ አምባሳደር በኩል የኮሙኒስቲ ትልቅ አድመኝነትን እንስቶዋልና ከሶቤት መንግሥት ጋራ ያለው የዲፕሎማቲክ ተግባር ማፍረስ ያስገድዳል ብሎዋል ።

ኒስ

ኢዛዶራ ዱንካን የምትባል የታወቀች ዘፋኝ መስከባዊት ሴት በኦቶመቢል ስትዛወር ሳለች ያአውቶመቢሉ ኋለኛው እግር ስለተነጠለ ታንቃ ቀረች ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ፡፡

COGNAC S. & E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ፡፡

AutOmObileSCHEVROLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቀቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጿ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓኒያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፥ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መኳላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ በለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ እመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፈታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሂስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፤ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ማጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክስሙ ጉድየር ይባላል፡ ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደ ጣሞ በልክ ይሄዳል። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆ ን አያስፈራም እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስ ቲክ ሁሉ ጠንካራነው በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድየር ግዙ ከሌላው ላስ ቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩ ል ነው ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘ ው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

ኤን ቤ ኤዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቱና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቱና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ኩባ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፣ ቁጥር ፵
3 me ANNÉE № 40

ሐሙስ መስከረም ፳፭ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 5 OCTOBRE 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ማስታወቂያ

የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ሶስት ወር ያህል ስለ ዕረፍት ተዘግቶ ነበር ። አሁን የትምህርት መጀመርና የትምህርት ቤቱን መክፈት ጊዜው ደርሷልና ስለዚህ በጥቅምት አንድ ቀን ትምህርት ቤቱ ተከፍቶ ትምህርት መጀመሩን ለሚማሩ ልጆችና ልጆቻቸው እንዲማሩላቸው ለሚፈልጉ ወላጆች እናስታውቃቸዋለን ።

የትምህርት ቤቱ ሹም ሐኪም ወርቅነህ ።

የብዙኃን ማርያም በዓል አከባበር ።

መስከረም ፳፩ ቀን የብዙኃን ማርያምን በዓል ለማክበር ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በክቡራን መኳንንቶቻቸውና በሠራዊቶቻቸው ታጅበው በጥዋት ወደ እንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ወጡ ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽ በደረሱ ጊዜም ቅዳሴ ገቡ ቅዳሴ ሲፈጸም ርእሰ ደብር ዘለቀ የተባሉ ካህን የሚከተለውን ቅኔ ተቀኙ ።

ክብር ይእቲ ።

ይሁዳ ነዳይ ተየውሀ ድኅረ ማዕደ ገፍዓ ፡
አምጣነ የዓርር ወርቀ ዘኢይከውኖ መብልዓ
ወኅየለ ይንሣእ ሥርዓተ ጸሎት ርቱዓ
ማዕከለ አይሁድ ፍናው እስመ ይጼሊ መልክዓ ክርስቶስ ኀቡዓ

ዕጣነ ሞገር

ሊቀ ደብረ ድኅግል ሰይፍ
እንዘ ትሠውዕ መሥዋዕተ
በአብዝኖ ልሳን ኢታኅዝን ካህናተ
ቶማስ ንብረትከ ለእመ ገበርከ ዘንተ
ኢረከበ በረከተ
ወእንዘ በልሳን ይቀስፍ ኵለሄ
ወለተ ቃለ አብ ትስብእተ
ሠናየ ንብረቶ ንስጥሮስ ነሥተ

ዓሥረ ንጉሥ

ምኒልክ ኄር ይምርሐነ ባሕርየ ፈጣሬ ፍኖተ
ለኃይለ ሥላሴ አዳም ፈጠሮ እምኅበ ነሥአ መሬተ
ወአስተሰነአወ ፍጥረታተ
ወኃይለ ሥላሴ ኢይበእ ዕራቆ ገነተ
እምኔሁ አነመ ንግሥተ

ቅኔውን ካመለጡ በኋላ ታቦቱ ወጣና ዑደት ተደረገ ዑደቱ በተፈጸመ ጊዜም ታቦቱ ቁሞ ልዑል የኢ. መ አ ወራሽና ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እከፍተኛ ቦታ ተቀምጠው ካህናቱና ሊቃውንቱ እመስኩ ሁነው ወአንቲኒ ታቦት እምኃበኒ መጻእኪ ወኅበኒ ተሐውሪ መድኃኒተ ኩኒ ለምኒልክ ንጉሠ ነገሥት እያሉ ሲወርቡ እጅግ ደስ ያሰኙ ነበር ።

ካህናቱና ሊቃውንቱ አስረግጠው በጨረሱ ጊዜ ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሕዝቡን መክረው አስተምረው አሳርገው ባርከው አሰናበቱት ። ከዚህ በኋላ መድፉ እየተተኰሰ ታቦቱ ገባ ፣ ትንሽ ቈይተው ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ከቤተ ክርስቲያኑ ወጡና ባማረ ዓጀብ ሁነው ወደ ከተማ ለመመለስ ጕዞ ተጀመረ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትንና ልዑል አልጋ ወራሽን አጅበ የሚሔደው መኳንንትና ሠራዊትም በሥርዓት ተሰልፎ ለምለም ሣርና የመስቀል አበባ የተሸለመውን ተራራ እየተጠመጠመ ሲወርድ በእንጦጦ ተራራ እግርጌ ሆኖ ለሚመለከት ሰው እጅግ ድንቅ ሁኖ ይታይ ነበር ።

ክቡር ግራዝማች ማህሉ የከተማ ዘበኞች ጠቅላይ አለቃም የከተማውን ዘበኞች አሰልፈው በመንገድ ቈዩና ሰልፋቸውን አሳምረው አሳዩ። ሙዚቃው እየተነፋ አጀቡ እንዳማረ እልፁል አልጋ ወራሽ ግቢ ገቡ ፫ልፁል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ግቢም በሰ ደቅ ዓላማና በአበባ ተጊጦ ነበረ ።

ሐዲስ ሐሳብ በኢትዮጵያ ።

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከስንፍና ንቅቶ ሓሳቡ ወደ እውቀት መመልከት መጀመሩ በእርግጥ ነው ። ግን ብዙ ሰው በብዙ ነገር ሲሳሳት ይታያል ፡ አሁን ብዙ ሰዎች የሚያስቡት ሐሳብና የሚናገሩት ነገር ከብዙ ሰዎች ስንሰማ የሚገርም ነገር ነው ፡ መንግሥት የንግድ ፋብሪካ አቁሞ የእርሻ ስራ ሰርቶ ወይም ሆቴል ወይም እነዚህን የመሰሉ ስራ አቁሞ ሰርቶ በዚያ እንዲጠቀም ሲመኙ እናያለን እንሰማለን ይኸም ሐሳብ የሚነሣው እንደቀድሞው የኢትዮጵያ ሕዝብ የዋህና ገር መሆንትተው ከመልካሙም ትምህርትና እውቀት ሳይደርሱ አንጉልብልጥ ከሆኑ ሰዎች ነው ፡ አሁን ሽማኔ እንኳ ሐዲስ ጥበብ ልብስ ሲሰራ የአንዱን ልብስ አይቶ በዚያ መዝገብ ይሰራል ፡ ስለዚህ እኛም ለመንግሥታችን የምንመኘው ምኞት ሌሎቹ የዓለም መንግሥታት የሚሰሩትን ስራ መንግሥታችን እንዲሰራ ብለን መመኘት ይገባናል እንጂ መንግሥት የአንድ ነጋዴ ስራ ሰርቶ ጥቅም እንዲያገኝ ብለን መመኘት ድንቁርና መሆኑን ብንረዳው ይሻላል ። እንደዚህ ያለው የ፩ ኩፓኒያ ስራ ወይም የ፩ ነጋዴ ስራ የሆነ ስራ መንግሥት ሰርቶ የሚጠቅምበትና የሚጠቅም ቢሆን ምነው ብዙ ትልልቆች መንግሥታት በዚህ ስራ የሰለጠነና ብዙ ሰራተኛ ያላቸው ለምን አይሰሩም ፡ እርግጥ ይኸ ትንንሽ ስራ ለመንግሥት የማይጠቅም መሆኑን ቢረዱት ነው ፡ ይልቁንም መንግሥት ለአገሩ ጥቅም የሚሆነውን ትልልቅ ስራ ሰርቶ ለማስተካከል ብዙ ይቸገራል መንግሥት ሊሰራ የሚገባውን ስራ ሰርተው የሚያስተካክሉ ሰራተኞች የሚያገኝ መንግሥት ብዙ የታደለ አገር ነው ፡ ተዋዲያ ብዙ ገንዘብና ብዙ በስራ የሰለጠኑ ሰራተኞች ያሏቸው መንግሥታት ሰርተው ያልተጠቀሙበትን ስራ እኛ ገና የስራውን ስም ስሙን እንኳን ለይተን ያለወቅን ሰዎች መንግሥታችን እንደዚህ ያለውን ስራ ሰርቶ እንዲጠቀምበት መመኘታችን ለምንድር ነው ፡

በእውነት የኢትዮጵያ አገር እንዲጠቀምና መንግሥታችን እንዲጠቀም ለማሰብ ከተነሣን መንገዱ ሌላ ነው ። የመንግሥት ሀብት የሚያድግና ከፍ የሚል የሕዝቡ ሀብትና ባለጠግነት ሲበዛ ሕዝቡ እውቀትና ባለጠግነት ሲያገኝ ነው ፡ ስለዚህ የመንግሥት ስራና ሐሳብ እርሻ እንዲለማ ንግድ እንዲሰፋ ለባለገሩ ግብርና ለነጋዴ ቀረጥ ደንብ ማውጣት ነው ። ቀጥሎም የትምህርት ቤት እንደሚቻል በየቦታው ማቆም ነው ከዚህም ቀጥሎ ምድር ባቡር ፖስታ ስልክና ቴሌግራም በየማእዘኑ መዘርጋት ነው ፡ ከብት በከንቱ በበሽታ እንዳያልቅ ፭ ፮ የከብት ሐኪሞች አስመጥቶ በየወረዳው ልክ ከብቶችን ማስከተብና ማሳከም ይኸኑ ስራ የሚቻል የሚቻለውን የአገር ልጆች ማስተማር ከብት ሲበዛም ማር ጠፍቶ ከብቱ ችጋረኛ እንደይሆን ከብቶቹ እንዲሸጡ ማድረግ ነው ፡ እንደዚህ ያለው ስራና ይኸን የመሰለ ስራ ሲሰራ ሕዝቡ ለባጠጋ ይሆናል ዛሬ ፲ ብር የሚገብረው ፻ ብር ይገብራል ዛሬ ፲ ብር የሚያስቀርጥ ነጋዴም ያን ጊዜ ፻ ብር ያስቀርጣል መንግሥትም ዛሬ ፲ሺ ብር በሚያገኝበት አገር ፻ሺ ያገኛል የመንግሥት ንግድ ማለት አገር ማልማት ብቻ ነው ። በቀረ ግን በንግድና በእርሻ መንግሥት ሰርቶ የሚያገኘው ጥቅም ከአንድ ሰው ትዳር አይሻልምና ከሁሉ በፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ ይኸን ማወቅ ያስፈልገናል ።

ዘለቀ እውነቱ ፤

ንዴትና ትዕግሥትን መርምሮ የተሻለውን ስለመያዝ

መጀመሪ ሰው በዚህ ዓለም ይፈጠርና እግዚአብሔር እንደከፈለው እኩሌታው በውቀቱ እኩሌታውም በከብቱ መንግሥቱን አገልግሎ እራሱንም ችሎ ለሰውም ተርፎ ይኖራል ። አንዳንዱ ግን እውቀት እያለው እንኳንስ ለሰው ሊተርፍ ለራሱም አጥቶ ይቸገራል ። ምነው እውቀት ሳለው ማጣቱ ? አንዳንዱ ደግሞ ምንም እውቀት ሳይኖረው ለራሱ ጌታ ሆኖ ይኖራል ። ምነው እውቀት ሳይኖረው ማግኘቱ እንግዴህ ምን እንላለን ወይስ እግዚአብሔር ግፍን ያደርጋል ። አይደለም ለሙሴ ብሎታልና የምምረውን እምራለሁ ። ለምራራለትም እራራለሁ ። አሁንም ይህ ለወደደም ለሮጠም አይደለም ። እግዚአብሔር ይቅር ላለው ነው እንጂ ሮሜ ፱ ፲፬ ፲፯። ተመልሼም አየሁ ፡ ከፀሐይ በታች ሩጫ ለፈጣን ። ሰልፍ ለኃያላን ። እንጀራም ለጠቢባን ። ባለጸግነትም ለብልሃተኞች ። ጸጋም ላዋቂዎች ። እንዳልሆነ ጊዜና መገናኘት ግን ሁሉን ያገናኛቸዋል ። መክ ፱ ፲፩ ድኅነትና ባለጸግነት በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ። ሲራክ ፲፩ ፲፯ ከዚህ በቀር ግን ይህ የሚሆንበት ሌላ መንገድ እንዳለው የሚያስረዳኝ ሰው ቢኖር በወደድኩ ያላወቀ አስረዳኝ ማለት መቼም ልማዱ ነውና ።

ሁለተኛ ፡ ደግሞ አንድ ነገር ትዝ ይለኛል ፡ እውቀት ማለት የጅ ጥበብና ሥራ ነውን ወይስ ቋንቋ ብቻ ፡ ለኔ እንደሚመስለኝ የእጅ ጥበብ ሥራ ነው ። እንግዲህ ሙሉ እውቀት ማለት የእጅ ጥበብ ሥራ ከሆነ ካሁን በፊት የሀገራችን የኢትዮጵያ ልጆች አውሮፓ ተሻግረን ተምረን መጣን የሚሉ ብዙዎች ናቸው ። የእጅ ሥራ ተምረው የመጡ በዚያውስ የሠሩበት እነማናቸው ቁጥራቸውስ ስንት ይሆን ከቶ የሀገራችን ልጆች ከቋንቋ በቀር የእጅ ሥራ ተምረው ያለመሥራታቸው ውርደት መስሏቸው ይሆን ፤ ውርደትስ አልነበረም ። እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሲና እንዲህ ብሎታል ተመልከት ፤ እኔ ባስልኤልን በስሙ ጸርቻለሁና የዑሪን ልጅ የሁርን ልጅ ከይሁዳ ወገን የእግዚአብሔርንም መንፈስ መላሁት ጥበብ ለማስተዋልም ለእውቀትም በሥራ ሁሉ ብልሃት እንዲያስብ የወርቁንና የብሩን ሥራ ያደርግ ዘንድ የናሱንም ደንጊያ ቆርጦ ለማስናዳት ለማስገባትም የእንጨቱንም አጠራረብ ሁሉ ለመሥራት ዘፀአ ፴፩ ፪ ፫ ፴፰ ፴ ፴፫። ሁራም የጢሮስ ንጉሥ ለሰሎሞን እንዲህ ሲል ላከለት ፤ እነሆ አስተዋይና እጅግ አዋቂ ሰው

ሁራም አቢ የሚሉትን ሰደድኩልህ የሴት ልጅ ከደን ልጆች
ወገን አባቱም ከጢሮስ ነው ። ወርቅና ብርም ይሠራ ዘንድ
ያውቃል ናስና ብረትም ድንጋይና እንጨትም ቀይና ሰማያዊ
ሐርም ማለፊያ ጥጥና ወርቀ ዘቦም የሚያሸውንም ሥራ ሁሉ
ይቀርጽ ዘንድ ያውቃል ። ፪ ዜና ፪ ፲፫ ፲፬ ። እነሆ በእግዚአብ
ሔር በንጉሥ ዘንድ እንዲህ መመስገንና ይህን ትልቅ ስም
ማግኘት እንዴት ያለ ታላቅ ክብር ነው ። እንግዲህ እግዚአብ
ሔር ከነገሥታት ወገን ከይሁዳ የሚወለደውን ሰው ይህን ሥራ
ብሎ ሲያዝ ጊዜ የኔ ብጤው ደሀ የእጅ ጥበብ ሥራ መናቁ
ለምን ይሆን ይገርማል ። እንግዲህ ለኢትዮጵያ ልጆች በዓይን
ብቻ የአውሮፓን ሥልጣኔና ጥበብ ዓይቶ መምጣት ጥቅሙ
ምንድነው ትምሕርቱ ሲቻላቸው ተምረው ስለማይሠሩና ስለ
ማያስተምሩ በልብስና በንግግር ብቻ ስለሚራቀቁ ሰዎች ጌታ
በቅዱስ ወንጌሉ እንዲህ ይላቸዋል ። ሥራቸውን ይሠራሉ ።
ለሰው ሊታዩ የቀሚሳቸውን እጅጌ ያሰፋሉ ፤ የልብሳቸውንም
ዘርፍ ያስረዝማሉ ። በምሳም በላይ በላይ መቀመጥ ይወዳሉ ።
በሸንጎም የፊተኛ ወምበር ፤ ገበያ ለገበያም መሳለም ፤ ሰው
መምሕራን (አዋቆች) ይላቸው ዘንድ ማቴ ፳፫ ፭ ፯ ሉቃ ፲፩
፵፫ ። ትምሕርታቸው ለቋንቋ ብቻማ ከሆነ እዚሁ አገራችን
ባሉት ትምህርት ቤቶች ገብተው የተማሩት ወንድሞ
ቻችን ለዛሬ መቼ አነሱ ከነዚሁም ብዙዎቹ በመንግሥት ሥራ
ላይ ሆነው በትጋት ያገለግላሉ ፤ ይልቁንም የሀገራችን ልጆች
በጽሕፈትና በሂሳብ በደብተርም ሥራ በሀገራችን ፊደል በጣም
ሰልጥነዋል ፤ ሥራቸውንም በትክክል ያስኬዳሉ ፤ በዚህ ችግር
የለብንም ችግራችን የእጅ ጥበብና የፋብሪካ ሥራ ነው ፤ ወደ
አውሮፓ ለትምሕርት የሚሄዱት ልጆች ይህን የሚቸግረንን
ሥራ ተምረውልን የማያመጡ ከሆነ መንግሥታችን ብዙ ልጆች
ወደ አውሮፓ መላኩ ብዙም ገንዘብ መክሰሩ ለምኑ ነው ምንስ
ይጠቅመዋል ። ለወደፊቱ ግን የእጅ ጥበብና የፋብሪካ ሥራ
በብዙ ተምረው እንዲመጡልን ተስፋ እናደርጋለን ።

አሁን ይህቺን ቲንሽ ቃል ለመጻፍ ያሳሰበኝ እግዚአብ
ሔር ዋጋቸውን አያስቀርባቸው እንጂ ግርማዊት ንግሥታችንና
ልዑል ጌታችን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ
መኰንን በሀገራቸው ጥበብና እውቀት ፀቆሎ እንዲገባና እንዲ
ሰለጥን ስለ አሰቡ ብዙ የኢትዮጵያ ልጆች እየመረጡ ለትም
ሕርት ወደ አውሮፓ ይልኩሉና እነዚህ ወንድሞቻችን ትምሕ
ርታቸው ቋንቋ ብቻ ሳይሆን የእጅ ጥበብና የፋብሪካ ሥራ
ሁሉ በያይነቱ ተምረው መጥተው በየክፍሉ ሆነው አገራቸውን
እንዲረዱና መንግሥታቸውን እንዲያገለግሉ ለውጭ ሰውም
የምንሰጠውን ገንዘብ እንዲያስቀሩልን ስል በትምሕርት ቤት
ላሉ ወንድሞቼ ለማሳሰብ ነው እንጂ የመቃወም ኃሳብ አይደ
ለም ። ቆሮ ፬ ፲፬ ምናልባት ቅር የሚለውም ሰው ቢኖር ይቅ
ርታ እለምናለሁ ።

እንግዲህ ወደቀደመው ነገሬ ልመለስ ከዕለታት አንድ ቀን
ሐሳብናምኞት በሚባለው መሬት ስወጣ ስወርድ ውዬ ደክሞኝ
ተቀምጬ ሳለ አቶ ስንፍና የሚሉት ሰው መጥቶ እረበል ወን
ድሜ የዚህ ዓለም ነገር እኮ ይገርማል አለኝ ። እንዴምን አል
ኩት ። አቶ ቸርነት ያን ያህል ማስተዋል ያን ያህል እውቀት
ያን ያህል ትጋት ያለው አጥቶ ተቸግሮ ይኖራል አቶ ንፍገት
ግን በዚያ ድንቁርናው በዚያ ትእቢቱ በዚያ ላይ ጌትነት አግ
ኝቶ ይኖራል እያለ ሲያጫውተኝ ሰርክ የማይለዩኝ አቶ ንዴ
ትና አቶ ቍጣ የሚባሉ ሁለቱ ወዳጆቼ አጠገቤ ነበሩና ይኸ
ውልህ አንተ እውቀት ባገኘሁ እያልክ ትለፋለህ እንጂ በጌት
ነት የሚኖሩ እነድንቁርና እነንፍገት እነኩራት ናቸው እያሉ
በብስጭት ቃል ሲያጫውቱኝ እኔም እውነት እያልኩ አብረን
ስንናደድ እንደነሱ በጣም የማልወደው አቶ ትእግሥት የሚ
ባል ደግ ጎረቤት ነበረኝና እሱ በድንገት መጥቶ ምንሆናችሁ
ትናደዳላችሁ ምንስ ያስቆጣችኋል አለን እኔም በቍጣና በንዴት
ቃል (አዋቂ ሣለ ደንቆሮ ቸር ሣለ ነፉግ ይከብራል) እንግ
ዲህ እውቀትስ ደግነትስ ምን ያደርጋል ብለን ነው አልኩት
እሱም ለጊዜው ቆሞ ነበርና ወደኔ ቀርቦ ተቀምጦ እንዲህ አለኝ
ሰማህን ወዳጄ ሰሎሞንና ሲራክ ኢዮብ ያሉትን አልሰማህምን
አለኝ ምን አልኩት ስለ ምድራቱ አመፀኝነት አለቆቹ ብዙ ሆኑ
አስተዋይ ጥበበኛ ቢኖር ግን ዘመኑ ይረዝማል ምሳ ፳፰ ፪ ። በጠ
ማማ መንገድ ከሚሄድ ባለጸጋ በቅንነት የሚሄድ ደሀ ይሻላል
ምሳ ፳፰ ፮ ። ባለጸጋ በይኑ ዘንድ ጠቢብ ነው አዋቂ ደሀ ግን
ይመረምረዋል ምሳ ፳፰ ፲፩ የታመነ ሰው እጅግ ይባረካል ባለ
ጸጋ ለመሆን የሚቸኩል ግን ሣይቀሠፍ አይቀርም ምሳ፳፰ ፳
ሸጢሞ ፮ ፱ ፲ ባለጸጋ ለመሆን የሚቸኩል ሰው በሌላው ይመ
ቀኛል ችጋርም እንዲያገኘው አያውቅም ምሳ፳፰ ፳፪ ። ተግሣጼን
ውሰዱ ብርም አይደለም ከምዝምዝ ወርቅ ይልቅ እውቀትን
ምረጡ ጥበብ ከሉል ትበልጣለችና ያማረ ነገር ሁሉ አይተካ
ከላትም ምሳ፰ ፲ ፲፩ ። ጥበብ ዓይነተኛ ነገር ናትና ጥበብንግዛ በከ
ብትህም ሁሉ ማስተዋልን አትርፍ ምሳ ፬ ፯ ። ለመክበር የሚቸ
ኩል በሥራም የሚደክም ደክሞም ፊጽሞ የሚቸገር አለ ቆሎ
ቆርጥሞ ወህም ጠጥቶ ራሱን በመንፈጉ ብዛት ሌላውንም እየ
ነፈገ የሚከብር ሰው አለ ተድላውንና ደስታውንም በሥሥት
ይፈጽማል በልቶ ጠጥቶ አይደለም ነፍጎ ነው እንጂ ሲራክ
፲፩ ፲፰ ። ቍጡ አመጸኛ ሰው እስኪሞት ድረስ ሃይማኖትና ምግ
ባርን ሰርቶ አይጸድቅም በበተቆጣ ጊዜ ቶሎ ይጠፋልና ሲራክ
፩ ፳፩ የክፉዎች ሰዎች ሰርቀውና ቀምተው መክበራቸው አያስ
ቀናህ በሚሰጥህ በእግዚአሔር እመን እንጂ ። ቍጣና ብስጭት
የተጠሉ ናቸው በክፉ ሰው ዘንድ ግን ተወደው ይኖራሉ ሲራክ
፲፩ ፳፩ ፳፯ ፴ ። ደንቆሮን ሰው ቍጣ ይገለዋል ስንፍንም ቅንዓት
ያጠፋዋል ኢዮብ ፭ ፪ ወዳጄ ሆይ ንዴትና ቍጣ ያጠፋት ሰው
ብዙ ነው አንተንም እንደዚሁ ደግሞ የመከሩህ መስለው ያጠፉ
ሃልና ተጠንቀቅ የነሱም ወዳጅነት ይቅርብህ ብሎ መከረኝ ።
እኔም ከትእግሥት ወዲያ መልካም ነገር እንደሌለ አውቄ
የቍጣንና (የንዴትን) ወዳጅነት ንቄ በትእግሥት ነፍሳችሁን ትገ
ዛላችሁ የሚለውን የወንጌሉን ቃል አስቤ ያቶ ትእግሥትን
ወዳጅነት አጸናሁ ሉቃ፳፩ ፲፱ ። ከዚህ በኋላ አሳብና ምኞት የሚ
ባለው መሬቴ እጅግ አድክሚና አስቸጋሪ ስለ ሆነብኝ ከዚያ
ተመልሼ ሥራ በሚባለው በመልካሙ እርስቴ ተቀምጬ እግ
ዚአብሔርን እያመሰገንሁ ንጉሥን እየመረቅሁ በደሥታ እኖር
ጋርመርሁ ዘፍጥ ፫ ፲፱ ሲራክ ፲፩ ፳ መክ፫ ፲፪ ።

ከቡራን አንባቢዎች ሆይ ከንዴት ትእግሥት ከሐሰት እውነት ከምቀኝነት ገርነት ከድንቁርና እውቀት ከንፍገት ቸርነት ከኩራት ትሁትነት ከስንፍና ትጋት ከጠላትነት ወዳጅነት (ገላትሬ ፭፥፱)መሸሉን የብርሃን ልጆች እንደምታውቁት አምናለሁ የዘነጉ እንዳሉ ለማስታወስ ፪ጴጥ ፩ ፲፱ ። በናንተ በብልሆች መካከል ይህችን ያልተካከለች ትንሽ ቃል ስለጻፍኩ ድፍረት ሳታደርጉብኝ በጉደለ ሞልታችሁ በተሳሳተ አርማችሁ እንድታነቡልኝ ስል ይቅርታችሁን ጭምር እለምናችኋለሁ ። ተስፋዬ ካሣ

ለሁሉ አገባብና ገባያ አለው

፩ኛ ሰው ያወቀውን ጥበብ ደብቆ ጥቅሙን ለራሱ ብቻ ቢያደርግ አልማዙን በጥልቅ ውቅያኖስ እንደ መደበቅ ያለ ነው ይህንን የጻፍኩበት ምክንያት ባገራችን የቆየ ነገር ለመግለጽ ነው ብዙ ሰዎች ብዙህ ዓይነት ጥበብ ለመሥራት የሚችሉ አሉ ነገር ግን ለሕዝብ ሳይገልጹት ልጆቻቸው እንኳ ሳያውቁት ይሞታሉ በዓለም ሁሉ እንደዚህ ጥበባቸውን ቢደብቁ እስካሁን ባቡር አቶሞቢል ኤሮፕላን ባላየን ነበር ተመልከት በነዚህ መኪኖች ሥራው ሁሉ በፍጥነት እንደተከናወነ ደግሞም ጥበብ ቢኖራቸው ባገራችን ስድብ እንደሆነ ልብ እናደርጋለን ይህ ሁሉ የታወቀ ድንቁርና ነው ግድፈት ነው ሸማኔ ብረት ሰሪ የሆነ እንደሁ ጠይብ ይባላል ደብተራ የሆነ እንደሁ ተማሪ ተብሎ ይናቃል ይህም የታወቀ ነው ታላቅ ግድፈት ነው እኔ እንደራሴ እንደሚመስለኝ ማንም ሰው የሚያውቀውን ጥበብ ወይም ያሰበውን አስቀድሞ የገንዘብ እርዳታ ወደ መንግሥት ማመልከትና ሥራውን ጀምሮ ማብዛት መልካም ይመስለኛል

ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ብረት መዳብ ወርቅ ማውጣት የሚችሉ ሰዎች አሉ ነገር ግን ብዙ አያወጡም ለብዙ ንግድ የሚሆን እርዳታ ቢኖራቸውና ብዙህ ሠራተኞች ተከራይተው በብዙህ ቢያወጡ ጥቅሙ ብዙ ነው ክብትም የሚገኘው ክብዛት ነው ልብ አድርግ ይህንን ዓይነት ሥራ ወይም ሌላ ነገር ለመሥራት ብትፈልግ ብዙ ሠራተኛና ገንዘብ እንዲያስፈልግህ በዚያ ላይ ዋጋህ ትርፍ እንዳለው ለብዙህ ሰውም ትርፍ መሆንህን ብዙህ ሰውም ባንተ ውስጥ እንዲበለጥግ አገርም ለም እንዲሆን ።

፪ተኛ ፡ አንባቢ ሆይ አስብ ማናቸውንም በብዙህ አድርገህ ንግድ ለማድረግ ብትፈልግ ብዙ እረዳት እንዲያስፈልግህ ወኪልም በውጭ አገር እንደሚያስፈልግህ ስለዚህ ኩፓንያ ማቆም ያስፈልጋል ፡

አስቀድሜ ለሁሉም ነገር አገባብ አለው ያልሁበት ምሳሌ ይህ ነው ፫ ሰዎች ቆዳ ወርቅ ሰም ዝባድ በብዙ መግዛት ቢጀምሩ ባገር ውስጥና ወደ ውጭ አገር ኩባንያ ወኪላቸው ለመሸጥ ይችላል ትርፋቸውም ብዙ ይሆናል ሁሉም ነገር እንደዚህ በእምነት ተተሰራ በውጭ አገርም አገራችን ኢትዮጵያ ትመሰገናለች ክብረቱዋም እየበዛ ይሄዳል ፡ አንባቢ ሆይ ምናልባት ይህ የታሰበ ይሆናል ግን ሁሉንም እንደከናወኑ ማድረግ ነው ታልተጀመረ ሁሉም ነገር አያልቅም ።

ገብረ ጻድቅ ጋሻው ፡

የሥልጣኔን ጕዳና ስለመቀዳደም ።

እግዚአብሔር ሰውን ፈጥሮ ለዓይኑ ደስ የሚያሰኘውን ሁሉ አድርጎ በገነት አኖረው ፤ ከትእዛዙም እንዳይወጣ አዘዘው በኋላ ግን ምንም ቢሆን ከሰው ስሕተት አይጠፋምና ከፈቃዱ ወጥቶ ጌታው ያዘዘውን ቃል አፍርሶ ዕፀ በለስ በልቶ ለዚህ ዓለም መከራ በቃ ጌታችንም አልቦ ጕልቍ ወአልበ መስፈርት ለማህለ ትእዛዝከ የተባለ መሐሪ አምላክ ነውና አዳም ንስሐ ገብቶ ቢለምነው ከቀደመ ቦታው መልሶ አገባው ። እንደዚሁም ከእግዚአብሔር በታች ንጉሥ በምድር መኖሩ ሕግ እያፈረሰ ሁሉም ባለፈቃድ ሆኖ ያሰበውን ክፉ ሥራ እንዳይሠራ ሠርቶም ቢገኝ ሊቀጣው ነው ። እኛም በወገናችን ያለውን ሰው ወደ ክፉ ሥራ እንዳይሔድ መምከር የተገባን ነው ነገሥታቱም በየዘመናቸው አዋጅ መንገራቸው አንዱ አንዱን እንዳይበድል ነው ። አዋጁም መነገሩ ከሕግ እንዳንወጣ ነው ወንድሞቼ እስቲ እንመልከት ከንጉሥ ትእዛዝ እየወጡ በማይረባውና በከንቱ ሥራ በወህኒና በዘብጥያ ታስሮ የተቀመጠው ሰው ስንት ይመስላችኋል (?) የተነገረው አዋጅ ብዙ ነበረ የሚመለከተው ሰው ታጣ ። ንጉሣችንም አጼ ምኒልክ የጀመሩት መልካም ሥራቸው ሁሉ በየወገኑ ተጽፎ ይገኛል ። አሁንም በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በልዑል አልጋ ወራሽ ዘመን በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ጊዜ የተጀመረው ሥራ ሁሉ እየተፈጸመ አገኘነው ። ለዚሁም ምሳሌ ንጉሥ ዳዊት ለእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እሰራለሁ ብሎ ቢጀምር አኮ አንተ ዘተሐንፅ ሊተ ቤተ አላ ወልድከ ዘይወፅእ እምሐቌከ ብሎት ነበረና ልጁ ሰሎሞን ቤተ መቅደስን ሠራ ። ስለዚህም የተጀመረው ሥራ ሁሉ መፈጸሚያው ዛሬ ነው ብሎ ጌታችን ልዑል አልጋ ወራሽን ሰጥቶን ከዚህ ቀደም ያልተሠራውን ለሰውነት ደስ የሚያሰኘውን መልካሙን ሥራ በይነት በይነቱ እያደረጉ ለሕዝባቸው ሁሉ ስላስታወቁት የነቃው ይህነኑ ተመስርቶ የተጀመረውን ጕዳና እየተከተለ ይሔዳል ። የተኛውም ከእንቅልፉ ነቅቶ የዚህኑ ሥራ ፍለጋ ሲመለከት ስንኳን ባገራችን ያለው የውጭ አገር ሰው እንዴት በቅናት ተይዟል ይመስላችኋል ?

ከዚህም ቀጥየ የማመለክታችሁ ትንሽ ቃል አለኝ ። ግን ያለፉትን ሰዎች ለመንቀፍ አይደለም ሥራ የበዛባቸው ስለሆነ ነው እንጂ በስንፍና አይደለም ። ፍርዳቸው ሁሉ የተዋበ ነው ደግሞም ባንዳንድ ምክንያት እየታሰረ የሚጉላላው ብዙ ሰው ነበረና ይህ ጉዳት ስንኳን ባገራችን በውጭ አገር የሚወራ ነበረ ። የሰሎሞን አምሳል ልዑል አልጋ ወራሽ በየቦታው ብዙ ደምብ ካቆሙ ወዲህ አሁን ባለፈው በሰኔ ወር በተለየ የወንጀለኛ ቅጣት ፍርድ ቤት ከነደምቡ ስላቆሙ የዚህኑ ሥራ አኳኋን ለማየት ወዳጄ ብርሃንና ሰላም አነሳስቶኝ ሔጄ ነበረና ግና ከበሩ ስደርስ ብዙ ሰው በሰንሰለት ታስሮ አገኘሁ ። ይህ ሁሉ ሰው ታስሮ የተቀመጠው እንዴት ነዋ ብዬ ብጠይቅ ከመካከላቸው አንዱ ተነሥቶ ዋ ወንድሜ ሆይ ሥራው እንደ ተጀመረ ቀደም ብለህ መጥተህ ቢሆን እንዴት በደነቀህ ኑሮ አሁንማ እድሜ ለልዑል አልጋ ወራሻችን ይህነን የወንጀለኛ

ቅጣት ፍርድ ቤት ስላቆሙልን ስንቱ ድኃ ተጠቀመ ብዙ ዘመን እስረኛ ይዞ ስንቁ እያለቀበት የተቀመጠው ብዙ ሰው ነበረ አሁን ሰው ሁሉ የያዘውን እስረኛ በቶሎ ስላስረከበ ከደስታው ብዛት የተነሣ እድሜ ለልዑል አልጋ ወራሽ እያ አገሩ የሔደው ስንት ሰው ይመስለሃል ከቁጥር ይበዛል ይል ቁንም የሚያሳዝነው ቤትና ንብረት የሌለው ሰው ብቻውን ነፍስ ገዳይ ይዞ የሚመጣው ነው ፤ እኛም የያዝነውን እስረኛ ለነዚሁ ዳኞች በቶሎ አስረክበን እንሄዳለን ብለን ተስፋ አለን ብሎ ከነገረኝ በኋላ ይኸ ንግግሩ ደስ አሰኝቶኝ ወደመስሪያው ቤት ገብቼ የሥራውን አኳኋንና የተሰጠንን ደምብ ብመለከተው እጅግ ደስ በማሰኘቱ ይበል ይበል ያድርገው ያሰኛል ሥራው የተጀመረበትንም ቀንና ወር ብጠይቅ በሰኔ ወር ፲፯ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ነው ብለው በወር በወሩ የተሰራውን ሥራ ሰራተኞቹ ቢያሳዩኝ በፍርድ ያለቀለትንና ወደ ልዑል አልጋ ወራሽ ችሎት ቀራቢ ያደረጉትን ነገሩን በጣም እየመረመሩና እያጣሩ ያሰናዱትን አሳይተውኝ እጅግ ደስ ስላለኝ ከሰኔ ፲፯ቀን ጀምሮ እስከ ጳጉሜ፫ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ድረስ ነገሩ በፍርድ ያለቀለትንና ወደ ልዑል ችሎት ቀራቢ ያደረጉትን ለመጻፍ ሙሉ ፈቃዴ ስለሆነ እርሳሴንና ወረቀቴን ተኪሴ አውጥቼ ለወዳጆቼ ለማስታወቅ ስል በዚሁ በወንጀለኞች ቅጣት ፍርድ ቤት በፍርድ ነገሩ ያለቀለትና በነፍሰ ገዳይ በሌላም በትልልቅ ኃጢአት ተይዘው ወደ ልዑል ችሎት ቀራቢ ናቸው የተባሉትን በድምር ብጽፈው ነገሩ በፍርድ ያለቀለት የሰው ቁጥር ሰማንያ ሆነ ። ደግሞ ወደልዑል ችሎት ቀራቢ የሆነው የሰው ቁጥር ሥልሳ ሆነ ።

ሰስተኛም ስንቁ እያለቀበት ቁራኛ ሆኖ በዘበኝነት የመጣውን የወር ተረኛውንና የገባሩን ጉዳት እየተመለከቱ ተቀብለው ለመመርመሪያ ቤት ከሚባለው ያደረጉት እሥረኛ አምሳ ሰው አየሁ እስቲ ተመልከቱት በፍርድ ነገሩ እያለቀለት የተፈታው ሰማኒያ ሰው ነው ወደ ልዑል ችሎትም ቀራቢ የሆነው ሥልሳ ሰው ነው የተባለው በደምበኛ ውስጥ ያንዱ እሥረኛ ነገር ካንድ ቀን እስከ አሥራ አምስት ቀን ድረስ እየተመረመረ ነው እንጂ ባንድ ቀን ብቻ አይደለምና ነው ። ደግሞ ነገሩ እስኪጣራ ከዘበኛው እጅ የተቀበሉት አምሳ እሥረኛ በዘበኛው እጅ ሆኖ ነገሩ ተጣርቶ ወደ ወህኒና ወደ ዘብጥያ እስቲገባ የሚጉላላውን መመልከት ነው ። እነዚሁም ዳኞች ወደፊት ለሥራው በጣም እንዲተጉበት አሳስበቸዋለሁ ። እኔም ይህነን ሁሉ ከየሁ በኋላ ከዚህ ቀድሞ ዳኞቹ ሥራ እየበዛባቸው ብዙ ድኃ መጉላላቱን እያየሁ የብዙ ሰው ትዳር ይጠፋ ስለነበረ ይህ አዲስ ሥራ ቆሞ የዳር አገሩ ሰው የያዘውን እሥረኛ አለት እለቱን እያስረከበ በደስታ ወዳገሩ በመሔዱና ማናቸውም እሥረኛ ነገሩ እስከ አሥራ አምስት ቀን በእውነት ተመርምሮለት ወደ ቅጣት በማለፉ መልክም ሥራ ተጀምሯልና ይህነን ሥራ ለጀመሩልን ለግርማዊት ንግሥታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን ብዙኅ ዕድሜ አምላክ ሰጥቶልን ያላየነውን ለማየት የተጀመረውንም ለመፈጸም ያብቃን ደግሞ እንተ ታውኀዝ ሐሊበ ወመዓረ ገነተ ትፍሥሕት ኢትዮጵያ ኪያሃ አውረሰሙ የተባለችውን ሀገራቸውን ባዕድ እንዳይገባበትና ዓይን ንስር እንዳያያት በፍቅርና በስምምነት ሆነን እንድንጠብቃት ወንድሞቼን እለምናለሁ ።

ነገር ግን መንገድ አሳሥቶኝ ወደዚህ ወደ ፍርድ ቤት ሥራ ሔድኩ እንጂ ሐሳቤ እግዚአብሔር አዳምን ከዘዘው ቃል ቢወጣ ብላዕ በሐፈ ገጽከ ብሎ እንዳዘዘው ማናቸውም ሰው ከፋ ሥራ ሠርቶና በማታለል የሰው ገንዘብ ወስዶ ወደቅጣት እንዳይደርስ ሠርቶ መብላትን ለማሳሰብ ደግሞ በማይረባ ነገር የሰውን ሕይወት ለማጥፋት ከመድከም ሁሉም የሚገኘው ከመሥራት ነውና እንደ ዓቅሙ ሥራ ሠርቶ እንዲኖር አገሩንም እንዲጠብቅ ነበረ ። የሁላችሁም ፈቃድ ሆኖ በየመጽሐፉ ውስጥ ያለውን ትእዛዝ ተመልክተን ወደቅጣት የሚያደርሰውን ተንኰልንና ክፉውን ሥራ ትተን በፍቅር ተያይዘን አገራችን እንድትለማ ማሰብና ንጉሦቻችንን ደስ ማሰኘት አዋጃቸውንም ማጥበቅ ይገባናል ቅዱስ ጳውሎስ ቅንዖ ለእንተ ተዓቢ ጸጋ ብኋል ለሀገራችንና ለመንግሥታችን መቅናት ይገባናል ይህነንም ያልኩበት ምክንያት አገር ገጋሮች ስለተባሉት ሹማምቶች ሁልጊዜ በብርሃንና ሰላም የተጻፈውን ስላነበብኩት ነገር ከራሳቸው ጥቅም ይልቅ ለመንግሥታቸው ማሰብ ይገባቸው ስለነበረ ነው ።

ደግሞ እንደኔስ ከሆነ ኵሉ ኃላፊ ወፈላሲ ወኵሉ ከመ ልብስ ይበሊ ያለውን እየተመለከቱ ካሁን በፊት በነበራቸው ገንዘብ የተማሪ ቤት እያቆሙ በግዛታቸው ውስጥ ያሉትን ሕፃናት እየሰበሰቡ ቢያስተምሯቸው ሕፃናቱ በእውቀት ከደጉ ወደ ውስልትናም አይሔዱም ነበር ። እነርሳቸውም ይህነን ሥራ ስለሠሩ በዚህ ዓለም ትልቅ ምስጋና አግኝተው በወዲያኛው ዓለም በጌታችን በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ሀቡ እሁበክሙ እንዳለ ። መንግሥተ ሰማያትን ያገኙዋት ነበር ብዬ ሐሳቤን በዚህ እወስናለሁ ።

የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ ባልተከናወነ ሐሳብ የጻፍኩትን ቃል አይታችሁ ። የጠፋ ብታገኙበት አርማችሁና አቃንታችሁ እንድታሰናዱት ፈቃዳችሁን እለምናለሁ ።

ወንድማችሁ ኃይለ አጋዕዝት በ ።

ያገር ውሥጥ ወሬ

የክቡር ደጃዝማች አያሌው ብሩ ከደባት ወደ ትግሬ ጉዞና የሚያስደንቀው ሰልፍ ። ክቡር ደጃዝማች አያሌው ወደ ትግሬ ሲመጡ ጊዜው ክረምት ስለሆነ ትግሬንና ጠለምትን የሚለያየው ተከዜ የሚባለው ትልቁ ወንዝ በጣም ሞልቶ ለማየት የሚያስፈራ ሆኖ ነበረና ጉዞዋቸውን እያሸገሩ ከዚያ ወንዝ ፲ቀን ሰነበቱ ። ነገር ግን የመንግሥቱን ትእዛዝ በመፈጸም የሚገኘው ስቃይ ሁሉ ስለ ሰማእትነት ይቆጠራል በማለት ነው እንጂ ዓይን ያለው ሰው ያንን እያየ በክረምት ከዚያ ባሕር ውስጥ ለመግባ እጅግ እጅግ የሚያስፈራና የሚያንቀጠቅጥ ነበረና ከወሃው ብርታት የተነሣ ከተከዜ ወዳገራቸው የተመለሱ አሽከሮቻቸው ልክ መጠን የላቸውም ። እርሳቸውም ወንዙን ከተሻገሩ በኋላ ወደ ታዘዙበት አገር ሲጓዙ ሰንብተው ሐምሌ ፳፫ቀን አክሱም ገቡ ያገባባቸውም አኳኋን ከዚህ በታች

እንደ ተጻፈው ነው ። መጀመሪያ እንደ ኢትዮጵያ ሰልፍ ሆነው ልክ የሌላቸው ወታደሮች በማረ ሰልፍ ተሰልፈው አለፉ ። ቀጥሎም ሀር የመሳሰሉ ሻንቅሎች የየመአርጋቸውን ጠርቡሽ ጠርቡሻቸውን አድርገው ነጋሪቱን አብዝር እያሰኙ ቢያልፉ የነጋሪቱ ድምጽ ከተማውን ያናውጠው ነበር ። ቀጥሎም ጥሩንባ ነፊዎችና መለከተኞች በማረ ድምጽ እየነፉ ሲያልፉ እጅግ ደስ ያሰኝ ነበር። ከዚህም ቀጥሎ እንደ አውሮፓ ስርዓት አንድ ዓይነት ከትና ገንባሌ የለበሱ ዝናር ዝናራቸውን ባንገታቸው እንግተው ልክ የሌላቸው ሰልፈኞች ቢያልፉ የከተማው ሰዎች በወሬ የሰማነውን በይናችን አየነው እያሉ በጣም ይገረሙ ነበር ቀጥሎም ነጭ ከት በለበለሱ በብዙ ዘበኞች ተከበው በወርቅ ያማረበት ካባቸውን ለብሰው ነጭ ሃር ጃንጥላቸውን እንደዘረጉ ክቡር ደጃዝማች አያሌው ብቅ ባሉ ጊዜ የከተማው ሰው ስፍራ አልበቃ ስላለው አንዱ ባንዱ ላይ እየተንጠላጠለ እርሳቸውን ለማየት ይጨናነቅ ነበር ይልቁንም የከተማው ሴቶች እልልታቸውን በለቀቁ ጊዜ ከብዛቱ የተነሣ ለሰሚ ጆሮ ያሸግር ነበር ። ከዚህም ቀጥሎ የመትረየስ ዘበኞች መትረየሶችን አስጭነው የሰልፍ ከታቸውን ለብሰው ሲያልፉ የልክ አካሄዳቸው ላይን ያታክት ነበር ። ከዚህም ቀጥሎ መኳንንቶቻቸው በማረ ሰልፍ ሆነው አሽከሮቻቸውን የቀትር ንብ አስመስለው አሰልፈው ሲያልፉ የሰዉ ብዛት እጅግ ያስገርማል እውነትም ከተከዜ የተመለሱ አሽከሮቻቸው ከርሳቸው ጋራ ትግሬ ገብተው ቢሆን ምን መሬት ይበቃቸው ኑሮዋል ።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ፀሐየ በዛብህ አክሱም

የውጭ አገር ወሬ ።

በነሲያ ። ኮፖ እስክንይደር በሚባል (ዋንጫ) ውብሰተር የተባለው የእንግሊዝ አረዮፕላን በ፲፱፻፶፫ሺ ፪፻፹፪ ኪሎ ሚትር ስለ ተገመተለት ቀዳመዊ የሆነለት እሽቅድድም ተደርጎበት በነበረ ጊዜ ባዓለም ኤድሮቦላንት በራሪዎች የቀልጣፋነት ፍትትን ሁኖ ነበርና ፬፻፷፭ሺ ፬፻፪ ኪሎ ሚትር የተገመተለት ኪንከይድ የሚባል ነጅ የነዳው ኤድሮቦላንት በልጦዋል ። የፍትትኑ ሥራ ከለቀ በኋላ ባልቦ የሚባል ኢጣሊያዊ የበራሪዎች ጽሕፈት ቤት ጸሐፊ ትእዛዝ ምክትል ፡ ኢጣሊያ እንደገና ድለኛ መሆን ተስፋ እንዳላት እያመለከተ የእንግሊዝ አረዮፕላኖች ነጅዎችን እንኳን በደኅና ተመለሳችሁ ለማለትና ለሰሶን (እንግሊዝ) ጸሐፊ ትእዛዝ ምክትልም ስለድለኛ መሆን ለማመስገን ወደነሱ ሄድዋል ።

ቦልሳኖ ኢጣልያ ። የባሕር ጠሀ እዳር ወጥቶ ያጥለቀለቃቸው አገሮች ህዝቡን ለመርዳት የሄደ የምድር ባቡር ኢዛርኮ ተሚባር ወንዝ ገብቶ እዚሁ ውስጥ ስለጠለቀ ፲፯ የምድር ሠራተኞች ሙተዋል ። ፕሬዝዳን ሙሶሊኒ ይልቁንም በባልቲንና በአልቶአዲጆም (አገሮች) ላይ ሲሆን አብሶ ወሀው ያጥለቀልቃቸውን አገሮች ሁሉ ለመርዳት ስለ ማስተዳደር ሱዋርድ የሚባል የጸሐፊ ትእዛዝ ምክትልን ወደ ቦታው ልኮታል ።

ሎንድራ ። እየተቀኙ ሰላምታን ያቀርቡለት በእስክንይደር ዋንጫ ላይ በተደረገው ፍትትን የእንግሊዝ ድለኛነትን ከፍ ከፍ እያደረጉ ጋዜጦች ደፋር የሆነች የኢጣሊያ በራሪነት ከንግሊዙ በራሪነት የምታንስ ናትና በቀጥታ ለፍትትን ተስተዳድራ ለ፬ደፊት በምትገጥምበት ጊዜ የበለጠ ዕድልን ለማግኘት የተገባች ናት ይላሉ ። የኢጣሊያ ጋዜጦች ሁሉ በሙሶሊኒ መወለድ (መነሣት) ወሬ ሲያነሱ ለሙሶሊኒው ቤተ ሰዎች ደስ የሚያሰኝ በኢጣሊያ ስም ሁነው አሁን በቅርብ ለተወለደው ሰላምታን ያቀርባሉ ፤

ጀኖባ ኢጣሊያ ። ሰናተር ጉልየልም ማርኮኒ ስለጥበብ ሥራ ቁሞ ያለው ማሕበር ጠርቶት ወደ ኒዩ ዮርክ ለመሄድ ቢያንኮማኖ ከሚባል መርከብ ተሣፍሮ ተነስቶዋልና እዚያ አሁን በቅርብ በመጨረሻ ጊዜ እራሱ አግኝቶት ባለው የራዲዮ ቴሌግራፍ አዲስ ሥራ ያሚያሣይ በጥበብ ነገር ጉባኤ ሊያደርግ ነው ፡ ሰናተር ጉልየልሞ እሱ እራሱ ባወጣው የማገናኛ ብልሐት የዓለም ነገሥታት ሁሉ አብረውበት ተሚውሉ በምድርም በባህርም እያስፋፉ እንዲሄድ ለማስተዳደር እዋ ሺንግቶ፻ ተሚደረገው ጉባኤም የኢጣሊያ እንደራሴ ሁኖ ሊቀርብ ነው ።

ፒዛ ኢጣሊያ ። የአሜሪካ ወታደሮች ከጀኖባ(ከኢጣሊያ)ተነስተው ወዲህ ደርሰዋልና ፡ እሌጋሩ ዘንድ መንግሥትና ብዙ ሕዝብም በማክበር ተቀብለዋቸዋል ። ወታደሮቹ የከተማውን ሐውልት ካዩ በኋላ ንጉሡ እቤተ መንግሥት አዳራሽ ተቀብሎ ወዳጅነት በሚያነሣሣ ንንግግርን የፍቅር ቄይታን አድርጎላቸዋል ። ወታደሮቹ ከኩለ ቀን በኋላ ወደ ሮማ ለመሄድ ይነሣሉ ።

ኒዩ ዮርክ ። ዊልያም የተባለው አረዮፕላን ነጅ ተነንት (አለቃ) ከእስ ከንይደር ዋንጫ እሽቅድድም ተመልሶ ፡ የእንግሊዝ ድለኛነትን ሲያስታውቅ የኔም አረዮፕላን እንደዚሁ ልክ ቀልጣፋ ነውና አበነሲያ ሊሆን ተውስኖ ባለው እሽቅድድም ድል ለማድረግ አሳብ አለኝ ብለዋል ።

ቡዋኖስ አየሮስ ፡ ጎያ ተሚባል ጋለሪ ሲኒማ ሲደረግበት በነበረ ጊዜ ጋለሪው ስለፈረሰ ፳ ያህል ሰው ሙቶዋል ፪ የሚያህል ቈስለዋል።

ማስታወቂያ ።

የኔው አውቶሞቢል የሎተሪ ወረቀት የገዙ ሰዎች የወረቀቱን ዋጋ ያልከፈሉ ብዙ ስለሆኑ ደግሞ ብዙ ወረቀት ስላልተሸጠ ሎተሪው ጨርሶ መቅረቱን አስታውቃለሁ ገንዘብ ለሰጡኝ ጥቂት ሰዎችም ገንዘባቸውን እንዲመለስላቸው አስታውቃለሁ ።

ሀብተ ሥላሴ ።

ማስታወቂያ ።

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠራል ።

ኒኮላ ።

COGNAC S.E.A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ሱቅ ይገኛል ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቀቅዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳም ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።



ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ እመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አሉ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክበሙ ጉድደር ይባላል፡፡ሲሄድ እንደ ማጭድ ይደዛል ደ ግሞ በልክ ይሄዳል። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆ ን እያስፈራም እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስ ቲክ ሁሉ ጠንክራነው በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድደር ግዙ ከሌላው ላስ ቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩ ል ነው ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኝ ው ዓረብያን ትሬደንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጉምሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ስፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀ ሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያፈ ላኣስ ሐዲስ ከሚዎን አቶመቢል የፈታውራሪ ዶሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በንርንርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምቡሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፤ መጫሚያ በያይነት፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፤ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሦስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፩
3 me ANNÉE № 41

ሐሙስ ጥቅምት ፪ ቀን ፡ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 13 OCTOBRE 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ትምሕርት

ማናቸውም ነገር አለ ትምሕርት ምንም የቁም ነገር ሥራ እንደማይሆን ወደፊትም እንደማንገሩ እንወቅ ። የትምሕርት ጥቅም እጅግ ብዙ ነው ። ግን ባጭሩ ዋና ዋና ነገሩን አመለክታለሁ ። መጀመሪያ ሰውነትህ ምን እንደሚሆን ምን ማድረግ ምን መተው እንዲገባህ ያስታውቃል ። ፪ኛ ፡ በመላ ዓለም ምን እንደነበረ ምን እንዳለ ። ምን እንደሚመጣ ለማወቅ ትችላለህ ፫ኛ ፡ ከዚህ ዓለም ሰዎች እንዴት ብለህ መኖር እንደሚገባህ ከሚተላለፍ በሽታም በእንዴት ያለ መንገድ እንደምትድን ለመለየት ትችላለህ ። ፬ኛ ፡ በጤና እንድትኖር ሕይወት ያለው መብልና መጠጥ ለይተህ የሚዘነም ልክ አውቀህ ሰውነትህን በእንዴት ያለ ንጣት ሊኖር እንደሚገባው ትረዳለህ ። ፭ኛ ፡ በዚህ ዓለም ሰዎች የሚሠሩትን የሆነ ሁሉ ሥራ እንዴት እንደሚሆን በመጽሐፍ አጥንተህ ሚሠሩት በዓይንህ ተመልክተህ ቀድተህ ለመሥራት ይቻላል ። ፮ኛም ፡ አንዳንድ ሰዎች በእንደዚህ ያለ አእምሯቸው ከሰሩና ማሰብን ከለመዱ ወዲያ ከነሱ በፊት ያልታሰበና ያልተሠራ አዲስ ጥበብ ሊፈጥሩ ይችላሉ ። እነዚህ ሰዎች ከነሱ የሚገኝ ጥቅም ዓለም በያዘችው ኃብት ተገዝቶ የማይገኝ ስለሆነ ከዚህ ሁሉ ሕዝብ እጅግ የከበሩና የተመሰገኑ ናቸው ። ሥራቸውን ለዘለዓለም የማይሞት ስለሆነ እንዳይረሱ ሞያቸው በመጽሐፍ ተጽፎ ፊታቸውም በሃውልት ተቀርጦ ይኖራሉ ።

እኛ የኢትዮጵያ ልጆችስ እንዴት አእምሯችን እንደነሱ ሰፊ ጉልበታችን ብርቱ ሳለ እየተመራን እንኑር ፡ የዚህ የዓይናችን እመምስ መድኃኒቱ ምን ይሆን ለኔ ትምሕርት ይመስለኛል ። እንግዲያስ እኛ በዓለም ካሉ ጥንታውያን ሕዝብ ጋራ ተቆጥረን ከዓለም በኋላ ቀርተን ያለን ከነዚህ ሰዎች ማኅበር ለመሆን ልንችል በብዙ ፍለጋና ትጋት እንማር ። (እውቀት የወደደ ጠቢብ ይሆናል እንዳለው የጠቢብን አበት) ያልተማረ ሰውና እውር አንድ ናቸው ።

እውር ሞላ ሕይወቱ መሪ ካላገኘ ካለበት ስፍራ ለመንቀሳቀስ አይችልም ። የተንቀሳቀሰ እንደሆነም ወደ ገደልና ጉድጓድ ይወድቃል ። ባይገጥመው ደግሞ ቤቱን ለመመለስ አይችልም ። እውነት ነው አባቶቻችን ከነሱ ዘመን ከነበሩ ሰዎች መጠን ኃይለኞችና ጅግኖች ስለ ነበሩ በምሥራቅ በምዕራብ በሰሜን በደቡብ በሁሉ መአዝን እየተታገሉ ሥጋቸውን እየቈረሱ ደማቸውን እያፈሰሱ ከልደተ ክርስቶስ ብዙ ዓመት በፊት ጀምረው አቈይን ከቀን ብዛት ግን እናታችን ኢትዮጵያ ልጆችዋ ሊረሷቸው ብቻ ከበሬታ በመፈለጋቸው እርስ በርሳቸው እየተጣሉ ከነበረችው ስፋትዋ ተቀንሳ ከነበራት ኃይሏ ደክማ የተረፈችውን በትንንሽ ነገሥታት ተከፋፍላ ነበረች አሁን በቅርቡ ባባ ዳኘው ምኒልክ ጊዜ ነቃ ነቃ ልትል እጅዋና እግሯም ወደ ግራና ቀኝ ሊንቀሳቀስ ጀመረ ። አሁንም እግዚአብሔር በምሉ ሲታረቀን ሰላማዊና ብርሃንዋ ተፈሪ ልክ በቶሎ ወደ ፊት የምትራመድ ይመስላል ። እርምጃዋ ፤ እንደ ጃፖን መንግሥት እንዲያደርግላት የኢትዮጵያን ልጆች ሁላችን ዕድሜና ጤና ለዘውዲቱና ለተፈሪ እያልን ሌት ከቀን ፈጣሪችንን እንለምናለን ። በውነት በላይኛው ደረጃ ለመድረስ ከፈለግን ቀምበሩ ለልዑል አልጋ ወራሽ ብቻ ሳንጭን ክቡር ነጋድራስ ደስታ በብርሃንና ሰላም እንዳሉት ቂምና በቀል የሚሉትን አጥፍተን አገራችን ሰፊ ነውና በየያዝነው ሞያ ብንሰራ ለኛ በቅቶ ለውጭ አገር ሰዎች እንኳ በተረፈ ፡ አንድ ሰው ብቻየን ልሥራው ቢል የማይሆን ነገር ነው ለአንድ ፕሮፌሶር በዓለም ያለ እውቀት ሁሉ አንድ ሰው አጥንቶ ለመጨረስ ሁሉ ጊዜ ሳያቋርጥ እየተማረ ስንት ዕድሜ በበቃው ብዬ ብጠይቀው መጀ

መሪያ ሊያጠናውና ሊይዘው አይችልም የሚችል ቢሆን ደግሞ ፩ሺ ዓመት እንኳ ሲያንሰው ነው ብሎ መለሰልኝ እዩት እውቀት እንዴት ሰፊ እንደ ሆነ በአዋቂዎች ቤትም ስንት ሥራ እንዳለ ።

አገራችን ኢትዮጵያ ምን መሆንዋን የማትታወቀው የነበረች የዓለም ታሪክና የግራፊ ጸሐፊዎችም አንድ ሰፊ የአረመኔ አገር በየነገዱ ሁሉ ጊዜ ሲተራረድ የሚኖር ብለው ለህዝቦቻቸው አስረድተውት የነበረ ልዑል አልጋወራሽ ተ መ ኤውሮፓ ሂደው በክርስትና ቍማ በነጻነት እንደኖረች ለወደፊቱም ቢቀሎ ወደእውቀት ደረጃ እንደምትራመድ አስታውቀው የዓለም ነገሥታት ጓደኛ ከደረጓት ወዲህ ዓለም በመላ በአሚሪካ በእስያ በአውስትራልያ በመላ ኤውሮፓም ታወቀች ። ስለዚህ ንጉሥታቶቹና መሳፍንቱ መኳንንቱና ህዝቦቹ ተስማምተው ያቆሙት አዲስ ደንብና አዲስ ወግ የተሻለም ሕግ ለመስማት ዓለምን በመላው ጆሮውን ከፍቶ ያዳምጣል ። ትምህርት የተባለ መሳርያ ካልሆነ ሌላ የሚጠቅመን እንደሌለ ከሁላችን በፊት ልዑል አልጋ ወራሽ በትክክል ተረድውታል ። ጌታችን በፍሬያቸው ታውቁዋቸዋላችሁ እንዳለ የስራቱን ፍሬ ይመሰክርላቸዋል ። ቀጥሎም የልዑል አልጋ ወራሽ ተመ አሳብ ተከተለው ክቡር ፊታውራሪ ዴሬሳ ያስታወቁትን አሳብ ብዙ መልካም ስራ ለአገር የሚያለማ ለመንግሥት የሚያሰፋ ለሕዝብ የሚያበረታ መሆኑን ጥቅሙ ብዙ ሰው እንደተረዳው በብርሃንና ሰላም አንብበነዋል ቢሆንም አገራችን ሰፊ ስለሆነ በትንሽ ቀን የሚያገናኝ የቀና መንገድና ባቡር የመሰለ ሁሉ ስለ ጐደለብን የተረዱት ሰዎች እኒህ ትንሽ የብርሃን ጩራ ያዩ በአዲስ አበባ ዙርያ ያሉ ሰዎች ካተቀር የበለጠ ኢትዮጵያችን እንኳን አሳቡን በትክክል ሊረዳው ወሬውን ያልሰማው እንኳ አይጠፋም ይመስለኛል ስለዚህ የተዋጣ ገንዘብ ብዙ አልተጠራቀመም ኢትዮጵያን የሚያህል አገር በዚህ ብቻ እንደማይጠቀም ሁሉ ሰው አይስተውም ።

እንበቢ ሆይ ምንአልባት ገንዘባችን አውጥተን ስራው ሳይፈጸም ቢቀርሳ የሚል አሳብ ይገባህ ይሆን? ስራው እየተፈጸመ ወደ ፊትም እየገፋ ሌላ አዲስ ስራም እየቆመ እንዲሄድ የሰው አሳብ ሳይንቁ የሚቀበሉ ልዑል አልጋ ወራሻችንን ተ መ ቢሰነብቱልን እስበ ለማውጣት ይቸግራል እንጂ ቢልሆች ያሰናዱት ሕግና ደምብ ገልብጦ ለማቆም አያስቸግርም ።

በፊት ትምህርት ቤቱ ቢቆም ከአሁንም በፊት በአዲስ አበባና በድሬ ዳዋ እንደተጀመረ እንዲሁም በየአውራጃው በትንንሽ ገጠሮች እንኳ ሳይቀር ፤ የመንግሥት ገቢና የማዘጋጃ ቤት ገቢ ተለይቶ ፡ በትክክል ቢሠራ እንዲህ ብሎ ተዋጥቶ የቆመ ትምሕርት ቤትና ሌላ ትልልቅ ፋብሪካና ባቡር ቢቆምም እየለማና እየሰፋ እንዲሄድ መንግሥትና ማዘጋጃ ቤት ምን ማድረግ እንደሚገባቸው እኔ ያቅሜን ያህል እጽፋለሁ ። እንዲሁም እውነተኞች የኢትዮጵያ ልጆች ወንድሞቼ ከኔ ይልቅ እጅግ አብልጠውና አሳምረው እንዲጽፉት የታወቀ ነው ። ጌታሁ ልቡና ልዑል አልጋ ወ ተ መ ጕምሩክን ለመጕብኘት ሂደው መንግሥት ያለ ገንዘብ ወደ ግራና ቀኝ ሊንቀሳቀስ እንደማይችል የተናገሩትን ቃል ፤ በልባችን ጽፈን ለዘለዓለም እንድናስቀምጠው ይገባናል ። አንድ አንዱ ተከራካሪ ምክንያት አያጣምና ፡ ገንዘብ የሚገኘው በሥራ ነው እንጂ በትምርት አይደለም ይል ይሆናል? ይህንን አሳብ ግን መሬት ከተሸከመችው ሁሉ የሚከብድ ሞኝነት ነው ። መጀመሪያ ሰው ካልተማረ የሥራን ጥቅም አያውቅምና ሥራ አይወድም ። ሁለተኛም የአሠራሩን እግርና ራሱን ለመለየት አይችለውምና ሠርቶ ወደ ቁም ነገር ለመድረስ አይችልም ። አካላት ሁሉ ያለ ራስ እንደማይሆን ሥራ ሁሉም ያለ ትምርት አይሆንም ። አንድ አንዱ የአገሬ ሰው ግን ብሩን ከግምጃ ቤት እየፈለቀ የሚያድር ይመስለዋልና እንኳን ገንዘቡን አውጥቶ አንድ ሞያ ለማቆም ሊያስብ ለኔ ሳልሠራ አብላኝ እያለ ለመንግሥት ሲያስቸግርና ሥራውን ሲያስፈታው ይኖራል ።

ክቡራን ጌቶቼና አባቶቼ ሆይ ከኔ እጅግ በሚበልጠው አእምሮዋችሁ በብዙ መንገድ ለአገራችሁ ጥቅም አስባችሁ እንደምትሆኑ የታወቀ ነው ። እኔ በሁሉ ነገር በእናንተ ፊት ከአንድ ፍሬ ጤፍ ያነስኩ ነኝ ። ስለዚህ ይህነን አድርጉ ብዬ ለማዘዝ ትልቅ ድፍረትና ርግማን ይሆንብኛል ። ግን ብርሃንና ሰላም ሰውን ሳይለይ ያገሬ ልጆች ሁላችሁ በመአርግ የበለጣችሁም ያነሳችሁም በአእምሮ ከፍ ያላችሁም የጐደለባችሁም የልባችሁ አሳብ አስታውቁ ብሎ ካወጀ ፤ እኔማ እንደ አቅሜ ከሁሉ በፊት የእውቀትን መክፈቻ እንዴት አድርገን ዋጋው አጠራቅመን ልናቈመው እንደሚገባን ልናገር የግድ ሆነብኝ

አገራችን ኢትዮጵያ ሰው እጅግ ትንሽ አይደለም ብዙም ድሃ አይደለም ። የዓመት ግብሩን በትክክል አውጥቶ ለሰራተኛው እንደሚገባው በስርአት ዘርዝሮ ፡ ባቂው ወደ መንግሥት የሚያገባው ቢጠፋ አንድ ቁም ነገር ሳይሰራበት በከንቱ እየባከነ ቢቀር ነው እንጂ ገንዘቡ እጅግ ብዙ እንደሆነ ማንም አይስተውም ። ይህነን ስራም ለአገራችን ጥፋት ለህዝባች ጕዳት ለመንግሥታችን እፍረት እንደሆነ ብዙ ሰው ተረድቶታል ። ለዚህ ብዙ የገማ ቍስላችን መዳኛ ሰላማዊና ብርሃናዊ ልዑል ጌታችን ተ መ የመሰረቱት ክቡር ፊታውራሪ ዴሬሳም በአገራቸው ፍቅር የተጠመዱ የተከተሉት ገንዘቡ ከዚህ ቀጥሎ እንደሚጻፈው ቢዋጣ እንደኔ አሳብ ብዙ መልካም ተመስሎ ይታየኛል ። ያገራችን ህዝብም እንኳን ለልጁ ማስተማሪ ለሌላ ነገር በብዙ ሲከፍል ይኖራል ። ስለዚህ በመንግሥት አዋጅም ስለሆነ በብዙ ደስታ እንደሚከፍለው የታወቀ ነው ።

፩ዓመት ከሞላው ልጅ ጀምሮ እስከ ታላቁ ከድሃው እስከ ኃብታሙ እያንዳንዱ ሁለት ሁለት ብር አገር ያወቀው ለማኝና ቤት የዋለ ሽማግሌ ከሆነ ፡ እያንዳንዱ አንድ አንድ ሩብ ፩ዓመት ከሞላው ጀምሮ በላምና በበሬ በበቅሎ በፈረስ በግመል ቍጥር አንዳንድ ብር ፩ዓመት በሞላው አህያ ቍጥር አንዳንድ ሩብ ፩ዓመት በሞላው በግና ፍየል ቍጥር ፪ ፪መሐለቅ በሚኖርበት ቤት ቍጥር አንዳንድ ሩብ በሚከራይ ቤት ሁለት ብር በ፩ቀላድ ሶስት ብር በ፩ርስት አንድ ብር የመንግሥት ዘበኛ በተቀር በ፩ብረት አላድ በ፩ሽጕጥ አንድ ሩብ በ፩ጕራዴና በ፩ሾ

ተል ሁለት መሐለቅ እንዲህ አድርጐ በአዋጅ ቢያወጣ ሠራተኛውን ችሎ ከሃምሳ ሚሊዮን ብር የሚበልጥ እንዲሰበሰብ እርግጥ ነው ።

ከአሁን በፊት ይህንን ተደርጎ እማይታወቅ የሚል ሰው የተገኘ እንደሆነ በአውሮፓ በውሽ ሳይቀር በየዓመቱ ግብር እንደሚከፍሉ ይጠይቅ ። ይልቁንም የጀርመን መንግሥት በጠርነት ከደከመ ወዲህ በገንዘብስ ይቅርና በፈቃዳቸው ለመንግሥታቸው አለገንዘብ የሚሠሩ እጅግ ብዙ ናቸው ። አንዱ ክርስቲያን ነኝ ቢል የክርስቶስን መንገድ ካልተከተለ ቀጣፊ ነው ። እኛም እንዲሁ በአፋችን አገሬን እወዳለሁ በነጻነት ለመኖርም እፈልጋለሁ እያልን በአፋችን ብንለፈልፍ ቁም ነገር የለውም እያቅማችን ያሀል ብንሠራላት ነው እንጂ ። እንዲህ ሆኖ የወጣ ገንዘብ ከሁሉ በፊት በየአገሩ አውራጃ በየራስ ከተማው ሁለት ዓይነት ትምርት ቤት ይቆማል አንዱ ለዕድሚያቸው ትንንሽ ለሆኑ የእውቀትን ትምርት የሚማሩበት ሁለተኛው ጊዜ ያቸው ለአለፈባቸው ፈቃድ ግን ያላቸው ሰዎች ጥበብ የሚማሩበት ማለት ብረት መቀጥቀጥ ማኪና ማጋጠም ሸማ መሥራት ጫማ መስፋት ማነጥ መግንባት መኪና መዘወር እንዲህ የመሰለ ሥራ ሁሉ የሚማሩበት እየአገሩ ገገርም ባይ በልጥ በዚሁ ልክ ያቁም አልችልም ገንዘብ የለኝም ቢል ግን መንግሥት ጸፊና ተቆጣጣሪ በየውራጃው ይላክበት ። በዚህም ላይ ሌላ እየዞረ የሚፈትሽ ይሹምበትና አገር ለሚጠብቅ ወታደር በቀቶ በከንቱ የሚያባክነውን ገንዘብ ያሰመርምረው መንግሥት ለዚህ ሥራ የሚልካቸው ሰዎች ግን ብዙ ብልሃት አለና እጅግ የታመኑ ሰዎች ያስፈልገዋል ። ይህንን አሳብ ሰው ቢቀበለው ለዚህ ተንኰል ለማጥፋት ለአዋጁ አጋጋር የሚሆን እንዴት ያለ እንደሚሻል ለወደፊቱ አስታውቃለሁ ።

ሚከኤል ተሰማ ።

የሥልጣኔን ጐዳና ስለመቀዳደም ።

ለሀገራቸው ጥቅም የሚሠሩ ከብዙዎቹ አንዳንድ ሰዎች ይገኛሉ ። የነሱም ትጋት ሌሊትና ቀን አይለይም ይኸውም የሆነ በመጽሐፈ ምሳሌ ምዕ ፮ ቁ ፱ እስከ ፲ ድረስ የተጻፈውን በመመልከት ነው ። መቸም የመንግሥት ጉዳይ ያለው በየመኳንንቱ ቤት ነውና ከወዳጄ ከብርሃንና ሰላም ጋራ ስንጫወት ለመንግሥት ጉዳት የሚሆን ትልቅ ነገር ልንገርህ ። ነገር ግን አንተ ብቻ ሰምተኸው ልተቀር አይደለም ወዳጆችህና የኔም ወዳጆች ሊሰሙት ነው አለኝ ። አይሰሙኝም እንጂ ከሰሙኝማ ምን ከፋኝ ። ነገሩን እስቲ አስቀድመህ ንገረኝ ብለው ቢሰሙህ ይስሙህ ። ባይስሙህ ግን ባንተ ይፈረዳልን ብሎ ነገሩን ጀመረልኝ ። ንግግሩም ይህ ነው ። መቸም መሔድ የማያሰማው ጉድ የለምና አንድ ቀን አለቃዬ ወረቀት ይዘህ ሂደህ ለሥራህ በቶሎ ተመለስ ብሎ ወዳንድ ሰው ቤት ልኮኝ ነበር እኔም የመንግሥት ሠራተኛ ስለሆንኩ ወደ ሥራዬ በልክ እንድገባ የሥራ መግቢያ ሰዓት እለብኝ ። ከዚያ ባልፍ ያችው ያለችኝ ቀለቤ እንድትቆረጥብኝ አውቃለሁ ። ወደዚያም ወደ ተላኩበት ሰው ዘንድ የተጻፈው ደምብ በጣም የጠነከረ ነው ብለው ነግረውኝ ነበርና ከደጁ በደረስሁ ጊዜ እናቶ ንገሩልኝ የሚባሉትን አገኘኋቸው ። ተልኬ መጥቻለሁና እባካችሁ ንገሩልኝ ብላቸው አሁን ጌቶች አልተነሱም ገና ናቸው ጥቂት ጠብቅ አሉኝ ። እኔም ጌታው ደምብ የሚያውቁ ናቸውና ከሁኝ አሁን ይነሳሉ ብዬ ስጠብቅ ደመወዜ የሚቆረጥበት ሰዓት ደረሰብኝ ። ሰዓቱንም ተኪሴ አውጥቼ የሰዓቱን መድረስ ተመልክቼ አዝኜ ሳለሁ ከወደ አልፍኝ ወደ መታጠቢያ ቤት ዞረዋል የሚባል አሸከር ብቅ አለ ። እናቶ ንገሩልኝም ይህ ሰው ከመጣ ቆይቷል እባክህ ንገርለት ቢሉት ገና አሁን ከእንቅልፋቸው ተነስተው ወደ መታጠቢያ ቤት ገብተዋልና ከዚያ ተመልሰው ሲደርቁ እነግርልሃለሁ ። ቆይ አለኝ ። ወንድሜ ሆይ እኝህ ጌታህ ደምብ የሚያውቁ ናቸውና በቤት ተነስተው የመጣውን እንግዳ አሰናብተው በቆሙት ሰዓት ልክ ወደ ሥራቸው በቶሎ ይገቡ መስሎኝ እስከ አሁን ቆየሁ ። አሁን ደግሞ ወደ መታጠቢያ ቤት ዞረዋል ካልከኝ የታጠቡት ጐፈሪያቸውና አካላታቸው እስቲደርቅ ብዙ ሰዓት ያስፈልጋል ። ደግሞ በተለየ እለት እለቱን እየተለዋወጠ የሚለብሱት ልብስ አላቸው ፤ ያ ቀርቶ በኦዶኰሎኝና በሌላም ጣዕም ባለው ሽቱ ተቀብቶ እስቲቀርብ አንድ ሰዓት ያሀል ይቆያል ብዬ የያዝኩትን ወረቀት ላንዱ ጓደኛዬ ጌቶች ወደ መታጠቢያ ቤት ገብተዋል አሉኝ የታጠቡትን ደርቀው በወጡ ጊዜ እንድትሰጥልኝ ብሎት ሔደ እያሉ ሰዎች ሲጫወቱና ሲስቁ ሰማሁ ፤ ለኤም ይህ ነገር ስለደነቀኝ ያ ወረቀት ይዞ መጥቶ የቆየው ሰው አለቆቹ እንደምን አደረጉት ብዬ ብጠይቅ ፤ የፈራው አልቀረምና እስከ አሁን ለምን ቆየህ ቢሉት ነገሩን ከስሩ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ቢያጫውታቸው ከት እያሉ እየሳቁ የጌቶች ገላና ጐፈሬ ደርቆ እስቲወጡ ድረስ አትቆይም ኑሯልን ። ይህማ ወዴት ይሆናል ይህን ምክንያት አድርገን አንቀበልህምና ይልቅ እንደ ሚገባው ዋስ ጥራ ከደመወዝህ የሚቆረጠውን በኋላ እናስታውቅሃለን ብለውታል ብለው ሲላጫወቱኝ ለዚህ ደኃ እግዚአብሔር ዋጋውን ይክፈለው እንጂ ምን ይደረጋል ብዬ ይህንን ነገር ላንተ ለመናገር ያሰብኩት እንደዚህ ያለ ግፍ እንዳይሰራ ነው ። እስኪ ተመልከተው ወንድሜ ሆይ ከቤት ጀምሮ እስከ ጌቶች መነሳት ድረስ ስንት የመንግሥት ጉዳይ ይፈጸም ይመስልሃል ። እኔም ይህን ስለ ነገርኩህ ልብስህን አትጠብ ። ገላህን ንጹሕ አታድርግ ለማለት አይደለም በቤትህ ውስጥ ብዙ ፈጣኖች አሽከሮች ሞልተዋል እነሱ በስርዓት ተጠንቅቀው እንዳሰቡከው አሰናድተው ያቀርቡልሃልና ከሌሊቱ በ፲፩ ሰዓት ከተነሳህ ልብህ ያሰበውን ለመፈጸም ትችላለህ ። በ፲፪ኛውም ሰዓት የሰማይ አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ ብለህ እስከ መጨረሻው ጸሎት አድርገህ ተቸግሮ የመጣውን እንግዳና የመንግሥቱን ጉዳይ በትጋት ብትፈጽም ግን በንጉሡ ዘንድ ክብርና ምስጋና ታገኛለህ ። በእግዚአብሔርም ፊት ስለበጎ ሥራህ መልካም ዋጋ ታገኛለህ ። ምሳሌ ፳፫ ቁ ፲፩ ታዳጊያቸው ጽኑ ነው ። እርሱም ፍርዳቸውን ከንተ ጋራ ይፈርዳል ይላል ።

እንቅልፍ በጣም ጣፋጭ ነው ዘለዓለም ተኝተው ቢኖሩ የማይጠገብ ነው ። ከሰማኸኝ ዘንድስ የእንቅልፍ ብዛት ጨርቅ ያለብሳል ፤ የሚለውን ብትመለከት መልካም ነው አንዳንድ

ሰው ትጉህ የሆነውን ሰው ይህ ደንቆሮ እያለ ይሳደባል የርሱ እውቀት በልጋ ላይ ተኝቶ ስለዋለ ነውን ድንቁርና ማለትስ የርሱ ነው ምሳሌ ምስ ፩ ቁ ፳፱ የአፍህን ጠማምነት ከንተ አውጣ አሰተኞችንም ከንፈሮች ከንተ ፈጽመህ አርቅ ያለውን ባይመለከት ይሆናል ።

ደግሞ ለመንግሥታቸው አስበው ሌሊቱን ሁሉ የሚሰሩ ሰዎች ወዴት ታገኛለህ የምትለኝ እንደሆን እነሆ እንቅልፍ ሳታበዛ ነቃ ተህ ፍለጋዬን ለመከተል ወደሚገሰግሱ ሰዎች ደጅ ብትሄድ ለጌትነታቸው ብዙ ገንዘብ ከሰበሰቡትና አሽከሮች ከበዙት ሰዎች ጋራ ትክክል ናቸው ። ትክክል ናቸው ። ያልኩህም በጌትነታቸው ነው እንጂ በእውቀትማ የበለጡ ሁነው ታገኛቸዋለህ ወደነሱም ደጅ በደረስህ ጊዜ አንተ እንቅልፍህን ጠግበህ እስክትነሳ ድረስ ከሩቅ አገር የመጣውን እንግዳና የተቸገረውን ሰው አሰናብተው ለመንግሥት ሥራ ተልከው የመጡትን ሁሉ ጉዳይ ፈጽመው ታገኛቸዋለህ መቸም አንተ እንቅልፍ ታበዛለህና ይህንን ሥራ ለመመልከት የሔድክው ከጧቱ ባንድ ሰዓት ይሆናል ። እነርሱም ይህንን ሥራ ሲሰሩ ራሳቸው ናቸው ። እንጂ እናቶ ንገሩልኝና እነወደመታጠቢያ ቤት ገብ ተዋል የሚባሉት ጭፍሮች የሉሉበት ነው ብሎ ወዳጄ ብርሃንና ሰላም በመከረኝ ጊዜ የድሆቹ ነገር ትዝ ብሎኝ እንባ እንቅ እንቅ እያደረገኝ ።

ወዳጄ ሆይ ለዚህ ምንም መልስ አላገኝልህ ለነርሱም ይህነኑ መልክም ምክርህን ብነግራቸው ጌትነት በዝቶባቸዋልና አይሰሙኝም ከዚህ ቀድሞ ወዳጆችህ ለሀገራቸው የሚሆን ብዙ ጥቅም ያለው መማሪያ እንዲገዛና አገርን ለማልማት ባይነት ባይነቱ የስራ ትምሕርትን እንድንማር መክረውን አልነበረምን ስድ ባቸው እያስለቀቀን በ ጊዜ ለሁሉ እያልን እንቆያለን ምን ይሆናል ሐሳብ ሁሉ ባንድ ሰው ላይ ወድቋልና ለርሱ እድሜ እየለመንን መቆየት ነው ። እኛም ያላየነውን ለማየት ያልሰማነውን ለመስማት ያብቃን ብየ ነገሩን በዚህ አቆየሁት ልብ ያለው ይመልከት ምሳሌ ምዕ ፱ ቁ ፩ እስከ ፱ ድረስ ።

ኃይለ እግዚአብሔር ቀፀላ በ

መቅድም ፤

እንደ እውነቱ የፍቅር እና የብርሃን መንገድ በመልክም ያስጀመረን አምላክ በመልክም ያስፈጽመን መልክም ሥራ ሊአደርግ ለሚቃጣ ሰው እንዳይፈጽመው መቃወም አይገባም እንዲህ ይላል ፤ ከለዚህም ከታናሾቹ በኔ ከሚያምኑት አንዱን ያሰናከለ የወፍጮ ደንጊያ ባንገቱ ታስሮ ወደጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለዋል ማቴ ፲ ፲፪ ፤ እንግዴህ እርሱ በርሳችን እንፋረድ ይህንን ፍረድ እንጂ ። ሰንቅፋት ወይም መሰናከያ ለወንድማችን እንዳናደርግ ፤ ሮሜ ፲፬ ፲፫ ፤ ክቡራን ወንድሞቼ ሆይ ይህንን ብዙ ያልታረመ መጽሐፍ ቃል ለመጻፍ ያነሳሳኝ ምክንያቱን ልግለጽላችሁ በውል ለሚያጠናው ሰው የሚያገኛቸውን ጥቅም ደግሞ ማሰብ ነው ። አገራችን ኢትዮጵያ ውያን በየአውራጃው እንደኤሮፓ ትምህርት ያውቁ ዘንድ በትጋት ስለተነሱ ቤት በማስተዋልም ስለጀመሩት እጅግ ያስ ደንቃል ፤ ይህንን ጥበብ አየሁ ከፀሐይ በታች እርሷም በኔ ዘንድ ታላቅ መሰለችኝ ታናሽ አገር ነበረች ጥቂት ሰዎችም ነበሩባት ታላቅ ንጉሥ መጣባት ከበበትም ታላቅ ግምብም በዙሪያዋ ሰራባት ደሀ ሰውም ብልሃተኛ ተገኘባት ያችንም አገር በብልሃቱ አዳናት ከዚያ በፊት ያነን ደሀ ሰው ማንም አላሰበውም ነበር ። እኔም አልሁ ከኃይል ጥበብ ትበልጣለች ከጋሻና ከጦር ይልቅ ጥበብ ትሻላለች ። መክ ፱ ፲፫ ፲፰ ።

ሁለተኛ ክፍል ።

ስለ ቋንቋ ትምሕርት የተማረ ሰው ጥቅሙ በፊት የማያውቀውን ብልሃትና ጥበብ ያውቅ ዘንድ አዲስም ብልሃት ይገለጽለታል ። ዓይኑም ይበራል ፣ ልቡም ይሰፋል ፤ ከትልልቆች ጌቶችና መኳንንቶች ያለ አስተርጓሚ ይነጋገራል ። እንዲህ ይላልና የተከፋፈሉች የእሳት ልሳን ታየቻቸው ከርሳቸውም በያንዳንዱ ተቀመጠችባቸው በሁሉም መንፈስ ቅዱስ መላበቸው በሌላም ቋንቋ ይናገሩ ዘንድ ጀመሩ ። መንፈስ ቅዱስ እንደሰጣቸው ይናገሩ ዘንድ ። ግብ ፪ ፫ ፬ አሁንም የሚጠቅመውን ነገር በውል የተማረ ሰው ከትልቅ ማዕርግ ይደርሳል ። ነገሥታትም በኔ ይነግሣሉ ሹማምንት የቀናውን ነገር ይናገራሉ ምሳ ፰ ፲፭ ።

ሶስተኛ ክፍል

በሾህ ውስጥ የበቀሉ አትክልት አሉ ስማቸውም ሎሚ ትርንጎ ፣ ተምር ፣ ወይንና በለስ እንክይና ክል ፤ መአዛቸው የሚጣፍጥ መልክቸውም የሚያምር ደግሞም በበረሃ ውስጥ ብዙ አትክልት አሉ ፍሬያቸው የሚበላ እሾኻቸው የሚዋጋ ። እስተዋይ ሰው ግን ፍሬያቸውን በብልሃት ቆርጦ ይበላል ። አለ ብልሃት ቆርጦ እበላለሁ ብሎ ለሚገባ ሰው እጁን ይወጋዋል ። ወይም እግሩን እንድ ሳይዝ ተመርሮ ምነው በቀረብኝ አፈር በበላሁ ይሻለኝ ነበር ብሎ ይሄዳል ፤ ሆዱም ሳይበላ እግሩ እያነከሰ ይሄዳል ፣ በነፍስ ተመቅበዝብዞ በዓይን ማየት ይሻላል ። መክብ ፯ ፱ ።

በሰነፍ እጅ የጥበብ መግዣ ገንዘብ ቢኖር ጥበብ ይገዛ ዘንዶ አእምሮ የለውምና ምን ይጠቅመዋል ። በለስ ጨብጨብ ወይኖችም አበቡ የሽታቸውን መዓዛ ሰጡ ብልሃት ያለው ግን አትክልቱን ከትኩቶ ወህ አጠዋቶ ሰውነቱም ከፍሬው በረከት በልቶ ይጠግባል ለጌታውም ገጸ በረከት ይሰጣል ።

አራተኛ ክፍል ።

ልዑል ሆይ ትንሽ ላመልክት
ከባትዎ ከዳዊት የተቀበሉት ።
እውቀት የሰሎሞን ጥበብ መሰረት ፤
እንዲጠፉ ኩራት ደግሞም ትዕቢት ።
እውቀት ያለውን እናጥፋህ ሲሉት ።
የማያውቀውን ሁሉ እንደማመልከት ።
ያወቀውንም አጠፉት በምቀኝነት ።
እንዲህ ከሆነ አይሰፋም እውቀት ፤
እርስዎ ካልሆኑት ጥበብ መድኃኒት ።

የማይጠረጠር አላት ማህቶት ፥
ወራሽዋም አንተ ማንም አይነካት ።

አምስተኛ ክፍል

ተማሪ ሆይ እንደምን ተምሬ እንደምን አውቄ እንደምን ጀምሬ እጨርሰዋለሁ አትበል ሀኬትና ስንፍናን አታሳየው አንተ ታኬት ወደ ግብረ ጉንዳን ሂድ መንገዱን ተመልከት ጠቢብም ሁን አለቃ ያላትም አዛዥና ገዥም፡፡ መብሏን ግን በገበታ ታሰናዳለች የምትበላውንም በመከር ትሰበስባለች አንተ ታካች እስከ መቼ ትተኛለህ ከመኝታህስ መቼ ትነሳለህ መክብብ ምስ ፪ ፳ ትንሽ ምሳሌ ልንገርህ ሠራተኛ ሰው አለ ትልቁን ድንጋይ በመራጃ ሰብሮ በመጥረቢያው ጠርቦ ወደ መዓዘን ወደ ዓምድ ያደርገዋል ። ገበሬ ከእህሉ ግርድና ገለባውን ለይቶ ፍሬውን ወደ ጎታ እንዲሰበስብ እንዲሁ አስተማሪ ለተማሪው ተግቶ አስተምሮ ድንቁርናውንና ስንፍናውን ለይቶ አሳውቆ ወደ ማስተዋል ያደርሰዋል ። አንተም በመታገስና በመቆየት ከድንቁርና ነፃ ሁነህ እውቀትን ታገኛለህ እኔም ብርሃን ከጨለማ እንዲሁ ከድንቁርና ጥበብ እንድትበልጥ አየሁ ፤

ስድስተኛ ክፍል

ለአንካሳም ምርኩዝ ለእውርም መሪው ።
ለራበው ለጠማው ፈቃጅ መጋቢው ፤
ለደንቆሮው እውቀት አስተዋሽ ልብም ፍቅር የመላው ።
አስደነቀኝ ባስብ ብመለከተው ።
ብጹዕ ተፈሪ የኢትዮጵያ ተስፋው ፤
ከሰው አገር ቅናት ሕዝብም ሊድን ነው ።
ታጥቀው ተነስተዋል በዘንን አባረው ።
በትምህርትም ወገን እኛም እንርዳቸው ።
ጥቅሙም ለኛ ነው ለሐገር ሕዝባቸው ።

ይኸንን ብዙ ያልታረመ ቃል መጻፌ እውቀት ኖሮኝ ራሴን ለማስመስገን አይደለም ያገሬ ፍቅር ቢይዘኝ ነው እንጂ

አበበ ተክለ ጊዮርጊስ ፡፡

ይኸንን ደብዳቤ ለብርሃንና ሰላም አመለከታለሁ ።

የክፉንና የደግን ኑሮ ክፉ ለራሱ ደግም ለራሱ ነው ክፉ እራሱን ጎድቶ ሰውን ጨምሮ ይጎዳል ላጥፋ እንጅ ላልማ አይልም በሰው ላይ ምቀኝነት ሰውና ሰውን በመካከላቸው ነገር አዋስቦ ማቀያየምና በማይረባ ነገር ማጋደል ነገራቸውን እንዳይጣጣሙ ማድረግ መስራት እያለ የሰው ክብት መስረቅ ይህ ሁሉ ከንቱ ነገር እግዚአብሔር የሰራውን አካል የገዛ እራሱን እከ መጉዳት ነው ሰው ለኑሮው ስራ ሰርቶ ደክሞ ማስኖ ለጌታ ወይም ለቤተ መንግሥት ቢያገለግሉ ገበሬም አርሶ እህሉን ቢያከማች ክብርና ሃብት ብልጽግና በተገኘ እረ ይህ ሰው በዋዛ በፈዛዛ እድሜውን በከንቱ ለምን አሳለፈው ዛሬን እንጅ ኋዘን የማያውቅ አንድ ጨከኝ ክፉ የተባለ የዘረፈውን ገንዘብ ይዞ እርህራሄ የሌላቸው ከሚባሉ ጓደኞቹ ጋር ወደ ጋለሞታ ቤት መሸታ ሊጠጡ ገቡ ይበላም ይጠጣም ጀመር አዝማሪም ሊጫወት ቆመ ያዝማሪውን ድምጽ እየሰሙ ብዙህ ስራ ፈቶች ገቡ ላዝማሪውም ግጥም ይነግሩታል በፊት ጨከኝ የሚባለው ሽፍታ እንዲህ ይላል የሚፈራው የለ ፈረሴ ጨከኝ ። አንድ ቀን አይከፋኝ ችግር አይነካኝ ። ሁልጊዜ በተድላ እኔ ብቻ ነኝ ። ወዲያስ ወዲህ ብዬ መቼ ጎሎብኝ ። ይልና ሰነፎች ደግሞ እንዲህ ይቀኛሉ ጥንቱንም አለመድን አርሰን ስራ ሠርተን በባቶቻችን ቤት አደገን ተቀማጥለን መቼ ቸግሮናል ለየጉሮሯችን ተስከርና ዝክር እየቀላወጥን እያሉ ሰስንፍና አባጨከኝ ይቀልዳሉ ነገር ግን እርህራሄ በሌለው ጭካኔ የስንፍና በህርይ እየሰረቁና ሲነጥቁ ይኖራሉ ኖረው ኖረው አሽከላ ሳይገቡ አይቀሩምና አምላክ ይፈርድባቸዋል ንጉሥም ይቀጣቸዋል ይሞታሉ እነኝህ ከንቱዎች መጨረሻቸው ከንቱ ነው የክፉ መጨረሻው ክፉ ነውና የሰው ገንዘብ በመይረባ ቢነጥቁ ቢዘርፉትም ብድር በምድር አይቀርም ያከፋፍላል ወንድሞቼ ከንደዚህ ያለው ላይ መሰብሰብ ነው ክፉ ለመስራት ይቅርና ክፉ ከሚሰሩ ጋር ለመዋል አያስፈልግም ክፉ ያስተምራሉና ።

ደግ ለራሱ የተባለው ኑሮው ደግ ነው እርሶ ደክሞ ወጥቶ ወርዶ ከዚያ ከደከመበት ገንዘቡ ለምስኪን ለችጋረኞች ይሰጣል ሰው ቢሞት አልቅሶ ቢጣሉ አስታርቆ ይኖራል ከስራውም አይደክምም ከሰነፎች ጋርም አይውል ሰው ከሱም ጋር ቢውል መልካሙን ትጋት መስራት ማትረፍን ያስተምረዋል ቅሉ እገሌ ወዴት ዋለ ቢባል ከገሌ ጋር ሲሰራ ዋለ ሲባል ብርቱ እንጂ ሰነፍ አይባልም ደግሞ ሰው በከንቱ እድሜውን ለምን ያሳልፈዋል ጓደኞቹ ሲሰሩ እሱም እንደነሱ ቢሰራ ቢጣጣር እንዴት የተሻለ ኑሮ በሆነ ነበር ይህ መባሉ በጅ ሥራ ብቻ አይደለም በምክር በመታመንም በመስራትም ሆነ ለገጋር ተገጋር መሆን ይኸንን በመሰለ ስራ ሁሉ ነው በቤተ መንግሥት መከር ቢሆኑ እራሴ ልጠቀም ሳይሉ ላገርና ለመንግሥት የሚጠቅመውን ምክር መፈለግ ግምጃ ቤት ወይም ባለምዋል ቢሆኑ መታመን ግምጃ ቤትም ተጠንቅቆ ገንዘቡን መጠበቅ ገባያም እቃ ሊገዛ ቢወጣ የሚያተርፍ እቃ ቢያገኝ ለራሴ ሳይል ትርፉን እስከዋናው ወደ ግምጃ ቤት መመለስ መከርና ባለምዋል ቢሆን ጌትዮው ምስጢር ቢያጫውተው ምሥጢሩ እውጭ እንዳይገኝ አለማባከን ነው የጌታና የባልንጀራ ምሥጢር እንደ ዕንቍ ይከብራልና ደግ ቢሆኑ ደግነት በሕይወትም ሳሉ በሕይወትም ሲያልፍ ይጠቀማል ።

ጥበብ ሞልቶ ካገር አለመማራችን ። በሥላሴ አርአያ ተፈጥረን ሁላችን ። ሰነፎች ተብለን ምነው መቅረታችን ። ሌላስ አዶለ አዳም አባታችን ። ከሁሉ እኩል ነን በተፈጥሮታችን ። መልካምን ጐዳና አለመሄዳችን ። ወንድሞቹ ሆይ ይህችን እንድታነቡልኝ አበረከታችኋለሁ ። ባጠፋሁ እከሳለሁ ባሻ አ…

ከግሪክ ታሪክ የተገለበጠ

እንዴት ይጓዛሉ ሕዝባቸውን ለማየት ሶስት የንጉሥ
ልጆች ከብዙ ጊዜም በኋላ ወዴት ደረሱ ፤

አንድ ዘመን አንድ ንጉሥ ነበረ ፥ ይኸውም ሶስት ልጆች ነበሩት ፥ ሁለቱ ትልልቆች ክፉና ቂሎች ነበሩ መጨረሻ ትንሹ

የዋህና ርጉ ነበረ ። አባታቸው አንድ ቀን ጠርቷቸው እንዲህ አላቸው ። ልጆቼ አሁን ከደጋችሁ ያስፈልጋችኋል መንዝ ሕዝብን እንድታውቁ አሁንም የተሻለና ፈላስፋነትን አውቃችሁ እንድትመለሱ ሂዱ አላቸው ፤ ሲሄዱ ሲሄዱ ሶስቱ ወንድማማቾች አንድ የጉንዳን ዋሻ አገኙ ፡ ሁለቱ ትልልቆች አሉ ኑ አደጋ እንጣልባቸው ምን እንደሚያደርጉ ትንንሾቹ ጉንዳኖች ወደ ላይና ወደ ታች ሲሮጡ እንቁላላቸውንና ምግባቸውን ሲያመላልሱ እንይ ትንሽየው ወንድም ለዚህ ለወንድሞቹ ክፉ ሃሳብ አዘነ ለመከረኞቹም እንስሳዎች አይደለም አትንኳቸው እኛ ቤታችንን ሊያፈርሱብን ገንዘባችንን ሊያጠፉብን እንደማንፈልግ እንደዚሁም ጉንዳኖች ራቅ ብለው አንድ ኩሬ አገኙ ዳክየዎች ይዋኙበት ነበር ። ትልልቆቹ ወንድሞች ኑ ሁለቱን ይዘን እንጥበሳቸው አሉ ። ትንሽየው አይደለም እንልቀቃቸው ይጫዋቱ የፀሐይን ረድኤትም ያግኙ አለ ። ራቅ ብለው አንድ የንብ ቀፎ አገኙ ። እውስጡም ብዙ ማር ነበረበት ። ኑ እውስጡ ጢስ አጢሰንበት ንቦቹን አስከረን ማሩን እንውሰድባቸው አሉ ሁለቱ ትልልቆች ወንድሞች ተዋቸው በደኅና ይቀመጡ ደኅናዎቹ እንስሳዎች አንድም ክፉ ነገር አልሠሩን ስለምን እኛስ ክፉ እንስራባቸው አለ ትንሽየው ወንድም ሲሄዱ ሲሄዱ ሶስቱ ወንድማማቾች በመጨረሻ አንድ ጥሩ ጽ(.)ሐ መንግሥት ደረሱ ማድቤቱ ከፈረሶች ሙሉ ነበረ ። ሐውልት ሁነው በሮቹ ክፍቶች ነበሩ ግቢውም ማር በቅሎበት ነበረ ።

ትንሹ ግርላ ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው ([illegible])ማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲፪ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፫ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር ።	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነርትጓሜው	፯ብር
ኅሐ ጽባሕ ።	፫ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትንርሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ሩብ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ከ፫ ሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲ ብር ፫ ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር ተኩል ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፫ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፮ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲፩ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲ ፫ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፵፫ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፯ ብር
፡፡ ባለ ድመት ፡፡		፻፴፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፪ ብር
፡፡ ባለሳቤ ግመል	፡፡	፻፳፯ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፫ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፰ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ
አንድ ብር	፲፩ ሊሬ እስከ ፺፫ ሳንቲም
ባንድ ጊኒ	፲ ብር ፳፯ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር

ማመልከቻ ።

ቀይ ዝጉርጉር ጭራዋ ቆራጣ ጆሮዋ ትልልቅ የኢጣልያን ውሻ ጠፍታለችና ይችን ውሻ አግኝቶ ለፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው የሰጠ ሰው እንደሚገባ ጉርሻ ያገኛል ። መስከረም ፳፬ ቀን ፲፱፻፳ ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

COGNAC S.a E.a A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሐ ሚ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVRGLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

የእጅ ሰዓት ዝኒት



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶሞቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል"አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ"ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፡በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪከን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ክች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፣ ሸቱ ፣ ለስ ዮን ፣ አድከሎኝ ፣ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፣ ኳኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፣ ከፈይ ምንጣፍ ፣ ደገሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና ከሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፣ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ኤን ቤ ኔዲሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሸቶና ሎሲዮን አዶከሎኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሸቶና የአዶኮሎኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ። የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቀውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

ዓ ለ ም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠ ራል ። ኒክላ ።



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አስ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲከ ጉድየር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደ ግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆ ን አያስፈራም እንደልብ ያስኬዳል በድጥም በፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስ ቲክ ሁሉ ጠንካራነው በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድየር ግዙ ከሌላው ላስ ቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩ ል ነው ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘ ው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

ጉዶደርገዘ

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤኼስኪልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፣ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፣ መጫሚያ በያይነቱ፣ ወንበር በየዓይነቱ፣ ብረት ማጥን በየዓይነ ቱ፣ ቢሲግሌት ፣ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፣ ፋኑስ በየዓይነቱ ፣ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፣ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፪
3 me ANNÉE № 42

ሐሙስ ጥቅምት ፱ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 20 OCTOBRE 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ትምሕርት ቤት መከፈት ።

የልዑል አልጋ ወራሽ ትምሕርት ቤት ስለ አስተማሪዎችና ስለ ተማሪዎች ዕርፊት ተዘግቶ ከርሞ ነበርና ጥቅምት አንድ ቀን ተከፈተ ። በዚሁ ቀን ተማሪ ቤቱ በልዩ ልዩ አበባ አጊጦ ነበር ። ተማሪዎቹም መለዮ ልብሳቸውን ለብሰው ለማየት የሚያስጐመጁ ሆነው ይታዩ ነበር ፤ ልክ ፲ ሰዓት ሲሆን ልዑል አልጋ ወራሽ በኦቶሞቢል በደረሱ ጊዜ ጣዕመ ዜማው በሚያምር ሙዚቃ መዝሙር ተዘመረ ። ተማሪዎቹም ካስተማሪዎቻቸው ጋራ ተሰልፈው የክብር ሰላምታ ሰጡ ። ከዚህ በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽ በየክፍሉ እየገቡ ያዩ ጀመር ። ተከትለዋቸው የነበሩትም መኳንንቶች የቤቱን መታደስና የሥራውን መከናወን እያዩ ሲያደንቁ ይሰሙ ነበር ። ከዚህ በኋላ በልዩ ወደተሰናዳው ቤት ገቡና የሻይ ግብዣ ሆነ ። ይህ ሁሉ ሲሆን ሙዚቀኞች በውጪ ሆነው ይዘምሩ ነበር ። ተማሪዎቹም ግራና ቀኝ ተሰልፈው የኢትዮጵያን ብርሃን ዘለዓለም ያኑርልን የሚለውን መዝሙር ዘመሩት ።

ከሻይ በኋላ ክቡር ሙሴ ቶማስኒ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ልዑል ሆይ ።

የአሁኑ መከፈት ተማሪ ቤቱ ከቆመ አራተኛውን ዓመት መጀመሩ ነው ። የዚህ ተማሪ ቤት መቆምም የልዕልናዎ የስልጣኔ አሳብና የብልህነትና የእውቀት መውደድ ይመሰክራል ደግሞ ልዕልናዎ የቀንጆይቷ የኢትጵያን ልጆች ከውጭ አገር ስልጣኔና እውቀት ማግኘቱ እንዲያው በደግነት ነውና የቸርነት ሃሳቡን ይመሰክራል ።

ልዑል ሆይ ልዕልናዎ እየተመላለሰ የትሕምርት ቤቱን በመጐብኘቱ ለቆመው ሥራ የሚያስበውን ጥቅም ሁሉ ያሳያል ይኸንን ጥቅም ለኛ ላስተማሪዎችና ለተማሪዎች አንድ የከበረ ማበረታቻ ነው ። ስለዚህ የማክበር ጥልቅ ምስጋናችንን ለልዕልናዎ በጓደኞቼና በተማሪዎቹ ስም አቀርባለሁ ። ልዕልናዎ የኢትዮጵያውያንን ተማሪዎች ብዙ ዓይነት ከማንም አብልጦ ያውቀዋል ፤ በምሳሌ በነሱ ዘንድ የሥራ መውደድ በንዴት ያለ ከፍተኛ ደረጃ እንዳለ እርሱ ያውቃል ። እጅግ ትልቅ የሆነውን ችግር ለማሸነፍ የሚችል ኃይል እዚህ ካንድ ጠሊቅ ብልህነትና ካንድ የተገባ ቡሩክ ሃሳብ የገጠመ ነው ። ስለ አገሩ ደህንነት መማር ደግሞ እንደዚህ ካለ ጥንክሬ ጋራ ከዚህ ዓመት ጀምረን አንድ እውነተኛ ማሕፈድ ለማከናወን የተቻለን እንደ ሆነ ምን ያስደንቃል ። በአራት ዓመት ብቻና በፍጹም አደራረግ የፈረንሣዊ የመካከለኞቹ ተማሪ ቤቶች የስድስት ዓመት ትምህርት ማስታወቂያ ስለዚህ ልዑል ሆይ ልዕልናዎ የሚጥረውን ሁሉ ተማሪዎቹ ፍጹም ማወቃቸውን ለማወቅ ይቻለዋል ያባትነት ምክሩን በሚገባ ይቀበላሉና ፡ ይኸም ዓመት እንደ ዘ● ትር ያለንድ ጥርጣሬ ማለት በቀስታ ግን በርግጥ ያዲሲቱ ኢትዮጵያ ልማት እያሰፉ በሙሉ ልባቸው ያጠናሉ ።

ከዚህም ቀጥሎ ክቡር አቶ ኤፍሬም ተወልደ መድኅን የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ልዑል ሆይ

የተማሪ ቤቱ ሹም ክቡር ሐኪም ወርቅነህ ወደ አውሮፓ አገርና አሜሪካን አገር ተልከው ስለሄዱ ዛሬ ቀን እመካከላችን ባለመዋላቸው እያዘንኩ በርሳቸው ስምና በሙሉ ተማሪ ቤቱ ስም ሆኜ ተማሪ ቤታችን ከዕረፍት ወራት በኋላ በሚከፈትበት በዚሁ ቀን በመምጣታችሁ የተገባ ምስጋናችንን ላቀርብላችሁ እለምናለሁ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለተወደደችው አገራቸው ከሚያስቡላት ትልልቅ ኃሳቦች

እንዲ ኢትዮጵያ በትምህርትና እውቀት ከፍ እንድትል ስለሆነ ይህን ተማሪ ቤት በብዙ ኪሳራ አቁመው ሲያበቁ እያደገና እየሰፋ እንዲሄድና የበለጡ ተማሪዎች ሊማሩበት ፈቃዳቸው ስለሆነ ይኸው አዲስ የመማሪያ ክፍሎች ያሠራሉ ። የትምህርቱንም ሥራ እንዲሰፋ ብለው አዲሶች የፈረንሳይና የእንግሊዝ አስተማሪዎች ለማስመጣት ስለተላላኩ ከትንሽ ቀን በኋላ ይገባሉ ብለን እንጠባበቃለን ። ደግሞም የቋንቋዎች ትምህርት ብቻ አይበቃም ብለው የኢትዮጵያ ልጆች የእጅ ሥራና ጥበብ እንዲማሩ ብለው በዚህ ተማሪ ቤት ግቢ ውስጥ የእጅ ጥበብ ሥራዎች መማሪያ ቤቶች አቁመዋል ።

ልዑል ሆይ

ሰው ለሚደክምበት ነገር ሁሉ የድካሙን ፍሬ ለማየት ነው ዋና ተስፋውና በዚህ በተማሪ ቤትዎ የሚማሩ የኢትዮጵያ ወጣቶች በብልህነታቸውና በትጋታቸው ባለተስፋዎች መሆናቸውን አረጋግጥልዎ ዘንድ እየለመንሁ ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥት ዕድሜ ለልዑልነትዎ ሰላምና ደስታ ለኢትዮጵያ እመኛለሁ ።

ከዚህ በኋላ ለተማሪዎቹ ጣፋጭ ምግብ ተሰጠና የተማሪ ቤቱ መከፈት ተፈጸመ ።

መልካም አርአያ

፲፱፻፲፱ ዓ ም ሐምሌ ፲፰ ቀን ወይዘሮ የሽመቤት ተፈሪ ንና የርሳቸውን ፫ ልጆች የክቡር ብላታ ጎሩይን ልጅ ክቡር ሐኪም ወርቅነህ ይዘው ወደ እንግሊዝ አገር ስለሔዱ ዘመዶቻቸው ሁሉ ያዝኑ ይሆናል ። ማለት ከዚህ ቀደም ያልተለመደ ነገር ነውና ይህንንም ሀዘንና ጭንቅ ተመልክቶ ካሰብንበት በኋላ ክርስቶስ በደህና ስላደረሰን ደስታችንን ለሁሉ እንገልጻለን።

ክቡራን ወይዛዝርና መኳንንት ሆይ ።

ወይዘሮ የሽ እመቤት ተፈሪ ስለጤናቸው ወደ እንግሊዝ አገር መሔዳቸውን ሌላም ብዙ ቁም ነገርና አርአያ ይከተለዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ። ፩ኛ በጤናቸው ምክንያት ከዚህ ሲቀመጡ ትምህርት ያገኛሉ ትምህርት ብቻ እንኳ ቢሆን በሌላም በኤውሮፓ አገር ይገኝ ነበር ። ነገር ግን አብረዋቸው የሔዱት ልጆች የተማሩት እንግሊዝ ስለሆነና ለርሳቸውም ጤና የሚስማማ የእንግሊዝ አገር ስለሆነ ነው ።

ደግሞ አንድ ነገር ላመለክታችሁ እወዳለሁ እኒህ ሴቶች ልጆች ለትምህርት ወደ ኤውሮፓ መሔዳቸው ለሀገራችን እንግዳ ነው ። ነገር ግን ዋና ጥቅም ነው ። ማለት ትምህርት ለሁሉ የሚያስፈልግ ነው ።

ስለዚህም የታመኑ አሽከራቸውን ምክር ሰምተውና ለሴቶች ትምሕርት ማስፈለጉን ተረድተው ለሕዝብ ምሳሌ እንድትሆን በመጀመሪ የርሳቸውን ልጅ የሥልጣኔ መሥዋዕት አድርገዋልና ልዑል የኢ መ አ ወ ተፈሪ መኰንን ማዳነቅና ማጋነን ይገባናል የዚህንም ጥበብም ለገለጹ ለክቡር ሐኪም ወርቅነህ ምስጋና ይገባቸዋል ። ይህንንም ማለታችን የኢትዮጵያ መኳንንትና ሕዝብ የመንግሥት አርአያ ተከታይ ነውና እንደዚሁ የኢትዮጵያ መንግሥት ሕዝብ ሁሉ ሴቶችና ወንዶች ልጆቻቸውን በመላ ኤውሮፓ ፈጥነው መስደዳቸው አይጠረጠርም ይኸውም ሊታወቅ ብልሁ ዶጃዝማች ወንድይራድ ልጃቸውን ለትምህርት ከኛ ጋራ ወደ ፈረንሳዊ አገር በመላካቸው የመኳንንቱና የሕዝቡ አሳብ ለትምህርትና ለስልጣኔ መሆኑን ይገልጽልናል ለወደ ፊትም ኢትዮጵያ የጃፓንን መንገድ ተከትላለች ለማለት ይቻለናል ይህንንም መንገዳችን በተፈሪ ሥልጣን በፍጥነት እንራመደዋለን ስል ታላቅ ተስፋ አደርጋለሁ ። ይልቁንም የሴቶች መማር ለመንግሥትና ለወንዶች ህይወት ነው ስለምን ማለት ።

፩ኛ የተማረች ሴት ያለችው ሰው ለቤት አሳብ የለበትም ሁሉም በርሷ ሥልጣኔ ይከናወናል እርሱም ባንድ ልቡ የመንግሥቱን ሥራ በጥንቃቄ ያስኬዳል ይህ የሀገር ጥቅም ነው

፪ተኛ ለመንግሥቱና ለትዳሩ በ፪ ወገን ያስብ የነበረው ሰው አንዱን አሳብ እርሷ ትችልለታለች ልጆቹን ታስተምራለች ጤናቸውን ትጠብቃለች በመልካም ግርአያ ታሳድጋለች ።

ይህ የወንዶች ጥቅም ነው ። ይህም ሊታወቅ ለምሳሌ ክብርት ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ (፩ደኛ) ባላቸውን ከቤት አሳብ አድነዋል ።

፫ተኛ ዛሬ ክቡር ሐኪም ወርቅህ ስለ ተላኩ የርሳቸውን ሥራ ሁሉ በትክክል በፍጹም እምነት ይሰሩላቸዋል ። እንዲህ የሴቶች ትምህርት ለወንዶች ጥቅም ነው ከራሳቸውም ይልቅ ወንዶችን ይረዱብታልና ስለ ዚህ የሴቶች ተማሪ ቤት መስራት ያስፈልገናልና በጣም እናስብበት ።

ክቡራን ወይዛዝርና መኳንንት ሆይ ።

ይህ የሴቶች ልጆች ወደ ውጭ አገር መሔድና መማር ያዋ ተለመደ ነገር ሆነና ዛሬ ቢያሳዝናችሁ ለኋላ ደስ ደስ ይላችኋልና የሴቶችንም የትምህርት ጥቅም ከላይ እንዳልነው ትረዱታላችሁ ።

ለምሳሌ ከዛሬ በፊት የወንዶች ተማሪ ቤት በቆመ ጊዜ ወንዶች ልጆች ለትምህርት ወደ ውጪ በሔዱ ጊዜ ታዝኑ ነበር አሁን ግን ጥቅሙን ስለ ወቃችሁ በደስታ ብዙ እርዳታ ታደርጋላችሁ እንደዚሁ ወደ ፊት የሴቶች ልጆች መማርና የሴቶች ተማሪ ቤት መስራት ደስ እንዲያሰኛችሁ አይጠረጠርምና ይህችን ማስታወሴን እንድትቀበሉኝ እመኛለሁ ስህተትም ቢኖርበት ይቅርታችሁን በትህትና እለምናለሁ ።

መስፍን ቀለመ ወርቅ

ሰለ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ምስጋና

ልዑል ሆይ ኢትዮጵያን አገርዎን ሊአስፋፉአትና ሊአክብሯት በትምህርትና በጥበብ ከውጭ አገር እንዲበልጥ ብለው አስበው የስንፍናን ንጉሥ ድንቁርናን አባረው የትምሕርት ቤት አሰርተው የጨለማውን ማብረሪያ ብርሃኑን አምጥተው ኢትዮጵያን አገርዎን በሙሉ ብርሃን የከበብዋት በልዑል ኃይል ፈጽሞም ብርሃን የሆነልን ። አሁንም ልዑልን የልዑላን በላይ ያድርግልን የኢትዮጵያ ብርሃንና ሰላም ክትውልድ እስከ ትው

ልድ ያስተላልፍልን ይህ በየሰምንቱ ሐሙስ ሐሙስ ለት የምናየው ብርሃንና ሰላም እንዳይጐድልብን እስከ መጨረሻ ዓለም ያኑርልን ብዬ የደስታ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

አሁን እኔ የምስኪናን ድሐ ነኝ ይህንን ቃል ከልዑል ፊት ቁሜ ለመናገር አልችላውም ገና በሩቅ ሳለሁ በወደቅኹኝ በነር ድንጋጤ ነገር ግን ብርሃንና ሰላምን የልዑልን ጋዜታ ለኢትዮጵያ መብራት ለጠላት መመከቻ ጋሻ ለአገርዎ ጥቅም ለድሃዎ ተስፋ የሆኑበትን በብዙህ ገንዘብ የጽህፈት መኪና ገዝተው የትምህርት ቤት አሰርተው በዚያ ተምረው የልዑል ጸሐፊዎች ጋዜታውን አትመው የመጣውን ታምርና ድንቅ የሚባል ነገር ባየሁና በሰማሁ ጊዜ እንብዛም ደስ አለኝ ከብዙ ደስታም የተነሳ ምን ምን እለብስ እያልኩ ሌትና ቀን አስብ የነበርኩ ምስኪን ድሐ የልዑልን ታምርና ድንቅ በጋዜታ ብመለከተው አሳቤ ተረስቶኝ እንቅልፍ ተኝቸ አደርኩ ። የዓይን ብርሃ ልብን ደስ ያሰኛል መልከም ወሬም መስማት አጽንት ያለመልማል መ ምሳሌ (፲፫ም ቁ ፴ ፳፫ም ቁ ፳፭) በቅንነትና በበረከበት አገር ከፍ ከፍ ትላለች ምሳሌ ፲፩ም ቁ፲፩ አሁንም ልዑል አልጋ ወራሽ ኢትዮጵያን በቅንነትና በደግነት እያስተዋሉ ንጉሥ ነኝና እንደልቤ አደርገዋለሁ ሳይሉ በፍቅርና በትህትና ድሐቸውን አክብረው ድሐ ነው ብለው ሳይንቁ እግዚአብሔር በሚወደው አገሩን ገዝተው ያልተማረው አስተምረው የሌለውን ሰጥተው የራበውን አብልተው የጠማውን አጠጥተው አመጠኛውን ቀጥተው በሙሉ ብርሃን ከበው ከፍ ከፍ ስለ አደረጓት አገርዎ ኢትዮጵያ በደስታ ጨኸት በሰዓት በሰዓት እልል ትላለች ።

ደግሞ እኔ እንደዚህ እልኩ እንኳን ትውልዴ በዚህ ዘመን ሆነ ብዬ ስለምን ማለት ቀድሞ ያለፉት ዘመዶቻችን አባቶቻችን እንደዚህ ያለ ታምር የሆነ ነገር ሳያዩ በወዲያ አገር እንደዚህ ያለ ነገር ይደረጋል እያሉ በወሬ አለፉ ደግሞ የቀድሞ ሕዝብና ነገሥታት አይስማሙም ነበሩ በምን ማለት ነገሥታቱም አሳባቸው ሹመትና ቁመት ከልክ እያልፍም የሚባል ተረት አለ ይህንን እያሉ እያሉ ድሐቸውን እያጻፉ እያጋፉ ይገዙት ነበር ደግሞ ንጉሥ ወደመንገድ ሲወጣ አብሮ የሚወጣውን ዋና ገበር አድርገው ያለመጠን ይበድሉት ነበር ስለዚህ ድሐውም እኛ ምን ቸገረን መቸም ከመገዛት አናልፍ እያለ ጠላት ሲመጣ ዝም ብሎ መንገድ ለቆ ያሳልፍ ነበር ። ንጉሥና ድሐ አንድ ቃል ቢሆን የኢትዮጵያ ድንበር ብዙ ሳይመስለኝ አይቀርም ድሐ ለንጉሥ ባለመርዳቱ አጼ ቴዎድሮስ ከመክከል አገር በጠላት እጅ ሞቱ ይባላል ይህ ትልቅ መታሰቢያ ነው ። አሁን ግን እስመ አልቦ ነገር ዘይሰዓኖ ለእግዚአብሔር እንዳለ ቅዱስ ገብርኤል ቸርነቱ የማያልቅበት አምላክ እስከሁን ያለፈውን ጥፋታችንን ድንቁርናችንን አስቦ ለኢትዮጵያ መብራት ለጠላት መመከቻ ጋሻ አድርጎ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ብርሃንና ሰላም ብለው ሰይመው በወሬ የምንሰማውን በዓይናችን ያሳየን አምላክ ቸርነቱ ይብዛ ምስጋናው አይጓደል ክብሩም ለዘላለም ይሁን ያ የኢትዮጵያ ብርሃን ብሎ የሰየመልን ከብርሃኑም ላይ ብርሃን ይጨምርለት ለሰላሙም ሰላም ያብዛልን ። የጠላት መመከቻ ጋሻ ይሁናችሁ ብሎ የሰጠንን ጋሻውም ወርቅ በወርቅ ላይ ይደረ‌ረብ የልዑልን እድሜአቸውን ያርዝምልን መንግሥቱን ያስፋልን የማይነቃነቅ የብረት ምሰሶ ያድርግልን አሁን እኔ ይህን ማለቴ ታምራቱንና ድንቁን ከሰው እየተዋሰኩ በመለከተው ባነበው የልብ ደስታ ይዞኝ ነው እንጂ እውነት ከልዑል ፊት የሚነበብ ጽሕፈት ተችሎኝ አይደለም ድሐ የጠገበ ለት እራቁቱን ይውላል እንደሚባል እኔም ጻያፉን የማላውቀው እንደመሰለኝ እንደታየኝ ጻፍኩኝ ክቡራን አንባቢዎች ሆይ የከበራችሁና የተመሰገናችሁ ጸያፉን አርማችሁ ልታነቡልኝ ከጫማችሁ ወድቄ እለምናለሁ

ኃይሉ ገብረ ማርያም መቀሌ ።

የ፫፻፴፭ ገጽ ተከታይ ።

ከግሪክ ታሪክ የተገለበጠ

የእብነ በረዱን መሰላል ወጥተው ትልልቆቹን የጽርሐ ንጉሡን አዳራሾች አልፈው ግንቦቹ በስዕል ተሸልመው ነበሩ ። ደረጃውም በባለ ብዙ ዋጋ ሥጋጃ ተነጥፎ ነበረ ። ክሪስታል ማብሪያ ብዙ ተሰቅሎ ነበረ ። በወርቅ ቀፎችም ውስጥ የድንጋይ ምሮች ነበሩበት ። ዘጠና ዘጠኝ አዳራሽ አልፈው በመጨረሻው መቶኛው አዳራሽ ደረሱ ። በሩ ዝግ ነበረ ። በመከከሉ አንድ ቀዳዳ ነበረው ሶስቱም ጐንበስ ብለው አዩ አንድ ሽማግሌ ባለ ነጭ ሪዝ አንድ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ። አዩ አንድ ጊዜ ጠሩት ሁለተኛ ጠሩት አልሰማም በሶስተኛው ግን ሰምቶ ተነስቶ በሩን ከፍቶ በሶስቱ ንጉሥ ልጆች ፊት አልፎ በጁ ጠቀሳቸው እንዲከተሉት ወደ አንድ እልፍኝ የከበረ ገበታ የተዘረጋበት ወሰዳቸውና ሄደ ።

እንዴት ዳኑ የንጉሥ ልጆች ከአንድ የሚያስፈራ አደጋ

ሶስቱ ወንድማማቾች ምሳቸውን ደሕና አድርገው ከተጋበዙ ወዲያ ለግሩመኛው ጽርሐ መንግሥት መነጋገር ጀመሩ ሁለቱ ትልልቆች ይፈሩ ነበሩ ትንሽየው ግን እያበረታታቸው ይላቸውም ነበረ ለምን እንፍራ ክፉ ነገር ስራን አይደለም እንግዲአውስ እግዚአብሔር ያለእርዳታ አይለቀንም አታስታውሱምን ስንት ጊዜ ስንት ጊዜ አባታችን ይለን ነበር ። (ጉም የሌለበት ሰማይ መምብረቅ አይፈራም) ትልልቆቹ ግን ራሳቸውን እየነቀነቁ ከፍራታቸው ይንቀጠቀጡ ነበሩ ያን ጊዜ ዝምተኛው ሽማግሌ ሲመጣ አይተው ሶስቱም ተነሱ ማን ልበል ወዴት ነው ያለነው አለ በድፍረት ትንሽየው ሽማግሌው ግን በዚህ ጥያቃ መልስም አልሰጠ ጥየቃውንም የሰማ አልመሰለ እጁን ብቻ አነሳና ትልቅየውን ወንድም እንዲከተለው ጠቀሰ እሱም በድንጋጤ ተከተለው ትንሽየው ያን ጊዜ ወንድሙ ከጠገቡ ሲአልፍ አትፍራ አንድ ነገር የመጣብህ እንደሆነ ጥራን አለው ።

ሽማግሌው መራ የንጉሡን ልጅ ከአንድ የንጨት ጠረጴዛ በጣቱ ጠረጴዛው ላይ የፍልፍል ጽፈት ተጽፎበት የነበረውን አሳየው የንጉሡ ልጅ ጐንበስ ብሎ አነበበ ።

መጀመሪ ሙከራ ሺውን አልማዝ ከንጉሷ ልጅ ወደዱር የወደቀበትን ፀሐይ ሳትጠልቅ ያገኘህ እንደሆነ የመጀመሪ የጽ

ርሐ ንጉሡ ነፍስ ይመለሳል ። ያላገኘሀ እንደሆነ አንተም ሐውልት ሁነህ ትቀራለህ ።

ታላቅዬው ወንድም ወደዱር ሮጦ ሺውን አልማዝ የንጉ ሡን ልጅ ሊፈልግ ፀሐየዋም ጠለቀች መዱ ስንኳን አላገኘም ያኔውን እሱም ሐውልት ሁኖ ያለመንቀሳቀስ በጽርሐ መንግ ሥቱ ግቢ መካከል ቆመ በሌላው ቀን ሁለተኛው ሄደ ከጠዋት እስከ ማታ አልማዙን ሊፈልግ ግን አምሰም አላገኘ ። ያኔውን ፀሐይ እንደጠለቀች እሱም ሐውልት ሆነ በ፫ኛው ቀን የትንሽዬው ተራ መጣ ወደ ዱር ሮጠ ያኒውን የጉንዳኑን ንጉሥ አገኘ በጉዞ ጊዜ ነፍሱን ያዳነውን አትጨነቅ መስ ፍኔ አለው ብድር መላሹ የጉንዳን ንጉሥ እኔና ሕዝቤ አልማዙን እናገኝልሃለን ያኔውን ጉንዳኖቹ ወደ ዱር ተበታት ነው በአንድ ጊዜ አንድ ቁልል አልማዝ ከየዋሁ የንጉሥ ልጅ እግር በታች ተገኝቶ ነበረ መጀመሪያው ሙከራ አለቀ ሁለተ ኛው ሙከራ ነበረ ከኩሬው ስር የአደራሹን ቁልፍ የንጉሡን ልጅ የተቀለፈበትን እንዲያገኝ እሕ አንዴት ልውረድ ያስብ ነበረ ያኔ ድምጡን ሰሙ ዳኪየዎች ነፍሳቸውን አድንዋቸው የነበረው፣ ወደ ስር ሰምጠው ያኔውን የንጉሱዋን ልጅ ቁልፍ አመጡለት ሶስተኛው መጨረሻው ሙከራ በባም የተሰናከለ ነበረ በሩን የከፈተ ጊዜ አንድ ትልቅ አልጋ ታየ በዚያም ሶስት ውቦች ሴቶች ተኝተውበት ነበረ ።

ማን ናት የንጉሡ ልጅ ሶስቱም በጣም ይመሳሰሉ ነበረ ። እናትየዋ እንኳ ልጅዋ ማን እንደሆነች ልትለያቸው ችግር ነበ ረ ግን አንድ መለዮ ብቻ ነበራቸው ገና ሐውልት ሳይሆኑ በነፍሳቸው ሳሉ የንጉሡ ልጅ ትንሽ ማር በልታ ነበረ ሁለቱ ገረዶቿ ግን አንድ አንኳር ሱኳር በልተው ነበሩ ። ትንሽዬው ወንድም ያያቸው ነበረ ግን ለመለየት አልቻለም ይሰማው ነበ ረ ጉልበቱ መቀዝቀዝ ጀመረ ልቡም መቆም ጀመረ እብነ በረድም መሆን ጀመረ ያኔ ግን በከፍቱ መስኮት የንብ ንግ ሥት መጥታ ነፍሷን ያዳናትን በንጉሷ ልጅ ከንፈር ላይ ተቀ መጠች የንጉሡ ልጅ ገባውም ዓለም ይቺ ናት የንጉሡ ልጅ ጎንበስ ብሎ እጅዋን ብድግ አደረጋት ያኔ ሁሉም ጽርሐ ንጉ ሡ ተግሩመኛው እንቅልፉ ተነሳ ፈረሶቹ ተንቀሳቀሱ ማድቤ ቱ ሁለቱ ወንድሞች ነፍሳቸው ተመለሰ ሐውልተኞቹ አሽከ ሮች ተነስተው አዲሱን የዋሁን ትንሽዬውን ወንድም ንጉሥ ሊቀበሉ ተዘጋጁ ሁለቱ ትልልቆች ወንድሞች ወደ አገራቸው ተመለሱ አፍረው እመንገድ ያገኙዋቸው እንስሶች አንድም እንንከ ሳይሉ አገራቸው ገቡ ትንሽዬውም ወንድም ንጉሥ ሆኖ በትእግስቱ በየዋህነቱ እንስሳንና ሰውን ክፉ ሊአደርጋቸው ባለ ማሰቡና ለሁሉም እርዳታቸውን በመስጠቱ ሚስጢረኛውን እና ግሩመኛውን የጽርሐ መንግሥቱን ይዞ ነግሦ ተቀመጠ፡ትንሹ ግስላ

ለስ አእምሮና ብርሃንና ሰላም

ይድረስ ከክቡር የብርሃንና ሰላም ዲሬክተር ብዙ ሰላምና ጤና ለርስዎ ይሁን ።

እኔ ባላገር ሁኜ በገጠር ተቀምጬ ሰው ሁሉ አዕም ሮና ብርሃንና ሰላም የሚባሉ መምህራን ተነስተው ዓለሙን ቀጾሩት እያሉ ብዙ ሰዎች ሲያወሩ እሰማለሁ ነገር ግን ያለ ሁበት ኑሮየና እውቀቴ በቤተ ክርስቲያን ስለ ተወሰነ ተላ ልፌ እኒህን መምህራን የማገኝበትን ሰዓትና ፈቃድ አልተ መቸኝም ነበር ከብዙ ቀን በኋላ የሁሉም ስማቸው ያም ራል ግብራቸው ከስማቸው ልዩ የሆነ እንደ ሆነ እሸሽለሁ እንጅ ከህን ሁኖ አእምሮ ማጣት አይገባም በጨለማ ውስ ጥም ሁኖ ብርሃን አይጠላም በዘመነ ሐከክም ሰላም ውድ ነው ብዬ አንድ እንዲወደኝ የማምነው ጎዝኤን የሚያስረሳኝ ወዳጅ አለኝ እስኪ መጀመሪያ ብርሃንና ሰላም የሚባለውን መምር አስተዋውቀኝና ምናልባት አእምሮውን ቢስልብኝ አል ኩት አምላክ ብርሃን ወ ሕ ርእሱ ለአእምሮ እንዲል እሱም የብርሃንና የሰላም ወዳጅ ባለ አዕምሮ ሰው ነውና ፈጥኖ መጋቢት ፩ ሐሙስ ቀን እኔ እርሻ ውዬ መሽቶብኝ በልጅነቴ የተማርሁበት ፊደል ነበረኝ ልጆች አስተምራለሁ ብዬ አቅር ቤው አርጅቷል ቀዳደው ጥለውት አዲስ ፊደል ወዳለበት ሂደው አገኙኣቸው የስንደዶ መብራት አብርቼ ያንን ፊደሌን ስቀጣጥል በቀጥሬ ውስጥ የብርሃን ጉርፍ ፈሰሰ የስንደዶ ውም መብራቴ ፈዘዘ ዓይኖቼም ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አሉ ርኢነ ተግባሮ ወበረከናሁ እንዲል ከዚሁ በኋላ ከድንጋጤየ ተዋናንቼ ምን ብርሃን ነው ማነህ ባለ መብራት ዝለቅልኝ ብለው እኔ መልእክ ሐሠት ያይደለሁ የብርሃንና ሰላም ወዳ ጅህ ያልኸኝን ይዤልህ መጣኋ አለኝ እኔም ልምዴን ወዳጅ ነኝና የስንደዶ መብራቴን ለቃቅሜ በግራር ልዋ አስሬ በራ ስጌየ አኑሬ ብርሃንና ሰላምን ብገልጠው አጋጥሜ አቶ ልማድ የሚባለውን አንቀጽ አገኘሁት ይህ ልማድ ብርታቱና መሠ ልጠኑ በሁሉ አገር መሆኑ ይልቁንም ባገራችንም በኢትዮጵያ እጅግ ስር ሰዶ መበርታቱ ሲገርመኝ ይኖር ነበረ ወላዲተ አምላክ ከነት ልማደ ያላት የመቤታችን ጽንዓ ፍቅሯን ወፈ ድፋደስ በጎበ ሕዝበ ኢትዮጵያ እንዲል የልማድ ነገር በብ ሉዩ እስራኤል ባሕር የከፈለላቸውን መና ከደመና ያወረደ ላቸውን ወሀ ከጭንጫ ያፈለቀላቸውን ፈጣሪአቸውን ትተው በኮሬብ ያዩትን ጥጃ ወደው አሮንን ባይናችን አይተን የምና መልካቸው ጠላት የሚገፋልን አማልክት ስራልን አሉት ልማድ ነው በሐዲሱም ሊቀ ካህናቱ ቀያፋ ምሑረ ኦሪት ነው አያም ተስፋ እንደ ተቀበለ ተስፋውም እንደ ደረሰ እያወቀ ለምን አምላክ ሰው ሆነ ለምን ሰው ዳነ ብሎ ድውያን ሲፈ ወሱ ሙታን ሲነሱ ከዋክብት ሲረግፉ ፀሐይ ጨረቃ ብርሃና ቸውን ሲሰውሩ እያየ አምላክ ነኝ አሉ ብሎ ተቆርቋሪ ሁኖ የማይገባውን ጽሕሙን ነጩ ልብሱን ቀደደ ልማድ ነው የቢሩት አገር ሰዎች ከጉልበታቸው ያበቀሉትን በማጎጻናቸው ያፈሩ ትን ልጆቻቸውን የሚለቅመውን አውሬ ድል ነስቶ በጠፍር አስጉትቶ ቅዱስ ጊዮርጊስ ግዳይ ቢጥልላቸው በደስታ ፋንታ ድንጋጤ ወደቀባቸው ልማድ ነው ምሥጢሩ ግን ምናልባት ሞት አይደፍረውምና የተነሣ እንደ ሆነ ማለት ይመስላል፡እኔም በልማድ ሰውን ሰው ሁሉ ሲገድለው አይቻለሁ ክቡር ራስ መኰንን ትግሬ ተሹመው የገዙ ጊዜ መቀሌ ገበያ አንድ ትግሬ ነጋዴ ከስቆጣ በቅሎ ገዝቶ አምጥቶ ሲሸጥ በቅሎው የሞተ በት የሐረር ወታደር ሽጥልኝ ዋጋ ንገር ቢለው አምላ ብሮ

አለው ብሩን ሊሰጥ ከረጢቱን ሲፈታ ምናልባት ያንን አዲሱን የሸዋ ብር እንዳትሰጠኝ አደራህን አለው እኔስ የምሰጥህ የዚህን ዓይነት ነው ብሎ በጁ የያዘውን አስር ብር የተለመደውን አሣየው ሲፈጣጠሙ እዳኞች ላይ ሲደርሱ አዲሱን አርባ ብር ቀላቅሎ ቢሰጠው አልቀበልም እንዳይል አዋጅ ፈርቶ ከንፈሩን እየነከሰ እንባውን እያፈሰሰ ወደ ዳር ወጥቶ ተቀመጠ ።

ያረርጌውም ወታደር ከተማነቱን አይቶ ውስጠ ዱር መሆኑን ሳይመረምር በቅሎውን ስቦ ወደሰፈር ሲገባ በሐምበር ወጨፎ ልብ ራሱን ብሎ በቅሎውንም ብሩንም እጅ አድርጎ በምክታር ገላውዲዎስ በኩል ወለቀ ኋላ ቀጥ ብሎ ሊገዛ ያን ጊዜ እንዲህ አልነበረምና ከመቀሌ ጨለቆት ከመቀሌ ፈለግ ዳር መሄድ ላማራ ሳይናዘዝ ጦር ሳይታዘዝ አይመችም ነበር ። ይህ ሁሉ ልማድ ነው እንጅ ፈደሉ የማይታወቅ ስእሉ ከማይታወቀው ብርማ መልኩ ያማረ አካሉ የወፈረ ፊደሉ የተመረመረ የደጉ ምኒልክ ስእል ያለበት የለምለሚቱ አገራችን የኢትዮጵያ ስም ያለበት ብር እንኳን ያጋድል ክፉስ ያናግራልን ልማድ ነው ።

የመንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

መጀመሪያ መንግሥት ገበሬ እረስ ቄስ ቀድስ ነጋዴ ነግድ ወታደር ፈረስ በቅሎህን ቀልብ ብሎ አዋጅ ቢነግር አገባብ ነው ። ሐተታ ገበሬ ማረሱ ያመት የጉልበት ግብሩ ልክ ካል ገባ ለራሱም ለንጉሡም ሳይሰራ በጭቃሹም እየተጐተተ ስራ መፍታት የታወቀ ነው ። ካህንም ነፃነት አግኝቶ ካላገለገለ ወረዳ እያሰረ ቅዳሴ ያስታጕላል የካህን ዳኛ ቢያስረው ለቅዳሴ ይለቀዋል የቁም እስር ያደርገዋል ። ካህን ቤተ ክርስቲያን ነፃ ከሆነችለት በኋላ ያገሩን ትምህርት መሠረት ዘይቤን ካወቀ በኋላ ሃይማኖቱን ተዋህዶን ሳይለቅ ሌላ ቋንቋ ቢጨምር ያልተወገዘበት አንቀጽ ነው ። ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ታድሰው በአእምሮ ጐልምሰው ሰብአ አንድ ቋንቋ ቢናገሩ ምቀኞቹም ፍላሎቱ ያልወጣለት የወይን ጠጅ ጠጥተው የሆነ ያልሆነውን ይቀባጥራሉ ሆነ ቢሉ አልተጐዱበትም በነቃፎች ፈራሽ ነገር ተባለ እንጂ ነጋዴ ነግድ ማለት የነጋዴ ማደሪያ ተብሎ የተጀመረው ስራ ተጨርሶም የተሰራ ገንዘብ ከባላገር ወጥቶ ሳይሠራው የቀረ አለ ያ በትክክል ተጨርሶ በ፯በ፮ ሰዓት ልክ መቶ መቶ ዘበኛ ከተማ አርጎ ቢሾኘው ነጋዴም ከፍርሃት ያርፋል በስጠኛም ደህና ያልፋል ። የሚያስፈልገውም ከጀምጀም ጀምሮ እስከ ጠረፍ ነው ይመስለኛል። ወታደርም ከኪሱ ሚዶውንና ገላ ሳሙናውን መስተዋቱን አውጥቶ የጠጉር መናደፍያ ደጋኑን ጨምሮ ለሚገባቸው አስረክቦ ፈረስ በቅሎ መቀለብን መቀርቀቢያ አጋሰስ ማሰብን ቢይዝ መንገድ እስኪሠራ ሠረገላ እስኪነዳ ንጉሥ አገር ለማየት ቢወጣ ይቸግራል ።

ይህንም ያሰብሁበት ከሰገሌ በፊት አዳል ተዘምቶ ሳለ እንዲህ ያለው ዓይነት ወታደር እርከትና ቅል ሳይዝ ዘምቶ ውሀ እያለ በመስኩ ተዘርቶ የጉተናው ብዛት መስኩ የሰው ጠጉር ያበቀለ መሰለ በየኪሱ ቅድም የተቈጠሩት ዕቃዎች ተገኙ ብሎ ከሞት የተረፈ ከጥላ ያረፈ ዘማች ነግሮኝ ነው ። ይህንም መጻፌ ላገር መጣርን ብርሃንና ሰላም ሲያስተምር ሰምቼ ነው እንጂ ሰው ለመንቀፍ አይደለም ።

አለቃ መርስዔ ኀኅዘ ።

ስለ ክብርት ወይዘሮ ስኂን ዕረፍት



ክብርት ወይዘሮ ስኂን የወሎና የቤገምድር የትግሬና የጎጃም ንጉሥ የነበሩ የንጉሥ ሚካኤል ልጅ የልዕልት ወይዘሮ መነን እናት ናቸው ። በተወለዱ በ፶፯ ዓመት ከ፱ ወር በ፲፱፻፳፰ ዓ ም በዘመነ ዮሐንስ ጥቅምት ፫ ቀን አረፉ ። ልጃቸው ልዕልት ወይሮ መነን የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ባለቤት ከልዑል አልጋ ወራሽ ጋራ ሁነው መልካም አድርገው ፍታት አስፈትተው ዓፅማቸውን በአዲስ አበባ በመድኀኒዓለም ቤተክርስቲያን በክብር አሳርፈዋል ።

ብርሃንና ሰላም ለልዕልት ወይዘሮ መነንና ለልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለዘመዶቻቸውም ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

ስለ ሕይወታቸው ታሪክና ስለ ልቅሶዋቸው አኳሆንም በሚከተለው ቁጥር ይታተማል ።

የከተማ ወሬ ።

በአዲስ አበባ ዙሪ ያለ አገር እህሉ ስላማረና ገበሬ ብዙ እህል ለመሰብሰብ ተስፋ ስላለው በከተማ የእህል ሽመታ እየተሻለ ይሔድ ጀምሯል ።በያለበት መስከም ሣር አጨዳ ተጀምሯል የክረምት ነፋስ ተለውጦ የመከር ነፋስ ይነፍስ ጀምሯል

የውጪ አገር ወሬ ።

የለት ወሬ ሮማ ። ምንስትሮችና የጸሐፊ ትእዛዝ ምክትሎችም የመንግሥት አለቆችም የሕዝብ ትልልቆችም አብረው በት በነበሩ ጊዜ ተመጋብያው አዳራሽ ያገሪቱ የስንዴውን ገቢ መጀመሪ ጊዜ ተመርቆዋል ። ፕረዚዳን ሙሶሊኒ በ፲፱፻፳፮ና በ፲፱፻፳፯ ዓ ም የስንዴውን ጦርነት ድል ያደረጉ ገበሬዎችን ስለ የሞያቸው ስጦታን ከሰጣቸው በኋላ በድርቅ ብዛት ተቋቋሚነት የተነሣ የዓመቱ እርሻና ጉዳት እንደደረሰበትና ስለእዚሁ ምክንያት የፋሽስቲ መንግሥት ለወደፊት ያለውን መሳሪያ ሁሉ በመስጠት በቦይ ለማጠጣት ማሰብ የሚያስገድድ እንደ መሆኑ እያነሣ ዲስኩርን ተናግሮዋል ። ከመሬቱ የተገኘው ፍሬ ምድር ፶፫ሚሊዮን ኩንታል ነውና የመንግሥቱ ሕዝብ ስለ እርሻ የተደረገውን አስተዳደር እጅግ ደስብሎታል እንቃቅቶ ትማል እህሉ ተነግሮበት ተነበረ ከፍ ብሎዋልና ካስተዳዳሪዎቹ የሚደርሱ ማስታወቂያዎች የሚያስደንቅ የማረስ ሥራ ስራዊት ማለት ኢጣልያ በመላዋ በሰላም ዝም ብላ ማረስ ነው ይላሉ ጋዜቶች ሙሶሊኒ በመጀመሪያ የፍርያሱ አስተዳደር ሲመርቅ

ሳለ ወደቁም ነገር ለመድረስ አገሪቱን ፍሬያት የሚያስገኙበት ብርቶችን አብሮ ለማስተዳደር የሚያስገድዳት ስለ መሆኑ በግልጥ እንጂ ንግግር በማሰብ ቃል ሳይሆን የኢጣሊያ ጠቀሜቶች የሚገኙበትን ስለ እርግጠኛ አኳሆን የሚበልጥ ዲስኩርን ስለ ተናገረ የዲስኩርን አነጋገር አመስግነውለታል ጋላርዶ የአርጀቲና ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከጀነራል ግራኖ ሀውልት ምርቃት አብሮ ለመዋል ወደ ጀኖባ ለመሄድ ተነስቶዋል ።

ፓሪስ ፤ ብሪያንድና ዘለውስኪ የፖሎንያ ውጭ ጉዳይ ምኒስትርም ሁነው በሚበልጥ በፖሎንያና በመስኮብ መካከል አደጋ መጣልነት እንዳይኖር ውልን በሚያሳይ ሲሆን ለፕሎንይም ፈረንሳዊም በሚጠቅሙ ሥራዎች ያህል ብዙ ቆይታን አድርገዋል ። በስኮንና በባንሴቴንም የተነሣ ከፈታኞች ጋራ ሰንቀን ከሚባል (ከተማ) ዘንድ አምባጓሮ ስለተደረገ አያሌ ቈስለዋል ። ከሳተና ለብሪክ የሚባሉ የአረዮፕላን ነጅዎች ከስነጋል ወደ ናተልም ወደ ጀነዩሮም ለመዘር አሳብ ወደ ቡዋኖስ አየሮስ ለመሄድ ተነስተዋል ።

በልግራድ ፤ ከብዙ ትግል በኋላ ሁለት የጀነራል ከባቾቢክ ገዳዮች ተገድለዋል ፤ ሶስተኛም ተይዘዋልና ቢመረመር የመቄዶንያውያን ዱለት አለቆች ግደሉት ብለው ስላዘዙን ገድለነዋል ብለው አምነዋል ብሎ እጀንስ አብላ የተባለው ጋዜጥ ያወራል ።

መሲኮ ፤ (አመሪክ) አሁን በመጨረሻ ጊዜ እንደ ደረሱ ወሬዎች ዘንድ ጎመጽ የተባለው ጀነራል ድኖዋልና በፕረዚዳን ከለስ ላይ ጦርነት ማድረግ ይቀጥላል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፰ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነርትጓሜው	፯ብር
ኅሐ ጽባሕ	፰ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትጓርሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ሩብ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ከ፫ ሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲ ብር ፫ ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ።
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር ተኩል ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፲፩ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፯ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፭ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲፩ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፭ ብር
አቡጀዲ መነጸር	፩ ኮረጃ	፺፭ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፺፯ ብር
፡፡ ባለ ድመት ፡፡		፻፴፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፪ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፯ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፺፫ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፫ ብር ።
ጋዝ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ
አንድ ብር	፲፩ ሊሬ እስከ ፺፫ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ፳፯ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር

ማስታወቂያ ።

ጥቅምት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓመት የሚደረገው ሎተሪ በሆቴል ቴራስ ፈጽሞ አስቀርተነዋልና የተቀበልነውን ገንዘብ መመለሳችንን ለሰጡን ሰዎች እናስታውቃለን ።

መታፈሪያ ወልዴ ።

COGNAC S. E.& A. METAXA
LE PIREE-GRECE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ፡፡

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የሚባል ባለአንበሳ ስዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ፡፡

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሖ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ፡፡

Automobiles CHEVRGLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆን በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል"አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ"ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።



ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ካኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመከከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ኤን ቤ ኤዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

ዓለም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠራል ።

ኒከላ ።





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አሉ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድዬር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደ ጣሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆ ን አያስፈራም እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስ ቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድዬር ግዙ ከሌላው ላስ ቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ያበረክታል ዋጋው ግን እኩ ል ነው ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘ ው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

ጉድዬር ግዙ

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤዤስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፤ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ማጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፫
3 me ANNÉE № 43

ሐሙስ ጥቅምት ፲፯ ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም
JEUDI 27 OCTOBRE 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ሰለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ይስደዱ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። ባሳምንቱ ሲገዙ ለፊደን ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres



ክብርት ወይዘሮ ስኂን ።

ስለ ክብርት ወይዘሮ ስኂን ዕረፍት



የተወደዱት የልዑል አልጋ ወራሻችን ሚስት የልዕልት ወይዘሮ መነን እናት ትልቋ የተከበሩት ሴት ወይዘሮ ስኂን በጥቅምት ፫ ቀን ስለ ሞቱ በዛሬው ጋዜጣችን እንድንጽፍ ትእዛዙ ሰጥተን ነበረና የሕይወታቸው ታሪክና የልቅሶው አኳሆን እንደሚከተለው ነው

ሙዋችዋ ክብርት ወይዘሮ ስኂን ዘረ ትልቋ በሕይወታቸው ሳሉ ለደሐ አዛኝ እርኅሩኅ ቸር እረዳት ነበሩ ነገር ግን ይልቁንም ትልቁ ሥራቸው ታማኝነትና ሃይማኖታዊነት ነበረ እግዚአብሔርን ስለወደዱና በኢየሱስ ክርስቶስ ስለታመኑ የት ቀደሰችዋን አገር ኢየሩሳሌምን ጐብኝተው የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ መቃብር ስመው የኢትዮጵያ መን

ሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከኤሮፓ ጉዞዋቸው ሲመለሱ አብረው ወደዚህ ተመለሱ ።

ዘወትር ለቤተ ዘመዶቻቸው ሩኅሩኅ ደግ እናት ለአሽከሮቻቸው ቸር ነበሩ ።

የንጉሥ ልጅና ወደፊትም የቤት ንግሥት እናት ሆነው ሳሉ አይኰሩም ነበረ ነገር ግን ዘወትር አመለ ደግ እሩኅሩኅ ምሕረተኛ ነበሩ ። ሕመም ከጀመራቸው ብዙ ጊዜ ነበር በሽታቸውም አንደየ ሻል ብሏቸው አንደየ ደግሞ ይብሳል አሁን ግን ተሽሏቸው ነበረ እነደገና ጠንቶባቸው ለማረፍ ደረሱ ።

የልጃቸው የልዕልት ወይዘሮ መነንና የልዑል አልጋ ወራሽ በጥንቃቄ ማስታመምና የሐኪሞች በየተራ ማከም ትልቋን ሴት ለማዳን አልቻለም ነበረና ቤታቸውን በሰዎች ላልተሰራው ለዘለዓለሙ ቤት ለውጠውት ሔዱ ።

ኀዘኑም በመላ ኢትዮጵያ ከተማ በዝቶ ነበር ዳሩ ግን ትልቁ በረታው ኀዘን የርኅሩኋን ልጃቸውን የልዕልት ወይዘሮ መነንን ልብ ነካው ፤ ሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር ለሰው የሚሞት ሕይወት ሰጠው ለሰው ሕይወትን ሰጦ መልሶ ይወስዳታል

እንዲሁ ይህን ብርቱ ሐዘን የሚያጽናና ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር እሱ ብቻ ነው ።

የክብርት ወይዘሮ ስሂንም ቀብር ለክብራቸው በሚገባ ስርዓት ሆኖ በትክክል ተደረገ ።

የተወደዱት ንግሥታችን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የቤተ መንግሥቱ ሰዎችና የኢትዮጵያ ሚኒስትሮች ታላላቅ አለቆችና ብዙ ሕዝብ ከየከተማው ከፍሎ መጥተው ነበሩ ከቤታቸውም ትልልቅ ድንኳኖች ተተክለው ነበሩ ከዚያም ውስጥ ሆነው ልዕልት ወይዘሮ መነንና የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለቅሶ የሔደውን ቁጥር ስፍር የሌለውን ሕዝብ ሁሉ ይቀበሉ ነበረ የኤሮፓውያን ሚኒስትሮችና ቆንስሎች ብዙም የተከበሩ ከዚህ ነዋሪ የሆኑ የኤሮፓ ሰዎች ከዚያው እየሄዱ እግዚአብሔር ያጽናችሁ እያሉ ሐዘናቸውን እያቀረቡ ሔዱ ።

ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በፍጹም እምነት ልንታዘዝ እንደሚገባን ሲያስተምረን እንዲህ ይላል ሞት መበረከን ደስታንና የዘለዓለምን ሕይወት ያመጣል

ወደዚህ ደስታና ለዘለዓለም ወደሚሆነው ክብር ያለው ሕይወት ሃይማኖተኛዋን ክብርት ወይዘሮ ስሂንን እግዚአብሔር ያድላቸው

መታሰቢያቸው ለዘለዓለም ይኑር

ስለ ስልጣኔ እርምጃ

በሌላው ዓለም ሕዝብ በጅዖግራፊና በጆርናል ወሬውን እንደምንሰማው እጅግ ያስገርማል ። ደግሞም በዚያ ግምት የሀገራችንን የስልጣኔ አኳኋን ስናስብና ስንመለከት ምን ያህል ወደ ኋላ እንደቀረንና በአንዴት ያለ ትልቅ እርምጃ ለመከተል እንደሚያስፈልገን ብናስተውለው በጣም የሚያሳዝን ነው ። መቼም የአውሮፓንና የአሜሪካን አኳኋን ለመጻፍ ብዙ እሩቅ ነውና አያስፈልገንም ።

ወንድሞቼ እኛን ላለፈው ጉዳታችን እንደ ዓለም ለመሆን ለጠፋው ላለፈው ጊዜያችን ሊያስጠጥተንና ሊያሳዝነን ለሚመጣውም ጊዜ ሊያነቃንና ሊያተጋን ልብ ቢኖረን የጃፓንን አኳኋን ብቻ በጥቂቱ ባጭሩ ብንጽፍና ብናነብ ይበቃናል ።

ይኸ ጃፓን የሚባል ሕዝብ ከዛሬ ፷ ዓመት ወዲህ እውቀትና የስልጣኔ ትምሕርት ወደ አገራቸው እንዲገባ ነጻነታቸው እንዲጠበቅ መክረው ንጉሡም መኳንንቱም ሕዝቡም ታጥቀው በትልቅ ብርታት ተነሡ ይኸን ማድረጋቸውም ያለ ስልጣኔ ትምሕርት ነጻነታቸው እንዳይጠበቅ ቢያስረግጡ ነው አሁን ዛሬ በጃፓን ፵፫ሺ፺፰ የትምሕርት ቤቶች አሉ ። ፲፰ የእውቀትና የጥበብ የሥራ መማሪ ዩኒቨርስቲዎች አሉ ዩኒቨርስቲ ማለትም የመንግሥት ፖለቲክ መሐንዲስነት ሐኪምነት የወረቅ መሐንዲስነት የመሣሪ ሥራ መሐንዲስነት ሌላም ይኸን የመሰለ ሁሉ የሚማሩበት ትልቁ የትምሕርት ቤት ነው በጃፓን ፵፫ሺ የትምሕርት ቤቶች አሉ ሲባል በሀገራችን ፵፫ በኰሌጅ የተማሩ ሰዎች አለማግኘታችን በጃፓን ፲፰ ዩኒቨርስቲዎች አሉ ሲባል በሀገራችን ፲፰ ሰዎች በዩኒቨርስቲ የተፈተኑ አለማግኘታችን ልብ ላለው ሰው ምን ያህል የሚያሳዝን ነገር ነው ። በዚህ በ፵፫ቱ ሺ የትምሕርት ቤቶች የሚማሩ የጃፓን ህጻናቶች ወንዶች ባለፈው በ፲፱፻፲፱ ዓም ፭ ሚሊዮን፺፻፹ሺ ህጻናት ናቸው ።

ልጃ ገረዶች ፬ሚሊዮን ፺፻፩፬ሺ ልጃ ገረዶች ናቸው በ፲፰ቱ የጥበብ መማሪ ዩኒቨርስቲ ትልልቅ ሥራ የመንግሥት ፖለቲክ ጉዳይ መሐንዲስነት ሐኪምነት ይኸንንም የመሰለ የሚማሩ ፱ሺ ፫፻፴፯ ሰዎች ናቸው ። ደግሞ ዛሬ በጃፓን ያሉ የመጻሕፍት ማተሚያ ቤቶች ፪ሺ ፱፭ ቤቶች ናቸው ። ለኛ ግን ገና ፩፱ የመጻሕፍት ማተሚያ ቤቶች የሉንም ደግሞ ፫ሺ፩፻ ፴፪ ጋዜጣ የሚያትሙ የማተሚያ ቤቶች አሉ የጃፓን መንግሥት ያመት ገቢ ግብር ፩፱ ሚሊዮን ፬፻፵ሺ ጊኒ ነው ይኸም በብር ሂሳብ ፭ሺ ፩፻፵፬ ሚሊዮን ብር ነው ይኸም ቃል ባለፈው ዓመት በጃፓን ጆግራፊ ተጽፎ የተገኘ እርግጥ ቃል ነው እንጂ ወሬ አይደለም ይኸ ሁሉ ሀብት መገኘቱ በትምህርትና በእውቀት ነው እንጂ የጃፓን ምድር በመልክምነት ከኢትዮጵያ በልጦ አይደለም ትምህርትና እውቀት መገኘቱም እንደ ዝናም ከሰማይ ወርዶ አይደለም ሕዝቡ ተባብሮ ስልጣኔ ወደገሩ ለማግባት በትጋት ቢሠራ ነው እንጂ እኔም ከዓለሙ ሁሉ በተለየ የጃፓንን መጻፌ ከዛሬ ፷ ዓመት በፊት ጃፓን እንደኛው ነበረ ከዛሬ ፷ ዓመት ወዲህ ግን በታላቅ ብርታት የትምህርት ቤት ለማስፋት ታጥቀው ተነሡ እንስሳቸውም እንዛሬው እንደኛ የስልጣኔ እርምጃ አንድ ሰው ብቻውን ይሥራ ብሎ በመመልከትና በትልቅ ድካም በማዘገም አልነበረም በብዙ ተጋት ነበረ እንጂ ። ደግሞም የፋርስ መንግሥት እንደኛው ወደኋላ ቀርቶ ነበረ አሁን ግን በነገሩ ነቅቶ ብዙ የትምህርት ቤቶች ባገሩ አቁሞአል እንዲያውም ሌላ የፋርስ ንጉሥ ልጅ አልጋወራሹ የስልጣኔን ትምህርት ለመማር ወደ እንግሊዝ አገር ትምህርት ቤት ሄዶ ሲማር ሰንብቶ አሁን ቀርብ ቀን ለእረፍት ወዳገሩ ይሄድ ነበር በምስር በኩል እስክንድርያን አይቶአለፈ ይባላል

በዓለሙ ሁሉ ላይ የዓለም ሕዝብ የሰልጣኔን ትምህርት ከሁሉ ሥራ በላይ ይቆጥረዋል ከሁሉም ሥራ የበለጠ በስልጣኔ ትምህርት ጉዳይ ይታሰባል በኛ በኢትዮጵያ ሕዝብ ሐሳብ ግን የስልጣኔ ትምህርት ከሁሉ ሥራ መጨረሻ ትንሽ ጉዳይ እንደሆነ ይታሰበል ሰለዚህ መሪያችንን በመናቅ ትንሽ ደሃ ሕዝብ ሆነን እንኖራለን ወንድሞቼ ይኸን ሁሉ ቃል መጻፌ በወሬ ለማስደነቅና ለማስገረም አይደለም ።

በእውነት ባገራችን የስልጣኔን ትምህርት ለማግባትና ያገራችንን ነጻነት ለመጠበቅ ብናስብ በስልጣኔ ትምህርት ጉዳይ የሚያስቡና የሚማከሩ ብልሆች ሰዎች ተመርጠው መንግሥት አንድ ያማከሪ ቤት ቢያቆም ደግሞም ህዝቡም አንድ ያማከሪ ቤት ቢያቆም እነዚህ ሰዎች ዘወትር እየተማከሩ የስልጣኔን ትምህርት ጉዳይ ቢያስኬዱት እርግጥ ስራው በትክክል መጀመሩ ይሆናል ለማለት ነው ። ደግሞም ዋናው ሐሳቤ ይኸንን ቃል የጻፍሁበት ምክንያት የዛሬ ፫ ዓመት በህዝብ ማህበር እንድናቆም ጽፌ የነበረው የትምርት ቤት እስከሁን መቆየቱ የስልጣኔ ትምህርት አማከሪ ቤት ባለመኖሩ መሆኑን ስለ አሰብሁ ነው ደግሞም ይኸ የሕዝብ ትምህርት ቤት ገንዘብ በማነሱ ፩ ፩ ሰዎች የቀረ መስሏቸው እንደሚናገሩ አልቀረም አሁን በቅርብ ቀን በኋላ ተፈሪ መኰንን ቸርነትና እርዳታ እንዲቆም ሙሉ ተስፋ አለኝ በቅርብ ቀን ይቆማል ።

ልባም ሆይ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን የወሮች ጫዋታ ተመልከት ልብ አድርገው

ከባሕር ማዶ ከሩቅ አገር ፡ የተያዘች ወፍ ስትነጋገር ፡ በአየር ከሚበሩት ከወዳጆቿ ጋር ፡ ብላ ተናገረች በብዙ መመረር ፡ በድንገት ተያዝሁ ሳልከረከር ፡ ነገሩ ሳይገባኝ ሳልጠረጥር ፡ ልቤን እየሳቡ በወርቅና ብር ፡ ስበው ቆለፉብኝ ይኸን ከበድ በር ።

ዋዘ ይመስላችኋል ይኸ ነጻነት ፡ በእጅ የያዙት ወርቅ ይመስላል ብረት ፡ እንደኔ ከመሆን ይሻላል መሞት ፡ ከወጥመድ ገብቶ ከመንገላታት፤አሁን መጠንቀቅ ነው ያለመሞኘት ።

ያልተያዘች ወፍ ምላሽ

ከብረት አጥር ግቢ ጥሩ ሐር ለብሰሽ ፡ ይኸንን ያህል ምን አሳዘነሽ ፡ በሌሎቹ ድካም እየተመገብሽ ፡ በወርቅና በብር እየተጫወትሽ ፡ በዚህ ምቾት ኑሮሽ ምኑን ተጠጠትሽ ፡ ምንም ደስ ባይልሽ ነጻነት አጥተሽ እጅግ ተድላ ነው መልካሙ ኑሮሽ

የተያዘችው ወፍ ምላሽ

ያለማየት ጉድ ነው ያለመቀጣት ፡ ባርነት ያስመኛል ለመቅመስ ውርደት ፡ ይኸ የኔ ኑሮ ነጻነት ማጣት ፡ ላልተያዘችው ወፍ ኑሮ መሰላት ፡ እጅግ ብዙ ብር ገንዘብ ማግኘት ፡ ጥሩ ሐር ለብሶ ባርነት መግባት ፡ ለየዋሂቱ ነፍስ ክብር መስላት ፡ ስንፍና እስራት ነው ታላቅ ሰንሰለት ፡ አውልቀሽ ጣይው ይኸን መዘንጋት ፡ ጥበብን ልበሽው እሱ ነው ብርታት ። ፊ ዴሬሳ

ምክር ሠናይት ለኵሉ ዘይገብራ ።

በ፫ ኛው ዓመት ቁጥር ፴ ፪ በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ባፋሲ የምትኖር ሽባሽ የምትባል የሚያናግር አጋንንት አድረውባት ብዙ ሰው ወደ ወገንዋ እየሳበች እንደ አሳተች ስሰማ እኖር ነበር ልጅ ተፈራ አበቤም የጻፈውን ቃል አንብቤ ተደንቄሁ ብዙ ሰው በድፍረት ቃል ይቅርና በፍርሃት ቃል እንኳን ስምዋን የሚጠራት የለም ። በሽበሽ መጀን እያሉ በግና ዶሮ ፍየል እያረዱ በዛፍ ስር ዘበረትም ለሰይጣን ሲገብሩ የሚኖሩ ብዙ ናቸው ። እንዲህም አድርገው ለአጋንንት ሲገብሩ የሚኖሩ ከሕመምና ከሞት አንድ የዳነ አይገኝም ። አያል ሴቶችም ጨሌ የሚሉት ጠጠር ወይም ጠርሙስ በየዓይነቱ ቀለም ቀብተው ነጋዴዎች ይሸጡታል ያንን ከገበያ ገዝተው አምጥተው በንገታቸው ያጠልቁና ገንፎ ያገኑፉና የሴቶች አጋንንት ስም ይጠራሉ አቴቴ ሐራ አቴቴ ግንቢ አቴቴ ዱላ እልል እልል ይላሉ ከብታችንን አርቢ ልጆቻችንን አሳድጊ ብለውም ይለምኑዋቸዋል ። ከዚህ ነገር የተከለከሉት ሰዎች ብዙ ቢሆኑ ከስካር መጠጥና ከማመንዘር የሚድን ራሱን የሚጠብቅ እጅግ ብዙ አይመስለኝም ።

ስለ ዚህ በምንም በምን ምክንያት ብሎ ሰይጣን ብዙ ሰዎች ማርኳልና መምሕራን ተፋጥነው ሊያስተምሩ ቄሶችም የንስሐ ልጆቻቸውን እየመከሩ በንስሐ መመለስ ይገባቸዋል ይህንንም ባያደርጉ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ይወቅሳቸዋል ። ወዮላቸው ለጠባቆች የበጎቼን መንጋ ለሚባትኑ ። እንዲህ ይላል እግዚአብሔር አምላክ እነሆ እኔ በጠባቆች ላይ ነኝ በጐቼንም ከእጃቸው እሻለሁ ሕዝቅ ም ፴ ፱ ቁ ፲ ። አንባቢ ሆይ ምንም ከዚህ ነገር ሁሉ አንተ ንጹ ብትሆን ቤተ ሰቦችህንና ወገኖችህን በንስሐ አባት ልታስመክርና በስርአት ልታኖር ይገባሃል ራስን መጠበቅ ብቻ ምንም አይረባውም ። በኃጥአን ብዛት አገር ትጠፋለችና ቤተ ሰቦችህ ኃጥአን እንዳይሆኑ በስርዓት ጠብቀህ ልታኖራቸው የግድ ያስብሃል ። ቀድሞ ኃጥአን ቢበዙ በማየ አይኅ የዚህን ዓለም ፍጥረታት አጥፍቷል ከዚያ በኋላም በረኃብ በመቅሠፍት በጦርነት ሲያጠፋ ይኖራልና ጊዜያችንን በሰላም እንድንፈጽማት በየ ወገኑ ሁሉም በጎ ሥራ ልንሠራ ይገባናል ።

እንዲህ ይላል እግዚአብሔር አምላክ ወደኔ ተመለሱ እኔም ወደናንተ እመለሳለሁ ዘከር ፩ ፫ የኃጢአተኛን ሞት አልሻም ኃጢአተኛ ከኃጢአት ይመለስ ዘንድ እንዲድንም እንጅ ተመለሱ ከክፉ ሥራችሁ ንስሐ ግቡታችሁ ተመለሱ ከክፉ መንገዳችሁ ስለምን በኃጢአታችሁ ሳላችሁ ትሞታላችሁ ስለምንስ ከገሃነመ እሳት ገብታችሁ ትኰነናላችሁ እናንተ የእስራኤል ወገኖች ሕዝ ፴፫ ፲፩ አእምሮ የሌላቸው እንስሳ አህያ ጅብን ፍየል ነብርን ዶሮ ምጥማጥን አይከተሉም አጥፊያቸውን ያውቃሉና አእምሮ ያለው ሰው ምነው ሰይጣንን ይከተላል ክፉውን ሥራ ሁሉ መሥራት ሰይጣንን መከተል እንደሆነ እያወቀው ።

ምነው አሁን ሰዎች ሁሉ ቢያውቁ ። ከነፍሳቸው ጠላት ቢርቁ ።በሰይጣንም እጅ ባይወድቁ ። ከሥጋዊው ተድላ ቢነቁ ። የዚህ ዓለም ተድላ ቀሪ እንደሆነ ሲያውቁ ።

የጋሎች አምልኮ ሥራ ተምራችሁ ። ገንፎ አገንፍታችሁ ጨሌን አጥልቃችሁ ። አውልያ ብላችሁ ሰይጣንን ጠርታችሁ ቡናን አፍልታችሁ ቆሎን በትናችሁ ። አበረት ለጋኔን ጥቁር

በግ አርዳችሁ ፡ ለባላጋራችሁ እየገበራችሁ ከሞት ከኵነኔ የታል ያዳኑዋችሁ ከእግዚብሔር በቀር ማነው አምላካችሁ መዝ ፲፰ ፴፱ ንስሐ ገብታችሁ ካልተመለሳችሁ ሉቃ ፲፫ ፫ መዝ ፯ ፲፫ አሁን ብትገበሩት ኋላም የሰው ናችሁ ይህንን አመቁ ጥዛ እንዳይመስላችሁ ። ከዚህ ሁሉ የኃጢአት ሥራ ይድኑ ዘንድ ክህናት ሕዝቡን ባይጠብቋቸው በጕቼን ጠብቁ ብሎ ቢሰጣችሁ ። ላትሰበስቡ የትም በትናችሁ ። ክፉ አውሬ ሰይጣን ነጥቆ ወሰ ደባችሁ ባለቤቱ መጥቶ ሲተሳሰባቸሁ ምን ትሰጡት ይሆን ወዮ ወዮላችሁ

ቄም ጸሐፊ ገብረ ጻድቅ

ምስጋና

ዶክተር ካይማኪያን የከብት ሀኪም ለክቡራን ወዳጆቹ ምስ ጋናውን ያቀርባል ምሽቱ በሞተችበት ቀን መጥተው ስላቃበሩት ወዳጆቹና እቤቱ ድረስም መጥተው ስላጽናኑት ወዳጆቹ ደግ ሞም በደብዳቢያቸው እግዚአብሔር ያጥናህ ላሉት ሁሉ ምስጋ ናውን ያቀርባል ።

ስለ ኢትዮጵያ ነፃነት ማደስ ።

ኢትዮጵያ ሀገራችን ባሁኑ አረማመድ በቶሎ ወደፊት እንድትገፋ ስንጠባበቃትና ተስፋ ስናደርጋት የሚከለክላትና ፅንቅፋት እየሆነ ሁሉ ጊዜ የሚያውከት ብዙ ነገር አለበት ብሎ ልባችን ወደ መጠርጠር ይከጅላል ዳሩ ግን ይህ ሁሉ ምክንያት ጭነት የከበዳት አህያ የተሸከመችውን ጭነት ወደ ምታደርስበት ስፍራ በቶሎ አድርሣ አራግፋ እንደማረፍ ወደ ሰው ብትጠጋ ወይንም ሰውን ብትገፋ የቀለላት እንደሚመስ ላት እንዲሁም ብዙ ሰው ጉዳቱናን ጭንቀቱን ውርደቱንና ችግሩን ተረዳድቶ እንደማጥፋት ወደ ሌላ ሰው ቢያመኻኝ አን ድም እውነትህ ነው የሚለው የለም ይልቅ የስራልብሱን ልብሶ ለመበርታት ይጣጣር

ነገር ግን ክቡር አንባቢ ሆይ ኢትዮጵያ የምትጠቀምበት መንገዷ አጭር ነው ይህንንም እንድትፈጽመው ተስፋ እናደ ርጋለን ኢትዮጵያ የምትጠቀምበት መጀመሪያ የሚበቃትን ገንዘብ (እንዳገባቡ) እንደሚገባ ማከማቸት ነው ሁለተኛ በዚሁ ገንዘብ ትምህርት ቤትና በያይነቱ ጥበበትን ማቆም ነው አንደኛ ነገር ለኢትዮጵያ ማሠልጠኛ የሚበቃ ገንዘብ እንዴት አድርጎ ሊገኝ ይችላል ቢባል በዚህ አከሄድ እንገልጻለን/ይህም ቢፈጸም ድኃን ማደህየት ቀርቶ የሚከብርበትና የሚባለጥግበትን የሚ ሠለጥንበትንም መንገድ መከተል ነው ሁለተኛ መንግሥት መንግ ዷቱን ቀርቶ ብዙ ጥቅም የሚያገኝበት ማለፊያ ነገር ነው መጀ መርያ የኢትዮጵያ ድኃ ገበሬ አርሶ እህል ቢያከማች ላም ቢያ በዛ ፍየል በግ ቢያረባ ሌላም እንደዚህ የመሠለ ነገር ቢያገኝ ለውጪ የሚያተርፍበት ትርፍ አላገኘም ሌላውስ ይቅርና ላገሬ ገዠው የሚበቃ የሚከፍለውን ግብር እያጣ ያለውን መሬት ለቀቶ ከጨረሰ በኋላ አገር ለቆ መሄዱ አይቀርም እንዲሁም ነጋዴ እቃች ወርዶ እላይ ወጥቶ ለፍቶ ደክሞ ከሚነግድበት ገንዘብ ማትረፉ ማበሩ ቀርቶ አጥፍ መልፋቱን ተረድቶት አገ ሩን ትቶ ሠርቶ የእለትም ምግቡን ወደሚያገኝበት አገር ይሠ ደዳል እንዲሁም ወታደር መንግሥቱን አገልግዬ ሀገሬን ረድቼ እሾማለሁ እሸለማለሁ ማደሪያም ይወጣልኛል ሲል ለሀገሩ በቅ ንነት ሲያገለግል ይኖራል ስለ ሀገሩም ደሙን እያፈሰሰ እየሞተ የጀግነነቱን ሲፈጽም በመኖሩ ብዙ ብልህና አስተዋይ ሰው ያውቅለታል

አሁን ወደ መጀመርያ ሐሣሳባችን እንመለሳለን ኢትዮ ጵያ የምትጠቀምበት በገንዘብ ነው ብለናል ይህም የገንዘብ አወ ጣጥ ከዚህ አስከትለን እንገልጻለን ክቡር አንባቢ ሆይ ይህ ጽሕፈት ኢትዮጵያ ከድንቁርና በእውቀት የምትታደስበት የምትሰለጥንበት ህዝቧን ድኃዋን በደምብ በሥራት የምታስተ ዳድርበትን ሐሣብ የሚገልጽ መሆኑን እንድትረዳው አልጠራ ጠርም ደግሞም ኢትዮጵያ ከብዙ ኃያላን መንግሥታት በፊት ራስዋን ችላ ነጻነትዋን ጠብቃ በኃይል በጥበብ መኖርዋን ብዙ ህዝብና ብዙ ታሪክ ይነግርላታል ።

አሁን ግን የገንዘቡን አወጣጥ እንደሚከተለው እናመለ ክታለን ከእህል ረገድ ከያይነቱ እንደሚያስፈልግ ሁኖ አገር እንደማይራብ ህዝብ እንደ ማይጨነቅ አድርጎ ማዘጋጃ ቤት ደህና ደህና የታመኑ ሠራተኞች ቀጥሮ እህል ከያገሩ ሸምቶ ባላገሩ መቶውን ኪሎ ባምስት ብር እንደሆነ የሚሸምተው መንግሥት ግን ባላገሩ ሳይደኸም በቤቱ ማለ መቶውን ኪሎ ባስር ብር ሊገዛው ይገባል ይህንም ማድረጉ ድኃውም እሩቅ ሳይሄድ ቢከብርለትና ቢበለጥግለት መንግሥት ከበረ ሀብት አገኘ ማለት ነው ማዘጋጃ ቤቱም እንደሚያስፈልግ ሀገር እንዳይራብ እያደረገ ከያይነቱ እህል አንዳንድ ሚሊዮን ጆንያ ሊገዛ የሀገራችን እህል ሥራ ፊቱ የሚቀመጥ ብዙ ነውና ሀገር ሊራብ አይችልም ይህም የገዛው ከያይነቱ እህል ከኢት ዮጵያ እስከሚሸጥበት አገር ድረስ ከዋናው እስከ ኪሳራ ኻያ ብር ቢሆን አንዱ ጆንያ ሠላሣ ብር ቢሸጠው አሥር ብር ካንዱ ጆንያ ማትረፉ ነውና ትርፉ ብዙ ነው ።

እንዲሁም ከእንስሳትም አራዊት በያአይነቱ ቢያስገዛ አንድ በሬ ባኢትዮጵያ አምስ ብር የሚያወጣ የሆነ እንደ ሆነ መንግሥ በመቶ ብር ሊገዛው ይገባል ።

እንዱ አንበሳ ባላገሩ በሺ እንደሆነ የሚሸጠው መንግ ሥት አትርፎ ሊገዛው ይገባል መንግሥት እንደዚህ አድርጎ ባገራችን ስራ ፊትና ለኛ ጥቅም ሳይሆን አጣብቦን የሚኖር ወደሌላ አገር ልክ ለሕዝቡ ጥቅም ቢያስመጣበት ጥቅሙ አን ድና ሁለት ዓይነት ብቻ አይደለም እጅግ ብዙ ነው ምስጋና ውም ይበን ያህል ነው ተብሎ ሊወሰን አይቻልም ። እንዲ ሁም መንግሥት በዚሁ ገንዘብ በየከተማውና በየገጠሩ ልዩ ልዩ ተማሪ ቤት ቢያቆሙበት የሕዝብ ጤና መጠበቂያ ሕክ ምና ቤት ቢሰራበት ልዩ ልዩ የብልሐት ስራ ፋብሪካ ቢያስመ ጣበት ከያይነቱ ጥበባት ሕጻናትን ቢያስተምር የኢትዮጵያ ህዝብ በማናቸውም ስራ የማያሳፍር ብልህ በቶሎ እውቀትና ጥበብ የሚገባው ነውና ለኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን ችሮታ ቢፈጽሙ ለት በምድር ዋጋውን ይከፍላል በሰማይም ያጸድቃል አገሬ

ችን እንደዚህ በሚመስል ወደፊት ብትገፋ ህዝቧ ቢሰለጥን ከዓለም መንግሥታት በማናቸውም ነገር አናንስም ነበረ ። ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ይህንን ሁሉ ሐሣብ ለመጻፍ ያነሳሳኝ ምክንያት ለማስታወስ ነው እንጂ መንግሥታችን የበለጠ እንደሚያስብበት እርግጥ ነው ። ነገር ግን በጋዜታችን በብርሃንና ሰላም በየጊዜው እንዳመለከት ነው ልጅ አባቱ ብዙ ጥቅም እንዲያስብለትና እንዲጨነቅለት ልቡ ሲያውቅ ወይንም መብሉን መጠጡን ልብሱን ርስቱን መሬቱን የሚያሰናዳው ለሱ መሆኑን ሲያውቀው ይህንን ልብላ ይህንን ልጠጣ ልልበስ ማለትስ አይቀርምና ስለዚህ የከበሩ ጌቶቻችን ይህንን ሐሣብ በድፍረት ብንጽፍ እንደማይቆጡንና እንደማይከፉብን ልባችን ስለታመነ ነው።

ይግዛው ጎሹ

ስለ አቶሞቢል ነጂዎች ምክር

አሁን ባለፈው ሳምንት ውስጥ አንድ ቀን ከሥራ ምላሽ በ፲፩ ሰዓት በባቡር መንገድ ስሄድ አንድ የሚያሳዝን ነገር ስለ ዓየሁ ይህንኑም የብርሃንና ሰላም ወዳጆች እንዲሰሙት ፈቃዴ ስለሆነ ልጽፍ ግድ ሆነብኝ ።

ከራስ መኰንን ድልድይ ላይ አንድ ባላገር ሰውዬ በግ ተሸክሞ ሲሄድ ሳለ ከኋላው አንድ አቶሞቢል ነጂ ጡሩምባውን ሣይነፋ ድምጡን አጥፍቶ በድንገት ከተፍ አለበት። ይህን ጊዜ ይህ ባይተዋር ሰውዬ ተጨንቆ ግራ ገባውና ለመዳን ወደአሰበበት ስፍራ ሽሽት ዠመረ ።

ግራኛው አቶመቢል ነጂ ግን ወደሚሸሽበት ስፍራ ፍለጋውን ተከትሎ ይነዳ ጀመር ። ዳሩ ግን ይህ ሁሉ የሚደረገው በጠባቡ መንገድ በድልድዩ ላይ ስለሆነ ባላገሩ ሰውዬ ወደ ድልድዩ መጨረሻ ወደ ወንዙ ስለሄደበት ለአቶሞቢል አልተመቸምና ነጂው ሐሳቡ አልተፈጸመለትም ።ከዚህ በኋላ ሸሽቶ በመዳኑ ተናዶ የታባትክ አንት ደንቆሮ አህያ እያለ ስድቡን እያንጎደጐደ መንገዱን ቀጠለ ። ሰውዬውም እንኳን ነፍሴ ዳነ እንጂ ስድቡስ አይጎዳኝም እያለ ወደመንገዱ ሄደ ። ይህን የዋህ ባላገር እግዚአብሔር ከነበግህ ዳን ቢለው ወደ ወንዙ ሸሸ እንጂ ወደፊትስ ሸሽቶ ቢሆን እንደ ነጂው ሐሳብ ባልዳነም ነበር ።

አሁን ይኸ ነጂ ልጅ ከትምሕርት ጉድለት ስነ ተፈጥሮውን ባለ ማወቅ የእግዚአብሔርን ፍጥረት ሥሩት የኢትዮጵያን ሕዝብ ብዛት ባለማወቅ የተነሳ ይህ ለማስዳጥ የፈለገው ሰው የገዛ ወንድሙ የአዳም የኖህ ልጅ መሆኑን ፈጽሞ አልተረዳውም ። ነገር ግን በነጂው ክፋት በባላገሩ የዋህነት ረቂቅ ፍርድ አዋቂው እግዚአብሔር ስላዳነው በመገረሚ በትክክል አልገመትኩትም እንጂ ይህ ነጂ ልጅ ሐያ ዓመት እድሜ ያለው አይመስለኝም ባገራችን ሽማግሎች እንደሚሉት ሐያ ዓመት ያልሞላው ልጅ ወደምክር እንኳ አይገባም ይላሉ ። ይልቁንም ታላቅ ዕውቀትና ትዕግሥት የሚያስፈልገው የአቶሞቢል ሥራ በኢትዮጵያ ሕዝብ ይልቁንም በአዲስ አበባ ሰው ብዛት በአቶሞቢልም ፍጥነት የሰው ሞት የውሻ ሞት የሚመስለው ስነ ተፈጥሮውን ያልመረመረ ነፍስ ያላወቀ ልጅ ሲነዳ ለሕዝቡ እንዴት ያለ ችግር ነው ነፍስማ ላወቀ ሰው እንኳን የሰው ልጅ የለስራኤል ደምና የውሻ እንኳ ደም አለአገባብ በከንቱ ሲፈስ ያሳዝነዋል ።

እኔ ይህን ማለቴ ሊዳጥ የነበረውን ባላገር ሊድጥም የነበረው ነጂ ሁለቱንም አውቄያቸው አይደለም እንዲያው ነገሩ የግፍ መሆኑ ቢያሳዝነኝ ነው እንጂ

ይህም ከዚህ በላይ የተጻፈ የግፍ ሥራ እንዳይሠራ ሲል ማዘጋጃ ቤት ዘወትር በየጊዜው ለሕዝቡም ለነጂውም የሚስማማ ደንብ በማስታወቂያ ማውጣቱ አልቀረም ዳሩ ግን ደንቡን ከሰማው ሕዝብ ያልሰማው ሕዝብ ስለበዛና ያልተማሩና ያልተቀጡ ትዕግሥት የሌላቸው አቶሞቢል ነጂ ልጆች ስለበዙ ሕዝቡ ተጨንቆ ይህንም መጻፌ ከዚህ በላይ በተጻፈው ነጂ ክፋት እሱን የመሰሉትን ለመምከር ነው እንጂ እጅግ የታመኑ ዕውቀትና ትዕግሥት የመላቸው ነጂዎች በሥራቸው የተመሰገኑ ብዙ የኢትዮጵያ ልጆች መኖራቸውን የሳትኩት መስሏቸው እንዳይቀየሙኝ ያቅርታቸውን እለምናለሁ ።

አቶሞቢል ነጂዎች ወንድሞቼ ሆይ እግዚአብሔር ሰፊ ልብ ትዕግሥት ይስጣችሁ አቶሞቢል ላይ ሆናችሁ ሰው ብትገድሉ መዳን የለም በመሬት ቆማችሁ ይፈረድባችኋል ፤ ሰው ገድሎ አቶሞቢል ላይ ቁጭ ብሎ መቅረት የለም ይህም ነገር ለመንግሥታችን ሁለት ጉዳት ይሆንበታል ፤ አንደኛ ደንቡን ያላወቀ ባላገር ሰው ባላሰበው አደጋ ድንገት በመሞቱ ፤ ሁለተኛ እንደዚህ በድፍረት ነድቶ ጥሩንባውን ሳይነፋ ሰው አስድጦ የገደለ ነጂ በፍርድ ባለመዳኑ መንግሥት ባንድ ጊዜ ሁለት ሰው ያጣል ።

አሁንም ለወደፊቱ በመንገዱ ላይ ቆሞ አላስኬድ እንኳ ቢላችሁ ይዛችሁ ለዘበኛ ስጡና የሚገባውን መቀጫ አስከፍሉት እንጂ ለሚያልፍ ንዴት ብላችሁ ወንድሞቻችሁን ለማስዳጥ አትድፈሩ ስል ወደፊት ተስፋ እያደረግሁ በሙሉ ኢትዮጵያ ባላገር ስም ሆኜ አጥብቄ እለምናችኋለሁ ።

ተስፋዬ ካሣ

የአቶሞቢል አደጋ

ጥቅምት ፲፱ ቀን ሙሴ ፖፖዱብሉ ከሚስታቸውና ካንድ ወዳጃቸው ከሙሴ ሚናስም ልጅ ጋራ በሆቴል ዳንስ ሲያደርጉና ሲጫወቱ አምሽተው በአቶሞቢል ሲመለሱ ከጐለሌ ተነስተው አፈ ንጉሥ ነሲቡ ድልድይ ሲደርሱ አቶሞቢሉ መንገድ ስቶ አወንዙ ገብቶ እንክትክቱ ወጣ ። አብረዋቸው የነበሩ ሰዎች ቈሰሉ ሙሴ ፖፖዱብሉ እሆስፒታል ገብተው ወዲያው በቶሎ ሞቱ ሌሎቹ ይታከማሉ ።

ብርሃንና ሰላም ስለ ሟቹ ሐዘኑን እየገለጠ አቶሞቢል ለሚነዱ ሰዎች በራሳቸውና አቶሞቢል በተቀመጡ ሰዎች እንደዚህ ያለ አደጋ እንዳይደርስባቸው በጣም መጠንቀቅ እንደሚያስፈልጋቸው ያሳስባቸዋል ይልቁንም አቶሞቢል የሚነዳ ሰው የሚያሰክር መጠጥ ሊጠጣ አይገባም ። የሰከረ ሰው አቶሞቢል መንዳት ይቅርና የገዛ ራሱን በትክክል መንዳት አይችልም ።

ስለክቡር ሙሴ እስጢፋን ፖፖዝያኑ ከአውሮፓ መምጣት ።

ቀድሞ የኢትዮጵያ መንግሥት የረቂቅ ጥበብ ሥራ መሐንዲስ አርኪቴክት የነበሩ ሙሴ እስጢፋን ፖፖዝያን አውሮፓ አንድ ዓመት ቆይተው አሁን ወደ አዲስ አበባ መመለሳቸውን በደስታ እንሰማለን

እዚያም ሲኖሩ የነቁ ስለሆኑ ሰው ያልሰራውን ከሀሣባቸው አውጥተው የሰሩት መጀመሪያ ሊንድቤርግ የሚባል ያሜሪካን ሰው የሰማይ መርከብ ተቀምጠው ከሜሪካ አገር ተነስተው የትም የትም ሳይወርድ ሳያርፍ አንቅልፍም ንቀው ባሕሩንም ምድሩንም ሳይነካ ከነፋስ ውስጥ ብቻ ሁኖ በቀጥታ አስቀድሞ በተወሰነው ሰዓት ልክ ብቻውን ደርሶ ፓሪስ ስለገባ ዓለምን ሁሉ አስደነቀ ስለዚህ ካንድ ንጉሥ የሚበልጥ ከበሬታና ምስጋና ያገኘ ስለሆነ እሱ የሰራውን በመታሰቢያ አርገው የምስጢሩ ሀሣብ በወረቀት ላይ በስዕል ገልጸዋል ፤ ሁለተኛ ኑንጀሴሮና ኮሊ የተባሉ ደፋር የሆኑ ሁለት የሰማይ መርከብ የፈረንሳይ ነጂዎች እንዲሁ በጣም የተራራቁ ካንድ አገር ተነስተው ወዳንድ አገር በሰማይ ሲበሩ እስከዛሬ በደህና መድረሳቸው ሳይታወቅ ስለቀረ በጉብዝናቸው የተደነቀ የተገረመ መሆኑን የሚያሳስብ ሀሣብ በዕል አርገዋል ።

ሰስተኛ ቢርድ የሚባል ያሜሪካን ሰው ያሜሪካን ሕዝብ ፍቅርና የፈረንሳይ ሕዝብ ፍቅር ለማጥናት ብለው አመሪካ አገር በፈረንሳይ መንግሥት እርዳታ አርንታቸውና ነፃነታቸውን ያገኙበትን በጣም ያረጀና የተቀዳደደ የጥንት ሰንደቅ ዓላማቸውን ደግሞ ያመሪካን መንግሥት እሰታ ደብዳቤ ይዘው ለፈረንሳዊ መንግሥት በሰማይ መርከብ ከሰማይ መንገድ ያመጣበትን ምስጢር ሀሣብ የሚያሳስብ ስዕል አዘጋጅተዋል ። ይህም ሁሉ ባመሪካንና በፈረንሳይ አገር ደስ አሰኝቶ በጣምስለተመሰገን ለሕዝቡም መማሪያ እንዲሆን ብለው ደግሞ መታሰቢያም እንዲሆን ብለው ሊቆቹ እመንግሥት መታሰቢያቤት አግብተው ተቀምጧል ። ከዚህ በላይ የተጻፈው ለፔቲ ከተባለ ጋዜጣ የተገለበጠ ነው

ሙሴ እስጢፋን ቀድሞም የመንግሥታችን ሰራተኛ ስለነበሩ ። ደግሞ ኢትዮጵያን ወደው የኖሩበት አገር ስለሆነ ከፈረንጅ አገር ያገኙትን ክብርና ምስጋናው ለነርሱ ብቻ ሳይሆን ለኛ ላገራችንም ነው ። አሁንም በገራችን እንዲህ ብልሀተኛና ጥበብ አዋቂ ሰዎች የሚወደዱ ስለሆኑ ሙሴ እስጢፋን እዚህ ተቀምጠው ላገራችን ያገለግላሉ ብለን እንመኛለን ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዝይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፭ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፪ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
ኀሐ ጽባሕ	፭ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማርኛ ሰዋሰው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዑል ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማርኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ከ፫ ሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር ፫ ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ። ተሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ።
ጋዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፩ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፯ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፯ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲፩ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፯ ብር
አቡጀዲ መንጸር	፩ ኮረጃ	፻፵፩ ብር
፡፡ ባነሳይጣን	፡፡	፻፵፯ ብር
፡፡ ባለ ድመት ፡፡		፻፴፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፯ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፴ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፩ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፰ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ	፲
አንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ	፰ ሳንቲም
ባአንድ ጊኒ	፲ ብር ፪	ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፱ ብር	

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ማስታወቂየ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሐ. ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET
AGENTS

H. M. ZERVOS & Cie.

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የሚባል ባለአንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቀቅዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሰያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል"አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ"ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዴልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አሉው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ለ/ተከ፡ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንዳርድ ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ክች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኪንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፥ ሽቱ ፥ ለስ ዩን ፥ አድኮሎኝ ፥ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፥ ኳኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፥ ከፈይ ምንጣፍ ፥ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና ከሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፥ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ኤን ቤ ኤዲሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ ። የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቋውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

ዓለም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠራል ።

ኒኮላ ።



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድደር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዘል ደ ጓሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆ ን አያስፈራም እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያደጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስ ቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድደር ብዙ ከሌላው ላስ ቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩ ል ነው ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

ጉድደር ገዛ

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሂስኪልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፥ ባለ አጉበርና አጉበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፤ መጫሚያ በያይነቱ፥ ወንበር በየዓይነቱ፥ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፥ ቢሲግሌት ፥ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፥ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፥ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፫
3 me ANNÉE № 43

ሐሙስ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 3 NOvembre 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።	የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ደክፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ደሸጣል ።	Abonnements Ethiopie: Un an 5 Thalers Etranger: Un an 7 Thalers le numero 2 piastres

የኢትዮጵያ ጭንቀት ።

የኢትዮጵያ ጭንቀት ብዙ ነው ከብዙውም አንዱ ይህ የሚከተለው ነው ለአዲሱ ትውልድ ወይም ለኢትዮጵያ ወጣት ሁሉ ለማስተማርና ለማሳደግ የሚገባና የሚበቃ ስላልተደረገ ይህ ለሕዝባችን ትልቅ ጭንቀት ነው ።

ወጣቶቹ በሁሉ ነገር በስርዓት ባይማሩ የትምሕርትና የጥበብ ወዳጆች ያንሳሉና እነኝህ ለሕዝብ የሚጠቅመውን ነገር ሊያደርጉ አይችሉም ። ያልተማረውን ሕዝብ ወደ ስልጣኔ ለመጐተትና ለመምራት ብዙ ያስቸግራል ። ደግሞም ከቶ የማይቻል ነው ። በሌላው መንገድም የሕዝቡ ልብና አሳብ ባንድ ሊሰበሰብና ሊስማማ አይሆንም ። ትምሕርት በሕዝቡ ይልቁንም በወጣቶቹ ቢሰለጥን ግን ያንጊዜ ለሕዝቡ የሚጐዳውና እውነተኞች መሻቶቹም በማወቅ ሊስማማ ይቻላል ። ስለዚህ ይሄው ነገር ኢትዮጵያ መንቃት በጀመረችበት ዘመን ዓይነተኛ ነገር መሆኑ ታወቀ ። ሁሉ እንደሚያውቀው በግርማዊው ንጉሠ ነገሥት በዳግማዊ ምኒልክ ፈቃድ ተማሪ ቤት ማቆም ተጀመረ ወደውጪ አገር ሳይቀርም ለማስተማር አንድ አንድ የላኩ ይመስለኛል ። ከርሳቸውም በኋላ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ይህ ደስ አሰኝቷቸው ተማሪ ቤቱ እየተሻለና እየበለጠ እንዲሄድ በብዙ ትጋትና በጽኑ ፈቃድ ይጠባበቁታል ። እንዲሁም የኢትዮጵያመንግሥት አልጋ ወራሽ ጌታችን ልዑልተፈሪ መኰንን የጃንሆይን ፍለጋ ተከትለው ሌላውን ተማሪ ቤት አቆሙ ። ደግሞም ብዞች ወጣቶች ዓመት ላመትወደውጪ ይልካሉ ይህሁሉ መልካም መጀመሪያ ነው ። ጃንሆይ ተማሪ ቤቱን ለማቆም የፈቀዱ ፤ ትምሕርትና ጥበቡ ዕውቀትም ለእውነተኛው የሕዝብ ኑሮ መሰረት ስለሆነ ተረድተውት ነው ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑልአልጋ ወራሽም ይህን የተሳጣቸውን ምሳሌ ጠብቀው ፤ የጃንሆይን የተጀመረው ስራ ወደ ፍጽምና ሊያደርሱት የሚጣጣሩትን ብዙ እናመሰግናቸዋለን ። ለወደፊትም በዚሁነገር ከቶ እንደማይደክሙ በኢትዮጵያ ያለውንም ጨለማነት በፍጹም እንዲያበርሩት ጽኑ እምነት አለን ። ደግሞም ብርሃኑ እያበራ ጨለማው ወደኋላው እያፈገፈገመራቅእንደጀመረ እናየዋለን ።

ቢሆን በሕዝባችን ሰልጥኖ ያለጨለማነት እጅግ ብርቱ ነው በማይደክም መንፈስ ጽኑ ስራ ያስፈልጋል ። ግን ይህን ነገር ለማድረግ ከመንግሥት ብቻ መፈለግ የሚገባ አይደለም ። የዚህን ብርሃን ጣፋጭነት የቀመሱ የሆኑ ሁላቸውም የትምሕርትን ብርሃን በሀገራችን እንዲሰለጥን ሊያግዙና ሊረዱ ትልቅ ዕዳቸው ነው ። እንያም የትምሕርት ብርሃን በሕዝባችን እንዳያበራ የሚቃወሙ ያሉ ወይም ይህ ብርሃን የታመመውን የአእምሮዋቸው ዓይን እየሣቀ የሚኖረውን በፍጥነት ሊፈውሱት ያስፈልጋቸዋል ብርሃንን ለማየት ሊችሉ ። ብርሃን ሕይወት ነውና ። ፊት በገዛ ራሳቸው የብርሃኑን ጥቅም ይሞክሩት ከዚያ ወዲያ ይህ ትምሕርት ለሕዝብ ፊተኛው የደህንነት መሻት እንዲሆን ሊያዩ ይጀምራሉ ።

ከፍ ባለው ትምሕርት ለመድረስ ብዙ ገንዘብ እንደሚያስፈልግ ሁሉ የሚያውቀው ነው ። እ፡ግዲህ ወደዚህ ለመድረስ ገንዘብ የሚያስፈልግ ከሆነ ሀብታሞች ብቻ በእግዚአብሔርና በሰው ፍርድ ሊያደርጉት እንደተገባቸው ይፈርድባቸዋል ። ስለዚህ እነኛ ሀብታሞች ሰዎች ትልቅ ወቀሳ አላቸው ሊያመልጡበት የማይችሉትን ። ኢትዮጵያ ባለቤትዋ እኒህን ሰዎች ትከሳቸዋለች ። ገንዘባቸው ለኢትዮጵያ ጠቀሜት ከማጥፋት ይልቅ ለከንቱ ነገር እርሳቸውም በገዛ ራሳቸው በሕይወታቸው መጨረሻ ወደ ሚጠጡበት ሲያፈሱትና ሲጫወቱበት ይውላሉ ። ኢትዮጵያ ግን በብርቱ ጭንቀት ትኖራለች ። የተሻሉቱ የሚባሉም ባይጫወቱበት ለኋለኛው ቀን ይሆነናል በማለት በጽኑ ስፍራ ወይም አባንክ አኑረውት ይሆናል ። እንዲህ ያለ ሥራ

ግን ሕዝብንና መንግሥትን አያሠለጥንም ለሕዝብና ለመንግሥት ጠቀሜት ያልተሠራለት መዝገብ ግን ለጠላት ይጠበቃል ። የሕዝቅያስ ንጉሥ ገንዘብ ወደ ባቢሎን እንደ ተማረከ ማሰብ ይገባል ። (ኢሳ ፴፱ ፯) የገንዘብና የሀብት እውነተኛ አዋዋል ከትምሕርትና ከጥበብ ወደ ሚያደርስ ነገር ማዋፋት ብቻ ነው ። በዚህ የጠፋ ገንዘብ ፍሬውን በብዙ ዕጽፍ ይዞ ይመለሳል ። እንዲህ ያሉ ሀብታሞች ሰዎች ደግሞ ኢትዮጵያን እንወዳታለን የሚጠቅማትንም ነገር እናስብላታለን የሚባል የሰናፍጭ ቅንጣት የምታሕለውን የንጹሕ አሳብ ከልባቸው ውስጥ ያላቸው እንደሆን የኢትዮጵያ ወጣቶችን በገንዘባቸው ማስተማር ብቻ ነው ። አለዝያስ በሌላ መንገድ ከቶ ሊረድዋት አይቻላቸውም ። ደግሞም የሌሎችን ልጆች ማስተማር እንዳይከብድባቸው የገዛ ልጆቻቸው የገዛ ዘመዶቻቸው የገዛ ወዳጆቻቸውን እንኳ ቢያስተምሩ ለኢትዮጵያ ብዙ ጠቀሜታ በሆነላት ። ባይሆን ኃይል ካገኙ የትምሕርትንና የዕውቀትን ስጦታ የተሰጣቸውን ወጣቶች የማናቸውም ልጆች ቢሆኑ በትምሕርት መርዳት ይገባ ነበር ። ይህ ባይሆን ግን የገዛ ልጆቻቸውን ቢያስተምሩ ትልቅ ሥራ ነው ። ዛሬ እንዲህ የመሰሉ ሰዎች ልጆቻቸውን ባያስተምሩ እኒህ ልጆች የትምሕርትና የዕውቀትን ጣዕምና ብልጫ ሳይረዱት አይቀርምና ። ስለ አላስተማሩዋቸው ወላጆቻቸውን መራራ እርግማን የሚረግሙባቸው ቀኖች ይመጣሉ ። አንድአንድም ድሮ ወላጆቻቸውን በሚቻላቸው ስለ አላስተማርዋቸው ሊረግሙዋቸው ጀምረዋል ።

ቅዱስ ጳውሎስ በግብረ ሐዋ ፲፯ ፴ እግዚአብሔር የድንቁርናውን ወራት አሳልፎታል ይላል ። ማናቸው ነው እንግዲህ እኔስ በድንቁርናዬ ልኖር እወዳለሁ የሚል ። እንዲህ የሚወድ ያለ በእግዚአብሔር አዋጅ ዓመጸኛ ሆኖ ይገኛል ። እግዚአብሔር ሲያውጅ ፤ እኔ የድንቁርናውን ዘመን አሳልፌዋለሁ የዕውቀትና የትምሕርት የብርሃን ዘመንም አዝዣለሁ ። ሰማያዊው ንጉሥ እንዲህ ብሎ ሲያውጅ ምድራዊዉም መንግሥት ይህን አዋጅ ሰምቶ በመንግሥቱ ግዛት ቢያውጅ ምን ማድረግ ይገባል

እያንዳንዱ በሥጋ በነፍስ በመንፈስ ያመጣለትን እውቀት ለማግኘት ሊተጉል ያስፈልገዋል ። ይህም አይበቃም ። በእጅግ ፍጥነት ከድንቁርና ቦታ ወጥተን ወደ እውቀት ቦታ ልንሻገር ይገባናል ። ወደ እውቀት ብርሃን የደረሱ አያሌ ናቸው ። ዳሩ ግን መጠነከከር ያስፈልጋቸዋል ። ብርሃናቸውን ዘወትር ያክሉለት ከድንቁርና ነፋስ እየተጠበቁ ፤ ለወደፊትም መራመድ ከቶ አይሰልቹ ። በመጨረሻ ብርሃን ሊያሸንፍ ነውና ፤ ዳሩ ግን ይህ አለመስዋዕትና አለመጋደል አይፈጸምምና ፤ በዚህ በሥራቸው ተስፋ ሳይቆርጡ በጽኑ እስከ መጨረሻው ይጋደሉ ። በጎ ነገር ለመሥራት ተስፋ መቁረጥ የድል መነሣት ፊተኛ ምልክት ነውና ማንም በጎ ፈቃድና አሳብ ያለው ተስፋ ሊቆርጥ አይገባውም ። በትዕግስትና በጽኑ በማይናወጥ ኃይል በጎ ስራን የሰራ ምንምለጊዜው የድካሙንና የልፋቱን ፍሬ ባያይ በመጨረሻው እርሱ ቢያየው ወይም ባያየው የበጎ ስራው ፍሬ ሳይገልጥ የማይቀር ነው ። በእንዲህ ያለ ጽኑ ጠባይና መንፈስ የተደረገ ስራ ብቻ ነው ደግሞ ፍሬ ሊያፈራ የሚቻል እንጂ በመጠራጠርና በመስጋት ተስፋ በመቁረጥም ወይም ሊያደርጉት ያሰቡትን እስከ መጨረሻ አጽንተው ባለማያዝ በሚሰራ ስራ ጥቅም የለውም ።

ወዳጆችና ወንድሞች ጌቶችም ባለጠጎችም ይህንን በቁም ነገር እንድታስቡበት እለምናችኋለሁ ። ይህ የኢትዮጵያ ወጣት ምን ይሁን እንዲያው ድንቁርና ይግዛው የሕዝባችን ትልቅ ጭንቀት ይኸውላችሁ ። እያንዳንዱ ወጣት የትምህርት መጀመሪያ እውቀቶች (ኤለመንታር) ሊማር ግድ ያስፈልገዋል ። እንዲሁም ከፍ ያሉ የልዩ ልዩ እውቀት ትምህርት እንደሰጥዎታው መጠን ሊማር ያለዚህ ትምህርት ሕዝባችን ይጉዳል ። ስለዚህ እንዲህ ያለ ጩኸት ከያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ በቁም ነገር እንዲገባና ችሎት ያለውም ይህን ምክር ለማድረግ እንዲፈጥን ተስፋ አለኝ አሁንም ያሉ ሀብታሞች መኳንንቶች አገረ ገዦዎችም አንድ አንድ ወጣትን በብስልነት ትምህርት ለማሳደግ መቸ በቸገራቸው ። እንዲህ ቢያደርጉም የድንቁርናው ጨለማ በቶሎ በጠፋ ጨለማ ብርሃንን ቢያበዙበት ነው የሚቀር እንጅ በሌላው አይሸሽም በሕዝብ ያለው ድንቁርናም የተማሩ ሲበዙ ይጠፋል ።

ትምህርት በማለቱ ግን እንዲያው የአእምሮ የማጥናት የሆነ ብቻ እንዳልሆነ አስታውሳለሁ ለልብና ለጠባይ ለህይወት ለአካሄድም ሊያድስ የሚችል ትምሕርት ይህ ነው ። እውነተኛው የእውነተኛው ትምህርት ፍሬ ይህ ነው ። እንግዲህ በመንግሥት ተማሪ ቤቶችና በሌሎችም ያሉት ሁሉ በማስተማርና ራሳቸውን አርአያ እያደረጉ ሊያሳድግዋቸው በእግዚአብሔር ፊት ጽኑ ጥያቄ ያለው አግበአቸው ነው ። ይልቁንም ነፍሳቸውን ለሚያስተምሩዋቸው ልጆች በምሉ ነገር ምሳሌ ሊሆኑዋቸው ግድ መሆኑን እንዲያስቡ ምንም መልካም ትምህርት ቢሆን መምህራኖቹ እንደ ሚያስተምሩቱ በተማሪዎቹ ፊት ባይኖሩና የገዛ አካሄዳቸው ባይቀና ከቤታቸው ሆነው የሚማሩቱ ልጆች ብዙ ይጎዳሉ ልብንና አካሔድን በቀናው መንገድ ለመምራት አናንዋርንና ልማድንም ሊለውጥ የማይችል ትምህርት ዝም ብሎ ልፋት ነው ። እንደዚህ ሆነው በባህርያቸው በደግነት ያልተለወጡት ልጆችና ወጣቶች ለሀገራቸውና ለመንግሥታቸው የባሰ ጉዳት እንጅ አንዳች ጥቅም አያመጡላትም ።

እንዲሁም እንደ መጻሕፍቶች ልጆች ሊያነቡዋቸውና ሊማሩዋቸው የሚገባቸውም ደግሞ ልጆችን ለማስተማርና ወደ በጎ እውቀት ሊያደርሱዋቸው የበቁ እንዲህ ያለውንም ትምህርት በሙሉ የያዙ ሊሆኑ ያስፈልጋል ። ለተማሪ ቤቶችም አንዱ ካንዱ በኋላ እየከታተሉ በተራ እስከ አምስት እስከ ስድስት ሔጻሕፍት ያስፈልጋል ። እነኝህም መጻሕፍቶች ለማስተማር የበቁ መሆናቸው ተመርምሮ በመንግሥት ታይተው ሊታተሙ በመንግሥቱ ውስጥ ያሉ ተማሪ ቤቶችም ሁላቸው የመንግስቱ ሆኑ የሚስዮኖቹ በነዚህ መጻሕፍት ብቻ ሊማሩ ግድ ያስፈልጋል መጻሕፍቶቹ ግን መካከለኛ አሳብ ያለባቸው እንጅ በአንዳቸ ነገ የሌላውን አሳብ የማይጐዱ ለሁሉ ተማሪ ቤቶች የሚስማሙ ሊሆኑ ይገባቸዋል ይህም ማለት የሃይማኖትን ትምሕርት የሚወስኑ እንዳይሆኑ ሁላቸው ግን በተማሪ ቤቶቻቸው ሊሰሩላቸው

የሚቻላቸውን በሁሉም እጅግ የተቀበሉ ሊሆኑ ይህም እንደ አጻጻፋቸው ነውእንጂ አያስቸግርም ። ጠቀሜታቸው ባልተመረመረና ባልተመሰከረላቸው መጻሕፍቶች ማስተማር ረብ የለውም ደግሞም ልጆቹን ባንዲት መጽሐፍ ብቻ ማመላለስ ፍሬ አይገኝበትም ። ከቀለለው ወደ በረታው በየደረጃ ባይሻገሩ ተማሪዎቹ ይከብዳቸውና ይጐዳሉ ። በተራ በተስማማ መንገድ ለአእምሮአቸውና ላቅማቸው እንደተገባ ቢማሩ ግን እየጨመሩ ይሄዳሉ ። እንዲህ ብለውም ከፍ ወደላዉ ደረጃ ይደርሳሉ ። እንግዲህ ተማሪ ቤቶችን የአካሔዳቸውም ነገር በጽኑ መጠባበቅ ሁለ ጊዜ ያስፈልጋል የማናቸውም ተማሪ ቤት ቢሆኑ በሥርዓት ተማሪ ቤት ተብለው ከተከፈቱ መምሕራኖችም ይህንን ነገር በእጅግ ትጋትና በምሉ የአገራቸውን ፍቅር እንጂ እንዲያው ደሞዛቸውን ለማግኘት ብቻ በሚፈልግ አሳብ እንደማያደርጉት ተስፋ አለኝ ፣

እንግዴህ ልጆችንና ወጣቶችን ማስተማር ከፊተኞቹ ከዓነተኞች የህዝብ ጠቀሜት እንዲሆን ይህነንም ችላ ማለት በዚህም በፍጥነት ለወደፊት አለመገፋት ለሕዝባችን ብርቱ ጭን እንዲሆን እርግጥ ነው ። ሕዝባችንን ከፍ ወዳለው የሕዝብ ኑሮ ደረጃ ለማድረስ በዚህ ብቻ ነው ። የሚቻል ወደቀኝና ወደግራ ልንዘነብል አይገባንም የሕዝባችንን መጀመሪያ ጠቀሜቶችና እንዲሁም መጀመሪያ ጉዳት የሚያመጡብንን እያየን የተለሳንን ስራ ልንፈጽም እንጋደል ።

ከዚህ ሁሉ ጋር ግን የተማሪ ቤቶችና የሁሉ ትምሕርት መጨረሻው የሚፈለገው ነገሩ ምን እንደሆን ለመምሕራኑ በጕልህ ሆኖ ሊገልጥላቸውና ሊረዱት ይገባል ። ይህም ልጆችና ወጣቶቹ በባሕርያቸው የሚታደሱበትና የሚያቃኑበትም ነው ። ክቡር ሙሴ ሙሶልኒ በተማሪቤቶች ማሕበር ጉባኤ ለአሳዳጎች ወይም ለመምሕራን ሲናገሩ ሳሉ እንዲህ አሉ ፡ ተማሪ ቤት ሁሉ ተማሪ ቤት ከሁሉ አስቀድሞ አሳዳጊ የባሕርይ ሰብሳቢ ንጹሐዊ እንዲሆን አሳቤ ነው ። ባለፈውና ባሁኑ ባለው ሊቅነት አናትን ማጠጣት አያስፈልግም ሊቅነት አናትን ለማሳደግ እንደሚያስፈልግ እንደ አንድ አይነት የሽዌድን ጂምናስቲክ(የአካል መንቀሳቀስ ትምሕርት) እንጂ ከዚህ አልፎ ሌላ ሊሆን አይቻልም ። የሚጠቅመውም ቶሎ እስከ መረሳቱ ነው በዚያ በማይጠቅመውና በማያስፈልገው ምርምር ። ግን ተማሪ ቤት የኢጣልያኖችን ባሕርይ የሚያድስ ሊሆን የሚያስፈልግ ነው ። ባልንጀሮቼ ሆይ ይሄውላችሁ ያነጊዜ ነው አግበዋችሁ መጠን የሌለው ቍም ነገር የሚሆን ። የተማሪ ቤት ሪም ከሚል ጋዜጣ የተገኘ ሮማ ፲፫ ታሕሣሥ ፲፱፻፳፫ ፱ ኛኛው ተራ።ይሄው እጅግ እርግጥ የሆነ ነገር ነው ፤ የትምሕርት ሁሉ መጨረሻ የሥጋ የነፍስ የመንፈስም ጠቀሜት ሲገኝለት ነው እንግዲህ በትምሕርት ቤቶች ያሉ አስተማሪዎች መጋደላቸው ወጣቶችን ለሕዝባቸውና ለመንግሥታቸው የሚጠቅሙ ሊያደርግዋቸው ከሆነ ። እኒህን እርእሰተ ነገሮች አድርገው ያስተምሩዋቸው ፡ ምሉ የአካሔድ ስርዓት (ዲሲፕሊን) እውነት መናገር ፡ አመለኝነት ወይም ክፉ ልማድ የሌለባቸው መሆን ፡ ትዕግስተኞች የታመኑ ልዝቦች ትሑታን ታዛዦች ሥራ ወዳጆች በባሕርያቸው የጸኑ ጀግኖች አስተዋዮች በመሞላቀቅ የማይኖሩ ኢትዮጵያን አገራቸው በጣም የሚወዱ ጤናዎች በአካል በልብስ በመንፈስ የጠዱ ። ይህንንም የመሰሉ ። እንዴህ ብለው ሲያድጉ ለአገራቸው ብዙ በረከት ያወርዳሉ። በተቀር የትምሕርቱአኳኋን እንዴህ ያሉትን አብነቶች ዓይነተኞች ነገሮች አድርጎ ሳይነካ የቋንቋ የጽሕፈት እንዴሁም የሚመስለውን የራስ ዕውቀት ብቻ ሆኖ እንዳይቀር ያስፈራል። ስለዚህ በትምሕርት ቤቶች ያሉ መምሕራን የእውነተኛው አስተማሪ ደምብ በአስተማሪነት ፔዳጎጂ ስርዓት የሚገኘውን አጽንተው እየመረመሩና እየተመለከቱ ሊያስተምሩ ይገባቸዋል ። ያንጊዜ ኢትዮጵያን በእውነት የሚጠቅሙዋትና ሕይወትዋንም ሊያድሱና ሊመሩ ኃይል ያላቸው ወጣቶች ይገኛሉ ። ወጣቶቹ ለኋላው የሚኖሩበት ሕይወት በተማሪ ቤቶች ይኖሩት እንደ ነበር ልክ ነው የሚኖሩ ። አንድ አንድ ተማሪ ቤቶች ወጣቶችን በጣም የሚጐዱ አሉ ። ስለዚህ ተማሪ ቤት ስለ ተባለ ሁሉ እኩል ሆኖ የሚጠቅም አይሆንም ። እንደ መምሕራኖቹና እንደ ደምቡ እንደ ተማሪ ቤቱም አኳኋን ነው ። እንግዴህ በተማሪ ቤቶች የሚማሩ ያሉትን ወጣቶች እንደሚገባቸው ተምረዋል ሊባሉ የሚቻለው ትምሕርታቸው ለልባቸውና ለነፍሳቸው ለመንፈሳቸውም ቢለውጥ በሕይወታቸውና በሥራቸውም ሁሉ በቀናውም ጐዳና ሊመራቸው የሚችል ሲሆን ነው

ቢሆን ግን ብዙ ጊዜ እኛ ልናደርገው በሚገባንና በሚቻለን ነገር ሳይቀር በመንግሥት ብቻ እናከብዳለን መንግሥት ይህን ቢያደርግ ይህንንም ቢፈጥር እንላለን ዳሩ ግን ከሕዝባችን ልጆች ለመንግሥታችንና ለወገናችን እውነተኛ ጠቀሜታ የሚሆን ያሰዩ አለማን ናቸው ስንትስ ይሆናሉ በሰፊውና በጥልቁ አሳብ ስለ ሕዝባቸው የሚያስቡ ደገኞች አሉ ቢሆንብዙች አይደሉም ጉዳቱም ይህ ነው እንግዴህ ኢትዮጵያን በቁም ነገር የምንወዳትና በጎውን ነገር ሁሉ የምንመኝላት ብንሆን ልናደርገው በምንችለው ነገር ሁሉ ፍቅራችንን በማድረግ እና ሳያት ከሁሉ በፊት እራሳችንን እናስተምር እኛ በተገባ ዕውቀት እኛንና ሕዝባችንን በሚያድን እውቀት እንደግ ከዚህ በኋላም የኢትዮጵያን ወጣቶች ለማስተማርና እንደሚገባ ለማሳደግ እንሻማቸው ይህንን በውነት ከፈጸምን ኢትዮጵያን ከለልባችን ውስጥ እንደምንወዳት ይታያል እንዲህ ባሉ ወጣቶች ብቻ ኢትዮጵያን ለማዳን ይቻለናል ስለዚህ ጊዜ ያልፋልና በቶሎ ይህን ለመጸም እንትጋ ። ዕ ገ ።

ስለ መረዳዳት ።

በብርሃንና ሰላም ፴ ቁጥር ፫፻፺፯ ገጽ ስለኢትዮጵያ ቆንጃጅት በቀለ ዘለቀ የጻፈውን የኃሳቡን አካሄድ እስኪ አራቅቀን እንመርምር ለክቡራት ወይዛዝር እንቁጣጣሽ ብያችኋለሁ ሲል ያየባችሁን ጉድለት ስለመምከሩ በጣም የሚገባ ምክር ነውና በማክበር ያቀረበላችሁን እንቁጣጣሽ ከልባችሁ ልትቀበሉት ውዴታችሁ ይሁን ። እኔም እነሆ ቁጭ ብዬ ሳስተነትንና ሳስብ ሳለሁ ያገሬን ሴቶች ቈንጆናችሁን የሚቃወም ይህ ጕኑ ስፊና ቁመቱ ረጋሮም ተሚላቸው ደግሞ ጸጉራችሁንና ፊታችሁን በሙሉ የምትሸፍኑበት ሻሽ ወይም ዓይነ ርግብ የተባለ ያ ክፉ

ልምዳችሁ እነዚህ ፫ቱ ብቻ ናቸው ይመስሉኛል ። ያገሬ የኢትዮጵያ ሴቶች ትንሹም ትልቁም ሁሉ የደም ግባትና የቁንጅ የመልክ ማማር እድል ሰ ቶችሁ ወደ ስልጣንና አልተጋችሁምና ስለዚህ እጅግ ውብ የሆነ መልካችሁ ባለባበስና በመሸፋፈን ይበላሻል ።ነገር ግን ለማየቱ የሚያስቀይም ነገር እንኳ ቢሆን በሰው ዓይን ሊሸፈን ግድ ነው እስኪ ፊታችሁን የሚያምር ጸዳላችሁን ፈገግ ብሎ እንዳይታይስ እንደሚደበቅ ነውር ሁሉ ሸፍናችሁ መሄዳችሁ ከቶ ለምን ነው ። ምሳሌ ከናቷና ከመምህሯ በቀር ሰውን የማትጓደድ አንዲት ልጃገረድ ወደ ማታ ጊዜ የጤና ንፋስ ለመቀበል ከቤቷ በታች ወዳለው ወንዝ ሄደች ከዚያም ንስፋ የሚቀበሉ ብዙ ሰዎች አየችና አፍራ ፊቷን በመንዲል ሸፈነችና ወደ ቤቷ ሄዳ ሰዎች ቢያዩኝ አፍሬ ተመለስኩ ብላ ለመምህሯ ነገረች መምህሯም ብዙ ጊዜ ምክርና እውቀትን ሲያስተምራት ኖሮ በመጨረሻው ይህን ግብዝናዋን ስለሰማ ተሥፋ ቆረጠና እንዲህ አለ ፊትሽ እንዳይታይ ለመደበቅ ከፊለግሽ ሁሉን ነገር ሊሸፍንና ከሰው ዓይን ሊደብቅ የሚችል ቤት ነውና ስለዚህ ከቤትሽ ባልወጣሽ በተሻለሽ ነበር አላት እሷም ሰው እንዳያያት ፊቷን በመሸፈኑዋ ትልቅ ነውር እንዳደረገች በህሊናዋ ተረድታ ከዚያን ለት ወዲህ በውጭ ሆና የሰውን ልማድና ባህርይ መረመረች ።ፊት ያደረገችውንም ሁለተኛ አልደገመችውም እናንተም የዚች ልጅ ትጋት ሊገባችሁ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያን ወዳጆች ልማድና ባህርይ መርምሩ ከዚያ በኋላ ይህንን ለማድረግና ለመፈጸም ኃሳባችሁ እንዲፈቀድላችሁ አይጠረጥርም ስለ ቁንጅና በዓለም ላይ ስማችሁ ከፍ ብሎ ስለተጠራ ፈረንጆች እንኳ እንዲህ እያሉ በዜማ ይዘፍናሉ ለፋም አቢሲኒ ጕርሊ ኮም ደሎ ትርጓሜው የኢትዮጵያ ሴቶች ቁንጆዎች እንደ ጥሩ ውሃ ማለት ነው ። በዚህ በተሞገሰ ቁንጅናችሁ ስልጣኔን ከጃችሁ አድርጋችሁ ባለባበስ ብትቀለጥፉና ለሥራ ብትተጉ ኢትዮጵያ እንዴት ደስ በላት ነበር ። ደግሞ መልሶ ያገራችን ሰው ሲተርክ ሆድና ግንባር አይሸሸግም ይላል እያችሁን ይህን ምሳሌ ባገራችንም እክ ፊትን መሸሸግ ከትልቅ ነውር የሚቆጠር ነው ። ይህን መሠረት የሌለው ልማድእን ዲቀር እግዚአብሔር ሕሊናችሁን ወደ ሥልጣኔ እንዲያቀናላችሁ ተስፋ እናደርጋለን ። ጅማ ወልደ ገብርኤል ።

ስለ ብርሃንና ሰላም አላላክ ።

ብርሃንና ሰላም ሳያቋርጥ በየሳምንቱ ስለ እውቀት በውጪ አገር ለተሰደድነው የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ እየደረሰን የቅድስት አገራችንን ወሬና ዳግማዊ ሰሎሞን ልዑል ጌታችን ላገራቸውና ለህዝባቸው የሚያሰሩትን ትልልቅ ሥራና ብልሆች ወንድሞቻችን ስለ ኢትዮጵያ ትልቅነት የሚሠሩትን ሥራና የሚመክሩት ምክር ሁሉ በየሳምንቱ ከብርሃን እየቀዳን በሰላም እየጠጣን ላገራችንና ለህዝቧ የሚጠቀመውን ብልሀት እየመደብን ተምረን ነገ ኢትዮጵያን ረጂና ህዝቧን ጠቃሚ እንድንሆን ሲል የብርሃን ግቢ የሚሠራው ሥራ እጅግ የታወቀ ትልቅ ነው ። እኛ ለቀለምና ለወረቀት ማሰናጃ አንዳንድ መሐለቅ እንኳ ለጊዜው የማንረዳ ተማሪዎች ነን ። እውነት ነው ። ተማሪ በእውቀቱ እንዲረዳ በመማሪያው ጊዜ መረዳት የተገባው ነው ።ያገሩን ጥቅም የሚሻ ሰውና ገበሬ አንድ ናቸው ። ዘር አውጥቶ መዝራትን እጅ ለጊዜው መበተኑን ማየት ለሚያመርት ሰው የማይገባ መሆኑን የተረዳው ብርሃንና ሰላም ከተወለደ ጀምሮ ለሁሉ ያስተምራል ። ተማሪዎቹም በጥቅሉ ብዙዎች ናቸው ። ወደ መምህራቸው ቃል ያዘነበሉት ጥቂቶች ናቸው ።

ክቡር ሆይ ብርሃንና ሰላም በውጪ አገር ላለነው ተማሪዎች የሚልኩልን ላገራት ጥቅምና ለመንግሥታችን ጥቅም ሲሉ በሰው አገር ያለውን ለመምከርና የኢትዮጵያችን ወሬ ለመስጠት ሲሉ ነው እንጂ ብርሃንና ሰላም የተገባውን ጥቅም አግኝቶ አይደለም ይልቁንም የወረቀትና የቀለም ማሰናጃ ከሚሆነው ገንዘቡ ለቴምብር ለፍራንኩቦል ይከሰክሳል ። የሚገባውን ገቢ ገንዘቡን ሳያገኝ ላገር ጥቅም ሲል ለተማሪዎች ሲሄድ ለቴምብር የሚያወጣው ገንዘብ ያልተገባው ነው ። ላገርና ለመንግሥት ጥቅም የሚላክ መልክተኛ ያለቀረጥ ኬላ ማለፍ የተገባው ነውና ስለዚህ ይህ አወጣጥ የማይገባው መሆኑን ለቦስታና ለተሌግራፍ ሚንስቴርም ግልጥ ሆኖ የሚታይ ነገር ነው ።

ከእንግዲህ ወዲህ ብርሃንና ሰላም ለጊዜው ገቢ ለማያገኝበት ላገርና ለመንግሥት ጥቅም እንዲሆን ወደ ተማሪዎች ሲላክ ቴምብር መግዛት አይገባውምና ይቅር ። ስለአገርና መንግሥት ጥቅም ለተማሪዎች ያለገቢ መላኩ እንዲያስታውቅና ከሌላው እንዲለይ በንበልጡ ላይ በማህተሙ ብቻ መመስከር ያስፈልገዋል ያመት ሆነ የዕለት ሆነ ገቢ ገንዘብ ለሚያገኝበት ሰው ግን ሲሄድ የተገባውን ቴምብር እንደ ደንቡ እየገዛ መያዝ በግድ ያስፈልገዋል ።

የገንዘብ ገቢ ለማያገኝበት ላገርና ለመንግሥት ጥቅም እንዲመክር በየሳምንቱ ተከያው ወደሚበልጥ ቦታ ላሉ ተማሪዎች የሚላኩ ይመስለኛል እንግዲህ በየሳምንቱ ለያንዳንዱ ሁለት ሁለት መሐለቅ ሂሳብ ለቴምብር የሚያወጣው በወር (፲፮) መሐለቅ ይሆናል ለኸያው ብቻ የሚወጣው ባንድ ዓመት ግን (፲፩) ብር ነው በማይገባው እንደዚህ ለቴምብር ማውጣቱ ቀርቶ ለቀለምና ለወረቀት መግዣ ይህ ገንዘብ ይጨመርና ብርሃንና ሰላም እንዲያድግልና እንዲሰፋ እንዲያደርጉልን ቢሆን መልካም ነበር የሚል ምኞቴን አጥብቄ ለክቡርነትዎ አመለክታለሁ ። ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ።

መ ወ ስ ።

የማይሞት ደግ ሥራ ።

፩ኛ ፤ የኢትዮጵያውን ቸርነት ይልቁን በመመጽወትና እንግዳ በመቀበላችን በታሪክ ሁሉ በጣም የተመሰገን ነበርን ግን ታሪኩ በአንድ ገጽ አሞግሶ በሁለተኛው ሲያማስነው ፣ ልብ አድርጎ ለተመለከተው ሰው እጅግ ያሳዝናል ። ኢትዮጵያውያን ቸሮች ተብለን ስንጠራ ፤ ፩ በጣም የተጐዱ ትልልቆች ድሆች በላያችን ተጭነውብን ሲኖሩ ፣ አለ መደንገጣችን ፣ ምናልባት የመዘንጋት ያህል እንዳይሆን ነው እንጂ ፤ በጭከናስ አይጠራጠርብንም ።

በዓለም ሁሉ ሲታሰብባቸው በኢትዮጵያ ብቻ የተረሱ ፬ ዓይነት ድኆች ልጆች አሉ ። እነዚህ ድኆች ሠርተው እንዳ ይበሉ ኃይል የላቸውም ፣ በምቾት እንዳይኖሩ ገንዘብ የላቸውም በጣም በሚያሳዝን ችግር እንደ ተንከራተቱ ከዚህ ዓለም ይለ ያሉ ። በድኅነት አጽረሞት የሚሳቡ ያሉ ልጆችዋን ኢትዮጵያ መቸ ታስታውሳቸው ትሆን ? አንዱ እንኳ ሊመልስ አይችልም ትንሽ ለማስተንፈስ ግን ፣ (ዕድሜያቸውን ያርዝም ነፍሳቸውን ይማር ዘር ዘራቸውን ከኢትዮጵያ ጋራ ለዘለዓለም ይኑር) ልዑል ተፈሪ ነፃነት ከሰጡት ፫ ዓመት ሁነዋል ።

፬ ፡ ድኆች ልጆች ኃይላቸውን ገንዘባቸውን ደማቸውን ጨርሰው ለእናታቸው ገብረውላታል ይገብሩባታልም እርስ ዋም ምን ልታደርግላቸው ይገባታል ? ብልህ ፈራጅ እሚያሰፈ ልግ ፤ የገበሩላትንልትጦራቸው የሚገብሩላትን ልታሳድጋቸው

በማናቸውም አገር መንግሥት አባትና እናት የሌላቸው ልጆች ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች ጠዋሪ የሌላቸው ሽማ ግሎች አሉ ። የመንግሥት የኢንዱስትሪዎችና የነጋዴዎች ሠራ ተኞች ለነሱ የመሰሉ የልዩ ልዩ ሥራ ጌታዎችም ፣ ለሠራተኞች ዘክታሞች ምሽቶችና ልጆች ለሽመገሉ ሠራተኞች መጠወሪያ የሚሆን ፣ ቀጥሎ እንደሚጻፈው ደምብ አድርገው በ፬ ዓይነት መንገድ ገንዘብ እያዋጡ ያጠራቅማሉ ።

፩ኛ የገንዘብ አወጣጥ ዓይነት መንገድ ።

የመንግሥት ሠራተኛ እንደ አቅሙ (ማለት እንደ ደመ ወዙ መብዛት) ለምሳሌ ፲ ብር በወር የሚበላ ሩብ ፣ ፻ ብር በወር የሚያገኝ ፪ ብር ተአላድ በየወሩ ከግምጃ ቤት እየተ ቆረጠ ወደ ባንክ ይገባል ። ይህ ገንዘብ ስለ አገራቸው በጦር ነት ለሞቱ ሰዎች ልጆች ፣ (ለሥራ እስኪደርሱ ድረስ በጣም ህጻናት ማሳደጊያ ፤ ለጉበዛዝት ማስተማሪያ ፤ ለሴቶችም እንደ ገና ሌላ ባል ካላገቡ መጠወርያ ይሆናል ። ማናቸውም የመን ግሥት ሠራተኛ ፲ ዓመት ካገለገለ ወዲያ ቢሞት ፣ ምሽቱና ለሥራ ያልደረሱ ልጆቹ እንደነዚሁ የሰማዕታት (አርበኞቹ) ልጆችና ምሽቶች ይታሰቡባቸዋል (የመንግሥት ሠራተኛ ፳ ዓመት ካገለገለ ወዲያ ይበቃኛል ብሎ ሥራውን ቢተው ደግሞ ለኑሮው የሚበቃው ታይቶ ፣ ማለት በፊት ከሚወስደው የነበረ ትንሽ አሳንሰው ፣ እስኪሞት ድረስ ደመወዝ ከመንግሥት ገቢ ያገኛል ።

ምናልባት አንዱ ተከራካሪ ግን ኢትዮጵያ ለሰማዕታት የል ጆች ልጆችዋ መቸ ረሳቻቸው ? ይል ይሆናል ። አዎን አሳቡስ ደግ ነበር ። እኔም አልዘነጋሁትም ግን ነገሩ አለ አገባብ ስለ ሆን ፣ ለመንግሥታችን ትልቅ ጉዳት ለነሱም ምን ያህል ረብ የለበትም ለሴትየዋ የሚበቃትን እየላኩ በመስጠት ፋንታ በብ ላሽ ፋንታ ከገባሮች አንቺ ተታገዪ ፣ እንዲሁም ለህጻኑ በእው ቀት ትምህርት በማሳደግ ፋንታ የማይችለውን ሂድ የአባትህን ሹመት ወይም ሥራ ያዝ ማለት የልጆች ጨዋታ ይመስል ለጠላት ያስቃል ለወዳጅ ከአንጀት ያስለቅሳል ።

፪ኛ የገንዘብ አወጣጥ ዓይነት መንገድ ።

ኢንዱስትሪ ማለትም እንደ ጦርነት ያህል ነውና ፣ ከመኪ ናዎች ፋብሪካዎች ፍጥነት የተነሳ እሳት የሚቃጠሉ ወይም እጃቸው እግራቸው የሚቈረጥ በድናሚት በከሰል ድንጋይ መቈ ፈር በብረት ዘር ሁሉ ማውጣት በመንገድም በአውቶሞቢል በትራም በባቡር የሚዳጡ በእንደዚሁ የመሰሉ ልዩ ልዩ ድን ገት አለ ጊዜያቸው የሚሞቱ ብዙዎች ናቸው ።

የነዚህ ምሽቶችና እጓለማውታን ልጆችስ ወይም ሠራተኞቹ ቢሽመግሉስ ማን ይጠውራቸው ? እንደ መንግሥት ሠራተ ኞች ልክ እነኝሁም ደማቸውና (ሕይወታቸው) ኃይላቸው የገ በሩላቸው የኢንዱስትሪ ጌቶቹና ነጋዴዎች ናቸው የሚጠው ርዋቸው በነሱ ሥራ ውስጥ በማናቸውም ምክንያት ቢሞቱም ሐላፊዎቹ የሥራ ዋኖች ጌቶች ናቸው ። ተከራካሪው በምሳሌ አንዱ ሰክሮ መጥቶ ሊገነባ ወጥቶ ወድቆ ቢሰባበር እ ዱት ጌታው ነው ። አላፊ ቢል ይሆናል ሊል ይችላል ። ለዚሁ አሳብ ምላሹ አጭር ነው ፤ ሠራተኞቹ ወደ ሥራ ቤት ሲገቡ ፤ ዲሬክ ተሩ ሳይፈትሽ (ሳይመረምር) እንዳያንባቸው በሥራ ቤቱም መጠጥ እንዳይገባ ተደንብተዋልና ፤ ጥፋቱ የጌታው ነው ።

፫ኛ የገንዘብ አወጣጥ ዓይነት መንገድ ።

አንድ ሠራተኛ ሰው ፣ ጌታውን ሳይለውጥ በያዘው ሥራ ቀጥ ብሎ ፳ ዓመት ካለፈው ወዲያ ሥራው ይበቃኛል ብሎ ቢተወው (እንደዚያው በፊት ያመለከትኩት የመንግሥት ሠራ ተኛ ለኑሮው የሚበቃው ያህል ማለት ከሚወስደው የነበረ ትንሽ ቀነስ (አነስ አድርገው ካገለገለበት ሥፍራ ጌታ ሠራ ተኛው እንደመረጠው ባንደዬ ብዙ ገንዘብ ወይም እስኪሞት ድረስ ትንሽ ትንሽ እየቀነሱ ደመወዝ ይሰጡታል ይልቁን እንደ እንግሊዝ የመሰለ ሀብታም መንግሥት ማናቸውም ተሸጋሪ ሽማግሌ ፳ ፫ ዓመት ያለፈው መንግሥቱ ያግዘዋል ።

እኒያ እየ ተንቀባረሩ ዛሬ ካንዱ ጌታ ነገ ከሁለተኛው እየ ዞሩ የሚሰሩትስ ምን ይሁኑ ? ባለቤቱ የሞተ እንደሆነስ ምሽቶቻቸውና እጓለማ ውታንልጆቻቸው የት ይፍሰሱ ዛሬ ክር ስትና ከስልጣኔ ጋራ ሲነግሥ ሰውን ርህራሄ ወርሶታል ለም ሳሌ አንድ ገንቢ አናጢ ወይም ልብስ አጣቢ በአንድ ወር ፴ ብር ደመወዝ ቢቈጥር ጌታው ፳፤ ብር ከ፫ ሩብ ለሰራተኛው ይሰጠዋል ሁለት ብር ከሩብ ግን ተቈርጦ ወደ ባንክ ይገ ባል ። የባንኩ ማሕበረተኞች የሠራተኞቹን ገንዘብ እያጠራቀሙ ያስወስዱታል ። አንዱ ሠራተኛ ፳ ዓመት ከሞላው ወዲያ ለኑ ሮው የሚበቃው ከማሕበረተኞቹ ደመወዝ ያገኛል ፳ ዓመት ሳይሞላው የሞተ እንደሆነም ምሽትና ለሥራ ያልደረሱ ልጆች ቢኖሩበት ይጦሩዋቸዋል ። አለዚያ የተጠራቀመው ገንዘቡ ዘመዱ ወይም ወዳጁ ሊወርሰው አይችልም ። ለሌላ ዘክታም ማገገሚያ ሊሆን ማሕበረተኞቹ ያስቀሩታል እንጅ ። ሚካኤል ተሰማ

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ማስታወቂያ ።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ችን ከተገባው ቀኑ ካሙስ በኋላ ቆይቶ መውጣቱ ማተሚያ ቤታችን ዱሮ በነበረበት ቦታው ወጥቶ በቤተ ሳይዳ ዘተፈሬ መኰንን ሆስፒታል አጠገብ እንዲሆንና ሥራው በዚያ እንዲ ሠራ ዕቃ ስናግዝና መሳሪያውን ስናሰናዳ ስለ ሰነበትን መሆኑን በማክበር እናስታውቃችኋለን ።

ከዛሬ ጀምሮ ለወደፊቱ መጽሐፍ መግዛትና ሥራ ማሠራት ለሚፈልግ ሰው ሁሉ አዲስ በተሰናዳው በቤተ ሳይዳ ዘተፈሪ መኰንን ሆስፒታል አጠገብ እየ መጡ መጽሐፍ እንዲገዙና የፈለጉትን ነገር እዲያሰትሙ እናመለክታለን ።

ስለአሊያንስ ፍራንስ ኢትዮጲ ትምሕርት ቤት የእረፍት ጊዜ

የትምሕርት ቤት ሁሉ ካመት ውስጥ ሁለት ወር ስለ ተማሪዎችና አስተማሪዎች እረፍት ስለ ሚደረግ የአሊያንስ ትምሕርት ቤትም በጥቅምት ፲፰ ቀን ይዘጋል ብለው ክቡር ሙሴ ሞሬል የትምሕርት ቤቱ ዲሬክተር ለየአስተማሪዎቹ ለተ ማሪዎች ፈተና እንዲያደርጉ አስታውቀው ነበር ፡ አስተማሪዎ ቹም ተማሪዎቻቸውን በየክፍሉ ሲፈተኑ ሰንብተው ነበር ። ተማ ሪዎቹም በውሀ ዳር የተተከለች ፍሬያማ አትክልት አበባዋንና ፍሬዋን በየጊዜው ለባለቤቷ እንደምትሰጥ ሁሉ ተማሪዎቹም በፈተናቸው አስተማሪዎቻቸውን እጅግ ደስ ስላሰኙ ዲሬክተ ሩም በጥቅምት ፲፱ ቀን ከጧቱ በ፫ ሰዓት መጥተው ሲኒማ እንዲአዩ አስታወቁአቸው ልጆቹም በዚያው በተቀጠሩበት ሰዓት በመጡ ጊዜ ልጆቹም በየክፍል በየክፍሉ ካስተማሪዎ ቻቸው ጋራ ሆነው ወደ ሲኒማው ቤት ሲሔዱ ለሚአየአቸው በጣም ደስ ያሰኙ ነበር ። ወዲያውም ሲኒማውን ካዩ በኋላ ለ፮ ሰዓት ሩብ ሲቀረው ዲረክተሩም ከተማሪዎቹ ተሰነባብተው ካስተማሪዎቹ ጋራ ወደ ቤታቸው ሔዱ ፡ ስለ ዚህም የዕርፌት ቀን በደህና ዕረፍታችን ከፈጸምን በኋላ ተማሪ ቤታችን ተከ ፍቶ እንድንማር ከልዑል እግዚአብሔር የማያቋርጥ ተስፋችን ን እንለምናለን ብለው ህጻናቱም ንግግራቸውንፈጽመው ሔዱ ።

ከዚህ ቀጥሎ አንዱ ያሌያንስ ተማሪ እንዲህ ይላል ሃሳ ቤንም ልጻፍ እስከ ሚቻለኝ ፡ እንዳትቆጥሩብኝ ስህተትም ቢገኝ ፊደል የቆጠርኩኝ ሃን ተማሪ ነኝ ፡ ጥበብን ለመማር ሙሉ ተስፋ አለኝ ፡ ሁሉም የውቀት ቤቱን ሲያመሰጋግናት ፡ እኔም መማሬዬን አሌያንስ ልበላት ፡ እማርባታለሁ እያመሰገንኳት እውቀት ስትመግበኝ እንደናት እንዳባት ፡ ልዑል እግዚአብሔ ርም በረከቱን ይስጣት ፤ እውር የነበርኩኝ ጀመርኩ ፊደሉን ፡ አለመሬ በቀን ልሔድ በብርሃን ፡ ጥበብና ኃይሉን ላውቅ የእግ ዚአብሔርን ፡ ይክበር አምላካችን ሳውቅ መንገዱን ፡

በቀለ ዘለቀ

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰ ንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፫ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነርትጓሜው	፯ብር
ኅሐ ጽባሕ	፫ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትጓርሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋሰው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ከ፫ ሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር ፫ ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ። ተሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፮፩ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፯ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፮ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲፩ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲ ፮ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፵፫ ብር
፡፡ ባለሰይጣ ፡፡		፻፵፮ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፴፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ ፡፡		፻፳፮ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል ፡፡		፻፴ ብር
ባለ አንበሳ ፡፡		፻፵፫ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፰ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ	፲
አንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ	፰ ሳንቲም
ባአንድ ጊኒ	፲ ብር ፪	ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፱ ብር	

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የሚባል ባለአንበሳ ስዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቀቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል"አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ"ብቻነው።

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፥ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ኤን ቤ ኤዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶኮለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ኮዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

ዓለም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠ ራል ።

ኒኮላ ።



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አሉ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክስሙ ጉድየር ይባላል፡፡ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደ ጥሞ በልክ ይሄዳል። ብገደልም በጭቃም ላይ ቢሆ ን አያስፈራም እንደልብ ያስኬዳል በድጥም በፍራ አያድጠውም በድንጋዩም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስ ቲክ ሁሉ ጠንካራነው በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድየር ግዙ ከሌላው ላስ ቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩ ል ነው ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘ ው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።



ጉደየር ግዙ

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤኔስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጎበርና አጎበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፤ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፭
3 me ANNÉE № 45

ሐሙስ ጥቅምት ፴ ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 10 NOvembre 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé "Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፊስን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፫፻፵፱ገጽ ተከታይ ።

የማይሞት ደግ ሥራ ።

፩ኛ የገንዘብ አወጣጥ ዓይነት መንገድ

በዚህ ዓለም በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ በሰው ፊት የሚያሳፍር ብዙ ጸያፍ ሥራ ይሠራል አንድ አንድ ተቀጥተው ያላደጉ ባለጌዎች ሰዎች ከአንድ ድንግል ባል የሌላት ሴት በዓመጽ ወይም በአታላይ ውድ ያስነውርዋታል ። ባልተደነበ አካሄድ የሚፈጠሩ ልጆች ነገ ለመንግሥታቸው አገልጋዮች ለአገራቸው ረዳቶች ሊበቁ የሚችሉ የነበሩ በልዩ ልዩ ድህነት የሚበልጡ ይሞታሉ የቀሩትም በሚያስደነግጥ ችግር አድገው ከአገራቸው እየተሰደዱ ይጠፋሉ ።

፩ኛ ለምሳሌ አንድ ሴት በስራት ያላገባች እንደሆነች ለዘመዶችዋ ፊርታ አግብታ እንደሆነች ለባልዋ ፊርታ ባልተገባ መንገድ ያገኘችውን ዲቃላ ልጅ ጨካኝ እንደሆነች ትገድለዋለች ርህሩህ እንደሆነች ሰው በሚያልፍበት ቦታ ወይም በከተማ ወስዳ ትጥለዋለች ። ፪ኛ የሚያስፈራት ነገር ባይኖር ደግሞ አገሩና ርስቱ ያልታወቀ አንድ አላፊ ወታደር ይሆናል ወይም አንድ ድሃ ብጤ ይሆናልና በግብር ወይም በሌላ ነገር የተሸገረ እንደሆነ ጥሏት ይጠፋል ድሃይቱ ሴት ከህጻኑ ጋራ ስትለምን ወይም ስትሰደድ የሚያገኛት ድንገት ብቻ ነው ። ፫ኛ አንድ አንድዋም በአፍረት ወይም በብዙ ሌላ ልዩ ልዩ ምክንያት አባቱ ልትገልጥ የማትፈልግ ወይ ደግሞ የማትችል አለች ። ፬ኛ አንድ አንድ ያላዋቂ ሰውም ከጨዋ ወይም ከከበርቴ የተወለድኩ ነኝ እያለ የሚመካ አለ ግን በድንቁርና የተገዛ ባለጌነቱ ጐትቶ ከማገኛዪቱ ሲያልከሰክሰው ይኖራልናበመኻከሉ ልጅ የተገኘ እንደሆነ በወሰጡ ማሳደጊያው ገንዘብ እንዳይከፍል በስስት ተይዞ ይህች ዛርያ ነች ያች ጠቢብ ነችና ዘሬን ታበላሻለች አመሀኝቶ ልጄ አይደለምብሎ ቢክድ እንደ አገራችን ደምቡ በመሐላና ግዝት እውነቱን ሊወጣ ይቅርና የሰው ፍጥረት አኳሆን ሙሉ ዕድሜአቸው መማርና መመርመር ለሆነ ስራቸው የፈረንጆች አዋቂዎች እንኳ መልኩን ቀርቶ ደሙን እየበጡ ቢመረምሩት በትክክል እውነቱን ሊገልጡት ገና አልተቻላቸውም ፤

እንግዲያስ እኒህ በእውነት አባታቸው ያልታወቀ እጓለማውታን ማን ይጠውራቸው ጠዋሪዎቹ አውደልዳዮቹ ናቸው እንያ ከ፳፩ ዓመት እስከ ፷፭ ዓመት ውስጥ ሴቶች ያላገቡ የሚገኙ ወንዶች በ፫ ክፍል ተመድበው በየዓመቱ ከሕዝብ ሁሉ በላይ የተለየ ግብር መንግሥታቸው ያስከፍላቸዋል ፤ ለምሳሌ ማናቸውም ሴት ያላገባ ወንድ ከ፳፭ ዓመት እስከ ፴ ዓመት ፫ ብር ታላድ ከ፴ ዓመት እስከ ፵፭ ዓመት ፩ ብር ከ፵፭ ዓመት እስከ ፷፭ ዓመት ፪ ታላድ በየዓመቱ ይከፍላሉ ። ለሃብታሞቹ ደግሞ በዚሁ በላይ ትርፋቸውን እያዩ ያስጨምሩዋቸዋል። አሁን ደግሞ ለወደፊቱ ለነዚያ ምሽት ያገቡ ልጆች ግን የሌሉዋቸው ሰዎችም ለብዙ ልጆች ያሉዋቸው አባቶች ማገገሚያ ሊሆን ከነዚያ ምሽት ያላገቡ ሰዎች ግብር አነስ የሚል ሊከፍሉ ሕግ ሊቆም ነው ይባላል ። ይህ ገንዘብ በየዓመቱ እየተሰበሰበ በባንክ ገብቶ እየወለደ ፤ ለነኝሁ ባልተደነበ መንገድ የተፈጠሩ ልጆች ሥራ እስኪደርሱ ፤ ለህጻውንቱ ማሳደግያ ለጐበብዛቹ ማስተማሪያ ይሆናል ።

እዩት ክርስትና ከስልጣኔ ጋራ ሲነግሥ ስንት የማይሞት ደግ ሥራ ይሠራል ለዚሁ ዕጹብ ፤ ግሩም ፤ ድንቅ ፤ መልካም የሚቃወም (ሰይጣን የወረሰው ካልሆነ) ይገኝ ይሆን ሕዝብ ከነሰ የቅኝ (ኰሎኒያ) ለመሆን ይደረሳል እንዳለው አንድ ትልቅ የፖለቲክ ሰው ፤ ከአርነት ባርነት ፤ ከጌትነት ሎሌነት ፤ ከክብረት ውርደት ፤ ከሃብታምነት ድህነት ፤ የሚመርጥ ሰው ይገኝ ይሆን

ምላሹ ከበድ ነው ። አእምሮ ያለው ከሆነ ጭርሱን አይገኝም እንዳልል አንድ አንድ ዐየሁ ወገኖች አይታጡምና ፡ የመንግሥታቸውን ምስጢር ሲያወጡ ፡ እናታቸው (አገራቸው) ሲሸጡ የተገለጡ እንደሆኑ ፡ እብለት ቃል እንዳይሆንብኝ ያሠጋኛል ።

፪ኛ ክፍል ።

በአገራችን ኢትዮጵያ እስከ ዛሬ ድረስ ባለ መታሰቡ በጣም የሚያሳዝን ትልቅ ሥራም አለ ። ቤቶቻችን በድንገት ወይም በልዩ ልዩ ዓይነት ጠላቶች ምክንያት እሳት ይቃጠላሉ ይልቁን በአገር ቤት (ገጠር) ለተመለከተ ሰው ፡ (የሽፍቶችና የክፉዎች ምቀኞች ሁሉ ይቅርና) አንድ መንገድ አላፊ ያላ ሳደረኝ ወይም ያላስተናገደኝ ብሎ ፤ የባላገሩን ቤት አቃጥሎ የሚሄድ ሰው አለ ።

እኒህ ድኆች ኃይላቸው የለፉበትን ገንዘባቸው የሰዉበትን ድንገታሞች ገባሮችስ ምን ይሁኑ? ጮራ ብርሃን በገባበት አገር ፍትሕ አይጐድልም ። ለዚሁ አላፊዎችም ብርቱዎች የማይንቀሳቀሱ ማሕበሮች ይነሣሉ ። ለምሳሌ በመቶ ብር የሚሠራ ቤት ፭ ብር ፡ ሺ ብር የሚፈጅ ቤት ፪፻ ብር የቤቱ ዋና ለማሕበረተኞቹ አንዴ ይከፍላል ። ማሕበረተኞቹ ከማናቸውም አገር መንግሥት በሞላ ፤ በሚሠራ ቤት ቁጥር እንደ አቅሙ እያዋጡ ገንዘቡ እየሰበሰቡ ፤ እባንካቸው አግብተው ያስወልዱታል ። በዚሁ ገንዘብ እሳት አጥፊዎች (ዘበኞች) አቁመው በትልልቆች አደራሶች ለእሳት ማጥፊያ የሚመቹ ተወርዋሪዎች የውኃ ቦምቦች እንደ ገቡ ፡ በእሳት አጥፊዎች (ዘበኞቹ) አውቶሞቢሎች የወኃ ቦምቦች እንደተዘጋጁ ፡ ሌት ከቀን እጅግ በሚያስደንቅ ብዙ ጥንቃቄ ይጠባበቃሉ ።

አንድ ቤት እሳት የተቃጠለ እንደሆን መቼም በማናቸውም ቤት በበቱ ወጭ እኩል በልዩ ለእሳት አጥፊዎች መጥሪያ በመስትዋት የተዘጋ ቴሌፎኖ አለና ማናቸውም ሰው መስትዋቱን ሰብሮ ሊጠራቸው ይችላል ። እሳት አጥፊዎች ሲነሱ ጊዜ የአውቶሞቢሎቹ ጩኸት በጣም ከፍ ያለና የተለየ ነውና ከቤታቸው እስከ እሳት የተቃጠለ ቤት በመንገዱ ሁሉ ጩኸቱን እንደለቀቀ ሳያቋርጥ ይደርሳል ያን ጊዜ መኪና ወይም ሰው ቢሆን ይቆማል ወይም መንገዱን ለቆ ይሄዳል እንጂ አይንቀሳቀስም ፡ ሰው ተድጦ የሞተ ወይም መኪናው የተሰባበረ እንደሆነም እነሱ አላፊነት የለባቸውም በማናቸውም ስፍራ ቤት እሳት ቢቃጠል ካ፭ ደቂቃ የሚበልጥ ጊዜ አያሳልፉምና ቤቱ የተጐዳው ወይም መጥፋቱ አቅታቸው ጭርሱን የተቃጠለ እንደሆነ ሐላፊዎቹ ማኅበረተኞቹ ናቸው ። እንደገና እንደነበረው ልክ አስመስለው በባንክ ከሰበሰቡት ገንዘብ አድርገው ያሰሩታል፤

እኒህ ፫ቱ የማይፈርሱ ማኅበረተኞች በአገራችን ኢትዮጵያም በጥልቅ ተመስርተው ሊቆሙ በብዙ ተስፋ እንጠባበቃለን ። የአሁኑ የአዲሲቱ ኢትዮጵያ ወጣቶች ልጆች ስልጥናን ገንዘብ ያላቸው ይህ ለመንግሥት ጥቅም ላገር ረድኤት የሆነ የማይሞት የደግነት ሥራ ታሪክ ሞያው ለኋለኞች ትውልዶች በመጠባበቅ እንደማያሳልፉት ባለመጠራጠር እንታመናለን ።

ሚካኤል ተሰማ

እለ ታፈቅርዎ ለእግዚአብሔር ጽልዕዋ ለእኪት መዝ ፺፯ ፲

ወደ አዋቆችና ወደሚርተኞች አትሂዱ ምንም ነገር አትጠይቋቸው እንዳትረክሱባቸው እኔ ነኝ እግዚአብሔር አምላካችሁ ዘሌዋ ፲፱ ፴፩ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ ሌሎች አማልክት አይሁንልህ በፊቴ ሥዕልንና ምሳሌንም ላንተ ከቶ አታድርግ በላይ በሰማይ ካለው በፀሐይ በጨረቃ በኮከብ በታችም በምድር ላይ ካለው በዛፍ በደንጊያ ስር ተቀምጠው አድባር ነው ብለው የከብት ደም እያፈሰሱ ለሰይጣን የሚገብሩ አሉና በውሀም ውስጥ አጋንንት አሉ ብለው የሚጠሩና የሚገብሩ አሉና አትስገድላቸው አታምልካቸው እኔ እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነኝና ያባቶችን ኃጢአት በልጆች የምቀጣ እስከ ሶስት እስከ አራትም ትውልድ ድረስ በሚጸሉኝ ዘፀአት ፳ ፪ ፭አንተም አምላክህን ውደድ በልብህም ሁሉ በነፍስህም ሁሉ በኃይልህም ሁሉ ባሳብህም ሁሉ ዘዳግም ፯ ፪ ፭ ባልንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ውደደው ያለውን ይህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አፍርሰው እግዚአብሔርን ባለመፍራት ለሰይጣናት መስገድና ማገልገል መገበር ሰውንም ወደስህተት ነገር ማድረስ ክፉውን ነገር ሁሉ መሥራት ራሱን የጠላ ነው ። ተዋቸው ዕውሮች ናቸው ዕውሮችን የሚመሩ ። ዕውር ዕውርን ቢመራው ሁለቱ ተያይዘው ወደጉድጓድ ይወድቃሉ ማቴ ፲፭ ፲፬ ለራሱ ያላወቀ ለማን ያውቃል ተብሎ ይጠየቃል በፊት ለራሱ በስጋው ከቅጣት በነፍሱ ከገሃነመ እሳት ከመግባት የሚድንበትን አያውቅም ነበር ። በጠንቋዮች ዕውቀት ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ሀብትና ዕድሜ ያገኘ ማነው ነፍሱንስ ያለእግዚአብሔር ፈቃድ ጠንቋይን በመጠየቅ ከሞት ያዳናት ማነው ነፍሱንስ ከገሃነመ እሳት የሚያድናት ማነው ።

ለራሱ ሳያውቅ ለኔ ዕወቅልኝ የሚሉትን ሰዎች መጻሕፍት ተባብረው እንዲህ ብለው ይመክሩታል፤በሚመክሩዋችሁ ብዛት ደክማችሁ አሁንም እስኪ ይነሡ ያድኑዋችሁ የሰማይን ከከብ ቁጣሮች ከከብን የሚመለከቱ በወር መባቻ በናንተ ላይ የሚመጣባችሁ ነገር የሚናገሩ እነሆ እርሳቸው እንደ ገለባ ሆኑ እሳትም አቃጠለቻቸው ሰውነታቸውንም ከእሳት ነበልባል እጅ አያድኑም ። ኢሳ ፵፯ ፲፫ ፲፬ የቤት ጣዖት የማይረባውን ነገር ተናግሯልና ጠንቋዮች ሐሰት አዩ ሕልምም የሚያዩ ሰዎች በከንቱ ተናገሩ ዘካር ፲፡፪ ሕልም ፫ ወገን ነው ። ፩ ኛ የመልአክ ። ፪ ኛው ። የሰይጣን ፫ ኛው የሞት ነውና ። ሰይጣን የሚያሳያቸውን ። ሕልም ወሰገል ከንቱ አለ ። ሌሎችን አማልክት አትከተሉ ታመልኳቸው ዘንድ ትሰግዱላቸው ዘንድ ። በጃችሁም ሥራ አታስቈጡኝ ክፉ እንዳላደርግባችሁ ። ኤርም ፳ ፳ ፯ ።

ወዮ ለንፍሳችሁ በክፋታቸው ለራሳቸው መከራ ሰርተዋልና ኢሳ ፫ ፱ ። ሕዝቤ የተመለስህ እንደሆነ ወደኔ ተመለስ ከፊህት እንቅፋትህን ብታወጣ አትናወጥምና፡ኤርም፬ ፩እግዚአብሔርንም ከሰማይ የሰውን ልጆች ተመለከተ የሚያስተውል እግዚአብሔር የሚፈራ ሰው እንዳለ ያይ ዘንድ ሁሉም ዓመፁ በንድም ረከሱ በጐን ሥራ የሚሠራ የለም ፩ስንኳ የለም ። መዝ ፲ ፬ ፪ ሌባ በተያዘ ጊዜ እንዲያፍር እንዲሁም በፍርድ ቀን ዓመፀኞች በእግዚአብሔር ፊት ያፍራሉ ። ኖኅ ከቤተሰቡ ብቻ ጋራ ከማየ አይኅ

እንደ ዳነ ። ሎጥ ከሰዶም እሳት ከቤተ ሰቦቹ ብቻ ጋራ እንደ ወጣ ። እንዲሁም በምጽአት ይህን ዓለም ሊያሳልፍ ሲመጣ በዚያን ጊዜ ከሚጠፉ ከብዙ ዓመፀኞች ቁጥር የሚድኑ ጻድቃን ጥቂቶች እንደሆኑ ያመለክታል ። የሚጠፉ ብዙ ናቸው ። የሚመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸው ማቴ ፳፱ ፣ ፲፬ ።

እንዲህ ከሆነ ሁላችን ለየ አንዳንዳችን ከዓመጸ ነገር ራሳችንን ልንጠብቅና በዓመፀኝነት ያሉትን ተረዳድተን ልንመልስ የግድ ያሳስበናል ። እኔ ቀድሞ የማውቀው ያሩሲ ጋላ ፲፰ ዓመት ሐረር ኑሬ ብመለስ ሞላው ሕዝብ እስላም መሆኑን አየሁ ። ይህም መሆኑ ከኛ ወገን አስተማሪ ስለ አልኖረ ከረርጌ ጀምረው አረቦች ያስተማሩት እርስ በርሱ እያስተማረ እስከ ዚህ ደረሰ።አሁንም በየአገሩ ፪ና ፫ ዳውላ እህል ለቀለብ ፫ ብር ለወር ጨው ላስተማሪ እንዲሰጥ ለየአገረገዢው ትእዛዝ ከመንግሥት ቢወጣ ከዚያው ከየቤተ ክርስቲያኑ አንዱ አገልጋይ ለማስተማር ፈቃዱ ይሆን ነበር ። የስላምም አስተማሪ ጋላውን እንዳያስተምር በየአገረ ገዢው ባዋጅ ቢከለከል ደግ ነገር ይመስለኛል።ይህ ካልተደረገ የስላም ሃይማኖትና የጋላ አምልኮ ጠንቋይና አቴቴ እየሰፋ ሳይሄድ አይቀርም የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ከወጣ ትንሽም ብትሆን ትልቅ የተቻለውን ያህል እውቀቱን የሚገልጥበት ስለ ሆነ የተቻለኝን ያህል ጻፍኩ ።

ጠንቁሎ አስጠንቁሎ በብዙ ቢለፉ ። በነፍስ በሥጋቸው ብዙ ሰዎች ጠፉ ። ከእግዚአብሔር መጣላት ምድን ይሆን ትርፉ ። አልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌየ ብሎን በመጻፉ ። ሌላ ጥቅም የለውም ገሃነም ነው ትርፉ ፤

ለብው ዘንተ ኵልክሙ እለ ትረስእዎ ለእግዚአብሔር ።

ቄም ጸሐፊ ገብረጻድቅ ።

ይሉባቡር በጎሬ ከተማ የተደረገ ደስታና መልካም ሀሳብ ።

፲፱፻፳ ዓ ም ጥቅምት ፪ ቀን በ፱ሰዓት በክቡር ራስ ናደው ቃል ወደ ታላቁ ግቢ ቤታቸው ተጠርተን ነበርና በሄድን ጊዜ የተጠራው ሰው ሁሉ ተሰብስቦ በየማዕረጉ ከተቀመጠ በኋላ መልካም ሀሳባቸውን በወረቀት ጽፈውት ኖሮ በጉባኤው መካከል አቅርበው አስነበቡ ቃሉም ይህ ነው ።

አሁን ዛሬ ያስጠራኋችሁ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል ላማከራችሁ ነው ። እንደምታውቁት ከአጼ ምኒልክ ጀምሮ እስከሁን በየጊዜው ስለመንግሥት ሥልእክት በኤውሮፓ በአሜሪክ በሌሎችም ክፍል ስመላለስ ሊነገር የማይቻል ብዙ ልዩ ልዩ ሥልጣኔና ከፍ ያለ ሀብታቸውን እያየሁ ለዚህ ሁሉ መሰረቱና ደረጃው ትምህርት እንደሆነ እያሰብኩ ይልቁንም አፊት የነበረችው አገራችን እኋላ በመቅረቷ እያዘንኩ ምንም በየለውራጃዋ ብዙ የተማሪ ቤት ቢያስፈልግ ቁጥር ካንድ ነውና እኔም በምገዛው አገር እንደችሎቴ መጠን የተማሪ ቤት ለማቆም ከሰብኩ ብዙ ጊዜ ነበር ። ይልቁንም በ፲፱፻፲፭ ዓ ም በሆነው መሰብሰብ ኢትዮጵያ ወደ መንግሥት ማኅበር እንድትገባ ለማስታወቅ ወደ ጋርኔብ በሄድን ጊዜ ትግባ እየተባለ በነበረው ክርክር መሐከል እንደተመለከትኩት ለኢትዮጵያ ያለትምህርት ዋስ ወይም ጋሻ እንደሌላት ፈጽሜ ተረዳሁት ግን እንደምታውቁት በዚህ አገር ከክረምቱ ጽናት የተነሣ መንገዱ ሁሉ ማጥ እየሆነ ወንዙም እየመላ ብዙ ተላላፊ መንገደኛ ተጐዳ ንግድም ቆመ ስለዚህ የሕዝቡ ስቃይ ቢሰማኝ የመንገዱንና የድልዩን ሥራ ለማስቀደም አስቤ ነበርና ይኸውም በግርማዊት ንግሥታችንና በልዑል አልጋ ወራሻችን ሀብት በናንተ በወንድሞቼ ጸሎት በፈቃደ እግዚአብሔር የጀመርኩት ሀሳብ አለቀልኝ ። አሁንም በልቤ ሁለት ሀሳቦች ተፈጥረዋል ፤ እነሱም ቤተክርስቲያንና የተማሪ ቤት ናቸው ። ግን አንዱ አሁን ለጊዜው በያለበት ቆይቶ አስቀድሞ የተማሪ ቤቱን በቶሎ ለማቆም የቁርጥ አሳብ አድርጌአለሁና እንግዲህ ስለዚህ የሚሆነውንና የሚያስፈልገውን ጉዳይ ትንሹም ትልቁም እንድታማክሩኝ የልቤን ምኞት ገልጬ አሳስበቻኋለሁ ብለው ንበቡ በለቀ ጊዜ ከዳር በደስታ እየተመላለሰ ሶስት ጊዜ ተጨበጨበ ወዲያው አቶ ታከለ ወልደሐዋርያት የሚከተለውን ቃል ተናገረ ።

ክቡርነትዎ ታናሽና ታላቅ ሳይመርጥ የመልካም ሀሳብ ምክር ስለጠየቀ እናገር ዘንድ ፈቃድ ለመጠየቅ አያስታውሰኝምና በኔና በክቡራን መኳንንቶች ስም ሆኜ በጥቂት ቃል ሀሳቤን እገልጻለሁ ። ክቡር ሆይ ከሁሉ በፊት ይህን ያሳሰበዎ አምላክ የተመሰገነ ይሁን ዛሬ በዚች ሥፍራ ሰብስበው ባገር ፍቅር የተዋበ ተስፋዎን ስለሰጡን ሰሎሞን መልካም ወሬ አጥንት ያለመልማል እንዳለው ሰውነታችን እምነትን አብባ ደስታን አፈራች ። ክቡር ሆይ ደግሞ አሁን በንበቡ እንዳሉት በኤሮጳና በአሜሪክ በሌሎች አገር በየሄዱበት ሁሉ ስላገራቸው መልካም የሰሩ ተብለው በልዩ ልዩ ጌጥ መልካቸው ተቀርጾ ሐውልት የቆመላቸው ሰዎች አይተዋል።እስኪ እንግዴህ በሥጋና በመንፈስ ተጽናንቶ በጉልህ ደም ለተፈጠረ ሰው በምድራዊ ዓለም ለድካሙ ከዚህ የተሻለ ምን ዋጋ አለው ማለት ከብዙ ዓመታት በፊት የነበረው ሰው መታሰቢያው ሲታይ ወይም ስራው ሲነሣ በሚከታተለው ትውልድ ልብ እየታሰበ በዓይን ህሊና የማያየው የለምና በሕይወት ሥጋ እንዳለ ማለት ነው ። አሁንም ለሕይወትዎ መታሰቢያ ክቡርነትዎ ካደረገው መልካም ስራ ሁሉ አውራ ነገሮችን እናድሳቸው ዘንድ ያሁኑ ተስፋዎ ያስታውሰናል ። (፩ኛ) ከአጼ ምኒልክ ጀምረው እስከሁን የመንግሥትዎ ቃል እየሆኑ በዓለም ሁሉ ሲላኩ ሀሳብዎ ሳያፍር ጉዳዩን እያከናወኑ በመመለስዎ ታማኝ የተባለ ስም ተሰጥትዎ ነበረ ።

፪ኛ እንደምንሰማው በዚህ አገር በቀድሞዎቹ አገረ ገዦች ጊዜ እንኳንስ በባላገሩ በከተማው ቢሆን ወንበዴው ለስርቆት ደህናውን ሰው ቤቱን በመጠበቅ ተኝቶ የሚያድር ሰው አልነበረም ይባላል ። አሁን ግን በዘመንዎ ተግተው ሌባ የያዘውን አርበኝነቱን አመስግነው እየሸለሙ የተያዘውን በጥብቅ እየቀጡ ከእድልዎ ጋራ ላገሩ ሰላም በመስጠትዎ የማያመሰግንዎ የለምና ትጉህ አሳቢ መባልን አገኙ ። ፫ኛ ላገር ሀብትና ሥልጣኔ መፍጠር ከሚያስፈልጉ ዋና ክፍሎች አንዱ መንገድና ድልድይ ስለሆነ አስበው ከብቱን እስከጭነቱ እየዋጠ ያስቀር የነበረውን የከተማ መንገድ አዘጋጅተው የሶርንና የጋቡንም ድልድይ ሠርተው በሰውና በከብት የነበረውን ችግር ባሻ

ዳንዎ ርኅሩኅና ሥልጣኔ ወዳጅ ማለትም ስምዎ ነው ፡፡ ፪ኛ ያሁ ንግ ውጥንዎ ከኢትዮጵያ መልክ አንድ ቁጥር ሆኖ በትውልድ ልብ በደስታ ተቀርጾ እንዲኖር ጥርጥር የለውም ፡፡ ደግሞም ልሳን የማያሟሟው ሞት የማያስረሣው በብርሃን ልጆች ፍቅር የተጌጠ የዘለዓለም ሕይወት የተባለውን ስም ሽልሞዎታልና የሀሳብዎ ተካፋይ ከሆኑ ወገኖችዎ ጋራ እጅግ ደስ ይበልዎ ፡፡ ይኸም ሀሳብዎ በሚሰማው ጆሮ ሁሉ ውድ ስለ ሆነ ባስተዋዮችም ዓይን ሞገስ ያለው ነውና ስብከትዎ ከጓደኞችዎ ተከታይ ያጣል ብለን አንጠራጠርም ፡፡ ደግሞ ከብርሃንና ሰላም ስብከት አንድ ንባብ እጠቅሳለሁ እነሆ የኢትዮጵያ አድል ልዑል ተፈሪ መኰንን አገሬን እወዳለሁ ማለት ያፍ ልማድ ብቻ እንዳይሆን ያገሩ ወዳጅ ማለት ፍቅሩን አውጥቶ በስራው ገልጦ ሲያሳይ ነው ብለው እንዳሳሰቡት ለስራ የሚበቃ ምስክር አግኝተዋልና ፤ ያገርዎን ጥቅም በመፈለግ የሀሳባቸው ተከታይ በመሆንዎ ጉልህ ምስጋናዎን ከጌቶችዎ እንዲቀበሉ ይገባል ልንል እንደፍራለን ፡፡ አሁንም የተሰማኝን ተናግሬ የተጠየቅሁትን ማለፍ አይገባምና የተማሪ ቤቱን አቋቋም ለመናገር አሁን ባይደርስልኝ በእምነትና በአደራ የተቀበሏትን ህጻን ሀገርዎ ዛሬ ከጥበብ መንፈስ ሁለተኛ የተወለደችበት ጊዜ ነውና የተማሪ ቤቱ ስም ተርኀወ ገነት ተብሎ እንዲጠራ ምክሬን አቀርባለሁ ለተማሪ ቤቱም ለብርዕና ለቀለም መግዣ የሚረዳ በቆምኩበት ደረጃ እሳካለሁ አሁን ለጊዜው ፴ ብር እሰጣለሁ ፡፡ ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ፡፡ እንዲህ ብሎ ከጨረሰ በኋላ ቀጥለው ሙሴ መጅድ አቡድ እንዲህ ብለው ተናገሩ ፡፡

ክቡር ሆይ ፡፡ እኔም የተሰማኝን ለመናገር እስቢያለሁና ፈቃዳችሁ እንዲሆን እለምናለሁ ፡፡ የኢትዮጵያ አምድ ልዑል ተፈሪ መኰንን ካዲስ አበባ ያቆሙት ብርሃን በኢትዮጵያ ምዕራብ ዛሬ የደረሰበት ጉዞ ነውና የአውራጃዋ ሕዝብ ሁሉ በዓል ሊያደርገው ወይም ሊቀበለው ይገባል ፡፡ እነሆ ፈላጊው ብርሃኑን አቁሞ ያገሩን ሀብት ጥበብን ሲፈልግ የማይከተለው ሰው ፈሪ ይባላል ፈሪ ማለትም ያገሩ ጠላትና ምቀኛ ወይም ሰነፍ ተብሎ ይተረጐማል ፡፡ ክቡር ራስ ናደው ግን የፍለጋው ተከታይ ሲሆኑ በንዲራቸውን ታጥቀው ከጥበብ አንዱን ማርከዋልና ያርበኞች መጀመሪያ ተብለው ይጠራሉ ፡፡

ክቡር ሆይ ፡፡ ተማሪ ቤት ማለት ልዩ ልዩ የሀገር ጥቅም መፍጠሪ ነውና ከተማሪ ቤቱ በውቀት እየተሸለሙ በሚሰማሩት ህጻናት አፍ ቸርነትዎ ሀውልት ሆኖ ይጠራል፡፡አሁንም ድንቁርና የተባለውን ጠላት ሊያጠፉ ሲጥሩ በተቻለው የማይረዳ ሰው ጉዳቱ ለራሱ ነውና እኔም እንደ ድህነቴ መጠን ፺ ብር እሰጣለሁ ብለው ከጨረሱ በኋላ አስከትሎ አቶ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልዳማኤል እንደሚከተለው ቃል ተናገረ ፡፡

ክቡር ሆይ፡፡ በዚች በዛሬ ቀን ጠርተውን ይኸን የከበረ ሀሳብዎን ስለገለጹልን በጣም ደስ ብሎናል ፡፡ ይኸውም የከበረ ሀሳብዎ ለሐገራችን ጥቅም ለመንግሥታችን ርዳታ ነውና እንደኔ ሀሳብ በቶሎ እንዲፈጽሙት እግዚአብሔር ይርዳዎ ብዬ አብልጨ አጸናዎት ዘንድ እፈቅዳለሁ ፡፡ የስምዎ የዘወትር አሳብዎ ለሐገርዎ ጥቅምና ለመንግሥትዎ እርዳታ መሆኑን የሚመስክርልዎን ምንም እስከ ዛሬ ድረስ የሰሩትን ነገሮች ሁሉ በዝርዝር ልቆጥር ባልችል አሁን በቅርቡ የሰሩትን ነገሮች አስታውሳለሁ ፡፡ መጀመሪ ካዲስ አበባና ከድሬ ዳዋ በቀር በያለበት ያሉት አገረ ገዢዎች ያላደረጉት በርስዎ ግዛት ውስጥ በገነት ከተማ ያለውን መንገድ በገንዘብዎ ማሰራትዎ ፡፡ ፪ኛ የድኃውን ችግር አይተው በቡን እስራት የነበረውን መከራ ማቅለልዎ ፫ኛ አሁን በቅርቡ የሶርንና የገባን ድልድይ በድካም ለፍተው ማሰራትዎ ለሐገርዎ ጥቅምና ለመንግሥትዎ ርዳታ መጣርዎን የሚያስረዳ ነው ፡፡ አሁን ደግሞ እጅግ መልካም የሆነ ሀሳብ ጀምረዋልና ይኸን የከበረ ሀሳብዎን እንደማይፈርስ አድርገው ቢመሠርቱት ለዘላለም ስምዎ እንዳይጠፋ ሐውልት የሚያሳስብልዎ ነው ፡፡ ለኔም ይኸ የከበረ ሀሳብዎ እጅግ ያለ መጠን ደስ ስላለኝ የደስታዬን ምልክት አሁን ሊያቆሙ ላሰቡት የተማሪ ቤት እንዳቅሜ ፳ ብር ልረዳ የተዘጋጀሁ መሆኔን ለክቡርነትዎ እገልጻለሁ ፤ ብሎ በጨረሰ ጊዜ የተሰበሰበው ሰው ሁሉ ከልቡ ደስታ እየፈነቀለው ለተማሪ ቤቱ ይኸን ያህል እረዳለሁ እያለ ነገሩ ከልሳኑ ሲወረወር ሰልፍ ቀንቷቸው የተመለሱ ያርበኞች ፉከራ ይመስል ነበረ ፡፡ እንረዳለንም ብለው ቃላቸውን ለጊዜው የሰጡት ሰዎች ስምና የገንዘቡ ልክ በተራው ይህ ነው ፡፡

አቶ ታከለ ወልደ ሐዋርያት	፴	ብር
ሙሴ መጅድ አቡድ	፺	ብር
ባሻ ወርቄ	፶	ብር
አቶ ኃይለ ጊዮርጊስ	፳	ብር
ፊታውራሪ አስፋው ወስኔ	፶	ብር
ፊታውራሪ ባልቻ	፻	ብር
ፊታውራሪ ከበደ ዘውዴ	፳	ብር
ቀኛዝማች እንዲሮ	፵	ብር
አቶ ካብትህ ይመር	፶	ብር
ፊታውራሪ ከልካይ	፴	ብር
ፊታውራሪ መኰንን	፲	ብር
ፊታውራሪ ቢራቱ	፳	ብር
ፊታውራሪ ዱባለ	፲	ብር
ቀኛዝማች ነምሮ	፲	ብር
ነጋድራስ አባሴኮ	፲፫	ብር
ቀኛዝማች ወልደ ዮሐንስ	፲	ብር
ፊታውራሪ መኰንን	፲	ብር
ሙሴ ሳሊም	፻	ብር
ሙሴ ጉሊኖ	፴	ብር
ሙሴ ባዮናኪስ	፻	ብር
ቀኛዝማች ወልደ ጻድቅ	፲	ብር
ፊታውራሪ ጀማነህ	፳	ብር
አቶ ወልደ ሚካኤል	፳	ብር
ባሻ ወልደ ማሪያም	፫	ብር
አቶ አልዩ	፭	ብር
አቶ ወልደ ጊዮርጊስ	፫	ብር
ቀኛዝማች አየለ	፴	ብር

አቶ በቀለ ታፈሰ	፳	ብር
ግራዝማች ይገዙ	፭	ብር
ቀኛዝማ ውቤ	፭	ብር
ግራዝማች መኰንን	፭	ብር
ቀኛዝማች ሞላ	፲	ብር
ፊታውራሪ መታፈሪ	፲	ብር
አቶ ኃይለማርያም	፲	ብር
አቶ መኰንን	፲	ብር
አጋፋሪ ወልደሚካኤል	፫	ብር
አቶ መኰንን	፲	ብር
ግራዝማች መንገሻ	፱	ብር
ግራዝማች ዲንቃ	፪	ብር
ግራዝማች ገብረ ማርያም	፯	ብር
አቶ ወልደ አረጋይ	፳	ብር
ፊታውራሪ አምጠው	፵	ብር
ፊታውራሪ ደስታ ወሌ	፶	ብር
ፊታውራሪ ባንቲ	፲	ብር
ቀኛዝማች ቁምላቸው	፭	ብር
ቀኛዝማች ሺፈራው	፭	ብር
ሙሴ ቆስጠንጢኖስ	፻	ብር
ሙሴ ኩስማስ	፻	ብር
ሙሴ ዶስካላኪስ	፶	ብር
ሙሴ አርቲን	፻	ብር
ሙሴ ሙራይድ	፶	ብር
ሙሴ ኒኮላ	፻፶	ብር
ሙሴ ዣርጋር	፶	ብር
ሙሴ ማርኬት	፶	ብር
ሙሴ ጳውሎስ	፳	ብር
ሙሴ ዲሚትሪ	፱፻	ብር
ሙሴ ያኒ	፲	ብር
ሙሴ ራክሲስ	፳	ብር
ሙሴ ቆስጢ	፶	ብር
ህዋጃ ምኖ	፲	ብር
ሙሴ ዮሐንስ	፳፭	ብር
ሙሴ ወስሌ	፲	ብር
ፊታውራሪ መንገሻ	፳	ብር
ሙሴ ሙሊዲዎስ	፶	ብር
ቀኝአዝማች ነጋሽ	፭	ብር
ድምር	፱፰፻፶	ብር

ከዚህ ወዲህ የተቀመጡት ፈረንጆች በተራ እየተነሡ ሲሰ ናበቱ ተከትሎ የተጻፈውን ቃልና ምክር እያንዳንዱ ተናገሩ ።

(መጀመሪያ ሙሴ ኩስማስ) ትምሕርት ማለት ብርሃን ማለት ነው ብርሃን ከሌለ ሰው የሚጠፋውንና የሚያጐዳውን የሚ ጠቅመውንና የሚያጐለውን ምንም ለይቶ አያውቅምና ። በጨ ለማ ውስጥ ያለ ሰው ተራምዶ የማይሠራ ችግረኛ ይባላል ። ደግሞ ልዑል ተፈሪ መኰንን በጣም የተማሩ መሆናቸው በዓ ለም ተሰምቷል ሥልጣኔአቸውም በስራቸው ታይቷል ። ግን ረዳት የሌለው ሰው ምንም ቢያውቅ እ'ደማያውቅ ይሆናል ለምሳሌ አንድ ሰው ዓይን ቢኖረው ብዙዎች እውሮች ቢሆኑ በጽኑ ጭለማ ውስጥ ከውሮቹ ይልቅ ያይናማው ሰው ብልጫ እንግዴህ ምንድነው ስለዚህ ረዳት የሌለው ሰው ባንድራሱ ሰርቶ ለመቀመጥ ችግር ነውና እናንተ የኢትዮጵያ ጐልማሶች ይህን በመሰለ ሀሳብ ብትረዳዱ የኢትዮጵያ ብርሃን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከፍ እያለ በዓለም ሁሉ ይታያልና ። እግዚአብሔር ሀሳብ ምን ያቅናልዎ ። እኔም አሁን ለጊዜው ፻ ብር ስለረዳሁ ደግሞ በየመቱ አምሳ አምሳ ብር እሰጣለሁ አሉ ። ቀጥሎ ሙሴ ኒኮላ አንድሪዮቲስ) እንዲህ አሉ ፡ ሰው በተፈጥሮ በሚሰጠው መን ፈስ ሙሉ አዋቂ ነው ስለሆነ ዓይን ቢኖረው አያይም ጆሮ ውም አይሰማም በሰውነቱም ያሉ ህዋሳቶች ሁሉ በሙሉ ተን ቀሳቃሾች አይደሉም ፡፡ ግን ትምሕርት የያዘውን ሲጠርግለት የደነዘው ሲስልለት ማናቸውም ሰው የዕውቀት መዣ ይሆናል ያልተማረ ሕዝብ በድን እንጂ በለሕይወት አይባልምና ። የጀ መሩትን ለመፈጸም ያብቃዎ አሉ ። ቀጥሎ ሙሴ ቆስጠንጢ ኖስ ፡ ያልተማረ ሕዝብ ሕፃን ማለት ነውና በድኩም የተገኘ ውን ወርቅ ወይም የጠራውን ዕንቁ ቢያቀርቡለት የጨዋታ እንጂ የሀብት ጠቀሜታ መሆኑን አያውቅምና ። ለሰጭው እጅግ ያሳዝናል የተማሬ ሕዝብ ግን አስተዋይ ነውና አንዱ ከንዱ ያገኘውን ስጦታ ከፋና በጐውን ለይቶ ሲቀበል ለሰጭው ተስፋ ለተቀባዩም ደስታ ነው ። ስለዚህ ይህ ያሁኑ ዘራችን በሚ ማሩት ህፃናት ፊት ሲበቅል ልምላሜውን ተስፋ ፍሬውን ደስ ታ በማድረግ ኋውቀው እንዲቀበሉት ተስፋ አለንና ። ከብዙ ጊዜ የነበረው የኢትዮጵያና የግሪክን ህዝብ ወዳጅነት በማስ ታወስ እየታደሰ እንደሚሄድ ጥርጥር የለውም ። በዚህም ተየ ማሬ ቤት ሙሉ ደስታ አድርገናልና ሀሣብዎን አምላክ ያቅና ልዎ አሉ ። ቀጥሎሙሴ ሳሊም ታቢት የዚህ የተማሬ ቤት ጥቅ ምና ደስታ ለኢትዮጵያ ሰዎች ብቻ አይደለም በትውልድና በመልክ ብንለይ በባሕርና በፍቅር አንድነት ኢትዮጵያውያን ለሆነው ሁሉ ነው ። አሁንም የቋንቋ ትምሕርት ብቻ አይበ ቃም ማለት ቋንቋ ብቻ የተማረ ሰው የድኛ አፉ ተከፈተ እን ደማለት ነው የጅ ጥበብ የተማረ ግን የታሠረ ህዋሳቱ ተፈታ ማለት ነውና ። ይህም ሀብታም ሰራተኛ ይባላል ። እንግዴህ በዚህ በተማሬ ቤት እኛም የሶርያ ሰዎች የኢትዮጵያን ፍቅር የምንገልጽበት ስለሆነ ምስክራችን እንለዋለንና ፡ እኛንም አብ ዝቶ ለመርዳት እርስዎንም ለመጨረስ ያብቃዎ አሉ ። ቀጥሎ ሙሴ አናሲ ዲ ባዮናኪስ ትምሕርት ያገር ሀብትና ጥቅም የመ ንግሥት ኃይልና ኩራት ነውና እግዚአብሔር ይህን ተማሬቤት ለኢትዮጵያ መልሚያ ለመሆን ያብቃው ብለው ሲጨርሱ ሌሎ ቹም ሁሉ እጅግ በማረ ቃል እየመረቁ እየቤታቸው ሄዱ ግን መስማትና ማየት ለየብቻው በይሆን ለጊዜው የነበርነው ሰዎች ለደስታውና ለምርቃኑ ምሳሌ ለመስጠት አልቻልንም ።

ከቡራን ሆይ በዚህ ምሳሌ እንደ ተመለከትነው ። ላገር መሠረቱና የነፃነት ኃይሉ ትምሕርት እንደሆን ከሁላችሁ የተ ሠወረ አይደለምና ። የሚቻላችሁ ራሳችሁ አቁሙ የማትች ሉም እንደመጠናችሁ ለተማሬ ቤት ለመርዳት ከልባችሁ ቸል

አትበሉ ብዬ በብርሃንና ሰላም ልጆች ቃል በእግረ ትህትና ቂሚ እስታውሳችኋለሁ ።

ከብርሃንና ሰላም መላክተኛ አንዱ ፡፡

የተገባ ጥያቄ ።

ኢትዮጵያ አገራችን በውስጧ ያለ ብዙ ዓይነት እህል ነቀዝ በልቶት ሲፈስ ከህንድ እስያ የስንዴ ዶቄት መፈለግ ምክንያቱ ምን ይሆን ሕዝባችንስ እህሉን የሚሸምትለት አጥቶ ከብር ማጣት የተነሣ ድኅነት አጥቅቶት እያየነው ላንድ ጆኒያ ዶቄት በ፳፰ ብር ሸምተን መብላታችን ብልሀቱ ምንድር ነው ወይስ ቅርቡን ሩቅ ብዙውን ጥቂት አስመስሎ የሚያሳየን ያለ ስረ ነገሩ ምን ይሆን ኢትዮጵያስ በዚሁ ነገር ራስዋን ትችላለችን ወይም አትችልም ራስዋን ለመቻልስ ምን ማድረግ ያስፈልጋታል ለዚሁ ጥያቄ ካያሌ ብልሆች ኢትዮጵያውያን መልሱን ለማግኘት በብዙ ትሕትና እጠብቃለሁ ።

ተማኙ ሮምሃ ።

የውጭ አገር ወሬ ፤

ሬውተር ቴሌግራም ፡፡

የጥቅምት ፳፮ ቀን ፲፱፻፳፯ የዕለት ወሬ ።

ማፋልዳ የተባለ የኢጣልያን መርከብ እባሕር በሰጠመ ጊዜ ሺ ፯፻ ሰዎች ነበሩበት ፤ በመርከቡ የነበሩ ሰዎችም ከመቶ አሥር ሰዎች በተቀር (ኢሚግራንት) ወደ ስደት የሚሔዱ ሰዎች ነበሩ ፤

ማፋልዳ ከኢጣልያን መርከቦች ከጥሩዎቹና ከፈጣኖቹ አንድ ነው ፤ ማለፊያ ያትክልት ቦታና ሲኒማ ነበረበት ። በውስጡም ዕለት ዕለት እዚያው እየታተመ የሚወጣ ጋዜጣ ነበረበት ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፩ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፭ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	ፀብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነርትጓሜው	፯ብር
ሐ ጽባሕ	፭ብር
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ሩብ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትጓርሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ከ፫ ሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲ ብር ፫ ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ተ፫ሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ፡፡
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፩ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፯ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፯ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲ ብር ተኩል
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፯ ብር ተሩብ
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፵፯ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፯ ብር
፡፡ ባለ ድመት ፡፡		፪፴፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፯ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፰ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፭ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፰ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ	፲፪ተ፲፭ ሳንቲ
አንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ	፰ ሳንቲም
ባአንድ ጊኒ	፲ ብር ፲፭	ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር	

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - ΜΕΤΑΞΑ

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ፡፡



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የሚባል ባለአንበሳ ስዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሖ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ፡፡

Automobiles CHEVROLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል"አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ"ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ክች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልክም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ካኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፡ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ኤን ቤ ኔዲሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን አዶክለኝ አምበሬ ጭቃ በያይነቱ የሽቶና የአዶክለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ከውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ሰንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቀ በታች ርካሽ ነው ።

ዓ ለ ም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠ ራል ። ኔከላ ።





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አሜ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክስሙ ጉድዬር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደ ግሞ በልክ ይሄዳል። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆ ን አያስፈራም እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስ ቲክ ሁሉ ጠንካራነው።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድዬር ግዙ ከሌላው ላስ ቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩ ል ነው ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘ ው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

ጉድ ዬ ር ግ ዙ

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤኔስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጎበርና አጎበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፡ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፮
3 me ANNÉE № 46

ሐሙስ ኅዳር ፯ ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 17 NOvembre 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህን ጋዜጣ ብርሃኔና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen , Héritier du trône d' Ethiopie , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

(ኢካቦድ) ክብረት ወዴት አለ ? ክብረት የለም ፡፡

(፩ ሳሙ ፬ ፲፱ ፳፪ ።)

እሥራኤል በመሣፍንት የተመሩበት ዘመን አራት መቶ አምሳ ዓመት ያህል ነበር፡፡ከነዚሁም መሣፍንቶች ኋለኞቹ ዔሊ ሊቀ ካህናቱና ሳሙኤል ናቸው ፡፡ ከዚህ በኋላ ግን እግዚአብሔር ነገሥታት ሰጣቸው ፡፡ መሥፍኑም በነበረበት ዘመን በመንፈሳዊና በስጋዊው ሕይወታቸው ይመቻቸው ነበር ፡፡ እግዚአብሔር እነኝህን ሊረዱዋቸው ያስነሳላቸው ነበርና ፡፡ በዔሊ ዘመን ግን ዔሊ በእግዚአብሔር መንገድ ሊመራቸውና ሊጠብቃቸው አልቻለምና ፍልስጥኤማውያን (ኤሎፍሊ) በሚባሉ ጠላቶቻቸው በጣም ተዋረዱ ፤ ኃጢአት ሁሉ ግዜ የተገባውን ቅጣት ሳይከተለው የማይቀር ስለሆነ ፡፡ ስለዚህ የኢያንዳንዱ ሕዝብ መጨረሻ ጥቃቱ የእግዚአብሔርን ጸጋና ቸርነት ሲርቀው በጠላት እጅም ሲወድቅ ጊዜ ነው ፡፡

በዚህ በላይ በተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንደሚነግር ይህ ሁሉ አንዲት ሴት አወቀችው ። እርስዋም የፊንሐስ የዔሊ ልጅ ሚስት ናት ። የዚህችው ሚስት ታሪክ ምንኛ በጣም የሚያሳዝንና የሚያስደነግጽ ነው ይልቁንም ስቃይዋን ስናስብ ። የርስዋ ታሪክ ለትምሕርት ሊሆነን በአምላካውያት መጻሕፍት ተጽፎአል ፡፡ ከሁሉ በላይ የእግዚአብሔርና የአገራችንን ፍቅር በልባችን ይቃጠል ዘንድ ። እሥራኤል ከፍልስጤማውያን ጋራ ጦር ገጠሙና ድል ተመቱ ። ባልዋና አማችዋ በሰልፍ ወደቁ የእግዚአብሔር ታቦት ተማረከች ። ዔሊ ይህን ሁሉ ወሬ በሰማ ጊዜ ከወንበሩ በስተኋላው ወድቆ ተሰበረና ሞተ ። ይህ ሁሉ ወሬ ባንድ ጊዜ ስትሰማ ለመውለድ ቀርባ ነበርና በድንጋጤ ምጽ ደርሶባት ወንድ ልጅ ወለደች ። አዋላጆችም አይዞሽ የተወለደው ወንድ ልጅ ነው ቢሉዋት ይህን ከልብዋ አላገባችውም ። እግዚአብሔርንና አገሩዋን እጅግ ትወድ ነበረችና ለተወለደው ልጅዋ ኢካቦድ (ክብረት ወዴት አለ?) ብላ ስም አውጥታለት ወድያው አረፈች ። እዩ በንዴት ያለጻር ተይዛ ነበር ። ዳሩ ግን ልበብርቱዩቱ ሴት ይሄው ብርቱሥቃይዋ በእግዚአብሔርና በአገርዋ ፍቅር ምክንያት ረሳችው ። የሕይወትዋ መጨረሻ ከምታስብ ያገሬ መጨረሻ ምን ይሆን በማለት ማሰብ ወደደች ። እውነተኛው የአገር ፍቅር የገዛው ልብ መከራንና የሆነውንም ችግር በደስታ ሊቀበል ይችላል ። ስለዚህ ቤተክርስቲያን ሰማዕታት እንዳልዋት እንዴሁም አንድ ሕዝብ ሰማዕታት ሊኖሩለት ይገባዋል ።

ቢሆን ግን ራሱን የሚወድ እግዚአብሔርንና አገሩን ሊወ አይችልም ። እግዚአብሔርንና አገሩንም የማይወድ ስለነዚህ ሊሞት አይወድም ስለምትወደው እንጅ ስለ ማትወደው ነገር መሞት አይቻልምና፡፡ይህችው ሴት ግን ራስዋን አላወደደችምና ራስዋንና መከራዋን ረሳች ። በሕይወትዋና በሞትዋ የተቀደሰው ፍቅር አሸነፈ ። ስለዚህ ሞትዋም ስለ እግዚአብሔርና ስለ አገርዋ መሆኑ ይታወቅላታል ። በዚች ሴት ከፍ ያለው የእግዚአብሔር ሕግ አሳብ ተፈጸመ እግዚአብሔር አምላክህን ከሁሉ በላይ ባልንጀራህንም እንደራስህ ውደድ የሚለውን ፡፡

ዛሬም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ወንድ ሆነ ሴት ሆነች እንደዚህ ያለውን የጠራና የተቃጠለ የእግዚአሔርና ያገር ፍቅር በልቡ እንዲገዛ ያስፈልጋል ። እንዴህ ባለች ፍቅር ብቻ ኢትዮጵያ ትድናለች ፡፡ ሕዝቦቹም የሚሰለጥኑበት በእግዚአብሔርና ባገራቸው ፍቅር መጠን ነው ። ይህ ሁሉ የሚያችንፍ ፍቅር ያደረበትም እርሱ ብቻ ነው እውነተኛ ብርታት ያለው፤ ብዞች ሕዝቦች የሚበልጡን መጀመሪያው በዚሁ ነው ። እግዚአብሔርና አገሩን የሚወድ ብዙ ይታፈራል ። ይህ ፍቅር የሠለጠነበት አገር አንዳች ድካም የለበትም ፡፡ ብዞች በጦር ጊዜ

ይህን ያህል ሠራዊት እናቆማለን ይላሉ ። እኛ ኢትዮጵያ ውያን ግን ሁላችን ወታደሮች ነን ። ከዚህ ሁሉ ጋርግን ይህ ምሳሌ የሌለው ፍቅር በአገሩ ሁሉ እንዲዘረጋ ብቻ ማድረግ ያሻናል ። እኛ ራሳችንን እንፈራለን እንጅ ሠራዊት አንፈራም ። ከንደዚህ ያለ የባሕርይ አርበኝነት እንዴህ ያለ ፍቅር ሲቀላቀልበት ማን ነው የሚነካን? የአገራችን እውነተኛ ፍቅር ቢሠለጥንብን ብዙውን ነገር ማድረግ ይቻለን ነበር ። ስለዚህ እውነተኛ ሥልጣኔ አገሩን እንደራሱ አድርጎ በመውደድ ነው የሚጀርና እኛም በዚሁ እንጀምር ። አገሩን አጥብቆ የማይወድ ሰው ስለ ነጻነቱም አንዳች አያስብም ። እንዲህ ላለው ሰው የሆነው ቢገዛው ለርሱ አንድ ነው ። ልቦናቸውና ነፍሳቸውን የነቃ ሰዎች ግን ነጻነታቸውን ከሁሉ ይልቅ የከበረች ናትና ከሁሉ ይልቅ እንደ ከበረች አድርገው ይይዟታል ። እነኝህ አገራቸው ነጻነታቸው ከጠፋባቸው ሁሉ ነገር ጠፋባቸው ማለት ነው ። ይህች ሴት የእሥራኤልን ክብር እንደጠፋት ከዚአወዲአም ሕይወትዋን እንዳልፈለገች ። አገርና ነጻነት አንድ ጊዜ ከጠፉ ሊመለስ አይቻልም ቢመለስም ለመመለሱ ብዙ ያስቸግራል ። ዳሩ ግን ያለውን ነጻነቱን መጠበቅ ቀላል ነገር ነው ።እንግዴህ ሴት ያወቀችውን እኛ አንወቅ ወይ? ሕዝብና መኳንንት ትልቅ ትንሽ ወንድ ሴት በጣም ልናቀው ይገባናል ። ይህ የደህንነታችንና የኃይላችን መጀመሪአ ምንጭ ነው።ይልቁንም በኢትዮጵያ ጸጋ ሀብታሞችና ከበርቴዎች ጌቶች ወይዛዝሮች የሆኑትን በዚሁ ነገር በጣም ሊያስቡ ይገባቸዋል ። እናታቸው ኢትዮጵያ እንዴህ ያኰራቻቸው ያከበረቻቸው ሊጠብቋትና ሊያጸኑዋት ነው የሚገባቸው ። ብዙች ስለ አገራቸው ፍቅር ነፍሳቸውን ያሳልፋሉ ። እኛ ግን ያለንን የተቻለነን ስአገራችን ጥቅም ለመሠዋት አንደፍርም፡አገር ራሱን በመውደድና በድንቁርናም በብዙም የስንፍና ስራ ይጠፋል ። አገር ከጠፋም ለሰው ከበጎው ነገር ሁሉና ከክብር ምኑን ነገር ይቀርለታል ? ነጻነቱን ክብረቱን ያጠፋ ሁሉን አጠፋ ። ኢትዮጵያችን ደግሞ እንዲህ ያለ ፍቅር ብቻ ነው በነጻነት ሊጠብቃት የሚችል ።

እንደ ህ ያለ ዓይነት ፍቅር ደግሞ በቀድሞ ሕዝብ ታሪክና ባሁኑ ሕዝብ ዘወትር ይታያል ። በግሪክ አገር አንዲት ሴት ልጅዋ ወደ ጦር ለመሄድ ሲነሣ እንዴህ አላት ፤ እናቴ ከቤቴ ያለው ሰይፍ አጭር ነው ። እርስዋም ልጄ ሆይ አንድ እርምጃ ብቻ ወደፊትህ ብታክልለት ይበቃሀል አለችው ይባላል ። እንዴሁም አራሲዮክሊት የተባለ ሮማዊ ጀግና ሮማ ሊገቡ የመጡትን ጠላቶች ከተማው በሚያገባው ድልድይ ሆኖ ተዋጋቸው ። ግን እዳይበረቱበት ፈርቶ ድልድዩንአፈረሰው ጠላቶችም መግቢያ አጡ እንዲህ አድርጎም ከተማውን አዳነ እርሱም ዋኝቶ አገሩ ገባ ሙሴ ሸበለ ሮማዊም ያገሩን ጠላት ፖርሳና የተባለውን የኤትሩስኪን ንጉሥ ሊገድል ሔደ የንጉሡ ጸሐፊ ያጌጠ ልብስ ለብሶ ነበርና እርሱ ንጉሥ ነው ብሎ ገደለው ። ንጉሡም አስያዘው እሱም ስለሳተ አዝኖ ቀኝ እጁን በንጉሡ ፊት ባለው እሳት ዘርግቶ አቃጠላት ንጉሡም በዚሁ በጭከና ሥራ ተደንቆና ፈርቶ ሮማን ሊያጠፋ ከጅሎ የነበረውን አሳቡን እንደተወ ይተረካል ።

እንዴሁም አንዲት ልጅ ክሌሊያ የተባለች አገርዋን በማፍቀር ትልቅ ድፍረት አሳየች ፤ አገሩን የማይወድ ከሰው ቊጥር አይገባም ። አገሩን የማይወድ ነጻነቱን ያጠፋል ፤ ነጻነት የሌለውም አንዳች ክብር የለውም ፣ የሰውን አገር መመኘት ኃጢአት ነው ፣ ስለ አገሩ መሞት ግን ጽድቅ ነው ፣ እግዚአብሔር ጽድቅን ብቻ እንጂ ዓመጻን ሊያሠለጥን አይወድም ። እግዚአብሔርን መፍራት በሕጉም መኖር አገሩንም በእውነት መውደድ አገርን ያድናል ።

ለኢትዮጵያ ሊታወንት ማስተዋሻ ።

ልዑል እግዚአብሔር በማይመረመር ጥልቅ ምስጢራቱ ሰውንና እንስሳትን በዚች ዓለም ፈጥሮ ሲያበቃ ሰውን በአእምሮ አብልጦ ክፉዉንና ደጉን ለመለየት እውቀትን ሰጥቶ በምድር ለሚኖሩ ፍጥረታት ሁሉ ገዥ አደረገው ። ፩ኛ ሰውን በዚች ምድር እንዲኖር ከደረገው በኋላ ሚሽት አግብቶ ልጆችን እንዲወልድና ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ሕግ እየፈጸመ እንዲኖር ፤ የወለዳቸውንም ልጆች አስተምሮ በእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ ቆመው በጥበቡና በብርሃኑ እንዲኖሩ ያደርጋቸው ዘንድ ይህን የጠበቀ አዋጅ ከልዑል እግዚአብሔር ተቀብሏል ። ፪ኛ የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው እንደ ተባለ የዓለም ሕጋጋት ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው ። እነዚህም የሰው ልጅ ሊመራባቸው የሚገባው የመንፈሳዊንና የሥጋዊን እውነተኛ መንገድ ያሳያሉ መጻሕፍትንና ታሪኮችን ልዩ ልዩ ጥበባትን ተምሮ ጊዜዉን በእውቀት ብርሃን ያሳለፈ ሰው በእውነት ይህ ሰው ጊዜውን በደህና አሳልፈ ለማለት ይቻላል ። ነገር ግን በዚች ዓለም ያሉን ያአንዳንዱን ሕዝብ አናኑዋር ብንመለከት ከንብረት ሊቆጠር አይቻልም ። አሁን ለምሳሌ ላንድ ሰው ባልተ ሳለመጥረቢያ ዛፍን ለመቁረጥ በጀመረ ጊዜ የሚጨርስበትን ኃይልና የሚጠፋው ጊዜ እጅግ ያሳዝናል ። ያ ህ ሰው ደህና የተሳለ መጥረቢያ ይዞ ዛፉን ለመቁረጥ ቢነሳ ኃይሉን ሳይደክም ጉልበቱን ሳይጨርስ እንጨቱንም ሳያበላሽ ጊዜውንም በከንቱ ሳይጠፋ በማስተዋል ቢሰራ ድካሙ ለጥቅም ይሆንለት ነበር ደግሞም አንድ ምሳሌ ብጨምር አይከፋም የማናቸው ወገን ሕዝብ ቢሆን በድንቁርናና በጨለማ ንብረት ቢኖር ንብረቱን እያሻሻለ ከጭለማ ወደ ብርሃን ከድንቁርናና ወደንእውቀት ካለ መማር ወደ ትምሕርት እየተለዋወጠና እየታደሰ ቢሔድ እግዚአብሔር የወሰነለትን ጊዜ በሚገባ ስላሳለፈ ይመሰገናል እንጂ በዚች ምድር ሲኖር ትእዛዛቱን ባንድ ጊዜ ለምን አልፈጸመ ተብሎ ሊፈረድበት አይቻልም ። ልዑል እግዚአብሔር ሰንኳ ሰማይና ምድርን በነሱ ላይ ያሉትን ፍጥረታት ሲፈጥር ባንድ ቀን አልፈጠራቸውም እንደዚሁም ሁሉ በየጊዜው ንብረቱን የማያሻሽልና ጥበብን የማይፈልግ ሕዝብ በዚች ምድር መከራ በሰማይም ኩነኔ እንዳያጣው አይጠረጠርም ፤ ልዑል እግዚአብሔርም ትእዛዙን ጠብቀን እርስ በራሳችን በፍቅር ተዋደን ለጥቅማችን የሚሆኑ ልዩ ልዩ ጥበባትን ልንሠራ በእርግጥ ፈቅዶልናል።

ክቡር አንባቢ ሆይ ይህን ሁሉ ሐተታ ያመጣሁበት ምክንያት በላይ ለጻፍሁት ስለ ኢትዮጵያ ሊቃውንት ማስታወሻ ለሚለው አርእስት መግለጫ (ማስረጃ) ነውና ወደዚሁ ሐሳባችን እ. መለስ። በፊት እንደተናገርሁ ሰው ልጅ ወልዶ ከእግዚአብሐር የ ተቀበለው መንፈሳዊና ሥጋዊ ጥበብን እንዲያስተምረው ከእግዚአብሔር ዘንድ መታዘዙን አስረድተናል ።

በደምብ የቆመ ትምህርት ቤትና የሚበቁ መጻሕፍት ሳይኖርዋት እንዲያው በትጋታችሁና በብርታታችሁ ያገኛችሁትን ሊቅነትና እውቀት ለልጆቻችሁ ብታከፍሉት በሰማይ ከልዑል እግዚአብሔር የማያልፈውን መንግሥተ ሰማያት በምድርም የድካማችሁን ፍሬ ትቀበላላችሁ ያዬም የሰማም ያደንቅላችኋል ያመሰግናችኋልም እኔም ልጃችሁ ከላይኛው የተጻፈውን ዋጋ እንድታገኙና አገራችን ኢትዮጵያም በእውቀትና በትምህርት እንድትሰለጥን ቅዱሳት መጻሕፍትና በኢትዮጵያ ያሉትን የታሪክ መጻሕፍት ለልጆቻችሁ በትጋት እንድታስተምሩዋቸው በትሕትና ከጫማችሁ ወድቄ እለምናችኋለሁ እነሆ የኢትዮጵያ ሊቃውንት መልካቸው የምናውቀው ወሬያቸውን የምንሰማው ብዙ ናቸው ። ነገር ግን ከጥቂቶች በቀር የሚበዙት የተማሩትንና ያወቁትን የእውቀት ብርሃን ለልጆቻቸው ሳይገልጹና ሳያከፍሉ ወይም በትምህርት እውቀት ልጆች ሳይወልዱ የሞቱት ብዙ በመሆናቸው የስማቸውን መጠሪያ ሳይተኩ በመሄዳቸው እጅግ እናዝናለን። ክቡራን አንባቢዎች ግን ያገርህን ሊቃውንት ለምን እንዲህ በድፍረት ትወቅሳቸዋለህ እነሱም ይህን ሁሉ ሐሳብ ለመፈጸም መንግሥት ባይረዳቸው ደምብ ባይወጣላቸው እንዲያውም ተናግረው መክረው ለፍተው ደክመው ሳይሆንላቸው ቢቀር ነው እንጂ ሳይደክሙበትና ሳያስቡበት መቸ ቀሩ ይመስልሃል ይሉኝ ይሆናል ። የከበረ ቋንቋችን እየሰፋ እንዲሄድ በየከተማውና በየገጠሩ የግዕዝና ያማርኛ ትምህርት ቤት እንዲቆም እንዲሁም መጻሕፍትን እየጻፉ ከልዑል አልጋ ወራሽ አስፈቅደ ው እንዲታተሙ ቢያደርጉ ይችሉ የለምን ስል እመልስላቸዋለሁ።ደግሞስ ኢትዮጵያ አገር መሆን ከጀመረች አንስተው እስከ ዘመናት ሲወርድ ሲዋረድ በነበሩት ባሉት ያገርህ ሊቃውንት ኢትዮጵያ ከብዙ ዘመናት ጀምረው አገራቸውን በመንፈሳዊና በሥጋዊ እውቀት ብርሃን ስለ ገለጡላት እንደምን ሥራቸውንና ድካማቸውን ሞያቸውንስ አይተህ አታመሰግንም ይሉኝ ይሆናል ለዚህም አጭር ምላሽ አቀርባለሁ ። እነሆ በምጽፈው ብርሃንና ሰላም መስመሮች ቢመለከቱ ያገሬ ሊቃውንት ለኢትዮጵያ አገራችው በደከሙላትና በገለጹላት የእውቀት ብርሃን ድካማቸውንና ሞያቸውን ሳላስቀር በሙሉ የበቃ ምስጋናዬን አቅርቤላቸዋለሁ ። ደግሞም ጥቂቶች ያገራችን ሊቃውንት የገለጹትን የእውቀት ብርሃን ፣ ያጻፏቸውንም መጻሕፍት በልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታትሞ አግኝተን አንብበናቸው ብዙ እውቀትና ተግሣጽ (ምክር) ትምሕርትንም ስላገኘንባቸው ብዙ ደስብሎናል ። ይልቁንም እነዚህን መጻሕፍት የጻፉ ሊቃውንት ባለሟልነትን ዘመናይነትን ንቀው ፤ ብዙ የመንግሥት ጉዳይና የብዙዎች ሰዎች ደጅ ጥናት ፈጽመው ሲያበቁ ለዚሁ ጊዜ ማግኘታቸው እጅግ ይገርማል ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ይህን ሐሳብ መጻፌ በጽሕፈቴ አርእስት እንዳመለከትሁ ለሊቃውንት ለማስታወስ ነው እንጂ ለመንቀፍ አለመሆኑን እንድትረዱት አልጠራጠርም ።

ይግዛው ጎሹ ።

ስለዘማውያን ።

አፅምዑ ሕዝብየ ሕግየ መዝ ፸፰፩ ።

ሕይወቱን የሚወድ ሰው ማነው በጎንም ዘመን ለማየት የሚሻ መላስህን ከክፉ ከልክል ከንፈሮችህንም የሽንገላን ነገር ከመናገር የእግዚአብሔር ፊት ክፉ በሚያደርጉ ላይ ነው ፣ መታሰቢያቸውን ከምድር ያጠፋ ዘንድ መዝ ፴፬ ፲፩ እስ ፲፯ በሰውክፋት የሀገር ጥፋት በኃጥአን ብዛት ለደጎች ሰዎችእግዚአብሔር ጥፋት እንዳያመጣብን በጎን ሥራ ልንሠራ ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተምረናል የክርስቶስን ሥጋውን ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ ለናንተ ሕይወት የላችሁም ዮሐን ፮ ፫ እንዲህ ብሎ የተናገረውን ቃል ተላልፈው በምንዝርነት በሚስት ላይ ቁባት የሚያስቀምጡትን መጻሕፍት ተባብረው የሚገሥፁትን ከየምዕራፉ አወጣጥቼ እጽፋለሁ እንጂ ከልቤ አውጥቼ አይደለምና መስሚያ ልቡና ያለው ይስማ በነፍሳችሁ ግን ተጠንቀቁ ሉቃ ፳፩ ፴፬ ከዝሙትም ከሴሰኝነትም ሮሜ ፲፫ ፲፫ ለክርስቲያኖች በሚስት ላይ ቁባት ማስቀመጥ ወይም ከሌላው ሰው ሚስት መሄድ አይገባም ኢየሱስ ክርስቶስ ወርዶ ተወልዶ ሥርዓት ከሠራልን ወዲህ ሥጋዬን ብሉ ደሜን ጠጡ ብሎ ወንድ ካንድ ሴት አይለፍ ሴትም ካንድ ወንድ አትለፍ ወንድም ሚስቱን ካላመነዘረች በቀር አይፍታት ማቴ ፲፬፱ ሚስቱ የሞተችበት እንደሆነ ግን ያለሴት መቀመጥ የማይችል እንደሆነ እያመነዘር ቆርቦ ያግባ ።ሴቲቱም ባልዋ ቢሞትባት ተፈታች ቆርባ ሌላውን ታግባ ፩ቆሮ ፯ ፴፱ ሮሜ ፯ ፪ ፫ ይህን ብርሃን የሆነ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚያፈርሱ ሌቦች ብርሃንን እንደ ማይወዱ ሁሉ እንዲሁም ኃጢአተኞች የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አይወዱትም ያፈርሱታል ። ሚስቱን ትቶ ከባልንጀራው ሚስት ጋራ ለማመንዘር ቢሄድ ባልዋ አብረው ቢያገኛቸው ይገድለዋል በሥጋው ክፉ ሞት ቢሞት በነፍሱስ ገሃነመ እሳት ቢገባ ከሁለት ወገን ጥቅም የሌለው ነገር ነው ። እራሱን ለማጥፋት ለምን ይደክማል ሰሎሞን ፯፻ ንግሥታት ፫፻ ቁባት ሺህ ሴቶች ነበሩት ነገሥት ቀዳ ፲፩ ፫ እግዚአብሔርም ተቀየመው ይህን ስላደረግህ መንግሥትህን ከሁለት እከፍልብሀለሁ ለባሯህም እሰጠዋለሁ አለው

ሰሎሞንም ሴቶችን ማብዛት እንዳልጠቀመው አይቶ ለኛ ተግሣፅ ጻፈልን ፫ት ነገር ይገርመኛል አራተኛውን ከቶ አላስተውለውም የንስር መንገድ በሰማይ ላይ ፤ የባብ መንገድ በደንጊያ ላይ ፤ የመርከብ መንገድ በባሕር መካከል ፤ የሰው መንገድ ከቆንጆ ጋራ እንዲሁም በልታአፏን የምታብስ አንዳችም ክፉ ነገር አላደረግሁም የምትል ያመንዝራ ሴት መንገድ ናት ምሳሌ ፴ ፲፰ ፤

ልጄ ሆይ ስለምን እንግዳ ሴት ትወዳለህ የሌላይቱንስ ብብት ለምን ታቅፋለህ ምሳሌ ፫፳ ጌታም አፍቅሩ ጸላእተክሙ ቢለን ጠላትንስ መውደድ ይቅርና አክሉ የምትሆን ሚስቱን

ወደ.ት ለሥጋ ወደሙ ሳያደርሳት በላይዋ ቁባት አስቀምጦ ወይም የጭን ገረድ አድርጎ ሲያስቀይማት ሲፋቱና ሲታረቁ ዕድሜያቸውን ቢጨርሱ ያም የሞት ቀን በድንገት ሳያስቡት ቢደርስባቸው የሰማይ ቤታቸውን ኑሮ ምን እንደሆነ ሳያውቁት መሄዳቸው ትልቅ የከበደ ድንቁርና ነው ። ባልና ሚስት ያልተፋቀሩ ሌላው ሰው ማንና ማን ተፋቅረው መንግሥተ ሰማያት ትገኝ ይሆን ።

እንዲህ ከሆነ እግዚአብሔርን ፈርተን እርስበራሳችን ተፋቅረን አንዱ ላንዱ ተረዳድተን ሚስቶቻችንን ወደን ባለፈው ክፋታችን ንስሐ ገብተን ሥጋ ወደሙ ተቀብለን የሰማይ ቤታችንን አበጅተን ልንኖር ግድ ያሳስበናል ። ዘሰ አፍቀረ ለዓመፃ ጸልአ ነፍሶ መዝ ፲፩ ።

ዘበልዓ ሥጋየ ይሄሉ ምስሌየ ብሎ አስተምሮአችሁ ዮሐ ፮፥፶፮ ፤ ሥጋውን በልታችሁ ደሙን ካልጠጣችሁ ። ቃልኪዳኑን አይፈርስም ትኩነናላችሁ፡፡ እንደዚህም ብሎ ሲያሰናብታችሁ ። እኔም አላውቃችሁ ወዴት ነበራችሁ ። ከኔ ወዲያ ራቁ ዓመፀኞች ናችሁ ። ማቴ ፳፭ ፵፩ ለዘለዓለም ኑሩ ከሲኦል ገብታችሁ ። ጥርስ ማፋጨት ነው ልቅሶን አብዝታችሁ ። ማቴም ፲፫ ፶ ቁም ጸሐፊ ገብረጻድቅ ።

ስለ ክቡር ራስ ናደው ።

ክቡር ራስ ናደው ከግዛታቸው ሽፍታና ሌባ ማጥፋታቸውን የከተማ መንገድ በገንዘባቸው ማሰራታቸውን በገዛና በሰር ወንዞች መንገደኛና ነጋዴ በሚያስጨንቁ በ፪ ውሆች ድልድይ ማሰራታቸውን የይሉ አባ ቦር የቡን አስራት ለባላገሩ ትልቅ መከራና ችግር ሆኖ ሲኖር የተሻለ ጥሩ ደንብ ማውጣታቸውን ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ስንሰማ ቆይተናል ። ዛሬ ግን በብርሃንና ሰላም ተጽፎ አነበብነው ።ይልቁንም አሁን የትምሕርት ቤት ለማቆም አስበው መነሳታቸውን በአነበብሁ ጊዜ ብዙ ገረመኝ ። ይኸንንም ማለቴ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የትምሕርት ቤት ለማቆም እርዳታ ስንለምን ለእርዳታ እንኳን ትንሽ ገንዘብ ከኪሳችን አውጥተን እንሰጣለን ያሉ ጥቂቶች ናቸው።ክቡር ራስ ናደው ግን በሚገዙት አውራጃ ትምሕርት ቤት ከመኳንንቶቻቸው ጋራ ብቻቸውን ለማቆም ተነሱ።ይልቁንም የገረመኝ እንረዳለን የሚሉ ብዙ አገራቸውን የሚወዱ መኳንንቶች ማግኘታቸው ነው ። እነዚህ አገራቸውን የሚወዱ መልክከሞች መኳንንት በምን እጣ በዚያ አገር ተሰበሰቡ ይሆን ። የይሉ አባ ቦርስ አገር በምን እድል ክቡር ራስ ናደውን የመሰሉ ከገንዘብ ይልቅ አገራቸውን የሚወዱ ብርሃን ገዢ አገኘች ይሆን ? መቼም የሚያሳዝነኝ ለጊዜው ኢትዮጵያ አገራቸው እንደሆነች ከማያስቡ ሰዎች ይልቅ ትንሽ ብር ደስ ከምታሰኛቸው ጋራ ራስ ናደው መቆጠራቸው ነው ።

ክቡር ሆይ እንዲህም ስላልሁ የግድ ስምዎን ታሪክ ጸሐፊዎች ያስቀድማሉ በዘመኑም ታሪክ ስምዎ ልቆ ይጻፋል የሚያቆምዋትም የትምሕርት ቤት ኢትዮጵያ እስካለች ስምዎን ታስጠራለች ። በቀድሞ ጊዜ ኢትዮጵያን ጠላቶቿ ሲወጓት የኢትዮጵያ ኃያላንና ጀግኖች ከጠላታቸው ገለው ግዳዩን ከንጉሡ ፊት ጥለው በመፎከራቸው ንጉሡንም ደስ ያሰኛሉ ስማቸውንም ያስጠራሉ የአገራቸውንም ነጻነት ይጠብቃሉ በዚህም ሥራ ይቀዳደማሉ ወደ ኋላ የቀረም ይናቃል ።

ዛሬ ግን እንደዚያ ጊዜ ያለ ጦርነት በእድሜያችን እስካሁን ከውጭ አልመጣብንም ስለዚህ የዛሬው የኢትዮጵያ ጠላት ድንቁርና ነውና ክቡር ራስ ናደውም ድንቁርና ከሚባለው ጠላት ገድለው ከመንግሥታቸው ፊት ግዳይ መጣላቸው ነው።አዝማሪ ሰንጎ መገን ሲል አይድረስ እንጂ ድንገት ቢናጋ ቀደም የሚል የማነው ሰንጋ ይላል እንደዚህም ሁሉ ታሪክ ጸሐፊ የኢትዮጵያ መኳንንት ሲያነሣ የራስ ናደውን ስም ጽፎ ማንን ይጨምር ይሆን ። መቼም በዛሬ ጊዜ ያለብን ጦርነትና ጀብዱ ድንቁርናን ገድሎ ግዳይ መጣል ብቻ ነውና ማን ይሆን ክቡር ራስ ናደውን ግዳይ በመጣል ሲቀዳደም የምናገኘው አይታጣም ይሆናል በቀረ ግን ልዑል አልጋ ወራሽን እራስ ናደው ብቻ ተከትለው ከድንቁርና ይዋጉ ብንል በዘመኑ ታሪ መሣቂያ እንሆናለን እየ የኢትዮጵያ ጀግኖች አሳዘናችሁኝ አሁንከ መድፍና መትረየስ ተጠምዶ የአረር በረዶ ቢዘንብ ለአገሩ ብሎ ከዚያ እሳት ውስጥ ገብቶ የሚያልቅ የኢትዮጵያ መኳንንት አይቆጠርም ወይ አለመጠየቅና ነገሩን አለመረዳት ይኸ ነገር ወደ ፊት በታሪክ ላይ ስማችውን የሺህ ዓመት እርምጃ ወደ ኋላ የሚያስቀር በይመስላቸው ከ ው ። እንባቦች ልጆችና አሽከሮች ይህችን ቃል ለአባቶቻችሁና ለጌቶቻችሁ ንገሩ ስማቸው በታሪክ የዓመት መንገድ ወደ ኋላ እንዳይቀር ያስፈራል ። ደግሞም ይኸን ቃል መጻፌ ክቡር ራስ ናደውን ለማመስገን ብቻ አይደለም ለዚህ ለሚያቆሙት ትምሕርት ቤት ሲቆም ሁላችን መርዳት እንዲገባን ለማስታወቅ ነው።አሁን ለምሳሌ ባንድ ወረዳ አገር ጦር ቢነሣ ሁላችን መርዳት እንደሚገባን የታወቀ ነው ይኸም እንደዚያው እንደጦርነት ሁሉ ድንቁርና ጨለማን እንውጋ ብለው ክቡር ራስ ናደው ሲነሱ ሳንረዳ ብንቀር ይኸ ሐሳባችን ጠላትም ቢመጣ ያለመርዳታችንን ይመስክርብናል ። እኔም ሌላ የትምሕርት ቤት የምረዳው ስላለብኝ ብዙ መርዳት አልችልምና ክቡር ራስ ናደው ለሚያቆሙት ትምሕርት ቤት አርባ ብር እረዳለሁ።ወንድሞቼ ሁላችንም እንርዳ ገንዘብ ጠፊ ነው ግን በቁም ነገር ብናጠፋው ይሻላል ይህ መርዳታችን ለሳቸው መርዳት እንዳይመስለን ለአገራችን መርዳት መሆኑን እንወቀው ።

ፊ ዴሬሳ ።

ስለ ብርሃንና ሰላም ምስጋና ።

ይድረስ ለክቡር ብርሃንና ሰላም ። ብርሃንና ሰላም ከዘመን እዘመን እንኳን ያደረሰህ ። ሰላምታ አቀርባለሁ እንዲሆን የልብህ ፡ እስቲ በስመ አብ ብዬ ምስጋና ልናገር ። ብርሃንና ሰላም ሊያቀና ነው አገር ፡ ተደፍና ስትኖር አንዲት ቡርክት አገር ፡ ቀናች ተቃወመች አየች የኒያን አገር ፡ ቡርክት ኢትዮጵያ ልጅዋን ልካ ነበር ፡ አይቶ ተመለሰ የሰራውን ነገር ሊያቀናት ሊያለማት ያስተምራት ጀመር ፡ ኢትዮጵያ ደኅ አገ

ኞች ደግ መምሕር ። እየመራረጠ ልጆች የሚያስተምር ። ልጆቹም ተማሩ ስሙንም ሰየሙለት ለመምሕራቸው ። ብርሃን ዘኢ. ኢትዮጵያ ሠረቀ ብለው ፣ ብርሃን ከጨለማ እንዲበልጥ አውቀው ፤ እያልኩ ምስጋናና ሰላምታየን ሳልጨርሰው ፤ ፩ትልቅ ሰውዬ የብርሃን ልብስ የለበሰ የሚያንጸባርቅ ከተፍ አለብኝ እኔም ስፈራ ስቸር ስንቀጠቀጥ ልዑል ጌታ ተየት መጡና አስደነገጡኝ ብየ አልኩት እርሱም መለሰና ልጄሆይ አትፍራ አሳብህንና ምስጋናህን ስራ ። ልጆቹን አመስግን ከናታቸውና ከባታቸው ጋራ ፣ እኔ አግዛቸዋለሁ በሚያስቡብትና በሚሰሩት ስራ ፤ ከዚያች ሴትወይዘሮ ኢትዮጵያ ጋራ ። ቀድሞም ነግራኛለች የልብ አሳብዋን ። እኔም አያታለሁ አዘቅዝቄ እኗን፡ እርስዋም እንድትተው አይሆንም በዩን ። መርጣ መርጣ ታውጣ ብልህ ልጆችዋን ፤ በጣም እንድትለማ ኃያል እንድትሆን፡ እንድትነቃ በጣም ትመረጥ ልጆቿን ፤ እንዲደበድቡት አይሆንም ብዩን ፤ ብልህ ብልህ ትምረጥ ታስቀር ሰነፉን ፤ እኔ አልልም ነበር ከሰው ሰው ምረጡ ። ባያቸው ነው እንጂ ደግ ሥራን ባይመርጡ ፣ ይህን ታደረገች ማነው የሚነካት ። ተልከ እማ ያፍር አርበኛ ልጅ አላት ፣ መራርጣ ልጆቿን ምክር ታስመከረች ፤ ለተቀዋሚዋ ታንቀጠቅጣለች ፤ መች ልጅ አጣችና መክን ነኝ ትላለች ። ከሠረቀ ብርሃን ልጆች ትመርጣለች ። አንድ ሁለትመቶ ሰው ምኒስቴር ታቆመች ። ለሁሉም ፋብሪካ ስራ ታሰራለች አለኝና ሁለተኛም እመጣብሀለሁ ተጠንቀቅ ብሎ የሚያስፈራራ ብርሃን ልብሱ ተጎናጥፎ አረገ ። ክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ ይኸ ሰው ሳይመጣብን በማናቸውም ስራችን አገራችንን አክብረንና ተጠንቅቀን ብንቆየው ይሻላል ይመስለኛል ስል ሰላምታየን አቀርባለሁ ።

ደጃዝማች በላይ አሊ. ሚ ።

ታላቅ ደስታ ።

በሰው አገር ላለነው ተማሪዎች በ፳፰ኛው ቁጥር የታተመው የኢትዮጵያ መንግሥት የርሻ ሚኒስቴር የከብት ህክምና ሥራ ተብሎ የወጣውን ማስታወቂያ ርነብብን ግዜ ደስ ያለንን ደስታ ጥልቅነት የዚህን ስራ ጥቅም የሚያውቁ የኢትዮጵያ ወዳጆች ፈጽሞ ሳይገባቸው አይቀርም

ደስታዬ በጣም ጥልቅ ስለሆነ ።

ያለችኝን ገንዘቤን የተማረ ስጦታዬን ክቡር የኢትዮጵያ የርሻ ሚኒስቴር የተማረ ስጦታው ምስጋና ብቻ መሆኑን አውቀው በማክበር የማቀርበውን የተገባቸውን ምስጋና እንዲቀበሉኝ እለምናለሁ ።

ቀጥዬም የዚህን የኢትዮጵያ መንግሥት የርሻ ሚኒስቴር ያቆሙትን የከብት ህክምና ስራ ቤት ጥቅም ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ባጭሩ በማክበር ላስታውስ እወዳለሁ ።

ለመንግሥት ብርታቱ የህዝቡ ህይወት ነው ይባላል፡፡ህዝብ እየበረከተ ካልሄደ መንግሥት አይበረታም ። ህዝብም በክንቱ ከሚፈጅ በሽታ ካልተጠበቀ ክምች አይድንም ። ስለዚህም የኢትዮጵያ ህዝብ እስከዚህ ዘመን ድረስ እንደ ዝንብ ያልቃሉ ይሉናል ።

ከማናቸውም ግዜ ይልቅ የሕፃንነት ወራት እጅግ አስቸጋሪ ነው ። ሕፃኖችን የሚፈጅ ዓይነት በሽታ በጣም ብዙ ነው ። ብዙውም የበሽታው ዓይነት የሚመጣው ከሚታለቡት ላሞች ከወተታቸው ከሚታረዱትም ከብቶች የሚነሳ ነው ። እዚህ ባለንበት አገር ሃኪም ያልፈተሸው ከብት ታርዶ ስጋው እንዳይበላ በመንግሥት ስራት ተከልክሏል ሃኪም ያልፈተሻት ላም ታልባ ወተቱ እንዳይጠጣም ክልክል ነው ። ስለዚህ በሕፃንነታቸው ወራት የሚያልቁት ልጆች ቁጥራቸው እንደ ኢትዮጵያውያኖች አይበዛም ።

አሁን እዚህ ሁኜ እንደሚመስለኝ ባዲስ አበባ የከብት ሀኪም ቤት ተከፈተ መባልን ሲሰሙ የታመሙትን ከብቶች ለማዳን የሚጓጉ ይበዛሉ እንጂ መታመማቸው ያልታወቀውን የየከብቶቻቸውን ህይወት ለማወቅ የሚያስፈትሹ ይበዙ አይመስለኝም ። ይኸ የተጀመረው ስራ ወደፊት በጣም እያደገ የሚሄድ መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን ግን አሁን ለግዜው ከዚህ ቀጥዬ የማስታውሰውን ክብር የርሻ ሚኒስቴር ኢትዮጵያን በሚወደው ልባቸው መርምረው ቢከተሉት ታላቅ ሥራ በዚህ በተከፈተው ስራቤት ይሰራ ይሆናል ።

መጀመሪያ ፤

በአዲስ አበባ የሚሸጠውና የሚገዛው የቀንድ ከብት ላም በግ ፍየል በሬ ይኸነን የመሰሉ የምግብ እንስሶች ሁሉ በዚህ በመስሪያ ቤት ሰራተኞች ኃኪሞች ሳይመረምሩ እንዳይሸጡ መከልከል ያስፈልጋል ። ተመርምሮ ከብቱ ደህና ነው የሚል ምልክት ታትሞበት ያልፋል ። በሽታ ቢገኝበት ሳይታተም ያልፋል ። ይኸም ያልታተመ ከብት ተገዝቶ በስጋ ሻጮችና ስጋ በላተኞች እጅ እንዳይገባ ክልክል ይደረጋል ። ክልክሉንም አፍርሶ አርዶ የተገኘ ስጋ ሻጭም ቢሆን አርዶም ለራሱ በላተኛ ቢሆን በመንግሥት ዘበኛ ተይዞ የተደነባውን መቀጮ በግድ ይከፍላል ። የሚገባውም ገንዘብ ለስራ ቤት ይሰጣል ።

ሁለተኛ

ባዲስ አበባና ባውራጃዋ ያሉ ባለ ላሞች ሁሉ የመንግሥቱን ኃኪም እየወሰዱ ላሞቻቸውን እንዲያፈትሹ በግድ ያስፈልጋቸዋል ። ያልተፈተሸች ላም ወተት ታልባ ሲጠጣ የተገኙ እንደሆን ለመንግሥት መቀጮ ይከፍላሉ ።

መልአኩ በያን ።

በዚህ የቀረ በሚከለው ይታተማል ።

ማስታወቂያ

እኔ ወይዘሮ አፀደ ገነሜ መስከረም ፲ ቀን አቤቱ ያለውን እቃ ሁሉ ሰርቆ የማኅተሜን ቁልፍ ሰብሮት እመሬት ጥሎት ስለተገኘ. ከዚያ በፊት ከኔ ጋራ ውል ያለው ሰው ሁሉ ህዳር ፳፩ እከንቲባ ነሲቡ ላይ እማዘጋጃ ቤት እምጥቶ ያላሳየ በቁርጥ ውሉ ያለመርጋቱን አስታውቃችኋለሁ ።

ወይዘሮ አፀደ

ማስታወቂያ

በልዑል ተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ግቢ በቆመው የእጅ ጥበብ ስራ መማሪያ ቤት እየተሰራ በርካሽ ዋጋ የሚሸጥ ብዙ ዓይነት ጨርቅ አለ ዓይነቱም ከዚህ በታች የተጻፈው ነው ፡ የገላ ሹራብ ከሎስ ሐር በያይነቱ የገላ ሹራብ የጥጥ በያይነቱ ፎጣ የጥጥ በያይነቱ ትልቅና ትንሽ ፍሉሀ ሲታጠቡም የሚለበስ ቀብ ከሎስ ሀር በየዓይነቱ ትልቅና ትንሽ የጥጥ ቀብ በያይነቱ ትልቅና ትንሽ ጥበብ ኩታ ጨርቅም በየዓይነቱ አለ ። ለመስኮት የሚሆን መጋረጃና ለጠረጴዛና ላልጋ ልብስ የሚሆን ፡ ሌላም ዋጋውን ተቋርጦ እንደፈለገው ዓይነት ሊያሰራ ይችላል ። ለመግዛትም የሚፈልጉ ሰዎች ከቅዳሜና ከእሁድ በቀር ከ፪ ሰዓት እስከ ፲፩ ሰዓት እልዑል ተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት መጥተው ሊገዙ ይችላሉ ።

ሐኪም ወርቅነህ

የውጭ አገር ወሬ

ጥሪንስተፐስ ማፋልዳ የተባለው መርከብ የሰጠመው ምክንያት ምን እንደሆነና ስለ አላፊነቱም ለመመርመር ፡ መንግሥት ማሪና በሚባል ኰሎኔል አለቃ ፕሬዚደንነት በተለየ ሽማግሌነት ሥራን አቀምዋል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሚቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው ፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው ፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው ፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው ። ፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ ፰ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር ፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው ፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ ፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነርትጓሜው ፯ብር
ጎሐ ጽባሕ ፰ብር
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ ፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ፩ ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጤ ፩ሩብ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው ፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ ፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትጓሜው ፬ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትንርጓሜው ፪ብር
የሕይወት ታሪክ ፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት ፩ብር
የማሪኛ ሰዋስው . . . . ፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ አላድ
ወዳጄ ልቤ ፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ አላድ
ያማሪኛ ፊደል ሩብ
አሳብና ምኞት ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር ፪መ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ከ፫ ሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲ ብር ፫ ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ተ፫ሩብ
ስም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፩ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፯ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፯ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲ ብር ተኩል
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፯ ብር ተሩብ
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፶፯ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፯ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፴፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፯ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፰ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፰ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፰ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ	፲፪ተ፲፰ ሳንቲ
አንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ	፰ ሳንቲም
ባአንድ ጊኒ	፲ ብር ፲፰	ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር	

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሚጋ የሚባል ባለአንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVRGLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቀቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል"አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ"ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤሄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፡ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፤ መጫሚያ በያይነቱ፡ ወንበር በየዓይነቱ፡ ብረት ማጥን በየዓይነ ቱ፡ ቢሲግሌት ፡ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፤ ፋኑስ በየዓይነቱ ፡ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፡ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

ዓለም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠ ራል ።

ኒኮላ ።

ጉድዬር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይ ነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄ ዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢ ሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬ ዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌ ላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌው ላስቲክ ሁሉ ሁለ ት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፯
3 me ANNÉE № 47

ሐሙስ ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፳ ዓ.ም ።
JEUDI 24 NOvembre 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ
ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix ".

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

እናት ።

አባትህንና እናትህን አክብር ።

ከሕጻንነት ጀምሮ እስከ መጨረሻ እርጅና ድረስ እየተደ
ጋገሙ የሚወሱ ሁለት ስም አሉ ። እርሳቸውም እግዚአብሔ
ርና እናት ናቸው ፤ ሁለታቸው ርኅራኄና የደህንነት አሳብ ፍቅ
ርም ያሳያሉ ። ትንሹ ልጅ በልጅነት ፍርሃትና ክርሱ በሚበረ
ታው ጠላት ሲከበብ ጊዜ ወይም ከረሐብ ቀስቃሽ የተነሳ ጊዜ
እናቴ ብሎ ይጮሃል ፤ ታማሚም በአልጋው ላይ ተጋድሞ በመ
ጨረሻ የጻዕረ ሞቱ ጊዜ እናቱን ይጠራል ።

ጀግናው ጎበዝ ጭቃና አፈር በሞላው ጉድጓድ በደሙ
በተለወሰ ጊዜ የሰዉም ጠላትነት ሁሉ ሲከበው እርሱ ስለ
ጠቀሜቱ የሚመክትና የሚከላከል ጥፍጡን የናት ስም ይጠ
ራል ፤ በእግዚአብሔርና በናት መሀከል የጸና መስማማት አለ
ደግሞም በእናት ልብና በልጅ ልብ መሀከል የማይበጠስ ሊበ
ጥስም የማይቻል ማሰሸ አለ ። ይህ ማሰሸም ከሥጋና ከደም
ሰርቶ በርሱም የእጅግ ጥሩ ፍቅር ባሕርይ አግብቶ እግዚአብ
ሔር በገዛ እጁ አለመው ።

አስቀድማ የተቀደሰች እናት ትገኝ ፤ ከዚያ ወዲያ ደገኛ
ልጅ ይገኛል ፤ አስቀድማ አስተዋይ እናት ትገኝ ። ከዚያ ወዲ
ያም ዕድላም ልጅ ይገኛል ፤ ብዙች እናቶች አሉ ወንዶችን
የወለዱ እውነተኛይቱ እናት ግን ብርቅናት ፤ ጋብቻን አጽንታ
ችሁ ቀድሱ ከዚያ በኋላ ከተማውና ሕዝቡም መንግሥቱም ክ
መጸኞች ይነጣሉ ። እናት በዓለም የእውነተኛው ሥልጣኔና የ
እውነተኛው ትድጊት መሠረት ናት በተቀደሰው በጋብቻ ሥር
ዓት ኑሩ ፤ እናታችሁንም አክብሩ እግዚአብሔር ይህን ይወዳል
እግዚአብሔር ይላል አባትህንና እናትህን አክብር እናት ሁሉ
ጊዜ ከከንፈሩዋ የጥበብና የማስተዋል ቃል ሊወጣ ይገባል ል
ጆችም ሁሉ ጊዜ ወደ እናታቸው ማድመጽ ይገባቸዋል እርሱ
ዋ የእግዚአብሔር መልክ በሚታይበት በዓይኖችዋ ታስተው
ላለች በልብዋም ትናገራለች እናት ስለ ልጆችዋ ብዙ ልትጸ
ል የሽታል ደገኛ እናትም ኃይሉዋ ጸሎት ነው እግዚአብሔር
ሆይ ልጆቼን መልካምን ነገር ላደርግላቸው እንድችል እርዳኝ
አምላክ ሆይ እንድወዳቸው አንተ ታውቃለህ ልትል ይገባታል

ቀድሞ ዘመን በምስር በትልቁ ወንዝ በኒል ዳር ከሸምበ
ቆ ተሠርታ በቅጥራንም የተቀባች ትንሽ ቅርጫት ለኋላው ትል
ቅ የሚሆን ጨቅላ ሕጻን የያዘች ተቀምጣ ነበር አዬ ደገኛይ
ቱ እናት ዮኬቤድ በዚህች ሳጥን ልጇዋን አስቀምጣ ከወንዙ
ዳር ስታኖረው ስንት አልቅሳ ትሆን አንድ ብርቱ ጨካኝ ንጉ
ሥ የእስራኤል ወንድ ልጅ በተወለደበት ጊዜ ወዲያው በኒል
ወንዝ እንዲጣል አዋጅ ነግሮ ነበር አዛኝቱ አዬ ልጄ ሊሞት
ነው እያለች ታለቅስ ኑራ ትሆን ልብዋ ግን ሊያድነው ይፈ
ልግ ነበር ።

ስለዚሁ እርስዋ ልብዋን በእውነተኛ ጸሎት ወደ እግዚ
አብሔር አቀናች ልጅዋን እንዲያድንላት ። ከዚሁ ሁሉ ጋር
ግን ከእኅቱ በቀርም በወንዙ በስተ ወዲህና በስተወዲያ ያችን
ሳጥን እንስሳ ሆነ ሌላም ነገር ሆነ እንዳይነካት አጽንተው የሚ
ጠብቁን በር ። እርሳቸውም የእግዚአብሔር መላእክት ናቸው ።
እግዚአብሔር በለቤቱ ከሳጥኒቱ ጋራ ነበር ። እንሆ ታሪኩ
የእግዚአብሔር መጽሐፍ እንደሚ ነግረው ፤ ያን ጊዜ የንጉሥ
ሴት ልጅ ወደ ወንዙ ልትታጠብ ወረደች እርስዋም ሳጥኒቱን
አየችና አስመጣቻት ። በከፈተቻትም ጊዜ የሚያለቅስ ሕጻን
አገኘችላት ። አዝናም አዳነችው ። ይህም ሕጻን ሙሴ ተባለ ፤
ማለቱ ከውኃ የዳነ የእናት ጸሎትና የእግዚአብሔር የማያልቀ
ውን ርኅራኄ ሙሴን አዳኑት ፤ የናት መልእክት ወይም ስራ

ይህ ነው ፡ እንጂ ሌላም አይደለም ፡ የገዛ ልጆችህን ለማዳን መንቃት ፡

ልጆችን ማሳደግ የሰው ሁለተኛ ገጹ ነው ። አካል ሊያድግና ሊጨምር ይችላል ምግብን በማግኘት ዳሩ መንፈሱ በውስጡ ባይገን ሰውነ ደሎ ነው ፡ ይህም ማደግ በቅጣትና በማስተማር በመገሠጽም በመምከርም ይሆናል ። የሥጋ ገጽ ማደግ ብቻ ማሰብ እንደ እንስሳ ማደግ ብቻ ነው ከርሱ አይበልጥም ። እንዲህ ተሆነ ሰውን መውለድ ብቻ የምታውቅ የወለደችውን ግን ልክ ሰው ሊሆን አሳብ የሌላት እናት ወዮላት ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታችን አንድ ቀን አለ ያሰው (ይሁዳ) ባይወለድ ይሻለው ነበር ሰው በባሕርዩ መጥፎ ከሆነ ሕይወት ለርሱ ለምኑ ነው የጋብቻ ስርዓት የእግዚአብ ሔር መቅደስ ነው ፡ በእናት ቤት ነው መጀመሪያው ተማሪ ቤትና ቤተክርስትያኑ ሊጀመር የሚገባው ፡ አስቀድማ እናት በቤትዋ ለልጆችዋ ደገኛ አስተማሪ ልትሆን ይገባታል ልጆች ዋን በውነት መንገድ እንድታሳድጋቸው ለንዴህ አድርጋ በትምሕርትቤት ላሉት አስተማሪዎች ልታሳልፋቸው ያስፈል ጋታል ተማሪ ቤትም በምላት አስተምሮ በደግነት መንገድ ሁሉ አሳድጎ ለቤተክርስትያንና ለሕዝብ ለመንግሥትም ማሳለፍ ይህ ነው መንገዱ ። ስለዚህ የእናት አላፊነት በእግዝአብሔር ፊት ብርቱ ነው የሚበዙቱ ሰዎች በናታቸው ስበብ እንጅ በራሳቸው ስበብ አልጠፉም ፡፡

እናት በትዳርዋ የልጆች ካህን ናት ልጆች ጺያፍ የሌለባ ቸው ደገኞች ሁነው በሁሉ ነገር ለማደግ መጀመሯ ከእናታቸው ነው ሊማሩት የሚገባቸው ግን ይህን ሁሉ ባታ ስብበት ለራስዋም መጥፎ እናት ብትሆንስ የተቈደሰው የሃይ ማኖት እሳት በእግዚአብሔር ፍርሃት በቤትዋ ባይቃጠልሳ እናት መልእክትዋን ባታስተውል ወይም ራስዋ ከእግዚአብሔር መንገድ ብትወጣ ለልጆችዋ ምን ይቀርላቸዋል በነብያት መጽሐፍ እንደ ተባለው ብቻይ ፈጸማል እንደ እናትዋ እንዲሁ ልጅዋ ፡፡

አንዲት አስራሰስት ዓመት ያደረገች ሴት ልጅ በብዙ ስርቆ ትዋ ተይዛ ምላሽልትሰጥ በዳኞች ፊት አቆሙዋት ያች መከረ ኛይቱ ፍጥረትም ብዙ እንባ እያፈሰሰችና እየተንሠቀሰቀች ፈራጁን አለች እናቴ ለመስረቅ አዘዘችኝ እናት ለራስዋ በጽድ ቅ መንገድ ስላልሄደች ልጅችዋንም እንደሚገባ ስላላሳደገች ወህኒ ቤቶች በዓለሙ ሁሉ በተሳሳቱቱ ወጣቶች ሞልትዋል

ልጆችን በእናት ቤት ለደግነት ማሳደግ ለሕዝብ መልካሙ አናንዋር መጀመሪአው ምንጭ ነው የተሻሉቱ ሰዎች ለሰው ወገን እጅግ ትልልቅ ደግ ሥራ የሰሩቱ ሰዎች ከእንዲህ ያለ ቤት ነው የተገኙ ድልመንግሣታቸውና ክብረታቸው በገዛ እናታ ቸው ረድኤት ነው የደረሱት እናቶች ሹመታችሁ ስንት ትልቅ ነው ሥራችሁስ ስንት ጽኑ ሥራ ነው ስማችሁን አታስነውሩ የማሕፀኖቻችሁንም ፍሬ አታበላሹ በሰው ወገን መከከል ትልቁ የእግዚአብሔር መቅደስ ሰሪዎች መጀመሪያዎች እናንት ናችሁ ልጆችን ማቀፍ ከጀመራችሁበት ቀን ይዛችሁ በበጐነት ሁሉ እንድታሰድግዋቸው ፈቃዳችሁ ይሁን እንዲህ ብታደርጉ ባደጉ ጊዜ ባልተቀጡና በደግነት ባላደጉት ከሚወርደው መከራ ማም ለጥ እንዲችሉ ታደርግዋቸዋላችሁ እላንትም በደግነት ስለ አሳ ደጋችኋቸው በደግነትና በቅጣት በማስተማር ባላሳደጉ እናቶች ላይ ከሚወርደው ኃዘንና ልቅሶ ትድናላችሁ ፡፡

ሕፃንን የሚሔድባትን መንገድ አስተምረው በሸመገለም ጊዜ ከርስዋ ፈቀቅ አይልም (ምሳ ፳፪ ፡ ፮ ።)

የ፫፻፷፭ ገጽ ተከታይ

የሥጉያ ሥራ መመልከት

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ከዚህ በላይ የጻፍሁት እኔ በማ ንበብና በመስማት ከተገኘው ሃሳብ እየተነሳሳ የተገለጸልኝ ነው ግን አስከትዬ የምጽፋቸውን ቃሎች ስራዬ ብዬ ከሐረርጌ እንደ ወሎ የሚርቅ መንገድ ያህል ሂጄ ባይኔ እያየሁ ልብ ያደረኩ ትን ልጽፍላችሁ እመኛለሁ ።

በዚህ ባለሁበት አገር የስጋ ከብት በየቤቱና በየከተማው ብዙ አይታረድም ከ፻፲፭ ሚልዮን የሚበልጥ ሕዝብ ሁሉ የሚ መገበው ሥጋ በዚያው ባንድ ከተማ እየታረደ እየተዘጋጀ ይሄ ዳል ፡ ይኸውም ከተማ ኢለኖይ በሚባለው አውራጃ ያለው ችካጐ የሚባለው ከተማ ነው ። ችካጐ ፬ ሚልዮን ህዝብ የሚ ኖርበት ታላቅ ከተማ ነው ፡፡

እንግዲህ አንድ በሬ ከተወለደበት ቦታ ካገር ቤት ወጥቶ ተሽጦ ለመታረድና ለመበላት እንዲበቃ ያለበትን ሃተታ እን ዳስረዳ ምኞቴ ነውና በሚከተሉት መስመሮች እሞክርአለሁ

መጀሪያ ፡ባላገር በሬውን ቀልቦ ያወፍርና ሌሎቹንም ብዙ ለመሸጥ የተዘጋጁትን የቀንድ ከብቶቹን ይወስድና ወደዚህ ወደ ታላቅ ገበያ ለመሄድ በባቡር አሳፍሮ ይዟቸው ይሄዳል ፡፡

ሁለተኛ ፡ በገበያው በደረሱ ጊዜ ባቡር ይቆማል ። ባለከ ብቶች አስቀድሞ ፳፫መህለቅ በጭራ ሊከፍል የተከራየው በረት አለና ወደበረቱ እንዲገቡ ከባቡር እመውጫቸው ላይ ከደጃፍ አንድ የከብት ሃኪምና አራት ወይም አምስት ረዳቶች ቁመው ይመለከቷቸዋል ፡፡ ከብቶቹ ደህና የሆኑ እንደሆነ ዝም ብለው ያስገቧቸዋል ። ግን እከክ ሊጀምረው የሆነ አንድ ከብት በመ ክከላቸው ያገኙ እንደሆን ወይም ማናቸውም በሽታ የጠረጠ ሩት እንደሆን ይመረምሩታል ፡፡ እከክ እንደሆን የተገኘበት ከቈስሉ ላይ ይቀረፉትና በመስተዋት ላይ ለጥፈው በማጉሊያ መነ ጽር ይመረምሩታል በርግጥ በሽታው የተገኘበት እንደሆን እነ ዚያን አብረውት የተገኙትን ከብቶች ሁሉ በቶሎ ሄደው እን ዲታረዱ መንግሥት ዋጋቸውን ይከፍለዋል ግን በሽታ ሳይገኝ ባቸው ሁሉም ያለፉ እንደሆነ እገበያው በረት ገብተው እንዲ ሰነብቱ ይገባሉ ባለቤቱም በጭራ ፳፫ መሐለቅ ከፍሎ ከገቡ በኋላ የተወሰነ ቀን የለበትም እዚያ አሰንብቶ ሲሸጥ ይሰነብ ታል ግን በዚህ በገበያው በረት ሳሉ ዘወትር በጥንቃቄ በመ ንግሥት ሃኪሞች ይሰልላሉ ጢት ጢት ጸሐይ ስትወጣ ሃኪ ሞችና የሃኪሞች ረዳቶች እየዞሩ በየበረቱ ያሉትን የቀንድ ከብቶች ይመረምራሉ አመራመራቸውም እንዲህ ነው ሃኪሙ ዝግ ብሎ ይሄድና በበረቱ ዳር ቁሞ ይመለከታል በጀርባው ትንሽ ጠባሳ ያየበት እንደሆነ በረቱን ይከፍትና ገብቶ ተጠግቶ

ይመለከተዋል ከዚያም በኋላ ነገሩ የሚያጠራጥር የሆነ እንደ ሆነ ረዳቶቹን ይጠራና አብረው ይመለከቱታል በዓይናቸውም ሳይረዱ የቀሩ እንደሆነ እንስሳውን ይዘው ያንን የቆሰለውን በታ እየቧጠጡ ወስደው በማይክሮስ ኮፕ ይመለከቱታል ወቼም የከኳን ነፍሳት ፈጽመው ያውቁታልና ከመግሉ ውስጥ ያገኙት እንደሆነ ለማወቅ አያስቸግራቸውም ግን በሽታው ሌላ የሆነ እንደሆን ማለት በሽታው ሐሰት ሁኖ የተገኘ እንደሆን እንስሳውን ለባለቤቱ ይለቁለታል ።

አንድ አንድ በሽታ ደግሞ እንስሳውን ያንቀጠቅጠዋል አንድ አንድ በሽታም ያስለቅሰዋል አንድ አንድ በሽታም ጠጉሩን እያቆመ ያከሳዋል ግን አጥብቀው የሚጠነቀቁት የሚያሳክክ በሽታ ይዞት እንስሳ ከከብቶች እንዳይደባለቅ ነው ። እንደ ዚህም ማድረጋቸው እከክ የያዘው ከብት ታርዶ ቢበላ የሚያስፈራ ሁኖ አይደለም ለዚያስ ያከክ ከብት ቢበላ ቆዳው ነው እንጂ ያከከው ሥጋው አይደለም ቆዳውን እንኳን በጣም አይጎዳውም ብለው ነግረውኛል ፤ ግን ጉዳቱ እንዲህ ነው እከክ የያዘው ከብት ዘወትር እንደከሳ ያድራልና ሲቀለብ ኖሮ ያገኘውን ስጋ በከንቱ ሳያጐድል ማረድ ይሻላል ብለው ነው ወዲያውም የከብት እከክ በጣም የሚጋባ በሽታ ነውና ብዙዎችን ሳያበላሽ መቅደም ይሻላል ብለው ነው ።

ሰስተኛ፤ እንግዲህ ያላመቃረድ ሊሸጥ የመጣ እንስሳ በሽታ ሳይገኝበት ቀርቶ ፈተናውን ሁሉ ያለው እንደሆነ የርድ ከብት ገዢዎች ይገዙታል መቼም እዚህ አገር የርድ ከብት የሚገዙ ኩባንያዎች ናቸው እንጂ እቤቱ ለማረድ የሚገዛ የለም የርድ ከብት ሲገዛ እየተመዘነ እንደክብደቱ ነው የሚሸጠው መቼም መከበዱ ብዙ ሥጋ ቢኖረው ነውና ስለዚህ ከባዳው ባለ ብዙ ዋጋ መሆኑ አይጠረጠርም ።

አራተኛ ፤ የሥጋ ቤቶች ስራ የከበረ ሁኖ ተገኘ እንግዲህ ኩባንያው የሚታረዱትን ላሞችና በሮች ገዝቶ ለመንግሥት ሥጋ ቤቶች ያስረክባል ።

አምስተኛ ፤ እንግዲህ ሥጋ ቤቶቹ ይረከቡና ወደ ማረጃ ቤት ያገቡዋቸዋል የላሞችና የበሬዎች አስተራረድ በሃገራችን እንደምናውቀው እንዳይመስላችሁ የሚታረዱት ከብቶች እየተነዱ አንድ ጠባብ የሆነች የብረት በሚከፈት ሳንቃ የተዘጋች ውስጥ ሰስቱን ወይም አራቱን ያስገቡዋቸዋል ከዚህ በኋላ አንድ ሰው ታላቅ መዶሻ ያነሳና አንደኛው ተንጠራርቶ ግንባሩን ይመታዋል እንስሳውም ወደ ሰማይ ይጉንና ተመልሶ ይወድቃል ሁለተኛ ሲደግመው ፈጽሞ ይሞታል ከዚህ በኋላ ሳንቃውን ሲከፍተው ተንከባሎ ወደውጪ በበረቱ ይርቃል ከዚያ በፍጥነት አንድ እግሩ ላይ ሰንሰለት ይጠልፉና ይሰቅሉታል ወዲያው በአምስት ደቂቃ ሁለት ሰዎች ቆዳውን ገፈው ይፈጽማሉ ከዚህ በኋላ አንደኛው የከብት ሃኪም የእንስሳውን ሆድ ይቀድና የሆዱን እቃ ሳንባውን ጉበቱን ልቡን ኩላሊቱን ይኸንንም የመሰሉትን ብልቶቹን ሁሉ እየቆራረጠ ይመረምረዋል በሽታ ያገኘባቸው እንደሆነ ተበላሽቷል የሚል ማህተም እያተመ ይወረውራቸዋል ከዚያ እያነሱ ወደ ላፊር የሚሆን ቅባት ወደ ሚሠራበት መኪና ይወረውራቸዋል ግን በሽታ ያላገኘባቸው እንደሆን በመንግሥት መርማሪዎች ፈቃድ አለፈ የሚል ማህተም እየታተመ ያሳልፏቸዋል የቀሩትንም ትልልቆቹን ብልቶች አንደኛቸው ሃኪም እያጸዳዳ በሽታ የጀመራቸው ትንንሾች ሥጋዎች ያገኘ እንደሆነ እየቆረጠ ይጥላቸዋል ግን በሽታው በሰራ አካላቱ ተነዝቶ ብዙውን የሥጋውን ክፍል ነክቶት ያገኘው እንደሆነ በሬው በመላ እንዳይበላ ተበላሽቷል የሚል ማህተም ያትምበታል እጅግ አድርጎ የገረመኝ አንድ በጣም የሚያስቀይም የከሲታ በሬ ሥጋ መልክም ያለበሽታ ማለፉን የሚመሰክር ማህተም ሲገኝበት ያንድ እጅግ አድርጎ የሰባ የሚያስጐመጅ የበሬ ሥጋ በመላ ተበላሽቷል ብለው ሲጥሉት ባየሁ ጊዜ ነው ዋ ያገሬ ሰዎች ስንት ጊዜ ባለማወቅ የታመመ ከብት ሥጋ እየበላችሁ አልቃችሁ ይሆን ።

ስድስተኛ ፤ እንግዲህ ከዚህ የይለፍ ከሚታተምበት ክፍል ካለፈ በኋላ እጅግ ቀዝቃዛ በሆነ ቤት ከሰባት እስከ አስራ አራት ቀን ድረስ ተሰቅሎ እንዲቀዘቅዝ ይገባል።

ሰባተኛ፤ ከዚህ በኋላ እስድስት ቦታ ተመርምሮ ካለፈ በኋላ በታረደ በሰባት ወይም ከሰባት እስከ አስራ አምስት ቀን ከቆየ በኋላ በሬውን ገዝቶ እንዲታረድለት ላስረከባቸው ኩባንያ ያስረክቡታል ከዚህ በኋላ ለህዝብ በገበያ እንዲሸጥ ከመንግሥት እጅ ወጥቶ ወደ ነጋዴዎች እጅ ይገባል ስለዚህ ነጋዲዎቹ በለምሉ ነጻዎች ይሆኑበታል አንድ አንድ ሰራተኞች በዚህ ነገር ይናደዳሉ ማለት መንግሥት ለፍቶ ለፍቶ በንጽህና አሰናድቶ ያቀረበውን ነጋዴዎች እንዳያበላሹ አለማዘዙና ስልጣን አለማግኘቱ ለህዝብ የሚጐዳ መስሎ ስለታያቸው ነው።

መልአኩ በየነ ።

ከዚህየቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ሐበሻ ስለ ተባለው ቃል

አበሻ ማለት ከዓረቦች የተሰጠን የንቀትና የስድብ ስም እንደሆነ ብዙ የውጭ አገር ታሪከኞች ጽፈውብናል ።እኛም ይህ ቃል ከምን እንደ ተገኘ ትርጓሜውስ ምን እንደሆነ ሳንረዳው ጠላት ያወጣልንን የቅጽል ስም ተሸክመናል ። እነዚህም ታሪከኞች አቢሲኒአ ወይም ሃቤሲኒአ ሃቤሽ ከሚለው ከዓረቢኛ ቃል የመጣ ነው ይላሉ ። ትርጓሜውም ድብልቅ ዝብርቅርቅ ማለት ነው ብለውታል ። በዓረብኛም አጻጻፉ ሐበሻ ነው ይላሉ ይኸም ሲተረጐም አፈስ ደበስ ፈለገ ይሆናል እያሉ ባለ ቋንቋዎቹ ይነግሩናል ስለዚህ ቃሉ በዝቶ ተዘበርቆበቸውና ተደባልቀባቸው ይሆናል እንጂ እኛስ ድብልቆች አይደለንም ። ቃሉም የኛው የበላጋሮቹም የተወላጆቹ ነው እንጂ ከውጭ የመጣብን አይደለም ። ይኸም ይታወቅ ዘንድ እስከ ዛሬ ድረስ በምዕራብ ኢትዮጵያ ይልቁንም ወለጋዎች በረሃውን አበሻ ይሉታል ። ይኸም ቃል በቆዩት ሽማግሌዎች ዘወትር ሲነገር ይሰማል ። የዛሬውን ኀበዛዝት ግን በረሃ ማለት በጋልኛ ምንድርነው ብለው ቢጠይቋቸው በረሃ ነው ብለው ይመልሳሉ እንጂ አበሻ ነው ሊሉ አይችሉም ምክንያቱም እንዲህ ነው የዛሬው የጋላ ትው

ልድ ከአጼ ምኒልክ መንግሥት ወዲህ ውሎውናል አዳር ከአማራ ጋራ ስለሆነ ብዙ የጋልኛ ቋንቋ ዘንግቷል በዚያም ፋንታ አንዳንድ አማርኛ አግብቶ ይናገራል ። አማሮቹም እንዲሁ ጀምረዋል አንዳንድ ጊዜ ሲጽፉ ደኑን ሚክ ሲሉት እናያለን ። ይህ መሆኑ ከለ መጠንቀቅና ከመዘንጋት የተነሳ ነው ። ጥንት ጋሎች ግን በረሃ ሲሉ አበሻ ይሉ ነበርና እስከ ዛሬም የጥንት ሽማግሌዎች ይነጋገሩበታል ። እንዲሁም ከጋላ አባቶች ሲያያዝ የመጣሡ ቃል አበሻ ብዙዎች ረስተውት ጥቂቶች ሲናገሩበት ይሰማሉ ። ትርጓሜውም በረሃ ማለት ነው እንጂ ድብልቅ ማለት አይደለም ።

አገራችንም በሁለት ስም መጠራትዋ አሁን በቅርብ ነው እንጂ የጥንት ስሟን ዓለም ሁሉ ያሠ ቀዋል ። ከአጼ ምኒልክ መንግሥት ጀምሮ እንደ ዛሬው አገር ሳይሰፋና ሳይቀና በአጼ ቴዎድሮስ መንግሥት የነበችረው ኢትዮጵያ ለዛሬዋ ኢትዮጵያ ችን ሲዖ ነበረች ይባላል ። በዙርያዋም ብዙ ባዶ ተራራና በረሃ እንደ ነበረ ዛሬም እንዳለ የታወቀ ይኸንም አበሻ የተባለ ስም በአጼ ምኒልክ የቀናችው ኢትዮጵያ ከባላገሮችዋ እንዳገኘችው መረዳት ይገባናል ።

ደግሞም የአበሻ አቅኒዎች አማሮች ብቻ አይዶሉም ጋሎችም ጭምር ናቸው በቀድሞ ዘመን ከግቢ በታች ጋሎች አልነበሩም እያደር አገር እያነሳቸው ቦታ እየጠበባቸው ከግቢ ፈልሰው ሻንቅላ እያለቀቁ በረሃ እያቀኑ ተቀምጠዋል። ይልቁንም «ሃቤሻ» አበሻ ከሚለው ቃል የተገኘ መሆኑን የሚያስረዳ አንዱ ከዚህ በታች እንደ ተጻፈው ነው

በቀደሞ ዘመን ዓረቦች ከደቡብና ከደቡብ ምዕራብ አበሻ ጠረፍ ብዙ ጋሎችና ሻንቅሎች እያስፈነገሉ ለባርነት ይወስዱ ነበርና ከሕዝቡ ንግግር የሰሙት ይመስላል ። ቋንቋም በተዘመተበት አገር ያገር ቋንቋ ይሆንና የመጣበት ግዕዙ ሲታጣ መሰል ትርጓሜ እንዲቀበል ማንም አይስተው ። ለዚህም መግለጫ የሁለት ቃሎችን በቅርብ ቀን መገኘት ጽፌ አመለክታለሁ ።

፩ኛ ፤ ፎዘ በግሥ ብልሃቱ ወይም ፍችው ታጥቶ ይኖር ነበርና የጎንደር ሊቃውንት ነባቡን እየሄዱ ትርጓሜውን ሳያውቁት ይኖሩ ነበር ይባላል ። ከዘመናት አንድ ቀን አንድ ሊቅ ከጎንደር ወደ ትግሬ ሄደ ባንዱ ቤት እንግድነት ተቀምጦ ሳለ ሴትዮ ምጣድ ጥዳ እያነኰረ እያስቸገራት ባጠገቧ ያለች ሴት በትግርኛ ፋዚዮ ብትላት ማሰሻዋን አንስታ ታስስ ጀመር ። ከዚያ በኋላ ያ ሊቅ ፎዘ ትዝ አለውና ፎዘ ማለት አሠሠ ወለወለ ማለት ነው ብሎ የተማረው ሊቅ ካልተማረች ሴት የፎዘን ፍች ተረድቶ ገባ ተመልሶም ለጎንደር ሊቃውትን አበረከተ ሁሉም በደስታ ተቀበሉት እስከ ዛሬ የፎዘ ግሥ ወለወለ መሆኑን ሊቃውንት ሁሉ ተረድተውታል ።

፪ተኛ ፡ ድጓ ማለት ከጸሐፊው ወዲህ ትክክለኛው ትርጓሜ ሳይታወቅ ይኖር ነበር ይባላል ። ለዚህ ሊቃውንት የታጣውን ነገር ለማግኘት መጣር ልማዳቸው ነውና የድጓን ትርጓሜ እንደ መሰላቸው በስም ሞክሼ ሲተረጉሙት ይኖሩ ነበር ። ትርጓሚዎቹም እንደሚቀጥሉት ነበሩ ። ድጓ ያለውን ለቤት ክርስቲያን ሠርጓ ይሉት ነበር ሠርጓማለትም ሽልማቷ ማለት ነው ።

ይኸንንም ያሉበት ምክንያቱ ይኸው ድጓ የተባለ መጽሐፍ አሠርገዋ ለምድር በስነ ጽጌያት ። አሠርገዎ ለሰማይ በከዋክብት ብሩህ ያለውን ይዘው ነበር ይባላል ። ደግሞም አላልተው ድጓ የቤተ ክርስቲያን መቀነትዋ ብለው ይተረጉሙት ነበር ። ግን ነገርን ከባላበት ሲረዱት ይጣራልና ከዘመናት አንድ ቀን አንዱ በደው አድዋ ከተማ ጨው ጭኖ መጥቶ ለከብቶቹ ገፈራ ለመግዛት ሲፈልግ ድጓ ሽጡልኝ አለ ይባላል ። አንተ እስላም ድጓ ምን ያደርግልሃል ቢሉት ለከብቶቼ አበላዋለሁ ቢላቸው ብልህ አይታጣምና ዓይነቱን አሳየን አለው በዓውድማ የተቆለለ የጤፍ አበቅ አሳይቶ ድጓ ያልሁት ይኸን ነው አለ ይባላል ። እነሱም የእብቅን ብዛትና ደቃቅነት የድጓንም ብዛቱንና ረቂቅ ጽፈቱን አመዛዝነው ድጓ ማለት ለመጽሐፉ የባሕርይ ስሙ መሆኑን ተረድተው ድጓ ብዙን ረቂቅ ብለው ተረጕሙት ይባላል ።

እኔ ግን ሊቅ አይደለሁም ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ጋላ ከብት ጠፍቶት ሲፈልግ ውሎ ወደ ማታ አግኝቶ ይዞ ሲመለስ ጐረቤቶቹ ከወዴት አገኘኸው ቢሉት በኬ አበሻ ኬሳ ሲል ሰማሁት ቀረብ ብዬ አሁን ቢጠይቁህ ምናልክ ብለው ይኸንኑ መለሰልኝ እና ምን ማለት ነው ብለው ሰው ከሌለበት በረሃ ማለት ነው ብሎ ፍችውን ነገረኝ እኔም ተገርሜ ይኸን ቃል ሌሎች ይናገሩበታል ወይ ብዬ ብጠይቀው ። አዎን ከአያት ከቅድማያት የመጣ ነው አባቶቼም ሲናገሩበት ሰምቻለሁ ምነው እንዲህ ደነቀህ አለኝ አይ እንዲያው ነው ብዬው አለፍሁ ከዚያም ወዲህ ብዙ ሽማግሌዎች ብጠይቅ ይኸንኑ ነገሩኝ። በቀን ብዛት እያነሰ ሄዶ ነው እንጂ አበሻ ግዕዙ ከባላገሮች የወጣ መሆኑን ለራሴ ተረድቻለሁ ። አረቦችም እንዴህ ያለ በስም ሞግሼ የሆነ ቃል እንዳላቸው ለሳቸው ያድርጉት እንጂ እኔ ፣ ልቀበላቸውም ።ከወገኖቼም መከከል በዚህ ነገር የሚተባበረኝና የበለጠ ማስረጃ የሚሰጥ አላጣም በማለት ፍጹም ተስፋ አለኝ ። ጥቅምት ፲ ፱ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ሰዮ ።

(የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።)

ጥበብና ድንቁርና

ጥበብና ድንቁርና በመንገድ ተገናኙ ሲገናኙ ሳለ እንዴት ዋልክ ተባባሉና ሁሉም በየአዳራቸው እየተጫወቱ ሲሄዱ ሳለ በነገር ተራ ተጣልተው እኔ እበልጣለሁ እኔ እበልጣለሁ ተባባሉና ለተወላወል ከዳኛ አድርስን ተባባሉና ከብርሃንና ሰላም ዳኛ ደረሱ ብርሃንና ሰላምም አቶ ተወላወል በምን ነገር ተጣልተው አመጣሁቸው አሉት እኔስ ጌታዬ ድንቁርና ቢናገር የትዕቢቱን የኩራቱን የስንፍናውን የችጋሩን ነው ፤ ጥበብ ሲናገር ስልጥንናውን ትሕትናውን አዳሩን ትዳሩን ልብሱን ጉርሱን ምክሩን ዝክሩን ነው ለኔም ለራሴ ብልሐቱ ተሰወረኝና ለእነሱም አደርሳለሁ እኔም እሰማለሁ ብዬ መጣሁ አለ ብርሃንና ሰላምም አቶ ድንቁርናን በልእስቲ ተናገር ኑሮህ እንደምንድነው አሉት እሱም መለሰ እኔማ ኑሮየን ስናገር ከሰማይ

ብታች ከመሬት በላይ እንደኔ ያለ ኩሩ ከፍናናም የለ እንኳን ለራሴ ለሰው እተርፋለሁ አለ እንደምን አሉት እኔማ ብረት እንዳልሰራ ጠቢብ እንዳይሉኝ ጨርቅም እንዳልሰራ ሸማኔ እንዳይሉኝ እንዳልሰፋም ሰፊታ እንዳይሉኝ አራሽም እንዳል ሆን ገበሬ እንዳይሉኝ ወርቅና ብር እንዳላፈስ አንጠረኛ እንዳ ይሉኝ እንጨትም እንዳልቀርጥ ፈላሽ እንዳይሉኝ ቄስም እን ዳልሆን እረሳ መሬ እንዳይሉኝ ጸሐፊም እንዳልሆን ወረቀት ቀዳጅ እንዳይሉኝ ብየ በኩራትና በትዕቢት ተነፍቼ እጄን እግ ሬን አለስልሼ ቁምጣ ሱሪ ታጥቄ ነጠላ ለብሼ መሟጫየን ከቀ ርሴ ሰክቼ ፯ ምላስና ፱ ዓይን ያላቸው ባልንጀሮች አሉኝ ከነሱ ጋር ከአፋፍ ላይ ቁጭ ብዬ እውላለሁ አለ እነዚያስ ባልንጀሮ ችህ ፯ ምላስና ፱ ዓይን ያላቸው ባልንጀሮችህ እነማን ይባላሉ ቢሉት ባልንጀሮቼ ክራርና ዋሽንት ገበጣ ናቸው አለ ይህን ሁሉስ ጥበብና ሥራ ራሱን የሚጠቅም ለመንግሥት የሚሆን ውን ድኃ የሚአድርበትን ንጉሥ የሚነግሥበትን ቤተ መቅደስ የሚሠራበትን ስመ እግዚአብሔር የሚጠራበትን ጠላት የሚ ገፋበትን ነገር ጥበብና ሥራ ትምህርት ሁሉ ንቀህ በኩራትና በትዕቢት ተነፋህና እጅህን እግርህን አለስልሰህ ከጠራሆቸው ባልንጀሮችህ ጋራ ከአፋፍ ላይ ተቀምጠህ ስትጫወት ዋልክ ለምግብህ እሳ እንደምን ትኖራለህ አሉት ለልብሴና ለምግቤ ብገኝ እቀላውጣለሁ ባጣ ወይ እስርቃለሁ ወይም እቀማለሁ ደግሞ በዚኸውም በአገሬ ቀማ ሠረቀ አመጠ ሸፈጠ አልባ ልም ክራር ሲመታ ዋሽንት ሲነፋ ገበጣ ሲጫወት አየነው እንጂ ሰረቀ ቀማ ሸፈጠ አልባልም ትልቅ ሰው ጨዋ ተብዬ እፈራለሁ እከበራለሁ ያንተንስ ሰማነው እስቲ አቶ ጥበብ ንገ ረኝ አሉት እኔማ ስናገር ቀድሞስ ቢሆን ጋኔን የሰፈረበት ስን ፍና ያደረበት ሌላን ቁም ነገር ይሠራልን ክራር ሲመታ ዋሽ ንት ሲነፋ ገበጣ ሲጫወት መንደር ለመንደር ሲዞር ሲሸፍጥና ሲአፍጭ አይደለም የሚውለው አሁን ድንቁርና የሚሉ እር ኩስ የዲያብሎስ አሽከር ቀድሞ ለጌታው ለዲያብሎስ ጌታ ለመ ላእክት አለቃ አድርጐ ቢሾመው ውርደት ይሻለኛል ብሎ እኔ ንኝ ንጉሥ አለና በዚያው ባሰበው ነገሩ በሰናስለ እሳት ታስሮ ታሕት እመቅ ወርዶ በበርባሮስ ጨለማ ተዘግቶ ይኖራል ይላሉ ደግሞ ዛሬ ድንቁርና የሚሉ የዲያብሎስ አሽከር እንደኔ ያልሆ ንክ እያለ ያሰድበኛል ያዋርደኛል መብሉ መጠጡ ውሎው አዳሩ ከኔ ይህንን አልችልም የሚፈልጉኝና የሚወዱኝ አሉ ከነሱ እሄዳለሁ ወይም እሱን አባሩልኝና እቀመጣለሁ እንጂ ከድንቁርና ጋራ እኩል እነጋገራለሁ ወይም ሞያውና ሞያየ ይቆጠርና እንማዘን አለ ለአቶ ድንቁርና መልስ ቢሉት እኔስ ጌታዬ ዲያብሎስ አደናክር አደናቁር አለኝ እንጂ ከጥበብ ጋር በሞያ ተለካከም አላለኝ አለ እንግዲያስ የቀድሞ ጥፋትህ አን ሰህ ደግሞ ዛሬ አገሬን ልታጠፋ ነው እኔ ከገዛሁት አገር አት ቀመጥ አሉት እሱም ተፈጥሞ ለቀቀ ጥበብም ሙሉ ሽልማት ተሸልሞ በመላ አገሩ ተሾመ ልዑል አልጋ ወራሽም ሒር አስ ትምር አሉት እሱም ከትልቅ ተራራ ላይ ዘለቀና እንዲህ አለ የኢትዮጵያ ልጆች ቀድሞስ መቸም ብነግራችሁ አልሰማች ሁኝም አሁን ግን በቅርቡ በጃንሆይ በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ጥቂቶች ሰዎች ብነግራቸው ያውም እየፈሩ ልብ ማድረግ ጀም ረው ነበሩ ወዲያውም በመካከሉ ተውት እኔም ይገሉኛል ብዬ ፈርቼ ሸሽቼ ሂጄ ከዋሻ እቀመጥ ነበርኩ አሁን ግን የኢትዮ ጵያ መብራት ብርሃንና ሰላም አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አገ ራቸውን ለመጥቀምና ለማስፋት ድኃቸውን ለመጠገን ከድንቁ ርና ወደ እውቀት ለመመለስ በውጭ አገር ያሉ ሰዎችም ከሚ ሰድቡት ስድብ ለማዳን ከኛ የሚበልጥ ማን አለ ብለው ከሚ ኩሩበት ጥበባቸው ለማስተካከል አስበው እንደ ኢትዮጵያ ነገ ሥታት ለገንዘባቸው ሳይሳሱ በብዙህ ገንዘብ የጽሕፈት መኪና ገዝተው የተማሪ ቤት አሰርተው የዲያብሎስን መዝጊያ ድንቁ ርናን ከፍተው ለኢትዮጵያ ጥቅምና ተስፋ ለጨለማው ብርሃን ለጠላት መመከቻ ጋሻ ለሆኑት ለልዑል አልጋ ወራሻችን ፍሬ አቸውን ያብላን እድሜያቸውን ያርዝምልን ። ደግሞ የኢትዮ ጵያ ልጆች ልንገራችሁ ጥበብን ተማሩ ድንቁርናን አባሩ ለጌታ ችሁ ታዘዙ አዋጁን አትናቁ የንጉሣችሁን ቃል ታዋቃችሁና አቅንታችሁ ስሙ አንድ ልብ ሁኑ የቀድሞ አገራችሁን በድ ቁርና የቀረውን አስቡ ምክሬን ስሙኝ በድንቁርና አትዘንጉ ትምህርት ተማሩ ሲል ተናገረ ። ከዚህ በኋላ ድንቁርና ከአገር መልቀቁ ፈጽሞ ታወቀውና የትካዜ ነገር እየተከዘ ሄደ ቃሉም ይህ ነው ። ወይኔ ድንቁርና ወይኔ ድንቁርና ትልቅ ተብዬ ጨዋ ሰው ተብዬ ስጠራ ነበርኩኝ ። ጥበብ በሚሉት ሰው ካገር ተሰደ ድኩኝ ። ወይኔ ድንቁርና ራሴን ብነጨው ከንፈሬን ብነከሰው እንግዲህ ማን ቀርቦን በጥበብ ያለ ሰው ። ወይኔ ድንቁርና ልቤም ደነገዘ እርጅና መጣና ወይኔ ድንቁርና የሸዋ መኳንንት ሁሉ ቢያባርረኝ አዘበና አራያ ዳዬ ተቀበለኝ ሰው ጠልቶታል ብለው ወግድ ሂድ አሉኝ ዳዩና አላማጣ ገቡቲ ሳለኝ ።

ወይኔ ድንቁርና ዳዩና አላማጣ የበና ገቡቲ ሳሉኝ አባቶቼ ትግሬና በጌምድር ሳሉኝ ወንድሞቼ ፡ ጐጃምና ወሎ ሳሉኝ አጐቶቼ ሽንቅላና ጥልጣል ሳሉኝ አሽከሮቼ ፡ የጁ ላይ አለ ሁኝ አንድ ቤት ሠሪቼ ፡

ወይኔ ድንቁርና ነጋዴ ስቀማ ወያኔ ስዋጋ ከጠላ ቤት ሂጄ ግዳይ ስፎክር አልነበረም ሌላ እንደኔ የሚያምር ፤

ወይኔ ድንቁርና ከአደን እስከ ሰናር ከጅድጋ እስከ በርበ ር ሁሉንም ገዛሁት በዋዛ ፈዛዛ ቀኑን አሳለፍኩት ፤

የኔማ ጠላቴ አቶ ጥበብ ነው ጨርሶ አባረረኝ ወዳጅ በዴ ርገው ፤

ከዚህ በኋላ ሁለቱም መልስ ተመላለሱ ።

ወይኔ አቶ ጥበብ ቢጠሩህ አትሰማ ቢጠቅሱህ አታይ ዳ ግም ከኔ ጋራ ትናገር ነወይ ፡ ወይኔ ድንቁርና በጥበብ በትም ሕርት አንተ በለጥክና ትናገረኝ ጀመርክ አፍክን ሞላህና ወ ይኔ አቶ ጥበብ ቤት እንኳን የሌለህ የምትገበበት ቁርንጮ እንኳን የለህ የምትኖርበት ፡ ደግሞ ድንቁርና ጌጥ ሁኖ ትምሕ ርት ስም አገኘሁ ብለህ ልትፎክርበት ።

ወይኔ ድንቁርና ፍቅርና ትሕትና የሚሉት ምንድር ነው ትዕቢትና ኩራት ዋናው ከኔ እንጂ ነው ወይኔ አቶ ጥበብ ደግሞ ድንቁርና ስም ሁኖ ተገኝቶ ይናገርበታል አፉን ሙሉ

ሞልቶ ወይኔ ድንቁርና ከኔ የበለጠ አለ ሳይመስለኝ፡ ለካስ ተምሮ ነው ሁሉ የሚገኝ።

ይህንን እያለ ሲመጣ ወረይሉ ሲደርስ ሴቶች እንጀራ አቀላወጡት ከቤ ላይ ሲደርስ ሌጣ በቅሎ አገኘ በሌጣዋ ቀቅምጦ ደሴ ደረሰ ከዚያ አደረና በነጋው ተከተማው ሳይገባ ላይ ላዩን አድርጎ በማርየ ወረባቡን እያየ ውጫሌ ገባ፡ ዘተ ት ሲደርስ ፫ ወያኖችና ፩ አረሆ አታሞ ይዞ አገኘ፡ ተነስተ ው እንዳይገናኙት ልብስ አልቆበተው አፈሩና ዝም አሉ። ም ነው ቢላቸው ልብስ አጥተን አሉት፡ ምነው አንችም ቆንጆ ነሽ ዘፍነሽና አመንዝረሽ አትለብሽም። እናንተስ ጉበዞች ና ችሁ ወያኔ ተዋግታችሁ ጦር ማርከችሁ አትለብሱም ብሎ የ ተሸሸገውን ምክር ነገራቸው እነሱም ከጫማው ወድቀው ሸኝ ተውት ተመለሱ፡ እሱም እንደዚህ እያለ ከወንዙ ውላ ከሚባል ደረሰ፡ ከዚያም የዛር አለቃ የደንቆሮ ቤት እንሥራ እያለ ወያኔ ሲዋጋ የዋለው እንጨቱንና ልጡን እየያዘ ሰነፎች ማረሻና መጥረቢያ እየያዙ መጡና ቤቱ ፫ ክንድ አደራሽና ፬ ክንድ አልፍኝ ሠርተው ከዚያ አገቡት እሱም ረድኤቴ አይራ ቃችሁ ይህችን ያባታችሁን ልማድ አትተው ቆሌው እንዳይጣ ላችሁ ብሎ መረቃቸው፡ እነሱም አትርሳን ብለው ከጫማው ወደቁ፡ እሱም ከዚህ በኋላ ወደዳዬ ሲሔድ ዋጃ ሲደርስ የደ ከሙ ነጋዴዎች አገኘ፡ እነሱን አሳረገና ዳዬ ደረሰ፡ ከዚያ ቡን ጦሳይ ቀመሰና ጥልጣል መዝመት ነው አለ ወዲያውም አለፈና ገባቲ ገባ ከዚያ ውሎ አድሯል እኔስ የምለው የልዑል አልጋ ወራሽ ከዚያ ከሚነበበው ከገድሉ ጸበል ቢረጩበት ፈ ጽሞ በተባረረ ይመስለኛል፡ መንገደኛም እንደልቡ በሄደ እድ ሜ ለአልጋ ወራሽ እያለ ክቡር አንባቢዎች ሆይ እኔ በመሰለ ኝ ባደረግሁት ነገር አርማችሁ ልታነቡልኝ ከጫማችሁ ወድቄ እለምናችኋለሁ።

ትንሹ ልጃችሁ ኃይሉ ገብረ ማርያም።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስዮሐንስስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፫ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፬ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
ኀሐ ጽባሕ	፭ብር
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ሩብ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ከ፫ ሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲ ብር ፫ ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ተ፫ሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ።
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፩ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፯ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፯ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲ ብር ተኩል
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፯ ብር ተሩብ
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፵፯ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፯ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፴፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፯ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፳፰ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፭ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፰ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ	፲፪ተ፲፭ ሳንቲ
አንድ ብር	፳ ሊሬ እስከ	፳ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ፲፭	ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፱ ብር	

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

የእጅ ሰዓት ዝኒት



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የሚባል ባለአንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብርሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሐ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳም ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበትለይወኪል"አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ"ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው ።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፣ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፣ ሽቱ ፣ ለስ ዮን ፣ አድኮሎኝ ፣ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፣ ኩኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፣ ከፈይ ምንጣፍ ፣ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፣ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በሙሴ ሳሙኤል ቤኄስኒልያን በየአይነቱ የሐርና የጥጥ ጨርቅ ፣ ባለ አጐበርና አጐበር የሌለው አልጋ የሚታጠፍ የመንገድ አልጋ በየዓይነቱ ፣ መሜሚያ በያይነቱ ፣ ወንበር በየዓይነቱ ፣ ብረት ሣጥን በየዓይነ ቱ ፣ ቢሲግሌት ፣ ጥቁር የሚብለጨለጭ ቀለም ለብረ ትና ለእንጨት የሚሆን ፀሐይና ዝናም የማያበላ ሸው ፣ ፋኑስ በየዓይነቱ ፣ የቡና ማቅረቢያና የምሳ መውሰጃ በየዓይነቱ ፣ የቡናና የሻይ ባለወርቅ አበባ ያጌጠ ስኒ በየዓይነቱ ። ልዩ ልዩ ዓይነት የቤትና የመንገድ ዕቃ ከዚህ ያልተጻፈ ይገኛልና የምትፈ ልጉ ሰዎች በሚገባ ዋጋ ይሸጣሉ ።

ዓለም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠ ራል ።

ኒኮላ ።

ጉድይር ግዙ



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይ ነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄ ዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢ ሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬ



ዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌ ላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌው ላስቲክ ሁሉ ሁለ ት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፰
3 me ANNÉE № 48

ሐሙስ ኅዳር ፳፩ ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 1 DeCembre 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

መርዶክዮስ የሕዝቡን ደኅንነትና የማይጠፋውን በጎ ሥራ የሠራ

ይህ ሰውዬ በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት ሥራ ላሉቱ ለእያንዳንዱም የእውነት ሰው ሊሆን ለሚወድ ምሳሌ ነው።ሁሉ በያለበት የሕዝቡን በጎ ነገር ሊፈልግ ለዚሁም በመታመን ሊሠራ እንዲገባው ።

ብዙች ግን ወደ ሥልጣኔና ወደ ሀብት ወደ ኃይልም ሲደርሱ ይበላሻሉ በተቻላቸው ኃይል ሕዝባቸውን ከመጥቀም ያን ጊዜ ይልቅ ሕዝባቸውን በአመፃ ያጠቃሉ ።መርዶክዮስ ግን ሕዝቡን በጣም ይወድ ነበርና እንዲህ ያለ መጥፎ ሥራ አልሠራም በድህነቱ ሆነ በባለጠግነቱ ዕድሜው ልክ የሕዝቡን ጠቀሜታ ያስብ ነበር ።ይልቁንም የኃይሉና የክብረቱ ዘመን በደረሰለት ጊዜ ሕይወቱን የሕዝቡን ደኅንነት በመሥራት አሳለፈው ስለዚህ በማያልፈው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ይህነንም መጽሐፍ በሚመለከቱ ሰዎች ሁሉ ደግነቱ ሲታሰብለትና ሲደነቅለት ይኖራል።እውነተኛው ክብረት እንዲህ ያለ ዓይነት ነው ራሱን ብቻ ማሰብ እኔን ይመቸኝ የሌላውን ምን ተጻዬ ብሎ ማሰብ ብርቱ ኃጢአት ነው እንዲህ ከሆነ ሰውም በጎ ነገርንና በረከት ለሰዎች አያተርፍም ።

መርዶክዮስ ድሀ ነበር ። በእግዚአብሔር ዓይን ግን ድሀ ሀብታም የሚባል ልዩነት የለም ሁሉ በፊቱ ትክክል ነው ። እግዚአብሔር የሚንቀው አንድ ነገር ብቻ ነው ።እርሱም መጥፎ አሳብና መጥፎ ሥራ ነው ። ደገኛና ንጹሕ ልብ ያለው በእግዚአብሔር ዓይን የከበረና የተወደደ ነው ። ይህ ሰውዬ በንግሥት አስቴር እርዳታ እርሱ እራሱም ለመንግሥት ባደረገው በጎ ሥራ ወደ ትልቅ ክብረት ደረሰ።ይህም የተገባ ነገር ነው ሕዝቡንና መንግሥቱን በቅንነት ሥራ የሚጠብቅ እንዲህ ያለ ሰው ብቻ ክብር በተገባው ።እንግዲህ ንጹሕንና ቅን ሥራ በጎውንም አሳብ የሞላባቸው ማናቸውንም ቢሆን ሊከበሩ ይገባቸዋል ። መርዶክዮስም ድኃ ሰው ነበር ዳሩ ግን ከመጀመሪያው ጀምሮ ደገኛ ሰው በመሆኑ ሀብታም ሰው ነበር ። በሕዝቡና በቤተ መንግሥት የታመነ ነበር ። ሰው በገንዘብ ሀብታም ከሚሆን በደግነት አሳብና ሥራ ሀብታም መሆን ይበልጠዋል ። ይህ ሰው ለመንግሥት ትልቅ ሥራ ሠርቶ ነበር ፡፡ ግን ይህ በጎ ሥራው ምንስ በመንግሥቱ መዝገብ ተጽፎ ታስቦለት ኖሮ ቢሆን ወረታውን ቶሎ አልተፈጸመለትም ።እርሱም ወረታውን እንዲመለስለትና እንዲታሰብለት በማለት አላደረገውም በዚሁ ነገርም ከንጉሡ አንዳች ነገር አገኛለሁ ብሎ አላሰበም ። ድኅነቱን ተሸክሞ ብቻ የሕዝቡን ጠቀሜታ አሰበ ። ሕዝቤ እንዳይጐዳና እንዳይጠፋ የሚል አሳብ መንፈሱን ገዝቶት ነበር።በዚያን ጊዜ ሕዝቡ (አይሁድ) በብዙ ችግር ተከበው ነበር ። ሐማን የተባለ የንጉሥ ቢትወደድ በተቆረጡ ቀኖች በትክክልነት በአይሁድ ሁሉ የሚፈጸም ብርቱ ጥፋት መክሮ አዘጋጅቶ ነበር ። ከዚህ ቀድሞ እንዲህ ያለ ክፉ ምክር በላያቸው ተመክሮ አያውቅም።መርዶክዮስም ይህን ሁሉ ስላወቀ ብርቱ ኃዘን አዘነ ዳሩ ግን በትጋትና በሃይማኖት በዚሁ ነገር ሊያደርገው የሚገባውን ምክር መከረ።የመከረውንም በጎው ነገር ለንግሥቲቱ ለአሥቴር አስታወቀ ። እርስዋም አይሁዳዊት ነበረችና የሚገባትን ሥራ ለማድረግ ታጠቀች ፡፡ ሥራው ግን ለርስዋ ጉዳት የሚያመጣባትን ነገር ነበር ግን እርስዋም ሕዝቧን ለማዳን ሕይወቷንም አሳልፋ ከመስጠት ከቶ አልደነገጠችም ። በንጉሡ ፊትም ሞገስ አገኘች ነገሩንም ተመረመረና ታወቀ የሐማን ጥል ይህ ሁሉ እንዳደረገም ተገለጠ ። በዚሁ ነገር ለህዝቡ ደህንነትና ነፃነት ሆኖላቸው ። ሐማንም መርዶክዮስን ሊያስሰቅል አይሁድንም ከምድር ፈጽሞ ሊነቅላቸው ያሰበውን በራሱ ተመለሰ ። መርዶክዮስን ይሰቀለው ዘንድ ባዘጋጀው አምሳ ክንድ በሚሆን ግንድ ተሰቅሎ ሞተ ። አሥር

ልጆቹንም ቤተ ሰዎቹንም ቃረዱ ። እንዲሁም በዚህ በሐማን ጠላትነት ከተባበረቱ ብዙ ሰዎች በአይሁድ እጅ ጠፉ ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን መርዶክዮስ የታመነ አሽከር ሆኖ ቀድሞ ለንጉሡ የሠራለትን ደግ ሥራ ወረታውን አልተፈጸመለትም ነበር ። ግን እርሱም ይፈጸምልኛል ብሎ አስቦ ባይኖር በጎ ሥራ ጠፍቶ አይቀርምና ይህ ትልቅ ሥራው የሚታሰብለት ጊዜ መጣ ደገኛው ሥራውም እንዲህ ነበር ፤ አንድ ቀን የንጉሥ የእልፍኝ አስከልካዮች ሁለት አሽከሮች ቤግታናቴርስ የተባሉ በንጉሡ ላይ እጃቸውን ያነሡ ዘንድ መክረው ነበር መርዶክዮስም የንጉሥ አሽከር ነበርና ይህን ምክር አወቀ ወዲያውም ንጉሡን አስታወቀ ። እንዲህ አድርጎ የንጉሡን ሕይወት አዳነ ዓመጸኞችንም ገለጠ ይህም ሥራ የማይረሳ ስለሆነ በመንግሥቱ መዝገብ ተጽፎ ተቀመጠ ። ይህ የመርዶክዮስም ሥራ በውነት ታላቅ ሥራ ነው ። ንጉሡ ከእግዚአብሔር የተሾመ ነበርና ንጉሡንም መጉዳት ስሙንም ማቃለል በእግዚአብሔር ላይ መነሳት ነው ፤ እንዲህ የሚያደርጉም በብርቱ ቅጣት ሊቀጡ ይገባቸዋል ። ቅዱስ ዳዊት አብኔርን የሳኦልን የዘበኞች አለቃን እንዳለው እናንተ ንጉሣችሁን ያልጠበቃችሁ ሞት እንዲገባችሁ ሕያው እግዚአብሔር ነው እንዲሁም ክርስቲያን የሆነ ሰው ሁሉ እንኳንስ ለደገኛው ላመጸኛውም ቢሆን በመታመን ሊያገለግል ይገባዋል ። ስለዚሁ መርዶክዮስ ይህን ድል ነገር ማድረግ አልወደደም የንጉሡን ሕይወት ከጥፋት አዳነ በዚሁ ነገር ስሙና በጎ ሥራው በመንግሥት መዝገብ ተጻፈለት ይኸው ጽሕፈት በራሱ የመርዶክዮስ ወረታ ሆነለት ሰሎሞን ከመልካም ሽታ መልካም ስም ይሻላልና እንዳለ ።

ከዚህ ሁሉ በኋላም መርዶክዮስ ብዙ ክብርና ኃይል አገኘ ። አንድ ሌት ንጉሡ እንቅልፍ አጣ ። የመግሥቱንም መዝገብ ያመጡለት ዘንድ ከርሱም እንዲያ ነቡለት አዘዘ ። ሲመረምርም የመርዶክዮስን ስምና ሥራ ተጽፎ አገኘ ። ሎሌዎቹንም ጠየቀ ። ለዚህ ሰው የምን ወረታ እንደ ተደረገለት ። አንዳች እንዳልተደረገለትም በወቀ ጊዜ ሐማንን አስጠራ ጠየቀውም ፤ ንጉሥ ለሚወደው ሰው ምን ነገር ይደረግለት ዘንድ ይገባል ብሎ ፡ እርሱም ንጉሥ ከኔ ይልቅ የሚወደው የለምና እኔን አስቦ ይሆናል ብሎ እንዲህ መለሰለት ፤ ንጉሥ ለሚወደው ሰው ንጉሡ የሚቀመጠው ፈረስ እንዲቀመጥ ንጉሡንም የሚለብሰውን የሐር ልብስ እንዲለብስ ንጉሡም በራሱ የሚጭነውን አክሊል እንዲጭን ይገባዋል ብሎ መለስ ። በዚያን ጊዜ ንጉሡ እንደተናገርከው ልክ ለመርዶክዮስ ፈጽምለት ብሎ አዘዘው ። ሐማንምንጉሡ እንዳዘዘው አድርጎ መርዶክዮስን በሕዝቡ ሁሉ ፊት በታላቅ ክብረት አከበረው ። እንዴህ ብሎም የንጉሡ ሁለተኛ ለመሆን ደረሰ ። የመርዶክዮስም ታሪክ እጅግ የሚደምቅበት ከተሾመ ወዲህ ነው ። በዚህ ባገኘው ኃይልና ክብር በፍጹም ልቡ ለሕዝቡ የሚበጀውን ሥራ ሠራ። ስለዚህ የአስቴር መጽሐፍ በጉነቱን በማመስገንና በማስተዋስ ይጨርሳል ። የኢትዮጵያ ሕዝብም ይህን ሰውየ በበጎ ሥራውና በደግነቱ እብነት ሊያደርገው አይሻምን?ሰው በጎ ሥራን ሕዝቡን የሚበጀውን ነገር ሊያደርግ አይደለምን የሚኖር ? በበጎ ሥራና በደገኛ አሳብ ሕይወቱን የማያሳልፍ ሕይወቱንና ስሙን ያስነውራል ። እንደዚህያለ ንጹሕ አሳብ ሊገዛን ልባችንን እንክፈት ።

አቶ ተማኑ ሮምሃ ለጻፈው ቃል መልስ

ግሩም ድንቅ እኮ ነው በሰው ልጅ ላይ ያለ የሀሳብ ጦርነት ብስጭት ያለ መማርን ያስመኛል ።

ሰው በተማረው እውቀቱ ለመንግሥትና ለሐገሩ ወይም ለራሱ ካልሰራበት የተማረው እውቀት የበጋ አዝመራና የድንጋይ ቡቃያ ሆነበት ማለት ይቻላል ።

ከዚህም ወዲያ ወደአቶ ተማኑ ሮምሃ ጥያቄ እንመለስ በ፵፭ኛው ቁጥር በ፴ ጥቅምት በ፲፱፻፶፰ኛው ገጽ የሐገሩና የሕዝቡ ጉዳት አሳዝኖት ጠያቂው እርሳሱን አንስቶ እንዲህ ሲል ጥየቃውን አቀረበ ።

በሐገራችን ብዙ ዓይነት እህል ነቀዝ በልቶት ሲፈስ ከሀንድ አስያ የስንዴ ዶቄት መፈለጉ ምን ይሆን ስላለ ዛፍ ሁሉ ፍሬውን ይሰጣልና እኔም የታየኝን ለጠያቂው እመልስለት ዘንድ እወዳለሁኝ ። ጠያቂ ሆይ መቸም ሰው የሐገሩንና ያደገበትን ምግብ ለማግኘት ሕሊናውና ሕዋሳቶቹ ሁሉ አጥብቀው ይናፍቃሉና ። ስለዚህ የኤውሮፓውያን ሰዎች በሐገራችን በኢትዮጵያ ላይ በስደት ስለመጡም የመርከቡና የባቡሩም መንገድ ስለተመቻቸው ዶቄትንና ሌላውንም ጣፋጭን ሁሉ ከሐገራቸው ያስመጣሉ ። ከዚሁም ምግብጋር የሐገራችን ሰዎች በስልጣኔ ደረጃና እርምጃ ላይ የደረሱት በቤታቸውና በሆቴልም ከምግቡጋር ስለተላመዱ ፈላጊዎችም የሚበዙ አይመስሉም ። እንደዚሁም ለምሳሌ በግምት በኢትዮጵያ ውስጥ ዘመትር ፈላጊዎቹ ከ፳ሚሊዮን ሕዝብ ውስጥ ፩፻ሺ ሰው ስንኳን ይገኛል ተብሎ አይታሰብም ። ይኸውም የሀንድ ነጭ ስንዴ የሐገራችን ቡቃያ ስላይደለ በመርከብና በባቡር ተመላላሽ ነውና የኖሉና የቀረጡ እስታትስቲኩ ለነጋዴው ስለሚበዛበት በርከሽ ለመሸጥ የገንዘቡ ጉድለት ዋጋውን ውድ ለማድረግ ልቡናው ይነቃቃበታል ማለት ነው ።

፪ኛም ህዝባችንስ እህሉን የሚሸምትለት አጥቶ ክብር ማጣት የተነሳ ድህነት አጥቅቶት እያየነው አ፻ድ ፳ንያ ዶቄት በ፳፰ብር እየገዛን መብላታችን ብልሀቱ ምንድርነው ስላለ በመጀመሪያ እንዳልነው የነጭን ዱቄት ፈላጊዎቹ አብዛኙ ባዲስ አበባ ብቻ ስለሆነ ነው እንጂ ባገርቤትና አገር ያለው ሕዝባችን ምግብነቱን ስንኳን አይመኘው፤ የበላገሩም እህል የሚረክስበት ምክንያትበየዳር አገራችን በየትልልቁ ከተማችን ውስጥ የባቡር አለመግባትና ለነጋዴና ለአውቶመቢል መንገድ ያለ መበጀት ደግሞም ለፈላጊዎቹ የእህልን ኮንትራት ያለመፍቀድ ስለሆነ የሐገራችን ገበሬዎች ለፍቶ እንዳልደከመ ይሆናሉ ። ጠያቂው የእህልን ኮንትራት ስለምንለውጭ አገር ሰው እንፈቅዳለን ቢለኝ ስንኳን መሬታችን በእጃችን ሆነች እንጂ የምድራችንን ፍሬ በንግድ ከኤውሮፓውያኖችጋር እየተከፋፈልን ፋብሪካና ጥቅማችንን የሚሰጠንን ልዩ ልዩ ዓይነቶች ሁሉ ብንአስመጣበት እንዳይጐዳን አዋቂዎች ሁሉ ይዘነጉታል ተብሎ አይነገርም

፫ኛም ቅርቡን ሩቅ ብዙውን ጥቂች አስመስሎ የሚታየን ስረ ነገሩ ምንይሆን ኢትዮጵያስ በዚህ ነገር ራስዋን ትችላለችን

ወይም አትችልምን ራስዋን ለመቻልስ ምን ማድረግ ያስፈልጋታል ስላለ ቅርቡን እሩቅ የሚአስመስል ስንፍናና የልብ ኩራት ነው ። ብዙውንም ጥቂት የሚአስመስለው የገበሬ ብዛትና የነጋዴ ማነስ ደግሞም በላገር ለሀሉን እስተማ ለማምጫ በቡርና አውቶመቢል ማጣት ሳይሆን አይቀርም ።

፩ኛም ኢትዮጵያስ በዚህ አገር እራስዋን ትችላለችን ወይም አትችልምን እራስዋን ለመቻልስ ምን ማድረግ ያስፈልጋታል ስላለ የዛሬውን የኢትዮጵያን ፈተናዋን በየአውራጃዋ ያሉት ሹማምንቶችዋ ሁሉ ባንድ ልብ ሆነው ከላሽቫሉላችና የብርሃን ፋኖሳቸውን እየተከሉ በየወረዳቸውን የትምህርት ቤት ከላቆሙላት እንዲያው ባፈጣኤ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ቃል ገብቶላታል እያልንና የልዑል ተፈሪ መኰንን ድካም ብቻ ብንመለከት ያንድ እጅ ጭብጨባ ያንድ ዓይን ፍጥጫ ያንድ እግር እሩጫ መሆኑን ይታጣልን አይታጣም ።

እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ቃልን ብቻ አልሰጠም እውቀትንም ጨምሮ ነው እንጂ ። ወዮላቸው በእናታቸው በሐገራቸው ለሚለግሙት ሰዎች የዚህን ጉዳት ስንኳን ዓይነ ስውርና ልበ ዕውርም ቢሆን የሚዘነጋው አይመስልም ። ለምሳሌው እንድ ተረት አለ ፬ሴቶች ባንድ ቤት ዳኛ ነበሩ ፩ኛይቱ ባላንድ ጡጉር ፪ኛይቱም ባላንድ ዓይን ፫ኛይቱም ባላንድ ጥርስ ፬ኛይቱም ባላንድ ጣት ነበሩናከመኝታቸው ጡዋት ሲነሱ ባላንድ ጠጉር እስኪ ልነሳናትፈርዬን አበጥሬ ጕረቤቶቼን ልጠይቅ አለች ፪ኛይቱም ባላንድ ዓይንም ከቶአንቺ የደላሽ ነሽ እኔስ ዓይኔን ልኳልና እገብያ ልውጣ አለች።ባላንድ ጣትም ከቶ እንደናንተ የተመቸው የለም ያሰርኩትን እንሶስላዬን ልፍታና ቤታችንን ልጥረግ አለች ፬ኛይቱም ባላንድ ጥርስ የሁሉንም ነገር ልብ አድርጋ ተመልክታ ኖሮ ። እህህ እህህ እህህ ጥርሴን ተነቅሻለሁና እባካችሁ አታስቁኝ አለች ይባላል ። ክቡር አንባቢ ሆይ በነኝህ ሴቶች ላይ አንዳንድ ጉድለት መገኘቱ ምን ይመስልሀል ።ያለ አካል ጌጥ መፈለግ አያስደንቅምን ። ለወንድ ልጅስ ያለ ትምሕርት ድንቁርና አያስጐዳውምን ። በጣም ያስገርማል ።

ስለሆነም ይህንን ቃል እኔም መጻፌ የሚአኩራ ትምህርት አለኝ ብዬ አይደለምና በቶ ተማኑ ሮምሃ ላይ ያስቸገረው ሐሳብ እኔንም ቀንም አላስበላም ሌትም አላስተኛም ስላለኝ ነው እንጂ ።

ይህንን መልስ ለመስጠት አያስገድደኝም ነበር ። ለእንደ ዚህም ላለው ነገር መልስ መስጠት የሚገባቸው ለከተማው ከንቲባና የእርሻ ምኒስቴር ስራ ስለሆነ እኔ ያለስራዬ ስለገባሁና ክፉ ሐሳብ ለሚመስላቸው ይቅርታን እለምናለሁ ።

ደነቀ ተክለ ጊዮርጊስ ።

ስለ ባለ ጸጎች ።

ወተገሠፁ ኵልክሙ እለ ትኄንንዋ ለምድር መዝ ፪ ፲ ፊታውራሪ ዴሬሳ የክቡር ራስ ናደውን በግዛታቸው ውስጥ የተማሪ ቤት ማቆማቸውን በብርሃንና ሰላም ስለ አመሰገኑ ብዙ ሰው ደስ ሳይለው አይቀርም ። ለርሳቸውም ለዘላለም መታሰቢያቸው ሁኖ ስማቸው ሲጠራ ይኖራል ። እንደ እርሳቸውም በየግዛቱ ውስጥ የተማሪ ቤት የሚያቆም ለገባርም ሌላ ደግ ሥርዓትና ደንብ የሚያወጣ ሰው ቢገኝ የሰማ ሰው እንደዚሁ ሁሉ በብርሃንና ሰላም ቢያስታውቀን በብዙ ደስ ይለናል ። ገንዘብን በዚህ ዓለም አከማችቶ ለማንም ላልደከመበት ትቶ ከመሄድ ወደዘለዓለም መኖሪያ አስቀድመውት መሄድ መልካም ነገር ነው ። ገንዘብም በዚህ ዓለም አከማችተው ትተው የሚሄዱትን ባለጸጎች መጻሕፍት ተባብረው ይመክሯቸዋል ። አሁንም ሂዱ እናንተ ባለጸጎች አልቅሱ ዋይም በሉ በሚመጣባችሁ መከራ ። ባለጠግነታችሁ ጠፍቷልና ልብሳችሁንም ብል በልቶታልና ወርቃችሁና ብራችሁ ዛገ ዝገቱም ምስክር ይሆንባችኋል ሥጋችሁንም ይበላዋል እንደ እሳት ለኋለኛውም ቀን አከማቻችሁት ። ያዕቆ ፭ ፩ ። እናንተ ባለጸጎች ወዮላችሁ ደስታችሁን በምድር ጨርሳችኋልና ብራችሁንና ወርቃችሁ በእግዚአብሔር ቁጣ ቀን ሊያድናችሁ አይችልም ሰፎንያስ ፩ ፲፰ ። ወዮለት በክፉ ንፍገት ለቤቱ የሚሰበስብ ባለጠግነቱን ከሁሉ በላይ ያደርግ ዘንድ ከክፉ ነገር ይድን ዘንድ ብሎ ። ዕንባቆም ፪ ፱ ገንዘብን የሚወዱና የሚያከማቹ ሰዎች የዲያብሎስ ባሮች ይባላሉ እንጂ የእግዚአብሔር ባሮች አይባሉም ወግሪስ ፲፫ አንድ ባሯ ለሁለት ጌቶች መገዛት አይቻለውም ወይም አንዱን ይወዳል አንዱንም ይጠላል ወይም አንዱን ያከብራል ሁለተኛውንም ይንቃል ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ ትገዙ ዘንድ አትችሉም ማቴ፮ ፳፬ ። ፩ ነገ ፲፰ ፳፩ ። ሉቃ ፲፯ ፲፫ ። ገንዘብን አግኝቶ አለመስጠት እኔ ያገኘሁትን ሌላው ሰው ለምን ያገኘው ብሎ ማከማቸት ምቀኝነት ነው አፈወርቅ ተግሣጽ ።

ያከማቻሉ የሚሰበስቡትም ለማን እንደሆነ አያውቁትም መዝ ፴፱ ፯ ። የዚህም ዓለም ባለጠግነት በክፉ ሥራ ትጠፋለች ልጅም ቢወልዱ በጁ እንዳች የለውም ከናቱ ሆድ ራቁቱን እንደወጣ ይሄድ ዘንድ እንዲሁ ይመለሳል ከደከመበትና ከሰበሰበው ገንዘብ አንዳች ይዞ አይሄድም መክ ፭ ፲፬ ሰው በዚህ ዓለም ባለጸጋ ቢሆን ዓለሙን ሁሉን ቢገዛ በገንዘቡም ብዛት ደስ ቢለው በነፍሱ ገሃነመ እሳት ገብቶ ከተጎዳ ምንድነው ትርፉ ። ሉቃ ፱ ፳፭

ብርና ወርቅን ማናቸውንም ገንዘብ ሁሉ አከማችቶት በቁመናው እንዳይሰጥ ሰቶ ለልጆቹና ለዘመዶቹ ይሁን ብሎ ትቶት ቢሞት ልጅና ዘመድ ተከፋፍለው እንደፈቃዳቸው ቢያደርጉት ለዚያ ለሞተው ሰው ምንድነው ጥቅሙ በቁመናው ከሰጠው በቀር በተቸገሩ ሰዎች ምሳሌ ሆኖ ኢየሱስ ክርስቶስም በምጽአት ቀን እንዲህ ብሎ ይወቅሳቸዋል ።

ትምህርት እንጀራን ተርቤ ነበር አላሰተማራችሁኝም ተጠምቼ ነበር አላጠጣችሁኝም ከአምልኮተ እግዚአብሔር ስደተኛ ነበርኩ አስተምራችሁ አልመለሳችሁኝም ።

ከትምሕርት ታርዤ ነበር ትምሕርት ልብስን አላለበሳችሁኝም ። ታመምኩ አልጐበኛችሁኝም ታስሬ ነበር አልጠየቃችሁኝም ማቴ ፲፭፴፭ በፍቅረ ንዋይ የተጐዱ ብዙ ናቸውና ገንዘብን አጥብቃችሁ አትውደዱ። የሰው ጌጡ ቸርነቱ ነው ምሳ ፲፱ ፳፪ ትምሕርት አጥተው ለታወሩ ሰዎች ዓይን ዕውቀትን ለመግለጥ ተረዳዱ ተፉጠኑ ።

በዚህ ዓለም ኑሮ አገር የገዛችሁ በዚህ ዓለም ተድላ በወርቅ ያጌጣችሁ ስጡ ብሎ ነበር አምላክ የሰጣችሁ ትታችሁ ስትሄዱ ከመሬት ቀብራችሁ ዓመፀኛው ገንዘብ አይከተላችሁ ሉቃ ፲፮፻ በብዙ አልቅሱ ዋይ ዋይ እያላችሁ ለነፍስ መከራ ነው ትኩነናላችሁ ። ሥጋ የለበሰ ማነ ሲቀር አያችሁ ። ላምላክም አልቀረ ያው እንደ ሰማችሁ ማቴ ፳፯ ፶ ቶሎ ተመለሱ ወደፈጣሪያችሁ ። ጾም ጸሎት አድርጉ ልብን አትግታችሁ ሉቃ ፳፲፯ እንዳ ርቅ እንዳሸሽ ሰይጣን ጠላታችሁ ። እንዳትኰንኑ ገሃነም ገብታችሁ ።

እርስት ቢበዛ በያገሩም ቤት ቤዛ አይሆነውም የከብት ብዛት የቀበረውም ወርቅ የብሩ ዝገት ምስክር ይሆናል ለነፍሱ ጉዳት ሲኦል ያወርደዋል መቀመቅ ዓዘቅት ።

ቁም ጸሐፊ ገብረ ጻድቅ ።

የ፫፻፹፩ ገጽ ተከታይ

ስለሚታለቡ ላሞች ።

የሚታለቡ ላሞች ሁሉ በመንግሥት ሳይመረመሩ ተሽጠው አይታለቡም ።

የሚመረመሩትም ዋነኛው ነገር ስለ ቲውበረክሎስስ ስለምታስለው በሽታ ነው ፤ ይኸ፤ን በሽታ ለመመርመር እጅግ የሚያስቸግር አይደለም ። አመራመሩም እንደሚከተለው ነው ።

የከብት ሐኪም ይኸነን ቲውበረክሎስስ የምታስነሳውን የበሽታ ትል አሰናድቶ ይመጣና በላሚቱ ጭራ ውስጥ ይቀብርባታል ። በዚች በእንስሳ ውስጥ ይህ በሽታ ተፈጥሮባት እንደሆነ ይህን መድኃኒት በተከተበችበት በ፫ኛው ቀን ያች የተከተበችባት የጭራዋ ጫፍ የአውራ ጣት የምታህል እንደ እጢ የሆነች እበጭ አብጦባት ይገኛል ። ግን እንስሳይቱ ከዚህ ከሳል በሽታ ነጻ እ፤ደሆነች ምንም ምልክት አትሰጥም። ስለዚህ በደህናነቷ ተመስክሮላት ታልፍና በገበያ ቄማ ተሽጣ እየታለበች ወተቷን ሕዝብ እንዲመገበው ያደርጓታ፤ ። በሽታው የተገኘባት እንደሆነ ግን ዋጋዋን እንደሚገባ መንግሥት ለድሃው ይከፍልና እንድትታረድ ወደ ማረጃ ቤት ትላካለች ። ከታረደችም በኋላ ሥጋዋን የከብት ሐኪሞች እየመረመሩ የተበላሸ የተበላሸውን ተበላሽቷል እያሉ እየቆረጡ ለዕቃ ቅባት ዘይት ወደሚበጅበት መኪና ለሚወስዱት ይጥሉላቸዋል ። በሽታው የቆየ ሁኖ ሥጋው በመላ ተበላሽቶ ያገኙት እንደሆን በመላ የላሚቱን ሥጋ እንዳይበላ ከልክለው ወደ መኪናዎቹ ሠራተኞች ለዕቃ ዘይት እንዲያወጡት ይጥሉላቸዋል ።

እንባቢዎች ሆይ ፤ ይህ ሁሉ ሐተታ ይህ ሁሉ ልፋት መንግሥት መልፋቱ የሕዝቡን ሕይወት ለመጠበቅ ነው እንጂ ሌላ የንግድ ትርፍ አግኝቶበት አይደለም ። ስለዚህ ሕዝቡ እየበረከተ መንግሥቱም ኃይል እየጨመረ ይሄዳል ።

ከቶ ሕልሜ እየሰፋና እየተባዛ ስለሚሄድ አብረውኝ የሚያልሙትና አብረውኝ ለሕዝብ ሕይወት የሚያስቡ ተማሪዎች ብዙ ስላልመሰሉኝ አጥብቄ አዝናለሁ እንጂ ይህነን ከዚህ በላይ በዓይኖቼ አይቼ የጻፍኩላችሁን ሁሉ እስከ አሥር ዓመት በሀገራችን እንድንሠራው አምናለሁኝ ። ግን ዛሬ ወደ ውጪ አገር ከተላኩት ተማሪዎች ብዙዎቹ ሐኪሞችና የከብት ሐኪሞች እንዲሆኑ በጣም እጓጓለሁና አገራቸውን በውነት ለማገልገል ለሚመኙ ሕፃናት የቀለም ጓደኞቼ የመረጡትና የተመረጠላቸው ሥራ የሌላቸው ሁሉ የሕክምናንና የከብት ሐኪምነት አጥብቆ አስፈላጊ መሆኑን እየመረመሩ እነኝህን ትምሕርቶች ብዙዎቹ እንዲማሩ አጥብቄ እመኛለሁ ። እንባቢዎች ሆይ ፤ ሕይወት ክብረት መሆኑን ሳትረሱ አብራችሁኝ እንድትሰጉበት እለምናችኋለሁ ።

ስለ ተከፈተልን የከብት ሐኪም ቤት የርዳታ ማስታወሻ ።

ከዚህ በላይ የዚህን የሥራ ነገር ባይኔ አይቼ ሳልመረምር በመስማት ካገኘሁት እውቀት ጽፌ ነበር ። አሁን ግን ደግሞ የተረጋገጠ አሳቤን ስለዚህ ሥራ ልሰጥ እደፍራለሁ ። አስቀድሜ እንደጻፍኩት ይህ የከብት ሐኪም ቤት እንዲያው የታመሙ የሚመጡትን ብቻ በማከም የሚሰጠውን አገልግሎት አይበቃምና በየወረዳው እየዞሩ ከብቱን ከበረቱ እየመረመሩ የታመመ የታመመውን ከደህኖቹ መካከል እያስወጡ ወደ ሐኪም ቤት ቢልኩት ጥቅሙ ታላቅ ይሆናል ። ይህ ላንባቢዎች ቀላል መስሎ ይታይ ይሆናል እንጂ ጥቅሙ መጠን የለውም ።

በየወረዳው የሚታለቡትንም ላሞች ሁሉ የመንግሥት ሐኪም እየዞረ ቲውበረክሎስስ (የሳል በሽታ) ያላቸውን እየመረጠ በመንግሥት ሥጉያ እንዲታረዱና ሥጋቸው እየተመረመረ ተበላሽቶም እንደሆን እንዲወድቅ እንዲያደርግ ያስፈልጋል አሁን እኔ ስንቱን ጽፌ ለማመልከት እችላለሁ ? ጊዜዬ የተወሰነ ነው ። ሐኪሞቹን እንደሚገባ እንዲሠሩ ስልጣን ሰጥቶ ቢያዟቸው ይህነን የጻፍኩትንና ያልጻፍኩትንም ሁሉ ያውቁታል ።

ስለ ከብት ገበያና ሥጉያ ።

የከብት ገበያ በከተማ መካከል መሆኑ ለከተማው ሕዝብ ሕይወት እጅግ መልካም አይደለም ። እኔ የአሳቤን ብቻ ከመናገር ይልቅ እዚህ ባይኔ የማየውን ብጽፍ ላንባቢዎች ደስ ያሰኝና አሳብ በልባቸው ይፈጥር ይሆናል ። ስለዚህ ከዚህ ቀጥዬ ባይኔ የማየውን እጽፋለሁ ።

ከብት የሚሸጥበት ገበያ የተሰናዳው ነጋዴዎች ኩባንዮች ነው እንጂ መንግሥት አልታከተበትም ። ኩባንዮቹ አርባ አምሳ ከብት የሚችሉ በረቶች በብዙው አሰርተዋል ። በረቱም መሬቱ በሸክላ ተነጥፎ እንዳይጨቀይ ተበጅቷል ። በበረቱ ውስጥም በሁለት ሶስት ገንዳዎች ውስጥ እየመላ ወደ ውጪ የሚፈስ ጥሩ ውሀ በቧንቧ ይንቆረቆራል ። ባለከብቶችም በመጡ ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው እየተከራዩ ከብታቸውን ያገባሉ ። ለበጎች ለብቻቸው እንደዳስ እየተሠራ በረት አላቸው ። ያሳሞችም በረት ለብቻው የቀንድ ከብቶችም ለብቻው ነው ።

ላሳማዎች ሲያከራዩ ባለከብቶቹን አስራ ሁለት መሐለቅ በጭራ ያስከፍሏቸዋል ። ለበጎች ስምንት መሐለቅ በጭራ ያስ

ክፍሏቸዋል ። ለላሞች ሀያ አምስት መሐለቅ በጭራ ያስከፍሏ
ቸዋል ። ባለከብቶቹ አንድ ጊዜ ከተከራዩ እፈቀዳቸው ቀን
ድረስ ለማቆየት ይችላሉ ። ማለት ላንድ ጊዜ ገበያ ወሰን የለ
ባቸውም ።

ባለከብቶቹም ለእንስሶቹ ምግብ እየጫኑ እየመጡ በከብት
ገበያ ሁለት ሶስት ሳምንት እየሰነበቱ ሸጠው ሲጨርሱ ወደ
አገራቸው ይመለሳሉ ።

እንደዚህ ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው የአገራችን
ሰዎች ኩባንያ እየቆሙ እንዲህ ያለ ገበያ እንዲያዘጋጁ መንግ
ሥት ቢያመለክታቸውና ቢረዳቸው ለሕዝብም ጥቅም ለገበሬም
(ለባለ ከብት) እርዳታ ይሆናል ለኩባንዮቹም መክበሪያ ይሆናል
ይህ ሁሉ ሲሆን የመንግሥታችን ኃይል እንዲበረታ ይረዳናል ።

አንባቢዎች ሆይ ሕልማችንን እውነት እያደረገ ተማሪዎች
ሁሉ የምናልመውን ጥቅም ለመሥራት ረዳቶች ለመሆን
እንዲያበቃን ወደ ኢትዮጵያ አምላክ መጸለይ አትዘንጉ ።

ስለ ታላቁ በሽታ ማስታወሻ ።

ብዙ አጥብቆ የሚያሳዝነን ነገር በአገራችን ያለ ወደፊት
የሚታሰብበት ብዙ ሳለ በኢትዮጵያ ያሉ የቆማጦች እናንዋር
ይልቅ አጥብቆ ያሳዝነናል።እያደረም በትምህርት እያደግን የበሽ
ታውን ምስጢር ሳንመለከተው ከቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈጽሞ
በዚህ በሽታ ሳይታመም በመኖሩ እግዚአብሔርን እናመሰግና
ለን ።

አንባቢዎች ሆይ፤በዚህ ነገር አስቀድሜ ያሰብኩበት እኔ
መስያችሁ እንዳትገረሙ ልዑል የኢትዮጵያ ብርሃን ተፈሪ መኰ
ንን ከብዙ ዘመን አስቀድመው እንደ ተጨነቁበትና እንዳሰቡበት
አውቃለሁና አሳቡ የልዑላችን መሆኑን አንርሳ ። የአሳባቸው
ንም አበረታት የሚያስረዳን ባሜሪካ « ቻሊ ሙግሬ » የሚባል
ዛፍ የቁምጥና መድኃኒት የሆነ መገኘቱን ቢሰሙ ወደ አሜ
ሪካ የርሻ ሚንስቴር ልከው ብዙ የዚህን የዛፍ ችግኝ ወደ
ኢትዮጵያ መጥቶ እንዲተከል አድርገው ነበር።ግን የተተከሉት
ችግኞች ይጽደቁ አይጽደቁ ፍጻሜውን አልሰማሁም ። ሆነም
አልሆነም የልዑላችንን አሳብ ይገለጻል ።

ወትሮ በአገራችን እንደሚባለው ቁምጥና በዘር የሚጋባ በሽ
ታ ነው ይባል ነበር ። በዚህ ዘመን ግን የመድኃኒት ሊቃውን
ቶች ቁምጥና በዘር አለመጋባቱን አውቀው በፍጹም አስመስክ
ረዋል ። አንድ አንድ ሰዎች መከራከር ይወዳሉና ። ባይናችን እያ
የን መች ነጋሪ እንፈልጋለን የገሌ አያት ቆማጣ ነበር አባቱም
ዛሬም እርሱም ቆማጣ ነው ይሉ ይሆናል ። ስለዚህ በጣም አሳ
ጥሬ ቅን በሆነ ቋንቋ ላንባቢዎች እንዲገባ በሚከተሉት መስመ
ሮች ላስረዳ እሞክራለሁ ።

ቁምጥና በትል የሚጋባ በሽታ ነው። እጅግ አድርጋ ላይን
የረቀቀች ትል በደም በገባችጊዜ በገባችበት ደም እየዋኘች ትረ
ባለች ከጥቂት ዘመንም በኋላ ትሎቹ ሲበዙ እያሳከኩ ስጋውን
ይቆርጡታል ።

አንድ ቆማጣ ሲሄድ ደሙ በንጨት በዘንግ ወይም በመ
ሬት የፈሰሰ እንደሆን አንድ ሰው በጁ ወይም በግሩ ወይም በማ
ናቸውም ገላው ቢሆን ትንሽ ቁስል ኑሮት በዚያ በቁስሉ ያች
ደም የፈሰሰችበትን ቦታ የነካው እንደሆን እነዚያን የቁምጥና
ትሎች ይዘግንና በዚያ ትንሽ በቆሰለችው ሰውነቱ ምድራፍነት
የዘለዓለም መጥፊያውን ጠረኞች ጠላቶቹን ያስገባል !

እንግዲህ ይህ ሰው እነኝህ ትሎች በሰውነቱ መግባታቸው
ን አያውቅምና በሽታውም እስከ ብዙ ዘመን ድረስ አይሰማው
ምና ፈጽሞ መበላሸቱ እስኪገለጽበት ድረስ እየተታለለ ደህና
መስሎ ይኖራል ።

መልአኩ በያን ።

ከዚህየቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ስለኢትዮጵያ የስልጣኔ አካሄድ

ቀድሞ በኢትዮጵያ ብር አልነበረምና ሸማ ፍሪዳ ፤ ፈረስ
በቅሎ የሚገዛበት አሞሌ ጨውና ማረሻ ነበር ። የምሥራቁን
አገር እስላም በሸማ ክርስቲያኑን በማር ፤ በጨው ፤ በማረሻ
በጠገራ በዝተት በከብቱ አገር በፍሪዳ ፈረስ በሚያረባው አ
ገር በፈረስ ግንደ በሉን ዳውላ ዶሮ በጦም ቆሎ በዚያ ዘመን
በነበረው ለትዳራቸው እንዲመች ተከለውት ኖረ ።

ይህ ላሁኑ ዘመንለገዢውም ለተገዢውም ያልተመቸ ነው
ግብሩ በብር ቢሆንለት መልከም ይመስለኛል ። አሥራት አየ
ለቀቅም የጉልበት ሥራ ይቅርለት ግንደበሉ ዳውላውን ዶሮ
ውን የጦም ቆሎውን ሰጥቶ አጋሠሥ ይቀልባል ቢከሳበት ከአ
ስር እስከሐያ ብር ይሰጣል ። አጋሠሥ ስቦ ተራዳ ቀንድ ተሸ
ክሞ ይዘምታል አዲስ አበባ ድረስ መጥቶ ድርቆሽ ያጭዳል
እስር ይጠብቃል ። ቢያመልጠው የነፍስ ዋጋ ዳኝነት ይከፍላል
ገባሩ ማሩን ክፍሎ ኩዳድ ሲሶ ያርሣል ። ጕተራ ቤት ይሠራል
ድርቆሽ ያጭዳል ይፈጫል እንጨት ጭኖ ተሸክሞ ያገባል ዱ
ቄት ጭኖ ይዘምታል ፈረስ ፤ በቅሎ ፤ ምሪት ይጠብቃል የወ
ታደሩንም የለጓሚውንም የቋሚውንም ይሠራል ማለት ነው ።
ይህ ሁሉ እያደረ የተጨመረ ይመስላል እንጅ ቀድሞ እንዲበ
ያደረጉት አይመስልም ። አሁን ከዚህ ሁሉ መከራው ቀለል
አድርጎ ፤ በዓመት ሠላሣ ብር ቢሆንለት ይሻለዋል ። በየዕለቱ
መምጣቱን ትቶ እርፎ ከቤቱ ከዋለ ተግቶ ያርሳል እህል ይበ
ዛል ፤ አገርም ይለማል ።

መንግሥትም የደሐውን ጉልበት ከለቀቀ ሁሉ ጊዜ ግብር
ማብላቱን በግድ ይተዋል ። በዓመት ሶስት ጊዜ ይበታል ቀድሞ
ፍሪዳው ተዘርፎም ይመጣል ፤ ይመለመልማል ዋጋውም ሁለት
ብር ነው ። በየዳር አገሩም ሰንጋውም ማሩም እንደጕርፍ ይ
መጣል ። የማሩም ዋጋ ጕንዶው ሁለት ብር ነበር ዛሬ ማርና ፍ
ሪዳ ዋጋው የትና የት ነው ። ለደጋፊ ድካሙ ከግሬው ብዙ
ነው ። ማታ ከቤቱ ሂዶ መብላቱን አይተወውም አንድ ቀን ካ
ላሳደረ ለዚህ ምን ያደክማል ። የባላገር ጉልበቱ ከርሻው ላይ
ካልሆነ የመሬቱ ግብር በብር ካልሆነ መንግሥት ሁለ ግዜ
ግብር ማብላቱን ካልተወ ምንም መሠልጠን የለም በዚህ
በሥራ ምክንያት ሹምና ባላገር ዘወትር ተጣልተው ነው የሚ
ኖሩ ሳትመጣ ቀርተሃል አምሽተሃል አርፍደሃል ዋስ ጥራ አዳፋኝ
አምጣ ይለዋል ያስጨንቀዋል ዋሱን ያግትበታል አቤቱታ ይ

ሄዳል ዳኛውን ያጣዋል በዚህ ሲወጣ ሲወርድ ብዙ ሥራ ይፈታል ። ግብሩ በብር የሆነለት እንደሆነ ዋናው የሥልጣኔ መጀመሪያ ይህ ነው ሕዝቡን በተከከለ ደምብ አስማምቶ ማሳደር ግብሩ ሥራውን ፈትቶ አህያውን ጭኖ እንጨቱን ተሸክሞ መንግሥት በውድ ማር ፍሪዳ ገዝቶ በየሳምንቱ በድግሥ ለፍቶ መኖሩ ጥቅም የሌለው የልማድ ሥራ ነው ።

አሁን መንግሥት ኢትዮጵያን ለማልማት ለማሰልጠን ሕዝቧን ለማበርታት ነፃነቷን ለማጥናት ነውና አሳቡ ገንዘብ ማባከን አይገባውም ። አሁንስ የታሰበውን ሥራ መጀመር ነው ። እግዚአብሔር ያከናውነዋል ። መሐንድሱም መኪናውም ይምጣ አቡጀዲዱም ጥይቱም ይሥራ ወርቁም ብሩም ነሐሱም ብረቱም የድንጊያ ከሰሉም በመሬት ያለው ገንዘባችን ይውጣ እንየውደስ ይበለን ። ባውሮጳም በዚህም ከትምሕርት ቤት ካሉት ልጆቻችን እንምረጥላቸው እንግዲህ ሥራ አያስፈቱም የመሥሪያውን መዝገብ ካነበቡ ከመሐንድሱ ጋራ ከዋሉ አይቸግራቸውም ። አሁንስ ልዑል ሥራ በዝቶባቸዋልና በሥራውም ላይ የተሾሙት ምኒስትሮች እየተዋዋሉ መኪናውን ያስመጡ መንግሥትም ገንዘብ ሞልቶታል ነገር ግን አንድ ዓመት እጁን ሰብሰብ ያድርግ ። መንግሥቱ ደህና ይሁን እንጂ የሚከፍለው እያጣም ብዙ ሥራ ያሰበ መንግሥት ካላወቀበት የሚረዳው አልተገኘም ። ወንድሞቼ እስታሁን በብርሃና ሰላም ብልሆች የጻፉትን በየው አንድ ሁነን ተፋቅረን ሠልጥነን አገራችንን እናልማት እንጠብቃት ነው እንፋቀር እንሰልጥን ማለት ባላገሩንና ወታደሩን የሚያስማማ ደምብ ነው ስል መጀመሬ በብርሃንና ሰላም ያየኋችሁን ብልሆች ተማምኜ ነው አውጥታችሁ አውርዳችሁ ከልክ እንድታደርሱት እናንተንተሰፋ አድርጌ ነውና በጣም ብትፈትሹት ደስ ይለኛል ።

ሕዝቡ ይህን አውጥቶ አውርዶ ይልመደው እንጂ የበላተኛው ነገር አይቸግርም ስሜንም ያለመጻፌ መቼም የሚያውቀኝ የለም ስል ነው ።

ኀዘን

የክብርት ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ እያት ወይዘሮ ነግሂቱ በተወለዱ ፸፰ ዘመናቸው ኅዳር ፲፮ ቀን ዓረፉ ።

ብርሃንና ሰላም ለክብርት ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅና ለዘመዶቻቸው እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚገኙ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፫ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጤ	፩ሩብ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ከ፫ሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር ተኩል
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፰ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፰ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፯ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ከረጂ	፱ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጂ	፲፰ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ከረጂ	፻፵፫ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፰ ብር
፡፡ ባለ ድመት ፡፡		፻፷፰ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፯ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፷፫ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፫ ብር ።
ሱከር	፩ ጁኒያ	፳፯ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ	፲፪ተ፲፰ ሳንቲ
አንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ	፰ ሳንቲም
ባንድ ጊኒ	፲ ብር ከ፰	ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር	

COGNAC S&E&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

የእጅ ሰዓት ዝኒት



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የሚባል ባለአንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል"አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ"ብቻነው·

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።



ደግሞ በኒዮርክ በፊላዴልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፥ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠጫብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፤ ሽቱ ፤ ለስ ዮን ፤ አድኮሎኝ ፤ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፤ ካኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፤ ከፈይ ምንጣፍ ፤ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፤ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ዓለም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠራል ።

ኒኮላ ።

ማመልከቻ ።

በብርሃንና ሰላም ውስጥ ማስታወቂያ ማሰተም የሚፈልጉ ነጋዴዎች እስከ ፈለጉት ጊዜ ድረስ ባማርኛም ሆነ በፈረንጅ ቋንቋ በርካሽ ዋጋ እንደምናትምላቸው እናስታውቃቸዋለን

ጉድ ይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይ ነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄ ዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢ ሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬ ዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌ ላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌው ላስቲክ ሁሉ ሁለ ት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሁለተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፱
2 me ANNÉE № 49

ሐሙስ ኅዳር ፴ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ።
JEUDI 9 DECEMBRE 1926

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

የጋዜጣው ዲሬክተር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።
Gabré Christos Taklé Haymanot
Diréсteur

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ስለ አቡነ ማቴዎስ እረፍት

አባታችን አቡነ ማቴዎስ በ፲፰፻፵፫ ዓመተ ምሕረት ከምድረ ግብጽ በምንያ ወረዳ በኒኻልድ አገር ተወልደው በትምሕርት ቤት እየተማሩ አደጉ ። ከዚህም በኋላ በገዳመ ጳኩሚስ (ደብረ ቍስቋም) ገብተው በምንኵስና ሥርዓት ይኖሩ ነበር ። ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ የእግዚአብሔር ፈቃዱ በሆነ ጊዜ በዚያ ዘመን የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት የነበሩ አቡነ አትናቴዎስ አረፉ ። ያን ጊዜም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አፄ ዮሐንስ ነበሩና ፤ አገሬ ኢትዮጵያ ሰፊ ስለሆነች አራት ጳጳሳት ይምጡልኝ ብለው ወደ እስክንድርያ ፓትርያርክ ወደ አቡነ ቄርሎስ መልእክተኞች ላኩ ። ፓትርያርክ አቡነ ቄርሎስም አቡነ ጴጥሮስን ሊቀ ጳጳሳት ፤ አቡነ ማቴዎስን አቡነ ሉቃስን አቡነ ማርቆስን ጳጳሳት አድርገው ሹመው ወደ ኢትዮጵያ ሰደዷቸው ። አቡነ ማቴዎስም ጳጳስ ሁነው ተሹመው ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ዕድሜያቸው ፴፫ ዓመት ይሆን ነበር ። አፄ ዮሐንስም ሊቀ ጳጳሳቱን አቡነ ጴጥሮስን ለራሳቸው በትግሬ አስቀርተው አቡነ ማቴዎስን ለሸዋ ንጉሥ ለዳግማዊ ምኒልክ ፤ አቡነ ሉቃስን ለጐጃም ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሰደዱላቸው አቡነ ማቴዎስም የሸዋ ጳጳስ ተብለው ሲኖሩ አፄ ዮሐንስ በመጋቢት ፪ ቀን ፲፰፻፹፩ ዓመተ ምሕረት በደርቡሽ ጦርነት መተማ ላይ ስለ ሞቱ በጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፰፻፹፪ ዓመተ ምሕረት ዳግማዊ ምኒልክ በአቡነ ማቴዎስ እጅ ተቀብተው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆኑ ። አቡነ ማቴዎስም በዚሁ ምክንያት የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት እንዲባሉ ከእስክንድርያ ፓትርያርክ ከአቡነ ቄርሎስ ዘንድ ፈቃድ መጣላቸው ። አፄ ምኒልክም እጅግ ስለወደዷቸውና ስለ አከበሩዋቸው መኳንንቱም ሕዝቡም ሲያከብሩዋቸው ኖሩ በማናቸውም ዘመን ቢሆን ከአፄ ምኒልክ ተለይተው አልኖሩም ። በዚያ በትልቁ ሰልፍ በአዱዋ ጦርነት እንኳ ከዳግማዊ ምኒልክ ተለይቼ አልቀርም ብለው ዘምተው ነበር።

ደግሞ ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ ከመስኮብ ንጉሥ ጋራ ወዳጅነታቸውን ለማስፋትና ለማጽናት በፈለጉ ጊዜ በ፲፰፻፺፬ ዓመተ ምሕረት አቡነ ማቴዎስን ልከዋቸው ነበርና በመስኮብ ዋና ከተማ ሲደርሱ የመስኮብ ንጉሠ ነገሥት አክብሮ ተቀበላቸው ። የተላኩበትንም የወዳጅነት ጉዳይ ተነጋግረው ከጨረሱ በኋላ ለሊቀ ጳጳስነታቸው የሚገባ ሽልማት በወርቅ የተሠራ ልብስና የወርቅ አክሊል ኒሻንም ሸለሚቸው ። ከመስኮብም ሲመለሱ እግረ መንገዳቸውን ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ እስክንድርያ ደርሰው ከፓትሪያርክ አቡነ ቄርሎስ ቡራኬ ተቀብለው ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ ።

ከዚያ አስቀድሞ ወደ ኢትዮጵያ የመጣ ጳጳስ እን ደገና ወዳገሩ ሔዶ ተመለሰ ሲባል ተሰምቶ አያውቅም ነበርና አቡነ ማቴዎስ በኢትዮጵያ ከኖሩ በኋላ ወደ እስ ክንድርያ ሔደው በመመለሳቸው የኢትዮጵያ ሰው ሁሉ አደነቀ ይባላል ። ከዚያም ወዲህ ከጃንሆይና ከመኳንንቱ ጋራ ብዙ ዘመን አብሮ ከመኖር የተነሣ የተጣላውን በማ ስታረቅ ለተቸገረው እያማለዱ በማሰጠት ስለ ደከሙ ትል ቁም ትንሹም ይወዳቸውና ያከብራቸው ነበር ።

ደግሞ በመስከረም ፲፯ቀን ፲፱፻፱ ዓ ም ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ ነግሠው ልዑል ተፈሪ መኰንን የኢት ዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ በሆኑ ጊዜ መንግሥቱ እንዲጸና ብለው ከግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና ከል ዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፈቃድ እንዳትወጡ እያሉ እየገዘቱ ለመዋጋት ወደ ሰገሌ የሚዘምቱትን ወታደሮች ሁሉ እየመከሩና እያበረታቱ ይሰዷቸው ነበር ።

በዚሁም ዘመን በየካቲት ፬ቀን ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በአቡነ ማቴ ዎስ እጅ ተቀብተው ንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ ተባሉ ።

ደግሞ በ፲፱፻፲፫ ዓመተ ምሕረት ብርቱ በሽታ ታመው ነበርና ስለጤናቸው ወደ ምድረ ግብፅ ወርደው በሐኪሞች ከታከሙ በኋላ በጎ ሆነው ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ ። ስለ ሆነ ግን ከዚያ ዘመን ጀምሮ እስከሁን እስከ ዕረፍታቸው ቀን ድረስ ፍጹም የሆነ ጤና አላገ ኙም ነበርና ስለ በሽታቸውም ስለ ሽምግልናቸውም ሰው ነታቸው እየደከመ ይሔድ ጀመር ።

ከዚህም በኋላ በኅዳር ፲፯ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓመተ ምሕ ረት በድንገት ኮንገርቲዎ ፕሌሞኒር በሚባል በሽታ ታመው የሚያክሟቸው ዶክቶር ዘርቦስ ነበሩና በሽታቸውን መር ምረው ብርቱ በሽታ መሆኑን ለግርማዊት ንግሥት ዘው ዲቱና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አስታወቁ ። ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽም በየቀኑ ወደ አቡነ ማቴዎስ ቤት እየተመላለሱ የበሽታቸውን አኳኋን ይጠይቁ ነበር ። ነገር ግን ንጉሥም ቢሆን ጳጳስም ቢሆን ከእግዚአብሔር ፍርድ ለማምለጥ የሚችል የለምና በተ ወለዱ በ፹ ዓመት በተሾሙ ፵፫ ዓመት በታመሙ በ፱ኛው ቀን በኅዳር ፳፫ ቀን በ፰ ሰዓት ነፍሳቸው ከሥጋቸው ተለ ይታ አረፉ ።

ወደ ማታም በ፲ ሰዓት በከተማው በየአድባራቱ ያሉት ደወሎች ሁሉ በኃዘን ደወል ተደወሉ ። በዚሁም በደወሉ ምልክት የከተማው ሰው ሁሉ የአቡነ ማቴዎስን ማረፍ አወቀው ።

ክቡር እጨጌ ገብረመንፈስቅዱስም በአዲስ አበባ ከተማ በየአድባራቱ ያሉት ካህናቱ በሙሉ እየተሰበሰቡ መጥተው ሲፈቱ እንዲያድሩ አዘው ነበርና ካህናቱ ሁሉ

ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ የኢትዮጵያ ሊቀጳጳሳት ።

በ፲፪ ሰዓት ገብተው ከማታው በንድ ሰዓት ጀምረው ሲፈቱ አደሩ ። በፍታቱም መካከል አለቃ ወልደማርያም እንደዚህ ብለው ተቀኙ ።

መወድስ ።

ሃይማኖተ ወንጌል ኤልሳዕ እመ ኢነገረ ፡
ፍኖተ ሃገሩ ማርቆስ ወእስክርያ ንብረቱ ፡፡
እንዘ እብል እነግር ለማኅባራኒሁ እሙንቱ ።
ለኤልሳእ ሃይማኖት ዝየ ሃገሩ ወዝየ ፍኖቱ ፡፡
በከመ ጳውሎስ ሰብአ ዓይን ፡
እምጣነ ማቴዎስ መጽአ ለነቢበ ኵሉ ሥርዓቱ ።
እለሰ ይትሐዘቡኒ በንባበ አፉየ ዝክቱ ፡፡
ይወድቁ በጊዜሃ ውስተ መስገርተ ሞት ዘታሕቱ ፡
ወኢይበሉ ሐሰት ነገረ ዚአከ ዝንቱ ፡
ይሥጳእ ለትርጓሜ ቄርሎስ ሰማዕቱ ።

በቅጥሩም ግቢ ትልቅ ድንኳን ተተክሎ ነበርና በዚያ ውሥጥ ቅዳሴ ተቀደሰ ። ልዑል አልጋ ወራሽም ከሌሊቱ በ፲ ሰዓት መጥተው በታላቅ ኃዘን እቤታቸው ከተላቀሱ በኋላ ወደ ድንኳን ገብተው ቆመው አስቀደሱ ፡፡

ቅዳሴውም በዚያው በድንኳን ውሥጥ የሆነበት ምክ ንያቱ ቀኑ እሁድ ስለሆነ ቅዳሴ በማለዳ ነውና ሬሳቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመውሰድ መኳንንቱና ሕዝቡ በሌሊት ሲመጡ እንዳይቸገሩ ነው ፡

ሁለተኛም ስለ አቡነ ማቴዎስ ሞት ክብር የውጪ አገር መንግሥቶች ሚኒስትሮችና ቆንስሎች ተጠርተው ነበሩና እነዚያ ሁሉ በሌሊት ለመምጣት የማይደርሱ ስለ ሆነ ነው ፤

ቅዳሴውም ከተፈጸመ በኋላ እንደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የጉዞ ፍታት ተጀመረ ፤

ግርማዊት ንግሥትም በአቡነ ማቴዎስ ሞት እጅግ ስለ አዘኑ በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ድንኳን አስተክለው በዚያው ውሥጥ ሁነው በጽኑ ኃዘን እያለቀሱ የሬሳውን መምጣት ይጠብቁ ነበር ።

አራት ሰዓትም በሆነ ጊዜ ሬሳቸው ያለበት አጎበር በሊቀ ጳጳስነታቸው የወርቅ ልብስ ተሸፍኖ ኒሻናቸውና የወርቅ አክሊላቸው በላዩ ተደርጎ በቆሞሳትና በቀሳውስት በዲያቆናትና በመዘምራኑ መኻከል ሆኖ ከቤት ውስጥ ወጣ በዚያ ጊዜ የውጭ አገር መንግሥቶች ምኒስቴሮችና ቆንስሎች ሁሉ ደረሱ ። የሬሳውም ጉዞ እጅግ በሚያስደንቅ በአዲስ አኳኋን ይጓዝ ነበር ። ዋና ኃዘንተኞች የሆኑት የቤታቸው ሰዎች ከሬሳው በጣም ቀድመው ይጓዙ ነበር ከነዚያም ቀጥሎ ካህናቱ፡ ከካህናቱም ቀጥሎ ልብሰ ተክህኖ የለበሱት ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ፡ ከነዚህም ቀጥሎ የሬሳውን አጎበር የተሸከሙ ቆሞሳቱ፡ ከነዚህ ቀጥሎ እንደገና ካህናቱ፡ ከነዚህም ቀጥሎ ሁለቱ ሊቀ መኳሶችና ሌሎችም ትልልቆች የመንግሥት ባለሙዋሎች፡ ከነዚህም ቀጥሎ ልዑል አልጋ ወራሽ ክቡር ራስ ካሣና ክቡር ራስ ሥዩም ደግሞ የውጭ አገር መንግሥቶች ሚኒስቴሮችን በቀኝና በግራ አድርገው ይጓዙ ነበር ። በስተኋላም ደጃዝማቾችና ሌሎች ትልልቆች መኳንንቶች (ውጭ አገሮች ቆንስሎችም ይጓዙ ነበር ። ከዚህም በኋላ መኳንንቱ ሁሉ በየማዕርጉ ይጓዝ ነበር ። የከተማው ዘበኞች በየመንገዱ ዳርና ዳር እንደ ሰልፍ አካሔድ በፀጥታ ይጓዙ ነበር ።

፭ ሰዓት ሲሆን ካሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ደረሱ ። ሬሳቸውም ከቅጥር ግቢ በገባ ጊዜ ግርማዊት ንግሥትና አብረዋቸው ያሉት መኳንንቱም ወይዛዝሩም በታላቅ ኃዘን አለቀሱ ፡ ቆሞሳቱም ሬሳውን ወደ መቅደስ አግብ ተው አሳልመው አሳረፉ ።

ልዑል አልጋ ወራሽም በተነጠፈው ደረጃ ላይ በ ስተውጪ ከመኳንንቱ ጋራ በተቀመጡ ጊዜ የውጪ አገር ሚኒስትሮችና ቆንስሎች ሌሎችም ፈረንጆች እየ ቀረቡና እየተሰናበቱ ወደቤታቸው ተመለሱ ፡ ከነዚሁም ከውጭ አገር ሚኒስትሮች የቤልጅኩ ሚኒስትር ብቻ በ አውሮጳ ትልቅ ሰው ሲሞት የሚለበሰውን ልብስና የሚ ደረገውን ባርኔጣ አድርጎ ነበር ።

ከዚህም በኋላ ካህናቱ ወተቀበልዎ መላእክት በስ- ብሐት ወበማኅሌት ወአብእዎ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ለማቴዎስ ሊቀ ጳጳሳት እያሉ በቤተ ክርስቲያኑ ከዞሩ በኋላ በስተደቡብ ቆመው የፍታቱን ሥርዓት ጨረሱ ። ቤተ ሰ ዎቻቸውም ፎቶግራፋቸውን ይዘው እየዞሩ ያለቅሱ ነበሩ ከዚህ በኋላ በ፯ ሰዓት ተኩል ታቦቱን አውጥተው ከሬ- ሳቸው በስተፊት አድርገው ዑደት ታወደና በስተምሥራቅ በኩል ተቀበሩ ።

በዚያም ጊዜ በተፈሪ መኰንን ትምሕርት ቤት የሚማሩ ልጆች የሃይማኖት አባታቸውን ሞት ስለ ማክበር አበባ እየያዙ መጥተው ነበርና በመቃብራቸው ላይ አድርገው ተመለሱ ። ግብአተ መሬትም በሆነ ጊዜ ስለ አቡነ ማቴዎስ ሞት ክብር አምስት ጊዜ መድፍ ተተኰሰ

ከዚህም በኋላ ክቡር እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በስተምዕራብ በኩል በልዑል አልጋ ወራሽና በመኳንንቱ በሕዝቡም መኻከል ቆመው አቡነ ዘበሰማያት አሳርገውና ባርከው አሰናበቱ ።

ክቡር እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሰው በሞተ ጊዜ የቀቢፀ ተስፋ ኃዘን ማዘን አይገባም እያሉ የዮሐንስ አፈ ወርቅን ተግሣጽ እየጠቀሱ ብዙ ጊዜ ለሕዝቡ አስ ረድተው በመጨረሻው ሲያስረዱ አውጃዘው ነበርና ዛሬ በአባታችን በአቡነ ማቴዎስ ሞት ፊቱን ነጭቶ ደረቱን ገልጦ የቀቢፀ ተስፋ ልቅሶ ባለመለቀሱ መልከም የክርስ ቲያንነት ምልክት ስለሆነ ለወደፊቱ ሰው ሁሉ ይህን ሥርዓት አጥብቆ ይይዛል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ።

ይህም ሁሉ ከተፈጸመ በኋላ የአባታችን የአቡነ ማቴዎስ ዕረፍት በእስክንድርያና በግብጽ አውራጃ ሁሉ እንዲሰማ ቴሌግራም ተላከ ። በኢትዮጵያም ስልክ በገ ባበት አገር ሁሉ በስልክ ተነገረ ። ፍታቱም በምሉ ኢትዮጵያ በየአድባራቱና በየገዳማቱ ከዕለት እስከ ፴ ፣ በየገጠሩ ግን በሣልስታቸው በሰባታቸው በ፲፪ታቸው በ፴ቸው በ፵ቸው እየተፈቱ እንዲቆረብ ትእዛዝ ተደርጓል

አቡነ ማቴዎስ አርባ አምስት ዘመን ያህል በኖሩ በት አገር ስለ ሞቱና በሞታቸው ይህን የሚያህል ትልቅ ክብር ስለ ማግኘታቸው እጅግ የታደሉ ሰው መሆናቸ ውን ያስረዳል ።

አቡነ ማቴዎስ የሙሉ ኢትዮጵያ ሕዝብ አባት ናቸ ውና ብርሃንና ሰላም የሙሉ ኢትዮጵያን ሕዝብ እግዚ አብሔር ያጥናችሁ (ያበርታችሁ)ይላል ።

የ፫፻፹፰ ገጽ ተከታይ

መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ።

አሁን ወደአንድ አገር መንደር ብንሔድ በዚያም አንድ በርኖስ ሰፊና አንድ ገበሬ ሲገበያዩ ብናይ ፡ ባለ በርኖሱ ስድ ስት ቀን የደከመበትን በርኖሱን ለገበሬው ሲሸጥ ስድስት ቀን የተሰራበት እህል ይፈልጋል።ማለት የበርኖሱ ሽያጭ የበጉን ጠጉር ቆርጦ ነድፎ ፈትሎ በርኖሱን ሰርቶ እስኪጨረስ ድረስ ስድስት ቀን የፈጀበት እንደሆን ፡ ገበሬውም ይህንን በርኖስ ለመግዛት ቢፈልግ አርሶ ጐልጕሎ አርሞ አጭዶ ወቅቶ በስ ድስት ቀን ሂሳብ ያገባውን እህል ለባለ በርኖሱ ይሰጣል ።እን ግዲያስ ዋጋ ማለት የሥራ መለኪያ ማለት ነው ። ይህ ሳይቀር ባለ በርኖስ አሥር ቀን የደከመበትን በርኖስ ስድስት ቀን ለተ ደመከበት እህል መለወጥ የግድ ሲሆንበት ሥራው የማይጠ ቅም እንደሆነ ይረዳልና እራሽ ይሆናል ፣

አራሹም እንዲሁ አሥር ቀን የለፋበትን ጤፍ ስድስት ቀን ለተለፋበት በርኖስ መለወጥ የግድ ሲሆንበት ሥራው የማጠቅም እንደሆነ አይቶ እርሻውን ትቶ ሥራው የበርኖስ ሠሪ ይሆናል ። በሌላውም ሥራ ሁሉ እንደዚሁ ነው ። ብረት ሠሪና ሸሀላ ሰሪም ሌላም ሠራተኛ ሁሉ እንደሥራው መጠን ዋጋውን ካላገኘ የዱሮ ሥራውን ትቶ እንደድካሙ መጠን ዋጋ የሚያገኝበትን ሌላ ሥራ ይፈልጋል ። ተጠራጣሪው አንባቢ ግን ደግሞ እንደዚህ ይል ይሆናል ።

አንጠረኛው ብረት ሠሪው ሸማኔው ገበሬው እርሱ ራሱ ገበያ አይወርድ ።ነገር ግን ሁሉን ነገር ወደ ገበያ አውርዶ ዋጋውን ከፍና ዝቅ የሚያደርገው ነጋዴ ነው ። ነጋዴው ግን አይሠራም ዕቃውን ግን ዋጋውን ከፍና ዝቅ እያደረገ እንደወደደ ይሸጣል ። የዕቃውን ዋጋ ዝቅ የሚያደርግ ሌላ ባላአንጣ ነጋዴ እርሱ የሚሸጠውን ዕቃ ሲሸጥ ያየ እንደሆነ ንግዱን ያቆማል ወይም ጨርሶ ሥራውን ለመተው ያስባል ። ባላንጣ እንደሌለው ሲያይ ግን እቃውን ሁሉ ብርቅ አድርጎ ከፍ ያለ ዋጋ ይፈልግለታል ። ስለዜህ ዋጋ የሥራ መለኪያ መሆኑን በምን እንረዳው ፡ ለዜህም ምላሽ አለው ። የበርኖስ ሠሪና አራሹ ሸማኔውም ጐረቤቶች የሆኑ እንደሆነ እቃቸውን እንደእየሥራቸው መጠን እንዲለዋወጡ የታወቀነው ። ቤቶቻቸው የእኩል ቀን ያህል የተራራቁ እንደሆኑ ግን አራሹ ስድስት ቀን የተደከመበትን በርኖስ ወይም ሸማ መግዛት ሲፈልግ ከዚያ ሔዶ በርኖሱን ወይም ሸማውን ገዝቶ እስኪመለስ ድረስ የአንድ ቀን ሥራ ይፈታል ። ስለዚህ በርኖሱን ወይም ሸማውን ይዞ ከቤቱ ሲገባ ያ በርኖስ ወይም ሸማ ስድስት ቀን የፈጀበት ጤፍና የአንድ ቀን መንገድ ድካም ይፈጅበታል ።

የበርኖሱ ጌታና ሸማኔውም ቢሆኑ እንደዚሁ ስድስት ቀን የተደከመበት ጤፍ ሲፈልጉ እስከ አራሹ ቤት ድረስ ሔደው የስድስት ቀን ድካም በርኖስና ሸማ ስድስት ቀን የተደከመበትን ጤፍ ለውጠው ወደቤታቸው እስኪመለሱ ድረስ የሰባት ቀን ድካም ይሆንባቸዋል ።

ስለዚህ ዋጋ የሥራ መለኪያ ነውና ጤፉን በቤታቸው ካገቡት በኋላ ሌላ ከጐረቤት መጥቶ በበርኖስ ወይም በሸማ ለውጡኝ ቢላቸው ሰባት ቀን የተደከመበትን ሸማ ወይም በርኖስ አምጣ ይሉታል ። እንደዚሁም ገበሬው ስድስት ቀን በተለፋበት ጤፍ የገዛው በርኖስ ሌላ ጐረቤት መጥቶ በጤፍ ለውጠኝ ቢለው ያ ገበሬ ስድስት ቀን የለፋበትን ጤፍ ፩ድ ቀን የገዛበትን ያስብና ሰባት ቀን የተለፋበትን ጤፍ አምጣ ይለዋል ። አራሹ በርኖሱን ለመግዛት እርሱ ራሱ ባይሔድ ነገር ግን ልጁን ወይም ምሽቱን ቢልክ ያው ነው ፡ ከቤት ይረዱት የነበረውን ሥራ ይፈቱበታል ። ያንን ለማምጣት አንድ ቀን ሥራ ፈተው ውለው እርሱ ሠርቶ ካገባው እህል ይመገባሉ ።

ነገር ግን የነዚህ ሁሉ ቦታ የተራራቀና የሶስት ቀን መንገድ የሚያውል የሆነ እንደሆነ የፈለጉትን ነገር ወይም ለማምጣት ሰስት ቀን ይለፉ ይሆንን ። እንዲህ አይደለም ነገር ግን በመካከላቸው ተላላኪዮች የሚሆኑዋቸው ሌሎች ሰዎች ይገኛሉ ። እነዚህም ተላላኪዮች ስድስት ቀን የተደከመበትን ጤፍ ይዘው ሂደው ዘጠኝ ቀን የተደከመበትን በርኖስና ሸማ ገዝተው ይመለሳሉ ከነዚያ ወዲያ ሸማውና በርኖሱ ፲፪ት ቀን የተደከመበት ተብሎ ይታሰባል ሌላ ጐረቤት መጥቶ በጤፍ ለውጡኝ ያላቸው እንደሆነ ፲፪ት ቀን የተደከመበት ጤፍ አምጣ ይሉታል እርሱም በዚያው ስሌት ገዝቶ ይሄዳል ። ተላላኪዮቹም የስድስት ቀን ድካም ጤፍ በ፫ት ቀን ሥራ ትርፍ ያገኛሉ ። እነዚህ ተላላኪዮች ጥቂቶች የሆኑ እንደሆነ ለጊዜው መልካም ትርፍ ያገኛሉና የቀሩት አራሾች ይህንን ትርፍ ተመልክተው እርሻቸውን ትተው ተላላኪዮች ይሆናሉ ቆይቶ የተላላኪዮች ቊጥር በዝቶ የላኪዮች ቊጥር ያነሰ እንደሆነ ግን ተላላኪዮች የድካማቸውን ዋጋ እንደፊተኛው ሊያገኙ አይችሉም ዋጋቸው እያነሰ ይሄዳልና የተላላኪዮች ሥራ እንደማይጠቅም አይተው ሌላን ሥራ ለመፈለግ ይሄዳሉ ። ተላላኪዮች ቊጥራቸው በመጠን የሆነ እንደሆነ ዋጋቸውንም እንደድካማቸው መጠን ያገኛሉ ። እነዚህ ተላላኪዮች የምንላቸው ሰዎች ነጋዴዎች ናቸው ። ስለዚህ ነጋዴ ያንዱን እቃ ዋጋ ከፍና ዝቅ ቢያደርግ ለጊዜው ነው እንጂ የእቃው ዋጋ ውሎ አድሮ በተሰራበት ሚዛን መግባቱ አይቀርም ። ነጋዶችም የእቃውን ዋጋ ከፍና ዝቅ ቢያደርጉ የመንገዱንና የርቀቱን ሚዛንና ድካም ሲያስተካክሉ ነው እንጂ ዋጋና ሥራ በትክክል ይሄዳል ። ከገበሬው ቤት እስከ ባለበርኖሱ ቤት የሚወስድ መንገድ ገደልና ጐርፍ ቢኖርበት የተላላኪ ድካሙ ብዙ ነውና ዋጋው ይበዛል መንገዱ ግን ገደሉ ቢደለደል ወንዙም ይልድይ ቢሠራበት የተላላኪው ድካም ያንሣልና ዋጋውም ያንሳል ። ከዚሁም የተሻለ ሆኖ መንገዱ ጋሪ እንደሚያስኬድ ሁኖ ቢጠረግም የግድ የበለጠ ድካሙ ይቀላል ዘጠኝ ተላላኪዮች ተሸክመው የማይችሉትን እቃ ወይም እህል በጋሪ አንድ ፈረስ ጎትቶ ያመጣዋል ። እንደዚህ የሆነ እንደሆነ ባለሸማና ባለበርኖስ ጤፍ ሲፈልጉ ባለጤፍም በርኖስና ሸማ ሲፈልግ እንደዱሮ ለተላላኪ ብዙ ዋጋ አይሰጡም ።

የምድር ባቡር ከተሠራ በኋላ ግን የተላላኪው ዋጋ ፈጽሞ ጥቂት ይሆናል ። ስለዚህ ባንድ አገር ውስጥ እውቀት ሲበዛ የነጋዴው ፡ ማለት ፡ የተላላኪው ዋጋ ያንሳል ። ስለዚህ እውቀት ሲበዛ ለኑሮ የሚያስፈልገውን ማናቸውንም ነገር ለማግኘት መሰናከያ ያንሳልና ። የማናቸውም ዋጋ ሁሉ ዝቅ ይላል ። እውቀት እያነሰ ሲሄድ ግን ለኑሮ የሚያስፈልገው ዕቃ ሁሉ ይወደዳል እንደዚህም ባንድ አገር ውስጥ የተሠራው የጋሪ መንገድና የወሀ ድልድይ ሲበላሽ በቶሎ ያልታደሰ እንደሆነ ፡ ባለበርኖሱ ጤፍ ሲፈልግ ባለጤፉም በርኖስ ሲፈልግ እንደፈለጉት በጋሪ ሊመጣላቸው አይችልም በሰው ሸክም ሊያመጡ ግድ ይሆንባቸዋል ሰው ግን የፈረስ ጋሪን ያህል መሸከም አይችልምና አንድ ጋሪ ባንድ ቀን የሚጎትተውን እስኪያመላልስ ድረስ ዘጠኝ ቀን ያስፈልገዋል ። ስለዚህም ጤፉ ለባለ በርኖሱ ፤ በርኖሱም ለባጤፉም ይወደድበታል ። ስለዚም ባንድ አገር ውስጥ እውቀት ሲበዛ የነጋዴው ጥቅም እንዲያንስ የሠራተኛው ጥቅም ግን እንዲያድግ ግልጽ ነው ። ባንድ አገርም ውስጥ እውቀት ሲበዛ ሠራተኞች አይራራቁም ። በየመንደሩ በየመንገዱ በየወረዳው ዕቃው ሁሉ አጠገብ ላጠገብ በያይነቱ ይሠራልና ለመለዋወጥ ሩቅ መንገድ መሄድ አያሳስባቸውም ። ስለዚህ የተላላኪው ነጋዴ ዋጋ ይቀራል ።

የዕቃ ሁሉ ዋጋ እውቀት ሲበዛ እያደር ዝቅ እያለ መሄዱ በምን ምክንያት እንደሆነ ለመረዳት ፥ እስቲ እንደገና ተመልሰን እንመርምር ።

ያ ለምሳሌ ወደ ባሕር ዳሴት ተሰዶዶ ያልነውን ሰው መጀመሪያውን ቀስት ሲያበጅ አስቀድሞ በእግሩ ሩጦ አውሬን ይዞ ገድሎ ጅማቱን አበጅቶ ነው ። የመጀሪያው ቀስት ከተበጀ በኋላ ግን ሁለተኛውን ቀስት ለማበጀት የፊተኛውን ያህል አያደክመውም ። እንግዲህ አውሬንም ለመግደል እንደፊተኛው ሩጦ ለመያዝ አያሳስበውም ፊት ባበጀው ቀስት ይገድላል እንግዲህ ቀስት በመጀመሪያ እስኪሠራ ድረስ ውድ ነው ። ከተሠራ በኋላ ግን በገዛ እጁ ዋጋውን ዝቅ ይላል ።

በሌላም ነገር ሁሉ እንደዚሁ ነው ። አሁን ከሰል የብረትን አፈር ለማቅለጥ የሚያስፈልግ ስለ ሆነ በመጀመሪያ ይወዳል የብረቱ አፈር ቀልጦ መጥረቢያና ዶማ ከተሠራ በኋላ ግን ብዙ ከሰል ለማግኘት ድካሙ ያነሣል ።

ብዙም ከሰል ከተገኘ በኋላ ብዙ የብረት አፈር አቅልጦ ብዙ መጥረቢያና ዶማ ያለ ብዙ ድካም ለመሥራት ይቻላል።በዚህ ምክንያት መሣሪያ ሁሉ በገዛ እጅ ዋጋው ይረክሳል መሣሪያም ሲረክስ ለሰው ሁሉ ኑሮ ደሚያስፈልግ ነገር ሁሉ ይረክሳል ።

ጋሪውም ቢሆን የእንደዚሁ ነው የመጀመሪያው ጋሪ እስኪበጅ ድረስ እጅግ ያስቸግራል ። እንጨቱ ያለበት ሥፍራ እሩቅ ነውና ፤ መሸከሙም ያቀታል ። የመጀመሪያው ጋሪ ከተሠራ በኋላ ግን ለሁለተኛው ጋሪ የሚሆን ያለ ብዙ ድካም ይመጣል ስለዚህ የሌላው ጋሪ ዋጋ ዝቅ ይላል ።

ለኑሮም የሚያስፈልግ ነገር ሁሉ ሲረክስ ሰው በዓለም ላይ ሙሉ ጌትነት ማግኘቱ ነውና ይከብራል ከዚህም ጌትነቱ የተነሣ ድካሙ ያነሣል እንግዲህ እውቀት እየበዛ ሲሄድ የዕቃው ሁሉ ዋጋ እያደር እንዲረክስ ከዚህ ቀድሞ የሰማነውን ቃል ፈጽሞ ያስረዳናል ።ነገር ግን ሌላ ማስረጃ ነገር ብነጨምር ይሻላል ፥

ባንድ መንደር የሚኖሩ ሰዎች ጠበንጃና መጥረቢያ ዶማም ሲኖራቸው መሣሪያቸው ትክክል ነውና አንዱ ባንድ ቀን የሠራውን ዕቃ ሲለውጥ ፤ ያ የሚቀበለው ዕቃ አንድ ቀን የተሠራ እንዲሆን የታወቀ ነው ዱሮ ደህና መሣሪያ ሳይኖር ሰዎቹ የሚኖሩበት ሥራው ብዙ ደሚያደክም ኑረዋል ዛሬ ግን ደህና መሣሪያ ተገኝቷልና ቤት ሆነ ወይም ሌላ ሥራ ያለ ብዙ ድካም በፍጥነት ሊሠራ ይችላል እንግዲህ ያ የዱሮ ቤትና ሥራ አዲሱ መሳሪያ ከተገኘ ወዲህ ይረክሳል ። ዋጋ የሥራ መለኪያ ነው ስለ ተባለ ዕቃ ሁሉ ሲገመት ዱሮ በተሠራበት አይደለም ነገር ግን በዚያው በተገመገመበት ጊዜ ተሰርቶ ቢሆን የሥራው ድካም ስንት እንደሆን እየታሰበ ነው ። የሥራውን አቀለጣጠፍ በዚህ ያሳያል ። አንድ ሰው መቶ ኪሎ ዕቃ ሰባት ኪሎሜትር የሚያህል መንገድ በሰዓት ሊጐትት ይችላልን? አንድ ፈረስ ግን ፴፪ ኪሎ ዕቃ በሰዓት ሊጐት ይችላል እንግዲህ ያንድ ፈረስ ኃይል የ፱ ሰው ኃይል ስለ ሆነ ሰው ግን በእውቀቱ ፈረሱን አልምዶ እንዲያገለግለው ያደርጋል በዚሁም እውቀቱ ሥራው ይፋጠንለታል ።

ከዚያም ቀጥሎ ራሱ እስበ ባቡር ይሰራል የባቡር ኃይል ከሁሉ የበለጠ ስለሆነ እነሆም ስድስት ሰዎች በሰበሰቡት ከሰል መቶ ፈረሶች የማያንቀሳቅሱትን ሸክም ባንድ ጊዜ ለመሣብ ይችላል ። እውቀት የሌለው ሕዝብ ግን ይህነን የመሰለ እርዳታ ሊያገኝ አይችልም ። ስለዚህም በመኪና የተሠራውን ዕቃ ሁሉ ሲገምት ያንን ነገር እስኪያገኝ ድረስ ስንት ድካም እንዲያስፈልገው ገምቶ በዚያው ዋጋውን ይሰጣል ። ብዙው ነገር ግን በእውቀት ሥራ እንጂ በጉልበት ሥራ የማይገኝ ይሆናል ።

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት መጽሐፍ ነው ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

የ፫፻፺፫ ገጽ ተከታይ።

፩ኛ ፤ የኢትዮጵያ ያለፈውና የሚመጣው ትውልድ ።

«ትውልድ ይሄዳል ትውልድም ይመጣል ። መክ ፩ ፬» ባለፈው ትውልድ ብዙ መናገር አያስፈልግም ። ያለፈው አልፏልና ላለፈው ነገር ደግሞ አንዳች ሊደረግለት አይቻልም ። ባለፈው ዘመን አንዳች እንደሚገባ ስላልተደረገም ኃዘንና ጠጠትን አትርፈን እንቀራለን ። ብዙዎች ናቸውና በድንቁርናና በጨለማ ያለፉቱ ፥ አሁን ግን ላለውና ለሚመጣው ትውልድ ብዙ ነገር ሊደረግለት ይችላልና አሁን የሞላው የሕዝባችንና የመንግሥታችን አሳብ ምን ሊሆን ይገባዋል ። አሁንሳ ይኸው የከበረው ያለውና የሚመጣው ትውልድ እንደ ቀደሙቱ ትውልድ ዝም ብሎ በድንቁርናና በብርቱ ጨለማ ተሸፍኖ ይለፍን እዩ ፥ ይኸው የሚመጣው ትውልድ በእኛ በሕያዋኖች እጅ ነው ያለ ፥ እኛም እንዳደረግነው ይሆናል ። እንግዴህ ትውልድን ለማሳደግና ለትምሕርት ፥ ለጥበብ ፥ ለልዩ ልዩ ሥራ ባናዘጋጀው ግን በከንቱ ሊያልፍ ነው ።

ስለዚህ የሚመጣውን ትውልድ በእውነተኛ ሥራ ልንጠቀመው ቢሆን አሳባችን ፥ ብዙዎችን ልጆች ሥልጣኔ ወዳላቸው ሕዝብ ልከ እንዲማሩ ማድረግ ግድ ነገር ነው ። በዚህ ነገር ልዑል ጌታችን ተፈሪ መኰንን ከዚህ ቀደም ብዙ ትልልቅ ሥራ አቅንተዋል ። ግን ይኸው ሥራ የእርሳቸው ሸክም ብቻ ሆኖ ቢቀር ብዙ ያሳዝናል ። ሌሎችም ይህን ነገር ለማድረግ ችሎት ተሰጥቷቸው ያሉ ሁሉ ይህን ሥራ ለማድረግ በቶሎ እንዲነቁበት እነለምናለን ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትም እንደ ትልቂቱ አያታቸው እንደ ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማትና ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም እንደ መጡ ፥ እርሳቸውም በግርማዊው በመንግሥታቸው ችሎት አያሌ ልጆችን በውጪ ለማስተማር ተግተው ቢፈቅዱላቸው ፤ እውነተኛው ብርሃንና ሰላም በተወደደችው በኢትዮጵያ መኻል በደመቀ ። የእውነተኛው የሰሎሞን ልጅ ዙፋንም በምስጋና ጸንቶ በገነነ ።

እንዲህ ያለ ሥራ ማለት አዲስ ትውልድን በትምሕርት ማሳደግ የመንግሥት ጽናትና ሥልጣኔ የሚሠራ መሆኑ በሁሉ የተረዳ ነገር ነው ። ማንም ሕዝብ ወይም መንግሥት ይህን ነገር አጥብቆ ያልተጋበት ጠፍቶ ቀረ እንጂ ለወደ ፊት የገፋ አይገኝም ። የነገሥታቱም የሐሳባቸውና የእውቀታቸው ስፋት መለኪያም ነው ። ይህን ማለታችን ደግሞ የባዕድን ሃይማኖት ይማሩ ብለን አይደለም ። ሃይማኖት ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ እንጂ ከሌላ አይቀዳም ። መጽሐፍ ቅዱስም ከሌሎች ሕዝብ

በፊት በእጃችን አለ ። ዳሩ ግን በአእምሮና በጺጋ በዕውቀትም ከባልንጀሮቻቸው የበለጡ ልጆችን አይቶ መርጦም በጥበብ ማሳደግ ለሚመጣው ሕዝብና መንግሥት ሥልጣኔ እንዲያውበጭራሽ የሚያስፈልግ ነገር ነው ። ይኸው ሥራ ከልቡ ያልተ በራለት ሕዝብና መንግሥት ወይም ይህን በችኩላ የማይፈጽም ጠፊ ነው ።

በቀድሞ ዘመን ሳይቀር መንግሥታቸውን በእንደዚህ ያለ ሥራ ያሠለጠኑ ያገራቸውንም ስም በጭር ዘመን ያስወጡ እንናቡከደነፆርን እናነሣለን ። እርሱ አያሌ ልጆችን ለመንግሥት አገልግሎት ሊያሳደግ ታጥቆ ነበር ። እንደዚህ ያሉ ልጆችንም በማሳደግ በጣም እንደ ተጠቀመ እናገኛለን ። እንዲሁም በሌሎች ሕዝብ የወደቀውንና የተበላሸውን የመንግሥታቸውንና የሕዝባቸውን ኑሮ ሊያድሱና ሊያቀኑ ሲፈልጉ የሚመጣውን ትውልድ በልዩ ልዩ ትምርትና ዕውቀት ዘመናቸው ሊሰጣቸው የሚችለውን ትምርት በማስተማር በማሳደግም ይጀምሩታል ።

ስለዚሁ መኳንንቶቻችንና የሕዝባችን ትልልቆች ሆይ ሀብታሞች ሰዎች ነጋዴዎችም ይህን ነገር በቶሎ እንደ ችሎታችሁ መጠን ይህን ሥራ ልትጀምሩት እናማጥናችኋለን ። እንግዴህ ያገር ፍቅር በየት እኩል ነው ያለ፣ ቢሆን ፣ ደግሞ ከዚሁ በፊትግድ ሊጠፉ የሚገባቸው ጠላቶች አሉና ፣ እርሳቸውን ሳናጠፋ ይህ ሥራ ከቶ ሊፈጸም አይቻልም ። እነርሳቸውም ፣ ራሱን መውደድ የራሱን ረብ ብቻ መፈለግ እኔን ይመቸኝ ምን አግዶኝ የኔ ስምና እውቀት ብቻ እንዲጠራ ሌሎች አዋቂዎች እንዳይገቡና እንዳይታወቁ እንደዜሁ የሚመስሉም ብዙች ናቸው ። ግን የተደለበ ወርቅ ያላቸው ሰዎች ለኋላው ምንሊያደርጉት ነው? ለኋለኛው ዓለም ያሸግሩታልን ? ወርቃቸውስ ለእነርሳቸው መሆኑን ለእንግዴህም ማንም ሊወስድባቸው አስከማይቻል ማን ዋስ ቀጠረላቸው ? ብዙ የደንቆሮው ገንዘብ በአዋቂ እጅ ይወድቃል ብዙ ጊዜ የተከመረና የተደለበ ሀብት በጠላት እጅ ይወድቃል እውቀትንና አእምሮን ጥበብንም በገንዘባቸው የሚያተርፉ ግን ይህን የሚወስድባቸው የለም ። «ወርቃችሁና ብራችሁ ዛገ ዝገቱም ምስክር ይሆነባችኋል« ያለው በሕዝባችን ሰዎች እንዳይፈጸም ገንዘባችንን ዓቅማችንንም ፈጣሪ በሰጠን ችሎት ሁሉ ለእግዚአብሔር ስም ለሀገራችን ጥቅም እናውለው ። ለራሱ ብቻ መኖር ዓመፃ ነው ። ስለዚህ ይኸው መንፈስ ከትልቅ ከትንሽ ባይርቅ ከቶ ሕዝባችን አይጠቀምም ። ያ የዓመፃው መንፈስ ግን እንደራቀ ምስክሩ በዚህ ረገድ የተፈለገው ሥራ በተፈጸመ ጊዜ ነው ። በሕዝባችን መካከል እንዴህ ያለ ሥልጣኔ እንዳይገዛ የሚያጫንቅ ወይም የሚከለክል ሥራ እንዳለ እውቅ ነው ፣ ምነው እንዴህ ያለ ሥልጣኔ ያልገባላቸውንና ያልተመሠረተላቸውን ሕዝቦች ለመጉረስ ቀላል ነገር ስለሆነ ፣ እንዴህ ያለ እውቀትና አእምሮን ዓርነትንም ያወቀ ሕዝብ ግና ዓርነቱን እንዳያጠፋ ብሎ እስከ ኋለኛዪቱ የደም ነጥብ ሳትቀር በእጅግ ውድና ጅግንነት ደሙን ያፈሳል ። የሕዝብ ክብረትና ነፃነት ሥልጣኔም ከሁሉ የበለጠ ነገር መሆኑን ያውቃልና ፣ እንዲህ ያለ ዕውቀት የሠረፀባቸው በባዕድ ሕዝብ ተገዢዎች የሆኑ ደግሞ ነፃነታቸውን ለመመለስ ሁከትንና ጦርን አድርገው የጠላትን ቀምበር እንደሚጥሉ አያሌ ጊዜ እናያለን ። በድንቁርናና በጨለማ ሳይማር የሚኖር ሕዝብ ግን ዕድሉ እንደ ዓሣው ነው ። ዓሣ በመቃጥን ያለች የምትበላውን ብቻ ይመለከታል እንጂ ለኋላው በእርስዋ ምክንያት የሚደርስበትን አያውቅም ። ስለዚሁ በመንጠቆ ይያዛል ። እንግዴህ የሕዝባችን ሰዎች ሆይ ለሚመጣው ለኢትዮጵያ ትውልድ እንደቀደሙቱ በከንቱ እንዳይሄድ የሚደረግለትን በአንድነት ለማሰብና ለማዘጋጀት እንፍጠን ። አለዚህ ደህንነት የለምና ።

ብርሃንና ሰላምን የሚናፍቁ ኢትዮጵያውያን ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ቁጥር ይታተማል ።

የጥያቄ መልስ ።

ብርሃንና ሰላም በሁለተኛው ዓመት ፵፯ኛ ቁጥር ፣ አገረ ገዢዎች መኳንንቶች አገራቸው እንዲለማ ፣ ሕዝባቸው እንዲበለጥግና እንዲሠለጥን ምን ማድረግ ይገባቸዋል ብሎ ጠይቋል ። ደግሞ ቀጥሎ በ፵፰ተኛው ቁጥር የአገረ ገዢዎች ዋና ጥረታቸው በየግዛታቸው ውስጥ ባመት ባመት ስንት ተማሪ ቤት እንደ ተጨመረ በዘመን ታሪክ እንዲጻፍላቸው ብቻ ነው ብሎ ጽፏል ። ይህ ነገር እንዴት ይሆናል ፣ አገረ ገዢ ሁሉ በየግዛቱ ያለውን ሕዝብ አስጨንቆ የተማሪ ቤት ፈሰሴ እያወጣ ለስሙ መጠሪያ ብቻ ያልተከናወነ ተማሪ ቤት ቢያቆም ለመንግሥት ጥቅሙ ምንድነው ። በየወንዙ ሃሴ የሚሉትም ምሳሌ በዚሁ ሊፈጸም ይችላል ። ላንድ ቤት ባለቤቱ አንድ እንዲሆን እንዲሁም ላንድ መንግሥት አማከሪዎቹን ብቻ ይዞ ንጉሠ ነገሥቱ ብቻ ባለ ሙሉ ሥልጣን ሊሆን ከጥንት የተመደበ ነገር ነው ።

ለኔስ እንደሚመስለኝ ላገረ ገዢዎች የሚያስፈልጓቸው ሁለት ነገሮች ናቸው ። መጀመሪያ ግዛታቸውን ለመንግሥት ለቀው እነሱ በደመወዝ ቢያድሩ አሳብ ይቀልላቸዋል ። ሁለተኛ ፣ አሽከር እያሉ የሰበሰቡት እጅግ በዝቶባቸዋልና ለቤታቸው የሚበቃቸውን አስቀርተው የቀረውን ሠራዊት ለመንግሥት ቢሰጡትና መንግሥት ሥራ ቢያሲዘው እነሱ ከከበደ ሸክማቸው ያርፋሉ ። አንዳንዶች አራትና አምስት መቶ ሰው አስከትሎ በንዝሕላል መኖርን ከትልቅ መዓርግ ይቈጥሩታል ። በብዙ ጦር ታጅቦ መታየት የሚያስፈልገው በጦርነትና በበዓል ሠልፍ ቀን ብቻ ነው እንጂ ለዘወትርስ አያስፈልግም ። በግድ የሚያስፈልግ ቢሆን እኔ እራሴ ባደረግሁት ነበረ ። ለጋሱ ልዑል ተፈሪ መኰንን በ፫፻፴ ወታደር ላይ ሥልጣን ሰጥተውኛል ። እንግዴህ ሁለት መቶውን በሥራ ላይ አስቀምጬ መቶ ሰላሳውን ወታደር በምሔድበት ቦታ ሁሉ አስከትዬ እየተግተለተልሁ ብሄድ እስከሻር ድረስ የሚከለክለኝ ባልነበረ ። ዳሩ ግን ነፃነቴን እወዳታለሁና ላደርገው አልችልም ።

አስታጥቄ ወልዳማኤል ።

ፋክክር

ከቤቴ ተነሥቼ ብርሃንና ሰላምን ለመቀበል ስመጣ በመንገድ ላይ ፪ት ሰዎች ሲፎከከሩ ደረስሁ ። ፩ኛው በብዙኅ ጥንቆላው ታፍሮ ተፈርቶ የሚኖር ነው ፤ ፪ኛው ፣ ብርቱ ተዋጊ ጉበዝ

ብሀገር የመጣውን ጠላት ሁሉ እየገደለ አገር ጠብቆ የሚኖር ነው ። ፫ኛው ፡ የተማረ ብልህ አገሩን መክሮ በምክር አገሩን ጠብቆ የሚኖር ነው ። እነዚህ ፫ቱ ከቀን አንድ ቀን ተገናኝተው ለዚች ለሀገራችን እኔ ነኝ ጥቅሟ እኔ ነኝ ጥቅሟ ተባብለው ተጣሉ ። ቢጣሉ አንደኛው አንሥቶ እኛ አንጣላ ሕዝቡ ተሰብስቦ እገሌ ነው ጥቅማችን ብሎ ይምረጠን ብሎ ሕዝቡን ሰብስቦ በሉ ምረጡ አለ ፤ ወይንስ ጠንቋዩ ነው ጥቅማችሁ ፤ ወይንስ ጐበዝ ነው ጥቅማችሁ ። ወይንስ የተማረው መካሩ ብለው ጥቅማቸውን ቢጠይቋቸው፡ሕዝቡ ተሰብስበው፡ጠንቋዩንም ጥቅም አይደለህም ብንለው ይጣላና ፩ ነገር ያመጣብናል ። ጎበዙንም ጥቅማችንም አይደለህ ብንለው ይቀየምና አገራችንን ይደፈራል የተማረውን ብልሁን መካሩን ጥቅም አይደለህም ብንለው ጥበቡንና ምክሩን ይደብቅብናል ። ሶስታችሁ ለኛ ጥቅማችን ናችሁ እንመርጥም ብለው መለሱላቸው ።

ሰወስቱም እኔን ይመርጣል እኔን ይመርጣል ሲባባሉ የአገር ሕዝብ እኩል ናችሁ አለ ። አሁንስ እንዲህ እናድርግ ከማያውቁን አገር ሄደን የማያውቀን ሕዝብ ይምረጠን ብለው ወደሌላ አገር ለመመረጥ ተጓዙ ፡ ከሩቅ አገር ሂደው ሀያጅ እግር ከብዙ ሥፍራ ያደርሳል እያጣምና ከጭራቅ ቤት ገቡ የጭራቅ ቤት መሆኑን ሳያውቁት ያ ጭራቅ ደስ ብሎት መሣ- ሯቸውን ተቀብሎ ዘመዶቹን ጠርቶ ቀቅሎ ሊበላቸው የመቀቀያውን አፍላል ሲጥድ ባዩ ጊዜ ይህ ሰው ሊቀቅለን ነው በል አንተ ጠንቋይ መመረጥ ይህን ጊዜ ነው በላ አድነን አሉት ይኸማ የት ይሆንልኛል ዝም ብለን መቀቀል ነው እንጂ አላቸው ፤ በላ አንተ ጐበዝ ጀግና ነኝ ማለት ለሰው ጥቅም መሆን ዛሬ እኛን ከዚህ ጭራቅ እጅ ያዳንኸን እንደሆን ነው ቢሉት ተናንቄ እንዳልሞት መሣሪዬን ከጂ አስቀድሞ ወሰደው ዝም ብሎ መቀቀል ነው እንጅ ጉብዝና ዛሬ የት አለልህ አለው ።

በላ አንተ የተማርህ ብልህ ብልሃትና ጥበብ ዛሬ እኛን ከዚህ ከጭራቅ እጅ ያዳንኸን እንደሆን ነው አሉት ፤ ከዚህ እጅ ያዳንሁ እንደሆን መብለጤ አይደለም አላቸው ፡ አዎን መብለጥህ ነው አሉት ። ያ የተማረ ብልህ ተነሥቶ ለዚያ ለጭራቅ እግዚአብሔር ያሣይህ በሐገራችን ድርቅ ሁኖ እህል ጠፍቶ ሕዝቡ በረኃብ ሊያልቅ ቢሆን ከአንተ አገር እህል አለ ቢሉን ሕዝቡን ከጋራ ወደዚያ አስፍረን ካንተ ጋራ በለት በለት ፫ ፫ ሰው ለምግብህ እንሰጣለን አንተም በወርቃችን እህል አሽምተን ስንል ነው ተልከን ከሕዝቡ የመጣነው ብሎ ቢለው የት ነው ሕዝብ በል ይዛችሁኝ ሒዱ እኔም እህሉን አሸምታችኋለሁ ። እነሱም በለት በለት ፫ ፫ ሰው ለምበላው ይሰጡኛል ይዛችሁኝ ሒዱ እንማ ማል ብሎ መሣርያቸውን መልሶ ወደ መጡበት መንገድ ከጭ ራቁ ጋራ ሲሔዱ ከወንዝ ዳር ሲደርሱ ያ የተማረ ብልህ ያንን ጭራቅ አንገቱን አለውና ገደለው ። ያንተንም ጥንቆላ ነጥቄ ከቤቱ ያንን ጭራቅ አውጥቼ አመጣሁት ። ያንተንም ጉብዝና ነጥቄ ይኸውና ይኸንን ጭራቅ ገደልሁት ።

የኔ መማር የኔ ዕውቀት የሁላችሁንም ማደሯ ብላችሁ የያ ዛችሁትን አልጠቀለልሁም ወይ ቢላቸው አዎን ጠቀለልኸው አሉና ፤ ከዚህ በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ተመለሱ ትምሕርት ሲማሩ ከዳዊት በደረሱ ጊዜ ፡ አጽንዕዋ ለጥበብ ከመ ኢይትመ ዓዕ እግዚአብሔር ወኢትትሐጐሉ እምፍኖተ ጽድቅ መዝሙር ፪ ቁጥር ፲፪ ሲደርሱ ፡ ያ ጐበዝና ያጠንቋይ ። ወንድሜ ወንድሜ ተባባሉና የዚህችን ንባብ ትርጓሜዋን ሳናውቀው ለመሔድ አንገባም ብለው ሲተናነቁ ዕድሜያቸውን ጨረሱ ። ዕድሜን ከመማርና ከዕውቀት ጋራ ቢጨርሱት መልካም ነው ስል ለብርሃንና ሰላም አመለክታለሁ።

ቀኛዝማች አክሎግ ካሣ ።

መልካም እርዳታ ።

በብርሃንና ሰላም እየተመላለሰ ባውቶ ሞቢል አደጋ ያለቁትን ሰዎች አነበብሁና የመዛጋጃ ቤት ሠራተኞች ለእግረኞች የሚሆን የመንገድ ሥራ መጀመር ትዝ አለኝ ። እውነት ነው ይህን የመንገድ ሥራ ተረዳድተነው ቢሠራና ቢያልቅ ወንድሞቻችንን ባውቶ ሞቢል አደጋ ከሚመጣው ሞት መሠወራችን መሆኑን የሚዘነጋው ሰው የለምና እኔም ያቅሜን ያህል ለእግረኞች መንገድ ለሚሆነው ሥራ አምስት ብር እረዳለሁ ፤ ይኸንኑም እርዳታዬን ለመንገዱ ሥራ ዋና አስታዋሽ ለሆነው ላቶ ከበረ ኃይለሥላሴ በደረሰኝ አስረክቤአለሁ ።

ርእሰ ደብር አጽናፍ ሰገድ ዘመካነ ሥላሴ።

በሽታን ስለ ማቅለል ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ምስጋና ።

ይህነን ሐኪም ክቡር ዶክቶር ሐነርን ስለ ሕዝባቸው ጥቅም ብለው ስለ አመጡ ምስጋና ይገባቸዋል ። እኔ ፯ት ዓመት ሙሉ ብርቱ በሽታ ይዞኝ አልሞት አልድን ብዬ ተስፋ ቆርጬ ነበር ። የክቡር ዶክቶር ሐነርን ዜና ሰምቼ ከለቀምቴ ወደ አዲስ አበባ መጥቼ ከደዌ (በሽታዬ) ተገላግዬ ዕድሜ ላልጋ ወራሽ እያልኩ ለዘላለም አመሰግናቸዋለሁ ። ምስጋናዬንም ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እገልጻለሁ።

ወይዘሮ አየለች ለቀምቴ ።

ስለ ኃዘን ።

የትምህርት ቤት መዘጋት ።

ስለ ብፁዓዊ አቡነ ማቴዎስ ዕረፍት ኅዳር ፳፮ ቀን ሰኞ የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ስለ ኃዘኑ ተዘግቶ ዋለ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ያንደኛውም ሆነ የሁለተኛው ዓመት የብርሃንና ሰላም ዋጋ ላልከፈሉ ማኅበረተኞች ዋጋውን እንዲከፍሉ በማክበር እናሳስባቸዋለን ።

የሊቅ ምክር ። ሞትን ስለ ማሰብ

ወዳጄ ሆይ ከሞትህ በኋላ ማን ያስብሃል ። ስላንተስ ጸሎት ማን ያደርጋል ፡ ወዳጄ ሆይ የምትሞትበትን ጊዜ አታውቅምና ማድረግ የምትችለውን ሁሉ አሁን አድርግ ፡ ደግሞ ከሞትህ በኋላ የሚመጣብህን አታውቅምና ጊዜን አግኝተህ ሳለህ የማይጠፋን ባለጠግነት አጠራቅም ፡ ከመዳንህ በቀር ምንምን አታስብ ፤ የእግዚአብሔር የሆነውን ብቻ ፈልግ ፤ ከሞትህ በኋላ በዘላለማዊ ድንኳን እንድትገባ እግዚአብሔርን አክብር ሕጉን እየተከተልህ እርሱን ብቻ ወዳጅ አድርገው ።

ማስታወቂያ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሙዋቸው በማተሚያ ቤታቸውም የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው፥

የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው ፤	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው ፤	፲	ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ ።	፭	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውርጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር ።	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፫	ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው ፤	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው ።	፪	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት ፤	፩	ብር
ያማሪኛ ሰዋሰው ።	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ፤	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን ።		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
ወዳጄ ልቤ ።		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ ።		አላድ
ያማሪኛ ፊደል ፤		ሩብ
አሳብና ምኞት ፤		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት ።		ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር ።	፪	መ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ፤	፩	ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰኔደቅ ዓላማ ያጌጠ ።	፩	ሩብ

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ ከጕሙሩክ ከየታጁሮቹ ቤት ወደ ለጋር እቃ የሚያመላልስ በሌላም ሥፍራ በከተማ ውስጥ መንገድ በተበጀሁሉ በቀላል ዋጋ የሚያመላልስ ሐዲስ ከሚዎን ሞቶመቢል የፊታውራሪ ዴሬሳ መጥቷልና እቃ ለማስጫን የምትፈልጉ ሰዎች ከሙሴ ሳሙኤል በሂስኒልያን ጋራ እየተነጋገራችሁ በደኅና ዋጋና በእምነት ልታስጭኑ ትችላላችሁ ።

ኤን ቤ ኔዱሪአን

በዚህ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ በማዘጋጃ ቤት አጠገብ በጎርጎርዮስ ቤት ፊት ለፊት ከወደ ላይ ወገን አዲስ መደብር ከፍቻለሁ ።

በዚሁ መደብር ውስጥ ለጊዜው አሁን ያለው ማለፊያ ዓይነት የጀጠባብ ጨርቅና ጥሩ ጥሩ ባርኔጣ ድርብም ነጠላም ሽቶና ሎሲዮን ኦዶኮለኝ አምበሬጭቃ በያይነቱ የሽቶና የኦዶኮለኝ ማርከፍከፊያ የግድግዳ ሰዓት ትልቅ የወሐ ፊልትር የቡና ከዳ ካውያ የልብስ መተኮሻ ብርጭቆ በያይነቱ በጋዝ የሚነድ ምድጃ ስንና ብርት ሳህን ዘይት ይህ ሁሉ በያይነቱ አለ።የሱቁን ስፍራ ለማመልከት ነው እንጂ ከዚህ ያልተጻፈ በያይነቱ ብዙ ዕቃ አለና ለመግዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ቢመጣ የፈለገውን ያገኛል ። የቃውም ዋጋ ከሁሉ ሱቅ በታች ርካሽ ነው ።

Berliet



ቤርሊዬ ኦቶሞቢል

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የቅኝ አገር ሶማሊ ቤርሊዬ ኦቶሞቢልና በእንጨት የሚሄድ ካሚኦን በጠንካራነቱ በሁሉ ዓለም የተመሰገነ ዋና እኔደራሴ አርመናክ ዛማኒያን ከማዘጋጃ ቤት አጠገብ ወደ ፍል ወሀ መውረጃ።

ARMENAK ZAMANIAN

AGENT GÉNÉRAL

Pour l'Abyssinie et Djibouti

ማስታወቂያ

በጥሩ የፈረንሳዊ አገር ጨርቅ ለኢትዮጵያ መኳንንቶች የሚገባ በጥንቃቄ የተሰፋ ካባ ከሙሴ ፕሬቶ ዘንድ ይገኛል ቤታቸውም በእንግሊዝ ባንክ ቤት አጠገብ ነውና ለሚገዙ ሰዎች ሁሉ በማክበር እናስታውቃለን።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፶
3 me ANNÉE № 50

ሐሙስ ታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 15 Decembre 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ስፈስን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

እግዚአብሔርን መፍራት ።

እግዚአብሔርን መፍራት ከሞት ወጥመድ ለማምለጥ የሕይወት ምንጭ ነው ። (ምሳሌ ፲፬ ፳፯ ፡)

እግዚአብሔርን መፍራት ለምን ያስፈልጋል ? እርሱ አባታችን አይደለምን ? እንዴህ ያለጥያቄ በልብ ሊነሣ ይቻላል ከሁሉ አስቀድሞ ግን እግዚአብሔርን ስለ መፍራት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደ ሆኑ አልቀው የሚናገሩ ማስተዋስ ያስፈልጋል ። በሐዲስ ኪዳን በቅዱስ ጳውሎስ መጻሕፍት እንዴህ ያለ ንግግር ከሁለት ስፍራ ላይ ብቻ ይገኛል ። የሐዲስ ኪዳን አሳብ በዚሁ ነገር በ፩ኛ መልክት ዮሐንስ ምዕ ፬፤ ፲፯ ና ፲፰፤ ተገልጦ ይነገርለታል ፡፡ « እግዚአብሔር ፍቅር ነው ፡፡ በፍቅር ፍርሃት የለም ፍርሃትም ቅጣትን ያመጣልና የሚፈራም በፍቅር ያልሞላ ስለሆነ የሞላች ፍቅር ፍርሃትን ከሜዳ አውጥታ ትጥላለች ።"

በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን መፍራት ሲል የሥጋ ፍርሃት አይደለም የሚያስብ ። እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ባርያ ወይም ሎሌ በጌታው ፊት እንዲንቀጠቀጥ አይደለም ። ምሳሌ እንደሚለው ፤ እግዚአብሔርን መፍራት የሕይወት ምንጭ ነው ።ሌላው ፍርሃት ግን ሕይወትን ከሚያሠለጥን ይልቅ ሕይወትን አኰል ያደርጋል ። ቅዱስ ዳዊት ይላል ፤ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ብፁዕ ነው ፡፡ (መዝ ፻፲፪ ፡ ፩ ፡) በዚህ ትዩ ግን ሰው በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ሲገዛ ደስታን ከቶ አያገኝም ፡፡

እግዚአብሔርን መፍራት ግን በመድቄስና በመጨቄን ፈንታ ፍጥረታትን ያበረታልና ያጸናናል ፡፡ እግዚአብሔርን የምትፈሩት ሁሉ በርሱታመኑ እርሱ በርሱ ለሚታመኑ ረድኤትና ጋሻ ነው ፡፡ (መዝ ፻፲፫፤ ፲፩፤) ይህ የምሳሌ መጽሐፍም ይላል ፤ እግዚአብሔርን በመፍራት ብርቱ ጽናት አለ እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ልጆችም መጠጊያ ይሆናቸዋል ። (ምዕ ፲፬ ፡ ፳፮ ፤) ስለዚህ እግዚአብሔርን መፍራት የመታመንና የጽናት መንገድ እንደሆነ ያመለክተናል ፡፡ እንዴህ ቢሆን ከዚያ ከሚያስጨንቅ ኖሮ ሕይወትን ከሚያስከፋና ከከንቱ አሳብ በክፎች መናፍስት ኃይል ከማንቀጥቀጥ ስንት እንድናለን ።

እነዚያ ዕለት ዕለት በሚገጥማቸው መከራና ፈተናዎች ዘወትር የሚንቀጠቀጡየጀነራል ዱሮአ(Druot) ሃይማኖት ሊገዛቸው ያስፈልጋል ፡፡ ንጉሠ ነገሥት ናፓልዮን በጦር ጊዜ ስለብርቱ ድፍረቱ ያመሰገነውን ፡፡ ጄኔራሉ እንዴህብሎ መለሰ ፤ "ጃንሆይ እኔ እግዚአብሔርን ብቻ እፈራለሁ ። ናፖልዮንም እንዴህ ብሎ መለሰለት ፤ ስለዚህ እከነዎ እንዲህ ጀግና መሆንዎ" ። እርግጥ ነው የእግዚአብሔር ፍርሃት የሕይወት ምንጭ ነው ፡፡ በሕይወት ነገሮች በላይ የእግዚአብሔር ፈቃድና ኃይል ይይዛል ። ከሐዋርያም ጋራ ይፎክራል ፤ እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ የሚነካን ማን ነው? (ሮሜ ፰ ፡ ፴፩ ፤)

እግዚአብሔርን መፍራት ሐጢአትን በመጥላት ይገለጣልና ስለዚሁ ነው የሕይወት ምንጭ የሆነው ። የሥጋ ሕይወት ወይም የባሕርይ ድህነት ሲሆን ሁሉ ጊዜ ይህ ክፉ አለ። ሕማም ወይም ሐጢአት። እንግዴህ እግዚአብሔር መፍራት ክፉውን መጥላት ነው ።(ምሳ ፰፤ ፲፯) ይሄው ምስክር በሌላዎች በብሉይኪዳን መጻሕፍት የጸና ነው ። የኢዮብ መጽሐፍ (ም ፴፰ ፡ ፳፰ ።) እንዴህ ይላል ፤ እንሆ እግዚአብሔር መፍራት ጥበብ ነው ። ከሐጢአትም መራቅ ማስተዋል ነው ። መዝ ፴፬ ፤ ፲፩ ፲፯ ልጆቼ ሆይ ኑስሙኝ እግዚአብሔርን መፍራት አስተምራች ኋለሁ ። መላስህን ከክፉ ከንፈሮችህንም ሽንገላን ከመናገር ክልክል ። ከክፉ ራቅ መልካምንም አድርግ። ሰላምን እሻ ተከተላትም። የእግዚአብሔር ዓይኖች ጻድቃንን ያያሉ የእግዚአብሔር ፊትግን (በቁጣ) ክፉ በሚያደርጉ ላይ ነው

ትምሕርት

ትምሕርት ሁሉን ይጠቅማል እንጅ ማንንም አይጐዳም ። ለህብታሞች ለድሆች ለሁላቸው ይጠቅማል ። ሠራተኛም ቢማር ሥራውን ያስከብራል ። በራሱም ብርቱና ነፃነት ያለው ይሆናል ። ጥቂት ብቻም ቢማር አይበቃውም ። እንዲህ ቢሆን ምን ይሆናል ? ያን ተምሮት የነበረውን ያጠፋል ። እንዲህ የሆነ ሰው ምንም ትልቅ ቢሆን በጓደኞቹ በተማሩት ማኸል እንደ ልጅ ይቈጠራል ። በመጨረሻም የሚያነብለትና የሚጽፍለትን ይፈልጋል ። በገዛ ሥራውም የሚመራውና የሚያቃናው ምክርም የሚሰጠው ግድ ያሻዋል ። ብዙ ዘመናትም በኖረበት መጠን የባሰ ደንቆሮ ሆኖ ይቀራል ። ከዚህ በኋላ እንዲህ የሆነ የሚማር በትን ጊዜ መቼ ያገኝ ይሆን ?

ብዙዎች አይመቸኝም ጊዜም የለኝም አይሆንልኝም እያሉ ያመኻኛሉ ። በጎ ፈቃድ ያለው ግን ሁሉን ይችላል ። ብዙዎች በዓለም በትምሕርታቸው ሆነ በጥበባቸው ወይም በሥራቸው የተመሰገኑ ። በሥርዓት ከተማሪ ቤት ሳይገቡ የተማሩ ናቸው ። የጊዜ ለጋስ ግን አንዳች ነገር ሳያገኝ ይቀራል ። ማንበብ ጊዜን ማጥፋት አይደለም ። ደህና ዕውቀት ያለው ሠራተኛም ቢሆን የራሱን ክብር ያተርፋል ። በሚያውቁት ዘንድም ይከብራል ። ድንቊርና በምትሸሸበት ልክ ጥበብ ትመጣለች ። ብልህ መሆንም የሚበዛ ጊዜ ደስተኛ መሆን ነው ።

ማንበብ እጅግ ደግ ነገር ነው ። ማንበብ በሌላዎች ሰዎች አእምሮ በኩል የገዛ ራሱን አእምሮ ማበርታት ማለት ነው ። ሌላዎች የሰሙትን መስማት ከተሳቀቡት ጋራ መሳቀይ የሌላዎች ሰዎች ደገኞችን ሥራ ማወቅ ማለት ነው ፡ ከኛ በፊት የነበሩትን ሰዎች ተሞክሮዋቸውን መማር ማለት ነው ።

በሕይወት ልንኖር ሰውነታችን ጤናማና የሚበቃ ምግብ ዕለት ዕለት እንዲያስፈልገው እንዲሁም አእምሮዋችንና ልባችንን በመልካም ንባብ ሊመገቡ ያስፈልጋቸዋል ። ማንበብ የሚያውቅ ተራራን እንደሚወጣ ሰው ነው ። በወጣበት ልክ የሚያየው ነገር እየሰፋለት ይሔዳል ። ሊማር ብሎ ዘወትር የሚያነብ ዕለት ዕለት ወደ ከፍታ እንደ መውጣትና ብዙዎችን ነገር እንደማየት ነው ። አንድ መጽሐፍ ማንበብ ወዳጅን እንደገና ማየት ነው ። ብዙ የሚያነብ ብዙ ያውቃል ብዙም ይከብራል ። ቢሆን ግን መልካም አድርጎ ማንበብ ብቻ አይበቃም ። ደግሞም ደገኞችንም መጻሕፍት ማንበብ ያሻል ፡ አእምሮን የሚመግቡ ልብን ከፍ የሚያደርጉ ደገኞችንም አሳቦች የሚያነቃቁ መጻሕፍት ሊሆኑ ይገባል ።

ትንንሾች ልጆች ክፉውንና መልካሙን ሊለዩ አይችሉም እንዲሁም በአእምሮ የደኸዩም እንደ ሕጻናት ናቸውና የሚጠቅማቸውን በጣም ሊያስተውሉ አይቻላቸውም ። ሰው በበረሃ የማያውቀውን ፍሬ ወድቆ ቢያገኘው የሚበላ መሆኑን ባያውቅ እንዳይጐዳ አስቀድሞ ይጠይቃል ። እንዲሁም መጻሕፍቶችን መምረጥ ያስፈልጋል ። ብዙ መጥፎ መጻሕፍት አሉ ። ክፎችንም መጻሕፍት ማንበብ ለነፍስ እንደ መርዝ ናቸው ክፎችን መጻሕፍቶች በማንበብ በሥጋቸውና በነፍሳቸው የጠፉ ብዙዎች ናቸው ።

የከበሩ መጻሕፍቶች አሉ ብዙ ከፍ ያለ ትምሕርት የሚገኝባቸው ። የሰውን አግቦ ለእግዚአብሔር በሚደርስ የልጅ ለወላጆቹ የሕዝብ ላገሩና ለመንግሥቱ ባለ ትዳር ለትዳሩ ወታደር ለሰንደቅ ዓለማው ሰውም ለገዛ ራሱና ለባልንጀራው ሊፈጽመው የሚገባውን የሚያስተምሩ ። እንዲሁም የተፈጥሮውን ሁኖታ ነገር የእንስሳ ወገን (ዞኦሎጂ) የአትክልት (ቦታኒክ) የብረት ወገን (ሚነራሎጂ) የከዋክብት (አስትሮኖሚ) የምድር መለኪያ (ጂኦሜትሪ) የሒሳብ (አሪትሜቲክ) የፍልስፍና (ፊሎሶፊ) የሐኪምነት (ሜደሲን) የጤንነት (ሀይጂን) የኢንዱስትሪ የመካኒክ የታሪክ (ሂስቶሪ) የዓለምና የቤተ ክርስቲያን ። የእግዚአብሔር ቃል ትምሕርት (ቴኦሎጊ) እንዲሁም የሚመስሉ ብዙ ትምሕርት አሉ ለሰው የሚጠቅሙ ። እያንዳንዱ በተፈጥሮ እንደ ተሰጠው ጸጋ ሊሰለጥንባቸው የሚገባው ። የሕዝባችን ወጣቶችም አንዱ በዚህ ሁለተኛውም በዚያ ሌላውም በሌላው ዓይነት ትምሕርት ቢሰለጥኑ ሕዝባችን እጅግ በተበረከ ። ዕውቀቶቹን የኛ የገዛ ራሳችን ሳናደርጋቸው በብድር ብንኖር በብድር ብን ሰራ ከቶ አንጠቀምም ። እንግዴህ ኢትዮጵያችንን በውነት ከሚጠቅሟት አንደኛው መጀመሪአው ነገር ልክ የሌላቸው ወጣቶች በስጦዎታችው በጣም እንዲሰለጥኑ ማድረግ ነው ።

ሁሉ ነገር እንደዚህ ያለ ሥራ ከቶ ሊጠፋ አይችልም ። ለዚሁ ትምሕርት ሁሉ ግን ዓይነተኛው መሠረት እንዳለው አለመርሳት ። የመጻሕፍት መጽሐፍ፣ራስ መጽሐፍ አንድ ብቻ አለ እርሱም መጽሐፍ ቅዱስ ነው ። የሕዝብ አኗኗር በዚህ ብቻ ሊመሠረትና ሊቆም ይገባዋል ። መጽሐፍ ቅዱስ የማይከብርበትና የማይሠለጥንበት ሕዝብ ጠፊ ነው ። ይህ መጽሐፍ የአምላክ ቃል ስለሆነ ትልቅ ኃይል አለው ፡ ሌሎች መጻሕፍት ምንም መልካካሞች ቢሆኑ በሥጋዊው ነገር ብቻ ይጠቅማሉ ። በሜጻዊው በሚደርስም አካሔድን የሚያሳምሩ አሉ ከልብ የሚደርስ ለአሳብ ለፈቃድ ሊቀድስና ሊያነጻ የሚችል ኃይል ያለው መጽሐፍ ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ በተቀር ሌላ የለም ። እንግዴህ ከሚያነቡቸው መጻሕፍት በላይ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነቡና የሚመረምር ብፁዕ ነው ።

ከሁሉ ይበልጥ ያገር ነገር ይቆጫል ያንገበግባልም ።

በኢትዮጵያ ድንበርና ዙሯዋን ባለው በረሃና ለምለም አገር የዝሆን ጥርስ ወርቅ ላስቲክ እጣን ይህንንም የመሰለ ብዙ ጥቅም የሚገኝበት አገር መሆኑን ሁላችሁ የምታውቁት ነው ፡ ስለሆነም የውጭ አገር ሰዎች እየመጡ ሰው ያለበትን አገሬውን ባላባቱን በጥቂት ነገር እየደለሉ አኩሌታውንም ደከም ያለውን በጉልበት ጠፍ የሆነውንም ዝም ብለው እየያዙ ከገራቸው ተርፈው በዚህ በረሃ በማያውቁት አገር ገብተው ተርበው ተጠምተው ተንገላተው ሕይወታቸውን ላረመኔ እየሰጡ ለመንግሥታቸው ይረዳሉ ይሞታሉ ። ምይልቁንም እገሌ በእንደዚህ ያለ አገር ሄዶ ሲያቀና ለመንግሥቱ ሞተ እንዲባል ምኞቱን ፈቃዱ ነውና ሌሎቹም ባገራቸው ያሉት በእንደዚህ ያለው አሟሟቱ እገሌ አገር ሲያሰፋ ለመንግሥቱ ሞተ ሲባል በዚህ ሰው ያለ መጠን ይቀናበታል ይባላል ። እስቲ እኛም ይህን እንመልከት ለመሆኑ

ስንኳንስ ለማድረግ የሚያስብና የሚመኝ ይኖር ይሆን ይልቁንም ለመከለል አንድ አንድ የታመኑ ሰዎች ታዘው ቢሄዱ ተካለው ባንዳንድ ዛፍ ብረት እየመቱ ዝም ብለው ከመመለስ በቀር እድንበር ላይ አንድ ዋና የጠነከረ የወሰን ምልክት ስለ አላደረጉ በየዓመቱ ይቆረሳል የዚያም አውራጃ ገገር ባመት ባመቱ ግብር ለመቀበልና አገር ለመጐብኘት ይሄዳልና ከፊተኛው ግዛቱ ብዙ መሬት አልፎ ጥቂት ቤቶች ተሠርተው ዘበኛ ቆሞበት ይገኛል ዝም ብሎ ቆይቶ ከግዛቱ በመጣ ጊዜ እንደዚህ ሆኖአል ሲል መናገሩ አይቀርምና ደግሞ እላይ እንደተባለው እገሌ ወርደህ ተከለል ይባላል እንግዲህ ሰው መቼም ሁሉም እኩል ሥጋ የለበሰ ነው ያገርን ፍቅር ያለ ማወቅ ነው እንጂ እንግደያውማ ለበረሃውስ ማባላችን ልንጠነክር ነበር ዳሩ ግን ምንም ጐበዝና ጠንካራ ቢሆን ያገር ፍቅር ካላደረበት ከንቱ ነው።ደግሞ ሥጋውም ቅቤውም የሚተርፈውን እዚያው አይሆንምን ከከተማ ሥራ ፈቶ ከመኖርም ላገሩና ለመንግሥቱ እድንበሩ ላይ አገልግሎ የማይረሳ ስም መተከል አለበት።አማካሪና ሹማምንትም እንደዚህ ያለውን ሁሉ በቶሎ ብላችሁ ልታስቡበት ያስፈልጋል።አንድ ሰው ብቻ እስንት ይሆናል ሁሉም በተሰጠው አገርና በተሾመበት ሥራ ይህንን ተሾምኩ እያሉ ተመኩራት፡ እንደክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ እንደክቡር ከንቲባ ነሲቡ እንደነ አቶ ገብረ እግዚአብሔር ለአገራችሁ ብትደክሙና በእውነት ብትሰሩ እናታችሁ ኢትዮጵያ ምንኛ ፈጥና በገነነች ነበር ። እነሆ አሁን በጂጂጋ አውራጃ በልዑል ተፈሪ መኰንን ፈቃድ የሐረርና ያውራጃዋ ሁሉ ደጃዝማች እምሩ እስከ ድንበሩ ባ፲፱፻፲፩ ዓ ምሕረት ወርደው አይተው እድንበሩ ላይ ከተማ እንዲሰራ የጂጂጋውን ሹም አዘው ተሰርቶ ስሙም ተፈሪ በር ተብሎ ተሰይሟል።እንዲሁም በየግዛታችሁ ባላንጣ ያለባቸሁ ገጆዎች እንዲህ ማድረግና መንቃት የሚያስፈልጋችሁ ነውና እናሳስባችኋለን ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ፡እኔ ትንሽ አንድ ድሃ ልጅ ነኝ ነገር ግን ይህንን ለመጻፍ ያሳሰበኝ አንድ አንድ ወንድሞቻችን በንግድ ምክንያትና ላገረ ገዢ እያደሩ አሽከር እየሆኑ ሂደው ኖረው የዚሁኑ አገር አኳኋን ብዙ ጊዜ እየነገሩኝ መቼም የአገር ነገር ለጌታውም ለድሃውም እኩል ያስቆጫልና ብዙ ጊዜ እንዳቅማጌ አዝኜ ነበረና ሁለተኛም ብርሃንና ሰላም በሶስተኛው ዓመት በ፵፮ ቁጥር ከ፫፻፷፩ ገጽ እስከ ፫፻፷፪ ስላገር ፍቅር የተጻፈውን አይቼ ልቤን ስለ ነካኝ ነው ። ሽማግሌ ሲተርት ጨው ለራስህ ብትል ጣፍጥ ባትጣፍጥ ግን ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሃል ይላልና አሁን ዛሬ በድንበር ላይ ካላጠነከራችሁና ካላሰባችሁበት ሰፊ አገር መግዛት ለለመዳችሁት ወዮላችሁ እንጂ እኛማ ድሆቹ ምንም ብንቆረቆር ሰሚ እናገኛለን ብለን አንጓጓም ። ነፋስን እንደመከተል ያለ ነው።መክብብ ም፩ ቁ፲፯ ላለፈውም መሰረቷ ለኢትዮጵያ ተፈሪን የመሰለ ልጅ የሰጣት አምላክ ያውቅላታል ።

ታላቁ አጼ ዳዊት በትንቢት ሲናገር ። ስለ ኢትዮጵያ እንዲህ ብሎ ነበር ፡፡ እዴሃ ታበጽሕ ኀበ እግዚአብሔር ። ከዚያችም ይወጣል የሚጐበኝ አገር ። ጥበብ የሚሸምት ድንቁርና የሚያበር ፡፡ ፈጸመው ተፈሪ ይኸን ሁሉ ነገር ።

እኛም ተረዳነው ትንቢቱ ደረሰ ። ተፈሪ ተጉዞ እየገሰገሰ ፡፡ ነጻ አደረገ አገሩን የልቡ ደረሰ ፡፡ እነምቀኝነት ምክራቸው ፈረሰ ፡፡

ያልጋ ወራሽ ኢጎብ ደስ ቢለኝ ላገሬ ፡፡ ሳይበዛ በመጠን በጥቂት አሳጥሬ ፡፡ ይህንን ጽፌያለሁ የሺጥላ ማሬ ።

የኢትዮጵያ ጉዳት።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች።ብርሃንና ሰላም የሚመክረውን ምክር እየሰማሁ ለልቤ ደስ የሚያሰኙኝና የሚያንቃቃኝ ስለ ሆነ በድንቁርና፡ማዕበል ታውኮ፡የነበር፡ልቤ ከደስታው የተነሣ ቢንቀሳቀስ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል ላስታውስ ወደድሁ ፡፡ እንዲሁም ለወደፊቱ ላገራችሁ ልጆች እንድታነቃቁዋቸውና እንድታበረታትዋቸው ምሉ ተስፋ አለኝ። አሁንም እንደ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት ዳግማዊ ፀሐይዋ ላገራቸው ምኞት በኢትዮጵያ ብርሃንና ሰላም የተባለ ጋዜጣ ከወጣ በደመቀ ብርሃን ለመመላለስና በሰላም ለመኖር የሚወዱ ሰዎች በያገሩ ውስጥ እጅግ ብዙ ናቸው ። እኒህ ሁለት ቃሎች እንደ አባትና እናት ሁነው ይታዩኛል አባትና እናት የተወደዱ ልጆቻቸውን በእንዴት ያለ ፍቅርና መከባከብ ሲያሳድጉዋቸው ለጥቅማቸው እንደሚያስቡላቸው አውቀው በፍቃዳቸው ካልተመላለሱና ካልታዘዙዋቸው ድካማቸውና ምክራቸው ከንቱ ሁኖ እንደሚቀር የታወቀ ነው ሰለዚህ ብርሃን አባታችን አሁን ተነሡ ልጆች ጨለማን ድል አድርጌላችኋለሁ ይለናል፡፡ቀጥላም እናታችን የምሥራች ልጆች ሆይ ደስ ይበላችሁ በብርሃኑ ላይ ሰላም ልጨምራችሁ እንግዲህ በሰላም ተቀመጡ በገራችሁ የወላጆቻችሁ ምክር እየሰማችሁ ለዘላለም ኑሩ ተስማምታችሁ ከተስማማችሁ ጠላትማይደፍራችሁ ሁሉ ቀን ታጥቃችሁ አገልግሉዋት ኢትዮጵያ እናታችሁ፡እንግዲያስ እኒህ አገልጋዮች የተባሉ እነማን ይሆኑ ለማገልገል ሁሉም በያቅሙ በቅናትና በፍቅር ሊያገለግል የተገባ ነው ዳሩ ግን አብልጠው ሊያገለግሉዋትና ሊያለሙዋት የሚገባቸው ችሎትም ያላቸው መኳንንቶችና አገረገዦች ናቸው ። በሌሎች መንግሥቶች ግን እንኳን መኳንንቶችና አገረገዦች ማንም ቢሆኑ ትንሽ አቅምና ጉልበት ካገኙ ባገራቸው መታሰቢያ ትተው ስማቸው በዚያ አስጽፈው የማይሞት ስም ሆነው በየዓይነቱ ላገራቸው ጥቅም የሚሆን አስርተው የሚሞቱ በጣም ብዙ ናቸው።ምንም ቢሞቱ ስማቸው በዚያ ያሰሩትን ሥራ ተጽፈዋልና።እንዳልሞቱ ለዘላለም እየተመረቁና እየተመሰገኑ ይኖራሉ እንደዚህ ያለሥራ አለ ፊተኛው አርበኛ ክቡር ራስ ናደው የልዑል ተከተይ መሆን ባገራችን ገና አልተለመደም ነገር ግን ለወደፊቱ እየተለመደ እንዲሔድ ብርቱ ተስፋ አለኝ ፡፡ ክቡራን አገረገዦች በእግዚአብሔርና በመንግሥት ፍቃድ የተሰጣችሁ ሥልጣን የታመኑ እረኞች በጎቻቸውን በጥንቃቄ እንዲያሰማሩ እንዲሁም ሕዝባችሁ በየወገናችሁ ልትጠብቅዋቸውና ልታሰለጥንዋቸው ይገባል።አገረገዦች የሚሰሩት በግራችንና በቀኛችን ብንመለከት ሕዝባቸው አለ አምላክ ፍቃድ አንድም እንዳይጐድልባቸው በያገሩ ሐኪሞች አቁመው የታመሙትን ታክመው

የተወለዱትንም በቤተ መንግሥት ተጽፈው የሞቱትንም በመጽሐፈ ሙታን ታትመው ያሉቱንም ተቈጥረው ሐብታሙን ድኃውን እየመኖርያው ተሰክቶ ምድርም ቢጠብ አከናው ነው በሰላም ያኖሩታል ፡፡

ይህም በሕዝባቸው ይቅርና በየቅኝውም ያደርጉታል ካንድ መንደር ወደ ሌላው ቅርብ አገር በትንሽ ነገርም ቢሆን አለ መንግሥት ፍቃድ ፍንክች ብሎ የሚወጣ የለም እንዲህ በማድረጋቸውም በሰስተኛው ዓመት ብርሃንና ሰላም በቁጥር ፵ በገጽ ፪፻፵፩ ባጤ ምኒልክ ተማሪ ቤት በትያትር ጨዋታ የተደረገ ምሳሌ እንደጠበቁ ያስረዳል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን መሬት የሰፋው ወደ እየስደቱ የሔደ ቁጥርም የለውም ይልቁንም አእምሮ ያለው አጥብቆም ለመረመረው አስተዳዳሪና ከልክይ ከማጣት የተነሣ ከማራ አይበል ከትግሬ ይልቁንም ከጎጃም በየዓመቱ በመጨመር ፈንታ የሚቀነሱብን ስንትና ስንት ሺ ናቸው ። ነገር ግን ተንኰለኛ ተኵላ ቀስ እያለ በጎቹን ከጨረሰ በኋላ እረኞቹንም ደግሞ ቤዛቸውን የሚያልፍላቸው አልቀዋልና የግድ የሚበላው ሲያጣ ወደ እረኞቹም ደርበስበስ ማለት አይቀረውም ፡፡

ሕዝባችን ከሐብታሙ ድሐው የሚበልጥ ምን ይሆን ብልሐቱ በወንጌለ ማቴ በም ፪ በቍጥ ፲፰ ድምፅ በራማ ተሰማ ልቅሶም ዋይታም ጩኸትም እድግ ራሔል ስለ ልጆችዋ አለቀሰች መጸናናትም አልተቻላትም የሉምና እንደሚለው እንዲሁ አሁን ኢትዮጵያ ይህን የሚያህሉ ልጆቹ በከንቱ ጠፉብኝ እያለች በኀዘን ያማረ ፊትዋን ጠቍሮ ለዘላለም ስታለቅስ ትኖራለች ይልቁንም ከ፲፱፻፫ ዓ ም ጀምሮ እስከ አሁን በየወሩ አንዳንድ ሺ ሰዎች እየሔዱ ላገራቸው ሳይሆን እንደ ቅጠል የሚረግፉበት ቦታውን ለይታ ታውቀዋለችን ፡፡ ?

በተቀረስ አገራችን በሐብትዋ ከሌሎች የበለጠች አየርዋም የሚስማማ ሳለች ሕዝብዋም ጠንካሮችና ጀግኖች ሳሉ በያገሩ ሐኪሞች በማጣትና እንዲህ እየሆኑ በማለቃቸው ሕዝብዋ በቁጥር ያነሰ ነው ብለው ያወሩላታል ። አገር እንዲለማና ሕዝብ እንዲጠነክር አገረገዦችና መኳንንቶች ለወደፊቱ እንዲያስቡለት በማክበር አስታውሳለሁ፤ ክቡራን አንባቢዎች ይህ ሁሉ መናገሬ ኢትዮጵያ አገራችን ከሁሉ ይልቅ ይህ ትልቅ ጉዳትዋ ሁኖ ሲታይብኝ ነው ።በትንሽ እውቀቴ ለማስታወስ የወደድሁና በስሕተቴ ሁሉ የከበረ ይቅርታችሁን እለምናለሁ ለዘላለም ትኑር እናታችን ።

ትንሽ ተማሪ ገብረ አብ ቢያድግልኝ ።

ማሰብ መናገር መሥራት ።

ያለፈ የያዝነው የሚመጣ ዘመን ታሪክ ።

ትልቅነትና ትንሽነት ።

የሰው አገሩ ምግባሩ እንደሚሉ ሁሉ የሰው ትልቅነቱ ቁም ነገረኛነቱ ትንሽነቱ ወስላታነቱ ነው ። ትልቅ ሰው ቁም ነገረኛ ሰው ሥራውም ሐሳቡም መልካም ነው ። መጥፎም ልሥራ ቢል አይችልም ። አስቀድሞ ውስልትናንና መጥፎ ሥራን ስለማያውቅ ልሥራም ቢል አያውቅበትም ። ትንሽ ወስላታ ሰው ሥራውም ሐሳቡም ሁል ጊዜ መጥፎ ነው ። ደግ ሥራ ልሥራም ቢል አይችልም ። ሐሳቡ ልምዱ ሁለንተናው በሐሰት መንገድ በክፋት እውቀት የተሰለፈ ነውና፤ሁል ጊዜ ሥራውና ሐሳቡ ክፉ ነው ። ነገር ግን ሁል ጊዜ እየዘርን ከነገር ፍች ላይ እንወድቃለን ። ይህም ግድ ሆነብን፤ ቁም ነገር መልካም ሥራ ውስልትናና መጥፎን ሥራ ለይቶ እስከ ስር ጫፋቸው ማወቅ የግድ ያስፈልጋል አለዚያ ግን ቋንቋ ለቋንቋ የማይተዋወቁ ሶስት ሰዎች በሐሳባቸው አንድ መንገድ ይዘው ለመሄድ እየወደዱ በንግግር አለመተዋወቅ ሐሳብ ለሐሳብ የተለያዩ መስለው እስከሞት ድረስ ስለመጣላታቸው ያህል ነው።

ለኔ እንደሚመስለኝ ሰው ቁም ነገረኛ ሊባል የሚገባው ከነገር ሁሉ በፊት የአገሩን የወንድሞቹን ጥቅም ከራሱ ጥቅም አስቀድሞ እንዳይበላሽ ባለው አቅሙ ሲጠብቅ እንደ እውቀቱ መጠን ባለው አቅሙ ለመሥራት ሲተጋ ነው ።እንደዚህም የሚሠራ ሰው መልካም ሠራ ስልጡን ነው ተብሎ ከሁሉ የበለጠ የክብር ስም ቁም ነገረኛ ተብሎ ሊጠራ ይገባዋል ። ወስላታ ከሚባል ደግሞ የራሱን ጥቅም ከሀገሩና ከወንድሞቹ ጥቅም አስቀድሞ አለዚያም የአገሩንና የወንድሞቹን ጥቅም ንቆ የኔ ጥቅም ይበልጣል ብሎ የሚሠራ ነው ። በጭሩ ደግሞ ቁም ነገረኛ መልካም ሠሪ፤ ወስላታ መጥፎ ሠሪ ነው ። ልብ በሉት ባለፈው ብርሃንና ሰላም ስልጡን ጥቅሙን ፈላጊ፤ ባለጌ ጥቅሙን የማይፈልግ ነው ብያችሁ ነበር ፡፡ ነገር ግን ያለፈውን ብርሃንና ሰላም ከዛሬው ጋራ እያነበባችሁ ምን ትሉ ይሆን ። የሆነው ሆኖ መልካምና መጥፎ ሥራ ምንድነው እንዴትስ ነው የሚሠራው ። ለዚህ ጥያቄ በብርሃንና ሰላም መልሱን ለመስጠት ብዙ ሰው ይህ ቀላል ነው ብሎ ለመጻፍ የሚቸኩለው ቁጥሩ ይበዛል ። አስበ መዝኖ የሚጽፍልን ግን ምንም ያህል አይገኝ ይመስለኛል ። የዚህንም ስለ ምን ለማወቅ የሚፈልግ ሰው እንዲረዳው ልማድ በሚባል ድንቁርና ባሕር ገብተን መዋኘት የለመድን ሰዎች ነጻነት በሚባል ሜዳ ወጥተው በግራቸው እንደሚሮጡ ሰዎች መምሰል ያስቸግራል ብየ ነው ። ነገር ግን ይህን የመሰለ ነገር እያፍታታ እያከናወነ ሊጽፍልን የሚችል ባለፈው ብርሃንና ሰላም ከዚያም ከዚያም እየዘለልኩ የጻፍኳቸውን ትልልቅና መልካም ሰዎች ታሪክ አኑዋዋር ትልቅነት ትንሽነት የዚችን ዓለም ደስታና መከራ የሚመረምር ብቻ ነው ፡፡ እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ሥራ የሚመራመር ሰው ይበጅም ይከፋም የተገራ የተጣራ እውቀት አለውና ከፍርድ ፍርድ ይበልጣል ። ከአሳብ አሳብ ይበልጣል እያለ ማመዛዘን ይችላል ፡፡ ለዚሁም ባጭሩ መልካም ሥራ እውነት ፍርድ ነገር ነው ። መጥፎም ሥራ ሐሰት ግፍ ነገር የሆነ ሁሉ ነው ። ይህንንም በመሰለ ነገር ኃይል ሆኖ የሚያናግረን እውነትነት ፍርድ ያልሆነ ነገር ሁሉ መልካም ነው ሊባል አይቻልም ። ሐሰትነት ግፍነት ያለበት ነገር ሁሉ የመጥፎ መጥፎ መሆኑ ውልውል የለውም ፡፡

እንግዲህ ቁም ነገር በመልካም ሥራ ከተፈታ መልካም ሥራ ደግሞ በውነት በፍርድ ነገር ከተፈታ ውስልትና በመጥ

ፎ ሥራ መጥፎ ሥራ ደግሞ በሐሰት በግፍ ሥራ ከተፈታ
ይህንን ነገር ልብ ብሎ መርምሮ የባዕድ አገር አይደለም ።
ባላገርም አይደለም ፤ የጥሮ አዳሪ ድኃንም አመል አይደለም ፤
ግንዘብ ያልቸገራቸውን በማዕርግ ላይ የተቀመጡትን ጌቶች
እኑዋኖርና አኳኋን ልብ ብሎ ሲያዩት እንዴት ሰውነታችንን
ይንቀው ምን ያህል የሰው ልጅ ወራዳ ከንቱ ፍጥረት መስሎ
ይታይ ። መልካም እድል ያለው ትልቅ ሰው ከሁሉ በፊት ነገር
እውነትን ይፈልጋል ፤ እውነትን ይከተላል ፤ እውነትን ይወዳል ፤
ዕለት ዕለትም ወደማትጠፋ ወደማታስንቅ ክብርና ንጽሕና
ጤናና ደስታ ወደ ሞላባት ከፍታ ቦታ እየተጠጋ ይሄዳል ።
እድለ ቢስ ትንሽ ሰው ደግሞ ልቡ ጠማማ እውቀቱ እድፍ
ሁለንተናው ወልጋዳ ነውና በማንኛውም ነገር ቢሆን ትልቁን
ፍጥረቱን ትንሽ እያደረገ ወደ ውርደትና ወደ መከራ የሚ
ገፋውን ሥራ ብቻ ነው የሚሠራ ከዚህም የተሻለ ለመሥራት
አይችል ። እንግዴህ ትልቅ ሰው ትልቅ ሥራ ይሠራል ። ትንሽ
ሰው ትንሽ ይሠራል ስላችሁ ረቂቅ ምሥጢር ያለውን
ቋንቋ ሁሉ ልብ እያላችሁ ተመልከቱ ። ጋዜጣ ነው እንጂ
መቸም መጽሐፍ አይደለም የምጽፈው ። ትልቅና ትንሽ ሰው
ስል ግዙፍ ቁመተ ረጅም ፤ ጎነ ሰፊ ወይም ጌታ ትልቅ ሹም
አለዚያም አጭር ቀጭን ድኃ ደካማ አይደለም ። ይህ ሁሉ ፍሬ
የለውም ። ትልቅ ሰው ትንሽ ሰው እንዴት ነው ብላችሁ
ለማሰብ የምትችሉት የዚችን ዓለም ነገር ማንኛውንም ሳትንቁ
ከባድና ቀላል ነገር ሳትሉ ሁሉንም በጠቅላላው ማየት ነው ።
አባቶቻችን እንደሚተርቱት እባብ ቀጭን ነው ተብሎ ራሱን
እንደማይረገጥ ግፍም ሆነ ፍርድ ሥራ ቀላልና ከባድ ሆኖ
በአሳባችሁ እንደሚገባ ታገኙታላችሁ ። በቅጡ ልብ እንድትሉ
ት ፍርድ ሥራ መሥራት ነው ። ግፍ ሥራ መሥራት መዋረድ ነው
ኩሩ ሰው በሰው ፊት እየኮራ ለብቻው ሲሆን ወራዳ አይደ
ለም ። ሁል ጊዜ እንደኮራ ይቀመጣል ። ወራዳም ሰው በሰው
ም ፊት ሆነ ለብቻው ሁል ጊዜ እንደተዋረደ ነው ። ግን
ሰው አለ የለም እያለ የሚኮራና የሚልከሰከስ የውርደት
ውርደት በሽታ የያዘው ነው ።

እውነትና ሐሰት ፤ ሕይወትና ሞት ናቸው ። ፍርድና ግፍ
ሥራ ጽድቅና ኵነኔ ናቸው ፤ ብልህ ሰው ትልቅ ሰው ምንም
ቢቸግረው ሞትና ኵነኔን ለራሱ ይቅርና ለሰው አይመኝም ክፉ
ትንሽ ሰው ደግሞ ወዶን አይደለም እድሉ ነው ሞትንና ኩነኔን
ከጡዋት እስከማታ እንደ ትልቅ ብልጥግና አጥብቆ ይፈልጋል ።
ይህም ደመ ነፍስነት ነው ። ብልህ ቁም ነገረኛ ሞኝ ባንድነት
በመልካም መንገድ ይሄዳሉ ። ወስላታ ተንኮለኛ ክፉ ልበጠማማ
ባንድነት በመጥፎ መንገድ ይሄዳሉ ። የፊተኞቹ መልካም መጽ
ሐፍ መልካም መብራቶች የሚአምሩ ነገሮች ናቸው ። የኋለኞቹ
መርዘኛ እሾሆች ክፉ እንቅፋቶች የተንኮል ምንጮች የሰው
አተሎች ማለት እውነተኛ አጋንንቶች ናቸው ። እነኝህንም
ከመሰሉ ሰዎች ተጠንቅቆ መጠበቅ እርቆም መሸሽ ያስፈል
ጋል ። ይህ ሁሉ ሆኖ እስከሞት ድረስ የሚአሳዝነኝ አንድ
ነገር አለ ይህም እንዲህ ነው ።

የሰው ልጅ ልብ ብሎ አንድ ባንድ ሲመረምሩት በማንኛ
ውም ዓይነት አኑአኖር የሚቀመጥ ሰው ቢሆን እንደ ልበ ቸል
ቅንነቱና ልበ ትንሽነቱ መጠን ይደግ ይነስ እንጂ የስስት መንፈስ
ያላደረበት ሰው በዚህ ዓለም ይገኝ አይመስለኝም ። በዚሁም
ምክንያት ብዙም የተማረ ደግም ክፉም ሞኝም ሰው ሳይቸግ
ረው ሰበብ ሳይኖረው ያላንድ ጥቅም ብዙ ጊዜም ይልቅ ጥቅ
ሙን የሚያጠፋ ነገር እየሆነ ብቻ ተፈጥሮ ባሕርይ ስለሆነበት
የስስት ሥራ ይሠራል ። የሰው ልጅ የስስት መንፈስ በተፈ
ጥሮ ባሕርዩ አላደረበት ቢሆን መከራ መች ይታወቀው ነበር
የድንቁርና የክፋት የመጥፎ ነገር ሁሉ ምንጭ ስስት እንደሆን
ማነው ልብ የሚለው ። የስስት ዋናውን ምንጭ ብናገረው ደስ
ይለኝ ነበር ነገር ግን ልማድ የሚሉ ድንቁርና እንጎላችንን ባ
ርያ አድርጎ ስለ ገዛው ለአሳቤ የሚሰማውን የሚታወቀውን
ደፍሬ አልናገረው ብቻ ነገርን በውቀት ሊመራመር ለሚፈልግ
ሰው በሥጋዊም መንገድ ሆነ በመንፈሳዊ መንገድ በማንኛ
ውም ዓይነት ሥራ የሰውን ልጅ አሠራር አነጋገር አስተሳሰብ
ሲመለከቱት የሰው መንፈስ ሁሉ ጊዜ አዘምብሎ ያለው ወደ
ስስትና መቀናናት ነው ።

ደግሞ ማንኛውንም ነገር በንጹሕ ልቡና በረቂቅ ምስጢር
ልብ ብለው ሲመረምሩት አንድም መልካም ነገር ያለ አይመ
ስል ይህም መሆኑ ሰው በዚች ዓለም ላይ ከንቱ ነው ለዚህም
ምሳሌ አንድ መልከ መልካም ወጣት ጕበዝ እንደሚገባ አጊአ
ጊጦ በመንገድ ላይ ሲወዛወዝ አንድ መልከ ጥፉ ትል በመንገዱ
ላይ ቢገጥመው አለመጠን እንዲጠየፈው የታወቀ ነው ። ነገር
ግን ለኛ እንደሚመስለን ያ ትል ደመ ነፍስ ነውና ስለዚህ ምን
ያህል የሚአስጠይፍ መሆኑን አያውቅም ያውቅ ቢሆን ግን የ
ሚጠየፈው ሰው ሲመጣ በየ ጊዜ ተሰውሮ ማሳለፉ አይቀርም
ነበር ። ግን ይህ በሰውና በትል ስለ መሰልኩት ሰው እርስበርሱ
ሳይሰራራው የቀረ አይመስለኝም ። የተዋበም ሰው ይሁን የተ
ናቀ የሰው ልጅ በማነኛውም በኩል መጨረሻው ከንቱ ነው ።
በዚች ዓለም የሚቀመጣትን እርምታህል ጊዜውን በደስታ
በመልካም አኑአኖር እያስጌጠ ቢአሳልፋት አለ ድረስ ለሱም ከ
ሁሉ ነገር የሚበልጥበት ሞገሱና ክብረቱ ነው ለወራሾቹም አስ
ቀድሞ መማሪያ ቀጥሎም መከበሪያና መኩሪያቸው ነው ። አለ
ዚያማ የሰው ልጅ እንኳንስ ክፉ ሥራ ሠርቶና እንዲያውስ ቢ
ሆን መች የሚአኮራ ፍጥረት አለው ። የሰው ልጅ ፍጥረት
በዚች ዓለም ከምናየው ተንቀሳቃሽ ፍጥረት ሁሉ የከፋ ነው
ይህን የማያምር የተዋረደ ፍጥረቱን አስጊጦ አስከብሮ የምያስ
ቀና የሚአደርገው ወይም በሚአጸጽት ፍጥረቱን ላይ ጸጋት የ
ሚጨምረው መልካምና መጥፎ ሥራው ነው ።

አሁንም በአእምሮም ሆነ በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ላይ ስንት
ትልልቅ ሰዎች በሥራ ላይ የተቀመጡ ስለ አገራቸው ስለሕዝብ
ጥቅም ብዙ ምክር ይሠጣሉ ምክራቸው በዛም አነሰም አገርም
ሆነ ሕዝብ የሚጠቅም ሁሉም ማለት ተናጋሪውም ሰሚውም
በየበኩሉ እንደሚችለው እንዳቅሙ የሠራ እንደሆነ ነው አለ
ዚያ ግን ከንቱ ነው ። ይልቁንም ብዙ ሰዎች በሥራ ላይ እያሉ
ሊሠሩ እየቻሉ በክፋታቸው በልበ ጠማማነታቸውም ይሁን ወ
ይም እንደሚናገሩት ልክ ለመሥራት የበቃ እውቀት ሳይኖራ
ቸው ይሁን አለዚያም ደግሞ ባለመታደል ከመላሳቸው የሚ

ሰማማ ሥራ ለመሥራት ከቶ አይሆንላቸውም ። ደግሞ ብዙ ሰዎች አሳባቸው ሁሉ በግብጽ በአውሮፓ ሕዝብ ስልጣኔ ላይ እየተንጠለጠለ እንደ ሰውነቱ ትጋት መጠን ምነው እንደ ፈረንጆች አንሠራ እያለ ይናደዳሉ እንዴምንስ ብናደርግ መች እንደ ፈረንጅ ለመሥራት ይሆንልናል እንሥራስ ብንል ታሪካችንስ አመላችንስ የአገራችንስ አቀማመጥ ጥቅማችንስ ይፈቅድልናል፡፡ፈረንጆች እንዲህ ለመሥራት እንዲህ ለመኖር ለመብቃት የቻሉት የስንት ዓይነት ኑሮ አኑአኖር ሞክረው ነው ። እንዲህ ከሆነ ለኛ ይበጀን የሚመስለኝ መንገድ ታሪካችንን አመላችንን ያገራችንን አቀማመጥ የአገራችንን ንፋስ ልውጥነት ይህን የመሳሰለውን ነገር ሁሉ ሳንረሳ በጥንቃቄና በትጋት ላገራችን መልሚያ ለነጻነታችን መጠበቂያ ለሰውነታችን መጠቀሚያ የሚሆነውን መሥራት ነው ፡ ይህንም ለማድረግ ብንወድ ከሁሉ በፊት ያገራችን ፍቅር በልባችን ውስጥ ይደር ያገርም ፍቅር ካለን በማነኛውም መንገድ አገራችንን ሕዝባችንን የሚጎዳ ሥራ አንሥራ ቀጥለንም ትልቁም ትንሹም ጌታም ድኃም ፈራሂ እግዚአብሔር አድሮብን ደኅንነት ነገር እንጂ ግፍ ነገር እንጥላ ።

ልሳነ ወርቅ ።

ጊዜን በመልካም ማሳለፍ ።

ትልልቆች ወደመሆን ሲደርሱ እጅግ ከሚያሳዝኑቱ ነገሮች ጊዜን በትንሽነታቸው በከንቱ ስላሳለፉት ነው ። መልካካሞቹ የሕይወት ቀኖች በሐኬት ማሳለፍ እንዴት ያለጉዳት እንዲያመጣ ያን ጊዜ ብቻ ማስተዋል ይቻላል ።

ሐኬተኛ ሕፃን ወይም ወጣት በጊዜዋ እንደማታብብና በጊዜዋም ፍሬ እንደማትሰጥ እንዳንዲት ተክል ይመስላል ።

ጊዜው በሰዓት መለኪያ ተለክትዋል ። የሰዓቱም መለኪያ ሊቆም ይችላል፡፡ጊዜው ግን ሁለጊዜ ይሮጣል ። ከቶም አይቆምም ስናገኘውም በንጠቀምበት ወዮልን ።

ሲቻለው የማይወድ ። ሲወድ አይቻለውም ። ጊዜ የከበረ ገንዘብ ነው ።

ማስታወቂያ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፳ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ሩብ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፭ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ከሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ከ፫ሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ተኩል
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፰ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ክረጃ	፱ ብር ተኩል
የፍየል ሌጦ	፩ ክረጃ	፲፰ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ክረጃ	፻፵፫ ብር
። ። ባለሰይጣን	። ።	፻፵፰ ብር
። ። ባለ ድመት ።		፻፴፰ ብር ።
። ። ባለአህያ	። ።	፻፸፮ ብር
። ። ባለሳቢ ግመል	። ።	፻፴፫ ብር
ባለ አንበሳ	። ።	፻፵፫ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፯ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ	፲፪ተ፲፰ ሳንቲ
አንድ ብር	፰ ሊሬ እስከ	፰ ሳንቲም
ባንድ ጊኒ	፲ ብር ከ፰ ሳንቲም	
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፱ ብር	

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ፡፡

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የሚባል ባለአንበሳ ስዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ፡፡

ማስታወቂያ ፡፡

ሺብርሌ አቶሞቢል ፡፡
በኢትዮጵያ ወኪል ፡፡
ሐ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ፡፡

Automobiles CHEVROLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ፡፡

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ፡፡

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቀቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ፡፡

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል"አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ"ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው፡፡

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው፡፡

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ፡፡



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚ ሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስ ዮን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያ ይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስ መጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክ ታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ዓለም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠራል ። ኒከላ ።

ማመልከቻ ።

በብርሃንና ሰላም ውስጥ ማስታወቂያ ማሳተም የሚፈልጉ ነጋዴዎች እስከ ፈለጉት ጊዜ ድረስ ባማርኛም ሆነ በፈረንጅ ቋንቋ በርካሽ ዋጋ እንደምናትምላቸው እናስታውቃቸዋለን

ጉድ ደር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይ ነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄ ዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢ ሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬ ዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌ ላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለ ት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፶፩
3 me ANNÉE № 51

ሐሙስ ታኅሣሥ ፲፫ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 22 Decembre 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈሰገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

እግዚአብሔርን መፍራት

ይሄው ዓይነት ፍርሃት በመንቀጥቀጥና በድንጋጤ በእግዚ አብሔር ፊት መቆም አይዶለም ። ከርሱ ሊለየንና ሊያርቀን ከሚችል ሁሉ መፍራት ብቻ ነው እንጂ ።እንግዲህ እግዚአብ ሔርን መፍራት ማለት የመንፈሳዊና የሥጋዊ ጥፋት ምክን ያት የሚሆን ክፉውን ነገር በጣም መፍራት ነው ። የራሳች ንም ፈቃድ ከተገለጠልንና ፍጹምም ከሆነው ከእግዚአብሔር ፈቃድ በታች ማድረግ ነው ፡፡ ከሁሉም በላይ ስለኛ በቀራንዮ በመስቀል የሞተልንን ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታችንን በሃይማኖት እየያዝን እግዚአብሔር የሚወደውን መውደድ እንድንማር ነው። እግዚአብሔርን መፍራትም ክፉ ከሚመስለው ደግሞ መለየት ነው እንጂ ከክፉ ብቻ መራቅ አይደለም ። (፩ ተሰ፭፳፪) እግዚ አብሔር መፍራት ማለት ጽድቅንና ፍቅርን የሚገልጥ የእግ ዚአብሔርን ሕግ መታዘዝ ከዓለማዊ ነገርም ፈጽሞ መለየት ነው ፡ እንደነህምያ ለማለት መቻል ነው ።እርሱ ከርሱ በፊት የነበሩትን የሹማምንቶችን ክፋትና ዓመጻ አስቦ ስለገዛሩ በቅን ልቦና እንዲህ ብሎ መሰከረ ፤ እኔ ግን እግዚአብሔርን ስለፈራሁ እንዲህ አላደረግሁም ፡፡ (ነህ ፭ ፡ ፲፭ ።) ባጭሩ የም ሳሌው ቃል እንደሚለው ልክ ነው ። ሰው እግዚአብሔርን በመ ፍራት ከክፉ ይርቃል ። (ምሳ ፲፮ ፯)

እንግዲህ እንዲህ ከሆነ ከሁሉ አስቀድሞ እውነተኛው ፍርሃተ እግዚአብሔር በውስጣችን እንዲገኝ ይሁን ፡፡ በሉቃስ ፲፭ኛው ምዕ ስለጠፋው ልጅ የሚናገረውን ምሳሌ ባልተገባ አሳብ እንዳንተረጕመው እጅግ መጠንቀቅ ይገባናል ። እግዚብአ ሔር በኃጢአታችንና በዓመጻችን ግድ የለም ብሎ በደላችንን አሳንሶ የሚያይ እንዳይመስለን ፡፡ እግዚአብሔር መሐሪና ቸር ቢሆን ደግሞ ብርቱና ጻድቅ ፈራጅ መሆኑ ከቶ አንርሳ ። የእ ግዚአብሔር የሰማያዊው አባት ምሳሌ የሆነው በምሳሌ የሚ ነገርለት አባት ንስሐ የገባውንና ወደርሱ የተመለሰውን ልጁን ነው ያበትነቱን እጆች ዘርግቶ የተቀበለውና ትልቅ በዓል ያደ ረገለት ከዚህ በፊት ኃጢአቱን ያመጣበትን ሥቃይና መከራ ድህነትንም ይሞክረው ተወው ፡፡ ሰው የዘራውን ዘር እርሱን ያጭዳል ፡፡ (ገላ ፯ ፯) እንክርዳድ የዘራ ስንዴን ሊያጭድ አይ ሆንለትም ። የተፈጥሮው ሕግ አይፈቅድለትምና ያልዘራውን አያጭድም ፡፡ እንዴሁም የመንፈሳዊ ሕግ እጅግ የጸና ነው ፡፡ ክፉውን ነገር ዘርቶ በጎውን ነገር የሚያጭድ የለም ፡፡

ይሄው ልጅ ግን ኃጢአቱንና ክፉውን ኑሮውን አውቆ በትሕትና ወደርሱ ሲመለስ አባቱ የፈረደበትንም ቅጣት ሊቀ በል ሲወድ ጊዜ ከዚያ ወዲያ ነው በደስታ ሊቀበለው የተቻ ለው ፡፡

በወንጌል የሚገለጥልን ቸሩ አምላክ ያው በብሉይ ተገ ለጠው ጻድቅና ቅዱስ አምላክ ነው ፡፡ እግዚአብሔር አይለወ ጥም ። እሱ ፍቅር ነውና ፍጥረቶቹን ይወዳል ። ቅዱሳንም እን ዲሆኑለት ይፈልጋል ይህም ማለት ወደ ዘለዓለማዊ ጥፋት ከሚያደርሳቸው ነገር ሁሉ ነፃ ሊሆኑ ይመኝላቸዋል ። ጌታችን ይላል ፤ በሰማይ ያለው አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ ፡፡ (ማቴ፭ ፵፰ ።) ቅዱስ ጳውሎስም እንዴህ ይላል ፤ እግዚአብሔርን በመፍራት ቅድስናችንን እንፈጽም ። (፪ ፤ ቆሮ ፯ ፤ ፩ ።)

እግዚአብሔር መፍራት የጥበብ መጀመርያ ነገር ነው ። (ምሳ ፩ ፤ ፯ ።)እግዚአብሔር ግን ከዚሁ ከማንም ከማይጠቅመው ፍርሃት ሌላ እውነተኛ ፍርሃት ይፈልግብናል ። ልንወደው በፍ ቅርም ልናገለግለው ይፈልጋል ፡፡ በማቴ ፳፭ ፤ ፲፬ ፴ ። ካለው የመክሊትምሳሌ እንደዚሁ እውነተኛው ፍርሃተ እግዚአብሔር በእንዴት ያለሥራ እንደሚገለጥ ነው የምንማረው ። በምሳሌው ከሚነገርላቸው ከሰስቱ ባሮች አንዱ ጌታውን እንደሚገባው

አላስተዋለም ። አንተ ጽኑ ሰው እንደሆንህ አውቃለሁ አለው ። (ቍጥር ፳፱ ፣) ስላዚህ መክሊቱን እንዳይነግድበት በጨርቅ ጠቅሎት ተገኘ ። ሁለቱ ባሮች ግን አንዱን አምስት ሁለተኛውንም ሁለት መክሊት የሰጣቸውን ባደረገላቸው ቸርነት ጌታቸውን በጣም አመስግነው በዕጽፍ ሊሠሩ ወድያው በደስታ ተፈጣጠኑ ።

በዚሁ ምሳሌ እውነተኛውና አሰተኛው ፍርሃተ እግዚአብሔር በጉልህ ይታያል ። እነኝሁ ሁለቱ ባሮች ጌታቸውን፤በማመስገንና በፍቅር በመታመንም ፡በሚሠሩቱሥራ፟እውነተኛውን ፍርሃተ እግዚአብሔር አሳዩ ። ሶስተኛው ባርያ ግን አምላክን ደስ የማያሰኝ አሰተኛ ፍርሃተ እግዚአብሔርን ተገኘበት ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በዚሁ በሶስተኛው ባርያ እጅግ አጠንክሮ ተናገረ ምን ለከ ጌታው ጋራ ኖሮቢሆን የገዛ ጌታውን ደግነትና ፈቃድ አላወቀምና ስለዚህም ክፉ ሐኬተኛ ባርያ ተብሎ ተወረፈ ። ጌትዬው ግን እግዚአብሔርን መፍራት ምን መሆኑን ያወቁትን ሁለቱን ባሮች እያንዳንዳቸውን እንዴህ በሚለው ቃል አመሰገናቸውና ሾማቸው አንተ መልካምና የታመነህ ባርያ በጥቂት የታመንህ በብዙ እሾምሀለሁ ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ፤ በአኗኗራችን ሁሉ ጌታ ሳይቈጣጠረን አይቀርም ። ከሕዝበ ክርስትያን ይህን የሚስተውአንድም የለም ። የታመን ወይም ያልታመን ሆነን ልንገኝ ነው ። ሁላችንም የክርስቶስ ባሮች ልንሆን ተጠርተናል ። እያንዳንዱ በሥራው ቅንነት እውነት እምነት ሊያሳይ ይገበዋል ። ደግሞም የሆነው ሰው እግዚአብሔርን ሊያገለግል በማገልገሉም እግዚአብሔርን መፍራት ሊገልጥ ይቻለዋል ። ብዙዎች ግን ይህን ነገር ያስደንቃቸዋል እንዴህም ያስቡ ይሆናል ፤ እውነት ነው ፍርሃተ እግዚአብሔርስ ቀሳውስት ዲያቆናት አስተማሪዎች የሆኑቱ ሊያሳዩ ይገባቸዋል ። እኔ ግን ወታደር ሹመኛ ነጋዴ ገበሬ አገልጋይ ነኝ ። እንደዚህም የሚመስለዉን ይሉ ይሆናል ። እንዴህ በማለትም ማንላቸው ሰው እግዚአብሔርን መፍራት እንዲችል ቀር ይላቸዋል ። እውነተኛው ፍርሃተ እግዚአብሔር ግን ምን መሆኑን ባለቤቱ የአምላክ ቃል ተርጕሞታል ሌላ ፍች የለውም ።

እርሱ የሚጠላውን መጥላት ከዚህ በቁምም ነገር መራቅ ብቻ ነው ። የእግዚአብሔርም ፍቃድ አስቀድም በሕሊናችን ኋላም በቃሉ ተጽፎ፣ ናል ። እንግዲህ ፍርሃተ እግዚአብሔርምን እንደሆነ በዕለት ዕለት ሥራችን እንፍታው ፤ ነጋዴ በመሸጡና በመለወጡ በስፍር በሚዛን በዕቃው ዓይነት በዋጋውም ሳያታልል ቢሸጥ ቢገዛ እግዚአብሔርን መፍራት አይዶለምን ? እንዴሁም ገበሬ ሳይሰሳ በቅን መንገድ እህሉን ቢያቀና ሸመታውመቸ ያነ ስልኛል ግርዱንም መቸ እሸጣለሁ ሳይል ድኃውንም ሳያጫንቅ ቢሸጥ ይህ እግዚአብሔር መፍራት አይደለምን? (የክፉ ገበሬ አሳብ አንብቡ ፤ (አሞጽ ፰ ፣ ፬ ፣ ፳ ።) ወታደርም ከበላዩ ከሉ ሹማምንቶች የታዘዘውንም በእውነትና በትክክልነት ቢፈጽም ይሄው እግዚአብሔርን መፍራት አይደለምን ፤ ፈራጆችና ልዩ ልዩ ችሎት የተሠጣቸውም ፍርድን ማስተካከል ቢገልጡ ከዚህ የበለጠ ፍርሃተ እግዚአብሔር ይገኝ ይሆን እንዴሁም አገረገዦች ቢሆኑ የሕዝባቸውን አኗኗር እንዲሻሻል ግብሩንም እንደ ባላገሩ ዓቅም ቢጥሉበት በዚህ ይጐዳል በዚሁ ይጠቀማል እያሉ በዕውቀትና በቸርነት ቢገዙት ይሄው እግዚአብሔርን ማወቅ አይደለምን ፤

ስለዚህ ሹማምንቶች ከፍያለውን መዓርጋቸውና ሥራቸውን እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋራ ሊሰማማ እንዳይችል ሆኖ ይታያቸው ይሆናል ። እንዲህ ማሰብ ግን ስሕተት ነው ። ፍርሃት እግዚአብሔር ለማድረግ ብቻ የሚቻላቸው አይደለም ። ከሌሎች ይልቅ ደግሞ እርሳቸው እግዚአብሔርን መፍራት የሚገልጡበትን ኃይል እንዳገኙ ሊያስተውሉ ይገባቸዋል ። ብዙዎች በመጽሐፍ ቅዱስ የታወቁትን ሰዎች ቢመለከቱ ሊያስተውሉት ይቻላቸዋል ፤ መልከ ጻዴቅ የሳሌም ንጉሥና የእግዚአብሔር ልዑል ካህን ነበር ። (ዘፍጥ ፲፬፡፲፰) በነዚሁ ሁለት የተለያዩ ሹመቶችም ባንድ ጊዜ በቅንነት ሊያገለግል እንደቻለ ከዚህ ተገልጦ ይታያል ። እንደ ንጉሥ ኢየሩሳሌምና አገሮችዋን ይገዛ ይዳኝ ይጠብቅ ነበር እንደ ካህንም ለእግዚአብሔር በሚደርስ ነገር መሥዋዕቶቹን ጸሎቱን ምስጋናውንም ያቀርብ ሕዝቡንም በእግዚአብሔር መንገድ ያስተምር ነበር ።

በምስር መንግሥትም በፈርዖን ዮሴፍ ተሾመ ። የንጉሡ እንደ ራስየውም ነበር ። ግን እርሱ በዚሁ በአረመኔው መንግሥት ሲያገለግል እግዚአብሔርን መፍራት ወይም አምላኩን ማገልገል ተወን ፤ የዮሴፍን ታሪክ የሚያነብ ይህን ነገር አጥብቆ ሊረዳው ይቻለዋል ። ዮሴፍ እግዚአብሔርን በመፍራቱ ዓለምን ከረሐብ አዳነ ። ኢያሱ ወልደ ነዌ ሳሙኤል እርሱንም የመሰሉ ብናስብ እግዚአብሔርን ስለፈሩ ሕዝባቸውን ከክፉ ነገር ሁሉ አዳኑና ጠበቁ ።

ዳዊትም የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔርን እንዴት አድርጎ ይፈራ እንደ ነበር ሁሉ የሚያውቀው ነው ። አምላክ ባለቤቱ እንደ ልቤ ያለ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ ብሎ መሰከረለት ። ዳዊትም በዚህ እግዚአብሔርን መፍራቱ ሕዝቡንና መንግሥቱን አከበረ ። ዳዊት እግዚአብሔርን አጥብቆ ስለፈራ እርሱ ሳይቀር በዙሪያው ያሉትን ሕዝብና መንግሥታት እጅግ ያሰፈራቸውና ያንቀጠቅጣቸው ነበር ። የዳዊት እግዚአብሔርን መፍራት ግን እግዚአብሔር በቃሉ የገለጠለትን ፈቃድ በማድረግ ነበር ፡ ደግሞ ነቢዩን ዳንኤልን መመልከት ይገባል በአረመኔው በባቢሎን ውስጥ በትልቁ በናቡከደነፆር ንጉሥ ጀምሮ እስከ ዳርዮስ የሜዶ ፋርስ ንጉሥ ድረስ እግዚአብሔርን በመፍራት አገለገለ ። እንግዴህ ሁሉ በያለበት በየተሾመበት እግዚአብሔርን ሊያገለግል ይቻለዋል ። እውነተኛ ፍርሃት እግዚአብሔር በውነትና በቅንነት በመታመን የታዘዘበትን ሥራ መፈጸም ማለት ነው እንጅ ሌላ ፍች የለውም ።

እንዴሁም ቀሳውስት መምሕራን በቤተ ክርስቲያን የተሾሙቱ፡ወእለሂ ትሜህሩ መሀሩ ቃሎ ለእግዚአብሔር (፩ ጴጥ ፬ ፲፩ ፤)እንዲል ሕዝባቻቸውን በእውነት አስተምረው ከነፍስና ከ ሥጋጨለማነት አውጥተው በመንግሥተ ሰማያት እንዲገቡ ቢያደርጉዋቸው ከዚህ የበለጠ ፍርሃት እግዚአብሔር ይገኛልን እንዴሁም ከሰው በታችም ያልሆነ ሰው ሥራውን ለገዛሩ የሚ

ሥራ በሥራውና በአካሔዱ እግዚአብሔርን መፍራት ሊያሳይ ይገባዋል ፡፡

ከዚህ ሁሉ በኋላ ግን በመጨረሻው እግዚአብሔርን መፍራት ምን ነገር እንዳይደለም እጅግ ማወቅና መረዳቱ ያስፈልጋል በእውነተኛው ፍርሃተ እግዚአብሔርና በአሰተኛው ፍርሃተ እግዚአብሔር ያለውን ልዩነት በጣም መለየት ፡፡ እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ሥራውን ትቶ መቦዘን ማለት አይደለም ፡፡ በማናቸውም ምክንያት በሥጋዊው ሆነ በመንፈሳዊውም ምክንያት ሥራን ማስቀረት አይደለም ፡፡ ሰሎሞን ለሁሉ ጊዜ አለው አለ ፡፡ ይህም የእግዚአብሔር ሕግና ፍርድ ነው እንጅ የሰሎሞን አይደለም ። እግዚአብሔር ይህንን ቃል በሰሎሞን አፍ ተናገረ ፡፡ እንግዲህ ስለ ማንኛቸውም ነገር ምክንያት ብለን የሥራ ጊዜን በሌላው ምክንያት እንዳናጠፋ መጠንቀቅ ያስፈልጋል ፡፡ ሰሎሞን ያለውን ዘወትር ማሰብ ይገባል ፤ ለሁሉ ጊዜ አለው ። እስከንደዚህ ሞኝ የሆነም የሚገኝ አይመስለኝም መጥፎ ነገር ራሳችንን ወይም ባልንጀራችንን የሚጐዳውን ነገር ለማድረግ የትኛው ጊዜ እንደተሰጠን ለማለት የሚደፍር ጊዜ ያችን ሁሉ በጎ ለማድረግ እንጅ ለሌላ አልተሰጠንም ። እንዲሁም ሥራችንን ትተን ጊዜውን ሁሉ ቀንና ሌሊቱን በጸሎት ብቻ ብናሳልፈው አንዳችን ነገር ሳንሰራ ሥራችንን ማን ይሠራልናል ፡፡ ዳዊት እግዚአብሔርን ይፈራ ነበር ዳሩ ግን ሊያደርገው የሚገባውን ዕለት ዕለት በትጋት ይሠራ እንደነበር በታሪኩ ይነግረናል ። ስለዚህ እግዚአብሔርን እፈራለሁና እርሱ ያድነኛል ብዬ ሥራዬን ትቼ ቍጭ ብል ይህ እግዚአብሔርን መፈታተን እንጅ ሌላ አይደለም ። እግዚአብሔር ሥራንና ትጋትን አሳብን ምክርን የሚከተሉትን ይረዳል እንጅ ሥራ ፈቶችን ሐኬተኞችንም አይረዳም ። እንዲህ ያለ መታለል ያጠፋል ። ከዚህ በፊት እንዳልነው ፤ ዳዊት እግዚአብሔርን እጅግ ይፈራ ነበር ። ዳሩ ግን በሕዝቡና በመንግሥቱ ይሰራው የነበረውን ብንመረምር አያስደንቅምን የሠራዊቱ ብዛት የሠራዊቱ ልዩ ልዩ ዓይነቶች አከፋፈል የወታደሮቹም ትምሕርት መርሳት አይገባም ። ከዳዊት ወታደሮች በወንጭፍ ጦር የሚችሉ ነበሩት ። በመሣፍንት ዘመንም ከነገደ ኤፍሬም ብቻ ሐያ ስድስት ሽህ ሰይፍ የሚመዙ ነበሩ ። እንዲሁም በግራ እጃቸው ወንጭፍ አወንጭፈው አንዲት ጠጉር የማይስቱ ሰባት መቶ አርበኞች ነበሩ ። (መሣ ፳ ፤ ፲፭ ፲፮ ፡፡) ይህ ሁሉ በትምሕርት በመላመድ እንጅ በተአምራት እንዳልተማሩት ወይም እንዳላወቁት ደግሞ ልናስብ ይገባናል ። እንግዲህ እግዚአብሔርን እየፈራን ሥራችንን በትጋት እንፈጽም ።

የጤና ዓሰርቱ ቃላት ።

፩ ፤ ጥዳትን በብዙ ጥብቅንት በመከተል ጤንነትህን ትጠብቃለህ ሰውነትህን ዕቃህንም የምትኖርበትንም ስፍራ በውስጥ በዙሪያው እጅግ የጠዳ እንዲሆን ዘወትር ተግተህ ጠብቅ ሁሉ ጊዜ ጥዋትና ማታ ሳሙናን ጨምረህ ፊትህን ታጠብ ፡፡ አፍህን ጥርሶችህንም መታጠብ አትርሳ ። እንዲሁም በጥሩ ጨርቅ በቶሎ ማድረቁን አስብ።ያፍንጫህንም ውስጥ የጠዳ ይሁን

፪ ፤ የሚበዙቱ በሽታን የሚያሳልፉ ለዓይን የማይታዩ ትንንሾች ፍጥረቶች በአፍ እንደገቡ አስብ ፡፡ ስለዚህ ከመብላት አስቀድመህ እጆችህን በጣም ታጠብ ። አንዳች ነገርም በማናቸውም ስፍራና ምክንያት ይልቁንም ቍሻሻ ነገርና እድፍን በያዝህ ጊዜ መታጠብ ያስፈልግሃል እንደዚህ በማድረግ ከሚራቡ በሽቶች ታመልጣለህ ከተቅማጥ ከተስቦ።እንዲሁም ከሚመስሉ፡፡

፫ ፤ ከጥሩ ምንጭ ያልተቀዳውን ውኃ ከቶ አትጠጣ ። መልካሙን ውኃ በእርግጥ ልታገኝበት መድረስ እስከምትችል ጥማትህን ታገሥ ፡፡

፬፤የሆነው ነገር የምትበላው በጥሩ ውኃ ሳይታጠብ አትብላ

፭፤እያንዳንዱ ሳይታወቀው በሽታን የሚያራቡ ምክንያቶች ሊገቡበት ይቻለዋልና በምትኖርበት ቤት በምትተኛበትም በሆነውም ስፍራ ሰው በሚሰበሰብበት በምድር እንትፍ አትበል ፡፡ ማንጠስ ወይም ሰዓል በምትስልበት ጊዜ እጅህን ወይም መንዲልህን በአፍህ ማድረግ ይገባል ።

፮ ፤ በሰምንቱ ብዙ ጊዜ ልብስህን ልትለዋውጥ ብይቻልህ እንኳ ምንም ብዙ የሚቸግርህ ቢሆን የሚቻልህን የጥዳት ልክንት እንድታገኝ ይሁን ። ልብሶችህንም የአካልህ ሆነ የአልጋህ ዘወትር እንዲታጠብ ትጋ ።

፯ ፤ እንዲሁም ነስና ሽንት የትልቆች በሽተኞች ማሳደሪአ መሆናቸውን ከቶ አትርሳ ። እንደዚህ ያሉትን ብዙ የማይቈጠረውን ጉዳት የሚያመጡትንበመሬት ላይ ክፍት ወይም ግልጥ ሆነው ሊጣሉ አይገባም ። ለነዚሁ በተወሰነው በልዩ ስፍራ ሊሆኑ ይገባል ። ያውም ጥልቅ ጉድጓድ ሊጠረጉና ሊጠዱ እንደሚቻል አድርጎ ቤት መለየት እንዲህ ያሉ ስፍራም ዘወትር እንዲጠዱ መጠንቀቅ ያስፈልጋል ።

፰ ፤ የምግቡንም የመጠጡንም ቅሬታ ወይም የሌላው ነገር በምትቀመጥበት በዚያው ወይም ባጠገቡ አትጣል ፡፡ እድፍ የሆነውን ሁሉ ቢበዛም ቢያንስም የጉድፍ መጣያ ተብሎ ከቤትህ እጅግ ራቅ ብሎ በተለየ ስፍራ መጣል ያስፈልጋል ፡፡

፱ ፤ ዝንቦች ቱኳኖች ቍንጫች ቅማሎች ሌሎችም በሽታን የሚያራቡ ፍጥረታት በሽታን እንደሚያመጡ እንደብርቱ ጠላቶችህ አድርገህ ዕወቃቸው ስለዚህ እንደዚህ ያሉትን ፍጥረቶች ለማጥፋት ዘወትር አደንና ወይም ጦርን ለማድረግ ታጠቅ ከምትበላውና ከምትጠጣው ዝንቦችን ሌሎችንም እንደቅማል የመሰሉትን ከልብሶችህና ከሰውነትህ አንድ ስፍራ አትስጥ ። ጥዳትን ብትከተል እኒህን ለማጥፋት ቀላል ነገር ነው ። እኒህም ጠላቶች ቢበረቱብህም ሐኪምን መጠየቅ ነው ፡፡

፲ ፤ እኒህን ሕግጋት አጥብቀህ ተከተል ሌሎችን ጓደኞችህንም እነዚህን ትእዛዛት አስተምራቸው ፡፡ እንዲከተሉዋቸውም ትጋ ይህንንም ሥራ ራስህንና ጓደኞችህን በጣም እንዲረባ አስረዳቸው ። ጤና ከገንዘብ የከበረ ነው ፡፡

ደግ ምክር

አንድ ፈላስፋ ለደቀ መዝሙሩ የጻፈለትን እሰማ ነበር ። ከክፉ ሰዎች ጋራ የተጐራበተና የተወዳጀ በባሕር ላይ እንደ ተቀመጠ ሰው ነው ።

ከውኃው መሥጠም ቢድን ከውኃው ውስጥ ካለ ከሚያስፈራው ነገር ሁሉ አይድንም ሲል ።

የድኃ ክፉ ጐረቤቱ በገመድ ተለክቶ ኸተሰጠው ቦታና የቀላድ መሬት ንጉሡም ከሰጠው የአገር ግዛት ተላልፈው በመቀኛነት የያዝኩትም ይበቃኛል በለማለት ወደ ጥፋት ነገር የሚደርስ ሰው ነው ።

ሰውነቱንም ከጥፋት የማያድን ሰው አእምሮ ከሌላቸው ከእንስሳት ይቈጠራል ። እንስሳት እንኳን የሚጠቀሙባቸውን ሲፈልጉ የሚጐዳቸውን ሲሸሹ የደመ ነፍስ ዕውቀት አላቸው ወደ ሚያጠፋቸው ነገር ወደ ገደል ቦታ ሰውነታችውን ሲወስዱ አላየናቸውም ወደ ሚያጠፋቸው ወደ ገደል ቦታ በቀረቡም ጊዜ በደመ ነፍሳቸው ዕውቀት አውቀው ላካላቸው ሳስተው ራሳቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ከዚያ ቦታ ሸሽተው ርቀው ወደሌላ ቦታ ይሄዳሉ ። አእምሮ ያለው ሰው ወደጥፋት ቦታ የሚያደርሰውን ሥራ ለምን ይሠራ ይሆን ። ያነኑ የድንቁርና ዕውቀቱን አክብሮ እንጂ ነው ። የራሴ ዕውቀት ይበቃኛል ብሎ ብቻውን የሆኑ በማናቸውም ነገር በሆነበት ቦታ ለወዳጁ ምክር ሳያካፍል ቀርቶ በዕውቀቱ ያደረ ሰው ረዳትም የለው እሱም ጠፊ ነው ። አእምሮ ያለው ሰው በብልሃቱና በዕውቀቱ የሚያገኘውን ነገር በኃይልና በብዙ ሠራዊት በብዙ ፈረስ ፈልገው ሊያገኙት አይቻልም ።

የዚህም ምሳሌ እንዲህ ነው ። አንዲት ድርጭት የምትባል ያፍ ጊኖን ውኃ ሊጠጣ በሚመላለስበት መንገድ ላይ ቤቷን ሠርታ ዕንቁላል ጥላ ነበረች ። ከዕለታት ባንድ ቀን ዝኆን እንደ ጥንት ልማዱ ውኃ ሲሄድ የድርጭቷን ቤት ረግጦ ዕንቍላሏን ሰብሮ ልጁዋን ገደለባት ።

እሷም ያገኛትን መከራ በየች ጊዜ ይህን ያደረጋት ዝኆን መሆኑን አውቃ በራ እያለቀሰች በራሱ ላይ አረፈች ። ዝኆኑንም ጠየቀች እንዲህ ስትል ንጉሥ ሆይ እኔ ባንተ ጥግ ስኖር ስለምን እንቍላሌን ሰብረህ ልጆቼን ገደልክብኝ ይህን ሥራ የሠራኸው አቅሜን አሳንሰህ ነገሬን አቃለህ ስለ እኔ ንቀት ብለህ ነውን ብላ ብትጠይቀው ። ይኸን ሥራ ለመሥራት ያደረሰኝ ነገር ይኸው አንቺው ያልሺው ነገር ነው አላት ። እሷም ትታው ተነሥ ወደ ዖፎች ሠራዊት ሄደችና ዝኆን የበደላትን ነገረቻቸው እነሱም ዖፎች ነን ምን እናድርገው ብለሽ ነገርሽን ቢሏት ጭልፊቶችንና ቁራዎችን ከኔ ጋራ ሄዳችሁ ሁለት ዓይኑን እያነቈራችሁ እንድ ታጠፉልኝ እፈልጋለሁ ከዚያም በኋላ ሌላ ብልሐት ፈልጌ የማደርገውን እኔ አውቃለሁ አለቻቸው ። እነሱም ፈቃድዋን ለማድረስ ወደ ዝኆኑ ሂደው ዓይኑን እያነቈሩ አጠፉት ።

እሱም ወደምግቡና ወደመጠጡ መንገድ መሄድ አቅቶት ባጠገቡ ያለውን ከመሬት ያገኘውን እየለቃቀመ ሲበላ እሷም የሱን እንዲህ መሆኑን አይታ ብዙ እንቍራሪቶች ወዳሉበት መንዝ ሄዳ ዝኆን የበደላትን ለነሱ አዋየች ። እነሱም ለዝኆን ኃይል የምናገዝሽ ምን አቅምና ኃይል ብልሐት አለን አሏት ወደሱ ቀረብ ወዳለችው ጉድጓድ ቦታ ከኔ ጋራ ሄዳችሁ ከፍ ያለ ቃል እንድትጮሁ እፈልጋለሁ እሱም ያለጥርጥሬ ውኃ ያለ ይመስለውና በጉድጓድ ውስጥ ይወድቃል አለቻቸው ። እነሱም የሷም ፈቃድ ለማድረስ ወደአለችበት ቦታ ሄደው በጉድጓድ ውስጥ ተሰብስበው ጮሁ ዝኆኑም የእንቍራሪትን ድምፅ በሰማ ጊዜ ያለመጠን ውኃ ጠምቶት ነበርና በውነት ውኃ ያገኘ መስሎት ወደጉጓድ ሄደ ወድቆም ተሰበረ ። ድርጭትም መጥታ በራሱ ላይ ተቀምጣ ክንፏን እያራገበች አንት በኃይልህ የምትመካ ጥጋበኛ ሰው ናቂ ኵራተኛ ነገሬን አቃለህ ሰውነቴን እንዳሳነስከው ከአካሌ ማነስ ጋራ የብልሃቴን ትልቅነት ያንተን ገዚፍነት የዕውቀትህን ማነስ የልቡናህን ስንፍና አየኸውን አለችው ። ሰውን ስለ ጉስቁልናውና ስለ ድህነቱ አትናቀው ። ከአዕዋፍ ሁሉ ንብ ታንሳለች ፍሬዋ ግን ከሁሉ ይጥማል ቀን በመጠጡ ያዘኑትን ሰዎች ደስ ያሰኛል ። ሌሊት ጨለማውን አጥፍቶ በብርሃኑ ደስ ያሰኛልና ። በባለጸጎች ዓይን ፊት የተናቀ ጐስቋላ ድኃ ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ የተከበረ ነውና ። በነፍሳችሁ ጉዳት እንዳያገኛችሁ ድኃን አትናቁ አታጉላሉት በተቻላችሁ ነገር ሁሉ እርዱት ብሎ ይመክራል ።

ቁም ጸሐፊ ገብረ ጻድቅ ።

ጠንቋይ ንብረት ያስፈታል ፤
ከእግዚአብሔር ጋራም ያጣላል ተጠንቀቁ ።

በአሩሲ በኩል አንዲት ጠንቋይ እስላም በጥንቆላዋ ብዙ ሰው ታሰግዳለች ተብሎ ተወራ ። ኋላ ግን መንግሥታችን የገዛ ድኃው በድንቁርና ልቡ የጥንቆላ ነገር ጥቅም ያለበት መስሎት እንዳይበላሽ ሲል ያቺን እስላም የሞኝ ሥራ እንዳትሠራ ብሎ ከለከላት ወረሳት ። መልካም አደረገ ። ጠንቋይቱ ግን እንኳን ስሌላው ገና የሚመጣውን ነገር ታውቅ በራሷ በኩል የመጣባትን መከራ አስቀድማ ሳታውቅ ተገኘች ። በዚህ የተነሳ እንኳን ለብልሆቹ ለደንቆሮዎች ሳይቀር ጠንቋይ እንኳን ለሌላው ለራሱ የሚመጣበትን ነገር እንዳያውቅ ተገለጸላቸው ። ያቺ እስላምስ እስቲ ባልተማረው ዘደንቆሮ አሩሲ ጋላ ስታላግጥ ኖረች ። አሁን የሚደንቀው በብልሁ በተማረው አገር በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አንዲት ተንኰለኛ ቀጣፊ ሴት አውቃለሁ እጠነቁላለሁ እያለች ብዙዎች ሴት ወይዘሮዎች ስታላስትና ንብረታቸውን በሐሰት ስታስፈታ ትኖራለች ። ይሄ ነገር ብዙ የሚአስጠነቅቅ ነው ። እሷስ እስቲ በተንኰል መንገድ ገንዘብ ለማግኘትና ድኃ ባሏን ለመቀለብ ብላ ታድርገው ። እንዴት የዛሬ ዘመን ሰው በማስጠንቆል የሀብት ደጃፍ ይከፈትልኛል መስሎት የተከፈተለትን ያማረውን ንብረቱን በገዛ ጁ ይዘጋዋል ። እንደምንስ የእግዚአብሔርን እምነትና አምልኮት አዙሮ ላንዲት ቀጣፊ ደንቆሮ ጠንቋይ ይሰጠዋል ።

የጐጃሙ ገብሩ መድኃኔ ዓለም አንድ ስመ ጥሩ ጠንቋይ አለቃ ሙረዋ የሚባል ነበራቸው ይባላል ። አንድ ቀን ከራስ ደስታ ጋራ ሲዋጉ ተሰልፈው ሳለ ያ ጠንቋይ ሮብ አይግጠሙ አሙስ ማለዳ ቢገጥሙ ድል ያደርጋሉ ። ድል ካደረጉ በኋላ የምስራቹን የጐጃምን ሁሉ ሊቀ ካህናትነት ለኔ ሊሰጡ ቃል ይግቡልኝ አላቸው ። ገብሩ መድኃኔ ዓለም እሺ ብለው ምለው ማኅተም ሰጡት ። አሙስ ማለዳ ጦርነቱ ተጀመረ ወዲ

ያው ያ ጠንቋይ ደረቱን በጦር ተሰነጠቀና ከፊታቸው ሞቶ ለከ ብራሱ የሚመጣበትን ሳያውቅ ትሬል ለኔ የሚያታልለኝ ብለው በሞኝነታቸው አዘኑ ወዲያውም ድል ሆኑ ። ንጉሥ ተክለ ሃይ ማኖት ገና ራስ አዳል ሲባሉ ራስ ወልደ ማርያምን ሊወጉ አፄ ዮሐንስ አዘዟቸው ይባላል ። ተጉዟም ገሥግሠው ስማዳ ደረሱና ሲዋጉ ሲሰናዱ አንድ ትልቅ ባለግርማ መነኩሴ የበሬ ዳባ እስተ ከስማው ለብሶ ከዋልድባ ገዳም መጣሁ አሰኝቶ ንገ ሩልኝ አለ ። ራስ አዳል አስገቡና ምን አመጣዎ አባቴ አሏቸው ። ያ መነኵሴ ከሰማይ ተልኮ እንደወረደ ሁሉ ዓይኑን ወደላይ ወደታችም እጭለማልሞ ከንፈሩን እንደ ጥንቅሽ አገዳ እየመጣጠጠ ጨረቃይቱ እስክትወለድ ጦርነት አይጀምሩ ይጠፉሉ አሏቸው ። ይሂማ በጨረቃ ማመን ይሆንብኝ የለምን አሉ ። ያ መነኩሴ በጾምና በጸሎት ተወስኖ የሚኖር መነኵሴ የሚነግረዎን ቢሰሙ ይሻላል አሏቸው።ምላሹን ነገ እሰጥዎታለሁ እስከዚያው ከበጅሮንዴ ጋራ ይቆዩ አሉና ሌሊቱን ገሥግሠው ሲነጋ ራስ ወልደ ማርያምን ድል አድርገው ቆራርጠው አባይ ላይ ጣሉና ያንን ባለዳባ መነኵሴ ሒድ አንተም ጨረቃ እስ ክትወለድ ድረስ ራስ ወለደ ማርያምን አጫውት ብለው በርጥብ ቆዳ አስጠቅለው አባይ ውኃ አስጣሉት ይባላል ። እንዲህ በሞ ኞች ጊዜ እንኳን ጠንቋይን የሚያምን ሰው ሳይኖር ዛሬ ዓይን በተገለጠበት ጊዜ ጠንቋይን አምኖ መሄድ ይቻላል? እንዴትስ ያችን ደንቆሮ ቀጣፊ ሴት አምኖ ብር እያስታቀፉ ማስጠንቆል ይቻላል ፡ የሰው ሞኝነት ብዙ ያስደንቃል ይቺውም ሴት የአንዱ የውጭ አገር ወንድ አገባሁ ብላ መምጣት ነው እ ፲ የኢት ዮጵያ ዜጋ ናት ። በጥንቆላዋ ሰው ማታለሏን ትታ በቶሎ ወደ ነበረችበት አገር ካልሄደች ስሟን ገልጠን ለማስታወቅና ለማስ ቀጣት የተሰናዳን ነን ። ወደእስዋ እየሄዱ የሚአስጠነቁሉቱንም እንዳያፍሩ እናስታውቃለን ።

ካሣ ገብሬ።

ያገር ውስጥ ወሬ ።

በታኅሣሥ ፲ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ክቡር ሐኪም ወርቅነህን ሊቀበሉ ከወረዱት መኳንንቶች የሚበዙቱ የፍቅርና ያገልግ ሎት ማኅበሮች ስለሆኑ ፣ አብረዋቸው የመጡትን ታላላቅ መኳ ንንቶች አዋሽ ላይ ራት ጋበዙ ። ለግብዣውም ከተጠሩት መካ ከል የታላቁ ፤ የገናናው የጀርመን መንግሥት ባለሙሉ ስል ጣን ሚኒሲቴር ፤ ከነሚስታቸው ሙሴ ፍሬዘር ፤ ሙሴ መክኒ ክቡር ግራዝማች ለጥይበሉ ፤ ክቡር አቶ ዮሐንስ የጀርመን ሌጋ ሲዮን ቱርጁማን፤ክቡር አቶ ተድላ ነበሩ። በሺምፖኝም ጊዜ ክቡ ር አቶ ኀበረ ኃይለ ሥላሴ፣ የፍቅርና ያገልግሎት ማኅበር ምክ ትል አለቃ (ሱ ፕሬዚዳንት) የሚከተሉት ቃላትተናገሩ ።

ክቡራን ሆይ ።

የፍቅርና ያገልግሎት ዋና አለቃ አባታችን ክቡር ሐኪ ም ወርቅነህ ስለሐገርዎ ስለ ኢትዮጵያ ጉዳይ ከመንግሥትዎ ተመርተው የተላኩበትን ሁሉ ፈጽመው በደህና መመለስዎ ለሐገርዎ ለኢትዮጵያ ክቡርና ለኛም ለልጆችዎ ታላቅ የሆነ የደስታ ምልክት ይሄች ማኅበር የቆመችበት ጊዜያት ምንም ቅርብ ስለሆን ፤ ሥራዋን ከጀመረች አንስቶ እስካሁን ድረሲ በጌታችን በልዑል አልጋ ወራሽ ትጋት በርስዎ ባባታችን ብር ታት እነሆ ፳፫ የሚያህሉ ባሮች ነጻነትን ተቀብለው ደስ ብሏ ቸው ይኖራሉ ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አገርዎ የምትወን ጀልበትንና መንግሥትዎ የምትከሰስበትን በዛሬ ዘመን የተና ቀውን ሁኔታ ለማስወገድ የዘወትር አሳባቸው ስለሆነ በባርነት ተይዘው የነበሩ ወንድሞቻችን የኢትዮጵያ መንግሥት ነፃ እን ዲወጡ የሰጠው ደንብ ስለተፈጸመለት ወዳገራቸው ለመግባት ያልፈቀዱ ባሮች እንደገና መንገላታት እንዳያገኛቸው ይህ ማሕ በር ተቀብሎ ያሳድጋቸዋል ።ባዲስ አበባም በየሥራው የተቀጠ ሩት ከ፬ሺህ በላይ ደርሰዋል ስለዚህ ይህች ማሕበር በሁለት ዓመት ውስጥ ይህን መልካም እርምጃ የሠራች እስከ አምስት ዓመት ድረስ ፈጽማ ወደ ሌላ አገልግሎት የምትራመድ ናት ብለን ተስፋችን የተስፋፋ ነው ። ክቡር ሐኪም ወርቅነህም ለዚህ ሁሉ ሥራዎ መንፈሳዊ ኵራት ይገባዎታል ። የምንወዳቸውን ወንድሞቻችንነን ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅንና ልጅ ቴዎድሮስ ወርቅነህን እርስዎን አባታችንን አቅፎ ደግፎ የመለሳችሁን እግ ዚአብሔርን እናመሰግናለን ። ልዑል እግዚአብሔር ለግርማዊት ንግሥታ ችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን እረጅም እድሜ ሰጥቶ የተጀ መረው አዲስ ሥራት እየሰፋ ሂዶ ቀድሞ እንደዚህ ነበር ለማ ለት ያብቃን ስል ጽዋዬን እጠጣለሁ ብለው በጨረሱ ጊዜ ተጨበጨበ ።

ከዚህ በኋላ ክቡር ሐኪም ወርቅነህ የሚከተሉትን ቃላት ለመናገር ሲነሱ ሙሴ ፍሬዘር እንደ ማጨብጨብ ሲቃጣቸው አይተው ፣ በገበታው ላይ የነበሩት ፳፫ቱ ሰዎች የጭብጨባ ውን ዋዜማ ጀማመሩትና ተግ ሲል ዲስኩሩን ጀመሩ ።

ክቡራን ወንድሞቼና ልጆቼ ።

በናንተና በኔ መካከል ያለውን ፍቅር ለማስረዳት ስትሉ ዛሬ በተደረገው ግብዣና አገራችሁን ለማገልገል በተነሣችሁ ሁበት ላመስግናችሁና ላበረታታችሁ እወዳለሁ ።ዛሬ እኔንና ከኔ ጋራ የመጡትን የመንገድ ጓደኞችን ይልቁንም የጀርመን መንግሥት ባለሙሉ ስልጣን ምኒስቴርን ከነሚስታቸው በመ ጋበዛችሁ ጥልቅ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። እንዳላችሁት ሁሉ ኢት ዮጵያ ነፃነቷን በጥንቃቄ ጠብቃ የቆየች መንግሥት ናትና አገ ሩን የሚወድ ክርስቲያን ከአእምሮው ተማክሮ መልካም አገል ግሎት ቢአደርግ ፣ ከመመስገን በቀር ጉዳት የለበትም ። አሁንም ወደፊት ለግርማዊት ንግሥታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን እረጅም እድሜ እየተመኘን ያሰባችሁትን አስፈጽሞ ተፋቅረን ኢትዮጵያን አቅፈን ለመኖር ያብቃን ስል ጽዋዬን እጠጣለሁ ብለው ሲቀመጡ እረጅም ጭብጨባ ተደረገ ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ፣ የፍቅርና ያገልግሎት ማኅበር እንደዚህ ለሐገራቸው ታጥቀው የኢትዮጵያን ልማት መፈለ ጋቸው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነውና ምንም ከማኅበሩ አብሬ ባልጠጣ ፊትም እንደሰማሁት ፤ አሁንም እንዳየሁት ፍቅርና ፡

መሰማማት የሚወዱ ናቸውና በማናቸውም እርዳችንን በሚፈልጉት ሁሉ ልንረዳቸው የተዘጋጀን እንሁን ።

ሥመኝ መኰንን ።

ስለ ክቡር ሐኪም ወርቅነህ መግባት ።

ክቡር ሐኪም ወርቅነህ የልዑል አልጋ ወራሽ ትምህርት ቤት ዋና ሹም ወደ አሜሪካና ወደ ኤውሮጳ ደርሰው የተላኩበትን ጕዳይ ፈጽመው በታሕሣሥ ፲ ቀን አዲስ አበባ ገቡ ።

ክቡር ሐኪም ወርቅነህ የጀመሩትን ሥራቸውን ሁሉ በመታመንና በቅንነት ስለሚያከናውኑ ሰው ሁሉ ያመሰግናቸዋል ይወዳቸዋልም። ስለዚህ በገቡበት ቀን የልዑል አልጋ ወራሽ ትምህርት ቤት ተማሪዎችና ሌሎችም መኳንንት ሁሉ እባቡር ማረፊያ ወርደው በደስታ ተቀበሏቸው ከዚህ በኋላ በልዩ በታዘዘላቸው አውቶሞቢል ሆነው ማታ እቤታቸው ሲደርሱ ነፃ የወጡ ተማሪዎች በየእጃቸው ፋናና አበባ ይዘው ተሰልፈው እየዘመሩ ተቀበልዋቸው ። ክቡር ሐኪም ወርቅነህ እቤታቸው በደረሱ ጊዜ በዚያ የነበረ ሰው ሁሉ በደስታ ፈንደቀ ከዚህ በኋላም ሰው ሁሉ እቤት ገብቶ በክቡር ሐኪም ወርቅነህና በክብርት ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ ፊት ተቀምጦ ሸምፓኝ ተጋበዘና በሸምፓኝ ጊዜ ስለ ክቡር ሐኪም ወርቅነህ በደህና መግባት ምርቃት ተደርጎ ሰዉ እየተሰናበተ ሔደ ። ብርሃንና ሰላም ክቡር ሐኪም ወርቅነህ ልጅ ቴዎድሮስ ክቡር ልጅ መስፍን ቀለመወርቅንም እንኳን ደኅና ገባችሁ ይላል ።

ማስታወቂያ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ፀቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፭ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	ፀብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፮ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፮ብር
ጎሐ ጽባሕ	፭ብር
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጤ	፩ሩብ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ከሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ከ፫ሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ተኩል
የገዘሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፰ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፱ ብር ተኩል
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፰ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፵፭ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፰ ብር
፡፡ ባለ ድመት ፡፡		፻፴፰ ብር ፡፡
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፯ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፴፭ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፭ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፮ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ	፲፪ተ፲፰ ሳንቲ
አንድ ብር	፳ ሊሬ እስከ	፳ ሳንቲም
ባንድ ጊኒ	፲ ብር ከ፳	ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፱ ብር	

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ፡፡



የእጅ ሰዓት ዝኒት

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የሚባል ባለአንበሳ ስዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ፡፡

Automobiles CHEVRGLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳየ ስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል"አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ"ብቻነው።

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።



ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድሪስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስዑን ፡ አድከሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኵታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ዓ ለ ም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠራል ።

ኒኮላ ።

ማመልከቻ ።

በብርሃንና ሰላም ውስጥ ማስታወቂያ ማሳተም የሚፈልጉ ነጋዴዎች እስከ ፈለጉት ጊዜ ድረስ በማርኛም ሆነ በፈረንጅ ቋንቋ በርካሽ ዋጋ እንደምናትምላቸው እናስታውቃቸዋለን

ጉድ ደር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሶስተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፶፪
3 me ANNÉE № 52

ሐሙስ ታኅሣሥ ፲፱ ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 29 Decembre 1927

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ይስታወቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፊደን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ብርሃንና ሰላም ።

ብርሃንና ሰላም ጋዜጣችን ከተጀመረ ሶስት ዓመት መሙላቱ ነው ። ይህ የዛሬ ቍጥር ጋዜጣ የሶስተኛ ዓመት መጨረሻ ነው ። የብርሃንና ሰላም ያራተኛ ዓመት መጀመሪያ ቍጥር በታኅሣሥ ፳፮ ቀን ይጀምራል ።

ብርሃንና ሰላም በክቡር እየሰበሰቡ የሶስቱን ዓመት አስጠርዘው እንደ መጽሐፍ አድርገው የያዙትን ሰዎች ምስጋና ይገባቸዋል ።

ይልቁንም ደግሞ ላገራቸው ሕዝብ የሚጠቅም እያሰቡ ጽፈው ለላኩልን ሰዎች ሁሉ ጥልቅ ምስጋናችንን እናቀርብላቸዋለን ። በሚመጣው ጊዜ ሁሉም እንደዚሁ በጎ ሐሳባቸውን በትጋት እየጻፉ እንዲልኩልን ተስፋ እናደርጋለን ።«ሐጺን ለሐጺን ይትበላሕ» እንደሚሉት ሁሉ ያንዱን ብልህ ሐሳብና ንግግር አንዱን ብልህ ይረዳልና እርስ በርሳችን እንድንረዳዳ እግዚአብሔር ኃይልና ብርታት ጥበብና የሞቀ ላገር ቅናት ይስጠን ።

ከብዙ ብልሆች ለሕዝብ ጥቅም ላገር ልማት ለመንግሥት ጽናት የሚሆነውን በብርሃንና ሰላም የተነገረው ነገር ብዙ ነውና ሁሉን ባንዳንድ መቍጠር አያስፈልገንም ። ግን የተፈጸመውንና በተስፋ የሚጠበቀውን ነገር ማስታወስ የሚፈልጉ ሰዎች ያለፉትን ቍጥሮች እየገለጡ መመርመር እንደሚያስፈልጋቸው እናሳስባቸዋለን ።

አስጀምሮ ላስጨረሰን አምላክ ምስጋና ይግባው ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነግሥታት ዘውዲቱና ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ጽናትና ልማት ለተከበረች አገራችን ይሁን ።

ማመልከቻ ።

በኢትዮጵያ ላሉ መምሕራንና ሊቃውንት በየአድባራቱ ለተሾሙ ክቡራንና ግሩማን አለቆች ።

ስለ ትምህርትና ትምርት ተዘምዶ ። ስለ ድንቁርና ባዕድነት፡ከዕለታቱ ባንድ ቀን እንጦጦ ጥግ ወጥቶ የኪዳን ምሕረትን ቤተ ክርስቲያን እጅ ነስቸ ። በልዑል አ ወ ተ መ ተማሪ ቤት አጠገብ ባለው መንገድ ስመለስ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ። ያጌጠ ጫማ ጫማቸውን ተጫምተው ። ኩፌት ኩፌታቸውን ደፍተው ከዘራ ከዘራቸውን መዘው መጣፍ መጣፋቸውን ይዘው። ብዙ ወጣቶች እንዳሸን ሲፈሉ አይቸ ገርሞኝ ቁሜ አስተውዬ አስተውዬ አሁን እኒህ ልጆች እንዲህ አጊጠው የተማሩት ትምርት ምን ሊረባ ነው ። አባቶቻችን ተርበው ተጠምተው የተማሩትን ትምርት ለማርከስ ሥርዓታችንን ለማፍረስ ነው እንጅ እያልሁ በመቋሚያየ ምድሩን እየወጋሁ ስተክዝ ከትክልቶች ውስጥ ብርሃንና ሰላም የሚባለው አፍለኛ መምሕር ፊቱ እንደ ፀሐይ እያበራ የለበሰው ልብስ እንደ በረድ ነጭ ሁኖ ። ብቅ አለና አንቱ ካህን ምነው አውራ መንገድ ቆመሁ ትተክዛለሁ አለኝ ። እኔም እኔ ያልተከዝሁ ማን ይተክዝልኝ አገሬን እንግዳ ትምርት ሲወርሰው አልሁት ። ከዚህ በኋላ ያለመጠን ከት ብሎ ሳቀና እረ በሉ አለኝ።አቤት አልሁት ፡፡ ትምርት ወደ ሕዝቡም ወደ አሕዛቡም ቢደርስ ሰው ሁሉ የፈጣሪውን ስራና ። የራሱን አኳኋን መርምሮ አውቆ ተማሪ ቢበዛ ይሻላል እንጂ ቤተ ክርስቲያን የሁሉ እናት ስትሆን ባምስት ሰሞነኛና ባስራምስት አወዳሽ ብቻ ተዘግታ ልጆቿ ሁሉ አዋቆች በመባል ፈንታ አጥቢያ የሚባል የዜጋ ስም ወጥቶላቸው ቢቀሩ መጠቀሟ መሆኑ ነውን ፡፡ በዚያውስ ላይ ሰው ሁሉ ባይማር አይደለምን ፡፡ መጻሕፍት ሲነበቡ ሲተረጐሙ የፍየል ቆዳ ብትለፈልፍ ሰማይ ደርሶ የመጣ የለ ብሎ ሸማውን አጣፍቶ እየዘበተ የሚሄድ ፡፡ ይልቁንስ ተማሪ ከበዛ ከደጇ ሰላም ያጋፋኛል ብለሁ ትፈሩ እንደሆን ነግደሁ እርስሁ ጽፈሁ ደጉስሁ ጨምሩበት ካለኝ በኋላ ቀና ብዬ ሕፃንነቱን

አይቸ ። አሁን ቅናንት ተወልደህ ትበልጠኛ እውነትም ብርሃን ዘእምብርሃን ጨዋ የጨዋ ልጅ አሳዳጊህ ተ መ ይባረክ ብዬ ካልሀስ እኔንም ብዙ የሚቆጨኝ ነገር አለ ከብዙውም አንዱ ይህ ነው ። አለመማር ብርቅ ሁኖ ጅግናውም ፈሪውም አንድ መስሎ ፣ የተማረ ወዳጅ ቢቀር ምን አባቱ ። ሾተል ሲመዙበት ይላል ባዛኝቱ እያለ ሲተረትብን አሁን ግን እንዳፋህ ያድርግልንና ሰው ሁሉ ተማሪ ከሆነ ከዚህ ተረት ድነን ። ወይ እኛም በሰይፍ ማማታት አሰይፎ ነው አያውቀውም እንጂ ያል ተማረ ሰው ብለን እንተርት ይሆናል ብዬ ከቤተ ክርስቲያን ስመኤስ የተከተለኝ መንፈሳዊ ሁከት የሚባል ተማሪ ነበረ ። መወድስ ተመራኝ አልሁት እሱም ፈጥኖ ፈኑ ብርሃነከ ወጽድቀከ ። ብሎ ቀረበ ቅኔውም ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ተስፋ ብዙኃን ትምሕርት ። እመ ውኁዳን ።
ብርሃነ ሰላም ነሥአት እምእደ ጠባባት ሐምስ ።
ወአስተፋጠነት ትባዕ መንግሥተ ሰማይ መቅደስ ።
ዘእንበለ ኖኅት ይትዓፀው ።
ለስመ በዝኍ ደቂቃ በአዝማን ሠላስ ።
ወአብዝኅት መናብርተ
ባሕቲታ ኢትንበር ከመ ዖፍ ውስተ ናሕስ
በታቦርሂ አመ ተከሥተ ትምሕርተ ወንጌል ሐዲስ ።
መጽኡ ይርአይዎ ሙሴ ወኤልያስ ።
ወደቂቀ ወንጌል ያዕቆብ ወዮሐንስ ።
ሐነፁ በሕሊና ለእሉ ቤተ ጴጥሮስ ።

ከዚህ በኋላ ሰላመ እግዚአብሔር ይጠብቅህ ብሎኝ ወደ ተማሪ ቤት ገባ

በኢትዮጵያ ላሉ ጅግኖችና የጅግንነት ተስፋ
ላላቸው ወጣቶች የማነቃቃት ማመልከቻ ።

ወንድሞቼ ሆይ በያገሩ ያሉ ጅግኖች ያገራቸውን ፍቅር ማጥናታቸው ስለ ሃይማኖትና ስለ ምግባር ተቆጥሮላቸው በቀቶው እንደ መላእክት በክንፍ ይበራሉ ማለትን ጆሮአችን ይሰማል እኛስ ስላገራችን ፍቅር ወንሕነሰ ነዓቢ በስመ እግዚአብሔር አምላክነ እያልን ፈረሶቻችንን እየቀለብን በየጉግሱ ወደ ላይ ብናዘልላቸው ነውር ይሆን ፈረስ መልአክ ነው፤መባሉ በፍጥነቱና ወደ ሰማይ እያደገ በመሮጡ ነው እንጂ በተፈጥሮ እንዳይመስለው ማንም ያውቀዋል ምሳሌ የደጋ ወፍ ጠባቂ ለገብሱ ። የቆላ ወፍ ጠባቂ ለማሽላውም ጥበቃ ከወፎች የሚከላከልበት መሰላል አቁሞ ፣ ወፎች ፍሬውን ለመልቀም የሚበሩበትን ዓየር መጥኖ ወንጭፉን ይዞ ይጠባበቃል ፣ ከነዚሁም ወፍ ጠባቆች አንዱ ከምድር ርቃ በዓየር መጥቃ የምትሄደውን ክንፏ ላዩ ጥቁር ከፊይ ውስጡ ቀይ ከፊይ የሆነውን ሶሬት የምትባለውን ወፍ ጠልፎ ገድሎ ወርዶ ቢያያት የመልኳን ማማር አይቶ አሳዝናው ጥበቃውን ጥሎ ውሎ አድርጎ ሲያለቅስ ዋለ ይባላል ። የልቅሶውም ግጥም ከዚህ ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው ። ቀኑ ሊያልፍ ፣ እህሉ ሊተርፍ ፣ ለምን ገደል ኩሽ አንቺ ወፍ ነው፣አሁንም ቀይ ጥቁር ረጅም አጭር የማይል እውነተኛ ሰማያዊ ንጉሥ በቸርነት ጥበቡ ክንፍ ለማስረጽ እስኪያበቃን። በፈረሶቻችን ደጅ ብንጠናው ምንው ። የጥንት ፈረሰኞች የጉግስ ዜማ ፈረሱ እንዳሞራ ። እሱ እንደ ንብ አውራ እንደ ምን ተፈጥሯል እንደ ምን ተሰራ ይባል ነበረ ይባላል ።

ስለ እግረኞች ነፍጠኞች ማነቃቃት ።

ወንድሞቼ ሆይ አባቶቻችን በግር እየሮጡ ዋሊያ በሩጫ አንበሳ በርግጫ ነብር በጡጫ ይገሉ ነበር ይባላል ። ይህንም ሰርተው ሲመለሱ ከንጉሡ ፊት እኔ አሽከርህ ደረቴን ለጦር ግምባሬን ላረር እግሬን ለጠጠር ከጠሁልህ ይሉ ነበር ። እኛስ ባገራችን በመላው መንገድ አልተዘረጋበት ደረጃ አልተነጠፈበት ያንድ ከተማ ጠጠር ፈርተን ለምን እግራችንን እንሸሽገዋለን ። ብዙ ዳገትና ቍልቁለት ብዙ ረግረግና ብዙ ያል ተደለደሉ ፈሳሽ ወንዞች አሉ ለምን እግራችነን አስቀድመን እንሸሽገዋለን ። ወደ ውጭ አገር ስለ ትምሕርትም ስለ ንግድም ። ስለ መንግሥት ጉዳይም የሄዱት ወንድሞቻችን የነበሩበት አገር መንገዱ ስል ተወሰነ ያገሩም ልማድ የግድ ስለ ሆነባቸው እግራቸውን ቢሰውሩ አገባብ ነው ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በመላው ትምሕርትን እንዲወድ ስለማትጋት

ወንድሞቼ ሆይ ባገራችን ያለውን ያማርኛችን መሠረት የግዕዝ ቋንቋ ባለ ማወቅ እጅግ አጥብቀን ተጐዳን ። አሁን በዘመናችን ዕድሜ ለንግሥታችንና ላልጋ ወራሻችን ። ይህ ላይናችን እንግዳ የሆነው መሳርያ ሁሉ ነበር ነው ። ግዕዝ የሚያውቁ ምሑራት ሁሉ በጆሮአቸው ጠግበውታል ፣ በልባቸው ተረድተውታል ። በቃላቸው ይተረጉሙታል ። ከሁሉ ይልቅ ብርቅ የሆነብን እንደ ሰው የሚናገረው ሙዚቃ ነው ። ኀለይተ ብርት ተብለው ተነግረዋል።እንዲያውም በመጻሕፍት ከተነገሩት መሳርያዎች ያ፤ናቸው እጅግ ያንሳሉ ። ግዕዙ ቋንቋ እንኳን ለሕዝቡ ለካህናቱ ሩቃችን ነው ። ከምንሰማው የማንሰማው እንበዛለን ። በግምት ሶስት መቶ ካህን ካለበት ትልቅ ደብር ሰባ ግዕዝ የሚሰማ አስራ ሁለት ካህን ካለበት ገጠር አንድ ዘይቤ የሚሰማ ካህን ቢገኝ እኒያ ደብሮች እጅግ እድላሞች ናቸው ። ስንኳን ሌላ ትልቁ ዳግማዊ ምኒልክ አዕምሮ ብለው ሰይመው ለሁሉ ማሰልጠኛ ትልቅ የውቀት መሪ ፊደል ቢያወጡ። ከዝያም ቀጥለው በግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ ጊዜ ።ል አ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ብርሃንና ሰላም የሚባል መብራት አብርተው በግዕዝ መጋረጃ የተሠወሩትን መጻሕፍት ባማርኛ ቢገልጡ ። ፊደል የቆጠረው ሰው ጥቂት ከመሆኑ የተነሳ ያልሰማው ብዙ ሆኑዋልና ትምሕርት ቤት ከልቆመ ሕዝብ እንዳይጠቀም የታወቀ ነው ። ከዚህም ቀጥሎ የእጅ ሥራ መማር እንዲገባ አስቀድሞ እግዚአብሔር አዳምን በነፍስ ሕያው አድርጎ ፈጥሮ በገነት አክብሮ አኖረው ተብሎ ከሚነገረው ። ወጥተህ ወርደህ ጥረህ ግረህ ብላ ያለው ይጐላል ። ሰላም ካለው ፍቅር ያለው እንዲጐላ ፣ ከዚያም በኋላ ዓለምን በንፍር ውሀ ካሳለፈ በኋላ በጥበቡ የሰወረውን ኖህን ወጥተህ ተክል ትክል ዘር ዝራ አለው እንጅ የሥራ ፈት ኑሮ አልፈቀደለትም ። ዳግመኛም በሮ፻ አድሮ ተግባረ እድን ሲያስተምር ። ወዘይደሉሰ ለመሲሐውያን እምነ ግብራት ለሕይወተ ሥጋ ፩ ክፍል አለ ። ይህም ባማርኛ

ለሥጋ ደህንነት ከሚሠራው ሥራ ወገን ለክርስቲያን የሚገባው ሥራ ሁሉ ሁለት ወገን ነው ከሁለት ይከፈላል ማለት ነው ፡ ከዚህም ቀጥሎ ሥራውን ከምሉ በክፍሉ ከብዙ በጥቂቱ ይቆጥራል ። ዘር መዝራት ፡ ማጨድ ፡፡ ዓሣ ማጥመድ ። ልብስ መሥራት ። መስፋት ፤ ግንብ መገንባት ፤ ከርፈዝ ፤ ማረሻ ፤ መጥረቢያ ፤ ማጭድ መሥራት ፤ ጠራቢ ከሌለ ሕንፃ አይገኝምና ። መጥረብ ፤ አንጥረኛ ከሌለ ። ሥጋዊ መሣርያ ጩፋ ቢተዋ ። መንፈሳዊ መሳርያ ፃሕል ጽዋ አይገኝምና ብር መሥራት ፤ ጸሐፍት ከሌሉ መጻሕፍት አይገኙምና ፤ ጽሕፈት ። ቀለምም የሚያገባ ከሌለ ግምጃ ዝጋጃ አይገኝምና ቀለምም ማግባት ፡፡ መምሕራንም ከሌሉ ትምሕርት አይገኝምና ትምሕርት ይገባል ብሏል ። ይህን ሁሉ ያስፈለገኝ ጅግኖችን አነቃቅቼ አገር እንዲጠብቁ ብዬ ነው ፡፡ አገር ካልተጠበቀ በደጅ ብርሃንና ፡ በደጅ ሰላም ያላሳብ መኖር የለም በማለት ነው እንጂ እኔ ከዚህ ሁሉ አንዱን አልሰራሁምና አንባቢዎች ሆይ ይቅርታችሁን እለምናለሁ ።

የብርሃንና ሰላም ወዳጃችሁ አለቃ መርስዔ ኀዘን ።

መልክም መድኃኒት ።

ብዙ ጊዜ የብርሃንና ሰላም ወንድሞቻችን ኢትዮጵያ እናታቸው ቀደምት ከተባለ ቀሚሷ ላይ ጥበብ የተባለ ኩታ ለብሳ እንድትከራላቸው ሲመኙና ሲጣጣሩ እናያለን ። ነገር ግን በጥባጭ ሳለ ማን ጥሩ ይጠጣል እንደሚሉት ተረት እኩሌቶቹ ልጆቿ ልማድ የሚባል ጋሻቸውን መክተው እስከለሁ ይመቸኝ የሚባል ትምሕርት እያስተማሩ ኋላ መቅረት የሚባለውን ድሪቶ እንደለበሰችው ትኑር ብለው ያስቸግራሉ እነዚህ ሰዎች ግን የበሽታ ይሆናል እንጂ እውነትስ በጤናቸው እያሉ ከብርሃን ጨለማ ከጣፋጭ መራራ ይሻላል ብለው አይደለም ። በሽታቸውም እኔ እንደሚመስለኝ ምቀኝነት የሚባል ትልቅ ወስፋት ከሆዳቸው ሰፍሮ እየተገላበጠ አላስቆም አላስተኛ አላስኬድ አላሠራ ብሎ ያስጨንቃቸው ይሆናል ስለሆነም ሕመሙን ተናግሮ መድኃኒቱን መደበቅ በእግዚአብሔር ዘንድ ያስፈራል በማለት ከዚህ በታች የጻፍነውን የመድኃኒት ስም ተመልክተው ሊያደርጉት እናሳስባቸዋለን ።

መጀመሪያ ይህ ብዙ ቀን ስር የሰደደ ወስፋት ምክር በሚባል መድኃኒት የሚወጣ አይደለምና ኃይል በሚባል ኃኪም (ኦፒራቲኦ opération) የሆድ መቀደድ ደንብ ቢደረግላቸውና ያ አስቸጋሪው ወስፋት ሁለተኛ እንዳይመለስ ቅጣት በሚባል መቀስ ቀንጥቦ መጣል ነው ። ከዚህ በኋላ ስጋት የሚባል መድኃኒት ቀብቶ ያለፈው ይብቃ በሚባል ክር መስፋት ነው ፤ ይህንንም ስለመከርናቸው ይቀየሙብን ይሆናል ምንግዜም በእውቀት ያልሰለጠነ ሕዝብ ጠቀሚታውን የሚጠላ ሕፃንን ይመስላልና አሁን ለጊዜው ቢጠሉን ለሁሉም ዘመን አለው እንደአለ ። ምሳ ፫ ቁ፩ ይህንን ምክር የሚወዱበት ዘመን ይመጣ ይሆናል ።

ጥሩነህ ከ ፡፡

የፈረስ እሽቅድድም ።

ታሕሣሥ ፲፪ ቀን የፈረስ እሽቅድድም ተደርጎ ነበርና ክቡር ጃንሆይ በ፰ ሰዓት ልዑል የኢትዮጵያ መ አ ወ ተፈሪ መኰንን በመኳንንቶቻቸውና በሠራዊታቸው ታጅበው እሽቅድድም እንዲደረግበት በተሰናዳው እጃን ሜዳ ወጡ ።

፩ኛ እሽቅድድም ፡፡

የሚዳው ርዝመት ፳፻ ሜትር ።

ባንደኛ እሽቅድድም ማሱድ የተባለ የሙሴ ጋሊብ ፈረስ ቀደመና ኖቢስ ዋንጫ የጆወርጅ ዋንጫ ተቀበለ ፡፡ ሁለተኛ ቀዳሚ ፒስቶላ የተባለ የማዳም ኩራ ፈረስ ቀደመና ሰላሳ ብር ተቀበለ ። ሶስተኛ ሸሪፍ የተባለ የሙሴ ጋሊብ ፈረስ ቀደመና ስምንት ብር ተቀበለ ፡፡

፪ኛ እሽቅድድም ።

የሜዳው ርዝመት ሺ፰፻ ሜትር ።

በሁለተኛ እሽቅድድም ፊተኛ ቀዳሚ ቱምቱ የተባለ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ቀደመና ዋንጫና አምሳ ብር ተቀበለ ። ሁለተኛ ቀዳሚ ግራንድ ሺልም የተባለ የሙሴ ዶሴሞንቴ ፈረስ ሆነና ሰላሳ ብር ተቀበለ ፡፡ ሶስተኛ ቀዳሚ ተስፋዬ የተባለ የማዳምዋዜል የውብዳር ብሩ ሆነና ፲፭ ብር ተቀበለ ፡፡

፫ኛ እሽቅድድም ።

የኢ. መኳንንቶች እሽቅድድም ፡፡

የሜዳው ርዝመት ሺ፪፻ ሜትር ፡፡

በሶስተኛ እሽቅድድም ቀጭኔ የተባለ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፈረስ ሆነና አምሳ ብር ተቀበለ ፡፡

፬ኛ እሽቅድድም ሐሪንግቶን ዋንጫ ።

የሜዳው ርዝመት ሺ፪፻ ሜትር ።

ባራተኛው እሽቅድድም ፕሪንሴስ የተባለ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ቀደመና ዋንጫውንና አርባ ብር ተቀበለ ፤ ሁለተኛ ቀዳሚ ማርከሻ የተባለ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፈረስ ቀደመና ሰላሳ ብር ተቀበለ ። ሶስተኛ ቀዳሚ ቦራ የተባለ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሆነና ፲፪ ብር ተቀበለ ፡፡

፭ኛ እሽቅድድም ፡፡

የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዋንጫ ፡፡

የሜዳው ርዝመት ፪ሺ ሜትር ፡፡

ባ፭ኛ እሽቅድድም በለው የተባለ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ቀደመና ዋንጫውንና አምሳ ብር ተቀበለ ፪ኛ ቀዳሚ ፒርክም የተባለ የሙሴ ምግነር ፈረስ ቀደመና ሰላሳ ብር ተቀበለ ። ፫ኛ ቀዳሚ ሴፔሊሲሙስሲ የተባለ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ሆነና ሀያ ብር ተቀበለ ፡፡

፮ኛ እሽቅድድም ፤

የኢጣሊያ ዋንጫና ሙሴ ቤንቲንክ ፤

የሰጡት ትንሽ ዋንጫ ፤

በስድተኛ እሽቅድድም ፊተኛ ቀዳሚ ዋቮት የተባለ የሙሴ ቻምበርሊያን ፈረስ ሆነና ፪ዋንጫና ፵ብር ተቀበለ ፤ ሁለተኛ

ቀዳሚ ሴፕሊስሙስ የተባለ የሙሴ ቤንቲንክ ፈረስ ሆነና ፴ብር ሶስተኛ ቀዳሚ ሳሂብ የተባለ የሙሴ ክራ ፈረስ ሆነና አስር ብር ተቀበለ ፤

፯ኛ እሽቅድድም ፤

የፍራንስ ዋጋ እሽቅድድም ፤

የሚጻው ርዝመት ፪ሺ ፭፻ ሜትር ነው ፤

በሰባተኛ እሽቅድድም ፊተኛ ቀዳሚ ጃንጀር የተባለ የማዳም ቤንቲንክ ፈረስ ሆነና የጥበብ ዕቃና አርባ ብር ተቀበለ ሁለተኛ ቀዳሚ ቡሎ የተባለ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ሆነና ሰላሳ ብር ተቀበለ ፤ ሶስተኛ ቀዳሚ ሳሂብ የተባለ የሙሴ ጋሊብ ፈረስ ሆነና ሀያ ብር ተቀበለ፡

፰ኛ እሽቅድድም ፤

ሂአርድ ዋንጫ ዝላይና ስለ ልዑል ኤስ ኤር ፤

ዱክ ዴዝ አብሩዝ ዋንጫ ፤

የሚጻው ርዝመት ፫ሺ፪፻ ሜትር ፤

በስምንተኛ እሽቅድድም ፊተኛ ቀዳሚ በላይ የተባለ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ሆነና ሁለት ዋንጫና አምሳ ብር ተቀበለ ፡ ሁለተኛ ቀዳሚ አሩሲ የተባለ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ሆነና አርባ ብር ተቀበለ ፡ ሶስተኛ ቀዳሚ ፋንፋላ የተባለ የሙሴ ክራ ፈረስ ሆነና ሰላሳ ብር ተቀበለ ፤

የደስታ አቀባበል ።

ክቡር ሐኪም ወርቅነህ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ዋና ሹም በደህና ስለገቡ የትምህርት ቤቱ ዲሬክተርና አስተማሪዎች ታሕሣሥ ፲፪ ቀን የቻይ ግብዣ አድርገው ብዙ የውጭ ሰዎችና መኳንንቶች ጠርተው የደስታ በዓል አድርገው ነበር ። ከሻምፓኝ በኋላም ብዙ ንግግር ተደረገ ንግግሩም ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

ክቡር ሆይ ፡

ይህ የዛሬ ቀን መሰብሰባችን ከመካከላችን እርስዎን በማየታችን ደስታችን እንደምን ትልቅ እንደሆነ ያስረዳል ፡ እርስዎም በሌሉበት በረጅም ጉዞዎ በልዩ ልዩ የደረሱበትን የተከበሩ ባለቤትዎ ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ መልክም ፈቃዳቸው ሆኖ እያስታወቁ ሐሳባችን በሄዱበት ሁሉ እርስዎን ተከትሎዎት ነበር ። ይኸንኑ የሚአስረዳ ሊሔው በትልቅ ሥራና ይልቁን በፍጹም አንድነት ሆኖ ያገኙታል መልክም ፍቅርን የተመላ አንድነትም እንደአስተማሪዎቹ በተማሪዎቹም ዘንድ ይገኛል ።

ለአስተማሪዎቹም ሥራቸውን ለማከናወን ለተማሪዎቹም ትምሕርታቸውን ለመያዝ የሚአስፈልገው ዋናው ነገር አንድነት ነው ይኸውና እንግዲህ እርስዎ ከተመለሱ ይህ ስምምነት እየበረታ ይሄዳልና የተማሪዎቹም ሥራ ይገለጻል እያንዳንዳችንም ትክክል ሀሳብዎንና ደግነትዎን እየተረዳን ሥራችንን በትክክል ማስኬድ በልባችን ያድርብናል ።

ክቡር ሆይ ፤

ጥሪያችንን በመልክም ፈቃድዎ ስለተቀበሉን በሥራ ጓደኞቼ በአስተማሪዎቼና በተማሪዎቹ ስም ሁኜ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ ።

ደግሞ እንኳን ደህና ገቡ ከሚል ከመልክም ምኞታችን ጋራ ጤና ለእርስዎና ለውድ ቤተ ዘመዶችዎ ይሁን ብለን እንለምናለን ።

እንደዚሁም በዚህች አዳራሽ ውስጥ ያሉትን የደስታችን ተካፋይ ሆነው እዚህ በመኖራቸው የከበሬታ ግብዣችንን ስለ አከበሩልን እናመሰግናቸዋለን። በመጨረሻውም እረጅም ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ይሁን እያልን በኢትዮጵያ መልክም የተማሪ ቤት እየመሠረቱ በምትጠቀምበት ሁሉ የጥንቱን እየለወጡ የሚአድሷትን ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን እያመሰገንን ለአገልግሎት መሰናዳታችንን ጥልቅ ከበሬታችንን እናቀርባለን ። ሙሴ ቶማዚኒ

ክቡር ሆይ፣

በደህና ወዳገርዎ ለመመለስ ያበቃዎን አምላክ እያመሰገንን የገቡባችን ቀን ለማክበር ብለን ባሰናዳነው በዓል ጥሪያችንን አክብረው ስለመጡልን በተማሪቤቱ ስም ሆኜ ለክብርዎ የተገባ ምስጋና ለማቅረብ እለምናለሁ ።

ክቡር ሆይ ፤ ምንም እንኳን ያሜሪክ ርቀት የውቅያኖስ ስፋት እመካከላችን ሆኖ ለያይቶን ቢኖር ሐሳባችን በሔዱበት ሁሉ በቃላቅ ናፍቆት ይከታተልዎ እንደነበረ ላረጋግጥልዎ ደስ ይለኛል ። አንድ ጊዜ ወረቀትዎ በደረሰልኝ ጊዜ ተማሪዎቹ ለምሳ ተሰብስበው ሳሉ ምክርዎንና ሰላምታዎን በነብላቸው ደግነትዎንና አባትነትዎን አስበው እንዴት እንደባቡ አሁን ይታየኛል ። ይሁን እንጂ የፍቅራቸውን መጠን በቃል ብቻ ለማስረዳት ምንም እንኳ የማይቻል ቢሆን ምክርዎን ተከትለው ብትምህርታቸው መትጋትና በባሕርያቸው ማሳመር ለፍቅራቸው ለናፍቆታቸው የሚበቃ ምስክር ነው ። አስተማሪዎቹም ምንም እንኳ ስራቸውን በመታመን ቢፈጽሙ የመሪነትዎ ብርሃን ጣዕም መጉደሉ በጣም እንደተሰማቸው አውቃለሁ ። ግን አሁን ይህ ሁሉ በደስታችን ብዛት ውስጥ ተለውጥዋልና እንኳን በደህና የተመለሱልን ፡ ለወደፊትም ከተወደዱ ቤተሰዎችዎ ጋራ በጤናና በደስታ ይጠብቅልን ብለን እንመኛለን ።

ደግሞ ወንድሞቻችን ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅንና ልጅ ቴዎድሮስ ወርቅነህን በማየት ደስታችንን እየገለጥን እንኳን በደህና ገባችሁ እንላለን ።

ለዚሁ በዓላችን የመጣችሁልን ክቡራን መኳንንት ሆይ የደስታችን ተካፋዮች ስለ መሆናችሁ ፍጹም ምስጋናችንን እያቀረብን ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥታችን ዕድሜ ለልዑል አልጋ ወራሻችን ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ብለን እንመኛለን ።

አቶ ኤፍሬም ።

ክቡራን ወይዛዝርና መኳንንት ሆይ ፡

አስቀድሜ መልክም መሪ አባታችንን ሐኪም ወርቅነህንና የምንወዳቸው ወንድሞቻችንን ልጅ መስፍን ቀለም ወር

ቅን ልጅ ቴዎድሮስ ወርቅነህን በሕይወት መልሶ በፊታችሁ ይህን ቃል ለመናገር ያበቃኝን እምላክ አመሰግናለሁ ።

ባለፈው ዘመን ሐምሌ ፲፰ቀን ለኢትዮጵያ የሚበጅ ሥራ ለማድረግ በመንግሥትዎ ፈቃድ ወደ ውጪ አገር ተልከው በታኅሣሥ ፲ቀን ስለተመለሱ ጊዜውን ስንቈጥረው ፭ወር ብቻ ነው ግን ለኛ በናፍቆት አሳባችን ካንድ ዓመት የበለጠ መስሎ ታይቶን እንደነበረ አይጠረጠርም ። ይኸውም መሆኑ የማይጠገብ ደግነትዎና እንቅልፍ አጥተው ከማሰብና ከመሥራት ተርፈው እኛንና እኛንም የመሰሉ ብዙዎች የኢትዮጵያን ልጆች እያተጉ አድራጊና አስደራጊ በመሆን የደግ ሥራ ሁሉ መሪ ንትዎ እየተሰማን ነው ።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ከመልካም አድርጐትዎችዎ ውስጥ ጥቂቶቹ ን እገልጻለሁ ፤ መጀመሪያ ስለ ኢትዮጵያ ክብርና የሕዝባቸውምጥቅም በሀገራቸው እንዲሰፋ ሌትና ቀን የሚያስቡ አልጋ ወራሻችን ልዑል ተፈሪ መኰንን ገንዘባቸውን እንደ ጕርፍ ውሀ እያፈሰሱ ዘያይነቱ የቋንቋና የመኪና የእጅ ሥራም ትምህርት ቤት አቁመው እንድንማር የሰበሰቡን አዳሪና ተመላላሽም ሆነን ለምንማር ቍጥራችን ከሁለት መቶ ፳ ለምንበልጥ ሕጻናቶች ከወለዷቸው ልጆች አብልጠው ጉዳት እንዳያገኘን ሁልጊዜ የጤናችን ጠባቂ በመሆንና መምህሮቻችን በማትጋት የልዑልን ደንብ ጠብቀው መሥራትዎ በልባችን እንደ ሐውልት ተቀርጾ ለዘለዓለም መታሰቢያ እንዲሆን አምናለሁ።

፪ተኛ የፍቅርና የአገልግሎት ማኅበር ከተመሠረተች ፪ዓመቷ ነው በዚህ በሁለት ዓመት ውስጥ በጌታችን በልዑል ኃይልና በናንተ በጌቶቻችን እርዳታ ባሁኑ ጊዜ ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋትን ዋና ቁም ነገር ያለበትን የነርያ ነፃነትን ሥራ ለማድረግ ለሚጣጣሩ የኢትዮጵያ ወጣቶች እንዳንድ ከመሆን ይልቅ አባት ሆነው ረዳትና የጥቃታቸው ተከላካይ መሆንዎ ለኢትዮጵያ የመጀመሪያ አገልጋይነትዎን ያስረዳል ።

በዚህማ ያሉትን ሥራዎችን ሁሉ ክብርት ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ በታላቅ ትጋት አንዱ ሳይጐድል በቅንነት ማስኬዳቸው የከተማው ሰው ሁሉ አድንቋል ። እናንተም በውጪ አገር ሳላችሁ ሳትሰሙት ትቀራላችሁ በማለት አልጠራጠርም ።

ክቡራን ሆይ ፤ የገቡበትን ቀን ለማክበር አሁን በተሰበሰቡት ወንድሞቼና በኔም በራሴ ስም ሆኜ እንኳን ደህና ገባችሁ እያልሁ ለግርማዊት ንግሥታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን ረጅም ዕድሜና ጤና ሰጥቶ መልካም አሳባቸውን ያስፈጽማቸው ስል እመኛለሁ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

ተስፋ ያየህ ይራድ

ከዚህ በኋላ ክቡር ሐኪም ወርቅነህ የሚከተሉትን ቃላት ለመናገር በተነሡ ጊዜ ዳር እስከ ዳር ንግግሩ እስኪፈጸም ድረስ ጸጥታ ሆነ ።

ክቡር ዲሬክተር ክቡራን ወይዛዝር ክቡራን የትምሕርቤቱ አስተማሪዎችና የተወደዳችሁ ተማሪዎች ። ወዳገሬ በደህና ስለተመለስሁ ከልባችሁ በናፍቆት ተቀብላችሁ ዛሬ በዚህ ጊዜ ስላስተናገዳችሁኝና ይህን ክብር ስላደረጋችሁልኝ ምስጋናዬ ብዙ ነው ። አምስት ወር ሙሉ ከናንተ ተለይቼ አሁን ተመልሼ ስመጣ ሁላችሁንም ደህና በማግኘቴና በስራችሁ ተግታችሁ ደስ አሰኝታችሁ በመቆየታችሁ እጅግ ደስ እንዲለኝ አሳስባችኋለሁ ።አሜሪካና አውሮጳ ውስጥ ማናቸውም በስልጣኔ እኳሆን ስለሚታይ እጅግ በጣም የሚያስደንቁ አገሮች ናቸው ። ይሁን እንጅ በማናቸውም ተከናውነው ደስ ቢያሰኙ የተወለዱበት አገር ከሆነ ምንም የመከናወን ስልጣኔ ባይኖረው እንኳ እንደሱ የሚናፈቅ ከቶ ስለማይገኝ ከተወዳዳችሁ ወንድሞቻችን ለመቀላቀል ስንል ፤ እኔ ራሴ ልጅ መስፍንና ልጄ ቴዎድሮስ ጨምሮ ወደ ውድ አገራችን ወደ ኢትዮጵያ እንመለስ ዘንድ ፈቃዳችን ሆነ ። የኛን ወደ ኋላ መቅረት ከአሜሪካና ከአውሮጳ ስልጣኔ ብናመዛዝነው ጸጸት የሚሆነን በሌላ ቀን ልጅ መስፍን ሊያስረዳችሁ የተዘጋጀበት ብዙ ልዩነት አለ ። ዳሩ ግን እናንተ ያሁኑ ትውልድ ወጣቶች በማናቸውም ተግታችሁ የስልጣኔን ደረጃ ብትከተሉና ትምሕርትን ብትመረምሩ ውበት የሞላበት አገራችንን በማናቸው ከጐረቤቶቿ ልታስተካክሏት እንድትችሉ ተስፋ አለኝ ።

ክቡር ሐኪም ወርቅነህ

የተወዳዳችሁ ልጆች ከጐረቤቶቻችን ለመስተካከል ወደፊት የምንሰራው ብዙ ስላለን ጊዜ ከዕንቀሉ የከበረች ናትና እስከ ዕረፍተ ሞት ድረስ ጊዜያችሁን በከንቱ ሳታሳልፉ ለመማርና ዕውቀትን ለማግኘት ሳትቦዝኑ ያገር ፍቅር በልባችሁ ይደርባችሁ በመጨረሻው በፍቅር ተባብራችሁ አስተማሪዎቻችሁንና ታላቆቻችሁን አክብራችሁ በስራችሁ ትጉህ ሆናችሁ እንድትኖሩ እየተመኘሁ ለዚህ ሁሉ መስተንግዶዋችሁ ምስጋናዬን አቅርቤ ለግርማዊት ንግሥታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን ረጅም ዕድሜ ይስጥልን ስል ጽዋዬን አጠጣለሁ ብለው በጨረሱ ጊዜ ግሩም ሆኖ ተጨበጨበ ።

ገንዘብ ደገኛ ሎሌ ወይም ክፉ ጌታ ሊሆን ይችላል

ገንዘብ እንንዲጠቀሙበት ማድረግ በሚያስፈልግ ሌሎችንም ሊጠቅም በሚችል ደግ ሥራ ማዋፋት። ገንዘብ የሚገዛው ሰው ግን ወዮለት ከሁሉ የባሰ ክፉ ባርነት የገንዘብ ባርያ መሆን ነው ። የገንዘብ ባርያ በዓለም ላይ ደስታ አያገኝም ። መላ ሕይወቱ በልዩ ልዩ የሚሰቅዩ መሻቶችና ፍርሃቶች የተገዛ ሆኖ ይቀራል ።

ገንዘብን የሚንቁ ይሳሳታሉ (ብቻ ጥቂቶች ናቸው) በገንዘብ ብዙ መልካም ሥራ ሊደረግ ይቻላል ። ገንዘብ የሚገዛቸው እርሱን እንደ ጣዖት የሚያደርጉትና ለሌላው መልካም አሳብና ፍቅርም ልባቸውን በገንዘብ የሚዘጉ ግን ይፈረድባቸዋል። በውነት ሀብታሞች የሚቀናባቸው ዕድላሞች ሰዎች ናቸው ቢሆን ግን ለራሳቸው የፍቅርን ደስታና ደግሥራ ለመሥራት ችሎት ስለ ተሰጣቸው እንጅ በሌላ ነገር አይደለም የሚቀናባቸው

ሀብታሞች ስለሆኑም አይዶለም ደስታን የሚያገኙ ሥራ የሚወዱ ሰዎች ብቻ ናቸው ለተገባው መሻታቸው የሚበቃ ሲያገኙ ደስ የሚላቸው ። እነዚሁ ብቻ በጎን ሕሊና ያተርፋሉ ። ያ ከንድ አራሽ የተገኘው እንዴህ የሚለው ምሳሌ እጅግ መልካም ነው ። ሀብት እንደፍግ ብቻ ነው ። ፍግ ባንድ ስፍራ ሲሰበሰብ ይገማልና ይሸታል ። ከእርሻ ላይ ሲበተን ግን እርሻውን ያለመልማል ።

እንግዴህ ሀብታሞች ሰዎች በገንዘባችሁ ላገራችሁ ለሕዝባችሁ ለመንግሥታችሁ የሚበጀውን ሥራ ስንት ያህል ለማድረግ በቻላችሁ ።

ማስታወቂያ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፳ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
ነገሐ ጽባሕ	፳ብር
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪ ፱
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጤ	፩ሩብ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ከሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ከ፫ሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፰ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፱ ብር ተኩል
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፰ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፵፭ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፵፪ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፫ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፵፭ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፭ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፯ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ	፲፪ተ ፳ ሳንቲ
አንድ ብር	ሊሬ	
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ከ፺ ሳንቲም	
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር	

BRITISH MUSEUM 22 MAY 29

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



ባአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሚጋ የሚባል ባለአንበሳ ስዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሖ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ፡፡

Automobiles CHEVROLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚሀ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቀቅዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳም ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል"አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ"ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው ።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፥ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው ።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ. መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ዓ ለ ም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠራል ።

ኒኮላ ።

ማመልከቻ ።

በብርሃንና ሰላም ውስጥ ማስታወቂያ ማሳተም የሚፈልጉ ነጋዴዎች እስከ ፈለጉት ጊዜ ድረስ በማርኛም ሆነ በፈረንጅ ቋንቋ በርካሽ ዋጋ እንደምናትምላቸው እናስታውቃቸዋለን

ጉ ድ ይ ር ግ ዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።